ዶክተር ተወልደ ትኩእ




# የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣሊያ





# የኢትዮጵያ አንድነት

# እና

# ኢጣሊያ

ከዶክተር ተወልደ ተኩአ

ሚያዝያ 1990 ዓ. ም.

አዲስ አበባ

## ማሳሰቢያ

ገጽ 293 የነበረው 29[illegible] ተብሎ ይነበብ

ገጽ 295 የነበረው 293 ተብሎ ይነበብ ፤

ለተፈጠረው የገጽ ቁጥር ስህተት በቅድሚያ ይቅርታ

እንጠይቃለን ።

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

## ማውጫ


1. መቅድም ገጽ 1-9
2. ክፍል አንድ የኢትዮጵያ ታሪክ ምዕራፍ አንድ ጥንታዊት ኢትዮጵያ ገጽ 9-38
3. ምዕራፍ 2 የአክሱም ዘመን ገጽ 38-59
4. ምዕራፍ 3 ኢትዮጵያ ድኅረ ዘትዌ በሰሎሞናውያን ነገሥታት ዘመን ገጽ 59-131
5. ምዕራፍ 4 ኢትዮጵያ ከሰሎሞናዊ አገዛዝ በኋላ ገጽ 131-154
6. ምዕራፍ 5 የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አመሠራረት ገጽ 154-190
7. ምዕራፍ 6 የኢጣሊያ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ማግኘት የነበራቸው ሚና ገጽ 190-238
8. ምዕርፍ 7 የሰሐቲና የዶጋሊ ጦርነቶች 238-264
9. ምዕራፍ 8 በአፄ የሐንስ በምትመራው ኢትዮጵያ ላይ በጣሊያኖች የተፈጸመባት የማዳከም ሰውር ደባ ገጽ 264-300
10. ምዕራፍ 9 ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ወረራዎችና ጦርነቶች ገጽ 300-346
11. ምዕራፍ 10 ኤርትራ በቋንቋ በጉሳ ወዘተ ገጽ 346-380
12. ምዕራፍ 11 ለማይጨው ጦርነት ዝግጅት ገጽ 380-422
13. ምዕራፍ 12 የማይጨው ጦርነት ገጽ 422-457
14. ምዕራፍ 13 የኢጣሊያ ቂም በቀል ገጽ 457-485
15. ምዕራፍ 14 ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አስተዳደርና የአርበኝነት ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ታሪክ ገጽ 485 565

ክፍል 2 የኢጣሊያ ዘረኝነት 565 640

ዋቢ መጻሕፍት ገጽ 640 642

ማውጫ 642

## መቅድም ፣

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክና ሥልጣኔ አላቸው ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሣባ የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየትና ዕውቀቱንም ለማድነቅ ወደ ኢየሩሳሌም ከተጓዘችበት ጊዜ ጀምሮ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የሀገራችን የታሪክ መነሻ አድርገን ስለምንቆጥረው፣ ኢትዮጵያ የ 3000 /የሶስት ሺህ/ ዓመት ታሪክ አላት ማለት እንወዳለን፡፡ ይህ አባባል ሐቅ ሊሆን የሚችለው ሰለሞናዊ ሐረግ ያላቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት የታሪካችን መነሻ ለማድረግ የፈለጉን እንደሆነ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻና መጥጠሪያ ልናደርገው ስለማይቻል አባባሉ እርማት ሊደረግበት ይገባል፡፡ መላው ዓለም የሚያውቀው የዓለም ሥልጣኔ መሠረትና ምንጭ የሆነው የግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከግብጽ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ የጥንት ግብጾችና ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት የኩሽ ዘር ስለሆነ ፣ ከአሁኖች የግብጽ ነዋሪዎች /ዐረቦች/ ይልቅ፣ የጥንታዊት ግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ባለቤቶችና ወራሾች እኛ መሆናችን ሊሰማን ይገባል፡፡ የግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ የተጀመረው ከ 4000 /አራት ሺህ ዓመት/ ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ማለት ከዛሬ 6000 /ስድስት ሺህ ዓመት/፡፡ የኢትድጵያ ታሪክም ከግብፅ እኩል ወይም ቀደምትነት ያለው በመሆኑ ቢያንስ 6000 ዓመት ታሪክ አለን ማለት እንችል ነበር፡፡ በዚህም ሳንወሰን በዘር መጠሪያችን መሠረትም በብሉይ ኪዳን ኩሽ የኖረው ከክርስቶስ ልደት 6000 /ስድስት ሺህ/ ዓመት በፊት ስለሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ የተጀመረው ከዛሬ 8000 /ስምንት ሺህ / ዓመት በፊት ነው ለማለት እንችላለን፡፡

በታሪክ ሂደት እንኳ ብናየው የኩሽ ወይም የካም ኢትዮጵያውያን ዘሮች በኢትዮጵያና በግብጽ ብቻ ተወስነው አልኖሩም፡፡ ነጮች /አሪያኖች/ ወደ አውሮፓ ከመፍለሳቸው በፊት የካም ወይም የሴም ዘሮች አውሮፓ ሰፍረው እንደነበሩና የመጀመሪያ የሥልጣኔ መሠረት እንደጣሉ በታሪክ ጸሐፊዎች የሚታመንበት ጉዳይ ነው፡፡ የታሪክ አባት ተብሎ የሚጠራው ግሪካዊ ሄሮዶቱስ በግሪክ ሀገር ነጮች ከመስፈራቸው በፊት ነዋሪዎቹ ፐላስጂ Pelasgi የተባሉ ከአፍሪካ ወይም ከእስያ ፈልሰው የመጡ የካም ወይም የሴም ዘሮች ነበሩ ብሉ ጽፎዋል፡፡ ከእነሱ ሌላ ከአፍሪካና ከእስያ የመጡ ግሪክ ሀገር የሰፈሩ 1ኛ. ቄክሮፕ Cecrope ፣ 2ኛ ዳናዎ Danao ፣ 3ኛ. ፔሎፕ Pelope 4ኛ. ካድሞ Cadmo የተባሉ የካም ወይም የሴም ዘሮች ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ የኢትዮጵያን ጥንታዊነትና ገናናነት ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳየን ነው፡፡ አፍሪካውያን ስለ አውሮፓ ባህል ሥልጣኔና ታሪክ የጻፉት ነገር የለም፡፡ ባንፃሩ ግን አውሮፓውያን ስለ አፍሪካ ብዙ ጽፈዋል፣ አሁንም እየጻፉ ናቸው፡፡ በተለይም ስለጥንታዊት ግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ብዙ አስተያየቶች ሰንዝረዋል፡፡ ከነዚህ አስተያየቶች መሐል ጥቂቶቹ ሀገር ጐብኚዎችና ታሪክ አጥኚዎች አፍሪካን ተዘዋውረው በጐበኙበት ጊዜ የግብጽ ሥልጣኔ መሰል ምልክቶች በመላው አፍሪካ ተስፋፍቶ ነበረ በማለት አስተያየታቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ ነገር ግን ሌሎች የግብጽ ታሪክ ተመራማሪዎች ይህ ከዚህ በላይ የተሰጠው አስተያየት ትክክል አለመሆኑን አስተውለው፣ ነገሩ የተገላቢጦሽ መሆኑን ገልጸው ጽፈዋል፡፡ ይህ ማለት ከግብጽ ወደ ሌላው አፍሪካ ሳይሆን፣ ግብጽ ከሌሎች አፍሪካውያን የሥልጣኔዋን መሠረት እንዳገኘች የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ የቁሳቁስ ምልክቶች ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ ኢትዮጵያውያንን የሚመስሉ ቀያይ ሰዎች መገኘታቸው የግብጽ ግዛት በመላው አፍሪካ

ተስፋፍቶ እንደነበረ የሚጠቁም ነው በማለት ተተችቷል፡፡ ነገር ግን ይህ አባባልም ትክክል እንዳልሆነ ተቃራኒ አስተያየት ተሰንዝሮበታል፡፡ በመላው አፍሪካ የተገኙ የግብጽ ሥልጣኔ መሰል ቁሳቁሶች ከግብጾች ተሠርተው የተሠራጩ ሳይሆን የአፍሪካውያን የራሳቸው የፈጠራ ውጤት መሆኑን በብዙ ተመራማሪዎች የታመነበት ጉዳይ ሆኖዋል፡፡ ግብጻውያንን የሚመስሉ ቀያይ ሰዎች በመላው አፍሪካ ቢገኙም ግብፆች ግይሆኑ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ታምኖበታል፡፡

እኛ ከምናስበው በላይ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያውያን በአፍሪቃ በሰፊው ተሠራጭተው ስለነበረ በዘመናችን አፍሪካውያን የኢትዮጵያ ደም የሌላቸው አይገኙም፡፡ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ያልተከለሱ፣ ያልተበረዙ የኩሽ ዘሮች የሚገኙባት ብቸኛ ሀገር ብትሆንም አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ከሌሎች አፍሪካውያን ዘር የተደባለቁ ናቸው፡፡ በንግሥት ሳባ ጊዜ የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን እንደዛሬ ከግብጽና ከኢትዮጵያ መሐል ሱዳን ሳትፈጠር ፣ ከቀይ ባሕር ግብጽ ወደ ሰሜን መሐል ገብቶ ከበረኒስ /Berenice / ከኤኳተር በስተሰሜን ከ24 ዲግሪ ከምድር ወገብ፣ ግለት ከራስ ባናስ / Ras Banas/ ጀምሮ፣ እስከ 20 ዲግሪ ደቡብ ከምድር ወገብ የመጽሐፍ ቅዱስ /እሬር/ የዛሬዋ ሶሮላ ይደርስ እንደ ነበረ የእንግሊዝ ሙዚየም /ብሪቲሽ ሙዚየም/ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሚስተር ቤንትና /Mr. Bent / ሌሎችም ምሁራን ገልፀውታል፡፡ ሚስተር ቤንትን በመጥቀስ ኢጣሊያዊ ሻለቃ ፐሪኒ /Perini /[1] "መረብ ምላሽ" በሚል አርእስት በደረሰው መጽሐፍ እንደተነገረው፣ ለንግሥተ ሣባ ወደ ኢየሩሣሌም እንድትጓዝና ከንጉሥ ሰለሞን ጋራ እንድትገናኝ መርከቦች የተሠሩላት በሶሮላ ወደብ ነበረ፡፡

የታሪክ አባት ሔሮዶቱስ የግብጽ ስርወ መንግሥት ከተመሠረተ ጀምሮ እስከ 18ኛው ስርወ መንግሥት /ዲናስቲ/ ግለት ከክርስቶስ ልደት በፊት 3400 እስከ 17888 ዓመት፣ 330 ነገሥታት እንደነገሡና ከእነሱ ውስጥም 18 ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ጽፈዋል፡፡ በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ በግብጽ ታሪክ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተች ያስረዳል፡፡ ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙ ጣሊያኖች እንኳን፣ ግብጽ የመጀመሪያ የሥልጣኔ ጮራ ያገኘችው ከኢትዮጵያ ነው ብለው ጽፈዋል፡፡[2]

የኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፈው በኤውሮፓውያን ነው፡፡ ኤውሮፓውያን ዛሬ በሥልጣኔ በጣም የተራቀቁ ናቸው፡፡ ያገራችንን ታሪክ በመፃፋቸው በእጅጉ ውለታ የሰማናል፡፡ ይሁን እንጂ ችሎታ ቢኖረን ያገራችን ታሪክ ራሳችን ብንጽፈው ይመረጣል፡፡ ዛሬ አውሮጳውያን በመላው ዓለም በሥልጣኔም በኃይልም፣ በበጎ ሥነ ምግባርም የመሪነትን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን የሥልጣኔ ጀማሪዎች አይደሉም፡፡ የዘመናዊ ሥልጣኔ ጀማሪዎችና አንጋፋዎች ግብፆች ሲሆኑ፣ ከእነሱ ቀጥሎም አሲሮ-ዛቢሎናውያን ነበሩ፡፡ ከእነሱ ቀጥሎም ይሁዶች ነበሩ፡፡ እንዲሁም በጥንታዊ ሥልጣኔ በተደምትነት የሚጠሩ ፊኒሲያኖች ነበሩ፡፡

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ሕዝቦች የከምና የሴም ዘሮች ነበሩ፡፡ ከእነሱ ቀጥሎ ግን የዓለምን ሥልጣኔ ወደ ላቀ ደረጃ ያደረሱ የነጭ ዝርያ ያላቸው መዲዮ ፐርሺያኖችና ግሪኮች ናቸው፡፡ በተለይ ግሪክ ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተችው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ግሪኮች በሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ በደረሱበት ጊዜ በሰሜን ድንበራቸው ወረራ ያደረጉባቸው

---

[1] Perini Mereb Melash p. 19-20

[2] La Formazione Impero Coloniale Italiano (F.I.C.I) V.I p 62



የነበሩ፣ ኋላ ቀር ዘላን የነጭ ዘሮች .."ባርባሪያን".. /ኋላ ቀርና ጨካኞች / ብለው ይጠሩዋቸው ነበር፡፡ እንዲሁም ግሪክኛ ቋንቋ መናገር የማይችሉ ሁሉ ሮማውያንም ጭምር "ባርባሪያን" ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ዛሬ ባርባሪያን ተብለው ይጠሩ የነበሩ ሕዝቦች የዘመናችን የተራቀቀ ሥልጣኔ የመሪነቱን ቦታ ይዘዋል፡፡ ግሪክ ግን በኤውሮጳ ወደ መጨረሻ ደረጃ ትገኛለች፡፡

300 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የግሪክ ሥልጣኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረበት ጊዜ ከውጭ ኃይል እንቅፋት ባያጋጥመው ኖሮ፣ ዓለም በበለጠ ፍጥነት በሥልጣኔ ተራምዶ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት አስቀድመን አሁን ያለንበት የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ በደረስን ነበር፡፡ መንግሥታውያን ከተሞች እውቀትን ለማስፋፋት ብቻ የተመሠረቱ መሆናቸውን የሚያሳይ አቋም ለብዙ ሺህ ዓመታት ይዘው ከኖሩ በኋላ፣ በመጨረሻ በማከሴዶናዊ ንጉሥ ፊሊጶስና በልጁ በታላቁ እስክንድር አንድነታቸውን መሥርተው ኃይልኛ ማእከላዊ መንግሥት ባቋቋሙበት ጊዜ፣ የጥንታዊት ግሪክ ባህል በተለይ የሥነ ጽሁፍ ኤለኒክ ይባል የነበረው "ኤሊኒስቲክ" ተብሎ ጥራቱ ያነሰ ሆኖ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ግን ግሪክ በተጠናከረ ሁኔታ ለመላው ዓለም የዕውቀት ማእከል ለመሆን በቅታ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚሁ ጊዜ ከግሪክ በስተምዕራብ በሮም በኃይል ብቻ የሚያምን ዕ ውቀት አልባ አንድ ጠንካራ መንግሥት ተመሥርቶ ግዛቱን በማስፋፋት ላይ ይገኝ ነበር፡፡ አውሮፓውያን ሁሉ የሮማ መንግሥት አክብሮትና አምልኮት እንዳላቸው እውቃለሁ፡፡ ነገር ግን በገለልተኛ ዓይን ሲታይ የሮማ መንግሥት ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተው ነገር ቢኖር ከጥቅሙ ጉዳቱ በጣም እመዝኖ ይገኛል፡፡ የሮማ መንግሥት ታሪክ ሲታይ የግሪክን ሥልጣኔ ታሪኳንና ነፃነቷን ለማጥፋት ባጠቃላይ የዓለምን ሥልጣኔ ለማውደምና ለመቀልበስ የተመሠረተ ይመስላል፡፡ የግሪክን ሥልጣኔ ማውደም የጀመረው በደቡባዊ ኢጣሊያ፣ በግሪክ አስተዳደር ዓይነት የተቋቋመው በዕውቀትና በሀብት የበለፀጉ መንግሥታዊ ከተሞች ነበሩ፡፡ እነዚህ ከተሞች በቋንቋና በባህል ግሪካዊ ሆነው፣ አጠቃላይ ስማቸው /ማኛ ግሪቺያ/ /ትልቋ ግሪክ/ ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን ፅዋ የቀመሰችው በደቡባዊ ኢጣሊያ የምትገኘው የግሪክ ትልቋ መንግሥታዊ ከተማ በጣሊያንኛ ታራንቶ TARANTO ባላቲኒኛ ታራንቱስ TARANTUS በግሪክኛ ታራስ TARAS ተብላ የምትጠራ ነበረ፡፡ ታራንቶ የተቆረቆረችው ከስፓርታ የፈለሱ ግሪኮች ከክርስቶስ ልደት በፊት በ708 ነበረ፡፡ ከ10 ዓመታት መከላከል በኋላ በሮማውያን እጅ የወደቀችው ለ436 ዓመት ግሪካዊት መንግሥታዊ ከተማ ሆና ከቆየች በኋላ በ270 ነበረ፡፡ ከታራንቶ ጋራ ሌሎች በደቡባዊ ኢጣሊያ ይገኙ የነበሩ የግሪክ አነስተኛ መንግሥታዊ ከተሞች በሮማውያን እጅ ወደቁ፡፡ 68 ዓመት ከታራንቶ መውደቅ በኋላ፣ ሮማውያን የግሪክ ሥልጣኔን በአጠቃላይ የዓለም ሥልጣኔን ለማውደም ከፈጸሙዋቸው ወንጀሎች ትልቁ በሲሲሊ ደሴት የምትገኘውን ዝነኛዋን የሲራኩዝ የግሪክ መንግሥታዊ ከተማን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ200 ዓመት በቁጥጥራቸው ሥር ማድረጋቸው ነው፡፡ ሲራኩዝ በእውቀት ማእከልነቷ በእኩል ደረጃ ከአቴናና ከእስክንድሪያ ትወዳደር ነበር፣ በሕዝብ ብዛት ግን በአንደኝነት ደረጃ ነበረች፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4ኛ ምዕተ ዓመት ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ ይኖርባት ነበር፡፡ ከታላላቆች ዜጎቿ መካከል ዝነኛው የሂሣብ ምሁር አርኪመደስ ነበር፡፡ አርኪመደስ ከሰር አይዛክ ኒዮቶንና ከአልበርት እንስታይን እኩል ደረጃ የታላቅ ሳይንቲስት ስም ተሰጥቶታል፡፡ የእሱ ግኝቶች ለ17 ምእተ ዓመታት ተረስተው ከቆዩ በኋላ እንደ አጋጣሚ በሶስተኛ ወገን ለኤውሮጳውያን ቅጅ

ከተገነባችበት ጊዜ ለዓለም ሥልጣኔ አስተዋጽኦ ማድረግ ቀርቷል፡፡ ይህ ማለት የዓለም ሥልጣኔ ለ17 ምዕተ ዓመታት ወደ ኋላ ቀርቷል ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሲራኩዝ ሮማውያን እጅ በመውደቋና አርኪመደስ በሮማዊው ወታደር በግፍ በመገደሉ ምክንያት ነው፡፡[1] ሲራኩዝ በሮማውያን እጅ በወደቀችበት ወቅት አርኪሚዲስ ከተማዋን ከሮማውያን ወረራ ለመከላከል እቅድ እያወጣ ነበር፡፡ ሮማውያን ከተማዋን በተቆጣጠሩት ሰዓትም አርኪሚደስ ቤቱ ውስጥ ሆኖ የጂኦሜትሪ ሥዕል ይሠራ ስለነበር ሮማዊው ወታደር አቤቱ ውስጥ ሲገባ እንዳይረብሸው ቢጠይቀው ወታደሩ ተናዶ ገደለው፡፡ ዛሬ ሲራኩዝ ከሲሲሊ ደሴት 9 አውራጃዎች አንዷ ብትሆንም፣ በ1987 ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ የነዋሪዎቿ ብዛት 123,000 ሆኖ ከ9ኙ የአውራጃ ከተሞች በ4ኛ ደረጃ ትገኛለች፡፡

ሮማውያን የዓለምን ሥልጣኔ የማውደም ሥራቸውን በመቀጠል የደቡባዊ ኢጣሊያ እና ደሴቶቿ ይዞታቸውን ካጠናከሩ በኋላ ዋናው ጠላታቸውና ተቀናቃኛቸው የነበረችው ዝነኛዋና ትልቋ አፍሪካዊት ሀገር ካርታጅ "ፑኒክ" ጦርነቶች ተብለው በሚጠሩ በ119 ዓመታት ውስጥ ሶስት ዙር ጦርነቶች ካካሄዱ በኋላ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ146 ዓመት ከተማዋን በተቆጣጠሩ ጊዜ በዓለም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በእሣት ከማጋየታቸው ሌላ፣ ዳግም እንዳታንሰራራ በግረሻ አረሷት፡፡ ካርታጅ በጊዜው ከነበሩ ኃያላን መንግሥታት አንዷ ነበረች፡፡ ግዛቷ በሰሜን አፍሪካና በሜዲተራንያን ብቻ ሳትወሰን እስከ ምዕራብ አፍሪካ ጊኒ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅ አውሮፓ እስከ ባልቲክ ባሕር ይደርስ ነበር፡፡ ካርታጅ የተቆረቆረችው በፊኒሳውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ850 ነበር፡፡

በ146 ክክርስቶስ ልደት በፊት ነበር የግሪክ ነፃነትም ማብቂያ የሆነው፡፡ ግሪኮች ከሮማውያን ለመከላከል በመጨረሻ በኮሪንት ተሰብስበው ጦርነት ገጥመው ነበር፡፡ ነገር[1] ግን ግሪኮች ስለተሸነፉ ኮሪንት ተቃጥላ ሀብቷም ወደ ሮም ተዘርፎ ተወሰደ፡፡ በጊዜው ይኖር የነበረው ታዋቂው የግሪክ ታሪክ ፀሐፊ ፖሊቢየስ POLIBIUS [1] ስለ ግሪክና ካርታጅ አወዳድሮ በማወዳደር ሲጽፍ ምንም እንኳን ካርታጂያውያን የደረሰባቸው ጥፋት ከግሪኮች የበለጠ ከባድ ቢሆንም እንዳንድ ሰው ግን በግሪኮች የደረሰ ውድመት ከካርታጂናውያን እያንስም እንዲያውም ይበልጣል ይላሉ ምክንያቱም ካርታጂናውያን በሙሉ ከገፀ ምድር የጠፉ ስለሆነ የሚያፍሩበት ምክንያት አይኖርም፣ ግሪኮች ግን ውርደታቸው ለልጆቻቸው የሚተላለፍ ስለሆነ ከካርታጂናውያን የበለጠ የሚያሣዝኑ ናቸው፡፡

በትምህርት ማእከልነቷ በዘመኑ ከነበሩት ታዋቂ ታላላቅ ከተሞች አንዷ የነበረችው የግብጽ እስክንድሪያ፣ በተለይም በዝነኛው ቤተመፃህፍቷ፣ የምሁራን መሰብሰቢያ ማእከል ሆና ስታገለግል የነበረችው፣ የሌሎች ታላላቅ ከተሞች ተመሣሣይ እጣ በሮማውያን ወራሪዎች ሣይደርሳት ብዙ ጊዜ አልቆየችም፡፡ በ48 ከክርስቶስ ልደት በፊት ጁሊየስ ቄሣር የሥልጣን ተቀናቃኙ ፖምፒዮስን ለመውጋት ወደ ግብጽ በዘመተበት ጊዜ ከፋፍለህ ግዛ በሚለው የቆየ የሮማውያን ፍልስፍና ለሥልጣን ሽኩቻ ይታገሉ ከነበሩት ሁለት የግብጽ መሪዎች ክሊዎፓትራን በመደገፍ ግብጾችን እርስ በርስ በማዋጋር እንዳለ ዝነኛው የእስክንድሪያ ቤተመፃህፍት ስለተቃጠለ

---

[1] New Standard Encyclopedia VA 1965

[1] Calogero Fazio Corso di Storia V.1 p. 205



አገልግሎትና ሕልውናው አቷርጠ ፣ የዓለም ሥልጣኔም ለብዙ ዓመታት ወደ ኋላ እንዲመለስ ሆነ፡፡

በአውሮፓውያን የታሪክ ፀሐፊዎች "ሚድል ኤጅስ" Middle ages የተባለው የታሪክ የጨለማ ዘመን ግማሹ የክርስትና የሃይማኖት እምነት በሚላን አዋጅ መሠረት ማንም ሰው እንዲያምንበት በይፋ የተፈቀደበት ቀን /313 ዓ.ም./ የጨለማ ዘመን መጀመሪያ ብለው ሲቆጥሩ ፣ ሌሎች ደግሞ የመጨረሻ ምዕራባዊው ሮማዊ ንጉሥ ነገሥት ከሥልጣን የወረደበት ቀን /476 ዓ.ም./ የዘመኑ የመጀመሪያ መቁጠሪያ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ስሕተት ነው፣ ምክንያቱም በተጠቀሱት ሁለቱ ዘመናት የዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ እንዲመለስ ወይንም ወደ ጨለማ ዘመን እንዲገባ የሚያበቃ የተሠሩ ልዩ ክንዋኔዎች የሉም፡፡

የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን የገባ ወይንም ወደፊት እንዳይራመድ እንቅፋት የሆኑበት ምክንያቶች ከላይ የተጠቀሱ ዘመናት ሳይሆኑ የግሪክ ነፃነት ያከተመበት ዓመት /146 /፣ ካርታጅ ከገፀ ምድር የጠፋችበት ዘመን /146/ መሆን ይገባዋል፡፡ ወይንም ደግሞ አርኪመዲስ በሮማዊ ወታደር የተገደለበት ዘመን፣ ሲራኩዝ በሮማውያን እጅ የገባችበት ጊዜ /202 ከክርስቶስ ልደት በፊት/ የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን እንደገባ ብለን መቁጠር ብንጀምር የበለጠ ትርጉም ይኖረው ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ በደቡባዊ የዛሬዋ ኢጣሊያ ከግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች አንዷ ታራንቶ በሮም እጅ ከወደቀችበት ዘመን ጀምሮ /270 ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስክንሪያ ቤተመፃህፍት እስከተቃጠለበት ዘመን 48 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት ዓመታት ውስጥ የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን ገባ ብለን በማሰብ "የሚድል ኤጅስ" የመጀመሪያ የመቁጠሪያ ዘመን ቢደረግ መሠረት ያለው አቆጣጠር በሆነ ነበር፡፡ ሮማውያን የዓለምን ሥልጣኔ አውዳሚዎች ናቸው እንጂ ገምቢዎች አይደሉም፡፡ ሮማ የምትታወቀው የዓለም አቀፍ መንግሥት ዋና ከተማ ለተወሰነ ጊዜ በመሆኗ ነው፡፡ የሮማ ታሪክ ወራሽ መሆን የሚገባው ዓለም አቀፋዊው የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ነው፡፡ ጣሊያኖች ሮማውያን ነን እያሉ ይኩራሩበታል፣ ሐቁ ግን ሮማ የዓለም አቀፍ መንግሥት ዋና ከተማ ነበረች እንጂ በተለይ የኢጣሊያ ዋና ከተማ አልነበረችም፡፡ ሮማ በኢጣሊያ ሀገር መገኘት ለኢጣሊያ ያበረከተችው ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም የለም፡፡ ሮማ አንድ ብሔራዊ መንግሥት በኢጣሊያ ምድር እንዳያቈጠቊጥ አውደሚ ሚና ተጫውታለች፡፡ በመጀመሪያ በኢጣሊያ ምድር ቀደምት ኗሪ ጐሣዎች ለምሣሌ በሊጉራውያን ወይንም በኢትሩትካውያን መሪነት ብሔራዊ ስሜት ያለው መንግሥት እንዳይቋቋም ሮማ እንቅፋት ከመሆንዋም በላይ ቋንቋቸው ባህላቸውን አጥፍታለች፡፡ ኢታሊክ Italic የሚባል ጐሣ ከሄሌኒክ የሚዛመዱ፣ ላቲኖች በተለይም ሳኒዎች የተባሉ ጐሣዎች ወዘተ... በኢጣሊያ ምድር ብሔራዊ መንግሥት ለማቋቋም ያደረጉት ሙከራ በሮም አምባገነናዊ አገዛዝ ሁሉም ቋንቋቸውና ባህላቸው ጠፍቶ በማያንሠራሩበት ሁኔታ ተደመሰሱ፡፡ ስለዚህ ሮም ካርታጅናውያን ብቻ አላጠፉችም፡፡ ~~ዛሬ ኢጣሊያዊ ተብለው የሚጠሩ አብዛኛው ከሮማ ፍጆት~~ የተረፉ ጐሣዎች ናቸው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ከተቋቋሙ የባርባሪያን አዲስ መንግሥታት አስቀድማ ኢጣሊያ የራሷ መንግሥት ለመመሥረት በቻለች ነበር፡፡ ጣሊያኖች ሁሉ ግን ሮማዊነት ስለሚሰማቸው በሮም ተጨፍጭፎ ታሪካቸው ከምድረ ገጽ የጠፋ ሕዝብ ጠላታቸው አድርገው በመገመት ይደሰቱበታል፡፡

ሮማውያን ማለት የአንድ ጎሳ ስምም አልነበረም፡፡ የ 3 ጐሳ ቅልቅል ናቸው፣ እነሱም ራሚ Rammi = Latini ላቲናውያን 2ኛ. Tizii = Sabini ሳቢናውያን 3ኛ. Luceri Etruschi ኢትሩስካውያን የተባሉ ናቸው፡፡ ጥቂት እረኞች ይኖሩባት የነበረች የሮማ ስም ነው፣ ትርጉሙም ከወንዝ አጠገብ ማለት ነው፡፡ ሮማውያን የራሳቸውን ቋንቋ አልነበራቸውም፡፡ በጉረቤታቸው በላቲኖች ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር፡፡ በዘራቸው የ3 ጐሳ ቅልቅል ሲሆኑ፣ በባሕል በኩል ብዙ ነገር ከኢትሩስካውያን የወረሱት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሮማ የኢጣሊያ በተለይ ዋና ከተማ አልነበረችም፣ ለምሣሌ ቪየና ፣ ሊዝቦን ፣ ማድሪድ፣ ፓሪስ፣ ለንደን፣ በርሊን የየሀገሮቻቸው በፖለቲካ በአስተዳደር በትምህርት በኢኮኖሚ ማእከል በመሆን ነው ያደጉና አገልግሎት የሰጡ፡፡ ሮማ ግን ለኢጣሊያ ማእከል ሆና አታውቅም፣ በኢጣሊያ አንድነት ትግል እንደማእከል፣ መሣቢያ ሆና አላገለገለችም፡፡ ኢጣሊያ አንድነቷን አግኝታ ከተቋቋመች በኋላ የጥንታዊት ሮማ ዝና ለማግኘት ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ ግዛት በኃይል ነጥቃ ነው ኢጣሊያ እንደተለጣፊ የራሷ ዋና ከተማ ያደረገቻት፡፡

የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች ምዕራባዊው የሮማ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከማከተሙ በፊት /476/ ማንኛውም የሮማ መንግሥታት ከማድነት ከኢጣሊያ ብሔራዊ ጥቅም አኳያ ይወሰዷቸው የነበሩ እርምጃዎች ከማድነት በስተቀር ሊተቹ አይታዩም፡፡ የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች በቁጭት የሚጽፉት ከ476 ዓ.ም. በኋላ በኢጣሊያ ስለተቋቋመው የባርባሪያን መንግሥታት ነው፡፡ የመጀመሪያ ባርባሪያን መንግሥት በኢጣሊያ የተቋቋመው በአድሪያቲክ ባሕር የምትገኘው በራቬና ዋና ከተማ በማድረግ በኢዶዋከሬ መሪነት ነበረ፡፡ ይህ በትክክል ጎሣው የማይታወቀው ባርባሪያን መሪ በራሱ ወታደሮች ለአመጽ አነሣስቶ የመጨረሻ ምዕራባዊ ንጉሠ ነገሥት ሮሙለሥ አውግስተስ አውርዶ ራቅ ያለ ቦታ ወስዶ ወደ እስር ቤት ካገባው በኋላ፣ ራሱን ዝቅ አድርጉ በመገመት ባርባሪያን እንደመሆኑ መጠን ንጉሠ ነገሥት መሆን የማይገባው፣ የማይችልና ህግ እንደማይፈቅድለት በማመን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስምሥራቃዊው ንጉሠ ነገሥት ዜና በመላክ አስረከበ፡፡ ይህ 476 ዓ.ም. ምዕራባዊ የሮም ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ፍጻሜ ተብሎ በታሪክ ይታወቃል፡፡ ኢዶዋከሬ ፓትሪሲያን /እንደራሴ/ የሚል ማዕረግ ከንጉሠ ነገሥት ዜና ተሰጥቶት ይገዛ ነበር፡፡ ኢዶዋከሬን አሸንፎ ሥልጣን የያዘ የኦስትሮጉቶች መሪ ቴዮዶሪክ Teodoric ነበር፡፡ እሱም እንደ ኢዶዋከሬ በምሥራቅ ንጉሠ ነገሥት ስም ኢጣሊያን ከአስተዳደረ በኋላ በ526 ዐረፈ፡፡

የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች በቁጭት የሚተቹት ኢዶዋከረና ቴኦዶሪክ ስምሥራቃዊ ንጉሠ ነገሥት ዜና በማጉብደድ ፋንታ የራሳቸው ዘውድ ጭነው ሥልጣን ቢይዙ ኖሮ በኢጣሊያ ምድር አንድ ኢጣሊያዊ መንግሥት ይመሠረት ነበር በማለት ነው፣ ምዕራባዊ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትም ህልውናው ሣይቋረጥ ይቀጥል ነበር ይላሉ፡፡

የቀድሞ ቀኝ ገዥዎቻችን ጣሊያኖች ከስር መሠረታቸው ማወቅ ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አባቶቻችን የሚሏቸው ሮማውያን ካርታድናውያንን እና ሌሎችን ሕዝቦች ከምድረ ገጽ እንዳጠፉ ሁሉ እኛንም ለማጥፋት እቅድ አውጥተብን እንደ ነበረ ማስረጃዎች አሉን፡፡ እንኳንስ የሰው ልጅ አውሬዎችም ዘራቸው እንዳይጠፉ መከላከያ ይደረግላቸዋል፡፡ ካርታጂናውያንም በሮማውያን ተፈጅተው ከምድረ ገጽ ሲጠፉ የጥንት ግብፃውያንም ከዓረቦች ወረራ በኋላ ባህላቸው ዘራቸውንና ቋንቋቸው ከዓረብ ጋር ተደባልቆ ጠፍቷል፡፡ በእኛ ላይ ከዚህ የባሰ ወንጀል ለመፈጸም እመቺ ጊዜና ሁኔታ ነበር ይጠባበቁ የነበረ፤ የተመቸ ጊዜ ግን ሳይመጣ ስለቀረ እኛ



ከአደጋ አመለጥን፡፡ የቀድሞ ቅኝ ገዢዎቻችን ሀገር ኢጣሊያ በሃዘመናት የወጣላቸው በሬዎች ሰዎች አፍርታ በከፍተኛ ኃላፊነትንና በታላቅ አስቀምጣቸዋለች፣ አከብራቸዋለች፡፡ ፀረ ዘረኛነት ወይንም የበጎ አድራጊ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ አቋም ያላቸው ሰዎች ግን አፍርታ አታውቅም፡፡ ይህ ነው ደግሞ ከሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ልዩ የሚያደርጋት፡፡

ጥንታዊት ግብጽ ስትመሠረት ጀምሮ፣ ከመመሥረትዋ በፊትም ኢትዮጵያ ሥልጣኔዋን በመጋራት እንደኖረች እንደ ሄሮዶቶስ የመሳሰሉ ታሪክ ፀሐፊዎች ሌሎችም ይመሰክራሉ፡፡ አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ [1] በጻፈው መጽሐፍም ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ፣በግብጽ 25ኛ ስርወ መንግሥት /ዲናስቲ /፣ብዙ የኤውሮፓ ታሪክ ፀሐፊዎችን በመጥቀስ የፈርኦን ዘውድ ጭነው ግብጽን እንደገዙ መዝግበዋል፡፡

ግብጽና ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ጉረቤት ቢሆኑም በጣም የተለያየ የመሬት አቀማመጥ አላቸው፡፡ ግብጽ ሜዳማ በመሆኗ እንዲሁም ሶስት ክፍላተ ዓለም አገናኝ በመሆኗ /ማለት አፍሪካ፣ እስያና ኤውሮፓ/ ለውጭ ወራሪዎች፡፡ የተጋለጠች ስትሆን ኢትዮጵያ ግን ተራራማ በመሆኗ ለውጭ ጠላት ወራሪ አትመችም ይህም በመሆኑ ግብጽ በረጅም ጊዜ ታሪኳ ብዙ ወራሪ ኃይሎች ደፍረዋታል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1090 ጀምሮ አሲራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ ፐርሲያውያን እንዲሁም ኢትዮጵያውያንና ሊቢያውያን በየተራ ግብጽን ወረው ገዝተዋል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ332 ታላቁ እስክንድር የግዛቱ አንድ ክፍል አድርጓታል፡፡ በ30 ከክርስቶስ ልደት በፊት የሮማ የግሪክ Bizantine ግዛት ሆነች፡፡ በ616 ዓ.ም. በፐርሲያኖች ተወራ ተያዘች፡፡ በ639 ዓ.ም. በዓረቦች ተይዛ እስላማዊት ዓረባዊት ሀገር ሆነች፡፡ በ1517 ግብጽ በቱርክ ኦቶማኖች አገዛዝ ሥር ወደቀች፡፡ በ1798 ቀዳማዊ ናፖሊዮን ግብጽን ከያዘ በኋላ በእንግሊዝ አስገዳጅነት ሊለቅ የአልባንያ ተወላጅ መሐመድ ዓሊ ከ1801 ጀምሮ ለ40 ዓመታት ግብጽን ገዝቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋራ በጉርብትናም በሃይማኖትም የጠበቀ ግንኙነት ቢኖራትም የግብጽ መነሣትና መውደቅ የበይ ተመልካች ሆና ከማየት በስተቀር ወራሪዎች ከግብጽ አልፈው ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ጊዜ የለም፡፡ 1 ኢትዮጵያ ግብጽን ብቻ ባይሆን ከጥንት ጀመሮ የነበሩ ኃያላን መንግሥታት እንደ ባቢሎናውያን፣ አሲራውያን፣ ሮማውያን፣ ቢዛንቲናውያን፣ ኦቶማን ተርኮች ወዘተ... ሲወጡና ሲወርዱ አይታለች፡፡ በቅርብ ጊዜም ቀንደኛ ጠላቶቿ የኢጣሊያና የጀርመን አምባገነን አብሪተኞች ዓለመን ሙሉ በግፍ ለመግዛት ሲነሱና ሲወድቁ አይታለች፡፡ ያለ ኢጣሊያ በስተቀር ኢትዮጵያን ለመያዝ የተመኘ ሀገር የለም፡፡ መጠነኛ ሙከራ ያደረጉት ቱርክና ግብጽ ብቻ ነበሩ፡፡ እነሱም በቀላሉ በኢትዮጵያ ጦር ተሸንፈው ከሀገራችን ወጥተዋል፡፡ ኢጣሊያኖች በአውሮፓ በውትድርና ጀግንነት ጥሩ ዝና እንደሌላቸው የታወቀ ነው፣ ለዚህም ማስረጃ መጥቀስ ቢያስፈልግ በ2ኛ የዓለም ጦርነት ጊዜ ኢጣሊያ ትንሿን ግሪክ ማሸነፍ

---

[1] አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ አክሱም ዛጉዬ 1ኛ [illegible] ገጽ 118-119

አቅቷት፣ ጀርመኖች ጣልቃ ሲገቡ ግን ሣምንት ባልሞላ ጊዜ የግሪክን ጦር መደምሰስ መቻላቸው የጣሊያኖች ደካማነት አሣይቷል፡፡

ኢትዮጵያን ለመያዝ ግን ኢጣሊያ የተሳካላት አንድ ዘዴ ይዛ ነው፡፡ ይኸውም የጥንት ሮማውያን ዋና መፈክራቸውና ዘዴያቸው የነበረው የከፋፍለህ ግዛ ስልት በመጠቀም ነው፡፡ በዚሁ ዘዴ ባይጠቀሙ ምሽጋችን ዘሆኑት በተራራዎቻችን ገብተው አሸንፈውን ሊገዙን ባልቻሉ ነበር፡፡ ጣልያኖች ጥሩ ተዋጊዎች ካለመሆናቸው ሌላ በቅኝ አገዛዝም ልምድ አልነበራቸውም፡፡ ከሌሎች ልምድ መውሰድም ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ ምክንያቱም ሮማውያን ነን እያሉ አጉል ትምክህተኝነት ስላላቸው ነው፡፡ ጣሊያኖች ባለፈው ጊዜ እርስ በርሳችን በማጣላት ተሳክቶላቸው የቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ከመብቃታቸው ባሻገር አሁንም እርስ በርሳችን የምንፋጀው እነሱ በመሐላችን አቀጣጥለውት በሄዱት መርዝ ነው፡፡

ከዚህ በመነሣት ነው ጣልያኖች በቅኝ ግዛት ሲያስተዳድሩን በነበረ ጊዜ ያደረሱብንን በደል ባጭሩ በዚሁ መጽሐፍ የምዘረዝረው፡፡ ታሪካችን ከጣሊያን ቅኝ ገዦች ጊዜ የተጀመረ አይደለም፡፡ ታሪካችንም ጠንቅቀን ማወቅ ግዴታ እንደለብን ለማስገንዘብ የኢትዮጵያ ታሪክ ዋና ዋና ክንውኖች ባጭሩ አቅርቤያለሁ፡፡



# ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ታሪክ
## ምዕራፍ አንድ ጥንታዊት ኢትዮጵያ

### 1. የኢትዮጵያውያን ጥንታዊነት

የኢጣሊያ መንግሥት የአሰብን ወደብ ለመግዛት ከባላባቶቹ ጋራ በተደራዳሪነት የረዳው ሣፔቶ የተባለው ኢጣሊያዊ ቄስ ቀደም ሲል በተደራዳሪነት... ሊጉሪያ የተባለው የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር ጊሊዮናዊ የነበረ ነው፡፡ ሳፔቶ ሊጉሪያ የተባለው የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር ከስፈሩት ጉሣዎች ቀደምትነት ተወላጅ ነው፡፡ ሊጉራውያን በኢጣሊያ ሀገር ከስፈሩት ጉሣዎች ቀደምትነት ያላቸው ናቸው፡፡ አርያኖች ወይንም ከሙካዚያኖች ነገዶች አይደሉም፡፡ ዝርያቸው አውሮፓ ከመስፈራቸው በፊት እስያ ይኖሩ የነበሩ ናቸው፡፡ ዝርያቸው በደንብ ተለይቶ የማይታወቅ ቢሆንም የሴም ወይንም ካም ዘሮች እንደሆኑ ይገመታሉ፡፡ የኢጣሊያን ስም በመላ ዓለም ያስጠሩት በመርከብ ሥራና በባህር ጉዞ ሙያ ነው፡፡ አሜሪካን ያገኘ ሰው ክሉምቦስ ሊጉሪያዊ ነው፡፡ ሌላ አርያን ነጭ ያልሆኑ ኤትሩስካን የተባሉ ጉሳዎች የኢጣሊያ ሥም ገናና ያደረጉት በኪነ ጥበብና ሥነ ጽሁፍ ነው፣ ለኢጣሊያም ቋንቋ የፈጠሩ እነሱ ናቸው፡፡ ሳፔቶ ስለሀገራችን ግዛናዊ የሆነ በጉ አመለካከት የነበረው ሰው ነው፡፡ ይኸውም ለመገመት የሚቻለው /ኢትዮጵያ[1] በተባለው በደረሰው መጽሐፉ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ከገጽ 3 እስከ 17 ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት እና የሥልጣኔ ቀደምትነት ያቀረበው ጽሁፍ ከዚህ በታች ዋና ዋና ነጥቦችን ለአብነት እጠቅሳለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ግብፃውያን ታሪክ ቀደምትነት አለው ብለው ከሚያምኑ አንዱ ፕሮፌሰር ሳፔቶ ነው፡፡ በአንፃሩም ኢጣሊያዊው ዋና የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂ ተብሎ የሚታወቀው ኮንቲ ሮሲኒ ይህ አባባል ከማይቀበሉት አንዱ ነው፡፡ ሳፔቶ ወደ ኢትዮጵያን የግብጽ ሥልጣኔ በኩር ልጅ ብሎ ይጠራታል፡፡ ሳፔቶ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ሶሪያ በነበረበት ጊዜ ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች የጥንት ሥልጣኔ በሚገባ አጥንቷል፡፡ የኢትዮጵያ ሥልጣኔና ታሪክ ከነዚህ አገሮች በማነፃፀር ነው የሚያስቀምጠው፡፡ የዛሬ ኢትዮጵያውያን ዝቅተኛ የድህነትና የጉስቁልና አኗኗር ሲታይባቸው፣ በጥንት ጊዜ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ደርሰው እንደነበሩ ማመን ያዳግታል፡፡ በኢትዮጵያ ምድር የሚታዩ የጥንት ከፍተኛ የሥልጣኔ ምልክቶች ብዙዎቹ የታሪክ ፀሐፊዎች ከውጪ የመጡ ሰዎች የገነቡዋቸው ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ እኛም በጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ራሳችን እንደ አክሱም ሐውልት የመሳሰሉት አባቶቻችን ተሠርቷል ብለን ደፍረን ለመናገር እንቸገራለን፡፡ ፕሮፌሰር ሳፔቶ ግን ኢትዮጵያውያን ራሳቸው የከፍተኛ የጥንት ሥልጣኔያቸው ባለቤት እንደ ነበሩ ማስረጃ በማቅረብ ይደመድማል /ገጽ 9/፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ አሁን የሚኖርበት የኋላ ቀር የቤት አሠራር፣ ከሚጠቀሙባቸው ልብሶች፣ ቁሳቁሶች፣ የሥነ ጽሁፍም ባለመኖሩ ሲታወቅ በጣም ኋላ ቀር ጥላቸው፣ የታሪካቸውና የነገሥታታቸው ከበሬታ ከተረት አያልፍም ነበር፡፡ የሕዝቡም አኩሪ ሥራ፣ ዘራቸው ከፍ ለማድረግ የሌላቸውን ሙያ በልበ

[1] G Sapeto Ethiopia p. 3-17

ወለድ ታሪክ ዝና ለማግኘት የፈጠሩዋቸው ናቸው ለማለት ግንም ሰው በቻለ ነበረ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያውያን በኢትኖግራፊ፣ ቋንቋ፣ ህግጋት፣ ባህል ዘለቅ እድርጉ ለመረመረ ሰው ሁሉ በህግ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በነገሥቶቻቸው ትልቅነት በሐውልቶቻቸው ግዙፍነት በመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች ታሪክ ውስጥ ዝነኞች ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ባይሆን ኖር ግማሽ የሰው ልጅ የሲቪል፣ የሀይማኖት፣ የባህል ታሪክ መካድ ያስፈልገን ነበር፡፡ ሄሮዶትስን፣ የጥንት ግብፃውያን ቀሣውስት ታሪክን መካድ ያስፈልገን ነበር፡፡ ሳፔቶ የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች የጥንት ሥልጣኔ ያጠናና በጥልቀት የተመራመረ በመሆኑ ስለ ኢትዮጵያ በጽሁፎቻቸው የሚያወሱ ባገኘው እውቀት መሠረት እነዚህ ሕዝቦች በግጥሞቻቸው፣ በተረቶቻቸው ኢትዮጵያውያን ኃይለኞች አግልክቶች እንደ ነበሩዋቸው፣ ከፍተኛ ቤተ መቅደስና ቤተመንግሥቶች እንደ ነበሩዋቸው፣ የተደራጀ የጦር ኃይልና ሰፊ ንግድ እንደነበራቸው፣ በፖለቲካና በሀይማኖት በግንበር የመኖር ባህል በዓለም ጀግሪዎች መሆናቸውን የሚገልፁ የተረት ግጥም ጽሑፎች መካድ ያስፈልገናል ብሏል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያን ትልቅነት ለመካድ ታሪካቸው መካድ ያስፈልጋል፡፡ ታሪካቸው ግን በሀውልቶች፣ በቋንቋ፣ በሀውልቶች የተቀረጹ ጽሁፎች የማያሻማ ማስረጃ ያለው ታሪክ ነው፣ የታወቁና የተከበሩ የታሪክ ምሁራንን ያረጋገጡት ነው፡፡ ከክርስትና በፊት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣን የሚያገኙት ከእግዚአብሐር መሆኑን የሚገልጽ በግዕዝ የተፃፈ ጽሑፍ በአክሱም ይገኛል፡፡ እንደ አንዳንድ የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች የኢትዮጵያ ነገሥታት ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ልዩ ፍጡር ሆነው ባይቆጠሩም ሥልጣናቸው ከእግዚአብጤር የተሰጠ መሆኑን ኢትዮጵያውያን እምነት አላቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረው የእስራኢላውያን ዓይነት የመንግሥት ሥልጣን እስከ ቅርቡ ጊዜ ድረስ በኤሮፓ ከነበረው የነገሥታት መለኮታዊ ሥልጣን ብዙ ልዩነት የለውም፡፡ ሩቅ ሣንሄድ አጼ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት በማስታወስ ሥዩመ እግዚአብሐር ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብለው ሲጠሩ እንደነበረ እናውቃለን፣ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ሴቶች ነገሥታት ሳይሆኑ በወንድ ነገሥታት ብቻ ለብዙ ጊዜ በመገዛት ኢትዮጵያ በዓለም ብቸኛ ሀገር ያደርጋታል፡፡ እንደ እስራኤላውያን ሠለሞናዊ መለኮታዊ በወንድ ነገሥታት ብቻ የተሠረተ አገዛዝ በኢትዮጵያም የመጀመሪያ ልጅ የወንድ ልጅ ብቻ ንጉሣዊ አገዛዝ ከእግዚአብሐር የተሰጠ ነው ተብሎ ይታመንበታል፡፡ ማንኛውም ወንድ ልጅ ለመጀመሪያ ልጅ ሥልጣን ቢነጥቅ ሕገ ወጥ እያሰኝም፡፡ በሴቶች ከተያዘ ግን ሀገ ወጥ ይሆናል፡፡ ከማን እንደተጀመረ ይህ ደንብ በውል ባይታወቅም ንግሥተ ሣባ ያወጣችው ደንብ ነው ብለው የሚያምኑም አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከንግሥተ ሣባ በፊት ከእስራኢላውያንም በፊት የተለመደ ደንብ ነው ይላሉ፡፡ ከኢትዮጵያውያን የመጣ ባህልና የንጉሣውያን መዛግብቶች መሠረት አንድ ዕብራዊ አዛርያስ የተባለው ቄስ ከሙሴ ብሉይ ኪዳን ህጐች የይሁዳዊ ንጉሣዊ ህገ መንግሥት እንደመጣ ይናገራሉ፡፡ ከፍልስጥኤም ነገሥታት ደምብ ቀዳማዊ ሚኒልክ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ እንደ ይሁዳውያን ዳዊትና ሰለሞን ሥልጣን ሰጥቶት እንደቀባው ያምናሉ፡፡ የሰው ሥልጣን ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ፣ ዘግ አውጪ ዘግ አስፈፃሚ ብቻ እንደነበረ እና በመለኮታዊና መንፈሳዊ ሥልጣን ከእግዚአብሐር የሚያገናኝ ስለሆነ የቄሶች ተግባር እንደነበረ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ነው የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደጥንታዊት ግብጽ ጥንታዊት ፐርሲያና እንደ እለፈው ሮማዊ ጳጳስ መንግሥት ንጉሡ መንፈሳዊ ሥልጣን የሌለው፡፡ ክርስትና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ነገሥታት



የእግዚአብሐር ልጆች ተብለው የተጠሩበት ጊዜም ነበረ፡፡ ለዚህም ማስረጃ ሊጠቀስ የሚቻለው በአክሱም ሐውልት የሚገኘው ጽሑፍ ከይፀናና ሳይፀና የግርስ /አርፃስ/ ልጆች እያሉ እንደግብፃውያን ፈርኦኖች የእግዚአብሐር ልጆች ተብለው ይጠሩ እንደ ነበር ነው፡፡ ከክርስትና በኋላ ግን በአክሱምና ኑቢያ ሀውልቶችና ጽሑፎች የእግዚአብሐር ልጆች አይባሉም፡፡ ሆኖም ሥልጣናቸው ከእግዚአብሐር እንደተሰጣቸው አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ በተግባር የሚታየው መንፈሳዊ አባቶችና ቄሶች በመሾምና ከሥልጣን በማውረድ ቤተክህነትን በንጉሡ ፍርድ ቤት በማቅረብ ጣልቃ ገብነት ይታያል፡፡ ይህ ግን ለንጉሡ ሕገ ወጥ ተግባር አይቆጠርበትም፡፡ ምክንያቱም በሲኖዶስ የቤተ ክህነት ህግ ንጉሡ መጠቀም ስለሚችል ጣልቃ ገብነት ሀጋዊ የሚያደርጉ አንቀጾች በህግጋቱ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ ሥልጣን በመጠቀም ነው አፄ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ሀይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት እንዲሆን. ያዘዙ ምክንያቱም የሀጉ አንቀጽ የንጉሡ ፈቃድ የህዝቡም የሀገሪቱም መሆኑን ያዛል፡፡ የሱሲኒዮስ ልጅ አፄ ፋሲለደስ በመብቱ ተጠቅሞ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን እና ኢትዮጲያዉያን ካቶሊኮች እንዲገደሉ አድርጓል አፄ ቴዎድሮስም በዚሁ ህግ ተጠቅሞ ካቶሊክ እርቶዶክስም ቄሶች መነኮሣት ራሱ ፓትሪያርኩም ይሾምና ይሽር ነበር፣ ይኸም ሆኖ በኢትዮጵያ ምን ጊዜም ንጉሡ እንደመለኮታዊ ተቆጥሮ አያውቅም፡፡ ከሃይማኖት ድጋፍ ቢያገኝም በሥልጣኑ ቢጠቀምበትም ፈላጭ ቆራጭነቱ የሰው ልጅ በመሆን ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ በሌሎች የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች የታየው የጭቆና አገዛዝ አልተከሰተም፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሣዊ አገዛዝ ልዩ ባህርይ በሌሎች ሀገሮች እንደታየው የውጭ ዜጋ ወይም ዘር የሆነ መሪ /ንጉሥ/ በሥልጣን የወጣበት ጊዜ የለም፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታት የነገሡባት ሀገርና ሕዝብ እንደ ባዕድ ጠላት በጦርነትና ዘመቻ የተገኘ ለባርነት፣ ለከባድ ግብር መጠቀሚያ፣ እሲያም ለእልቂት መዳረግ የተከሰተበት ወቅት የለም፡፡ የኢትዮጵያ ትልቅነትና ጥንታዊነት ብሉ ከሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ፐሮፌሰር ሳፔቶ ነገሥታት በአክሱም የነገሥታት ዘውድ ሲጭኑ ይደረግ የነበረ እክባበር ነው፡፡ ለዚህም የአጼ ሱሱኒዮስ ለምሣሌነት ይጠቀሳል፡፡

## 2. የአጼ ሱሱኒዮስ መንገሥ ሥነ ሥርዓት

ምንም እንኳን የመንግሥቱ ዋና ከተማ ጉንደር ብትሆንም አጼ ሱሲንዮስ አዲስ የአስተዳደር ዘመን ለመፍጠር በማሰብ ተረስቶ የነበረው የጥንት ነገሥታት የሥልጣን መረከብ ሥነ ሥርዓትና ከመንፈሳዊ ቅባት ጋራ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ መጫን እንደገና ታጅቦ እንዲከበር ወሰነ፡፡ በምሥራቃውያን ንጉሠ ነገሥታት እለባበስ ዓይነት አሸብርቆ ሌሎች የመንግሥት ሹሞች በሙሉ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ የአለባበስ ውበት አሸብርቀው ወደ አክሱም ተጓዘ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ቡኒ ቀለም ጨርቅ ለብሰዋል፡፡ በቀኝ እጁ መስቀል ጨብጧል፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት በትረ መንግሥት ብርቅና ውድ የሆኑ ቁሣቁሶች በተሸለመ ፈረስ ጀርባ ወጥቶ የአጀቡ ለልፍ ይመራ ነበር፡፡ በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት እንደደረሰ በእግሩ ወደ መሬት ወረደ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ልጃገረዶች የቤተክርስቲያን በር ደረጃዎች ለመውጣት ሲሞክር በደረጃዎች ላይ ነጭ ልብስ የለበሱ ልጃገረዶች ወደ እሱ በማምራት መንገዱን በመዝጋት “ማንነህ አንተ በአክሱም ቤተክርስቲያን መግባት “የምትፈልግ” ብለው በመጠየቅ ጥሶ

እንዳይገባ ከለከሉት ሰጥያቄው ንጉሠ ነገሥቱ "እኔ የእናንተ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነኝ" ብሎ መሰሰላቸው፡፡ ልጃገረዶቹም "አይደለህም አንተ የእኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አይደለህም" አሉት፡፡ ለሶስት ጊዜ በዚህ ዓይነት ለመግባት ሞከሮ ልጃገረዶቹ እንዳይገባ ከለከሉት፡፡ በአራተኛ ጊዜ "እኔ የጽዮን ንጉሥ ነኝ" በማለት ቤተመቅደሱን ለሚጠብቁ ልጃገረዶች በመናገር ጉራዴውን አውጥቶ መጋረጃውን ቀዶ ሲገባ እልልታና ጭብጨባ በማሲንቆና በክበሮ የታጀበ በቀድሞ ጊዜ ያለፉት ነገሥታት ይቀቡበት የነበረ የተቀደሰ ድንጋይ ተወሰደ፡፡ የምሁራን ዜማ ጭፈራ፣ የካህናት ቅዳሴና ፀሎት እያደረጉለት በእግዚአብሔር ስም ኢትዮጵያን እንዲመራ ለክርስትና ሀይማኖት እምነት ለመድከም ተቃራኒዎችንም ለማጥፋት ከግለ በኋላ ከአክሱም ቤተክርስቲያን ጳጳስ እጅ ሹመቱንና በትረ መንግሥቱን ተቀበለ፡፡ በፕሮፌሰር ሳፔቶ አባባል የኢትዮጵያ ነገሥታት ዋና ከተማ ከአክሱም ወደ ላሊበላ፣ ወደ ሸዋ ጎንደር መዛወር ሕዝቡ በነገሥታቱ አክብሮትና ከእግዚአብሔር የተቀቡ መሆናቸውን መቀበል እንደሚቀንስ ጽፏል፡፡ በመቀጠል ሰፔቶ እንደሚያስበው የኢትዮጵያ ነገሥታት በጦር ኃይል ሥልጣናቸው ለመጨበጥ ቢችሉም ዋና ከተማውና መቀመጫቸው ወደ አክሱም ካላዛወሩ በቀር የአክሱም ንጉሠ ነገሥት ወይም የጽዮን ንጉሠ ነገሥት ተብለው በአክሱም ዘውድ ጭነው ካልተቀቡ በቀር እንደ ድሮ ጊዜ ሥልጣናቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሆኑን በሕዝቡ ፀንቶ ሊኖር አይችልም፡፡ በሮማም የዚህ አይነት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው፡፡ የሕዝቡ ስሜት ያወቀ ይመስላል ልጅ ካሣ የነበረው የትግራይ መስፍን ንጉሠ ነገሥት በሆነበት ጊዜ በአክሱም ሥርዓተ እንጋገሥ እንዲከበር ያደረገው፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት በአውሮፓ እንደ ተከሰተው በሕዝብ ዐመጽ አልተደመሰሱም፡፡ ደግሞ በምሥራቃውያን ነገሥታት እንደተፈጠረው በመጥፎ ሥነ ምግባራቸው ከሥልጣን አልወረዱም፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣናቸው እየቀነሰ የመጣ በነገሥታት ችሎታ ማነስ፣ አርቆ መመልከት ማነስ፣ እንዲሁም ደካማ በመሆናቸው የተነሳ ነው፡፡ የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ብቻ ማድረግ ሲገባቸው ለበታች ሹሞች በማስረከባቸው ነው፡፡

## 3. የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ሞገስ

ከዛሬ ጉስቋላ ሹሞች ሳይቀሩ የሣር ቤቶች ኑሮ የማይጣጣም፣ በቋንቋ፣ በንግግር የተዋበ አነጋገር እና በሥነ ሥርዓት ጥንታዊነታቸው ምልክት የሆነው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት አቀባበልና ሥነ ሥርዓት ከጥንት የዓረብ ቤተ መንግሥቶችና ከቀድሞ የስፔይን በዓለም ኃይለኛ መንግሥት ደርሳ በነበረችበት ጊዜ የነበረው ውብ ሥነ ሥርዓት የሚወዳደር ነው፡፡ ለተመልካች ግልጽ ሆኖ የሚታየው በጥንት ጊዜ የኢትዮጵያ የተዥ መደብ በቋንቋ ንግግር ከፍተኛ ውበት እንደነበረው ሁሉ በባህልና በፍትህ፣ አቀባበል ሥነ ሥርዓት በሀብት ከበለፀጉ እና ከተደራጁ ሀገሮች የሚወዳደር ነበር፡፡ ሳፔቶ ለግለረጃነት ራፍሬይ የተባለው ደራሲ አጼ ዮሐንስ ለፈረንሣዩ ምክትል ቆንስል ያደረገው አቀባበል ሥነ ሥርዓት ይጠቅሣል፡፡ አቀባበሉ እውነትም ከፍ ያለ ነበረ፡፡ በአንድ ድንኳን መጨረሻ ዳር በተዋቡ ምንጣፎች ላይ የተዘረጋ አልጋ ላይ እንደ መለኮት ተኩራምቶ በወርቅ የተዋበ በባርኖስ ተሸፍኖ ሶስት ጊዜ የወርቅ ዙሪያ ያለው ዘውድ በራሱ አጥልቆ ንጉሠ ነገሥቱ ተቀምጦ ነበረ፡፡ በዙሪያው በክብ ረጅም ቀይ ጨርቅ በወርቅ የተዋበ በራሳቸው የወርቅ ዘውድ ያጠለቁ ራሶች ነበሩ፡፡ ከእነሱ በስተኋላም በእጃቸው



ጦር፣ የጨበጡ በክንዳቸው ጋሻ የያዙ፣ ትክሻቸው በአጉራ ቆዳ የተሸፈነ ጥሩር የለበሱ ራሳቸው ባዶ፣ ጠጉራቸው የተሠራ እና ቅቤ የተቀባ ብዙት ያላቸው መኳንንቶችና ጦረኞች ቁመው ነበሩ፡፡ በዚሁ ሥነ ሥርዓት ምንም የቀረ ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ልዩ ምልክት የሆነ የቆየው አንበሳም አልቀረም ነበረ፡፡ እሱም በነፍሱና በሥጋው ሙሉ በሙሉ ነፃ ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ከጌታው እግር ተኝቶ ይታይ ነበር፡፡ ቢያንስ የሚባለው ሴላ ኢጣሊያዊ፣ ሀገሩን ለጉብኝት የመጣ ከአጼ ዮሐንስ የተደረገለት አቀባበል እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡ ግቢው 3 ትላልቅ የግርማዊነታቸው ቤቶች የያዙ ነበረ፡፡ ቤቶቹ ከሌሎች በሀገሩ ውስጥ ከሚሠሩ ቤቶች የተሻሉ ትልቅ በደህና የተገነቡ የተሻሉ፣ ጽዳት ያላቸው ናቸው፡፡ የመጨረሻው ቤት ለግርማዊነታቸው መኝታ ክፍል የሚያገለግል ንፁህ ክፍል ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ግንቦቹ 6 ሜትር ርዝመት ያላቸው በጭቃና በግር የተሠሩ አንዳንድ ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው ኢትዮጵያውያን በሚጠቀሙበት ቢሚያኑ የተሠሩ ነበር፡፡ አጼ ዮሐንስ ቁጭ ብለው ነበር ወይንም እንደ ሐበሾች ተቆራምደው ተቀምጠው ነበረ፡፡ ሐበሾች እንደ ቱርኮች ዓይነት በትንሽ አልጋ መቀመጥ ያዘወትራሉ፡፡ አልጋው በሰፌ ምንጣፍና በጨርቅ ልብስ የተሸፈነ ነበረ፡ በእነዚያ የሹማምንቶች ጉጆ ቤቶችም ሆነ በንጉሠ ነገሥቱ ሕንፃዎች ብዙት ያላቸው በተለያየ ስም የሚጠሩ ባሰባቶች የተሞላ ነበረ፤ ማለትም የቤተ መንግሥት ዘቦች፣ አሽከሮች፣ የእልፍኝ አስከልካይ፣ የክብር ዘቦች የሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች፣ እንግዳ ተቀባዮች፣ የጦር አለቆች ፤ የሲቪል ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ ቄሶች፣ የደብር አለቆች፣ ደብተራዎች፣ ሌሎች፣ የቤተ ክህነት ትምህርት አዋቂዎች፣የከዋክብት አዋቂዎች ወዘተ...፣ በሌሎችም አለቃና አዛዦች አሏቸው፡፡ ግብዣው ከመጀመሩ በፊት የሚባርከውና በመጨረሻ ቡራኬ አስምቶ የሚያሰናብት ካህን ነበረ፡፡ ለንጉሠ ነገሥቱ ጥሬ ሥጋ የሚያጉርስ፣ መጠጦችን የሚያማስል፣ የሚያድል፣ ትርፍራፊዎችን የሚሰበስቡ ወዘተ ነበሩ፡፡

## 4. ፊዊዳሊዝም በኢትዮጵያ

ፊዊዳሊዝም በማእከላዊ መንግሥት ሙሉ በሙሉ የማይታዘዙ ከልላዊ አገዛዝ የሰፈነበት አስተዳደር ነው፡፡ በኢትዮጵያ የዚህ ዓይነት አስተዳደር የጀመረው ሰለሞናዊ ሐረግ የላቸው ነገሥታት ወርደው የዛጉዌ መንግሥት ሲመሠረት ነው፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ የውጪ ወረራና መሣፍንቶች የሥልጣን ሽኩቻ፣ የክፍለ ሀገሮች እርስ በርስ ቅራኔዎች፣ የሀይማኖት ክርክሮች፣ የአንዳንድ አለቆች እምባገነንነት ተፈጠሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የክፍለ ሀገሮች ዋና ከተማ፣ ዜጎችም ከንጉሣቸው የሚያስተሳስራቸው የነበረ አንድ መንፈስ ተቃወሰ የመንግሥት አንድነት ለመቃደራዊና የፊዊዳላዊ አገዛዝ ተሸነሸነ፡፡ በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ የፊዊዳሊዝም መጥፎ ተክል ተፈጠረ፡፡ ይህ ሁኔታ የአንድ ሀገር ሕዝቦች ከአንድ እናት ሀገር የተወለዱ ልጆች ሲሆኑ የተለያዩ ጉጣዎች መሆናቸው በማስመሰል የአንድ ሀገር ህዝብ እንደ ጠላት እንዳአደረጋቸው ፕሮፌሰር ሳፔቶ ዘግበዋል፡፡

## 5. የኢትዮጵያ ስም አጠራር

እኛ በምሥራቅ አፍሪካ የምንገኝ ሕዝቦች ስለታሪካችን አንዳንድ ውሱን ማስረጃዎች ለመስጠት ብንችልም በተለይ ስለስማችን አጠራር ግን የምናውቀው ነገር ምንም የለም፡፡ ሁሉም የውጭ አገር ሰዎች የሰጡን ስም ነው፡፡ አብዛኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያ ማለት በግሪክ ቋንቋ የመጣ ነው ይላሉ፡፡ ፊቱ በፀሐይ የተቃጠለ ሕዝብ ማለት ነው ብለው ይተረጉሙታል፤ ሀበሻ ማለት ደግሞ ድብልቅ፣ ህዝብ ነው ብለው ይተረጉሙታል፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው በነበሩበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት ስማችንን ትተው ኢጣሊያዊ ምሥራቃዊት አፍሪካ የሚል ስም ሰጥተውን በዚህ ስም በይፋ ስንጠራ ነበረ፡፡ ይህ ስም ኤርትራንና ሱማሊያን የሚያጠቃልል ነበረ፡፡ ስለስማችን አጠራር በሚመለከት የተሰጡት አስተያየቶች ከዚህ በታች ለማቅረብ ይቻላል፡፡

1ኛ. የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁር የሆነው ኮንቲሮሲኒ በ1937 ዓ.ም. በደረሰው መጽሐፍ የራሱ መንግሥት ያወጣው ስም "ምሥራቃዊት ኢጣሊያዊት አፍሪካ" የሚለው አጠራር ወደ ጐን በመተውና በመቃወም "ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ[1] በተባለው መጽሐፍ ከ3ቱ ከላይ ከተጠቀሱ ስሞች ኢትዮጵያ የሚል በመምረጥ ትክክለኛ ስማችን መሆን ያለበት ስለአመነበት አስፍሮበታል፡፡ 1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ይኖር የነበረው ታዋቂው የታሪክ ግጥም ደራሲ ሆሜር ሀገራችንን ኢትዮጵያ እያለ ገጥሞላታል፡፡ ከሱ በፊትም በመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ ስም ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የሚለው ስማችን ጥንታዊነቱ አያጠራጥርም፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ አበሻ ማለት በዓረቢኛ ቋንቋ ድብልቅ ሕዝብ ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው የሚለው አባባል ከእውነት የራቀ መሆኑን ጠቅሶ ሐበሻ የአንድ የትግራይ ጐሣ ስም መሆኑን ገልጿል፡፡ የሐበሻ ስማችን ከኢትዮጵያ ስማችን በጥንታዊነት ቀደምትነት እንዳለው ኮንቲ ሮሲኒ ጠቅሶ ኢትዮጵያ የተለመደው ከብርስትና ሲሆን አበሻ ግን ከክርስትና በፊት የምንጠራበት ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የተከለለች ከተፈጥራዊ ገጽታዋ አንድ ምድረ ገጽ አንድነት ያላት አገር ስትሆን ዋና አካሏ ግዙፍ የሆኑ ተራራማ በታዎቿ ናቸው፡፡ እንደዚሁም ጥልቀት ባላቸው የመሬት ቁፋሮ የተከፋፈሉ ከፍተኛ በታዎች ያላት አገር ናት፡፡ በምሥራቅ ቀይ ባሕር የአደን ባህረሰላጤና የህንድ ውቅያኖስ ያዋስኗታል፡፡ በምዕራብ የሚያዋስኗት የናይል ወንዝና የናይል ሰፊ ቆላማ በታዎች ናቸው፡፡ በሰሜን የናይል ቆላማ በታ ቀጥሮ ሲሆን፣ እንደዚሁም በደቡብ የዚሁ ቆላማ በታ ቀጥ.ያ ያዋስኗታል፡፡ ኢትዮጵያ በዘርዋ በኩል ዋናው የኩሽ ህዝብ ሀገር ተብላ ልትጠራ ትችላለች፡፡ በሰሜን ከናይል ወንዝ በስተምሥራቅ እስከ መሀል እካልዋ የሆነ አንድ ክፍል ብቻ ተቆርሶበታል፡፡ ይህም ማለት ሰሜን ሱዳን ከሰላ አውራጃ ማለት ነው፡፡ በደቡብና ምሥራቅም ከዘሮችዋ አንድ ክፍል የሆነ ከትርብ ጊዜ ወዲህ ተቆርሶባት ይገኛል፡፡ ኬኒያና ጅቡቲ፡፡ አቢሲኒያ ሲባል በደቡብ በኩል አዋሽን የሚያዋስናት ሲሆን በዘርና በቋንቋን የኩሽና የሴም ቋንቋ የወሰዱ ሕዝቦች የሚኖሩባት ናት፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ሲባል በተፈጥሮ ምድረ ገጽና ዘር ክልል የሚያመለክት ሲሆን አቢሲኒያ ሲባል ግን የአንድ ታሪካዊ ሂደት ወይም ወቅት የሚገልጽ ነው፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች አውጥተውልን

---

[1] Conti - Rossini Ethiopia e genti d' Etiopia p 1-2



[illegible] 3ኛ ስም ግን በታሪክም ረገድ በቋንቋም በዘርም እጉል አጠራር ለሆን እንደ ኬኒያ ኡጋንዳ ታንዛኒያ የመሳሰሉት ምሥራቅ አፍሪካ ስላሉ፣ [illegible] የነበረ ፋሽስታዊ አገዛዝን ሣይፈራ ኮንቲ ሮሲኒ ወድቅ አድርጉታል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ በተጠቀሰው መጽሐፉ ስለ ኢትዮጵያ ወሰኖች አንስቶ ሲጽፍ ኢትዮጵያ ማለት በ3ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የተገኘው የኢትዮጵያ ማስረጃ ኢትዮጵያውያን ከሐበሻ መንግሥት በስተምዕራብ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው ብሎ መዝግቧል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ አጠራር በኢትዮጵያውያን እየተለመደ መጥቷል፡፡ ግሪኮችም ኢትዮጵያውያን ብለው የሚጠሯቸው በደቡብ የሚገኙ ህዝቦች እስከ አትላንቲክ ውቅያኖስ ነበረ፡፡ 2ኛ. አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ[1] ስለ ኢትዮጵያና ሐበሻ ስም አጠራር ጠቅሶ በፃፈው እንደፈረንጆች አባባል ሐበሻ ማለት የዘር ድብልቅ መሆኑ እንዳለ በመቀበል ነው፡፡ እንደዚሁም ሐበሻና ሌሎች የሴም ጐሣዎች ከዓረብ ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱ መሆናቸውን የሚለው የፈረንጆች አባባል እንዳለ በመቀበል ነው፡፡ አንድ የስም አጠራር በሚመለከት በሚጠራበት ህዝብ ተቀባይነት የሚያገኝ መሆን አለበት፡፡ ኤውሮጳውያን በእውቀት ከእኛ የሚበልጡ ስለሆኑ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ስለ ስማችን ትርጉም ከዓረብ ሀገር ስለመምጣታችን የሚነግሩን ታሪክ ምናልባት በቀላሉ እውነት መስሏቸው ሊቀበሉ ይችሉ ይሆናል፡፡ ሌላ ኢትዮጵያውያን ግን ከእምነታችን ውጪ የሆነ ይህ አባባል አይቀበሉትም፡፡ ከእምነታችንና ባህላችን ውጪ ስለሆነ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ተቀባይነት የለውም በእውነተኛ ታሪክ ይሁን በተሣሣተ ታሪክ ይሁን ባይታወቅም በሰሜን የሚገኙ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤል እንደሚወለዱ እምነት አላቸው፡፡ ከዓረብ ዘርያ እንዳለ ግን አያምኑበትም፡፡ ሐበሻ ድብልቅ ዘር መሆናችን የሚለው አባባል እንደተራ ስድብ ችላ ብለን ከማለፍ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሐበሻ ተብለን መጠራታችን እንኮራበታለን እንጂ አናፍርበትም፡፡ ይህ ነገር በስህተት ተደጋግሞ የተነገረ ነገር በጊዜ ብዛት እንደ ሀቅ ይወሰዳል የሚለው አባባል የተለጠፈብን የፈጠራ አተረጓጐም ከመሆን አያልፍም፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የደረሰው ዋና መጽሐፉ ከደቡብ ዓረቢያ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ዓረቦች መግባታቸውን በሰፊው የፃፈ ሲሆን፣ መልሶ ግን በሌላ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በሚለው መጽሐፉ ገጽ 44 ስለ ሐበሻ ሕዝብ ከዓረቦች በኩል መፍለሳቸው ያለው አስተያየት ሲጽፍ "ከእስልምና በፊት በዓረብ ሀገር ይኖሩ የነበሩ ዘፈኖች ተረቶች ሐበሻ እውነተኛ አፍሪካዊ ከዓረቦች የተለየ ተብሎ ይወሰድ ነበረ፡፡ ምን ጊዜም ከዓረብ ፈልሰው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ገቡ ስለሚባሉ ሕዝቦች ከዓረቦች የተጠቀሰ ነገር አይገኝም" ሲል ይህ አባባሉ ግን እርስ በርሱ የሚጋጭ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ዓረቦችና ኢትዮጵያውያን የማይቀበሉት ከኤሮፓውያንም በቂ ማስረጃ ያልቀረበበት የዓረብ ክልስ ተብለን መጠራታችን ተገቢ አይመስለኝም፡፡

3ኛ. ስለአበሻ ስማችን ጥልቅ ምርምር ያካሄደው ሰው ፈረንሳዊው ዣን ደረስ ነው[2] በአፍሪካ ቀንድ የሚል እርእስት መጽሐፉ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዓመት በጥንታዊት ግብጽ የተደረገው የባህር ጉዞ በቴብ ቤተ መቅደስ ተቀርጾ የሚገኘውን ታሪካዊ ስዕል በሚመረምርበት ጊዜ ነበረ፡፡ ይህ 5 መርከቦች ያቀፈ 350 ሰዎች ባህረተኞች ተካፍለውበት የነበረ ኮንቲ ሮሲኒ በዓለም የመጀመሪያ ትልቁ የባህርና የምድር ገጽታ (ጂኦግራፊ) ጉዞ ብሎ

---

[1] ተክለ ፃድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ አክሱም ዛጉዌ. ገጽ 16-18

2 Jean Doresse Histoire Sommaire de la Corne Orientale d'Afrique p 56


ሰይሞታል፡፡ ይህ ታሪካዊ ጉዞ ለማዘጋጀት ስሟን ታዋቂ ያደረገው አታሱ /ራማካ/ ማካራ ተብላ የምትጠራ ንግሥት በትሆን፣ እንደንግሥት የራሷን ሐውልት እንድታሠራ፣ በራስዋ ስም ቤተመቅደስእንድታሠራ በ18ኛው ዲናስቲ የቱትሞሲስ 1ኛ ልጅ ናት፡፡ የቱትሞሲስ 3ኛ እህትና ሚስትም ናት፡፡ መርከቦቹ የሄዱበት ሀገር ምን ይባላል ወደ ሚለው ጥያቄ ስንገባ አምላኩ አሞን ንግሥቷን በማመልከት የተናገረው ቃል ኛን ዶሬስ የሄሮግሊፍ ጽሁፍ ከአጠና በኋላ አምላኩ አሞን ሀገሩ የፑንት ሰዎች ነው፣ የሐበሻ ሀገር ነው፣ የእግዚአብሔር ሀገር ነው ብሏል፡፡ በስዕሉ የሚታዩ የሴቶች አለባበስ በዛሬ ጊዜ በምሥራቅ ወሎ የሚገኙ የኦሮሞ ሴቶች አለባበስ የሚመስል ነው፡፡ ሕዝብ የሚለው ቃል የግብጽ ታሪክ ምሁራን በስህተት እስከ ዛሬ ድረስ ግብፃዊ ቃል በማሰብ እንደ አራቾች ወይም እንደጢግሞች ይተረጉሙት ነበር፡፡ ይህ አጠራር ግን የሐበሻ ሕዝብን የአክሱም መንግሥት ከመሠረቱት አንዱ ሲሆን የበድብ አጠራር ዓረብኛ ቋንቋ ድብልቅ የሚለው ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ አቢሲኒያ ተብላ ትጠራለች፡፡ በጥንት ጊዜ ዓረቦች ቀይ ባህርን <u>“ባህር አል ሐበሻህ”</u> ብለው ይጠሩት እንደነበረ ኮንቲ ሮሲኒ[1] ባአወጣው የጥንት ጂኦግራፊ ካርታ ያስረዳል በዚሁ መሠረት ንጉሥ ኢዛና የአቢሲኒያ ንጉሥ ተብሎ ነበር ይጠራ ነበረ፡፡ የግብጽ ባህረተኞች የሠፈሩበት ትክክለኛ ቦታ፣ ከሀገሩ ሀዝብ ያደረጉት ግንኙነት ወዘተ...፣ በቤተመቅደሱ የሚገኙ ስዕሎች አተረጓጉም መሠረት በማድረግ ከላይ የጠቀስኳቸው 3 የታሪክ ፀሐፊዎች የበጡት ሃሣቦች ብቻ በማተኮር ከዚህ በታች የአንዳንድ አስተያየት አቀርባለሁ ፡፡ 1/ አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ እንደሚለው ሀታሱ ንግሥት ወታደሮችዋን ወደ ፑንት ልካ እንዳስመታች፣ ከፑንት መሰፍን ፓሪሁ ጋራ ተዋግተው እንደአሸነፈችና እንደ ማረከች ክዚያ የሚያስፈልጋቸውን እጣን፣ ከርቤ፣ ሽቶ፣ የዝሆን ጥርስ ወዘተ... ከባሪያዎች በርፈው ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱ /ቴብ/፣ ከተማረኩትም በሃል የሀገሩ መሪ ፓሪሁ እንደ ነበረ ቦታውም በኡጋዴን በአውሣ፣ በሶማሌ እንደነበረ በማለት ደምድመዋል፡፡ 2/ ኮንቲ ሮሲኒ የግብጽ ወታደሮች የሁለቱ ሀገሮች /ፑንትና ግብጽ/ የጋራ አምላክ የሆነው በአሞን ትእዛዝ ወደ ፑንት ሀገር በሰላም እንደደረሱ ያመለክታል፤ ገፀ በረከት በሰላማዊ መንገድ ላገሩ ንጉሥ ለፓሪሁ እንደ አቀረቡ፣ ፓሪሁም በደስታ እንደተቀበላቸው፣ አቲ የምትባለው ሚስቱም በእህያ ወጥታ እንደ መጣች፣ ግብጾችን ሲቀበሏቸው ፓሪሁ የሚከተለውን ንግግር እንዳደረገ ይገልፃል፡፡ “በዚህ የግብጽ ሰዎች የማታውቁት ቦታ እንዴት መጣችሁ? በሰማይ ነው የመጣችሁት ወይንስ ከእግዚአብሔር ሀገር በመርከብ ነው እናንተ የመጣችሁት?፡፡ ከፀሐይ ነው ምክንያቱም ከግብጽ ንጉሥ ትንፋስ ተለይቶ መኖር አይቻልም፣ እኛም በእሱ ትንፋስ ነን የምንኖረው”፡፡ ከዚህ በኋላ የወዳጅነት ግንኙነት ይፈጠራል፡፡ የሚለዋወጡት እቃዎች ግብር የመክፈልና የማስከፈል ሣይሆን የንግድ ልውውጥ ማድረግ ይመስላል፡፡ ምንም እንኳን እንደማሊያኖች የተለመደ አነጋገር የፑንት ሰዎች “እንዲዝኒ” ብለው ቢጠሩቸውም የግብጾች ተልእኮ በሰላማዊ መንገድ የንግድ ልውውጥ እንደተፈፀመ አመልክቶ፣ ነገር ግን ወደ መጨረሻ ግብጾች ከሚንዋቸው ነገሮች የሀገሩ ሰዎች ከነልጆቻቸው በመርከብ ተጭነው ነበረ፡፡ ስለዚህ በመጨረሻ ግብጾች ሀገሩን እንደዘረፉና አንዳንድ ሰዎችን ለባርነት ማርከው እንደወሰዱባቸው ያስመስላል ብለዋል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ባህረተኞች ያረፉበት

[1] C, Conti - Rossini = Storia d' Etiopia tavola XV



L'Arabia del sud-ovest nei tempi antichi secondo dati epigrafici

ቀይ ባሕር በጥንት ጊዜ ስሙ ያበሻ ባሕር እንደነበረ የሚያሳይ ፎቶ ኮፒ ከኮንቲ ሮሲኒ Storia d' Etiopia tavola xv የተወሰደ



ቦታም በሚመለከት በቶካር ሰምሀር አካባቢ መሆን እንዳለበት ብሎ ደምድሞዋል። [1] ጀንዶሬስ የግብጽ መርከቦች የንግድ መሆናቸውን ከአመለከተ በኋላ ለወረራና ለዘረፋ የሚውል የጦር መሣሪያ እንዳልጫኑ፣ የሚሄዱበት ሀገርም ንግድ በሰላማዊ መንገድ የሚካሄድበት ሠላማዊ ወዳጅ ሀገር መሆኑን፣ ሀገሩንም የእግዚአብሐር ሀገር ተብሎ የሚጠራ ቅዱስ ሀገር መሆኑን የሁለቱ ሀገሮች /ግብጽና ፑንት/ የጋራ እግዚአብሐር በአሞን የሚያምኑ መሆናቸውን ይገልጻል። ባሀረተኞች ያረፋበት ቦታም በኤደን ባሀረ ሰላጤ አካባቢ መሆን እንዳለበት ገምቷል። ስለዚህ ዘረፋ ሊካሄድ እንደማይችል ይገመግማል፤ ይኸም ትክክለኛ አገላለፕ ይመስላል።

## 6. የኢትዮጵያውያን በጉሣ መከፋፈል

የኤውሮፓ ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያ የሚል ስም የሰጡን ግሪኮች ናቸው ትርጉሙም በፀሐይ ፊቱ የተቃጠለ ነው ብለን አምነን እንድንቀበል አድርገውናል። እንደዚሁም ካም የሚለው ስም የተሰጠን ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ተብሎ ተወስዷል። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን የነገሥታት ስም ዝርዝር ተብሎ የቀረበው ጽሁፍ እንደሚያመለክተው ከነገደ ዮቅጣን ኢትዮጵስ 1ኛ የሚባል ንጉሡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1771 ኢትዮጵስ 2ኛ በ1730 እንደነበረ ያመለክታል። ይህ ማለት ከግሪኮቹ ሆሜርና ሄሮዱቱስ 1000 ዓመት በፊት መሆኑ ነው። ካምና ኩሽ የሚል ስም የተሰጠንም እስራኤሎች መጽሐፍ ቅዱስ በሚጽፉበት ጊዜ ከግብፃውያን በመውሰድ ነው። በሀገራችን ፀሐፊዎች የቀረበ ጽሁፍ ትክክለኛ ያልሆነ ታሪክ ነው ብለን ልንክደው አንችልም፤ ምክንያቱም ከግሪኮች እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ያላነሰ ማስረጃነት አለው። አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ አክሱም፣ ዛጉዌ የሚለው መጽሐፉ በአጠቃላይ በደረሳቸው የታሪክ ግምገማዎች በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የመቃወሚያ ሃሣብን ለማቅረብ እገደዳለሁ 1ኛ. መሠረተ ሃሣብ ብሎ የያዘው የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የአክሱም ነገደ ሴም ዮቅጣን ከደቡብ ዓረብ ለመጡ ለአሁኑ መንግሥታችን ሥጣኔአችን ፊደላችን ቋንቋችን ዘራችን ልማዳችን መሠረትና አባት የሆነውና ንግሥተ ሣባና ሐበሻ የመጡባት፣ በአንፃሩም፣ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የምትባለው ኑቢያ ለዛሬው ሥልጣኔያችው ፊደላችን ቋንቋችን ልማዳችን መሠረትና አባት ያልሆነው የነገደ ካም ማለቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ልዩነት ቢኖር እንኳን የዘር ልዩነት አይደለም፣ የቋንቋ ልዩነት ብቻ ነው። ቋንቋም ቢሆን ኢትዮጵያ በሙሉ የአማርኛና የትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብቻ አይደለችም። ከደቡብ ዓረብ የመጡ የሚለው የማንቀበለው በባህላችን የሌለ ከተረት የማይለይ ታሪክ በመሆኑ ነው 2ኛ. ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ናፓታ ባይደርስም በመፅዋ አካባቢ በዘመቻ ከአክሱም ሄደው የሰፈሩበት ሣይሆን ከጥንት ጀምሮ ሀገራቸው ነው። ከየመን ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው የመጡ 3 ነገድ ተባብረው ነገደ ዮቅጣን ሳባ በትግሬ አበል በአፋር፣ አፊር በአጋዴን ሰፍረዋል። ራማ የሚባለው በጭቆና ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረ የሀንድ ንጉሥ አሸንፎ ነገደ ካም ብቻ ሰፍሮባት የነበረች ኢትዮጵያ ነፃ ስለአወጡ ነፃ አውጪዎች አግአዚያን ተባሉ፣ ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ የሚለው ታሪክ ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ 3 የዮቅጣን ልጆች ግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ነበር። አሁን በተግባር የሚታየው ግን ሣባ ብቻ የግዕዝ ተናጋሪ ሲሆን አባልና አፊር ግን በኩሽ የሚመደቡ አፋሪኛና

[1] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ibd ገጽ 26



ሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው። ታሪኩ እውነተኛነት ቢኖረውም በቋንቋ ሳይሆን በዘር ነው 3ኛ ሣባ ኢትዮጵያዊት መሆንዋ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ሀ/ መጀመሪያ እስዋ በነበረችበት ዘመን የደቡብ ዓረብ /የመን/ በታሪክ አትታወቅም ነበረ። ለ/ የኢትዮጵያ ምሁራን በታሪክ ነገሥት የቀድሞ ነገሥታት ስም ተብሎ የወጣ ስም ዝርዝር ከካም ነገድ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2404 የሣባ ስም ተጠቅሶ ይገኛል።[1] እንዲሁም ከነገደ ዮቅጣን ከክርስቶስ ልደት በፊት የሣባ ስም በ1985 ሣባ 2ኛ በ1871 ሐ/ በ1453 ሣቢ መ/ በ1036 ሣቢ ተብሎ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህ ማለት ከየመናዊት ሣባ ሀልውና በፊት በኢትዮጵያ የሣባ ስም የተለመደ እንደነበረ ነው የሚያሣየው። የየመን ሣባ ስም ለንግሥተ ሣባ ክብር ከኢትዮጵያ የተወሰደ መሆን አለበት። በአቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ የሁለቱ ሀገሮች የመንና ኢትዮጵየ ንግሥት ነበረች የሚል አስታራቂ ሃሣብም እናትና ልጅ በእኩል ደረጃ ማወዳደር ስለሚሆን ጥንታዊት አንጋፋ ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ ከትንሽዋ የመን ሣባ ማወዳደር ተገቢ አይሆንም። 4ኛ/ አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ ኢትዮጵያውያን የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት የእስራኤል የሙሴ ህግ ይከተሉ ነበር የሚለው ታሪክ፤ እንደዚሁም ላስታ አገው ነገደ ይሁዳ መሆናቸውን የሚለው ታሪክ አይቀበለውም። የኢትዮጵያ ነገሥታት በናፓታ የሚገኘው በአሞን ቀሣውስት እለቃ ተከታይ ነበሩ እንጂ እንዳንዶቹ የእኛ ሊቃውንት እንደሚሉት በኦሪትና በእግዚአብሔር የሚያመልኩ አልነበሩም በማለት አጥላልቶ ጽፈዋል። ስለአገው ነገደ ይሁዳ መሆናቸው ከአለቃ ታዬ የተፃፈው ታሪክም ሲታይ አለቃ ታዬ የአገውን ዘር ከዳዊት ከእስራኤል ንጉሥ የልጅ ማድረጋቸው ነው ይኸውም ሲሆን የአገው ዘር ኩሽ መሆኑ ቀርቶ ሴማዊ ሊሆኑ ነው ካለ በኋላ አለቃ ታዬ ለአፃፃፋቸው ይላሉ አሉ እንጂ አላረጋገጡም በማለት ጽሁፉን ደምድመዋል ገጽ 392። ነገር ግን አለቃ ታዬ ስለአገው ላስታ ነገደ ይሁዳ መሆናቸውን በግላቸው የፈጠሩት ታሪክ ሣይሆን የቆየ በሁሉም የታወቀ ታሪክ ነው። ምና መሠረታቸው ላስታ ሆኖ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ህዝቦች በዳሞት በጎጃምና በላስታ ብቻ አይደለም የሚገኙት። በኤርትራ አንድ አውራጃ ሠሉ /ሠራዬ/ ከላስታ የፈለሱ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ናቸው፣ እንደዚሁም ሉጉ የመሰሉ በሐማሴን በሠራዬና በአካለ ጉዛይ አውራጃዎች የሚገኙ፣ በተጨማሪም ሣሐርቲ የተባሉ በሐማሊን አውራጃ የሚጠቃለሉ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ናቸው። የዩዲት መነሣት ታሪክ የተከሰተው እንደሚባለው ከክርስትና በፊት የነበረ የእስራኤል የኦሪት ህግ ተተው አብዛኛው ህዝብ የክርስትና ሀይማኖት ሲቀበል በላስታ፣ በአገው በዳሞትና በሰሜን የነበረው ህዝብ ግን የክርስትና ሀይማኖትን መቃወም የተደረገ ጦርነት አስከፊና የሰው እልቂት እንደአስከተሉ ታሪካችን ይመሰክራል። በዩዲት ጊዜ ብቻ ሣይሆን በሌሎች የኢትዮጵያ ነገሥታትም እንደ አጼ መላክ ሰገድ በ1580 ዓ.ም. በሰሜን በተለይ በፈላሾች ላይ ዘመቻ በማድረግ ብዙ የሰው እልቂት ተፈጽሟል። ትዳሚ ይከበራል እዩከበርም በሚለው ክርክርም በየዘመናቱ ብዙ ውዝግብ አስነስቷል፣ የሰው እልቂትም አስከትሏል። ይህ ሁሉ የሚያሣየው የኢትዮጵያ ህዝብ ቅድመ ክርስትና የኦሪት ህግ ይከተል እንደነበረ ነው። ቀዳማዊ ሚኒልክ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰበት ጊዜ 12 ነገደ እስራኤል አጅበውት መጥተው እንደነበረ ይተረካል። ከነገደ ይሁዳ እላይ የተጠቀሱ ህዝቦች ሲሆኑ ከነገደ ሌዋዊም እንወለዳለን የሚሉም አሉ። እነሱም በኤርትራ በሐማሴንና

[1] ተክለፃድቅ መኩሪያ ገጽ 24

በአክሱማይ የሚኖሩ ናቸው፡ የእስራኤል ባህል በኢትዮጵያ መግባት በዚሁ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ እስከ አሁን የሚታየው የጋብቻ መሳሳትና የወንድ ልጅ ግርዝ ክርስትና ከመንግሥቱ በፊት፣ በጸናጽልና በከበሮ እየታጀቡ እየተወዛወዙ መንፈሳዊ ፀሎት ማድረግ ወዘተ ከእስራኤል የተወረሱ ናቸው። አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ከክርስትና በፊት በናፓታም ሆነ በአክሱም የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት እንዲሁም ህዝብ ህገ ኦሪት አልተቀበሉም ብሎ በመጽሐፉ በተደጋጋሚ የሚጽፈውና የሚጠቅሳቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ለቀድሞ አማልክቶቻቸው በሐውልቶቻቸው የተቀረፁ የምሥጋናና የአምልኮት ጽሁፎች በመመልከት ይሆናል። ነገር ግን ይህ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። በዚያን ጊዜ የሀይማኖት ቅራኔና ጥላቻ አልነበረም። የታችኛይቱ ግብጽ አምላክ ፕታህ የላዕላይ ግብጽ ግን አሞን ሲሆኑ ንጉሡ ለሁለቱ በእኩል ደረጃ ያከብር ነበረ። ደግሞም አዲሱ የኦሪት እምነታቸው በግል ይዘውት ይሆናል የቀድሞ አማልክቶቻቸው ደግሞ እንደብሔራዊ ባህል ይወስዱት ይሆናል። በሀይማኖት ምክንያት በዓለም ቅራኔና ጥላቻን የተፈጠረ ከእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት በኋላ ነው። የሮማ መንግሥት ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረ በሃይማኖት ምክንያት ሳይሆን መንግሥትን ለመገልበጥ ዓላማ አላቸው ብሎ ይጠረጥራቸው ስለነበረ ነው። ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የግብጾች ሀይማኖት ከኦሪት ሕግ ጋር ተማሣሣይነት አለው ተብሏል። የእስልምና እምነትም ከክርስትና እምነት ጋራ ተመሣሣይነት እንዳለው ለማሳመን ተሞክሮ ነበር። በዚህ መሠረት የጥንት ግብጻውያን ሃይማኖት የኦሪት ህግን የክርስትና ሃይማኖቶችን የእስልምና ሃይማኖትን እንደፈጠሩ መሠረት የጣሉ ናቸው ለማለት ይቻላል። ይኸውም ከሌላ ሥልጣኔያቸው በቀደምትነት ለዓለም ካበረከቷቸው ሌላ በተጨማሪ ግብጻውያን በሀይማኖትም አባቶችና መሥራቾች መሆናቸውን ያስረዳናል። ነቢዩ መሐመድ የእስልምና ሀይማኖት ያሠራጨው ለየሀገሩ መሪዎች ስለ ዓላማው በማብራራት ደብዳቤ በመፃፍ ነበር። በዚሁ መሠረት ለኢትዮጵያ ንጉሥም ደብዳቤ ጽፎ ነበረ። ደብዳቤውም እንደሚከተለው ነበረ። "እኔ መሐመድ ነቢዩ[1] በአንድ አምላክ አምናለሁ። ኢየሱስ የማርያም ልጅ መሆን እመሰክራለሁ እሱም የእግዚአብሔር መንፈስና ቃሉ ነው። በማርያም ድንግል እንዲወርድ አድርጎ ተወለደ። የእኔን ሃይማኖት ተከታይ ሁን። እኔ የእግዚአብሔር ሐዋርያ ነኝ። ጃፋር የሚባል የአጎቴ ልጅ ከአንዳንድ ሙስሊሞች ጋር ወደ አንተ ግዛት ልኬዋለሁ። ድጋፍህ እንዳይለየው፣ ለሚያስፈልገው ሁሉ እርዳው። የኢትዮጵያ ንጉሥ የመሐመድ ደብዳቤና መልእክተኞች በታላቅ አክብሮት ነበር የተቀበለው። መሐመድ ይሁዶችንና በጣኦት የሚያመልኩ ይዋጋል፣ በአንድ ግዚአብሔር ብቻ ያመልካል። ኢየሱስና ማርያም ያከብራል፣ ስለዚህ እንደ እኛ እውነተኛ ኦርቶዶክስ ነው በሚል እምነት ነበረ አቀባበል የተደረገለት። የመሐመድ ደብዳቤዎች በሌሎች ሀገሮች ተጨባጭ ውጤት ሲያገኙ በኢትዮጵያ ግን ከወዳጅነት በቀር በጣም አነስተኛ ተከታዮች ነበረ ሊያፈራ የቻለው። መሐመድ ከኢትዮጵያ በኋላ ለግብጽ የክርስቲያን ሀይማኖት መሪ ማኩካስ የላከው ደብዳቤ ግለሰቡ በቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት አገዛዝ በነበረው የግል ጥላቻ የተነሣ ተቀባይነት አግኝቶ ግብጽ እስላማዊት ሀገር በመሆንዋ ኢትዮጵያም በተዘዋዋሪ ስለነካት ከክርስትና ዓለም ተከታዮች ግንኙነትዋን እንድታቋርጥ አድርጓታል። የሀይማኖት ጥላቻ ባለመኖሩ ኢትዮጵያ ለመሐመድ ያደረገችው አቀባበል ለውጥ ባያመጣም፣ ግብጽ

[1] Alberto Pollera Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa p 275



በሞልቱኝነት ለመሐመድ ያደረገችለት ጥሩ አቀባበል በዛች ሀገር ስር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ ችሏል። ግብጽ የክርስትና ሃይማኖትዋን ለውጣ ታሪኳን ቋንቋዋንና ባህልዋን የሚቀይር ስር ነቀል ለውጥ እንድታመጣ ያደረገው ማኩካስ የተባለው ሰው ስሙ እንደሚያስረዳው ግብፃዊ አይደለም ግሪካዊ ነው። ኢትዮጵያም እንደግብጽ የነብዩ መሐመድ ጥሪ ተቀብላ ብትሆን ኖሮ ኢትዮጵያውያን የግብፃውያን ዓይነት እጣ ይደርሰብን ነበረ፣ ቋንቋችን፣ ባህላችን ረስተን ዓረባውያንና እስላማውያን እንሆን ነበረ። የኦሪት ሕግ ከጥንት ግብፃውያን ሀይማኖት የተቀዳ ስለሆነ የሙሴ የኦሪት ህግና የግብጽ አምልኮት ተመሣሣይ አለው ተብሏል። በዚህ መሠረት አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የኦሪት ህግ ተቀብላለች ወይም አልተቀበለችም የሚለውን ጥርጣሬ በራሱ መጽሐፍ በመጥቀስ መልስ እሰጣለሁ።

"በፊት ዳግማዊ ራምሲስ ወደ ሶሪያና ወደ ፓለስታይን በዘመተ ጊዜ ወታደሮቹ ሸሽተውበት እርሱ ብቻውን ተጋጠመ ከሚለው ሥፍራ ላይ አምላኩን አሞንን እንደምን እንደ ለመነው አሞን በምን አኳኋን መልስ እንደሰጠው አሁን ደግሞ ፒያንኪ ለንምሩድና ለታፍክት የሚልከው ወታደሮቹን ተዋጉ ብሎ ሰልክ የተናገረው ወታደሮቹና ታፍነቅት ለርሱ የሚሰጡት ያነጋገር ሁኔታ ልክ እስራኤሎች እርስ በርሳቸው ወይም ከእውነተኛው አምላካቸው ጋር ከሚያደርጉት ንግግር ፀሎት ጋር ይመሳሰላል። የግብፅ ፈርዖኖችና የጣኦት ካህናት ለአማልክቶቻቸው የሚያቀርቡት ንግግር ጋር ተመሣሣይነቱ ግልጽ ነው። ይህን የመሰለ የፒያንኪና የታፍነክታን አነጋገር የመሰለ በዳዊት መዝሙር በብዙ ቦታ ይገኛል።

እስራኤሎች 400 ዓመት ያህል በግብጽ ሲኖሩ የግብጽን ሥልጣኔ አጻጻፍና አነጋገር መውረሳቸው የታወቀ ነው። በተለይ የእስራኤሎች የመጀመሪያው መሪ ሕግና ሥርዓት ጽፎ የሰጣቸው ሙሴ በዳግማዊ ራምሲስ ቤተ መንግሥት የፈርዖን የልጅ ልጅ እየተባለ የግብጾችን ግናቸውንም ጥበብና ዕውቀት እየተማረ ካደገ በኋላ ሕጉንና ሥርዓቱን እርሱም ሌሎችም ሊቃውንት እነ አሮን ከግብጽ የወረሱትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለእስራኤሎች ሰጥተው ይህ እውቀት ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዳዊት ከዚያም እስከ ልጅ ልጅ ደርሶ ይሠራበት ነበር ማለት ነው።

እንደዚሁም የኢትዮጵያውያን የፒያንኪ ያባቶቹና የተከታዮቹ ሥልጣኔና ልማዳቸው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታቸው ንግግርና አፃፃፋቸው በሙሉ የግብጾች መሆኑ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን እነዚህን የናፓታና የመረዌ ነገሥታት በግብጻውያን የጣኦት አማልክት በነአሞን በነፕታህ ማምለክ ብቻ ሣይሆን ነገሥታቱ ለአማልክቱ ሊቃነ ካህናት እየሆኑ የሠሩትን በኦሪት እንደሚያምኑ እውነተኛውን እግዚአብሔር እንደሚያመልኩ አድርገው ያገራችን ሊቃውንት ከቀድሞ ጀምሮ የፃፉት እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከክርስትና በፊት በህገ ኦሪት እያመኑ እውነተኛው እግዚአብሔርን ያምኑ ነበር እየተባለ ይነበባል። ይህንንም የናፓታንና የመርዌን የአክሱምን ታሪክ ከማጥናቴ ከአሥር ዓመት በፊት እኔ ራሴ አምን ነበር። ነገር ግን ምናልባት ዛሬ ባንድ ክፍል በሰሜን ወይም በቤገምድር ግዛት እንደሚገኙት ፈላሾች ያንጊዝም የነዚህ አባቶች ከእስራኤል ሀገር መጥተው በእግዚአብሔር እያመኑ ባንዱ ክፍል አንዳንድ ነገድ ሆነው ተቀምጠው ይሆናል እንጂ ህዝቡ ከንጉሡ በዚያን ዘመን በኦሪት ህግና በእውነተኛው አምላክ የማያምኑ መሆናቸውን የሐውልቱም የብራናውም ፓፒሩስ ጽሁፍ ያስረዳል። ያንዳንዶ

ስም አስተርካሚን አርድ አሚን አስሮ አርከሚን ሲል የአሞን አሚን ቤተ መቅደስ አገልጋይነታቸውንና የዚህ ጣኦት ፍቅረኛ መሆናቸውን ስመግለጽ ነው፡፡ እንኳን እነርሱ የመጀመሪያ ካማዊ ንጉሥ የምናደርገው ሰዋታህ የሚባለው በታሀታይ ግብጽ ዋነኛ አምላክ በፕታህ የሚያምን መሆኑ ስሙ ያስረዳል!!

ተራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነኝ ሐበሻ ነኝ ይላል፣ ነገር ግን የኩሽ ወይም የካም ዘር ነኝ ብሎ አያምንበትም፡፡ ይህን የሚሉት ከኩሽ የኖህ የልጅ ልጅ በማዛመድ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ምሁራን ናቸው፡፡ የውጭ ሀገር ምሁራንም የቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ነገር ግን ከኩሽ የኖህ ልጅ ጋራ ሳያዛምዱ ኢትዮጵያውያንን የኩሽ ወይም የካም ዘር ብለው ይመድቡዋቸዋል፡፡ የኢትዮጵያውያን የኩሽ ወይም የካም ዘር ተብለው የተመደቡበት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ዘር በካም፣ ሴም፣ያፌት በመመደባቸው አይደለም፡፡ ካም ወይም ኩሽ የሚል አጠራር ለኢትዮጵያውያን ከኤውሮጳውያን ምሁራን የተሰጠ ስያሜ ከሌሎች አፍሪካውያን ጥቁሮች እንደዚሁም ከዓረቦች፣ ኤውሮጳውያን፣ ከብጫ ህዝቦች ለመለየት እና በዘር ተለይተን እንድንመደብ ብቻ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ የሰው ዘር አከፋፈል በሀይማኖት የተመሠረተ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ እንዲሁም በኤሮጳውያን የተሰጠን የዘራችን አጠራር ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምክንያቱም ካምና ኩሽ በማለት ዘራችን መጥራት የኢትዮጵያ ህዝብ ስሜትና ፍላጐት ከግንዛቤ ስለማይገባ ነው፡፡ የኤውሮጳውያን ምሁራን በአንድ በኩል ኩሽ ወይም ካም ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሰጠ ሲያሚ ሲያደርጉ በሌላ በኩልም በአካባቢያችን የሚመሳሰሉን ህዝቦች (ግሩፕ) አንድ አካል አድርገው ይመድቡናል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ የካም ዘሮች በአንትሮፖሊጂስቶች ኢትዮጵያውያን ተብለው ይጠራሉ ካለ በኋላ የአመጣጣቸው የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዳሉ ይጠቅሣል፡፡

1ኛ/ አንዳንዶቹ የነጭ ዘርና የጥቁር ዘር ድብልቅ ክልሶች ናቸው ይሉዋቸዋል፡፡

2ኛ/ ሌሎች ንፁህ ህዝብ ራሱን የቻለ ዘር ያልተከለሰ አፍሪካዊ የሆኑ አድርገው ሲመድቧቸው

3ኛ/ ሌሎችም የነጭ ዘር መደብ የሆኑ የዓረቦችና የጥቁሮች ክልሶች ያደርጋቸዋል፡፡

ኮንቲ ሮሲኒ በፊሎሎጂ በኩል ስለካም ወይም ኩሽ ዘሮች የተደረሰበት የቋንቋ አከፋፈል የካም ቋንቋዎች ሁሉ ካማዊ ወይንም ኩሻዊ የተባሉ የጋራ ጠባያቸው ተለይቶ የሚታወቁ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በ3 ይከፈሉ እንደ ነበረ ገልጸ፣ እነሱም

1ኛ/ ኢትዮጵያዊ 2ኛ/ የጥንት ግብጻዊ 3ኛ/ የበርበር ሊቢያዊ ተብለው ይታወቁ እንደነበረ በማለት ይዘረዝራል፡፡ ከካም ቋንቋዎች ጐን ለጐን የሚሄዱ የሴም ቋንቋዎችም አሉ፡፡ እነሱም 1ኛ/ የአሲሮ ባቢሎናውያን 2ኛ/ ፊኒሻውያን 3ኛ/ ዕብራይስጥ 4ኛ/ ዓረብኛ ናቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተካሄዱ ምርምሮች ግን ከላይ የተጠቀሱ ቋንቋዎች ሁሉ ለአራት ይከፈላሉ፣ እነሱም 1ኛ/ ጥንታዊ የግብጽ ቋንቋ 2ኛ ሴማዊ 3ኛ/ በርበር ሊቢያዊ 4ኛ/ ኩሻዊ ተብለው ሲጠሩ፣ በመካከላቸው ትስስርና ግንኙነት ያላቸው ናቸው ይባላል፡፡ ይህ የቋንቋ ግንኙነት መሠረቱ የት እንደተፈጠረ ለሚቀርበው ጥያቄ የተለያየ መልስ ተሰጥቶበታል፡፡ 1ኛ/ ከማዕከላዊ አፍሪቃ 2ኛ/ ከዓረብ ሀገር 3ኛ/ ከሌላ እስያዊ ሀገር፡፡



በኢትዮጵያ የኩሽ ቋንቋዎች በበኩላቸው 1ኛ/ ላይኛው ኩሽ፣ በጃ 2ኛ/ ማዕከላዊ ኩሽ አገው 3ኛ/ ደቡብ ምሥራቅ ኩሽ የታችኛው ኩሽ፣ ሣሆ፣ አፋር ፣ ሶማል፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ የተባሉ ይከፈላሉ፡፡

ኮንቲ ሮሲኒ ከተጠቀሰው የካም ዘር አጠራርና አከፋፈል ሌላ ሊዶ ቺፕሪያኒ የተባለው ኢጣሊያዊ በአንትሮፖሎጂ ወይንም በፊሎሎጂ የዘር አከፋፈል ሣይራቀቅ በደፈናው ኩሻውያን ሁሉ በአንድ የጋራ ስም ኢትዮጵያውያን ብሎ በመጥራት ነው፡፡ ሊዶ ቺፕሪያኒ ኢትዮጵያውያን፣ ሶማሊያውያን፣ ሱዳናውያን በአጠቃላይ የምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች ብቻ አይደለም ኢትዮጵያውያን ብሎ የጠራቸው፣ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ መልክ ያላቸው ሕዝቦች ኢትዮጵያውያን ናቸው ወይም የኢትዮጵያ (ጉሩፕ) ናቸው ይላቸዋል፡፡ እንደ ምሳሌ ብሎ የሚያቀርባቸው በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ዙሉ የተባሉ ጎሳዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ግን ሊዶ ቺፕሪያኒ ማነው የኢትዮጵያ እና የመላው አፍሪካ ጥቁር ሕዝብ ጠላት እንጂ ወዳጅ ተብሎ የሚጠረጠር ሰው አይደለም፡፡ ፀረ- አፍሪካውያን በርካታ መጻሕፍቶች የደረሰ አክራሪ ዘረኛ ግለሰብ ነው፡፡ አፍሪካውያንን ለማጥናት በመላው አፍሪካ በመዘዋወር ከደረሳቸው መጻሕፍቶች በአጭሩ አንዳንድ ፍሬ ነገር ለመጥቀስ ያህል ኢትዮጵያዊ በአፍሪካ ምድር የተፈጠረ ሰው ነው ወይስ ከእስያ የመጣ ነው የሚሉ ጥያቄዎች ቀርቧል ለወደፊትም ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህም ጥያቄ የነጭና ጥቁር ዘር ድብልቅ እንዳልሆነ በአፍሪካ የተፈጠርን ራሳችንን የቻልን ንፁህ ዘር መሆናችንን የሁሉ ኢትዮጵያውያን እምነት መሆኑን እገምታለሁ፡፡ መሬት ብዙ የዕፀዋት አይነት እንደምታፈራ ሁሉ ብዙ ዓይነት የሰው ዘርም አፍርታለች፡፡ ከሰው ዘሮች እንዱ ክፍል እኛ ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ ኤውሮጳውያን ማስረጃ ሳይኖራቸው የሌላ ዘር ቅጥያ ሊያደርጉንም አይገባቸውም፡፡ ኢትዮጵያውያን ለሴምና ለኩሽ እንደሚከፈሉ በሰፊው ይነገራል፤ እንዲሁም ሴም የሚባሉ የኢትዮጵያ ታሪክ ሰሪ ሌሎች በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ታሪክ ያልተጫወቱ ይባላሉ፡፡ ይኸውም አባባል አሳሳች ነው፣ የቋንቋ ጉዳይ ነው የዘር ጉዳይ አይደለም፡፡

[1] ሊዶ ቺፕሪያኒ ዘረኛ ብቻ ሊባል አይገባም የሰውየውን ማንነት በትክክል አይገልፀውም የዘረኞች አለቃ፣ አንፀባራቂ ኮከብ ዘረኛ ቢባል ምናልባት ማንነቱን በመጠኑ ይገልፅ ይሆናል፡፡ ቺፕሪያኒ እንደ ጀርመኖች ዘረኝነቱን ያተኮረው በይሁዶች አይደለም፣ የቺፕሪያኒ ዘረኝነት በጥቁሮች ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ አፍሪካን እየተዘዋወረ ከነበረ በኋላ በደረሳቸው መጻሕፍቶች ስለ ጥቁሮች የሐንጎል ዝቅተኛነት ከመፃፉም በላይ አፍሪካውያን ዝቅተኞች ሰዎች ናችሁ በሚሉበት ጊዜ ቅሬታ ሊያድርባቸው አይገባም፣ እንዲያውም ማንነታቸውን አውቀው የነጮች የበታች መሆናቸውም ቅር ሳይላቸው አምነው ተቀብለው፣ ዝቅተኛ የጉልበት ስራዎች በቅንነት አገልግሎታቸውን መሥጠት አለባቸው በማለት ለጥቁሮች ምክሩን ይለግሳል፡፡ ይህን የምርምር ስራ በሚባሉበት ከፍተኛ ድጋፍ ለሰጡት በደቡብ አፍሪካ የኢጣኒያ አምባሳደር ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ መጽሐፉም ወደ እትመት ሊቀርብ ደጋፊና አስታዋዋቂ የነበረው ከማርቲኒ በኋላ የኤርትራ ገዢ የነበረው ኮራዶ ዞሊ የተባለው ሰው ነበረ፡፡ ቺፕሪያኒ እንደሚለው አፍሪካ መጥተው ከማያውቁ ኤውሮጳውያን ብዙ ተቃውሞ እንዳጋጠመው ጠቅሶ፣ ነገር ግን በአፍሪካ ብዙ ጊዜ ከኖሩ ኤውሮጳውያን ውስጥ ካነጋገራቸው ሚሲዮናውያን፣

[1] Lido Cipriani: Considerazioni Sopra Il Passato E L'Avvenire Delle popolazioni Africane

ሳይንቲስቶች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ያላቸው ዝብረዎች ከእሱ ሃሳብ እንደሚስማሙ ስለሚያውቅ በስራው እንዲዝፉበት አድርጎዋል።

የሰው አንጎል የውጭም የውስጥም በመለካት አስተማማኝ የከፍተኛ እና የዝቅተኛ ዘር ምልክት ስላልተገኘ በደም ምርመራ ማስረጃ የሚሆን ስለጠፋ የጥቁር ሕዝቦች ዝቅተኛ ፍጡር መሆናቸውን የሚረዳ ማስረጃ የባዮሎጂ ጉዳይ ነው ወይም "የሚገንታል" ጉዳይ ነው በማለት ምርምራ በማድረግ ተጥሏል። አፍሪካውያን በአሁኑ ጊዜ ዘራቸው በወሊድ ማነስ እየመነመነ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ለወደፊት አፍሪካን የሚኖሩባት ነጮች ናቸው። ከነጮች ውስጥም እንደ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ የመሳሰሉት ያረጁ ሕዝቦች አምራች የሰው ኃይል መስጠት የማይችሉ ስለሆኑ አምራች የሰው ኃይል መስጠት የምትችል ኢጣሊያ ብቻ ናት ይላል።

ወደፊት አፍሪካ ኢጣሊያዊት እንደምትሆን ጥርጥር የለውም። በመላው አፍሪካ ከጥቁር ሰዎች ጐን ቀያይ ሰዎች እንደሚገኙ አመልክቶ፣ ይህ ሁኔታ ብዙ የኤውሮጳ ተመራማሪዎች የጥንት ግብጾች ግዛት በመላው አፍሪካ ተስፋፍቶ እንደነበረ ብለው ሲተረጉሙት፣ ቺፕራያኒ ግን በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው የሚገኙ ቀያይ ዘሮች የጥንት ግዞዎውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እምነቱ ይገልፃል።

በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጥንት የግብፅ ቁሳቁሶችና የስልጣኔ ምልክቶች ከግብፅ የመጡ ሳይሆኑ ከአፍሪካውያን ወደ ግብፅ የተሰራጩ መሆናቸውን እምነቱ ይገልፃል።

በዚህም መሠረት ለታላቁ ለግብፅ ስልጣኔ መሠረት የጣሉት አፍሪካውያን መሆናቸውን ይገመግማል። ቺፕራያኒ ኢትዮጵያውያን በሚመለከት በተለይ ወገናዊነት የሌለው አስተያየቱ ለመስጠት ያሀል በማለት የዛሬ እና የአለፈው የአፍሪካውያን ታሪክ በማጤን የስብዕናቸውና የእውቀታቸው እያሽቆለቆ በመሄድ ላይ በመሆኑ በአፍሪካ ባደረገው ሰፊ ጥናት መሠረት ኢትዮጵያውያን ስልጣኔን የመቀበል ችሎታ እንደሌላቸው በማያሻማ ሁኔታ መወሰን እንደሚቻል ገልጧል።

የመጽሐፉ አስተዋዋቂ መጽሐፉ በታተመበት ጊዜ የኤርትራ አገረ ገዥ የነበረው ኮራደ ዞሊ የተባለው የቺፕራያኒ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ከፍ ያለ አድናቆት ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ዘር /የካም ዘር/ በአፍሪካ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በሚመለከት በሞላው አፍሪካ ለምርምር የተካሄዱ ቁፋሬዎች የአንድ ጥቁር /ኔግሮ/ ወይም ቡሺማን ወይም ድንክ ሰው የሚመስሉ የጭንቅላት አጥንት ቅሪቶች አልተገኙም። በአንፃሩ ኢትዮጵያውያን የሚመስሉ በብዛት ተገኝተዋል። አንዳንድ ምሁራን ጥቁሮች /ኔግሮ/ በአፍሪካ የታዩበት በክርስቶስ ልደት በፊት 1500 አካባቢ ሲያደርጉ ይሄ ባይሆንም ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ3200 ዓመት እንደማያልፍ ገምተዋል

አፍሪካ የኢትዮጵያውያን ዋና ሀገራቸው መሆኗን ብዙ ማስረጃዎች አሉ ካለ በኋላ በዋዜንት በርቶን የተባለ ደራሲ ይጠቅሳል፣ የኢትዮትጵያውያን ዓይነት የሰው ልጅ ሰድሜ በአፍሪካ ጥንታዊነት በብዙ ሺህ ዓመት ተብሎ የሚለካ አይደለም። በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ሰደሜ የሚወሰን ነው።

በአፍሪካ የተካሄደው ማንኛውም ስልጣኔ በኢትዮጵያውያን ወይም ከኢትዮጵያውያን የተዛመዱ ሕዝቦች ውስጥ በመሆናቸው የአፍሪካ የጥንት ታሪክ የኢትዮጵያ ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል።



ንፁህ ጥቁር /ኔግሮ ዘር/ በጊኒ ከባሕረ ሰላጤ አካባቢ ካልሆነ በስተቀር በሌላ የአፍሪካ ምድር ቢበዛም ቢያንስም ከኢትዮጵያውያን ያልተላቀሉ አይገኙም።

ከአፍሪካ ምድር ወገብ በታች የሕዝቡ 2/3 የባንቱ ዘር ናቸው። በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው የሚገኙ ባንቱ የተባሉ ጎሳዎች የኢትዮጵያውያን ክልሶች ናቸው ተብሏል። በተለይ የሚጠቀሉ የደቡብ አፍሪካ ዙሉ፣ የሩዋንዳ ብሩንዲ፣ ሳንኩሩ፣ የዛምቢያ፣ ባይላ፣ የሰኔጋል፣ ቁኩለቺና ሰንኪ ሌሎችም ፉልቤ እና ወሎፍ የተባሉ ይገኙባቸዋል። ሌሎች በዘር የተለያዩ ሲሆኑ በተለይ ከኢትዮጵያውያን የሚገናኙ የናይጀሪያው አውሳ የተባሉ በቋንቋ ነው።

ፀረ- ጥቁር ሕዝብን የኢጣሊያ ዘረኝነት ከፋሽስት የመጣ አይደለም። የኢጣሊያ ፋሽስቶች መሪ ሞሶሎኒ ዘረኛ አልነበረም፣ ዘረኞች ግን ተጠቅመውበታል።

ጣሊያኖች በሙሉ ፀረ- ጥቁር ሕዝብ ዘረኞች ናቸው ለማለትም አይቻልም ይሆናል። ቺፕራያኒ የሚወክለው በተለይ የአንድ የኢጣሊያ ክፍለ አገር የኢትሩስካ ወይንም ቶስካና ነው።

ኢትሩስካውያን ዘራቸው በትክክል ባይታወቅም የነጭ ዘር ወይም አሪያን ካውካዘያን ዘር እንዳልሆኑ ግን ተረጋግጧል። ይሄም ሆኖ በአሁን ጊዜ እንደ ቶስካና ከማርቲኒና ቺፕራያኒ ጀምሮ ነጮች ነኝ በማለት የሚኮሩ ሌላ ነጭ ዘር ያለ አይመስለኝም። ኢትሩስካውያን የሮማ መንግሥት ከመሠረቱ ሦስት ጎሳዎች አንዱና ዋንኛው ናቸው። ወደ ኢጣሊያ የሰፈሩት ከትንሿ እስያ መጥተው ነው። ቶስካና በተለይ ዋና ከተማዋ ፊሬንትሴ ለኢጣሊያ ቋንቋ የፈጠረች ናት። በኢጣሊያ ፋሺዝም ስርገው ገብተው ዘረኛ እንዲሆን ያደረጉ እነሱ ናቸው። በኤርትራ ዘረኝነት እንዲመሠረት፣ ሕዝቡ ትምህርት አልባ ሆኖ እንዲኖር ያደረገ ትልቁ አገረ ገዥ ነኝ እያለ ራሱ ይጠራ የነበረው ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የቶስካና ተወላጅ ነው። ቺፕራያኒም የዘረኝነት ሞያው ያካሄድ የነበረው ፊሬንስ ከተማ ዋና ጣቢያው በማድረግ ነው።

ይህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች እያንጃበበብን እኛ እርስ በርሳችን እየተፋጀን የዓለም ሕዝብ መሳቅያ በመሆን እንገኛለን። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን አይደለንም እያልን ስማችን እና ዘራችን እስከ መካድ ደርሰናል። በታሪክና በዘር የሚያቀራርበን ከመፈለግ ይልቅ የሚለያዩን ጥቃቅን ጉዳዮች እንዲንፀባረቁ እያደረግን እንገኛለን። ኩሽ ወይም ካም የሚለው መጠሪያ ትተን እንደዚሁም በቋንቋ መለያየታችን መሠረታዊ ልዩነት አለመሆኑም እምነን ሁላችን ዘረኛው ቺፕራያኒ እንኳን ያመነበት በአንድ ኢትዮጵያዊ የሚለው መጠሪያ ተሰባስበን ሀገራችንን ብንገነባ አዋቂዎች ያደርገን ነበር፣ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች መግረፍም አንሆንም ነበር።

የቋንቋ ጉዳይ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፣ ቋንቋዎች እርስ በእርሳቸው ተጠዳድረው ተቀባይነት ያገኘ የተስፋፋ ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋ ይሆናል፣ ሌሎች ቋንቋዎች ይጠፋሉ። አውሮጳውያንም በዚህ አይነት ነው አንድ ቋንቋ ለመናገር የቻሉት። በቋንቋቸው እንጠቀማለን የሚሉ ቡድኖች ካሉ እንገዳ ሳይደረግባቸው ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ አማርኛ ግን እንዲዳብር መጣር ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሁሉ ተግባር ነው።

የተለያየ አስተሳሰብ ያላቸው የውጭ ሀገር ሰዎች ሳይቀሩ ኢትዮጵያውያን ብለው ሲጠሩን እኛ ግን በስማችን መጠቀም እንኳን

አንፈቅድም፡፡ ተፈጥሮ አንድ ያደረገን በሰው ሰራሽ ለማፍረስ እየሞከርን እንገኛለን፡፡

ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ለመሆን መመዘኛ የሚያሟላ አማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ቢሆን የሚጠቀም እንጂ የሚጐዳ ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደታየው ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷ በፅኑ መሠረት የተገነባ ባይሆን ኖሮ ከፍ ያለ አደጋ ለሕልውናችን የሚያሰጋ ይደርስብን ነበረ፡፡ አንድ ሀገር የቋንቋ አንድነት ከሌለው አንድነቱ አስተማማኝ እንዳይሆን ሊያደርገው ስለሚችል በተቻለ መጠን አንድ ቋንቋ ብቻ መፍጠርና መጠቀም ይኖርብናል፡፡

ፈረንጆች ኢትዮጵያውያንን የኅሳዎች ክምችት ወይንም የኅሳዎች ሙዘየም /ሞዛይክ/ እያሉ ይጠሩናል፡፡ ይሄ ግን የራሳቸው ኅሳዎች በመርሳት ነው፣ ለምሳሌ ጣሊያኖች ከእኛ የበለጠ ጐሳዎችና ቋንቋዎች ነበሯቸው፣ አሁንም አሏቸው፣ ነገር ግን ቋንቋቸው ቋንቋ ተብለው አይጠሩም ዲያሌክት ተብለው እየተጠሩ አሁንም ይጠቀሙብታል፡፡

## 7ኛ. የደቡብ ዓረብ ሳባውያን እና ኢትዮጵያውያን

ኤውሮፓያውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ሁሉ በአቀራረብ ቢለያዩም አማርኛ እና ትግሪኛ ተናጋሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዓረብ ክልስ አድርገው ይመድቧቸዋል፡፡ ይህ አባባል የሕዝቡ ስሜትና እምነት ያልተከተለ፣ በታሪክም በቂ ማስረጃ ያልተገኘበት፣ መሠረት የሌለው ስለሆነ የታወቀው ኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ደራሲ ኮንቲ ሮሲኒ አቀራረብ በመከተል እቃወመዋለሁ፡፡ ከቀይ ባሕር በስተምስራቅ ዓረቦች ከጥንት ጀምረው ሰፍረው ይገኛሉ፡፡የደቡብ ዓረብ /የመን/ ከሌሎች የተለዩ ናቸው፣ ይህውም ብዙዎቹ ምሁራን [illegible] ደንበኛ ዓረቦች አይደሉም፡፡ የደቡብ ዓረብ /የመን/ መሬት ከዓረቦች በፊት ቀድሞ የሠፈሩበት የካም ዘሮች መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ ስብዙ ዘመናት ዓረቦች ተብለው ይጠሩ የነበረ የማእከላዊና ሰሜናዊ የዓረብ ክፍለ ሀገር ብቻ ነበሩ፡፡ በቋንቋም ልዩነት አላቸው በሰሜናዊ ዓረብኛ እንደ ፈረንጆች አርቲክል ለመግለጽ ሲፈልጉ "አል" በቃሉ መጀመርያ ይጨምራሉ፣ አልማሊክ፡፡ በደቡብ ዓረብ ግን በቃሉ መጨረሻ "አን" ይጨምራል ማሊካን፤(1) በአማርኛ ንጉሡ የሚለው ከደቡብ ዓረብ ተመሳሳይነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ደቡብ ዓረቦች አንድ ኅሳ ብቻ አልነበሩም፤ ሚአይና ሰባውያን የታወቁ ሲሆኑ በቅድሚያ የበላይነት የነበራቸው ሚአናውያን ነበሩ፤ በኋላ ዘመን ሳባውያን ን የበላይነት ጨብጠው ነበር፡፡ ደቡብ ዓረቦች የንግድ ሰዎች ነበሩ፣ ንግዳቸውም እጣን፣ ከርቤ፣ ወርቅ፣ ሽቶ፣ ወዘተ... ነበረ፡፡

ከየመንና ከአካባቢያቸው ወደ የሥልጣኔ መእከል ሆነው የነበሩ የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች በግመል ማመላለስ ከእነሱም የሚያስፈልጓቸውን ሸቀጦች ወደ ሀገራቸው ማምጣት ነበረ፤ በኋላ ጊዜም በባሕር ንግድ ያደርጉ ነበረ፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ከ18ኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት ጀምረው ደቡብ ዓረቦች በባሕር ንግድ ግብፃውያንን ተከተው እንደነበረ ብሎ የፃፈው ትክክል አይመስልም፣ ምክንያቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዓመት /18ኛው ዲናስቲ/ ደቡብ የመን የታወቁ አልነበሩም፡፡

[1] Conti - Rossini : Storia d' Etiopia p 91



## 8ኛ የኢትዮጵያ ፊደል

ደቡብ ዓረቦች ወደ መካከለኛ ምሥራቅ በንግድ ሲመላለሱ ፊደል ከቀደሞ የግሪክ ከነሶናንታዊ ፊደል ወደ ሀገራቸው አስገብተው ነበር፡፡ ስለሚኒ ዓረቦችም ሲያስረዱ በትተዋል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ(1) ከነሶናንታዊ ደቡብ ዓረቦች ከግሪክ የወሰዷቸው ፊደሎች አስራ አንደኛው መቶ ክ/ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው ይላል፣ ይህ ግን ሊሆን የማይችል ነው፣ ምክንያቱም ግሪኮች ራሳቸው ከፊኒሳውያን ፊደል የተማሩት በ1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው፡፡(2)

ስለዚህ ሳባውያን ከግሪኮች ፊደል የወሰዱት ቢያንስ 2-3 መቶ ዓመት በኋላ መሆን አለበት፡፡ ስለፊደል በምናስብበት ጊዜ የእኛ ፊደል የሳባውያን ፊደል ነው እየተባለ በአሁን ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን የላቲን ፊደል ነው የሚስማማን እያሉ በላቲን ፊደል ሲጠቀሙ እናያለን፡፡ ነገር ግን ትክክል አዘማማይ አይደለም፣ ወደ ኋላ ሲጉትታቸው ካልሆነ በስተቀር የላቲን ፊደል ለቋንቋቸው የሚስማማቸው አይደለም፡፡

የፊደል ፈጣሪዎች እንዳልሆን ተቆጥረን ከባዕድ ፊደል መበደር አሳፋሪ ነው፡፡ በዓለም ፊደል /የሄሮግሊፊክ/ ፊደል ፈጣሪዎች ግብፃውያን መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1500 ባለው ጊዜ /ፊኒሳውያን/ ባለኮንሶናንት ብቻ የሆነ ፊደል 20 የግብፃውያን ምልክቶች በመዋስ የሴማውያን ፊደል በ1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ፈጠሩ፡፡ ግሪኮች ስልጣኔ በሄዱበት ሀገር ሁሉ ፊደላቸው ስላስፋፉ ሮማውያንም ከግሪኮች ወስደው ባለ 23 ፊደል አቋቋሙ፡፡ ለሄሮግሪፊክ ፊደሎች ሁሉ መሠረት የሆነው ሰናስታውስ ወደ ሀገራችን የሚሰዘን ነገር አለ፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ እንደገለፀው የግብፅ ሄሮግራፊክ ጽሑፈት ምልክት በፈረንሳዊው ቻምፖሊዮን ጥበብ ሊነበብ የተቻለ ሲሆን፣ በመሮዊ የሚገኘው ጥንታዊ /ያልሰለጠነ/ የሄሮግራፊክ ፊደል እስከ አሁን ሊነበብ ስላልተቻለ ብዙ የሀገራችን ታሪክ ታፍኖ ቀርቷል፡፡

ሊነበብ ያልተቻለ ጥንታዊው የሄሮግሊፊክ ፊደል በሞሮዌ ብቻ አይደለም የተገኘው፣ በአክሱም፣ በዳዕሮ(3) ጳውሎስም ከአስመራ በስተደቡብ ተመሳሳይ ጽሁፍ ተገኝቷል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚለው ከግብፃውያን የተሰረቁ የስልጣኔ ምልክት ነው ብሎ ይተረጉመዋል፡፡ ነገር ግን ያልሰለጠነ ጥንታዊ ጽሑፍ ወይም ስእል ከግብፃውያን ሊመጣ አይችልም፤ ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የፈጠሩት የመጀመርያ ስእል ወይም ፊደል ቀብሎ መወሰድ አለበት፡፡ ግብፀውያን የኢትዮጵያውያንን ሄሮግሊፊክ ፊደል አሻሽለው አዲስ የሄሮግሊፊክ ፊደል ፈጥሯል ቢባል ትክክለኛ ታሪክ ይመስላል፡፡ ለፊደል ጀማሪዎች እንግዶች ስላልነበርን ነው፣ ከሳባውያን ፊደል ወሰደን አሻሽለን አዲስ ለቋንቋችን የሚስማማ ፊደል የፈጠርነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ፊሮን ታርሐቃ የተባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት 788፣ በስራ ላይ ባዶውልም "ዲሞቲክ" የተባለ ፊደል ፈጥሮ ለግብፃውያን ዘርግቶላቸው ነበረ፡፡ ግብፃውያን ግን የተሻሻለ ዘመናዊ ፊደል ቢመጣም የቀደሞው ፊደላቸው ሄሮግሊፊክ መጠቀም ቀጥሏል፡፡ ኤሮጳውያን የሀገራችን ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያውያንን ታሪክ አልባ፣ ስልጣኔ አልባ አድርገው በመቁጠር፣

(1) Conti - Rossini ibd p 94
(2) New Standard Encyclopedia V.A
(3) Conti - Rossini Storia d' Etiopia p 108

በአንፃሩም ዓረቦች የስልጣኔ አባቶች በመገመት፣ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ፣ ስልጣኔ፣ ፊደል አስገቡ እያሉ በሐንጎላችን እንዲቀረጽ አድርገውብናል።

በአጠቃላይ በዓለም የፊደል መፈጠር እንደትውልድ ሀረግ ስንገመግመው

1. የመጀመርያ ኢትዮጵያዊ የሄሮግሊፊክ ምልክት ፊደል ሲፈጠር
2. የግብፃውያን የሄሮግሊፊክ ምልክት ፊደል ቀጣዩ ሆነ
3. የፊኒሳውያን ደንበኛ ባለ ኮንሰናንት ብቻ ሴማዊ የመጀመርያ ፊደል ተፈለሰፈ
4. ከፊኒሳውያን ተበድረው የኤውሮጳውያን ኮንሰናንት እና ቫውል ያለው የግሪክ ፊደል ተፈለሰፈ
5. የላቲን ፊደል ከግሪክ ተበድሮ ተሻሽሎ የተፈጠረ ነው
6. የራሺያ " " " " " "
7. የሳባውያን" " " " " "
8. የዓረብኛ ፊደል ከሳባውያን ተሻሽሎ የተፈጠረ ነው
9. የዕብራይስጥ " " " "
10. የኢትዮጵያ ፊደል " " " "

ኮንቲ ሮስኒ እንደጻፈው ከመቼ እስከ መቼ ብሎ ባይገልፅም የደቡብ ዓረቦች /የመን/ ለብዙ መቶ ዘመናት ዓረቦች ተብለው አይታወቁም እና አይጠሩም ነበር።[1] ዛሬ ሳባውያን የሉም የመኖች ዓረቦች በሚል ስም ተጠቃልሏል፣ ፊደላቸውም የለም። የላቲን፣ የሩስያ፣ የሳባውያን ፊደሎች የግሪክ ፊደሎች ተብለው እንደማይጠሩ ሁሉ የኢትዮጵያ ፊደልም የተወሰደው እንደ ዓረብኛ ከሳባውያን ይሁን እንጂ በጣም ተሻሽሎ እና ተለውጦ የተሰራ ስለሆነ ኢትዮጵያዊ ተብሎ ይጠራል እንጂ ሳባዊ ተብሎ አይጠራም። ኮንቲ ሮሲኒ የሌሎች ሙሁራን ሃሳብ በማንፀባረቅ የሳባውያን ፊደል መልክ ማለት በቆንጆና በዓለም ካሉ ፊደሎች ተወዳዳሪ የለውም ብሎ ፅፏል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ፊደልም ከብዙ መቶ ዓመታት የለውጥ ሂደት በኋላ የሳባውያን ፊደል ወደ ቋሚ የኢትዮጵያ ፊደል ተለውጧል። ኢትዮጵያውያን በጥንታዊ ሳባዊ ፊደል ያደረጉት ለውጥ መጠነኛ ሲሆን ሳባውያን ግን የራሳቸው ፊደል ብዙ ለውጥ አድርገውበታል፣ ቀጥንት የሳባውያን ፊደል አፃፃፍ እንደ የጥንቱ የግሪክ አፃፃፍ ከቀኝ ጀምሮ ወደ ግራ፣ ከዚህም ወደ ቀኝ፣ እንደገና ወደ ግራ እያለ የሚሄድ ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን ከሴሜናች ተለይተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከግራ ወደ ቀኝ ብቻ መፃፍ አዘወተሩ። በዕብራይስጥ እና በዓረብኛ ግን ከቀኝ ወደ ግራ አቅጣጫ አፃፃፍ በመያዝ ቋሚ ሆኖ ቀረ። ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከሳባውያን ፊደሎች አንዳንድ በማስቀረት 30 ፊደሎች ብቻ ወሰዱ። እነዚህ መሰረታዊ ፊደሎችም 7 ዓይነት የቫወል ድምፆች በመስጠት በ7ት ተባዝተው በድምሩ 202 ፊደሎች በማድረግ ኢትዮጵያውያን ከሴሜናውያን ውስጥ ዕብራይስጥና ዓረብኛ ወዘተ... የቫወል ድምጹ በመፍጠር የመጀመሪያዎቹ ሆኑ፣ እኛ የፊደል አባቶች፣ የፊደላት ፈልሳፊዎች ሆነን ዛሬ በሀገራችን ማጽ ፊደል የላቲን የመጠቀም አዝማሚያ ይታያል። ይህ አዝማሚያ ግን መታረም ያለበት ነው። የኢትዮጵያ ፊደል የዳግማዊ ምኒልክ ፊደል ነው

[1] Conti-Rossini Stöiad Ethiopia p 91



አይስማማም ብሰው የሚያምኑ እንኳን ቢሆን፣ በላቲን ፊደል መጠቀም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያዘነብላል። የኢትዮጵያ ፊደል ተቃዋሚዎች አብዛኛዎቹ እስላሞች እንደመሆናቸው መጠን በዓረብኛ ፊደል ቢጠቀሙ እንኳን መንገድ ያለው ሊሆን ይችላል።

ኤውሮውጳውያን የራሳቸው ፊደል መፍጠር ሲገባቸው በሮማውያን ላይ አከብሮትንና አምልኮት ስለነበራቸው ለቋንቋቸው የማይስማማ በላቲን ፊደል ይጠቀማሉ። የላቲን ፊደል ለእንግሊዘኛ ቋንቋ በተለይ አይስማማም። ለሌሎችም የኤውሮጳ ቋንቋዎችም አይስማማም። ሳባውያን እና የደቡብ ዓረቦች ከሌሎች የመካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች ሲታዩ ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው የሚባሉ አይደሉም፣ ኃይለኛ የታወቀ መንግሥትም አላቋቋሙም። በጥቃቅን ወሰላዎች ተከፋፍለው ሙካሪብ በሚባሉ በአምልኮት መንፈሳዊ አለቆች መሪነት ይተዳደሩ ነበር።

ሳብውያን ለመጀመርያ ጊዜ ስማቸው በታሪክ የተጠቀሰ በአሲሪያ ንጉሥ ሳርጎን(1) ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት 710 ዓመት ነው፣ በሐውልት ጽሑፉ የሳባ ሙካሪብ ገጽ በረከት ለፈርኦን አበርክተዋል የሚል ነበረ። ለሁለተኛ ጊዜ የሳባውያን ስም ተጠቅሶ የተገኘው በፐርሲያ ንጉሥ ዳርዮስ ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት 510 ዓመት የሳባ ንጉሥ ተብሎ ሁለት ጊዜ ተጠቅሶ ተገኝቷል። ይህ አነስተኛ የሳባ መንግሥት ብቻው ሆነ ከሌሎች የደቡብ ዓረብ ጎሳዎች ጋራ ሆኖም ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው ከሀገሩ ሕዝብ ጋራ በኃብቻ ተደባልቀው ኢትዮጵያን ሊፈጥሩ አይችሉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደቡብ ዓረቦች ጋራ ዝምድና እንዳለው አያምንበትም። የአባቶቻችን እሌ ታሪክ ከሳባውያን ሕልውና እና ዕድሜ በላይ እስከ ንጉሥ ሰለሞን ቀዳማዊ ምኒልክ እፈ ታሪክ ከነሱም በላይ ታሪክ አስተላልፈውልናል፣ ከሳባውያን ዓረቦች እንወለዳለን የሚል ታሪክ ግን አልተውልንም፣ የሳባውያን ፊደል በመጠቀማችን መሠረት በማድረግ ብቻ ኤውሮጳውያን የፈጠሩት ለበወሰድ ታሪክ ነው። የሳባዊ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ የማስተላለፍ ጉዳይ በግዴታ በሳባውያን በኩል መሆን የለበትም። ይሁዶችም ሊሆኑ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ ዛሬ ድረስ የእስራኤል አምላክ ሲል ነው የምንሰማው፣ የዓረብ አምላክ ሲል አልሰማንም። እስራኤሎች የጥንት ሀገራቸው ዓረብያ እንደነበረ ይነገራል። በደቡብ ዓረብም ከፍተኛ ግዛት ስለነበራቸው የስልጣን ተቀናቃኝ ለመሆን የበቁ አይሁዶች ስለነበሩ ወደ ኢትዮጵያ ሃይማኖታቸውን ባገቡበት ጊዜ የሳባውያን ፊደል አስገብተው ሊሆኑ ይችላሉ። ኮኒቲሮሲኒም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ደብቡ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ስለመምጣታቸው የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ኮተረት የማያልፉ ናቸው። ኤውሮጳውያን የሀገራችን ታሪክ ጸሀፊዎች ዘራችን ጩዋ ለማድረግ ከእስራኤሎች፣ ከዓረቦች እንወለዳለን እያልን የብዙ መቶ ዓመት ታሪክ በመዝለል ማዛመድ እንደምንሞክር አድርገው ይተቹናል። ነገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ የደቡብ ዓረቦች ባህል ብሎ ያቀረበው ሕብረተሰቡ በባላባቶች እና በተራ ዜጎች መካፋፈል ነው፣ ሳባ የሚባል ደሴት ከምፅዋ አጠገብ ይጠቀሳል፣ እሰብ ከሳባ የመጣ ስም ብለው ይተረጉሙታል። ሰሐርቲ፣ ሐውዜን፣ ሳራዌ /ሰራዬ/ ወዘተ... ከደቡብ ዓረብ የተወረሱ ስሞች ያደርጉታል። ይህ ሁሉ ግን ታሪክ አይደለም ተረት ነው።

የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሚሉት እውነተኛ ታሪክ ቢሆን ኖሮ ሌግውያን ናቸው የሚባሉ ትግሬ፣ ትግሬኛ፣ አግርኛ፣ ጉራጊኛ፣ አደሬ፣

(1) Conti Rossini Storia d' Ethiopia 1928 p 98

ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች አፋርኛ፣ ሶማልኛ፣ ኦሮሚኛ፣ ሲዳምኛ፣ ወላይትኛ፣ ካፌኛ፣ ወዘተ… ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች በመልክ /በዘር/ ከፍተኛ ልዩነት ይታይ ነበረ፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ መሀል በቆዳና በቀለም በኩል በመሀላቸው ምንም ልዩነት አይታይም፡፡ ልዩነት የሚታየው በቋንቋ ብቻ ነው፣ ይህ ሁኔታ ብቻ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልግ የደቡብ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ፈልሰው መምጣታቸው ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ከደቡብ ዓረቦች ብቻ ሳይሆን ከእስራኤሎችም ጭምር ብዙ ቃላቶችና ባህሎች ወስደናል፣ በዘር ግን አልተቀላቀልንም፡፡ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል የተባለብት ዘመን የመኖች ዓረቦች ተብለው ይጠሩ አልነበረም፡፡ ሰሜን ዓረቦች /የዛሬዋ ሳውዲ ዓረብያ/ ብቻ ነበሩ ዓረብ ተብለው የሚጠሩ፡፡ ደቡብ ዓረብ መሬት ውስጥ የመጀመሪያ ኗሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ይባላል፡፡ የካም ዘሮች ያልሰፈሩበት ቦታ አልነበረም፡፡ ሄሮዶቱስ የግሪክ ቀደምት ነዋሪች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል፡፡ የካምና የሴም ዘሮች ጉን ለጉን የተፈጠሩ እና የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የካም ዘሮች ሆነው ከሴም ቋንቋ ተመሳሳይ የሆነ ግእዝ የሚናገሩ ሕዝቦች በሰሜን ኢትዮጵያ ተፈጥረው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ተመሳሳይነት ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር የአውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች ከባሕላችንና ከአባቶቻችን የወረስነው ታሪክ የደቡብ ዓረቦችም የማያውቁት ታሪክ ዓረብ ገዥ ኢትዬጵያ ተገዥ ዓረብ አሰልጣኝ ኢትዮጵያ ሰልጣኔ በደንብ የመቀበል ችሎታ የሌሰው /ሰልጣኝ/ አድርገው በመቁጠር ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያውያን የዓረብ ክልስ በማሰት ዘራችን ሊያስተምሩን መብት የላቸውም፡፡

ሳባ የምትባለው የደቡብ ዓረብ አነስተኛ መሬት ወደ አፍሪካ ተሻግራ ኢትዮጵያን የሚሀል መሬት በቀኝ ግዛት ይዛ ብትሆን ኖሮ ዝናዋና ታሪኳ በዓለም አቀፍ በማያሻማ ሁኔታ ይታወቅ ነበር፡፡

ሳባውያን ከአሰተዳደር ይልቅ ዝና ያገኙት በንግድና ከግሪክ ፊደል ወስደው ለዓርቦች ለኢትዮጵያውያንና ለይሁዶችም በማሰራጨታቸው ነው፡፡ ለዓረቦች ፊደል በመስጠታቸው ገዝቷል እንዳልተባሉ ሁሉ ለኢትዮጵያም ፊደል በመስጠታቸው ገዝተዋል ሊባሉ አይችሉም፡፡ ሮማውያን ገዥዎች ሆነው ከተገዥዎቹ ከግሪኮች ፊደል ወስደዋል፡፡ ኤውሮጳውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት ከፊደል ሌላ ሰልጣኔን በሚመለከት ነው፡፡ ሳባውያን ከባቢሎን ባለፎቅ የሕንፃ ግንባታ ተምረው በሀገራቸው አሰገብተው በሥራ ላይ አውለውታል፡፡ በሀገራችን ግን እንኳን ፎቅ ቤት የድንጋይ ቤትም ልምድ ምንም ምልክት የለም፡፡ በአክሱም የቆሙ ሐውልቶች ዓይነት በሳባ የሉም፡፡ በአምልኮትና በቤተመቅደስ አሰተዳደርም በኢትዮጵያ አይታዩም፡፡ በቋንቋችን የሚገኙት ብዙ የዕብራይስጥ ቃላቶች የሀይማኖት ሳይቀር በአንዳንድ ቦታዎች፣ የኤውሮጳውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ተገቢ ትኩረት አልሰጡበትም፡፡ ክርስትና ከመቀበሏ በፊት ኢትዮጵያ የእስራኤሎች የሙሴ ሕግ ተቀብላ ነበር የሚል የኢትዮጵያ የቤተክህነት ምሁራን አባባል በቂ ጥናት አልተደረገበትም፡፡ ይኸም ሲባል አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት የኢትዮጵያውያን እና የእስራኤሎች አባቶች የጋራ ሀገር ዓረብ ነው ብለው መገመት ተቀባይነት የሌለው መሠረተቢስ ታሪክ ነው፡፡



## ፱ኛ. ኢትዮጵያ ሱዳንና ግብፅ

አብዛኛዎቹ ኤውሮጳውያን ታሪክ ፀሐፊዎች በአፍሪካ ከግብፅ ሥልጣኔ ከስተት በቀር ምንም የራሷ ሰልጣኔ ያልፈጠረ ሕዝብ የጭለማ ክፍለ ዓለም ብለው ይተርካሉ፡፡ ግብፆች አፍሪካውያን አይደሉም ሴማውያን ናቸው ይሉዋቸዋል፣ እንዳንዶቹ የነጭ ዝርያ አርያን ናቸው ይሏቸዋል፡፡ ከግብፅ ሀገር ክልል በስተደቡብ በናፓታ ዋና ከተማ የነበረው የኑቢያ መንግሥት አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ብሉ ሲጠሩ ኮንቲ ሮሲኒ የናፓታ /ኑቢያ/ መንግሥት የተቋቋመው በቴብ ግብፃውያን ቤተመቅደስ አለቆች ነው ይላል፡፡ ይህ ማለት የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የተባለችው በግብፅ የተቋቋመች ሰልጣኔዋን ከግብፀ ያገኘች ማለት ነው፡፡ ይህ አባባል እውነት ቢሆን ኖሮ ሳባውያን ቋንቋቸውና ዘራቸው ቀይ ባሕር ተሻግረው አሰገዙ እንደተባለ ሁሉ ግብፃውያንም ቋንቋቸውና ጽሑፎቻቸው ወደ ናፓታ አስገብተዋል በማለት ወደ መጨረሻ ግምገማ መድረስ በተቻለ ነበረ፡፡ የግብፅ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ወደዚሁ ግምገማ መድረስ ተስኖቸዋል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚለው ግብፅ ከመካከለኛ ምስራቅ በምታደርጋቸው ዘመቻዎች የተነሳ እየደከመች ስለሄደች ናፓታ ከግብፅ እየተስየች ሄደች ከክርስቶስ ልደት በፊት 573 [1] 533፣ ለአሞን /እግዚአብሔር/ ቤተመቅደስ በሜሮዌ ተሰራ፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት 440 - 350 መሮዌ የኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬዋ ሰሜን ሱዳን ዋና ከተማ ሆነች፡፡ የዋና ከተማ መሸጋሸግ የግብፅ ሰልጣኔ ውድቀት አስከትሏል፡፡ በናፓታ የግብፅ ሰልጣኔ መልኩን ቀይሮ ደሕይቶ ነበረ፡፡ ወደ መረዌ ዋና ከተማ በተዘዋወረበት ወቅት ግን ሰልጣኔው ወደ ኋላ ቀርነት /ባርባሪያን/ ተለውጦ በሐውልት ጽሑፎች ቋንቋም ተሰውሟል፣ የህዝቡም ዘር ተቀይሯል፡፡ ሕዝቡ ጥቁር በመሆኑ ለኪነ ጥበብ፣ ለሃይማኖት፣ ለእውቀት ማስፋፋት፣ የራሱ ችሎታ አልነበረውም፡፡ ይበዛም የኖ ግን ያለፈው ሰልጣኔ በፒራሚዶችና በቤተመቅደስ በመንግሥት መስተዳድር በሀገሩ ሕዝብ ዘንድ አድናቆት የሚያተርፍ ነበረ፡፡ በሐውልቶች የነበሩ ጽሑፎች በመረዌ ቋንቋ ነበሩ፡፡

ስለዚህ አብዛኛው የሀገሩ ታሪክ ማወቅ አልቻልንም፡፡ በስእሉቹ የሚታየው የሴት ንጉሥት ግን በበኛ ሕዝብ ዘንድ የሴት አክብሮት ባሕል ያሳየናል፡፡ የመርዌ ኪነ ጥበብ የሚያንፀባረቅ የሚመስል በአንድ ዋሻ በዳዕር ሰሎሙስ [2] አጠገብ ከአሰመራ በስተደቡብ ተገኝቷል፡፡ ስእሉ ያልሰለጠነ የግብፃውያን የተለመደ የሶስት ሰው /አንድ ወንድ አንድ ሴት አንድ ልጅ/ የሚያሳይ ሲሆን ምናልባት የእግዚአብሔራቸው ምልክት ሳይሆን አይቀርም ተብሉ ተገምቷል፡፡ የኮንቲ ሮሲኒ አባባል በዘረኝነት መንፈስ የተመረኮዘ ነው፡፡ አንድ ሰልጣኔ ካልሰለጠነ ወደ ሰለጠነ ይሻሻላል እንጂ ወደ ኋላ መመለስ መልኩን ቀይሮ ካልሆነ በስተቀር ራሱ ሰልጡን ሕዝብ ወደ ናፓታና መረዌ የሚያስተላልፈው ሰልጣኔ የመጨረሻ ውጤት መሆን አለበት፡፡ የጽሑፉ ቋንቋም መሮዌ ሳይሆን ቤጃ መባል ነበረበት፡፡ መሮዌ ዋና ከተማ እንጂ የጎሳ ስም አልነበረችም፡፡ በመሮዌ የተገኘው ጽሑፍ የግብፃውያን ቋንቋ ስላልሆነ በቻምፖሊዮን ዘዴ ጥበብ ሄሮግሊፊክ ሊነበብ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ የናፓታና የመሮዌ ታሪክ እስከ አሁን ያልታወቀ ታሪክ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ያልሰለጠነ እንደ መሆኑ መጠን ከግብፆች የተወረሰ ሰልጣኔ ብሉ ከመተርጎም

[1] Conti Rossini Storia d'Ethiopia p 106 - 107
[2] Conti Rossini ibd p 108

ከግብፅ ስልጣኔ በፊት የነበረ ለግብፅ ስልጣኔ ቅድመ ሁኔታ የፈጠረ ተብሎ መወሰድ ይገባዋል፡፡ በዚህ መሠረት አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ እንደ ገመገመው ሳይሆን ከግብፅ እና ከቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬዋ ሰሜን ሱዳን በስልጣኔ ማን ይቀድማል ለሚለው ጥያቄ ያለምንም መወላወል የኢትዮጵያ ስልጣኔ ነው የሚቀድመው የሚል መልስ መሆን አለበት፡፡ የግብፅ መንግሥት በሜነስ (Menes) ሲመሠረት ከክርስቶስ ልደት በፊት 5 ሺህ ወይም 4 ሺህ አመት ከሆነ የቀድሞዪቱ የኢትዮጵያ ታሪክ 2000 ሁለት ሺህ ዓመት ታሪክ ከግብፅ በፊት መሆን ስለሚገባው የኢትዮጵያ ታሪክ ዕድሜ በ7 ወይንም ለ8 ሺህ ዓመት መሆን አለበት፡፡ ሰሜን ሱዳን የኢትዮጵያ አካል ናት ለማለት የምንችለው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ታሪክ ብቻ አይደለም፡፡ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ቢሆንም የሰሜን ሱዳን አብዛኛው ክፍሎች ከኢትዮጵያ ተቆርሰው የተወሰዱ መሆናቸውን በሌላ ምዕራፍ እንመለከተዋለን፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ታሪክ መሠረት ሀገራችን ኢትዮጵያ ከንግሥተ ሳባ በመጀመር የ 3000 ዓመት ታሪክ አላት የሚል አባባል ትተን 6-7 ሺህ አመት ታሪክ አላት ለማለት እንችላለን፡፡

[1] ሉካ ዴይ ሳበሊ የተባለው ኢጣሊያዊ ታሪክ ጸሐፊ ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዘ ኢትዮጵያ በታሪክ መኖር በመቁጠር ኢትዮጵያ 2500 ዓመት ታሪክ አላት ብሎ ጽፏል፡፡ የአቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ አቀራረብ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊት ሰሜን ሱዳን የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ብሎ መለየሙ ትክክል አጠራር ይመስላል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ጎሳዎች በሙሉ የኩሽም ሆነ የሴም ከእስያ መጥቷል ማለቱ ባሕላችንና አፈታሪካችን ትተን ኤውሮጳውያን የሚያስተምሩን ታሪክ መከተል ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፣ ልበወለድ ታሪክ ነው፡፡ የሳባውያን /የመን/ ዘሮች መሆናችን አባቶቻችን አላስተማሩንም አቶ ተክለ ፃዲቅ በመጽሐፉ በገፅ 23 የሁለተኛ ምዕራፍ ማምገማ የቀድሞዪቱና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ልዩነት በማስመልከት እንደሚከተለው ጽፏል የኑቢያ ታሪክ ከግብፅ የተያያዘ የአክሱም ከደቡብ ዓረብ የተዛመደ ለአሁኑ መንግሥታችንም ለሥልጣኔውም ለፊደሉም ለቋንቋውም ለዘሩም ለልማዱም ሳባና ሐበሺት የመጡበት ይኸው ደቡብ ዓረብ መሆኑን በሰፊው እናያለን፡፡ ለዛሬው ስልጣኔያችንና ፊደላችን ቋንቋና ልማዳችን አባት ያልሆነውን የኑቢያን ታሪክም በሰፊው ስንመለከት ከአክሱም ጋራ የልዩነት ወይም የግንኙነት ማጤን ... በዛሬ ጊዜ የመንና ሱዳን ዓረብ ሀገር ተብለው ነው የሚታወቁ፣ በድሮ ጊዜ ግን ሱዳን ኢትዮጵያዊት ነበረች የመንም ዓረባዊት ያልሆነች ሳባውያን ሚናውያን ሐድራሞታውያን ወዘተ ጎሳዎች የሚኖሩባት ሀገር ነበረች ምናልባትም ፑንት ከሚባሉ ሕዝቦች ውስጥ ትቃለል ነበረች፡፡ ስለፊደሉ ጉዳይ እላይ ዝርዝሬዋለሁ፡፡ ስለ ቋንቋችን ግን ግእዝ በግድ ከዓረብ የተፈጠረ ነው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ሴም ቋንቋዎች ውስጥ ዕብራይስጥ፣ የደቡብ ዓረብና ዓረብያን የሶርያና የፍልስጤም ዓረብኛ ልዩነት እንዳለው ሁሉ በቀይ ባሕር /የሐበሻ ባሕር/ በስተ ምዕራብ በሀገራችን በዘር ዓረብ ያልሆኑ ንፁህ የኩሽ ዘር የሆኑ ሕዝቦች ዓረብኛ የሚመስል ቋንቋ ሊኖራቸው ይችላል /ግሕዝ/፡፡ ቋንቋ ከደቡብ ዓረቦች ተምረናል ለማለት ግን የማንቀበለው ነው፡፡ በዘርና ልማድ ጨርሶ ከዓረቦች ጋራ አንመሳሰልም፡፡ ስሁለት ተከፍላ የነበረች ግብፅ ያዋሀደው ከንጉስ መኔስ በፊት የነበረው ስልጣኔ በናፓታ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ነው፡፡

[1] Luca Dei Sabelli Storia di Abissinia V.I p 100



የግብፅ ታሪክና ስልጣኔ በተለይ ሄሮግሊፊክ ጽሁፍ ሊነበብ ከተቻለበት ጊዜ ጀምሮ በሚገባ የሚታወቅ ሲሆን፣ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ታሪክ ያልለለበነ የሄሮግሊፍክ ጽሑፍ ስለሆነ የቋንቋንም ልዩነት ሊኖር ስለሚችል ሊነበብ ስላልተቻለ የሀገራችን ታሪክ ለማወቅ አልታደልንም፡፡ እነ ሄሮዶቱስና ዲዮዶር ግብፅን ያስለጠነች እና በስልጣኔ ቀደምትነት ያላት ኢትዮጵያ ናት ያሉት እውነተኛውን ታሪክ መቀበል ይኖርብናል፡፡ የኑቢያ ታሪክ ለዛሬ ስልጣኔያችንና ቋንቋችን ልማዳችን አባት አይደለም ለማለት እንችልም፡፡

መሮዌ የምትገኘው እትባራ እና አባይ የሚገናኙበት ሲሆን በዚሁ ቦታ የሰፈሩ ሰዎች እሁንም ያሉት ቤኒዓመር የሚባሉ ሊሎችም ቤጃና ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ በተለይ ቤኒዓመር ተብለው የሚጠሩ ጎሳዎች ሁለት ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው፣ ትግሬና /ግእዝ/ ቤጃ ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ጎሳዎች ናቸው፡፡ ሁለት ቋንቋ እየተናገሩ አንድ ጎሳ የነበሩ የሚታወቁም ከብዙ ዘመናት /በብዙ ሺህ/ ዓመት ጀምሮ መሆኑን ተገምቷል፡፡ ምናልባትም ከናፓታ ዘመን ጀምሮ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት ሁለት ኢትዮጵያ ለማለት እንችልም፡፡ በናፓታና በመሮዌም ግእዝ ተናጋሪ ከቤጃ ተናጋሪ ጋራ ሆኖ ስልጣኔ እንደፈጠሩ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ትግሬ ተናጋሪ /ግእዝ/ ከደቡብ ዓረብ መጥተው እስከ መሮዌ ቋንቋቸው አስፋፍቷል በማለት ኤውሮጳውያን ታሪካችን ብለን እንድንቀበለው የሚያደርጉብን መከራ ተረት ነው፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያ አንድ ነበረች፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ስለተዳከመች ግን አንድነቷን ለማስከበር አልቻለችም፡፡ በመሠረቱ ኢትዮጵያውያን በነገድ አንለያይም፣ ብንለያይም በቋንቋ ነው፡፡ ቋንቋ ለአንድነታችን መሰናከል መሆን አይገባውም፡፡ ነገደ ሴም ወይንም ነገደ ዮቅጣን የምንላቸው ከሴም ቋንቋ ትንሽ ድብልቅ ያለው፣ ሌላ ደግሞ ቋንቋ ድብልቅ የሌለው ሁሉም ነገዶች ከጥንት ጀምሮ ተደባልቀው የኖሩ ናቸው፡፡ በአፍሪካ የተፈጠሩ ከእስያ ያልመጡ ጎሳዎች ናቸው፡፡ ምናልባትም በናፓታ ቤጃ ብዛትና የፖለቲካ የበላይነት ሊኖራቸው ይችላል በአክሱም ደግሞ ግእዝ ተናጋሪ ብዛት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

## 10. ኢትዮጵያና ንግሥተ ሳባ

ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት አይደለችም ተብሎ ሲነገረን ሁላችን እናውቃለን ምን ያህል የተቃውሞ ስሜት እንደሚሰማን፡፡ ከዚህም በላይ የንግሥተ ሳባ ዘር ነን የሰለሞን ዘር ነን፣ የሳብያውያን ዘር ነን በምንልበት ጊዜ ዝቅተኛ የሆነ ዘራችን ከፍ ለማድረግ ጨዋ ዘር ለመሆን ፈልገን ነው ተብሎ ሲነገረን፣ የኢትዮጵያ ዘር ከማን ዘር ያንሳል በሚል ስሜት ተቃውሞዋችን በቁጣ ሊገነፍል ይችላል፡፡ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ታሪካችን ሐሰተኛ ማድረግ የታሪካችን ትምህርት ማዋረድ ነው፡፡ ንጉሥ ሰሰሞን ተረት ሳይሆን በታሪክ የታወቀ የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ ሁሉ፣ የንግሥተ ሳባ ታሪክም ተረት አይደለም፡፡ የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት መሆንዋ ኢትዮጵያውያን ሙሉ እምነት እንዳላቸው ለሴቶቻችን ሳባ! ማከዳ፣ አዜብ ብለን ስም መስጠታችን በቂ ማስረጃ መሆን በቻለ ነበረ፡፡ ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት እንጂ ዓረባዊት ልትሆን የማትችልበት ምክንያቶች ከብዙ ባጭሩ

1. የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬይቱ ሰሜን ሱዳን ስሟ ኑብያ ነው፣ ዋና ከተማዋ ናፓታ ነበረ። በአስልታ ንጉሥ ጊዜ /573-553/ ዋና ከተማ ወደ መሮዌ ተዛውወረች። አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ንግሥተ ሳባ የመረዌ ንግሥት አይደለችም ለማለት መሮዌ የተቆቀቆረችበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ አምስተኛና አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገቅ በማድረግ፣ ንግሥተ ሳባ ከነበረችበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ስለሚራራቅ በፍፁም ሊታመን አይችልም ካለ በኋላ ከኑቢያ ሐውልቶች እና ጽሑፎች የንግሥተ ሳባ ስም አይገኝም ወደ ፊትም ሊገኝ የሚችል አይመስልም፣ ምክንያቱም የሷ ንግሥትነት ከነገዷ ክፍል ከሆነው ከዓረብና ከኢትዮጵያ ሰሜን /ሳባ ትግሬ/ ሊዘል አይችልም ይላል። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያውያን ቋንቋቸውና ዘራቸው የካም ነው ፊደላቸውም ስልጣኔያቸውም ከግብፅ የተወረሰ ነው። የንግሥተ ሳባ ዘርና ቋንቋ ከደቡብ ዓረብ ከሳባውያን የመጣ ነው ይላል። በመጨረሻም ንግሥተ ሳባ [1] የሁለቱ ሀገሮች ኢትዮጵያና የደቡብ ዓረብ /የመን/ ንግሥት ልትሆን ስለምትችል የኢትዮጵያ ናት ወይም የዓረብ ንግሥት ናት እያሉ መሻማት ከንቱ ነው በማለት አስታራቂ ሃሳብ በማቅረብ ጽሑፉን ደምድሟል። ይህ አስታራቂ ሳብና አስተያየት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። እላይ እንዳልኩት ኢትዮጵያውያን ለሁለት የካምና የሴም ዘር መክፈል ስህተት ነው። ኢትዮጵያውያን ሁሉ በቋንቋ ካልሆነ በቀር በዘር በኩል አንድ ናቸው፣ የካም ኢትዮጵያዊ ዘር ናቸው። በቋንቋም ቢሆን የሴም ተብሉ የሚመደቡ አነስተኛ የሴም ቃላቶች ተደባልቀው ስለሚጠቀሙ እንጂ ቋንቋው በመሠረቱ የካም ኢትዮጵያዊ ነው። ስለዚህ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ /ኑቢያ/ እና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዘር አንድ ከመሆናቸውም በላይ በቋንቋም አንድ ናቸው። ምክንያቱ በሁሉም በልማድ የካምና የሴም ተብለው የሚመደቡ ቋንቋዎች በእኩል ደረጃ ተስፋፍተው ይገኛሉ። በኑቢያ የሚኖሩ ኩሽ ተብለው የሚጠሩ ዘሮች፣ ሌላ አይደሉም ጥንትም ይኖሩ የነበሩ አሁንም ኗሪ የሆኑ ቤጃ ናቸው። ከነሱ ጎንም በጥንትም ይኖሩ የነበሩ አሁንም የሚኖሩ ግዕዝ "ትግሬ" ቋንቋ ተናጋሪ አሉ። ስለዚህ ንግሥተ ሳባ የመሮዌ ንግሥት የማትሆንበት ምክንያት የለም። ዘሯም ወይም ቋንቋዋ ሴማዊ ወይም ዓረባዊ ወይም ግእዝ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ አልተገኘም። ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ባለፀጋ ሆና በማስረጃ ማግኘት ግን አልታደለችም። ታሪካችን አሁንም ተደብቆ ነው የሚገኘው። በቂ ቁፋሮና ምርምር አልተደረገበትም። በመሮዌ የሚገኘው የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ ግን ከግብፃውያን ቋንቋ የተለየ በመሆኑ ጥንታዊ፣ ያልሰለጠነ ከግብፃዊው ቅድሚያ ያለው በመሆኑ ሊነበብ አልተቻለም። ስለዚህ ታሪካችን ሳይገለፅ ለዘላለም ይኖራል። እንደሚነገረው ትግሬ ተናጋሪ ሰዎች በአንድ የአክሱም መንግሥት ዘመቻ የሰፈሩ አይደሉም፣ ከጥንት የተፈጠሩበት አገር ነው። ምናልባትም እንደ ግእዝ ቋንቋ መለዋወጥ ሲታይ የግዕዝ ቋንቋ የተመሰረተበት ሀገር ኑቢያ ሳትሆን አትቀርም ብዬ እገምታለሁ። ያልሰለጠኑና የማይነበብ የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ በኑቢያ ብቻ አልተገኘም። ጀምስ ብሩስ [2] የተባለው እንግሊዛዊ በአክሱም የማይነበብ የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ አግኝቷል።እላይ እንደገለፅኩትም ከእሥመራ በስተደቡብ በዓዕር ቆሎሉብ አጠገብ አንድ ዋሻ ውስጥ የጥንታውያን ግብፆች የሚመስል ስእል ተገኝቷል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ሥልጣኔ ከኢትዮጵያ ተጀምሮ ወደ ግብፅ እንደተላለፈ ነው።

[1] ቀክል ሺደት ገጽ 193
[2] Conti Rossini ibd p.82



ከግብፅ የመጣ ቢሆን ኖሮ ጽሑፉ ከመጨረሻው የግብፃውያን ጽሑፍ አንድ ዓይነት መሆን ነበረበት።

2. የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነት በሌላ መንገድ ስንመለከተው ማለት በደቡብ ዓረብ ያለው ሁኔታ በኩል፣ በ1ኛ ተራ ቁጥር ከቀረብኩት ያላነሰ ኢትዮጵያነቷን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ለማቅረብ ይቻላል። በመጀመሪያ ንግሥተ ሳባ በነበረችበት ዘመን ደቡብ ዓረቦች ዓረብ ተብለው አይጠሩም ነበር። የዓረብ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ የሌላውን ሕዝብ መዋብና ማዋዘድ ችሎታ ስላለው ሰሜን ሱዳን ኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ዓረብ ተብላ ከመመደቧ በላይ ቋንቋዋ ተቀይሮ ዓረብኛ ተናጋሪ ሆናለች። ደቡብ ዓረብ የመን በኋላ የተከፋፈለች መሆንዋን በማየ እንደሚታየው፣ ዛሬ ቀይ ባሕር ተብሎ የሚጠራው "የሐበሻ ባሕር" ተብሎ ይጠራ ነበረ። በታላቁ እስክንድር ቀይ ባሕር የተባለም እኛ ኢትዮጵያውያን ቀያይ ሰዎች የምንኖርበት ስለሆነ ነው ተብለዋል።

የመን ለትናንሽ መንግሥታት የተከፋፈለች እርስ በእርሳቸው የማይስማሙ፣ የሚተዳደሩም በመጀመሪያ ጊዜ በአምልኮት መንፈሳዊ መሪዎች ነበረ። እነሱም ሚናውያን፣ ሳባውያን ሀውሳውያን ካታባውያን ሀድራሙታውያን ተብለው የሚታወቁ ነበሩ። እኛን በሚመለከት አብዛኛው ሳባውያን ናቸው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ንግሥተ ሳባ ትኖርበት የነበረ ዘመንና ግሪኮችም ከፊኒሳውያን ፊደል ተበድረው የወሰዱበት በዚሁ ዘመን ነበረ። ደቡብ ዓረቦች ግን በዚህ ጊዜ በዓለም አይታወቁም ነበረ። በእንፃሩ ኢትዮጵያ ፑንት፣ ኩሽ፣ ኢትዮጵያም /አበሻ/ ተብላ እየተጠራች በዓለም የታወቀች ነበረች። ሳባ የምትባል ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስሟ በታሪክ ተጠቅሶ የተገኘው በአሲሪያዊ ንጉሥ ሳርጎን ከክርስቶስ ልደት በፊት 715 ዓመት ሙክሪብ ተብለው በሚጠሩ በአምልኮት ቤተክህነት መሪዎች በምትስተዳደርበት ጊዜ ነበር [1] ።

ሳባ መሪዎቿ ንጉሥ ተብለው በታወቁበት ጊዜ በታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ ልትጠቀስ የበቃችው በንጉሥ ዳሪዮስ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓመት ነበር። በዚህ መሠረት የየመን ደቡብ ዓረብ ሳባውያን ከግሪክ ፊደል ተበድረው የራሳቸው ፊደል ፈጥረው ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለዓረቦችም ለማስተላለፍ የታወቁ ቢሆንም እነሱ ሳይታወቁ በፊት ትኖር የነበረች ንግሥተ ሳባ የእነሱ ዘርና ንግሥት ማለት ፈፅሞ የማይቻል ነው። ሳባውያን ብቻቸው ወይንም ሁሉም ደቡብ ዓረቦች አንድ ላይ ሆነው ኢትዮጵያን በቀኝ ግዛት ይዘው ቋንቋቸውና ፊደላቸውን አስተላልፈዋል ማለትም ኢውሮጳውያን የታሪክ ጸሐፊዎች የፈጠሩት ታሪካዊ መሠረት የሌለው ተረት ነው። እኛ የዘራችን ሀረግ ከሳባውያን በፊት እስከ ንጉሥ ሰለሞን መቁጠር የምንችል፣ ከሳባውያን ወይንም ከዓረቦች የምንወለድ ብንሆን ኖሮ በአንፃራዊ አጭር የሆነ ጊዜ መቁጠር አይሳነንም ነበር። ይህ በመሆኑ በእኛ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በዓረቦች የዚሁ [illegible] ታሪክ የሚያስታውስ ማስረጃ የለም።

ፊደል መበደር የተለመደ ነው፣ በቀይ ባሕር /የሐበሻ ባሕር/ ለካባቢ የታወቀ ፊደል የሳባውያን ስለነበረ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ብንበደርም በእኛ ሀገር ምሁራን ወይንም በዓረቦች ወይም በይሁዶች አማካኝነት ይሁን

[1] C. Conti - Rossini ibd p 98

አይታወቅም፡፡ በቅኝ ግዛት ይዞ ማስተዳደርና ስልጣኔና ዘርን ማስተላለፍ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ደቡብ ዓረቦች ይኽንን ተግባር ለማካሄድ የሀገራቸውና የሕዝባቸው አነስተኛነት ሲታይ ከአቅማቸው በላይ ከመሆኑም በላይ በታሪክ ያልተመዘገበ፣ ሁለቱ ሕዝቦች ኢትዮጵያና ደቡብ ዓረብ የማያምኑበት ነው፡፡

ስለዚህ ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት ናት እንጂ ዓረባዊት አይደለችም፡፡ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ፣ ከዚያ በፊትም የሚያቀርቡት የነገሥታት ስም ዝርዝር አንዳንድ ስሀተት ሊኖረው ይችላል፣ ነገር ግን ስለታሪክነቱ ሊካድ የማይቻል ሀቅ ነው፡፡

ሳባውያን ኢትዮጵያን አቀኑ፣ በቀኝ ግዛት ያዙ ከማለት ይልቅ ገናና ስም በነበራት ንግሥተ ሳባ ስም ሳባ የሚባል ሀገር በየመን ተሰየመ ማለት ይቀላል፡፡ የነገሥታቱ የስም ዝርዝር[1] ስንመለከተው ሳባ ወይም ሳቢ የሚል ስም ከክርስቶስ ልደት በፊት 1875-1985-1971-1453-1036 እንዲሁም ኢትዮጵያ የሚለውን 1856 እና 1730 እናገኛለን፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሳባ የሚለው ስም ቀድሞ በኢትዮጵያ ከደቡብ ዓረብ በፊት የተለመደ እንደነበረ ነው፣ የኢትዮጵያ ስምም የኽው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አክሱማይ የሚለው ስም ከክርስቶስ ልደት በፊት 788 እና 778 የአክሱም መንግሥት ከመመስረቱ በፊት ተጠቅሶ ይታያል፡፡ ይሄም የሚያሳየን አክሱም ቀደም ብላም ታውቃ እንደነበረች ነው፡፡ እንደዚሁም የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የነገደ ኩሽ ዘር ብቻ እንዳልነበረች ከዛሬዪቱ ኢትዮጵያም የነገደ ሴም ወይም ዮቅጣን ብቻ እንዳልነበረች ነው፡፡

ሁለቱ ነገዶች ድሮም ተከፋፍለው እንዳልኖሩ አሁንም ተከፋፍለው እንደማይኖሩ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ሁላችን ነገደ ኩሽ ወይም ነገደ ኢትዮጵያዊ መሆናችን ብቻ ነው የምናውቀው፡፡ በነገሥታት ስም ዝርዝር አባቶቻችን ሁለት ነገድ ለይተው ያወጡት ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ አሁንም በነገደ ኩሽና በነገደ ዮውቅጣን ተከፋፍላ እንደማትታወቅ የሚያስረዳ ነው፡፡ አሁንም ሰሜን ሱዳን ያሉት ኢትዮጵያውያን ቋንቋቸው ለውጠው ዓረብኛ ቋንቋችን ብለው ቢቀበሉም ዓረቦች አይደሉም፡፡ በሃይማኖትም ቢሆን ሰሜን ሱዳናውያን የእስልምና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት አስተድመው ተቀብለውት የነበረ የክርስትና ሃይማኖት ነበረ፣ ከዚያ በፊትም የሌላ እምልኮት እምነት ነበራቸው፡፡ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንም እንደዚሁ ክርስትና ከመቀበላቸው በፊት ሌላ እምልኮት ይከተሉ ነበር፡፡ በዘር ግን ሁለቱ ሕዝቦች ለነገድ ኩሽና ለነገደ ዮቅጣን ወይንም በዘመናችን ቋንቋን መሠረት በማድረግ ብሔር ብሔረሰብ አጠራር ተሰጥቷቸው ሊከፋፈሉ የማይችሉ አንድ ዘር አንድ ነገድ ናቸው፡፡

የሰው ልጅ በሚናገረው ቋንቋ ወይም በሚከተለው ሃይማኖት እንደ ዘር ተቆጥሮ ሊከፋፈል አይገባውም፡፡ ይህ ክስተት በሀገራችን ብቻ አይደለም የሚታየው በሌላ ሀገርም ለምሳሌ እንደ ፓኪስታን፣ ባንግላዴሽ የተከፋፈሉት በሃይማኖት እንጂ በዘር አይደለም፡፡ በሀገራችን ያለው ሁኔታ ስንመለከት ኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ሰሜን ለውጣ ሱዳን እንዴት እንደተፈጠረች ብለን በምንጠይቅበት ጊዜ፤ የማእከላዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ደካመት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከአክሱም መንግሥት ጀምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሱዳንን ከኢትዮጵያ ጋር ለማቀላቀል ያልሞከሩበት ጊዜ የለም፡፡ ሆኖም ዓቅማቸው ስላልፈቀላቸው ዓላማቸው ከግብ

---

[1] ተከለጻድቅ ገጽ 193



ለማድረስ አልቻሉም፡፡ ኢትዮጵያ ለሁለት ተከፍላ የሰሜኑ ክፍል ባዕድ ሀገር የሆነበት የኢትዮጵያ ማእከል ከናፓታ መሮዌ ወደ አክሱም የተዘዋወረበት የሽግግር ጊዜ ታሪክ ገልፅ አልሆነልንም፡፡ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያና የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ብሎ ስም መስጠት ይቻል ይሆናል፣ ቢሆንም አንድ የነበረች ኢትዮጵያ ለመሮዌና ለአክሱም ተብላ ተከፋፈለች ቢባል የተሻለ ይመስላል፡፡

# ምዕራፍ 2
# የአክሱም ዘመን፣

1ኛ ዝንኛው በታሪኳ የምንከራበት የአክሱም መንግሥት የተቋቋመበት ዘመን ለማወቅ ምንም ማስረጃ የለንም፡፡ የአክሱም መንግሥት በጽሑፍ ተጠቅሶ የተገኘው በአጋጣሚ ነው፡፡ በአንድ በአነስተኛ ድንጋይ ጽሑፍ በግሪክ ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው ከአሲመራና ከከረን ማህል [1] በሚገኘው ደቀመሐሪ በተባለው መንደር ከዓደ ተከለዛን በስተሰሜን ነው፡፡ ያፃፈው ንጉሥ ሰምብሩተስ ይባላል፡፡ ስሙ እንደ ኤውሮጳውያን የኢተዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ሴማዊ አይመስልም፣ ካማዊ ነው፡፡ ዘመኑ በሁለተኛ ወይም በሦስተኛ ክፍለ መቶ ዘመን ዓ.ም. ነው፤ ጽሑፉም የአክሱሞች ንጉሠ ነገሥት ትልቁ ሰምብሩተስ ከነገሠበት በ24ኛው ዓመት ይኸንን ጽሑፍ አሰራሁ የሚል ነው፡፡ በዚሁ መንደር አካባቢ የቀድሞዎቹ አምልኮት ቤተመቅደስ እንደነበረ ተገምቷል፡፡ ንጉሡም ሐውልቱን ያሰራው ለመንፈሳዊ ጉብኝት ወደ ቦታው በሄደበት ወቅት መሆኑን ይመስላል፡፡ በተቀራረበ ዓመተ ምህረት በግሪክ ቋንቋ የተፃፈባቸውን ሌሎች ሐውልቶች ተገኝቷል፣ 1ኛው በአዱሊስ ምፅዋ አጠገብ 2ኛው በእንዳ አባ ፓንተሌዮን ከአክሱም አጠገብ ናቸው፣ የንጉሡ ስም አልተፃፈባቸውም፡፡

ለአክሱም መንግሥት ታሪክ ትልቁ ወሳኝ ማስረጃ ሆኖ የተወሰደው በአዱሊስ[2] ሐውልት የተገኘው ጽሑፍ ነው፡፡ የተገኘው እንደ አጋጣሚ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሐውልቱ በቦታው አይገኝም፣ ጠፍቷል፡፡ ጽሑፉ ያገኘው አንድ ቢዛንታናዊ በ525 ዓ.ም. ከሕንድ ጉብኝት መልስ እንደአጋጣሚ አዱሊስ ተገኝቶ የነበረ ኮዝማስ ኢንዲኮፕለውስተ Indicopleuste የተባለው ደራሲ ነው፡፡ ኮዝማስ ከአንድ የሲናይ ተወላጅ የሆነው ነጋዴ ጋራ ሆኖ አባስ በተባለው የራሂት /ሲናይ/ ሀገረ ገዥ ጽሑፉ እንዲቀዳው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአንድ የንጉሥ ዙፋንና በአንድ የእብነበረድ ድንጋይ የተቀረፁ የ2 ንጉሦች ረጅም ጽሑፎች መሬት ወድቀው ተሰባብረው አግኝተዋቸው ጽፎ እንዳስቀራቸው ገልጿል፡፡ አንደኛው ንጉሥ ግብፃዊ ነው፣ የሚተርከውም በእስያ ስላደረጋቸው ጦርነቶች እና ስለተቀዳቻው ድሎች ነው፡፡ ሁለተኛው ንጉሥ ኢትዮጵያዊ በየብስና በባሕር ስላደረጋቸው ጦርነቶች እና ስለተቀዳጃቸው ድሎች የሚያወሩ ናቸው፡፡ የሁለቱ ንጉሶች ስም ሐውልቶቹ በመሰበራቸው ሊታወቅ አልተቻለም፡፡ በዚሁ "አዱሊታዊ" ተብሎ የሚጠራ ሐውልት ማስረጃ መሠረት ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ሰፊ ዘመቻዎች ማካሄዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የአክሱም ታሪክ የምናውቀው በፈራረሱ ድንጋዮችና ሐውልቶች በተጻፉትም ጭምር የሚገኙ ንጉሦች ለዝናቸው ብለው ያስቀረፁዋቸው ጽሑፎች ብቻ ነው፣ እነዚህም ማስረጃዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ የአክሱም ታሪክ የምናውቀው ከመጀመርያው በሚቋቋምበት ጊዜ አይደለም፡፡ በጠፋው የአዱሊስ ሐውልት የምናገኘው ጽሑፍ የአንድ አዲስ መንግሥት ሳይሆን የአንድ ረጅም ታሪክ ያሳለፈ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት፣ የተደራጀ፣ የምድር ጦርና የባሕር

[1] Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p 120

[2] Carlo Conti - Rossini ibd p 121



ኃይል ያለው፣ ከታላቁ የሮማ መንግሥት በጦር ሜዳ የሚፋለም መንግሥት ነው፡፡ ንጉሡ የሚተርከው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስላደረጋቸው ዘመቻዎች ነው፡፡

## 2. የአክሱም መንግሥት በሀገር ውስጥ ዘመቻዎች፣

በሀገር ውስጥ ባደረጋቸው ጦርነቶች ንጉሡ አሸነፍኳቸው፣ አስገበርኳቸው ከማላቸው ሕዝቦች የአክሱም መንግሥት መስራቾች መሆን ይገባቸው የነበረ ከማእከላዊ መንግሥት ቅርብ የሚገኙ አግዓዚያን እና ዓጋሜ ናቸው፡፡ ሌሎች ስማቸው ለመለየት የሚያስቸግር ሲጀን ሲሆኑ፣ በአዱሊስ አካባቢ የሚገኙ ሻሚኒ የተባሉ ሕዝቦች፣ ሰው በማይሄድባቸው በበረዶ በተሸፈኑ ተራራዎች የሚኖሩ ተጠቅሰዋል፣ ሀገሩም ብርዳማ ነው፣ በረዶም የሰው ጉልበት ድረስ ይደርሳል፡፡ በዚሁ አካባቢ ፍል ውሃ ያላቸው ሀገሮች ኢንዲ፣ ላዚኒ፣ ዘአጋባራ፣ የተባሉ ሕዝቦች ማስገበሩን ይተርካል፡፡ ቀጥሎም ተንጋይቲ የተባሉ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ የሚኖሩ ሕዝቦች አሸንፎ መንገድ እንደሰራ ይናገራል፡፡ አነነ በመቲነ፣ ሰሳያ፣ በተራራዎች የሚኖሩ ከቦ ከማረካቸው በኋላ ሴቶችና ልጆች በባርነት ወስዶ ንብረታቸውን እንደዘረፈ ገልጿል፡፡

## 3. መጠነ ሰፊ አክሱም ዘመቻ በግብጽ እና በሰሜን ዓረብ፣ የፓልሚሪ ጦርነት

ይህ ባሕርን አቋርጦ የተካሄደ ዘመቻ ኮንቲ ሮሲኒ ያልተለመደ ከኢትዮጵያውያን አቅም በላይ ብሎታል[1]፡፡ በየብስ ወደ ግብፅ መንገድ እያሰራ በመርከብ ተሻግሮ ወደ ሰሜን ዓረብ የተደረጉ ዘመቻዎች የተያያዙ ናቸው፡፡

ለደቡብ ዓረቦች የንግድ እንቅስቃሴ ደህንነት ለመጠበቅ የተደረገ ዘመቻ ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶት ነበረ፡፡ የአክሱም ጣልቃ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሠረት ነው ተብሏል፡፡ ከግብፅ ዘመቻ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ግን ፀረ- ሮማ መንግሥት መሆኑን ያስረዳል፡፡ በተዘዋዋሪ መንገድ አክሱም ፓልሚራን በመደገፍ በፀረ- ሮማ መንግሥት በጦርነቱ ተካፍሉ እንደነበረ ያስረዳል፡፡ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ወደ መጨረሻ ውድቀት የዳረጓት የሮማ መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ23 ዓመት ናፓታን ባወደማት ጊዜ ነው፡፡

በመሮዌ ደካማ መሆን በመጠቀም የአክሱም መንግሥት ወዳጅ የሆነው የብሌሚ በጃ መንግሥት ተቋቁሞ ነበረ፡፡ አክሱም ከብሌሚ ቤጃዎችና ከደቡብ ዓረቦች ጋራ ወዳጅነት ለመፍጠር ለብዙ ዘመናት ፀረ ሮማውያን የግብት ማስፋፋት ፖሊስ ትግል ስታካሄድ ቆይታ ነበር፡፡ ይህ ትግል በከፍተኛ ደረጃ የተከሰተው በ262 ዓ.ም. ነበር፡፡ የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ባልካናዊ አውሬሊያኑስ ነበረ፡፡ በዚሁ ጊዜ ፓልሚራ የተባለው በሰሜን ዓረቢያ ተቋቁሞ የነበረ መንግሥት ሶሪያ፣ ኢራቅና፣ ግብፅን፣ ሊሎችንም የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን ከሮማውያን እጅ አስለቅቆ ጦርነት በገጠመ ጊዜ አክሱም ከወዳጆቿ መንግሥታት ከብሌሚ ቤጃና በደቡብ ዓረቦች

[1] Carlo Conti - Rossini ibd p 123

በመታገዝ ለፓልሚራ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታ ነበር፡፡ ጦርነቱ በሮማውያን ድል አድራጊነት ስለተፈፀመ በንጉሠ ነገሥቱ [1] አውሬሊያኖስ መሪነት ድል አድራጊዎች ሮማ ሲገቡ ሮማውያን እንደ ልማዳቸው በ274 ዓ.ም. ከጦር ምርኮኞች ውስጥ ከፓልሚራ ንግሥት ዞኖቢያ ጋራ ብለሚ፣ቤጃ፣ አክሱማውያን እና የደቡብ ዓረቦች ምርኮኞች በሮማ አደባባይ በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓት በሰልፍ አልፈዋል፡፡ ስለ ጦር ምርኮኞች በሰልፍ ማለፋቸው የተረከው ቮቢስኮ የተባለው በጊዜው የነበረው ሮማዊ ታሪክ ፀሐፊ ነው፡፡

ትልቁ የዓረቦች ዘመን መነሳትና የዓረቦች ስልጣኔ ማስፋፋት ያልደረሰ በመሆኑ የፓልሚራ ሰሜን ዓረብ መንግሥት ተደምስሷል፡፡ ምናልባት ግን ለዓረቦች መነሳት መንገድ በመክፈት አስተዋጽኦ አድርጉ ይሆናል፡፡[2] ፓልሚራ ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ለሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት ለነበሩ ለሮማና ለፐርሲያ መንግሥታት ተቋቁማ ነፃነቷን ጠብቃ ቆማ ነበር፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት 23 ዓመት ናፓታ ከተደመሰሰችበት ጊዜ በኋላ ደካማው የመሮዌ መንግሥት ከሮማውያን ጋር ግንኙነት ነበረ[illegible] ሌላው ክፍል ግን ከሮማውያንና መሮዌ ጦርነት በኋላ ባዶ ቦታ በረሃማ የነበረው ብለሚ ሰፍረውበት፣ መንግሥት አቋቋመውበት ነበረ፡፡ ሮማዊ ታሪክ ጸሐፊ ቮቢስኮ ቢለሚ ቤጃ የአክሱም አጋርና ወዳጅ ናቸው ብሏቸዋል፡፡

የአክሱም መንግሥት የቤጃ ብለሚ ወዳጅ ስለሆነ በናፓታ ግዛት አልፎ ወደ ሰሜን እስከ ግብጽ ግዛት ዘመቻ ከማድረጉ በላይ መንገድም ሰርቷል፡፡ ይኽ የሚያሳየን የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያና የአክሱም ግንኙነት እንዳልተቋረጠ ነው፡፡

ራሱ የአክሱም መንግሥትም የቤጃ ተወላጆች ሰላሉበት ግዛቱ እስከ ባርካና እስከ አባይ የሚደርስ ነበር፡፡ ቤጃዎች ወደ ግብጽ ግዛት ዘልቀው እየገቡ ዘረፋ ያካሄዱ ስለነበር ከሮማውያን ጋር የፀብ መንስኤ ነበሩ፡፡ አክሱም በጦርነቱ ጣልቃ እንድትገባም አስከትሏል፡፡ ጥንታዊት መሮዌ እየተዳከመች ብትሄድም ከግብጽና ከሮማውያን ግንኙነትና ወዳጅነት ለመፍጠር ሞክራ ነበር፡፡ ከሁሉ ይበልጥ ግን ከአክሱም ጋር የበለጠ ግንኙነት ነበራት፣ የባሕር በሯ አዱሊስ ነበር፡፡ የአክሱምና የመሮዌ ወዳጅነት የሚገልፅ "ኢትዮፒካ" የተባለው መጸሐፍ በ"ትረካ"[3] አቡን የተፃፈው ይገልፃል፡፡ የሳባውያን ጽሑፍ በመሮዌ መገኘት የአክሱም ወይንም የየመን ነጋዴዎች ወደ መሬዌ ይመላለሱ እንደነበረ ያስረዳል፡፡ እንደገና መሬዌ በ254 ዓ.ም. በሮማዊ ንጉሠ ነገሥት ትሬቦኒውስ ጋሉስ ዘመን ከሮማ መንግሥት ጋራ ወዳጅነት ለመፍጠር የሞከረችበት ዘመን ነበረ፡፡

ተረር አማኒ የተባለው የመሮዌ ንጉሥ የአክሱምና የብለሚ ወዳጅነት ሰላስፈራው ከበባውን ለመበጠስ በማሰብ ከሮማውያን ጋራ መቀራረብ አስቦ እንደነበረ የሚያስረዳ ፊሌ በተባለው የመሮዌ ከተማ "በዲሞቲክ" ከተቀረፀ ጽሑፍ፣ መሮዌ ወደ ሮማ መልእክተኞቿን መላኳን ይገልፃል፡፡ ይህ የመሮዌ አቋም ግዛቷ በአክሱም ሠራዊት እንዲወረር ምክንያት ሆኗል፡፡ ምናልባት የመሮዌ መንግሥት ተቋርጦ በብለሚ መንግሥት የተጠቃለለው የብለሚ መንግሥትም የአክሱም አንድ ክፍለ ሀገር ከመሆን አልፎ አንድ መንግሥት ሆኖ አያውቅም፡፡ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የቤጃ ወረራ በማለት ይጽፋሉ፡፡ ነገር ግን ቤጃ በወረራ ሀገር ይዘው ገዝተዋል ለማለት አይቻልም፡፡

---

[1] C. Conti - Rossini ibd p I24
[2] C. Conti - Rossini ibd p 126
[3] C. Conti - Rossini ibd p 124



ምክንያቱም ዘላን ስለሆኑ በቋሚነት አንድ ቦታ ሰፍረው መንግሥት አቋቁመው አያውቁም፡፡ ሆኖም ግብፅ በሮማውያን እጅ በነበረችበት ጊዜ ተባይድ እየገቡ ይዘርፉ ነበር፡፡ በሰሜን ሱዳን ብቅ እያሉ የሚጠፉ ጥቃቅን የቤጃ መንግሥታትም ነበሩ፡፡ ቤጃ በጎርዶፋን፣ ሰናር፣ ገዚራ ሰፍሯል፡፡ እንድሁም በዛሬይቱ ኤርትራ ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ከሰላ በወረራም በስፈራም ዘራችን ቤጃ ነው የሚሉ ሰዎች ይገኛሉ፡፡ በከበሳ ከመረብ በስተሰሜንና በስተ ደቡብም ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ቤጃ በሄዱበት ቦታ አንድ ጠባይ አላቸው፤ ይኸውም ቋንቋቸውን ትተው የአካባቢውን ሕዝብ ቋንቋ በመናገር የአካባቢውን ሕዝብ መስለው የመኖር ችሎታ አላቸው፡፡ በዚሀ መሠረት በግብፅና ሱዳን የዓረብኛ ተናጋሪ ሆነው ዓረብ ሆነዋል፡፡ በኤርትራ እና በትግራይ ትግረኛና ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል፡፡ በኤርትራ ሰሜን ምዕራብ ሰፍረዋል፡፡ በሃይማኖትም እንደዚሁ እስላሞችና ክርስቲያኖች ሆነዋል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ በመጽሐፉ ምዕራፍ 12 ስለቤጃ የስልጣኔ ቅሪት ምልክቶች ብሎ ጽፏል፡፡ ቤጃም ሆነ ግእዝ ተናጋሪ ለእኛ ልዩነት የለውም፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የኩሽ ዘሮች ናቸው፡፡ የቤጃ ተብሎ የተገኘው የታሪክ ቅሪቶች በደምቢዛን እና በካርነሽም /ሀማሴን/ ፊደል መስል የተባሉ በድንጋይ ስሌዳ የተቀረፁ ጽሑፎች ናቸው፡፡ እንደ ፊደል ለማንበብ የማይቻል ቢሆንም ቅድመ "ሂሮግሊፊክ" ጽሑፍ የሚል ግምት ብንሰጣቸው ተገቢ ይመስላል፡፡ የቤጃ ቅሪት የተባሉ በየቦታው የተገኙ ሬክታንግል ቅርፅ ያላቸው መቃብር ናቸው፡፡ በሱዳን በባርካ፣ በሳሄል፣ ከሰላ አካባቢ በብዛት ይገኛሉ፡፡ እነዚሀ መቃብሮችም ቅድመ ፒራሚድ ተብለው ግምት ቢሰጣቸው ተገቢ ይመስላል፡፡ ይህ ሁሉ ሲታይ ኢትዮጵያ በስልጣኔ ከግብፅ ቀደምትነት አላት ለማለት የሚያስደፍር በቂ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ድሮም ሆነ አሁን በሰሜን ነገደ ኩሽ በደቡብ ነገደ ዮቅጣን የተከፈሉ ሕዝቦች እንዳልነበሩና እንደሌሉ እንገነዘባለን፡፡ የኢትዮጵያ ማእከል ወደ አክሱም የተዛወረበት ዋናው ምክንያት የግብፅ መንግሥት እና ስልጣኔ መውደቅ ነው፡፡

ኮንቲ ሮሲኒ[1] ቤጃ በ5 ጎሳዎች ይከፈላሉ ብሎ ጽፏል፣ እነሱም

1. አባብደ ( Ababde ) በደቡብ ግብፅ የሚኖሩ ዓረብኛ ተናጋሪ የሆኑ ከዓረብ የተዳቀሉ
2. ቢሺዓሪ (Bishiari) ሱዳን የሚኖሩ ቋንቋቸው ዓረብኛ
3. ሀደንዶዋ (Hadendoa)
4. ሐለንጋ (Halenga) (ኤርትራ)
5. ቤኒአመር በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሲሆኑ ቋንቋቸውም ግማሽ ትግሬ ነው፡፡ ግማሾቹ ቤጃ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው፡፡

የቤጃ ሕዝብ ምንም እንኳ ቋንቋቸው ወደ መጥፋት የተቃረበ አነስተኛ ሕዝብ ቢመስለም በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በጥንታዊት ግብፅ ታሪክና ስልጣኔ በቀጥታም ሆነ በተዛዋዋሪ የተከፈሉ ናቸው፡፡ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት ነበሩ፡፡ የዛሬዪቱ ሱዳን በሕዝብ በብዛትም በአመራርም የበላይነት ያላቸው ናቸው፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ተሰራጭተው የሚኖሩ ናቸው፡፡ በተለይ ቤጃ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ በኢትዮጵያ ብቻ ስለሚገኙ የቤጃ ሀገርና ማእከል ኢትዮጵያ ናት ለማለት ይቻላል፡፡ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የምትባለው መስኗ ከየት ወዴት እንደሆነ በትክክል ባይታወቅም ዋና ከተማዋ ናፓታ በነበረበት ጊዜ በአሁኑ አስተዳደር ሱዳን ውስጥ ሲሆን፣ ዋና ከተማዋ መሮዌ በነበረበት ጊዜ ግን በአሁኑ

---

[1] C. Conti - Rossini ibd p 271

አስተዳደር በኢትዮጵያ ግዛት (ኤርትራ) ውስጥ ናት፡፡ ስለዚህ በአሁኑ አስተዳደርም ቢሆን የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ በሙሉ በሱዳን ውስጥ አይደለችም፡፡ አነስተኛ ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ አለች፡፡ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከናፓታ ወደ መሮዌ መዛዋወሩን ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ ድሮም እንደዛሬ የቋንቋ አቀማመጥ ከሆነና የግእዝ ቋንቋ ከደቡብ ዓረብ የመጣልን ነው ብለን ካላመንን መረዌ አካባቢ የኖረው የግእዝ ቋንቋ ተናጋሪ ሌላ ቋንቋ የካም ቋንቋ ተናጋሪ በናፓታ አካባቢ በሚኖረው ሕዝብ ኃይሉ የአስተዳደር ስልጣን በመረከቡ ነው ብለን ትርጉም ልንሰጠው እንችላለን፡፡ በአጠቃላይ ይሄ የአክሱም መንግሥት ያደረገው ዘመቻ የግዛት ማስፋፋት ሳይሆን የአንድነት ማስከበርና የሁለቱ ሕዝቦች መወሀድ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1581 ዓመት ጀምሮ በተለያዩ የግብፅ ፈርኦኖች አማካኝነት ግብፅ በቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ /ኑቢያ/ ወሰን እያለፈች ገዝታለች የሚለው አባባል ትክክል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የግብፅ እና የናፓታ መንግሥታት ሁለቱም በጋብቻ የተሳሰሩ ስለነበሩ ሁለቱ መንግሥታት መዋሀድ የተለመደ ነው፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1200 አመት ግብፅ በእስያም በአፍሪካም ሽንፈት በገጠማት ነበረ፡፡ በዚሁ ዘመን ሊብያዊ ፈርኦን ሆኖ በቴብ መቋቋሙ ለመቃወም የቤተ መቅደስ አለቆች ከሊቢያውያን ቀድሞ የነበሩ የስርወ መንግሥት ወራሾች በመያዝ በናፓታ መንግሥት ለመመስረታቸው ኢትዮጵያ ከግብፅ ተገነጠለች፡፡ በተራቸው ዘመን ጠብቀው የናፓታ ነገሥታትም በግብፅ ላይ የበላይነት በመቀዳጀታቸው ናፓታ ከግብፅ ከተገነጠለች 500 ዓመት በኋላ ሁለቱ መንግሥታት አዋሕደው ፈርኦን ተብለው 75 አመት ግዝተዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ካስሀታ የፒያንኪ 2ኛ አባት የፈርኦን ሴት ልጅ አግብቶ ስለነበረ ልጁ የፒያንኪ የፈርኦን ዘውድ ይገባኛል፣ ተወላጅ ነኝ በማለት በኃይል ወሮ ከያዘ በኋላ የተዋሀዱ የግብፅና የኢትዩጵያ ናፓታ ፈርኦን ለመሆን በቅተዋል፡፡[1]

## 3. መጠነ ሰፊ የአክሱም በባህር ዘመቻ ወደ ደቡብ

በመርከቦች ወደ ደቡብ የተደረገው ዘመቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ተደርጎ የማይታወቅ ነው፡፡ ምንም እንኳን ተጨማሪ ሌላ ማስረጃ ባይገኝም ከሁሉ የበለጠ የአክሱም መንግሥት የመጨረሻ ዓላማው ነበረ፡፡ የእዱሊስ የሐውልት ጽሑፍ[2] የሚለውን ብቻ በመጥቀስ ረሐውሲና ሰላተ ሰማሊያና ከአባንያ በታች ያሉ ሕዝቦች እጣን ከሚነግዱ የበርበር ሀገር በስፊው ሚዳዎች ውሃ የማይገኝባቸው የሚኖሩ ሕዝቦች አስገብሮ የባሕር ወደብ እንዲጠብቁ አዘዛቸው ካለ በኋላ ከባርባሪ ሰዎች ደቡብ አገራቸው ተራራዎች የበዙበት ሲሆን ራሴ በጦር ሜዳ ተዋግቼ ከአሸነፍኳቸው በኋላ ግብር እንዲከፍሉ አዝዤ በነፃ ለቀቅኳቸው ይላል፡፡

ወደ ደቡብ ሀገሮች ዘመቻ የመጨረሻ ዓላማ የሀገሩ ስም ባይታወቅም የወርቅ ሀገር ለመድረስ ነበረ ብለዋል፡፡ ይህ ስሙ ያልታወቀ ሀገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚለው ወሊጋ ሊሆን አይችልም፡፡ ወርቅ በብዛት የሚገኝበት ንግሥተ ሳባም ወደ ንጉሡ ሰለሞን ከመሄዷም በፊት በመርከብ የተሳፈረችበት በመጽሐፍ ቅዱስ ኦፌር ተብሎ የሚጠራው ወደብ ሶፎላ ወደብ ነው፡፡ የወርቅ ሀገርም ዝነኛው ትልቁ የሞኖሞታፓ መንግሥት ሀገር ዚምባቡዌ ነው፡፡

---

[1] C. Conti - Rossini ibd p 271

[2] C. Conti - Rossini ibd p 121



ስለዚሀ ይህ የአክሱም ዘመቻ የደረሰበት ሀገር ዚምባቡዌ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ በቀድሞ ጊዜ የወርቅ ግዕድን በሚመረትበት ጊዜም የኢትዮጵያውያን እጅም እንደነበረበት ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ፡፡

## 4. የአክሱም መንግሥት ደቡብ ዓረብን ከግዛቱ ማቀላቀል

የአክሱም መንግሥት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በደቡብ ዓረብ የግዛቱን ማስፋፋት ዘመቻ አካሂዶ ነበር፡፡ ነገር ግን ዘመቻ መካሄዱ የሚገልፁ ማስረጃ የለም፡፡ በተዘዋዋሪ ግን ዘመቻ መካሄዱ እና ደቡብ ዓረብ በአክሱም መንግሥት ቁጥጥር ስር መዋሏን የሚገልፁ ሁኔታዎች ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚከተለው ያብራራዋል፡፡ በ281 ዓ.ም. ደቡብ ዓረብ ዝነኛው የነበረው ሻሚር በተባለው ንጉሥ ትገዛ ነበረ፡፡ ይሀ በጉረቤት ሳሀርታን ጦርነት ገጥሞ ያሸነፋቸው ለመሆኑ የሚገልፅ ጽሑፍ በመገኘቱ ሳሀርታን ማለትም የአበሻ ጎሳ በመሆናቸው አድራጊቱ የአክሱም መንግሥት ያስቆጣል፡፡ ከጭፍጨፋ የተረፈ ሕዝብም እርዳታ ስለጠየቁ የአክሱም መንግሥት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ የመንን ከግዛቱ ማጠቃለሉ የሚገልፁ ምልክቶች ብሎ ኮንቲ ሮሲኒ በመጻፉ የጠቀሳቸው የአክሱም መንግሥት ከዚህ በፊት ሲጠራበት የነበረው የአክሱም መንግሥት የሚል ስያሜ በተጨማሪ የሒሚያር፣ የራይዳን፣ የሳባና የሳልሄን ንጉሥ ተብሎ በመጠራቱ ከንጉሥ ሻሚር በኋላ የየመን ንጉሦች ተራ ቀይረው በታሪክ ተቋርጦ በመገኘቱ፣ የመን ለብዙ ዓመታት በአክሱም መንግሥት ቁጥጥር ስር እንደነበረች የሚያስረዳ ነው፡፡[1]

ዘመቻውን ያካሄደው አክሱማዊ ንጉሥ ማን ነበረ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ቀጥተኛ የሆነ የጽሑፍ ማስረጃ ከየመን ከኢትዮጵያ፣ ከግሪክና፣ ከሮማ ገለልተኛ ሀገሮችም ማስረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ በመሆኑ ኑሚዝማቲክ (Numismatic)[2] በጊዜው የነበሩ ንጉሦች ያሳተሟቸው ገንዘቦች በመጠቀም በአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በአክሱም የነበረ ንጉሥ አፊላስ እንደነበረ ባሳተማቸው ገንዘቦች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት ድል አድራጊው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አፊላስ መሆኑን ለመገመት ተችሏል፡፡ አፊላስ በገንዘቡ ላይ የተጠቀመበት ፊደል ግሪክኛ ነበር፡፡ ከሱ በኋላ የነገሡ ኢንዲቢስና ዋዜብ የተባሉ ኢትዮጵያውያን ንጉሦች ግን በገንዘቦች ላይ የተጠቀሙበት ፊደል ኢትዮጵያዊ ነበር፡፡ ትልቁና ዝነኛው የአክሱም ንጉሥ ኢዛና የሚያሳትማቸው ገንዘቦች በግሪክ በደቡብ ዓረብና በኢትዮጵያ ፊደል ነበሩ፡፡

የኢዛና መጠሪያም 1. የአክሱም 2. የሰጊምያር 3. ሳባ 4. የራይዳን 5. የሳልሄን 6. የሐበሻ 7. ዲያሞ 8. የካሱና 9. የቤጃ ንጉሥ የሚል ነበረ፡፡

2ኛ. 3ኛ. 4ኛ. 5ኛ. መጠሪያዎች የደቡብ ዓረብ መጠሪያዎች ናቸው፡፡ ሐበሻ የሚለውም አክሱም ከሚለው አንዳንድ ጊዜ ይጠቃለላል፡፡ እንደዚሁም አክሱም የሚለው ኢትዮጵያ ተብሎ አንዳንድ ጊዜ ይጠራል፡፡ እንደ ሀገር ሌላውን ሀገር ጉልበት አግኝቶ ከገዛ ቋንቋውን ባሕሉንና ዘሩን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ የአክሱም መንግሥት ደቡብ ዓረብን መግዛቱ በታሪክ የተረጋገጠ ሲሆን ደቡብ ዓረብ ግን ኢትዮጵያን መግዛቷ በታሪክ የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ኢውሮጳውያን

---

[1] Carlo Conti - Rossini ibd p 126

[2] Carlo Conti Rossini ibd p 128

ማንኛውንም ስልጣኔ ከእስያና ከኤውሮጳ ነው ወደ አፍሪካ ሊሄድ የሚችለው የሚል ዘረኛ አስተሳሰብ ስላለቸው ቀደምት አባቶቻችን የሳብያውያን ፊደል በመውሰዳቸው ልበወለድ ታሪክ በመፍጠር ደቡብ ዓረብ ኢትዮጵያን በቀኝ ገዥነት ይዛ እንደነበረ ስልጣኔዋና ቋንቋዋን ባሕሏንና ፊደሏን እንደሰጠች በማስመሰል በባሕላችን የሌለው ታሪክ እንድንቀበለው በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሀቁ ግን ደቡብ ዓረብ በሳሐርታን ይገኙ የነበሩት የሐበሻ ሕዝቦች በቅድመ ታሪክ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ዓረብ ተሻግረው ወይንም እዛው ተፈጥረው የሰፈሩ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ የአክሱም መንግሥታት ከላይ እንደተገለፀው ሌላ ሀገርን ለመውረር ሳይሆን ዘሮቻቸው የሆኑ የሐበሻ ሰዎች ከደቡብ ዓረቦች ጥቃትና ጭፍጨፋ ለማዳን ዘመቻ አካሂደው ለብዙ ዓመታት ከ281 እስከ 360 የመንን በቁጥራቸው አድርጉዋቸው እንደነበረ በታሪክ የተረጋገጠ ነው፡፡ ዘመቻውና ጦርነቱ አስልጣኞቻችን እና አባቶቻችን በተባሉት በሳብያውያን ላይ ነበረ፡፡ ኢውሮጳውያን ምሁራንም ቢሆን ነጮች እና እሲያውያን ከፍተኛ ዘር አፍሪካውያን ዝቅተኛ ዘር ከሚለው አመለካከት ሊላቀቁ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ ታሪክ ለመፃፍ ችግር አለባቸው፡፡

የሳባ የራይዳኒት የሐድራሙት የሳማናት ንጉሥ ተብሎ የሚጠራ ሻሚር የሐበሻ ጉላ የሆኑ ሰሐርታን ዳዋእት በተባሉ ጦርነት ገጥሞ እንዳሸነፋቸው የሚገልፅ ጽሑፍ በአንድ ድንጋይ የተቀረፀ በየመን ይገኛል፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ከአክሱም ንጉሥ እርዳታ በጠየቁት መሠረት እፈላስ ወደ የመን ሊዘመት ችሏል፡፡ ሰሐርቲ የሚባል ሀገር በኢትዮጵያ ከመረብ በሱተሰሜንና በስተደቡብ ይገኛል፣ በየመንም ይገኛል፡፡ በየመን ሳሐርታን የሚባለው አካባቢ የመን ባሕር ዳርቻ የሚገኘው የሚኖሩ ሕዝቦች ዓረቦች እንደራሳቸው ጎላ አይቆጥሯቸውም፣ ሐበሻ አፍሪካዊ የሚኖርበት ሀገር የዓረቦች እምነት መሆኑን ኮንቲ ሮሲኒ ገልጿል፡፡[1] ስለዚህ ሰሐርቲ የዓረብ ስም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ስም ነው ዛዋእት የተባሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡

እላይ እንደተገለጸው በኮዝማስ ዘአዱሊስ ሐውልት የተገኘው ማስረጃ ያፃፈው ንጉሥ የመጀመርያና ብቸኛ ከእኔ ጎላ ነገሥታት ዘማለቱ የአክሱም መንግሥት መሥራች ሊሆን እንደሚችል ተገምቶ ነበረ በማለት ኮንቲ ሮሲኒ ጽፏል፡፡ ማስረጃም የተጻፈው በ250 ዓ.ም. ስለሚገመት አሁን ካለንበት ዘመን 1995 ዓ.ም. 250 ሲቀነስ 1745 ዓ.ም. ዝቅ ይላል ማለት ነው፡፡ ታሪካችን ከንግሥተ ሳባ በመጀመር ኢትዮጵያ 3000 ዓመት ታሪክ አላት እየተባለ ሲነገር የምንሰማው ጉዳይ ነው፡፡ ኤውሮጳውያን የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች ደግሞ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ዘመን የታሪካችን መነሻ በማድረግ ደቡብ ዓረቦችም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የመጡት በ250 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ስለነበሩ ኢትዮጵያ የ2500 ዓመት ታሪክ አላት ትባላለች፡፡

## 5. የኢትዮጵያ ፊደል

የኢትዮጵያ ፊደልም በሚመለከት ጉዳይ እንደገና በማንሳት አባቶቻችን ፊደሉን የፈጠሩት በጣም አሻሽለው ነው፡፡ በመጀመርያ ቡስትሮፈዶን (Bustrophedon)[2] የሚባል የነበረው ማለት ከግራ ወደ ቀኝ አፃፃፍ

[1] C. Conti - Rossini ibd p 127

[2] C. Conti - Rossini ibd p 220



በማስቀረት እንደ ግሪኮች ከሴማውያን የመጀመርያና ብቸኛ ከግራ ወደ ቀኝ አፃፃፍ በመከተል አሻሽለውታል፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ብዙ ለውጥ በማምጣት በ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ[1] ፊደል ሊፈጠር ችሏል፡፡ የደቡብ ዓረብ ነው የተባለ ጽሑፍ በግብፅ ዋዲ ሐማማት (Wadi Hamamat)[2] የተገኘው ጽሑፍ የኢትዮጵያ ፊደል ይሁን ወይንም የተሻሻለ የደቡብ ዓረብ ፊደል ይሁን መለየት የሚያስቸግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ ራሳቸው ሳባውያን የዓረብኛ ፊደል ከመከተላቸው በፊት በኢትዮጵያ ፊደል መጠቀም መጀመራቸውን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩልም አንዳንድ ምሁራን የተሻሻለው ብዙ ቆይቶ ወይስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው የሚል አስተያየት ተሰንዝሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ በዓዲ ቀይህ አጠገብ የሚገኘው በእውዳሉ ተራራ፣ እንዲሁም በአዲ ቀይህ እና ደራ መሐከል የሚገኘው ደራ በተባለው መንደር የተገኙ ጽሑፎች የሳባውያን ፊደል ለውጥ ሂደት የሚገልፁ በመሆናቸው ምሁራን ያቀረቡት ሐሳብ ውድቅ በማድረግ ለውጡ የተደረገው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑ ጽፏል፡፡ የመጀመርያው የኢትዮጵያ ፊደል ጽሑፍ የተገኘው በአንድ መቃብር ሐውልት[3] መታራ (Metara) በተባለማው መንደር በአከለጉዛይ ነው፡፡

ከኢዛና በፊት የነበረ ዋዘብ (Wazeb) የተባለው የአክሱም ንጉሥ ያወጣቸው ገንዘቦችም በአዲሱ የኢትዮጵያ ፊደል የተጻፈ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፊደል ጥንታዊነት የሚያረጋግጡ በመሆናቸው የምሁራኑ ተቃውሞ ለውጡ የመጣው በ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመርያ አጋማሽ አለመሆኑን የሚያቀርቡት ማስረጃ የለም፡፡

2. ሌላ ጥያቄም ተነስቷል ለውጡ ያመጡት ማን ነበሩ? የሚል ነበረ[4] የኢትዮጵያ ፊደል ከሕንድ ፊደል ግንኙነት አለው በማለት የተወረሰው ከሕንድ ፊደል ነው ብለው የተከራከሩ ነበሩ፡፡ ይህ አባባል ግን ሊሆን የማይችል ነገር ነው፣ ምክንያቱም ሕንድና ኢትዮጵያ በጣም የተራራቁ ስለሆነ የቅርብ ግንኙነትም ስላልነበራቸው ተቃውሞው ውድቅ ሆኗል፡፡

3. ፊደሉን ያመጡት ሚሲዮናውያን ክርስቲያኖች ናቸው የሚል አስተያየትም ተሰጥቷል፡፡ ይኸም አባባል ትክክል አለመሆኑን የምንረዳው ለውጡ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት በቅድመ ክርስትና በነበረው አምልኮት ጊዜ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

4. ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በግሪኮች ምሁራን አማካኝነት ነው የሚሉም ነበሩ፣ ይኼም ቢሆን የማይመስል አስተሳሰብ ነው፣ ምክንያቱም ግሪኮች ለኢትዮጵያ ፊደል ለመፍጠር ይጨነቃሉ ብሎ ማሰብ የማይመስል ነው፡፡

5. ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት የኢትዮጵያ ምሁራን ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አስተያየትም ተሰንራዝራል፡፡ ይኸም በቂ ማስረጃ ባይኖርም ትክክል የሚመስል ነው፡፡

6. በሰሓርታን ደቡብ ዓረብ ባሕር ዳርቻ ሰፍረው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ከሳባውያን ይፈጸምባቸው የነበረ በደልና እልቂት ለማዳን ወደ ደቡብ ዓረብ ፀረ ሳባውያን የአክሱም መንግሥት ዘመቻ መሪ የነበረው

[1] C. Conti - Rossini ibd p 221

[2] C. Conti - Rossini ibd p 221

[3] C. Conti - Rossini ibd p 221

[4] C. Conti - Rossini ibd p 221

የአክሱም ንጉሥ አፈላስ የዘመተበት ዘመን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፊደልም ከሳባውያን የተወሰደው በዚህ ዘመን በመሆኑ የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ ያገባ አፈላስ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ፊደሉ የተሻሻለውም በኢዛና ንጉሥ ዘመነ መንግሥት መሆኑን አጠያያቂ አይሆንም ብዬ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ሳባውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አፈላስ መሆኑን ብለን መደምደም እንችላለን፡፡

7. ከአፈላስ በፊት የነበሩት ነገሥታት በሐውልቶች ያስቀርጿቸው የነበሩ ጽሑፎች አፈላስ ራሱም ተከታዩ ንጉሥ እንዲሊቢስም ይጠቀሙ የነበሩ በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ቀጥሉ የነገሠ ንጉሥ ዋዚብ ግን በኢትዮጵያ ፊደል ሻወል የሌለው ተጠቅሟል፡፡ ከእሱ ቀጥሉ የነገሠ ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ ኢዛና እንደአስፈላጊነቱ በሳባ፣ በግእዝ፣ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ሻወል የሌለው በመጨረሻም በግእዝ ፊደልና ቋንቋ ሻውል ያለው ይጠቀም እንደነበረ ታውቋል፡፡ ስለዚህ ከሳባውያን ተወስዶ ተመሳሳይ ፊደል በኢትዮጵያ የተፈጠረው ኢትዮጵያዊ ፊደል እንደሚባለው ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት የመጡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስተኛ እስከ ሁለተኛ ያለው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይሆን ኢትዮጵያ በአፈላስ ንጉሥ መሪነት ዘመቻ አካሂዳ የመንን ከግዛቷ ያጠቃለለችበት ጊዜ በ4ኛው መቶ ክፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሲሆን፣ ስራ ላይ የዋለውና የተሻሻለውም በንጉሥ ዋዚብ እና በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት መሆኑን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች በተጨማሪ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከአፈላ የየመን ዘመቻ በፊት የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ የሚያመለክት በታሪክ የተመዘገበ ነገር የለም፡፡ ለወደፊት በአርኪአሎጂ ቁፋሮ ሌላ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ባሉት ቀቲት ማስረጃዎች መሠረት ግን ከንጉሥ አፈላስ በፊት የአክሱም ነገሥታት በድንጋይና በሐውልቶች ጽሑፎቻቸው ይጠቀሙበት የነበሩት ቋንቋ ዓለም አቀፋዊ እውቅና በነበረው በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ብቻ እንደነበረ እንረዳለን፡፡ እንደ ኮንቲ ሮሲኒ አገላለጽ ንጉሥ ኢዛና ከግሪክ ቋንቋና ፊደል በተጨማሪ በሳባና በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ያጻፈው ዝናው በአካባቢ ሀገሮች እንዲታወቅለት በማሰብ ሲሆን፣ በሳባ ፊደል፣ በግእዝ ቋንቋ የሳባ ቋንቋ አንዳንድ ጊዜ የተቀላቀለበት መገኘቱ የሳብያውያን ቋንቋ በቤተመንግሥቱ እንብዛም እንደማይታወቅ የሚያስረዳ ምልክት ነው ብሎታል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ይገዛ የነበረው የደቡብ የመን እንዲገባቸው [1] የኢትዮጵያ ነገሥታት በሐውልቶቻቸው በሳባ ፊደልም ይጽፉ ነበር፡፡

አንድ ሀገር ቋንቋው በፊደል ጽፎ ከተጠቀመ እስቀድሞ በሥልጣኔ የደረጀ መሆን ይጠበቃል፡፡ እኛ የሥልጣኔ ቀደምትነት ያለን እንደመሆናችን መጠን የተሻሻለ ፊደልም በአፈላስ ዘመቻ ዘመን ከየመን ወስደን እንጂ፣ ደቡብ ዓረቦች ጊዜው በትክክል የማይታወቅ ዘመን ወደ ሀገራችን አምጥተው ሰጡን አስተማሩን ማለት ልበወለድ ታሪክ ነው፡፡

[1] Conti - Rossini ibd p 132



## 6. የአክሱም መንግሥት ወደ ዓረብ አገር ተሻግሮ የተካሄደው ቅዱስ /የመስቀል/ ጦርነት[1]

ዘመቻው የተካሄደው በንጉሥ ካሌብ በ525 ዓ.ም ነበረ፡፡ የተካሄደበትም ምክንያት የጥንት አምልኮት ተከታይ የነበሩ ዓረቦች በክርስትና ተከታይ ዓረቦች ያደረሱት በደልና የጅምላ ጭፍጨፋ ለመበቀል ነበር፡፡ በዚሁ የአክሱም መንግሥት ጣልቃ ገብነት ዘመቻ መካሄድ ብዙ የማስረጃ ምንጮች አሉ፡፡ ነገር ግን በብዙ መንገድ እና አስተያየት ታሪኩን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የመስቀል ጦርነት ከአውሮጳውያን የመስቀል ጦርነቶች የሚለይበት በአውሮጳውያን በወዶ ዘመቾች የተካሄደ ሲሆን የኢትዮጵያ ግን በንጉሡ የሚመራ ነበረ፡፡

1. ከኮዝማስ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ቀድቶ ለታሪክ ያስቀረ
2. ከቢዛንታይን
3. ከሶርያ
4. ከዓረብ
5. ከኢትዮጵያ ወገን ምንጮች ናቸው፡፡

ጦርነቱ ስ 3 ክፍል መከፈል ይቻላል

1ኛ. በመጀመርያ የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው የዘርቢያ ዓረባዊ መንግሥትን ለመረዳት ይሁን እንጂ፣ ከግዙፍ የሮማ መንግሥት ጥቃት፣ ፀረ- ሮማ መንግሥት ነበር፡፡

2ኛ. በሁለተኛው የአክሱም መንግሥት ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ያበሻ ዘሮች ከጭፍጨፋ ለማዳን ፀረ ሳባዊ መንግሥት ነበር፡፡

3ኛ. የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ሃይማኖታዊ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ከእልቂት ለማዳን ፀረ - ሂሚያር ይሁዳዊ ዓረባዊ መንግሥት ነበረ፡፡ የ1ኛና 2ኛ ጦርነቶች የተካሄዱት በኢትዮጵያ ፍላጐት ብቻ ሲሆን 3ኛ ጦርነት ግን ተጠቃሚና አይዞህ ባይ 3ኛ. ወገን ትልቁ የቢዛንታይን መንግሥት እጅ ነበረበት፡፡ ይህ መንግሥት ራሱ ምንም ሳይንቀሳቀስና ስጦርነቱ አስተዋፅኦ ሳያደርግ የአክሱም መንግሥትን ብቻ በቀጥታ ልመና በመገፋፋት፣ እንዲሁም የግብፅ እስክንድሪያ ፓትርያርክም የደቡብ ዓረብ ክርስቲያኖችን እንዲረዳ የአክሱም መንግሥትን እንዲያግልጹ በማድረግ፣ በውጭ ኃይሎች ግፊት የተደረገ ጦርነት ነበር፡፡ የቢዛንታይን መንግሥት የፔርሲያን መንግሥት ለማሸነፍ ሰላቃተው ኢትዮጵያን መሣሪያ ያደረገበት ብቻዋን በጦርነት እንድትካፈል ያጋለጣት ወቅት ነበር፡፡ ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ፍልሚያ በሚያደርጉበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጥቅም በማይነካ ጉዳይ ብቻዋን በጦርነት አዘቅት መግባት አይገባትም ነበር፡፡ ስለጉዳዩ ዝርዝር ሰንገባ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ድል አግኝታለች፣ ለሃምሳ ዓመታት የመንን ገዝታለች፡፡ እንዳንዶቹ 72 ዓመት ያደርጉታል እስከ 597[2] ነገር ግን የዓረብ ሕዝብ ጥላቻ ብቻ ነበር ያተረፈችው፡፡ ዘመቻው ግዙፍ ነበር፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቀይ ባሕርን ሲያቋርጡ በ191 በቢዛንታይን የንግድ መርከቦችና በ170 አገ

[1] C. Conti - Rossini ibd p 167
[2] C. Conti - Rossini ibd p 199

ካሌብ ባሰራቸው መርከቦች ተሳፍረው ነበር፡፡ የመን የደረሱትና አጼ ካሌብ ዘመቻ ያካሄደው በሁለት ዙር ነበር፡፡

በመጀመርያ ጦርነት ሳይገጥመው የሒምያር ንጉሥ እጁን ስለሰጠ ወድያውኑ አጼ ካሌብ ራሱ የሾመው በየዓመቱ ግብር የሚከፍል ክርስቲያን ንጉሥ ትቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ፣ ነገር ግን ስለከዳውና የክርስቲያን ጭፍጨፋ ስለቀጠለ እንደገና ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ይዞ ከዓረቦች ጋራ ጦርነት ገጥሞ ድልን ተቀዳጀ፡፡ ሒምያር ንጉሥ ሸሽቶ በፈረስ እየጋለበ ቀይ ባሕር ውስጥ ገብቶ ሞተ፡፡ አዲስ የተሾመ ንጉሡም ብዙ አልቆየም አጼ ካሌብ ንጉሥ አድርጎ የሾመው አብርሃ የተባለውም ወዲያውኒ ከዳ፡፡ ከኢትዮጵያ ወታደሮች ግማሾቹ ከዓረብ ሀገር ተባረሩ፡፡ በመጨረሻ አብርሃ የንጉሥነት ስልጣን ነጥቆ ያዘ፡፡ ቆይቶ ከአጼ ካሌብ ወኪል ጋር ቢታረቅም እንደ ነፃ ንጉሥ ሆኖ ሀገሩን ይመራ ነበር፡፡ በኢትዮጵያውያን በኩል እስከ ዘመናችን ድረስ አጼ ካሌብ እጽብሀ ተብሎ እየተጣራ አብርሃ ወአጽብሀ እየተባሉ ከአቡነ ፍርሚናጦስ ከሣቴ ብርሃን እኩል ወደ ኢትዮጵያ ክርስትና ያስገቡ ተብለው እንደ ቅዱሳን ይከበራሉ፡፡ በዓረቦች ዘንድ ግን ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ጥላቻ ነበረ የዘመኑ ያተረፉት፡፡ የሕዝብ ዘፈኖች ፀረ- ኢትዮጵያ የጭቆና አገዛዝ ነበሩ፡፡ የዓረብ ጸሐፊዎች "ሴቶች የሚገርዙ፣ የቁላ ብሊታዎች" ወዘተ... እያሉ ኢትዮጵያውያንን እያጥላሉ ይፅፉ ነበር፡፡ የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች የሚተርኩት በኢትዮጵያና በደቡብ ዓረብ ያለው የስጋ ዝመድና የሚያስታውስ ሲሆን፣ ከዓረብ ወገንም ሆነ ከኢትዮጵያ ወገን ግን ይህን ዝምድና የሚያስታውስ ምንም ማስረጃ የለም፡፡

ዓረቦች ብቻቸው ከኢትዮጵያ ቀንበር አገዛዝ መላቀቅ ስላልቻሉ ለቢዛንታይን መንግሥት ስሞቻቸውን ሊያሰሙ የሚያዳምጧቸው ስላጡ ፊታቸው ወደ ፋርስ ንጉሥ አዞሩ፡፡ ፋርስ ከቀይ ባሕር ብዙ የሚርቅ ሀገር በመሆኗ፣ ቀይ ባሕር ለመድረስም በረሀማ ቦታዎች አቋርጣ ማለፍ ስለሚያስፈልጋ፣ በደቡብ ዓረብ አስተዳደር ጣልቃ እንድትገባና የዓረቦች ጥያቄ ለመቀበል ተላል አልነበረም፡፡ በመጨረሻ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያላት መሆኑን ስላወቀች 800 ወታደሮች ብቻ በመላክ የመንን ይገዛ የነበረው የአብርሃ ልጅ ማብሩክ የተነሳበት የሕዝብ ዐመፅ በቁጥጥሩ ስር መዋል ስላልቻለ በፀረ ኢትዮጵያ ዐመፀኞች እየተረዳ የፋርስ መንግሥት በቀላሉ ድል ሊቀዳጅ ችሏል፡፡ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዓረብ የተወለዱ ክልሎችም ጭምር ተገደሉ፡፡ ኃይለኛ እንደ አጼ ካሌብ ንጉሥ በኢትዮጵያ ቢኖር ኖሮ ለኢትዮጵያ ታሪክና ሕልውና ከሃይማኖት ጉዳይ ሌላ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለነበረ ሌላ የተጠናከረ ዘመቻ ማድረግ ባስፈለገ ነበር፡፡ ይህ ባለመደረጉ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት መሆኗ አከተመ፡፡ ቀይ ባሕርም እንደ ጥንቱ ያበሻ ባሕር ኢትዮጵያዊ የሚል ስያሜ ተሸር በግሪኮች አጠራር ለዘለቄታ ቀይ ባሕር ተባለ የሶማሌ ባሕርም ባርባሪያ ባሕር ተብሎ ይጠራ የነበረው ሕንድ ውቅያኖስ ሆነ፡፡ የአዛንያ አጠራርም ተሰርዞ ሶማሊ ኬንያ ታንጋኒካ ወዘተ... የሚል ስም ተሰጣቸው፣ ኢትዮጵያ ግዛት ክልል ከባብ ኤል መንደብ በስተ ደቡብ ያለው አጣች፡፡ ለጥቂት ጊዜ ኢትዮጵያ ከዓለም ታላላቅ መንግሥታት ቁጥር ገብታ የነበረችበት ነበረ፡፡[1] በአንፃሩም የውድቀቷ መጀመርያ ምዕራፍ ሆነ፡፡

ከስለጠነ ዓለም ለመገናኘት በየብስ በግብፅ በኩል እንዳትገናኝ ግብፅ እንደቀድሞ ክርስቲያናዊት አፍሪካዊት ሀገር መሆኗ ቀርቶ እስከማዊት

[1] C. Conti - Rossini ibd p 200



ዓረባዊት ሀገር ስለሆነች፣ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነት ውሱን ነበር፡፡ የባሕር በርም ምንም እንኳን ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ብሎ ቢወድስም በሀገሩና በእስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ ሀገሮች በኩል ሁሉ ለኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት ውለታ ያሳዩት በጎ አመለካከት አልነበረም፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ለመሄድ የሚሞከሩ ምእመናን ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ የሞት ዕጣ ነበር የሚጠብቃቸው፡፡ በአንፃሩ የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የእስልምና ሃይማኖት ሰብከ ተስፋፍቶባቸው ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ከፋፈሉን፡፡ በመጨረሻም በተለይ በመሐመድ ግራኝ ጊዜ ለአርስ በርስ ጦርነት ገፋፍተው ኢትዮጵያን ለባሰ ለሥልጣኔ ኋላ ቀርነት ዳረጓት፡፡ የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷ የተከፈላት ውለታ በጠላትነት ነበረ፡፡ የአክሱም መንግሥት ውድቀት በደረሰበት ዘመን በ705 715 ዓ.ም. በሰሜናዊ ዐረብያ ከመሀት ባሕር 100 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ በአንድ በኡማያዲ ቤተ መንግሥት ሕንፃ የካሊፎች መዝናኛ ቦታ በትልቁ ዋና ክፍል ግርግዳ ላይ በካሊፋ የተሸነፉ 4 ከዓለም ታላላቅ ነገሥታት ተስለው ይገኛሉ. እነሱም[1]

1ኛ. የቢዛንታናዊ ቄሳር ንጉሠ ነገሥት
2ኛ የፋርስ ንጉሥ ኮስርዮ
3ኛ. የስፓኝ የመጨረሻ ቪዚጎት ንጉሥ ሮድሪጎ
4ኛ. የኢትዮጵያ ንጉሥ ናጃሺ ናቸው፡፡

## 7. በሰሜን ኢትዮጵያ የታሪክ ቅሪቶችና ቦታዎች

ስለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቦታዎች ስናስታውስ ትዝ የሚሉን አብዛኛው "ኦቤሊስክ" ተብለው የሚጠሩ በአክሱም ቆመውና ወድቀው የሚገኙ የአክሱም ሐውልቶች ናቸው፡፡ አንድ መቶ የሚጠጉ የአክሱም ሐውልቶች "ኦቤሊስኮች" ብቻ አይደሉም የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ቅሪቶች፡፡ ደቡብ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ይዘው የመጡ ፊደላቸው ብቻ አይደለም፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች በማለት አንድ ካርታ[2] አውጥተዋል በዚሁ ካርታ መሠረት በዚሁ ታሪካዊ ቦታዎች የሚገኙት ከአክሱም በስተሰሜን ከናቅፋም በስተሰሜን የሱዳን ግዛትም የሚያጠቃልሉ በባሕር ዳርቻዋም ከአዱሊስ እስከ ራሄይታ የሚደርሱ ናቸው፡፡ ከፍተኛ ስልጣኔ በዳበረባቸው ቦታዎች የከተማ የቤት ፍርስራሾች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መቃብሮች፣ አቤሰኮች፣ ዙፋኖች፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ ስእሎች እና የሸክላ ስእሎች ፈራርሰው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ቅሪቶች ከደቡብ ዓረብ ስልጣኔ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ሲገባ ምንም ተመሳሳይነት የላቸውም፡፡ የፈራረሱ ቤቶች የሚገኙ በጥንት ቦታዎችና በአሁኑ ጊዜ ትግሪኛ ተናጋሪ አካባቢ የሚሰሩ የቤቶች አሰራር አንድ ዓይነት ነው፡፡ አራት ማእዘን ያለው "ሕድሞ" የተባለው የቤት አሰራር ከደቡብ ዓረብ ሆነ ከግብፅ የቤት አሰራር ስለማይመሳሰል፣ በአክሱም ጊዜም የተለመደ ነው ተብሎ በመገመት አክሱማዊ የቤት አሰራር ተብሏል፡፡ ክቡ የቤት አሰራር ግን በመላው አፍሪካ ስለሚገኝ አፍሪካዊ የቤት አሰራር ተብሏል፡፡ ብዙ የመቃብር ዓይነቶች ተገኝቷል፡፡ ከቤተክርስቲያንና ቤተመቅደስ አጠገብ ወይንም ከምድር ቤት በልዩ ሞያ የተሰሩ ወይንም መሬት ቆፍረው ብቻ የተቀበሩ ረጃጅም ኦቤሊስኮች በአክሱም ብቻ ሲገኙ አነስተኛ ቁመት ያላቸው በብዙ ታሪካዊ ቦታዎች

[1] Carlo Conti -Rossini Storia d' Ethiopia p 124
[2] C. Conti -Rossini ibd Indice delle tavole XXVI

ይገኛሉ፡፡ ግን እንደሰራቸው ለማወቅ አይቻልም፡፡ በደቡብ ዓረብ የአቤሊስክ ስራ እምብዛም የተለመደ አልነበረም፡፡

ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊሰሯቸው አይችሉም፣ ከግብፅ የመጡ ባለሙያዎች እርዳታ የተሰሩ ናቸው ከማለት በስተቀር የአሰራራቸው ታሪክ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ዙፋኖች በብዛት የሚገኙት በአክሱም ነው፡፡ በአዱሊስ፣ በዲክዲክ /ናቅፋ/ ተገኝቷል፡፡ ሰአሎች፣ የሸክላ ስራ ምስሎች ወዘተ... ከማንም ሐገር በአሰራራቸው የሚቀራረቡ ሆነው አልተገኙም፡፡ ደቡብ ዓረቦች ለንግድ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚመላለሱበት ጊዜ ፊደል ብቻ አይደለም የተማሩት፣ ባለ ብዙ ፎቅ የቤት አሰራርም ከባቢሎኒያ ተምረው ወደ ሀገራቸው አምጥተው በሰፊው እንዲለመድ አድርገው ነበር፡፡

የመዳብ ማእድንን ማቅለጥና መዳቡ ላይ መጻፍ ደቡብ ዓረቦች ከክርስቶስ ልደት በፊት ተምረው ልዩ ችሎታ ነበራቸው፡፡ ከጋዛ ተምረው ባለብርና ባለወርቅ የአቴንና የሮማውያን ገንዘቦች በ4ኛ መቶ ክፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ይሰሩ ነበር፡፡ የቤተመቅደስ ፓንቴዮን የመስራት ችሎታ ነበራቸው፡፡ የዚሁ ሁሉ እውቀታቸው በኢትዮጵያ የታየ ነገር የለም፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ የጥንት የሰው ስራዎች ጥቂቶች እንኳን የደቡብ ዓረብ ናቸው የሚባሉ የሉም፡፡

ስለዚህ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሕዝቡ ጋራ ተዳቅለው አዲስ ሕዝብ ሴም ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ፈጠሩ ማለት የፈጠራ ታሪክ ነው፡፡ ሀገራችን ከጣሊያን በስተቀር በማንም ሕዝብ ተገዝታ አታውቅም አያልን፣ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት እንደወረዳ የቆዳ ስፋት ያላቸው ሳባውያን ገዙን፣ ፈጠሩን ብለን መናገር የማይመስል ከመሆኑም በላይ አሳፋሪም ነው፡፡ ደቡብ ዓረቦች በብዛት ሰፈሩባቸው ተብለው የተገመቱ ቦታዎች ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ ያሉት ጥቅጥቅ ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች በደቡባዊ አከለጉዛይ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው፣ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ሕዝቦችም ቢሆኑ የዓረብ ድብልቅ ዘር የለባቸውም፣ የተለዩ ሕዝቦች መስለው አይታዩም፡፡ ከፍተኛ ስልጣኔ ዳብሮባቸው የነበረ ንፁሕ ኢትዮጵያውያን ዘሮች መሆናቸው ብቻ የሚታዩ በቆሐይቶ አካባቢ /አከለጉዛይ/ ተቆፍሮ የተገኙ አስከሬኖች ጠጉራቸው ጥጥ መሳይ እንደ ጥቁሮች /ኔግሮዎች/ ሳይሆን፣ ወይንም ሉጫ እንደ ዓረቦች ባይሆን እንደ አሁኖቹ ኢትዮጵያውያን በመጠኑ ከርዳዳ የሆነ ፀጉር እንደ ነበራቸው ተረጋግጠዋል፡፡ [1] የጭንቅላታቸው አጥንትም የኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተረጋግጠዋል፣ ይኸም ደቡብ ዓረቦች በሰሜን ኢትዮጵያ እንዳልሰፈሩ የሚያስረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ቆሐይቶ እንደ ደቡብ ዓረብ ተመሣሣይ ውሃ ማጠራቀሚያ ግንዳዎች ቅሪቶች ያሉባት መንደር ናት፡፡ በአዱሊስ ይኖሩ የነበሩ ደቡብ ዓረቦች ከቀይ ባሕር ሐሩር ወጣ ብለው ብርዳማ አየር የሚያገኙበት የመዝናኛ ቦታ ነበረች የተባለች መንደር ናት፡፡ በዚሁ መንደር የዓረቦች ራሳ ምልክት ካልተገኘ የትም ቦታ ሊገኝ አይችልም፡፡ ቆሐይቶ እንደ መንደር የሚቆጠር አይደለም፡፡ ከአክሱም በፊት የአክሱማውያን ዋና ከተማ የነበረ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ይህ ባይሆንም ከቆሐይቶ እስከ አክሱም ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች ፍርስራሾች እንደ ትኩንዳዕ፣ ከስከሰ፣ ሰንዓፈ ወዘተ... የሚያጠቃልል ከፍተኛ ታሪካዊ የሐውልቶች ፍርስራሾች የሚገኙባቸው ራሳቸው የቻሉ እንደ ግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች የሚቆጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ለማለት የሚያስኘ ነው፣ ለምርምር በቂ ቁፋሮዎች

[1] Carlo Conti - Rossini Stori● d' Etiopia p. 237



አልተደረገም፡፡ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ቁፋሮዎች ያተኮሩት በአክሱም አካባቢ ብቻ ነው፡፡ ፐሪፕለስ የቀይ ባሕር ዙሪያ ጉዞ የሚል መጽሐፍ የደረሰው ሰው አክሱማውያንን የሚገዛ ዞስካለስ የተባለ በጣም ስስታም የሆነ ገንዘብ ማጠራቀም ብቻ የሚወድ በሌላ በኩል ግን ጉበዝና የግሪክ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ[1] ንጉሥ ነበረ ብሎ ጽፏል፡፡ ዞስካለስ ይኖር የነበረ በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 2ኛው አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን የሳባ ቋንቋና ፊደል ከማወቃቸው በፊት የግሪክ ቋንቋ ያወቁ እንደነበረ የሚጠቁም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ለማወቅ በቂ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ባይደረግም ከመሬት በላይ የሚታዩ ቅርሶችና አሻራዎች በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ከዘሰላ እስከ ሐይቅ (ወሎ) በብዛት ይገኛሉ፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ምንም እንኳን እነዚህ የታሪካችን ምልክቶች በውጭ ሀገር ሰዎች የተሰሩ ናቸው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ የአናሳ ሴማውያን ሥልጣኔ ነው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ ሐውልቶቹን ከመረመረ በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም ከሚገኙ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ካላቸው ሀገሮች መካከል በእኩል ደረጃ እንድትሰለፍ የሚያስችሏት መሆናቸው ጽፏል[2] ፡፡

በአክሱም ከሚገኙ ቁጥራቸው አንድ መቶ የሚደርሱ አቤሊስኮች አንዱ በቁመት በመላው ዓለም ከሚገኙ ተመሳሳይ ሐውልቶች አንደኛነት ያለው ነው፡፡ ላሊበላ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በዓይነታቸው በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው ተብለው ተደንቀዋል፡፡

## 8. የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን

ስለታወቀው የምዕራባውያን ሀገሮች የጨለማ ዘመን (Middle Age) ተብሎ የሚጠራ ታሪካቸው በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ አስተያየቴን ሰጥቻለሁ፣ የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የምዕራባውያን ተመሳሳይ የሆነ የታሪካችን የጨለማ ዘመን አለ ብለው ጽፈዋል፡፡ የሀገራችንና የምራአባውያን ሀገሮች ታሪክ የተለየ ቢሆንም እንደ አጋጣሚ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ በሁለቱ ሀገሮች የክርስትና ሃይማኖት ከገባበት ዘመን ጀምሮ ነው፡፡ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የጨለማ ዘመን ብሎ የሚጠራው ከናግራን፣ በአጼ ካሌብ ዘመን፣ በ525 በተደረገው ጦርነት እስከ ዩዲት መነሳት 942 ዓ.ም. 317 ዓመት ያለው ጊዜ ነው፡፡ የተባለበትን ምክንያት ሲያብራራ የአክሱም ነገሥታት የሰሩትን ሥራ በታሪክ የተመዘገበ ስላማይገኝ ነው፡፡ በኤውሮጳውያን የጨለማ ዘመን ትርጉሙ አንድ ሀገር ከነበረው ከፍተኛ ስልጣኔ ወደ ኋላ የተመለሰበት ዘመን ነው፡፡

ሀገራችን በእነ ንጉሥ ኢዛና እና አጼ ካሌብ ከነበረው ባለ መልካም ዝና ታሪኳና ስልጣኔዋ ወደ ኋላ መመለስ የጀመረችበት ጊዜ ከአጼ ካሌብ ጀምሮ መስሎ አይታየኝም፡፡ የሀገራችን ታሪክ ከምዕራባውያን ሀገሮች በማመሳሰል ብንፈልግ እንኳን የጨለማ ዘመን ተብሎ መጠራት የሚገባው ከአጼ ካሌብ ከናግራን ጦርነት ጀምሮ መሆን የለበትም፡፡ የታሪክ ማስረጃ በመጥፋቱም ታሪክ አልተሰራም ለማለት አይቻልም፡፡ ከንጉሥ ኢዛና በፊት ወደ ሰሜንና ደቡብ ዓረብ የተደረጉ የአክሱም ዘመቻዎች ማስረጃዎች የተገኙ

[1] Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 119
[2] C. Conti - Rossini ibd p. 239

በአጋጣሚ ከሀገራችን ወጪ ነበር። ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን አለ ቢባልም መጀመር ያለበት ከእስልምና ሃይማኖት መከሰትና መስፋፋት በኋላ በተለይም ግብፅ በዓረብ እስላሞች ስር ከወደቀችበት ዘመን ከ 642 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን ይገባዋል። ከዚሁ ዓም ጀምሮ ግብጽና ኢትዮጵያ የክርስትና የጋራ እምነታቸውና ግንኙነታቸው ባይቋረጥም አደጋ ላይ የወደቀበት ዘመን ኮፕቲክ የአንድ የክርስቶስ ባሕርይ የክርስትና እምነት ተከታዮች ነበሩ። ኢትዮጵያ ግንኙነቷ የተቋረጠው ከግብጽ ጋራ ብቻ አልነበረም። ከሰለጠኑ ምዕራባውያን የክርስትና እምነት ተከታይ ሀገሮች ሁሉ ጭምር ነበረ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነቷን እና ሕልውናዋን ለመጠበቅ ለብዙ ዘመናት የትጥቅ ትግል የጀመረችበት ዘመን ነበር።

ስለዚህ ይህ ዓመተ ምሀረት ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን የጀመረችበት ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ኮንቲ ሮሲኒ የሀገራችን ታሪክ የጨለማ ዘመን 500 ዓመት ያደርሰዋል፣ ከ7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን[1] እስከ ተመለሱባት ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ ሰለሞናዊ ነገሥታት በስልጣን እስከ ተመለሱባት ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ በዚሁ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ የምናገኛቸው ከተለያዩ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ነው። የጨለማ ዘመን ከመግባቱ በፊት በ525 አንደ ግሪካዊ ግብፃዊ ዜጋ የሆነው ኮዝማስ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ሰፊ ታሪካዊ ዘገባዎች ተንትነዋል። ወደ ሕንድ ሀገር በምሄድበት ጊዜ ባርባርያ /ሶማልያ/ በጎበኘበት ጊዜ ከሶማልያ ጥን የነበረውን የዘንግ መንግሥት ለመጎብኘት ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ባሕርተኞች ስላስፈራሩት ፍላጎቱም አልተሳካለትም። ከሕንድ ሀገር ሲመለስ አዱሊስ እና አክሱምን ጎብኝቶ በመሬት እስከ አባይ በመሄድ ግብፅ ሀገር ገብቷል። ኮዝማ እንደጻፈው አዶሊስ የንግድ መናኸሪያ፣ግሪኮችና ሮማውያን ነጋዴዎች የሚያዘውትሩባት ናት በማለት ጽፏል። በንግድም የምትገናኘው ከየመን ብቻ አይደለም፣ ከፔርሲያ፣ ከሕንድ እና ከሰይሎን ጋራም ትገኛለች። አክሱም ከብለሚዮች ጋራ በወዳጅነት የተመሰረተ ግንኙነት አላት ከዘርባሪያን ጋር በመሬትም በባሕርም ትገናኛለች። አዱሊስና አክሱም ሐውልቶችና ቤተክርስቲያኖች አሏቸው። ኮዝማስ አጼ ካሌብ የመንን ለመውረር ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ ተመልክቷል። ኮንቲ ሮሲኒ ከአጼ ካሌብ የየመን ዘመቻ በኋላም ቢሆን ኢትዮጵያ በ6ኛና 7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ስልጣኔዋን እና የክርስትና ሃይማኖትን ወደ ደቡብ አስፋፍታ እንደ ነበረ የሚያመለክት ሰሜን ሱማሊያ፣ የሶኮትራ ደሴትም ጭምር ክርስቲያን ሆነው እንደነበሩ ብሎ ጽፏል። /ለ/ 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ግንኙነቷ ከደቡብ ዓረብ ጋራ ሲሆን 7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ግን በእስልምና ሃይማኖት መመስረት ምክንያት ግንኙነቷ ከሰሜን ዓረብ ሆኗል። የሀገራችን ታሪክ በዚሁ ዘመን እና በሚቀጥሉት ዘመናት ለማወቅ የምንችለው ከዓረቦች ጸሐፊዎች ምንጮች በምናገኛቸው ማስረጃዎች ብቻ ነው። በዚሁ ጊዜ የዓረቦች አስተያየት ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነበት ሀገር፣ ስደተኞች ዓረቦችን የምትቀበል ተብላ ትታወቅ ነበር። ታማኝ የነቢዩ መሐመድ ባርያዎች ኢትዮጵያውን ነበሩ። ነቢዩ መሐመድ በዓለም ከነበሩት 6 ታላላቅ ነገሥታት የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ደብዳቤ ከላከላቸው ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበረ። ነቢዩ መሐመድ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋራ የወደጅነት ግንኙነት ነበረው። "ከልነኳችሁ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ነገር አትጫሩ፣ 9/10 የሰው ዘር ድፍረትና ጀግንነት ለጥቁሮች ነው የተሰጠው"

(1) Conti - Rossini ibd p. 323



በማለት ነብዩ መሐመድ ለቅርብ ረዳቶቹ የተናገረው ቃል ስለኢትዮጵያውያን የነበረው አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው።

/ሐ/. በ872 ዓ.ም. አል ላኩቢ (Ahmed Ibn Wadhih Al- La - Kubil[1] የተባለው የዓረብ ታሪክ ጽሐፊ ዓለምአቀፍ ታሪክ በሚለው መጻሐፍ ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፍ ከናይል ወንዝ እስከ ቀይ ባሕር ብዙ ነገሥታት እንዳሉ ይዘረዝራል 1ኛ. የናኪስ ዘር የተባሉ ኅሳዎች ከአሰዋን እስከ ባርካ የሚደርስ፣ ዋና ከተማው ሐጂያር 2ኛ ባክሊን ይባላል 3ኛ. በአዘን 4ኛ ጀረን 5ኛ. ከታአብ 6ኛ. የናጃሺ መንግሥት ሰፊና ኃይለኛ ነው፣ ዋና ከተማው ካባር ነው። በግዛቱ ውስጥ ብዙ ከተሞች አሉት፣ ዓረቦች ለንግድ ይሄዳሉ፣ የባሕር ዳርቻው ዳህላክ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዙ ነገሥታት በአንድ ንጉሥ ይታዘዛሉ፣ ግብርም ይከፍላሉ፤ ሃይማኖታቸውም ክርስትና ነው፣ የመጨረሻ በስተደቡብ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከሲንድ የሚዋሰን የዘንግ ንጉሥ ከደቡብ ሶማልያ በስተደቡብ ይገኛል። የዓረብ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸው ንግድ ብዙ ነው፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለችም ብለዋል።

/መ/. ማሱዲ (Masudi)[2] የተባለው የታወቀው የዓረብ ታሪክ ጸሐፊም እስከ ማዳጋስካር ድረስ ብዙ ጉብኝት አድርጐ ራሱ በቀጥታ ለላየው ነው የሚጽፈው። በመጨረሻ ጊዜ በ916/7 ጉብኝት ስላደረገበት ስለ ኢትዮጵያ በሚያደርገው ዘገባ፤ ኢትዮጵያ የበለጸገች ሀገር ናት ብሎ ጽፏል። ዋና ከተማዋ ጋባር ናት፤ ሌሎች ብዙ ከተሞችም አሉ፣ ግዛቷ እስከ ሐበሻ ባሕር ይዘልቃል። በዚሁ ባሕርም ዘይላ ዳሕላክና ባጼ /ምፅዋ/ የተባሉ ወደቦች አሏት። በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዓረቦች በሰላም ግብር እየከፈሉ መኖር ይችላሉ። ኢትዮጵያ በብልጽግና ዘመን እንደነበረች የሚያስረዳ በንጉሡና በየመን መሪ ኢብራሒም ቤን ዚያድ በ901-2 የተደረገው የወዳጅነት ውል መሠረት የንግድ መርከቦች ብዙ ሸቀጦች ይዘው በ3 ቀን ውስጥ በሁለቱ ሀገሮች ለንግድ ያመላልሱ ነበረ እያለ ጽፈዋል።

/ሰ/. ኦማር የመናዊ የተባለው ሌላ የዓረብ ታሪክ ጸሐፊ በአባቱ በኢብራሂም ተተክቶ በ981-2 ዓ.ም. የየመን መሪ የነበረው አቡ አል (Abu Al ) ጂያይስ ኢሳክ Jiais Jshak የተባለው ለ80 ዓመት በስልጣን የቆየው ከኢትዮጵያ ጋራ ግንኙነት እንደነበረው እና ስጦታ በማበርከትም ወዳጅነትን ይፈልግ እንደነበረ ጽፏል።

/ረ/. 977/8 ዓ.ም. የጆግራፊ ምሑር የነበረው አቡ አልከሲም Abu - Alkasim ኢብን ሀውካ የተባለው፡ የዓረብ ተወላጅ ስለዘይላ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ክፍለ ግዛትና በሁሉም ባሕር ዳርቻ ከየመን ፊት ለፊት የሚኖሩ በንግድ ከየመን ጋራ መልካም ግንኙነት ያላቸው ናቸው ካለ በኋላ የኢትዮጵያ መሬት ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለም ብሏል።

/ሠ/. በ951 -2 ሌላ ዓረባዊ የጆግራፊ ምሑር አል አስታክህሪ Al - Istakhri የተባለው ተመሳሳይ ሀሳብ ገልጧል። በተደጋጋሚ ዘይላ ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያን መሆኗ መጠቀሱ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ደቡብ መስፋፋቱን

(1) C. Conti - Rossini ibd p. 274
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 281

ያመለክታል። የዚሁ መስፋፋት ከሚታዩ ብዙ ታሪካዊ ማስረጃዎ እንደምሳሌ የሚከተሉት መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ማስፋፋት ማተኮሩዋ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች አንዱ በ1154 ዓ.ም. ኤድሪስ የተባለው የሲሲሊ ንጉሥ የጂዮግራፊ ምሑር ስለዓለም አቀፍ የጂዮግራፊ በደረሰው መጽሐፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ አንስቶ ሲጽፍ የኢትዮጵያ የባሕር ወደቦች ምጽዋ ምንም ሳይጠቅስ ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ መርካ ሌሎችም የደቡብና የሰሜን ሶማሊ ጠቅሶ ጽፏል። ወደ ሰሜንም ታጁራ ዳህላክ እና ሰዋኪም የኢትዮጵያ ወደቦች ናቸው ብሎ ጽፏል። ሌሎች እንደ ኢበን ሰኢድና አልዲማስኪ የተባሉ የዘመኑ የጂዮግራፊ ምሁራን ዓረቦችም ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምቃዲሾ፣ መርካ፣ የኢትዮጵያ ወደቦች መሆናቸውን ጽፈዋል።

/ቀ/. [1] የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በ921-933 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ አቡነ ጴጥሮስ በተላኩበት ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ግዛት ስፋት ሲጽፍ ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ በመሆኗ የተነሳ ንጉሡ ጉብኝት ለማድረግ ሲፈልግ በጉሩን ጉብኝት ለመጨረስ 1 ዓመት ይወስድበት ነበር ብሏል። በላሊበላ ዘመን ጊዜ 1210 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መልክተኞች ካይሮ መጥተው ስለነበረ ስለ ኢትዮጵያ ለማወቅ ፍላጐት ከነበራቸው ብዙ ሰዎች አንዱ አቡ ባሊሕ ሻዲድ ኢብን ባና የተባለው የአርመን ተወላጅ በደረሰው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከዳዊት ዘር አይወለድም፣ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ በነበረበት ጊዜ ከንጉሡ ሴት ልጅ ጋራ በተደረገው ጋብቻ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘር የሚሆነው ሊወለድ ችሏል ካለ በኋላ፣ ንጉሡ በጣም ኃይለኛ ነው ከሰሩ ያሉት ነገሥታት ግዛት ጉብኝት ለማድረግ አንድ ዓመት ይፈጅበታል ብሎ ጽፏል።

## 9. ታሪካዊ ቦታዎች በደቡብ ኢትዮጵያ

በሰሜን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም የጥንት ታሪካችን ምልክቶች ፍርስራሾች ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ፋንፋኔ ጠበል አጠገብ የአክሱም ስልጣኔ ማስፋፋት የሚያመለክት የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ ይገኝ ነበረ። እንደዚሁም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ጀባልቲ በተባለው ተራራ የአንዲት የአክሱማዊት የከተማ ፍርስራሽ ይገኛል።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የአክሱም ወደ ደቡብ ማስፋፋት በተያያዘ ሁኔታ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ማእከል እንድትሆን የተመረጠችው በአጼ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ዘመን መሆኑ ቀርቶ በአክሱም ዘመነ ምንግሥት መሆኑ ነው። አጼ ምኒልክም አዲስ አበባ ዋና ከተማ እንድትሆን የመረጠበት ምክንያት በኢትዮጵያ ሌሎች የፍል ውሀ ጠበል ቦታዎች ጠፍተው ሳይሆን ቀደምት አባቶቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፈለግ በመከተልና በማእከልነት ተመርጦ የነበረው ቦታ በመቀበል ነው። ከአክሱም አጉላ አሸንጌ የሚወስደው ጥንታዊ መንገድ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም ከአክሱም ወደ አሸንጌና ፈንፈን መስፋፋቱ ያሳያል። በዚሁ መሠረት ከአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አባል የሆነው አንድ ወታደር የሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም ገንዘብ አግኝቷል። በዚሁ አካባቢ በአክሱም ጊዜ ሕዝብ ሰፍረውበት የነበሩ ምልክቶች በስተምዕራብ የአሸንጌ ሐይቅ ተገኝቷል። በዝዋይ ሐይቅ ትራቪርሲ፣ ሚሊዮስና ዲካስትሮ የተባሉ ጣሊያኖች በአጼ ምኒሊክ ጊዜ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የአክሱም መሰል

[1] C. Conti - Rossini Storia d'Etiopia p 289



ሐውልቶች፣ አቤሊስኮችና መስቀሎች በብዙ ቦታዎች አግኝተናል ብሏል። ኪያሪኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ሀገር ጐብኚ ከአንኮበር በስተምስራቅ የግሪክ የድንጋይ አሰራር የሚመስል በአንድ ሕንጻ በተለይም በበሩ ደጃፍ አግኝተዋል። በአጉላ በምስራቅ ትግራይ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የቤት ፍርስራሾች ተገኝተዋል። ሀገራችንን የጐበኘ ቼኪ የተባለው ሌላም ኢጣሊያዊ በሸዋ ከአንኮበር በስተምስራቅ 6.35 ሜትር ርዝመት ያለውና ሌላው ደብረ ብርሀን አጠገብ አቤሊስክ አግኝቷል። ዳባዲ ታዋቂው የፈረንሳይ ሀገር ጐብኚ ከአባይ በስተደቡብ በሲበን ሁለት ሜትር ርዝመት ያለው አቤሊስክ አግኝቶ ነበር፣ ነገር ግን ደጃዝማች ጐሹ ወልዴ ለአሮሞዎች የጣኦት እምልኮት ነው ብሎ ሰባብሮታል።

ሀረሪ /አደሬ/ በሀረር ከተማ የተወሰነ ቋንቋ እንዲሁም የጉራጌ ቋንቋ በመሀል አገር በሰፊው የተሰራጨ ከትግሪኛና ከአማርኛ ቋንቋዎች ጋራ የሚዛመዱ የሴም ቋንቋ ተብለው ሊመደቡ የተለመደ ነው። በነዚህ ሁለቱ ለአካባቢዎች የአክሱም ስልጣኔ ምልክቶች ተገኝተዋል።[1] በትግራይና የሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የስልጣኔ ምልክቶች ከጥንት ግብፃውያን ወይንም ደቡብ ዓረብ ጠበብቶች የተሰሩ ናቸው እንደሚባለው ሁሉ፣ በሌላ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የሚገኙ የስልጣኔ ቅሪቶች በደፈናው ከአክሱም የመጡ ናቸው ይባላሉ። አልፎ አልፎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ አቤሊስቶች የቤተክርስቲያን ህንፃ ፍርስራሾች የአክሱም ሥልጣኔ መስፋፋት ጊዜ የተሰሩ ሲሆኑ ሌሎች እንደ መቃብሮች የመሳሰሉት ግን ከቀደምት ነዋሪ ሕዝብ የተሰሩ ለጥንት ግብፃውያን የሥልጣኔ ምልክት የሆኑት ፒራሚዶች እንዲዳብሩ መሠረት የጣሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጉራጌ ሙሄር ሶዶ አካባቢ ጢአ፣ ሰምቦ፣ ሰደን ወዞተ የተባሉ ቦታዎች ሁለት ከስማንያ ሜትር ያላነሰ ቁመት ያላቸው በግዙፍ የድንጋይ ከምችት ከፍታ ያላቸው በገዥ ቦታዎች የተሰሩ በተለይ ባሰደን 150 የሚሆኑ ባለአራት ማእዘን መቃብሮች ተገኝተዋል። በመቃብሮቹ የተካሄደው ምርምር አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘበት ምክንያት ሬሳዎቹን የሚሸፍነው ድንጋይ የአሲድ ጠባይ ስላለው አጥንቶች አመድ ሆነው ስለተገኙ ነው። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሮቹ ላይ ስእል ተገኝቷል። እንደዚሁም የግብፃውያን መሰል ጉራዴና ቢላ ተገኝተዋል። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሩ ላይ ሐውልት የሚመስል ወይንም በአክሱም የኢዛና ጽሑፍ ያሉባቸው ድንጋዮች የሚያስታውሱ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ስራዎች በአክሱማውያን የተሰሩ መሆናቸውን አያጠራጥርም። በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሐረር 50 ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ አባ አዘይስ የተባሉ ፈረንሳዊ ካቶሊክ ላዛሪስት ሚስዮናዊ "ደልመን" ብሎ የጠራቸው መቃብሮች አግኝተዋል። ደልመን በብዙ የዓለም ክፍሎች ተገኝተዋል፣ በግብፅ ግን አልተገኘም። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌ የተገኙ መቃብሮች በኮንቲ ሮሲኒ አስተያየት ደልመን ሳይሆኑ በሰሜን ኢትዮጳያ ከሚገኙ መቃብሮች ተመሳሳይ ናቸው። በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ዋናውና ትልቁ በአክሱም ከተማ ንፋስ መውጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው መቃብር ነው። የሐረር ጉራጌ ቋንቋዎች የተፈጠሩት ከጥንታዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ከግዕዝ በቀጥታ ወይንም ከግዕዝ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፣ ከትግሪኛ ጋራ ብዙ ይዛመዳሉ። መቃብሮቹ የተሰሩበት ዘመን ለማወቅ ጨርሶ አይቻልም። የሐረር እና የጉራጌ አካባቢ

[1] Conti -Rossini ibd p . 282-3

የአክሱም ስልጣኔ ሳይጠፋ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ነው እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ከምዕራብ ክፋ እስከ ምስራቅ ከሰሜን እስከ ደቡብ ኦሞ የአክሱም ስልጣኔ ምልክት የሌለበት አካባቢ አይገኝም፡፡ በዓረብ ሀገር የፖለቲካና የወታደራዊ ሽንፈት ካጋጠማት በኋላ በአፍሪካ ብቻ ተወስና፣ እንቅፋት ባያጋጥማት ስልጣኔዋና ቋንቋዋን በማስፋፋት ኢትዮጵያ ባለ አንድ ቋንቋ ሀገር ልትሆን ትችል ነበር፡፡ ይህ ባይቻልም አሁን የሚታዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ እንደ ሀረሪና ጉራጌ የግዕዝ ቋንቋ ድብልቅ መሆናቸው አይተርም ነበር፡፡

ስለዚህ አሁን ትግሪኛ አማርኛ አደሪኛ ጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ተብለው እንደሚመደቡ ሁሉ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ይባል ነበር፡፡ ነገር ግን የአክሱም መንግሥት ወደ ደቡብና ምዕራብ ያደረገው ማስፋፋት ከባድ እንቅፋት ስላጋጠመው ብዙ ሳይቆይ በ10ኛ ክፍለ መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ማቋረጥ የተገደደበት በዩዲት ጊዜ ነበረ፡፡ ኢትዮጵያ በዩዲት እርስ በእርስ ጦርነት ዘመን ጀምሮ ከምስራቅ ሰሜን ሱዳን እስከ ደቡባዊ ሶማሊያና ሱኩትራ ደሴት ድረስ የነበረ ግዛቷ የደቡብ ክፍላተ አገሮች ሎምር ከቁጥጥሯ ውጭ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ የአስተዳደር መዋቅርም በጦርነት ስለ ወደሙ ይህ የዩዲት ዘመን የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ የዛግዌ ዘመነ መንግሥትም የግዛት አንድነት ለማስከበር ትኩረት ስላልሰጠ በዚሁ ረገድ ከጨለማ ዘመን ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል፡፡ ሰሎሞናዊ ንጉሣዊ አገዛዝ ከተመሰረተ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ከግዛቷ ተነጥለው የነበሩ የምሥራቅ እና የደቡብ ክፍላተሀገር፣ ከሰሜንም፣ ለማስመለስ የጣረችበት ዘመን ስለነበረ የጨለማ ዘመን አብቅቷል ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ጥረቱ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት በምሥራቅ የአፋርና የሶማሌ ግዛቷ የእስልምና ሃይማኖት በመቀበላቸው እንደገና ለማዋሀድ ቀላል ሆኖ ስላልተገኘ ነው፡፡

በመሐመድ ግራኝ እና በኦሮሞዎች እርስ በእርስ ጦርነት ጊዜ የሥልጣኔዋ ቅርሶች በባሰ ሁኔታ ስለወደሙባት እስከፊ የሆነው እንደገና በጨለማ ዘመን ወድቃለች ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ይህ ዘመን የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል፡፡ የቀሩት ዘመናት ግን እላይ የጠቀስኳቸው የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያስረዱ የጨለማ ዘመን ተብለው ሊጠሩ አይገባም፡፡

## 8. የዮዲት ዘመን

ዮዲት የምትባለው ንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ መከሰቱ በሁሉም የማይካድ ቢሆንም ዝርዝር ታሪኳ እና ማንነቷ በሚመለከት ግን በትክክል አይታወቅም፡፡ ዩዲት የነገሡች በ921-933 ዓ.ም. የእስክንድርያ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ኮዝማ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው የተላኩ በየዋሁ አቡነ ጴጥሮስ ላይ ኢትዮጵያ የፈጸመችው ግፍ እግዚአብሔር የላከባት የቅጣት መቅሰፍት ነው ተብሏል፡፡ እንደ ሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች አቀራረብ ዮዲት አይሁዳዊት ናት የኦሪት ሕግ በመደገፍ የክርስትና ሐይማኖት እንቀበልም ያሉት በሰሜንና፣ በወገራ፣ ወልቃይት፣ በላስታ የነበሩት ፈላሾች አሰባስባ ወደ ትግራይ ዘመታ በደብረ ዳሞ ተራራ ይኖሩ የነበሩትን ከነገሥታት የሚወለዱትን መሣፍንት አሳርዳ የነገሡች ናት ብሏታል፡፡ የእስክንዲሪያ ፓትያራኮች ታሪክ ላይ ዮዲት የባኒ አል ግግያሀ ንግሥት ብሉ ይጠሯታል፡፡ በኢትዮጵያ ግን በዚሁ ስም



የሚጠራ ክፍለ ሀገር የለም[1] ከአጼ ካሌብ ጀምሮ እስከ ዮዲት ዘመን 300 ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ ብዙ የታሪክ ማስረጃዎች የማይገኙበት ዘመን ስለነበረ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ዘመን ምናልባት ኢትዮጵያ ስልጣኔዋን ያስፋፋችበት ጊዜ ስለነበረ ወርቃማ የብልጽግና ዘመን ነበር፡፡[2]

በ979 - 1003 ዓ.ም. በእስክዲሪያ መንበረ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ፊለተዎስ Fileteus[3] በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ ከአቡነ ጴጥሮስ ጀምሮ ሕጋዊ አቡን ስላልነበራት ሰይፈ አረድ የተባለ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጊዮርጊስ ለተባለው የኑቢያ ንጉሥ የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ይልኩ ዘንድ እንዲያማልደው ደብዳቤ ጽፎ ነበር፡፡ የኑቢያ ንጉሥ የግብፁ ፓትሪያርክ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲልኩ ባቀረበው ልመና መሠረት አቡነ ዳንኤል ሲላኩ ኢትዮጵያውያን በታላቅ ደስታ ተቀብሏቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለኑቢያ ንጉሥ በግእዝ ቋንቋ የፃፈው ደብዳቤና የወቅቱ የኢትዮጵያውያን የታሪክ ፀሃፊዎች ያቀረቡት ዘገባ የሚጠቁመን ነገር ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን በታሪኳ በወሳኝ ምዕራፍ ትገኝ እንደነበረ ነው፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ መዛግብቶች በዓመተ ምሀረትና በአንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች ቢለያዩም በመሠረቱ ታሪኩ በማይለያዩበት ሁኔታ ገልፀውታል፡፡ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ሊጠፋ ትንሽ ነበር የቀረው፡፡ ክርስቲያን ሕዝብም ባሪያ ሆኖ ከመሸጥ ያመለጠ ሸሽቶ ወደ ሌላ ክፍላተ ሀገር ይሰደድ ነበር፡፡ ንጉሡም ወደ ሸዋ በመሸሽ የሞት ሽረት ፍልሚያ በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘመናችን የጎሳ ጦርነት የተደረገበት ጊዜ የለም፡፡ የሃይማኖት ጦርነቶች ግን ተደርጓል፡፡ በዮዲት የተቀለቀሰው ጦርነትም የኦሪት ሕግ ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን መሀከል የተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ያቀረቡት ዘገባ ይኸንን ሁኔታ መኖሩን የሚያስተጋባ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ዘመናትም በእስላሞች ኢትዮጵያውያን እና በክርስቲያኖች መሀከል ጦርነቶች ተካሄዷል፡፡

ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ታሪክ ጨርሶ ሳይክዱ የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በኒ አል ሐሙያሀ ብሎ የጠሯት ንግሥት የአጻጻፍ ስሀተት ነው ብለዋል፣ አል ደሙታሀ ተብሎ መነበብ እንዳለበት በማመን ዮዲትን ከአባይ በስተደቡብ ይገኝ የነበረው ትልቁ ዳሞት የዛሬው ምዕራብ ሸዋና ወለጋ ንግሥት አድርጓታል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ዳሞት የሚባል መንግሥት ተዘግቧል፡፡ በመጨረሻ ዮዲት በመሞቷ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ድል አድራጊነት ቢደመደምም ጦርነቱ ኢትዮጵያ ደካማ መንግሥት አድራጓት ነበረ ያብቃው፡፡ ኢትዮጵያ የደቡብ ክፍለ ሀገሮች ለመቆጣጠር ሳትችል ከመቅረቷ ሌላ እስከ 10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. ክርስቲያን የነበሩ እንደ ዘይላ፣ በርበራ፣ የባሕር ጠረፍ ወደቦቿ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍተውባቸው ስለነበረ በኢትዮጵያውያን መሐከል

---

(1) C. Conti - Rossini ibd p. 286
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 285
(3) C. Conti - Rossini ibd p. 286

በክርስቲያኖችና በእስላሞች የሃይማኖት ጦርነቶች እንዲካሄዱ መንገድ ከፍቷል።

ቀደም ብሎ የእስልምና ሃይማኖት የገባ በዳህላክ ሲሆን፣ በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በሱዋኪን እስልምና ገብቶ ነበር። እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ የባርካ፣ ቤጃ ጎሳዎች እና የሳሆ ጎሳዎች፣ ታጁራ ወደብ አካባቢ እስላም ሆነው ነበረ። በአጠቃላይ በባሕር ጠረፍ ወደቦች ብቻ ሳይሆን ወደ መሀል ሀገር በ13 መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሐረር፣ ዝዋይ፣ ሀዲያ ድረስ እስልምና ተስፋፍቶ ነበር።

ዮዲት ወደ ትግራይ ዘመቻ አድርጋ በመጣችበት ጊዜ በደብረ ዳሞ ታጥር ይኖሩ የነበሩ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ከፊቶቹ በኋላ ከእልቂት ያመለጡ ጥቂቶች ወደ ሸዋ መንዝ ሸሽተው ሄደው ነበር።

ዮዲት መሞቷ ሲሰማ አምበሳ ውድም በተባለው የተድሞው ንጉሥ ልጅ ወደ ትግራይ በመምጣት ለ20 ዓመት እንደገና በአባቶቹ ዙፋን ተቀምጦ ሲገዛ ቆይቶ ሞተ። ልጁ ግን መንግሥት ለመያዝ ከላስታ የተነሳ ዓመፅ ሊቋቋም ስላልቻለ እንደ አባቱ እንደገና ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሽቶ ሄደ። መራ ተክለሃይማኖትም የዛጉዌን ላስታ መንግሥት መሠረተ።



# ምዕራፍ 3

# ኢትዮጵያ ድኅረ ዛጉዌ በሰለሞናውያን ነገሥታት ዘመን

በ1268 ዓ.ም. የመንግሥት መሪነት ስልጣን ከዛጉዌ ነገሥታት ወደ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ነገሥታት በይኩኖ አምላክ መሪነት በሰላማዊ መንገድ በወሎ ሐይቅ በሚገኘው ገዳምና በደብረ ሊባኖስ ሸዋ ከሚገኘው ገዳም አባቶች አማካኝነት ሊዘዋወር ችሏል። የአስተዳደር ማእከልም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሸዋ ተዛወረ። ሸዋ በጆኦግራፊ አቀማመጧም የኢትዮጵያ ማእከል በመሆኗ፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በምሥራቃዊ የሀገሪቷ ክፍል በተቋቋሙት እስላማውያን ትናንሽ መንግሥታት የሀገሪቷን አንድነት የሚያናጉ የሚሰነዝሩባት ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ብሎም ለመግታት እንዲቻል፣ የኢትዮጵያ መስተዳደር በሸዋ ማእከላዊነት መሆኑ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። በሰለሞናዊ ነገሥታት መሪነት በሸዋ ማእከላዊነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው ደካማ ጐን እንደ ቀድሞ ጊዜ እንደ አክሱምና ላሊበላ ቋሚ ዋና ከተማ መፍጠር ያለመቻሉ ነው። ይህ በመሆኑ የማሕበራዊ ኑሮ ማንባታዎች በማከናወን ለመጪው ትውልድ ታሪክ ማስተላለፍ አልቻለም። ጠንካራ ጐኑ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በየወቅቱ የተከናወኑትን የመንግሥት ሥራዎች በጽሑፍ ለወጪው ትውልድ ማስተላለፍ ነው። ሌላ ጠንካራ ጐኑ ወሳኝ ፈተናዎች በማሳለፍ የሀገር አንድነትን ለመጠበቅ አስደናቂ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት የታየበትና በታሪክ የተመሰከረበት ዘመን ነበረ። ለ300 ዓመት ገድማ የዘለቀው በሸዋ ማእከላዊነት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በሃይማኖት የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ተቋቁሞ ኢትዮጵያ በአክሱም መንግሥት ዘመን የነበራት የመሬት ስፋት ከሞላ ጐደል ተረካቢ ሆና ለመጠበቅ ሞክረዋል፣ አንስተኛ የግእዝና የአማረኛ ስነ ጽሑፎችም ዳብረዋል፤ ከምዕራባውያን ጋራ የውጭ መንግሥታትም ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረዋል፤ ዘመኑ ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ መኖሩዋን በትክክል ያወቁበት ነበር። የሰለሞናዊ ነገሥታት ስልጣን ሲጨብጡ የኢትዮጵያ አመራር ብሩህ ተስፋ አልጠበቃቸውም። በባሕር ጠረፍ የሚገኙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የእስልምና ሃይማኖት የሆኑ ለማዕከላዊ የክርስቲያን መንግሥታት የማይታዘዙ መንግሥታት ተቋቁመው ነበረ። ይኸም ሁኔታ ለእርስ በእርስ ጦርነት የሚጋብዝ ነበር። ከይኩኖ አምላክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ግራኙ መሐመድ ሞት ድረስ ለ300 ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ በእስላሞችና ክርስቲያኖች የማያቋርጥ ጦርነት የተካሄደበት ጊዜ ነበር። ይህ በሀገራችን የተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት በመካከለኛ ምስራቅና በኤውሮጳ የተካሄደው ጦርነት አካልና ነፀብራቅ ነበር። ዓረቦች በእስልምና ሃይማኖት በመመራት በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ባልታሰበ ሁኔታ ወታደራዊ ወረራ በመፈጸም መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን በቁጥጥራቸው ለማድረግ ችሏል። ነብዩ መሐመድ ከሞተ በኋላ በስድስተኛው ዓመት በ689 ዓ.ም. ግብፅ በዓረቦች እጅ ወደቀች። ዓረቦች ወደ ሰሜን አፍሪካ ወረራቸውን በመቀጠል በ689 በካርታጅ ከባድ

ጦርነት አካሂደው ከማረኳት በኋላ በእሳት አቃጠሏት፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ስሟ ከታሪክ ተሰርዟል፡፡ በ711ዓ.ም. በበርበር የተገነባ 12,000 የዓረቦች ጦር የጂብራልታር ካናል ተሻግሮ ወደ ስፓኝ ገባ፡፡ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ የቪዚጎት መንግሥትን አሸንፎ መላው ስፔኝን ለመቆጣጠር በቅቶ ነበር፡፡ ቀጥሎም ዓረቦች ወደ መሐል ፈረንሳይ ዘልቀው በመግባት መላው ኤውሮጳ እስላማዊት ዓረባዊት ለማድረግ ተቃርበው ነበር፡፡ ነገር ግን በቻርል መደሻ የሚመራው የፈረንሳይ ጦር ፑዋቴ በተባለው ቦታ በ732 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት በዓረቦች ላይ ድል ስለተቀዳጀ የዓረቦች ወረራ ለዘለቄታው ሊገታ ችሏል፡፡ ከዚሁ ጦርነት በኋላ የክርስትና ሃይማት ሕልውና እና የኤውሮጳ ሀገሮች ነፃነት ተከብሮ ሊቆይ ችሏል፡፡ ከ300 ዓመት በኋላ ሌላ እስላማዊ የቱርክ መንግሥት ተነስቶ በዓረቦች ተተክቶ በዓረቦች ያልተያዘውን የቢዛንታይን መንግሥት በቁጥጥሩ ከማዋሉ በላይ በምስራቅ በኩል በኤውሮፓ ላይ ወረራ በማድረግ ሀንጋሪና አስትሪያ ድረስ ደርሶ ነበረ፡፡ የኤውሮጳ ሀገሮችም ተባብረው ያደረጓቸው የመስቀል ጦርነቶች ውጤት አልሰጡም ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜም ኤውሮፓ በቱርክ እስላማዊ መንግሥት ስር ለመውደቅ ተቃርባ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ቱርኮች በቪዬና አጠገብ ሽንፈት ስለደረሰባቸው ኤውሮጳ ከቱርኮች ወረራ ልትድን ችላለች፡፡

የዓረቦችም ሆነ የቱርኮች ግዛታቸውና ሃይማኖታቸውን የማስፋፋት ዓላማ ዋና ትኩረታቸው ወደ ኤውሮፓ ቢሆንም ወደ ሀገራችንም ወኪሎቻቸው መላካቸው አልቀረም፡፡ በየጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትም በክፉ ዓይን የሚያዩዋቸው በሀገራቸው መሬትና የራሳቸው ሕዝብ በእስላማዊ ሐይማኖት የሚያምኑ መንግሥታት ዙርያቸው መቋቋማቸው በማየት በመንግሥታቸው ሕልውና አደጋ ማንጃበቡ መገንዘባቸው አልቀረም ነበር፡፡

ይኩኖ አምላክ ስልጣን በያዘበት ጊዜ የሁኔታው አሳሳቢነት በመመለከት ከቢዛንታይን መንግሥት ጋር ግንኙነት ለማድረግ በመፈለግ ደብዳቤና ስጦታ ልኮ ነበር፡፡ ነገር ግን ራሱ የቢዛንታይን መንግሥት የራሱ ሕልውና እንኳን ለማስከበር በማይችልበት ወቅት ስለነበረ ሙከራው ውጤት ሊያገኝ አልቻለም፡፡

ይህ በመሆኑ በይኩኖ አምላክ የተተካ ንጉሥ ከግብፅ ጋራ መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ከከበቡት ኢትዮጵያውያን የእሳላም መንግሥታት ግንኙነት አሻሽሎ በሰላም ለመኖር አስቦ፣ ወሰኑ ለእስላም ነጋዴዎች ክፍት አድርጎ ነበር፡፡ ይህ በሰላም የመኖር ሙከራ ግን ጥሩ ውጤት ሊሰጥ አልቻለም፡፡

## 9. <u>አጼ ዓምደጽዮን</u>[1]

በኢትዮጵያውያን እስላሞችና ክርስቲያኖች እርስ በእርስ አስከፊ ጦርነቶች የተጀመሩበት በይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ በሆነው በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡ ዓምደ ጽዮን የነገሠው ከ1312 - 1342 ዓ.ም. ለሰላሳ ዓመታት ነበረ፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩበት ዘመናት ነበሩ፡፡

ኤውሮጳውያን እንዳደረጉት ሁሉ በክርስትና እምነታቸው ፀንተው ለመኖር ያደረጉት ትግል ነበረ፡፡ ከዩዲት ጦርነት በኋላ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ተቋቁመው የነበሩት መንግሥታት ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

---

(1) Luca Dei Sabelli ibd VI p 267



1ኛ. በአጠቃላይ ስማቸው ሲዳማ ተብለው የሚጠሩ፣ ወይም የደቡብ ኩሽ የሚባሉ፣ በጥንት ጊዜ ከሰሜን የፈለሱ ናቸው የሚባሉ፡፡ የአክሱም መንግሥት አሁን የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ደቡባዊ ወሰን ከዝዋይ ሐይቅ እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ከከፋ እስከ ዘይላ፡፡ የባሕር ወደብም እስከ ደቡብ ሶማሊያና አባኒያ ተቆጣጥሮ እንደነበረ ታሪክ ያረጋግጣል፡፡ ከሲዳማ መንግሥታት መሐል 1ኛ ጃንጀሮ 2ኛ በሻ 3ኛ እናሪያ (ሊሙ) 4ኛ እንፌሎ ምዕራብ(ወሊጋ) 5ኛ ጋፋት የተባሉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከነገሥታትም ሆነ ከባለባቶች ከሰሜን እንወለዳለን የማይሉ የሉም፣ ይህም የሚያረጋግጠው የአክሱም መንግሥት ተቆጣጥሯቸው እንደነበረ ነው፡፡

2ኛ. የእስልምና እምነት የሚከተሉ የሱልጣን መንግሥታት ተብለው የሚጠሩ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1ኛ. ሐዲያ፣ ጉራጌን የሚያጠቃልል 2ኛ. ፋጢጋር 3ኛ. ይፋት 4ኛ. ዳዋሮ 5ኛ. ባሊ 6ኛ. ሐረር ከተማ 7ኛ. ማና 8ኛ. አዳል፡፡ ጦርነቱ የተካሄደው በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትና በተጠቀሱት 8 እስላማዊ መንግሥታት መሐል ነበር፡፡ የሲዳማ መንግሥታት የያዙት ገለልተኛ አቋም ነበረ፡፡

ከእስላም መንግሥታት ከሁሉም ኃይለኛና የበላይነት የነበረው የይፋት መንግሥት ነበረ፡፡ ይህ መንግሥት በክርስቲያኖች ዘንድ የአረመኔዎች መስፍን ተብሎ ይጣራ ነበር፡፡ ይፋት ወላዝማ ተብለው በሚጠሩ የነገሥታት ዘር ሀረግ ይመራ ነበር፡፡ ይህ ስርወ መንግሥት የተመሠረተው በዑመር ወላዝማ ነው፡፡ እሱም ከነቢዩ መሐመድ ጎሳ ከሆነው ከኮሬይሰቶች ከሚወለደው ከያህያ የሚወለድ ነበር፡፡ እሱም በበኩሉ አል ሐሰን ከተባለው ከነብዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የሚወለድ ነው፡፡ በአጼ ዓምደ ጽዮን ጊዜ የይፋት ንጉሥ ሐክ አዲን የተባለው ነበረ፡፡ ጦርነቱ የተቀሰቀሰው የግብፅ መንግሥት በአስከንድሪያ ፓትሪያርክ ሰለሚፈጽመው በደል ለመበቀል አጼ አምደ ጽዮን የአባይ ወንዝ አቅጣጫውን እቀይረዋለሁ ብሎ በመዛቱ፣ እንዲሁም በእስላም ነጋዴዎች የበቀል እርምጃ በመወሰዱ ነው፡፡ አክ አዲን አጠፋውን በመመለስ ቤተክርስቲያኖችን በማቃጠል ቄሶችን ሐይማኖታቸው እንዲክዱ በማድረግ በክርስቲያን መንግሥት ውስጥ ግዛት ዘልቆ በመግባት የዓምደ ጽዮን ሚስት ባሪያ እንደሚያደርጋትና የቤቱ እሀል እንድትፈጭ እንደሚያደርጋት ዛቻ ያሰማ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ወደ ካይሮ ተልኮ የነበረ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በመማረክ ሃይማኖቱን አልክድም በማለቱ በአሰቃቂ ሁኔታ ስለገደለው በሕዝቡና በመንግሥቱ ቁጣ ስላስከተለ ነበረ፡፡ አጼ ዓምደ ጽዮን ጠሩን በመምራት ባደረገው ዘመቻ ይከተለው የነበረው መመሪያ፣ ጠሩ በብዙ አቅጣጫ በማስማራት ድንገተኛ አደጋ በመጣል ለጠላት ፋታ አለመስጠት በጠላት ላይ ሽብርና ፍርሀት መፍጠር ነበር፡፡

ሐክ አዲን በሌሊት አደጋ በመጣል ቢሞክርም አጼ ዓመደ ጽዮን ሙከራውን በማከሸፍ የሐክ አዲን ወንድም ወደ ነበረበት ጦር ግንባር ጥቃት በመሰንዘር በጉራዲ ራሱ ከገደለው በኋላ ጥቃቱን በመቀጠል በፈረሰኞች እየተረዳ የጠላቶች መደናገጥ በመጠቀም ጠላቶችን በማሳደድ ሐክ አዲንን ማርኮ ግዛቶቹ ይፋትና ፋጢጋርን በኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ አስተዳደሩ ለሐክ አዲን ወንድም ለሳብር አዲን በመስጠት በ1328 ዓ.ም. የመጀመሪያ የአጼ ዓመደ ጽዮን ዘመቻ በድል አድራጊነት ፍጻሜ ሆነ፡፡

የእስላሞች የተባበሩት ነገሥታት ሱልጣኖች ግን ሽንፈታቸው አላመኑም ነበር፡፡ በወገራ፣ በሰሜን፣ በደንቢያ፣ በቤጌምድር፣ በጣና ሐይቅ አካባቢዎችና በተከዚ ወንዝ አካባቢ የኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በክርስትና እምነት አያምኑም ነበረ፡፡ ከአረት ሕግ ገና አልተላቀቁም ነበር፡፡ ሳብር አዲን

እንዲተባበሩትና የክርስቲያን መንግሥትን እሱ በምስራቅ ሲዋጋ በሰሜን እንዲወጉት ወኪሎቹን በመላክ ያስብካቸው ጀምሮ ነበረ። የሐዲያና የዳዋሮ ሱልጣኖቹም ከሳብር አዲን ጎን ቆመው ነበረ። አጼ ዓመደ ጽዮን ግን የጣላቶቹ እቅድ በሚገባ ስላወቀ ለየብቻቸው ጥቃት ለመፈጸም ባወጣው እቅድ መሠረት ወታደሮቹ ወደ ሀዲያ ልክ የሐዲያ ሱልጣን ድንገተኛ ወረራ ስለተፈጸመበት ተማረከ። ሌሎች የአጼ ዐምደ ጽዮን ወታደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ከሐዲያ በሚያዋስነው ወረራ በመፈጸም ድል ተቀዳጁ። ሳብር አዲን ወደሚገኝበት ስፈር ደርሰው ነበር። ነገር ግን ሱልጣኑ ሸሽቶ ሊያመልጥ ችሏል። አጼ ዐምደ ጽዮን በዳዋሮ ጣቢያ በማድረግ ወደ ፋጢጋር አመራ። ሳቢር አዲን ጦርነት ለመግጠም ተገዶ ተሸነፈ። ሚስቶቹና ልጆቹ ተማረኩ! ከተማው ወደመ። በአጼ ዐምደ ጽዮን ሚስት በኩል ምህረት በመጠየቅ አማላጅ ላከ። ዐምደ ጽዮን ግን ራሱ እሬቱ መቅረብ አለበት ብሎ የሚስቱ አማላጅነት ሳይቀበለው ቀረ። ሳብር አዲን ድንጋይ በትከሻው ጭኖ ይቅርታ በጠየቀበት ጊዜ የዐምደ ጽዮን ወታደሮች እንዲገደል ቢጠይቁም! ንጉሡ ግን እንዲታሠር ብሎ ፍርድ ሰለሰጠ ታስሮ በእስር ላይ እንዳለ ሞተ።

በሐዲያ! ፋጢጋር! ይፋት! ዳዋሮ ሱልጣኖች ላይ የተደረገው ጦርነት እንዲያበቃ አሁንም የመንግሥቱን ስልጣን ለሳብር አዲም ወንድም ለጀማል አዲን ሰጥቶ ወደ ሸዋ በሚመለስበት ጊዜ የአዳልና የማራ ሱልጣኖች ወደ ኋላ የሚመለሰው የአጼ ዐምደ ጽዮን ሠራዊት በደፈጣ ውጊያ በመጠቀም ማጥቃት ጀመሩ! ብዙ ወታደሮችም ፈጁ። በዚሁ ጊዜ አጼ ዐምደ ጽዮን በጠላት ውጊያ ስልት በመጠቀም እነሱም ወደሚሰበሰቡበት በፈረሰኞች ደፈጣ በማድረግ ጠበቋቸው። እቅዱ ሙሉ በሙሉ ስለተሳካ ደፈጣው ሞክረው ተመልሰው በተሰበሰቡበት ቦታ አግኝቷቸው ፈጃቸው። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ይፋትንና አካባቢዋን መልሶ ለመያዝ ግንኛውም ምኞት ውድቅ ስለሆነ ወታደሮች የተማረከውን ንብረት ይዘው ወደ ተጉለት ለመመለስ ተጉዘው ነበር። የንጉሡ አስተሳሰብ ግን ሌላ ነበረ። ጠላቶቹ ወታደሮቻቸውን ይዞ ወደ ተራራማ ደጋ ቦታዎች ተዋጉ እንጂ ቆላ ሀገራቸው ግን በጦርነት ስላልተነካ እንደገና ጦርነት ሊያስነሱ ይችላሉ የሚል ነበር። ስለዚህ ተከታትሎ በማጥቃት በተገኘው ድል በመጠቀም ጠላት ተመልሶ እንዳያንሰራራ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚል ነበር። በዚህ መሠረት ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ከይፋት ወደ ዳዋሮ ጉዞውን ጀመረ። ወታደሮቹ ወደ ቆላ እንሄድም ብለው ተቃወሙት። ነገር ግን ንጉሡ የቁርባን ሕብስት በግውጣት ጠላቶችን ሳልደመሰስ አልመለስም ብሎ በመማል ሰኔ ወር 1330 ዓ.ም. ወደ ቆላ ሀገር አመራ። የአጼ ዐምደ ጽዮን ጦር የሚያቋርጠው የቆላ ሀገር በባሕር በኩል ከምጽዋ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ሲሆን ወደ መሀል ሀገርም እስከ ዝዋይ ሀይቅ ጨርጨር ሐረር ወዘተ… የሚዘልቅ ነበረ። ወደ ቆላ ሀገር የሚያመራው የኢትዮጵያ ጦር የአዳልና የማራ ሱልጣኖች በቆላ ከሚገኙ ጎሳዎች ከተመለመለ ጦራቸው በደፈጣ ያለማቋረጥ ያስወጉት ነበረ። ዓላማው ፊት ለፊት ውጊያ በማስወገድ ወራሪውን ጦር በማድከም በሽታ በድካም! በውሀ እጥረት! ጦሩ እንዲያልቅ ነበረ። የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ወታደሮች በከባድ ችግር መሆናቸውን ስላወቁ እስላሞች ጥቃታቸውን መሰንዘር ጀመሩ። በዚሁ ጊዜ ንጉሡ የመንፈስ ጥንካሬ ስለነበረው ወታደሮቹን በማነቃቃት አጥቂዎቹን ለመቋቋም አስችሏቸዋል። በሁለቱ ወገን ወሳኝ ፍልሚያ ነበረ። በቀሶች ስብከት የተተኮሱ ብዛት ያላቸው ዝበሬዎች እንደ መስቀል ጦርነት ጊዜ የንጉሡን ጦር ያጠናከሩ ነበር። በበኩላቸው እስላሞች ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ በማወጅ ያላቸው ኃይል



[በሙሉ] አሰልፈው ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት በማያውቀው በቆላ ሀገር በ[illegible] ተወጥሮ መሆኑን ስላወቀ በአጼ ዓምደ ጽዮን ቀደም ብሎ በያዘው የእ[illegible] ሀገሮች ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሾሞ የነበረው ጀማል አልዲን ከድቶ የኢትዮጵያ ጦር በስተጀርባ ወደኋላ ሸሽቶ እንዳያመልጥ ውጊያ ለማድረግ ሞክሮ ነበረ። የእስላም ጦር በሙሉ አስተባባሪም በመካ ባላባት ቤተሰብ ተወላጅ! በሆነው ሼክ ሰሊህ በተባለው ሐረር ከተማ ዋና ሠፈሩን ማዕከል በማድረግ ነበረ! ተጨማሪ ጎሳዎችም በጦርነቱ ገብተው ነበር። በዚሁ ዓይነት በተሰበሰበው የእስላም ጦር ቁጥሩ አርባ ሺህ /40,000/ ያደርስ ነበረ የባላል። በዚሁ ወሳኝ ፍልሚያ ጊዜ ንጉሡ ታመመ። ሠራዊቱ ሥጋት ላይ ወድቆ ነበረ። ክርስቲያኖች ከአደጋ ያዳናቸው እስላሞች በፈጸሟቸው ስህተቶች ነበረ። 1ኛ.ሼክ ሳለህና የአዳልና የማራ ሱልጣኖች የፈጸሟቸው ስህተት ጥሩ ውጤት ያስገኛቸው የነበሩ የደፈጣ ውጊያ ትተው በግንባር መግጠም ነበረ። 2ኛ. ስህተት የጀማል አልዲን ጦር እስኪቀላቀል ድረስ አለማጠበቃቸው ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ታሞ ስድስት ቀኖች ከአልጋ ሳይነሳ ምግብ ባይቀምስ ቆይቶ ነበረ። ግንባር ቀደም የነበረ ጦሩ ከጠላት ጦር ተጋጭቷል! ጠላት ለውጊያ ተዘጋጅቶ እየገሰገሰ መሆኑን በሰማ ጊዜ ከአልጋ ተነስቶ መቆም አቅቶት ነበር። ከጉኑ የነበሩ ሁለት ሚስቶቹ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ መከሩት! ዳሩ ግን ንጉሡ "እንደ ሴት ሆኘ ልሙት"! ብሎ መለሰላቸው። በዚሁ ጊዜ አንደኛዋ ንግሥት የዮርዳኖስ ውሀና የጎልጎታ መሬት ሰጠችው። አንድ ቄስ ረጨበት ድካሙም በቅጽበት ተወው! እሱም ራሱ ለወታደሮቹ ረጨባቸው። ከዚህ በኋላ ለጦርነቱ ትእዛዝ ሰጠ። የክርስቲያን የግንባር ጦር ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ተገዶ ነበር። ንጉሡ በጦሩ መሀል ገብቶ በእጁ የቀኝ ክንፍ የነበሩ መሪዎች ገደላቸው። ፈረሰኞችም የመሀል ጦር ግንባር አወደሙ! ቀሪውን በስተግራ የነበረውን ከየመን የመጡ ሀገሩን የማያውቁ ወታደሮች ነበሩ። ትንሽ ጊዜ ከቆዩ በኋላ እነሱም ማፈግፈግ ጀመሩ። ከዚህ በኋላ የክርስቲያን ጦር ፋታ ሳይሰጥ በመሸሽ ላይ የነበሩ እስላሞች ላይ እንዳያመልጡ መንገድ እየዘጋ ይጨፈጭፋቸው ጀመር። ከሬሳዎች መሀከል የሼክ ሳሌህ ነበረ። የግራ ሱልጣን የሚሸሹ ወታደሮችን ሰብስቦ ለመከላከል ሞክሮ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወኔ ግን ዕድል አልሰጠውም! ወታደሮቹ ተደመሰሱ! ሱልጣኑ ተማርኮ ተሰቀለ! ሚስቱም ክርስቲያኖች ጠንቋይ ይሏት የነበረ ተይዛ ገላዋን ተቀራርጦ ለጅቦች ተሰጠ። ጦርነቱ የተካሄደው ሐምሌ ወር ወደ መጨረሻ 1330 ዓ.ም. ነበረ። አሁንም የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አቅማቸው እንደተሟጠጠ ለንጉሡ ቢያመለክቱም ንጉሡ ግን አልተቀበላቸውም! እሬቱ መከላከል አቅም የሌላቸው የጠላት ቦታዎች ነበሩ። የዓምደ ጽዮን ወታደሮች እየገሰገሱ ጠላቶቹን መደምሰስ ቀጠሉ! ከተሞች ተቃጠሉ! ተዘረፉ! ተወሰደው ታረዱ። የአዳል ሱልጣንም ወረራውን ለማቆም ሞክር ነበር። ጦርነቱ ለክርስቲያን ፈረሰኞች ምቹ በሆነ ግልፅ ቦታ ተካሄደ። የእስላም ወታደሮች በክርስቲያን ፈረሰኞች ተከበው ማምለጫ አጥተው አለቁ! የአዳል ሱልጣን በጦር ሜዳ ሞተ። ወደ መጨረሻ የቀረ የሐረር ሱሰጣን ነበረ። የመጨረሻ ዕድል ለመሞከር በሱልጣኑ ዙሪያ የቀሩት እስላሞች በሙሉ ተሰበሰቡ! ከእነሱ ውስጥም 99 ባላባቶችና ሱልጣኖች ነበሩ! ሕዝቡም ወንድ ሴት ሳይለይ ተካፋይ ነበረ። አሁንም የወሳኝነት ሚና የተጫወተው ሱልጣኑን ከፈረሱ በጦር ወግቶ በመግደል ዓምደ ጽዮን ነበረ። አሁን ግን የሚቋቋመው ኃይል አልነበረም። ሁሉም የመሸሽ ብቻ ነበረ የተያያዙት። አሁን የቀረ ስራ መስጊዶችን ማፍረስ ከተሞችን ማቃጠል ሰዎቹንም ወንድ ሴት ልጅ አዋቂ ሳይለዩ መግደል

ነበረ፡፡ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አራት የተባለው በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ የነበረው ቦታ ደረሱ፡፡ በዚህ ቦታ ብዙ ክርስቲያኖች ጆሮዎቻቸውን አፍንጫቸውን የተቆረጡ እንዲሁም የተሰለቡ ስለነበሩ ንጉሡ ፊት ቀረቡ፡፡ በዚሁ ጊዜ ክርስቲያኖች ቁጣ ገንፍሎባቸው ስነበረ ወንጀለኞች የሀገሩ ሰዎች እንዳያመልጡ በማሰብ የመሸሽ በማስመሰል ወደኋላ ሲመለሱ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ተመለሰ፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች ተመልሰው በመምጣት በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው በደል በሙሉ በእስላሞች ላይ ስመድገም ቂም በቀል ፈጽመውባቸዋል፡፡ ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ተጉለት ሲመለስ የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል፡፡

### 3. አፄ ይስሀቅ

ያ ሁሉ የአጼ ዐምደ ጽዮን ጀግንነት ውጤት አልባ የሚያደርገው ጠላቶችን እስከ ባሕር ዳርቻ ምፅዋ፣ አሰብ፣ ታጁራ፣ ዘይላ ራሱ ባስማባረሩ ነው፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ቀጥሎ ከነገሡት ነገሥታት ወደ ባሕር ጠረፍ የደረሰ ከ1414 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሠ አጼ ይስሀቅ ነበረ፡፡ እንደነገሠ የይፋት ንጉሥ ሠኢድ አልዲን ጦርነት ከፈተበት፡፡ በመጀመሪያ ግጭት ለክርስቲያኖች የቀናቸው ነበር፡፡ ራሱ የይፋት ንጉሥም ለትንሽ ነበር ከመማረክ ያመለጠው፡፡ በ2ኛ ጊዜ ግን ሰይድ አልዲን ኃይሉን አጠናክሮ መጥቶ ወደ ክርስቲያን ምድር ዘልቆ በመግባት ሰፊ መሬት በመያዝ ብዙ ንብረትም ለመዝረፍ ችሎ ነበረ፡፡ 2ኛ. ዙር የክርስቲያን መንግሥት ሠራዊት ባሩዋ በተባለው የሚመራ ነበረ፡፡ ባሩዋ የተከተለው የጦርነት ስልትም እንደ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ሱልጣኖችን ለየብቻቸው መግጠም ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ጥረቱ የአዳል ሱልጣን ጦር ከሰዒድ አልዲን ጦር እንዳይገናኝ ማድረግ ነበረ፡፡ በአዳል ሱልጣን ሠራዊት ወረራ አድርጎ ሱልጣኑ በጦር ሜዳ ተገደለ፣ ወታደሮቹም ተደመሰሱ፡፡ ከዚህ በኋላ የሰኢድ አልዲን ሠራዊትን እያሳደደ መፍጀት ተያያዘው፡፡ በመጨረሻም በዘይላ ከተማ እንዲደበቅ አደረገው፡፡ ክርስቲያኖች የከተማዋን የውሃ መስመር እንዲቋረጥ በማድረግ ከተማውን ከማረኩ በኋላ ሰይድ አልዲን ፌብሯሪ 16 ቀን 1445 ዓ.ም. ተገደለ፡፡ የሱ አስር ልጆች ሸሽተው ወደ የመን ተሻገሩ፡፡ መስጊዶችን በማቃጠል በቦታቸው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩ፡፡ ዘይላ ክርስቲያን ሆና ለ20 ዓመት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ነበረች፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ስላልነበራት የወደብ አስተዳደርም ልምድ ስላልነበራት ለዘለቄታው በቁጥጥሯ አድርጋ ለመቆየት አልቻለችም፡፡ አስር የሰይድ አልደን ልጆችም በየመን መንግሥት እርዳታ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለጦርነት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ልትቆጣጠር አልቻለችም፡፡ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በጦር ሜዳ ባገኘው ድል እንደ ዓምደጽዮን ሲጠቀምበት አልቻለም፡፡ ዘይላ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የይፋት ነፃ መንግሥት ለዘላዓለም ተሰርዞ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ግዛት ውስጥ ተጠቃለለ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ፀረ ክርስቲያን መንግሥት መሪ ተዋናይ የሚሆነው የአዳል መንግሥት ነው፡፡ የወላዝማ ንጉሣዊ ቤተሰብ አንድ ዓመት ከዘይላ መያዝ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ ዋና ከተማቸው ያደረጋት ዳካር የምትባለው ቦታ ነበረች፡፡ አፄ ይስሐቅ፣ኮንቲ ሮሲኒ[1]፣ ጦረኛ ነበረ የሚለው የኢትዮጵያ ንጉሥ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ጦርነት አካሄዷል፡፡

[1] C. Conti - Rossini : Etiopia e genti d' Etiopia p 55



በመጀመሪያ ዘመቻ በዳሕላክ ደሴቶች ሱልጣን ሥር የነበረች ምፅዋ በአፄ ይስሐቅ ወታደሮች ተያዘች፣ ሁለተኛ ዙር ዘመቻ ትልቁ ዳሕላክ ተያዘ፡፡ በሦስተኛ ዙር ዘመቻ ምፅዋና የዳሕላክ ደሴቶች ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ውጭ ሆነው ስለነበረ እንደገና ተያዙ፣ በጦርነቱም መሪ የነበረ ቃዲ ተገደለ፡፡

ሌላ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ከኦሪት ሕግ ገና ያልተላቀቁ የነበሩ ወገራና ደምቢያ አውራጃ ነበር፣ ቤተፀሎታቸው ወድመው በቦታው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩላቸው፡፡ ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተ ደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/፣ እናሪያ /ሊሙ/፣ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ፡፡ ከዚሁም በስተደቡብ የነበረ የኢትዮጵያ መሬት ስፋት በትክክል ባይታወቅም ከስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በስተደቡብ እስከ ዛንዚባር፣ በምዕራብም እስከ ናይል ሸለቆ ይዘልቅ ነበረ[1]፡፡

ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/ እናሪያ /ሊሙ/ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ፡፡ ሁሉም ከኢትዮጵያ ጋራ በሸዋ ግዛት የተቀላቀሉ የቀድሞ ግዛታቸው የሰይድ አልዲን ልጆች፣ የወላዝማ የነብዮ መሐመድ ዘር የሱልጣኖች ቤተሰቦች የሆኑ ከየመን ተመልሰው መጥተው የአባታቸው ሞት ለመበቀል ከግብፅ የመጡ በቱርክ ውጊያ ስልት አሰልጣኞች እየተረዱ ዘመናዊ የጠብመንጃና የጦር መሣሪያዎች የነበራቸው፣ የይግም ግራኝ ተመሳሳይ የሆነ መሣሪያ ታጥቀው ሰፊ ዘመቻ ጀምረው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጠንካራ ይመስል የነበረ ወታደራዊ የማጥቃት ዘመቻ እንደ ተጠበቀው ውጤት አልሰጠም፡፡ ንጉሥ ይስሐቅም የጠላቶቹ እንቅስቃሴ ያውቅና ይከታተል ስለነበረ ለመልሶ ማጥቃት ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ የዘመቻው ሹም የነበረው የሳይድ አልዲን በኩር ልጅ ሳብር አልዲን ነበረ፡፡ የእስላም ወታደሮች በድንገት አደጋ ጥለው ሸዋ መሀል ገብተው በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ሽንፈት አድርሰው ነበር፡፡ ንጉሡም ለመበቀል በእስላም ነጋዴዎች ላይ ጥቃት ከማድረሱም በላይ ያልፈረሱ መስጊዶችን አቃጠላቸው፡፡ ጦርነቱ ከ2ቱ ወገኖች አሸናፊ ሳይለይ ለብዙ ዓመታት ቀጠለ፣ በመሀሉ ሁለቱ ወገኖች ለጊዜያዊ ሰላም ተስማሙ፡፡ በዚሁ ጊዜ በ1422 ዓ.ም. ሳብር አልዲን ሞተ፣ ወንድሙ ማንሱር መሪነቱን እንደተረከበ ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ ማንሱር ጦነቱን በማፋፋም በአማራ መሀል ለመግባት ችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ሽንፈት ስለደረሰበት በ1424 ተማረከ፡፡ ጀማል አልዲን ሌላ ወንድማቸው መሪነቱ ተረክቦ ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ ቤተክርስቲያኖችም ይቃጠሉ ነበረ፣ ክርስቲያኖች የጦር ምርኮኞች በባርነት ይሸጡ ስለነበረ የባሪያ ዋጋ በዓረብ ሀገሮች ረክሶ ነበረ፡፡ ጦርነቱ አሸናፊ ሳይለይ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ክርስቲያኖች መልሶ በማጥቃት ድልን ተቀዳጁ፣ እስላሞቹንም ከሀገራቸው ሊያስወጡ ችለዋል፡፡ በ1429 ዓ.ም. ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ በነበረበት ጊዜ አጼ ይስሐቅ ተገደለ፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ ታዋቂው ጀማል አልዲን ብቤተሰቦቹ በተፈጠረ ጠብ ሲገደል ሌላ ወንድሙ የመሪነቱን ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱ እንደቀድሞ ጭካኔ በተሞላበት ቀጠለ፡፡

[1] Coulbeaux : Histoire Pollitique et religieuse d' Ethiopia p. 285

## 4. አጼ ዘርአ ያዕቆብ

በክርስቲያን መንግሥትም ለአጭር ጊዜ ብዙ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ዝነኛው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ በ1434 ዓ.ም. ነገሠ። በእሱ ዘመነ መንግሥት ሰለሞናዊ ሀረግ ያላቸው ነገሥታት ከፍተኛ ዝናና የአስተዳደር መሻሻል እርምጃ የታየበት ጊዜ ነበር። ተላላፊ በሽታ በሀገሪቱ ገብቶ ስለነበረ ጦርነቱ ለተወሰነ ጊዜ ቆሞ ነበረ። ኢትዮጵያ በአጼ ዓምደጽዮን መሪነት በእስላሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሎች ዜና በመካከለኛው ምሥራቅና በምዕራባውያን ተሰምተው ነበር። ዜናዎች ቢሰሙም የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ፀረ እስላም የሚያካሂደው የሞት ሽረት ትግል ተቆርቋሪ በመሆን፣ የኢትዮጵያ እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች እርዳታ እንደሚያገኙ ሁሉ የክርስትና እምነት ያላቸው የኤውሮጳ ሀገሮች በምን ዓይነት መንገድ ለኢትዮጵያ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እርዳታ ማድረግ እንደሚችሉ የተደረገ ጥረት አልነበረም። ኢትዮጵያ ከኤውሮጳ መንግሥታት የትኞቹ መንግሥታት እንደሆኑ በቂ ወታደራዊ እርዳታ ሊያደርጉላት የሚችሉ የማወቅ ዕድል አልነበራትም። ለምሳሌ ብቸኛ ግለሰብ በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የደረሰና ስለ ኤውሮጳ ለአጼ ዘርአ ያዕቆብ ያወራ አንቶኒዮ ባርቶሊ የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ ነበረ። ኢጣሊያ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለራሷ በባእድ መንግሥታት የምትገዛ፣ በጥቃቅን መንግሥታት የተከፋፈለች፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት የምትመረጥ ሀገር አልነበረችም። ባርቶሊ ለአጼ ዓምደ ጽዮን ይሰጣቸው የነበሩ ዜናዎች ስለ እነዚህ የኢጣሊያ ታናናሽ መንግሥታት ከፍተኛ ስልጣኔና ስለ የሮማ ጳጳስ ትልቅነት ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ አስቸኳይ የክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ፈላጊ ቢሆንም ከማን ጋራ ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚያስረዳ ሰው ስለሌለው እንደ ቀድሞቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ዓምደ ጽዮንና ይስሐቅ ብቻውን ከእስላሞች ጋራ ጦርነት ገጠመ። ዘርአ ያዕቆብ ዘመጀመሪያ ያካሄደው ጦርነት በሀዲያ አውራጃ በራሱ ግዛት ነበረ። በዘርአ ያዕቆብ የዚሁ አውራጃ ገዥ ሆኖ የተሾመው የእንደኛዋ ሚስቱ ወንድም የሆነው ማሂኮ የተባለው ከአዳል ሱልጣን ጋራ በመመሳጠር ሸፍቶ፣ ነፃ መንግሥት አውጆ፣ ሌሎች አውራጃዎችን ወደ እሱ ለመሳብ በምስጢር ግንኙነት አድርጎ ነበር። ዘርአ ያዕቆብ እቅዱ ወደ ተግባር እስኪፈጸመ ድረስ አልጠበቀውም፣ ከሥልጣኑ አውርዶ ወረረው። ማሂኮ ወደ አዳል ሸሽቶ ለመሄድ ወደ ምሽግ ቦታ ለመግባት ሲሞክር የዘርአ ያዕቆብ ወታደሮች ስለደረሱበት ገደሉት፣ ኣንገቱን፣ እግሮቹን፣ እጆቹን ተቆራርጠው ወደ ዘርአ ያዕቆብ ተወሰደው በንጉሡ ቤት ደጃፍ ተሰቀሉ። ከሁሉ የላቀ ድል አጼ ዘርአ ያዕቆብ የተቀዳጀው ለአዳል ሱልጣን በጀማል አልዲን ስልጣን የያዘው የሰይዲ አልዲን ሌላ ልጅ በባድላይ ነበረ። በ1445 ዓ.ም. ባድላይ የዳዋሮን አውራጃ ወሮ ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ በአነስተኛ ወታደሮች ቢገጥመውም የገጠመው በወኔ ስለነበረ ድሉ የእሱ በመሆኑ በመጀመሪያ መስመር ሆኖ ይዋጋ የነበረ ባድላይ ከአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጋራ ተወግቶ ወደቀና ሞተ። አስከሬኑ ተቆራርጦ ለመላው የመንግሥቱ ግዛት ተከፋፍሏል። የባድላይ ወንድም በመሸሽ ላይ እንዳለ አሳድዶ አዋሽ ወንዝ ለመሻገር በሚሞክርበት ጊዜ ተገደለ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ሁለት ድሎችን በአጭር ጊዜ ቢጎናፀፍም የእስላሞች አደጋነት በሙሉ እንዳልተወገደ ስለተረዳና አሳሳቢ ስለሆነበት በሁለት መንገድ ዘላቂ መፍትሔ ብሎ የገመታቸው እርምጃዎች ወሰደ። የመጀመሪያ የክርስቲያኖች አንድነትና የእምነታቸው ማጠናከሪያ 2ኛ. ከዓለም ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ መጠየቅ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ በሁለቱ



መንገዶች ተጠቅመዋል። የክርስትና ሃይማኖት ለማስፋፋት በውድም በማስገደድም ሞክሯል። መንፈሳዊ መጽሐፎች ከውጭ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲሰጡ አስገድዷል። የማርያም ድንግል በዓላቶችና፣ ፆምን ወዘተ ወስኗል። አንዳንድ የውጪ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመግባታቸው በሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያለው ልዩነት የማዋዋያ እርእስት ሆኖ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ለማግኘት ለነበረው ምኞት ግን ውጤት አልባና ዓላማውን የሳተ ነበረ ለማለት ይቻላል። አጼ ዘርአ ያዕቆብ የኤውሮጳ መንግሥታትን ማንነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ በ1450 ዓ.ም. ለናፖሊ ንጉሥ መልእክት ልኮዋል። የናፖሊ መንግሥት፣ እንኳን ከኤውሮጳ መንግሥታት ሊወዳደር ቀርቶ፣ በኢጣሊያ ከነበሩ አነስተኛ መንግሥታትም ከሁሉም ኋላ ቀር የነበሩ መንግሥታት የሆነ ነበረ። ስለዚህ ምንም ዓይነት ጠቃሚ እርዳታ ለኢትዮጵያ መስጠት የሚችል አልነበም። የናፖሊ መንግሥት በሰዓሊ ሞያ ስም የላከው ብራንካሌዮ የሚባለው ግለሰብ ቀድሞ ቄስ የነበረ ስለሆነ ጊዜው ያሳለፈው የሃይማኖት ክርክር በመቀስቀስ ብቻ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ለዝነኛው የቢዛንታይን ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ እንዳይጠይቅ በዚሁ ጊዜ በቱርክ ኦቶማን መንግሥት ተሸንፎ በ1454 ዓ.ም. ዋና ከተማው ቆስጣንጥንያ የተማረከበት ወቅት፣ሕልውናውም ያበቃበት ጊዜ ነበረ።ሌላ አጼ ዘርአ ያዕቆብ በትልቅ ጉጉት እርዳታ እንዲያደርግለት ሲጠባበቅ የነበረው ከሮማ ጳጳስ ነበረ። ወቅቱ በቱርክ ኦቶማን አማካኝነት የእስልምና ሐይማኖትና መንግሥታት በኤውሮጳም በአፍሪካም ጥንካሬ ያገኙበት ነበረ። በዚሁ የተነሳ የሮማ ጳጳስ የመላው ዓለም ክርስቲያኖች ለማስተባበር በ1440 ዓ.ም. ጣሊያን ሀገር በፈሬንሴ ጉባዔ ጠርቶ ነበረ። ኢትዮጵያም የግብፅ ቤተክርስቲያንም መልእክተኞቻቸው ወደዚህ ጉባዔ ልከው ነበር። የግብፅ መልእክተኞች የተመሩት እንድሪያ በተባለው የቅዱስ አንቶንዮስ ገዳም አለቃ ነበረ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ቀሳውስት የተላኩት ከአባ ኒቆዲሞስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አለቃ ወክለው ነበረ። የሮማ ጳጳስ ዓላማ የዓለም ክርስቲያን በሙሉ የካቶሊክ እምነት ተቀብለው በእሱ ስር እንዲሆኑ ነበረ። ለክርስቲያኖች ትብብር እንቅፋት የሆነውም ይህ ቅድመ ሁኔታ መግባት ስለነበረ ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም እርዳታ ከክርስቲያን መንግሥታት ያላገኘችው በዚሁ ቅድመ ሁኔታ ምክንያት ነበር። የግብጽ መልእክተኛ ለጉባኤው ያደረገው ንግግር የሮማ ጳጳሳት በማወደስ ነበረ። ከተናገረውም ውስጥ የሮማን ጳጳስ በማስመልከት “በዚሁ ዓለም እርሶም እግዚአብሔር ነዎት እርስዎ የክርስትና እንደራሴ ነዎት፣ እርስዎ የዓለም ዓቀፍ ቤተክርስቲያን አለቃ ነዎት ለእርስዎ የመንግሥተ ሰማያት በር የመክፈት፣የመዝጋት ቁልፍ ተሰጥቶታል ወዘተ... የሚል ይገኝበታል። የግብፅ መልእክተኛ ንግግር ከተሰማ ሁለት ቀን በኋላ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ፈሬንሴ ገቡ፣ ከሁለቱ መልእክተኞች አንዱ ባደረገው ንግግር የግብፅ መልእክተኛ ካደረገው ንግግር ተመሳሳይ ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ሀገሩ ኢትዮጵያ በሚመለከት ያሰማው የሚያወድሱ ቃላቶች ነበሩ።

ወደ ሮማ ጳጳስ ፊቱን አተኩሮ ሲናገር “ከእርስዎ የተለዩ ሁሉ ወድቀዋል፣ ከሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከተለዩ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የእኛ ጠንካራና ኃይለኛ ነፃ ሆና ኖራለች፣ ምክንያቱም ሌሎች ቤተክርስቲያኖች ከእርስዎ የተገነጠሉ በክፋት በፍላጎታቸው ነው፣ እኛ ግን ተለይተን የኖርነው በመገደድ፣ ርቀት የተነሳ፣ በመንገዱ አደገኛነት ነው፣ ከእርስዎ በፊት [illegible]ነበሩ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ቸልተኝነት ነው።

"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በዚህ ዓለም ከሮማዊት ቤተክርስቲያን ጋራ ከመዋሐድ ሌላ ምኞት የለውም" ወዘተ... የሚል ይገኝበታል፡፡

አጼ ዘርአ ያዕቆብ ግዛቱ ወደ ደቡብ አስፋፍቶ ስለነበረ፣ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በኩራት አፉን ሞልቶ ሲናገር "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አንድ መቶ ነገሥታት እንደሚያዝዝ ለጉባኤተኞች ተናግሯል፡፡ የፌሬንሴ የጉባኤ በተሳካ ሁኔታ የተፈጸመ መስሎ ቢታይም መልእክተኞቹ ተመልሰው ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ካይሮ ሲገቡ የጉባኤው ውሳኔ ሳይፈርም በቀረ ብቸኛ በኢፌሶን ቤተክርስቲያን መልእክተኛ የሚመራ የጉባዔውን ውሳኔ የሚቃወም ንቅናቄ ተደርጎባቸው ሁሉም የምሥራቅ አበያተክርስቲያን የሚያጠቃልል ፀረ ሮማ ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ተነስቶ ነበር፡፡ ስለዚህ የፌሬንሴ ጉባዔ ለሮማ ጳጳስ ከባድ ክስረት ነበር የሆነበት፡፡ በአጼ ዓምደ ጽዮን የአጼ ይስሐቅና በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ በቀይ ባሕር ወደቦች በክርስቲያን ስም ከቱርክ ኦቶማን ጋራ ትፋለም የነበረችው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ኢትዮጵያ ግንኙነት አድርጋ ብትሆን ኖሮ በይማም ግራኝ ጊዜ እርስ በእርስ ጦርነትና የሀገሪቱ አበያተክርስቲያናት የቅርሳቅርሷ የመጻሕፍቶቿና የታሪኳ ውድመት አይደርስባትም ነበር፣ የኦሮሞ ታሪካዊ ማስፋፋት ክስተት አያጋጥማትም ነበረ፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ጀምሮ ከባህር ወደቦች በቀር የመሀለ ሐገር የአክሱም መንግሥት ዘመን ወደነበራት ስፋት ተመልሶ ነበረ፡፡

በአፈ ታሪክ አባባል ኢትዮጵያ 14 መንግሥታት ነበሯት፡፡ ከነዚህም ውስጥም 4 መንግሥታት የወርቅ ዘውድ የሚጭኑ ነበረ እነሱም 1. ትግራይ 2. አማራ /ጎንደር/ 3. ላስታ 4. ሸዋ /ጎጃም ናቸው፡፡ ሌሎች 4 ነገሥታት የብር ዘውድ የሚጭኑ እንደዚሁም ነገሥታት የነሀስ ዘውድ የሚጭኑ ስማቸው የማይታወቅ ነበረ፡፡

አልበርቶ (1)ፖሌራ እንደጠቀሰው በ1603 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ሚሲዮናዊ አባ ፓየዝ በጻተፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 35 መንግሥታትና 18 ራስ ገዝ አስተዳደሮች ነበሯት፡፡

እንደዚሁም ፖሌራ በ1629 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ፖርቱጋላዊ፣ ሚሲዮናዊ ፣ ዳሜዳ የጻፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 36 መንግሥታትና 17 የራስ ገዝ አስተደደር ያላቸው ግዛቶች ነበራት ካለ በኋላ፣ ባገኘው ሌሎች ዜናዎች ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት 60 መንግሥታት ክርስቲያን ያልሆኑ እንደዚሁም ሌሎች ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ገባር መንግሥታት ያዝዝ እንደነበረ ገልጧል፡፡

በተጨማሪም ፖሌራና ኮንቲ ሮሲኒ ገጽ 15 እንደጠቀሱት ከ1624 ዓ.ም. እስከ 1704 ዓ.ም. የኖረው ጀርመናዊ ሉዶልፍ የኢትዮጵያ ቋንቋና ታሪክ አዋቂ በጻፈው መሠረት በማድረግ በተለያዩ ጸሐፊዎች የሚነገረው የመንግሥታት ቁጥር የተለያየ ነው ብሎ ካስጠነቀቀ በኋላ ኢትዮጵያ 30 መንግሥታት ነበሯት በማለት ስማቸውን ይጠቅሳል፡፡ የመንግሥታቱ ስም በተመለከተ አብዛኛው አሁን ቢኖርም ያንዳንዶቹ ስም ግን አሁን የለም፡፡ ፓየዝ ባወጣው የ35 መንግሥታት ስም ዝርዝር እንደሚከተው ያቀርበዋል 1. ትግራይ ወሰኑ ከየት ወዴት መሆኑን ባይገልፅም በዛሬዋ ደቡብ ትግራይ ክፍል አበርጋለ፣ ሰሎዋ፣ ወገራት፣ እንዳርታ፣ እንደ አካል ነበረች 2. ደንከል /አፋር/ 3. አንጎት አብዛኛው የዛሬዋ ወሎ 4. ዶባ ከወሎ ትግራይና አፋር መሐል የነበሩ ሕዝቦች 5. አውሳ ደቡብ አፋር 6. አማራ ምናልባት ደቡብ ጎንደር 7. ላስታ 8. ሸዋ ከየት ወዴት እንደሆነ

(1) Alberto Pollera : Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa



አይታወቅም 9. ይፋት 10. ገዳም 11. ጋንች 12 ዳዋሮ/ ምናለባት የዛሬዋ ጨርጨር 13. ፋጢጋር ከይፋት በስተሰሜን የዛሬዋ አርጎባ 14. አዩዩ ከዝዋይ ሀይቅ በስተምሥራቅ 15. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሶማልያና ሕንድ ውቅያኖስ 16. ሀዲያ 17. አላባ /ቆቃ አካባቢ 18. አክሰለን 19. ቤቶ ቆቃ አካባቢ 20. ቤቴሪምራ 21. ጉራጌ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 22. ኮይራ /ከጁባ ወንዝ እስከ ስተፋኒያ ሀይቅ 23. በዙማ ከዝዋይ በስተደቡብ 24. ሱፍ ጋሞ የዝዋይ በስተደቡብ በአብያታ ሐይቅ እስከ ቆይራ ባሕር ጋ 25 ባሕር ጋ 26. ከንባታ 27. ቦሻ (ጅማ) 28. ጉመር /ከፋጢጋር በስተደቡብ 29. ጃንጃሮ 30 እናርያ (ሊሙ) 31. ኮንታ 32 ዳሞት 33. ጎጃም 34. ቤጌምድር 35. ደንብያ፡፡

በዚህ ስም ዝርዝር እንደምንመለከተው የዛሬዋ ጎንደር ክፍለ ሀገር ለቤጌምድር ደምቢያ አማራ መንግሥታትና በሰሜን ፀለምቲ ቦራ ፀገሌ ወልቃይት ማዘጋራ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ተከፋፍላ ነበረች፡፡ ላስታ በሁሉም ስም ዝርዝር አይገኝም፡፡ ወለጋ የቢሳሞ መንግሥት ተብላ ትጠራ ነበረ፡፡ ከዲዴሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ግን ጋፋት ተብሎ ይጠራ ነበረ፡፡ ይህ ሰፊ የኢትዮጵያ ግዛት በታሪክ በመልክአ ምድር አቀማመጥ በዘር አንድ የሆኑ ሕዝቦች በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ይተዳደሩበት የነበሩ ኢትዮጵያ በእስልምና እምነት ተከታዮች እርስ በእርስ ጦርነት ባትወጠር በተለይም በሌላ አርእስት እንደሚታየው የኦሮሞ የማስፋፋት ክስተት ባያጋጥማት በኬንያ በኩልም እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም በላም ለመድረስ በአካባቢው የተደራጀ ተቃዋሚ ኃይል ስላልነበረ እንቅፋት አያጋጥማትም ነበረ፡፡

ይህ በማድረጓም በአፍሪካ ስልጣኔ ለማስፋፋት የነበራት ታሪካዊ ተልእኮ መወጣቷ የሚያመለክት ስለሆነ የሚያስመሰግናት ነበረ፡፡ የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን የሚወቅሷት ይህንን ባለማድረጓ ነው፡፡ የዛሬዎቹ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ግን የደቡብ ምስራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ምኒልክ በዛሬ አንድ መቶ ዓመት በወረራ እንደያዛቸው ለማስመሰል እየሞከሩ ይታያሉ፡፡ ከንያ ውስጥ የሚኖሩ የኦሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ከኢትዮጵያ ተነጥለው ከኬንያ ጋራ የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ በኦሮሞች ምክንያት የጋጠማት የመንግሥቷ ድክመት ነው፡፡

በንግሥት ሳባ ጊዜ ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የት ድረስ ይደርስ እንደነበረ በማመልከት (1) ሻለቃ ሩፊሉ ፔሪኒ እንደሚመለከተው ይገልጸዋል "የባሕር ነጋሽ ሥልጣን ከበረኒስ የባሕር ወሰመጥ $24^0$ ዲግሪ በስተሰሜን እስከ የእጣኑ ሀገር ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም እስከ ሶፎላ $20^0$ ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዩድ ይደርስ ነበረ፡፡ በዚሁ ቦታ የብዙ ሳይንቲስቶች እምነትም ከነእሱ ውስጥም በመጨረሻ ጊዜ የብሪቲሽ ሙዝየም ስራ አስኪያጅ የነበረ ሚቼ ሚስተር ቤንት ባለበት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ኦፊር የሚባለው ምስጢራዊ ቦታ ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሡ ሰለሞን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንድትችል መርከቦች የተሰሩበት መሆኑን ገምቷል"፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እነ አጼ ይስሐቅ ወደ ደቡብ ያመሩበት የነበረ ሀገር የቅድመ አያቶቻቸው ይዞታ የነበረ መሆኑን በማስታወስ የሆናል፡፡

በነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ስፋት ሉካ ደይ ሳቤሊ(2) እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

(1) Perini Mereb-Melash (Al di qua del Mareb)

(2) Luca Dei Sabelli\ VII p. 15-17

1. ኢትዮጵያ በሰሜን ወሰኗ እስከ ምፅዋ ይደርስ ነበር፡፡ ሐማሴን፣ ሰራዬ፣ አከለጉዛይ አውራጃዎች እስከ ቀይ ባሕር ድረስ የባሕር ነጋሽ መንግሥት አካል ነበሩ፡፡ ዋና ከተማ ደባሩዋ ነበረች፡፡ ሳሄልና ባርካ በቁጥጥሩ ስር ነበሩ፡፡

2. ትግራይ ዋና ከተማ አክሱም ሆኖ በትግራይ መኰንን የሚታዘዝ ነበረ

3. ሰሜን አፋርና ደቡብ አፋር (አዋሳ)

4. ዳዋሮ (ጨርጨር)

5. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ በዚህ በኩል የኦሮሞ ክስተት ባያጋጥም ኖሮ የክርስቲያኖች ፖለቲካዊ መስፋፋት መቋቋም የሚችል ተቃዋሚ ኃይል አልነበረም

6. ፋጢጋር ከባሌ በስተምሥራቅ ከመካከለኛ አዋሽ ወንዝ እስከ ዋቢ ወንዝ ምንጭ የሚያጠቃልል

7. እይ ወይንም ወድ ይባል የነበረ ክፍለሀገር ማእከሉ በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ ነበረ፡፡ በዚህ አውራጃ በዛሬ አጠራር ስልጤ የተባሉ ቋንቋቸው ከሐረሪ የሚቀራረብ ጉራጌዎች ይኖራሉ፣ አመጣጣቸውም ከጥንታዊው አክሱም መንግሥት ነው፡፡

8. ከወደ በስተደቡብ ከዝዋይ ሐይቅ እስከ አባያ ሐይቅ ሱፍጋኖና ቡዛሞ የተባሉ ሁለት ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

9. በስተደቡብ ኮይራ ነበረ ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው ለወታደሮች የሚያገለግሉ ፈረሶች በማቅረብ ነበረ፡፡ የሚገኘውም ከላይኛው ጁባና ከአባያ ባሕር ሐይቅ መሐል ነበረ እስከ እስቴፋኒያ ሀይቅ ከንያን የሚያጠቃልል ነበረ

10. ወላሞና ጋሞ በንጉሥ ይስሐቅ ዘመቻ ጊዜ የተቀላቀሉ ከአባያ ሐይቅ በስተምዕራብ የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ግዛቶች ሁሉ የታወቀ ተቃዋሚ የተደራጀ ኃይል ስላልነበሩ ኦሮሞዎች ከኢትዮጵያ ባየገኑዋቿቸው ወሰናቸው እስከ ተፈለገ ሩቅ ሊዘልቅና ሊስፋፋ ይችል ነበር፡፡

11. በስተምዕራቡ በአጼ ይስሐቅ ወደ ማእከላዊ መንግሥት የተቀላቀሉ ትናንሽ መግሥታት ነበሩ ከነሱ ውስጥም እናሪያ /ሊሙ/ በሻ (ጅማ አባጅፋር) ወዘተ... ይገኙባቸዋል

12. በታችኛው እሞ ሰፈ የጃንጀር መንግሥት ነበረ

13. በስተሰሜን ከንባታ ነበረ፡፡ ከኦሞ በስተግራ እስከ አቢያታ ሀይቅ

14. ከከንባታ በስተሰሜን ከላይኛው አዋሽ እስከ ኦሞ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 1000 በሬዎች ግብር ለመንግሥት የሚከፍል የጉራጌ መንግሥት ነበረ

15. ከጉራጌ አዋሳኝ የሀዲያ ሱልጣን አገዛዝ ነበር

16. ከሐዲያ እስከ ሸዋ አሰማስ ቱጋር የሚባሉ ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

17. ከጋንዝ በስተምዕራብ ትልቁ ዳሞት ነበረ

18. በስተምዕራብ በዛሬዋ ወለጋ ቢዛሞ የሚባል መንግሥት ነበረ

19. ከዲዴሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ጋፋት ነበረ

20. አባይ ተሻግሮ ጎጃም ይገኛል

21. ከጣና ሐይቅ እስከ ተከዜ በጌምድር

22. በዛሬዋ ጎንደር ዙሪያ ደምቢያ ነበረ



23. ወደ ሰሜን ፀለምቲ፣ ፀጌሌ፣ ወልቃይት፣ ሰሜን፣ ማዘጋዘ፣ የተባሉ ከጥንት ጀምሮ አገውና ፈላሻ የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡

24. ከተከዜ ወንዝ በስተሰሜን ሰለዋና አበርጋሌ ይገኛሉ

25. ወገራትና እንደርታ አውራጃዎች ከጥንት ጀምሮ ራሳቸውን የቻሉ ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የተሰጣቸው ነበሩ

26. ከንደርታ በስተደቡብ ላስታ

27. ከላስታ በስተምሥራቅ አንጎት የዛሬዋ ወሎ አብዛኛውን የሚያቃልል

ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያ አስተዳደር አከፋፈል ካርታ ይሄንን የሚመስል ሲሆን ስፋቱ ከዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በጣም የሚበልጥ እንደነበረ ብዙ ማስረጃ ባይኖርም የኢትዮጵያ ግዛት ከንያም ያጠቃልል እንደነበረ የሚጠቁም 200 ዓመት ከአጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ በአጼ ፋሲለደስ ዘመነ መንግሥት በኋላ የ'ሞምባሳ Mombassa ንጉሥ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚታዘዝ መሆኑን ሉካ ደይ ሳበሊ[1] ገልፀዋል፡፡ እንደፈረንጆች ቃል አገላለፅ የኦሮሞ ፌኖሚኖን /Oromo phenomenon) በኢትዮጵያ ታሪክ ባያጋጥማቸው ኖሮ ጀግኖች አባቶቻችን በእነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት እንደ አክሱማውያን እስከ ሶፎላ ባይደርስም ከንያንና ደቡብ ሶማሊያ የሚያጠቃልል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ዘልቆ እንደነበረ፣ ይኸውም ለ200 ዓመት ቀጥሎ እንደነበረ ከላይ የተጠቀሰው የታሪክ ማስረጃ ያመለክታል፡፡ የኦሮሞ ፌኖሜኖን ያልኩበት ምክንያት የኦሮሞ ወደ መሀል ሀገር መስፋፋት የውጭ ወረራ አይባልም ወይንም በአንድ ሀገር ውስጥ በሁለት ጎሳዎች ወይም ክፍለ ሀገሮች የተደረገው እርስ በእርስ ጦርነት አይባልም፡፡ ከላይ ከአንደኛ እስከ 27ኛ ተራ ቁጥር የጠቀስኳቸው በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና ክፍላተ ሀገሮች ካርታ የኦሮሞ ስም አልነበረም፡፡ የኦሮሞ ክስተት የመጣው ከተጠቀሰው ዓ.ም. በኋላ ነው፡፡ አሁን የሚታየው የኦሮሞ አሰፋፈር ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ሐረርጌ እስከ ምዕራብ ኢሉባቡር ሌሎች ሕዝቦች ሰፍረውበት የነበሩ መሬት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸውም የኦሮሞ ክስተት በኢትዮጵያ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ዳግማዊ ምኒሊክ የሚወክለው የአማርኛ ቋንቋ በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ ወረራ በመፈጸም ሌሎች ሕዝቦች በቋንቋቸውና በባሕላቸው እንዳይጠቀሙ አድርገዋል የሚል ወቀሳ በአሁኑ ጊዜ ሲሰነዘር ይሰማል፡፡ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ ለአስተዳደር እንዲያመች የመንግሥት ቋንቋ አማርኛ ስለነበረ በአገሪቷ አስተዳደር በሚመለከት በተዘረጋው በጣም ዝቅተኛ የአስተዳደር መዋቅር የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋዎች ሳይነኩ ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ሁሉ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም ያስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ቆየቶ ነበር፡፡

የአማርኛ ቋንቋን ለማስፋፋት ምክንያት የሆነው ግን በይበልጥ ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ በኃይለሥላሴ ጊዜ ትምህርት ቤቶች ስለተስፋፉ ይሆናል፡፡ የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋና ባሕል ማጥፋት ብቻ ሳይሆን የሕልውናቸውም ማጥፋት የተፈጸመው በኦሮሞች የጋዳ አስተዳደር ዘዴ ነው፡፡ የኦሮሞ ቋንቋ በአጭር ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ መስፋፋት ሁኔታ በቂ ማስረጃ ባይኖርም ምናልባት ቀደም ብለው ሰፍረበት የነበረውን ሕዝብ በሙሉ እየፈጁ ማስለቀቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሕዝብ የሌላ ሕዝብ ቋንቋና ባሕል በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰላም ስለማይቀበል በከፊል ነዋሪ

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 384

ሕዝቡን እየጨረሱ ቋንቋውንና ባሕሉን የመቀየር ሂደት እንደተካሄደ አያጣራጥርም፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን የኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች የአንድ ነሳ አባል ሳይሆኑ የብዙ ነሳዎች ቅልቅል መሆናቸውን ለመረዳት አግኝቷል ለማለት ይቻላል፡፡ ብዙዎቹ አሁን በኦሮምኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ ሕዝቦች የድሮ ቋንቋቸው አማርኛ ነበር፣ ወይንም የሲዳማ ቋንቋ ነበረ ሌሎችም በደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ የሚገኙ የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሁን ልናውቃቸው የማንችል የተለያዩ ቋንቋዎች እንደነበሯቸው መገመት አያዳግትም፡፡ በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የኦሮሞኛ ቋንቋ ተቀብለው ስለነበረ አሁንም ይጠቀሙብታል፡፡

አጼ ምኒልክ 450 ዓመት ከነ አጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ ኢትዮጵያ የቀድሞ ግዛቷ በከፊል እንድታገኝ በማድረጉ የሚደነቅ ነገር አይደለም፡፡ ወገን ከወገኑ እንዲቀላቀል በማድረጉ ያስመሰግነዋል እንጂ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ወራሪ አያሰኝም፡፡ ሐቀኛ ኢትዮጵያውያን ምኒልክን የሚወቅሱት እንደ አጼ ይስሐቅ ዘይላን፣ በርበራን፣ ሞቃድሾን ችላ በማለት አለመያዙ ነው፡፡ በተለይም ኤርትራ ለኢጣሊያ ገፀ በረከት መስጠቱ በታሪክ ሲያስወቅሰው የሚኖር ስለሆነ ሀገሩን የሸጠ ከዳተኛ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሚል አጠራር ሲያስታውሱት ይኖራሉ፡፡

## 5. ንግሥት እሌኒ

የኢትዮጵያ መንግሥታት እስላሞችን ለማጥፋት በኃይል የማይቻል መሆኑን እየተረዱ ስለመጡ የክርስቲያን ግብጾችና ካቶሊኮች ድጋፍ መፈለግ ጀመሩ፡፡ ከዓረብ መንግሥታትም ቢቻል ወዳጅነት መፍጠር ካልተቻለም ገለልተኛ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ተሞክረዋል፡፡ የዓረብ መሪዎችም በሰላማዊ መንገድ አብረው በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ተሞክራል፡፡ የዚሁ ፖሰቲካ ቀስቃሽ ንግሥት እሌኒ ነበረች፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብም ቢሆን ከእስላም ጋራ በሰላም ለመኖር በመፈለግ ከሀዲያ አንድ ሚስት አግብቶ ነበር፡፡ ንግሥት እሌኒም ራሷ በልጅነቷ እስላም ነበረች፡፡ የአጼ ዘርአ ያዕቆብ ልጅ አጼ በእደ ማርያም ሁለት የእስላም ሚስቶች ነበሩት ንግሥት እሌኒና ንግሥት ሮማነ ወርቅ፡፡ እነሱም ከአዳል ሱልጣኖች የሚወለዱ ከታወቁት የየመንና የሀድራሞት የመንግሥታት ዘሮች ይዛመዱ የነበሩ ናቸው፡፡ በተለይ ንግሥት እሌኒ በዘርአ ያዕቆብ የተተኩ አራት የኢትዮጵያ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በውጭ ጉዳይ አመራር ተሰሚነት አግኝታ ነበር፡፡ ወደ ዓረብ ሀገር የሚመላለሱ አርሜን፣ ዓረብ፣ ሕንድ፣ ግሪክ፣ ነጋዴዎች መረጃ እንዲያቀብሏት ታደርግ ነበረ፡፡ 500 ሰዎች አባል የነበረው አንድ የኢትዮጵያ መልእክተኛ ቡድን ወደ ግብፅ ሱልጣን ተልኮ ነበረ፡፡ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና ሰልፍ በካይሮ በታየበት ጊዜ ተቃውሞ ከሕዝቡ ስለተቀሰቀሰበት በባለስልጣኖች እርዳታ ብቻ ከአደጋ ሊያመልጥ ችሏል፡፡ ንግሥት እሌኒ ክርስቲያን ብትሆንም ከአዳል ቤተሰቦቿ ግንኙነት አላቋረጠችም ነበር፡፡ ጥረቱንም ከንቱ አልሆነም፡፡ የአዳል ሱልጣን የነበረው መሐመድ ጦርነት ከማድረግ ይልቅ በሰላም አብሮ መኖር ፈላጊ ሆኖ ነበረ፡፡ በጋብቻ በመተሳሰርም በአንድ ሆኖ በስላም መኖር ደህና ውጤት ያስገኘ መስሎት ነበር፡ ነገር ግን የሱልጣኖች ስልጣን ስም ብቻ ሆኖ ራሳቸው ስልጣን የጨበጡ አሚር የተባሉ ከክርስቲያን ጋራ በሰላም መኖር የማይዋጥላቸው ሰዎች ተፈጥረው ነበረ፡፡ የሰላም ጥረቱም በይበልጥ የከሸፈው በኢውሮጳ በክርስቲያኖችና በዓረቦች እስላሞች መካከል



ይደረግ የነበረው ጦርነት ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት በሀገራችንም ስለተዛመተ ነበር፡፡

ወቅቱ ኤሮውጳ ግዛቷ ወደ ሌላ የዓለም ክፍሎች ማስፋፋት የጀመረችበት ነበረ፡፡ ከኢውሮጳውያን የማንባር ቀደም በመላው የኢውሮጳ ስም የፖርቱጋል ዓላማ የአፍሪካ የባሕር ጠረፍ ዙሪያ ለመቃኘት ነበረ፡፡ የሮማ ጳጳስ የፈሬንሲ ጉባኤ የጠራ ዓላማውን ገመደገፍ ማንኛውም የአፍሪካ ወደብ በፖርቱጋል የጦር መርከቦች ከተጎበኘ የፖርቱጋል እንዲሆን ስለፈቀዱ ፖርቱጋሎች ጥረታቸውን በመቀጠል ምዕራብ አፍሪካን ዞረው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ደረሱ፡፡ ከደቡብ ፖርቱጋሎች ቀይ ባሕር ሲደርሱ ቱርኮችም ከሰሜን ግዛታቸውን እያስፋፉ ቀይ ባሕር ደርሰው ነበር፡፡ በ1517 ዓ.ም. ቱርኮች በድል አድራጊነት ካይሮን ያዙ፡፡ በዚሁ ጊዜም ሱዋኪምና ምጽዋን ተቆጣጠሩ፡፡ በቀይ ባሕር ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በጭካኔ ይፋጁ ነበረ፡፡ በኢትዮጵያም በአዳል ሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ጦርነት እንዲቀሰቀስ አስተዋጽ ነበረው፡፡

## 6. አፄ በእደማርያም

አፄ በእደማርያም የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት በመጀመርያ ጦርነት ያካሄደው በሰሜን፣ በጸለምቲ፣ የነበሩ ፈላሾችና በዶባ ነበረ፡፡ በስተምሥራቅ የአዳል ሱልጣን መሀመድ ወደ በእደማርያም መልእክተኛ ልኮ ግብር እየከፈለ የበላይነት አምኖ በሰላም ለመኖር ስለተሰማማ ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ ነበር፡፡ የአዳል ሱልጣን መሐመድ በ1470 ዓ.ም. ሲሞት ልጁ ኢብራሂም ሲተካ ስልጣኑ በኢ﹁ሚሮች እጅ ሆኖ ነበር፡፡ ሱልጣኑ ለስም ብቻ ተቀምጦ ነበር፡፡ በ1474 ዓ.ም. ከአዳል ጋራ በተደረጉ ጦርነቶች ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንፈት ገጠማቸው በእደማርያም ከሞሞቱ በፊት 1478 ዓ.ም. ለግብፁ ሱልጣን በሰላም ለመኖር ውል ለማድረግና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን እርዳታ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ መልእክተኛ ልኮ ነበር፡፡ መልእክተኞቹ ከግብፅ ቤተክርስቲያን ወደ ፊልስጤም አምርተው ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ሮማ እንዲሄዱ ገፋፋቸው፡፡ በዚሁ መሠረት መልእክተኞች ወደ ቆስጠንጥኒያ በማሄድ ፋንታ ወደ ሮም አመሩ፡፡ ኖቬምንበር 1481 ዓ.ም. የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሲስቶ4ኛ. በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተቀበሏቸው፡፡ 1ኛ. አባ ፍራንችስኮ ሳጋራ 2ኛ. አባ ጆቫኒ ዲ ካላብሪያ 3ኛ. አስተርጓሚ ሆኖ ከኢየሩሳሌም አብሮ የመጣ አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲ ኢሞላ የሚባሉ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ፡፡ አባ ሳጋራ ካይሮ ሲደርሱ ሞተ፣ ሁለቱ ግን ኢትዮጵያ ደርሰው ንጉሥ እስክንድር ወደ አለበት ደረሱ፡፡ ነገር ግን አባ ጆቫኒ ዲአሞል ወደ ንጉሡ መቅረብ 8 ወር ጠብቆ ሳይሆንለት ሲቀር አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲአምሪ ወደ ኢየሩሳሌም ቁጥሩ የሚሲዮናውያንም ተልኮዋቸው ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ፡፡

## 7. አፄ እስክንድር

በበእደ ማርያም ምትክ እስክንድር የእደ ማርያምና የሮማን ወርቅ ልጅ ተተካ፡፡ በእደማርያም የሞተው በ1478 ዓ.ም. ነበር፡፡ እስክንድርም አንድ ጊዜ ብቻ በአዳል ያልተሳካ ጦርነት አድርጎ በ1495 ዓ.ም. ዐረፈ፡፡ በእስክንድር ዘመነ መንግሥት በፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ሁለተኛ አልፎንሶ

ዳ ዳያኘ ፔድሮ ዳ ኮቪልሃም የ ባሰው የሐበሻ መንግሥት የት እንደሚገኝ ፈልገው እንዲያገኙ በ1487 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጧቸው ወደ ግብፅ አመሩ፡፡ የሐበሻ ሀገር በአፍሪካ ይሁን በእስያ የማይታወቅ ስለነበረ ካይሮ ደርሰው ከሱዋኪም አደን ቢገዙም የሚነግሯቸው ሲያጡ አንዱ ወደ አፍሪካ አንዱ ወደ እስያ ሄደው እንዲፈልጉ ተስማምተው አልፎንሶ ዳ ፓይቫ በርበራ ደረሰ፣ እዚያው ተገደለ፡፡ ፔድሮ ዳ ኮቪልሀም ግን ሕንድ ገባ፣ ተመልሶ ወደ አፍሪካ በመምጣት የምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፎች ጎብኝቶ ካይሮ ገባ፡፡ እዚያም የጓደኛው ሞት ሰማ፡፡ ከፖርቱጋል ንጉሥ አዲስ ትዕዛዝ ስላልተሰጠው ወደ ጅዳ ሄደ፡፡ በመጨረሻ ዘይላ ገባ፤ ከዚያም ጦርነት የሚደረግበት የአዳል ሀገር በድፍረት አቋርጦ ንጉሥ እስክንድ ወደሚገኝበት ደረሰ፡፡ ንጉሡ ከታላቅ ክብር ተቀብሎ ወደ ዋና ከተማው ወደ ትጉለት ወሰደው፡፡ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ግን አልፈቀዱለትም፡፡ እስክንድር እንደሞተ አለመግባባት ተፈጥሮ የእስክንድር ልጅ የ7 ዓመት ሕፃን ቢነግሥም ሰሞተ፣ የእስክንድር ወንድም ናኦድ ንጉሥ ሆነ፡፡ የአዳል ሱልጣን በናኦድ ጊዜ የሰላም ጥረት ቢቀጥልም ማሩዲ የተባለው የሐረር ኤሚር ግን በክርስቲያን መንግሥት በየዓመቱ በፋሲካ ፆም ጊዜ ጦርነት እየቀሰቀሰ ክርስቲያኖችን እየወሰደ በባርነት እየሸጣቸው ስለነበረ ከብቶችም ይዘርፍ ስለነበረ ንጉሥ ናኦድ ጦርነት ገጠማቸው በሐሰት የመሸሸ የጦርነት ስልት በመጠቀም ከ0 የሐረር ኤሚር ወታደሮቹን ፈጃቸው፡፡ የማሕፉድ መሸነፍ: የእስላም ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ መንፈስ አቀዘቀዘው የአዳል ሱልጣንም ከንጉሥ ናኦድ ጋራ ሰላም ስለፈጠረ ለብዙ ዓመታት በምሥራቅ በኩል ሰላም ሰፍኖ ነበር፡፡

## 8. አፄ ልብነ ድንግል[1]

ንጉሥ ናኦድ ሲሞት በ1508 ዓ.ም. ልብነ ድንግል ብቸኛ ልጁ ሲነግሥ ሀገሪቱ ሰላም አግኝታ ነበር፡፡ በፖለቲካ በኩልም ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት በመፍጠር መልካም እርምጃ የታየበት ወቅት ነበር፡፡ ልብነድንግል ልጅ ስለሆነ የመንግሥቱ አመራር በእናቱ በንግሥት እሌኒና በታዋቂው የነበረው ሰው ወሰን ሰገድ ይመራ ነበር፣ ተቃውሞም አልነበረውም፡፡ በልብነድንግል ዘመነ መንግሥት 60 የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ይኖሩ ነበር፡፡ ንግሥት እሌኒ በመንግሥት ሞግዚትነት በነበራት ተደማጭነት የውጭ ሀገር ሰዎችም ምክር በመቀበል ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት ሰማጠናከር ትጥር ነበር፡፡ የክርስቲያን መንግሥት በእስላሞች ላይ በየጊዜው እንዳይወረር ያለው አማራጭ የባሕር በሮች ከእስላም መንግሥታት እንዳይገናኙ ማድረግ ነበር፡፡ ይኸንኑም ማድረግ የምትችለው እንደ ፖርቱጋል ጠንካራ የጦር መርከቦች ያላት መንግሥት መሆን ይገነዘባል፡፡ የፖርቱጋል መልእክተኛ ፔድሮ ዲ ኳቪልሃም ይኸንን ሐሳብ በመደገፍ የባሕር ወደብ ከተሞች ለፖርቱጋል ካልተሰጡ እርዳታ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ሐሳብ አቅርቦ ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ሐሳብ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለማቅረብ ማቴዎስ የተባለው አንድ አርመናዊ መልእክተኛ ለንግሥት እሌኒ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ወደ ፖርቱጋል ለመላክ ተወሰነ፡፡ ዘመኑ 1510 ዓ.ም. ነበረ፡፡ የልብነ ድንግል ሞግዚትነት ዘመንም 2ኛ ዓመት ነበረ፡፡ ማቴዎስ በመጀመሪያ የሄደው ወደ ሕንድ ነበረ፡፡ ከዚያም በመርከብ ተሳፍሮ ከ3 ዓመት በኋላ በ1513 ዓ.ም.

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 43



ሊዝቦን ገባ፡፡ ማቴዎስ መካና መዲናን አቋርጦ ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት የሚል እቅድ ለፖርቱጋል ንጉሥ ሐሳብ አቅርቦ ነበረ፡፡ የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል በታላቅ ክብር ነበረ የተቀበለው፡፡ የሮማ ጳጳስም ሊዮን 10ኛ መልእክተኛው ማቴዎስን ተቀብለው አነጋግረውታል፡፡ 3 ቄሶችም ከፖርቱጋል መልእክተኞች ጋራ ተቀላቅለው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዙ፡፡ ልብነ ድንግል በ1516 ዓ.ም. ከሞግዚትነት ወጥቶ ሰልጣን እንደያዘ የፖርቱጋል መልእክተኞች አፕሪል 7/1520 ዓ.ም. ምፅዋ ደረሱ፡፡ በመጀመሪያ የደብረ ቢዘን ቄሶች ምፅዋ ድረስ ሄደው ተገናኟቸው፡፡ ቀጥሎም ባሕር ነጋሽ ዶሪ ከአጼ ናኦድ እናት ሞጋሳ ወንድም ምፅዋ ሄደው ተቀበሏቸው፡፡ የክረምት ዝናም በመፍራት መልእክተኞቹ ደብረ ቢዛን ሄደው ተቀመጡ፡፡ እዚያው እንዳሉ ማቴዎስ ታሞ ሞተ፡፡ የሚተላለፍ በሽታ እንዳይሆን ፈርተው መልእክተኞቹ ወደ ድባሩዋ ሄዱ፡፡ ኦክቶበር 1520 ዓ.ም. ፖርቱጋሎቹ ደብረሊባኖስ ሸዋ ደርሰው ከንጉሡ ጋራ ተገናኙ፡፡ ፖርቱጋሎቹ ውድ ስጦታ ለንጉሡ አበረከቱ፣ ንጉሡ ግን በስጦታቸው አልተደሰቱም ነበር፡፡ ንጉሡ ይጓጓ የነበረው እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች የሚቀርብላቸው ዘመን ያፈራቸው የጦር መሣሪያዎች ነበረ፡፡ የንጉሡ የተዘፈዘ አቀባበል ፖርቱጋሎችን እያስቀየማቸው ነበር፡፡ ንጉሡ ከፖርቱጋሎች የሚፈልገው ሱዋኪም ምፅዋና ዘይላ በፖርቱጋል እንዲያዙ ብቻ ነበረ፡፡

በሌላ በኩልም ፖርቱጋል ኢትዮጵያን ወረራ ትያዛለች የሚል ፍራቻ ነበረ፡፡ ንግሥት እሌኒ ከአውሮጳውያን ጋራ መቀራረብ ትጥር የነበረችው ከአስተዳደሩ ተወግዳ በዕድሜም ገፍታ ስለነበረ ጎጃም ተሰሚነት አጥታ ትኖር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ አፋጣኝ ቅርብ ግንኙነት ከፖርቱጋል ጋራ ለመፍጠር ከማንኛውም ከእስላሞች የሚደርስባት አደጋ የሚያድናት ውል ለማድረግ ዕድል አመለጣት፡፡ መልእክተኞቹ ቁምነገር ሳይሰሩ በኢትዮጵያ 6 ዓመት ተቀምጠው ኤፕሪል 28/1526 ዓ.ም. ከምፅዋ ወደ ሀገራቸው ተነሱ፡፡ ጆቫኒ ቤርሙደስ ሐኪም በኢትዮጵያ እንዲቀር ተደረገ፡፡ እስላሞች ከባድ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀሙበት ጊዜ ተቃርቦ እንደነበረ ማንም ሰው አልተረዳውም ነበረ፡፡

አጼ ልብነድንግል በእስላሞች ላይ ባገኛቸው መጠነኛ ድሎች ተዝናንቶ ከመጠን በላይ የራሱ ኃይል ስለገመተ የንግሥት እሌኒ የበሰለ የውጪ ፖለቲካ መመሪያ ችላ በማለቱ ኢትዮጵያ ወደ ጥፋት አፋፍ ደረሰች፡፡ በኤሚር ማሕፉዝ ጊዜ የሚመሩ አዳሎች በአጼ ልብነድንግል የደረሰባቸው ሽንፈት ለመበቀል በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊያደርስባት በዘይላ በኩል አደጋ ይሰነዝርባት ነበር፡፡ ከመካ ከሌሎች አዳሎችም የጅሀድ ጦርነት ቅስቀሳ ይደረግባቸው ነበረ፡፡ የጦር መሣሪያዎችና ተዋጊዎች ለእስላሞች ይላክላቸው ነበረ፣ አዳሎችም ወጣት ሴትና ወንድ ባሮች በማድረግ ወደ ገበያ ወስደው በመሸጥ የጦር መሣሪያ ይገዙ ነበር፡፡ ለማሕፉዝ ክብር አንድ የጦር አርማ ልከው ነበር፤ አዳሎች ወደ ፋጢጋር በማምራት ወረራ ፈጸሙ፡፡ አጼ ልብነድንግል በአጼ ናኦድ የጦርነት ዘዴ በመጠቀም ከበባ በማዘጋጀት አዳሎች ወደ ፊት እንዳይጠጉ ካደረጋቸው በኋላ ማምለጫ መንገድ በመዝጋት ፈጃቸው፡፡ ማሕፉዝ ማምለጫ ሲያጣ ከአንድ ገብረ እንድሪያስ ከተባለው ቄስ ጋራ በጎራዴ ትግል ገጥሞ ቄሱ የማሕፉዙን አንገት ቆርጦ ለልብነ ድንግል አበረከተ፡፡ በዚሁ ጦርነት ብቻ 12,000 አዳሎች ሞተዋል ይባላል፡፡ ይህ የመጨረሻው የክርስቲያኖች ድል ነበረ፡፡ አጼ ልብነድንግል ዘመቻውን በመቀጠል የአዳል ሀገርን ወረው ወንድ ሴት ሳይለይ በመግደል ባሮችን አደረጋቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የእስላም ኃይሎች ዳግም ተመልሰው ለኢትዮጵያ

የሚያሰጋት ጠላት አይሆኑም ተብሎ ተገምቶ ነበረ። ድሉም በመላው ኢትዮጵያ ተከብሯል። እንደተባለውም በሚቀጥሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የብልፅግና የሰላም ዘመናት ነበሩ። አሕመድ ሼል ኢብራሂም ግራኝ በዓረቦችና በቱርኮች እየተረዳ ኢትዮጵያን እስላማዊት ለማድረግ በነበረው ፍላጎት በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተደራጅቶ በከፈተው ጦርነት ሳይቋረጥ በየሜካውና በየተራራው ለ20 ዓመታት እየተደበቀ ለሃይማኖቱ በመዋደቅ ኢትዮጵያን ከሞት አፋፍ ያዳኗት እጼ ልብነ ድንግል ነው። በአንፃሩ በዘይላ አሚር ማሕፉዝ በፉጢጋር (ናዝሬትና ሞጆ አካባቢ) ያገኘው ከፍተኛ ድል ተዝናንቶ በቸልተኝነት ኢትዮጵያ ለሞት አፋፍ የዳረጋት እጼ ልብነድንግል ነው።

ግራኝ የሚመለምላቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ ከሶማሌ ሲሆኑ የሚመጡለትም ለዝርፊያ ብቻ ነበረ። ዘርፈው ሃብት ሲያገኙ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ነበረ ፍላጎታቸው። ግራኝ ጥለውት እንዳይመለሱ ብዙ ትግል ማድረግ ነበረበት። በአጼ ልብነድንግል ሽንፈት ከደረሰባቸው ጀምሮ የአዳል ኤሚሮችና ሱልጣኖች እርስ በእርስ እየተጣሉ ከባድ ውድቀት ደርሶባቸው ነበር። ግራኝ ስልጣን እንዳይዝም ኃይለኛ ተቃውሞ አጋጥሞት ነበር። ግራኝ በቀላሉ ሊሰባሰብ የሚችል ጠንካራ የሰው ኃይል አልነበረውም። አጼ ልብነድንግል እንደ አምደጽዮንና ዘርአያዕቆብ ሳይቀደም ቀድሞ በማጥቃት የጦር ስልት በመጠቀም ጠላቶቹን ቢከታተል የሚወዳደረው ኃይል ሊፈጠር አይችልም ነበረ። ይኸንን ባለማድረጉ ግን ግራኝ እስኪጠነክር ድረስ ዝም በማለቱ በ1525 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች በዳዋሮ፣ (ጩርጩር) ሽንፈት ገጠማቸው። እንደገና በ1527 ዓ.ም. ክርስቲያኖች ስለተሸነፉ የቤተመንግሥት ልጆች የሚገኙባቸው 400 መቶ ልጆች ለባርነት ተወሰዱ። ግማሾቹ ለየመን አሚር ሱልጣን በባርነት ገፀበረከት ተሰጡ። ብዛት ያለው መሣሪያ ፈረሶች ድንኳኖች ተማረኩ። ግራኝ በፉጢጋር በኩል ወደ ተጉለት ድንገተኛ ወረራ አድርጎ ንጉሥን ለመያዝ አቅዶ ነበር። ወታደሮቹ ስለተቃወሙት እያለቀሰ ተመለሰ። ወታደሮቹን ለማሰልጠን ብዙ እንደሚቀረው ተረዳ። በ1528 ዓ.ም. ግራኝ ወደ ይፋት ዘመቻ አደረገ፣ ብዛት ያላቸው እስረኞች ተማረኩ፣ ከነሱ ውስጥም የቤተመንግሥት ሰለልት ነበረች። እሷ ግን 1775 ግራም የሚመዝን ወርቅ ሰጥታ ተለቀቀች፣ በአንጾኪያ የነበረ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ፣ በውስጡ የነበሩ ብዛት ያላቸው ወርቅም ግራኝና ተከታዮቹ ተካፈሉት። በ1529 ዓ.ም. ሽንብራ ኩሬ በተባለው ቦታ ማርች 11 ቀን ለአንድ ቀን ሙሉ በንጉሡ የሚመራው የክርስቲያን ሠራዊትና በግራኝ የሚመራው የእስላም ሠራዊት መካከል ጦርነት ተካሄደ በቀኑ መጨረሻ የክርስቲያን ሠራዊት 12,000 ሰው ሞቱበት፣ ንጉሡ ሸሽቶ ወደ ኋላ ተመለሰ። የእስላም ሠራዊትም ብዙ ሰው ሞቶበታል። ከሞቱት ሹማምንቶች መካከል የትግራዩ ሩቤል፣ ወንድሙ ዑቅባ ሚካኤል በግራኝ እጅ የተገደለ፣ የሸሬ ሹም የጸለምቲ ሹምና የዐጋሜ ሹም ይገኙባቸው ነበረ። ከተማረኩም መካከል የንጉሡ ሚስት ወንድም ተክለመድህን ነበረ። እሱ ግን 50 አውንስ ወይንም 18 ኪሎግራም ወርቅ ከፍሎ ተለቀቀ። ግራኝ ብዙ ወርቅ ስለነበረ በዘረፈው ወርቅ 7 መድፎችን ከነ ተኳሾች ዓረቦች ከዘይላ ገዛ። ፈረሶችና ሌሎች ተዋጊ ዓረቦችም ነበሩት። ግራኝ ለክርስቲያኖች እንግዳ የሆኑ መሣሪያዎችን በመጠቀም በ1531ዓ.ም. ከክርስቲያኖች ጋራ ይፋት ውስጥ ጦርነት ገጠመ፣ ድልም ተጎናፀፈ። እንደገና ተሰርቶ የነበረ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ። አጼ ልብነድንግል ተስፋ ሳይቆርጥ እስላሙ የተባለው የጦሩ አዛዥ ወደ ዳውሮ



እንዲሄድ አዘዘው። በባለታሪክ ተክለኢየሱስ የአንጎት (ወሎ) አገረ ገዥ የሚመራ ጦርም ለማጠናከሪያ ወደ ዳውሮ ተላከ። ነገር ግን ሁለት ከክርስቲያን የከዱ ባለስልጣኖች የንጉሡ እቅድ ለግራኝ ነገሩት፣ በዚሁ መሠረት ሁለቱ የክርስቲያን ሠራዊት ሳይቀላቀሉ ግራኝ ገጠማቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ እልቂት ደረሰባት፣ አብዛኛው ትግሬዎች የሆኑ 130 ሹሞች በጦር ሜዳ ተገደሉባት ከነሱ ውስጥም የሽሬ፣ የጸለምት፣ የሐማሴን፣ የቤጌምድር ሀገረ ገዦዎች ይገኙባቸዋል። ከጦርነቱ በኋላ ግራኝ ለንጉሡ እጁን እንዲሰጥ ላከበት፣ የንጉሡ መልስ ግን በእጁ ይገኙ የነበሩ እስላሞች የጦር እስረኞች በመግደል ነበረ፣ ጦርነቱም በጭካኔ ቀጠለ። የግራኝ ሠራዊት ሸዋን ወሮ ከዳር እስከዳር ተቆጣጠረ፣ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ አውራጃዎችና ክፍለአተ ሀገሮች ለግራኝ እጃቸውን ሰጡ፣ ሃይማኖታቸውንም ቀየሩ። ብዙ ሐብት ተዘረፈ ከነሱ ውስጥም አስደናቂ የነበረው ሽፋኑ በወርቅ የነበረ በአንድ በይፋት ቤተክርስቲያን የተገኘው መጸሐፍ ቅዱስ ነበረ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ክብደቱ ሁለት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ለማንሳት የሚያቅታቸው ነበረ። ጦርነቱ ከሸዋ ወደ አማራ ተዛውሮ ቀጠለ ከደብረብርሃን ወደ ሰሜን በሚያመራበት ጊዜ ይማም አግረ መንገዱ አንድ ድንቅ ቤተክርስቲያን አጋጠመው፤ ቤተክርስቲያኑ በወርቅ ያጌጠ ነበረ። የማታ ብርሃን ጨረር ወደ ቤተክርስቲያኑ በሚገባበት ጊዜ ወርቁ እንደ መብራት ያንፀባርቅ ነበር። ቤተክርስቲያኑን ለመገንባት 25 ዓመት ነበር የፈጀው። ከወርቅ ሌላ የቤተክርስቲያኑ ግድግዳ በሌላ ውድ ጌጣጌጥ የተዋበ ነበረ። ይማም እሁንም አወደመው ቤተክርስቲያኖችን እንዲዘርፉና እንዲያቃጥሉ ለየእንዳንዱ የግራኝ ሹማምንት ድርሻቸው ተከፋፍሎ ተሰጣቸው። ለግራኝ መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ደረሰው። በቤተክርስቲያኑ የተገኘው የወርቅና የጌጣጌጥ ብዛት ከተጠበቀው በላይ ነበረ። ጣራው የውስጥ ግድግዳው ሁሉ በወርቅ የተሰሩ ነበሩ። አንድ ሺህ ወታደር ወርቁን ለመንቀል ለብዙ ሰዓቶች ተሰማርተው ነበረ፣ አስተርአዮ ማሪያም በተባለው ቤተክርስቲያን በታቦቱና በሌላ መንፈሳዊ ቁሳቁሶች የነበረ ወርቅ 1000 አውንስ ማለት 35 ኪሎግራም የሚመዝን ነበረ። በበእደማርያም የተሰራ የደብረ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን የአንድ ሰው ቁመት ያለው ቅስት አድናቆት ያተረፈ ተዘርፏል። ዋናው የንጉሡ ንብረት ፍሰጋ ሌላ የግራኝ ጦር ወደ ወሰጋ ተወስዶ የነበረውን ወርቅና ሌላ ጌጣጌጥ እንዲሁም አልባሳት ከተደበቀበት ተገኝቶ በ500 ግመሎች ተጭኖ ተወስዷል። የይማም ጦር ወደ አንጎት (ወሎ)፣ ለማምራት ሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ደረሰ። ከቤተክርስቲያኑ ወርቅ ለመዝረፍ 150 ሰዎች የመጫን አቅም ያላቸው ሶስት ትልቅ ጀልባዎች ወርቁን ለመውሰድ ሦስት ዙር ወሰደባቸው። በደብረ እግዚአብሔር በ1342 ዓም በሰይፈ ዐረድ የተሰራ ቤተክርስቲያን የተገኘው ወርቅ ክብደቱ አንድ ሚሊዮን አውንስ ነበረ ማለት 35.000 ኪሎግራም ነበረ።

ግራኝ ወደ ደቡብ ክፍል ሀገር ሀዲያ፣ ከንባታ፣ ወላሞ፣ እሞ፣ ዝዋይ፣ አባያታ፣ ጊቤ፣ እናሪያ፣ ጋፋት ዘመቻውን በመቀጠል ዛላ በተባለው ቦታ በ1532 ዓ.ም. ባሸነፈ ጊዜ 3000 ክርስቲያኖች በጦር ሜዳ ሞቷል። የባሌ ሕዝብ በሙሉ የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበል ተገዶ የተቃወሙት ሁሉ ተገደሉ። ግራኝ ትግራይን ለመያዝ ያደረገው ጦርነት ከባድ ተቃውሞ ነበረ ያጋጠመው። በጦርነቱ 10,350 ሰዎች ተገድለዋል።

ግራኝ ሽሬ ሲደርስ በአባ ሳሙኤል ቤተክርስቲያን ያገኛቸው 500 ቀሳውስት ተገደሉ። አጼ ልብነድንግል በቤጌምድር ተራራዎች ተደብቆ

ስለነበረ ግራኝ ተከታትሎ በድንገት በእጁ ለማስገባት ያደረገው ሙከራ ከሸፈበት ንጉሡ ሸሽቶ ማምለጥ ችሏል፡፡ ግራኝ ወደ ኤርትራ በማምራት ሀገረ ገዢው ተሰፋ ልዑል አስወግዶ ቴዎድሮስ የሚባል ነበረ የሾመው፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ በተስፋ ልዑል መሪነት የደፈጣ ውጊያ ሰማድረግ የግራኝ ታማኝ የነበረ ቪዚር አዶሊ የሀገሩ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሹሞ የነበረ ሳይቀር ገድሎ እንገቱን ቆርጦ ወደ አጼ ልብነ ድንግል ለመላክ ከባድ ፍልሚያ አካሄዷል፡፡ ግራኝ በበጌምድር ንጉሥን ማሳደድ ትቶ አፍራ የተባለው ባሕር ነጋሽ ሾመ፡፡ ሠራዊ ግብር እንዲከፍል ተገደደ የሀገሩ አስተዳደርም በቴዎድሮስ ምትክ ወንድሙ ተሾመ፡፡ የሁሉም የበላይ አዛዥ በቪዚር አዶሊ ምትክ ቪዚር አባስ ሾመ፡፡ የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት የአክሱም ሳይቀር ተቃጠሉ፡፡ ተላላፊ በሽታም በሀገሩ ገብቶ ብዙ ሰው ፈጀ ከሞቱትም መካከል የግራኝ ልጅ ከጦር ሜዳ የተወሰደ ነበረ፡፡ ግን ሰላም እሰፍኖ ወደ ደምቢያ ሲመለስ ወዲያውኑ በሰራዌና በትግራይ የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ፡፡ ግራኝ ሰሜን እንዲይዝ ፈላሾች መንገድ ከፍተውለት ነበረ፡፡ የመጨረሻ ያልተያዘ ክፍለ ሀገር ወደ ጎጃም በማምራት ግራኝ ንግሥት እሌኒ ብዙ ንብረታቸው ያፈሰሱባቸው ቤተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ በነሱ ውስጥም መርጡ ለማርያም የተባለ ስመ ጥሩ ነበረ፡፡ በዚሁ ዓይነት መላው ኢትዮጵያ በግራኝ ቁጥጥር ውላ ነበረ፡፡ የቀረው ንጉሡን አሳዶ ማያዝ ብቻ ነበር፡፡ ለልብነ ድንግል የተሰፋ ጭላንጭል የነበረው የፖርቱጋል መልእክተኞች ውጤት ነበረ፡፡ ነገር ግን አጼ ልብነድንግል ከዚህ በፊት ያደረገላቸው አቀባበል የቀዘቀዘ ስለነበር እርዳታ የማግኘት ተስፋ አነስተኛ ነበረ፡፡ አስቸኳይ እርዳታ ከክርስቲያን ኤውሮጳ ለማግኘት የነበረው አማራጭ አጼ ልብነድንግልና ቤተመንግሥቱ በሙሉ የካቶሊክ ሃይማኖት መቀበል ነበረ፡፡

ነገር ግን ይኸም አማራጭ እርምጃ የሕዝቡ ተቃውሞ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተፈራ ሌላ ዘዴ ተቀየሰ፡፡ ይኸውም በዕድሜ የገፋ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ማርቆስ ለአንድ ካቶሊካዊ የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተው ስልጣናቸውን እንዲያስረክቡ ነበር፡፡ ይህ ዘዴ ጥሩ መስሎ ቢታይም ሕጋዊነት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም አቡኑም ለአንድ ካቶሊክ ጵጵስና መስጠት መብት አልነበረውም፣ ለጵጵስና ተሿሚ ግለሰብም መቀበል አይችልም ስለነበረ ነው፡፡ ለጵጵስና ማዕረግ የተመረጠ ሰው በርሙደስ ነበረ፡፡ ቤርሙደስ እንደ ተሾመ ሁኔታውን ለማስረዳት ወደ ሮም መሄድ ነበረበት፡፡ በ1536 ዓም ከአንድ ዓመት ገደማ በኋላ ከእስላሞች ብዙ አደጋዎች አምልጦ በርሙደስ ለሮም ሊቃነጳጳሳት ከአጼ ልብነ ድንግል የተላከ መልእክት ይዞ ሮም ገባ፡፡ በደብዳቤው ላይ አጼ ልብነ ድንግል የካቶሊክ ሃይማኖት እንደሚከተልና ከሮማ የተላከ አቡን በስተቀር ሌላ አቡን እንደማይቀበል ገልጾ ነበር፡፡ በርሙደስ ወደ ፖርቱጋል ከአጼ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ የተላከ መልእክት አቀረበ፡፡ ሁለቱ መንግሥታት የሮማና የፖርቱጋል የራሳቸው የውስጥ ችግር ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ችላ ብለውት ነበር፡፡ ሆኖም በርሙደስ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ሕዝብ ሁኔታ በሚገባ በማስረዳቱ የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል 5ኛ ከሕንድ 450 የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲላኩ አዘዘ፡፡ በርሙደስ ትዕዛዙን ይዞ ወደ ሕንድና ወደ ኢትዮጵያ የመልስ ጉዞ ለመጀመር በሚዘጋጅበት ጊዜ ለ3 ዓመት እስከ 1539 ዓ.ም. ታሞ ሀገሩ ተቀመጠ፡፡ የፖርቱጋል ወታደሮች ምፅዋ ሲወርዱ የቻሉት በ1541 ዓ.ም. ነበረ፡፡ በኢትዮጵያም ጦርነቱ እየተካሄደ ነበረ፡፡ በ1539 ዓ.ም. ግራኝ ለልብነ ድንግል በላከው ደብዳቤ በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የአጼ ልብነድንግል ልጅ ለማግባት ንጉሡ እንዲፈቅድ ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ



እስላም እንድትሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ አጼ ልብነ ድንግል በጦርነቱ ከተፋበት ሊያመልጠው እንደማይችል እና ቅጣቱ አስከፊ እንደሚሆን አስጠንቀቀው፡፡ አጼ ልብነ ድንግል ግን የሰላም ጥሪ ሳይቀበል ስለቀረ ጦርነቱ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ሳይያዝ ቀርቶ የነበረው የነገሥታት ዘር ማጎሪያ የተደበቀ ወርቅ ይገኛል ስለተባለ የእስላም ተዋጊዎች ሳይነቃባቸው ለመግረክ ስለቻሉ ከዘረፉት በኋላ አቃጠሉት፡፡ የተገኘው የወርቅ ብዛት የተነሳ "ወርቅ እንደ ድንጋይ ሆኖ ነበር ልብሶችም እንደ ቅጠል ሆነው ነበረ" በማለት የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበዋል፡፡

አጼ ልብነድንግል በ45 ዓመት ዕድሜው ሲሞት የደረሱ ልጆች ነበሩት፡፡ ቪክቶር የተባለው አልጋወራሽ ልጁ ወደ ዳዋሮ የሚያዋስነው ሄዶ የእስላም ሠራዊት ለሁለት ከፍሎ የመዋጋት ዓላማ ነበረው ሳይሳካለት ስለቀረ ግን በውጊያ ተገደለ፡፡ 2ኛ የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስ ከአባቱ ጋራ ሆኖ በዋግ አካባቢ ሲዋጋ በእስላሞች ስለተያዘ ባሪያ ሆኖ ለዘቢብ ፓሻ ተሸጠ፡፡ አጼ ልብነ ድንግል በደብረዳሞ አስተማማኝ መደበቂያ በመፈለግ ወደ ደብረ ዳሞ ሄደ፡፡ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ከግራኝ ወታደሮች አደጋ እንዳይደርስበት በማሰብ የገዳሙ መውጫና መግቢያ ዘብ በማቆም ይጠብቅ ነበር፡፡ ጥቂት ወራት ቆይቶ ሴፕቴምበር 5/1540 ዓ.ም. አጼ ልብነድንግል በቤተሰቦቹና በታማኞቹ ተከቦ በሰላም ዐረፈ፡፡

## 9. አጼ ገላውዲዎስ

አጼ ገላውዴዎስ ከአባቱ ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱን በጠንካራ መንፈስና በተሻለ ዕድል ቀጠለ፡፡ የአጼ ገላውዲዎስ እናት ንግሥት ሰብለ ወንጌል በሰሜን የሚኖሩ ሕዝቦችን በማነሳሳት ከአዲሱ ንጉሥ ጋራ እንዲቆሙ ያደረገችው ጥረት ስለተሳካላት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈላሾች ለኢትዮጵዊ አዲሱ ንጉሥ ለገላውዴዎስ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል ጸለምትም የእነሱ ምሳሌ ተከትለው ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ግራኝ ምርጥ አዛዦች በማሰማራት ሰሜን ለመያዝ ሊወጋቸው መጥቶ አልተሳካለትም፡፡ አጼ ገላውዴዎስ በሰሜን ተራራዎች ሆኖ ከጠላት ጋራ እየተፋለመ በነበረ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በደብረዳሞ ገዳም ሆና ታማኞችን እየሰበሰበች የጦር መሣሪያ ትሰጥ ነበረ፡ በዚሁ ጊዜ ፖርቱጋሎች ምፅዋ መድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ሕዝቡ በደስታ ፈነደቀ፡፡ ትግራይ ሁሉ ለንጉሡ ሙሉ ድጋፍ ሰጠ፡፡ ፖርቱጋሎች በቤርሙደዝ እየተመሩ ጉራዕ ገቡ፡፡ ከዚያም ድባርዋ ድረስ መጥተው ሰብለ ወንጌል ትጠብቃቸው ስለነበር ተገናኙ፡፡ በታኅሣሥ ወር ፖርቱጋሎች ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋራ በመሆን ምግብ እያቀረበችላቸው ከድባርዋ ተነሱ፡፡ አፕሪል 4/1542 ዓ.ም. በፖርቱጋሎችና በግራኝ የሚመራ የእስላም ሠራዊት እናሳ በተባለው ቦታ በእክለጉዛይ ጦርነት ተካሄደ የፖርቱጋሎች መድፎች በእስላሞች ላይ ሽብር ፈጥረው ነበር፡፡

ግራኝ ታፋው ላይ ቆሰለ፣ ፈረሱ ተገደለ፡፡ ግራኝ እስከ ዘቡል ተራራዎች ሸሽቶ በመሄድ ጦሩን ለማደራጀት ሞከረ፡፡ ከዓረብ ሀገር ሁለት ሺህ ዓረቦች፣ ቱርኮችና አልባናውያን ቅጥር ወታደሮች በዘይላ በኩል አስመጣ፡፡ የክርስቲያን ሠራዊት ግራኝን እያሳደደ እስከ አሻንጌ ሐይቅ ድረስ ገሠገሠ፡፡ ኦገስት በ1542 ዓ.ም. ግራኝ ከባድ ጥቃት አካሄዶ የፖርቱጋሎች ጦር አዛዥ ዶን ክሪስቶፎር ዳ ጋማን አቁስለውትና በአሰቃቂ ሁኔታ ገደሉት፡፡ የፖርቱጋል ጦርና ንግሥት ሰብለ ወንጌል አስቀድሞ ለክፉ ጊዜ ጦር ሰፈርና ጣቢያ አድርገውት የነበረ ወደ ሰሜን ሄዱ፡፡ ንጉሡም የእስላም ጦር ጥሶ

ከፖርቱጋሎች ጋራ ተቀላቀሰ። ንጉሡ ለፖርቱጋሎች ወረታውን በመመለስ በማሰብ ለእየእንዳንዱ ፖርቱጋል ወታደር 1000 አውንስ ወርቅ ሰጣቸው (135 ኪሎግራም)። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ በእስላሞት ከተዘረፉ ሃብቷ ሌላ ብዙ የቀራት ወርቅ እንደነበረ ሲሆን ይኸውም ምን ያህል የበለፀገችና ሃብታም ሀገር እንደነበረች የሚያመለክት ነበር።

የክርስቲያን ሠራዊት ከሰሜን ወደ ደቡብ ጎንደር እስላሞችን እያሳደደ ተጓዘ። ግራኝ ከነበረበት ከዘቡል ተራራዎች ዋና ከተማው ብሎ እዘዛቸው መርጠው ነበረ። እሱም ወዲያው ስለሞተ አንድ ክልስ ዝርያ ያለው አረቦስ ዲያዝ መረጡ። አጼ ግላውዴዎስ ከፖርቱጋሎች ጋራ በመመካከር ግራኝ ወደ ደንብያ እንደመጣ እንዲገጥሙት ተወሰነ፡ ዲያዝ በመጀመሪያ መሥመር ፖርቱጋሎቹን አሰማራ። እስላሞች እያጠቁ ሲመጡ ግራኝ ወታደሮቹ ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ፊት ለፊት እየመራቸው ስለነበረ በፖርርቱጋል መድፎች የእሳት እራት ሆነው ቀሩ። አንድ ፖርቱጋላዊ የቀድሞ የፖርቱጋሎች እዛዥ ጆን ኪሪስቶፎር ዳጋማ ጠባቂ የነበረው ፔድሮ ሲዮን የተባለው የጌታውን ገዳይ ለይቶ ስላወቀው በእሱ አነጣጥሮ በመተኮስ ግራኝን አቍሰሉ ጣለው። ግራኝ ግን ወታደሮቹ ተስፋ እንዳይቆርጡ በማሰብ በአንድ ዛፍ ስር ለመደበቅ ሞክሮ ነበር። ያቆሰለው ወታደር ግን ግራኝ የሄደበትን ቦታ ተከታትሉ ስላወቀ ሰሞት ሲያጣጥር ስላገኘው ላስረጅነት እንድ ጆሮውን ቆርጦ ወሰደበት፣ቦታውን አሁን ድረስ የግራኝ በር ተብሎ ይጠራል። የእስላም ወታደሮች ተሸንፈው ተበታተኑ።

ጦርነቱ በክርስቲያኖች ድል አድራጊነት ቢፈጸምም የሚቀጥለው ዙር በአጼ ግላውዴዎስና በበርሙደስ ያለው ጉዳይ መፍትሄ ማድረግ የሚኖርበት ነበረ። በርሙደስ በውሉ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡን መሆን አለብኝ ባይ ነበረ። አጼ ግላውዴዎስ ግን በቤተክህንነት ተጽእኖ በርሙደስ ወደ ጎን በመተው እንደ ቀድሞ ከእስክንድሪያ አቡን እንዲላክለት ጠየቀ። በዚሁ ጊዜ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከፍተኛ ጠብ ተፈጥሮ በርሙደስ የፖርቱጋል ወታደሮች ድጋፋቸውን እንዲሰጡት ፈልጎ ነበረ። ግማሾቹ የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ሕንድ ተመልሰው፣ ነበረ በኢትዮጵያ ቀርተው ከነበሩት መሐል ግን አብዛኛዎቹ ንጉሡን የሚደግፉ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ አዛዣቸው ዲያዝ በግልፅ ከንጉሡ ጋራ ከመቆሙም በላይ እንደገና በኦርቶዶክስ ክርስትና ተነስቶ ስሙ ማርቆስ ተብሏል። ሌሎችም የእሱን ምሳሌ ተከትሏል። በንጉሡ ሕይወት አደጋ እንዳይጥሉ በማለት በርመደስ ሌሎችም ፖርቱጋሎች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ ተደርጓል። በርሙደስ በመጀመሪያ ወደ ደቡብ ጋፋት ተልኮ ቀጥሎም ሌሎች ፖርቱጋሎች ወደ ነበረበት ወደ ዳውሮ ተወስዶ ከዚያም ወደ ድባርዋና ምፅዋ ሄደ። ከዚያም በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ አስታዋሽ አጥቶ ቀሪው ዕድሜው እላ ልፋል። ሌላው ከጦርነቱ በኋላ የተደቀነው ችግር የንጉሡ ነገሥቱ የማት እንድነት ማስከበር ነበር፣ ይሄም የተከናወነው በ1544 ዓ.ም. ነበር። ቪዚር አባስ የአቡን ልጅ የኢማም ወንድም ዳዋሮ፣ የዛሬዋ ናዝሬት መተሀራ አካባቢ እንደዚሁም ባለ ከአርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ነፃ መንግሥት እቋቁሞ መሪ ሆኖ ነበረ። የኢትዮጵያን ሠራዊት ለመቋቋም የሚችል መስሎት ነበር። አጼ ግላውዴዎስ በዋዲ አውራጃ በኩል ወደ ፋጢጋር እልፎ ገጠመው። በአንድ ቀን ጦርነት በኦክቶበር 1544 ዓ.ም. እስላሞች ተሸነፈ። በ1545 ዓ.ም. መጀመሪያው ላይ አባስ ተገደለ አጼ ግላውዴዎስ ወደ ዳውሮ ገባ፣ ቤተመንግሥት ሠራ፣ የፈረሱ ቤተክርስቲያኖችም ታነፁ። ባሌም



እንደገና ተያዘ፡ ሆኖም ባሌ በዚሁ ጊዜ ኦሮሞ የሚያደርገው መስፋፋት ዋና መነሻ ግብያ ሆና ስለነበረች ለብዙ ጊዜ ተይዞ አልቆየም። በ1547 ዓ.ም. ሐዲያ እንደ ቀድሞ ወደ ግዛቱ ተቀላቀለች። በ1548 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ዳሞት ከአባይ በስተደቡብ ዘምቶ ክርስትና ያልተቀበሉ ሕዝቦች ስለነበሩ ወለኑ እስከ ጊቤና ኦሞ ወንዞች ደረሰ። የሐረር መንግሥት በ1548 እና በ1550 ሁለት ጊዜ ከአጼ ግላውዴዎስ ጋር ጦርነት ገጥሞ ሁለት ጊዜ ተሸነፈች። 1552 ግላውዴዎስ ከንባታን አስገብረዋል፤ ጉመር የሚባል አውራጃ በዛሬዋ ደጋማ ክፍል አርሲ አስገብሯል። በዚሁ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ሰፋቱ ድሮ ወደ ነበረበት ተመልሶ ነበር። ሐረር እንደገና በ1552 ዓ.ም. ሸፍታ ጦርነት እውጃ ፋጢጋርን ወራ ወደ ሸዋ እምርታ ነበር። አጼ ግላውዴዎስ የደብረ ወርቅ ገዳም እያሰራ ይገኝ ስለነበረ፣ 12 ቀን ፈጣን ጉዞ አድርጎ ሐረር ስቅለት /አርብ ቀን/ ጦርነት ገጥሞ ተገደለ። የግራኝ ሚስት አጼ ግላውዴዎስ በመገደሉ የግራኝ መበቀል ሆኖ ሳለተሰማት ደስ አላት፤ የግላውዴዎስ ጭንቅላት ተቆርጦ በሐረር ከተማ መግቢያ ደጃፍ ለሦስት ዓመት ተሰቅሎ ነበር።

አጼ ግላውዴዎስ እንደሞተ ሦስት ቀን በኋላ ታማኞቹ አስክሬኑን ወደማሪያም ቤተክርስቲያን ወስደው ቀበሩት። የአጼ ግላውዴዎስ ጭንቅላት በሐረር ከተማ በር ደጃፍ ተሰቅሎ የነበረው፣ ክርስቲያን ነጋዴዎች ሰርቀው ወስደው በአንድ የይፋት ቤተክርስቲያን በክብር ቀበሩት። አጼ ግላውዴዎስ እንደ ሰማእት ሆኖ ይከብር ነበረ።

## 10. የክርስቲያን መንግሥት አሸናፊነት

ከግራኝ ጦርነት በኋላ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን እንደ ምፅዋ፣ አሰብ ታጁራ፣ ዘይላ የመሳሰሉት የባሕር ጠረፍ ከተሞች መቆጣጠር ባለመቻሉ ደካማ ጐን እንዳለው መስሎ ቢታይም በባሕር የሚመጡበትን አደጋዎች ጠላቶችንም ለመቋቋም ችሎ ነበረ። የክርስቲያን መንግሥት የእስራኤል ዝርያ የሆኑ ሰለሞናዊ ነገሥታት እንደነበረ ሁሉ በምስራቅ ኢትዮጵያ የነበሩ የእስላም መንግሥታትም የነቢዩ መሐመድ ዘመድ የሆኑ በዓረቦችና በቱርኮች የሚደገፉ ወላዝማ በሚባሉ ሱልጣኖች የሚመሩ ነበሩ። በመጀመሪያ በክርስቲያን መንግሥት ላይ የተነሳ ይፋት ነበረ። ይፋት ሲዳከም በአዳል ተተካ። አዳል የሚባለው መንግሥት በግራኝ እምባገነን አገዛዝ ቁጥጥር ስር ሆኖ የክርስቲያን መንግሥት ያልነበረው የጦር መሣሪያ ታጥቆ መላው ኢትዮጵያን የተቆጣጠረ ቢመስለውም የክርስቲያን መንግሥት ለ20 ዓመታት ወረራውን ለመቋቋም በመቻሉ፣ በመጨረሻ በጥቂት የፖርቱጋል ወታደሮች እርዳታ በአሸናፊነት ሊወጣ ችሏል። ከግራኝ መሸነፍ በኋላ ለማቆጥቆጥ የሞከረው የእስላም መንግሥት በሐረር ከተማ የተቋቋመው የግራኝ እና የወላዝማ ዝርያ የነበራቸው የግራኝ ሽንፈት ለመቀበል ፍላጐት ያልነበራቸው ሱልጣኖች ነበር። በረከት በተባለው የሐረር መንግሥት ሱልጣን ልጅና አሊ ጋራድ በተባለው የግራኝ ልጅ የሚመሩ የሐረር ወታደሮች ዳውሮን ወረሩ፡ ወረራው ግን የአውራጃው ክርስቲያን ሀገረ ገዥ የነበረው፣ በራሱ ሌላ እርዳታ ሳይጠይቅ ሊያከሽፈው ችሏል፣ መሪዎቹም ተይዘው ታሰሩ።

የግራኝ ሚስት ከዓረቦች ጋራ በነበራት ትውውቅ በመጠቀም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ውይይት ተደርጎ የእስረኞች ልውውጥ እንዲደረግ ተስማምተው ሚናስ የአፄ ግላውዴዎስ ወንድም በጦር ሜዳ

በግራኝ ተይዞ ወደ የመን ባሪያ ሆኖ ተወስዶ ስለነበር በሱ ለውጥ በረከት አሊ ጋራድ ወደ ሐረር እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ ትንሽ ጊዜ እንደቆዩ የሐረር መንግሥት በ1550 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ለመውረር ኑር በሚባለው ሱልጣን መሪነት ሌላ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ወረራው ይመራ የነበረው የሞጃሂድ ልጅ ነበረ፡፡ ከግራኝ ሞት ብኋላ የሞጃሂድ ቤተሰቦች የተድሞ የግራኝ ተዋጊዎች መሰብሰቢያ ሆነው ነበረ፡፡ እንዲሁም የግራኝ ሚስት ባቲ ድል ወምበራ ከሚደገፉ መካከል ዋና ተዋንያን ነበረች፡፡ የግራኝ ሚስት በአባቷ በኩል ኢትዮጵያን እየወረሩ ያስቸግሩ ከነበሩ አንዱ የነበረው የማሕፉዝ ልጅ ስትሆን የአሁኑ የኑር የሐረር መንግሥት መሪም በእናቱ የግራኝ እህት ልጅ ስለሆነ፣ ሙሉ እምነት ስለነበራት አጎቱን እንዲበቀል አስምላው ስለነበር ዋና ተልእኮዋና ዓላማዋ ሆኖ ነበር፡፡ አሁንም እስላሞች አልቀናቸውም በታዋቂው የኢትዮጵያ ጦር መሪ ፋኒል የሚመራ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኑር ብቻ ሸሽቶ ሲያመልጥ የቀሩት የሐረር ወታደሮች ተደመሰሱ፡፡ አጼ ገላውዴዎስ ለፋኒል ሐረርን ወር እንዲይዝ ትዛዝ ሰጠው፡፡ ማርች 13 ቀን 1550 ዓ.ም. ሐረር በፋኒል ጦር እጅ ወደቀች ነዋሪዎቿም ሸሹ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፋሲል ሞተ፤ አጼ ገላውዴዎስ የተገኘው ድል ለማክበር 5 ወር ሐረር ተቀመጠ፤ ክርስቲያን ባሪያ ሆኖ ተወስዶ የነበሩ ተለቀቁ፤ በአንፃሩም ብዙ እስላሞች ተገደሉ፤ ባሪያ ሆነውም ተወሰዱ፡፡ ሐረር ምንም እንኳን ከባድ ሽንፈት ቢገጥማትም ለ3ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትን ለማጥቃት ሞክራ ነበር፡፡ በኢሚር ኑር ምትክ ክርስቲያን የነበረው ዑትማን የተባለው በሐረር ሥልጣን ይዞ ነበር፡፡ በዚሁ ዘመን ሁለቱ የሐረር እስላሞችና የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በኦሮሞ የጋራ ጠላት ተከበው በችግር ላይ ወድቀው በነበሩ ጊዜ ሐረር ስለ ተዳከመች በሥልጣን ላይ የነበረው የግራኝ ዘመድ ይማም መሐመድ የኦሮሞች ወረራ ወደ ማያሰጋው ወደ አውሳ በ1577 ዓ.ም. ሐረርን ለቆ ለመሄድ የተገደደ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአውሳ ሱልጣን ተመሰረተ፤ የይፋት፤ የአዳል፤ የሐረር መንግሥታት ሀልውናቸው አከተመ፡፡

## 11. የቱርክ ወረራዎች በኢትዮጵያ

ሌላ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የነበረው ምፅዋ የሰፈረው የቱርክ አገዛዝ ነው፡፡ ቱርክ ሱዋኪንና ምፅዋን የያዘው በ1517 ዓ.ም. ነበር፡፡ የቱርክ መንግሥት በወቅቱ በዓለም ቅድመ ኃያል መንግሥት ለመሆን በቅቶ የነበረ ነው፡፡

ዓረቦች በምዕራብ አውሮፓ ገብተው አውሮፓን እስላማዊትና ዓረባዊት ለማድረግ እንደሞከሩ ሁሉ የቱርክ መንግሥትም በደቡብ ምስራቅ አውሮፓ እስከ መሐል ገብቶ አውሮፓን በቁጥጥሩ ለማዋል ተቃርቦ የነበረ መንግሥት ነው፡፡ ቱርኮች ከዓረቦች የበለጠ ዓላማቸው ተሳክቶላቸው በአንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች ሃይማኖት እንዲቀበሉ አድርጓል እንደ ቦስኒያ፣ አልባንያ የመሳሰሉት፡፡ ቱርኮች መሃል አውሮፓ ገብተው የአንድ ትልቅ አውሮፓዊ መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው በስልጣኔና በጥበብ የተራቀቀችው ቪየናን ለመያዝ በተቃረቡበት ጊዜ አውሮፓውያን በሙሉ ተባብረው አስካለቀቋቸው ድረስ አስፈሪ ኃይል ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ ግን ቱርኮች አራት ጊዜ ወረራ አድርገው ተሸንፈው ወጥቷል፡፡ የመጀመሪያ ወረራቸው በምፅዋ በኩል በ1557 ዓ.ም. ነበረ፡፡ በዚሁ ጊዜ ቱርኮች ምፅዋን ተቆጣጥረው ወደ ደጋ ዘልቀው በመግባት በደባርዋ ምሽግ በመስራት ባሕር ነጋሽን በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር አውለው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ገዳም የሆነው



ደብረ ዳሞት በቱርኮች ተይዞ ተዘረፈ፤ የባሕር ነጋሽ ቀላግ ሰሜናዊና ምዕራባዊ ጎሳዎች ቤጃ የተባሉ በፓሻ አከዝዳመር የሚመሩ እስላሞች ከቱርኮች ጋራ ተባብረው ነበረ፡፡ በባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በሚመራ የክርስቲያን ሠራዊት ሲደመሰሱ መሪያቸው ሸሽቶ ቱርኮች ወዳሉበት ወደ ዱባሩዋ ገብቶ ብዙ ሐብት ክርስቲያኖች የደበቁት አለ በማለት ቱርኮችን ሰለ አጓጓቸው ፓሻ ሁዝዳመር 800 ፈረሰኞችና በዛት ያላቸው ወታደሮች አስከትሎ ወደ ቦታው ዘመተ፡፡ ብዙ ከተጓዘ በኋላ የተባለው የሐብት ክምችት አገኘ፤ በመሀሉ ግን የቱርክ ፓሻ ትኩሳት ታሞ በቃሬዛ ተሸክሞት ተመለሰ፤ የዘመቱ ሰዎችና እንስሳት አብዛኛዎቹ ሞቱ፤ ከኢትዮጵያ ጦር በመሐሉ በድባሩዋ ጥቃት ፈፅሞ በመከበብ ቱርኮችን ያለምግብና ውሀ አስቀርቷቸው ነበረ፡፡ ቱርኮች ያገኙትን ሐብት ሌሊት ከድባሩዋ ለመውጣት ሲሞክሩ መሣሪያ በታጠቁ ገበሬዎች ተደመሰሱ፤ ሐብቱንም ማረኩት፤ ድባርዋም ተማረከች፡፡ የቱርክ ወታደሮች ከድባርዋ አምልጠው ወደ ምፅዋ ለመሸሽ ሲሞክሩ በታጠቁ ገበሬዎች ተገደሉ፤ የቱርክ ፓሻ ባዶ እጁ ሰለቀረ ሸሽቶ ሱዋኪም ገባ፡፡ የቱርክ ወረራ ተወግዶ ይዞታው በምፅዋ ተወሰና ቀረ፡፡ሁለተኛ የቱርክ ወረራ በአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት፤ ነበረ በአንደኛ የቱርክ ወረራ በጀግንነት ተዋግቶ ያባረራቸው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ሥልጣኔ ተሻሙኝ በማለት በንጉሡ ላይ ተቀየመ፡፡ አጼ ሚናስ መጀመሪያ ዮሐንስ በተባለው ጦር ላከበት፤ ነገር ግን ይስሐቅ በድንገት አደጋ ጥሎበት አሸነፈው፤ ይስሐቅ ከቱርኮች እርዳታ ለማግኘት ከድባርዋ እስከ ምፅዋ ያለውን መሬት ሰጣቸው፡፡ አጼ ሚናስ ፖርቱጋሎች ከይስሀቅ ጋራ ተስማምተው ይሆናል ብሎ ስለጠረጠራቸው በአንድ ተራራ እንዲቀመጡ አደረጋቸው፡፡ አቡኑ እርሺየዶና ተከታዮቹ አምልጠው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ወደ አለበት ደርሰው ድጋፋቸውን ሰጡት፡፡ በዚህ መሠረት ቱርኮች ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ካቶሊኮችና ሌሎችም የሚናስ ተቃዋሚዎች ግንባር ፈጠሩ፡፡ ፖርቱጋሎች ከሕንድ የጦር መርከቦች እንደሚያስመጡ ለይስሐቅ ተስፋ ሰጡት፤ አጼ ሚናስ ግን ጊዜ አልሰጣቸውም ኤፕሪል 20 1562 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት አሸናፊ ሆነ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አጼ ሚናስ ከዶባ ጎሳዎች ጋራ ጦርነት ባደረገበት ወቅት በትኩሳት ታሞ ሞተ፡፡ ጦሩም ጉዳት ደርሶበት ስለነበረ ቱርኮችን እስከ ባሕር ሳያባርራቸው ተመለሰ፡፡

ሦስተኛ የቱርክ ወረራ በኢትዮጵያ በአጼ መላክ ሰገድ ዘመነ መንግሥት ነበረ፡፡ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ እንደገና 1578 ዓ.ም. ከቱርኮች ጋር ተስማምቶ ለንጉሠ ነገሥቱ አልታዘዝም በማለት የንጉሡ መልእክተኞች ተልከውበት ከቱርኮች ጋራ እንዳይገጥም ቢጠየቅ "ከፓሻው ጋራ እርቅ አድርጌአለሁ፤ በአንድ ምንጣፍ አንድ ላይ በመቀመጥ" የሚል መልስ ሰለሰጠው መላክ ሰገድ ጦሩን ወደ ባሕር ነጋሽ አዘመተ የንጉሡ መምጣት ዜና ሲሰማ ተዋጊዎች ከባሕር ነጋሽ መክዳት ጀመሩ፡፡ በሠራዬ ዐረ ባሕር ነጋሽ ዐመፅ ተካሄደ፤ ይስሐቅና ቱርኮች እንጢጮ ተሰበሰቡ፤ በመጀመሪያ ግጥሚያ ኖቬምበር 13, 1578 ዓ.ም. ቱርኮች የመላክ ሰገድ ሠራዊት እንዲሸሽ አደረጉ፡፡ አራት ቀን በኋላ ቱርኮች 8 መድፎች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ተከሉ፤ በማንፃፀር ብዙ ጉዳት አደረሱ፡፡ በዚሁ ጊዜ መላክ ሰገድ የኦሮሞ ፈረሰኞች አሰማርቶ በቱርኮች ላይ አጠቃ፤ ብዙ ሳይቆይ መድፎቹ ተያዙ፤ የጠላት ይዞታዎችም ተያዙ፡፡ ከዚህ በኋላ ይስሐቅ ተስፋ ሰለቆረጠ እርቅ ጠየቀ፡፡ ንጉሡም ከቱርኮቹ ተዋጊዎቹ ለይቶ አውጥቶ ከክርስትያኖች ጋራ ቱርኮችን እንዲወጉ አድርግ የሚል መልስ ሰጠው፡፡ ይስሐቅ ከቱርኮች ጋራ እርቅ እንዲደረግ የሚል ሐሳብ አቀረበ፡፡ የቅርብ ረዳቶች ሳይቀሩ ከዱት፡፡

በተደረገው ሁለተኛ ግጥሚያ ቱርኮችና ይስሐቅ ሽንፈት ገጠማቸው የኢትዮጵያ ጦር የቱርክ ጦር ሰፈር ተቆጣጥሮ የቱርኮች አርማና መድፎችን ማረከ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደልማዱ ከአካባቢ ገበሬዎች ስንቅ ፍለጋ መሔዱ ሲያውቁ ቱርኮችና ይስሐቅ ከምሽጋቸው ወጥተው መድፋቸውን በንጉሡ ጦር እያተኩሩ መተኮስ ጀመሩ፣ ንጉሡ ግን ጥቃታቸውን አከሸፎ መለሳቸው፡፡ ይስሐቅም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ሆኖ ወደ ፊት እያመራ በማጥቃት ሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ለይቶ ሳያውቀው አድፍጦ ትከሻውን አቆሰለው፡፡ ይስሐቅ ብዙ ደም እየፈሰሰው ወደ መጣበት ተመልሶ ከፈረሱ ወርዶ በመሬት ተጋደመ፡፡ ስንቅ ፍለጋ ሔደው የነበረ የኢትዮጵያ ወታሮች ሲመለሱ የቱርክ ሠራዊትን ከበው ፈጁት፡፡ ይስሐቅ ሞቶ የቱርክ ፓሻ የጠፋን እልቂት ፈረሱ ላይ ወጥቶ ይመለከት ነበረ፡፡ ጀግናው አንድ የኢትዮጵያ ወታደር የናኢል የተባለው ደረቱን በመውጋት ሳላቆሰለው ከፈረሱ ወደቀ፡፡ ያቆሰለው ወታደርም ወደ ወደቀበት ሄዶ አንገቱን ቆርጦ ለንጉሡ አበረከተው፡፡ ቱርኮች የነበራቸው ሐብትና ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ የይስሐቅ ረዳቶችም ተማረኩ፡፡ ንጉሡ ከተማረኩት ዋና ዋናዎቹን መርጦ እንዲገደሉ አዘዘ፡፡

4ኛውና የመጨረሻው ኢትዮጵያ ከቱርክ ኦቶማን ጋራ ያደረገችው ጦር ፍልሚያ በአጼ መላክ ሰገድ ዘመነ መንግሥት (በ1589 ዓ.ም. ነበረ፡፡ ወልደ እዙም የተባለው በአሊቃው በትግራይ መኮንን ዳህራቦት ላይ ዐመጸ ተነስቶ ብዙ ባለሥልጣኖችን ገድሎ ቱርኮች ባለፈው ዘመናት ሊቆጣጠሯቸው ሞክረው የነበረ የባሕር ምድር ግዛቶች ለመያዝ በነበራቸው ምኞት ጥቃት ባካሄዱበት ወቅት በመጀሪያ ሲዋጋቸው ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ግን የቀድሞ የባሕር ነጋሽ ምላሰ በመከተል ለቱርክ ፓሻ እጁን ሰጥቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ከቱርኮች ተቀብሎ ከንጉሡ የተላከው ጦር ለመቋቋም ችሎ ነበረ፡፡ በአዲሱ ባሕር ነጋሽ ረዳትነት ቱርኮች ድባርዋን ለመያዝ ችለው ነበር፡፡

ዳህራጎት ሊያስወጣቸው ሞክሮ ከባድ ሽንፈት ደርሶበታል፤ ቱርኮች መረብን ተሻግረው ትግራይ ገብተው ነበር፡፡ ሕዝቡ ግን ተዋግቶ መልሷቸዋል፡፡ በሚመለሱበት ጊዜ ዑቅባ ሚካኤል የሚባለው መረብ አጠገብ ባደረገባቸው ደፈጣ ስለተከበቡ ከተያዙት 7 ቱርኮች ተሰለቡ፣ ሁለት የበላይ ሹሞች ተገደሉ፣ ንጉሡ ዑቅባ ሚካኤል በፈጸመው ጀግንነት ተደስቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ሰጠው፡፡ ዜናው በመላው ኢትዮጵያ እንደምሳሌ ተተረተ፡፡ ፓሻው የንጉሡ መምጣት ሳይጠብቅ ወደ ምፅዋ ሄደ፣ ንጉሡ ግን ቱርኮችን ለዘለዓለም ከኢትዮጵያ መሬት መንቅሎ ለማውጣት ምፅዋ ድረስ ሄደ፡፡ ቱርኮች በምሽጋቸው እና ከባሕር ከመርከባቸው ሆነው ተከላከሉ፡፡ ብዙ ቱርኮች ታስሩ ሁሉም እግሮቻቸውና እጆቻቸውን ተቆረጡ፡፡ ፓሻው ራሱ ቆስሎ ነበረ፣ ሰውነቱ ብረት ለብሶ ስለነበረ ግን ከሞት ተረፈ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ስንቅ ሳላለቀበት ወደ ደጋ መመለስ ግድ ሆነበት፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከበባው እንዳቆመ ወዲያውኑ ቱርኮች የእርቅ ውይይት ጀመሩ፡፡ ንጉሡ ከጂውን ወልደ እዙምን ማሳደድ ጀመረ፡፡ ዑቅባ ሚካኤለ ተከታትሎ ይዞ ገደለው፡፡ ንጉሡ ድባርዋ እንደተመለሰ እጅግ በጣም ብዙ ስጦታዎች ከፓሻው የተላኩ አገኘ፡፡ አጼ መላክ ሰገድ ስጦታዎችን ተቀበለ እርቅና ሰላምም ወረደ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ግንኛውም የቱርኮች መስፋፋት ምኞት ለሁሉ ጊዜ አከተመ፡፡ ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፎች የሚመጡባት ሁሉ የታላቁ የቱርክ መንግሥት ወረራዎች እንዲሁም በሃይማኖት መነሻ በምሥራቅ ሱልጣኖች የግራኝም ጭምር የእርስ በእርስ ጦርነቶች ከብዙ ዘመናት ፈተና በኋላ በአሸናፊነት ተወጥታለች፡፡



## 11. የኦሮሞዎች መስፋፋት ክስተት

ኢትዮጵያ ልታሸንፈው ያልቻለችው ሌላ ጠላት ነበራት፣ ይኸውም የኦሮሞ የመስፋፋት ክስተት ነው፡፡ የኦሮሞ ከደቡብ ወደ መሐል ሀገር መስፋፋት ምክንያት ኢትዮጵያ ከባድ ውድቀት ደርሶባታል፡፡ የደቡብ ምዕራብና የምሥራቅ ክፍላተ ሀገሮቿ እንድታጣ ተገደደች፡፡ በነዚህ ክፍላተ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ ማንነታቸው በውል የማይታወቁ በአጠቃላይ ሲዳማ ወይንም አማራ ብለን የምንጠራቸው ሕዝቦች ከምድረ ገፅ ጠፍቷል፣ ባይጠፉም ቋንቋቸው፣ ባሕላቸው፣ ታሪካቸውና ስማቸው ጠፍቶ በኦሮሞ ተተክቷል፡፡ አሁን ኦሮሞ ሕዝብ ተብለው ሰፍሮባቸው የሚገኙ መሬቶች ኦሮሞ ከመምጣታቸው በፊት ባዶ መሬት አልነበሩም፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ሌሎችም አሁን የደቡብ ሕዝቦች ብለን የምንጠራቸው ወይንም ሌሎች የጠፉት ሰፍረውባቸው ነበረ፡፡፡ ኦሮሞ ከመጡ በኋላ ግን በሙሉ ተገደሉ ለማለትም አይቻልም፡፡ ከኦሮሞ ጋራ ተቀላቅለው ዘራቸው ጠፋ ለማለት ይቀላል፡፡ ኦሮሞዎች እንደ ይፋት ወይንም እንደ አዳል መንግሥት አልነበራቸውም፣ ወረራ ፈጽመዋል ለማለትም አይቻልም፡፡ ኦሮሞዎች ያካሄዱት የመሬት ማስፋፋት ነው፣ ሰፈራ ነው፡፡ ኦሮሞዎች መንግሥት ስላልነበራቸው አንድ መሪ አልነበራቸውም፡፡ በይፋት፣ በአዳልና በቱርኮች ያልተሸፈነ የኢትዮጵያ መንግሥት በኦሮሞች ግን ተሸንፏል፡፡ ኦሮሞች እንደሌሎች ሕዝቦች ለምሳሌ ሶማሌ በጐሳ ተከፋፍለው እርስ በእርሳቸው የሚጣሉ አይደሉም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በሥልጣን ሹኩቻ ወይንም በሐይማኖት ምክንያት ከግራኝ ከሐረር እስላማዊ መንግሥት ያደረጋቸው እርስ በእርስ ጦርነቶቹ በመዳከሙ ኦሮሞዎች ተጠቅመውበት ወደ ባሰ ውድቀት እንዲደርስ አድርገውታል፡፡ ኦሮሞች አዲስ መሬት ለመያዝ እንደ ማዕበል ወደ ፊት ከመገስገስ በቀር የታወቀ ዓላማ አልነበራቸውም፡፡ መንግሥት ለማቋቋምም ዓላማ አልነበራቸውም፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ስልጣን ለማጋራት ወይንም የነበረውን መንግሥት ገልብጠው ስልጣን ለመያዝ ዓላማ አልነበራቸውም፡፡ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጥላቻ እንዳልነበራቸው የሚያስረዳ አንዳንድ ነገሥታት ለውትድርና እየመለመሉ ይጠቀሙባቸው እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ያጋጥም እንደነበረ ተዘግቧል፡፡

ኤውሮጳውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳና በቋንቋ ሲከፋፍሉት ኦሮሞችን ደቡባውያን የኩሽ ዘሮች ይመድቧቸዋል፡፡ የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዮችም የዚሁ ዓይነት አከፋፈል ነው የሚከተሉት፡፡ ይህ አሰራር ቋንቋና ጎሳን ለይቶ ለማወቅ ባለመቻሉ የአንድ ሰው ወይም ሕዝብ ማንነት ቋንቋው ብቸኛ መለከያ በመውሰድ የሚደረገው የዘር አመዳደብ ዘዴ ነው፡፡ በቋንቋው ብቻ የአንድ ሕዝብ ማንነት መመደብ ግን ትክክለኛው ሊሆን አይችልም፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ሴማዊ የተባለው የግእዝ ቋንቋ ከመስፋፋቱ በፊት ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየፈለሰ ስለሚሄድ ቋንቋውን ትቶ አዲስ የሰፈረበት ቦታ ቋንቋና ባሕል እንደሚይዝ የታወቀ ነው፡፡ ኦሮሞችም ከዚህ ሕግ አይወጡም፡፡ ቅድመ ታሪክ ኦሮሞዎች የሰፈሩበት ቦታ በሰሜን በደቡብ ወይንም በመሐል በምሥራቅ ኢትዮጵያ ይሁን አይታወቅም፡፡ አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 30 የሌሎች ጸሐፊዎች ታሪክ በመጥቀስ ከኑቢያ እስከ ኤርትራ ባሕር ተበታትኖ የነበረ ሕዝባችን የስም ዝርዝር ሲሰጥ በቁጥር 18 ጋሊ የተባለውን ጋላ ብለው ተርጉሞታል፡፡ መሠረት የሌለው አተረጓጎም

ነው ለማለት አይቻልም። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ሆኖ ያገለግል የነበረው ግብፃዊው የክርስትና ሐይማኖት ተከታይ ስሙ ቡትሮስ ጋሊ ሲሆን ይኸውም ስማቸው ወደ ዓረብኛ ያልቀየሩ የጥንት ግብፃውያን ስም ሊሆን ይችላል። ኢጣሊያዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ስለጥንታውያን ግብፅ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሰጡት አስተያየት በመጽሐፉ እንደተገለጸው ኢልሚ ኦርማ (የኦርማ ልጆች) ወይንም የኦሮሞ ልጆች ማለት መሆኑን የሚል ትርጉም ተሰጥቷል ይሄም ትርጉም የተሰጠው ቱቲ ሞሲስና ሌሎችም የግብፅ ፈርኦኖች በሐውልቶቻቸው ስለአስገበሯቸው የኩሽ ዘሮች ስም ዝርዝር ተቀርፆ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው።

ኮንቲ ሮሲኒ አስተማማኝ ታሪክነቱ በግሉ ቢከደውም ባለሞያዎች የሰጡት አስተያየት በደፈናው ሐሰት ነው ለማለት አይቻልም። ኦሮሞዎች ከ1520 ዓ.ም. በፊት ወደ መሐል ኢትዮጵያ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ደቡብ ኢትዮጵያ ቦረና አካባቢና ከኒያ ብቻ ሰፍረው እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው። ኦሮሞች ሰፍረውበት የነበረ ዋናው ማእከል ዋላቡ ከአብያተ ሀይቅ በስተምሥራቅ የሚገኘው ተራራ ነው ተብሏል። በዚህ አንድ አውራጃ የማያህል መሬት ሰፍረው ተውስነው ለብዙ ዓመታት ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎች በጥቂት ዓመታት ውስጥ መላው ኢትዮጵያን ማጥለቅለቃቸው በየትም የዓለም ክፍሎች ያልታየ ታእምራዊ ክስተት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ቋንቋውን ባሕሉን እና ሰልጣኔውን ከሰሜንና ቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ሞንባሳ በሚያስፋፋበት ጊዜ፤ አንድ መቶ መንግሥታት ወይንም 35 መንግሥታት ወዘተ... በሰሩ እሉት ይባል የነበረው፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአንድ አውራጃ ሕዝብ ብዛት እንኳን ያልነበራቸው ኦሮሞዎች ከስር መሠረቱ ሊያንኮታኩቱት የቻሉት በጦር መሣሪያ ተጠቅመው አይደለም። ጋዳ ወይም ጉዲፈቻ በተባለው የአስተዳደር ስልታቸው ተጠቅመው ነው። ኦሮሞዎች ለብዙ ዘመናት ከባንቱ ጎሳዎች በጉርብትና በኖሩበት ጊዜ ጋዳ የተባለው የዕድሜ ክልል መሠረት የሚያደርግ የአስተዳደር ዘዴ ከእነሱ በመውሰድ አስፋፍተውታል። በዚህ በባያቸው ከሌሎች የካም ዘሮች ይለያሉ። ሌሎች የካም ዘሮች ሁሉ እርስ በእርሳቸው የሚለያዩ በስጋ ዝምድና ሲሆን ኦሮሞዎች ግን እንደ ኮከብ ቆጠራ የአንድ ዕድሜ ክልል የሆኑ ሰዎች በአንድ ወገን ይመደባሉ። ጋዳ ብዙ ደረጃ አለው 1. ዳባሌ 2. ፎሌ 3. ቆንዳላ 4. ዶሪ 5. ሉባ እየተባሉ ይጠራሉ። የጋዳ ደጋፊዎች ዲሞክራሲ አስተዳደር ነው ይሉታል። ነገር ግን እጅግ ኋላ ቀር የሆነ አስተደደር ዘዴ ነው። ኦሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ከመሰራጨታቸው በፊት የሐማኖት መሪዎቻቸውና ጠንቋዮቻቸው አባ ሙዳ ይባሉ ነበር። ሁለት አባ ሙዳዎች ነበሩ። አንዱ በዳሎ ሜካ በገናሌ ወንዝ አጠገብ ሁለተኛው በዋላቡ ተራራ። በኋላ ጊዜ ኦሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ዘልቀው ገብተው የባሌን መንግሥት በተቆጣጠሩበት ጊዜ የአባ ሙዳ መኖሪያ የአቡል ቃሲን ተራራ ሜፍ ታዋቂው ሼክ ይኖርበትና ያረፈበት ሆነ። የሁለቱ እምነቶች ተዋሕደው የኦሮሞዎች ሁሉ ቅዱስ ቦታ ማእከል ለመሆን በቅተዋል። ኦሮሞዎች ለዘመናት በሰላም በደስታ ይኖርበት ከነበሩ ሰፈራቸው ለቀው ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንዲሰራጩ ምክንያት የሆኗቸው ሶማሌዎች ናቸው ተብሏል። በግራኝ ጦርነት ጊዜ ኦሮሞች አይታወቁም ስለነበረ ግራኝ ለውትድርና ሊመለምላቸው አላሰበም። ግራኝ ለተዋጊነት የተጠቀመባቸው ሶማሌዎች ብቻ ነበሩ። መጠነ ሰፊ የሆነ የቀንድ ከብቶች፣ ወርቅ የጦር መሣሪያና ባሮች



ከክርስቲያን ኢትዮጵያ ሶማሌዎች በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዘርፈው ያመጧቸው በማየታቸው ኦሮሞዎች በሶማሌዎች ከመሬታቸው ስለተፈናቀሉ ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንደ ባሕር ማእከል ተሰራጩ። ኦሮሞዎች ከመምጣታቸው በፊት ምዕራብ ወለጋ እንሬሉ ተብሎ ይጠራ ነበረ። ወሎም የቀድሞ ስሙ እንጎት ነበረ ወዘተ... ጋፋት፣ ትልቁ ዳሞት፣ ዳዋሮ፣ ፋጠጋር፣ ግራ፣ አዳል፣ ወዘተ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ክፍለተ ሀገሮች ወይንም መንግሥታት ታሪካቸውና ስማቸው ቋንቋቸውና ባሕላቸው ጠፍቷል፣ በኦሮሞ ቋንቋና ባሕል ተተክቷል ወይንም ዘራቸው በሙሉ ጠፍቷል።

ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን አውራዎች እንኳን ዘራቸው እንዳይጠፋ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በዛሬ አንድ መቶ ዓመት ላማግዊ አጼ ሚኒልክ የቀድሞ አባቶቻችን የገነቧት የኢትዮጵያ ግዛት አንድነት ባስከበረበት ጊዜ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ የተቀላቀሉት ክፍለ ሀገሮች ቋንቋቸው እና ባሕላቸው እንኳን ባይቻል የቀድሞ ስማቸው እንዲያገኙ ማድረግ ይገባው ነበር። አጼ ምኒልክ ይኸንን ባለማድረጉ የኦሮሞ ቋንቋና ባሕል እንዳይነካ በማድረጉ የዛሬ አንዳንድ ኦሮሞዎች አጼ ምኒልክን በወረራ እንደያዛቸው ሊቃቅሉ ይታያሉ። አጼ ሚኒልክ ያዘመተው የአማራ የኦሮሞ የትግሬ ወዘተ... ያሉበት የኢትዮጵያ ሠራዊትም ነፍጠኛ እየተባለ ስም ማጥፋትና ታሪካዊ ቅዱስ ዓላማውና ተልኮው የተወጣበት አድናቆትና ምስጋና ሲገባው የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚያናፍሱትን ወሬ በማስተጋባት ይገኛሉ። ዛሬ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው ክፍላተ ሀገሮች ምሥራቅ ደቡብና ምዕራብ ሸዋ፣ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ ኢሉባብር እና ጅማ ባዶ መሬት አልነበሩም። ቅድመ ኦሮሞ የነበሩ ሕዝቦች በግዴታ የኦሮሞ ቋንቋ በጉዲፈቻ በመውሰድ ኦሮሞ ተባሉ እንጂ በዘር ኦሮሞ አይደሉም። ስለዚህ ኦሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ ዘር አይደለም። በዘር ከሆነ ኦሮሞ የአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎሳዎች በውስጡ ያቀፈ ነው። ስለዚህ ኦሮሞ ተናጋሪ የሆኑት የሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ስለሆኑ በኢትዮጵያ ጎሳዎች ላይ ጥላቻና ቅራኔ ሊኖራቸው አይገባም። ኦሮሞ ሳይታሰብ ቋንቋውን በመላ ኢትዮጵያ አማርኛ ያልቻለው በተአምር ሊያስፋፋ ችሏል። ይህ በመሆኑ ኦሮሞዎች ሊደሰቱ ይገባቸዋል እንጂ በግንባር ቀደም በቋንቋችን እንዳንጠቀም ያለፉት መንግሥታት ጨቆኑኝ ለማለት አይችሉም። በኦሮሞ ፋንታ አማርኛ ከዳር እስከዳር ባለመስፋፋቱ ቁጭት ሊኖራቸው የሚገባ አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያድርበት ይገባል። በኦሮሞ መሬታቸውን ተነጥቀው ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ያጡ ሕዝቦችም በዕድላቸው ሊያዝኑ ይችላሉ። የኦሮሞ ሕዝብ ግን ከማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ መብቱ የተጠበቀለት ስለሆነ አሁን ሲነገር እንደምንሰማው መብቴ አልተከበረም ብሎ ቅሬታ ማሰማት ባለፈው ታሪካችን አንፃር ተቀባይነት የለውም። በማንኛውም ጦርነት እንደሚያጋጥም የምኒልክ ሠራዊትም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጭፍጨፋ ተፈጽሞ ይሆናል፣ ኦሮሞዎች ከፈጸሙት ጭፍጨፋ ግን የሚነጻጸር አይደለም። ብዙ የሰው እልቂት የተፈጸመ ወቅት ቢኖርም በምኒልክ ዘመቻ ጊዜ ከሁሉ የባሰ በኦሮሞዎች አካባቢ የተደረጉ ጦርነቶች አልነበረም። ከሁሉ የባሰ ጭፍጨፋ የተፈጸመው ኦሮሞዎች እንደ ጅማ አባጅፋር የተካፈሉበት በከፋ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዘመቻ ጊዜ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ቃላቶች ያለአግባብ እንጠቀማለን።

ለኦሮሞዎችና በሌሎች ሕዝቦች ያለውና የነበረው ግንኙነቶች ወራሪና ተወራሪ ገዢና ተገዢ ብለን ለመጠቀም ብንፈልግ ግን የኦሮሞ ሕዝብ ወራሪ ነው እንጂ በሀገሩ ላይ አለተወረረም። ለም መሬት ነጥቆ ከሌሎች በመያዙ

ገዥ ነው እንጂ ተገዢ አይደለም። የአማርኛ ቋንቋ እንኳን የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ ያላደረገው ኦሮሞዎች ሌሎች ሕዝቦች ቋንቋቸው ባሕላቸውና ስማቸው እንዲቀየሩ አድርገዋል። አማራ ማለት እንደ ኦሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ የጎሳ ስም አይደለም። አማርኛ እንደ ኦሮምኛ ብዙ ጎሳዎች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። አብዛኛው ዛሬ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ዘራቸው አገው ነው፣ አገው ባይሆኑም ከትግራይ የመጡ ናቸው።

ኦሮምኛ ቋንቋ እየተናገሩ ኦሮሞ እንዳልሆኑ ከሚያምኑ ሕዝቦች የወርጂ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ወርጂ ከትግራይ እንደሚወለዱ ያምናሉ።[1] በንጉሥ ዐምደ ጽዮን ዘመን ከአፋር ኗሪዎች እስላሞች ከሌሎች እስላሞችም ጋራ ሆነው ፀረ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ግንባር የፈጠሩ ተብለው ተጠቅሰዋል።[2] ዘራቸው ከአፋር ወይንም ከሶማሊ አይደሉም፤ ጉራጌዎች ከትግራይ መጣን እንደሚሉ፣ እንደዚሁም በሲዳማ የነበሩ የንጉሥታት ዘራቸው ከትግራይ መሆኑን እንደሚያምኑ፣ በተመሣሣይ ወርጂ ከትግራይ መምጣታቸው ይናገራሉ፤ በአዋሽ ከኦሮሞች ሚታ በቾ ይዋሰናሉ።

ኦሮሞች በታሪካቸው በሶማሌዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ እንዲፈልሱ ተደርገዋል፤ በባንቱ ከደቡብ ወደ ሰሜን እንዲፈልሱ ተገዷል፣ ቀጥሎም ከ100 ዓመት ባነሰ ጊዜ ከሲዳማ (ደቡብ ሕዝቦች) እና ከአማራ ባደረጉዋቸው ጦርነቶች አሁን የሚኖሩባቸው ሰፋፊ መሬቶች ለማግኘት በቅቷል። በመረሻም ጠብመንጃ ታጥቀው ሲዋጉዋቸው ከመጡ አዲሶች የአማራ ወራሪዎች ጋራ ጨቢሌ ይዘው እንኳን ለመከላከል ሳይሞክሩ ነፃነታቸው ተንጥቀዋል በማለት ቸሩሊ ስለ ኦሮሞች መስፋፋት ከስተት ባጭር ገልጸታል[3]። ኦሮሞ ድል የተመቱበት የማሩ ኩሬቻ (Sella Maru) በተባለው ቦታ በራስ ጉበና የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ነው። ራስ ጉበና ጨቢ በኦሮሞች ላይ ጦርነት ገጥሞ ድል ተጐናጽፎ ወደ ጊቤና ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመገስገስ መንገድ የከፈተበት ወሳኝ ድል የተጐናጸፈበት ቦታ ነው።

## 1. ጋዳ አስተዳደር

የኦሮሞና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ብዙ አይታወቅም። ስለ ኦሮሞ ተጽፎ የሚገኘው ስለ ጋዳ የዕድሜ አስተዳደር ነው። ቸሩሊ እንዳጸፈው ከባንቱ የተወረሰው የጋዳ አስተደደር መሠረት በድሮ ጊዜ አንድ ጉሣ በሁለት ዘር የተከፈ 10 የጋዳ ደረጃዎች ነበሩት። አባትና ልጅ በተቃራኒ ጋዳ ሲመደቡ፣ የልጅ ልጅ ከአያቱ ጋራ ይመደባል። እንደዚህ እያለ በየ8 ዓመት እየተቀያየረ 1ኛ ደባለ ከ1 እስከ 8 ዓመት ዕድሜ 2ኛ ፎሌ ከ8 እስከ 16 3ኛ. ቆንዳላ ከ17 እስከ 24 4ኛ ዶሬ ከ25 እስከ 28 5ኛ ሉባ ከ29 እስከ 32 6ኛ. ዩባ ከ33 እስከ 40 ተብለው ይከፈላሉ። የፖለቲካ ሥልጣን የሚገኘው በግል ችሎታ ሳይሆን በዕድሜ ነው። ልዩ ሥነ ሥርዓት እየተደረገ 8 ዓመት እንደተቈጠረ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ይዛወራሉ። ይህ ጥንታዊ የጋዳ አስተዳደር ሳይቀየር የቀጠለው በክርስቲያን ኦሮሞች ብቻ ነው፤ እስልምና የተቀበሉ ግን ጋዳ አስተዳደር ከእምነታቸው ጋራ አልተጣጣመም። በሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ

(1) Cerulli : Etiopia occidentale p. 14
(2) Cerulli : ibd p. 14
(3) Cerulli ibd p. 19



ጐሣዎች ጥንት 10 ጋዳ የነበሩ ለአምስት ስለተጠቃለሉ አባት ልጅና የልጅ ልጅ ወዘተ ባንድ ይመደባሉ 1ኛ ጂደ 2ኛ አቢቹ 3ኛ. ጉምቢቹ 4ኛ. ሜታ 5ኛ ጉለሌ 6ኛ. አቦራ የሚባሉ በምዕራብና ደቡብ ሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ ጐሣዎች በመሃላቸው ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖራቸውም የጋዳ ስምና ደረጃ ተመሣሣይ ነው። የጋዳ ስሞች 1ኛ. ሆራታ 2ኛ. ሚቺሌ 3ኛ. ዱሎ 4ኛ. ሮባሌ 5ኛ. ቢርማጂ ተብለው ይጠራሉ። የጋዳ ደረጃዎች 1ኛ. ደባለ 2ኛ. ፎሌ 3ኛ. ቆንዳላ 4ኛ. ዶሬ 5ኛ. ሉባ 6ኛ ዩባ ናቸው። በጂዳ ጐሣዎች ዶሬና ሉባ ለ4 ዓመት ብቻ ስለሚቈዩ የአንድ ደረጃ ንኡስ ክፍል ናቸው። በአቢቹ ጉሣ ዶሬ ቀርቷል፤ 8 ዓመት ሲጨርሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚተላለፉበት የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ቡታ ይባላል። ዩባ ደረጃ ካላቸው አንዱ ተመርጦ አባ ዳባለ እየተባለ ጋዳ የሚጀምሩ ልጆችን ዶዮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያቀርባቸዋል። ከሥነ ሥርዓቱ በኋላ ዩባ የሆኑ ሁሉ ይገረዛሉ። ፎሌ ደረጃ ያሉት ሁሉ ጅንጀሮ ቆዳ ፊታቸውን ሸፍነው ፎሮርሳ የተባለው ዱላ ይዘው ይዘዋወራሉ። ከመሃከላቸው በፎሮርሳ ዱላ ደብድቦ ከራማቸው ጉሳ ውስጥ አንድ ፍየል ወይንም አንድ በግ መዝረፍ የቻለ "ሐዩ" ተብሎ አለቃቸው ይሾማል። የተዘረዘረው በግ ወይንም ፍየል ወዲያውኑ ተሰብስበው ይበሉታል። ዶሬ ወደ ሉባ ደረጃ ሲሸጋገሩ የሚደረገው ቡታ በሬ አርደው ሥነ ሥርዓት አለቃቸው ሐዩን ይመርጡና፤ እሱም ጠጉሩ ተላጭቶ፣ ወተት ፈሶበት፣ በሉባ ደባለ እጅ ፊቱ በበሬ ቆዳ ግንባርና ቀንድ ይሸፈናል፤ እንደ በሬም ይጮሃል። ይህ ሽፋን ሒርዙ ይባላል። ጉሣቸውን ለመምራት የፖለቲካ ሥልጣን የሚሰጣቸው ዶሬ ወይንም ሉባ ደረጃ ያላቸው ናቸው። ኑቱ ደረጃዎች የጉሣ አባላት ለጋብቻ ዘር ለመቍጠር ይጠቀሙበታል። ከ5 ትውልድ በላይ ካልተቈጠረ ጋብቻ አይፈቀድም።

ኦሮሞች አጼ ምኒልክ ከግዛቱ ጋራ ከማዋሐዱ በፊት የ365 ቀናት የዓመት መቍጠሪያ ነበራቸው። ዓመቱ የሚጀምረው በመስቀል ስለሆነ የጥንት ከኢትዮጵያ አንድነታቸው የሚያሳይ ምልክት ነው። 1.ሙዳ መስከረም 2 ሐደሊቻ ነሐሴ ዳዋ ጥቅምት 4 ጥር ጥሪ፣ ኅዳር/ 5 ፉርማ (Furma) የካቲት 6 ሺያን ሰኔ 7 ቦሩ ሺያን ሐምሌ።
በሶማሊም የዓመት መጀመሪያ ቀን እሳት በማንደድ ይከበራል።[1]

ኦሮሞች በዙቋላ የሚገኘውን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ገዳም አቦ (አቡነ) በማለት ያከብሩታል። ኦቦ የሚል አጠራር በሁሉም የተለመደ ነው። እንደዚሁም በፌንፌኔ ጠበል ለአቦ ክብር እየተባለ በየዓመቱ በውሃው ውስጥ የፍየል ወተት ማፍሰስ፣ የወፎች ጠጉር ማበርከት ልምድ ነበረ። በተራሮችና በምንጮች እምነት ማዘውተር ከጣኦት እምነት የመጣ ነው ቢባልም፣ ክርስቲያንም በጣኦት እምነት የተተካ ስለሆነ የቀደምት አባቶቻችን የኢትዮጵያ የጋራ የክርስቲያን እምነት ምልክት መሆን አለበት[2]።

## 2. ኦሮሞና ሲዳማ

በኦሮሞች ወረራ ዘራቸውና ቋንቋቸው የጠፋ የሲዳማ ሕዝቦች የመጨረሻዎቹ ከአፄ ምኒልክ ዘመን በፊት በጅማ አካባቢ ብዙ ኦሮምኛ ያልሆኑ ቃላቶች ይቀላቀላሉ። ንጉሥ ለማለት በኦሮምኛ ሞቲ ሲሆን በልማድ ግን ጉይታ ተብሎ ይጠራል፤ ጉይታም ወደ ጎፍታ ተቀይረዋል 2 እልጋ

(1) Cerulli ibd p 58
(2) Cerulli ibd p 59

ወራሽ ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ዶናቾ ተብሉ ይጠራል፡፡ 3 የንጉሡ ሚስት ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ጌን ተብላ ትጠራለች፡፡ በጅማ አካባቢ የነበሩ ነገሥታት አንዳንድ ጉማዎች በጅምላ እንደ ባሪያ የመቍጠር ባሕል ነበራቸው፡፡ ጅማ አባ ጅፋር ይህ ባሕል ተቀብሉ አጋንኖ በሥራ ላይ ያዋለው በጃንጀሮ ሕዝብ ላይ ነው፡፡ ጅማ አባ ጅፋር አፄ ምኒልክ ምዕራብ ኢትዮጵያን በምይዝበት ጊዜ ከጦሩ ጋራ በመተባበሩ ውለታ ለመክፈል በመጠቀም ጅማ አባ ጅፋር የጃንጀሮ ሕዝብ የእሱ ባሪያ ሕዝብ መሆኑን አውጆ ግማሹ በክልሉ እየኖረ የሚሸጥ የሚሰወጥ ሲያደርገው ግማሹ በባርነት ተዘርው የነበረው ራስ ተሰማ የጃንጀሮ ሕዝብ እስተዳደር ከአባ ጅፋር ነጥቆ በአንድ አማራ እንዲስተዳደር ሥር ለማድረግ ግድ ሆነበት፡፡ 5 ጅማ አባ ጅፋር ወሮ ይዞ ከማዘቱ የቀለቀላቸው የሲዳማ መንግሥታት የመጨረሻ በሻ ነው፡፡ ስሙ· ቀይሮ ግን ጋና ተብሉ ተሰይሞ የጅማ ክፍለ ሀገር አካል ሆነዋል፡፡ በሻ ከከፋ ተመሣሣይ ጉማ ሲዳማ ናቸው፣ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል፣ ቋንቋቸውና ኦሮምኛ፡፡ በጅማ ከተገዙ ጀምሮ ሁሉም የእስልምና ሃይማኖት ተቀብሏል የቁድሞ የበሻ ነገሥታት ወራሾች ከፊል እስረኛ በመሆን ጅሬን ከተማ (ጅማ ከተማ) አጠገብ እንዲቀመጡ ተገዷል፡፡ ስማቸው አባ ቡሺየን ቡሳሲዬ ይባላሉ፡፡ የበሻ ነገሥታት ዘር ሐረግ ለከፋ፣ ለምሜና ለእንፈሉ ነገሥታት የሚሆኑ ሰዎች የሰጡ ናቸው፡፡

6 የጅማ ወሰን መግቢያ በሲዳማ አጠራር ከላ ይባላል፣ ነፃ መንግሥታት በነበሩ ጊዜም ገለልተኛ በወሰናቸው የሚገኘው መሬት "ሞገ" የተባለ ነበረ፡፡

7 ጅማ ሌሎችም ድሮ የኦሮሞ ነፃ መንግሥታት የነበሩ የሚስተደደሩ ከሲዳማ የተወሰደ በዘውድ አገዛዝ ስለሆነ የጋዳ አስተደደር አሰራር ጨርሶ ባይቀርም ንጉሡ የማይሾማቸው ባለሥልጣናት በሕዝብ ብቻ የሚመረጡ ሊኖሩ ስለማይችሉ የጋዳ አሰራር ከአዲሱ ሥርዓት መጣጣም ግድ ሆኖበት ነበር፡፡ የጋዳ ደረጃዎች ለሁለት ብቻ ተቀንሱ ራባና ሉባ የሚባሉ፡፡ ጋዳ የሚደራጁም በጉማ መሆኑ ቀርቶ በመንደር ነበር፡፡

8 የጅማ ኦሮሞች እስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ በቅርብ ጊዜ ነው፣ ባለፈው መቶ ዘመን አጋማሽ ነው፣ ሊቀበሉ የቻሉም ንጉሣቸው በወርጂና በዳሪታ የጉንደር እስላሞች ነጋዴዎች ተሰብኮ በመጀመሪያ እስልምና ሲቀበል፣ ዜጎቹም በእስላሞች የታረደ ሥጋ እንዲበሉ ስላስገደዷቸው ነው፡፡ ለሰነበረ ግዲታ እስላሞች መሆን ነበረባቸው፡፡ እስካሁን ድረስ የጅማ እስላሞች መስያ የሆነው እንደ ክርስቲያኖች ጠላና ጠጅ መጠጣታቸውና ጫት አለማዘውተራቸው ነው፡፡

9 ጅማ በኦሮሞች ከመያዙ በፊት ከከፋ ሕዝብ ተመሣሣይ ዘር የሆኑ የሲዳማ ሕዝቦች በንጉሥ አገዛዝ የሚስተዳደሩ ይኖሩበት ነበር[1]፡፡ ኦሮሞች ከቀድሞ ነዋሪዎች ከሲዳማ ተምረው የጋዳ አስተዳደር አስቀርተው የዘውድ አገዛዝ ተቀበሉ፡፡ አንዳንድ የኦሮሞ የጉማ መሪ የሀገር መሪ (ንጉሥ) ከእነሱ ጉማ ብቻ እንዲሆን ከመቻላቸውም በላይ፤ ከሕዝብ የሚመረጥም በጋዳ ሳይሆን በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ አደረጉ፡፡ የዚህም ምሳሌ የታየው በሲየካ ቀለም ሞቲ ተብሉ የሚጠራ ነበር፤ በሕዝብ የሚመረጠው ግን ሊየካ ዋዩ ይባል ነበር (Lieca wayou)

[1] Cerulli ibd p 91



10 ኪላ በከፋ ቋንቋ የቤት በር ሲሆን ኦሮሞች ግን፣ የነበሩ መንግሥታት ወሰን ለማመልከት ብቻ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

11 በኦሮሞች ለሴቶች ሥልጣን መስጠት ልምድ አልነበረም፣ ከሲዳማ ተምረው ግን ሴቶች ሥልጣን ተሰጧቸው "ጌኔ" ጌታ ንግሥት ተባሉ፡፡ መስፍን፣ እልጋ ወራሽም ከሲዳማ ተወስዶ ነውቲ፤ ዳኖ "ወደ ደንዞ" "ዶንዲዮ" "ዶናጂዮ" እየተሰወጠ በከፋ በ ጌሜ በእንፈሉ መስፍን ለማት የሚጠቀሙበት ነበር፡፡

12 በሰው ስም ብቻ ሳይሆን ከሲዳማ የተወ͡ረሉ በሀገርና በቦታ ስሞችም ኦሮሞች ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ የቦሶ ተራራ (ጅማ የሚገኘው) በሾ ከሚባለው የከፋ ጉማና ቦሺያ ከሚባለው የሲዳማ መንግሥት የተወሰደ ነው፡፡ ግና የሚባል ሰፈር በጅማና በከፋ አሉ፡፡ በጅማ ሳራዶ ተራራና ሳደሮ ወረዳ ሲኖር በከፋ ሺራይ ወረዳ አለ፡፡ ጌሺ ወረዳ በጅማ ሲኖር በከፋ ጌሻ አለ፡፡ በደቡባዊ ጅማ ሰማጾ ተብሉ የሚጠራ ወረዳ በከፋ ሺየማዶ የሚባል አለ፡፡ የሊሙ ዋና ከተማ ኮሳ ሲሆን በከፋም ኮሺየ የሚጠራ አለ፡፡ የሊሙ ሳፓ ከተማ ሲኖር በከፋ ሺያፓ አለ፡፡ የእግዚአትን ማርየም መቅደስ በሊሙ ጉዶ ማርያም ተብሉ የሚጠሩ ተራራ ሲኖር ጉዶ ማለት በከፋ ተራራ ማለት ነው፡፡ የጉማ መንግሥት የነበረው ስም በከፋ የአንድ ወንዝ ስም ነው፡፡ በጉማ የአጋሮ መንደር ሲኖር በከፋም አጋሮ የሚባል መንደር አለ፡፡ በጅማ የሚገኘው ያቦ ወንዝ ከከፋ ያቦ ዘባባ የተወሰደ ነው፡፡ የጌራ ወና ከተማ የነበራቸው ቼራ በከፋ ሰሙ ጥሩ ሺፒናዎ የኖረበት የተወሰደ ቦታ አለ፡፡ እንደራቻ የሰው ስም በጌራ ዋና ከተማ አጠገብ የሚገኘው ቦታ የከፋና ጌሜ ዋና ከተማ ስም ነው፡፡ በጅማ የኪየቼዮ ጠበል ሲኖር፣ በከፋም ኪየሺዮ ፍል ውሃ ጠበል ይገኛል፡፡ ያንጋቼያ የሚባለው የጌራ ከከፋ ኢንጋጂያ የመጣ ነው፡፡ የጠበቀ ጥናት ቢደረግ ብዙ ሌሎች ስሞች ሊገኙ ይችላሉ[1]፡፡

ቸሩሊ ከኢትዮጵያውያን አዋቂዮች አገኘሁ ብሉ እንደዘገበው የዛሬዪቱ ጅማ ክልል ሰሜን ምሥራቅ የጃንጀሮ መሐልና ደቡብ ክፍል የቦሻ እንስተኛ ክፍልም የእናሪያ ነበረ፡፡ የዛሬዪቱ ቦሻ ግደላግደል በመሆኑ ከሰሜንና ከምዕራብ የመጡባቸው ጠላቶች በመካከል ሸሽተው የሰፈሩበት ይመስላል፡፡ ተዋቂው በነበረ የእናሪያ መንግሥት ዛሬ በኦሮሞች ወረራ ከምድረ ገጽ የጠፋ ይናገረው የነበረ ቋንቋ ይበልጥ ተመሣሣይነት የነበረው ከከፋ ሣይሆን ከበሻ ቋንቋ ነበረ፡፡ ኦሮሞች ወደ ጅማ የመጡበት አቅጣጫ በሚመስከትም ሁሉም በአፈ ታሪክ የሚያረጋግጡት የጅማ ኦሮሞች ከመጫ ኦሮሞች አንድ ክፍል (አንድ ጉማ) መሆናቸውና ከወሲጋ ወለል ከሚባለው ቦታ መመጣታቸውን ይናገራሉ፡፡ 6ቱ የጅማ ጉማዎች ከወለል ተነስተው ወደ ምሥራቅ አምርተው ግማሾቹ በደቡብ የነበረው የሲዳማ ሀገር በመያዝ የዛሬዪቱ ጅማ መሠረቱ፡፡ ኦሮሞች ወደ ጅማ የገቡ በስተሰሜን ከጃንጀሮ የነበረው ጠባብ መተላለፊያ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አሁንም ከዳደሌና ድኖ የመጫ ጉማዎች ኩታ ገጠም ይገኛሉ፣ ከዚህም ወደ ምዕራብ የወሲጋ ሊየካ ይገኛሉ፡፡ ከ6ቱ የጅማ ጉማዎች ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ወረራ ያልተካፈሉ እስካሁን ከአባይ እስከ ግቤ ወንዝ ሰፍረው የሚገኙ ጅማ ገቦ 2 ጅማ ሆሮ 3 ጅማ ራሬ 4 ከሞግ ወንዝ የዲደሳ ገባር አካባቢ ጅማ አርጆ ሲሆኑ ሁሉም ከጅማ አባ ጅፋር ዝምድና እንዳላቸው የሚያስታውሱ ናቸው፡፡ ኦሮሞች ወደ ጅማ የመጡበት ዓመተ ምህረት በትክክል ባይታወቅም 1567 እና 1568 አ.ም መካከ ሰገድ ወደ እናሪያና ቦሻ የመጣበት ጊዜ የንጉሡ ታሪክ

[1] Cerulli ibd p 101 - 2

ፀሐፊ በእነዚህ መንግሥታት ኦሮሞች መገኘታቸው አልመዘገበም፤ ዳሩ ግን በ1703 ዓ.ም. ትልቁ አፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ወደ እናሪያ ሲዘምት ሀገሩ በሚጨ ኦሮሞች ተከበ ስላገኘው በጦር ኃይል ጦርነት በማካሄድ ብቻ መንገዱን በመክፈት ወደ እናሪያ የሲዳማ መንግሥት ሲደርስ ችሏል።

ከ1419 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሠው የአፄ ይስሐቅ ታሪክ ፀሐፊ በሻ ለኢትዮጵያ መንግሥት ግብር በወርቅ ከሚከፍሉ ግዛቶች አንዱ እንደነበረ፣ የእናሪያ አዋሳኝ እንደነበረ ስለተዘገበ የድሮ በሻ የዛሬ ጅማ በኦሮሞች ሲያዝ ስሙ ጅማ ካካ ነበረ። ካካ በኦሮሞ ቋንቋ ዘረፋ ማለት ስለሆነ ሀገሩ በዘራፊዎች እንደተያዘ ያሳያል። ቀጥሎም የአባ ጅፋር ጉሳ ባዲ ስለሚባል ሀገሩ ጅማ ባዲ ተብሎ ይጠራ ነበር። በ1840 በዳባዲ ዘመን (Abbadie) ጅማ በዚሁ ስም ትጠራ ነበር። በመጨረሻም በንጉሣዊ ስም ጅማ አባ ጅፋር ተብላ ተጠራች።

ጅማን ለማስገበር የጉጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒልክ ለውድድር ቀርበው በ1883 በእምባቦ ጀኑዋሪ ጦርነት ገጥመው ጉጃም በመሸነፉ ጅማ ወደ ሀገሩ የሚገቡ ነጋዴዎች ምኒልክን በጦር ኃይል መቋቋም እንደማይችል በሰጡት ምክር መሠረት ተሽቀዳድሞ ከንጉሥ ምኒልክ በመስማማት ከሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ተለይቶ ለንጉሥ ምኒልክ መገበር ጀመረ።' በዚህም ምክንያት የውስጥ አስተዳደር ነፃነት (ራስ ገዝ) አግኝቶ በኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይያዝ ለመኖር በቅቷል። ሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ግን በሰላም መገበር ባለመፍቀዳቸው በጦር ኃይል ብቻ በምኒልክ ጦር ሲያዙ ችሏል። የጅማ ዋና ከተማ በድሮ ጊዜ ጂረን ተብላ ትጠራ ነበር። አሁን ግን ዋና ከተማዋም ክፍለ ሀገሩም ስሙ ጅማ ተብለው ይጠራሉ። የጅማ አካባቢ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ከተዋሐደ ጀምሮ ዝነኛው የእናሪያ መንግሥት የቀድሞ ስሙ ማግኘት ነበረበት፣ ይህ ባለመደረጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ደካማነት ያሳያል። የሲሙ ጉሣ እንደ ጅማ ከቲላ ወሰል ወሊጋ የመጡ ናቸው። በቀድሞ ጊዜ የእናሪያ መንግሥት (በከፋ ቋንቋ ኢኖአሪ ቶቶ) ከጉጀብ ወንዝ ዳሪቻ ግራና ቀኝ የሚገኙ መሬቶች ያጠቃልል ነበር። ከእናሪያ ነገሥታት ትልቁ ዝነኛው ሺፒናዎ ነበረ። ዋና ከተማው ቸሪኮ አጠገብ ነበረ። በኋላ ግን በኦሮሞች ስለተሸነፈ ወደ ከፋ ክፍል ጉጀብ ተሰዶ ሄዶ ጨላ በተባለው ቦታ ጋዋተ ራሺዮ የከፋ ክፍለ ሀገር መቀመጫው አድርጎ ይኖር ነበር። በከፋ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያ እስከተያዘበት ድረስ የእናሪያ ንጉሥ የክብር መጠሪያ ብቻ ሆኖ ቆይቶ ነበረ። የእናሪያ ነገሥታት ወርቅ፣ በስደት የነበሩ የእናሪያ ነገሥታት ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ ያስተላልፍ ነበር። የሺፒናዎ ዋና ከተማ ቸሪኮ የምትገኘው ጌራ ውስጥ ቺያዳ በተባለው ተራራ ስር ዋራ በተባለው ቦታ የአምልኮት ቅዱስ ቦታ የነበረው አጠገብ ነበረች። ስለዚህ የእናሪያ መንግሥት ግዛት በሲሙ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፣ በትክክል ባይታወቅም ሰፊ ግዛት ያጠቃልል እንደነበረ ይገመታል። ሺፒናዎ ክርስቲያን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም የሄደው ከሀገሩ የመጀመሪያ ሰው ነው። ከኢየሩሳሌም ሲመለሱ ታቦት ይዞ መጥቷል። ስለ ሺፒናዎ በአፈታሪክ የሚወራ ብዙ ነው። ሺፒናዎ በእናሪያ ቤተክርስቲያን ሰርቷል፣ ከዚህ በኋላ አንድ ትልቅ ዘመቻ ወደ ከፋ አድርገዋል። ሺፒናዎ በመንገድ ሲጓዝ ሌሎች ሰዎች የሚጠቀሙበት መሰናክል አያጋጥመውም፣ በወንዞች ሲያልፍ ከመቅጽበት ትልቅ ድልድዮች ሠርቶ ያልፋል። በሰው እግር ለማለፍ የሚዳግቱ ተራራዎች ሲያጋጥሙት በጉራዴው በመስበር ያልፍ ነበር። ዛሬ እንደራቻ አጠገብ በረታ ወንዝ



በጉርጉቶ በሺፒናዎ የተሰራ ቸሩ በተባለው ቦታ ላይ በኩታ ክፍለ ሀገር አንድ ድንጋያማ ተራራ የእናሪያ ንጉሥ በጉራዴ የሰበረው ተመልካች ሁሉ የሚያደንቁቸው ይታያሉ። ሺፒናዎ ወደ ከፋ በምዕራብ በኩል ገብቶ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አነፀ፣ ከኢየሩሳሌም ያመጣው ታቦትም አረገበት። ከዚህም ወደ ጠቋቁሮች ሀገር ወደ ሻሻ ደርሶ ከዚያ ወዴት እንደሄደ ሳይታወቅ ጠፋ። ይህ እንደ ተረት የሚነገርለት የእናሪያ ንጉሥ ኮንቲ ሮሲኒ በአፄ መላከ ሰገድ ክርስትና የተነሳ የእናሪያ ንጉሥ ሰፐንሒ መሆኑን ትርጉም ሰጥቷታል። በበሐ ቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት መመሥረቱ እውነት መሆኑን የተረጋገጠ ነው። በታቦቱ ያለው ጽሑፍ በጌራ ወረዳ ይኖር የነበረ ካቶሊክ ቄስ ሚሲዮናዊ አባ ለዮን ቀድቶ ስለወሰደው፣ አንድ ኢጣሊያዊ ምሁር ተርጉሞታል[1] ትልቁ ዳሞት ሳይቀር ሁሉም ሌሎች የሲዳማ መንግሥታት በኦሮሞች ወረራ ፈራርሰው ሲጠፉ በምዕራብ ከሚገኙ ለዘመናት በንጉሣዊ አገዛዝ የሚስተዳደሩ ብርቱ ትግል አድርጎ ሳይጠፋ መኖር የቻለ የከፋ መንግሥት ብቻ ነው።

የኦሮሞ ሰዎች አንድ አማራ መግደል ዘሬ እንደ መግደል ነው ብለው ሲኩሩ የከፋ ሰዎችም በበኩላቸው እንደ ኦሮሞ መግደል ነብት እንደመግደል ይቈጠራል እያሉ ይዘፍኑ ነበር። የከፋ መንግሥት ሕልውናን ማስጠበቁ ብቻ ሳይሆን የሲዳማ ነገሥታት ዘር የነበሩ በኦሮሞች ሲወረሩ በግዛቱ በክብር የንጉሥ የክብር ማዕረግ ተሰጧቸው እንዲኖሩ ያደርግ ነበር። ለዚሁም የበቁ የዳሞትና የእናሪያ ነገሥታት ይጠቀሳሉ። ይኸንም የሚያደርግበት ምክንያት የራሱ ዘር የሲዳማ ዘር በመሆናቸውና የማይበገርነቱ እምነት ስለነበረው የምዕራብ ሲዳማ መንግሥታት ጠባቂ መሆኑም እምነት ስለነበረው ከአፄ ምኒልክ ሠራዊትም ጭምር ራሱን ለመከላከል እንደሚችል የነበረው እምነት፣ በኦሮሞች ላይ በነበረው የበላይነት ስሜት ተደፋፍሮ ነው። ይህ በመሆኑ ከፋ በአፄ ምኒልክ ሠራዊት የተሸነፈው ለ17 ዓመት ከተዋጋ በኋላ ነው። ከፋ ከጥንት ጀምሮ በዘውድ አገዛዝ የተመሠረተ መንግሥት መሆኑን በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ንጉሡ የሚገኙ ጉሣ የቡሻሾ ቤተሰብ ነበረ። የንጉሡ ፈላጭ ቈራጭነት ገደብ የሚወስኑ ደምቦችም ነበሩ። ① የንጉሡ የክብር ዘበኛ አዛዥ የሚሆነው ካታሚ ራሺዮ የሚባለው ከዚዮ ጉሣ ይመረጣል። ② የጊምቦ ክፍለ ሀገር አስተዳደሪ ከኢርጎ ጉሣ ③ የቢታ አስተዳዳሪ ከአማሮ ጉሣ ብቻ መመረጥ ነበረባቸው ወዘተ። ሹመቱም የሚሰጠው በልምድ ነበረ፣ ጉሣው በሚኖርበት አካባቢ አልነበረም። የከፋ ንጉሥ እንደ መልአክ ይቈጠር ነበር፣ ዜጎቹም ፊቱን ከማየት ይቈጠቡ ነበረ። የመጨረሻም የከፋ ንጉሥ ዘውድ የነበረ አፄ ምኒልክ ለስዊትዘርላንድ ተወላጅ ኢልግ ስለሰጠው በዙሪግ በሚገኘው በመሐንዲሱ ቤተሰብ ቤት ተቀምጦ ይገኛል። የንጉሡ መቀመጫ (ዋና ከተማ) ቦንጋ (ቦንጌ ዳቦ Bonghe Dabbo) በተባለው ንጉሡ ለሰማይ እግዚአብሔር አምልኮት ያደርግበት በነበረው ተራራ ፊት ለፊት ነበረ። 10 ኪሎ ሜትር ከቦንጋ የሚርቅ በእንደራቻ የከፋ ንጉሥ ሌላ ሁለተኛ መቀመጫ ነበረው ይህ ቦታ ግን ለውጭ ሰዎች የተከለከለ ነበረ። ንጉሡ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። አታለች የተባለ ሰው ንጉሡ የሚበላውና የሚጠጣው የሚቈጣጠር ነበረ። ንጉሡ ብዙ እንዳይበላም እንዳይጠጣም መከልከል መብት ነበረው። የንጉሡ ሥራዎች የሚከተሉት ነበሩ 1. ሀገረ ገዢዎች መሾም፣ 2. ከውጭ መንግሥታት ጋራ በመልእክተኞች በኩል ግንኙነት ማድረግ፣ 3. የዳኝነት ሥራ፣ የሞት ቅጣት፣

[1] Cerulli ibd p 197

በባርነት የሚሸጥ መብት፡፡ በከፋ በተለይ ለባርነት የሚዳረጉ ሰዎች ቁምር፣ ቡዳ ተብለው የሚከሰሱ ሰዎች ናቸው፡፡ ዶቾ (Doccio) በተባሉ ቄሶች በኩል ለፍርድ ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ያለ ምንም ሌላ ማስረጃ ይግባኝ የሌለበት ባርያ ተብለው ይፈረድባቸው ነበር፡፡ 4. በጦርነት ተሸንፈው ስለተማረኩ ሰዎች ዕጣ፣ ንጉሡ ባሪያ እንዲሆኑ ማድረግ ወይንም አለማድረግ መብት ነበረው፡፡ ባሪያ ናቸው ኩተባሉ ንጉሡ በጠየቀ ጊዜ ወደ ውጭ የሚሸጡ ናቸው፡፡ የዚሁ ዓይነት ዕድል ያጋጠማቸው ናዎ የሚባሉ ከጊጊሩ ጉሣ የሚመሣሠሉ፣ ከከፋ ደቡብ የሚገኙ ናቸው፤ ለንጉሡም የዝቢ ምንጭ ናቸው፣ ታቲ ናዎ (tate nao) ይባሉ ነበር (የንጉሡ ናኦ)፡፡ በኦሮሞ ነገሥታትም ናኦ ሞቲ እየተባሉ በታማኝነታቸው ተፈላጊ ነበሩ፡፡ 5. ንጉሡ የዝቅተኛ ዘሮች የበላይ ጠባቂ ነበረ፤ እንደ ብረት ቀጥቃጭ ሸክላ ሠሪ (Manna) አዝማሪ፣ ማንጆ (Manjio tato) ማንጆ ታቶ ለንጉሡ ብቻ ወርቅ የሚሠራ ነው፡፡ በጂማ አባ ጅፋርም ወርቅ ሰሪ ለንጉሡ ብቻ ነው ወርቅ የሚሠራ 6. ንጉሡ የውጭ ሀገር ሰዎች ጠባቂ ነው፤ ወደ ከፋ የሚገቡ ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ገበያዎች ለክርስቲያን በቦንጋና በካያ ብቻ ነበሩ፡፡ በቋሚነት ኗሪ መሆን ለሚፈልጉ እስላሞች 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ከካያ በሚገኘው ቶንኮላ በተባለው ቦታ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር፡፡ ክርስቲያን በካሬኛ አሮ በቦንጋ ልዩ መንደር ተሰጥቷቸው እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር፡፡ አማሮ እንደ ከፋ ጉሣ ሆነው የተዋሐዱ የቢታ ክፍለ ሀገር አስተዳደር መብት ያላቸው በድሮ ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጥተው የተዋሐዱ ናቸው፡፡ ከፋ ለ4 ትክፈል ነበር፤ 1 ቦንጋ 2 እናሪያ 3 ከፋ 4 ሐዲያ[1] የከፋ ጉሣዎች አስተዳዳሪ ሆነው የሚመረጡ የዝገር መደቦችና የማይመረጡ ለሁለት ይከፈሉ ነበር፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው 1 ሚንጆ የንጉሡ ዘር 2 ይሪንጎ 3 ሂዮ 4 አማሮ 5 አርገፓ 6 ሚየጠቺዮ የዝገር መደብ ያልሆኑ ጉሣዎች ሂኒማቾ (Hinnimachio) 2 ሂናካሮ (Hinacaro) 3 ሂኒቺዮ (Hinnucio) 4.አሾ 5 ቱራ ነበሩ፡፡ መንግሥቱ በጉሣ ልዩነት በመሬት ክልል የተከፈለ ነበረ፣ አስተዳዳሪዎች ራሺዮ ይባላሉ (ከአማረኛ ራስ የመጣ ቃል) ክፍለ ሀገሮች 10 ነበሩ ካፌ (Cafe) ጊምቢ፣ ቺያተታሉ፣ ኛቢ ቡተ፣ ቢተ፣ ጋዋተ፣ ጊዮሺየ፣ አዲ፡፡ ለቤተመንግሥት ብቻ የተወሰኑ 3 ራሺዮ ነበሩ፤ (ሀ) አዲዮ የክብር ዘበኛ ፈረሰኛ (ለ) ጉቼ የንጉሥ ባሪያዎች ሹም (ሐ) ካታሚ የንጉሡ ግቢ ዘብ አዛዥ፡፡ ከፋ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ አካል እንደነበረች በከፋ የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት መልክቶች ያስረዳሉ፣ ቤተክርስቲያኖችም ነበሩ፡፡[2] ከፋ ከኢትዮጵያ ተለይታ በኖረችበት ረጅም ዘመናት የጣኦት እምነት ብትከተልም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ዋና ዋና በዓላት ከማክበር ሕዝቡ አልከለከለውም[3]፡፡ የከፋ ንጉሣዊ አገዛዝ የማይናጋ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርገው የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ገደብ በማድረግ የሚቆጣጠሩ 6 አባላቱ ያሉት በንጉሡ አማካሪዎች የተደገፈ ስለነበረ ነው፤ እነሱም 1 ጉሺ ራሺዮ የካፌቾ ክርስቲያን ተጠሪ 2 ኩተማ ራሺዮ 3 አደል ራሺዮ ከኡኮ ጉሣ 4 አርባሽ ራሺዮ ከአርጋፓ ሐዲ ጉሣ ከኡኮ ጉሣ 5 አርባሽ ራሺያ ከአርግፓ ሐዲ ጉሣ 6 በንዳ ራሺያ ከአርጋፓ ሐዲ ጉሣ 7 አርሶ ራሺያ ከከፋ ማቹዮ ጉሣ፡፡ ሹመታቸው በምርጫ ሳይሆን በዘር የሚወረስ ነው፡፡ የአማካሪዎች የበላይ ሹም ጉሺ ራሺያ ነው፡፡ የዚሁ ጉሣ መሥራች በጥንት ከፋ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ የከፋ የጦር አዛዥ

---

(1) Cerulli ibd p 484

(2) A Cecchi : Da Zeila alle Frontiere di Kaffa VI p. 484

(3) A Cecchi ibd p. 486



በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኩሉና የጉሺ የንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ተሾሞ ስለነበረ ነው፡፡ የጉሺ ራሺዮ ሥልጣን ከፍተኛ ነበረ፡፡ ንጉሡ ሕግንና የሀገሩ ባሕልን የማያከብር ከሆነ ከሌሎች አባላት ጋራ በመመካከር ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ ተራ ሰው ሊያደርገው ይችላል፡፡[1]

## 3. ክርስትና በከፋ

ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አከባበር ወግና ሥነ ሥርዓት አስታዋፅታቸውን የሚሰጡ የኢጣሊያ ፀሐፊዎች ከጥንት ቅድመ ክርስትና ከነበረው የጣኦት አምልኮቶች ያልተላቀቀ መሆኑን እያሉ ሲጽፉ ይታያሉ፡፡ በከፋ ስለነበረው የክርስትና ሃይማኖት በዚሁ መንፈስ አጋንነው ጽፈዋል፡፡ ቸኪ በዶዮክ በሚባለው የጣኦት እምነት በከፋ አብዛኛው ሕዝብ የሚያጠቃልል ነው ካለ በኋላ በከፋ ለሰይጣን አምላክም ማምለክ እምነት ስለነበራቸው የተለያዩ ከብቶችን ለመስዋእትነት ያቀርቡላቸው ነበር ብሏል፡፡ በጣኦት አማልክቶች ማመን፣ መስዋትነትን ማቅረብ ከፋዎች የክርስትና እምነት ሥነ ሥርዓትንም ከማክበር አይከለከላቸውም ነበር፡፡ ከጣኦት አምልኮት በአስከፊነቱ የሚጠቀስ የጣኦት ቤተመቅደስ ሰዎች (ቄሶች) ቡዳ በተባሉ ሰዎች ሌሊት ወደ ጅብነት የሚለወጡ ናቸው ተብለው ተከሰው ወደ ቄሶች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ቡዳ ናቸው ብለው ከፈረዱባቸው፣ ምስክር ሳያስፈልግ፣ ይግባኝ በሌለበት ወደ ንጉሡ ቀርበው ባሪያ እንዲሆኑ ይፈረድባቸው ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ጊራ ይገኝ በነበረው የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ቄስ በአባ [illegible]ን ግምት በየዓመቱ ለከፋ ንጉሥ 500 ባርያዎች ያስገኝለት ነበር፡፡ ቸኪ አባባል በክርስትና ብቻ የሚያምኑ የከፋ ሰዎች በቀር ሌሎች በስም ብቻ ክርስቲያን ናቸው በተግባር አይደሉም፡፡ የክርስትና እምነታቸውን የሚገልጹትም 1ኛ. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ በማለት 2ኛ ጾም በማክበር 3 በመገረዝ 4 ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው እንደ ገና፣ ፋሲካ ፍልሰታ ወዘተ የመሳሰሉ ዋና ዋና የክርስትና በዓላት በማክበር ሊሆን፣ በሌላ ተግባራቸው ግን ከጣኦት አምላኪዮች የተሻሉ አይደሉም፤ እንደ እስላሞች ብዙ ሚስቶች ያገባሉ በማለት ተችተዋል፡፡ በከፋ ቤተክርስቲያኖች በመላው ኢትዮጵያ እንደሚሰሩ ዓይነቶች ናቸው፤ በዛፎች የተከበቡ ናቸው፣ የምውታን መቃብሮችም አሏቸው፡፡ ከሁሉ የታወቀ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ በዚሁ ቤተክርስቲያን የጣኦት ዶዮክ አምላክ የሚያምኑም ሳይቀሩ ወደ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት፣ ካፌቾ በሙሉ ለመጸለይና ስለት ለማድረስ ይሄዳሉ፡፡ በታቦቱ ያለው በግእዝ የተጻፈ ይለባቸው ነበር፡፡ ክርስትና ከፋ የገባው ምናልባት ከአክሱም ዘመነ መንግሥት መሆኑን መገመት እንችላለን፡፡ ቸኪ የ18 የከፋ ነገሥታት ስም ዝርዝር አውጥቷል[2] በ15ኛው ንጉሥ ጋንሺዮ ለ24 ዓመት የነገሠ የማዮ ራሺዮ ጉሣ ዘመን መንግሥትን ለመገልበጥ አሲረዋል ተብለው የተከሰሱ 600 ፈረሰኞችና ወታደሮች ተገድለዋል፡፡ በ16ኛው ንጉሥ ጋዋርሰሮ ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች ተገድለዋል፡፡ 17ኛው ንጉሠ ነገሥት ካም የጋዊ ዘሮ ልጅ ለ13 ዓመት የነገሠ በ1870 የሞተ፣ የዶአክ አምላክ አክራሪ ተከታይ ነበረ፤ እንደ አባቱ ብዙ ክርስቲያኖች ፈጅቷል፡፡ 18ኛ ንጉሥ በ1878 በሕይወት የነበረ የ45 ዓመት ጉልማሳ ስሙ ጋሊቶ ጋሊ ጋዎ (Gallito - Galli - Gao) ነበር፡፡ ሚንጂዮ ከማቶ ተረክቦ የቦንጋ

---

(1) A Cecchi : ibd p 488

(2) A. Cecchi : ibd p 490

ንጉሥ በመባል የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሲይዝ እናሪያን ከግዛቱ አጠቃለላት፡፡ በዚሁ ጊዜ እናሪያ ቡሳሰ በተባሉ በንጉሣዊ ቤተሰብ ትገዛ ነበር፡፡ የካቶሊክ ሚሲዮን በጌራ ሲመሠረት 70 (ሰባ) ከእነዚህ ቤተሰብ አባላት የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ለሃይማኖታቸው ሲሉ ከከፋ ተሰደው በ1878 ወደ ጌራ በመሄድ ከካቶሊክ ሚሲዮናውን ተቀላቅለው ለመኖር መምረጣቸው በቀድሞ እናሪያ የክርስትና ሃይማኖት እንዳልጠፋ ምስክር ነው፡፡[1] ወደ ጌራ የተሰደዱ የእናሪያ ሰዎች አለቃ 80 ዓመት ዕድሜ የነበረው አባ ታባኮ የተባለው ወደ ጌራ እንደመጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጌራው አባ ኮሮ የጦር አለቃ ሆኖ ተሾሞ በከፋ ላይ ለመዝመት ፈቃደኛ እንዲሆን የጌራ ንጉሥ ቢጠይቀው በሀገሬ ላይ አልዘምትም ብሎ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ የጌራ ንግሥትም ጉን እስላም እንዲሆን ብትጠይቀው እስላም ከሚሆን ገላው ተቈራርጦ ለአሞራዎች ቢሰጥ እንደሚመርጥ የሚል መልስ ሰጥቷታል፡፡ እንደዚሁም አንድ የቡላሲ ልዕልት ልጅዋ እስላም እንዲሆን ብላ ብትጠይቃት የሰጠችው መልስ ተመሣሣይ ነበረ፡፡ ከፋ የዓመት መጀመሪያና መስቀል የሚያከብረው ልክ እንደ ኢትዮጵያ አከባበር ነው፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ በዓመት መጀመሪያ ቀን ከእሱ በፊት የነበረው መቃብር ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ የከብቶች መስዋእት ያቀርባል ዘንቹም አበባ እያበረከቱ ረጅም ዕድሜ ይመኙለታል፡፡ በመስቀል ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ለሹማምንቶቹ ትልቅ የምሳ ግብዣ ያደርጋል፡፡ ግለሰቦችም መስከረም 17 በየቤታቸው ያከብሩታል፤ መስከረም 18 ብዙ የሚነድ ዕንጨት ይከማቻል፤ መስከረም 19 እውነተኛ የመስቀል በዓል ከንጉሡ ቤት ጀምሮ ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ ይደረጋል፤ 3 የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አርማዎች በመያዝ ኟ ባሮ ማስካሮ እያሉ እየዘፈኑ ይሄዳሉ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ ብዓሉ መጨረሻ ኘ ባሮ ማስካሮ እያለ ይዘፍናል፡፡

## 4. <u>ደቡብ ምዕራብ ከኢትዮጵያ ጋራ ማዋሐድ</u>

የመጨረሻ የጌራ ንጉሠ የነበረው የአባ ራጐ አጎት ለጉብኝት ወደ እሱ ለሄደው ኢጣሊያዊ ቸሩሊ (Cerulli) እንዳጫወተው ጌራ ለአፄ ምኒልክ ጦር የተማረከችው በጀግናው ኢትዮጵያዊው ደጃዝማች በሻህ አቡዬ የሚመራው ጦር አራት ጥይት ብቻ በመተኰስ ነበረ፡፡ ንግግሩም በመቀጠል ደጃዝማች በሻህ ደፋርና ጀግና ርሕሩሑም ነበረ፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በጦር ሜዳ በጣሊያኖች ተገድለዋል፡፡ እላይ እንደተገለጸው የከፋ የጥንት ታሪክና ባህል አድናቆት የሚስብ ነው፡፡ ጅማ አባጅፋር ከፋን ለማስገበር ከምኒልክ ጦር ጋራ በመሰለፉ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ላደረገው ውለታ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት እንደተሰጠው ሁሉ ለከፋም ለጥንታዊ ወጉና ባሕሉ ክብር እንዲሁም ላላየው ጀግንነት ከጅማ የበለጠ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ለማግኘት መመዘኛ ነበረው፡፡ አፄ ምኒልክ ግን በጠባብ የዘውድ ጥቅም ብቻ የሚመራ ስለነበረ ከፋ የጅማ ዕድል አልተሰጠውም፡፡ አፄ ምኒልክ እንደ አጋጣሚ ብቻ ፊት የተጣለበት "አደራ ኢትዮጵያ" ከደቡብ ምዕራብ ምሥራቅ ጥንት የነበሩዋት ግዛቶች ለማዋሐድ በተደረገው ትግል፤ የጅማ አባ ጅፋር ትብብር በደስታ ሲቀበል የጐጃሙ ንጉሠ ተክለሃይማኖት ግን በዘመቻው እንዳይካፈል ጦርነት ገጥሞ በማሸነፍ አስቀርቶታል፡፡ ከዚህም ሌላ የልጁ ዘውዲቱ ባል የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያ ሥላሴ በአባቱ ትእዛዝ በዘመቻው

(1) A Cecchi : ibd p. 341



ተካፋይ እንዳይሆን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሸዋ መጥቶ አፄ ምኒልክ በመጣበት እንዲመለስ አድርጎታል፡፡

የአፄ ምኒልክ ሠራዊት ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝመት በሚዘጋጅበት ጊዜ የጅማ ንጉሥ አባ ጅፋር የምኒልክ ጦር ለመቋቋም እንደማይችል በመገንዘቡ ለምኒልክ ለመገበር እንደወሰነ ሁሉ እንደዚሁም ቃቢየና በተባለው በጉራጌ ሀገር ሱልጣን የነበረው ያማር ባክስ የተባለው አክራሪ ሙስሊም የባሪያ ነጋዴ የነበረው፤ በየጊዜው ለሥራ ምክንያት ወደ ሸዋ በመመላለስ አፄ ምኒልክ የነበረው የጦር ኃይል ስለተረዳ ለምኒልክ በሰላም ለመገበር ተሸቀዳድሞ ወሰነ፡፡ በአፄ ምኒልክና በያማር ባክሳ መካከል የተደረሰው ስምምነት ያስከተለው ውጤት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የቻሃ፤ ምሑር፤ ጆቸሪት፤ እነሞር ጉራጌዎችና ከ2 ሺህ እስከ 3ሺህ የሚደርሱ አማራዎች በ1876 የደረሰ እልቂት ነው[1]፡፡ ኢማም ተብሎ የሚጠራው ያማር ባክሳ ከንጉሥ ምኒልክ እርዳታ እንዲያደርግላቸው አደራ ተብለው ወደ ጅማ ከፋ ለመዝለቅ ፈልገው ወደ ግዛቱ የመጡ ቸኪና ኪያሪኒ የሚባሉ ጣሊያኖች ወደ ግዛቱ ሲገቡ የሚከተለው ንግግር በማድረግ ተቀበላቸው፡፡ "አዳምጡኝ እናንተ እንደ እኔ ትልቅ ሰዎች ናችሁ፤ ንጉሥ ምኒልክ ወደ እኔ አደራ ብሎ ልከዋችኋል፤ ነገር ግን እናንተም ለእኔ ማድረግ አለባችሁ፡፡ እኔ እንደ ኦሮሞች ልብሶች መስተዋቶች ለዝቅተኛ ሰዎች የሚሰጡ እቃዎች አልጠይቃችሁም፡፡ እኔ ብዙ ጠላቶች አሉኝ፤ እናንተ ከእነሱ ለመገላገል እኔን መርዳት አለባችሁ የምጠይቃችሁ ከፈጸማችሁልኝ እኔ ራሴ ወደ ጅማ አባ ጅፋር እሸኛችኋለሁ፡፡ ብዙ ነገር አልጠይቃችሁም፡፡ የእናንተ አንድ ጠብመንጃ ብቻ በርቀት ሁኜ አንድ የጉራጌ ጕሣ ክርስቲያን የእኔ ጠላቶች ለመደምሰስ ይበቃኝ ነበር በማለት ጥያቄውን ደምድመዋል፡፡ ጣሊያኖች ግን አሁን ያሉን ጠብመንጃዎች ለራሳችን ለመከላከያ ብቻ የሚያገለግሉን ናቸው ሸዋ ለሚገኘው አለቃችን መልእክት ልከን ጠይቀን ግን እንዲሰጥህ ማድረግ እንችላለን አሉት፡፡ በዘመኑ በቃቤና በኩል በየዓመቱ 400 ባሪያዎች ተገዝተው ወደ ሸዋ ይወሰዳሉ፡፡ አብዛኞዎቹ ከቻሃና ከኡርባራግ በሌሊት ተሰርቀው የሚመጡ ናቸው፤ የሚገዙም በገንዘብ ሳይሆን በነሐስ ነጥር ነው፤ አንድ ነጥር 432 ግራም ነው የገበያ ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር

1 ወንድ ልጅ ቁመት 1ሜትር 20 ነጥር
2 ሴት ልጅ ቁመት 1 ሜትር 13 - 15 ነጥር
3 ትልቅ ልጅ 12 - 16 ዓመት 26 - 28 ነጥር
4 ሴት ልጅ 25
5 ወንድ ልጅ 20 - 24 ዓመት 20 - 30
6 ሴት ልጅ ቆንጆ 40
7 ሴት ልጅ መለስተኛ 30
8 ሴት ልጅ ዝቅተኛ 25 - 20 - 15
9 ቆንጆ ልጃገረድ 60 - 70
10 አሮጊት 6 - 7
11 ሽማግሌ 8 - 10
12 ሽማግሌ ጠንካራ 20

ዒማም ያማር ባክሳ ጠብመንጃ ከመጠየቅ አላቋረጠም፤ ጣሊያኖችም ተስፋ እየሰጡት ነበር፡፡ አንድ ቀን ኦገስት 25,1878 "ዐሽከሮቻችሁ

(1) A Cecchi : ibd VII p 52

ከንመሣሪያዎቻቸው ወደ አንድ ክርስቲያን ጉራጌ መንደር ከእኔ ጋራ ሄደው እንዲዘርፉ ፍቀዱልኝ የምናገኘው ገቢ እካፍላችኋለሁ ብሉ ጣሊያኖችን ጠየቃቸው፤ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች የጥያቄው አደጋነት በመገንዘብ፣ ከሁሉ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ስለሚፈልጉ ለአንድ ወገን ማዳላት እንደማይሹ ነገሩት፡፡

ጣሊያኖች ለጉዞዋቸው መሰናከል መሆኑን ስለተረዱ ከጉራጌዎች ጋራ መቀራረብ ፈለጉ፤ ጉራጌዎችም ሀገራቸውን እንዲጉበኙላቸው ጋበዙዋቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ከሁለቱ ጣሊያኖች አንዱ ወደ ጉራጌ ሀገር ሄዶ ጥናት እንዲያደርግ ወሰኑ፣ ዕጣም ለኪያሪኒ ደረሰው፡፡ መንገድ መሪዎች ጉራጌዎችን ይዞ ኪያሪኒ ወደ ጉራጌ መሬት ገባና ቤተክርስቲያኖችን አስጐበኙት፡፡ ወደ መጨረሻም አስጐብኚው ከዝናብ ለመጠለል ወደ ቤቱ አስገባው፡፡ በዚሁ ጊዜ ፈረንጅ ብዙ ሰው ተሰብስበው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር፡፡ ከቀረቡትም ጥያቄዎች ከየት ሀገር እንደመጣ፣ ሃይማኖቱ ክርስቲያን እንደሆነ ወይንም እስላም፣ ከሁለቱ ሃይማኖቶች የትኛው እንደሚሻል፣ በቀንደኛ ጠላቶቻቸው በእስላሞች ድል ይቀዳጁ እንደሆነ ወይስ አይቀዳጁም ወዘተ፡፡ ኢማም የግር ባከሳ ብቻ ሳይሆን የምኒልክ ወታደሮቹም ክርስቲያን መሆናቸው እያወቁ ከኢማም ተከታዮች ጋራ በመስማማት ያለ ምንም ርሕራሔ ያላቸውን ንብረት እየዘረፉ ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሳይቀሩ ያቃጥሉባቸው እንደነበረ በምሬት ያወሩለት ነበር፡፡ ጉራጌዎች ምሑር ስለ ሃይማኖት ብዙ ነገር ባያውቁም ሁሉም ግን ክርስቲያን ነን በማለት ይነግሩት ነበር[1] ፡፡ ኪያሪኒ እግረመንገዱ ከኢሻ ንጉሥ ጋራ ተዋወቀ ንጉሡም ፈረንጁ ያዛቸው መሣሪያዎች ካደነቀ በኋላ "አንተ ዓለምን ሙሉ ማቃጠል ችላለህ፣ የእኔ ሀገር አትንካ አንተ ቄስ ነህ እኔም እወድሃለሁ፣ አንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ እጬ ምኒልክና እስላም ንብረታቸው እየዘረፉ ሊያጠፏቸው እየጣሩ ያሉት እነዚህ ምስኪን ሕዝቦች ደስተኞች ልታርጋቸው ትችላለህ"፡፡ የሚል ንግግር አደረገ[2] ከንጉሡ ተሰናብቶ እንደሄደ የጣሊያኑ መምጣት ወሬ ስለተሰማ በፊት ቄስ ብቻ ይቈጥሩት የነበረ አሁን እንደ ቅዱስ ሰው ሁሉን ነገር የሚያውቅ አደረጉት፡፡ በሸዋ ሰዎች ልጆቻቸው የተወሰዱባቸው በሕይወት እንዳሉ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበር፡፡ ኪያሪኒ ከአካባቢው ተነስቶ እንደሄደ ቻሃ መሬት ደርሶ በዙሪያው ለተሰበሰበ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለሚያቀርብ ሕዝብ ዕድላቸውን እንዲነግራቸው፣ በጠላቶቻቸው በእግራ የተወሰዱባቸው ልጆቻቸው ወንድሞቻቸው የት እንደደረሱ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበረ፡፡ በመቀጠልም ኪያሪኒ ከዳሞ ንጉሥ ተዋወቀ፣ ጥሩ መስተንግዶ ተደረገለት፡፡ "የዚህ ሀገር ሕዝብ የቃበናውን ይግም አይደለም የሚፈሩ፤ በእሉ አማካኝነት የምኒልክ ጦር እንዳይወራቸው ነው ሲጋቷቸው[3]፡፡ ከእኛ ጋራ ሆነህ እንዝመት እስላሞችን እናጥፋቸው እያሉ ለክብሩ ይዘፍኑ ነበር፡፡ ንግሥቲቱም ለብቻው ወስዳ የቀቢየና ይግም እግራ እመጣባችኋለሁ እያለ እያስፈራራን ነው፣ ሙስሊን ሊያደርገን እየሞከረ ነው፤ የጉራጌ ሕዝብ እንደ በግ ነው የሚነዳው፣ ሃይማኖቱን ሊክድ ይችላል፤ እግሮች የማይመጡ መሆናቸው ቢያውቅ ግን ሕዝቡ ኢማሙን መሳቂያ ያደርገው ነበር፡፡ አንተ ትልቅ ሰው ነህ፣ ሕዝቡ ከውድቀት እንዲድን እድርገው፣ ቃልህን እንዲያምኑ ያዝካቸው መሣሪያዎችን አሳያቸው" ብላ ንግግሩዋን ከጨረሰች በኋላ ኪያሪኒ መልስ ለመስጠት

[1] A Cecchi ibd VII p 77
[2] A Cecchi : ibd p 80
[3] A Cecchi : ibd p 87



ተቸገረ[1] ንግሥቲቱ ላቀረበቻቸው እንገብጋቢ ጥያቄዎች ኪያሪኒ "የእናንተ ሁኔታ ይገባኛል የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ እግሮች ይመጣሉ እያለ የግር ባከሳ የማስፈራሪያ ጉራ ስለሚነዛባችሁ ጉዳይ አትቸገሩ፤ ንጉሥ ምኒልክ ባሁኑ ወቅት ለአፄ ዮሐንስ ግብር ለመክፈልና የበላይነት ለመቀበል ተስማምቷል፤ እዚህ መምጣት አይችልም ክርስቲያኖችን ከእስላሞች ጥቃት መጠበቅ አለበት እንጂ ክርስቲያኖችን አይፈጅም፡፡ እኔና ጓደኛዬ የእስላሞች ሀገር አቋርጠን ስለምናልፍ ችግር እንዳይፈጥሩብን አሁን ያልኳችሁ ነገር ለማንም አትናገሩ፡፡" በማለት የማደፋፈሪያ ቃላቶች ሰጣት፡፡ ንግሥቲቱም መልስ ስትሰጠው "በእስላሞች ሀገር ለማለፍ ግዴታ የለባችሁም፤ ወደ እኛ ከመጣችሁ በአቋራጭ መንገድ ምንም ሳትከፍሉ በጃንጀሮ ሀገር በኩል ወይንም በጅማ በኩል ወደ ከምባታ ወላሞ እናደርሳችኋለን፣ የጅማ ንጉሥ ሚስት የቻሀ ተወላጅ የአባጋስ ልጅ ናት" አለችው፡፡ ኪያሪኒ በንግሥቲቱ ንግግር በጣም ተደሰቶ አመሰገናት፡፡ ጉራጌዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚወለዱ ለኪያሪኒ ሲያስረዱ እንደሚከተለው ገልጸውለታል "ከአርሲ፣ ከረዩ፣ ቱሉማ፣ መጫ፣ ጋላ ተከበው በችግር ላይ በነበሩ ጊዜ ከሀገራቸው እንዲያባሩሯቸውና እንዲፈጁዋቸው ይፈልጉ ስለነበረ ጉራጌዎች ወደ ጐንደር ለንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኞቻቸው ልከው ከአሮሞች እልቂት እንዲድኑ እርዳታ እንዲያደረግላቸው በጠየቁት መሠረት እነሱ እጥናፍ ሰገድ የሚሉት ንጉሥ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ሱሲኒዮስ የሚሉት ንጉሥ የትግራዩ ሹም የነበረው አዝማች ሰብሐት ለእርዳታ ላከላቸው፣ እሱም የተላከበትን ዓላማ እንደተዋጣ፣ ወታደሮቹ ቍጥራቸው በመቀነሱ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመመለስ ስላልቻሉ በዝዋይ ሐይቅ የምትገኘው ትልቋ ደሴትና አካባቢው ለፍረ... ጉራጌዎች ንጉሥ ብሎ ራሱን ሰየመ፡፡ የአዝማች ሰብሐት ትውልድ ሐረግ ብዙ ዓመት ነገሠ፤ በመጨረሻ ግን በንጉሥ ሣሕለሥላሴ የምኒልክ አያት ተደመሰሰ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ጉራጌዎች እውነተኛ ንጉሥ የላቸውም፤ ጉልበት ያለው ሁሉ ደካሞችን እያስቸገረ ንጉሥ ይባል ነበር መሬታቸውንም ይነጥቁዋቸው ጀመር፡፡ በዚሁ የተነሳ የጉራጌ ቋንቋ ከግእዝ ተመሣሣይነት አለው[2] ፡፡

ከጉራጌዎች የክርስትና ሥነ ሥርዓት በጥብቅ የሚከተሉ ምሁር ናቸው፡፡ ኢንደጋን፣ የነር፣ መገር፣ እስላሞች ያረዱትን ስጋም ይበላሉ፡፡ ጉራጌዎች ባለሥልጣን አያውቁም፣ ሲለ ንጉሥ ሲያወሩ እንደ ተራ ሰው ነው የሚያከብሩት፣ ሃብት ያለው ብቻ ንጉሥ የሚባለው፡፡ ንጉሥ የሚባሉ ሃብትና ጀግንነት ያሳየ ሰው ነው፡፡ ከእነሱም ትልቁ ብቻ ዳሞ ወይንም ጉይታ ይባላል፡፡

ጣሊያኖች ወደ ከፋ ለመድረስ የቻሀ ንጉሥ ማጋናስ ባቀረበላቸው ሃሳብ መሠረት በጅማ ወይንም በሊሙ ከማለፍ፣ በጉሬጌ፣ ጃንጅሮ፣ ከምባታ፣ ወላሞ እንጓዝ ኪያሪኒ እምናበት ተስማምቶ ነበር፤ ሆኖም አብሮዋቸው የሚጓዙ ከበት ጫኞች መንገዱን ስለማያውቁ በዚሁ መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ፡፡ በመጨረሻ ከቃቢና ጥጂየር ወደ ሊሙ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ፡፡

አፄ ምኒልክ ተድሞ የኢትዮጵያ አንድ አካል የነበሩ፣ አሮሞች ባካሄዱት ጦርነቶች ምክንያት ከኢትዮጵያ ተለይተው ይኖሩ የነበሩ ግዛቶች መልሶ ለማዋሐድ የፈጸመው ተግባር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለዘለዓለም

[1] A Cecchi : ibd VII p 88
[2] A Cecchi : ibd VII p 89

የማይረሳ ውለታ የሚያስገኝለት ቢሆንም እላይ እንደተገለጸው አክራሪ ሙስሊሞች እንደ ኢማም የግር ባከሳ ባለሟል አድርጎ በጉራጌ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ጥቃት እንዲያደርስ መፍቀዱ ከባድ የአስተዳደር ስህተት በመፈጸሙ በታሪክ ያስወቅሰዋል፡፡

## 5. የእናሪያ የመሬት ስፋት

ተጓዦች ጣሊያኖች ቸኪና ኪያሪኒ ተፈቅዶላቸው ወደ ሊሙ ገቡ፡፡ በቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመን የእናሪያ የመሬት ስፋት ከአባየና አዋሽ ወንዞች ከፋም በውስጡ የሚያጠቃልል የግቤና የጉጀብ ሜዳዎች ያቀፈ ነበረ፡፡ ይህ ግዛት በንጉሥ እንደራሴ ይገዛ ነበር፡፡ ከ1545 ጀምሮ በኦሮሞ ሜጫ ወራሪዎች ግዛቱ ሲፈራረስ ገዢዎች ግማሾቹ ወደ ጉጃም ሲሸሹ ግማሾቹ በከፋ ሰሜናዊ ክፍል ሰፍረው ያጡት የሰፈ ሀገራቸው ስም የሰፈሩበት አንድ የከፋ ክፍለ ሀገር እናሪያ ብለው ሰይመው በቀድሞ ገባሮቻቸው ከነበሩ የወረታ ጉማዎች በመተባበር ለኦሮሞ ማስፋፋት ከፍተኛ መከላከያ በማድረጋቸው ለከፋ በነፃነት መቆየቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመፈራረሱ በፊትና እናሪያ በሜጫ ኦሮሞች ከመወረሩዋ በፊት የሀገሩ ነዋሪዎች አፈ ታሪክ እንዳቆዩው ሁለት የፖርቱጋል ወታደሮች ሲጋሮ (Sigaro) እና ሰፔራ (Sapera) የተባሉ፣ ከክሪስቶፎር ዳ ጋማ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ በአፄ ግላውዴዎስ ከሰሜን ኢትዮጵያ ተባርረው እናሪያ መኖሪያቸው አድርገዋት ነበር፤ በስነ ምግባራቸውም በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮት አግኝተው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የነበራቸው አክብሮት እየጨመረ በመሄዱ በእናሪያ የአስተዳደር የበላይነት አግኝተው ነበር፡፡ ሲጋሮ በሰሜን እናሪያ መኖሪያው አደረገ፣ ሳፔራ ወደ ደቡብ ሳፓ (Sappa) ተብላ የተጠራቸው መንደር ሰፈረ፡፡ ከሳፓ ቤተሰብ አንዱ የአባ ባጊቦ አባት አባ ጎሞሊ በክህደት የሲጋሮ ግዛት ወደ ግዛቱ አጠቃልሎ አንድ የሊሙ መንግሥት አቋቋመ፡፡ እንደ አቡነ ማሣያ ምስክርነት አባ ጎሞሊ የነጭ ዘር ይመስል ነበረ[1]፡፡ ሊሙ ከ80 ዓመት ወዲህ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ቢሆንም መስጊዶች በብዛት አይታዩም፡፡ ጣሊያኖች /ቸኪና ኪያሪኒ/ በነበሩበት ዘመን (1878) በሊሙ ተላላፊ በሽታ ተስፋፍቶ ነበር፡፡ በሊሙ የሕዝቡ ግማሽ በበሽታ አልቋል[2]፤ በጉማ 2/3 በበሽታ አልቀዋል፡፡ ጣሊያኖችም እየታመሙ ይድኑ ነበረ፡፡ ከሁለቱ አንዱ ኪያሪኒ ታሞ ሲሞት በጌራ ንግሥት ተመርዞ ነው የሞተ ተብሎ ተወራ፡፡

## 6. ጉማ

ጉማ በጥንት ጊዜ የሲዳማ አማራ የሚባሉ ይኖሩባት ነበር፡፡ በኦሮሞ ነዋሪዎች ጊዜ ነዋሪዎቹ በሙሉ ተገድለው አልቀዋል፡፡ ክርስቲያን ሕዝብ ይኖሩበት እንደነበረ በማያሻማ ሁኔታ ማስረጃ የተገኘው የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ በዲደሳ ወንዝ ዳሩ (Daru) ከተባለው ተራራ አጠገብ ጉልጉታ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በመገኘቱ ነው[3]፡፡ ጫላ የጌራ ዋና ከተማ የሁሉ ዓይነት የባሪያ ክምችት የሚታዩባት ናት፡፡

[1] A Cecchi : ibd VII p 156
[2] A Cecchi : ibd p 199
[3] A Cecchi : ibd p 239



1. ወረታ ጉማዎች ከኩሉ፣ ወሊሶ፣ ኮንታ መንግሥታት የመጡ
2. ካፊቾ 3 ጃንጀሮ 4 ጉራጌ 5 ከምባታ 6 ሻንቅላ 7 ጋላ የተሰያዩ ጉማዎች ሶዶ፣ ቡቱር፣ አጋሉ[1] ፡፡ የጌራ ሕዝብ የኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ አማራ ድብልቅ ነው፡፡ ሌላ ዋምባሪ የተባሉ ዝቅተኛ ዘር የሚገመቱም አሉ፡፡ የቤተመንግሥት ዘር የኦሮሞ ዘር ከወላሞ ምሥራቅ ደቡብ የመጡ ናቸው[2]፡፡ በጌራ ቤተመንግሥት ከ3000 ያላነሱ ባሪያዎች ይኖራሉ፡፡ እነሱም 12 የንጉሡ ሚስቶች በጋብቻቸው ጊዜ ለጥሎሽ ተሰጧቸው ይዞዋቸው የመጡ ናቸው፡፡ ባሮች ወደ ውጭ ይሸጣሉ በሀገር ውስጥም በእቃ ይቀየራሉ፤ 6-7 ባሪያዎች በአንድ የጦር ፈረስ ይለወጣሉ ወዘተ፡፡ ይህ ሁኔታ የአፄ ምንሊክ ጣልቃ ገብ ጦር እነዚህ ጥቃቅን መንግሥታትን መውረሩ ሕጋዊ ያደርገዋል፡፡

## 7. ጃንጀሮ

ጃንጀሮ ደብተሮችና የካፊቾ ሽማግሌዎች እንደሚተርኩ የዚሁ አካባቢ የመጀመሪያ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አፈታሪክ እንደሚናገረው ጃንጀሮና ሲዳማ በሐይቆች ይኖሩ የነበሩ የአንድ እናት ልጆች ናቸው፡፡ ጃንጀሮ የግቤ ዳውሮ አጠገብ አዞዎች ያመልኩ ነበር፡፡ ንጉሣቸው ኮርማ በሬዎች ለአዞዎች እንዲበሏቸው በመስዋእትነት ያቀርብ ነበር፡፡ ንጉሥ ሲታመም ጤና እንዲያገኝ ሰዎች ወደ ግቤ አዞዎች ለመስዋእትነት ይወረውሩ ነበር፡፡ ይህ የጣእት እምነታቸው ግን አንዳንድ የኢትዮጵያ የክርስትና ሥነ ሥርዓት እንደ አስተርእዮ ማርያምና መስቀል ከማክበር አያግዳቸውም[3] ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ከግራኝና ከኦሮሞ በፊት በግዛቷ በሙሉ የክርስትና ሃይማኖት ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም፡፡

## 8. ቦሻ

በቦሻ ከኦሮሞች ጋራ የሚኖር ሕዝብም ከትግራይ መምጣታቸውን ለማስታወስ "ቲግር ቦሻ" ተብለው ይጠራሉ፤ በሀገራቸው የቤተክርስቲያን ቅሪቶች ይታያሉ፤ ብዙ ዘመን ከአዋሽ በስተደቡብ ይኖሩ እንደነበረ ያወራሉ፤ በዚሁ ጊዜም ሀገሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ስር ሆኖ እናሪያ ተብሉ ይጠራ ነበር፡፡ በኦሮሞች ተገፍተው ከሀገራቸው ተፈናቅለው፣ በመጀመሪያ አሁን ቦቶር ባሉበት ይኖሩ ነበር፣ በመጨረሻ አሁን ባሉበት ሰፈሩ፡፡ ቋንቋቸው ከካፊቾ ተመሳሳይ ነው፡፡

## 9. ዋሬታ

በአጠቃላይ ስማቸው ዋሬታ ወይንም ዳውሮ ተብለው የሚጠሩ ሕዝቦች 1 ኩሉ 2 ኮንታ 3 ኩዊሽ 4 ማሮ 5 ጉልዳ ከኦሞ ወንዝ በስተምሥራቅ የሚገኙ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያውያን ታሪክ አዋቂዎች ደብተሮች አባባል በኢትዮጵያ ታሪክ ዝነኞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በ1300 ዓ.ም. በአፄ ዓምደ ፅዮን ዘመን መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ጋራ የተቀላቀሉ ናቸው፡፡

[1] A Cecchi : ibd p 258
[2] A Cecchi : ibd VII p 266
[3] A Cecchi : ibd p 355

ሕዝቡ ራሱም የቀድሞ የኢትዮጵያ አገዛዝ በሚገባ ያስታውሳል፡ ከአጼ ዓፄ ዮሐንስ ወታደሮች ጋራ ዘራቸው በጋብቻ የተደባለቁ መሆናቸውና በሀገራቸው ከብዙ ዘመን ጀምሮ እንደኖሩ ያወራሉ፡፡ የኢትዮጵያ አገዛዝ ምልክቶች ብዙ የትግሪኛ ቃላቶች በቋንቋቸው መገኘታቸውና የክርስትና ባሕሉት በአነስተኛ ደረጃ ቢሆኑም መገኘታቸው ለጥንታዊ ኢትዮጵያዊነታቸው በቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ እንደ ጋሮ በሻ ሕዝብ የዋራታ ሕዝብም ‟ኪስታን ወይንም" ቤት ኪስታን የሚሏቸው የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል ፣ የአባ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያኖች አሏቸው፡፡ በቤተክርስቲያኖችም በሬዎች እርደው እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ እያሉ ይጸልያሉ፡፡ በመልካቸው ወረታዎች ቁመታቸው አጠር ያለ ቢሆንም ከጥቁር ዘር ይልቅ ወደ ዓረብ ዘር ይሰባቸዋል፤ ከጉረቤቶቻቸው ከጥቁሮች የተቀላቀሉ ጠቁር ያሉም አሏቸው፡፡ ከዋራታዎች መሐል የኩሉ መንግሥት በከፋ መንግሥት ስር ተጠቃልሎ ነበር፡፡ ወላሞ ክርስቲያን ነበሩ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እስልምና እየተቀበሉ ናቸው፡፡ የክርስትና እምነት የሚያኮሩ እንደ ላሊበላ ቤተክርስቲያኖች በመሬት ተቈፍረው የተሰሩ ቤተክርስቲያናት አሏቸው፡፡ ከማሉና ወላሞ በስተደቡብ ዶኮ የሚባሉ ጥቁር ሕዝብ የሚኖርበት ሀገር ነው፡፡ ኩንታ ወይንም ቆቦ የሚባል ሕዝብ ሶማሊዎች አማራ ይሉዋቸዋል ምክንያቱም ከአማራ ነጋዴዎች ጋራ የመጡ ናቸው ይባላል፡፡ ጉረቤታቸው የሆኑ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች ከፉ ናቸው፣ ሰው ይበላሉ ይሏቸዋል፡፡ የእሞ ወንዝ ከዋረታዎች የተሰጠው ስም ነው፡፡

## የኦሮሞ ታሪክ የተለያዩ አስተያየቶች

ስለ ኦሮሞ ታሪክና አሰፋፈር ከተለያዩ የውጭ ሀገር ፀሐፊዎች የተለያዩ ተቃራኒ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ የቻሉት አብዛኛው ጊዜ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ማቀነባበር ባለመቻላቸው ነው፡፡ ቸኪ[1] የጠቀሳቸው ፀሐፊዎች ጋሊኒየ (Galinier) ኦሮሞች በአፍሪካ ምሥራቃዊ ደቡባዊ 5ኛ 10ኛ ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዮድ በዛንዚባር ይኖሩ የነበሩ ያደርጋቸዋል 2) Pellogrino Matteucci ፐለግሪኖ ማቴውቺ በአፍሪካ ካገኘናቸው ሕዝቦች ያስገረመኝ ኦሮሞች ነጭና ክርስቲያን በመሆናቸው ነው ካለ በኋላ ለምን ነጭ (ቀይ) ሆኑ ለምን ክርስቲያን ሆኑ ብሎ ይጠይቃል፡፡

3) Pricard ፕሪካርድ) እስከ ዛሬ ስለ ጋላ ያሉን መረጃዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ስለ ታሪካቸው የምናውቀው ነገር ባይኖርም፣ ከሥልጣኔ ሩቅ መሆናቸው ደምበኛ ኋላ ቀር መሆናቸውና የከብት ጭራ ተከትለው የሚኖሩ፣ ዘላኖች አረኞች ከኢትዮጵያ በስተደቡብ የሚኖሩ መሆናቸው ብቻ እናውቃለን ብለዋል፡፡

4)Cap. Owen (ሻምበል ኦወን) በኢኳቶሪያል አፍሪካ ጨካኝ ሕዝብ እስከ ጁባ ወንዝ የሚደርስ ጋላ ሕዝብ አለ፡፡ በባሕር ወደቦች ሶማሊዎች ይኖራሉ፣ ከጋላ ሕዝብ በጣም ይለያሉ፣ ጠባያቸው ለሰላሳ ነው፤ ጥሩ ነው፣ እስላሞች ናቸው፣ በባሕር ወደቦች ንግድ ያካሂዳሉ፡፡ ሶልት (Salt) እና ሌሎች ፀሐፊዎች ስለ ጋላ ቋንቋ ባደረጉት ጥናት ጋሎች፣ ሶማሊዎች፣ እንዲሁም አፋሮች አንድ ትውልድ ሀረግ እንዳላቸው ያሳያል ብሏል፡፡

[1] A. Cecchi : ibd VII p 496



5 ፈደሪኮ ሔልወርድ (Federico Hell ward) ኦሮሞች የሰፈሩበት መሬት እስከ ትልቁ የአፍሪካ ተራራ ኪሊማንጃሮ ይደርሳል፣ እንደ ሶማሊዎች ከጥቁር አፍሪካ ሕዝብ ጋራ አይመሳሰሉም ብሏል፡፡

6 ግራፕት(Grapt) ጋላ ወደ ሰው ሀገር ሄዶ የሚሰፍር ማለት ነው ብሏል፡፡

7 ብሬነር (Brenner) በባሕር ዳርቻ ያሉ ሕዝቦች ጋላ ማለት ሃይማኖት የሌለው ሰው ያደርጓቸዋል፡፡

8 ጋሎች ራሳቸው ኦሮሞ ተብለው ይጠራሉ ትርጉሙም ኃይለኛ ጀግና ማለት ነው

9 ብሩስ (Bruce) ጋላ በመጠኑ ቀያይ ናቸው፣ ጠጉራቸው ጥቁር ረዘም ያለ ነው፣ በቆላ የሚኖሩ ግን በጣም ጥቁር ናቸው ይላል፡፡

10 ውድ (wood) ጋላ በቆዳቸው ቀለም ከሐበሾች ይጠቊራሉ፤ ከዚሁ በመነሳት Johnstone (ጆንስቶን) የተባለ ፀሐፊ የጋላ ቃል ትርጉሙ ከካላ የመጣ ጥቁር ማለት ነው ብሏል፡፡

11. ለፌርቭር (Lefevre) ስለ ጋላ ቢያውሳም ስለ ዘራቸው ያለው ነገር የለም፡፡

12. ሃርትማን (Hartman) ጋላ ዋና ሀገራቸው ከኪሊማንጆሮ ተራራ ስር ነው፣ ንፁሕ ጥቁር ናቸው፣ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ሰፍረዋል፣ ከበጁ፣ አገውና ሐበሾች ጋራ ተዋሕደዋል ብሏል፡፡

13 ቸኪ የራሱ ሃሳብ ብሎ የሚያጠቃልለው ጋላ ከዓረብ ሀገር ወደ አፍሪካ መጥተው የቀድሞ ነዋሪዎችን አባርረው ከማንም ዘር ሳይቀላቀሉ የሚኖሩ ናቸው፡፡

## 2. የኦሮሞ አፈ ታሪክ

14. ቸኪ የኦሮሞች አፈ ታሪክ፣ ብዙ የሀገር ሽማግሌዎች የተለያዩ ጐሣዎችን ጠይቄ ያገኘሁት ነው ብሎ እንደሚከተለው ያቀርበዋል፡፡ ኦሮሞች ሁሉ በአንድ ድምጽ "እኛ የአንድ ሽማግሌ አባት ልጆች ነን፣ እሱም ኢላው ይባላል የከነአግ ጐሣ፡፡ ሐዳር የምትባለው ሚስቱ አገባና ኢሊፋስ ወለደች፣ ኢሊፋስም አመር ወለደ፡፡ ለቀድሞ እናታችን /አያታችን/ ሐደር ከብር እናት ለማለት ሐዳር እንላለን፡፡ ወደዚሁ ሀገር ከመምጣታቸው በፊት አባቶቻችን ገላድ የሚባል ሀገር ይኖሩ ነበር የኦሮሞ ልጅ መሬት ስለጠበበው ከጐሣው ተለይቶ ባሕር ተሻግሮ በርበራ ገባ፣ ከበርበራም ወደ ሐረር መጣ፣ ቀጥሎም ከአርሲ አጠገብ በወላሞ ሀገር ሰፈረ፡፡ ከኦሮሞች መሐከል አንድ ትልቅ አለቃ መሐን በመሆኑ ልጅ መውለድ ስላልቻለ አንድ አማራ ሴት በሀገሩዋ ወንጀል ሰርታ፣ ወንድ ልጇዋን ይዛ ከኦሮሞች ጋራ ትኖር ስለነበረ ልጇዋን በሞጋሳ ወይንም ጉዲፈቻ ደምብ መሠረት አሳደገው፡፡ ይህ ልጅ ለመጣንበት ሀገር ማስታወሻ ስሙ ገላድ ተባለ፡፡ ከዚሁ ስም በመውለድ አማሮች ኦሮሞችን ሁሉ ጋላ ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ ኦሮሞች ገላድ በሞጋሳ ያደገ ስለሆነ ጋላ ተብለው እንዲጠሩ አይወዱም፣ በኦሮሞ መጠራት ይመርጣሉ፡፡ አሳዳጊ አባቱ ሲሞት ገላድ ከጐሣው ተባረረና በግራኝ ጊዜ ከአብቦ /ወላሞ/ ሀገር ወደ ሸዋ ጠረፍ ሰፈረ፡፡ ገላድ 3 ሚስቶች ነበሩት፣ ከእነሱም 4 ልጆች ወልዷል በኩር ልጁ ከአንድ ባሪያ የተወለደ ነበረ፣ ስሙም መጫ ተባለ፣ ሕገ ወጥ ማለት ነው፡፡ 2ኛ ልጁ አርሲ 3ኛ ቱሉማ 4ኛ ኢቱ ተባሉ፡፡ ከበኩር ልጁ ከመጫ በቀር ሌሎች ከንፁህ ኦሮሞ ሴቶች የተወለዱ ናቸው፡፡ ገላድ ሲሞት ልጆቹ በመሬት አከፋፈል ምክንያት ተጣሉ፡፡ መጫ ከአዋሽ በስተደቡብ እናሪያ በሚባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሰፈረ፡፡ በዘመኑም ኢትዮጵያ በግራኝና በቱርኮች በተከፈቱባት ጦርነቶች ተቋክማ

የአክሱም ንጉሥ እሬላስ የዘመተበት ዘመን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፊደልም ከሳባውያን የተወሰደው በዚህ ዘመን በመሆኑ የሳባ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያገባ እሬላስ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ፊደሉ የተሻሻለውም በኢዛና ንጉሥ ዘመነ መንግሥት መሆኑን አጠያያቂ እይሆንም ብዬ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ሳባውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ እሬላስ መሆኑን ብለን መገመት እንችላለን፡፡

7. ከእሬላስ በፊት የነበሩት ነገሥታት በሐውልቶች ያስቀርጸዋቸው የነበሩ ጽሑፎች እሬላስ ራሱም ተከታዩ ንጉሥ ኢንዲቢቢስም ይጠቀሙ የነበሩ በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ተኮሉ የንጉሡ ንጉሥ ዋዜብ ግን በኢትዮጵያ ፊደል ቫወል የሌለው ተጠቅሟል፡፡ ከእሱ ተኮሉ የነገሡ ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ ኢዛና እንደእስፈላጊነቱ በሳባ፣ በግእዝ፣ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ቫወል የሌለው በመጨረሻም በግእዝ ፊደልና ቋንቋ ቫውል ያለው ይጠቀም እንደነበረ ታውቋል፡፡ ስለዚህ ከሳባውያን ተወስዶ ተመሳሳይ ፊደል በኢትዮጵያ የተፈጠረው ኢትዮጵያዊ ፊደል እንደሚባለው ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት የመጡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስተኛ እስከ ሁለተኛ ያለው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይሆን ኢትዮጵያ በእሬላስ ንጉሥ መሪነት ዘመቻ አካሂዳ የመንን ከግዛቷ ያጠቃለለችበት ጊዜ በ4ኛው መቶ ክፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሲሆን፣ ስራ ላይ የዋለውና የተሻሻለውም በንጉሥ ዋዜብ እና በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት መሆኑን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች በተጨማሪ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከእሬላ የየመን ዘመቻ በፊት የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ የሚያመለክት በታሪክ የተመዘገበ ነገር የለም፡፡ ለወደፊት በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ ሌላ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ባሉት ጥቂት ማስረጃዎች መሠረት ግን ከንጉሥ እሬላስ በፊት የአክሱም ነገሥታት በድንጋይና በሐውልቶች ጽሑፎቻቸው ይጠቀሙበት የነበሩት ቋንቋ ዓለም አቀፋዊ እውቅና በነበረው በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ብቻ እንደነበረ እንረዳለን፡፡ እንደ ኮንቲ ሮሲኒ አገላለጽ ንጉሥ ኢዛና ከግሪክ ቋንቋና ፊደል በተጨማሪ በሳባና በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ያጻፈው ዝናው በአካባቢ ሀገሮች እንዲታወቅለት በማሰብ ሲሆን፣ በሳባ ፊደል፣ በግእዝ ቋንቋ የሳባ ቋንቋ አንዳንድ ጊዜ የተቀላቀለበት መገኘቱ የሳብያውያን ቋንቋ በቤተመንግሥቱ እንብዛም እንደማይታወቅ የሚያስረዳ ምልክት ነው ብሎ:ታል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ይገዛ የነበረው የደቡብ የመን እንዲገባቸው [1] የኢትዮጵያ ነገሥታት በሐውልቶቻቸው በሳባ ፊደልም ይጽፉ ነበር፡፡

አንድ ሀገር ቋንቋው በፊደል ጽፎ ከተጠቀመ እስተድሞ በሥልጣኔ የደረጀ መሆን ይጠበቃል፡፡ እኛ የሥልጣኔ ቀደምትነት ያለን እንደመሆናችን መጠን የተሻሻለ ፊደልም በእሬላስ ዘመቻ ዘመን ከየመን ወስድን እንጂ፣ ደቡብ ዓረቦች ጊዜው በትክክል የማይታወቅ ዘመን ወደ ሀገራችን እምጥተው ሰጡን እስተማሩን ማለት ልዘወለድ ታሪክ ነው፡፡

(1) Conti - Rossini ibd p 132



## 6. የአክሱም መንግሥት ወደ ዓረብ አገር ተሻግረው የተካሄደው ቅዱስ /የመስቀል/ ጦርነት[1]

ዘመቻው የተካሄደው በንጉሥ ካሌብ በ525 ዓ.ም ነበረ፡፡ የተካሄደበትም ምክንያት የጥንት አምልኮት ተከታይ የነበሩ ዓረቦች በክርስትና ተከታይ ዓረቦች ያደረሱት በደልና የጅምላ ጭፍጨፋ ለመበቀል ነበር፡፡ በዚሁ የአክሱም መንግሥት ጣልቃ ገብነት ዘመቻ መካሄድ ብዙ የማስረጃ ምንጮች አሉ፡፡ ነገር ግን በብዙ መንገድ እና አስተያየት ታሪኩን የሚገልጹ ሆነው፡፡ የኢትዮጵያ የመስቀል ጦርነት ከአውሮጳውያን የመስቀል ጦርነቶች የሚለይበት በአውሮጳውያን በወዶ ዘመቻች የተካሄደ ሲሆን የኢትዮጵያ ግን በንጉሡ የሚመራ ነበረ፡፡

1. ከኮዝማስ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ቀድቶ ለታሪክ ያስቀረ
2. ከቢዛንታይን
3. ከሶርያ
4. ከዓረብ
5. ከኢትዮጵያ ወገን ምንጮች ናቸው፡፡

ጦርነቱ ለ 3 ክፍል መከፈል ይቻላል

1ኛ. በመጀመርያ የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው የዘሮቢያ ዓረባዊ መንግሥትን ለመረዳት ይሁን እንጂ፣ ከግዙፍ የሮማ መንግሥት ጥቃት፣ ፀረ- ሮማ መንግሥት ነበር፡፡

2ኛ. በሁለተኛው የአክሱም መንግሥት ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ያበሻ ዘሮች ከጭፍጨፋ ለማዳን ፀረ ሳባዊ መንግሥት ነበር፡፡

3ኛ. የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ሃይማኖታዊ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ከእልቂት ለማዳን ፀረ - ሂሚያር ይሁዳዊ ዓረባዊ መንግሥት ነበረ፡፡ የ1ኛና 2ኛ ጦርነቶች የተካሄዱት በኢትዮጵያ ፍላጐት ብቻ ሲሆን 3ኛ ጦርነት ግን ተጠቃሚና እይዞሀ ባይ 3ኛ. ወገን ትልቁ የቢዛንታይን መንግሥት እጅ ነበረበት፡፡ ይህ መንግሥት ራሱ ምንም ሳይንቀሳቀስና ለጦርነቱ አስተዋፅኦ ሳያደርግ የአክሱም መንግሥትን ብቻ በቀጥታ ልመና በመገፋፋት፣ እንዲሁም የግብፅ እስክንድሪያ ፓትርያርክም የደቡብ ዓረብ ክርስቲያኖችን እንዲረዳ የአክሱም መንግሥትን እንዲያግልዱ በማድረግ፣ በውጭ ኃይሎች ግፊት የተደረገ ጦርነት ነበር፡፡ የቢዛንታይን መንግሥት የፔርሲያን መንግሥት ለማሸነፍ ስላቃተው ኢትዮጵያን መሣሪያ ያደረገበት ብቻዋን በጦርነት እንድትካፈል ያጋለጣት ወቅት ነበር፡፡ ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ፍልሚያ በሚያደርጉበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጥቅም በማይነካ ጉዳይ ብቻዋን በጦርነት አዘቅት መግባት አይገባትም ነበር፡፡ ስለጉዳዩ ዝርዝር ስንገባ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ድል አግኝታለች፣ ለሃምሳ ዓመታት የመንን ገዝታለች፡፡ አንዳንዶቹ 72 ዓመት ያደርጉታል እስከ 597[2] ነገር ግን የዓረብ ሕዝብ ጥላቻ ብቻ ነበር ያተረፈችው፡፡ ዘመቻው ግዙፍ ነበር፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቀይ ባሕርን ሲያቋርጡ በ191 በቢዛንታይን የንግድ መርከቦችና በ170 እኔ

C. Conti - Rossini ibd p 167
C. Conti - Rossini ibd p 199

ካሌብ ባሰራቸው መርከቦች ተሳፍረው ነበር። የመን የደረሱትና አጼ ካሌብ ዘመቻ ያካሄደው በሁለት ዙር ነበር።

በመጀመርያ ጦርነት ሳይገጥመው የኢምየር ንጉሥ እጁን ስለሰጠ ወደየውኑ አጼ ካሌብ ራሱ የሾመው በየዓመቱ ግብር የሚከፍል ክርስቲያን ንጉሥ ትቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ። ነገር ግን ስለከዳውና የክርስቲያን ጭፍጨፋ ንጉሥ ትቶ ወደ ሀገሩ ... ስለቀጠለ እንደገና ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ይዞ ከዓረቦች ጋራ ጦርነት ገጥሞ ድልን ተቀዳጀ። ኢምየር ንጉሥ ሸሽቶ በፈረስ እየጋለበ ቀይ ባሕር ውስጥ ገብቶ ሞተ። አዲስ የተሾመ ንጉሡም ብዙ አልቆየም አጼ ካሌብ ንጉሥ አድርጎ የሾመው አብርሃ የተባለውም ወዲያውኑ ከዳ። ከኢትዮጵያ ወታደሮች ግማሾቹ ከዓረብ ሀገር ተባረሩ። በመጨረሻ አብርሃ የንጉሥነት ስልጣን ነጥቆ ያዘ። ቆይቶ ከአጼ ካሌብ ወኪል ጋር ቢታረቅም እንደ ነፃ ንጉሥ ሆኖ ሀገሩን ይመራ ነበር። በኢትዮጵያውያን በኩል እስከ ዘመናችን ድረስ አጼ ካሌብ እጽብሀ ተብሎ እየተጣራ አብርሃ ወአጽብሀ እየተባለ ከአቡነ ፍርሚናጦስ ከሣቴ ብርሃን እኩል ወደ ኢትዮጵያ ክርስትና ያስገቡ ተብለው እንደ ቅዱሳን ይከበራሉ። በዓረቦች ዘንድ ግን ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ጥላቻ ነበረ ያተረፉት። የሕዝብ ዘፈኖች ፀረ- ኢትዮጵያ የጭቆና አገዛዝ ነበሩ። የዘመኑ የዓረብ ጸሐፊዎች "ሴቶች የሚገርዙ፣ የቁላ ብሊታዎች" ወዘተ... እያሉ ኢትዮጵያውያንን እያጥላሉ ይፅፉ ነበር። የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች የሚተርኩት በኢትዮጵያና በደቡብ ዓረብ ያለው የስጋ ዝመድና የሚያስታውስ ሲሆን፣ ከዓረብ ወገንም ሆነ ከኢትዮጵያ ወገን ግን ይህን ዝምድና የሚያስታውስ ምንም ማስረጃ የለም።

ዓረቦች ብቻቸው ከኢትዮጵያ ቀንበር አገዛዝ መላቀቅ ስላልቻሉ ለቢዛንታይን መንግሥት ሰሞቻቸውን ሊያሰሙ የሚያዳምጧቸው ስላጡ ፊታቸው ወደ ፋርስ ንጉሥ አዞሩ። ፋርስ ከቀይ ባሕር ብዙ የሚርቅ ሀገር በመሆኗ፣ ቀይ ባሕር ለመድረስም በረሀማ ቦታዎች አቋርጣ ማለፍ ስለሚያስፈልግ፣ በደቡብ ዓረብ አስተዳደር ጣልቃ እንድትገባና የዓረቦች ጥያቄ ለመቀበል ቀላል አልነበረም። በመጨረሻ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያላት መሆኑን ስላወቀች 800 ወታደሮች ብቻ በመላክ የመንን ይገዛ የነበረው የአብርሃ ልጅ ማብሩክ የተነሳበት የሕዝብ ዐመፅ በቁጥጥሩ ስር መዋል ስላልቻለ በፀረ ኢትዮጵያ ዐመፀኞች እየተረዳ የፋርስ መንግሥት በቀላሉ ድል ሊቀዳጅ ችሏል። ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዓረብ የተወለዱ ክልሶችም ጭምር ተገደሉ። ኃይለኛ እንደ አጼ ካሌብ ንጉሥ በኢትዮጵያ ቢኖር ኖሮ ለኢትዮጵያ ታሪክና ሕልውና ከሃይማኖት ጉዳይ ሌላ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለነበረ ሌላ የተጠናከረ ዘመቻ ማድረግ ባስፈለገ ነበር። ይህ ባለመደረጉ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት መሆኗ አከተመ። ቀይ ባሕርም እንደ ጥንቱ ያበሻ ባሕር ኢትዮጵያዊ የሚል ስያሜ ተሽሮ በግሪኮች አጠራር ለዘለቄታ ቀይ ባሕር ተባለ የሶማሌ ባሕርም ባርባሪያ ባሕር ተብሎ ይጠራ የነበረው ሕንድ ውቅያኖስ ሆነ። የአዛንያ አጠራርም ተሰርዞ ሶማሌ ኬንያ ታንጋኒካ ወዘተ... የሚል ስም ተሰጣቸው፣ ኢትዮጵያ ግዛት ክልል ከባብ ኤል መንደብ በስተ ደቡብ ያለው አጣች። ለጥቂት ጊዜ ኢትዮጵያ ከዓለም ታላላቅ መንግሥታት ቁጥር ገብታ የነበረችበት ነበረ።[1] በአንፃሩም የውድቀቷ መጀመርያ ምዕራፍ ሆነ።

ከሰለጠነ ዓለም ለመገናኘት በየብስ በግብፅ በኩል እንዳትገናኝ ግብፅ እንደቀድሞ ክርስቲያናዊት አፍሪካዊት ሀገር መሆኗ ቀርቶ እስከማዊት

[1] C. Conti - Rossini ibd p 200



ዓረባዊት ሀገር ስለሆነች፣ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነት ውሱን ነበር። የባሕር በርም ምንም እንኳን ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ብሎ ቢወድሰም በሀገሩና በእስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ ሀገሮች በኩል ሁሉ ለኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት ውለታ ያሳዩት በጎ አመለካከት አልነበረም። ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ለመሄድ የሚሞክሩ ምእመናን ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ የሞት ዕጣ ነበር የሚጠብቃቸው። በአንፃሩ የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የእስልምና ሃይማኖት ስብከ ተስፋፍቶባቸው ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ከፋፈሉን። በመጨረሻም በተለይ በመሐመድ ግራኝ ጊዜ ለእርስ በርስ ጦርነት ገፋፍተው ኢትዮጵያን ለባሰ ለሥልጣኔ ኋላ ቀርነት ዳረጓት። የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷ የተከፈላት ውለታ በጠላትነት ነበረ። የአክሱም መንግሥት ውድቀት በደረሰበት ዘመን በ705 715 ዓ.ም. በሰሜናዊ ዐረብያ ከሙት ባሕር 100 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ በአንድ በአማያዲ ቤተ መንግሥት ሕንፃ የካሊፎች መዝናኛ ቦታ በትልቁ ዋና ክፍል ግርግዳ ላይ በካሊፋ የተሸነፉ 4 ከዓለም ታላላቅ ነገሥታት ተስለው ይገኛሉ. እነሱም[1]

1ኛ. የቢዛንታናዊ ቀሳር ንጉሠ ነገሥት
2ኛ የፋርስ ንጉሥ ኮስርዮ
3ኛ. የስፓኝ የመጨረሻ ቪዚጎት ንጉሥ ሮድሪጎ
4ኛ. የኢትዮጵያ ንጉሥ ናጃሺ ናቸው።

## 7. <u>በሰሜን ኢትዮጵያ የታሪክ ቅሪቶችና ቦታዎች</u>

ስለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቦታዎች ስናስታውስ ትዝ የሚሉን አብዛኛው "ኦቤሊስክ" ተብለው የሚጠሩ በአክሱም ቆመውና ወድቀው የሚገኙ የአክሱም ሐውልቶች ናቸው። አንድ መቶ የሚጠጉ የአክሱም ሐውልቶች "ኦቤሊስኮች" ብቻ አይደሉም የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ቅሪቶች። ደቡብ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ይዘው የመጡ ፊደላቸው ብቻ አይደለም። ኮንቲ ሮሲኒ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች በማለት አንድ ካርታ[2] አውጥተዋል በዚሁ ካርታ መሠረት በዚሁ ታሪካዊ ቦታዎች የሚገኙት ከአክሱም በስተሰሜን ከናቅፋም በስተሰሜን የሱዳን ግዛትም የሚያጠቃልሉ በባሕር ዳርቻዋም ከአዱሊስ እስከ ራሄይታ የሚደርሱ ናቸው። ከፍተኛ ስልጣኔ በዳበረባቸው ቦታዎች የከተማ የቤት ፍርስራሾች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መቃብሮች፣ አቤሶኮች፣ ዙፋኖች፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ ስእሎች እና የሸክላ ስእሎች ፈራርሰው ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ ቅሪቶች ከደቡብ ዓረብ ስልጣኔ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ሲገባ ምንም ተመሳሳይነት የላቸውም። የፈራረሱ ቤቶች የሚገኙ በጥንት ቦታዎችና በአሁኑ ጊዜ ትግሪኛ ተናጋሪ አካባቢ የሚሰሩ የቤቶች አሰራር አንድ ዓይነት ነው። አራት ማእዘን ያለው "ሕድሞ" የተባለው የቤት አሰራር ከደቡብ ዓረብ ሆነ ከግብፅ የቤት አሰራር ስለማይመሳሰል፣ በአክሱም ጊዜም የተለመደ ነው ተብሎ በመገመት አክሱማዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ክቡ የቤት አሰራር ግን በመላው አፍሪካ ስለሚገኝ አፍሪካዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ብዙ የመቃብር ዓይነቶች ተገኝቷል። ከቤተክርስቲያንና ቤተመቅደስ አጠገብ ወይንም ከምድር ቤት በልዩ ሞያ የተሰሩ ወይንም መሬት ቆፍረው ብቻ የተቀበሩ ረጃጅም ኦቤሊስኮች በአክሱም ብቻ ሲገኙ አነስተኛ ቁመት ያላቸው በብዙ ታሪካዊ ቦታዎች

[1] Carlo Conti -Rossini Storia d' Ethiopia p 124
[2] C. Conti -Rossini ibd Indice delle tavole XXVI

ይገኛሉ፡፡ ግን እንደስራቸው ለማወቅ አይቻልም፡፡ በደቡብ ዓረብ የአቤሊስክ ስራ እምብዛም የተለመደ አልነበረም፡፡

ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊሰሯቸው አይችሉም፣ ከግብፅ የመጡ ባለሙያዎች እርዳታ የተሰሩ ናቸው ከማለት በስተቀር የአሰራራቸው ታሪክ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ዙፋኖች በብዛት የሚገኙት በአክሱም ነው፡፡ በአዱሊስ፣ በዲክዲክ /ናቅፋ/ ተገኝቷል፡፡ ስእሎች፣ የሸክላ ስራ ምስሎች ወዘተ... ከማንም ሐገር በአሰራራቸው የሚቀራረቡ ሆነው አልተገኙም፡፡ ደቡብ ዓረቦች ለንግድ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚመላለሱበት ጊዜ ፊደል ብቻ አይደለም የተማሩት፣ ባለ ብዙ ፎቅ የቤት አሰራርም ከባቢሎኒያ ተምረው ወደ ሀገራቸው አምጥተው በሰፊው እንዲለመድ አድርገው ነበር፡፡

የመዳብ ማእድንን ማቅለጥና መዳቡ ላይ መጻፍ ደቡብ ዓረቦች ከክርስቶስ ልደት በፊት ተምረው ልዩ ችሎታ ነበራቸው፡፡ ከጋዛ ተምረው ባለብርና ባለወርቅ የአቴንና የሮማውያን ገንዘቦች በ4ኛ መቶ ከፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ይሰሩ ነበር፡፡ የቤተመቅደስ ፓንቴዮን የመስራት ችሎታ ነበራቸው፡፡ የዚሁ ሁሉ እውቀታቸው በኢትዮጵያ የታየ ነገር የለም፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ የጥንት የሰው ስራዎች ጥቂቶች እንኳን የደቡብ ዓረብ ናቸው የሚባሉ የሉም፡፡

ስለዚህ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሕዝቡ ጋራ ተዳቅለው አዲስ ሕዝብ ሴም ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ፈጠሩ ማለት የፈጠራ ታሪክ ነው፡፡ ሀገራችን ከጣሊያን በስተቀር በማንም ሕዝብ ተገዝታ አታውቅም አያልን፣ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት እንደ ወረዳ የቆዳ ስፋት ያላቸው ሳባውያን ገዙን፣ ፈጠሩን ብለን መናገር የማይመስል ከመሆኑም በላይ አሳፋሪም ነው፡፡ ደቡብ ዓረቦች በብዛት ስፈሩባቸው ተብለው የተገመቱ ቦታዎች ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ ያሉት ጥቅጥቅ ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች በደቡባዊ አከለጉዛይ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው፣ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ሕዝቦችም ቢሆኑ የዓረብ ድብልቅ ዘር የለባቸውም፣ የተለዩ ሕዝቦች መስለው አይታዩም፡፡ ከፍተኛ ስልጣኔ ዳብሮባቸው የነበረ ንፁሕ ኢትዮጵያውያን ዘሮች መሆናቸው ብቻ የሚታዩ በቆሐይቶ አካባቢ /አከለጉዛይ/ ተቆፍሮ የተገኙ አስከሬኖች ጠጉራቸው ጥጥ መሳይ እንደ ጥቁሮች /ኔግሮዎች/ ሳይሆን፣ ወይንም ሉጫ እንደ ዓረቦች ባይሆን እንደ አሁኖቹ ኢትዮጵያውያን በመጠኑ ከርዳዳ የሆነ ፀጉር እንደ ነበራቸው ተረጋግጠዋል፡፡ (1) የጭንቅላታቸው አጥንትም የኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተረጋግጠዋል፣ ይኸም ደቡብ ዓረቦች በሰሜን ኢትዮጵያ እንዳልሰፈሩ የሚያስረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ቆሐይቶ እንደ ደቡብ ዓረብ ተመሣሣይ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ቅሪቶች ያሉባት መንደር ናት፡፡ በአዱሊስ ይኖሩ የነበሩ ደቡብ ዓረቦች ከቀይ ባሕር ሐሩር ወጣ ብለው ብርዳማ አየር የሚያገኙበት የመዝናኛ ቦታ ነበረች የተባለች መንደር ናት፡፡ በዚሁ መንደር የዓረቦች ሬሳ ምልክት ካልተገኘ የትም ቦታ ሊገኝ አይችልም፡፡ ቆሐይቶ እንደ መንደር የሚቆጠር አይደለም፡፡ ከአክሱም በፊት የአክሱማውያን ዋና ከተማ የነበረ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ይህ ባይሆንም ከቆሐይቶ እስከ አክሱም ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች ፍርስራሾች እንደ ትኩንዳሰ፣ ክስክሰ፣ ሰንዓፈ ወዘተ... የሚያጠቃልል ከፍተኛ ታሪካዊ የሐውልቶች ፍርስራሾች የሚገኙባቸው ራሳቸው የቻሉ እንደ ግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች የሚቆጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ለማለት የሚያሰኝ ነው፣ ለምርምር በቂ ቁፋሮዎች

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 237



አልተደረገም፡፡ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ቁፋሬዎች ያተኮሩት በአክሱም አካባቢ ብቻ ነው፡፡ ፐሪፕለ የቀይ ባሕር ዙሪያ ጉዞ የሚል መጽሐፍ የደረሰው ሰው አክሱማውያንን የሚገዛ ዞስካለስ የተባለ በጣም ስስታም የሆነ ገንዘብ ማጠራቀም ብቻ የሚወድ በሌላ በኩል ግን ጉበዝና የግሪክ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ(1) ንጉሥ ነበረ ብሎ ጽፏል፡፡ ዞስካለስ ይኖር የነበረ በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 2ኛው አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን የሳባ ቋንቋና ፊደል ከማወቃቸው በፊት የግሪክ ቋንቋ ያወቁ እንደነበረ የሚጠቁም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ለማወቅ በቂ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ባይደረግም ከመሬት በላይ የሚታዩ ቅርሶችና አሻራዎች በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ከከሰላ እስከ ሐይቅ (ወሎ) በብዛት ይገኛሉ፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ምንም እንኳን እነዚህ የታሪካችን ምልክቶች በውጭ ሀገር ሰዎች የተሰሩ ናቸው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ የአናሳ ሴማውያን ሥልጣኔ ነው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ ሐውልቶቹን ከመረመረ በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም ከሚገኙ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ካላቸው ሀገሮች መካከል በእኩል ደረጃ እንድትሰለፍ የሚያስችሏት መሆናቸው ጽፏል(2) ፡፡

በአክሱም ከሚገኙ ቁጥራቸው አንድ መቶ የሚደርሱ አቤሊስኮች አንዱ በቁመት በመላው ዓለም ከሚገኙ ተመሳሳይ ሐውልቶች አንደኛነት ያለው ነው፡፡ ላሊበላ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በዓይነታቸው በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው ተብለው ተደንቀዋል፡፡

## 8. የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን

ስለታወቀው የምዕራባውያን ሀገሮች የጨለማ ዘመን (Middle Age) ተብሎ የሚጠራ ታሪካቸው በዚህ መጻሐፍ መግቢያ ላይ አስተያየቴን ሰጥቻለሁ|፤የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የምዕራባውያን ተመሳሳይ የሆነ የታሪካችን የጨለማ ዘመን አለ ብለው ጽፈዋል፡፡ የሀገራችንና የምራእባውያን ሀገሮች ታሪክ የተለየ ቢሆንም እንደ አጋጣሚ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ በሁለቱ ሀገሮች የክርስትና ሃይማኖት ከገባበት ዘመን ጀምሮ ነው፡፡ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የጨለማ ዘመን ብሎ የሚጠራው ከናግራን፣ በአጼ ካሌብ ዘመን፣ በ525 በተደረገው ጦርነት እስከ ዩዲት መነሳት 942 ዓ.ም. 317 ዓመት ያለው ጊዜ ነው፡፡ የተባለበትን ምክንያት ሲያብራራ የአክሱም ነገሥታት የሰሩትን ሥራ በታሪክ የተመዘገበ ስላማይገኝ ነው፡፡ በኤውሮጳውያን የጨለማ ዘመን ትርጉሙ አንድ ሀገር ከነበረው ከፍተኛ ስልጣኔ ወደ ኋላ የተመለሰበት ዘመን ነው፡፡

ሀገራችን በእነ ንጉሥ ኢዛና እና አጼ ካሌብ ከነበረው ባለ መልካም ዝና ታሪኳና ስልጣኔዋ ወደ ኋላ መመለስ የጀመረችበት ጊዜ ከአጼ ካሌብ ጀምሮ መስሎ አይታየኝም፡፡ የሀገራችን ታሪክ ከምዕራባውያን ሀገሮች በማመሳሰል ብንፈልግ እንኳን የጨለማ ዘመን ተብሎ መጠራት የሚገባው ከአጼ ካሌብ ከናግራን ጦርነት ጀምሮ መሆን የለበትም፡፡ የታሪክ ማስረጃ በመጥፋቱም ታሪክ አልተሰራም ለማለት አይቻልም፡፡ ከንጉሥ ኢዛና በፊት ወደ ሰሜንና ደቡብ ዓረብ የተደረጉ የአክሱም ዘመቻዎች ማስረጃዎች የተገኘ

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 119
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 239

በአጋጣሚ ከሀገራችን ወጪ ነበር፡፡ ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን አለ ቢባልም መጀመር ያለበት ከእስልምና ሃይማኖት መከሰትና መስፋፋት በኋላ በተለይም ግብፅ በዓረብ እስላሞች ስር ከወደቀችበት ዘመን ከ 642 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚሁ ዓ.ም ጀምሮ ግብጽና ኢትዮጵያ የክርስትና የጋራ እምነታቸውና ግንኙነታቸው ባይቋረጥም አደጋ ላይ የወደቀበት ዘመን ኮፕቲክ የአንድ የክርስቶስ ባሕርይ የክርስትና እምነት ተከታዮች ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያ ግንኙነቷ የተቋረጠው ከግብጽ ጋራ ብቻ አልነበረም፡፡ ከሰለጠኑ ምዕራባውያን የክርስትና እምነት ተከታይ ሀገሮች ሁሉ ጭምር ነበረ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነቷን እና ሕልውናዋን ለመጠበቅ ለብዙ ዘመናት የትጥቅ ትግል የጀመረችበት ዘመን ነበር፡፡

ስለዚህ ይህ ዓመተ ምሀረት ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን የጀመረችበት ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ የሀገራችን ታሪክ ከ7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን[1] የጨለማ ዘመን 500 ዓመት ያደርሰዋል፤ ከ7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ ሰለሞናዊ ነገሥታት በሰልጣን እስከ ተመለሱባት ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ በዚሁ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ የምናገኛቸው ከተለያዩ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ነው፡፡ የጨለማ ዘመን ከመግባቱ በፊት በ525 እንደ ግሪካዊ ግብፃዊ ዜጋ የሆነው ኮዝማስ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ሰፊ ታሪካዊ ዘገባዎች ተንትነዋል፡፡ ወደ ሕንድ ሀገር በምሄድበት ጊዜ ባርባርያ /ሶማልያ/ በጎበኘበት ጊዜ ከሶማልያ ጥን የነበረውን የዘንግ መንግሥት ለመጎብኘት ፈልጎ ነበር፡፡ ነገር ግን ባሕርተኞች ስላስፈራሩት ፍላጎቱም አልተሳካለትም፡፡ ከሕንድ ሀገር ሲመለስ አዱሊስ እና አክሱምን ጎብኝቶ በመሬት እስከ አባይ በመሄድ ግብፅ ሀገር ገብቷል፡፡ ኮዝማ እንደጻፈው አዶሊስ የንግድ መናኸሪያ፣ግሪኮችና ሮማውያን ነጋዴዎች የሚያዘውትሩባት ናት በማለት ጽፏል፡፡ በንግድም የምትገናኘው ከየመን ብቻ አይደለም፤ ከፔርሲያ፣ ከሕንድ እና ከሰይሎን ጋራም ትገኛለች፡፡ አክሱም ከብለሚዮች ጋራ በወዳጅነት የተመሰረተ ግንኙነት አላት ከባርባሪያን ጋር በመሬትም በባሕርም ትገናኛለች፡፡ አዱሊስና አክሱም ሐውልቶችና ቤተክርስቲያኖች አሏቸው፡፡ ኮዝማስ አጼ ካሌብ የመንን ለመውረር ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ ተመልክቷል፡፡ ኮንቲ ሮሲኒ ከአጼ ካሌብ የየመን ዘመቻ በኋላም ቢሆን ኢትዮጵያ በ6ኛና 7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ሰልጣኔዋን እና የክርስትና ሃይማኖትን ወደ ደቡብ አስፋፍታ እንደ ነበረ የሚያመለክት ሰሜን ሱማሊያ፣ የሶኮትራ ደሴትም ጭምር ክርስቲያን ሆነው እንደነበሩ ብሎ ጽፏል፡፡ /ለ/ 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ግንኙነቷ ከደቡብ ዓረብ ጋራ ሲሆን 7ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ግን በእስልምና ሃይማኖት መመስረት ምክንያት ግንኙነቷ ከሰሜን ዓረብ ሆኗል፡፡ የሀገራችን ታሪክ በዚሁ ዘመን እና በሚቀጥሉት ዘመናት ለማወቅ የምንችለው ከዓረቦች ጸሐፊዎች ምንጮች በምናገኛቸው ማስረጃዎች ብቻ ነው፡፡ በዚሁ ጊዜ የዓረቦች አስተያየት ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነበት ሀገር፤ ሰደተኞች ዓረቦችን የምትቀበል ተብላ ትታወቅ ነበር፡፡ ታማኝ የነቢዩ መሐመድ ባርያዎች ኢትዮጵያውን ነበሩ፡፡ ነቢዩ መሐመድ በዓለም ከነበሩት 6 ታላላቅ ነገሥታት የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ደብዳቤ ከላከላቸው ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበረ፡፡ ነቢዩ መሐመድ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋራ የወደጅነት ግንኙነት ነበረው፡፡ "ካልነኳችሁ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ነገር አትጫሩ፣ 9/10 የሰው ዘር ድፍረትና ጀግንነት ለጥቁሮች ነው የተሰጠው"

[1] Conti - Rossini ibd p. 323



በማለት ነብዩ መሐመድ ለቅርብ ረዳቶቹ የተናገረው ቃል ስለኢትዮጵያውያን የነበረው አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

/ሐ/. በ872 ዓ.ም. አል ላኩቢ (Ahmed Ibn Wadhih Al- La - Kubil[1] የተባለው የዓረብ ታሪክ ጽሐፊ ዓለምአቀፍ ታሪክ በሚለው መጸሐፍ ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፍ ከናይል ወንዝ እስከ ቀይ ባሕር ብዙ ነገሥታት እንዳሉ ይዘረዝራል 1ኛ. የናኪስ ዘር የተባሉ ጎሳዎች ከአስዋን እስከ ባርካ የሚደርስ፣ ዋና ከተማው ሐጂያር 2ኛ ባክሲን ይባላል 3ኛ. በአዘን 4ኛ ጀረን 5ኛ. ከታአብ 6ኛ. የናጃሺ መንግሥት ሰፊና ኃይለኛ ነው፣ ዋና ከተማው ካባር ነው፡፡ በግዛቱ ውስጥ ብዙ ከተሞች አሉት፣ ዓረቦች ለንግድ ይሄዳሉ፣ የባሕር ዳርቻው ዳህላክ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዙ ነገሥታት በአንድ ንጉሥ ይታዘዛሉ፣ ግብርም ይከፍላሉ፤ ሃይማኖታቸውም ክርስትና ነው፣ የመጨረሻ በስተደቡብ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከሲንድ የሚዋሰን የዘንግ ንጉሥ ከደቡብ ሶማልያ በስተደቡብ ይገኛል፡፡ የዓረብ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸው ንግድ ብዙ ነው፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለችም ብለዋል፡፡

/መ/. ማሱዲ (Masudi)[2] የተባለው የታወቀው የዓረብ ታሪክ ጸሐፊም እስከ ማዳጋስካር ድረስ ብዙ ጉብኝት አድርጎ ራሱ በቀጥታ ስላየው ነው የሚጽፈው፡፡ በመጨረሻ ጊዜ በ916/7 ጉብኝት ስላደረገበት ስለ ኢትዮጵያ በሚያደርገው ዘገባ፤ ኢትዮጵያ የበለጸገች ሀገር ናት ብሎ ጽፏል፡፡ ዋና ከተማዋ ጋባር ናት፤ ሌሎች ብዙ ከተሞችም አሉ፤ ግዛቷ እስከ ሐዘሻ ባሕር ይዘልቃል፡፡ በዚሁ ባሕርም ዘይላ ዳሕላክና ባጼ /ምፅዋ/ የተባሉ ወደቦች አሏት፡፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዓረቦች በሰላም ግብር እየከፈሉ መኖር ይችላሉ፡፡ ኢትዮጵያ በብልጽግና ዘመን እንደነበረች የሚያስረዳ በንጉሡና በየመን መሪ ኢብራሒም ቤን ዚያድ በ901-2 የተደረገው የወዳጅነት ውል መሠረት የንግድ መርከቦች ብዙ ሸቀጦች ይዘው በ3 ቀን ውስጥ በሁለቱ ሀገሮች ለንግድ ያመላልሱ ነበረ እያለ ጽፈዋል፡፡

/ሰ/. ኦማር የመናዊ የተባለው ሌላ የዓረብ ታሪክ ጸሐፊ በአባቱ በኢብራሂም ተተክቶ በ981-2 ዓ.ም. የየመን መሪ የነበረው አቡ አል (Abu Al ) ጂያይስ ኢሳክ Jiais Jshak የተባለው ለ80 ዓመት በስልጣን የቆየው ከኢትዮጵያ ጋራ ግንኙነት እንደነበረው እና ስጦታ በማበርከትም ወዳጅነትን ይፈልግ እንደነበረ ጽፏል፡፡

/ረ/. 977/8 ዓ.ም. የጅግራፊ ምሑር የነበረው አቡ አልከሲም Abu - Alkasim ኢብን ሀውካ የተባለው የዓረብ ተወላጅ ስለዘይላ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ክፍለ ግዛትና በሁሉም ባሕር ዳርቻ ከየመን ፊት ለፊት የሚኖሩ በንግድ ከየመን ጋራ መልካም ግንኙነት ያላቸው ናቸው ካለ በኋላ የኢትዮጵያ መሬት ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለም ብሏል፡፡

/ሠ/. በ951 -2 ሌላ ዓረባዊ የጅግራፊ ምሑር አል እስታክሀሪ Al - Istakhri የተባለው ተመሳሳይ ሀሳብ ገልጧል፡፡ በተደጋጋሚ ዘይላ ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያን መሆኗ መጠቀሱ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ደቡብ መስፋፋቱን

[1] C. Conti - Rossini ibd p. 274

[2] C. Conti - Rossini ibd p. 281

ያመለክታል። የዚህ መስፋፋት ከሚታዩ ብዙ ታሪካዊ ማስረጃዎ እንደምሳሌ የሚከተሱት መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ማስፋፋት ማተኮሩዋ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች አንዱ በ1154 ዓ.ም. ኤድሪስ የተባለው የሲሲሊ ንጉሥ የጆዮግራፊ ምሁር ስለዓለም እቀፍ የጂዮግራፊ በደረሰው መጽሐፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ እንስቶ ሲጽፍ የኢትዮጵያ የባሕር ወደቦች ምጽዋ ምንም ሳይጠቅስ ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ መርካ ሌሎችም የደቡብና የሰሜን ሶማሊ ጠቅሶ ጽፏል። ወደ ስሜንም ታጁራ ዳህላክ እና ሰዋኪም የኢትዮጵያ ወደቦች ናቸው ብሎ ጽፏል። ሌሎች እንደ ኢበን ሰኢድና አልዲማሰኪ የተባሉ የዘመኑ የጂዮግራፊ ምሁራን ዓረቦችም ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምቃዲሾ፣ መርካ፣ የኢትዮጵያ ወደቦች መሆናቸውን ጽፏል።

/ቀ/. [1] የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በ921-933 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ አቡነ ጴጥሮስ በተላኩበት ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ግዛት ሰፋት ሲጽፍ ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ በመሆኗ የተነሳ ንጉሡ ጉብኝት ለማድረግ ሲፈልግ ሀገሩን ጉብኝት ለመጨረስ 1 ዓመት ይወስድበት ነበር ብሏል። በላሊበላ ዘመን ጊዜ 1210 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መልክተኞች ካይሮ መጥተው ስለነበረ ስለ ኢትዮጵያ ለማወቅ ፍላጎት ከነበራቸው ብዙ ሰዎች አንዱ አቡ ባሊሕ ሻዲድ ኢብን ባና የተባለው የአርመን ተወላጅ በደረሰው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከዳዊት ዘር አይወለድም፣ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ በነበረበት ጊዜ ከንጉሡ ሴት ልጅ ጋራ በተደረገው ጋብቻ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘር የሚሆነው ሊወለድ ችሏል ካለ በኋላ፣ ንጉሡ በጣም ኃይለኛ ነው ከሰሩ ያሉት ነገሥታት ግዛት ጉብኝት ለማድረግ አንድ ዓመት ይፈጅበታል ብሎ ጽፏል።

## 9. ታሪካዊ ቦታዎች በደቡብ ኢትዮጵያ

በሰሜን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም የጥንት ታሪካችን ምልክቶች ፍርስራሾች ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ፋንፋኔ ጠበል አጠገብ የአክሱም ስልጣኔ ማስፋፋት የሚያመለክት የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ ይገኝ ነበረ። እንደዚሁም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ጀባልቲ በተባለው ተራራ የአንዲት የአክሱማዊት የከተማ ፍርስራሽ ይገኛል።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የአክሱም ወደ ደቡብ ማስፋፋት በተያያዘ ሁኔታ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ማእከል እንድትሆን የተመረጠችው በአጼ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ዘመን መሆኑ ቀርቶ በአክሱም ዘመነ ምንግሥት መሆኑ ነው። አጼ ምኒልክም አዲስ አበባ ዋና ከተማ እንድትሆን የመረጠበት ምክንያት በኢትዮጵያ ሌሎች የፍል ውሀ ጠበል ቦታዎች ጠፍተው ሳይሆን ቀደምት አባቶቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፈለግ በመከተልና በማእከልነት ተመርጦ የነበረው ቦታ በመቀበል ነው። ከአክሱም አጉላ አሸንጌ የሚወስደው ጥንታዊ መንገድ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም ከአክሱም ወደ አሸንጌና ፈንፈኔ መስፋፋቱ ያሳያል። በዚሁ መሠረት ከአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አባል የሆነው አንድ ወታደር የሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም ገንዘብ አግኝቷል። በዚሁ አካባቢ በአክሱም ጊዜ ሕዝብ ሰፍረውበት የነበሩ ምልክቶች በስተምዕራብ የአሸንጌ ሐይቅ ተግኝቷል። በዝዋይ ሐይቅ ትራቪርሲ፣ ሚሊዮስና ዲካስትሮ የተባሉ ጣሊያኖች በአጼ ምኒሊክ ጊዜ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የአክሱም መሰል

[1] C. Conti - Rossini Storia d'Etiopia p 289



ሐውልቶች፣ አቢሊስኮችና መስቀሎች በብዙ ቦታዎች አግኝተናል ብሏል። ኪያሪኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ሀገር ጎብኚ ከአንኮበር በስተምስራቅ የግሪክ የድንጋይ አሰራር የሚመስል በአንድ ሕንጻ በተለይም በበሩ ደጃፍ አግኝተዋል። በአጉላ በምስራቅ ትግራይ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የቤት ፍርስራሾች ተገኝተዋል። ሀገራችንን የጎበኙ ቼኪ የተባለው ሌላም ኢጣሊያዊ በሸዋ ከአንኮበር በስተምስራቅ 6.35 ሜትር ርዝመት ያለውና ሌላው ደብረ ብርሀን አጠገብ አቢሊስክ አግኝቷል። ዳባዲ ታዋቂው የፈረንሳይ ሀገር ጎብኚ ከአባይ በስተደቡብ በሊበን ሁለት ሜትር ርዝመት ያለው አቢሊስክ አግኝቶ ነበር፣ ነገር ግን ደጃዝማች ጎሹ ወልዴ ለአሮሞዎች የጣኦት አምልኮት ነው ብሎ ሰባብሮታል።

ሀረሪ /አደሬ/ በሀረር ከተማ የተወሰነ ቋንቋ እንዲሁም የጉራጌ ቋንቋ በመሀል አገር በሰፊው የተሰራጩ ከትግሪኛና ከአማርኛ ቋንቋዎች ጋራ የሚዛመዱ የሴም ቋንቋ ተብለው ሲመደቡ የተለመደ ነው። በነዚህ ሁለቱ ለአካባቢዎች የአክሱም ስልጣኔ ምልክቶች ተገኝተዋል።[1] በትግራይና የሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የስልጣኔ ምልክቶች ከጥንት ግብፃውያን ወይንም ደቡብ ዓረብ ጠበብቶች የተሰሩ ናቸው እንደሚባለው ሁሉ፣ በሌላ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የሚገኙ የስልጣኔ ቅሪቶች በደፈናው ከአክሱም የመጡ ናቸው ይባላሉ። አልፎ አልፎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ አቢሊስቶች የቤተክርስቲያን ህንፃ ፍርስራሾች የአክሱም ሥልጣኔ መስፋፋት ጊዜ የተሰሩ ሲሆኑ ሌሎች እንደ መቃብሮች የመሳሰሉት ግን ከቀደምት ነዋሪ ሕዝብ የተሰሩ ለጥንት ግብፃውያን የሥልጣኔ ምልክት የሆኑት ፒራሚዶች እንዲዳብሩ መሠረት የጣሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጉራጌ ሙሄር ሶዶ አካባቢ ጢያ፣ ሰምቦ፣ ሰደን ወዘተ የተባሉ ቦታዎች ሁለት ከስማንያ ሜትር ያላነሰ ቁመት ያላቸው በግዙፍ የድንጋይ ክምችት ከፍታ ያላቸው በገዥ ቦታዎች የተሰሩ በተለይ በሰደን 150 የሚሆኑ ባለአራት ማእዘን መቃብሮች ተገኝተዋል። በመቃብሮቹ የተካሄደው ምርምር አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘበት ምክንያት ሬሳዎቹን የሚሸፍነው ድንጋይ የአሲድ ጠባይ ስላለው አጥንቶች አመድ ሆነው ስለተገኙ ነው። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሮቹ ላይ ስእል ተገኝቷል። እንደዚሁም የግብፃውያን መስል ጉራዴና ቢላ ተገኝተዋል። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሩ ላይ ሐውልት የሚመስል ወይንም በአክሱም የኢዛና ጽሑፍ ያሉባቸው ድንጋዮች የሚያስታውሱ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ስራዎች በአክሱማውያን የተሰሩ መሆናቸውን አያጠራጥርም። በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሐረር 50 ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ አባ አዘይስ የተባሉ ፈረንሳዊ ካቶሊክ ላዛሪስት ሚሰዮናዊ "ደልመን" ብሎ የጠራቸው መቃብሮች አግኝተዋል። ደልመን በብዙ የዓለም ክፍሎች ተገኝተዋል፣ በግብፅ ግን አልተገኘም። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌ የተገኙ መቃብሮች በኮንቲ ሮሲኒ አስተያየት ደልመን ሳይሆኑ በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ተመሳሳይ ናቸው። በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ዋናውና ትልቁ በአክሱም ከተማ ንፋስ መውጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው መቃብር ነው። የሐረር ጉራጌ ቋንቋዎች የተፈጠሩት ከጥንታዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ከግዕዝ በቀጥታ ወይንም ከግዕዝ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፣ ከትግሪኛ ጋራ ብዙ ይዛመዳሉ። መቃብሮቹ የተሰሩበት ዘመን ለማወቅ ጨርሶ አይቻልም። የሐረር እና የጉራጌ አካባቢ

[1] Conti -Rossini ibd p . 282-3

የአክሱም ስልጣኔ ሳይጠፋ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ነው እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ከምዕራብ ክፋ እስከ ምስራቅ ከሰሜን እስከ ደቡብ እዋ የአክሱም ስልጣኔ ምልክት የሌለበት አካባቢ አይገኝም፡፡ በዓረብ ሀገር የፖለቲካና የወታደራዊ ሽንፈት ካጋጠማት በኋላ በአፍሪካ ብቻ ተወስና፣ እንቅፋት ባያጋጥማት ስልጣኔዋና ቋንቋዋን በማስፋፋት ኢትዮጵያ ባለ አንድ ቋንቋ ሀገር ልትሆን ትችል ነበር፡፡ ይህ ባይቻልም አሁን የሚታዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ እንደ ሀረሪና ጉራጌ የግዕዝ ቋንቋ ድብልቅ መሆናቸው አይቀርም ነበር፡፡

ስለዚህ አሁን ትግሪኛ አማርኛ አደሪኛ ጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ተብለው እንደሚመደቡ ሁሉ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ይባል ነበር፡፡ ነገር ግን የአክሱም መንግሥት ወደ ደቡብና ምዕራብ ያደረገው ማስፋፋት ከባድ እንቅፋት ሳላጋጠመው ብዙ ሳይቆይ በ10ኛ ክፍለ መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ማቋረጥ የተገደደበት በዩዲት ጊዜ ነበረ፡፡ ኢትዮጵያ በዩዲት እርስ በእርስ ጦርነት ዘመን ጀምሮ ከምስራቅ ሰሜን ሱዳን እስከ ደቡባዊ ሶማሊያና ሶኮትራ ደሴት ድረስ የነበረ ግዛቷ የደቡብ ክፍላተ አገሮች ጭምር ከቁጥጥሯ ውጭ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ የአስተዳደር መዋቅርም በጦርነት ስለ ወደሙ ይህ የዩዲት ዘመን የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ የዛግዌ ዘመነ መንግሥትም የግዛት አንድነት ለማስከበር ትኩረት ስላልሰጠ በዚሁ ረገድ ከጨለማ ዘመን ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል፡፡ ሰሎሞናዊ ንጉሣዊ አገዛዝ ከተመሰረተ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ከግዛቷ ተነጥለው የነበሩ የምሥራቅ እና የደቡብ ክፍላተሀገር፣ ከሰሜንም፣ ለማስመለስ የጣረችበት ዘመን ስለነበረ የጨለማ ዘመን አብቅቷል ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ጥረቱ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት በምሥራቅ የአፋርና የሶማሌ ግዛቷ የእስልምና ሃይማኖት በመቀበላቸው እንደገና ለማዋሀድ ቀላል ሆኖ ስላልተገኘ ነው፡፡

በመሐመድ ግራኝ እና በኦሮሞዎች እርስ በእርስ ጦርነት ጊዜ የሥልጣኔዋ ቅርሶች በባሰ ሁኔታ ስለወደሙባት እስከፌ የሆነው እንደገና በጨለማ ዘመን ወድቃለች ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ይህ ዘመን የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል፡፡ የቀሩት ዘመናት ግን እላይ የጠቀስኳቸው የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያስረዱ የጨለማ ዘመን ተብለው ሊጠሩ አይገባም፡፡

## 8. <u>የዮዲት ዘመን</u>

ዮዲት የምትባለው ንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ መከሰቱ በሁሉም የማይካድ ቢሆንም ዝርዝር ታሪኳ እና ማንነቷ በሚመለከት ግን በትክክል አይታወቅም፡፡ ዩዲት የነገሡች በ921-933 ዓ.ም. የእስክንድሪያ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ኮዝማ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው የተላኩ በየዋሁ አቡነ ጴጥሮስ ላይ ኢትዮጵያ የፈጸመችው ግፍ እግዚአብሔር የላከባት የቅጣት መቅሰፍት ነው ተብሏል፡፡ እንደ ሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች አቀራረብ ዮዲት አይሁዳዊት ናት የኦሪት ሕግ በመደገፍ የክርስትና ሐይማኖት አንቀበልም ያሉት በሰሜንና፣ በወገራ፣ ወልቃይት፣ በላስታ የነበሩት ፈላሾች አሰባስባ ወደ ትግራይ ዘመታ ሐውልቶቹንና አብያተክርስቲያናትን አቃጥላ ሕዝበ ክርስቲያንን ፈጅታ በደብረ ዳሞ ተራራ ይኖሩ የነበሩትን ከነገሥታት የሚወለዱትን መሣፍንት አሳርዳ የነገሠች ናት ብሏታል፡፡ የእስክንዲሪያ ፓትያራኮች ታሪክ ላይ ዮዲት የባኒ አል ሓማያህ ንግሥት ብሎ ይጠሯታል፡፡ በኢትዮጵያ ግን በዚሁ ስም



የሚጠራ ክፍለ ሀገር የለም[1] ከአጼ ካሌብ ጀምሮ እስከ ዮዲት ዘመን 300 ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ ብዙ የታሪክ ማስረጃዎች የማይገኙበት ዘመን ስለነበረ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ዘመን ምናልባት ኢትዮጵያ ስልጣኔዋን ያስፋፋችበት ጊዜ ስለነበረ ወርቃማ የብልጽግና ዘመን ነበር፡፡[2]

በ979 - 1003 ዓ.ም. በአስከዲሪያ መንበረ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ፊሉተዎስ Fileteus[3] በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ ከአቡነ ጴጥሮስ ጀምሮ ሕጋዊ አቡን ስላልነበራት ሰይፈ አረድ የተባለ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጊዮርጊስ ለተባለው የኑቢያ ንጉሥ የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ይልኩ ዘንድ እንዲያግልደው ደብዳቤ ጽፎ ነበር፡፡ የኑቢያ ንጉሥ የግብፁ ፓትሪያርክ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲልኩ ባቀረበው ልመና መሠረት አቡነ ዳንኤል ሲላኩ ኢትዮጵያውያን በታላቅ ደስታ ተቀብሉዋቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለኑቢያ ንጉሥ በግእዝ ቋንቋ የፃፈው ደብዳቤና የወቅቱ የኢትዮጵያውያን የታሪክ ፀሃፊዎች ያቀረቡት ዘገባ የሚጠቁመን ነገር ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን በታሪኳ በወሳኝ ምዕራፍ ትገኝ እንደነበረ ነው፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ መዛግብቶች በዓመተ ምህረትና በአንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች ቢለያዩም በመሠረቱ ታሪኩ በማይለያዩበት ሁኔታ ገልፀውታል፡፡ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ሊጠፋ ትንሽ ነበር የቀረው፡፡ ክርስቲያን ሕዝብም ባሪያ ሆኖ ከመሸጥ ያመለጠ ሸሽቶ ወደ ሌላ ክፍላተ ሀገር ይሰደድ ነበር፡፡ ንጉሡም ወደ ሸዋ በመሸሸ የሞት ሽረት ፍልሚያ በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘመናችን የጎሳ ጦርነት የተደረገበት ጉዜ የለም፡፡ የሃይማኖት ጦርነቶች ግን ተደርጓል፡፡ በዮዲት የተቀሰቀሰው ጦርነትም የኦሪት ሕግ ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን መሀከል የተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ያቀረቡት ዘገባ ይኸንን ሁኔታ መኖሩን የሚያስተጋባ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ዘመናትም በእስላሞች ኢትዮጵያውያን እና በክርስቲያኖች መሀከል ጦርነቶች ተካሄዷል፡፡

ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ታሪክ ጨርሶ ሳይክዱ የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በኒ አል ሐሙያህ ብሎ የጠሯት ንግሥት የአጻጻፍ ስህተት ነው ብለዋል፣ አል ደሙታህ ተብሎ መነበብ እንዳለበት በማመን ዮዲትን ከአባይ በስተደቡብ ይገኝ የነበረው ትልቁ ዳሞት የዛሬው ምዕራብ ሸዋና ወለጋ ንግሥት አድርጓታል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ዳሞት የሚባል መንግሥት ተዘግቧል፡፡ በመጨረሻ ዮዲት በመሞቷ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ድል አድራጊነት ቢደመደምም ጦርነቱ ኢትዮጵያ ደካማ መንግሥት አድራጓት ነበረ ያብቃው፡፡ ኢትዮጵያ የደቡብ ክፍለ ሀገሮች ለመቆጣጠር ሳትችል ከመቅረቷ ሌላ እስከ 10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. ክርስቲያን የነበሩ እንደ ዘይላ፣ በርበራ፣ የባሕር ጠረፍ ወደቦቿ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍተውባቸው ስለነበረ በኢትዮጵያውያን መሐከል

---

[1] C. Conti - Rossini ibd p. 286
[2] C. Conti - Rossini ibd p. 285
[3] C. Conti - Rossini ibd p. 286

በክርስቲያኖችና በእስላሞች የሃይማኖት ጦርነቶች እንዲካሄዱ መንገድ ከፍቷል።

ቀደም ብሎ የእስልምና ሃይማኖት የገባ በዳህላክ ሲሆን፡ በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በሱዋኪን እስልምና ገብቶ ነበር። እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ የባርካ፣ ቢጃ ጎሳዎች እና የሳሆ ጎሳዎች፣ ታጁራ ወደብ አካባቢ እስላም ሆነው ነበረ። በአጠቃላይ በባሕር ጠረፍ ወደቦች ብቻ ሳይሆን ወደ መሀል ሀገር በ13 መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሐረር፣ ዝዋይ፣ ሀዲያ ድረስ እስልምና ተስፋፍቶ ነበር።

ዮዲት ወደ ትግራይ ዘመቻ አድርጋ በመጣችበት ጊዜ በደብረ ዳሞ ታጉሮ ይኖሩ የነበሩ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ክሬጆች በኋላ ከእልቂት ያመለጡ ጥቂቶች ወደ ሸዋ መንዝ ሸሽተው ሄደው ነበር።

ዮዲት መሞቷ ሲሰማ አምበሳ ውድም በተባለው የተደሞው ንጉሥ ልጅ ወደ ትግራይ በመምጣት ለ20 ዓመት እንደገና በአባቱ ዙፋን ተቀምጦ ሲገዛ ቆይቶ ሞተ። ልጁ ግን መንግሥት ለመያዝ ከላስታ የተነሳ ዓመፅ ሲቋቋም ስላልቻለ እንደ አባቱ እንደገና ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሽቶ ሄደ። መራ ተክለሃይማኖትም የዛጉዌን ላስታ መንግሥት መሠረተ።



# ምዕራፍ 3

# ኢትዮጵያ ድኅረ ዛጉዌ በሰለሞናውያን ነገሥታት ዘመን

በ1268 ዓ.ም. የመንግሥት መሪነት ስልጣን ከዛጉዌ ነገሥታት ወደ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ነገሥታት በይኩኖ አምላክ መሪነት በሰላማዊ መንገድ በወሎ ሐይቅ በሚገኘው ገዳምና በደብረ ሊባኖስ ሸዋ ከሚገኘው ገዳም አባቶች አማካኝነት ሊዘዋወር ችሏል። የአስተዳደር ማእከልም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሸዋ ተዛወረ። ሸዋ በጂዮግራፊ አቀማመጧም የኢትዮጵያ ማእከል በመሆኗ፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በምሥራቃዊ የሀገሪቷ ክፍል በተቋቋሙት እስላማውያን ትናንሽ መንግሥታት የሀገሪቷን እንድነት የሚያናጉ የሚሰነዝሩባት ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ብሎም ለመግታት እንዲቻል፣ የኢትዮጵያ መስተዳደር በሸዋ ማእከላዊነት መሆኑ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። በሰለሞናዊ ነገሥታት መሪነት በሸዋ ማእከላዊነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው ደካማ ጐን እንደ ቀደሞ ጊዜ እንደ አክሱምና ላሊበላ ቋሚ ዋና ከተማ መፍጠር ያለመቻሉ ነው። ይህ በመሆኑ የማሕበራዊ ኑሮ ግንባታዎች በማከናወን ለመጪው ትውልድ ታሪክ ማስተላለፍ አልቻለም። ጠንካራ ጐኑ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በየወቅቱ የተከናወኑትን የመንግሥት ሥራዎች በጽሑፍ ለወጪው ትውልድ ማስተላለፍ ነው። ሌላ ጠንካራ ጐኑ ወሳኝ ፈተናዎች በማሳለፍ የሀገር አንድነትን ለመጠበቅ አስደናቂ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት የታየበትና በታሪክ የተመሰከረበት ዘመን ነበረ። ለ300 ዓመት ገድግ የዘለቀው በሸዋ ማእከላዊነት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በሃይማኖት የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ተቋቁሞ ኢትዮጵያ በአክሱም መንግሥት ዘመን የነበራት የመሬት ስፋት ከሞላ ጐደል ተረካቢ ሆና ለመጠበቅ ሞክረዋል፣ አንስተኛ የማእዝና የአማረኛ ስነ ጽሑፎችም ዳብረዋል፤ ከምዕራባውያን ጋራ የውጭ መንግሥታትም ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረዋል፤ ዘመኑ ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ መኖሩዋን በትክክል ያወቁበት ነበር። የሰለሞናዊ ነገሥታት ስልጣን ሲጨብጡ የኢትዮጵያ አመራር ብሩህ ተስፋ አልጠበቃቸውም። በባሕር ጠረፍ የሚገኙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የእስልምና ሃይማኖት የሆኑ ለማዕከላዊ የክርስቲያን መንግሥታት የማይታዘዙ መንግሥታት ተቋቁመው ነበረ። ይኸም ሁኔታ ለእርስ በእርስ ጦርነት የሚጋብዝ ነበር። ከይኩኖ አምላክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ግራኝ መሐመድ ሞት ድረስ ለ300 ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ በእስላሞችና ክርስቲያኖች የማያቋርጥ ጦርነት የተካሄደበት ጊዜ ነበር። ይህ በሀገራችን የተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት በመካከለኛ ምስራቅና በኤውሮጳ የተካሄደው ጦርነት አካልና ነፀብራቅ ነበር። ዓረቦች በእስልምና ሃይማኖት በመመራት በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ባልታሰበ ሁኔታ ወታደራዊ ወረራ በመፈጸም መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን በቁጥጥራቸው ለማድረግ ችሏል። ነብዩ መሐመድ ከሞተ በኋላ በስድስተኛው ዓመት በ689 ዓ.ም. ግብፅ በዓረቦች እጅ ወደቀች። ዓረቦች ወደ ሰሜን አፍሪካ ወረራቸውን በመቀጠል በ689 በካርታጅ ከባድ

ጦርነት አካሂደው ከማረኳት በኋላ በእሳት አቃጠሏት፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ስሟ ከታሪክ ተሰርዟል፡፡ በ711ዓ.ም. በበርበር የተገነባ 12,000 የዓረቦች ጦር የጂብራልታር ካናል ተሻግሮ ወደ ስፓኝ ገባ፡፡ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ የቪዚጎት መንግሥትን አሸንፎ መላው ስፔኝን ለመቆጣጠር በቅቶ ነበር፡፡ ቀጥሉም ዓረቦች ወደ መሐል ፈረንሳይ ዘልቀው በመግባት መላው ኤውሮጳ እስላማዊት ዓረባዊት ለማድረግ ተቃርበው ነበር፡፡ ነገር ግን በቻርል መደሻ የሚመራው የፈረንሳይ ጦር ፑዋቴ በተባለው ቦታ በ732 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት በዓረቦች ላይ ድል ስለተቀዳጀ የዓረቦች ወረራ ስዘለቄታው ሊገታ ችሏል፡፡ ከዚሁ ጦርነት በኋላ የክርስትና ሃይማት ሕልውና እና የኤውሮጳ ሀገሮች ነፃነት ተከብሮ ሊቆይ ችሏል፡፡ ከ300 ዓመት በኋላ ሌላ እስላማዊ የቱርክ መንግሥት ተነስቶ በዓረቦች ተተክቶ በዓረቦች ያልተያዘውን የቢዘንታይን መንግሥት በቁጥጥሩ ከማዋሉ በላይ በምስራቅ በኩል በኤውሮፓ ላይ ወረራ በማድረግ ሀንጋሪና እስትሪያ ድረስ ደርሶ ነበረ፡፡ የኤውሮጳ ሀገሮችም ተባብረው ያደረጓቸው የመስቀል ጦርነቶች ውጤት አልሰጡም ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜም ኤውሮፓ በቱርክ እስላማዊ መንግሥት ስር ለመውደቅ ተቃርባ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ቱርኮች በቪዬና አጠገብ ሽንፈት ስለደረሰባቸው ኤውሮጳ ከቱርኮች ወረራ ልትድን ችላለች፡፡

የዓረቦችም ሆነ የቱርኮች ግዛታቸውና ሃይማኖታቸውን የማስፋፋት ዓላማ ዋና ትኩረታቸው ወደ ኤውሮፓ ቢሆኑም ወደ ሀገራችንም ወኪሎቻቸው መላካቸው አልቀረም፡፡ በየጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትም በክፉ ዓይን የሚያዩዋቸው በሀገራቸው መሬትና የራሳቸው ሕዝብ በእስላማዊ ሐይማኖት የሚያምኑ መንግሥታት ሁርያቸው መቋቋማቸው በማየት በመንግሥታቸው ሕልውና አደጋ ማንጃበቡ መገንዘባቸው አልቀረም ነበር፡፡

ይኩኖ አምላክ ስልጣን በያዘበት ጊዜ የሁኔታው አሳሳቢነት በመመለከት ከቢዛንታይን መንግሥት ጋር ግንኙነት ለማድረግ በመፈለግ ደብዳቤና ስጦታ ልኮ ነበር፡፡ ነገር ግን ራሱ የቢዛንታይን መንግሥት የራሱ ሕልውና እንኳን ለማስከበር በማይችልበት ወቅት ስለነበረ ሙከራው ውጤት ሊያገኝ አልቻለም፡፡

ይህ በመሆኑ በይኩኖ አምላክ የተተካ ንጉሥ ከግብፅ ጋራ መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ከከበቡት ኢትዮጵያውያን የእስላም መንግሥታት ግንኙነት አሻሽሎ በሰላም ለመኖር አስቦ፣ ወስኑ ለእስላም ነጋዴዎች ክፍት አድርጎ ነበር፡፡ ይህ በሰላም የመኖር ሙከራ ግን ጥሩ ውጤት ሊሰጥ አልቻለም፡፡

## 9. <u>አጼ ዓምደጽዮን</u>(1)

በኢትዮጵያውያን እስላሞችና ክርስቲያኖች እርስ በእርስ እስከፊ ጦርነቶች የተጀመሩበት በይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ በሆነው በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡ ዓምደ ጽዮን የነገሠው ከ1312 - 1342 ዓ.ም. ለሰላሳ ዓመታት ነበረ፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩበት ዘመናት ነበሩ፡፡

ኤውሮጳውያን እንዳደረጉት ሁሉ በክርስትና እምነታቸው ፀንተው ለመኖር ያደረጉት ትግል ነበረ፡፡ ከዚዲት ጦርነት በኋላ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ተቋቁመው የነበሩት መንግሥታት ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

(1) Luca Dei Sabelli ibd VI p 267



1ኛ. በአጠቃላይ ስማቸው ሲዳማ ተብለው የሚጠሩ፣ ወይም የደቡብ ኩሽ የሚባሉ፣ በጥንት ጊዜ ከሰሜን የፈለሱ ናቸው የሚባሉ፡፡ የአክሱም መንግሥት አሁን የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ደቡብዊ ወሰን ከዝዋይ ሐይቅ እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ከዚፋ እስከ ዘይላ፡፡ የባሕር ወደብም እስከ ደቡብ ሶማሊያና አዛኒያ ተቆጣጥሮ እንደነበረ ታሪክ ያረጋግጣል፡፡ ከሲዳማ መንግሥታት መሐል 1ኛ ጃንጀሮ 2ኛ ቦሻ 3ኛ እናሪያ (ሊሙ) 4ኛ እንፌሎ ምዕራብ(ወለጋ) 5ኛ ጋፋት የተባሉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከነገሥታትም ሆነ ከባለባቶች ከሰሜን እንወለዳለን የማይሉ የሉም፤ ይህም የሚያረጋግጠው የአክሱም መንግሥት ተቆጣጥሯቸው እንደነበረ ነው፡፡

2ኛ. የእስልምና እምነት የሚከተሉ የሱልጣን መንግሥታት ተብለው የሚጠሩ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1ኛ. ሐዲያ፣ ጉራጌን የሚያጠቃልል 2ኛ. ፋጢጋር 3ኛ. ይፋት 4ኛ. ዳዋሮ 5ኛ. ባሊ 6ኛ. ሐረር ከተማ 7ኛ. ማና 8ኛ. አዳል፡፡ ጦርነቱ የተካሄደው በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትና በተጠቀሱት 8 እስላማዊ መንግሥታት መሐል ነበር፡፡ የሲዳማ መንግሥታት የያዙት ገለልተኛ አቋም ነበረ፡፡

ከእስላም መንግሥታት ከሁሉም ኃይለኛና የበላይነት የነበረው የይፋት መንግሥት ነበረ፡፡ ይህ መንግሥት በክርስቲያኖች ዘንድ የእረመኔዎች መስፍን ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ይፋት ወላዝማ ተብለው በሚጠሩ የነገሥታት ዘር ሀረግ ይመራ ነበር፡፡ ይህ ስርወ መንግሥት የተመሠረተው በዑመር ወላዝማ ነው፡፡ እሱም ከነቢዩ መሐመድ ጎሳ ከሆነው ከኮሬይስቶች ከሚወለደው ከሃሺያ የሚወለድ ነበር፡፡ እሱም በዘኩሉ አል ሐሰን ከተባለው ከነብዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የሚወለድ ነው፡፡ በአጼ ዓምደ ጽዮን ጊዜ የይፋት ንጉሥ ሐክ አዲን የተባለው ነበረ፡፡ ጦርነቱ የተቀሰቀሰው የግብፅ መንግሥት በእስክንድሪያ ፓትሪያርክ ስለሚፈጽመው በደል ለመበቀል አጼ አምደ ጽዮን የአባይ ወንዝ አቅጣጫውን እቀይረዋለሁ ብሎ በመዛቱ፣ እንዲሁም በእስላም ነጋዴዎች የበቀል እርምጃ በመውሰዱ ነው፡፡ አክ አዲን አጠፋውን በመመለስ ቤተክርስቲያኖችን በማቃጠል ቄሶችን ሐይማኖታቸው እንዲክዱ በማድረግ በክርስቲያን መንግሥት ውስጥ ግዛት ዘልቆ በመግባት የዓምደ ጽዮን ሚስት ባሪያ እንደሚያደርጋትና የቤቱ እሀል እንድትፈጭ እንደሚያደርጋት ዛቻ ያሰማ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ወደ ካይሮ ተልኮ የነበረ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በመማረክ ሃይማኖቱን አልክድም በማለቱ በአሰቃቂ ሁኔታ ስለገደለው በሕዝቡና በመንግሥቱ ቁጣ ስላስነሳ ነበረ፡፡ አጼ ዓምደ ጽዮን ጦሩን በመምራት ባደረገው ዘመቻ ይከተለው የነበረው መመሪያ፣ ጦሩ በብዙ አቅጣጫ በማስግራት ድንገተኛ አደጋ በመጣል ለጠላት ፋታ አለመስጠት በጠላት ላይ ሽብርና ፍርሀት መፍጠር ነበር፡፡

ሐክ አዲን በሌሊት አደጋ በመጣል ቢሞክርም አጼ ዓመደ ጽዮን ሙከራውን በማከሸፍ የሐክ አዲን ወንድም ወደ ነበረበት ጦር ግንባር ጥቃት በመሰንዘር በጕራዴ ራሱ ከገደለው በኋላ ጥቃቱን በመቀጠል በፈረሰኞች እየተረዳ የጠላቶች መደናገጥ በመጠቀም ጠላቶችን በማሳደድ ሐክ አዲንን ግርኮ ግዛቶቹ ይፋትና ፋጢጋርን በኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ እስተዳደሩ ለሐክ አዲን ወንድም ለሳብር አዲን በመስጠት በ1328 ዓ.ም. የመጀመሪያ የአጼ ዓመደ ጽዮን ዘመቻ በድል አድራጊነት ፍጻሜ ሆነ፡፡

የእስላሞች የተባበሩት ነገሥታት ሱልጣኖች ግን ሽንፈታቸው አላመኑም ነበር፡፡ በመገራ፣ በሰሜን፣ በደንቢያ፣ በቤጌምድር፣ በጣና ሐይቅ አካባቢዎችና በተከዜ ወንዝ አካባቢ የኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በክርስትና እምነት አያምኑም ነበረ፡፡ ከእሪት ሕግ ጋር አልተላቀቁም ነበር፡፡ ሳብር አዲን

እንዲተባበሩትና የክርስቲያን መንግሥትን እሱ በምስራቅ ሲዋጋ በሰሜን እንዲወጉት መልእክተኞቹን በመላክ ይሰብካቸው ጀምሮ ነበረ፡፡ የሐዲያና የዳዋሮ የሚላቶቹ እትይ በሚገባ ስላወቀ ለየብቻቸው ጥቃት ለመፈጸም ባወጣው እቅድ መሠረት ወታደሮቹ ወደ ሀዲያ ልኮ የሐዲያ ሱልጣን ድንገተኛ ወረራ ስለተፈጸመበት ተማረከ፡፡ ሌሎች የአጼ ዐምደ ጽዮን ወታደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ከሐዲያ በሚያዋስነው ወረራ በመፈጸም ድል ተቀዳጁ፡፡ ሳብር አዲን ወደሚገኝበት ስፍር ደርሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ሱልጣኑ ሸሽቶ ሊያመልጥ ችሏል፡፡ አጼ ዐምደ ጽዮን በዳዋሮ ጣቢያ በማድረግ ወደ ፋጢጋር አመራ፡፡ ሳብር አዲን ጦርነት ለመግጠም ተገዶ ተሸነፈ፡፡ ሚስቶቹና ልጆቹ ተማረኩ፣ ከተማው ወደመ፡፡ በአጼ ዐምደ ጽዮን ሚስት በኩል ምህረት በመጠየቅ አማላጅ ላከ፡፡ ዐምደ ጽዮን ግን ራሱ እፊቱ መቅረብ አለበት ብሎ የሚስቱ አማላጅነት ሳይቀበለው ቀረ፡፡ ሳብር አዲን ድንጋይ በትከሻው ጭኖ ይቅርታ በጠየቀበት ጊዜ የዐምደ ጽዮን ወታደሮች እንዲገደል ቢጠይቁም፣ ንጉሡ ግን እንዲታሠር ብሎ ፍርድ ስለሰጠ ታስሮ በእስር ላይ እንዳለ ሞተ፡፡

በሐዲያ፣ ፋጢጋር፣ ይፋት፣ ዳዋሮ ሱልጣኖች ላይ የተደረገው ጦርነት እንዳበቃ አሁንም የመንግሥቱን ስልጣን ለሳብር አዲም ወንድም ለጀማል አዲን ሰጥቶ ወደ ሸዋ በሚመለስበት ጊዜ የአዳልና የሞራ ሱልጣኖች በመመሳጠር ወደ ኋላ የሚመለሰው የአጼ ዐምደ ጽዮን ሠራዊት በደፈጣ ውጊያ በመጠቀም ማጥቃት ጀመሩ፣ ብዙ ወታደሮችም ፈጁ፡፡ በዚሁ ጊዜ አጼ ዐምደ ጽዮን በጠላት ውጊያ ስልት በመጠቀም እነሱም ወደሚሰበሰቡበት በፈረሰኞች ደፈጣ በማድረግ ጠበቋቸው፡፡ እቅዱ ሙሉ በሙሉ ስለተሳካ ደፈጣው ሞክረው ተመልሰው በተሰበሰቡበት ቦታ አግኝቷቸው ፈጃቸው፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ይፋትንና አካባቢዋን መልሶ ለመያዝ ግንኛውም ምኞት ውድቅ ስለሆነ ወታደሮች የተማረከውን ንብረት ይዘው ወደ ተጉለት ለመመለስ ጓጉተው ነበር፡፡ የንጉሡ አስተሳሰብ ግን ሌላ ነበረ፡፡ ጠላቶቹ ግን በጦርነት ስላልተነኩ እንደገና ጦርነት ሊያስነሱ ይችላሉ የሚል ነበር፡፡ ስለዚህ ተከታትሎ በማጥቃት በተገኘው ድል በመጠቀም ጠላት ተመልሶ እንዳያንሰራራ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚል ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ከይፋት ወደ ዳዋሮ ጉዞውን ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ ወደ ቆላ እንሄድም ብለው ተቃወሙት፡፡ ነገር ግን ንጉሡ የቁርባን ሕብስት በማውጣት ጠላቶችን ሳልደመስስ አልመለስም ብሎ በመማል ሰኔ ወር 1330 ዓ.ም. ወደ ቆላ ሀገር አመራ፡፡ የአጼ ዐምደ ጽዮን ጦር የሚያቋርጠው የቆላ ሀገር በባሕር በኩል ከምጽዋ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ሲሆን ወደ መሀል ሀገርም እስከ ዝዋይ ሀይቅ ጨርጨር ሐረር ወዘተ... የሚዘልቅ ነበረ፡፡ ወደ ቆላ ሀገር የሚያመራው የኢትዮጵያ ጦር የአዳልና ሞራ ሱልጣኖች በቆላ ከሚገኙ ጎሳዎች ከተመለመለ ጦራቸው በደፈጣ ያስጨንቁ ያስጠቁት ነበረ፡፡ ዓላማው ፊት ለፊት ውጊያ በማስወገድ ወራሪውን ጦር በማድከም በበሽታ በድካም፣ በውሀ እጥረት፣ ጦሩ እንዲያልቅ ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ወታደሮች በከባድ ችግር መሆናቸውን ስላወቁ እስላሞች ጥቃታቸውን መሰንዘር ጀመሩ፡፡ በዚሁ ጊዜ ንጉሡ የመንፈስ ጥንካሬ ስለነበረው ወታደሮቹን በማነቃቃት አጥቂዎቹን ለመቋቋም አስችሏቸዋል፡፡ በሁለቱ ወገን ወሳኝ ፍልሚያ ነበረ፡፡ በቄሶች ስብከት የተቀሰቀሱ ብዛት ያላቸው ገበሬዎች እንደ መስቀል ጦርነት ጊዜ የንጉሡን ጦር ያጠቁ ነበር፡፡ በበኩላቸው እስላሞች ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ በማወጅ ያላቸው ኃይል



በሙሉ አስልፈው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት በማያውቀው በቆላ ሀገር በጦርነት ተወጥሮ መሆኑን ስላወቀ በአጼ ዓምደ ጽዮን ቀደም ብሎ በያዘው የእስላም ሀገሮች ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሾሞ የነበረው ጀማል አልዲን ከድቶ የኢትዮጵያ ጦር በስተጀርባ ወደኋላ ሸሽቶ እንዳያመልጥ ውጊያ ለማድረግ ሞክሮ ነበረ፡፡ የእስላም ጦር በሙሉ አስተባባሪም በመካ ባላባት ቤተሰብ ተወላጅ፣ በሆነው ሼክ ሳሊህ በተባለው ሐረር ከተማ ዋና ሠፈሩና ማዕከል በማድረግ ነበረ፣ ተጨማሪ ጎሳዎችም በጦርነቱ ገብተው ነበር፡፡ በዚሁ ዓይነት በተሰበሰበው የእስላም ጦር ቁጥሩ አርባ ሺህ /40.000/ ይደርስ ነበረ ይባላል፡፡ በዚሁ ወሳኝ ፍልሚያ ጊዜ ንጉሡ ታመመ፡፡ ሠራዊቱ ሥጋት ላይ ወድቆ ነበረ፡፡ ክርስቲያኖች ከአደጋ ያዳናቸው እስላሞች በፈጸሟቸው ስህተቶች ነበረ፡፡ 1ኛ.ሼክ ሳሊህና የአዳልና የሞራ ሱልጣኖች የፈጸሟቸው ስህተት ጥሩ ውጤት ይሰጧቸው የነበሩ የደፈጣ ውጊያ ትተው በግንባር መግጠም ነበረ፡፡ 2ኛ. ስህተት የጀማል አልዲን ጦር እስኪቀላቀል ድረስ አለማጠበቃቸው ነበረ፡፡ አጼ ዓምደ ጽዮን ታሞ ስድስት ቀኖች ከአልጋ ሳይነሳ ምግብ ባይቀምስ ቆይቶ ነበረ፡፡ ግንባር ቀደም የነበረ ጦሩ ከጠላት ጦር ተጋጭቷል፣ ጠላት ለውጊያ ተዘጋጅቶ እየገሰገሰ መሆኑን በሰማ ጊዜ ከአልጋ ተነስቶ መቆም አቅቶት ነበር፡፡ ከጉኑ የነበሩ ሁለት ሚስቶቹ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ መከሩት፣ ዳሩ ግን ንጉሡ "እንደ ሴት ሆኜ ልሙት"? ብሎ መለሰላቸው፡፡ በዚሁ ጊዜ አንደኛዋ ንግሥት የዮርዳኖስ ውሀና የጐልጎታ መሬት ሰጠችው፡፡ አንድ ቄስ ረጨበት ድካሙም በቅጽበት ተወው፣ እሱም ራሱ ለወታደሮቹ ረጨባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ለጦርነቱ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ የክርስቲያን የግንባር ጦር ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ተገዶ ነበር፡፡ ንጉሡ በጦሩ መሀል ገብቶ በእጁ የቀኝ ክንፍ የነበሩ መሪዎች ገደላቸው፡፡ ፈረሰኞችም የመሀል ጦር ግንባር አወደሙ፣ ቀሪውን በስተግራ የነበረውን ከየመን የመጡ ሀገሩን የማያውቁ ወታደሮች ነበሩ፡፡ ትንሽ ጊዜ ከቆዩ በኋላ እነሱም ማፈግፈግ ጀመሩ፡፡ ከዚህ በኋላ የክርስቲያን ጦር ፋታ ሳይሰጥ በመሸሽ ላይ የነበሩ እስላሞች ላይ እንዳያመልጡ መንገድ እየዘጋ ይጨፈጭፋቸው ጀመር፡፡ ከሬሳዎች መሀከል የሼክ ሳሊህ ነበረ፡፡ የሞራ ሱልጣን የሚሸሹ ወታደሮችን ሰብስቦ ለመከላከል ሞክሮ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወኔ ግን ዕድል አልሰጠውም፣ ወታደሮቹ ተደመሰሱ፣ ሱልጣኑ ተማርኮ ተሰቀለ፣ ሚስቱም ክርስቲያኖች ጠንቋይ ይሏት የነበረ ተይዛ ገላዋን ተቆራርጦ ለጅቦች ተሰጠ፡፡ ጦርነቱ የተካሄደው ሐምሌ ወር ወደ መጨረሻ 1330 ዓ.ም. ነበረ፡፡ አሁንም የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አቅማቸው እንደተሟጠጠ ለንጉሡ ቢያመለክቱም ንጉሡ ግን አልተቀበላቸውም፣ እፊቱ መከላከል አቅም የሌላቸው የጠላት ቦታዎች ነበሩ፡፡ የዓምደ ጽዮን ወታደሮች እየገሰገሱ ጠላቶቹን መደምሰስ ቀጠሉ፣ ከተሞች ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ፣ ተወስደው ታረዱ፡፡ የአዳል ሱልጣንም ወረራውን ለማቆም ሞክሮ ነበር፡፡ ጦርነቱ ለክርስቲያን ፈረሰኞች ምቹ በሆነ ግልፅ ቦታ ተካሄደ የእስላም ወታደሮች በክርስቲያን ፈረሰኞች ተከበው ማምለጫ አጥተው አለቁ፣ የአዳል ሱልጣን በጦር ሜዳ ሞተ፡፡ ወደ መጨረሻ የቀረ የሐረር ሱልጣን ነበረ፡፡ የመጨረሻ ዕድል ለመሞከር በሱልጣኑ ዙሪያ የቀሩት እስላሞች በሙሉ ተሰበሰቡ፣ ከእነሱ ውስጥም 99 ባላባቶችና ሱልጣኖች ነበሩ፣ ሕዝቡም ወንድ ሴት ሳይለይ ተካፋይ ነበረ፡፡ አሁንም የወሳኝነት ሚና የተጫወተው ሱልጣኑን ከፈረሱ በጦር ወግቶ በመግደል ዓምደ ጽዮን ነበረ፡፡ አሁን ግን የሚቋቋመው ኃይል አልነበረም፡፡ ሁሉም የመሸሽ ብቻ ነበረ የተያያዙት፡፡ አሁን የቀረ ስራ መስጊዶችን ማፍረስ ከተሞችን ማቃጠል ሰዎቹንም ወንድ ሴት ልጅ አዋቂ ሳይለዩ መግደል

ነበረ፡፡ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አራት የተባለው በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ የነበረው ቦታ ደረሱ፡፡ በዚህ ቦታ ብዙ ክርስቲያኖች ጆሮዋቸውን አፍንጫቸውን የተቆረጠ እንዲሁም የተሰለቡ ስለነበሩ ንጉሡ ፊት ቀረቡ፡፡ በዚሁ ጊዜ ክርስቲያኖች ቁጣ ገንፍሎባቸው ስነበረ ወንጀለኞች የሀገሩ ሰዎች እንዳያመልጡ በማሰብ የመሸሽ በማስመሰል ወደኋላ ሲመለሱ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ተመለሰ፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች ተመልሰው በመምጣት ቲም በቀል ፈጽመውባቸዋል፡፡ ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ተጉለት ሲመለስ የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል፡፡

## 3. አጼ ይስሀቅ

ያ ሁሉ የአጼ ዐምደ ጽዮን ጀግንነት ውጤት አልባ የሚያደርገው ጠላቶችን እስከ ባሕር ዳርቻ ምፅዋ፣ አሰብ፣ ታጁራ፣ ዘይላ ራሱ ባለማባረሩ ነው፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ቀጥሎ ከነገሡት ነገሥታት ወደ ባሕር ጠረፍ የደረሰ ከ1414 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሰ አጼ ይስሀቅ ነበረ፡፡ እንደነገሠ የይፋት ንጉሥ ሠኢድ አልዲን ጦርነት ከፈተበት፡፡ በመጀመሪያ ግጭት ለክርስቲያኖች የቀናቸው ነበር፡፡ ራሱ የይፋት ንጉሥም ለትንሽ ነበር ከመማረክ ያመለጠው፡፡ በ2ኛ ጊዜ ግን ሰይድ አልዲን ኃይሉን አጠናክሮ መጥቶ ወደ ክርስቲያን ምድር ዘልቆ በመግባት ሰፊ መሬት በመያዝ ብዙ ንብረትም ለመዝረፍ ችሎ ነበረ፡፡ 2ኛ. ዙር የክርስቲያን መንግሥት ሠራዊት ባሩዋ በተባለው የሚመራ ነበረ፡፡ ባሩዋ የተከተለው የጦርነት ስልትም እንደ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ሱልጣኖችን ለየብቻቸው መግጠም ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ጥረቱ የአዳል ሱልጣን ጦር ከሰዒድ አልዲን ጦር እንዳይገናኝ ማድረግ ነበረ፡፡ በአዳል ሱልጣን ሠራዊት ወረራ አድርጎ ሱልጣኑ በጦር ሜዳ ተገደለ፣ ወታደሮቹም ተደመሰሱ፡፡ ከዚህ በኋላ የሰኢድ አልዲን ሠራዊትን እያሳደደ መፍጀት ተያያዘው፡፡ በመጨረሻም በዘይላ ከተማ እንዲደበቅ አደረገው፡፡ ክርስቲያኖች የከተማዋን የውሃ መስመር እንዲቋረጥ በማድረግ ከተማውን ከማረኩ በኋላ ሰይድ አልዲን ፌብሯሪ 16 ቀን 1445 ዓ.ም. ተገደለ፡፡ የሱ አስር ልጆች ሸሽተው ወደ የመን ተሻገሩ፡፡ መስጊዶችን በማቃጠል በቦታቸው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩ፡፡ ዘይላ ክርስቲያን ሆና ለ20 ዓመት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ነበረች፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ስላልነበራት የወደብ አስተዳደርም ልምድ ስላልነበራት ለዘለቄታው በቁጥጥሯ አድርጋ ለመቆየት አልቻለችም፡፡ አስር የሰይድ አልደን ልጆችም በየመን መንግሥት እርዳታ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለጦርነት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ልትቆጣጠር አልቻለችም፡፡ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በጦር ሜዳ ባገኘው ድል እንደ ዓምደጽዮን ሲጠቀምበት አልቻለም፡፡ ዘይላ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የይፋት ነፃ መንግሥት ለዘላዓለም ተሰርዞ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ግዛት ውስጥ ተጠቃለለ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ፀረ ክርስቲያን መንግሥት መሪ ተዋናይ የሚሆነው የአዳል መንግሥት ነው፡፡ የወላዝማ ንጉሣዊ ቤተሰብ አንድ ዓመት ከዘይላ መያዝ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ ዋና ከተማቸው ያደረጋት ዳካር የምትባለው ቦታ ነበረች፡፡ አፄ ይሥሐቅ፣ኮንቲ ሮሲኒ[1]፣ ጠረኛ ነበረ የሚለው የኢትዮጵያ ንጉሥ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ጦርነት አካሄዷል፡፡

(1) C. Conti - Rossini : Etiopia e genti d' Etiopia p 55



በመጀመሪያ ዘመቻ በዳሕላክ ደሴቶች ሱልጣን ሥር የነበረች ምፅዋ በአፄ ይስሐቅ ወታደሮች ተያዘች፣ ሁለተኛ ዙር ዘመቻ ትልቁ ዳሕላክ ተያዘ፡፡ በሦስተኛ ዙር ዘመቻ ምፅዋና የዳሕላክ ደሴቶች ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ውጭ ሆነው ስለነበረ እንደገና ተያዙ፣ በጦርነቱም መሪ የነበረ ቃዲ ተገደለ፡፡

ሌላ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ከአሪት ሐግ ገና ያልተላቀቁ የነበሩ ወገራና ደምቢያ አውራጃ ነበር፣ ቤተፀሎታቸው ወድመው በቦታው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩላቸው፡፡ ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተ ደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/፣ እናሪያ /ሊሙ/፣ እና ኩሮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ፡፡ ከዚሁም በስተደቡብ የነበረ የኢትዮጵያ መሬት ሰፋት በትክክለ ባይታወቅም ከስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በስተደቡብ እስከ ዛንዚባር፣ በምዕራብም እስከ ናይል ሸለቆ ይዘልቅ ነበረ[1]፡፡

ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከግቤ በስተደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/ እናሪያ /ሊሙ/ እና ኩሮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ፡፡ ሁሉም ከኢትዮጵያ ጋራ በሸዋ ግዛት የተቀላቀሉ የቀድሞ ግዛታቸው የሰይድ አልዲን ልጆች፣ የወላዝማ የነብዩ መሐመድ ዘር የሱልጣኖች ቤተሰቦች የሆኑ ከየመን ተመልሰው መጥተው የአባታቸው ሞት ለመበቀል ከግብፅ የመጡ በቱርክ ውጊያ ስልት አሰልጣኞች እየተረዱ ዘመናዊ የጠብመንጃና የጦር መሣሪያዎች የነበራቸው፣ የይግም ግራኝ ተመሳሳይ የሆነ መሣሪያ ታጥቀው ሰፊ ዘመቻ ጀምረው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጠንካራ ይመስል የነበረ ወታደራዊ የማጥቃት ዘመቻ እንደ ተጠበቀው ውጤት አላሰጠም፡፡ ንጉሥ ይስሐቅም የጠላቶቹ እንቅስቃሴ ያውቅና ይከታተል ስለነበረ ለመልሶ ማጥቃት ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ የዘመቻው ሹም የነበረው የሳይድ አልዲን በኩር ልጅ ሳብር አልዲን ነበረ፡፡ የእስላም ወታደሮች በድንገት አደጋ ጥለው ሸዋ መሀል ገብተው በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ሽንፈት አድርሰው ነበር፡፡ ንጉሡም ለመበቀል በእስላም ነጋዴዎች ላይ ጥቃት ከማድረሱም በላይ ያልፈረሱ መስጊዶችን አቃጠላቸው፡፡ ጦርነቱ ከ2ቱ ወገኖች አሸናፊ ሳይለይ ለብዙ ዓመታት ቀጠለ፣ በመሀሉ ሁለቱ ወገኖች ለጊዜያዊ ሰላም ተስማሙ፡፡ በዚሁ ጊዜ በ1422 ዓ.ም. ሳብር አልዲን ሞተ፣ ወንድሙ ማንሱር መሪነቱን እንደተረከበ ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ ማንሱር ጦነቱን በማፋፋም በአማራ መሀል ለመግባት ችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ሽንፈት ስለደረሰበት በ1424 ተማረከ፡፡ ጀማል አልዲን ሌላ ወንድማቸው መሪነቱ ተረክቦ ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ ቤተክርስቲያኖችም ይቃጠሉ ነበረ፣ ክርስቲያኖች የጦር ምርኮኞች በባርነት ይሸጡ ስለነበረ የባሪያ ዋጋ በዓረብ ሀገሮች ረክሶ ነበረ፡፡ ጦርነቱ አሸናፊ ሳይለይ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ክርስቲያኖች መልሶ በማጥቃት ድልን ተቀዳጁ፣ እስላሞቹንም ከሀገራቸው ሊያስወጡ ችለዋል፡፡ በ1429 ዓ.ም. ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ በነበረበት ጊዜ አጼ ይስሐቅ ተገደለ፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ ታዋቂው ጀማል አልዲን በቤተሰቦቹ በተፈጠረ ጠብ ሲገደል ሌላ ወንድሙ የመሪነቱን ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱ እንደቀድሞ ሞካኒ በተሞላበት ቀጠለ፡፡

(1) Coulbeaux : Histoire Pollitique et religieuse d' Ethiopia p. 285

## 4. አፄ ዘርአ ያዕቆብ

በክርስቲያን መንግሥትም ለአጭር ጊዜ ብዙ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ዝነኛው የኢትዮጵያ ንጉሠ ዘርአ ያዕቆብ በ1434 ዓ.ም. ነገሠ፡፡ በእሱ ዘመነ መንግሥት ሰለሞናዊ ሀረግ ያላቸው ነገሥታት ከፍተኛ ዝናና የአስተዳደር መሻሻል እርምጃ የታየበት ጊዜ ነበር፡፡ ተላላፊ በሽታ በሀገሪቱ ገብቶ ሰለነበረ ጦርነቱ ለተወሰነ ጊዜ ቆሞ ነበረ፡፡ ኢትዮጵያ በአጼ ዓምደጽዮን መሪነት በእስላሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሉች ዜና በመካከለኛው ምሥራቅና በምዕራባውያን ተሰምተው ነበር፡፡ ዜናዎች ቢሰሙም የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ፀረ እስላም የሚያካሄደው የሞት ሽረት ትግል ተቆርቋሪ በመሆን፣ የኢትዮጵያ እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች እርዳታ እንደሚያገኙ ሁሉ የክርስትና እምነት ያላቸው የኤውሮጳ ሀገሮች በምን ዓይነት መንገድ ለኢትዮጵያ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እርዳታ ማድረግ እንደሚችሉ የተደረገ ጥረት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ ከኤውሮጳ መንግሥታት የትኞቹ መንግሥታት እንደሆኑ በቂ ወታደራዊ እርዳታ ሊያደርጉላት የሚችሉ የማወቅ ዕድል አልነበራትም፡፡ ለምሳሌ ብቸኛ ግለሰብ በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የደረሰና ስለ ኤውሮጳ ለአፄ ዘርአ ያዕቆብ ያወራ አንቶኒዮ ባርቶሊ የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ ነበረ፡፡ ኢጣሊያ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለራሷ በባእድ መንግሥታት የምትገዛ፣ በጥቃቅን መንግሥታት የተከፋፈለች፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት የምትመረጥ ሀገር አልነበረችም፡፡ ባርቶሊ ለአጼ ዓምደ ጽዮን ይሰጣቸው የነበሩ ዜናዎች ስለ እነዚሀ የኢጣሊያ ታናናሽ መንግሥታት ከፍተኛ ሰልጣኔና ሰለ የሮማ ጳጳስ ትልቅነት ነበረ፡፡ ዘርአ ያዕቆብ አስቸኳይ የክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ፈላጊ ቢሆንም ከማን ጋራ ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚያስረዳ ሰው ሰለሌለው እንደ ቀድሞቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ዓምደ ጽዮንና ይስሐቅ ብቻውን ከእስላሞች ጋራ ጦርነት ገጠመ፡፡ ዘርአ ያዕቆብ በመጀመሪያ ያካሄደው ጦርነት በሀዲያ አውራጃ በራሱ ግዛት ነበረ፡፡ በዘርአ ያዕቆብ የዚሁ አውራጃ ገዥ ሆኖ የተሾመው የአንደኛዋ ሚስቱ ወንድም የሆነው ማሂኮ የተባለው ከአዳል ሱልጣን ጋራ በመመሳጠር ሸፍቶ፣ ነፃ መንግሥት አውጆ፣ ሌሎች አውራጃዎችን ወደ እሱ ለመሳብ በምስጢር ግንኙነት አድርጎ ነበር፡፡ ዘርአ ያዕቆብ እቅዱ ወደ ተግባር እስከሚፈጽመው ድረስ አልጠበቀውም፣ ከሥልጣኑ አውርዶ ወረረው፡፡ ማሂኮ ወደ አዳል ሸሽቶ ለመሄድ ወደ ምሽግ ቦታ ለመግባት ሲሞክር የዘርአ ያዕቆብ ወታደሮች ሰለደረሰበት ገደሉት፣ ሬሳውን፣ እግሮቹን፣ እጆቹን ተቆራርጠው ወደ ዘርአ ያዕቆብ ተወሰደው በንጉሡ ቤት ደጃፍ ተሰቀሉ፡፡ ከሁሉ የላቀ ድል አጼ ዘርአ ያዕቆብ የተቀዳጀው ለአዳል ሱልጣን በጀማል አልዲን ሰልጣን የያዘው የሰይዲ አልዲን ሌላ ልጅ በባድላይ ነበረ፡፡ በ1445 ዓ.ም. ባድላይ የዳዋሮን አውራጃ ወሮ ነበረ፡፡ ዘርአ ያዕቆብ በአነስተኛ ወታደሮች ቢገጥመውም የገጠመው በወኔ ሰለነበረ ድሉ የእሱ በመሆኑ በመጀመሪያ መስመር ሆኖ ይዋጋ የነበረ ባድላይ ከአጼ ዘረአ ያዕቆብ ጋራ ተወግቶ ወደቀና ሞተ፡፡ አስከሬኑ ተቆራርጦ ለመላው የመንግሥቱ ግዛት ተከፋፍሏል፡፡ የባድላይ ወንድም በመሸሽ ላይ እንዳለ አሳድዶ አዋሽ ወንዝ ለመሻገር በሚሞክርበት ጊዜ ተገደለ፡፡ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ሁለት ድሉችን በአጭር ጊዜ ቢጎናፀፍም የእስላሞች አደጋነት በሙሉ እንዳልተወገደ ስለተረዳና አሳሳቢ ስለሆነበት በሁለት መንገድ ዘላቂ መፍትሔ ብሎ የገመታቸው እርምጃዎች ወሰደ፡፡ የመጀመሪያ የክርስቲያኖች አንድነትና የእምነታቸው ማጠናከሪያ 2ኛ. ከዓለም ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ መጠየቅ ነበረ፡፡ አጼ ዘርአ ያዕቆብ በሁለቱ



መንገዶች ተጠቅመዋል፡፡ የክርስትና ሃይማኖት ለማስፋፋት በውድም በማስገደድም ሞክሯል፡፡ መንፈሳዊ መጽሐፎች ከውጭ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲሰጡ አስገድዷል፡፡ የማርያም ድንግል በዓላቶችና፣ ያምን ወዘተ ወሰኗል፡፡ አንዳንድ የውጪ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመግባታቸው በሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያለው ልዩነት የማዋዋያ እርእስት ሆኖ ነበረ፡፡ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ለማግኘት ለነበረው ምኞት ግን ውጤት አልባና ዓላማውን የሳተ ነበረ ለማለት ይቻላል፡፡ አጼ ዘርአ ያዕቆብ የኤውሮጳ መንግሥታትን ማንነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ በ1450 ዓ.ም. ለናፖሊ ንጉሥ መልእክት ልኮዋል፡፡ የናፖሊ መንግሥት፣ እንኳን ከኤውሮጳ መንግሥታት ሊወዳደር ቀርቶ፣ በኢጣሊያ ከነበሩ አነስተኛ መንግሥታትም ከሁሉም ኋላ ቀር የነበሩ መንግሥታት የሆነ ነበረ፡፡ ስለዚህ ምንም ዓይነት ጠቃሚ እርዳታ ለኢትዮጵያ መስጠት የሚችል አልነበም፡፡ የናፖሊ መንግሥት በሰዓሊ ሞያ ስም የላከው ብራንካሊዮ የሚባለው ግለሰብ ቀድሞ ቄስ የነበረ ስለሆነ ጊዜው ያሳለፈው የሃይማኖት ክርክር በመቀስቀስ ብቻ ነበረ፡፡ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ለዝነኛው የቢዛንታይን ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ እንዳይጠይቅ በዚሁ ጊዜ በቱርክ ኦቶማን መንግሥት ተሸንፎ በ1454 ዓ.ም. ዋና ከተማው ቆስጣንጥንያ የተማረከበት ወቅት፣ሕልውናውም ያበቃበት ጊዜ ነበረ፡፡ሌላ አጼ ዘርአ ያዕቆብ በትልቅ ጉጉት እርዳታ እንዲያደርግለት ሲጠባበቅ የነበረው ከሮማ ጳጳስ ነበረ፡፡ ወቅቱ በቱርክ ኦቶማን አማካኝነት የእስልምና ሐይማኖትና መንግሥታት በኤውሮጳም በአፍሪካም ጥንካሬ ያገኙበት ነበረ፡፡ በዚሁ የተነሳ የሮማ ጳጳስ የመላው ዓለም ክርስቲያኖች ለማስተባበር በ1440 ዓ.ም. ጣሊያን ሀገር በፈሬንሴ ጉባዔ ጠርቶ ነበረ፡፡ ኢትዮጵያም የግብፅ ቤተክርስቲያንም መልእክተኞቻቸው ወደዚሀ ጉባዔ ልከው ነበር፡፡ የግብፅ መልእክተኞች የተመሩት እንድሪያ በተባለው የቅዱስ አንቶንዮስ ገዳም አለቃ ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ቀሳውስት የተላኩት ከአባ ኒቆዲሞስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አለቃ ወክሉ ነበረ፡፡ የሮማ ጳጳስ ዓላማ የዓለም ክርስቲያን በሙሉ የካቶሊክ እምነት ተቀብለው በእሱ ስር እንዲሆኑ ነበረ፡፡ ለክርስቲያኖች ትብብር እንቅፋት የሆነውም ይህ ቅድመ ሁኔታ መግባት ሰለነበረ ነው፡፡ ኢትዮጵያም ከዚሀ ቀደም እርዳታ ከክርስቲያን መንግሥታት ያላገኘችው በዚሁ ቅድመ ሁኔታ ምክንያት ነበር፡፡ የግብጽ መልእክተኛ ለጉባኤው ያደረገው ንግግር የሮማ ጳጳሳት በማወደስ ነበረ፡፡ ከተናገረውም ውስጥ የሮማን ጳጳስ በማስመልከት "በዚሁ ዓለም እርሶዎ እግዚአብሔር ነዎት እርሰዎ የክርሰትና እንደራሴ ነዎት፣ እርሰዎ የዓለም ኋቀፍ ቤተክርስቲያን አለቃ ነዎት ለእርሰዎ የመንግሥተ ሰማያት በር የመክፈት፣የመዝጋት ቁልፍ ተሰጥቶታል ወዘተ... የሚል ይገኝበታል፡፡ የግብፅ መልእክተኛ ንግግር ከተሰጣ ሁለት ቀን በኋላ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ፈሬንሴ ገቡ፣ ከሁለቱ መልእክተኞች አንዱ ባደረገው ንግግር የግብፅ መልእክተኛ ካደረገው ንግግር ተመሳሳይ ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ሀገሩ ኢትዮጵያ በሚመለከት ያሰማው የሚያወድሱ ቃላቶች ነበሩ፡፡

ወደ ሮማ ጳጳስ ፊቱን አተኩሮ ሲናገር "ከእርሰዎ የተለዩ ሁሉ ወድቀዋል፣ ከሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከተለዩ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የእኛ ጠንካራና ኃይለኛ ነፃ ሆና ኖራለች፣ ምክንያቱም ሌሎች ቤተክርስቲያኖች ከእርሰዎ የተገነጠሉ በክፋት በፍላጎታቸው ነው፣ እኛ ግን ተለይተን የኖርነው በመገደድ፣ርቀት የተነሳ፣ በመንገዱ አደገኛነት ነው፣ ከእርሰዎ በፊት የነበሩ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ቸልተኝነት ነው፤

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በዚህ ዓለም ከሮማዊት ቤተክርስቲያን ጋራ ከመዋሐድ ሌላ ምኞት የለውም" ወዘተ... የሚል ይገኝበታል፡፡

አጼ ዘርአ ያዕቆብ ግዛቱ ወደ ደቡብ አስፋፍቶ ስለነበረ፣ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በኩራት አፋን ሞልቶ ሲናገር "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አንድ መቶ ነገሥታት እንደሚያዝዝ ለጉባኤተኞች ተናግሯል፡፡ የፌሬንሴ የጉባኤ ቡተሳካ ሁኔታ የተፈጸመ መስሎ ቢታይም መልእክተኞቹ ተመልሰው ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ካይሮ ሲገቡ የጉባኤው ውሳኔ ሳይፈርም በቀረ ብቸኛ ንቅናቄ ተደርጎባቸው ሁሉም የምሥራቅ አበያተክርስቲያን የሚያጠቃልል ፀረ ሮማ ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ተነስቶ ነበር፡፡ ስለዚህ የፌሬንሴ ጉባዔ ለሮማ ጳጳስ ከባድ ክስረት ነበር የሆነበት፡፡ በአጼ ዓምደ ጽዮን የአጼ ይስሐቅና በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ በቀይ ባሕር ወደቦች በክርስቲያን ስም ከቱርክ አቶማን ጋራ ትፋለም የነበረችው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ኢትዮጵያ ግንኙነት አድርጓ ብትሆን ኖሮ በይማም ግራኝ ጊዜ እርስ በእርስ ጦርነትና የሀገሪቱ አበያተክርስቲያናት የቅርሳቅርሷ የመጻሕፍቶቿና የታሪኳ ውድመት አይደርስባትም ነበር፤ የኦሮሞ ታሪካዊ ማስፋፋት ክስተት አያጋጥማትም ነበረ፡፡ ከአጼ ዓምደ ጽዮን ጀምሮ ከባህር ወደቦች በቀር የመሀስ ሐገር የአክሱም መንግሥት ዘመን ወደነበራት ስፋት ተመልሶ ነበረ፡፡

በአፈ ታሪክ አባባል ኢትዮጵያ 14 መንግሠታት ነበሯት፡፡ ከነዚህም ውስጥም 4 መንግሥታት የወርቅ ዘውድ የሚጭኑ ነበረ እነሱም 1. ትግራይ 2. አማራ /ጎንደር/ 3. ላስታ 4. ሸዋ /ጎጃም ናቸው፡፡ ሌሎች 4 ነገሥታት የብር ዘውድ የሚጭኑ እንደዚሁም ነገሥታት የነሀስ ዘውድ የሚጭኑ ስማቸው የማይታወቅ ነበረ፡፡

አልቤርቶ [1]ፖሌራ እንደጠቀሰው በ1603 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ሚሲዮናዊ አባ ፓየዝ በጻተፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 35 መንግሥታትና 18 ራስ ገዝ አስተዳደሮች ነበሯት፡፡

እንደዚሁም ፖሌራ በ1629 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ፖርቱጋላዊ፣ ሚሲዮናዊ ፣ ዳሜዳ የጻፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 36 መንግሥታትና 17 የራስ ገዝ አስተዳደር ያላቸው ግዛቶች ነበራት ካለ በኋላ! ባገኘው ሌሎች ዜናዎች ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት 60 መንግሥታት ክርስቲያን ያልሆኑ እንደዚሁም ሌሎች ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ገባር መንግሥታት ያዝዝ እንደነበረ ገልጧል፡፡

በተጨማሪም ፖሌራና ኮንቲ ሮሲኒ ገጽ 15 እንደጠቀሱት ከ1624 ዓ.ም. እስከ 1704 ዓ.ም. የኖረው ጀርመናዊ ሉዶልፍ የኢትዮጵያ ቋንቋና ታሪክ አዋቂ በጻፈው መሠረት በማድረግ በተለያዩ ጸሐፊዎች የሚነገረው የመንግሥታት ቁጥር የተለያየ ነው ብሎ ካስጠነቀቀ በኋላ ኢትዮጵያ 30 መንግሥታት ነበሯት በማለት ስማቸውን ይጠቅሳል፡፡ የመንግሥታቱ ስም በተመለከተ አብዛኛው አሁን ቢኖርም ያንዳንዶቹ ስም ግን አሁን የለም፡፡ ፓየዝ ባወጣው የ35 መንግሥታት ስም ዝርዝር እንደሚከተው ያቀርበዋል 1. ትግራይ ወሰኑ ከዩት ወዴት መሆኑን ባይገልፅም በዛሬዋ ደቡብ ትግራይ ከፍል አበርጋለ፣ ሰሎዋ፣ ወገራት፣ እንዳርታ፣ እንደ አካል ነበረች 2. ደንከል /አፋር/ 3. እንጎት አብዛኛው የባሬዋ ወሉ 4. ዶባ ከወሉ ትግራይና አፋር መሐል የነበሩ ሕዝቦች 5. አውሳ ደቡብ አፋር 6. አማራ ምናልባት ደቡብ ጎንደር 7. አላቃ 8. ሸዋ ከዩት ወዴት እንደሆነ

[1] Alberto Pollera : Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa



አይታወቅም 9. ይፋት 10. ገዳም 11. ጋንች 12 ዳዋሮ/ ምናልባት የዛሬዋ ጨርጨር 13. ፋጢጋር ከይፋት በስተሰሜን የዛሬዋ አርጎባ 14. አዩዩ ከዝዋይ ሀይቅ በስተምሥራቅ 15. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሶማልያና ሕንድ ውቅያኖስ 16. ሀዲያ 17. አላባ /ቆቃ አካባቢ 18. አክስለን 19. ቤቶ ቆቃ አካባቢ 20. ቤቴሪምራ 21. ጉራጌ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 22. ኮይራ /ከጁባ ወንዝ እስከ ስተፋኒያ ሀይቅ 23. በዙማ ከዝዋይ በስተደቡብ 24. ሱፍ ጋሞ የዝዋይ በስተደቡብ በአብያታ ሐይቅ እስከ ቆይራ ባሕር ጋ 25 ባሕር ጋ 26. ከንባታ 27. ቦሻ (ጅማ) 28. ጉመር /ከፋጢጋር በስተደቡብ 29. ጃንጃሮ 30 እናርያ (ሊሙ) 31. ኮንታ 32 ዳሞት 33. ጎጃም 34. ቤጌምድር 35. ደንብያ፡፡

በዚህ ስም ዝርዝር እንደምንመለከተው የዛሬዋ ጎንደር ክፍለ ሀገር ለቤጌምድር ደምቢያ አማራ መንግሥታትና በሰሜን ፀለምቲ ቦራ ፀገሌ ወልቃይት ማፀጋራ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ተከፋፍላ ነበረች፡፡ ላስታ በሁሉም ስም ዝርዝር አይገኝም፡፡ ወሰጋ የቢላሞ መንግሥት ተብላ ትጠራ ነበረ፡፡ ከዲዴሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ግን ጋፋት ተብሎ ይጠራ ነበረ፡፡ ይህ ሰፊ የኢትዮጵያ ግዛት በታሪክ በመልክአ ምድር አቀማመጥ በዘር አንድ የሆኑ ሕዝቦች በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ይተዳደሩባት የነበሩ ኢትዮጵያ በእስልምና እምነት ተከታዮች እርስ በእርስ ጦርነት ባትወጠር በተለይም በሌላ አርእስት እንደሚታየው የኦሮሞ የማስፋፋት ክስተት ባያጋጥማት በኬንያ በኩልም እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም በላም ለመድረስ በአካባቢው የተደራጀ ተቃዋሚ ኃይል ስላልነበረ እንቅፋት አያጋጥማትም ነበረ፡፡

ይህ በማድረጓም በአፍሪካ ስልጣኔ ለማስፋፋት የነበራት ታሪካዊ ተልእኮ መወጣቷ የሚያመለክት ስለሆነ የሚያስመሰግናት ነበረ፡፡ የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን የሚወቅሷት ይህንን ባለማድረጓ ነው፡፡ የዛሬዎቹ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ግን የደቡብ ምስራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ምኒልክ በዛሬ አንድ መቶ ዓመት በወረራ እንደያዛቸው ለማስመሰል እየሞከሩ ይታያሉ፡፡ ከንያ ውስጥ የሚኖሩ የኦሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ከኢትዮጵያ ተነጥለው ከኬንያ ጋራ የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ በኦሮሞች ምክንያት የጋጠማት የመንግሥቷ ድክመት ነው፡፡

በንግሥት ሳባ ጊዜ ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የት ድረስ ይደርስ እንደነበረ በማመልከት [1] ሻለቃ ሩፌሎ ፔሪኒ እንደሚመለከተው ይገልጸዋል "የባሕር ነጋሽ ሥልጣን ከበረኒስ የባሕር ወሰመጥ 24⁰ ዲግሪ በስተሰሜን እስከ የእጣኑ ሀገር ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም እስከ ሶፎላ 20⁰ ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዩድ ይደርስ ነበረ፡፡ በዚሁ ቦታ የብዙ ሳይንቲስቶች እምነትም ከነእሱ ውስጥም በመጨረሻ ጊዜ የብሪቲሽ ሙዝየም ስራ አስኪያጅ የነበረ ሚቼ ሚስተር ቤንት ባለበት፣ በመጸሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ኦፊር የሚባለው ምስጢራዊ ቦታ ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሠ ሰለሞን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንድትችል መርከቦች የተሰሩበት መሆኑን ገምቷል"፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እነ አጼ ይስሐቅ ወደ ደቡብ ያመሩበት የነበረ ሀገር የቅድመ አያቶቻቸው ይዞታ የነበረ መሆኑን በማስታወስ የሆናል፡፡

በነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ስፋት ሉካ ደይ ሳቤሲ[2] እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

[1] Perini Mereb-Melash (Al di qua del Mareb)
[2] Luca Dei Sabelli\ VII p. 15-17

1. ኢትዮጵያ በሰሜን ወሰኗ እስከ ምፅዋ ይደርስ ነበር፡፡ ሐማሴን፣ ሰራዬ፣ አከለጉዛይ አውራጃዎች እስከ ቀይ ባሕር ድረስ የባሕር ነጋሽ መንግሥት አካል ነበሩ፡፡ ዋና ከተማ ድባሩዋ ነበረች፡፡ ሳሄልና ባርካ በቁጥጥሩ ስር ነበሩ፡፡

2. ትግራይ ዋና ከተማ አክሱም ሆኖ በትግራይ መኰንን የሚታዘዝ ነበረ

3. ሰሜን አፋርና ደቡብ አፋር (አዋሳ)

4. ዳዋሮ (ጨርጨር)

5. ባሊ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ በዚህ በኩል የኦሮሞ ክስተት ባያጋጥም ኖሮ የክርስቲያኖች ፖለቲካዊ መስፋፋት መቋቋም የሚችል ተቃዋሚ ኃይል አልነበረም

6. ፋጢጋር ከባሊ በስተምሥራቅ ከመካከለኛ አዋሽ ወንዝ እስከ ዋቢ ወንዝ ምንጭ የሚያጠቃልል

7. አይ ወይንም ወድ ይባል የነበረ ከፍለሀገር ግእከሉ በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ ነበረ፡፡ በዚህ አውራጃ በዛሬ አጠራር ስልጢ የተባሉ ቋንቋቸው ከሐረሪ የሚቀራረብ ጉራጌዎች ይኖራሉ፣ አመጣጣቸውም ከጥንታዊው አክሱም መንግሥት ነው፡፡

8. ከወደ በስተደቡብ ከዝዋይ ሐይቅ እስከ አባያ ሐይቅ ሱፍጋኖና ቡዣሞ የተባሉ ሁለት ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

9. በስተደቡብ ኮይራ ነበረ ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው ለወታደሮች የሚያገለግሉ ፈረሶች በማቅረብ ነበረ፡፡ የሚገኘውም ከላይኛው ጁባና ከአባያ ባሕር ሐይግ መሐል ነበረ እስከ እስቴፋኒያ ሀይቅ ከንያን የሚያጠቃልል ነበረ

10. ወላሞና ጋሞ በንጉሥ ይስሐቅ ዘመቻ ጊዜ የተቀላቀሉ ከአባያ ሐይቅ በስተምዕራብ የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ግዛቶች ሁሉ የታወቀ ተቃዋሚ የተደራጀ ኃይል ስላልነበሩ ኦሮሞዎች ከኢትዮጵያ ባየገነጧቸው ወሰናቸው እስከ ተፈለገ ሩቅ ሊዘልቅና ሊሰፋፋ ይችል ነበር፡፡

11. በስተምዕራቡ በአጼ ይስሐቅ ወደ ግእከላዊ መንግሥት የተቀላቀሉ ትናንሽ መግሥታት ነበሩ ከነሱ ውስጥም እናሪያ /ሊሙ/ በሻ (ጅማ አባጅፋር) ወዘተ... ይገኙባቸዋል

12. ሰታችኛው እሞ ሰፌ የጃንጀሮ መንግሥት ነበረ

13. በስተሰሜን ከንባታ ነበረ፡፡ ከእዋ በስተግራ እስከ አቢያታ ሀይቅ

14. ከከንባታ በስተሰሜን ከላይኛው አዋሽ እስከ እሞ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 1000 በሬዎች ግብር ለመንግሥት የሚከፍል የጉራጌ መንግሥት ነበረ

15. ከጉራጌ አዋሳኝ የሀዲያ ሱልጣን አገዛዝ ነበር

16. ከሐዴያ እስከ ሸዋ አሰግስ ቱጋር የሚባሉ ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

17. ኪጋንዝ በስተምዕራብ ትልቁ ዳሞት ነበረ

18. በስተምዕራብ በዛሬዋ ወለጋ ቢዛሞ የሚባል መንግሥት ነበረ

19. ከዲዴሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ጋፋት ነበረ

20. አባይ ተሻግሮ ጎጃም ይገኛል

21. ከጣና ሐይቅ እስከ ተከዜ በጌምድር

22. በዛሬዋ ጎንደር ዙሪያ ደምቢያ ነበረ



23. ወደ ሰሜን ፀለምቲ፣ ፀጌሊ፣ ወልቃይት፣ ሰሜን፣ ማዘጋዘ፣ የተባሉ ከጥንት ጀምሮ አገውና ፈላሻ የሚኖርባቸው ናቸው፡፡

24. ከተከዜ ወንዝ በስተሰሜን ሰሰዋና አበርጋሌ ይገኛሉ

25. ወገራትና እንደርታ አውራጃዎች ከጥንት ጀምሮ ራሳቸውን የቻሉ ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የተሰጣቸው ነበሩ

26. ከንደርታ በስተደቡብ ላስታ

27. ከላስታ በስተምሥራቅ አንጎት የዛሬዋ ወሎ አብዛኛውን የሚያቃልል

ከሞላ ጉደል የኢትዮጵያ አስተዳደር አከፋፈል ካርታ ይሄንን የሚመስል ሲሆን ስፋቱ ከዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በጣም የሚበልጥ እንደነበረ ብዙ ማስረጃ ባይኖርም የኢትዮጵያ ግዛት ኬንያም ያጠቃልል እንደነበረ የሚጠቁም 200 ዓመት ከአጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ በአጼ ፋሲሊደስ ዘመነ መንግሥት በኋላ የሞምባሳ Mombassa ንጉሥ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚታዘዝ መሆኑን ሉካ ደይ ሳበሊ[1] ገልፀዋል፡፡ እንደፈረንጆች ቃል አገላለፅ የኦሮሞ ፌኖሚኖን /Oromo phenomenon) በኢትዮጵያ ታሪክ ባያጋጥማቸው ኖሮ ጀግኖች አባቶቻችን በእነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት እንደ አክሱማውያን እስከ ሶፎላ ባይደርስም ኬንያንና ደቡብ ሶማሊያ የሚያጠቃልል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ዘልቆ እንደነበረ፣ ይኸውም ለ200 ዓመት ቀጥሎ እንደነበረ ፊከላይ የተጠቀሰው የታሪክ ማስረጃ ያመለክታል፡፡ የኦሮሞ ፌኖሜኖን ያልኩበት ምክንያት የኦሮሞ ወደ መሀል ሀገር መስፋፋት የውጭ ወረራ አይባልም ወይንም በአንድ ሀገር ውስጥ በሁለት ጎሳዎች ወይም ክፍለ ሀገሮች የተደረገው እርስ በእርስ ጦርነት አይባልም፡፡ ከላይ ከአንደኛ እስከ 27ኛ ተራ ቁጥር የጠቀስኳቸው በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና ክፍላተ ሀገሮች ካርታ የኦሮሞ ስም አልነበረም፡፡ የኦሮሞ ክስተት የመጣው ከተጠቀሰው ዓ.ም. በኋላ ነው፡፡ አሁን የሚታየው የኦሮሞ አሰፋፈር ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ሐረርጌ እስከ ምዕራብ ኢሉባቡር ሌሎች ሕዝቦች ሰፍረውበት የነበሩ መሬት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸውም የኦሮሞ ክስተት በኢትዮጵያ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ዳግማዊ ምኒለክ የሚወክለው የአማርኛ ቋንቋ በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ ወረራ በመፈጸም ሌሎች ሕዝቦች በቋንቋቸውና በባሕላቸው እንዳይጠቀሙ አድርገዋል የሚል ወቀሳ በአሁኑ ጊዜ ሲሰነዘር ይሰማል፡፡ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ ለአስተዳደር እንዲያመች የመንግሥት ቋንቋ አማርኛ ስለነበረ በአገሪቷ አስተዳደር በሚመለከት በተዘረጋው በጣም ዝቅተኛ የአስተዳደር መዋቅር የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋዎች ሳይነኩ ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ሁሉ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም ያስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ቆየቶ ነበር፡፡

የአማርኛ ቋንቋን ለማስፋፋት ምክንያት የሆነው ግን በይበልጥ ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ በኃይለሥላሴ ጊዜ ትምህርት ቤቶች ስለተስፋፉ ይሆናል፡፡ የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋና ባሕል ማጥፋት ብቻ ሳይሆን የሕልውናቸውም ማጥፋት የተፈጸመው በኦሮሞች የጋዳ አስተዳደር ዘዴ ነው፡፡ የኦሮሞ ቋንቋ በአጭር ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ መስፋፋት ሁኔታ በቂ ማስረጃ ባይኖርም ምናልባት ቀደም ብለው ሰፍሮበት የነበረውን ሕዝብ በሙሉ እየፈጁ ማስለቀቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሕዝብ የሌላ ሕዝብ ቋንቋና ባሕል በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰላም ስለማይቀበል በከፊል ነዋሪ

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 384

ሕዝቡን እየጨረሱ ቋንቋውንና ባሕሉን የመቀየር ሂደት እንደተካሄደ አያጣራጥርም፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን የኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች የአንድ ጎሳ አባል ሳይሆኑ የብዙ ጎሳዎች ቅልቅል መሆናቸውን አያስቸግርም፡፡ ስለዚህ ከአማርኛ የበለጠ የኦሮሞ ቋንቋ የማስፋፋት ዕድል አግኝቷል ለማለት ይቻላል፡፡ ብዙዎቹ አሁን በኦሮምኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ ሕዝቦች የድሮ ቋንቋቸው አማርኛ ነበር፣ ወይንም የሲዳማ ቋንቋ ነበረ ሌሎችም በደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ የሚገኙ የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሁን ልናውቃቸው የማንችል የተለያዩ ቋንቋዎች እንደነበሯቸው መገመት አያዳግትም፡፡ በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የኦሮሞኛ ቋንቋ ተቀብለው ስለነበረ አሁንም ይጠቀሙበታል፡፡

አጼ ምኒልክ 450 ዓመት ከነ አጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ ኢትዮጵያ የቀድሞ ግዛቷ በከፊል እንድታገኝ በማድረጉ የሚደነቅ ነገር አይደለም፡፡ ወገን ከወገኑ እንዲቀላቀል በማድረጉ ያስመሰግነዋል እንጂ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ወራሪ አያሰኝም፡፡ ሐቀኛ ኢትዮጵያውያን ምኒልክን የሚወቅሱት እንደ አጼ ይስሐቅ ዘይላን፣ በርበራን፣ ሞቃድሾን ችላ በማለት አለመያዙ ነው፡፡ በተለይም ኤርትራ ለኢጣሊያ ገፀ በረከት መስጠቱ በታሪክ ሲያስወቅሰው የሚኖር ስለሆነ ሀገሩን የሸጠ ከዳተኛ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሚል አጠራር ሲያስታውሱት ይኖራሉ፡፡

## 5. ንግሥት እሌኒ

የኢትዮጵያ መንግሥታት እስላሞችን ለማጥፋት በኃይል የማይቻል መሆኑን እየተረዱ ስለመጡ የክርስቲያን ግብጾችና ካቶሊኮች ድጋፍ መፈለግ ጀመሩ፡፡ ከዓረብ መንግሥታትም በቻል ወዳጅነት መፍጠር ካልተቻለም ገለልተኛ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ተሞክረዋል፡፡ የዓረብ መሪዎችም በሰላማዊ መንገድ አብረው በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ተሞክራል፡፡ የዚሁ ፖለቲካ ቀስቃሽ ንግሥት እሌኒ ነበረች፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብም ቢሆን ከእስላም ጋራ በሰላም ለመኖር በመፈለግ ከሀዲያ አንድ ሚስት አግብቶ ነበር፡፡ ንግሥት እሌኒም ራሷ በልጅነቷ እስላም ነበረች፡፡ የአጼ ዘርአ ያዕቆብ ልጅ አጼ በእደ ማርያም ሁለት የእስላም ሚስቶች ነበሩት ንግሥት እሌኒና ንግሥት ሮማን ወርቅ፡፡ እነሱም ከአዳል ሱልጣኖች የሚወለዱ ከታወቁት የየመንና የሀድራሞት የመንግሥታት ዘሮች ይዛመዱ የነበሩ ናቸው፡፡ በተለይ ንግሥት እሌኒ በዘርአ ያዕቆብ የተተኩ አራት የኢትዮጵያ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በውጭ ጉዳይ አመራር ተሰሚነት አግኝታ ነበር፡፡ ወደ ዓረብ ሀገር የሚመላለሱ አርሜን፣ ዓረብ፣ ሕንድ፣ ግሪክ፣ ነጋዴዎች መረጃ እንዲያቀብሏት ታደርግ ነበረ፡፡ 500 ሰዎች አባል የነበረው አንድ የኢትዮጵያ መልእክተኛ ቡድን ወደ ግብፅ ሱልጣን ተልኮ ነበረ፡፡ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና ሰልፍ በካይሮ በታየበት ጊዜ ተቃውሞ ከሕዝቡ ስለተቀሰቀሰበት በባለስልጣኖች እርዳታ ብቻ ከአደጋ ሲያመልጥ ችሏል፡፡ ንግሥት እሌኒ ክርስቲያን ብትሆንም ከአዳል ቤተሰቦቿ ግንኙነት አላቋረጠችም ነበር፡፡ ጥረቱንም ከንቱ አልሆነም፡፡ የአዳል ሱልጣን የነበረው መሐመድ ጦርነት ከማድረግ ይልቅ በሰላም አብሮ መኖር ፈላጊ ሆኖ ነበረ፡፡ በጋብቻ በመተሳሰርም በአንድ ሆኖ በሰላም መኖር ደህና ውጤት ያስገኘ መሰለት ነበር፡ ነገር ግን የሱልጣኖች ስልጣን ስም ብቻ ሆኖ ራሳቸው ስልጣን የጨበጡ አሚር የተባሉ ከክርስቲያን ጋራ በሰላም መኖር የማይዋጥላቸው ሰዎች ተፈጥረው ነበረ፡፡ የሰላም ጥረቱም በይበልጥ የከሸፈው በኤውሮጳ በክርስቲያኖችና በዓረቦች እስላሞች መካከል



ይደረግ የነበረው ጦርነት ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት በሀገራችንም ስለተዛመተ ነበር፡፡

ወቅቱ ኤሮውጳ ግዛቷ ወደ ሌላ የዓለም ክፍሎች ማስፋፋት የጀመረችበት ነበረ፡፡ ከኤውሮጳውያን የማንባር ቀደም በመሳው የኤውሮጳ ስም የፖርቱጋል ዓላማ የአፍሪካ የባሕር ጠረፍ ዙሪያ ለመቃኘት ነበረ፡፡ የሮማ ጳጳስ የፈሬንሲ ጉባኤ የጠራ ዓላማውን ግመደገፍ ማንኛውም የአፍሪካ ወደብ በፖርቱጋል የጦር መርከቦች ከተገበኘ የፖርቱጋል እንዲሆን ስለፈቀዱ ፖርቱጋሎች ጥረታቸውን በመቀጠል ምዕራብ አፍሪካን ዞረው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ደረሱ፡፡ ከደቡብ ፖርቱጋሎች ቀይ ባሕር ሲደርሱ ቱርኮችም ከሰሜን ግዛታቸውን እያስፋፉ ቀይ ባሕር ደርሰው ነበር፡፡ በ1517 ዓ.ም. ቱርኮች በድል አድራጊነት ካይሮን ያዙ፡፡ በዚሁ ጊዜም ሱዋኪምና ምጽዋን ተቆጣጠሩ፡፡ በቀይ ባሕር ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በጭካኔ ይፋጁ ነበረ፡፡ በኢትዮጵያም በአዳል ሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ጦርነት እንዲቀሰቀስ አስተዋጽ ነበረው፡፡

## 6. አፄ በእደማርያም

አፄ በእደማርያም የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት በመጀመርያ ጦርነት ያካሄደው በሰሜን፣ በጸለምት፣ የነበሩ ፈላሾችና በዶባ ነበረ፡፡ በስተምሥራቅ የአዳል ሱልጣን መሀመድ ወደ በእደማርያም መልእክተኛ ልኮ ግብር እየከፈለ የበላይነት አምኖ በሰላም ለመኖር ስለተስማማ ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ ነበር፡፡ የአዳል ሱልጣን መሐመድ በ1470 ዓ.ም. ሲሞት ልጁ ኢብራሂም ሲተካ ስልጣኑ በኢሚሮች እጅ ሆኖ ነበር፡፡ ሱልጣኑ ለስም ብቻ ተቀምጦ ነበር፡፡ በ1474 ዓ.ም. ከአዳል ጋራ በተደረጉ ጦርነቶች ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንፈት ገጠማቸው በእደማርያም ከሞቱ በፊት 1478 ዓ.ም. ለግብፁ ሱልጣን በሰላም ለመኖር ውል ስማድረግና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን እርዳታ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ መልእክተኛ ልኮ ነበር፡፡ መልእክተኞቹ ከግብፅ ቤተክርስቲያን ወደ ፊልስጤም አምርተው ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ሮማ እንዲሄዱ ገፋፉቸው፡፡ በዚሁ መሠረት መልእክተኞች ወደ ቆስጠንጥኒያ በሚሄድ ፋንታ ወደ ሮም አመሩ፡፡ ኖቬምንበር 1481 ዓ.ም. የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሲስቶ4ኛ. በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተቀበሏቸው፡፡ 1ኛ. አባ ፍራንችስኮ ሳጋራ 2ኛ. አባ ጆቫኒ ዲ ካላብሪያ 3ኛ. አስተርጓሚ ሆኖ ከኢየሩሳሌም አብሮ የመጣ አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲ ኢሞላ የሚባሉ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ፡፡ አባ ሳጋራ ካይሮ ሲደርሱ ሞተ፣ ሁለቱ ግን ኢትዮጵያ ደርሰው ንጉሥ እስክንድር ወደ አለበት ደረሱ፡፡ ነገር ግን አባ ጆቫኒ ዲአሞል ወደ ንጉሡ መቅረብ 8 ወር ጠብቆ ሳይሆንለት ሲቀር አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲአምሪ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው የሚሲዮናውያንም ተልኮዋቸው ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ፡፡

## 7. አፄ እስክንድር

በበእደ ማርያም ምትክ እስክንድር የአደ ማርያምና የሮማን ወርቅ ልጅ ተተካ፡፡ በእደማርያም የሞተው በ1478 ዓ.ም. ነበር፡፡ እስክንድርም አንድ ጊዜ ብቻ በአዳል ያልተሳካ ጦርነት አድርጎ በ1495 ዓ.ም. ዐረፉ፡፡ በእስክንድር ዘመነ መንግሥት በፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ሁለተኛ አልፎንሶ

ዳ ኳይሻ ፔድሮ ዳ ኮቪልሃም የ ባሰው የሐበሻ መንግሥት የት እንደሚገኝ ፈልገው እንዲያገኙ በ1487 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጧቸው ወደ ግብፅ አመሩ፡፡ የሐበሻ ሀገር በአፍሪካ ይሁን በእስያ የማይታወቅ ስለነበረ ካይሮ ደርሰው ከሱዋኪም አደን ቢገቡም የሚነግራቸው ሲያጡ አንዱ ወደ አፍሪካ አንዱ ወደ እስያ ሄደው እንዲፈልጉ ተስማምተው አልፎንሶ ዳ ፓይቫ በርበራ ደረሰ፣ እዚያው ተገደለ፡፡ ፔድሮ ዳ ኮቪልሀም ግን ሕንድ ገባ፣ ተመልሶ ወደ አፍሪካ በመምጣት የምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፎች ጎብኝቶ ካይሮ ገባ፡፡ እዚያው የጓደኛው ሞት ሰማ፡፡ ከፖርቱጋል ንጉሥ አዲስ ትዕዛዝ ስላልተሰጠው ወደ ጅዳ ሄደ፡፡ በመጨረሻ ዘይላ ገባ፤ ከዚያም ጦርነት የሚደረግበት የአዳል ሀገር በድፍረት አቋርጦ ንጉሥ እስክንድር ወደሚገኝበት ደረሰ፡፡ ንጉሡ ከታላቅ ክብር ተቀበሉ ወደ ዋና ከተማው ወደ ተጉለት ወሰደው፡፡ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ግን አልፈቀዱለትም፡፡ እስክንድር እንደሞተ አለመግባባት ተፈጥሮ የእስክንድር ልጅ የ7 ዓመት ሕፃን ቢነግሥም ስለሞተ፣ የእስክንድር ወንድም ናኦድ ንጉሥ ሆነ፡፡ የአዳል ሱልጣን በናኦድ ጊዜ የሰላም ጥሪ ቢቀጥልም ማሃፉዲ የተባለው የሐረር ኤሚር ግን በክርስቲያን መንግሥት በየዓመቱ በፋሲካ ፆም ጊዜ ጦርነት እየቀሰቀሰ ክርስቲያኖችን እየወሰደ በባርነት እየሸጣቸው ከብቶችም ይዘርፍ ስለነበረ ንጉሥ ናኦድ ጦርነት ገጠማቸው በሐሰት የመሸሽ የጦርነት ስልት በመጠቀም ከ0 የሐረር ኤሚር ወታደሮቹን ፈጃቸው፡፡ የማሕፉድ መሸነፍ የእስላም ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ መንፈስ አቀዘቀዘው የአዳል ሱልጣንም ከንጉሥ ናኦድ ጋራ ሰላም ስለፈጠረ ለብዙ ዓመታት በምሥራቅ በኩል ሰላም ሰፍኖ ነበር፡፡

## 8. አፄ ልብነ ድንግል[1]

ንጉሥ ናኦድ ሲሞት በ1508 ዓ.ም. ልብነ ድንግል ብቸኛ ልጁ ሲነግሥ ሀገሪቱ ሰላም አግኝታ ነበር፡፡ በፖለቲካ በኩልም ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት በመፍጠር መልካም እርምጃ የታየበት ወቅት ነበር፡፡ ልብነድንግል ልጅ ስለሆነ የመንግሥቱ አመራር በእናቱ በንግሥት እሌኒና በታዋቂው የነበረው ሰው ወሰን ሰገድ ይመራ ነበር፤ ተቃውሞም አልነበረውም፡፡ በልብነድንግል ዘመነ መንግሥት 60 የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ይኖሩ ነበር፡፡ ንግሥት እሌኒ በመንግሥት ሞግዚትነት በነበራት ተደማጭነት የውጭ ሀገር ሰዎችም ምክር በመቀበል ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት ለማጠናከር ትጥር ነበር፡፡ የክርስቲያን መንግሥት በእስላሞች ላይ በየጊዜው እንዳይወረር ያለው አማራጭ የባሕር በሮች ከእስላም መንግሥታት እንዳይገናኙ ማድረግ ነበር፡፡ ይኸንኑም ማድረግ የምትችለው እንደ ፖርቱጋል ጠንካራ የጦር መርከቦች ያላት መንግሥት መሆን ይገነዘባል፡፡ የፖርቱጋል መልእክተኛ ፔድሮ ዲ ኳቪልሃም ይኸንን ሐሳብ በመደገፍ የባሕር ወደብ ከተሞች ለፖርቱጋል ካልተሰጡ እርዳታ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ሐሳብ አቅርቦ ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ሐሳብ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለማቅረብ ማቴዎስ የተባለው አንድ አርመናዊ መልእክተኛ ለንግሥት እሌኒ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ወደ ፖርቱጋል ለመላክ ተወሰነ፡፡ ዘመኑ 1510 ዓ.ም. ነበረ፡፡ የልብነ ድንግል ሞግዚትነት ዘመንም 2ኛ ዓመት ነበረ፡፡ ማቴዎስ በመጀመሪያ የሄደው ወደ ሕንድ ነበረ፡፡ ከዚያም በመርከብ ተሳፍሮ ከ3 ዓመት በኋላ በ1513 ዓ.ም.

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 43



ሊዝበን ገባ፡፡ ማቴዎስ መካና መዲናን አቃጥሎ ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት የሚል እቅድ ለፖርቱጋል ንጉሥ ሐሳብ አቅርቦ ነበረ፡፡ የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል በታላቅ ክብር ነበረ የተቀበለው፡፡ የሮማ ጳጳስም ሊዮን 10ኛ መልእክተኛው ማቴዎስን ተቀብለው አነጋግረውታል፡፡ 3 ቄሶችም ከፖርቱጋል መልእክተኞች ጋራ ተቀላቅለው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዙ፡፡ ልብነ ድንግል በ1516 ዓ.ም. ከሞግዚትነት ወጥቶ ስልጣን እንደያዘ የፖርቱጋል መልእክተኞች አፕሪል 7/1520 ዓ.ም. ምፅዋ ደረሱ፡፡ በመጀመሪያ የደብረ ቢዘን ቄሶች ምፅዋ ድረስ ሄደው ተገናኟቸው፡፡ ተጥሎም ባሕር ነጋሽ ያሬ ከአጼ ናኦድ እናት ሞጋሳ ወንድም ምፅዋ ሄደው ተቀበሏቸው፡፡ የክረምት ዝናም በመፍራት መልእክተኞቹ ደብረ ቢዛን ሄደው ተቀመጡ፡፡ እዚያው እንዳሉ ማቴዎስ ታሞ ሞተ፡፡ የሚተላለፍ በሽታ እንዳይሆን ፈርተው መልእክተኞቹ ወደ ድባሩዋ ሄዱ፡፡ ኦክቶበር 1520 ዓ.ም. ፖርቱጋሎቹ ደብረሊባኖስ ሸዋ ደርሰው ከንጉሡ ጋራ ተገናኙ፡፡ ፖርቱጋሎቹ ውድ ስጦታ ለንጉሡ አበረከቱ፣ ንጉሡ ግን በስጦታቸው አልተደሰቱም ነበር፡፡ ንጉሡ ይጓጓ የነበረው እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች የሚቀርብላቸው ዘመን ያፈራቸው የጦር መሣሪያዎች ነበሩ፡፡ የንጉሡ የቀዘቀዘ አቀባበል ፖርቱጋሎችን እያስቀየማቸው ነበር፡፡ ንጉሡ ከፖርቱጋሎች የሚፈልገው ሱዋኪም ምፅዋና ዘይላ በፖርቱጋል እንዲያዙ ብቻ ነበረ፡፡

በሌላ በኩልም ፖርቱጋል ኢትዮጵያን ወራ ትይዛለች የሚል ፍራቻ ነበረ፡፡ ንግሥት እሌኒ ከኤውሮጳውያን ጋራ መቀራረብ ትጥር የነበረችው ከአስተዳደሩ ተወግዳ በዕድሜም ገፍታ ስለነበረ ኃይሏም ተሰሚነት አጥታ ትኖር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ አፋጣኝ ቅርብ ግንኙነት ከፖርቱጋል ጋራ ለመፍጠር ከማንኛውም ከእስላሞች የሚደርስባት አደጋ የሚያድናት ውል ለማድረግ ዕድል አመለጣት፡፡ መልእክተኞቹ ቁምነገር ሳይሰሩ በኢትዮጵያ 6 ዓመት ተቀምጠው ኤፕሪል 28/1526 ዓ.ም. ከምፅዋ ወደ ሀገራቸው ተነሱ፡፡ ጆቫኒ ቤርሙደስ ሐኪም በኢትዮጵያ እንዲቀር ተደረገ፡፡ እስላሞች ከባድ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀሙበት ጊዜ ተቃርቦ እንደነበረ ማንም ሰው አልተረዳውም ነበረ፡፡

አጼ ልብነድንግል በእስላሞች ላይ ባገኛቸው መጠነኛ ድሎች ተዝናንቶ ከመጠን በላይ የራሱ ኃይል ስለገመተ የንግሥት እሌኒ የበሰለ የውጪ ፖለቲካ መመሪያ ችላ በማለቱ ኢትዮጵያ ወደ ጥፋት አፋፍ ደረሰች፡፡ በኢሚር ማፉዝ ጊዜ የሚመሩ አዳሎች በአጼ ልብነድንግል የደረሰባቸው ሽንፈት ለመቀበል በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊያደርስባት በዘይላ በኩል አደጋ ይሰነዝርባት ነበር፡፡ ከመካ ከሌሎች አዳሎችም የጅሀድ ጦርነት ቅስቀሳ ይደረግባቸው ነበረ፡፡ የጦር መሣሪያዎችና ተዋጊዎች ለእስላሞች ይላክላቸው ነበረ፤ አዳሎችም ወጣት ሴትና ወንድ ባሮች በማድረግ ወደ ገበያ ወስደው በመሸጥ የጦር መሣሪያ ይገዙ ነበር፡፡ ለማሕፉዝ ክብር አንድ የጦር አርማ ልከው ነበር፤ አዳሎች ወደ ፋጦጋር በማምራት ወረራ ፈጸሙ፡፡ አጼ ልብነድንግል በአጼ ናኦድ የጦርነት ዘዴ በመጠቀም ከበባ በማዘጋጀት አዳሎች ወደ ፊት እንዳይጠጉ ካደረጋቸው በኋላ ማምለጫ መንገድ በመዝጋት ፈጃቸው፡፡ ማሕፉዝ ማምለጫ ሲያጣ ከአንድ ገብረ እንድርያስ ከተባለው ቄስ ጋራ በጎራዴ ትግል ገጥሞ ቄሱ የማሕፉዙን አንገት ቆርጦ ለልብነ ድንግል አበረከተ፡፡ በዚሁ ጦርነት ብቻ 12,000 አዳሎች ሞተዋል ይባላል፡፡ ይህ የመጨረሻው የክርስቲያኖች ድል ነበረ፡፡ አጼ ልብነድንግል ዘመቻውን በመቀጠል የአዳል ሀገርን ወረው ወንድ ሴት ሳይለይ በመግደል ባሮችን አደረጋቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የእስላም ኃይሎች ዳግም ተመልሰው ለኢትዮጵያ

የሚያስጋት ጠላት አይሆኑም ተብሎ ተገምቶ ነበረ። ድሉም በመላው ኢትዮጵያ ተከብሯል። እንደተባለውም በሚቀጥሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የብልፅግና የሰላም ዘመናት ነበሩ። አሕመድ ሼል ኢብራሂም ግራኝ በዓረቦችና በቱርኮች እየተረዳ ኢትዮጵያን እስላማዊት ለማድረግ በነበረው ፍላጎት በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተደራጅቶ በከፈተው ጦርነት ሳይቋረጥ በየሚካውና በየተራራው ለ20 ዓመታት እየተደበቀ ለሃይማኖቱ በመዋደቅ ኢትዮጵያን ከሞት አፋፍ ያዳኗት አጼ ልብነ ድንግል ነው። በአንፃሩ በዘይላ አሚር ማሕፋዝ በፋጢጋር (ናዝሬትና ሞጆ አካባቢ) ያገኘው ከፍተኛ ድል ተዝናንቶ በቸልተኝነት ኢትዮጵያ ለሞት አፋፍ የዳረጋት አጼ ልብነድንግል ነው።

ግራኝ የሚመለምላቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ ከሶማሌ ሲሆኑ የሚመጡለትም ለዝርፊያ ብቻ ነበረ። ዘርፈው ሃብት ሲያገኙ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ነበረ ፍላጎታቸው። ግራኝ ጥለውት እንዳይመለሱ ብዙ ትግል ማድረግ ነበረበት። በአጼ ልብነድንግል ሽንፈት ከደረሰባቸው ጀምሮ የአዳል ኤሚሮችና ሱልጣኖች እርስ በእርሰ እየተጣሉ ከባድ ውድቀት ደርሶባቸው ነበር። ግራኝ ስልጣን እንዳይዝም ኃይለኛ ተቃውሞ አጋጥሞት ነበር። ግራኝ በቀላሉ ሊሰባሰብ የሚችል ጠንካራ የሰው ኃይል አልነበረውም። አጼ ልብነድንግል እንደ አምደጽዮንና ዘርአያዕቆብ ሳይቀደም ቀድሞ በማጥቃት የጦር ስልት በመጠቀም ጠላቶቹን ቢከታተል የሚወዳደረው ኃይል ሊፈጠር አይችልም ነበረ። ይኸንን ባለማድረጉ ግን ግራኝ እስኪጠንክር ድረስ ዝም በማለቱ በ1525 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች በዳዋሮ፣ (ጨርጨር) ሽንፈት ገጠማቸው። እንደገና በ1527 ዓ.ም. ክርስቲያኖች ስለተሸነፉ የቤተመንግሥት ልጆች የሚገኙባቸው 400 መቶ ልጆች ለባርነት ተወሰዱ። ግማሾቹ ለየመን አሚር ሱልጣን በባርነት ገፀበረከት ተሰጡ። ብዛት ያለው መሣሪያ ፈረሶች ድንኳኖች ተማረኩ። ግራኝ በፋጢጋር በኩል ወደ ተጉለት ድንገተኛ ወረራ አድርጐ ንጉሥን ለመያዝ አቅዶ ነበር። ወታደሮቹ ስለተቃወሙት እያለቀሰ ተመለሰ። ወታደሮቹን ለማሰልጠን ብዙ እንደሚቀረው ተረዳ። በ1528 ዓ.ም. ግራኝ ወደ ይፋት ዘመቻ አደረገ፣ ብዛት ያላቸው እሰረኞች ተማረኩ፣ ከነሱ ውስጥም የቤተመንግሥት ለዕልት ነበረች። እሷ ግን 1775 ግራም የሚመዝን ወርቅ ሰጥታ ተለቀቀች፣ በእንጸኪያ የነበረ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ፣ በውስጡ የነበሩ ብዛት ያላቸው ወርቅም ግራኝና ተከታዮቹ ተካፈሉት። በ1529 ዓ.ም. ሽንብራ ኩሬ በተባለው ቦታ ማርች 11 ቀን ለአንድ ቀን ሙሉ በንጉሡ የሚመራው የክርስቲያን ሠራዊትና በግራኝ የሚመራው የእስላም ሠራዊት መካከል ጦርነት ተካሄደ በቀኑ መጨረሻ የክርስቲያን ሠራዊት 12,000 ሰው ሞቱበት፣ ንጉሡ ሸሽቶ ወደ ኋላ ተመለሰ። የእስላም ሠራዊትም ብዙ ሰው ሞቶበታል። ከሞቱት ሹማምንቶች መካከል የትግራዩ ሩቤል፣ ወንድሙ ዑቅባ ሚካኤል በግራኝ እጅ የተገደለ፣ የሸሬ ሹም የጸለምቲ ሹምና የዐጋሜ ሹም ይገኙባቸው ነበረ። ከተማረኩም መካከል የንጉሡ ሚስት ወንድም ተክለመድህን ነበረ። እሱ ግን 50 አውንስ ወይንም 18 ኪሎግራም ወርቅ ከፍሎ ተለቀቀ። ግራኝ ብዙ ወርቅ ስለነበረ በዘረፈው ወርቅ 7 መድፎችን ከነ ተኳሾች ዓረቦች ከዘይላ ገዛ። ፈረሶችና ሌሎች ተዋጊ ዓረቦችም ነበሩት። ግራኝ ለክርስቲያኖች እንግዳ የሆኑ መሣሪያዎችን በመጠቀም በ1531ዓ.ም. ከክርስቲያኖች ጋራ ይፋት ውስጥ ጦርነት ገጠመ፣ ድልም ተጎናፀፈ። እንደገና ተሰርቶ የነበረ የእንጸኪያ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ። አጼ ልብነድንግል ተስፋ ሳይቆርጥ እስላሙ የተባለው የጦሩ አዛዥ ወደ ዳውሮ



እንዲሄድ አዘዘው። በባለታሪክ ተክለኢየሱስ የእንጎት (ወሉ) አገረ ገዥ የሚመራ ጦርም ለማጠናከሪያ ወደ ዳውሮ ተላከ። ነገር ግን ሁለት ከክርስቲያን የከዱ ባለስልጣኖች የንጉሡ እቅድ ለግራኝ ነገሩት፣ በዚሁ መሠረት ሁለቱ የክርስቲያን ሠራዊት ሳይቀላቀሉ ግራኝ ገጠማቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ እልቂት ደረሰባት፣ አብዛኛው ትግሬዎች የሆኑ 130 ሹሞች በጦር ሜዳ ተገደሉባት ከነሱ ውስጥም የሸሬ፣ የጸለምት፣ የሐማሴን፣ የቤጌምድር ሀገረ ገዢዎች ይገኙባቸዋል። ከጦርነቱ በኋላ ግራኝ ለንጉሡ እጁን እንዲሰጥ ላከበት፣ የንጉሡ መልስ ግን በእጁ ይገኙ የነበሩ እስላሞች የጦር እስረኞች በመግደል ነበረ፣ ጦርነቱም በጭካኔ ቀጠለ። የግራኝ ሠራዊት ሸዋን ወሮ ከዳር እስከዳር ተቆጣጠረ፣ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ አውራጃዎችና ከፍለአተ ሀገሮች ለግራኝ እጃቸውን ሰጡ፣ ሃይማኖታቸውንም ቀየሩ። ብዙ ሐብት ተዘረፈ ከነሱ ውስጥም አስደናቂ የነበረው ሽፋኑ በወርቅ የነበረ በአንድ በይፋት ቤተክርስቲያን የተገኘው መጸሐፍ ቅዱስ ነበረ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከብደቱ ሁለት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ለማንሳት የሚያቅታቸው ነበረ። ጦርነቱ ከሸዋ ወደ አማራ ተዛውሮ ቀጠለ ከደብረብርሃን ወደ ሰሜን በሚያመራበት ጊዜ ይማም አግረ መንገዱ አንድ ድንቅ ቤተክርስቲያን አጋጠመው፤ ቤተክርስቲያኑ በወርቅ ያጌጠ ነበረ። የማታ ብርሃን ጨረር ወደ ቤተክርስቲያኑ በሚገባበት ጊዜ ወርቁ እንደ መብራት ያንፀባርቅ ነበር። ቤተክርስቲያኑን ለመገንባት 25 ዓመት ነበር የፈጀው። ከወርቅ ሌላ የቤተክርስቲያኑ ግድግዳ በሌላ ውድ ጌጣጌጥ የተዋበ ነበረ። ይማም እሁንም አወደመው ቤተክርስቲያኖችን እንዲዘርፉና እንዲያቃጥሉ ለየእንዳንዱ የግራኝ ሹማምንት ድርሻቸው ተከፋፍሎ ተሰጣቸው። ለግራኝ መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ደረሰው። በቤተክርስቲያኑ የተገኘው የወርቅና የጌጣጌጥ ብዛት ከተጠበቀው በላይ ነበረ። ጣራው የውስጥ ግድግዳው ሁሉ በወርቅ የተሰሩ ነበሩ። አንድ ሺህ ወታደር ወርቁን ለመንቀል ለብዙ ሰዓቶች ተሰማርተው ነበረ፣ አስተርእዮ ማሪያም በተባለው ቤተክርስቲያን በታቦቱና በሌላ መንፈሳዊ ቁሳቁሶች የነበረ ወርቅ 1000 አውንስ ማለት 35 ኪሎግራም የሚመዝን ነበረ። በበእደማርያም የተሰራ የደብረ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን የአንድ ሰው ቁመት ያለው ቅስት አድናቆት ያተረፈ ተዘርፏል። ዋናው የንጉሡ ንብረት ፍለጋ ሌላ የግራኝ ጦር ወደ ወለጋ ተወስዶ የነበረውን ወርቅና ሌላ ጌጣጌጥ እንዲሁም አልባሳት ከተደበቀበት ተገኝቶ በ500 ግመሎች ተጭኖ ተወስዷል። የይማም ጦር ወደ እንጎት (ወሉ)፣ ለማምራት ሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ደረሰ። ከቤተክርስቲያኑ ወርቅ ለመዝረፍ 150 ሰዎች የመጫን አቅም ያላቸው ሶስት ትልቅ ጀልባዎች ወርቁን ለመውሰድ ሦስት ዙር ወሰደባቸው። በደብረ እግዚአብሔር በ1342 ዓ.ም ባሰይፈ ዐረድ የተሰራ ቤተክርስቲያን የተገኘው ወርቅ ከብደቱ አንድ ሚሊዮን አውንስ ነበረ ማለት 35.000 ኪሎግራም ነበረ።

ግራኝ ወደ ደቡብ ክፍለ ሀገር ሀዲያ፣ ከንባታ፣ ወላሞ፣ እሞ፣ ዝዋይ፣ አባያታ፣ ጊቤ፣ እናሪያ፣ ጋፋት ዘመቻውን በመቀጠል ዛላ በተባለው ቦታ በ1532 ዓ.ም. ባሸነፈ ጊዜ 3000 ክርስቲያኖች በጦር ሜዳ ሞቷል። የባሌ ሕዝብ በሙሉ የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበል ተገዶ የተቃወሙት ሁሉ ተገደሉ። ግራኝ ትግራይን ለመያዝ ያደረገው ጦርነት ከባድ ተቃውሞ ነበረ ያጋጠመው። በጦርነቱ 10,350 ሰዎች ተገድለዋል።

ግራኝ ሽሬ ሲደርስ በአባ ሳሙኤል ቤተክርስቲያን ያገኛቸው 500 ቀሳውስት ተገደሉ። አጼ ልብነድንግል በቤጌምድር ተራራዎች ተደብቆ

ስለነበረ ግራኝ ተከታትሎ በድንገት በእጁ ለማስገባት ያደረገው ሙከራ ከሽፎበት ንጉሡ ሸሽቶ ማምለጥ ችሏል፡፡ ግራኝ ወደ ኤርትራ በማምራት ሀገረ ገዢው ተሰፋ ልዑል አስወግዶ ቴዎድሮስ የሚባል ነበረ የሾመው፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ በተሰፋ ልዑል መሪነት የደፈጣ ውጊያ ለማድረግ የግራኝ ታማኝ የነበረ ቪዚር አዶሊ የሀገሩ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሹሞ የነበረ ሳይቀር ገድሎ አንገቱን ቆርጦ ወደ አጼ ልብነ ድንግል ለመላክ ከባድ ፍልሚያ አካሂዷል፡፡ ግራኝ በበጌምድር ንጉሥን ማሳደድ ትቶ አፍራ የተባለው ባሕር ነጋሽ ሾመ፡፡ ሠራዊ ግብር እንዲከፍል ተገደደ የሀገሩ አስተዳደርም በቴዎድሮስ ምትክ ወንድሙ ተሾመ፡፡ የሁሉም የበላይ አባዥ በቪዚር አዶሬ ምትክ ቪጺር አባስ ሾመ፡፡ የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት የአክሱም ሳይቀር ተቃጠሉ፡፡ ተላላፊ በሽታም በሀገሩ ገብቶ ብዙ ሰው ፈጀ ከሞቱትም መካከል የግራኝ ልጅ ከጦር ሜዳ የተወሰደ ነበረ፡፡ ግን ሰላም አስፍኖ ወደ ደምቢያ ሲመለስ ወዲያውኑ በሰራዬና በትግራይ የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ፡፡ ግራኝ ሰሜን እንዲይዝ ፈላሾች መንገድ ከፍተውለት ነበረ፡፡ የመጨረሻ ያልተያዘ ክፍለ ሀገር ወደ ጎጃም በማምራት ግራኝ ንግሥት እሌኒ ብዙ ንብረታቸው ያፈሰሱባቸው ቤተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ በነሱ ውስጥም መርጡ ለማሪያም የተባለ ስመ ጥሩ ነበረ፡፡ በዚሁ ዓይነት መላው ኢትዮጵያ በግራኝ ቁጥጥር ውላ ነበረ፡፡ የቀረው ንጉሡን አሳዶ ማያዝ ብቻ ነበር፡፡ ለልብነ ድንግል የተሰፋ ጭላንጭል የነበረው የፖርቱጋል መልእክተኞች ውጤት ነበረ፡፡ ነገር ግን አጼ ልብነድንግል ከዚህ በፊት ያደረጓቸው አቀባበል የቀዘቀዘ ስለነበር እርዳታ የማግኘት ተስፋ አነስተኛ ነበረ፡፡ አስቸኳይ እርዳታ ከክርስቲያን ኤውሮጳ ለማግኘት የነበረው አማራጭ አጼ ልብነድንግልና ቤተመንግሥቱ በሙሉ የካቶሊክ ሃይማኖት መቀበል ነበረ፡፡

ነገር ግን ይኸም አማራጭ እርምጃ የሕዝቡ ተቃውሞ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተፈራ ሌላ ዘዴ ተቀየሰ፡፡ ይኸውም በዕድሜ የገፋ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ማርቆስ ለአንድ ካቶሊካዊ የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተው ስልጣናቸውን እንዲያስረክቡ ነበር፡፡ ይህ ዘዴ ጥሩ መስሎ ቢታይም ሕጋዊነት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም አቡኑም ለአንድ ካቶሊክ ጵጵስና መስጠት መብት አልነበረውም፣ ለጵጵስና ተሿሚ ግለሰብም መቀበል አይችልም ስለነበረ ነው፡፡ ለጵጵስና ማዕረግ የተመረጠ ሰው በርሙደስ ነበረ፡፡ ቤርሙደስ እንደ ተሾመ ሁኔታውን ለማስረዳት ወደ ሮም መሄድ ነበረበት፡፡ በ1536 ዓ.ም ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ከእስላሞች ብዙ አደጋዎች አምልጦ በርሙደስ ለሮም ሊቃነጳጳሳት ከአጼ ልብነ ድንግል የተላከ መልእክት ይዞ ሮም ገባ፡፡ በደብዳቤው ላይ አጼ ልብነ ድንግል የካቶሊክ ሃይማኖት እንደሚከተልና ከሮማ የተላከ አቡን በስተቀር ሌላ አቡን እንደማይቀበል ገልጾ ነበር፡፡ በርሙደስ ወደ ፖርቱጋል ከአጼ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ የተላከ መልእክት አቀረበ፡፡ ሁለቱ መንግሥታት የሮማና የፖርቱጋል የራሳቸው የውስጥ ችግር ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ችላ ብለውት ነበር፡፡ ሆኖም በርሙደስ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ሕዝብ ሁኔታ በሚገባ በማስረዳቱ የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል 5ኛ ከሕንድ 450 የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲላኩ አዘዘ፡፡ በርሙደስ ትዕዛዙን ይዞ ወደ ሕንድና ወደ ኢትዮጵያ የመልስ ጉዞ ለመጀመር በሚዘጋጅበት ጊዜ ለ3 ዓመት እስከ 1539 ዓ.ም. ታዋ ሀገሩ ተቀመጠ፡፡ የፖርቱጋል ወታደሮች ምፅዋ ሲወርዱ የቻሉት በ1541 ዓ.ም. ነበረ፡፡ በኢትዮጵያም ጦርነቱ እየተካሄደ ነበረ፡፡ በ1539 ዓ.ም. ግራኝ ለልብነ ድንግል በላከው ደብዳቤ በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የአጼ ልብነድንግል ልጅ ለማግባት ንጉሡ እንዲፈቅድ ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ



እስላም አንድ ሆን የእግዚአብሐር ፈቃድ ስለሆነ አጼ ልብነ ድንግል በጦርነቱ ከገፋበት ሊያመልጠው እንደማይችል እና ቅጣቱ አስከፊ እንደሚሆን አስጠነቀቀው፡፡ አጼ ልብነ ድንግል ግን የሰላም ጥሪ ሳይቀበል ስለቀረ ጦርነቱ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ሳይያዝ ቀርቶ የነበረው የነገሥታት ዘር ማጎሪያ የተደበቀ ወርቅ ይገኛል ስለተባለ የእስላም ተዋጊዎች ሳይነቃባቸው ለመግረክ ስለቻሉ ከዘረፉት በኋላ አቃጠሉት፡፡ የተገኘው የወርቅ ብዛት የተነሳ "ወርቅ እንደ ድንጋይ ሆኖ ነበር ልብሶችም እንደ ቅጠል ሆነው ነበረ" በማለት የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበዋል፡፡

አጼ ልብነድንግል በ45 ዓመት ዕድሜው ሲሞት የደረሱ ልጆች ነበሩት፡፡ ቪክቶር የተባለው አልጋወራሽ ልጁ ወደ ዳዋር የሚያዋስነው ሄዶ የእስላም ሠራዊት ለሁለት ከፍሎ የመዋጋት ዓላማ ነበረው ሳይሳካለት ስለቀረ ግን በውጊያ ተገደለ፡፡ 2ኛ የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስ ከአባቱ ጋራ ሆኖ በዋግ አካባቢ ሲዋጋ በእስላሞች ስለተያዘ ባሪያ ሆኖ ለዘቢብ ፓሻ ተሸጠ፡፡ አጼ ልብነ ድንግል በደብረዳሞ አስተማማኝ መደበቂያ በመፈለግ ወደ ደብረ ዳሞ ሄደ፡፡ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ከግራኝ ወታደሮች አደጋ እንዳይደርስበት በማሰብ የገዳሙ መውጫና መግቢያ ዘብ በማቆም ይጠብቅ ነበር፡፡ ጥቂት ወራት ቆይቶ ሴፕቴምበር 5/1540 ዓ.ም. አጼ ልብነድንግል በቤተሰቦቹና በታማኞቹ ተከቦ በሰላም ዐረፈ፡፡

## 9. አጼ ገላውዲዎስ

አጼ ገላውዴዎስ ከአባቱ ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱን በጠንካራ መንፈስና በተሻለ ዕድል ቀጠለ፡፡ የአጼ ገላውዲዎስ እናት ንግሥት ሰብለ ወንጌል በሰሜን የሚኖሩ ሕዝቦችን በማነሳሳት ከአዲሱ ንጉሥ ጋራ እንዲቆሙ ያደረገችው ጥረት ስለተሳካላት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈላሾች ለኢትዮጵዊ አዲሱ ንጉሥ ለገላውዴዎስ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል ጸለምትም የእነሱ ምሳሌ ተከትለው ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ግራኝ ምርጥ አዛዦች በማሰማራት ሰሜን ለመያዝ ሊወጋቸው መጥቶ አልተሳካለትም፡፡ አጼ ገላውዴዎስ በሰሜን ተራራዎች ሆኖ ከጠላት ጋራ እየተፋለመ በነበረ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በደብረዳሞ ገዳም ሆና ታማኞችን እየሰበሰበች የጦር መሣሪያ ትሰጥ ነበረ፣ በዚሁ ጊዜ ፖርቱጋሎች ምፅዋ መድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ሕዝቡ በደስታ ፈነደቀ፡፡ ትግራይ ሁሉ ለንጉሡ ሙሉ ድጋፍ ሰጠ፡፡ ፖርቱጋሎች በቤርሙደዝ እየተመሩ ጉራዕ ገቡ፡፡ ከዚያም ድባርዋ ድረስ መጥተው ሰብለ ወንጌል ትጠብቃቸው ስለነበር ተገናኙ፡፡ በታኅሣሥ ወር ፖርቱጋሎች ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋራ በመሆን ምግብ እያቀረበችላቸው ከድባርዋ ተነሱ፡፡ አፕሪል 4/1542 ዓ.ም. በፖርቱጋሎችና በግራኝ የሚመራ የእስላም ሠራዊት አናሳ በተባለው ቦታ ብእክለጉዛይ ጦርነት ተካሄደ የፖርቱጋሎች መድፎች በእስላሞች ላይ ሽብር ፈጥረው ነበር፡፡

ግራኝ ታፋው ላይ ቆሰለ፣ ፈረሱ ተገደለ፡፡ ግራኝ እስከ ዘቡል ተራራዎች ሸሽቶ በመሄድ ጦሩን ለማደራጀት ሞከረ፡፡ ከዓረብ ሀገር ሁለት ሺህ ዓረቦች፣ቱርኮችና አልባናውያን ቅጥር ወታደሮች በዘይላ በኩል አስመጣ፡፡ የክርስቲያን ሠራዊት ግራኝን እያሳደደ እስከ አሻንጌ ሐይቅ ድረስ ገሠገሰ፡፡ ኦገስት በ1542 ዓ.ም. ግራኝ ከባድ ጥቃት አካሄደ የፖርቱጋሎች ጦር አዛዥ ዶን ክሪስቶፎር ዳ ጋማን አቁስለውትና በእስቃቂ ሁኔታ ገደሉት፡፡ የፖርቱጋል ጦርና ንግሥት ሰብለ ወንጌል አስቀድሞ ለክፉ ጊዜ ጦር ሰፈርና ማብያ አድርገውት የነበረ ወደ ሰሜን ሄዱ፡፡ ንጉሡም የእስላም ጦር ጥሶ

ከፖርቱጋሎች ጋራ ተቀላቀለ፡፡ ንጉሡ ለፖርቱጋሎች ወረታውን በመመለስ በማሰብ ለእየአንዳንዱ ፖርቱጋል ወታደር 1000 አውንስ ወርቅ ሰጣቸው (135 ኪሎግራም)፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ በእስላሞች ከተዘረፉ ሃብቷ ሌላ ብዙ የቀራት ወርቅ እንደነበረ ሲሆን ይኸውም ምን ያህል የበለፀገችና ሃብታም ሀገር እንደነበረች የሚያመለክት ነበር፡፡

የክርስቲያን ሠራዊት ከሰሜን ወደ ደቡብ ጎንደር እስላሞችን እያሳደደ ተጓዘ፡፡ ግራኝ ከነበረበት ከዘቡል ተራራዎች ዋና ከተማው ብሉ ወደ መረጣት ወደ ደንቢያ መጣ፡፡ ፖርቱጋሎች ዶን አልፎንሶ ከልደራ ያሰው አሪዮስ ዲያዝ መረጡ፡፡ አጼ ግላውዴዎስ ከፖርቱጋሎች ጋራ በመመካከር ግራኝ ወደ ደንብያ እንደመጣ እንዲገጥሙት ተወሰነ፡፡ ዲያዝ በመጀመሪያ መሥመር ፖርቱጋሎቹን አሰማራ፡፡ እስላሞች እያጠቁ ሲመጡ ግራኝ ወታደሮቹ ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ፊት ለፊት እየመራቸው ስለነበረ በፖርርቱጋል መድፎች የእሳት እራት ሆነው ቀሩ፡፡ አንድ ፖርቱጋላዊ የቀድሞ የፖርቱጋሎች አዛዥ ጆን ክሪስቶፎር ዳጋማ ጠባቂ የነበረው ፔድሮ ሲዮን የተባለው የጌታውን ገዳይ ለይቶ ስላወቀው በእሱ አነጣጥሮ በመተኮስ ግራኝን አቍስሎ ጣለው፡፡ ግራኝ ግን ወታደሮቹ ተስፋ እንዳይቆርጡ በማሰብ በአንድ ዛፍ ስር ስመደበቅ ሞክሮ ነበር፡፡ ያቆሰለው ወታደር ግን ግራኝ የሄደበትን በታ ተከታትሉ ስላወቀ ስሞት ሲያጣጥር ስላገኘው ሳስረጅነት አንድ ጆሮውን ቆርጦ ወሰደበት፤ቦታውን አሁን ድረስ የግራኝ በር ተብሉ ይጠራል፡፡ የእስላም ወታደሮች ተሸንፈው ተበታተኑ፡፡

ጦርነቱ በክርስቲያኖች ድል አድራጊነት ቢፈጸምም የሚቀጥለው ዙር በአጼ ግላውዴዎስና በበርሙደስ ያለው ጉዳይ መፍትሄ ማድረግ የሚኖርበት ነበረ፡፡ በርሙደስ በውሉ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡን መሆን አለብኝ ባይ ነበረ፡፡ አጼ ግላውዴዎስ ግን በቤተክህንነት ተጽእኖ በርሙደስ ወደ ጎን በመተው እንደ ቀድሞ ከእስክንድሪያ አቡን እንዲላክለት ጠየቀ፡፡ በዚሁ ጊዜ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከፍተኛ ጠብ ተፈጥሮ በርሙደስ የፖርቱጋል ወታደሮች ድጋፋቸውን እንዲሰጡት ፈልጎ ነበረ፡፡ ግማሾቹ የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ሕንድ ተመልሰው፣ ነበረ በኢትዮጵያ ቀርተው ከነበሩት መሐል ግን አብዛኛዎቹ ንጉሡን የሚደግፉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተለይ አዛዣቸው ዲያዝ በግልፅ ከንጉሡ ጋራ ከመቆሙም በላይ እንደገና በኦርቶዶክስ ክርስትና ተነስቶ ስሙ ማርቆስ ተብሏል፡፡ ሌሎችም የእሱን ምሳሌ ተከትሏል፡፡ በንጉሡ ሕይወት አደጋ እንዳይጥሉ በማለት በርመደስ ሌሎችም ፖርቱጋሎች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ ተደርጓል፡፡ በርሙደስ በመጀመሪያ ወደ ደቡብ ጋፋት ተልኮ ቀጥሉም ሌሎች ፖርቱጋሎች ወደ ነበረበት ወደ ዳውሮ ተወስዶ ከዚያም ወደ ድባርዋና ምፅዋ ሄደ፡፡ ከዚያም በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ አስታዋሽ አጥቶ ቀሪው ዕድሜው አሳ ልፏል፡፡ ሌላው ከጦርነቱ በኋላ የተደቀነው ችግር የንጉሡ ነገሥቱ የግዛት አንድነት ማስከበር ነበር፣ ይሄም የተከናወነው በ1544 ዓ.ም. ነበር፡፡ ቪዚር አባስ የአቡን ልጅ የኢማም ወንድም ዳዋሮ፣ የዛሬዋ ናዝሬት መተሀራ አካባቢ እንደዚሁም ባለ ከአርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ነፃ መንግሥት አቋቁሞ መሪ ሆኖ ነበረ፡፡ የኢትዮጵያን ሠራዊት ለመቋቋም የሚችል መስሎት ነበር፡፡ አጼ ግላውዴዎስ በዋዲ አውራጃ በኩል ወደ ፋጢጋር አልፎ ገጠመው፡፡ በአንድ ቀን ጦርነት በኦክቶበር 1544 ዓ.ም. እስላሞች ተሸነፉ፡፡ በ1545 ዓ.ም. መጀመሪያው ላይ አባስ ተገደለ አጼ ግላውዴዎስ ወደ ዳውሮ ገባ፣ ቤተመንግሥት ሠራ፣ የፈረሱ ቤተክርስቲያኖችም ታነፁ፡፡ ባሊም



እንደገና ተያዘ፣ ሆኖም ባሌ በዚሁ ጊዜ እሮሞ የሚያደርገው መስፋፋት ዋና መነሻ ጣብያ ሆና ስለነበረች ለብዙ ጊዜ ተይዞ አልቆየም፡፡ በ1547 ዓ.ም. ሐዲያ እንደ ቀድሞ ወደ ግዛቱ ተቀላቀለች፡፡ በ1548 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ዳሞት ከአባይ በስተደቡብ ዘምቶ ክርስትና ያልተቀበሉ ሕዝቦች ስለነበሩ ወስኑ እስከ ጊቤና አሞ ወንዞች ደረሰ፡፡ የሐረር መንግሥት በ1548 እና በ1550 ሁለት ጊዜ ከአጼ ግላውዲዎስ ጋር ጦርነት ገጥማ ሁለት ጊዜ ተሸነፈች፡፡ 1552 ግላውዴዎስ ከንባታን አስገብረዋል፤ ጉመር የሚባል አውራጃ በዛሬዋ ደጋማ ክፍል አርሲ አስገብሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ሰፋቱ ድሮ ወደ ነበረበት ተመልሶ ነበር፡፡ ሐረር እንደገና በ1552 ዓ.ም. ሽፍታ ጦርነት አውጃ ፋጢጋርን ወራ ወደ ሸዋ አምርታ ነበር፡፡ አጼ ግላውዴዎስ የደብረ ወርቅ ገዳም እያሰራ ይገኝ ስለነበረ፣ 12 ቀን ፈጣን ጉዞ አድርጎ ሐረር ሰቅሰት /አርብ ቀን/ ጦርነት ገጥሞ ተገደለ፡፡ የግራኝ ሚስት አጼ ግላውዴዎስ በመገደሉ የግራኝ መበቀል ሆኖ ስለተሰማት ደስ አላት፣ የግላውዴዎስ ጭንቅላት ተቆርጦ በሐረር ከተማ መግቢያ ደጃፍ ለሦስት ዓመት ተሰቅሎ ነበር፡፡

አጼ ግላውዴዎስ እንደሞተ ሦስት ቀን በኋላ ታማኞቹ አስከሬኑን ወደማሪያም ቤተክርስቲያን ወስደው ቀበሩት፡፡ የአጼ ግላውዴዎስ ጭንቅላት በሐረር ከተማ በር ደጃፍ ተሰቅሎ የነበረው፣ ክርስቲያን ነጋዴዎች ሰርቀው ወስደው በአንድ የይፋት ቤተክርስቲያን በክብር ቀበሩት፡፡ አጼ ግላውዴዎስ እንደ ሰማእት ሆኖ ይከብር ነበረ፡፡

## 10. የክርስቲያን መንግሥት አሸናፊነት

ከግራኝ ጦርነት በኋላ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን እንደ ምፅዋ፣ አሰብ ታጁራ፣ ዘይላ የመሳሰሉት የባሕር ጠረፍ ከተሞች መቆጣጠር ባለመቻሉ ደካማ ጐን እንዳለው መስሎ ቢታይም በባሕር የሚመጡበትን አደጋዎች ጠላቶችንም ለመቋቋም ችሎ ነበረ፡፡ የክርስቲያን መንግሥት የእስራኤል ዝርያ የሆኑ ሰለሞናዊ ነገሥታት እንደነበረ ሁሉ በምስራቅ ኢትዮጵያ የነበሩ የእስላም መንግሥታትም የነቢዩ መሐመድ ዘመድ የሆኑ በዓረቦችና በቱርኮች የሚደገፉ ወላዝማ በሚባሉ ሱልጣኖች የሚመሩ ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ በክርስቲያን መንግሥት ላይ የተነሳ ይፋት ነበረ፤ ይፋት ሲዳከም በአዳል ተተካ፡፡ አዳል የሚባለው መንግሥት በግራኝ እምባገነን አገዛዝ ቁጥጥር ስር ሆኖ የክርስቲያን መንግሥት ያልነበረው የጦር መሣሪያ ታጥቆ መላው ኢትዮጵያን የተቆጣጠረ ቢመስለውም የክርስቲያን መንግሥት ለ20 ዓመታት ወረራውን ለመቋቋም በመቻሉ፣ በመጨረሻ በጥቂት የፖርቱጋል ወታደሮች እርዳታ በአሸናፊነት ሊወጣ ችሏል፡፡ ከግራኝ መሸነፍ በኋላ ለማቆጥቆጥ የሞከረው የእስላም መንግሥት በሐረር ከተማ የተቋቋመው የግራኝ እና የወላዝማ ዝርያ የነበራቸው የግራኝ ሽንፈት ለመቀበል ፍላጐት ያልነበራቸው ሱልጣኖች ነበር፡፡ በረከት በተባለው የሐረር መንግሥት ሱልጣን ልጅና አሊ ጋራድ በተባለው የግራኝ ልጅ የሚመሩ የሐረር ወታደሮች ዳውሮን ወረሩ፣ ወረራው ግን የአውራጃው ክርስቲያን ሀገረ ገዥ የነበረው፣ በራሱ ሌላ እርዳታ ሳይጠይቅ ሊያከሽፈው ችሏል፣ መሪዎቹም ተይዘው ታሰሩ፡፡

የግራኝ ሚስት ከዓረቦች ጋራ በነበራት ትውውቅ በመጠቀም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ውይይት ተደርጎ የእስረኞች ልውውጥ እንዲደረግ ተስማምተው ሚናስ የአጼ ግላውዴዎስ ወንድም በጦር ሜዳ

በግራኝ ተይዞ ወደ የመን ባሪያ ሆኖ ተወስዶ ስለነበር በሱ ለውጥ በረከት እሊ ጋራድ ወደ ሐረር እንዲመለሱ ተደርጓል። ትንሽ ጊዜ እንደቆዩ የሐረር መሪነት ሌላ ሙከራ አድርገዋል። ወረራው ይመራ የነበረው የሞጃሂድ ሱልጡን ነበረ። ከግራኝ ሞት ብኋላ የሞጃሂድ ቤተሰቦች የቀድሞ የግራኝ ተዋጊዎች ልጅ መሰብሰቢያ ሆነው ነበረ። እንዲሁም የግራኝ ሚስት ባቲ ደል ዋምበራ ከሚደገፉ መካከል ዋና ተዋንያን ነበረች። የግራኝ ሚስት በአባቷ በኩል ኢትዮጵያን እየወረሩ ያስቸግሩ ከነበሩ አንዱ የነበረው የማሕፉዝ ልጅ ስትሆን የአሁኑ የኑር የሐረር መንግሥት መሪም በእናቱ የግራኝ እህት ልጅ ስለሆነ፣ ሙሉ እምነት ስለነበራት አጎቱን እንዲበቀል አስምላው ስለነበር ዋና ተልእኮዋና ዓላማዋ ሆኖ ነበር። አሁንም እስላሞች አልተናቸውም በታዋቂው የኢትዮጵያ ጦር መሪ ፋኑኤል የሚመራ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኑር ብቻ ሸሽቶ ሲያመልጥ የቀሩት የሐረር ወታደሮች ተደመሰሱ። አጼ ገላውዴዎስ ለፋኑኤል ሐረርን ወሮ እንዲይዝ ትዛዝ ሰጠው። ማርች 13 ቀን 1550 ዓ.ም. ሐረር በፋኑኤል ጦር እጅ ወደቀች ነዋሪዎቿም ሸሹ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፋኑኤል ሞተ፣ አጼ ገላውዴዎስ የተገኘው ድል ለማክበር 5 ወር ሐረር ተቀመጠ፣ ክርስቲያን ባሪያ ሆኖ ተወስዶ የነበሩ ተለቀቁ፣ በአንፃሩም ብዙ እስላሞች ተገደሉ፣ ባሪያ ሆነውም ተወሰዱ። ሐረር ምንም እንኳን ከባድ ሽንፈት ቢገጥማትም ለ3ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትን ለማጥቃት ሞክራ ነበር። በኢሚር ኑር ምትክ ክርስቲያን የነበረው ዑትማን የተባለው በሐረር ሥልጣን ይዞ ነበር። በዚሁ ዘመን ሁለቱ የሐረር እስላሞችና የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በአሮሞ የጋራ ጠላት ተከበው በችግር ላይ ወድቀው በነበሩ ጊዜ ሐረር ለሰ ተዳከመች በሥልጣን ላይ የነበረው የግራኝ ዘመድ ይማም መሐመድ የአሮሞች ወረራ ወደ ማያስጋው ወደ አውሳ በ1577 ዓ.ም. ሐረርን ለቆ ለመሄድ የተገደደ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአውሳ ሱልጣን ተመሰረተ፣ የይፋት፣ የአዳል፣ የሐረር መንግሥታት ህልውናቸው አከተመ።

## 11. የቱርክ ወረራዎች በኢትዮጵያ

ሌላ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የነበረው ምፅዋ የሰፈረው የቱርክ አገዛዝ ነው። ቱርክ ሱዋኪንና ምፅዋን የያዘው በ1517 ዓ.ም. ነበር። የቱርክ መንግሥት በወቅቱ በዓለም ቅድመ ኃያል መንግሥት ለመሆን በቅቶ የነበረ ነው።

ዓረቦች በምዕራብ አውሮፓ ገብተው አውሮፓን እስላማዊትና ዓረባዊት ለማድረግ እንደሞከሩ ሁሉ የቱርክ መንግሥትም በደቡብ ምሥራቅ አውሮፓ እስከ መሐል ገብቶ አውሮፓን በቁጥጥሩ ለማዋል ተቃርቦ የነበረ መንግሥት ነው። ቱርኮች ከዓረቦች የበለጠ ዓላማቸው ተሳክቶላቸው በአንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች ሃይማኖት እንዲቀበሉ አድርጓል እንደ ቦስኒያ፣ አልባንያ የመሳሰሉት። ቱርኮች መሃል አውሮፓ ገብተው የአንድ ትልቅ አውሮፓዊ መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው በስልጣኔና በጥበብ የተራቀቀችው ቪየና ለመያዝ በተቃረቡበት ጊዜ አውሮፓውያን በሙሉ ተባብረው እስካልተቋቋሟቸው ድረስ አስፈሪ ኃይል ነበሩ። በኢትዮጵያ ግን ቱርኮች አራት ጊዜ ወረራ አድርገው ተሸንፈው ወጥቷል። የመጀመሪያ ወረራቸው በምፅዋ በኩል በ1557 ዓ.ም. ነበረ። በዚሁ ጊዜ ቱርኮች ምፅዋን ተቆጣጥረው ወደ ደጋ ዘልቀው በመግባት በድባርዋ ምሽግ በመስራት ባሕር ነጋሽን በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር አውለው ነበር። የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ንግሥ የሆነው



ደብረ ዳሞት በቱርኮች ተይዞ ተዘረፈ፣ የባሕር ነጋሽ ቆላማ ሰሜናዊና ምዕራባዊ ጎሳዎች ቤጃ የተባሉ በፓሻ አክዝዳመር የሚመሩ እስላሞች ከቱርኮች ጋራ ተባብረው ነበረ። በባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በሚመራ የክርስቲያን ሠራዊት ሲደመሰሱ መሪያቸው ሸሽቶ ቱርኮች ወዳሉበት ወደ ዱባሩዋ ገብቶ ብዙ ሐብት ክርስቲያኖች የደበቁት አለ በማለት ቱርኮችን ስለ አጓጓቸው ፓሻ ዑዝዳመር 800 ፈረሰኞችና በዛት ያላቸው ወታደሮች አስከትሉ ወደ ቦታው ዘመተ። ብዙ ከተጓዘ በኋላ የተባለው የሐብት ክምችት አገኙ፤ በመሀሉ ግን የቱርክ ፓሻ ትኩሳት ታሞ በቃሬዛ ተሸክሞት ተመለሰ፤ የዘመቱ ሰዎችና እንስሳት አብዛኛዎቹ ሞቱ፣ ከኢትዮጵያ ጦር በመሐሉ በድባሩዋ ጥቃት ፈፅሞ በመከበብ ቱርኮችን ያለምግብና ውሀ አስቀርቷቸው ነበረ። ቱርኮች ያገኙትን ሐብት ሊሊት ከድባሩዋ ለመውጣት ሲሞክሩ መሣሪያ በታጠቁ ገበሬዎች ተደመሰሱ፣ ሐብቱንም ማረኩት፣ ድባርዋም ተማረከች። የቱርክ ወታደሮች ከድባርዋ አምልጠው ወደ ምጽዋ ለመሸሽ ሲሞክሩ በታጠቁ ገበሬዎች ተገደሉ፣ የቱርክ ፓሻ ባዶ እጁ ስለቀረ ሸሽቶ ሱዋኪን ገባ። የቱርክ ወረራ ተወግዶ ይዞታው በምፅዋ ተወስኖ ቀረ። ሁለተኛ የቱርክ ወረራ በአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት፣ ነበረ በአንደኛ የቱርክ ወረራ በጀግንነት ተዋግቶ የአባረራቸው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ሥልጣኔ ተሻሙኝ በማለት በንጉሡ ላይ ተቀየመ። አጼ ሚናስ መጀመሪያ ዮሐንስ በተባለው ጦር ላከበት፣ ነገር ግን ይስሐቅ በድንገት አደጋ ጥሉበት አሸነፈው፣ ይስሐቅ ከቱርኮች እርዳታ ለማግኘት ከድባርዋ እስከ ምፅዋ ያለውን መሬት ሰጣቸው። አጼ ሚናስ ፖርቱጋሎች ከይስሀቅ ጋራ ተስማምተው ይሆናል ብሉ ስለጠረጠራቸው በአንድ ተራራ እንዲቀመጡ አደረጋቸው። አቡነ እርሺየዶና ተከታዮቹ አምልጠው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ወደ አለበት ደርሰው ድጋፋቸውን ሰጡት። በዚህ መሠረት ቱርኮች ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ካቶሊኮችና ሌሎችም የሚናስ ተቃዋሚዎች ግንባር ፈጠሩ። ፖርቱጋሎች ከሕንድ የጦር መርከቦች እንደሚያስመጡ ለይስሐቅ ተስፋ ሰጡት፤ አጼ ሚናስ ግን ጊዜ አልሰጣቸውም አፕሪል 20 1562 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት አሸናፊ ሆነ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አጼ ሚናስ ከዶባ ጎሳዎች ጋራ ጦርነት ባደረገበት ወቅት በትኩሳት ታሞ ሞተ። ጦሩም ጉዳት ደርሶበት ስለነበረ ቱርኮችን እስከ ባሕር ሳያባርራቸው ተመለሰ።

ሦስተኛ የቱርክ ወረራ በኢትዮጵያ በአጼ መላክ ሰገድ ዘመነ መንግሥት ነበረ። ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ እንደገና 1578 ዓ.ም. ከቱርኮች ጋር ተስማምቶ ለንጉሠ ነገሥቱ አልታዘዝም በማለት የንጉሡ መልእክተኞች ተልከውበት ከቱርኮች ጋራ እንዳይገጥም ቢጠየቅ "ከፓሻው ጋራ እርቅ አድርጌአለሁ፣ በአንድ ምንጣፍ አንድ ላይ በመቀመጥ" የሚል መልስ ስለሰጠው መላክ ሰገድ ጦሩን ወደ ባሕር ነጋሽ አዘመተ የንጉሡ መምጣት ዜና ሲሰማ ተዋጊዎች ከባሕር ነጋሽ መከዳት ጀመሩ። በሠራዬ ዐረ ባሕር ነጋሽ ዐመፅ ተካሄደ፣ ይስሐቅና ቱርኮች እንጢጮ ተሰበሰቡ፣ በመጀመሪያ ግጥሚያ ኖቬምበር 13, 1578 ዓ.ም. ቱርኮች የመላክ ሰገድ ሠራዊት እንዲሸሽ አደረጉ። አራት ቀን በኋላ ቱርኮች 8 መድፎች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ተኩሱ፣ በማነፃፀር ብዙ ጉዳት አደረሱ። በዚሁ ጊዜ መላክ ሰገድ የአሮሞ ፈረሰኞች አስግርቶ በቱርኮች ላይ አጠቃ፤ ብዙ ሳይቆይ መድፎቹ ተያዙ፣ የጠላት ይዞታዎችም ተያዙ። ከዚህ በኋላ ይስሐቅ ተስፋ ስለቆረጠ እርቅ ጠየቀ። ንጉሡም ከቱርኮቹ ተዋጊዎቹ ለይቶ አውጥቶ ከክርስትያኖች ጋራ ቱርኮችን እንዲወጉ አድርግ የሚል መልስ ሰጠው። ይስሐቅ ከቱርኮች ጋራ እርቅ እንዲደረግ የሚል ሐሳብ አቀረበ። የቅርብ ረዳቶች ሳይቀሩ ከዱት።

በተደረገው ሁለተኛ ግጥሚያ ቱርኮችና ዮስሐቅ ሽንፈት ገጠማቸው የኢትዮጵያ ጦር የቱርክ ጦር ሰፈር ተቆጣጥሮ የቱርኮች እርማና መድፎችን ማረከ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደልማዱ ከአካባቢ ዝርፊያ ስንቅ ፍለጋ መሔዱ ሲያውቁ ቱርኮችና ዮስሐቅ ከምሽጋቸው ወጥተው መድፋቸውን በንጉሡ ጦር እያተኮሩ መተኮስ ጀመሩ፤ ንጉሡ ግን ጥቃታቸውን አክሽፎ መለሳቸው፡፡ ዮስሐቅም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ሆኖ ወደ ፊት እየመራ በማጥቃት ሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ለዮቶ ሰላወቀው አድፍጦ ትከሻውን አቆሰለው፡፡ ዮስሐቅ ብዙ ደም እየፈሰሰው ወደ መጣበት ተመልሶ ከፈርሱ ወርዶ በመሬት ተጋደመ፡፡ ስንቅ ፍለጋ ሔደው የነበረ የኢትዮጵያ ወታሮች ሲመለሱ የቱርክ ሠራዊትን ከበው ፈጁት፡፡ ዮስሐቅ ሞተ የቱርክ ፓሻ የጠፉን አልቀት ፈረሱ ላይ ወጥቶ ይመለከት ነበረ፡፡ ጀግናው አንድ የኢትዮጵያ ወታደር ዮናኤል የተባለው ደረቱን በመውጋት ሰላቆሰለው ከፈረሱ ወደቀ፡፡ ያቆሰለው ወታደርም ወደ ወደቀበት ሄዶ አንገቱን ቆርጦ ለንጉሡ አበረከተው፡፡ ቱርኮች የነበራቸው ሐብትና ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ የዮስሐቅ ረዳቶችም ተማረኩ፡፡ ንጉሡ ከተማረኩት ዋና ዋናዎቹን መርጦ እንዲገደሉ አዘዘ፡፡

4ኛውና የመጨረሻው ኢትዮጵያ ከቱርክ አቶማን ጋራ ያደረገችው ጦር ፍልሚያ በአጼ መላክ ሰገድ ዘመነ መንግሥት በ1589 ዓ.ም. ነበረ፡፡ ወልደ እዙም የተባለው በአለቃው በትግራይ መኰንን ዳህራቦት ላይ ዐመጸ ተነስቶ ብዙ ባለሥልጣኖችን ገድሎ ቱርኮች ባለፉው ዘመናት ሊቆጣጠሯቸው ሞክረው የነበረ የባሕር ምድር ግዛቶች ለመያዝ በነበራቸው ምኞት ጥቃት ባካሄዱበት ወቅት በመጀረያ ሊዋጋቸው ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ግን የቀድሞ የባሕር ነጋሽ ምሳሌ በመከተል ለቱርክ ፓሻ እጁን በጥቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ከቱርኮች ተቀብሎ ከንጉሡ የተላከው ጦር ለመቋቋም ችሎ ነበረ፡፡ በአዲሱ ባሕር ነጋሽ ረዳትነት ቱርኮች ድባርዋን ለመያዝ ችለው ነበር፡፡

ዳህራጎት ሊያስወጣቸው ሞክሮ ከባድ ሽንፈት ደርሶበታል፤ ቱርኮች መረብን ተሻግረው ትግራይ ገብተው ነበር፡፡ ሕዝቡ ግን ተዋግቶ መልሷቸዋል፡፡ በሚመለሱበት ጊዜ ዐቅባ ሚካኤል የሚባለው መረብ አጠገብ ባደረገባቸው ደፈጣ ስለተከበቡ ከተያዙት 7 ቱርኮች ተሰሰቡ፤ ሁለት የበላይ ሹሞች ተገደሉ፤ ንጉሡ ዐቅባ ሚካኤል በፈጸመው ጀግንነት ተደስቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ሰጠው፡፡ ዜናው በመላው ኢትዮጵያ እንደምሳሌ ተተረተ፡፡ ፓሻው የንጉሡ መምጣት ሳይጠብቅ ወደ ምፅዋ ሄደ፤ ንጉሡ ግን ቱርኮችን ለዘለዓለም ከኢትዮጵያ መሬት መንቅሎ ለማውጣት ምፅዋ ድረስ ሄደ፡፡ ቱርኮች በምሽጋቸው እና ከባሕር ከመርከባቸው ሆነው ተከላከሉ፡፡ ብዙ ቱርኮች ታስሩ ሁሉም አግሮቻቸውና እጆቻቸውን ተቆረጡ፡፡ ፓሻው ራሱ ቆስሎ ነበረ፤ ሰውነቱ ብረት ለብሶ ስለነበረ ግን ከሞት ተረፈ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ስንቅ ስላለቀበት ወደ ደጋ መመለስ ግድ ሆነበት፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከበባው እንዳቆመ ወዲያውኑ ቱርኮች የእርቅ ውይይት ጀመሩ፡፡ ንጉሡ ከጂውን ወልደ እዙምን ማሳደድ ጀመረ፡፡ ዐቅባ ሚካኤል ተከታትሎ ይዞ ገደለው፡፡ ንጉሡ ድባርዋ እንደተመለሰ እጅግ በጣም ብዙ ስጦታዎች ከፓሻው የተላኩ አገኘ፡፡ አጼ መላክ ሰገድ ስጦታዎችን ተቀበለ እርቅና ሰላምም ወረደ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ግንኛውም የቱርኮች መስፋፋት ምኞት ለሁሉ ጊዜ አከተመ፡፡ ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፎች የሚመጡባት ሁሉ የታላቁ የቱርክ መንግሥት ወረራዎች እንዲሁም በሃይማኖት መነሻ በምሥራቅ ሱልጣኖች የግራኝም ጭምር የእርስ በእርስ ጦርነቶች ከብዙ ዘመናት ፈተና በኋላ በአሸናፊነት ተወጥታለች፡፡



## 11. የኦሮሞዎች መስፋፋት ክስተት

ኢትዮጵያ ልታሸንፈው ያልቻለችው ሌላ ጠላት ነበራት፤ ይኸውም የኦሮሞ የመስፋፋት ክስተት ነው፡፡ የኦሮሞ ከደቡብ ወደ መሐል ሀገር መስፋፋት ምክንያት ኢትዮጵያ ከባድ ውድቀት ደርሶባታል፡፡ የደቡብ ምዕራብና የምሥራቅ ክፍላተ ሀገሮቿ እንድታጣ ተገደደች፡፡ በነዚህ ክፍላተ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ ማንነታቸው በውል የማይታወቁ በአጠቃላይ ሲዳማ ወይንም አማራ ብለን የምንጠራቸው ሕዝቦች ከምድረ ገፅ ጠፍቷል፤ ባይጠፉም ቋንቋቸው፤ ባሕላቸው፤ ታሪካቸውና ስማቸው ጠፍቶ በኦሮሞ ተተክቷል፡፡ አሁን ኦሮሞ ሕዝብ ተብለው ሰፍሮባቸው የሚገኙ መሬቶች ኦሮሞ ከመምጣታቸው በፊት ባዶ መሬት አልነበሩም፤ አማራ፤ ጉራጌ፤ ሌሎችም አሁን የደቡብ ሕዝቦች ብለን የምንጠራቸው ወይንም ሌሎች የጠፉት ሰፍረውባቸው ነበረ፡፡፡ ኦሮሞ ከመጡ በኋላ ግን በሙሉ ተገደሉ ለማለትም አይቻልም፡፡ ከኦሮሞ ጋራ ተቀላቅለው ዘራቸው ጠፋ ለማለት ይቀላል፡፡ ኦሮሞዎች እንደ ይፋት ወይንም እንደ አዳል መንግሥት አልነበራቸውም፤ ወረራ ፈጽመዋል ለማለትም አይቻልም፡፡ ኦሮሞዎች ያካሄዱት የመሬት ማስፋፋት ነው፤ ሰፈራ ነው፡፡ ኦሮሞዎች መንግሥት ስላልነበራቸው አንድ መሪ አልነበራቸውም፡፡ በይፋት፤ በአዳልና በቱርኮች ያልተሸፈነ የኢትዮጵያ መንግሥት በኦሮሞች ግን ተሸንፏል፡፡ ኦሮሞች እንደሌሎች ሕዝቦች ለምሳሌ ሶማሌ በጐሳ ተከፋፍለው እርስ በእርሳቸው የሚጣሉ አይደሉም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በሥልጣን ሽኩቻ ወይንም በሐይማኖት ምክንያት ከግራኝ ከሐረር እስላማዊ መንግሥት ያደረጋቸው እርስ በእርስ ጦርነቶቹ በመዳከሙ ኦሮሞዎች ተጠቅመውበት ወደ ባሰ ውድቀት እንዲደርስ አድርገውታል፡፡ ኦሮሞች አዲስ መሬት ለመያዝ እንደ ማዕበል ወደ ፊት ከመገስገስ በቀር የታወቀ ዓላማ አልነበራቸውም፡፡ መንግሥት ለማቋቋምም ዓላማ አልነበራቸውም፤ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ስልጣን ለማጋራት ወይንም የነበረውን መንግሥት ገልብጠው ስልጣን ለመያዝ ዓላማ አልነበራቸውም፡፡ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጥላቻ እንዳልነበራቸው የሚያስረዳ አንዳንድ ነገሥታት ለውትድርና እየመለመሉ ይጠቀሙባቸው እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ያጋጥም እንደነበረ ተዘግቧል፡፡

ኤውሮጳውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳና በቋንቋ ሲከፋፍሉት ኦሮሞችን ደቡባውያን የኩሽ ዘሮች ይመድቧቸዋል፡፡ የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዮችም የዚሁ ዓይነት አከፋፈል ነው የሚከተሉት፡፡ ይህ አሰራር ቋንቋና ጎሳን ለይቶ ለማወቅ ባለመቻሉ የአንድ ሰው ወይም ሕዝብ ማንነት ቋንቋው ብቸኛ መለክያ በመውሰድ የሚደረገው የዘር አመዳደብ ዘዴ ነው፡፡ በቋንቋው ብቻ የአንድ ሕዝብ ማንነት መመደብ ግን ትክክለኛው ሊሆን አይችልም፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ሴማዊ የተባለው የግእዝ ቋንቋ ከመስፋፋቱ በፊት ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየፈለሰ ስለሚሄድ ቋንቋውን ትቶ አዲስ የሰፈረበት ቦታ ቋንቋና ባሕል እንደሚይዝ የታወቀ ነው፡፡ ኦሮሞችም ከዚህ ሕግ አይወጡም፡፡ ቅድመ ታሪክ ኦሮሞዎች የሰፈሩበት ቦታ በሰሜን በደቡብ ወይንም በመሐል በምሥራቅ ኢትዮጵያ ይሁን አይታወቅም፡፡ አቶ ተከለ ፃዲቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 30 የሌሎች ጸሐፊዎች ታሪክ በመጥቀስ ከኑቢያ እስከ ኢርትራ ባሕር ተበታትኖ የነበረ ሕዝባችን የስም ዝርዝር ሲሰጥ በቁጥር 18 ጋሊ የተባለውን ጋላ ብለው ተርጉሞታል፡፡ መሠረት የሌለው አተረጓጐም

ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ሆኖ ያገለገል የነበረው ግብፃዊው የክርስትና ሐይማኖት ተከታይ ስሙ ቡትሮስ ጋሊ ሲሆን ይኸውም ስማቸው ወደ ዓረብኛ ያልተቀየሩ የጥንት ግብፃውያን ስም ሲሆን ይችላል፡፡ ኢጣሊያዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ስለጥንታውያን ግብፅ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሰጡት አስተያየት በመጽሐፉ እንደተገለጸው ኢልሚ ኦርማ (የኦርማ ልጆች) ወይንም የኦሮሞ ልጆች ማለት መሆኑን የሚል ትርጉም ተሰጥቷል ይሄም ትርጉም የተሰጠው ቱቲ ሞሲስና ሌሎችም የግብፅ ፈርኦኖች በሐውልቶቻቸው ስለአስገበሯቸው የኩሽ ዘሮች ስም ዝርዝር ተቀርጾ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ኮንቲ ሮሲኒ አስተማማኝ ታሪክነቱ በግሉ ቢክደውም ባለሞያዎች የሰጡት አስተያየት በደፈናው ሐሰት ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ኦሮሞዎች ከ1520 ዓ.ም. በፊት ወደ መሐል ኢትዮጵያ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ደቡብ ኢትዮጵያ በረና አካባቢና ከኒያ ብቻ ሰፍረው እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው፡፡ ኦሮሞች ሰፍረውበት የነበረ ዋናው ማእከል ዋባቡ ከአብያተ ሀይቅ በስተምሥራቅ የሚገኘው ተራራ ነው ተብሏል፡፡ በዚህ አንድ አውራጃ የማያህል መሬት ሰፍረው ተውስነው ለብዙ ዓመታት ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎች በጥቂት ዓመታት ውስጥ መላው ኢትዮጵያን ማጥለቅለቃቸው በየትም የዓለም ክፍሎች ያልታየ ታአምራዊ ክስተት ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ቋንቋውን ባሕሉን እና ስልጣኔውን ከሰሜንና ቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ሞንባሳ በሚያስፋፋበት ጊዜ፤ አንድ መቶ መንግሥታት ወይንም 35 መንግሥታት ወዘተ... በስሩ አሉት ይባል የነበረው፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአንድ አውራጃ ሕዝብ ብዛት እንኳን ያልነበራቸው ኦሮሞዎች ከስር መሠረቱ ሲያንኮታኩቱት የቻሉት በጦር መሣሪያ ተጠቅመው አይደለም፡፡ ጋዳ ወይም ጉዲፈቻ ቡተባለው የአስተዳደር ስልታቸው ተጠቅመው ነው፡፡ ኦሮሞዎች ለብዙ ዘመናት ከባንቱ ጎሳዎች በጉርብትና በኖሩበት ጊዜ ጋዳ የተባለው የዕድሜ ክልል መሠረት የሚያደርግ የአስተዳደር ዘዴ ከእነሱ በመውሰድ አስፋፍተውታል፡፡ በዚህ ፀባያቸው ከሌሎች የካም ዘሮች ይለያሉ፡፡ ሌሎች የካም ዘሮች ሁሉ እርስ በእርሳቸው የሚለያዩ በስጋ ዝምድና ሲሆን ኦሮሞዎች ግን እንደ ኮከብ ቆጠራ የአንድ ዕድሜ ክልል የሆኑ ሰዎች በአንድ ወገን ይመደባሉ፡፡ ጋዳ ብዙ ደረጃ አለው 1. ዳባሌ 2. ፎሌ 3. ቆንዳላ 4. ዶሬ 5. ሉባ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ የጋዳ ደጋፊዎች ዲሞክራሲ አስተዳደር ነው ይሉታል፡፡ ነገር ግን አጅግ ኋላ ቀር የሆነ አስተደደር ዘዴ ነው፡፡ ኦሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ከመሰራጨታቸው በፊት የሐማኖት መሪዎቻቸውና ጠንቋዮቻቸው አባ ሙዳ ይባሉ ነበር፡፡ ሁለት አባ ሙዳዎች ነበሩ፡፡ አንዱ በዳሎ ሜካ በገናሌ ወንዝ አጠገብ ሁለተኛው በዋባቡ ተራራ፡፡ በኋላ ጊዜ ኦሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ዘልቀው ገብተው የባሌን መንግሥት በተቆጣጠሩበት ጊዜ የአባ ሙዳ መኖሪያ የአቡል ቃሲን ተራራ ሜፍ ታዋቂው ሼክ ይኖርበትና ያረፈበት ሆነ፡፡ የሁለቱ እምነቶች ተዋሕደው የኦሮሞዎች ሁሉ ቅዱስ ቦታ ማእከል ለመሆን በቅተዋል፡፡ ኦሮሞዎች ለዘመናት በሰላም በደስታ ይኖሩበት ከነበሩ ሰፈራቸው ለቀው ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንዲሰራጩ ምክንያት የሆኗቸው ሶማሌዎች ናቸው ተብሏል፡፡ በግራኝ ጦርነት ጊዜ ኦሮሞች አይታወቁም ስለነበረ ግራኝ ለውትድርና ሊመለምላቸው አላሰበም፡፡ ግራኝ ለተዋጊነት የተጠቀመባቸው ሶማሌዎች ብቻ ነበሩ፡፡ መጠን ሰፊ የሆነ የቀንድ ከብቶች፣ ወርቅ የጦር መሣሪያና ባሮች



ከክርስቲያን ኢትዮጵያ ሶማሌዎች በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዘርፈው ያመጧቸው በማየታቸው ኦሮሞዎች በሶማሌዎች ከመሬታቸው ስለተፈናቀሉ ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንደ ባሕር ማእከል ተሰራጩ፡፡ ኦሮሞዎች ከመምጣታቸው በፊት ምዕራብ ወለጋ እንፌሉ ተብሎ ይጠራ ነበረ፡፡ ወሎም የቀድሞ ስሙ አንጎት ነበረ ወዘተ... ጋፋት፣ ትልቁ ዳሞት፣ ዳዋሮ፣ ፋጢጋር፣ ግራ፣ አዳል፣ ወዘተ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ክፍለተ ሀገሮች ወይንም መንግሥታት ታሪካቸውና ስማቸው ቋንቋቸውና ባሕላቸው ጠፍቷል፣ በኦሮሞ ቋንቋና ባሕል ተተክቷል ወይንም ዘራቸው በሙሉ ጠፍቷል፡፡

ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን አውሬዎች እንኳን ዘራቸው እንዳይጠፋ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ በዛሬ አንድ መቶ ዓመት ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ የቀድሞ አባቶቻችን የገነቧት የኢትዮጵያ ግዛት አንድነት ባስከበረበት ጊዜ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ የተቀላቀሉት ክፍለ ሀገሮች ቋንቋቸው እና ባሕላቸው እንኳን ባይቻል የቀድሞ ስማቸው እንዲያገኙ ማድረግ ይገባው ነበር፡፡ አጼ ምኒልክ ይኸንን ባለማድረጉ የኦሮሞ ቋንቋና ባሕል እንዳይነካ በማድረጉ የዛሬ አንዳንድ ኦሮሞዎች አጼ ምኒልክን በወረራ እንደያዛቸው ሲወቅሱ ይታያሉ፡፡ አጼ ሚኒልክ ያዘመተው የአማራ የኦሮሞ የትግሬ ወዘተ.. ያሉበት የኢትዮጵያ ሠራዊትም ነፍጠኛ እየተባለ ስም ማጥፋትና ታሪካዊ ቅዱስ ዓላማውና ተልኮው የተወጣበት አድናቆትና ምስጋና ሊገባው የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚያናፍሱትን ወሬ በማስተጋባት ይገኛሉ፡፡ ዛሬ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው ክፍላተ ሀገሮች ምሥራቅ ደቡብና ምዕራብ ሸዋ፣ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቦር እና ጅማ ባዶ መሬት አልነበሩም፡፡ ቅድመ ኦሮሞ የነበሩ ሕዝቦች በግዴታ የኦሮሞ ቋንቋ በጉዲፈቻ በመውሰድ ኦሮሞ ተባሉ እንጂ በዘር ኦሮሞ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ኦሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ ዘር አይደለም፡፡ በዘር ከሆነ ኦሮሞ የአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎሳዎች በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡ ስለዚህ ኦሮሞ ተናጋሪ የሆኑት የሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ስለሆኑ በኢትዮጵያ ጎሳዎች ላይ ጥላቻና ቅራኔ ሊኖራቸው አይገባም፡፡ ኦሮሞ ሳይታሰብ ቋንቋውን በመላ ኢትዮጵያ አማርኛ ያልቻለው በተአምር ሊያስፋፋ ችሏል፡፡ ይህ በመሆኑ ኦሮሞዎች ሊደሰቱ ይገባቸዋል እንጂ በግንባር ቀደም በቋንቋችን እንዳንጠቀም ያለፉት መንግሥታት ጨቁኑኝ ለማለት አይችሉም፡፡ በኦሮሞ ፋንታ አማርኛ ከዳር እስከዳር ባለመስፋፋቱ ቁጭት ሊኖራቸው የሚገባ አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያድርበት ይገባል፡፡ በኦሮሞ መሬታቸውን ተነጥቀው ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ያጡ ሕዝቦችም በዕድላቸው ሊያዝኑ ይችላሉ፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ግን ከማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ መብቱ የተጠበቀለት ስለሆነ አሁን ሲነገር እንደምንሰማው መብቴ አልተከበረም ብሉ ቅሬታ ማሰማት ባለፈው ታሪካችን አንፃር ተቀባይነት የለውም፡፡ በማንኛውም ጦርነት እንደሚያጋጥም የምኒልክ ሠራዊትም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጭፍጨፋ ተፈጽሞ ይሆናል፣ ኦሮሞዎች ከፈጸሙት ጭፍጨፋ ግን የሚነጻጸር አይደለም፡፡ ብዙ የሰው እልቂት የተፈጸመ ወቅት ቢኖርም በምኒልክ ዘመቻ ጊዜ ከሁሉ የባሰ በኦሮሞዎች አካባቢ የተደረጉ ጦርነቶች አልነበረም፡፡ ከሁሉ የባሰ ጭፍጨፋ የተፈጸመው ኦሮሞዎች እንደ ጅማ አባጅፋር የተካፈሉበት በከፋ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዘመቻ ጊዜ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ቃላቶች ያለአግባብ እንጠቀማለን፡፡

ስለኦሮሞዎችና በሌሎች ሕዝቦች ያለውና የነበረው ግንኙነቶች ወራሪና ተወራሪ ገዢና ተገዥ ብለን ለመጠቀም ብንፈልግ ግን የኦሮሞ ሕዝብ ወራሪ ነው እንጂ በሀገሩ ላይ አልተወረረም፡፡ ለም መሬት ነጥቆ ከሌሎች በመያዙ

ገዥ ነው እንጂ ተገዢ አይደለም። የአማርኛ ቋንቋ እንኳን የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ ያላደረገው ኦሮሞዎች ሌሎች ሕዝቦች ቋንቋቸው ባሕላቸውና ስማቸው እንዲቀየሩ አድርገዋል። አማራ ማለት እንደ ኦሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ የጎሳ ስም አይደለም። አማርኛ እንደ ኦሮምኛ ብዙ ጎሳዎች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። አብዛኛው ዛሬ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ዘራቸው አገው ነው፣ አገው ባይሆኑም ከትግራይ የመጡ ናቸው።

ኦሮምኛ ቋንቋ እየተናገሩ ኦሮሞ እንዳልሆኑ ከሚያምኑ ሕዝቦች የወርጂ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ወርጂ ከትግራይ እንደሚወስዱ ያምናሉ።[1] በንጉሥ ዐምደ ፅዮን ዘመን ከአፋር ኗሪዎች እስላሞች ከሌሎች እስላሞችም ጋራ ሆነው ፀረ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ግንባር የፈጠሩ ተብለው ተጠቅሰዋል።[2] ዘራቸው ከአፋር ወይንም ከሶማሊ አይደሉም፤ ትራጌዎች ከትግራይ መጣን እንደሚሉ፣ እንደዚሁም በሲዳማ የነበሩ የነገሥታት ዘራቸው ከትግራይ መሆኑን እንደሚያምኑ፣ በተመሣሣይ ወርጂ ከትግራይ መምጣታቸው ይናገራሉ፤ በአዋሽ ከኦሮሞች ሚታ በቾ ይዋሰናሉ።

ኦሮሞች በታሪካቸው በሶማሊዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ እንዲፈልሱ ተደርገዋል፤ በባንቱ ከደቡብ ወደ ሰሜን እንዲፈልሱ ተገዷል፤ ቀጥሎም ከ100 ዓመት ባነሰ ጊዜ ከሲዳማ (ደቡብ ሕዝቦች) እና ከአማራ ባደረጉዋቸው ጦርነቶች አሁን የሚኖሩባቸው ለፋፌ መሬቶች ለማግኘት በቅቷል። በመረሻም ጠብመንጃ ታጥቀው ሊዋጉዋቸው ከመጡ አዲሶች የአማራ ወራሪዎች ጋራ ፍጭቢ ይዘው እንኳን ስመክላከለ ሳይሞክሩ ነፃነታቸው ገልጸታል[3]። ኦሮሞ ድል የተመቱበት የማሩ ኩረቻ (Sella Maru) በተባለው ቦታ በራስ ጉበና የሚመራው በኢትዮጵያ ሠራዊት ነው። ራስ ጉበና ጨቢ ስመገሰገስ መንገድ የከፈተበት ወሳኝ ድል የተጐናጸፈበት ቦታ ነው።

## 1. <u>ጋዳ አስተዳደር</u>

የኦሮሞና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ብዙ አይታወቅም። ስለ ኦሮሞ ተጽፎ የሚገኘው ስለ ጋዳ የዕድሜ አስተዳደር ነው። ቸሩሊ እንዳጸፈው ከባንቱ የተወረሰው የጋዳ አስተደደር መሠረት በድሮ ጊዜ አንድ ጉሣ በሁለት ዘር የተከፈ 10 የጋዳ ደረጃዎች ነበሩት። አባትና ልጅ በተቃራኒ ጋዳ ሲመደቡ፣ የልጅ ልጅ ከአያቱ ጋራ ይመደባል። እንደዚህ እያለ በየ8 ዓመት እየተቀያየረ 1ኛ ደባለ ከ1 እስከ 8 ዓመት ዕድሜ 2ኛ ፎሌ ከ8 እስከ 16 3ኛ. ቆንዳላ ከ17 እስከ 24 4ኛ ዶራ ከ25 እስከ 28 5ኛ ሉባ ከ29 እስከ 32 6ኛ. ዩባ ከ33 እስከ 40 ተብለው የሚጠሩ ይከፈላሉ። የፖለቲካ ሥልጣን የሚገኘው በግል ችሎታ ሳይሆን በዕድሜ ነው። ልዩ ሥነ ሥርዓት እየተደረገ 8 ዓመት እንደተቈጠረ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ይዛወራሉ። ይህ ጥንታዊ የጋዳ አስተዳደር ሳይቀየር የቀጠለው በክርስቲያን ኦሮሞች ብቻ ነው፣ እስልምና የተቀበሉ ግን ጋዳ አስተዳደር ከእምነታቸው ጋራ አልተጣጣመም። በሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ

(1) Cerulli : Etiopia occidentale p. 14
(2) Cerulli : ibd p. 14
(3) Cerulli ibd p. 19



ጕሣዎች ጥንት 10 ጋዳ የነበሩ ለአምስት ስለተጠቃለሉ አባት ልጅና የልጅ ልጅ ወዘተ ባንድ ይመደባሉ 1ኛ ጂደ 2ኛ አቢቹ 3ኛ. ጕምቢቹ 4ኛ. ሚታ 5ኛ ጉለሌ 6ኛ. አቦራ የሚባሉ በምዕራብና ደቡብ ሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ ጕሣዎች በመሃላቸው ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖራቸውም የጋዳ ስምና ደረጃ ተመሣሣይ ነው። የጋዳ ስሞች 1ኛ. ሆራታ 2ኛ. ሚቺሌ 3ኛ. ዱሎ 4ኛ. ሮባሌ 5ኛ. ቢርማጂ ተብለው ይጠራሉ። የጋዳ ደረጃዎች 1ኛ. ደባለ 2ኛ. ፎሌ 3ኛ. ቀንዳላ 4ኛ. ዶራ 5ኛ. ሉባ 6ኛ ዮባ ናቸው። በጂዳ ጕሣዎች ዶረና ሉባ ለ4 ዓመት ብቻ ስለሚቈዩ የአንድ ደረጃ ንኡስ ክፍል ናቸው። በአቢቹ ጕሣ ዶራ ቀርቷል፣ 8 ዓመት ሲጨርሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚተላለፉበት የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ቡታ ይባላል። ዩባ ደረጃ ካላቸው አንዱ ተመርጦ አባ ዳባለ እየተባለ ጋዳ የሚጀምሩ ልጆችን ይዞ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያቀርባቸዋል። ከሥነ ሥርዓቱ በኋላ ዩባ የሆኑ ሁሉ ይገረዛሉ። ፎሌ ደረጃ ያሉት ሁሉ ጅንጀሮ ቆዳ ፊታቸውን ሸፍነው ፎሮርሳ የተባለው ዱላ ይዘው ይዘዋወራሉ። ከመሃከላቸው በፎሮርሳ ዱላ ደብድቦ ከራሣቸው ጕሳ ውስጥ አንድ ፍየል ወይንም አንድ በግ መዝረፍ የቻለ "ሐዩ" ተብሎ አለቃቸው ይሾማል። የተዘረዘፈው በግ ወይንም ፍየል ወዲያውኑ ተሰብስበው ይበሉታል። ዶራ ወደ ሉባ ደረጃ ሲሸጋገሩ የሚደረገው ቡታ በሬ አርደው ሥነ ሥርዓት አለቃቸው ሐዩን ይመርጡና፣ ከሱም ጠጉሩ ተላጭቶ፣ ውትት ፈሰበት፣ በሉባ ደባለ እጅ ፊቱ በበሬ ቆዳ ግንባርና ቀንድ ይሸፈናል፣ እንደ በሬም ይጮሃል። ይህ ሸፋን ሒርቡ ይባላል። ጕሣቸውን ለመምራት የፖለቲካ ሥልጣን የሚሰጣቸው ዶራ ወይንም ሉባ ደረጃ ያላቸው ናቸው። 5ቱ ደረጃዎች የጕሣ አባላት ለጋብቻ ዘር ለመቍጠር ይጠቀሙበታል። ከ5 ትውልድ በላይ ካልተቈጠረ ጋብቻ አይፈቀድም።

ኦሮሞች አጼ ምኒልክ ከግዛቱ ጋራ ከማዋሐዱ በፊት የ365 ቀናት የዓመት መቍጠሪያ ነበራቸው። ዓመቱ የሚጀምረው በመስቀል ስለሆነ የጥንት ከኢትዮጵያ አንድነታቸው የሚያሳይ ምልክት ነው። ⁄ 1.ሙዳ መስከረም 2 ሐደለቻ ነሐሴ ዳዋ ጥቅምት 4 ጥር ጥሪ፣ ኅዳር⁄ 5 ፋርማ (Furma) የካቲት 6 ሺያን ሰኔ 7 ቦሩ ሺያን ሐምሌ።
በሶማሊም የዓመት መጀመሪያ ቀን እሳት በማንደድ ይከበራል።[1]

ኦሮሞች በዙቋላ የሚገኘውን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ገዳም አቦ (አቡነ) በማለት ያከብሩታል። አቦ የሚል አጠራር በሁሉም የተለመደ ነው። እንደዚሁም በፊንፊኔ ጠበል ለአቦ ክብር እየተባለ በየዓመቱ በውሃው ውስጥ የፍየል ወተት ማፍሰስ፣ የወፎች ጠጉር ማበርከት ልምድ ነበረ። በተራሮችና በምንጮች እምነት ማዘውተር ከጣኦት እምነት የመጣ ነው ቢባልም፣ ክርስቲያንም በጣኦት እምነት የተተካ ስለሆነ የቀደምት አባቶቻችን የኢትዮጵያ የጋራ የክርስቲያን እምነት ምልክት መሆን አለበት[2]።

## 2. <u>ኦሮሞና ሲዳማ</u>

በኦሮሞች ወረራ ዘራቸውና ቋንቋቸው የጠፉ የሲዳማ ሕዝቦች የመጨረሻዎቹ ከአፄ ምኒልክ ዘመን በፊት በጅማ አካባቢ ብዙ ኦሮምኛ ያልሆኑ ቃላቶች ይቀላቀላሉ። ንጉሥ ለማለት በኦሮምኛ ሞቲ ሲሆን በልማድ ግን ጉይታ ተብሎ ይጠራል፣ ጉይታም ወደ ጎፍታ ተቀይረዋል 2 እልጋ

(1) Cerulli ibd p 58
(2) Cerulli ibd p 59

ወራሽ ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ዶናቾ ተብሎ ይጠራል፡፡ 3 የንጉሡ ሚስት ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ጌን ተብላ ትጠራለች፡፡ በጅማ አካባቢ የነበሩ ነገሥታት አንዳንድ ጕሣዎች በጅምላ እንደ ባሪያ የመቍጠር ባሕል ነበራቸው፡፡ ጅማ አባ ጅፋር ይህ ባሕል ተቀብሎ አጋንኖ በሥራ ላይ ያዋለው በጃንጀሮ ሕዝብ ላይ ነው፡፡ ጅማ አባ ጅፋር አፄ ምኒልክ ምዕራብ ኢትዮጵያን በምይዝበት ጊዜ ከጠሩ ጋራ በመተባበሩ ውለታ ለመክፈል ጃንጀሮ ከግዛቱ ጋራ እንዲያጠቃልለው ተሰጥቶት ነበር፡፡ በዚሁ መብት በመጠቀም ጅማ አባ ጅፋር የጃንጀሮ ሕዝብ የእሱ ባሪያ ሕዝብ መሆኑን አውጆ ግማሹ በክልሉ እየኖረ የሚሸጥ የሚለወጥ ሲያደርገው ግማሹ በባርነት መልክ ወደ ምዕራብ ጅማ እንዲዛወር ተገዷል፡፡ ይህ ሁኔታ አይቶ ሀገሪ ፐርጡ የነበረው ራስ ተሰማ የጃንጀር ሕዝብ አስተዳደር ከአባ ጅፋር ነጥቆ በአንድ አሚራ እንዲስተዳደር ሥር ለማድረግ ግድ ሆነበት፡፡ 5 ጅማ አባ ጅፋር ወሮ ይዞ ከግዛቱ የቀለቀላቸው የሲዳማ መንግሥታት የመጨረሻ ቦሻ ነው፡፡ ስሙ ቀይሮ ግን ጋና ተብሎ ተሰይሞ የጅማ ክፍለ ሀገር አካል ሆነዋል፡፡ ቦሻ ከከፋ ተመሣሣይ ጕሣ ሲዳማ ናቸው፣ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል፣ ቋንቋቸውና እሮምኛ፡፡ በጅማ ከተገዙ ጀምሮ ሁሉም የእስልምና ሃይማኖት ተቀብሏል የቆድሞ የቦሻ ነገሥታት ወራሾች ከፌል እሰረኛ በመሆን ጅሬን ከተማ (ጅማ ከተማ) አጠገብ እንዲቀመጡ ተገዷል፡፡ ሰግቸው አባ ቡሺያን ቡሳሲዬ ይባላሉ፡፡ የቦሻ ነገሥታት ዘር ሐረግ ለከፋ፣ ለምጫና ለእንፌሎ ነገሥታት የሚሆኑ ሰዎች የሰጡ ናቸው፡፡

6 የጅማ ወሰን መግቢያ በሲዳማ አጠራር ከሳ ይባላል፣ ነፃ መንግሥታት በነበሩ ጊዜም ገለልተኛ በወሰናቸው የሚገኘው መሬት "ሞጎ" የተባለ ነበረ፡፡

7 ጅማ ሴሎችም ድሮ የእሮሞ ነፃ መንግሥታት የነበሩ የሚስተደደሩ ከሲዳማ የተወሰደ በዘውድ አገዛዝ ስለሆነ የጋዳ አስተደደር አሰራር ጨርሶ ባይቀርም ንጉሡ የማይሾማቸው ባለሥልጣናት በሕዝብ ብቻ የሚመረጡ ሲኖሩ ስለማይችሉ የጋዳ አሰራር ከአዲሱ ሥርዓት መጣጣም ግድ ሆኖበት ነበር፡፡ የጋዳ ደረጃዎች በሁለት ብቻ ተቀንሱ ራባና ሉባ የሚባሉ፡፡ ጋዳ የሚደረጁም በጕሣ መሆኑ ቀርቶ በመንደር ነበር፡፡

8 የጅማ እሮሞች እስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ በቅርብ ጊዜ ነው፣ ባለፈው መቶ ዘመን አጋማሽ ነው፣ ሲቀበሉ የቻሉም ንጉሣቸው በወርሺና በዳሪታ የጉንደር እስላሞች ነጋዴዎች ተሰብከ በመጀመሪያ እስልምና ሲቀበል፣ ዜጎቹም በእስላሞች የታረደ ሥጋ እንዲበሉ ስላስገደዷቸው ነው፡፡ ማንኛው ሰው ያረደው ሥጋ መብላት የዝቅተኛ ዘሮች ምልክት ይቈጠር ስለነበረ ግዲታ እስላሞች መሆን ነበረባቸው፡፡ እስካሁን ድረስ የጅማ እስላሞች መሰያ የሆነው እንደ ክርስቲያኖች ጠላና ጠጅ መጠጣታቸውና ሜት አለማዘውተራቸው ነው፡፡

9 ጅማ በእሮሞች ከመያዙ በፊት ከከፋ ሕዝብ ተመሣሣይ ዘር የሆኑ የሲዳማ ሕዝቦች በንጉሥ አገዛዝ የሚስተዳደሩ ይኖሩበት ነበር[1]፡፡ እሮሞች ከቀድሞ ነዋሪዎች ከሲዳማ ተምረው የጋዳ አስተዳደር አሰቀርተው የዘውድ አገዛዝ ተቀበሉ፡፡ አንዳንድ የእሮሞ የጕሣ መሪ የሀገር መሪ (ንጉሥ) ከአነሱ ጕሣ ብቻ እንዲሆን ከመቻላቸውም በላይ፤ ከሕዝብ የሚመረጥም ቢጋዳ ሳይሆን በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ አደረጉ፡፡ የዚህም ምሳሌ የታየው በሊየካ ቀለም ሞቲ ተብሎ የሚጠራ ነበር፤ በሕዝብ የሚመረጠው ግን ሊየካ ዋዩ ይባል ነበር (Lieca wayou)

(1) Cerulli ibd p 91



10 ኬላ በከፋ ቋንቋ የቤት በር ሲሆን እሮሞች ግን፣ የነበሩ መንግሥታት ወሰን ለማመልከት ብቻ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

11 በእሮሞች ለሴቶች ሥልጣን መስጠት ልምድ አልነበረም፣ ከሲዳማ ተምረው ግን ሴቶች ሥልጣን ተሰጧቸው "ጌኔ" ጌታ ንግሥት ተባሉ፡፡ መሰፍን፣ አልጋ ወራሽም ከሲዳማ ተወስዶ ነወቲ፤ ዳና "ወደ ደንዞ" "ዶንዲዮ" "ዶናጂዮ" እየተለወጠ በከፋ በ ሚጫ በእንፌሎ መሰፍን ለማት የሚጠቀሙበት ነበር፡፡

12 በሰው ስም ብቻ ሳይሆን ከሲዳማ የተ(ወ)ረሉ በሀገርና በቦታ ስሞችም እሮሞች ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ የቦሶ ተራራ (ጅማ የሚገኘው) በሸ ከሚባለው የከፋ ጕሣና በሺያ ከሚባለው የሲዳማ መንግሥት የተወሰደ ነው፡፡ ግና የሚባል ሰፈር በጅማና በከፋ አሉ፡፡ በጅማ ሳራዶ ተራራና ሳደር ወረዳ ሲኖር በከፋ ሺራይ ወረዳ አለ፡፡ ጌሼ ወረዳ በጅማ ሲኖር በከፋ ጌሸ አለ፡፡ በደቡባዊ ጅማ ሰግጸ ተብሎ የሚጠራ ወረዳ በከፋ ሺየግዶ የሚባል አለ፡፡ የሲሙ ዋና ከተማ ኮሳ ሲሆን በከፋም ኮሺዮ የሚጠራ አለ፡፡ የሊሙ ሳጋ ከተማ ሲኖር በከፋ ሺያጋ አለ፡፡ የእግዚእትነ ማርየም መቅደስ በሊሙ ጉዶ ማርያም ተብሎ የሚጠሩ ተራራ ሲኖር ጉዶ ግለት በከፋ ተራራ ግለት ነው፡፡ የጕማ መንግሥት የነበረው ስም በከፋ የአንድ ወንዝ ስም ነው፡፡ በጕማ የአጋሮ መንደር ሲኖር በከፋም አጋሮ የሚባል መንደር አለ፡፡ በጅማ የሚገኘው ያቦ ወንዝ ከከፋ ያቦ ዘባባ የተወሰደ ነው፡፡ የጌራ ወና ከተማ የነበራቸው ቾራ በከፋ ሰሙ ጥሩ ሺፒናዎ የኖረበት የተወሰደ ቦታ አለ፡፡ አንደራቻ የሰው ስም በጌራ ዋና ከተማ አጠገብ የሚገኘው ቦታ የከፋና ሜጫ ዋና ከተማ ስም ነው፡፡ በጅማ የኪየቺዮ ጠበል ሲኖር፣ በከፋም ኪየሺዮ ፉል ውሃ ጠበል ይገኛል፡፡ ያንጋቺያ የሚባለው የጌራ ከከፋ ኢንጋጂያ የመጣ ነው፡፡ የጠበቀ ጥናት ቢደረግ ብዙ ሌሎች ስሞች ሲገኙ ይችላሉ[1]፡፡

ቸሩሊ ከኢትዮጵያውያን አዋቂዮች አገኘሁ ብሎ እንደዘገበው የዛሬዪቱ ጅማ ክልል ሰሜን ምሥራቅ የጃንጀሮ መሐልና ደቡብ ክፍል የቦሻ አነስተኛ ክፍልም የእናሪያ ነበረ፡፡ የዛሬዪቱ ቦሻ ግደላግደል በመሆኑ ከሰሜንና ከምዕራብ የመጡባቸው ጠላቶች በመከላከል ሸሽተው የሰፈሩበት ይመስላል፡፡ ተዋቂው በነበረ የእናሪያ መንግሥት ዛሬ በእሮሞች ወረራ ከምድረ ገጽ የጠፋ ይናገረው የነበረ ቋንቋ ይበልጥ ተመሣሣይነት የነበረው ከከፋ ሣይሆን ከሞቻ ቋንቋ ነበረ፡፡ እሮሞች ወደ ጅማ የመጡበት አቅጣጫ በሚመለከትም ሁሉም በአፈ ታሪክ የሚያረጋግጡት የጅማ እሮሞች ከመጫ እሮሞች አንድ ክፍል (አንድ ጕሣ) መሆናቸውና ከወለጋ ወለል ከሚባለው ቦታ መመጣታቸውን ይናገራሉ፡፡ 6ቱ የጅማ ጕሣዎች ከወለል ተነስተው ወደ ምሥራቅ አምርተው ግማሾቹ በደቡብ የነበረው የሲዳማ ሀገር በመያዝ የዛሬዪቱ ጅማ መሠረቱ፡፡ እሮሞች ወደ ጅማ የገቡ በስተሰሜን ከጃንጀር የነበረው ጠባብ መተላለፊያ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አሁንም ከዳደሴና ድኖ የመጫ ጕሣዎች ኩታ ገጠም ይገኛሉ፣ ከዚህም ወደ ምዕራብ የወለጋ ሊየካ ይገኛሉ፡፡ ከ6ቱ የጅማ ጕሣዎች ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ወረራ ያልተካፈሉ እስካሁን ከአባይ እስከ ግቤ ወንዝ ሰፍረው የሚገኙ ጅማ ገቦ 2 ጅማ ሆሮ 3 ጅማ ራሬ 4 ከዋማ ወንዝ የሚደሳ ገባር አካባቢ ጅማ አርጆ ሲሆኑ ሁሉም ከጅማ አባ ጅፋር ዝምድና እንዳላቸው የሚያስታውሱ ናቸው፡፡ እሮሞች ወደ ጅማ የመጡበት ዓመተ ምሀረት በትክክል ባይታወቅም 1567 እና 1568 አፄ መላክ ሰገድ ወደ እናሪያና ቦሻ የመጣበት ጊዜ የንጉሡ ታሪክ

(1) Cerulli ibd p 101 - 2

ፀሐፊ በእነዚህ መንግሥታት ኦሮሞች መገኘታቸው አልመዘገበም፣ ዳሩ ግን በ1703 ዓ.ም. ትልቁ አፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ወደ እናሪያ ሲዘምት ሀገሩ በሚጨ ኦሮሞች ተከቦ ስላገኘው በጦር ኃይል ጦርነት በማካሄድ ብቻ መንገዱን በመክፈት ወደ እናሪያ የሲዳማ መንግሥት ሲደርስ ችሏል።

ከ1419 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሠው የአፄ ይስሐቅ ታሪክ ፀሐፊ በሻ ለኢትዮጵያ መንግሥት ግብር በወርቅ ከሚከፍሉ ግዛቶች አንዱ እንደነበረ፣ የእናሪያ አዋሳኝ እንደነበረ ስለተዘገበ የድሮ በሻ የዛሬ ጅማ በኦሮሞች ሲያዝ ስሙ ጅማ ካካ ነበረ። ካካ በኦሮሞ ቋንቋ ዘረፋ ማለት ስለሆነ ሀገሩ በዘራፊዎች እንደተያዘ ያሳያል። ቀጥሎም የአባ ጅፋር ጉሳ ባዲ ስለሚባል ሀገሩ ጅማ ባዲ ተብሎ ይጠራ ነበር። በ1840 በዳባዲ ዘመን (Abbadie) ጅማ በዚሁ ስም ትጠራ ነበር። በመጨረሻም በንጉሣዊ ስም ጅማ አባ ጅፋር ተብላ ተጠራች።

ጅማን ለማስገበር የጉጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒልክ ለውድድር ቀርበው በ1883 በእምባቦ ጆኑዋሪ ጦርነት ገጥመው ጉጃም በመሸነፉ ጅማ ወደ ሀገሩ የሚገቡ ነጋዴዎች ምኒልክን በጦር ኃይል መቋቋም እንደማይችል በሰጡት ምክር መሠረት ተሸቀዳድሞ ከንጉሥ ምኒልክ በመስማማት ከሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ተለይቶ ለንጉሥ ምኒልክ መገበር ጀመረ።' በዚህም ምክንያት የውስጥ አስተዳደር ነፃነት (ራስ ገዝ) አግኝቶ በኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይያዝ ለመኖር በቅቷል። ሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ግን በሰላም መገበር ባለመፍቀዳቸው በጦር ኃይል ብቻ በምኒልክ ጦር ሊያዙ ችሏል። የጅማ ዋና ከተማ በድሮ ጊዜ ጂረን ተብላ ትጠራ ነበር። አሁን ግን ዋና ከተማዋም ክፍለ ሀገሩም ስሙ ጅማ ተብለው ይጠራሉ። የጅማ አካባቢ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ከተዋሐደ ጀምሮ ዝነኛው የእናሪያ መንግሥት የቀድሞ ስሙ ማግኘት ነበረበት፣ ይህ ባለመደረጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ደካማነት ያሳያል። የሊሙ ጉሣ እንደ ጅማ ከቲሳ ወለል ወለጋ የመጡ ናቸው። በቀድሞ ጊዜ የእናሪያ መንግሥት (በከፋ ቋንቋ ኢኖአሪ ቶቶ) ከጉጀብ ወንዝ ዳሪቻ ግራና ቀኝ የሚገኙ መሬቶች ያጠቃልል ነበር። ከእናሪያ ነገሥታት ትልቁ ዝነኛው ሺፒናዎ ነበረ። ዋና ከተማው ቸሪኮ አጠገብ ነበረ። በኋላ ግን በኦሮሞች ስለተሸነፈ ወደ ከፋ ክፍል ጉጀብ ተሰዶ ሄዶ ጨባ በተባለው ቦታ ጋዋተ ራሺዮ የከፋ ክፍለ ሀገር መቀመጫው አድርጎ ይኖር ነበር። በከፋ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያ እስከተያዘበት ድረስ የእናሪያ ንጉሥ የክብር መጠሪያ ብቻ ሆኖ ቀይቶ ነበረ። የእናሪያ ነገሥታት ወርቅ፣ በስደት የነበሩ የእናሪያ ነገሥታት ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ ያስተላልፍ ነበር። የሺፒናዎ ዋና ከተማ ቸሪኮ የምትገኘው ጌራ ውስጥ ቺያዳ በተባለው ተራራ ስር ዋራ በተባለው ቦታ የአምልኮት ቅዱስ ቦታ የነበረው አጠገብ ነበረች። ስለዚህ የእናሪያ መንግሥት ግዛት በሊሙ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፣ በትክክል ባይታወቅም ሰፊ ግዛት ያጠቃልል እንደነበረ ይገመታል። ሺፒናዎ ክርስቲያን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም የሄደው ከሀገሩ የመጀመሪያ ሰው ነው። ከኢየሩሳሌም ሲመለሱ ታቦት ይዞ መጥቷል። ስለ ሺፒናዎ በአፈታሪክ የሚወራ ብዙ ነው። ሺፒናዎ በእናሪያ ቤተክርስቲያን ሰርቷል፣ ከዚህ በኋላ አንድ ትልቅ ዘመቻ ወደ ከፋ አድርገዋል። ሺፒናዎ በመንገድ ሲጓዝ ሌሎች ሰዎች የሚጠቀሙበት አይሄድም። ከሠራዊቱ ጋራ ሲሄድ በአቋራጭ መንገድ ይጓዝ ነበር። በጉዞው መሰናከል አያጋጥመውም፣ በወንዞች ሲያልፍ ከመቅጽበት ትልቅ ድልድዮች ሠርቶ ያልፋል። በሰው እግር ለማለፍ የሚዳግቱ ተራራዎች ሲያጋጥሙት በጉራዴው በመስበር ያልፍ ነበር። ዛሬ እንደራቻ አጠገብ በረታ ወንዝ



በጉርጉቶ በሺፒናዎ የተሰራ ቸሩ በተባለው ቦታ ላይ በኩታ ክፍለ ሀገር አንድ ድንጋያማ ተራራ የእናሪያ ንጉሥ በጉራዴ የሰበረው ተመልካች ሁሉ የሚያደንቃቸው ይታያሉ። ሺፒናዎ ወደ ከፋ በምዕራብ በኩል ገብቶ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አነፀ፣ ከኢየሩሳሌም ያመጣው ታቦትም አረገበት። ከዚህም ወደ ጠቋቁሮች ሀገር ወደ ሻሻ ደርሶ ከዚያ ወዴት እንደሄደ ሳይታወቅ ጠፋ። ይህ እንደ ተረት የሚነገርለት የእናሪያ ንጉሥ ኮንቲ ሮሲኒ በአፄ መላክ ሰገድ ክርስትና የተነሳ የእናሪያ ንጉሥ ሰፐንሒ መሆኑን ትርጉም ሰጥቷታል። በበሐ ቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት መመሥረቱ እውነት መሆኑን የተረጋገጠ ነው። በታቦቱ ያለው ጽሑፍ በጌራ ወረዳ ይኖር የነበረ ካቶሊክ ቄስ ሚሲዮናዊ አባ ለዮን ቀድቶ ስለወሰደው፣ አንድ ኢጣሊያዊ ምሁር ተርጉሞታል[1] ትልቁ ዳሞት ሳይቀር ሁሉም ሌሎች የሲዳማ መንግሥታት በኦሮሞች ወረራ ፈራርሰው ሲጠፉ በምዕራብ ከሚገኙ ለዘመናት በንጉሣዊ አገዛዝ የሚስተዳደሩ ብርቱ ትግል አድርጎ ሳይጠፉ መኖር የቻሉ የከፋ መንግሥት ብቻ ነው።

የኦሮሞ ሰዎች አንድ አማራ መግደል በሬ እንደ መግደል ነው ብለው ሲኩሩ የከፋ ሰዎችም በበኩላቸው አንድ ኦሮሞ መግደል ከብት እንደመግደል ይቈጠራል እያሉ ይዘፍኑ ነበር። የከፋ መንግሥት ሕልውናን ማስጠበቁ ብቻ ሳይሆን የሲዳማ ነገሥታት ዘር የነበሩ በኦሮሞች ሲወረሩ በግዛቱ በክብር የንጉሥ የክብር ማዕረግ ተሰጧቸው እንዲኖሩ ያደርግ ነበር። ለዚሁም የበቁ የዳሞትና የእናሪያ ነገሥታት ይጠቀሳሉ። ይኸንም የሚያደርግበት ምክንያት የራሱ ዘር የሲዳማ ዘር በመሆናቸውና የማይበገርነቱ እምነት ስለነበረው የምዕራብ ሲዳማ መንግሥታት ጠባቂ መሆኑም እምነት ስለነበረው ከአፄ ምኒልክ ሠራዊትም ጭምር ራሱን ለመከላከል እንደሚችል የነበረው እምነት፣ በኦሮሞች ላይ በነበረው የበላይነት ስሜት ተደፋፍሮ ነው። ይህ በመሆኑ ከፋ በአፄ ምኒልክ ሠራዊት የተሸነፈው ለ17 ዓመት ከተዋጋ በኋላ ነው። ከፋ ከጥንት ጀምሮ በዘውድ አገዛዝ የተመሠረተ መንግሥት መሆኑን በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ንጉሡ የሚንጆ ጉሣ የቡሻሾ ቤተሰብ ነበረ። የንጉሡ ፈላጭ ቈራጭነት ገደብ የሚወስኑ ደምቦችም ነበሩ። ① የንጉሡ የክብር ዘበኛ አዛዥ የሚሆነው ካታሚ ራሺዮ የሚባለው ከዚዮ ጉሣ ይመረጣል። ② የጊምቦ ክፍለ ሀገር አስተዳደሪ ከኢርጎ ጉሣ ③ የቢታ አስተዳዳሪ ከአማሮ ጉሣ' ብቻ መመረጥ ነበረባቸው ወዘተ። ሹመቱም የሚሰጠው በልምድ ነበረ፣ ጉሣው በሚኖርበት አካባቢ አልነበረም። የከፋ ንጉሥ እንደ መልአክ ይቈጠር ነበር፣ ዜጎቹም ፊቱን ከማየት ይቈጠቡ ነበረ። የመጨረሻም የከፋ ንጉሥ ዘውድ የነበረ አፄ ምኒልክ ለሰዋትበርላንድ ተወላጅ ኢልግ ስለሰጠው በዙሪግ በሚገኘው በመሐንዲሱ ቤተሰብ ቤት ተቀምጦ ይገኛል። የንጉሡ መቀመጫ (ዋና ከተማ) ቦንጋ (ቦንጌ ዳቦ Bonghe Dabbo) በተባለው ንጉሡ ለሰማይ እግዚአብሔር አምልኮት ያደርግበት በነበረው ተራራ ፊት ለፊት ነበረ። 10 ኪሎ ሜትር ከቦንጋ የሚርቅ በአንደራቻ የከፋ ንጉሥ ሌላ ሁለተኛ መቀመጫ ነበረው ይህ ቦታ ግን ለውጭ ሰዎች የተከለከለ ነበረ። ንጉሡ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። አታለች የተባለ ሰው ንጉሡ የሚበላውና የሚጠጣው የሚቈጣጠር ነበረ። ንጉሡ ብዙ እንዳይበላም እንዳይጠጣም መከልከል መብት ነበረው። የንጉሡ ሥራዎች የሚከተሉት ነበሩ 1. ሀገረ ገዢዎች መሾም፣ 2. ከውጭ መንግሥታት ጋራ በመልእክተኞች በኩል ግንኙነት ማድረግ፣ 3. የዳኝነት ሥራ፣ የሞት ቅጣት፣

(1) Cerulli ibd p 197

በባርነት የሚሸጥ መብት፡፡ በከፋ በተለይ ለባርነት የሚዳረጉ ሰዎች ቆዎር፣ ቡዳ ተብለው የሚከሰሱ ሰዎች ናቸው፡፡ ዶቾ (Doccio) በተባሉ ቁሶች በኩል ለፍርድ ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ያለ ምንም ሌላ ማስረጃ ይግባኝ የሌለበት ባርያ ተብለው ይፈረድባቸው ነበር፡፡ 4. በጦርነት ተሸንፈው ስለተማረኩ ሰዎች ዕጣ፣ ንጉሡ ባሪያ እንዲሆኑ ማድረግ ወይንም አለማድረግ መብት ነበረው፡፡ ባሪያ ናቸው ከተባሉ ንጉሡ በጠየቀ ጊዜ ወደ ውጭ የሚሸጡ ናቸው፡፡ የዚሁ ዓይነት ዕድል ያጋጠማቸው ናዎ የሚባሉ ከጊሚሩ ጐሣ የሚመሣሠሉ፣ ከከፋ ደቡብ የሚገኙ ናቸው፤ ለንጉሡም የዝቢ ምንጭ ናቸው፣ ታቴ ናዎ (tate nao) ይባሉ ነበር (የንጉሡ ናኦ)፡፡ በእሮሞ ነገሥታትም ናኦ ሞቲ እየተባሉ በታማኝነታቸው ተፈላጊ ነበሩ፡፡ 5. ንጉሡ የዝቅተኛ ዘሮች የበላይ ጠባቂ ነበረ፤ እንደ ብረት ቀጥቃጭ ሸክላ ሠሪ (Manna) አዝማሪ፣ ማንጆ (Manjio tato) ማንጆ ታቶ ለንጉሡ ብቻ ወርቅ የሚሠራ ነው፡፡ በጂማ አባ ጅፋርም ወርቅ ሰሪ ለንጉሡ ብቻ ነው ወርቅ የሚሠራ 6. ንጉሡ የውጭ ሀገር ሰዎች ጠባቂ ነው፤ ወደ ከፋ የሚገቡ ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ዝባዎች ለክርስቲያን በቦንጋና በካያ ብቻ ነበሩ፡፡ በቋሚነት ኗሪ መሆን ለሚፈልጉ እስላሞች 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ከካያ በሚገኘው ቶንኮላ በተባለው ቦታ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር፡፡ ክርስቲያን በካሬኛ አሮ በቦንጋ ልዩ መንደር ተሰጥቷቸው እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር፡፡ እማር እንደ ከፋ ጐሣ ሆነው የተዋሐዱ የቢታ ክፍለ ሀገር አስተዳደር መብት ያላቸው በድሮ ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጥተው የተዋሐዱ ናቸው፡፡ ከፋ ለ4 ትከፈል ነበር፤ 1 ቦንጋ 2 እናሪያ 3 ከፋ 4 ሐዲያ[1] የከፋ ጐሣዎች አስተዳዳሪ ሆነው የሚመረጡ የገዢ መደቦችና የማይመረጡ ለሁለት ይከፈሉ ነበር፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው 1 ሚንጆ የንጉሡ ዘር 2 ይሪንጎ 3 ሂዮ 4 አማሮ 5 አርጊፓ 6 ሚየጠቺዮ የገዢ መደብ ያልሆኑ ጐሣዎች ሂኒማቾ (Hinnimachio) 2 ሂናካሮ (Hinacaro) 3 ሂኒቺዮ (Hinnucio) 4.እሾ 5 ቱራ ነበሩ፡፡ መንግሥቱ በጐሣ ልዩነት በመሬት ክልል የተከፈለ ነበረ፣ አስተዳዳሪዎች ራሺዮ ይባላሉ (ከአማረኛ ራስ የመጣ ቃል) ክፍለ ሀገሮች 10 ነበሩ ካፌ (Cafe) ጊምቢ፣ ቺያተታሉ፣ ዋቢ ቡተ፣ ቢተ፣ ጋዋተ፣ ጊዮሺየ፣ አዲ፡፡ ለቤተመንግሥት ብቻ የተወሰኑ 3 ራሺዮ ነበሩ፤ (ሀ) አዲዮ የክብር ዘበኛ ፈረሰኛ (ለ) ቶቺ የንጉሥ ባሪያዎች ሹም (ሐ) ካታሚ የንጉሡ ግቢ ዘብ አዛዥ፡፡ ከፋ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ አካል እንደነበረች በከፋ የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት መለከቶች ያስረዳሉ፣ ቤተክርስቲያኖችም ነበሩ፡፡[2] ከፋ ከኢትዮጵያ ተለይታ በኖረችበት ረጅም ዘመናት የጣኦት እምነት ብትከተልም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ዋና ዋና በዓላት ከማክበር ሕዝቡ አልከለከለውም[3]፡፡ የከፋ ንጉሣዊ አገዛዝ የማይናጋ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርገው የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ገደብ በማድረግ የሚቈጣጠሩ 6 አባላቱ ያሉት በንጉሡ አማካሪዎች የተደገፈ ስለነበረ ነው፤ እነሱም 1 ጉሺ ራሺዮ የካፌቾ ክርስቲያን ተጠሪ 2 ኩተማ ራሺዮ 3 አደል ራሺዮ ከኡቶ ጐሣ 4 አርባሽ ራሺዮ ከአርጋፓ ሐዲ ጐሣ ከኡቶ ጐሣ 5 አርባሽ ራሺያ ከአርማፓ ሐዲ ጐሣ 6 በንዳ ራሺያ ከአርጋፓ ሐዲ ጐሣ 7 አርሶ ራሺያ ከከፋ ማቶዮ ጐሣ፡፡ ሹመታቸው በምርጫ ሳይሆን በዘር የሚወረስ ነው፡፡ የአማካሪዎች የበላይ ሹም ጉሺ ራሺያ ነው፡፡ የዚሁ ጐሣ መሥራች በጥንት ከፋ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ የከፋ የጦር አዛዥ

---

(1) Cerulli ibd p 484

(2) A Cecchi : Da Zeila alle Frontiere di Kaffa VI p. 484

(3) A Cecchi ibd p. 486



በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኩሉና የጉሺ የንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ተሾሞ ስለነበረ ነው፡፡ የጉሺ ራሺዮ ሥልጣን ከፍተኛ ነበረ፡፡ ንጉሡ ሕግንና የሀገሩ ባሕልን የማያከብር ከሆነ ከሌሎች አባላት ጋራ በመመካከር ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ ተራ ሰው ሊያደርገው ይችላል፡፡[1]

## 3. ክርስትና በከፋ

ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አከባበር ወግና ሥነ ሥርዓት አስታየታቸውን የሚሰጡ የኢጣሊያ ፀሐፊዎች ከጥንት ቅድመ ክርስትና ከነበረው የጣኦት አምልኮቶች ያልተላቀቀ መሆኑን እያሉ ሲጽፉ ይታያሉ፡፡ በከፋ ስለነበረው የክርስትና ሃይማኖት በዚሁ መንፈስ አጋንነው ጽፈዋል፡፡ ቸኪ በዶዮክ በሚባለው የጣኦት እምነት በከፋ አብዛኛው ሕዝብ የሚያጠቃልል ነው ካለ በኋላ በከፋ ለሰይጣን አምላክም ማምለክ እምነት ስለነበራቸው የተለያዩ ከብቶችን ለመስዋእትነት ያቀርቡላቸው ነበር ብሏል፡፡ በጣኦት አማልክቶች ማመን፣ መስዋትነትን ማቅረብ ከፋዎች የክርስትና እምነት ሥነ ሥርዓትንም ከማክበር አይከለክላቸውም ነበር፡፡ ከጣኦት አምልኮት በአስከፊነቱ የሚጠቀስ የጣኦት ቤተመቅደስ ሰዎች (ቄሶች) ቡዳ በተባሉ ሰዎች ሌሊት ወደ ጅብነት የሚለወጡ ናቸው ተብለው ተከሰው ወደ ቄሶች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ቡዳ ናቸው ብለው ከፈረዱባቸው፣ ምስክር ሳያስፈልግ፣ ይግባኝ በሌለበት ወደ ንጉሡ ቀርበው ባሪያ እንዲሆኑ ይፈረድባቸው ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ጌራ ይገኝ በነበረው የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ቄስ በአባ ወ(?)ን ግምት በየዓመቱ ለከፋ ንጉሥ 500 ባርያዎች ያስገኙለት ነበር፡፡ በቸኪ አባባል በክርስትና ብቻ የሚያምኑ የከፋ ሰዎች በቀር ሌሎች በስም ብቻ ክርስቲያን ናቸው በተግባር አይደሉም፡፡ የክርስትና እምነታቸውን የሚገልጹትም 1ኛ. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ በማለት 2ኛ ጾም በማክበር 3 በመገረዝ 4 ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው እንደ ገና፣ ፋሲካ ፍልሰታ ወዘተ የመሳሰሉ ዋና ዋና የክርስትና በዓላት በማክበር ሲሆን፣ በሌላ ተግባራቸው ግን ከጣኦት አምላኪዎች የተሻሉ አይደሉም፤ እንደ እስላሞች ብዙ ሚስቶች ያገባሉ በማለት ተችተዋል፡፡ በከፋ ቤተክርስቲያኖች በመላው ኢትዮጵያ እንደሚሰሩ ዓይነቶች ናቸው፤ በዛፎች የተከበቡ ናቸው፣ የምውታን መቃብሮችም አሏቸው፡፡ ከሁሉ የታወቀ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ በዚሁ ቤተክርስቲያን የጣኦት ዶዮክ አምላክ የሚያምኑም ሳይቀሩ ወደ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት፣ ካፌቾ በሙሉ ለመጸለይና ስለት ለማድረስ ይሄዳሉ፡፡ በታቦቱ ያለው በግእዝ የተጻፈ ይሰባቸው ነበር፡፡ ክርስትና ከፋ የገባው ምናልባት ከአክሱም ዘመነ መንግሥት መሆኑን መገመት እንችላለን፡፡ ቸኪ የ18 የከፋ ነገሥታት ስም ዝርዝር አውጥቷል[2] በ15ኛው ንጉሥ ጋንሺዮ ለ24 ዓመት የነገሠ የማዮ ራሺዮ ጐሣ ዘመን መንግሥትን ለመገልበጥ አሢረዋል ተብለው የተከሰሱ 600 ፈረሰኞችና ወታደሮች ተገድለዋል፡፡ በ16ኛው ንጉሥ ጋዊርሰር ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች ተገድለዋል፡፡ 17ኛው ንጉሠ ነገሥት ካም የጋዊ ዘሮ ልጅ ለ13 ዓመት የነገሠ በ1870 የሞተ፣ የዶእክ አምላክ አክራሪ ተከታይ ነበረ፤ እንደ አባቱ ብዙ ክርስቲያኖች ፈጅቷል፡፡ 18ኛ ንጉሥ በ1878 በሕይወት የነበረ የ45 ዓመት ጐልማሳ ስሙ ጋሊቶ ጋሊ ጋዎ (Gallito - Galli - Gao) ነበር፡፡ ሚንጂዮ ከማቶ ተረክቦ የቦንጋ

---

(1) A Cecchi : ibd p 488

(2) A. Cecchi : ibd p 490

ንጉሥ በመባል የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሲይዝ እናሪያን ከግዛቱ አጠቃለላት። በዚሁ ጊዜ እናሪያ ቡሳስ በተባሉ በንጉሣዊ ቤተሰብ ትገዛ ነበር። የካቶሊክ ሚሲዮን በጌራ ሲመሠረት 70 (ሰባ) ከእነዚህ ቤተሰብ አባላት የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ለሃይማኖታቸው ሲሉ ከከፋ ተሰደው በ1878 ወደ ጌራ በመሄድ ከካቶሊክ ሚሲዮናውን ተቀላቅለው ለመኖር መምረጣቸው በቀድሞ እናሪያ የክርስትና ሃይማኖት እንዳልጠፋ ምስክር ነው።[1] ወደ ጌራ የተሰደዱ የእናሪያ ሰዎች አለቃ 80 ዓመት ዕድሜ የነበረው አባ ታባኮ የተባለው ወደ ጌራ እንደመጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጌራው አባ ኮሮ የጦር አለቃ ሆኖ ተሾሞ በከፋ ላይ ለመዝመት ፈቃደኛ እንዲሆን የጌራ ንጉሥ ቢጠይቀው በሀገሬ ላይ አልዘምትም ብሎ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። የጌራ ንግሥትም ጉን እስላም እንዲሆን ብትጠይቀው እስላም ከሚሆን ገላው ተቈራርጦ ለአሞራዎች ቢሰጥ እንደሚመርጥ የሚል መልስ ሰጥቷታል። እንደዚሁም አንድ የቡሳሲ ልዕልት ልጅዋ እስላም እንዲሆን ብላ ብትጠይቃት የሰጠችው መልስ ተመሣሣይ ነበረ። ከፋ የዓመት መጀመሪያና መስቀል የሚያከብረው ልክ እንደ ኢትዮጵያ አከባበር ነው። ንጉሠ ነገሥቱ በዓመት መጀመሪያ ቀን ከእሱ በፊት የነበረው መቃብር ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ የከብቶች መስዋእት ያቀርባል ዜጎቹም እበባ እያበረከቱ ረጅም ዕድሜ ይመኙለታል። በመስቀል ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ለሹማምንቶቹ ትልቅ የምሳ ግብዣ ያደርጋል። ግለሰቦችም መስከረም 17 በየቤታቸው ያከብሩታል፤ መስከረም 18 ብዙ የሚነድ ዕንጨት ይከማቻል፤ መስከረም 19 እውነተኛ የመስቀል በዓል ከንጉሡ ቤት ጀምሮ ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ ይደረጋል፤ 3 የተለያዩ ቀለማት ያላቸው እርማዎች በመያዝ ፯ ባሮ ማስካሮ እያሉ እየዘፈኑ ይሄዳሉ። ንጉሡ ነገሥቱም ወደ ፀበሉ መጨረሻ ዣ ባሮ ማስካሮ እያለ ይዘፍናል።

## 4. ደቡብ ምዕራብ ከኢትዮጵያ ጋራ ማዋሐድ

የመጨረሻ የጌራ ንጉሥ የነበረው የአባ ራጉ አጎት ለጉብኝት ወደ እሱ ለሄደው ኢጣሊያዊ ቸሩሊ (Cerulli) እንዳጫወተው ጌራ ለአፄ ምኒልክ ጦር የተማረከችው በጀግናው ኢትዮጵያዊው ደጃዝማች በሻህ አቡዬ የሚመራው ጦር አራት ጥይት ብቻ በመተኰስ ነበረ። ንግግሩም በመቀጠል ደጃዝማች በሻህ ደፋርና ጀግና ርሕሩሑም ነበረ፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በጦር ሜዳ በጣሊያኖች ተገድለዋል። እላይ እንደተገለጸው የከፋ የጥንት ታሪክና ባህል አድናቆት የሚስብ ነው። ጅማ አባጅፋር ከፋን ለማስገበር ከምኒልክ ጦር ጋራ በመሰለፉ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ላደረገው ውለታ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት እንደተሰጠው ሁሉ ለከፋም ለጥንታዊ ወጉና ባሕሉ ክብር እንዲሁም ላሳየው ጀግንነት ከጅማ የበለጠ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ለማግኘት መመዘኛ ነበረው። አፄ ምኒልክ ግን በጠባብ የዘውድ ጥቅም ብቻ የሚመራ ስለነበረ ከፋ የጅማ ዕድል አልተሰጠውም። አፄ ምኒልክ እንደ [illegible] አደራ ኢትዮጵያ በደቡብና ምዕራብ ጥንት የነበሩዋት ግዛቶች ለማዋሐድ በተደረገው ትግል፤ የጅማ አባ ጅፋር ትብብር በደስታ ሲቀበል የጉጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ግን በዘመቻው እንዳይካፈል ጦርነት ገጥሞ በማሸነፍ አስቀርቶታል። ከዚህም ሌላ የልጃ ዘውዲቱ ባል የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያ ሥላሴ በአባቱ ትእዛዝ በዘመቻው

[1] A Cecchi : ibd p. 341



ተካፋይ ለመሆን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሸዋ መጥቶ አፄ ምኒልክ በመጣበት እንዲመለስ አድርጎታል።

የአፄ ምኒልክ ሠራዊት ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝመት በሚዘጋጅበት ጊዜ የጅማ ንጉሥ አባ ጅፋር የምኒልክ ጦር ለመቋቋም እንደማይችል በመገንዘቡ ለምኒልክ ለመገበር እንደወሰነ ሁሉ እንደዚሁም ቃቢየና በተባለው በጉራጌ ሀገር ሱልጣን የነበረው ሶማር ባክስ የተባለው አክራሪ ሙስሊም የባሪያ ነጋዴ የነበረው፤ በየጊዜው ለሥራ ምክንያት ወደ ሸዋ በመመላለስ አፄ ምኒልክ የነበረው የጦር ኃይል ስለተረዳ ለምኒልክ በሰላም ለመገበር ተሽቀዳድሞ ወሰነ። በአፄ ምኒልክና በሶማር ባክሳ መካከል የተደረሰው ስምምነት ያስከተለው ውጤት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የቻሃ፣ ምሑር፤ ጆቸሪት፣ እነሞር ጉራጌዎችና ከ2 ሺህ እስከ 3ሺህ የሚደርሱ አማራዎች በ1876 የደረሰ እልቂት ነው[1]። ኢማም ተብሎ የሚጠራው ሶማር ባክሳ ከንጉሥ ምኒልክ እርዳታ እንዲያደርግላቸው አደራ ተብለው ወደ ጅማ ከፋ ለመዝለቅ ፈልገው ወደ ግዛቱ የመጡ ቸኪና ኪያሪኒ የሚባሉ ጣሊያኖች ወደ ግዛቱ ሲገቡ የሚከተለው ንግግር በማድረግ ተቀበላቸው። “አዳምጡኝ እናንተ እንደ እኔ ትልቅ ሰዎች ናችሁ፤ ንጉሥ ምኒልክ ወደ እኔ አደራ ብሎ ልኮዋችኋል፣ ነገር ግን እናንተም ለእኔ ማድረግ አለባችሁ። እኔ እንደ ኦሮሞች ልብሶች መስተዋቶች ለዝቅተኛ ሰዎች የሚሰጡ እቃዎች አልጠይቃችሁም። እኔ ብዙ ጠላቶች አሉኝ፣ እናንተ ከእነሱ ለመገላገል እኔን መርዳት አለባችሁ የምጠይቃችሁ ከፈጸማችሁልኝ እኔ ራሴ ወደ ጅማ አባ ጅፋር እሸኛችኋለሁ። ብዙ ነገር አልጠይቃችሁም። የእናንተ አንድ ጠብመንጃ ብቻ በርቀት ሁኖ አንድ የጉራጌ ጉሣ ክርስቲያን የእኔ ጠላቶች ለመደምሰስ ይበቃኝ ነበር በማለት ጥያቄውን ደምድመዋል። ጣሊያኖች ግን አሁን ያሉን ጠብመንጃዎች ለራሳችን ለመከላከያ ብቻ የሚያገለግሉን ናቸው ሸዋ ለሚገኘው አለቃችን መልእክት ልከን ጠይቀን ግን እንዲሰጥህ ማድረግ እንችላለን አሉት። በዘመኑ በቃቤና በኩል በየዓመቱ 400 ባሪያዎች ተገዝተው ወደ ሸዋ ይወሰዳሉ። አብዛኛዎቹ ከቻሃና ከኡርባራግ በሌሊት ተሰርቀው የሚመጡ ናቸው፤ የሚገዙም በገንዘብ ሳይሆን በነሐስ ነጥር ነው፤ አንድ ነጥር 432 ግራም ነው የገበያ ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ወንድ ልጅ ቁመት 1ሜትር | 20 ነጥር |
| 2 | ሴት ልጅ ቁመት 1 ሜትር | 13 - 15. ነጥር |
| 3 | ትልቅ ልጅ 12 - 16 ዓመት | 26 - 28 ነጥር |
| 4 | ሴት ልጅ | 25 |
| 5 | ወንድ ልጅ 20 - 24 ዓመት | 20 - 30 |
| 6 | ሴት ልጅ ቆንጆ | 40 |
| 7 | ሴት ልጅ መለስተኛ | 30 |
| 8 | ሴት ልጅ ዝቅተኛ | 25 - 20 - 15 |
| 9 | ቆንጆ ልጃገረድ | 60 - 70 |
| 10 | አሮጊት | 6 - 7 |
| 11 | ሽማግሌ | 8 - 10 |
| 12 | ሽማግሌ ጠንካራ | 20 |

ዒማም ሶማር ባክሳ ጠብመንጃ ከመጠየቅ አላቋረጠም፣ ጣሊያኖችም ተስፋ እየሰጡት ነበር። አንድ ቀን ነሐሴ 25, 1878 “ዐሽከሮቻችሁ

[1] A Cecchi : ibd VII p 52

ከነመግሪያዎቻቸው ወደ አንድ ክርስቲያን ጉራጌ መንደር ከእኔ ጋራ ሄደው እንዲዘርፉ ፍቀዱልኝ የምናገኘው ገቢ እካፍላችኋለሁ ብሉ ጣሊያኖችን ጠየቃቸው፤ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች የጥያቄው አደጋነት በመገንዘብ፣ ከሁሉ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ስለሚፈልጉ ለአንድ ወገን ማዳላት እንደማይሹ ነገሩት።

ጣሊያኖች ለጉዞዋቸው መሰናክል መሆኑን ስለተረዱ ከጉራጌዎች ጋራ መቀራረብ ፈለጉ፤ ጉራጌዎችም ሀገራቸውን እንዲጎበኙላቸው ጋበዙዋቸው። በዚሁ መሠረት ከሁለቱ ጣሊያኖች አንዱ ወደ ጉራጌ ሀገር ሄዶ ጥናት እንዲያደርግ ወሰኑ፣ ዕጣም ለኪያሪኒ ደረሰው። መንገድ መሪዎች ጉራጌዎችን ይዞ ኪያሪኒ ወደ ጉራጌ መሬት ገባና ቤተክርስቲያኖችን አስጐበኙት። ወደ መጨረሻም አስጐበኘው ከዝናብ ለመጠለል ወደ ቤቱ አስገባው። በዚሁ ጊዜ ፈረንጅ ብዙ ሰው ተሰብስበው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር። ከቀረቡትም ጥያቄዎች ከየት ሀገር እንደመጣ፣ ሃይማኖቱ ክርስቲያን እንደሆነ ወይንም እስላም፣ ከሁለቱ ሃይማኖቶች የትኛው እንደሚሻል፣ ዘቀንደኛ ጠላቶቻቸው በእስላሞች ድል ይቀዳጁ እንደሆን ወይስ አይቀዳጁም ወዘተ። ኢማም ያግር ባክሳ ብቻ ሳይሆን የምኒልክ ወታደሮቹም ክርስቲያን መሆናቸው እያወቁ ከኢማም ተከታዮች ጋራ በመስማማት ያለ ምንም ርሕራሔ ያላቸውን ንብረት እየዘረፉ ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሳይቀሩ ያቃጥሉባቸው እንደነበረ በምሬት ያወሩለት ነበር። ጉራጌዎች ምሑር ስለ ሃይማኖት ብዙ ነገር ባያውቁም ሁሉም ግን ክርስቲያን ነን በማለት ይነግሩት ነበር[1] ። ኪያሪኒ እግረመንገዱ ከኤሻ ንጉሥ ጋራ ተዋወቀ ንጉሡም ፈረንጅ ያዛቸው መሣሪያዎች ካደነቀ በኋላ "አንተ ዓለምን ሙሉ ማቃጠል ችላለህ፣ የእኔ ሀገር አትንካ አንተ ቄስ ነህ እኔም እወድሃለሁ፣ አንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ እዬ ምኒልክና እስላም ንብረታቸው እየዘረፉ ሊያጠፉቸው እየጣሩ ያሉት እነዚህ ምስኪን ሕዝቦች ደስተኞች ልታረጋቸው ትችላለህ"። የሚል ንግግር አደረገ[2] ከንጉሡ ተሰናብቶ እንደሄደ የጣሊያኑ መምጣት ወሬ ስለተሰማ በፊት ቄስ ብቻ ይቈጥሩት የነበረ አሁን እንደ ቅዱስ ሰው ሁሉን ነገር የሚያውቅ አደረጉት። በሸዋ ሰዎች ልጆቻቸው የተወሰዱባቸው በሕይወት እንዳሉ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበር። ኪያሪኒ ከአካባቢው ተነስቶ እንደሄደ ቸሃ መሬት ደርሶ በዙሪያው ለተሰበሰበ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለሚያቀርብ ሕዝብ ዕድላቸውን እንዲነግራቸው፣ በጠላቶቻቸው በእግራ የተወሰዱባቸው ልጆቻቸው ወንድሞቻቸው የት እንደደረሱ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበረ። በመቀጠልም ኪያሪኒ ከዳሞ ንጉሥ ተዋወቀ፣ ጥሩ መስተንግዶ ተደረገለት። "የዚህ ሀገር ሕዝብ የቃበናውን ይማም አይደለም የሚፈሩ፤ በእሉ አማካኝነት የምኒልክ ጦር እንዳይወራቸው ነው ስጋታቸው[3]። ከእኛ ጋራ ሆነህ እንዝመት እስላሞችን እናጥፋቸው እያሉ ለክብሩ ይዘፍኑ ነበር። ንግሥቲቱም ለብቻው ወስዳ የቀቢየና ይማም አግራ እመጣባችኋለሁ እያለ እያስፈራራን ነው፣ ሙስሊን ሊያደርገን እየሞከረ ነው፤ የጉራጌ ሕዝብ እንደ በግ ነው የሚነዳው፣ ሃይማኖቱን ሊክድ ይችላል፤ እግሮች የማይመጡ መሆናቸው ቢያውቅ ግን ሕዝቡ ኢማሙን መሳቂያ ያደርገው ነበር። አንተ ትልቅ ሰው ነህ፣ ሕዝቡ ከውድቀት እንዲድን አድርገው፣ ቃልህን እንዲያምኑ ያዝካቸው መሣሪያዎችን አሳያቸው" ብላ ንግግሩዋን ከጨረሰች በኋላ ኪያሪኒ መልስ ለመስጠት

[1] A Cecchi ibd VII p 77
[2] A Cecchi : ibd p 80
[3] A Cecchi : ibd p 87



ተቸገረ[1] ንግሥቲቱ ላቀረበቻቸው አንገብጋቢ ጥያቄዎች ኪያሪኒ "የእናንተ ሁኔታ ይገባኛል የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ። እግሮች ይመጣሉ እያለ የግር ባክሳ የማስፈራሪያ ጉራ ስለሚነዛባችሁ ጉዳይ አትቸገሩ፤ ንጉሥ ምኒልክ ባሁኑ ወቅት ለእዬ ዮሐንስ ግብር ለመክፈልና የበላይነት ለመቀበል ተስማምቷል፤ እዚህ መምጣት አይችልም ክርስቲያኖችን ከእስላሞች ጥቃት መጠበቅ አለበት እንጂ ክርስቲያኖችን አይፈጅም። እኔና ጓደኛዬ የእስላሞች ሀገር አቋርጠን ስለምናልፍ ችግር እንዳይፈጥሩብን አሁን ያልኳችሁ ነገር ለማንም አትናገሩ።" በማለት የማደፋፈሪያ ቃላቶች ሰጣት። ንግሥቲቱም መልስ ስትሰጠው "በእስላሞች ሀገር ለማለፍ ግዴታ የለባችሁም፤ ወደ እኛ ከመጣችሁ በእቋራጭ መንገድ ምንም ሳትከፍሉ በጃንጀር ሀገር በኩል ወይንም በጅማ ዘኩል ወደ ከምባታ ወላሞ እናደርሳችኋለን፣ የጅማ ንጉሥ ሚስት የቻሀ ተወላጅ የአባጋስ ልጅ ናት" አለችው። ኪያሪኒ በንግሥቲቱ ንግግር በጣም ተደስቶ አመሰገናት። ጉራጌዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚወለዱ ለኪያሪኒ ሲያስረዱ እንደሚከተለው ገልጸውለታል "ከእርሲ፣ ከሪዩ፣ ቱሉማ፣ መጫ፣ ጋላ ተከበው በችግር ላይ በነበሩ ጊዜ ከሀገራቸው እንዲያባሩሯቸውና እንዲፈጁዋቸው ይፈልጉ ስለነበረ ጉራጌዎች ወደ ጎንደር ለንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኞቻቸው ልከው ከእርሞች እልቂት እንዲድኑ እርዳታ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሠረት እነሱ እጥናፍ ሰገድ የሚሉት ንጉሥ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ሱሲኒዮስ የሚሉት ንጉሥ የትግራዩ ሹም የነበረው አዝማች ሰብሐት ለእርዳታ ላከላቸው፣ እሱም የተላከበትን ዓላማ እንደተዋጣ፣ ወታደሮቹ ቊጥራቸው በመቀነሱ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመመለስ ስላልቻሉ በዝዋይ ሐይቅ የምትገኘው ትልቋ ደሴትና አካባቢው ሰፍረው ጉራጌዎች ንጉሥ ብሉ ራሱን ሰየመ። የአዝማች ሰብሐት ትውልድ ሐረግ ብዙ ዓመት ነገሠ፤ በመጨረሻ ግን በንጉሥ ሣሕለሥላሴ የምኒልክ አያት ተደመሰሰ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ጉራጌዎች እውነተኛ ንጉሥ የላቸውም፤ ጉልበት ያለው ሁሉ ደካሞችን እያስቸገረ ንጉሥ ይባል ነበር መሬታቸውንም ይነጥቁዋቸው ጀመር። በዚሁ የተነሳ የጉራጌ ቋንቋ ከግእዝ ተመሣሣይነት አለው[2] ።

ከጉራጌዎች የክርስትና ሥነ ሥርዓት በጥብቅ የሚከተሉ ምሁር ናቸው። ኢንደጋኝ፣ የነር፣ መገር፣ እስላሞች ያረዱትን ስጋም ይበላሉ። ጉራጌዎች ባለሥልጣን እያውቁም፣ ስለ ንጉሥ ሲያወሩ እንደ ተራ ሰው ነው የሚያከብሩት፣ ሃብት ያለው ብቻ ንጉሥ የሚባለው። ንጉሥ የሚባሉ ሃብትና ጀግንነት ያሳየ ሰው ነው። ከእነሱም ትልቁ ብቻ ዳሞ ወይንም ጉይታ ይባላል።

ጣሊያኖች ወደ ከፋ ለመድረስ የቻሀ ንጉሥ ማጋናስ ባቀረበላቸው ሃሳብ መሠረት በጅማ ወይንም በሊሙ ከማለፍ፣ በጉሬጌ፣ ጃንጅር፣ ከምባታ፣ ወላሞ እንጓዝ ኪያሪኒ አምናበት ተስማምቶ ነበር፤ ሆኖም አብሮዋቸው የሚጓዙ ክብት ጫኞች መንገዱን ስለማያውቁ በዚሁ መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በመጨረሻ ከቃቢና ጥጂየር ወደ ሊሙ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

እዬ ምኒልክ ቀድሞ የኢትዮጵያ አንድ አካል የነበሩ፣ እርሞች ባካሄዱት ጦርነቶች ምክንያት ከኢትዮጵያ ተለይተው ይኖሩ የነበሩ ግዛቶች መልሶ ለማዋሐድ የፈጸሙው ተግባር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለዘለዓለም

[1] A Cecchi : ibd VII p 88
[2] A Cecchi : ibd VII p 89

የማይረሳ ውለታ የሚያስገኝለት ቢሆንም እላይ እንደተገለጸው አክራሪ ሙስሊሞች እንደ ኢማም የማር ባክሳ ባለሟል አድርጎ በጉራጌ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ጥቃት እንዲያደርስ መፍቀዱ ከባድ የአስተዳደር ስህተት በመፈጸሙ በታሪክ ያስወቅሰዋል፡፡

## 5. የእናሪያ የመሬት ስፋት

ተጓዦች ጣሊያኖች ቸኪና ኪያሪኒ ተፈቅዶላቸው ወደ ሊሙ ገቡ፡፡ በቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመን የእናሪያ የመሬት ስፋት ከአባዩና አዋሽ ወንዞች ከፋም በውስጡ የሚያጠቃልል የግቤና የጉጀብ ሜዳዎች ያቀፈ ነበረ፡፡ ይህ ግዛት በንጉሥ እንደራሴ ይገዛ ነበር፡፡ ከ1545 ጀምሮ በኦሮሞ ሜጫ ወራሪዎች ግዛቱ ሲፈራረስ ነገሮዎች ግማሾቹ ወደ ጉጃም ሲሸሹ ግማሾቹ በከፋ ሰሜናዊ ክፍል ሰፍረው ያጡት የሰፊ ሀገራቸው ስም የሰፈሩበት አንድ የከፋ ክፍለ ሀገር እናሪያ ብለው ሰይመው በቀድሞ ገባሮቻቸው ከነበሩ የወረታ ጉሣዎች በመተባበር ለኦሮሞ ማስፋፋት ከፍተኛ መከላከያ በማድረጋቸው ለከፋ በነፃነት መቄየቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመፈራረሉ በፊትና እናሪያ በመጫ ኦሮሞች ከመወረሩዋ በፊት የሀገሩ ነዋሪዎች አፈ ታሪክ እንዳቄየው ሁለት የፖርቱጋል ወታደሮች ሲጋሮ (Sigaro) እና ሰፔራ (Sapera) የተባሉ፣ ክክሪስቶፎር ዳ ጋማ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ በአፄ ግላውዴዎስ ከሰሜን ኢትዮጵያ ተባርረው እናሪያ መኖሪያቸው አድርገዋት ነበር፤ በስነ ምግባራቸውም በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮት አግኝተው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የነበራቸው አክብሮት እየጨመረ በመሄዱ በእናሪያ የአስተዳደር የበላይነት አግኝተው ነበር፡፡ ሲጋሮ በሰሜን እናሪያ መኖሪያው አደረገ፣ ሳፔራ ወደ ደቡብ ሳፓ (Sappa) ተብላ የተጠራችው መንደር ሰፈረ፡፡ ከሳፓ ቤተሰብ አንዱ የአባ ባጊቦ አባት አባ ጎሞሊ በክህደት የሲጋሮ ግዛት ወደ ግዛቱ አጠቃልሉ አንድ የሊሙ መንግሥት አቋቋመ፡፡ እንደ አቡነ ማሣያ ምስክርነት አባ ጎሞሊ የነጭ ዘር ይመስል ነበረ[1]፡፡ ሊሙ ከ80 ዓመት ወዲህ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ቢሆንም መስጊዶች በብዛት አይታዩም፡፡ ጣሊያኖች /ቸኪና ኪያሪኒ/ በነበሩበት ዘመን (1878) በሊሙ ተላላፊ በሽታ ተስፋፍቶ ነበር፡፡ በሊሙ የሕዝቡ ግማሽ በበሽታ አልቋል[2]፤ በጉማ 2/3 በበሽታ አልቀዋል፡፡ ጣሊያኖችም እየታመሙ ይድኑ ነበረ፡፡ ከሁለቱ አንዱ ኪያሪኒ ታሞ ሲሞት በጌራ ንግሥት ተመርዞ ነው የሞተ ተብሎ ተወራ፡፡

## 6. ጉማ

ጉማ በጥንት ጊዜ የሲዳማ እማራ የሚባሉ ይኖሩባት ነበር፡፡ በኦሮሞ ነዋሪዎች ጊዜ ነዋሪዎቹ በሙሉ ተገድለው አልቀዋል፡፡ ክርስቲያን ሕዝብ ይኖሩበት እንደነበረ በማያሻማ ሁኔታ ማስረጃ የተገኘው የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ በዲደሳ ወንዝ ዳሩ (Daru) ከተባለው ተራራ አጠገብ ጉልጉታ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በመገኘቱ ነው[3]፡፡ ሜላ የጌራ ዋና ከተማ የሁሉ ዓይነት የባሪያ ክምችት የሚታዩባት ናት፡፡

---

[1] A Cecchi : ibd VII p 156
[2] A Cecchi : ibd p 199
[3] A Cecchi : ibd p 239



1. ወረታ ጉሣዎች ከኩሉ፣ ወሊሶ፣ ኮንታ መንግሥታት የመጡ
2. ካፊቾ 3 ጃንጀሮ 4 ጉራጌ 5 ከምባታ 6 ሻንቅላ 7 ጋላ የተለያዩ ጉሣዎች ሶዶ፣ በቶር፣ አጋሉ[1] ፡፡ የጌራ ሕዝብ የኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ አማራ ድብልቅ ነው፡፡ ሌላ ዋምባሪ የተባሉ ዝቅተኛ ዘር የሚገመቱም አሉ፡፡ የቤተመንግሥት ዘር የኦሮሞ ዘር ከወላሞ ምሥራቅ ደቡብ የመጡ ናቸው[2]፡፡ በጌራ ቤተመንግሥት ከ3000 ያላነሱ ባሪያዎች ይኖራሉ፡፡ እነሱም 12 የንጉሡ ሚስቶች በጋብቻቸው ጊዜ ለጥሎሽ ተሰጧቸው ይዞዋቸው የመጡ ናቸው፡፡ ባሮች ወደ ውጭ ይሸጣሉ በሀገር ውስጥም በእቃ ይቀየራሉ፤ 6-7 ባሪያዎች በአንድ የጦር ፈረስ ይለወጣሉ ወዘተ፡፡ ይህ ሁኔታ የአፄ ምንልክ ጣልቃ ገብ ጦር እነዚህ ጥቃቅን መንግሥታትን መውረሩ ሕጋዊ ያደርገዋል፡፡

## 7. ጃንጀሮ

ጃንጀር ደብተሮችና የካፊቾ ሽማግሌዎች እንደሚተርኩ የዚሁ አካባቢ የመጀመሪያ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አፈታሪክ እንደሚናገረው ጃንጀሮና ሲዳማ በሐይቆች ይኖሩ የነበሩ የአንድ እናት ልጆች ናቸው፡፡ ጃንጀሮ የግቤ ዳውሮ አጠገብ አዞዎች ያመልኩ ነበር፡፡ ንጉሣቸው ኩርማ በሬዎች ለአዞዎች እንዲበሏቸው በመስዋእትነት ያቀርብ ነበር፡፡ ንጉሥ ሲታመም ጤና እንዲያገኝ ሰዎች ወደ ግቤ አዞዎች ለመስዋእትነት ይወረውሩ ነበር፡፡ ይህ የጣኦት እምነታቸው ግን አንዳንድ የኢትዮጵያ የክርስትና ሥነ ሥርዓት እንደ እስተርእዮ ማርያምና መስቀል ከማክበር አያግዳቸውም[3] ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ከግራኝና ከኦሮሞ በፊት በግዛቷ በሙሉ የክርስትና ሃይማኖት ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም፡፡

## 8. ቦሻ

በቦሻ ከኦሮሞች ጋራ የሚኖር ሕዝብም ከትግራይ መምጣታቸውን ለማስታወስ "ቲግሮ ቦሻ" ተብለው ይጠራሉ፤ በሀገራቸው የቤተክርስቲያን ቅሪቶች ይታያሉ፤ ብዙ ዘመን ከአዋሽ በስተደቡብ ይኖሩ እንደነበረ ያወራሉ፤ በዚሁ ጊዜም ሀገሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ስር ሆኖ እናሪያ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ በኦሮሞች ተገፍተው ከሀገራቸው ተፈናቅለው፣ በመጀመሪያ አሁን ቦቶር ባሉበት ይኖሩ ነበር፣ በመጨረሻ አሁን ባሉበት ሰፈሩ፡፡ ቋንቋቸው ከካፊቾ ተመሳሳይ ነው፡፡

## 9. ዋሬታ

በአጠቃላይ ስማቸው ዋሬታ ወይንም ዳውር ተብለው የሚጠሩ ሕዝቦች 1 ኩሉ 2 ኮንታ 3 ኩዊሻ 4 ማር 5 ጉልዳ ከኦሞ ወንዝ በስተምሥራቅ የሚገኙ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያውያን ታሪክ አዋቂዎች ደብተሮች አባባል በኢትዮጵያ ታሪክ ዝነኞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በ1300 ዓ.ም. በአጼ ዓምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ጋራ የተቀላቀሉ ናቸው፡፡

---

[1] A Cecchi : ibd p 258
[2] A Cecchi : ibd VII p 266
[3] A Cecchi : ibd p 355

ሕዝቡ ራሱም የቀድሞ የኢትዮጵያ አገዛዝ በሚገባ ያስታውሳል፣ ከእጼ ዓምደ ፅዮን ወታደሮች ጋራ ዘራቸው በጋብቻ የተደባለቁ መሆናቸውና በሀገራቸው ከብዙ ዘመን ጀምሮ እንደኖሩ ያወራሉ፡፡ የኢትዮጵያ አገዛዝ ምልክቶች ብዙ የትግሪኛ ቃላቶች በቋንቋቸው መገኘታቸውና የክርስትና ባሕሎች በአንስተኛ ደረጃ ቢሆኑም መገኘታቸው ለጥንታዊ ኢትዮጵያዊነታቸው በቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ እንደ ጋሮ በሻ ሕዝብ የዋራታ ሕዝብም ኪስታን ወይንም ቤት ክስታን የሚሏቸው የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል ፣ የአባ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያኖች አሏቸው፡፡ በቤተክርስቲያኖችም በሬዎች እርደው እግዚእ መሐረነ ክርስቶስ እያሉ ይጸልያሉ፡፡ በሥልጣናቸው ወረታዎች ቁመታቸው አጠር ያለ ቢሆንም ከጥቁር ዘር ይልቅ ወደ ዓረብ ዘር ይሰባቸዋል፤ ከጐረቤቶቻቸው ከጥቁሮች የተቀላቀሉ ጠቁር ያሉም አሏቸው፡፡ ከዋራታዎች መሐል የኩሉ መንግሥት በከፋ መንግሥት ስር ተጠቃልሎ ነበር፡፡ ወላሞ ክርስቲያን ነበሩ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እስልምና እየተቀበሉ ናቸው፡፡ የክርስትና እምነት የሚያኩሩ እንደ ላሊበላ ቤተክርስቲያኖች በመሬት ተቈፍረው የተሰሩ ቤተክርስቲያናት አሏቸው፡፡ ከማሎና ወላሞ በስተደቡብ ዶኮ የሚባሉ ጥቁር ሕዝብ የሚኖርበት ሀገር ነው፡፡ ኮንታ ወይንም ቆቦ የሚባል ሕዝብ ሶማሌዎች አማራ ይሉዋቸዋል ምክንያቱም ከአማራ ነጋዴዎች ጋራ የመጡ ናቸው ይባላል፡፡ ጐረቤታቸው የሆኑ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች ከፉ ናቸው፣ ስው ይበላሉ ይሏቸዋል፡፡ የእሞ ወንዝ ከዋረታዎች የተሰጠው ስም ነው፡፡

## የኦሮሞ ታሪክ የተለያዩ አስተያየቶች

ስለ ኦሮሞ ታሪክና አሰፋፈር ከተለያዩ የውጭ ሀገር ፀሐፊዎች የተለያዩ ተቃራኒ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ የቻሉት አብዛኛው ጊዜ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ማቀነባበር ባለመቻላቸው ነው፡፡ ቸኪ[1] የጠቀሳቸው ፀሐፊዎች ጋሊኒየ (Galinier) ኦሮሞች በአፍሪካ ምሥራቃዊ ደቡባዊ 5ኛ 10ኛ ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዮድ በዛንዚባር ይኖሩ የነበሩ ያደርጋቸዋል 2) Pellogrino Matteucci ፐለግሪኖ ማቴውቺ በአፍሪካ ካገኘናቸው ሕዝቦች ያስገረመኝ ኦሮሞች ነጭና ክርስቲያን በመሆናቸው ነው ካለ በኋላ ለምን ነጭ (ቀይ) ሆኑ ለምን ክርስቲያን ሆኑ ብሎ ይጠይቃል፡፡

3) Pricard ፕሪካርድ) እስከ ዛሬ ስለ ጋላ ያለን መረጃዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ስለ ታሪካቸው የምናውቀው ነገር ባይኖርም፣ ከሥልጣኔ ሩቅ መሆናቸው ደምበኛ ኋላ ቀር መሆናቸውና የከብት ጭራ ተከትለው የሚኖሩ፣ ዘላኖች እረኞች ከኢትዮጵያ በስተደቡብ የሚኖሩ መሆናቸው ብቻ እናውቃለን ብለዋል፡፡

4)Cap. Owen (ሻምበል ኦወን) በኢኳቶሪያል አፍሪካ ጨካኝ ሕዝብ እስከ ጁባ ወንዝ የሚደርስ ጋላ ሕዝብ አለ፡፡ በባሕር ወደቦች ሶማሌዎች ይኖራሉ፣ ከጋላ ሕዝብ በጣም ይለያሉ፣ ጠባያቸው ለስላሳ ነው፤ ጥሩ ነው፣ እስላሞች ናቸው፣ በባሕር ወደቦች ንግድ ያካሂዳሉ፡፡ ሶልት (Salt) እና ሌሎች ፀሐፊዎች ስለ ጋላ ቋንቋ ባደረጉት ጥናት ጋሎች፣ ሶማሌዎች፣ እንዲሁም አፋሮች አንድ ትውልድ ሀረግ እንዳላቸው ያሳያል ብሏል፡፡

---

(1) A. Cecchi : ibd VII p 496



5 ፊደሪኮ ሔልወርድ (Federico Hell ward) ኦሮሞች የሰፈሩበት መሬት እስከ ትልቁ የአፍሪካ ተራራ ኪሊማንጃሮ ይደርሳል፣ እንደ ሶማሌዎች ከጥቁር አፍሪካ ሕዝብ ጋራ አይመሳሰሉም ብሏል፡፡

6 ግራፕት(Grapt) ጋላ ወደ ሰው ሀገር ሄዶ የሚሰፍር ማለት ነው ብሏል፡፡

7 ብሬነር (Brenner) በባሕር ዳርቻ ያሉ ሕዝቦች ጋላ ማለት ሃይማኖት የሌለው ሰው ያደርጓቸዋል፡፡

8 ጋሎች ራሳቸው ኦሮሞ ተብለው ይጠራሉ ትርጉሙም ኃይለኛ ጀግና ማለት ነው

9 ብሩስ (Bruce) ጋላ በመጠኑ ቀያይ ናቸው፣ ጠጉራቸው ጥቁር ረዘም ያለ ነው፣ በቆላ የሚኖሩ ግን በጣም ጥቁር ናቸው ይላል፡፡

10 ውድ (wood) ጋላ በቆዳቸው ቀለም ከሐበሾች ይጠቈራሉ፤ ከዚሁ በመነሳት Johnstone (ጆንስቶን) የተባለ ፀሐፊ የጋላ ቃል ትርጉሙ ከካላ የመጣ ጥቁር ማለት ነው ብሏል፡፡

11. ሰፌርቭር (Lefevre) ስለ ጋላ ቢያወሳም ስለ ዘራቸው ያለው ነገር የለም፡፡

12. ሃርትማን (Hartinan) ጋላ ዋና ሀገራቸው ከኪሊማንጃሮ ተራራ ስር ነው፣ ንፁሕ ጥቁር ናቸው፣ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ሰፍረዋል፣ ከበጁ፣ አገውና ሐበሾች ጋራ ተዋሕደዋል ብሏል፡፡

13 ቸኪ የራሴ ሃሳብ ብሎ የሚያጠቃልለው ጋላ ከዓረብ ሀገር ወደ አፍሪካ መጥተው የቀድሞ ነዋሪዎችን አባርረው ከማንም ዘር ሳይቀላቀሉ የሚኖሩ ናቸው፡፡

## 2. የኦሮሞ አፈ ታሪክ

14. ቸኪ የኦሮሞች አፈ ታሪክ፣ ብዙ የሀገር ሽማግሌዎች የተለያዩ ጐሣዎችን ጠይቄ ያገኘሁት ነው ብሎ እንደሚከተለው ያቀርበዋል፡፡ ኦሮሞች ሁሉ በአንድ ድምጽ "እኛ የአንድ ሽማግሌ አባት ልጆች ነን፣ እሱም ኢላው ይባላል የከነአግ ጐሣ፡፡ ሐዳር የምትባለው ሚስቱ አገባና ኢሊፋስ ወለደች፣ ኢሊፋስም ኦመር ወለደ፡፡ ለቀድሞ እናታችን /አያታችን/ ሐደር ክብር እናት ለማለት ሐዳር እንላለን፡፡ ወደዚሁ ሀገር ከመምጣታቸው በፊት አባቶቻችን ገላድ የሚባል ሀገር ይኖሩ ነበር የኦሮሞ ልጅ መሬት ስለጠበበው ከጐሣው ተለይቶ ባሕር ተሻግሮ በርበራ ገባ፣ ከበርበራም ወደ ሐረር መጣ፣ ቀጥሎም ከአርሲ አጠገብ በወላሞ ሀገር ሰፈረ፡፡ ከኦሮሞች መሐከል አንድ ትልቅ አለቃ መሐን በመሆኑ ልጅ መውለድ ስላልቻለ አንድ አማራ ሴት በሀገሩዋ ወንጀል ሰርታ፣ ወንድ ልጇዋን ይዛ ከኦሮሞች ጋራ ትኖር ስለነበረ ልጅዋን በሞጋሳ ወይንም ጉዲፈቻ ደምብ መሠረት አሳደገው፡፡ ይህ ልጅ ለመጣንባት ሀገር ማስታወሻ ስሙ ገላድ ተባለ፡፡ ከዚሁ ስም በመውሰድ አማሮች ኦሮሞችን ሁሉ ጋላ ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ ኦሮሞች ገላድ በሞጋሳ ያደገ ስለሆነ ጋላ ተብለው እንዲጠሩ አይወዱም፣ በኦሮሞ መጠራት ይመርጣሉ፡፡ አሳዳጊ አባቱ ሲሞት ገላድ ከጐሣው ተባረረና በገራኝ ጊዜ ከኡብቦ /ወላሞ/ ሀገር ወደ ሸዋ ጠረፍ ሰፈረ፡፡ ገላድ 3 ሚስቶች ነበሩት፣ ከእነሱም 4 ልጆች ወልዷል በኩር ልጁ ከአንድ ባሪያ የተወለደ ነበረ፣ ስሙም መጫ ተባለ፣ ሕገ ወጥ ማለት ነው፡፡ 2ኛ ልጁ አርሲ 3ኛ ተሉማ 4ኛ ኢቱ ተባሉ፡፡ ከበኩር ልጁ ከመጫ በቀር ሌሎች ከንፁህ ኦርሞ ሴቶች የተወለዱ ናቸው፡፡ ገላድ ሲሞት ልጆቹ በመሬት አከፋፈል ምክንያት ተጣሉ፡፡ መጫ ከአዋሽ በስተደቡብ እናሪያ በሚባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሰፈረ፡፡ በዘመኑም ኢትዮጵያ በግራኝና በቱርኮች በተከፈቱባት ጦርነቶች ተዳክማ

ስለነበረች ጫሜ የከፍለ ሀገሩ ንጉሥ ሆነ። ሜጫ ቾዌ እና ጉድሩ የሚባሉ ሁለት ልጆች ወለደ። ቾዌ 5 ልጆች ሊበን፣ ቁታይ፣ ጅማ፣ አሮ፣ አቦ የሚባሉ ወለደ። ጉድሩም 7 ልጆች ነበሩት እስካሁን ድረስ 7 የጉድሩ ጉጣዎች ተብለው ይጠራሉ።

ቸኪ ይህ የኦሮሞች አፈታሪክ እውነት መሆኑን ስላመነበት፣ በደዘብ ዐረብ የነበረው ታሪካዊ ሁኔታ በማብራራት ለኦሮሞች ወደ አፍሪካ መምጣት አመቺ ሁኔታ እንደነበረ ለማስረዳት ሞክረዋል። ኦሮሞች ወደ አፍሪካ የተሻገሩበት በግራኝ ዘመን ፖርቱጋሎች ወደ ኢትዮጵያ የመጡባቸው ዓመታት እንዳልሆነ ለማስረዳት ቀይ ባሕርን ከቱርኮች ወረራ ይጠብቁ የነበሩ ፖርቱጋሎች የኦሮሞ ፍልሰት በታሪክ ሳይመዘግቡት አያልፉም ነበር በማለት ውድቅ አድርጎታል።

## 3. የኦሮሞ መስፋፋት

ቸኪ የነበረውን ታሪክ በመ[illegible]ሉስ ዘመኑ በጣም ሩቅ እንደነበረ፣ በ200 ዓ.ም. አካባቢ እንደነበረ ጽፈዋል። ኦሮሞች በኢትዮጵያ የተስፋፉበት ዘመኑ በትክክል በ1542 ዓ.ም. አካባቢ መሆኑን ሁለት የፖርቱጋል ታሪክ ፀሐፊዎች በመጥቀስ አስቀምጧል። 1ኛ ፍራንችስኮ አልቫሬስ በ1516 የመጀመሪያዎቹ የፖርቱጋል መንግሥት መልእክተኞች አባል በመሆን ኢትዮጵያን የጎበኘ ስለ ኦሮሞች ምንም የጠቀሰው ነገር የለም። በዚሁ ዘመን ኦሮሞች ወደ መሐል ኢትዮጵያ መስፋፋት አልጀመሩም ነበር ማለት ነው። 2ኛ አባ ጀረላሞ ሎቦ በ1650 ኢትዮጵያን የጎበኘ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በወቅቱ የነበረው ሁኔታ አስተያየቱ ሲሰጥ እንዲህ በማለት ጽፈዋል። "የአማራ መንግሥት ሕዝቦች ከሁሉ የሰለጠኑና ትክክለኞች ናቸው። ከእነሱ በኋላ፣ እውነተኛ ሐበሾች የትግራይ ሕዝቦች ይመጣሉ፣ ቀጥሎም የዳሞትና የጋፋት ሕዝቦች አሉ። ሌሎች ግን ኋላ ቀር (ባርባሪያን ናቸው፤ ከእነዚህ መሐከል በዘግናኝ ጨካኝነቱ እንደ ጋሎች የታወቀ የለም። ጋሎች በኢትዮጵያ ብቅ ማለት የጀመሩ በ1542 ዓ.ም. ነበር። ዘተለያዩ ክፍላተሀገራትና መንግሥታት እየተስፋፋ፣ ባለፈበት ቦታ ሁሉ፣ ሴት ወንድ ሕፃን ሳይለዩ ፈጅቷል፣ መሬቱንም ያቃጥሉ ነበር። አባ ሎቦ እንደዚህ ብሎ በሚጽፍበት ዘመን ነው ሉዶልፍ፣ ዳመይ፣ አባ ፓይዝ (LUDOLF. D'AMEIDA, PAEZ) ኢትዮጵያ 35 መንግሥታት አሏት እያሉ የስማቸው ዝርዝር ይሰጡ የነበረ[illegible]ዛሬ ዳሞት፣ ጋፋት፣ እናሪያ ሌሎችም በኦሮሞች ስር የወደቁ መሬቶች ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ይኖሩበት የነበረ ሀገር ስሙ በሙሉ በመቀየሩ ሕዝቦችም በሙሉ ከምድረ ገጽ ጠፍቷል፣ ለናሙና አንኳን አልቀሩም።

## 4.የኦሮሞ ዘር ቋንቋ

ቸኪ የአርሲ መጫ፣ ኖኖ፣ ቦቶር፣ ሙራ፣ አጋሉ፣ ፀዳለ፣ ኦሮሞች ከአማራ፣ ከጉራጌ፣ ከሲዳማ፣ ከሻንቅላ ጋራ ያልተቀላቀሉ ንፁህ ኦሮሞች ናቸው ይላል።[1] ቸኪ ስለ ጋላ ዘር ሊያጠቃልል ከሐበሾች በመልክ ይበልጣሉ፣ ንፁህ ቆንጆ ዘር መሆኑንና እንደ ሐበሾችም ጋሎች የመጡበት ከእስያ መሆኑን በማለት ደምድሟል። የኦሮሞ ቋንቋ በሚመለከት ፈረንሣዩ

(1) A. Cecchi : ibd v.II p 479



ሀገር ጎብኚ ሳይንቲስት ደባዲ (D'ABBADIE) በ1843 ባደረገው ጥናት፣ የኦሮሞች ቋንቋ ከአማርኛ፣ ሶማሊኛ የሚቀራረብ ቋንቋ ከግእዝና ከዓረብኛ ቋንቋዎች ጋራ ግንኙነት እንዳለውና የሴሚቲክ አንድ ክፍል ንኡስ ሴሚቲክ መሆኑን ብሎ ያቀረበውን ሃሳብ በመደገፍ ቸኪ ኦሮምኛ የሴሚቲክ ቋንቋዎች አንድ ክፍል መሆኑን እንደሚያምን ገልጧል። ለዚህም አባባሉ በእሱ ጊዜ አብረው በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ፣ ከእሱ የበለጠ ችሎታ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሚሲዮኖች አቡነ ማሳያና ኪያሪኒ ስለዚሁ ጉዳይ የተናገሩት ቃል ጠቅሷል። ቸኪ ስለዚህ ጉዳይ ለአቡነ ማሳያ ላቀረበው ጥያቄ ጋላ በሚመለከት አፈታሪካቸው ከባሕር ማዶ እንደመጡ ያደርጋቸዋል፣ ቋንቋቸው ከሶማሌ ቋንቋ ጋራ ይቀራረባል። በፊሎሎጂ አሳካክ ሲታይ ኦሮምኛ ሙሉ በሙሉ እንደ አማርኛ ቋንቋ ነው። ኪያሪኒ ስለ ኦሮምኛ ቋንቋ ጉዳይ በግል ማስታወሻ ማሕደሩ እንደሚከተለው ነበረ የመዘገበው "የጋላ ቋንቋና የአማርኛ ቋንቋዎች ያላቸው ቅርርብ በጥንቃቄ በምናጠናበት ጊዜ፣ በግሥ አጠቃቀም፣ በሰዋስው ዓይነቶች፣ በተውላጠ ስሞች የአንድ እናት ቋንቋ ልጆች መሆናቸውን ያሳየናል። እነዚህ ሁለት ሕዝቦች /አማራና ኦሮሞ/ ከአንድ የጋራ ግንድ የመጡ መሆናቸውን ያሳየናል።

ከዚህ በላይ ስለ ኦሮምኛና አማርኛ ቋንቋዎች የተሰጡ አስተያየቶች መነሻ ብናደርግ፣ አሁን በሀገራችን ለትምህርት ቤቶች የተዘጋጁ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለሴሚቲክና ኩሺቲክ እየተከፈሉ የሚያስተምሩ መጻሕፍቶች ትክክለኛ መስሎ አይታዩም የሴምና የኩሽ ቋንቋዎች በፊሎሎጂ ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው።

በሌላ በኩልም ኦሮሞች ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከባሕር ማዶ ከእስያ መጥተናል ብለ[illegible]ውራትም ስሕተት ነው። ብዙ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ በዚህ መጽሐፍ አስተያየት ሰጥቻለሁ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የአፍሪካ ጥንታዊ ኗሪዎች፣ ባላባቶች፣ ስንሆን ሌሎች ጥቁር አፍሪካውያን (ኔግሮ) መጤዎች ናቸው። ምክንያቱም በአርኪዮሎጂ የተገኙ ጥንታውያን ተብለው የተገመቱ የሰው አጥንቶች የኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ተረጋግጧል። መላው አፍሪካ በኢትዮጵያውያን ተይዞ እንደነበረ እንረዳለን። ኔግሮች የተባሉ ኢትዮጵያውያንን አስለቀቁ እንጂ የተገላቢጦሽ አይደለም።

## 5. የኦሮሞ ታሪክ በኢትዮጵየውያን የቀረበ

ስለ ኦሮሞች ከላይ ከተገለጠ ታሪክም ሌላ ተብሎላቸዋል። ፍራንኬቲ (Franchetti) የተባለው ኢጣሊያዊ በደረሰው መጽሐፍ እንደገለጸው[1] ኦሮሞች በማዳጋስካር ይኖሩ ነበር፣ ቀጥሎም በኢኳቶሪያል ሐይቆች ሰፈሩ፣ ከዚሁ ተነስተውም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ባለ መጥተው ሰፈሩ። ፍራንኬቲ መረጃው ያገኘው አለቃ ታዬ ከደረሰው መጽሐፍ ሲሆን፣ አለቃ ታዬም የተጠቀመባቸው መረጃዎች ከኢትዮጵያውያን ያልታተሙ የእጅ ጽሑፎች መሆኑን ገልጧል። በዚሁ ማስረጃ መሠረት የጋላ ሕዝብ በርቱማና በረን ከሚባሉ መንድማማቾች ይወለዳሉ። በርቱማ 1. ክረዩ 2. መረቶ 3. ኢቱ 4. አኒቾ 5. ወረንሽ 6. ሐቡና የተባሉ ወለደ። ሀቡና 1. ራያ 2. አዘቦ 3. አሻንጌ የሚባሉ ልጆች ወለደ። ራያና አዘቦ ዛሬ በስማቸው በሚጠሩ መሬት ሰፍረው ይገኛሉ፤ አሻንጌ ከትግሬዎች ተቀላቅለው የአሻንጌ መሬቶች ማለት እንዳ መኮኒ፣ ወጂራት ሰፍረው ይኖራሉ። ኦሮሞች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ

(1) Raimondo Franchetti : Nella Dancalia Etiopica, p 334

የመጡበት በ937 ዓ.ም. ነበረ፣ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የተስፋፋበት ግን ብዙ ጊዜ ቆይተው በ1525 - 1542 ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ ኢትዮጵያ ከኢማም ግራኝ ጋራ ጦርነት አካሄዳ ተዳክማ ስለነበረ ኦሮሞች በሁኔታው ተጠቅመው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ገስግሰው፣ በምዕራብ በሰሜን ኢትዮጵያ በጉጃም በስማቸው የምትጠራ መሜን ያዙ፡፡ በምስራቅ ውሉንና የጁን ተቈጣጠሩ፣ ከአፋሮችና ከአበሾች መሐል ያለው መሬት ገብተው ራያና አዘቦ መሠረቱ፡፡ በዚሁ የተነሳ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች ወሎ እንደ ኦሮሞ ሀገር "ወሎ ጋላ" ብለው በመጥራት የቃላት አጠራር ለማሳመር ሲጠቀሙበት የሚታዩ፡፡ ሐቁ ግን እንኳን ወሎ፣ ወለጋም ጂማም የኦሮሞ ዘር ሳይሆኑ የኦሮሞ ቋንቋ የተስፋፋባቸው ሀገሮች ብቻ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ወሎ ግን የኦሮሞ ቋንቋም ሊስፋፋ ስላልቻለ ኦሮሞ ሊባል አይችልም፣ ጉጃምም እንዳንድ ወረዳዎች ግልጽ ባልሆነልን ምክንያት በኦሮምኛ ቃላት ቢሰየሙም ኦሮም ነው ሊባል አይችልም፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ግንኛውም ሰው ክርስቲያን ወይንም እስላም ያልሆነ ጋላ ተብሎ ይጠራ ስለነበረ በዘመኑ ሃይማኖት ያልተስፋፋባቸው ቦታዎች የሚኖሩ ሕዝቦች በጅምላ ጋላ ተባሉ፡፡ ምዕራብ ኢትዮጵያን፣ ደቡብና ምሥራቅ ሸዋ ለብዙ ዓመታት ከኢትዮጵያ ተለይተው ስለነበሩ በየቦታው የተደረገው የስም ለውጥ ለማወቅ ከአቅማችን በላይ ይሆናል፣ ወሎ ግን ከኢትዮጵያ ተለይቶ የማያውቅ፣ ብዙ የኦሮምኛ ቃላቶች እንዴት ሊመሠረቱ እንደቻሉ ለንቆቀልሽ ነው፡፡

## 6. ስለ ኦሮሞ ጥንታዊ ሀገሩና መስፋፋት ሌላ ታሪክ[1]

ስለ ኦሮሞች አመጣጥና ታሪክ ለየት ያለ ሐሳብ ያለው ሉካ ዳይ ሳቤሊ ነው፡፡ ኦሮሞች ከብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ ስንት እንደሆነ ሊገለጽ የማይቻል ምናልባት ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ ይኖሩበት የነበረ ሀገር፣ ከኤደን ባሕረ ሰላጤ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ባለው ባሰ ለሶስት ማእዘን ቦታ /ትሪያንግል/ ከባሕር ዳርቻ በሶማሌዎች፣ ከደቡብ በባንቱ ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንዲያመሩ ግፊት ተደረገባቸው፡፡ ኦሮሞች ከባንቱ የጋዳ አስተዳደር በኩሽ ዘሮች የሌለ አስተዳደር መውሰዳቸው በቁጥር አነስተኛ እንደነበሩና የባንቱ ተገዢነት እንደነበራቸው ያሳያል፡፡ በታሪክ ዘመን ጋላ የኖሩበት ሀገር ቦረና ነው፣ ዋላቡ (Walabu) በተባለው ተራራ ቡኪስ በሚጠራው ወረዳ፣ ከአቢያታ ሐይቅ (Regina Margherita) በስተምሥራቅ፤ ኦሮሞች ተዋቂ ፈረሰኞች ለመሆን የበቁት ድሮ የማያውቁት የነበረ፣ ከአማራ ተምረው ነው፡፡ ኦሮሞች ሌሎች ሕዝቦችን አጥቅተው ለመያዝ የተጠቀሙበት መሣሪያ የጋዳ አስተዳዳር ነው፡፡ ሶማሌዎች የጋዳ አስተዳደር ጦርነትን ለማካሄድ እንደ ኃይል ነው ብለውታል[2] በመሐል ባለ የሚገኙ የሸክ ሑሴን ጉማዎች እንደሚናገሩት ተረት ከሆነ ኦሮሞች ከባለጋሮቻቸው ተጣልተው በራቸው ሊጠፉ ተቃርበ ነበር፡፡ ከእልቂት ከቀሩት አንድ ሴት ከአንድ ሰይጣን ግንኙነት አድርጋ ብዙ ልጆች ልትወልድ ችላለች፡፡ እነሱም ባለን መያዝ በመቻላቸው ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገርም ለመዝመት መሠረት ፈጠረላቸው፡፡ በዚሁ የተነሳ ኢትዮጵያውያን ጋሎችን የጋኔን ልጆች ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ ሌላ ኢትዮጵያዊ የኦሮሞች ተረትም በአዋሽ ወንዝ አጠገብ ያለው ተራራ ታስሬ የነበረችው የእፄ ዘርአ ያዕቆብ ሴት ልጅ

(1) Luca Dei Sabelli : La Storia di Abissinia V II p 181
(2) Luca Dei Sabelli : ibd p 185



ከአንድ ባሪያ ያደረገችው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተገኘው ፍሬ የተወለዱ ናቸው ይላል፡፡ ኦሮሞች ከዋናው ስፈራቸው ወደ መሐል ኢትዮጵያ ሲዝቡ የያዙዋቸው መሬቶች እሁን ስማቸው የለም፡፡ በመጀመሪያ ባትራና ዋግ የሚባሉ ቦታዎች /ዋግ ሲባል የዋግ ሹም ሀገር አይደለም)፡፡ ቀጥሎም ጋሞ ከአቢያታ ወደ ምሥራቅ ከ1522 እስከ 1530 በጋዳ መልባሁ እየተመሩ ባሌን ያዙ፡፡ ከ1530 እስከ 1538 ያለው ጊዜ በጋዳ ሉባ መዳና ቢድለ የሚመሩ ዳዋሮ ፋጢጋርን ተኩጣጠሩ፡፡ ከ1554 እስከ 1562 ሉባ መስለ ጋዳ ሥልጣን ያዘ፡፡ በዳውሮ ደጎ በተባለው ቦታ በአንድ ታዋቂ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ዘንድ አዋራ የተባለው ሐመልማል የተባለው የአፄ ግላውዲዎስ የእኅት ልጅ የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ሽንፈት ገጥሞባቸው ሸሹ፡፡

የሲዳግ ሕዝቦች ሰሜናዊ ዋቢ ሸበሌ ለዘመናት በቁጥጥራቸው የነበረ፣ ሸሽተው ወደ ምዕራብ ተራራዎች አፈገፈጉ፡፡ የሸክ ሑሴን ሽኮች፣ ብዙ ሶማሌዎች ተዋጊዎች፣ ዓረቦች ሳይቀሩ ከኦሮሞች ወራሪዎች ጋራ ተቀላቀሉ፡፡ የኦሮሞች እለቃ መስለ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረስ መጠቀም ጀመረ፡፡ ከባለ ሰው ቀጥሎ የኦሮሞች ወረራ ተራ የደረሰው ሐረር ነው፡፡ የሐረር ኑር በአጼ ግላውዴዎስ ላይ ድል ተቀዳጅቶ ሲመለስ ሐዛለ በሚባለው ቦታ ከጋዳ መስለ ጋራ ጦርነት ገጥሞ አብዛኛው ወታደሮቹ ተገደሉበት፡፡ ሐረር በኦሮሞች ሽንፈት ብቻ ሳይበቃት፣ ድርቅ፣ ረሐብ፣ በሽታ ተፈራረቀባት፡፡ በበሽታ ከሞቱ መሐከል በ1568 ዓ.ም. ራሱ የሐረር ኤሚር ኑር ነበረ፡፡ ከእሱ ሞት በኋላ የሐረር እስላማዊ መንግሥት፣ ለማንሰራራት የማይችልበት ከባድ ውድቀት ደረሰበት፡፡ የሉባ መልባሀ ልጆች ከ1562 እስከ 1570 የቆዩ ጋዳ ሐርኑፋ መሠረቱ፡፡ ወረራው ወደ ጋን አንጎት (ወሎ) አመራና በቤጌምድር ተዛመተ፡፡ ሌሎች የኦሮሞች ወራሪዎች ከቈራ ተነስተው፣ ከአዋሳ በስተምዕራብ ወደ ጊቤ ግመንጫዎች አመሩ፤ እነሱም ጎምቢቹ፣ አደእ፣ መጫ የሚባሉ ጉሣዎች ነበሩ፡፡ መጫ የጉሳዎች የጋራ ቤት (መንግሥት ) የነበረው ነጥቀው ወሰዱ፡፡ ጎምቢቹ በትረ መንግሥቱ እንዲመለስላቸው ጠይቀው አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሳ በሁለቱ መሐከል ቅራኔ ተፈጥሮ መጫ በዚሁ ጊዜ ምዕራባዊ ድንበር የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ወሊጋ አመራ፡፡ በመሐል ወለጋ 3300 ሜትር ከፍታ ያለው ወለል የተባለው ተራራ ነበረ፡፡ እንደ ቦረናው ዋላቡ ወለል የእግዚአብሔራቸው መኖሪያ ጠባቂያቸው ቅዱስ ስፍራ አደረጉት፡፡ ከዚህ ቦታ ተነስተው ከአባይ ወንዝ እስከ አዋሽና እስከ ስምጥ ሸለቆ ይኖሩ የነበረ ትናንሽ የሲዳግ መንግሥታትና ሕዝቦችን በቁጥጥራቸው አውለው ፈጅተው አጠፏቸው፡፡ የአፈሉ ሲዳግ መንግሥት የግዛቱ ሰፋት ከአባይ እስከ ባሮ ወንዝ ይዘልቅ የነበረ ተቆጣጠሩት፡፡ ሜጫ ላጋማራ፣ እናሪያ ሲቆጣጠሩ፣ ጎምቢቹ ደቡባዊ ሸዋንና ታችኛው አዋሽን እስከ አፋር ያዙ፡፡ ወሎ የተባሉ በትግራይና ሸዋ መሐል የነበረው የመሬት ግንኙነትን እንዲቋረጥ አደረጉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የኦሮሞ ማስፋፋትን ሊቋቋም ያልቻለበት ምክንያት መላው ኃይሉ በሃይማኖት ንትርክ ተወጥሮ ስለነበረ ነው፡፡

## 13. የሃይማኖት ክርክሮች በኢትዮጵያ

ሌላ ኢትዮጵያ እንድትዳከም አስተዋፅኦ ያደረገው በሃይማኖት ምክንያት ይደረግ የነበረው ክርክር ነው፡፡ ፖርቱጋሎች ለኢትዮጵያ ለዘለዓለም የማይረሳ ባለውለታዎች ናቸው፣ ነገር ግን አባዛኛውን የፖርቱጋል ሚሲዮናውያን ባደረጉት የሃይማኖት ሰበካ ምክንያት በኢትዮጵያ እርስ በእርስ

የክርስትና ሃይማኖት ውስጥ አልባ ክርክር ለብዙ ዘመናት በመካሔዱ፣ ኢትዮጵያ እንድትዳከም አስተዋፅኦ አድርገዋል። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ኃላፊዎች በበርመደስ መሪነት አለመሳካት ተስፋ አልቆረጡም። በርመደስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሐኪም ሆኖ ነበር፣ አሁን አቡን ሆኖ ሲሾም በኢትዮጵያውያን ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም። በሮማ ጳጳስ በኩልም በርመደስ በቂ የሃይማኖት ትምህርት ስላልነበረው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ አድርጎ ሹመቱን ለማጽደቅ ችግር ተፈጥሮ ነበረ። የፖርቱጋል መንግሥት በበኩሉ ብዙ የተደከመበት ሥራ ከንቱ እንዳይቀር ለጳጳሱ ሚሲዮናውያን እንዲልኩ ይጎተጉት ነበር። በመጨረሻም ፓትሪያርክ ኑኔዝ የተባለው ሁለት አቡኖች ኦርቪዮዶና ካርኔሮ የተባሉ ረዳቶች እንደዚሁም 10 ቄሶች ኢየሱሳውያን ከተባሉ ገዳም ወደ ኢትዮጵያ ተመርጠው ተላኩ፣ ማርች 1556 ዓ.ም. በመጀመሪያ ምፅዋ ደረሱ። በሕንድ የፖርቱጋል ይዞታዎች ከሆኑትው ከጎዋ ከቅድሞ እንዲያውቅ ብሎ የሚሲዮናውያን መምጣት የሚያበስሩ መልእክተኞች ወደ ኢትዮጵያ ሜይ 1556 ዓ.ም. ላከ። ኢትዮጵያ ደርሰው አጼ ገላውዴዎስ በተላቅ ክብር ተቀበላቸው። ከኢትዮጵያ ያልተጠየቁ ሚሲዮናውያን መምጣታቸው ሲሰማ በኢትዮጵያ ሹማምንቶች ብዙ የተቃውሞ ድምጽ መሰማት ጀመሩ። አጼ ገላውዴዎስ ፖርቱጋሎች ድጋፍ ይሰጣቸው እንደሆን ቢጠይቋቸትም፣ ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ ሳይገልጽላቸውም ስለ ጉዳዩ አዋቂዎችን በማማከር ጊዜ ስለሚወስድ ውሳኔ ለመስጠት ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ወደ ሐገሩ የሚመጡ ሚሲዮናውያን ግን በክብር እንደሚቀበላቸው በመግለጽ ሸኝቷቸዋል።

ዋናው ፓትሪያርክ የሚሲዮናውያን ተልኮ አጠራጣሪ ሆኖ ስለታየው ምክትሉ አቡነ ኦርቪዮዶ ሁኔታውን ለማጥናት ለጊዜው ለመላክ ወሰነ። አቡነ ኦርቪዮዶ ማርች 1557 ዓ.ም. ምጽዋ ገባ፣ አጼ ገላውዴዎስ እንደተለመደው በክብር ተቀበላቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የቃልም የጽሑፍም ክርክሮች በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና በሚሲዮናውያን መካከል ይደረጉ ነበር፣ ንጉሡም ተካፋይ ይሆን ነበር። በተለይ በአባ ሮድሪገዝ የተደረሰ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክን አስቀየመው። በመጨረሻ ክርክሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እና በካቶሊክ ሃይማኖት መካከል ያለው ልዩነት መሆኑ ቀርቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥም በቡድን ተከፍለው በሃይማኖት ጉዳይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ብዙ ዓመታት የሃይማኖት ጉዳይ ከመሆን አልፎ በክፍለ ሀገር ልዩነት የፈጠረ ጦርነት የማማዘዝ ምክንያት ሆነዋል። የኢትዮጵያ ነገሥታት ሀገሪቷን ማስተዳደር፣ ዳር ድንበሯን ከጠላት በመጠበቅ ፋንታ፣ ጊዜያቸው በሃይማኖት ክርክር እንዲያሳልፉ ምክንያት ፈጠረ። የሕዝቡም የቤተክህነትም ትኩረት የሳበው ጉዳይ ስለነበረ ስለ ሀገሩ ጉዳይ ከውጭ ጠላት በመዋደቅ ፋንታ በሃይማኖት ቡድኖች መሐከል በነበረው ልዩነት ምክንያት ለብዙ ዘመናት እስከ አጼ ዮሐንስ 4ኛ. 1878 ዓ.ም ድረስ በአዲሶቹ ሚስዮናውያንም እንደ ካርድናል ማሳያ የሃይማኖት ክርክር ተቀስቅሶ ስለነበረ አሸናፊ ሳይኖረው የሃይማኖት ክርክር የፖለቲካ ክርክር በመሆን የብዙ ሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነዋል፣ ኢትዮጵያም እንድትዳከም አስተዋጽኦ ነበረው። አጼ ገላውዴዎስ ከሚሲዮናውያን ጋራ የሃይማኖት ክርክር ለመግጠም ይደሰት ነበረ። ዋናው ነጥብ የሮማ ጳጳስን ተቀብሎ ከእስክንድሪያ ቤተክርስቲያን የነበረውን ግንኙነት ማቋረጥ ነበረ። ይሄንን ለማድረግ ግን አጼ ገላውዴዎስ የሕዝቡ የማይቀር ተቃውሞ ስለሚያውቅ ለመቀበል አልደፈረም። ንጉሡ የሚሲዮናውያን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ዓላማ እ[illegible]ቸው ጥርጣሬ ነበረው። በሃይማኖት ቢከራከርም የኢትዮጵያ



ኦርቶዶክስ እምነትን በመደገፍ ሚሲዮናውያን መልስ እስከሚያጡ ድረስ ይከራከራቸው ነበር። በመጨረሻ ጊዜ አቡነ ኦርቪዮዶና አጼ ገላውዴዎስ ተገናኝተው በተነጋገሩበት ጊዜ፣ ንጉሡ ምን ጊዜም የአባቶቹ ሃይማኖት እንደማይቀይር "የገላውዴዎስ እምነት" በሚል አርእስት መግለጫ አውጥቶ ሐሳቡን ገልጸዋል። ከዚህ በኋላ በኑር ሞጃሂድ የሚመራው የሐረር መንግሥት የከፈተበትን ጦርነት ለመዋጋት ሂዶ በጦር ሜዳ በ1559 ዓ.ም. ዓርብ ስቅለት ቀን ቆስሎ ሲሞት አንገቱ ተቆርጦ ለኑር ተሰጠው። የግራኝ ሚስት የነበረች ባቲ ዲልዋንበራ በንጉሡ ሞት ተደስታ የተቆረጠው የንጉሥ አንገት በሐረር ግንብ መግቢያ በር በአንድ በረጅም ምሰሶ እንዲሰቀል አደረገች። ንጉሡ በሞተ ከሦስት ቀን በኋላ አሽከሮቹ በአንድ ቤተክርስቲያን ወስደው ቀበሩት። ከሞቱት ዓመት በኋላም ተሰቅሎ ይገኝ የነበረ አጥንቱም ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ነጋዴዎች ወደ አንጾኪያ የይፋት ዋና ከተማ ወስደው ስለቀበሩት ምእመናን እንደ ሰማእት አጥንት ያከብሩታል።

## 14. አጼ መላክ ሰገድ

ከአጼ ገላውዴዎስና ከአጼ ሚናስ ቀጥሎ በኢትዮጵያ የነገሠ አጼ መላክ ሰገድ ነው። የሀገር አንድነትን ለማስከበር ካደረጋቸው ዘመቻዎች የኦሮሞ ወደፊት መግፋት በመግታት የሲዳማ ሕዝቦችን ማጠናከር በሚል ዓላማ ተነሳስቶ በእናሪያ ያደረገው ዘመቻ በተለይ የሚጠቀስ ነው። ከሲዳማ መንግሥታት ከሁሉም ታዋቂነት የነበረው እናሪያ ነበር። በዘመኑ የእናሪያ ንጉሥ ስርኒሂ በሲዳማ ሲፒንሃዎ የሚባል ነበረ፣ ዋና ከተማው ቼሪኮ ይባላል። በ1567 ዓ.ም. መላክ ሰገድ ዳሞት ደርሶ ገብሩን ይዞ እንዲመጣ ለእናሪያ ንጉሥ አንድ መልእክተኛ ላከበት። የእናሪያ ንጉሥም ትዕዛዙን ተቀብሎ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ብዛት ያለው ወርቅ ይዞ ለመላክ ሰገድ አስረከበ። በእናሪያ ንጉሥ እየተረዳ አጼ መላክ ሰገድ ከእናሪያ በስተምሥራቅ ቦሻ የተባለው አነስተኛ መንግሥት ተዋግቶ ይዞ አስገበረው። በዚሁ ዓ.ም. ንግሥት ሰብለወንጌል የ4 ነገሥታት ዘመን መንግሥት በምክርዋ እየረዳች ያሳለፈች ዐረፈች። በ1570 ዓ.ም. አጼ መላክ ሰገድ ከሸዋ ተነስቶ ዘምቶ ዘዲያና ጉራጌን አስገበረ። ኦሮሞዎች ጎጃምንና ዳሞትን በአገኘው ድል በመጠቀም ከዚህ በፊት በሲዳማ መንግሥትን በማጠናከር የነበረው ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ለሁለተኛ ጊዜ በ1586 ዓ.ም. ወደ እናሪያ ዘመተ። ከሲዳማ ሕዝቦች ጋራ መቀራረብ ሊፈጠር የሚችለው በሃይማኖት መሆኑ ስላመነበት በዳንቼዩ የተባለው የቀድሞ የእናሪያ ንጉሥ ልጅ የእናሪያ ንጉሥ ሆኖ ስለነበረ የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበል በማስረዳት ስለተሳካለት አጼ መላክ ሰገድ እናሪያ ለመንግሥት የምትከፍለው ግብር በግማሽ እንዲቀንስ አደረገ። ቄሶች የክርስትና ሃይማኖት እንዲሰብኩ ተላኩ። ባዳንቼዩ ቤተሰቦቹና ሹማምንቶቹን ሰብስቦ የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበሉ አደረገ። ሕዝቡም ትልቅ ስብሰባ አድርጎ የንጉሡ ውሳኔ ተቀብሎ አጸደቀ። ከዚህ በኋላ አጼ መላክሰገድ የክርስትና ማንሳት ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸም አደረገ። አጼ መላክ ሰገድ ለባንቼዩ የክርስትና አባት በመሆን ክርስትና ስሙን በራሱ ልጅ ስም ዘማርያም ብሎ በመቀየሩ መንፈሳዊ ልጅ አደረገው፣ ውድ ስጦታዎችም አበረከተለት። የአጼ መላክ ሰገድ ምሳሌን በመከተል ሌሎች ሹማምንቶችም ስጦታ እያበረከቱ የክርስትና አባት እየሆኑ የእናሪያ ሹማምንቶች እንዲጠመቁ አደረጉ። በዚሁ መሠረት በሲዳማና በአማራ ባለስልጣናት መሀከል መንፈሳዊ ዝምድና ተፈጠረ፣ ቤተክሕነትም ሕዝቡን ክርስትና ማንሳት ቀጠለ። አጼ

መላክ ሰገድ የክርስትና ማንፃት አከባበር ሥነ ሥርዓት ምክንያት በማድረግ ለሕዝቡ ትልቅ ግብዣ በማድረግ ሕዝቡን ምሳ አብልቷል፡፡ የበዓሉ አከባበር እንደተፈጸመ አጼ መላክ ሰገድ የክርስትና በዓላት ቀኖችና የክርስትና ሕግጋት አውጆ፤ ቀሶችና ዲያቆናት በስፍራው እንዲቀመጡ አዘዘ፣ በዳንቺዩ በየመንደሩ ቤተክርስቲያናት እንደሚሰሩ በአጼ መላክ ሰገድ ፊት ቃል ገባ፡፡ የዚሁ ጊዜ ማስታወሻ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በታቦቱ ድንጋይ ላይ በሀ በሚባለው ቦታ አንድ ጽሑፍ ተቀርጾ ይገኛል፡፡

ተመሣሣይ ሥነ ሥርዓቶች በጎረቤት መንግሥት በቦሻ ተፈጽሟል፡፡ ለቦሻ ንጉሥ መላክ ሰገድ የክርስትና አባት ሆነዋል፡፡ ቀኑም የቅዱስ ጊዮርጊስ ቀን ስለነበረ የቦሻ ንጉሥ የክርስትና ስም ጊዮርጊስ ሆነ፡፡ የሲዳማ ሕዝቦች በአፈ ታሪካቸው የዚሁ ክንውን ያስተውሱታል፡፡ ስዚህም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጡት ለእናሪያ ንጉሥ ለሸፒናዎ ነው፡፡ እሱም በእንደራቻ አጠገብ ቦኒቻ ወንዝ ድልድይ በአንድ ቀን እንደተሰራ ይተረክለታል፡፡ የሲዳማ ግጠናከር እናሪያ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ የኦሮሞ ወረራ ተከላከሏል፡፡ ይህ የአጼ መላክ ሰገድ ሥራ ከስራቸው ቋሚ ስከታማ ስራዎች አንዱ ተብሎ ተመሥክሮለታል፡፡ አጼ መላክ ሰገድ 1597 ዓ.ም. በዳሞትና በግቤ የኦሮሞዎች ወረራ ለመከላከል ዘምቶ በተቅማጥ በሽታ ዐረፈ፡፡

## 15. የአጼ መላክ ሰገድ ተከታዮች

አጼ መላክ ሰገድ ሦስት ሴት ልጆችና ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩት፡፡ ትልቁ ልጅ ያዕቆብ የ7 ዓመት እድሜ ነበረ፡፡ አጼ መላክ ሰገድ ዘውድ እንዲወርስ የተናዘዘው ከልጆቹ አንዱ ሳይሆን የወንድሙ ልጅ የሆነው ለዘድንግል ነበረ፡፡ በቤተመንግሥት የነበሩ ሰዎች ግን ዘድንግልን ከስልጣን በማውረድና በጣና ሐይቅ ደሴት በማሰር በምትኩ የንጉሡ ልጅ ያዕቆብን አነገሡ፡፡ ዘድንግል ግን ወዲያውኑ ከእስር ቤት አምልጦ በየበረሀው ይኖር ጀመረ፡፡ ለዘውድ ተቀናቃኝ ዘድንግል ብቻ አልነበረም፤ ከእሱ የበለጠ ተቀናቃኝ ሱሲኒዮስ የልብነ ድንግል የወንድም ልጅ ነበረ፡፡ እሱም በቤተመንግሥት እንዲታሰር የሚፈለግ መሆኑን ሲያውቅ ወደ ኦሮሞዎች በመጠጋት ተደብቆ ይኖር ነበረ፡፡ የመላክ ሰገድ ሚስት ንግሥት ማርያም ሰና የአጼ ያዕቆብ አጋርና ጠባቂ እንዲሆን በመንግሥት ባለሥልጣኖች ከሁሉም ኃይለኛ የሆነውን ዘሥላሴ የተባለውን ከያዕቆብ ጐን አስቀመጡለት፡፡ ዘሥላሴ የደንቢያ ሀገረ ገዥ ነበረ፤ ትውልዱ ግን ጉራጌ ነበረ፤ በችሎታው ወደ ከፍተኛ ሥልጣን ደረጃ ደርሶ ነበረ፤ አካለ መጠን ያልደረሰ ንጉሥ ጠባቂ በመሆኑም የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ገብቶ ነበር፡፡ በ1603 ዓ.ም. አጼ ያዕቆብ ልጅ እንዳልሆነ ለማሳየትና ከሞግዚትነት ለመላቀቅ ዘሥላሴን ወደ እናሪያ የቁም እስር ላከው፡፡ ይህ ድፍረት የተሞላበት እርምጃ የቤተመንግሥት ሰዎችንም አስደነገጠ፤ ለያዕቆብ የሥልጣን ተቀናቃኝ እንዲሆን ዘድንግል ካለበት እንዲፈለግ ተደረገ፤ ሠራዊቱም ስላመጸበት ያዕቆብ ወደ ሰሜን ተራራዎች ሸሽቶ ለመደበቅ ሲሞክር ተይዞ ለአዲሱ ንጉሥ ዘድንግል ተሰጠ፡፡ ዘድንግል ሊነግሥ የቻለው በዘሥላሴ ብርታት ቢሆንም እሱም እንደ ያዕቆብ የዘሥላሴ የበላይነት ስለማይቀበል ከሥልጣኑ ሊያወርደው ቢሞክርም አልቻለም፡፡ ዘሥላሴ የቤተክህነት ድጋፍ ሲያገኝ ዘድንግል ግን በፖርቱጋል ካቶሊኮች ይተማመን ነበር፡፡ በወቅቱ የፖርቱጋል ሚስዮናውያን ኃላፊ የነበረ በችሎታው በትምህርቱ ብስለት በፊት ከነበሩት የተሻለ ሰው የተባለለት አባ ፓየዝ ነበረ፡፡ በፓየዝ አማካኝነት ዘድንግል እንደ ቀድሞዎች



ነገሥታት እንደ ልብነድንግልና ግላውዴዎስ ለሮማ ጳጳስና ለእስፓኝ ንጉሥ እርዳታ በመጠየቅ ደብዳቤ ጽፎ ነበር፡፡ አጼ ዘድንግል በይፋ ካቶሊኮችን ከመደገፉ በላይ በሮማዊ ሥነ ሥርዓት እሱ ባለበት ቅዳሴ እንዲቀደስ አዘዘ፡፡ የበዓላቶች አከባበርም አሻሻለ፡፡ በዚሁ ጊዜ ዘሥላሴ ተቃወመ፤ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክም አቡነ ጴጥሮስ በዘድንግል ላይ ውግዘት አሰሙ፡፡ ዘሥላሴ በመጀመሪያ ጎጃም ከጎኑ በማሳለፍ በንጉሡ ላይ እንዲያምፅ አነሳሳ፣ የንጉሡ ሠራዊትም እየከዳ ከእሱ ጐን እንዲሰለፍ አደረገ፡፡ በሁለቱ ሰዎች የተደረገው ጦርነት ዘድንግል ተሸንፎ ተገደለ ዘሥላሴ ሥልጣን ቢይዝም ዘውድ መጫን አልፈለገም፡፡ አሁን ተወናይ ለመሆን የሱሲኒዮስ ተራ ደረሰ፡፡ ዘድንግል ሲገደል ተቀናቃኞች ሁለት ብቻ ቀሩ፤ ሱሲኒዮስና ያዕቆብ፤ ሦስተኛው ዘሥላሴ ነበር፡፡

ሱሲኒዮስ አደገኛ ተቀናቃኝ ስለነበረ ዘሥላሴ ያዕቆብን ከተጋዘበት ከእናሪያ በመልዕክተኞች ተፈልጎ እንዲመጣና ዘውድ እንዲጭን ለማድረግ ሞክሮ ነበር፡፡ ሱሲኒዮስ በፍጥነት በመቅደም እሱ ንጉሥ መሆኑን እንዲያውቁለት ጠየቀው፡፡ ዘሥላሴም ያዕቆብ እስኪመጣ መዘግየት መረጠ፡፡ ሲስኒዮስ ሲያጋፍጠው ግን ለውጊያ ተዘጋጀ፡፡ የዘሥላሴ ወታደሮች እየከዱት ስለመጡ ለሱሲኒዮስ ለመታዘዝ ወሰነ፡፡ በዚሁ ጊዜ ግን ያዕቆብ ደንቢያ መድረሱን ወሬ ተሰማ፡፡ ዘሥላሴ አቋሙን በመቀየር ከያዕቆብ ጋራ ገጠመ፡፡ በ1606 ዓ.ም. እንደገና ያዕቆብ ንጉሥ ነገሥት ሆኖ ተሰየመ፡፡ ዘሥላሴ እንደቀድሞው በያዕቆብ ላይ በሥልጣን የበላይነቱ ማሳየት ይፈልግ ነበረ፡፡ በያዕቆብና በዘሥላሴ ጠብ በመጠቀም ሱሲኒዮስ የሥላሴን ጦር በድንገት ወሮ ዘሥላሴ ሲያመልጥ ጦሩ ግን ተደመሰሰ፡፡ በዚሁ ጊዜ ያዕቆብ ዘሥላሴን ታዛዥ ሊያደርገው ቢሞክርም ራሱ ለዘውድ ባበቃው ልጅ የበታች ሆኖ ከማገልገል ኃይል ካለው ከሱስኒዮ ጋራ መቀላቀል መረጠ፡፡ ያዕቆብና ሱሲኒዮስ ለጥቂት ጊዜ ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ሱሲኒዮስ ማጥቃት ጀምሮ ያዕቆብ ወዲያውኑ ተገደለ፤ ሠራዊቱ ግን በአቡነ ጴጥሮስ ቡራኬ የተወገዘውን ንጉሥ ሱሲኒዮስን እንዲዋጉ ተገፋፍተው ጦርነቱ ቀጠሉ፡፡ በሱሲኒዮስ ሠራዊት ውስጥ ይዋጋ የነበረው አንድ ሙስሊም የአቡነ ጴጥሮስ አንገት ቆርጦ ጣለው፡፡ በዚሁ ጊዜ የያዕቆብ ወታደሮች ሽሽት ጀመሩ፡፡ ከሁለቱ የአጼ ያዕቆብ ልጆች ግላውዴዎስ የተባለው በሱሲኒዮስ እጅ ተገደለ፡፡

2ኛው ጸጋ ክርስቶስ የተባለው የያዕቆብ ልጅ አምልጦ ወደ ሰናር ሱዳን ገባ ከዚያም ካይሮ ገባ፡፡

ስለ ጸጋ ክርስቶስ የአጼ ያዕቆብ ልጅ አልበርቶ [1] ፖሌራ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ፈረንሳይ በገር እስከሞተ ድረስ አጭር የሕይወት ታሪኩን ጽፈዋል፡፡ ጸጋ ክርስቶስ በመጀመሪያ የቀረበው ወደ ቬነስያ ቆንሲል በካይሮ ማንነቱን በመግለፅ የሕክምና እርዳታ በመጠየቅ ነበር፡፡ ሱዳን እንደደረሰ ሃይማኖት የሌለው የሀገሩ ንጉሥ ልጅ እንዲያገባ ተጠይቆ ስላልፈቀደ ንብረቱን ስለተዘረፈ እርዳታ አግኝቶ የአባቱ ዘውድ ለማስመለስ የነበረውን ፍላጎት ለሚሂላት ወደ ግብፅ ተሰዶ መጣ፡፡ እንደ አጋጣሚ በካይሮ ከቬነሲያ ቆንሲል ጋራ አንድ የቅዱስ ፋራንቼስኮ ገዳም ኃላፊ አባ ጳውሎስ የሉዲ ይገኝ ነበር፡፡ ገዳሙ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ ሚስዮናውያን ለመላክ ፍላጎት ስለነበረው ፀጋ ክርስቶስ ይጠቅመናል በማለት ወደ ገዳሙ ግረፍያ እንዲያገኝ አደረገ፡፡ ቁርኮች እንዳይሸጡት ወይንም እንዳይገድሉት ማንነቱ ሳይገልፅ ተደብቆ እንዲቀመጥ አደረገው፡፡ የተባለው አደጋ

[1] Alberto Pollero : Storie leggande e favole paese dei Negus XXV p 223

የሚያጋጥም ቢሆንም ቄሱ ግን ሁኔታውን አጋና ለፀጋ ክርስቶስ የነገረው ሌሎች የካቶሊክ ሚስዮናውያን ወይም የፕሮቴስታንቶች ከእሱ ነጥቀው እንዳይጠቀሙበት በመፍራት ነበር፡፡ ፀጋ ክርስቶስ በቂ ስንቅ ሳይሰጠው በቀጥታ ወደ ጣሊያን ሀገር እንዲሄድ የቀረበለትን ሐሳብ ካለደረሰው ብዙ ችግር በተአምር ያሳለፈው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ዘዉድ እንዲጭን እግዚአብሔር እንዲረዳው ለመለመን ኢየሩሳሌም ሔዶ በመሳለም ምስጋና ሳያቀርብ ወደ ጣሊያን ሀገር ለመሄድ እንደማይፈልግ ለአባ ጳውሎስ ሐሳቡን ገለጸለት፡፡ አባ ጳውሎስ ከሐሳቡ ሊያግደው ስላልቻለ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ለራሱ ገዳም ከአደራ ደብዳቤ ጋራ ሸኘው፡፡ ፀጋ ክርስቶስ 15 ሰዎች አስከትሎ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለ፡፡ ነገር ግን ለ15 ሰዎች የሚሸፍን ወጪ ስላልተሰጠው ከተከታዮቹ አንዳንዶቹ በመያዣ ተይዘው ለቁርኮች እንዲሸጡ ተደረገ፡፡ አንዳንዶቹም ራሳቸውን ችለው ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዙ፡፡ ከእሱ ጋራ ኢየሩሳሌም የደረሱ ሶስት ብቻ ነበሩ፡፡ ለአባ ጳውሎስ ጸጋ ክርስቶስ እውነተኛ የንጉሥ ልጅ አይደለም የሚል ወሬ ፡ከደረሰው ኢየሩሳሌም ለሚገኙ ማሕበሩም አካፍሏቸው ለፀጋ ክርስቶስ ይኼንን አስመልክተው ቢገልፁለት በጣም ተናዶ በኢየሩሰሌም የሚገኙት የግሪክ ወይም የአርመን ኦርቶዶክስ በእንግድነት ሊቀበሉት እንደሚችሉ ገልፀውለት እንደነበረ ሲነግራቸው ጥርጣሬያቸውን ትተው እንክክቤ ማድረግ ቀጠሉ፡

ፍራንቸስካውያን እና ኢየሱሳውያን የሚባሉ ገዳማት በኢትዮጵ.' ማን ሚስዮናውያ፣ ይላክ በሚል ውድድር ስለነበራቸው የጸጋ ክርስቶስን ስም ማጥፋት ከዚሁ የመነጨ ነበረ፡፡ ጥርጣሬ ቢኖራቸውም ፀጋ ክርስቶስን ከመደገፍ ሳያቋርጡ በኢየሩሳሌም የካቶሊክ ሃይማኖት እንደሚቀበል ፤ይፋ ከገለጹለት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ጠቃሚ መሣሪያ እንዲሆናቸው ወደ ሮማ ላኩት፡፡ የሮማ ጳጳስ ግን ማንነቱ አጣራጣሪ ስለነበረ ተቀብለው አላነጋገሩትም፡፡ የፀጋ ክርስቶስ ጥያቄ ጥርት ያለ ነበረ፤ ይኸውም የተነጠቀውን ዘውድ ለማግኘት ከኤውሮጳ ክርስቲያን መንግሥታት ወታደራዊና የጦር መሣሪያ እርዳታ ይፈልግ ነበር፡፡ የሮማ ጳጳስ መንግሥት በጥርጣሬ እንደሚያየው ስላወቀ ከቬኔስያ አንባሳደርና ከፈረንሳይ አንባሳደር ግንኙነት ማድረግ ጀመረ፡፡ በተለይ የፈረንሳይ አንባሳደር ወደ ፈረንሳይ ሀገር እንዲመጣ ጋበዘው፡፡ ወደ ፈረንሳይ ሀገር ለመሄድ ግን ገንዘብ አጠረው፡፡ ከቄሶች ጋር ለመኖርም ስለሰለቸው ከእንግሊዝና ሆላንድ ሰዎች ጋራ ተገናኝቶ ተነጋገረ፡፡ የፀጋ ክርስቶስ ከፕሮቴስታንት ሰዎች ጋራ መሆን ወደ ኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት እንዳይገባ የካቶሊክ ሃይማኖት መሪዎች ስላሰጋቸው ጣሊያንን ለማስነብኘት በሚል ሰበብ በቄሶች ጥበቃ ስር ሆኖ ከሮም እንዲወጣ ተደርጎ ቄሶቹም የመንገሥ ያለው ሃሳብ ቀይሮ ከፍራንቼስካውያን ቄሶች ጋራ ሆኖ በአንድ የቶስካና መንግሥት ወይንም የፈረንሳይ መንግሥት ወይንም የእስፔን መርከብ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ እንዲያግባቡት መመሪያ ተሰጣቸው፡፡ በዚህ መሠረት ወደ ቬነሲያ ተላከ፡፡ ነገር ግን የተፈለገውን እርዳታ አላገኘም፡፡ ከዚህ በኋላ ከተመደቡለት አራት መነኩሴዎች /ቄሶች/ እየተከታተሉት፤ የቄስ ልብስ ለብሶ ወደ ማንቶቫ፤ ፓርማ፣ ፒያቼንሳ ሔደ ነገር ግን ታሞ በገዳሙ ቦታ ተሰጥቶት ተቀመጠ፡፡ ሕመሙ እንደተሻለው በገዳሙ ውስጥ ረብሻ ስላስነሳ የገዳሙ አለቃ እንዲወጣ አደረገው፡፡ ከዚያ በኋላ ከ4ቱ ሞነክሴዎች ጋራ ሆኖ ወደ ቶሪኖ ተወሰደ፡፡ የመንግሥቱ መሥፍን በክብር ቢቀበለውም አራቱ ሞነክሴዎች ግን ከእንግሊዝና ሆላንድ ፕሮቴስታንቶች ጋራ እንዳይገናኝ ጥንቃቄ ያደርጉለት ነበር፡፡ ከፖርቱጋል አምባሲ ነገረ ፈጅም ተገናኝቶ ከፕሮቴስታንት ወኪሎች ከመገናኘት ከሌሎች



ካቶሊክ እምነት ያላቸው ሀገሮች ሰዎች ጋራ ተገናኝቶ ፖርቱጋልም ጭምር ፍላጎቱ ለሟሟላት እንደሚችል ተነገረው፡፡ ቶሪኖ ትንሽ ተስፋ በማግኘቱ አንድ ዓመት ተቀመጠ፡፡ ከዚያ በኋላ አንደኛው መነኩሴው ሁኔታውን አይቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ የቀሩት ሦስት መነኩሴዎች ግን እየተከታተሉት በቂ መተዳደሪያ ደሞዝ ተመድቦለት ወደ ፈረንሳይ ሀገር አመራ፡፡

በዚሁ ዘመን ሱሲንዩስ ከሥልጣን እንደወረደ ፋሲል ደስ ካቶሊኮችን የሚቃወም ንጉሥ በሥልጣን እንደወጣ ዜና ተሰማ፡፡ የፀጋ ክርስቶስ ጸባይም እየተቀየረ ሔደ፡፡ ቀድሞ ከነሱ ያሉት መነኩሴዎች ታዛዥ የነበረ የሚያደርጉበት ቁጥጥር እና የሚሰጡት መንፈሳዊ ምክር እየሰለቸው መጣ፡፡ ይህ በመሆኑ ሊዮን እንደገባ በድንገት ሚያ 1685 ቄሶችን አስናበታቸው፡፡ አንዱ ቄስ ምናልባት ሃሳቡን ይቀይር ይሆናል በማለት እስከ ፓሪስ ተከትሎት ሔደ፡፡ ነገር ግን የተደረገለት አቀባበል ከፍተኛ ስለነበረ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ እንደማይመለስ ስለተረዳ እሱም መከታተሉን አቋርጦ ወደ ጣሊያን ሀገር ተመለሰ፡፡ ከርዲናል ሪሺሊዮ ከፍተኛ ደሞዝ በመመደብ በታላቅ ክብር ተቀበለው፡ ንጉሥ ሉዊ 13ኛው ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም ንግሥቲቱ ግን ደጋፊ ነበረች፡፡ በፓሪስ በሐብት፤ በክብር ሲኖር ያሳለፋቸው የችግር ዓመታትና የንጉሥ ልጅ መሆኑን በሰፊው ሲወራ በከተማው ነዋሪ ሕዝብ ዘንድ እድናቆትና የመዋዋያ እርእስት ሆኖ ከኖረ በኋላ በ1638 ዓ.ም. ዐረፈ፡፡ ሩየል በሚባል ከተማ በካርዲናል ሪሺሊዮ ሕንፃ ውስጥ በአቅራቢያው የነበረ ቤተክርስቲያን ተቀበረ፡፡ ከጥንት ጀምሮ እንደ ዛሬ ጣሊያኖች እንደማይስማሙን፤ባንፃሩም ፈረንሣዮች እንግሊዞችና ፖርቱጋሎች እንደሚቀራረቡን ከዚህ በላይ የተጠቀሰ ታሪክ ጉልህ መረጃ ነው፡፡

## 16. አጼ ሱስኒዮስ

በ1607 ሱሲኒዮስ ነገሰ፡፡ ሱሲኒዮስ ብዙ ሚስቶች ነበሩት፡፡ ንግሥት የሆነችው ግን አሮሞ ነበረች (ወልደ ሰዓላ)፡፡ ሱሲኒዮስ የቤተክሕነት ድጋፍ አልነበረውም፡፡ እንደ ቀደምት ነገሥታት ወደ ሮማ ጳጳስ ጳውሎስ 5ኛና ወደ ስፔን ንጉሥ ፊሊጶስ 3ኛ አሮሞዎችን መቋቋም እንዲችል ወታደራዊ እርዳታ በመጠየቅ በ1607 ዓ.ም. ደብዳቤ ላከ፡፡ ከአሮሞዎች ሌላ ሱሲኒዮስን የሚያስጉ ሌሎችም ነበሩ፤ ከእነሱ ውስጥም ዘሥላሴ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ዘሥላሴ ወጥቶ ስክሮ ስለነበረ ሁለት ነገሥታት ዘድንግልና ያሰቆብን ከዙፋናቸው ማውረዱን እና ሦስተኛውንም ለማውረድ ብዙ ጊዜ እንደማይወስድበት ብሎ ስለተናገረ ሱሲኒዮስ ወሬውን ሰምቶ በአንድ አምባ በግዞት እንዲቀመጥ አደረገው፡፡ ዘሥላሴ ግን እምልጦ ጎጃም ገብቶ ሽፍቶ ይሸፍር ነበር፡፡ አሮሞዎች ደፈጣ አድርገው አንገቱን ቆርጠው ለሱሲኒዮስ ሲሰጡ በቤተመንግሥት ደጃፍ ተሰቅሎ እንዲቀመጥ አድርጉ ነበረ፡፡ ሱሲኒዮስ አብዛኛው ጊዜ በአሮሞች ላይ ጦርነት ከማድረግ ያረፈበት ጊዜ የለም፡ ሙሉ ተስፋ የነበረው በውጭ እርዳታ ነበር፡፡ ለእስፓኝ ንጉሥና ለሮማ ጳጳስ የላከቸው ደብዳቤዎች በ1609 ዓ.ም. መልስ አግኝተው ነበር፡፡ ነገር ግን የሱሲኒዮስ ወንድም እንደሚያስበው 1000 ወታደር መላክ በቀላሉ የሚገኝ አልሆነም፡፡ እነሱም ያለፈ የልብነድንግል ጊዜ የተደረገ ሙከራ ትምህርት ሳይሰጣቸው አልቀረም፡፡

ስለዚህ ስምምነቱ በተግባር የሚውልበት በመመካከር አባ ፋርዲናደዝና አንድ ኢትዮጵያዊው ፍቅር እግዚእ የተባለ ወደ ሮማ እንዲላኩ ተወሰነ፡፡ ምፅዋና ዘይላ በቱርክ የተያዙ ስለሆነ በፖርቱጋል ቁጥጥር ስር የሚገኘው ወደብ ለመፈለግ በጉጃም እናሪያ፣ ጃንጃሮ፣ ከንባታ፣ አሞ በኩል

ወደ ሕንድ ውቅያኖስ በልቀው እንዲሄዱ ታቀደ። ወደዚያው ሲያመሩ አላሳ በደረሱ የአላሳ ንጉሥ ለ9 ዓመት አሰራቸው። ይህ ሲሆን ግን እርስ በእርስ ጦርነትም አላቆመም ነበር። ከሁሉ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ፓትሪያርኩ በአቡነ ስምኦን መሪነትና ከአባ ዲዮስቆሮስ የተላኩ አክራሪ ተሳውስት የተቀሰቀሰው የሃይማኖት ነክ ጦርነት ነበረ።

የአጼ ሱስንዮስ ካቶሊክ መሆን የአደባባይ ሚስጢር ሆኖ ነበር። የንጉሡ ወንድም ስእለክርስቶስ በይፋ ካቶሊክ ሆኖ ነበረ። የሃይማኖት ክርክሮች ተፋፍመው ነበረ። አደባባይ ወጥቶ ስለ ሃይማኖት መከራከር መንሻ የሆነው ከንጉሡ የወጣ አዋጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕሪይ እንዳለው ለማመን የሚያስገድድ ሕግ ነበረ፤ ይኸውም የካቶሊክ ሃይማኖት ለመቀበል የሚያስገድድ ነበረ። ምክንያቱም ሁለቱ ሃይማኖቶች የሚለያዩበት ዋንኛው ነጥብ ይኸው ነበረ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ አሸናፊ የሌለው በቤተክህነትም በሕዝቡም የሃይማኖት ክርክር በመን ተጀመረ። አጼ ሱስንዮስ ሁልጊዜ ጦርነት እንደገጠመና እንዳሸነፈ ነበረ። በሕዝቡ ዘንድ ግን እንደ ከዳተኛ፣ የሚሲዮናውያን መሳሪያ ተቆጥሯል። የሱስንዮስ ጠላቶች ከቤተክህነት ሌላ የራሱ ቤተሰብ ነበሩ። ከተቃወመት መካከል ዋና ዋናዎቹ 1. ራሱ ልጁ ፋሲለደስ 2. በ1616 ዓ.ም. የአፄ ሱስንዮስ የልጅ ባል የሰሜን ሀገረ ገዥ ዘዮሊዮስ የተመራው ሀመፅ በአቡነ ስምኦንና በአባ ዲዮስቆሮስ የሚመራ የአክራሪ ካህናት ወደ ዋግ ተዘምቶ በንጉሡ ወንድም የማነ ክርስቶስ ድጋፍ አግኝቶ በዓሰዳ በተደረገው ጦርነት አቡነ ስምኦን አባ ዲዮስቆሮስ የቄሶቹ መሪና ዩልዮስ ሲገደሉ የማነ ክርስቶስ ወደ አንድ አምባ ተወሰደ። 2ኛ ፓትሪያርክ ነው በዚሁ ዓይነት የተገደሉ። 3ኛ በ1620 ዓ.ም. የቀድሞው የበጌምድር ሀገረ ገዥ ሸፍቶ በጋሎች ተገደለ 4ኛ በ1627 ዓ.ም. በመልክአ ክርስቶስ መሪነት በላስታ ሀመፅ ተቀስቅሶ በተክለጊዮርጊስ መሪነት የወ/ሮ ወንጌላዊት ባል የአፄ ሱስንዮስ ልጅ መሪነት ወደ ትግራይ ተዛመተ፣ በበጌምድር በልእክ ማርያም መሪነት ተዛመተ፣ እንዲሁም በጐጃም በሠርፀ ክርስቶስ መሪነት ሀመፅ ተቀስቀሰ። ሁሉም ሲገደሉ መልክአ ክርስቶስ ግን በአፄ ሱስንዮስ ድል ተቀዳጅቶ ነበረ ዳሩ ግን በትግራዩ ፀጋ ክርስቶስ ረዳትነት አፄ ሱስንዮስ ከሞት ሲድን ችሏል።

የአፄ ሱስንዮስ ታማኝ ከነበሬ መንድሙ ሳሕለክርስቶስ በይፋ የካቶሊክ ሃይማኖት ተቀብሎ የነበረ፣ እንዲሁም በላስታ በተካሄደው ጦርነት የትግራዩ ሀገረ ገዥ ቅባ ክርስቶስ ከንጉሡ ጐን ተሰልፎ ተዋግቶ ንጉሡን ከሽንፈት ያዳን ይገኙባቸዋል። በጥር 1617 ዓ.ም. ሱስንዮስ ጦርነት የገጠመው ከአባይ እስከ እናሪያ ሰፍረው ከነበሩ ኦሮሞዎች ጋር ነበረ። የሃይማኖት ጦርነትም አላቋረጠም ነበር፣ በመጀመሪያ የተመረጠው የደፈጣ ውጊያ ነበረ፣ በመጨረሻ ግን መላው ኢትዮጵያ ተካፋይ የሆነበት ጦርነት 400 ቀሳውስት ተካፋይ የሆኑበት በ1620 ዓ.ም. ተካሄደ አሁንም ሱሲኒዮስ አሸናፊ ሆነ። ሱሲኒዮስ ጦርነቱ ጋብ ባለበት ጊዜ በመጠቀም ለአባ ፓየዝ የካቶሊክ ሃይማኖት በይፋ የተቀበለ መሆኑን ለሕዝብ ለመግለፅ ሐሳብ እንዳለው ገለፀለት። በዚህ መሠረት ልጆቹ ማርቆስና ፋሲሊደስ፣ ወንድሙ ስእለክርስቶስ፣ እንዲሁም ሹማምቶቹን አስከትሎ ወደ አክሱም ሄዶ በአባ ፓየዝ ፊት ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት እደወጣ ገለጠ፣ የቤተክርስቲያን አለቃ የሮማ ጳጳስ እንደሆነ፤ በክርስቶስ ሁለት ባሕሪያት እንዳሉ የሚያምን መሆኑን መግለጫ አወጣ። የኢትዮጵያ ፓትሪያርኮች 1ኛ. አቡነ ማርቆስ 2ኛ. አቡነ ክርስተዱሉ 3ኛ. አቡነ ጴጥሮስ 4. አቡነ ስምኦን በልዩ ልዩ ወንጀል



እየተከሰሱ ታስሩ። ከሱሲኒዮስ መግለጫ ትንሽ ጊዜ በኋላ ሚያ 1622 ዓ.ም. አባ ፓየዝ ዐረፈ በጎርጎራ የሚሲዮናውያን ቤት።

አዲስ በኢትዮጵያ የተሾመ ካቶሊክ ፓትሪያርክ በ1626 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ገብቶ ከንጉሡ ጋራ ተገናኘ ፌብሯሪ 13። አዲሱ ፓትሪያርክ አቡነ መንደስ ስህተቱ ባሕል እንግዳ መሆኑን ከግንዛቤ ባለማስገባት በጅምላ አንዳንድ መሠረታዊ የሃይማኖት ልዩነቶች ያልሆኑ እንዲከለከሉ አደረገ 1. ግርዝ 2. ቅዳሜ እንደ በዓለ ቀን ማክበር 3. ሁለት ሚስት መያዝ 4. ፍቺ መፍቀድ 5. የቅዳሴ ቋንቋ በግዕዝ መሆኑ ቀርቶ በላቲን እንዲሆን 6. የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት በላቲን እንዲሆን 7. የቀን አቆጣጠር ካሌንደር እንዲቀየር 8. የበዓላት አከባበር 9. የፋሲካ በዓል አከባበርና ቀን መወሰን 10. ቁርባን ሥጋሁ ወደሙ መሆኑ ቀርቶ ስጋው ብቻ እንዲሆን፣ የፆም ቀን በሮቡዕ ቀርቶ ቅዳሜ እንዲሆን 12. ሕዝቡ በሙሉ እንደገና ክርስትና እንዲነሳ በመባሉ ከሁሉ በላይ ሕዝቡ ያስቆጣው ጉዳይ ነበረ 13. የቄስና ማዕረግ ውድቅ ሆኖ ቄሶች በሙሉ እንደገና የቄስና ማዕረግ እንዲሰጣቸው በመደረጉ ከባድ ተቃውሞ ያስከተለ ነበር። እነዚህ ሁሉ ደንቦች በንጉሡ በሕግ የፀደቁ ነበሩ። ሃይማኖትን የማይቀይር የመንግሥት ጠላት ይቆጠር ነበር። ቤተክህነት በአዲሱ ካቶሊክ ፓትሪያርክ ስር ነበሩ። የሃይማኖት አንድነት በኃይል በፀደቀ መጠን የሕዝቡ ተቃውሞ ኃይሉ እየጠናከረ ከመምጣቱ አላቋረጠም። ግንባር ቀደም ተቃዋሚ አልጋ ወራሹ ፋሲሊደስ ነበር። በንጉሡ የደረሰው የቤተሰብ ሞት ሐዘን፣ ማለት በበኩር ልጁ ማርቆስና በሴት ልጁ የትግራይ ሀገረ ገዥ ሚስት ወ/ሮ መለኮታዊት ሞት ሕዝቡ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው ብሎ ተርጉሞታል። በአቅጣጫው ተቃውሞ እንደቀጠለ ነበር። በተለይ በትግራይ ተክለ ጊዮርጊስ የወ/ሮ ወንጌላዊት የሱሲኒዮስ ልጅ ባል ዐመፅ አካሒዶ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ደጋፊ መሆኑን ገልፆ ፖርቱጋሎች ሚሲዮናውያን ወደሚገኙበት ወደ ፍሬሞና አመራ። ቄሶች ወሬ ሰምተው ሸሽተው አመለጡ አግፅያኖቹ አንድ ቄስ ጃኮሞ የተባለው ብቻ አግኝተው ገደሉት ሱሲኒዮስ በቅባ ክርስቶስ የሚመራ ጦር ልኮ ያመሰላቸው፡ ተክለጊዮርጊስ ተይዞ ሱሲኒዮስ ፊት ቀረበ። የሱሲኒዮስ ሚስትም ሌሎችም ምሕረት እንዲያደርጉለት ያቀረቡት ጥያቄ ሳይቀበል ለዐመፅ ከገፋፋችው እህቱ አደሮ ጋራ እንዲገደል አዘዘ። በቤተመንግሥት እና ቤተዘመድ እያዘኑለት በ1628 ዓ.ም. ተገደለ። የሱሲኒዮስ ልጁ ፋሲሊደስ ከዐመፀኞች ጋራ ይስማማል የሚል ዜና በየጊዜው ይደርሰው ስለነበረ የሰሜን ሀገረገዥ አድርጎ ሾመው። ሹመቱ ግን የተቃዋሚዎች መሪ እንዲሆን አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው። ፋሲሊደስ የሚቃወመው በኃይል ሳይሆን በሕጋዊ መንገድ ነበረ፣ ሱሲኒዮስ ስሕተቱን እያወቀ መጣ።

በመጀመሪያ የወሰደው የመሻሻል እርምጃ 1ኛ. የቤተክህነትና የቅዳሴ ቋንቋ እንደድሮ በግእዝ እንዲሆን. 2ኛ. ዕሮቡ ቀን ፆም ተፈቀደ 3ኛ. የበዓላት ቀኖች ከፋሲካ በስተቀር እንደድሮ እንዲሆኑ። ሕዝቡ ግን ማሻሻዮች በቂ አይደሉም ብሎ ውድቅ አደረጋቸው። የካቶሊኩ ፓትሪያርክ መንደስ ካቶሊኮቹን በመርዳት በጠነከረ መንገድ እንዲቀጥልበት ቢመክረውም ሱሲኒዮስ ሊቀበለው አልቻልም፣ ከየአቅጣጫው ዐመፁ እየበረከተ ሄደ፣ ሁኔታዎችን ያጣደፈው ግን ፋሲሊደስ ነበረ። የእስክንዲሪያ ሃይማኖት በይፋ ከመደገፉም በላይ አባቱ ፊት ቀርቦ ሹማምንቶችን ሰብስቦ ስለ ቤተክህነት ሱሲኒዮስ በቅርቡ በሚደረገው ውጊያ ድል ከተቀዳጀ የእስክንድሪያ ሃይማኖት እንዲመልስ ቃል በገባው መሠረት እንዲፈጽም ጠየቀው። የሱሲኒዮስ ሐሳብ ግን የሃይማኖት ነፃነት ብቻ ማወጅ ነበረ። በላስታው መልክአ ክርስቶስ

የሚመራው የተቃዋሚዎች ወገን ንጉሡ ወደሚገኝበት ወደ ደንከዝ አምርቶ መጥቶ ነበር፡፡ ሱሲንዮስ በትግራይና በቤገምድር ጦር እየተደገፈ ጦርነት ገጠመ፡፡ ሁለት የመልክአ ክርስቶስ የቅርብ ረዳቶች ተያዙ መልክአ ክርስቶስ ሸሽቶ አመለጠ፡፡

ከድሉ ሁለት ቀን በኋላ በ1631 ሱስንዮስ የቀድሞ ሃይማኖት እንዲመለስ አወጀ፤ ልጁ ፋሲለደስ እንዲነግሥ ፈቀደ፤ ጥቂት ወር ቆይቶም ሴፕቴበር 1631 ዓ.ም. ዐረፈ፡፡ ብዙ ሳይቆይ ፓትሪያርክ መንደስ ከሀገር ተባረረ፡፡ መንደስ ከምፅዋ ለአፄ ፋሲለደስ ደብዳቤ ጽፎ በካቶሊኮች ላይ ለዘብተኝነት እንዲያሳይ ጠይቆት ነበር፡፡ አጼ ፋሲልም በጻፈው መልስ ጄዝዊቶች የፈጸሙት ስሕተትና በደል በትክክል በማስተመጥ የመጨረሻው ጦርነት ካለቀ በኋላ ምሁራን ቤተክህነትና ሕዝቡ ለንጉሡ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መሐከል የሚከተሉት ይገኙባቸው እንደነበረ ገልፀዋል፡፡

የሮማ ሃይማኖት ከእኛ ሃይማኖት ምንም አይለይም የክርስቶስ ሁለት ባሕሪይ በሚመለከት ሁለቱ ባሕሪያት የተለያዩ አይደሉም አንድ ናቸው ግን ሳይደባለቁ፤ በአንድ የተዋሃዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሃይማኖታችን አንድ ነው፡፡ ይህ ችግር ግን ትኩረት የማይሰጠው አነስተኛ ጉዳይ ነው፤ ሕዝባችን የተቀየመበት በሚከተሉት ጉዳዮች ብቻ ነው፤ 1. ቁርባን በክርስቶስ ደም ምልክት ነቢት ወይን ጠጅ መከልከሉ 2. የሮቡዕና የፋሲካ ፆም ከአንድ ሳምንት በፊት ፆም መከልከል 3. እንቁላል ወተት በፆም ጊዜ መፍቀድ 4. በፆም ጊዜ ቅዳሴ በጠዋት መፍቀድ 5. ንፁሐንና ንፁህን ያልሆኑ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት መፍቀድ 6. የበዓላቶች መለወጥ 7. ኢትዮጵያውያን ሃይማኖት አልባ ሰዎች በመቁጠር እንደገና ክርስትና ማንሳት 8. የካህናትና የዲያቆናት ማዕርግ መግፈፍ እንደገና ማዕርገ ክህነትና ዲያቆንነት እንዲሰጣቸው ማድረግ 9. በእንጨት የተሰሩ ታቦቶች በድንጋይ በተሰሩ መተካት፡፡

በመጨረሻ አጼ ፋሲል ሚሲዮናውያን ወደ ፍሬሞና ሄደው እንዲቀመጡ ትዕዛዝ ካስተላለፈ በኋላ "የኢትዮጵያ ሕዝብ በሮማ ቤተክርስቲያን የሚታዘዝ ከሆነ እኛ ሃይማኖትን የማይቃወሙ በዓሎች እንፈቅድላችሁኋለን ትሉኛላችሁ፤ ነገር ግን ይኸን ለማድረግ ዘግይታችኋል፤ ጊዜው አልፎባችኋል" በማለት ንግግሩን ይደመድማል፡፡ ሚሲዮናውያኑ ፍሬሞና አልተቀመጡም፤ በባሕር ነጋሽ እጅ ከገቡ በኋላ፤ እሱም ለቱርኮች አስረከባቸው፤ ቱርኮችም ከምፅዋ ወደ ሱዋኪም ወስደው ከዘረፋዋቸው በኋላ፤ ገንዘብ ከፍለው ሀገር እንደሚለቁ ሲያደርጓቸው፤ የሚከፍሉትን ገንዘብ ስላልነበራቸው በአንድ ሕንድ ነጋዴ ዋስትና ፓትሪያርኩና አንድ ሌላ ሚሲዮናዊ በመያዣ ከቆዩ በኋላ ወደ ሕንድ እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው፡፡

## 17. አጼ ፋሲሊደስ፤ አጼ ዮሐንስ፤ አጼ እያሱ አጼ ተክለሃይማኖት

የእስፓኝ መንግሥት በዘመኑ በዓለም ርዕሰ ኃያል መንግሥት ስለነበረ አጼ ፋሲል በኢትዮጵያ ላይ የበቀል እርምጃ ይወስድ ይሆናል የሚል ፍራቻ ስለነበረው ከዋናው ጠላቱ ከእስላሙ የምጽዋ ፓሻ ጋራ ማንም ፖርቱጋላዊና ካቶሊካዊ በምጽዋ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ እንዲያደርግ ውል አደረገ፡፡ ቱርኮችም የኢትዮጵያ ዘብ ጠባቂዎች ሆኑ፡፡ ምዕራባውያን ክርስቲያን ሀገሮች የኢትዮጵያ ረዳቶች የነበሩ ተመልሰው ጠላቶች ስለሆኑ



ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ስልጣኔ ተገለለች፡፡ የሚሲዮናውያኑ ከሀገር መባረር በኢትዮጵያ የታየው ክስተት በሃይማኖት ጉዳይ ክርክር መስፋፋት ነበር፡፡ በሚሲዮናውያን እና በኢትዮጵያ ቤተክሕነት አተኩሮ የነበረ ዋና ክርክር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ነበረ፡፡ "ክርስቶስ የእግዚአብሔር አካል የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ስለተቀበለ ነው" የሚሉት የቅባት ደጋፊዎች ወይንስ "በሰው ባሕርዩ ከሁለተኛ እምላክ በቃል በመወሀድ ነው" የሚሉት የተዋህዶ ደጋፊዎች መካከል ነበረ፡፡ የጎጃሙ ደብረወርቅ የቅባት ደጋፊ ሲሆን የሸዋው ደብረሊባኖስ የተዋህዶ ደጋፊ ነበረ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚሁ ዓይነት የሃይማኖት ክርክር በ1621ዓ.ም. ለአጼ ሱሲንዮስ ቀርቦ ነበረ፡፡

እንደገና በአጼ ፋሲለደስ ዘመነ መንግሥት በ1654 እና በ1666ዓ.ም. ሁለት ሲኖዶሶች ተደርገው ነበረ፡፡ ይኸውም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ አንድ ፕሮቴስታንት ቄስ ባቀረበው ሃሳብ ነው ተብሏል፡፡ ነገር ግን ለኢትዮጵያውያን ሲኖዶስ ማድረግ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ክርክሩ የሃይማኖት ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የከፍለ ሀገራዊ ፖለቲካ ነክ ነበረ፡፡ በ1667 ዓ.ም. ፋሲለደስ በበሽታ ሞተ ልጁ ዮሐንስ 1ኛ ተተካ፤ መንፈሳዊ፤ ወግ አጥባቂ ንጉሥ ነበረ፡፡ ሲነግሥ የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ሲኖዶስ እንዲሰበሰብ ለማድረግ ነበረ፡፡ የዮሐንስ ልጅ አልጋወራሽ እያሱ ከአባቱ ጋራ ቅራኔ እየፈጠረ ነበር፡፡ በ1681 ዓ.ም. የቅባትና የተዋህዶ ደጋፊዎች ለማስታረቅ ጉባዔ ተጠርቶ በጉባዔው መጨረሻ አጼ ዮሐንስ የተዋህዶ እምነት ሲደግፍ አልጋወራሹ የተቃራኒ የቅባት እምነት ደጋፊ ነበረ፡፡

በአለፈው ጊዜ አልጋወራሹ ሸፍቶ እንደነበረ አሁንም ሸፍቶ ለማምለጥ ሲሞክር ተይዞ ታሰረ፡፡ ነገር ግን ብዙ ሳይቆይ ንጉሡ ኣለሞተ ስመ ጥሩ ትልቁ እያሱ አንደኛ በሚባል የሚታወቀው እያሱ በ2፣ በ1682 ዓ.ም. ነገሠ፡፡ የሃይማኖት ክርክሮች በእያሱ ጊዜም አላቋረጠም፡፡ ጎጃሞች እያሱ ከመንገሡ በፊት የቅባት እምነት ደጋፊ መስሏቸው ነበር፤ አጼ እያሱ ሁለቱ ተቀናቃኞችን ለማስታረቅ በ1686 ዓ.ም. አንድ ሲኖዶስ ጠራ፡፡ ፓትሪያርኩ እጨጌ፤ ምሁራንና 47 የደብር አለቆች ተካፋይ ነበሩ፡፡ ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እና ንጉሡ ነገሥቱም ነበሩ፡፡ የደብረሊባኖስ እምነት ድጋፍ ያገኘው "ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ስለተዋሀደ ነው" የሚል ነበር፤ የቅባት እምነትም ከዚህ የሚርቅ አልነበረም "የኢየሱስ ሰው መሆን እምላክ ከመሆኑ በፊት የነበረ ነው ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ሲቀበል እምላክነት አገኘ" የሚል ነበረ፡፡ ሁለት የቅባት ደጋፊዎች ሸፍተው ዳሞት ገብተው አሮሞዎችን አስነስተው ከተዋጉ በኋላ ተሸንፈው ምህረት ተደረገላቸው የነበሩ መታረቃቸውን ንጉሥ ዘንድ ሄደው አበሰሩት፡፡ አጼ እያሱ ወደ ሰናር ዘመቻ ሄዶ በነበረ ጊዜ ሁለቱ እምነቶች ጉባዔ ተቀምጠው ስለነበረ የቅባት ተከታዮች በተዋህዶ ተከታዮች ለመረታት ስለተቃረቡ ወኪላቸው "እኛ በስደት ስለምንገኝ መጀመሪያ ወደ እየቤታችን እንመለስ" የሚል ንግግር ስላደረገ በጉባዔ ተካፋይ የነበሩ ራስ አናስታሲዮስና አቡኑ ተቆጧቸውና አወገዙዋቸው ንጉሡም እንዲታሰሩ አዝዞ ወደ ስደት ላካቸው፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ "ስዱዳን" ተብለው ይጠሩ ነበረ፡፡ የቅባት ደጋፊዎች የደብረወርቅ ገዳም ብቻ አልነበሩም አጠገቡ የሚገኘው የደብረ ስሙናም ደጋፊ ነበሩ፡፡ የዚሁ ገዳም አለቃ ወደ አጼ እያሱ ሄዶ ሲኖዶስ እንዲጠራ እና የፓትሪያርኩ ዳኝነት ስላልፈለገ በሊቀመንበርነት እንዲመራ ንጉሡን ጠየቀ፡፡ ንጉሡ ግን ስራዬ አይደለም ብሎ እንቢ ስላለ ለአስክንድሪያ ፓትሪያርክ መልእክት ልኮ በአቡኑ ሲኖዳ ምትክ ሌላ አቡን እንዲላክ ጠየቀ፡፡ የግብፁ ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስም አቡነ ማርቆስ የሚባል

ላከ። አጼ እያሱ ተገርሞ አዲሱ ፓትሪያርክ ወደ ሰቃ የእናሪያ ዋና ከተማ ተወስዶ እንዲታሰር አደረገው መልእክተኞችም ማብራሪያ እንዲጠይቁ ወደ ግብፅ ላከ። ከአንድ ዓመት በኋላ መልእክተኞቹ ሲመለሱ ንጉሡ የገዳማት አለቆች በሙሉ በጎንደር እንዲሰበሰቡ አደረገ። በተሰበሰቡበት አጼ እያሱ ልብሰ ግዕረተ ለብሶ የግብፅ ፓትሪያርክ ደብዳቤ ከፍቶ አነበበላቸው "እኛ አቡነ ግርቆስን ሾመናል አቡነ ሲኖዳም ከሥልጣን አውርደናል " የሚል ነበረ። ቀጥሎ ንጉሡ "እንደ ፓትሪያርኩ ትዕዛዝ ይሁን" አለ። ከዚህ በኋላ አቡነ ግርቆስ ስለ ቅባትና ተዋህዶ እምነቶች ያለው ሀሳቡን እንዲሰጥ ተጠይቆ ቃሉም "ስለ አንድ ቅድስት ቤተክርስቲያን ማመን" የሚል ነበረ። በዚሁ መሠረት የጎጃም ገዳማት ነጥብ እንዳገኙ ተቆጠረላቸው።

በ1699 ዓ.ም. አጼ እያሱ ከአባይና ከአዋሽ እስከ ጊቤ ያሉ መሬቶች ሳፍረው የነበሩ ጉድሩና ሜጫ የተባሉ ኦሮሞች ላይ ዘመቻ ለማድረግ ከጎንደር ተነሳ። ከሲዳማ መንግሥታት መሐል እናሪያና፣ ከፋ በጀግንነት ኦሮሞዎችን ሲቋቋሙ ሌሎች ግን በኦሮሞች ስር ስለ ወደቁ ማዕከላዊ መንግሥት በከፋና በእናሪያ የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ ነበረ። የአጼ እያሱ ዘመቻ ዓላማ የሲዳማ መንግሥታት በኦሮሞዎች ከበባ ነፃ ለማውጣት ነበረ። ሸዋን ሰመያዝ ያሰጉ የነበሩ ጉድሩ ስለነበረ በመላክ ሰገድ ክርስትና የተቀበሉ አጼ እያሱ በመጀመሪያ በእነሱ ላይ ውጊያ ከፍቶ ግዙፍ ሰውነት በነበረው የኦሮሞ መሪያቸው በእጁ ቢገድለውም በመጨረሻ ግን እሮሞዎች ከባድ ጉዳት አድርሰውበት ወደ ጎንደር ተመለሰ። ከዚህ ቀጥሎ ግን አጼ እያሱ በኦሮሞዎች ላይ የሚከተለው ግንኙነት በመቀየር በጉልበትና በጦርነት መሆኑ ቀርቶ በሰላምና በስምምነት የበለጠ ውጤት ሰጥቶ ነበር። ስለዚሁ ተግባርም ኃላፊነት የተሰጠው ደጃዝማች ኢኖረ የጎጃም ሀገረ ገዥ ነበረ። በ1701 ዓ.ም. ከጉድሩ ባሶ የተባሉ ኦሮሞዎች በንጉሡ ነገሥቱ ስር ለመሆን በመስማማታቸው አጼ እያሱ አባይን ተሻግሮ ሊዋጋቸው ሄዶ ቱሉ አማራ የተባለው ሀገር አስገብሮ ወደ ጎንደር ተመለሰ። ቀጥሎም ባሶ ሊቤን ቃለ ጋንዳ ከተባሉ ኦሮሞዎች ተዋጊዎችን ሰለመለመለ ከኢኖረ የጎጃም ደጃዝማች እና ከልጁ ባል ቶሉ የዳሞት ደጃዝማች ተመካክሮ እንደገና አባይን ተሻግሮ በቱሉ አማሩ ሠራዊቱን ካሰባሰበ በኋላ ወደ ምሥራቅ ወደ ሸዋ ከማምራት ፈንታ ወደ ምዕራብ ወደ ወሰጋ አምርቶ በዲላም የሚመራ የኦሮሞ ሜጫ ተዋጊዎች ጦርነት ገጥሞ ራሱ መሪያቸው ተገድሉ የክርስቲያን ሠራዊት ሰላሸነፈ አጼ እያሱ በድል አድራጊነት እናሪያ ገባ። ሕዝቡም በታላቅ ደስታ ተቀበለው ቤተክርስቲያኖችን ገበያዎችን ጎበኘ፣ ከሕዝቡም ስጦታ ተቀበለ። ከዚህ ዘመቻ በተመለሰበት ወቅት ነበረ ከሁሉ ይወዳት የነበረ ሚስቱ ወ/ሮ ቅድስቴ የሞተችበትና በኃዘን ምክንያት ያለጊዜው የእርጅና መልክ የተሰማው።

ይህ በዚህ እንዳለ በተዋህዶ እምነት ተከታዮችም በእርስ በርስ ሹክቻ ለወልድ ቅብ እና ለፀጋ ልጅ ተብለው ለሁለት ተከፈሉ። አጼ እያሱ ከእናሪያ ዘመቻ መልሰ ሥልጣኑ በሙሉ ለመጀመሪያ ልጁ ቢተወደድ በመባል ለተክለሃይማኖት ሰጥቶ ወደ መንፈሳዊ ስራ ብቻ አዘንብሎ ነበረ። ከቅድስቴ የተወለዱ ልጆቹ ከጎኑ አይለዩም ነበረ።

ይህ በመሆኑ ግን ሚስቱ ንግሥት መለኮታዊትና በኩር ልጁ ተክለሃይማኖት ቅናትና ጥርጣሬ አድሮባቸው ነበር። የመንግሥት ታላላቅ ባለስልጣኖችም ተክለሃይማኖት ሥልጣን ቶሎ እንዲይዝ ይገፋፉት ጀመር። አጼ እያሱ ወሬ ስለደረሰው ተክለሃይማኖትን ልጁን አስጠርቶ የትግራይ ሀገረ ገዥ ራስ ፋሪስን የሰሜን ደጃዝማች ወ/ጊዮርጊስን ሌሎችም ባለሥልጣናት



ለምክር አስጠርቶ ሲጠይቃቸው "እንተን ወደ ወህኒ አውርዶ መጨረሻ ልጁን ለማንገስ ነው የሚጥረው በሚል አስተያየት ስላየለ በተሰበሰቡበት ተክለሃይማኖት ንጉሥ እንዲሆን ወስነው ለአባቱ ለአጼ እያሉ ላከበት። ለደጃዝማች ቱሉ የእህቱ ባል ወደ ጎንደር መጥቶ በባቱ ላይ እንዳያምፅ ተክለሃይማኖትን ለማግባባት ሞክሮ አልተሳካለትም። በ1706 ዓ.ም. አጼ ኢያሱ ልጁን በጦርነት ለመግጠም ወደ ጎንደር እየገሰገሰ መጣ። በመንገድ ግን ንጉሡ ታመመና "ከእግዚአብሔር የተላከ ማስጠንቀቂያ ነው" ብሎ ስለተረጎመው በመጨረሻው በዙሪያው ለነበሩት "ተክለሃይማኖት ልጄ እንዲነግሥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው" ብሎ ወታደሮቹን አሰናብቷቸው ለፀሎትና ለምንኩስና ኑሮ ወደ ጣና ደሴት ሄደ።

ሱዱዳን የተባሉ "ጎጃም ገዳማት ቄሶች የተክለሃይማኖት ደጋፊዎች ነበሩ። ተክለሃይማኖት ከንግሡ በኋላ አባቱ ያደረሰባቸው በደል በመዘርዘር ለ25 ዓመታት በስደት እንደኖሩ ቢገልፁለትም ተክለሃይማኖት "በንጉሥ ትእዛዝ ሃይማኖት አይቀየርም ባይሆን ሲኖዶስ ልጥራላችሁ" የሚል መልስ ሰጣቸው። የተክለሃይማኖት ውሳኔ ትክክለኛ ቢሆንም ለአጼ ኢያሱ ታማኝ የሆኑ ኃይሎች በሁኔታው በመጠቀም ደጃዝማች ቱሉ የዳሞት ሀገረ ገዥ ሱዱዳን ሌሎችም እንዲሰበሰቡ አድርጎ ዐመጽ ተጀመረ። ራስ ፓሪስ ደጃዝማች ቱሉን እንዲታሰር አደረገ። ወደ ትግራይ ተወስዶ ዓይኑ ሰውር እንዲሆን ተደረገ። ሌላ የኢያሱ ደጋፊ የጎጃም ሀገረ ገዥ አኖሬ ለዓመጽ ተነሳ፣ በራስ ፋሪስ የሚመራው ከትግራይ ሠራዊት ጋራ ጦርነት ገጥሞ ስለተሸነፈ ወደ ጎጃም ተመለሠ። አኖሬ ሌላ ኃይለኛ ጦር ይዞ ተጠናክሮ ማና ሐይቅ መጥቶ አጼ እያሱን ከገዳም አስወጥቶ ሊያነግሥ ነው የሚል ወሬ ሲሰማ ዳርሚንና ጳውሎስ የተባሉ የአጼ ተክለሃይማኖት አጎቶች (የእናቱ ወንድሞች) እስላሞችና እሮሞዎች ገዳዮችን ይዘው አጼ ኢያሱ ወደ አለበት ሄደው ከገደሉት በኋላ በእሳት አቃጠሉት። የገዳሙ ቄሶች ግን በክብር ያሁት ከአባቶቹ መቃብር አጠገብ ተቀበረ። ስጦታ ለቤተክርስቲያን የሰጣቸው የደብረብርሃን እና የጎንደር የደብር አለቆች እንዲሁም ምእመናን ሁሉ አለቀሱለት አርባ ቀን ሐዘን ሆነ። ማንም የኢትዮጵያ ንጉሥ የሕዝቡ ሐዘን የቀሰቀሰ አልነበረም። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንደሰማእት ታከብረዋለች።

ከታላቁ ቀዳማዊ አጼ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት /መጨረሻ/ ጀምሮ ኢትዮጵያ በታሪኳ ወደ አዲስ የሥልጣኔዋና የአንድነቷ የማሽቆልቆል ምዕራፍ ተሻግራለች ለማለት ይቻላል። ለፖለቲካ ውድቀትም ምክንያት የሆነው ሁለቱ የሃይማኖት እምነቶች ተዋህዶና ቅባት ከሃይማኖት አልፈው ስልጣን ለመያዝ ለሚደረገው ፍልሚያ ግልቃ ገብተው መሣሪያ በመሆናቸው ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ንጉሥ አጼ ኢያሱ በጦር ሜዳ ሳይሆን በክህደት ዓለም በቃኝ ብሎ ከሚወዳቸው ወ/ሮ ቅድስቴ ልጆች ተለይቶ ልጆቹን ለአጼ ተክለሃይማኖት ወደ ወሕኒ አምባ እንዲያገቧቸው አስረክቦ ወደ ገዳም ገብቶ እንዳለ በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ተገደለ።

ከአጼ ኢያሱ በፊት የነበሩት ነገሥታት በጎጃም ገዳማት ደብረወርቅ ደብረ ሳሙና ደብረ ማጉዮና የሚደገፍ የቅባት እምነትና በሸዋ ደብረሊባኖስ ገዳም የሚደገፈው የተዋሕዶ እምነት ደጋፊዎች ይደረግ የነበረው የተሟሟፈ የሃይማኖት ክርክሮች ከሞላ ጉደል የሸዋ ደብረሊባኖስን ነበረ ይደግፉ የነበሩት። ትልቁ አጼ ኢያሱ ግን 25 ዓ.ም. በቆየ ዘመነ መንግሥቱ ለአንድ እምነት ሳያዳላ የሃይማኖት ጉዳይ ለፓትሪያርኩ በመተው ገለልተኛ ለመሆን ሞክሮ ነበር። የጎጃም ገዳማት ግን የደብረሊባኖስ እምነት ይደግፋል በማለት ምናልባት ይደግፌን ይሆናል ብለው በማመን የአጼ ኢያሱ ልጅ ንጉሥ

ተክለሃይማኖት ሥልጣን ለመያዝ በአባቱ ላይ ባደረገው ዓመፅ ከጎኑ ተሰልፈው ነበር፡፡ ሆኖም ከላይ እንደተገለፀው ንጉሥ ተክለሃይማኖት ተቀብለበው ሄደው ላቀረቡለት ጥያቄ የሰጣቸው መልስ እንደጠበቁት አላስደሰታቸውም፡፡ በዚሁ ምክንያት በጎጃም ገዳማት ቀስቃሽነት አንድ ትልቅ ሕዝባዊ ዓመፅ ተነስቶ ዓምደጽዮን የተባለ ንጉሥ አነገሡ፡፡ ዳርመን በደጃዝማች አርሬ ቦታ የጎጃም ሀገረ ገዥ ሆኖ የነበረው በዓመፀኞች ላይ ጦርነት ከፍቶ ብዙ ሕዝብ ጨፈጨፈ፡፡ ከዓመፀኞቹ ግንባር ቀደም የቅባት እምነት መናኮሴዎች ተሰልፈው ነበረ፡፡ የአጼ እያሱ ታማኝ ወታደሮችም ነበሩ፡፡ ዓመጽ ያስነሱ ቂሶች በሙሉ ተገደሉ፣ ደጃዝማች አርሬ ተገደለ፡፡ የአጼ ተክለሃይማኖት እናት ንግሥት መለኮታዊት ቅስቀሳ አድርጋ ለዘውድ ያበቃችው እቴጌ የሚል ማዕረግ ተሰጣት፡፡ አጼ ተክለሃይማኖት በጦር ሜዳ ቢያሸንፍም ወዲያውኑ በቤተመንግሥት ውስጥ ከባድ ፀጥመድ ተጠነሰሰበት፡፡ ከአገው ምድር ወደ ጎንደር በሚለስበት ጊዜ ለአደን ብቻ/ ሠራዊቱን አሰናብቶ ወደ ጫካ ወሰዱት፡፡ አጼ ተክለሃይማኖት ጥርጣሬ ሳያድርበት ሲገድሉ፣ የነበራቸው ዓላማ ማወቅ ባለመቻሉ በእጃቸው ሲገባ ከበው ገደሉት፡፡ ከዚያም በፈረስ እየጋለቡ ሸሹ፡፡ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው አንድ ሰለሞናዊ ንጉሥ በሕዝብ ዓመፅ ሲገደል፡፡ አባቱ በማስገደሉ በራሱ ላይ የደረሰ የእግዚአብሔር ቅጣት ነበረ፡፡ ተክለሃይማኖትን የሚተካ ንጉሥ ለመምረጥ ሁለት እጩዎች ቀረቡ የመጀመሪያ እጩ በትግራይ ሀገረ ገዥ በራስ ፋሪስ የቀረበ ናእድ የተባለ የአራት ዓመት ልጅ የአጼ ተክለሃይማኖት ልጅ ነበረ፡፡

## 18. አጼ ቴዎፊሎስ

ቢጅሮንድ ዮስጦስ የናእድ በእጩነት መቅረብ በመቃወም ወደ ወሕኒ አምባ ሔዶ የአጼ እያሱ ወንድም ቴዎፊሎስ አምጥቶ እንዲነግሥ አደረገው፡፡ አዲሱ ንጉሥ አጼ ተዎፊሎስ ግልጽ የሆነ የማያወላውል አቋም ይዞ ነበረ የተነሳው፤ ይኸውም በፖለቲካ የወንድሙ የአጼ ኢያሱና የወንድሙ የአጼ ተክለሃይማኖት ገዳዮችን ለመበቀል ነበር፡፡ በሃይማኖት ጉዳይም ሲኖዶስ ባያስፈልገውም የባለሥልጣኖች በሙሉ ሰጉባዔ ጠርቶ ስመጀመሪያ ጊዜ የጎጃም ገዳሞች የሐይማኖት እምነት የቅባት የሚደግፍ ውሣኔ አወጣ፡፡ የአጼ ተክለሃይማት ደጋፊዎች በሙሉ ለግዞት ወደ ሐማሴን ተወሰዱ፣ ራስ ፋሪስ ወደ መሰረሃ ሐይቅ ተወሰደ፡፡ዮስጦስ ለሥልጣን ያበቃው የሰሜንና የትግራይ ሀገረ ገዥ ሆነ እስቂያስ የተባለው ሌላ የቴዎፊሎስ ታማኝ በአጼ ተክለሃይማኖት አጎት ጳውሎስ የአጼ ኢያሱ ነፍሰ ገዳይ ተይዞ የነበረ ቦታ በመውሰድ የቤጌምድር ሀገረ ገዥ ሆነ፡፡ የደብረሊባኖስ መሉኩሴዎችን በታተናቸው፣ በአንፃሩም በጎጃም ገዳማት እየተረዳ የአጼ ኢያሱን ነፍሰ ገዳዮች የአጼ ተክለሃይማኖት እናት ንግሥት መለኮታዊት ወንድሞች በሕዝብ ቁጣ ተይዘው ፍርድ እንዲሰጣቸው ለአጼ ቴዎፊሎስ አስረከቡት፡፡ ለየእንዳንዱ በፈጸሙት ወንጀል በጎንደር አደባባይ ተፈጸመባቸው፣ ንግሥት መለኮታዊትና ወንድሟ ጳውሎስ በስቅላት ተገደሉ፡፡ አንድ ንግሥት እና የንጉሥ እናት በስቅላት ስትገደል የመጀመሪያ ጊዜ ነበረ፡፡ ዳርሜን የአጼ ኢያሱ ገዳይና ገበማ ካሳ የአጼ ተክለሃይማኖት ገዳይ በጎራዴ ተገደሉ፡፡ ሌሎች የአጼ ኢያሱ ግድያ ተካፋይ የነበሩ በጎራዴና በጥይት ተገደሉ፡፡

አጼ ቴዎፊሎስም ሰላም አላገኙም፡፡ ቱጂ የተባለው ኦሮም ወደ ሐማሴን በግዞት ከተላከ በኋላ፣ ምህረት ተደርጉለት ተመልሶ ስለነበረ ወደ ኦሮሞ ሀገር ሄዶ ወታደሮችን መልምሎ እንደ ንጉሥ እንግሥ ጦርነት



ከልከፈተ አጼ ቴዎፊሎስ በአትሮዳላ ማርያም ቤተክርስቲያን ጦርነት ገጥሞ ድል ተቀዳጅቶ ሲመለስ ታሞ ስለሞተ መንገሥ የማይገባው ዮሥቶስ ከዛግዌ የዘመነ መንግሥት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀጥታ ሰለሞናዊ ያልሆነ ሰው ነገሠ፡፡

## 19. አጼ ዮስቶስ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ናፍቆት ስለነበረ የዮስጦስ ንጉሥ መሆን ተቃውሞ አላጋጠመውም፡፡ አጼ ዮስቶስ ምንም እንኳን በቀጥታ ሰለሞናዊ ዘር ባለመሆኑ መንገሥ የማይገባው ቢሆንም በእናቱ በኩል ሰለሞናዊ ዘር ስለነበረ በአጼ ቴዎፊሎስ ዘመነ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ከአጼ ኢያሱ ጀምሮ የአስተዳደሩ ቴፐኛይ ልምድ ያካበተ በመሆኑ በታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና በሕዝብ ድጋፍ የነበረው ይመስል ነበር፡፡ ሆኖም ጥቂት እንደቆየ ተቃዋሚዎች ሊነሱበት የቻሉት አደን ብሎ ወደ ጫካ በሚሄድበት ጊዜ ነበር፡፡ አጼ ዮስቶስ በአደን ምክንያት ብቻውን ወደ ጫካ በሚሄድበት ጊዜ ሌላ ዓላማ የሚያራምድበት ነበረው፡፡ ከካቶሊክ ሚሲዮናውያን በምስጢር ለመነጋገር ነበረ፡፡ ከ200 (ሁለት መቶ) ዓመት በፊት በአጼ ልብነድንግል ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ በኃይል እስላማዊት ለመሆን ተቃርባ በነበረበት ጊዜ ለሮማ ጳጳስና ለፖርቱጋል መንግሥት ልመና በተሳካ ሁኔታ አስፈላጊውን ወታደራዊ እርዳታ ስለተካላት የክርስትና ሃይማኖት እምነቷን ጠብቃ ለመኖር ስለቻለች ወደ ሥልጣን የወጡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ የሚያስታውሱት ነው፡፡ አጼ ዮስቶስ፣ አጼ ኢያሱ 1ኛ ከሚሲዮናውያን እርዳታ ለማግኘት ይገናኙ እንደነበረ ያውቅ ነበረ፡፡ አሁን የቪየሱ (Wies) ሊቤራቶ አውስትሪያዊ የሮማ ጳጳስ ልኡክ ከሌሎች ቄሶች ጋራ ሆኖ በ1711 ዓ.ም. ምጽዋ ደርሶ ሴፕተምበር 1712 ዓ.ም ጎንደር ደርሰው ንጉሡ እቀባበል አድርጎላቸው ከሕዝቡ ተቃውሞ ርቀው ወልቃይት እንዲቀመጡ አደርጓቸው ነበር፡፡

ንጉሡም እየሄደ ይጠይቃቸው ነበር፡፡ ሃይማኖቱም እንደቀየረ ወሬ ሲሰማ የሕዝብ ተቃውሞ ገጠመው፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሊገነዘቡ ያልቻሉት ኤውሮጳውያን በ200 ዓመት ውስጥ ያደረጓቸው ከፍተኛ የአስተሳሰብ ለውጦች ነው፡፡

ከሁለት መቶ ዓመት በፊት የነበሩ ሁኔታዎች ተለውጠው ኤውሮጳውያን አፍሪካውያንን ሁሉ የሚያዩን እስላምና ክርስቲያን ሳይለዩ በአንድ ወገን መድበውን በአንድ ዓይን ሁላችን በቀኝ ግዛት ለመያዝ የሚሽቀዳደሙበት ኋላ ቀር የሶስተኛ ዓለም ሕዝቦች ተብለን ነው፡፡ የሃይማኖት ጉዳይ የመስቀል ጦርነት ዘመን! በኤውሮጳውያን ጊዜ ያለፈበት ነው፡፡ እኛ ግን በስልጣኔ ወደፊት ሳንራመድ ባለንበት መቀመጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላ የገሸቁልቁል እንገኝ ነበር፤! በ1700 ዓ.ም. የኤውሮጳ ሀገሮች በሳይንሳዊ ግኝቶች ስለተራቀቁ የሃይማኖት ጉዳይ ወደ ጎን ትተው እርስ በእርሳቸው የበላይነት ለመቀዳጀት በቅኝ ግዛት ዓለምን ለመከፋፈል ይሯሯጡ የነበሩበት ዘመን ነበረ፡፡ በመስቀል ጦርነቶች ጊዜም ቢሆን ወዶ ዘመቶች እየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት በሚሄዱበት ጊዜ የሮማ ጳጳስ ዓላማ ግልፅ የሆነ ነበረ፣ ይኸውም የክርስትና እምነት ተከታዮች ሁሉ የትግል አንድነት ፈጥረው እስላሞቹን መዋጋት ሳይሆን የካቶሊክና የኦርቶዶክስ ልዩነት ተወግዶ አንድ ካቶሊክ ሃይማኖት ብቻ ለማድረግ ነበረ፡፡ ከዘማቾችም ድብቅ ዓላማ የነበራቸው ነበሩባቸው፣ ይኸውም የራሳቸው ግዛት ለማስፋፋት ነበር፡፡ ይኸ

በመሆኑ ከቱርኮች ነፃ የወጡ መሬቶች ለምሥራቃዊ ቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት እንዲያስረክቡ የገቡበት ውል በማጠፍ የራሳቸው ግዛት መሠረቱ፡፡ ነፃ የሚወጡ የኢየሩሳሌም ግዛቶችም ነዋሪ የነበሩ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችም ልክ እንደ እስላሞች ጨፈጨፋዋቸው፡፡ ኢትዮጵያ ይህ ሁኔታ ልትገነዘብ አልቻለችም፡፡ በአጼ ልብነድንግል ጊዜ የነበረውና በአጼ ዮስቶስ ዘመነ መንግሥት የነበረው የአውሮጳውያን አስተሳሰብ በጣም የተለያየ ነበረ፡፡ አጼ ልብነድንግል በአውሮጳ የነበረውን ብዙ ሁኔታ ተጠቅሞ ነው እርዳታ ሊያገኝ የቻለው፡፡ የቱርክ አቶማን እስላሞች አውሮጳን በቁጥጥራቸው ለማድረግ በሞከሩበት ጊዜ ኃያላን የአውሮጳ መንግሥታት ቱርኮችን በኃይል ለመቋቋም ተስኖዋቸው ነበር፡፡ በክርስቲያን አውሮጳ ኃይለኛ ፀረ እስልምና ሃይማኖት ጥላቻ መንፈስ ነበረ፡፡ ፖርቱጋልም ከቱርኮች ጋራ በቀይ ባሕር ፊልሚያ ታደርግ ነበር፡፡ ይህ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ቢያውቅበትና የአውሮጳ መንግሥታትም ቀና መንፈስ ቢያሳዩ ኢትዮጵያ ክርስቲያን ሀገር እንደመሆኗ መጠን ካገኘችው የበለጠ እርዳታ ማግኘት ዕድል ነበራት፡፡ በወቅቱ ለኢትዮጵያ የተደረገላት ወታደራዊ እርዳታ በስሕተት ነበረ ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የፖርቱጋል መንግሥትም ሆነ የሮማ ጳጳስ ካቶሊክ ላልሆነ ሕዝብና መንግሥት እርዳታ ለማድረግ ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ልብነድንግል ግን ሕዝቡን ሳያማክር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከነበሩ ከፖርቱጋል መልእክተኞች ጋራ ብቻ በመመካከር ደብዳቤ ለሮማ ጳጳስ የላከው ኢትዮጵያ የካቶሊክ ሃይማኖት መቀበሏን ከመግለፁ በላይ ኢትዮጵያ በካቶሊክ አቡን ነው የምትመራም ብሎ ለማሳመን ሕገወጥ የሆነ ማዕረግ ለአንድ ፖርቱጋላዊ ሐኪም የጵጵስና ማዕረግ በመስጠት ነው፡፡ የጵጵስና ማዕረግ የሚሰጥም ግብፃዊ እርቶዶክስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ነበረ፡፡ የሚገርመው ነገር ግብፃዊ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ እንዴት ለአንድ ካቶሊካዊ ጵጵስና ለመስጠት ፈቀደ ለሚለው ጥያቄ 1ኛ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ግብፃውያን ጳጳሳት የሃይማኖት መሪዎች ጥራት ይጎድላቸዋል፡፡

ለኢትዮጵያ ነገሥታት መታዘዝና መሣሪያ ከመሆን በቀር እውነተኛ የሃይማኖት ሥራ ሲያከናውኑ የታዩበት ጊዜ የለም፡፡ ስለዚህ የግብፃዊ አቡን እሺ ብሎ ከፖርቱጋሉ ሐኪም ለበርሙደስ የጵጵስና ማዕረግ የሰጠበት ምክንያት ይኸው ሊሆን ይችላል፡፡ 2ኛ. ግብፃዊ ጳጳስ በጣም እርጅቶ ስለነበረው የሚሰራው ሥራ አይቆጣጠርም ይሆናል 3ኛ. በኢትዮጵያ የነበረው አስጊ ሁኔታ በመመልከት በሃይማኖት የሚመሯትን ሀገር እስላማዊት ከምትሆን ተሸዋሚና ኢትዮጵያውያን ከተስማሙ ጊዜያዊ መፍትሄ ሊሆን ይችላል ብሎ ስላመነበት ሊሆን ይችላል፡፡ በፖርቱጋላዊ ቤርሙደስ በኩል እንዴት ከአንድ ኦርቶዶክስ ጳጳስ ማዕረገ ጵጵስና ለመቀበል እንደፈቀደም ብዙ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ 1ኛ. ሐኪም እንደመሆኑ መጠን በሃይማኖት ትምህርት ጥልቅ ዕውቀት ስለሌለው ለማገናዘብ ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል፡፡ 2ኛ. ጊዜያዊ መፍትሔ በመሆኑ ማዕረጉም በሮማ ጳጳስ ይፀድቃል ብሎ ተስፋ በማድረጉ ኢትዮጵያን የሚያህል ሰፊ ሀገር ካቶሊክ ማድረግ በመቻሉ ጓጉቶ ሊሆን ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ በኩልም ልብነድንግልና ሌሎች ባለሥልጣናትም ሕዝቡን ሳያማክሩ የሰሩ ቢሆንም የካቶሊክ አቡንና ቄሶች ለወደፊት የሚያመጡት ሰበብ እንደ ቋንቋ መቀየር! እንደገና መጠመቅ! ለቄሶች እንደገና ማዕረገ ክሕነት መስጠት ወዘተ የመሳሰሉትን ከግንዛቤ ባለማስገባት ከሕዝቡ ከባድ ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው በመተማመን ይሆናል፡፡ ከ200 ዓመት በኋላ ግን በአጼ ዮስቶስ ከእሱ በፊትም የነበሩ አጼ ኢያሱ ከእሱ በኋላም የነገሡ



ነገሥታት ጊዜ አውሮጳ በስልጣኔ ብዙ ወደፊት ተራምዳለች ያገኘቸባት የነበረውን የቱርክ ኦትማን አደጋ ተወግዷል፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የሮማ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ሚሲዮናውያን ለመላክ ፍላጎት ቢኖረውም በቅኝ ግዛት ለመያዝ ካልሆነ በስተቀር በሃይማኖት ዓላማ ወታደሮችን ለመላክ የሚፈልግ አውሮጳዊ መንግሥት አልነበረም፡፡ በዚሁ መንገድም ሞክረው ውጤት አልባ ሆነው የቀረው የደጃዝማች ውቤና የደጅ ንጉሴ እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ግን በከንቱ ተስፋ ለብዙ ጊዜ ተሞኝቷል፡፡ ዳግማዊ ሚኒልክም ሳይቀር የኢትዮጵያ ወደቦች አንድ በአንድ ለፈረንጆች ካስረከበ በኋላ ክርስቲያን መንግሥታት አንድ ወደብ ለሀገሬ ለኢትዮጵያ ይፈቅዱላት ይሆናል የሚል ተስፋ ነበረው፡፡ በ1716 ዓ.ም. ከአጼ ዮስቶስ ሞት በኋላ የነገሠው አጼ ዳዊት ነው፡፡

## 20. አጼ ዳዊት

አጼ ዳዊት የአጼ ኢያሱ ትልቁ ልጅ ነበረ፡፡ የደብረሊባኖስ ገዳም አለቃ ሲኖዶስ በአስቸኳይ እንዲሰበሰብ ብሎ በጠየቀው መሠረት ብዙ ካሕናትና ምእመናን በተሰበሰቡበት እጨጌ መዝሙር ሦስት ፈረንጆች ቄሶች በአጼ ዮስቶስ ተፈቅዶላቸው በወልቃይት በአባ ጎርጎሪዎስ ቤት እንደሚገኙና ንጉሡ በየጊዜው እየሔደ ቅዳሴ ያስቀድስ እንደነበረ ለጉባዔተኞች ገለጣ አደረገ፡፡ አጼ ዳዊት ከጉባዔተኞች ፊት እንዲቀርቡ አድርጎ አባ መዝሙር የኦርቶዶክስ እምነት ያወገዘ በማዕዶኒያ ጉባኤ ያምኑ እንደሆነ ጠየቃቸው፡፡ እነሱም አዎንታዊ መልስ ስለሰጡ ጉባዔተኞቹ እንዲገደሉ ስለጠየቁ የጉባኤው ሊቀመንበር የነበረው ሊቀ ሊቃውንት ክፍሌ ፍርዱን በከፍተኛ ድምፅ አሰማ፡፡ ሚሲዮናውያኑ ወደ ከተማ ተወስደው ተገደሉ፡፡ አባ ጎርጎርዮስ ከንጉሡ ታዝዤ ነው! ሃይማኖቴን አልቀየርኩም ስላለ ሕይወቱ ሊያተርፍ ችሏል፡፡ አጼ ዳዊት ጊዮርጊስ የተባለው የራስ አናስታስ ልጅ ቢተወደድ አድርጎ ሾመው በቢትወደድ ጊዮርጊስና በሌላው በቤተመንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ያለመግባባት ተፈጠረ፡፡ ንጉሡ የቢትወደድ ጊዮርጊስ ሐሳብ ደጋፊ ስለነበረ ራስ ወልደጊዮርጊስ ወደ ግዞት እንዲወሰድ አድርጎ ወዲያውኑ አዲስ ሲኖዶስ የደብረሊባኖስ ገዳም በጠየቁት መሠረት እንዲጠራ አደረገ፡፡ ቢትወደድ ጊዮርጊስ ባሳሰበው መሠረት ንጉሡ የሲኖዶሱ ጉባኤ ሊቀመንበር ሆኖ እንዲመራ ያቀረቡለትን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቶ ቢትወደድ ጊዮርጊስ ወኪሉ እንዲሆን አድርጎ ውጤቱን እንዲነገረው አዞ ስለነበረ የደብረሊባኖስ መነኩሳት ንጉሡ በሊቀመንበርነት የማይመሩት ጉባኤ የማይሳተፉ መሆናቸው ገለጡ፡፡ የደብረሊባኖስ ቄሶች ውሳኔ እንደሰማ አጼ ዳዊት ለጉባኤተኞቹ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ወደሚገኝበት ሄደው ሃሳቡን እንዲጠይቁ አዘዛቸው፡፡ አቡኑም እምነቱ ከእሱ በፊት ከነበሩ ፓትሪያርኮች ከአቡነ ሲኖዳና ከአቡነ ማርቆስ እንደማይለይ ነገራቸው፡፡

ይህ እምነት የጎጃሞች ፀጋ ቅባት የሚደግፍ ስለነበረ ለንጉሡ ሲነገረው በአደባባይ በቅባት ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚል እንዲታወጅ አዘዘ፡፡ የደብረሊባኖስ ቄሶች ተሸንፍን ብለው እጃቸውን አልሰጡም! ቢትወደድ ጊዮርጊስ በሌለበት ፓትሪያርኩን እንጠይቃለን ብለው እጨጌ የመጉወና ደብር አለቃ የሲኖዶስ ሊቀመንበርና የቤተክርስቲያን ምሁራን ባሉበት ፓትሪያርኩን ሐሳቡን እንዲገልፅ ጠየቁ፡፡ በዚሁ ጊዜ ፓትሪያርኩ እምነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በውሕደት ወልድ ልጅ ነው በቅባት መሲያስ ነው የሚል ቃል ሰጠ፡፡ የተዋህዶ እምነት ተከታዮች ተደሰቱ፡፡

ንጉሡ ግን በቢትወደድ ጊዮርጊስ እየተረዳ የደብረሊባኖስ ቄሶችን መጨፍጨፍ ጀመሩ፡፡ በአንድ ቀን ከመቶ ቄሶች የሚበልጡ ተገድለው በየመንገድ ተጣሉ፡፡ ማታ ንጉሡ ግድያ እንዲቆም አዘዘ፡፡ ፓትሪያርኩ በአደባባይ የንጉሡ አዋጅ ሲነገር እንዲያደምጥ አደረጉት፡፡ ብዙ ሳይቆይ አጼ ዳዊት ሜይ 1721 ዓ.ም. ዐረፈ፡፡ ይህ ሁሉ በሃይማኖት ጉዳይ ውጤት አልባ ክርክርና ግድያ የአንድ ሀገር የደካማነት ምልክት ነው፡፡ ኢትዮጵያም ትራመድ የነበረችው ወደ ውድቀት ጎዳና ነበር፡፡

## 21. አጼ በከፋ፣

በአጼ ዳዊት ምትክ የነገሠ ሌላ የአጼ ኢያሱ ልጅ በከፋ ነበረ፡፡ አጼ በከፋ በቤጌምድርና በላስታ የተነሱበት ዓመፀኞች ለመከላከል ዘመቻዎችን አካሄዷል፣ ያካሄደበት ምክንያት ባይታወቅም ወደ ቋራ ይፋዊ ያልሆነ ጉብኝት አድርጎ ነበረ፡፡ ንጉሡ ማንነቱ ሳይታወቅ በድንገት ታሞ ሲተኛ ወደ አንድ ቤት ተወስዶ አንድ የምታምር ልጅ ተገቢ እንክብካቤ አድረገችለትና ከበሽታውም ድኖ ወደ ጎንደር ሲመለስ ልጅቷን አስፈልጎ ሚስቱ አድረጋት፣ እቴጌ ምንትዋብ የምትባለው ከኢትዮጵያ ነገሥታት ሴቶች ተዋቂነት ያተረፈች ሆና ነበረ፡፡ ከቪከቶር የአጼ ሚናስ ወንድም የምትወለድ ከፖርቱጋል ወታደሮችም ዝርያ የነበራት ነበረች፡፡ ከምንትዋብ አጼ በከፋ አንድ ልጅ ኢያሱ ሁለተኛ ወልዷል፡፡

## 22. አጼ ኢያሱ 2ኛ

በ1730 ዓ.ም. አጼ በከፋ ሲሞት አጼ ኢያሱ 2ኛ ነገሠ፡፡ እናቱምሞግዚት ሆነች አጼ ኢያሱ 2ኛ በሥልጣን ሲቆይ የቻለው ብዙ ፈተናዎች በማለፍ አስከፊ የውስጥ ጦርነቶች በነበሩበት ጊዜ ነበር፡፡ በ1745 ዓ.ም. አቡን ክረስቶዶሎ ሲሞት ሌላ አቡን ለማስመጣት የተላኩ የኢትዮጵያ መልእክተኞች የደረሰባቸው ጥቃትና መዋረድ የኢትዮጵያ መንግሥት ክብር ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ወርዶ እንደነበረ የሚያሳይ ነበረ፡፡ ምፅዋ ሲደርሱ መልክተኞቹ ተዘረፉ፣ በመካ ሸሪፍ ትዕዛዝ በጅዳ ታሰሩ፡፡ ሲመለሱ አዲሱ አቡን ምፅዋ ሲደርስ ታስሮ ከፍ ያለ ገንዘብ ከፍሎ ብቻ ሲለቀቅ ችሏል፡፡ አጼ ኢያሱ የደረሰው ጥቃት የኢትዮጵያ ክብር የሚነካ ስለሆነ ለአርቂቆ ናይብ፣ በራስ ሚካኤል በትግራይ ሀገረ ገዥ በኩል ኢትዮጵያ ክብራን ለማስጠበቅ የምትወስደው እርምጃ እንዲነገረው አደረገ፡፡ ነገር ግን ለንጉሡ በደረሰው መረጃ መሠረት ራስ ሚካኤል ከናይብ ጋራ በምስጢር ተስማምቶ እንደነበረ የሚል ጥርጣሬ ስለተሰማ ንጉሡ ወንዶ በተባለው የእንደርታ ሀገረ ገዥ እየተረዳ ወደ ትግራይ ገስግሶ ሲመጣ ራስ ሚካኤል ግን ልዩ ተንኮል በመፍጠር አዘቦና ዶባ የተባሉ ሕዝቦች የትግራይ ምሥራቃዊ ክፍል እንዲወሩ ስላደረጋቸው አጼ ኢያሱ የተነሳበትን ዓላማ ትቶ እነሱም ወደመጡበት ለመመለስ ስለሄደ ወደ ራስ ሚካኤል የታሰበው ዘመቻ ለጊዜው ተደናቀፈ፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ራስ ሚካኤል ወደ ንጉሡ እንዲቀርብ የተሰጠው ትዕዛዝ አሻፈረኝ ስላለ እንደገና የንጉሡ ጦር ወደ ትግራይ መጥቶ ዓድዋ ተሰበሰበ፡፡ ራስ ሚካኤል ወደ አንድ ተራራ ሸሽቶ ሄደ፡፡ የማያዋጣው መሆኑን ስላወቀ ለንጉሡ አማላጅ በመላክ በትክሻው ድንጋይ ጭኖ ይቅርታ በመለመን ሲገባ እንዲገደል ተፈርዶበት ነበር፡፡ ይቅርታ ተደርጎለት በመጀመሪያ ታስሮ ከተያዘ በኋላ ከእስር ነፃ ወጥቶ ዋናው የዘውድ አማካሪ አደረገው፡፡ የሰፌ



ግዛት ሀገረ ገዥ አድርጎ ሹመት ሰጠው፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ራስ ሚካኤል ከንጉሡ ቀጥሎ ዋና የመንግሥት ሥልጣን ያዘ፡፡

## 23. ዘመነ መሳፍንት

### 1. ራስ ሚካኤል

ራስ ሚካኤል ትንሽ ቆይቶ ንጉሡን በቁጥጥሩ ሥር አዋለው፡፡ ከዚህ ዘመን ጀምሮ ክፍለሀገሮች የንጉሡ ነገሥቱ ሹመት በውድ ቢቀበሉም ራሳቸውን የቻሉ እንደነፃ መንግሥታት መተዳደር ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ ወደ ዘመነ መሳፍንት የተባለው ዘመን ተሸጋገረች፡፡ ብዙ የታሪክ ፀሀፊዎች ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ማእከላዊ መንግሥት አልነበራትም በተለያዩ መንግሥታት ተከፋፍላ ነበረ ይላሉ፡፡ ነገር ግን የንጉሡ ሥልጣን በመቀነሱ ይህ አባባል እውነት ያለው ቢመስልም በጥልቀት ለተመለከተው ሰው ግን ኢትዮጵያውያን ለዘውዱ አገዛዝና ለአንድነታቸው ጽኑ እምነት እንደነበራቸው ሁኔታዎች የሚጠቁሙ ነበር፡፡ ዋና ጥረታቸውና ምኞታቸው በጉንደር ከንጉሡ ነገሥቱ ጎን ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የሚቀመጥ ሰው ከማን ወገን ይመረጥ የሚል ካልሆነ በስተቀር ስለ ሀገር አንድነት የሚነሳ ክርክር አልነበረም፡፡ በግል ተዋርዶ ይታይ የነበረው የንጉሡ ክብር እንጂ የሀገሪቱ ክብርና ነፃነት አልነበረም፡፡ ዘመነ መሳፍንት በአፋጣኝ እንዲስፋፋ የአሟቻቹት ሁኔታዎች የእቴጌ ምንትዋብ ባል ኢያሱ መልመል የተባለው ከሞተ በኋላ ባልታወቀ ሁኔታ ምናልባት በቂም በቀል አጼ ኢያሱ 2ኛ ተገደለ፡፡ በዚሁ ጊዜ የመንግሥቱ አመራር እንደገና በእቴጌ ምንትዋብ እጅ ወደቀ፡፡ ለልጅዋ ለአጼ ኢያሱ ሁለተኛ እንዳደረገችው ሁሉ ለአልጋ ወራሽ ለነበረው ለልጅ ልጅዋ ዮሐንስ ዘውድ ጠባቂ የሚሆኑት ወንድሞቿ የቋራ ወገኖች በመንግሥት ሥልጣን እንዲኖራቸው አደረገች፡፡

አጼ ኢያሱ 2ኛ በእናቱ ወገኖች ከቋራ ድጋፍ እንዳገኘ ሁሉ ልጁ አጼ ዮአስም በእናቱ ከኦሮሞዎች የተዛመደ ከሰሜን ወሎ፣ የሚወለድ ስለሆነ በሁለቱ ወገኖች ለሥልጣን ሹኩቻ እየተካረረ ሲመጣ በመጨረሻ ግን ተጠቃሚ የሆነው የትግራዩ የቴምበን ተወላጅ ራስ ሚካኤል ነበር፡፡ ለሥልጣን ተቀናቃኞቹን የቋራና የየጁን አንድ በአንድ ከአሸነፋቸው በኋላ ራስ ሚካኤል ለው ልኮ ሊገድሉኝ አስተኩሶ ሳቱኝ በሚል ሰበብ አጼ ዮአስን ከሶ እንዲገደል ካደረገ በኋላ ብቸኛ መንግሥትን የሚቆጣጠር ሆኖ ቢቀርም የንጉሥ ዘውድ መጫን ስላልደፈረ የአፄ ኢያሱ ትልቁ 70 ዓመት ሰድሜ የነበረው ልጅ ዮሐንስ እንዲነግሥ አደረገ፡፡ ቆንጆና ወጣት የነበረችውን እህቱ ወለተ ሥላሴን ለሚሥትነት ንጉሡ እንዲያገባት አደረገ፡፡ ከራስ ሚካኤል ተቀናቃኞች አንዱ ከአፄ በከፋ ጀምሮ በታማኝነቱ ከፍተኛ ሹመት ያገኘው ከንጉሣውያን የሚወለድ ፋሲል የተባለው በራስ ሚካኤል አገዛዝ ላይ በ1768 ዓ.ም. ሸፍቶ ከተሸነፈ በኋላ እምልጦ ዳሞት ገብቶ ይኖር ነበር፡፡ ራስ ሚካኤል ወደ ዳሞት በፋሲል ላይ ለመዝመት ሲፈልግ ንጉሡ በሌሊቱ እንዳይከደው ስለጠረጠረው "አብሮ" እንዲዘመት ሲጠይቀው ንጉሡ ጦርነት ይጠላ ስለነበረ ከሚዘምት ወደ ወሕኒ አምባ ለመመለስ እንደሚመርጥ ስለገለፀለት መርዝ በመሥጠት ገደለው፣ በምትኩም አልጋ ወራሽ ልጁ ተክለሃይማኖት 2ኛ የ15 ዓመት ሰድሜ የነበረው እንዲነግሥ አደረገ፡፡ በዘመኑ በበሽታም የሚሞት ንጉሥ ቢኖር በመርዝ ተገደለ ተብሎ ይጠረጠር ነበር፡፡ በ1769 ዓ.ም. ራስ ሚካኤልና አዲሱ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ወደ

ዳሞት ዘምተው ድል ቢቀናቸውም ፋሲል ግን ሸሽቶ አመለጠ፡፡ የራስ ሚካኤል በጦርነቱ ያሳየው ጭካኔ ምክንያት ከሱ ጉን ተሠልፈው ከነበሩ መሪዎች ምሥት ተተናቃኞች በመተባበር ተስማምተው በራስ ሚካኤል ላይ አድም ስለመሰሉ፤ ራስ ሚካኤል ሊቋቋማቸው ስላልቻለ ከንጉሡ ጋራ ወደ አክሱም ሄዶ ተቀመጠ፡፡ እቴጌ ምንትዋብ የአፄ ዮአስ የልጅ ልጅ ለማንገሥ ሞከሩ ሦስት የቃል ኪዳን ጀነራሎች ግን ተክለሃይማኖትን በማውረድ ሱሲኒዮስ የተባለ የኢያሱ 2ኛ ልጅ እንዲነግሥ አውጀው ነበረ፡፡ በዚሁ ጊዜ ፋሲል ሜልታ በመግባት ሥልጣን ለመያዝ ሞከር ከሦስቱ የቃል ኪዳን ጀነራሎች ስላልተስማማ ዓላማው ሊከሸፍበት ችሏል፡፡ በዚህ ምክንያት ፋሲል አፄ ተክለሃይማኖት ሕጋዊ ንጉሥ መሆኑን አምኖ በይፋ ተቀብያለሁ አለ፡፡ ራስ ሚካኤልም በተፈጠረለት ሁኔታ በመጠቀም 40.000 የሚገመት ሠራዊት ይዞ ዲሴንበር 24/1770 ዓ.ም. ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋራ ሆኖ ጎንደር ገባ ሱሲኒዮስ ከጎንደር ሸሽቶ ወደ ቋራ አምልጦ ሄደ፡፡ ከዚያም የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ቀረ፡፡

## 2. ራስ ጉጁ

የራስ ሚካኤል ጭካኔ ከመጠን ያለፈ ነበር፡፡ አዝማሪዎች ሳይቀሩ ተገደሉ፡፡ አቡነ ሰላማ እንደ አንድ ተራ ወንጀለኛ ተገደሉ፡፡ እቴጌ ምንትዋብ እንደምትገደል የማይቀርላት መሆኑን ስላወቀች ጎጃም ትገኝ የነበረች አንድ ሴት ልጅዋ ጋራ ሄዳ ተቀመጠች፡፡ ተቃዋሚዎች ፋሲልና ሦስቱ ጀነራሎች ባሉባቸው በእቴጌ ምንትዋብ አስተባባሪነት በራስ ሚካኤል ሠራዊት ላይ ጦርነት ገጠሙ፡፡ ሳይሸናነፉ ስለቀሩ ራስ ሚካኤልም በዕድሜ ገፍቶ ስለነበረ ወደ ጎንደር ከተማ አፈገፈገ፡፡ ከሦስቱ የቃል ኪዳን መሪዎች አንዱ ጎሹ የጎንደር ራስ ሆኖ ተሾመ የራስ ሚካኤል ሠራዊት በጅምላ ወደ ተቃዋሚው ጦር ገባ፡፡ ንጉሡ ነገሥቱም አዲሱ የተፈጠረው ሁኔታ ተቀበለ፡፡ ራስ ሚካኤል ተይዞ ወደ ሸዋ በግዞት ተላከ፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ራስ ሚካኤል ምሀረት ተደርጎለት ወደ ድሮ ግዛቱ ወደ ትግራይ እንዲመለስ ተፈቀደለት፡፡ ጎንደር ከራስ ሚካኤል አገዛዝ ነጻ ስትወጣ እቴጌ ምንትዋብ ወደ ጎንደር ተመልሳ ቁስቋም በተባለው ቤቷ ገብታ ብዙ ሳትቆይ ዐረፈች፡፡ ራስ ሚካኤልም ብዙ ዓመት ሳይቆይ በርጅና ዐረፈ፡፡ ራስ ጎሹ እንደ ራስ ሚካኤል አፄ ተክለሃይማኖት ለስም ብቻ ንጉሥ ሆኖ እንዲቀመጥ ለማድረግ ሞክሮ ነበረ፡፡ ንጉሡ ግን ሥልጣን በእጁ ለማስገባት ስለሞከረ ራስ ጎሹ ንጉሡን ከሥልጣኑ ስላወረደው ወደ ገዳም እንዲገባ ተገደደ፡፡ ከዚህ በኋላ ደምበኛ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከ20 ዓመታት በላይ የቆየ የውድቀት ዘመን ከ1777 እስከ 1801 ዓ.ም. ተፈጠረ፡፡ በነዚህ ዓመታት ውስጥ 16 ነገሥታት ተቀያይረዋል፡፡

ከነዚህም ነገሥታት አንዱ የአፄ ተክለሃይማኖት ወንድም አፄ ተክለጊዮርጊስ 6 ጊዜ የንጉሥ ነገሥት ዘውድ ጭኖ 6 ጊዜ ወርዷል፡፡ የነገሥታቱ ዕጩዎች ይቀርቡ የነበሩና ለጎንደር ራስ ሥልጣን ሽኩቻ ይደረግ የነበረው በዳሞት፣ በትግራይ፣ በጎጃም በቤጌምድር፣ በትግራይም የቴምቤንና የእንደርታ ራሶች መካከል ነበር፡፡ ሸዋና ላስታ ተካፋይ አልነበሩም፡፡ በ1788-1789 ዓ.ም. 5 ነገሥታት በአምሥት ለሥልጣን ተፋላሚ ራሶች በእጩነት ለዘውድ ቀርበው ነበር፡፡ ሸዋ የመንግሥት ማእከል የነበረችው ኦሮሞዎች በሸዋና በጎንደር መሀከል በመስፈራቸው የተነሳ ራሷን አግልላ በጥሩ አስተዳደርና መሪዎች ትኖር ነበር፡፡ እንደዚሁም ላስታ ከመቶ ዓመት



በፊት ከማእከላዊ መንግሥት ተገልላ ለመኖር ትግል አድርጋለች ባለፉት 200 ዓመታት የአስተዳደሩ ማእከል ሚና የተጫወተችው ጎጃም ነበረች፡፡ ወደ ትልቁ ዳሞት፣ ጋፋት፣ እናሪያ፣ ከፋ፣ ከምባታ፣ ደቡብና ምዕራብ ክፍለተሀገሮች ለሚያስኬድ መንገድ በመተላለፍያ ታገለግል ነበር፡፡ የኦሮሞዎች ግፊት ለመግታት ከአባይ ወደ ደቡብና ምዕራብ ሕዝቦች ለመቆጣጠር እንደዚሁም በሃይማኖት ምክንያት ይደረግ የነበረው ፍልሚያ ሰፊው ተካፋይና ማእከል ነበረች፣ ከግራኝና ከኦሮሞች ጦርነት በኋላ በአፄ መለክ ሰገድና በአፄ ኢያሱ ትልቁ ወደ ደቡብ ምዕራብ የተደረጉ ዘመቻዎች ጎጃም በኩል አባይን አቋርጠው ነበር የሚሻገሩ፣ በቅርብ ጊዜም ራስ አሊ ወደ እናሪያ በጎጃም በኩል ዘመቻ ለማድረግ አስቦ ነበረ፡፡ ካርዲናል ማሳያ በኦሮሞ ሀገር የካቶሊክ ሚሲዮን ለማቋቋም ሲሄድ ያለፈው በጎጃም በኩል አባይን አቋርጦ ነው፡፡ እንደዚሁም ፈረንሳዊው ዳባዲ የተባለው ሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ ሰበብ ወደ እናሪያና ወደ ከፋ የሄደው በጎጃም መንገድ ተጠቅሞ ነው፡፡ በመጨረሻ ግን በዘመነ መሳፍንት ጎጃም ተከፋይነቷ ቀንሶ ታየቷል፡፡

## 3. የእንደርታ የየጁና የተምቤን መሪዎች ለሥልጣን ሹኩቻ

በዘመነ መሳፍንት የነገሥታቱ መሾምና መሻር ዋና አንቀሳቃሽ የነበሩ ኦሮሞች የሚባሉ የስሜን ወሎ መሪዎች የራስ አሊና በኋላም ልጁ የራስ ጉግሳ ወገኖች ነበሩ፡፡ ከትግራይ የእንደርታ መሪዎች ከየጁ ጋራ በመሆን የአፄ ተክለጊዮርጊስና የአፄ እስቲያኖስ ደጋፊ በመሆን በዙፋን እንዲወጡ ያደርጉ ነበር፡፡ በተቃራኒም የተምቤን የራስ ሚካኤል ወራሾች የእንደርታዎችን በመቃወም የተቀናቃኞች የአፄ በእደማርያምና አፄ ተክለሃይማኖት ደጋፊ በመሆን ዘውድ እንዲጭኑ ያደርጓቸው ነበረ፡፡ አፄ እስቲያስ ወደ ዙፋን ያስቀመጠው የጎንደር ራስ ሆኖ የነበረው ራስ አሊ ከእንደርታው ራስ ወ/ሥላሴ በመሆን ነበር፡፡ ራስ አሊ ሲሞት በምትኩ የየጁ ተወላጅ የጎንደር ራስ በመሆን አሁንም ከራስ ወ/ሥላሴ ጋር በመተባበር የአፄ እስትያስ ልጅ እጓለ በ1801 ዓ.ም. በዙፋን አስቀምጧል፡፡ ሁለቱ የእደርታና የየጁ መሪዎች የበላይነት ለመቀዳጀት ሁሉም ፍላጎት ስለነበራቸው ራስ ወ/ሥላሴ የንጉሥን ልጅ አገባ፡፡ የየጁ ራስ ጉግሳም በበኩሉ የተቃራኒው ሙከራ ለማኮላሸት ንጉሡ እህቱን እንዲያገባ አደረገ፡፡ ራስ ወ/ሥላሴ ከስሜኑ ራስ ወ/ገብርኤል ግንባር በመፍጠር የትግራይ መሪዎች የበላይነት የጨበጡ መሰሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ራስ ጉግሳ ወደ ራስ ሚካኤል ወገኖች በመጠጋት ሙከራቸው ሊያከሽፍባቸው ችሏል፡፡ የትግራይ መሪዎች እርስ በእርሳቸው አለመስማማት በራስ ሚካኤልም ጊዜ ከክፍለ ኢየሱስ ጋራ የተከሰተ ጉዳይ ነው፡፡

በራስ ሰባጋዲሥ በደጃዝማች ንጉሴና በደጃዝማች ጉብዜም ተከስቷል፡፡ ራስ ወ/ሥላሴ በ80 ዓመቱ ሲሞት በ1816 ዓ.ም. ራስ ጉግሳ ያለ ተቀናቃኝ ከዛ በኋላ በ1825 ዓ.ም. ሲሞት ልጁ ማሪዬ ወራሽ ሆነ፡፡ በ1818 ዓ.ም. አፄ እጓለ ወይንም ጓሉ ሞቶ ስለነበረ ዮአስ ሁለተኛ በምትኩ ንጉሥ ሆኖ ነበር፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላም የንጉሡ ልጅ ጅጋር ነግሦ፡፡ ከወልደ ሥላሴ ሞት በኋላ የመላው ትግራይ ገዢ ነኝ በማለት የዐጋሜው ሰባጋዲሥ ሥልጣኑ እያጠናከረ ከመምጣቱም በላይ ለጎንደር ራስ ለማሪዬ አልገብርም ለማለትም ደፈረ፡፡ አሁን ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የስሜኑ ገዥ ደጃች ውቤ የራስ ወ/ገብርኤል የልጅ ልጅ ነው፡፡

የራስ ወ/ገብርኤል ልጅ የራስ ጉግሣ ሴት ልጅ አግብቶ ውቤ ተወለደ፡፡ ደጃዝማች ውቤ የሰባጋዲስ ወገን ለመምሠል ልጁን ለሚስትነት ጠይቆ በ1830 ዓ.ም. አገባት፡፡ ሰባጋዲስና ማሬዬ ጦርነት ሲገጥሙ ግን ከማሬዬ ጋራ ሆኖ ሰባጋዲስን መውጋት ጀመረ፡፡ በጦርነቱ ማርዬ ቆስሎ ሞተ፡፡ ውቤም በበኩሉ ሰባጋዲስን በጦር ሜዳ ገደለው፡፡ በማሬዬ ቦታ ወንድሙ ዶሪ ሥልጣን ተረከበ ብዙ ሳይቆይ ግን ዶሪ ስለሞተ የራስ ማሬዬ ልጅ ራስ ዓሊ ሥልጣን ተረከበ፡፡ ደጃዝማች ውቤ የራስ ሰባጋዲስ ወገኖች ሥልጣኑን ሳይቀበሉ ለብዙ ዓመታት ይዋጉት ነበር፡፡ ፀረ ውቤ ተቃውሞ በሐማሴን በራስ ኃይሉ የሚመራ በቴምቤን በገብረ ሩፋኤል የሚመራ፣ በዐጋሜ በካሕሳይ የሚመራ የሰባጋዲስ ወገኖች ነበሩ፡፡ በ1839 ዓ.ም. ሦስቱም ወደ ዓድዋ ዘምተው ከተማዋን ያዟት፡፡ ነገር ግን ሦስቱም ጦርነት ገጥመው ስለተሸነፉ ይቅርታ ጠይቀው ከደጃዝማች ውቤ ጋራ ታረቁ፡፡ ደጃዝማች ውቤ በትግራይ ሥልጣኑን ሲያጠናክር ራስ ዓሊ የጉንደር ራስ ከትውልድ ሀገሩ ከሰሜን ወሎ የጁ በጌምድር መጣ፡፡ ራስ ማሬዬ ሲሞት ወንድሙ ራስ ዶሪ ሥልጣን ሲይዝ አፄ ጆጋርን ከሥልጣን አውርዶ አፄ ኢያሱ 4ኛ የአፄ ተክለሃይማኖት የልጅ ልጅ በዙፋን አስቀመጠ፡፡ አፄ ኢያሱ ራስ ዶሪ ሲሞት ሙሉ የንጉሥ ሥልጣን ለመያዝ ሞክሮ ነበር፡፡ ሆኖም ራስ ዓሊ ንጉሡን ከዙፋን አውርዶ በምትኩ ገብርክርስቶስ አስቀመጠ፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ አዲሱ ንጉሥ ሞተ፡፡ በምትኩ ራስ ዓሊ ሣህለድንግል ከአንድ ገዳም አውጥቶ የንጉሡ ነገሥት ዘውድ እንዲጭን አደረገ፡፡ አፄ ሣህለድንግል የቅባት ደጋፊ አይደለም ተብሎ ከሥልጣን እንዲወርድ ተደረገ፤ አፄ ገብረክርስቶስም ወደ ሥልጣን እንደገና ተመለሰ፣ ከ3 ወር በኋላ ግን ስለሞተ እንደገና ሣህለድንግል ወደ ሥልጣን ተመለሰ፡፡ ራስ ዓሊ ከጉሉ አማካሪው እናቱ ወ/ሮ መነን ነበረች፡፡ የቋራ አውራጃ በሽፍቶች ትተራመስ ስለነበረ የግብፅ መንግሥትም ግዛቱን ወደ ኢትዮጵያ ለማስፋፋት መግቢያ ቀዳዳ ሊያደርጋት እየሞከረ ስለነበረ ያንጃብብ የነበረ አደጋ ለማስወገድ ራስ ዓሊ ባለጋራው የነበረ ራስ ከንፉን ከእሥር ቤት አውጥቶ የቋራ አውራጃ ገዥ አድርጎ ሾመው፡፡ ራስ ከንፉ የተጣለበት አደራ በሚገባ በመወጣት የውጭ ወራሪዎች ግብፃውያን አባር የውስጥ ሽፍቶችንም በማጥፋቱ ባውለታ ስለሆነ ልጁ ካሳ አባቱ ሲሞት በአባቱ ቦታ ተሾመ፡፡ ራስ ዓሊና እናቱ መነን ጎጃምን ለማስገበር ባደረጉት ዘመቻ ካሳም ተካፋይ ሆኖ ነበረ፡፡ ራስ ዐሊ እንደ ቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት አባይን ተሻግሮ በመቋቋም ላይ የነበሩ ትናንሽ የኦሮሞ መንግሥታት ለማስገበር ግዛቱንም ለማስፋፋት እቅድ ነበረው፡፡ ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ራስ ካሳ በዘመቻው መሳካት ላበረከተው ሞያ ውለታው ለመመለስ የጎጃም ገዢ አደረገው፡፡ ራስ ካሳ ግን ሹመት እንዳገኘ ጎጃም ከሌሎች ክፍለሀገሮች በእኩል ደረጃ እንድትቀመጥ በመፈለግ ለራስ ዐሊ መታዘዙን አቆመ፡፡ ራስ ዐሊና እናቱ መነን ወደ ጎጃም በዘመቱ ወቅት በጎንደር ለሥልጣን ሽሚያ ረብሻ ስለተነሳ ዐማፅያንም ከንጉሡ ከሳሕለድንግል በመመሳጠር ሥልጣን ለመያዝ እቅድ እንደነበራቸው ስለተሰማ መነን በፍጥነት ከጎጃም መጥታ የዐመፁ መሪ የነበረው ወልደተክሌ በጦርነት አሸንፎ እስረኛ በማድረግ በድል አድራጊነት ጎንደር ገብታ አጼ ሳሕለድንግልን ከሥልጣን አወረደች፡፡ የታወቀው የኢትዮጵያ ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ ለድስት ጊዜ ንጉሡ ነገሥት ለመሆን የተመኘ ስድስት ጊዜ ከዙፋኑ የወረደ ዮሐንስ የተባለው የ23 ዓመት ዕድሜ የነበረው ልጁ በጎንደር ከተማ ይኖር ነበር፡፡ ራስ ዓሊና እቴጌ መነን አፄ ዮሐንስ ተብሎ በንጉሡ ነገሡት ዙፋን አስቀመጡት፡፡ ከመነን ጋራ ስለተጋባ ጀግናዋ ጦረኛዋ መነን እተጌ መነን ተብላ ንግሥት ሆነች፤ ሥልጣን ለማጋራት መብት አገኘች፡፡



## 6. ራስ ዐሊና ደጃዝማች ውቤ

ከዚህ በኋላም የተዋሀዶ እምነትም ለሁለት ወልድ ቅብና ፀጋ ልጅ የሚባሉ እምነቶች መከፋፈል ተፈጥሮ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት የጎጃም የቅባት ደጋፊ ሸዋ የፀጋ ልጅ ደጋፊ ትግራይና ሌላ የአማራ ክፍልም ወልድ ቅብ ወይም ካራ ደጋፊ በመሆን ወገን ለይተው ቡድኖች ተፈጥረው ነበር፡፡ ደጃዝማች ውቤ አቡነ ሰላማን የወልድ ቅብ ደጋፊ እንዲሆን ቢያደርገውም በሌሎች ራሶች ላይ ውግዘት እየሰማ ከውቤ ጋራ ብቻ በመቆም መላው ኢትዮጵያን በመቆጣጠር ስሥልጣን እንዲያበቃው ያቀረበለት ጥያቄ ተቀባይነት አላገኘለትም፡፡ አቡነ ሰላማ ከሌሎች ኢትዮጵያ ራሶች በምሥጢር ሲስማማ ውቤ ስለደረሰበት ከሀገር እንዲወጣ ፈረደበት፡፡ በኋላ ግን አቡኑ ይቅርታ በመጠየቁ ደብረ ዳሞት ገዳም ተወስኖ እንዲቀመጥ አደረገው፡፡ ከዚያም ሊያመልጥ ሲሞክር በውቤ እጅ ገባ፡፡ በዚሁ ጊዜ በደጃዝማች ውቤና በራስ ዐሊ መሐከል ጦርነት ተነሳ፡፡ የራስ ሀሊ ሚስት ሒሩት የደጃዝማች ውቤ እህት ስለነበረች ሁለቱ መሪዎች በጋብቻ የተሳሰሩ ነበሩ፡፡ ደጃዝማች ውቤ መሐል አማራ በድል አድራጊነት ጦርነት ከፍቶ ገባ፡፡ የጎጃም ራስ ጉሹም ከጎኑ ከተሰለፈ እህቱ ራስ ዐሊ ሲሸነፍ ለእሱ እንደሚደራት ቃል ገብቶለት ነበር፡፡

አጼ ዮሐንስ 3ኛው ለደጃዝማች ውቤ ድጋፍ ሰጥቶ ነበር፡፡ የትግራይና የጎጃም ሠራዊት በ1842 ዓ.ም. በቤጌምድር ደብረታቦር አጠገብ ሰፈረ፡፡ የራስ ዐሊ ጦር ስለተከበበ ተዋጊዎቹም የቂሶች ውግዘት በመፍራት ስለከዱት በቀላሉ ተሸንፎ ራስ ዐሊ በአንድ ገዳም ተቀመጠ፡፡ እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ራስ ሀሊ ስሙ እንደሚያመስክተው እስላም አልነበረም፡፡ ክርስቲያን በመሆኑ በአንድ ገዳም ገብቶ ለመኖር ችሏል፡፡ ደጃዝማች ውቤ አቡነ ሰላማና አጼ ዮሐንስ 3ኛ. ድላቸውን በሚያከብሩበት ወቅት ዐሊጋዝ በተባለው በራስ ዐሊ አጎት የሚመራ የራስ ሀሊ ደጋፊ ጦር እጁን ለመስጠት በመምሰል በተጠንቀቅ ያልቆመ ሠራዊት ሰፈር ገብቶ ተቃውሞ ሳይገጥመው ሶስቱ ሰዎችን በቁጥጥሩ ሊያውላቸው ራስ ጉሹ የተሰጠችውን ሚስት ትቶ ወደ ጎጃም ሸሽቶ ገባ፡፡ ራስ ዐሊ ከነበረበት ቦታ ገዳም ተጠርቶ እየተጠራጠረ ሲመጣ ተቀናቃኙ ታስሮ አገኘው ከሚስቱ ጋራም በደህና ተገናኘ፡፡ ራስ ዐሊ በቂም በቀል አልተነሳሳም፤ ሁለቱ መሪዎች ታረቁ ደጃች ውቤ ወደ ቀድሞ ሥልጣኑ እንዲመለስ ፈቀደለት፡፡ ሁለት ሺህ ብር ቅጣት እንዲከፍል፤ በየዓመቱ ግብር እንዲከፍል አድርጎ ወደ ትግራይ ተመለሰ፡፡

ትግራይ ውቤ መታሰሩ ሲሰማ ሌላ ሰው በሥልጣን ወጥቶ ነበር፡፡ ደጃዝማች ውቤ በራስ ዐሊ በመታገዝ ተቀናቃኙ ሊያሸንፍ ችሏል፡፡ አጼ ዮሐንስ 3ኛ ከራስ ዐሊ ይቅርታ አገኘ፡፡ አቡነ ሰላማ ይቅርታ አግኝቶ በጎንደር እንዲቀመጥ አቡነ ሰላማና ራስ ጎሹ በሚሥጢር ስምምነት ማድረጋቸውን ራስ ዐሊ ሲሰማ አቡኑ ተከሶ ፍርድ አቀረበው፡፡ አቡኑ ጥፋተኛ ስለነበረ ይቅርታ ጠይቆ ይቅርታ ቢደረግለትም እቴጌ መነን ግን የቤተክሕነት ሰዎች እንዲያጋልጡት ታደርግ ነበር፡፡ አቡኑ በጎንደር በይፋ የቅባት ደጋፊ መሆኑን ገልጾ፤ ከራስ ጎሹም ግንኙነት ፈጠረ፡፡ ከአንድ እምነት ወደ ሌላ እምነት በመቀየሩ ቀሶቹም ይወቅሱት ጀመሩ፡፡ አቡኑ ሰላልታረመ ጉባኤ ተደርጎ ወደ አንድ እምባ እንዲቀመጥ አደረጉት፡፡ ቀጥሎም በመደበኛ ፍ/ቤት ከሀገር እንዲባረር ተወሰነበት፡፡ ራስ ዐሊ ከሀገር ከማባረር ፍርዱን አሻሽሎ በጎንደር ቤተመንግሥት እንዲኖር አደረገው፡፡

አቴጌ መነን ግን ሞት እንዲፈረድበት ፈልጋ ነበር፡፡ በመጨረሻ በማሻሻል ከሀገር እንዲወጣ አደረገችው፡፡ በዚሁ ጊዜ አቡነ ሰላማ ከደጃዝማች ውቤ ጋራ ከመስማማት ሌላ አማራጭ አልነበረውም፡፡ በፍጥነት ሸሽቶ ከሕዝቡ ስድብ እየደረሰበት ወደ ደጃዝማች ውቤ ሄዶ ሲቀመጥ የወልድ ቅብ እንደሚከተል በመግለፅ ለ3ኛ ጊዜ ሃሳቡን ቀየረ፡፡ አቡነ ሰላማ ከጎንደር ከመባረሩ በፊት በጎጃም ቅሬታ አሳድሮ ስለነበረ ራስ ጎሹ በሕዝቡ ተገፋፍቶ ሠራዊቱን ይዞ ወደ ጎንደር ገብቶ ከተማዋን የእጨጌ ቤትን ዘረፈ፤ እጨጌም ለመሸሽ ጊዜ ስላላገኘ ወደ አንድ ተራራ ተወስዶ ታሰረ፡፡ ደጃዝማች ውቤ እንደ ልማዱ ከ5 ዓመት በኋላ ራስ ዐሊን በመካድ የቤጌምድር የላስታ የየጁ ራስ ጎሹን በመስበክ በቋራም ዐመፅ እንደሰፈነ ስለሚያውቅ በ1847 ዓ.ም. ወገራን መውረር ጀመረ፡፡ ነገር ግን ግጭቱ ቆሞ በሁለቱ መሪዎች እርቅ ወርዶ እስከ 1851 ዘለቀ፡፡ በዚሁ ዓ.ም. ውቤ በራስ ዐሊ ላይ ዘመተ፤ ሆኖም ውጤት አላገኘም፡፡ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸው ለማዋል ጥረታቸው አላቋረጡም ነበር፡፡ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በኋላም ጣሊያኖች በሌላ የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚያደርጉ ሁሉ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ይመርጡት የነበረ ዘዴ ያለደም መፋሰስ የበላይ ጠባቂ ለመሆን ውል ለማስገባት በመሞከር ነበር፡፡ በዚህ ሙከራ በመጀመሪያ በኃይል የደከሙ እንግሊዞች ነበሩ፤ ፈረንሳዮች ከእንግሊዞች ጋር መጋፋት የማያዋጣቸው መሆኑን ስላወቁ በኢትዮጵያ ጣልቃ ገብነታቸው እየቀዘቀዘ መጡ፡፡ በ1841 ዓ.ም. ሻለቃ ሃሪስ የተባለ እንግሊዛዊ ከመንግሥቱ ተልኮ ወደ ሸዋ ንጉሥ ሣህለሥላሴ መጥቶ ውል ተፈራረመ፡፡

በ1843 ዓ.ም. ፕላውደን የተባለ እንግሊዛዊ እንዳጋጣሚ በግብጽ ሀገር በግሉ የአባይን ወንዝ ለማጥናት ወደ ኢትዮጵያ ለመሔድ ተዘጋጅቶ የነበረ ቤል የተባለው ከአንድ እንግሊዛዊ ጋር ተገናኝተው አብረው ስለሔዱ ጎንደር ሲደርስ እስከ 1847 ዓ.ም. ከራስ ዐሊ ጋር ስለተቀመጠ፤ ወደ ሀገሩ በሚመለስበት ጊዜ ራስ ዐሊ ለንግሥት ቪክቶሪያ ስጦታ ለመላክ ከእንግሊዝ መንግሥት ለመቀራረብ ስለፈለገ ፕላውደን ብዙ ዐመታት በኢትዮጵያ የቆየ በመሆኑ ለእንግሊዝ መንግሥት ለማስረዳት ችግር አልገጠመውም፡፡ በጊዜው የነበረ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ፓልሜርስቶን በ1848 ዓ.ም. ፕላውደንን በምጽዋ፤ በኋላም በመላው ኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቆንስል ሹሞ ላከው፡፡ ፕላውደን በመጀመሪያ ከራስ ዐሊ ጋር በኋላም ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር አማካሪ በመሆን የለዘብተኝነት አቋም እንዲይዙ ረድተዋቸዋል፡፡ ፕላውደን ተቀማጭነቱ በደብረ ታቦር በማድረግ የምጽዋ ቆንስል ግን ባሮኒ የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ መድቦ ባሮኒም የእንግሊዝ ቆንስል በመሆን እስከመጨረሻ በታማኝነት አገልግሏል፡፡

በ1849 ዓ.ም. በራስ ዐሊና በፕላውደን መካከል በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኩሳት የእንግሊዝ መንግሥት ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ስምምነት ውል ተደረገ፡፡



# ምዕራፍ 4

# ኢትዮጵያ ከሰለሞናዊ አገዛዝ በኋላ

## 1/ አጼ ቴዎድሮስ

ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ዓይነት ሁኔታ እያለች አንድነት የላትም አንድነቷን የሚመሰርት ጠንካራ ገዥ /ንጉሥ/ ያስፈልጋታል ብሎ ማሰብ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ በውስጥ አስተዳደር የራስ ዐሊና የእቴጌ መነን እንደ ማእከላዊ የሚቆጠር መንግሥት በደጃዝማች ውቤና በራስ ጎሹ ላይ ለዘብተኝነት ያሳየው አቋም የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ በማስከበር ለወደፊት አስተዳደሩ የማሻሻል አቅጣጫ የሚጠቁሙ ነበሩ፡፡ ከግብጽ ሊሰነዘሩ ለሚችል ወረራ መመከት እንደሚችልም በደጃዝማች ክንፉ ጊዜ አሳይቷል፡፡ በውጭ ፖሊሲም በለዘብተኛነትና በእኩልነት የተመሠረተ ጥሩ አዝማሚያ የሚከተል ይመስል ነበር፡፡ የንጉሠ ነገሥቱና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን በሕግ ለመወሰን ቢቻል ኢትዮጵያ ጥሩ አማካሪ ቢኖራት ወደ ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አገዛዝ ዲሞክራሲ ቀስ በቀስ በመሸጋገር ይቻል ነበር፡፡ የክፍለ ሀገር ራሶች ሁሉ በዘውዳዊ ማእከላዊ መንግሥት የሚያምኑ ስለነበሩ የኢትዮጵያ አንድነት በአደጋ ላይ አልወደቀም፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ አንድነት መሥራች የአጼ ቴዎድሮስ ክስተት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ሥልጣን ለመያዝ ቢችልም እንደሌሎች ከእሱ በፊት የነገሡት ንጉሠ ነገሥት በማስቀመጥ እንደጠቅላይ ሚኒስትር ዓይነት ሙሉ ሥልጣን በእጁ በማስገባት ማስተዳደር ይችል ነበር፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ለመያዝ ከፈለገም የሰለሞን ዘር ነበረው ስለተባለለት ማስረዳት መቻል ነበረበት፡፡ ይህ ካልሆነም እንደ አጼ ዮሐንስና አጼ ሚኒልክ በሰላማዊ መንገድ አስተዳደር መመስረት ነበረበት፡፡ አጼ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነት አመጣ እያልን እስከ ዘመናችን ድረስ ማወደስ የዋህነት ነው፡፡ በኃይልም በዘዴም ጭምር እነ ራስ ዐሊ ከሰባት ትውልድ ጀምሮ ሀገርን የማስተዳደር ልምድ የነበራቸው ያልቻሉት የአጼ ቴዎድሮስ በኃይል ብቻ ተጠቅሞ አንድነትን ይፈጥራል ማለት የዋህነት ነው፡፡

አጼ ቴዎድሮስ እንደ አጼ ሱስንዮስ ሁልጊዜ ድል አድራጊ ነበረ፡፡ ነገር ግን ሰውን በመግደል ብቻ ሀገርን ማስተዳደር አይቻልም፡፡ እንኳን የውስጥ ጠላት የውጭ ጠላትም ሰብእዊነትና ምህረት ጥሩ አስተዳደር ካልታከለበት በኃይል ብቻ መጠቀም በቂ አይሆንም፤ ጀግንነትም አይደለም፡፡ አጼ ቴዎድሮስ የቋራ ሽፍታ በነበረበት ጊዜ ዓላማው የውጭ ወራሪዎች ግብጾችን ለመዋጋት ነበር፡፡ ሥልጣን እንደያዘ ግን የውጭ ጠላትን ለመዋጋት ጊዜ አላገኘም፡፡ በሀገራችን የሚታየው አጼ ቴዎድሮስ እንደ ብሔራዊ ጀግና የአንድነታችን አባት እያሉ መገመት ከታሪካዊ ስሀተት የመነጨ ነው፡፡

በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ለኢትዮጵያ የባሰ መከፋፈል እንጂ አንድነቷን አልተከበረም፡፡ አጼ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ልትቋቋመው የማትችለው ከውጭ ሀገር ሠራዊት ከታላቅ የእንግሊዝ መንግሥት አስፈላጊ ሳይሆን እንድትደፈር እና እንድትወረር አድርጓታል፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት ዓላማው ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ይሁን ወይም ወዳጅ ሀገር ለማድረግ ይሁን ባይታወቅም አጼ ቴዎድሮስ አስፈላጊ ሳይሆን ኢትዮጵያ



La presa di Magdala chiude vittoriosamente la spedizione inglese di Sir Napier nel 1868 (da uno schizzo dal vero)

የአፄ ቴዎድሮስ አስከሬን በእንግሊዞች ሲፈተሽ





ከእንግሊዝ መንግሥት ወደ ሕገ መንግሥታዊ አስተዳደር ለመሸጋገር እንድትችል ጠቃሚ ምክር ለመስጠት ይችል ነበር። የኢትዮጵያ አንድነት የነፃነትና ክብር በይበልጥ የተጠበቀ በአጼ ዮሐንስና በአጼ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው። በሀገራችን የአጼ ቴዎድሮስ ዝና ከፍ ለማድረግ እንደ ኢትዮጵያዊነት ምልክት መውሰድ የተለመደ ሆኖዋል። የታሪክ መጻህፍቶች ተደርሰዋል፣ መንገዶች፣ አደባባዮች በቴዎድሮስ ተሰይመዋል፣ በትያትርም አጼ ቴዎድሮስ ተወድሷል። የአጼ ቴዎድሮስ አስተዳደር በአድናቆት ከተቀበልን ማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ጠብመንጃ አንግቦ የአስተዳደሩ ጥራት ሳይገመገም መንግሥቱን ገልብጦ በኃይል የራሱ አስተዳደር ከመሰረተ ሁለገብ ድጋፍ ከሕዝብ ማግኘት አጠራጣሪ ይሆናል። አጼ ቴዎድሮስ ሃይማኖት አንድነት ለመመስረትም ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ብዙ ሳይቆይ ሃይማኖት አባቶች ዋናው የእስክንድሪያ ጳጳስ ሳይቀር ተቃውሞ ገጠመው። እንግሊዞች በፕላውደን አማካይነት ቴዎድሮስን ሲደግፉ ፈረንሳዮች በካቶሊክ ሚሲዮናዊያን መሪ በአቡነ ደ ያኮቢስ አማካይነት ዋናው የአጼ ቴዎድሮስ ተቃራኒ መሪ ደጃዝማች ንጉሤን ይደግፍ ነበር። ሁለቱ ሀገሮች ተስፋ ከመስጠታቸው አልፎ ተጨባጭ ጠቃሚ ድጋፍ አይሰጧቸውም ነበር። ቡተስይ ንጉሤ 12 ሺ የፈረንሳይ ወታደሮች እሱን ሥልጣን ለማስወጣት ይላኩልሃል የሚል ተስፋ አላሰፈም። በመሐሉ የተጐዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ሞንሲኞር ደ ያኮቢስ ለፈረንሳይ መንግሥት በጻፈው ደብዳቤ "በቴዎድሮስ እና በንጉሤ መሐል የሚደረገው ፍልሚያ ስወደፊት የዚህች ሀገር ዕድል የሚወስን ስለሆነ ደጃዝማች ንጉሤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ባይ አጼ ቴዎድሮስን ለመቋቋም እንዲችል ከፈረንሳይ መንግሥት የጦር መሣሪያና የሚቻል ከሆነም ወታደሮች እንዲላኩለት በመልዕክተኞቹ አማካይነት ጠይቋል" የሚል ይገኝበት ነበር። ብዙ ሳይቆዩ የዚህ ሁሉ ትርኢት ተዋንያን የነበሩ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አጼ ቴዎድሮስ ብቻ ቀረ። አጼ ቴዎድሮስ ከውቤ ልጅ ብዙነሽም ተጋባ። ፕላውደን ወደ ሀገሩ ሊመለስ ሲል በአጼ ቴዎድሮስ ላይ በዐመፁ ሽፍቶች ተገደለ። ንጉሤ የፈረንሳይ መልዕክተኞችን ለመቀበል በሚዘጋጅበት ወቅት በአጼ ቴዎድሮስ እጅ ገብቶ ተገደለ። ብዙ ሳይቆይ አቡነ ደ ያኮቢስ በበሽታ ሞተ። የአጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ በሥልጣን መውጣት ለኢትዮጵያ አንድነት ያስገኘው ጥቅም የለም። የኢትዮጵያ አንድነት ከዘመነ መሳፍንት አስተዳደር ጊዜ ጀምሮ ልምድ የነበራቸው የራስ ዐሊና እቴጌ መነን ሥልጣን ማጠናከር የበለጠ ይከበር ነበር።

ርዕሰ ብሔር የአንድነት ምልክት የሆነው የዘውድ አገዛዝ ሳይነካ ፈላጭ ቆራጭነት ለንጉሠ ነገሥቱ ሳይሰጥ በመሳፍንት ዘመን የነበረው አስተዳደር በማሻሻል ብቻ የኢትዮጵያ አንድነት ይከበር ነበር። ይህ ባይቻልም ሌሎች አማራጮች ነበሩ፣ ሀገሪቱን መምራት በቴዎድሮስ እጅ መውደቅ አልነበረበትም። ከብዙ ትውልድ ጀምሮ ብዙ ልምድ የነበራቸው ሌሎች ነበሩ። በእጩነት ባይቀርቡም ከንጉሠ ሣህለ ሥላሴ ጀምሮ በሸዋ የነበሩ ብዙ የአስተዳደር ልምድ የነበራቸው ነበሩ። ባለፈው ታሪኩችን በመውሰድ ሸዋ ስመ ጥሩ ነገሥታት እንደ አጼ እምደጽዮን የመሳሰሉት የተፈጠሩባት ስለሆነ አሁንም ኢትዮጵያን መምራት ማንነት ከማይታወቀው ከቴዎድሮስ በይበልጥ የሚመረጡ መሪዎች ልታቀርብ ትችል ነበር። ጎጃም ወደ ደቡብና ወደ ምዕራብ ክፍትተ ሀገራት ለመሔድ መተላለፊያ መንገድ ስለነበረች ከአጼ መላክ ሰገድ ጀምሮ ከዚያም በፊት በዮዲት ጊዜ አርሞዎችን ለመከላከል ይደረጉ የነበሩ ትግሎች ማእከል ስለነበረች አባይን ተሻግሮ ወደ

ደቡብና ምዕራብ የሚደረጉ ዘመቻዎች መተላለፊያ መንገድ ስለነበረች በሌላ በኩልም በሃይማኖት ክርክሮች እንደ ማእከላዊ ሆና ተሳትፎ ስለነበራት ማእከላዊ መንግሥትም ለማስተዳደር ብቁ የሚያደርጉት ነጥቦች ስለነበራት መሪዎች ሊታፈሩ የምትችል ክፍለ ሀገር ነበረች፡፡ በትግራዩ ደጃዝማች ውቤ ቤተሰብ ከሰባት ትውልድ ጀምሮ የአስተዳደር ልምድ ያካበቱ ለዘብተኛ መሪዎች ነበሩ፡፡

ቴዎድሮስ ግን የሽፍቶች መሪ ከመሆን ተነስቶ ነው የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን የያዘው፡፡ በቴዎድሮስ ዘመን ኢትዮጵያ በእንግሊዝ ጦር ስትወረር እንኳን አንድነቷ ሊከበር ሕልውናዋም በአደጋ ላይ ወድቆ ነበር፡፡ በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ የእንግሊዝ ወራሪ ሠራዊት ኢትዮጵያውያን ለሰተባበሩት ዘመቻውን በተሳካ ሁኔታ በመፈጸሙ ግብጻውያን ጣሊያኖች በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ እንዲያካሂዱ ስላደፋፈራቸው ኢትዮጵያ በወራሪዎች እንድትደፈር መንገድ ከፋች ሆኖዋል፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ስንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ስመያዝ የቢታው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች በሙሉ ተባብረው ሊያጠፉት ያስሰፋበት ኃይል በመበጣጠስ ነበር፡፡ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ አንድነት ለማስፈን እንደ ትንቢት ሲነገርለት ነበረ ስለተባለ የሕዝብ ድጋፍ ነበረው፡፡ በጸረ ቴዎድሮስ ተሰልፈው የነበሩ ኃይሎች መላው ኢትዮጵያ ናት ለማለት ይቻላል፡፡ እንደ ማእከላዊ መንግሥት ይቆጠሩ የነበሩ ከራስ ዐሊና ከእቴጌ መነን ሌላ የጸረ ቴዎድሮስ ጓዶች የጎጃሙ ራስ ጉሹ የትግራዩ ደጃዝማች ውቤ የሸዋው ኃይለመለኮት ነበሩ፡፡

የተባበሩት የጠሩ ጓዶች፣ግን ቴዎድሮስ እንደተመኘው ብዙ ሳይቆዩ ተበታተኑ፣ በዚህም ጊዜ ከሁሉም ኃይለኛ ተብሎ ተፈርቶ የነበረ ራስ ጎሹን ቴዎድሮስ በቡሬምባ ተራራ አጠገብ ደምቢያ ሰብቻው ጦርነት ገጥሞ በራስ ጎሹ ላይ ኖቬምበር 13 ቀን 1852 ዓ.ም. ድል ተቀዳጀ፡፡ ኤፕሪል 5 1853 ዓ.ም. ራስ ዐሊ 130 ሺ የሚገመት ጦር ዘመ ምራት ከቴዎድሮስ ሲሰ የማያህል ሠራዊቱ ጦርነት ገጥሞ በጉራጎራ ሳይቀናው ስለቀረ ለሁለተኛ ጊዜ ጁን 23 ቀን 1853 ዓ.ም. ጦርነት ገጥሞ ምንም እንኳን በጀግንነት ቢዋጋም ወታደሮቹ ለለከዱት የራስ ጎሹ ልጅ ብሩም አስቀድሞ ከቴዎድሮስ ጉን ለመሰለፍ ስለወሰነ ደጃዝማች ውቤም ከጦር ሜዳ ራሱን ስላገለለ ራስ ዐሊ ተሸናፊ በመሆን ሸሽቶ ወደ ደራ ሄደ፡፡ ቴዎድሮስ ወደ ትግራይ እና ወደ ሸዋ ከመዝመቱ በፊት ሜይ 1/1854 ዓ.ም. ወደ ጎጃም ዘምቶ በራስ ብሩ ላይ የራስ ጎሹ ልጅ ጦርነት ገጥሞ በቀላሉ ድል ተቀዳጅቶ ራስ ብሩ ተማርኮ በወታደሮች ፊት በእሳት እንዲቃጠል አደረገው፡፡





አጼ ቴዎድሮስ ሎርድ ናፒር

LORD NAPIER.



ፌብሯሪ 3 ቀን 1855 ዓ.ም ወሳኙ ጦርነት በደጃዝማች ውቤና በቴዎድሮስ መሐል በሰሜን፣ ደራጌ በተባለው ቦታ ተካሂዶ በመጀመሪያ የጦርነቱ እንቅስቃሴ የነበረው አሸቱ የተባለው የውቤ ልጅ ከተገደለ በኋላ ደጃ ዝማች ውቤ በከሃዲው አስታራቂ ይመስል የነበረው ደጃዝማች ውቤ በኩኩቤ ተይዞ ለቴዎድሮስ ስለተሰጠ ቴዎድሮስ አሸናፊ በመሆን ንጉሠ ነገሥት እየተባለ በወታደሮቹ ታጅቦ በደራጌ ቤተክርስቲያን በአቡነ ሰላማ እጅ ካሣ የነበረው ስሙ ቴዎድሮስ በመባል የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭኗል።

ሰፕቴምበር 1858 ዓ/ም ወደ ወሎ መቅደላ አጠገብ ደርሶ ከወርቂቱ ወታደሮች ጦርነት ገጥሞ ከአሸነፋቸው በኋላ ዲሰምበር 1656 ዓ/ም ሸዋ ገብቶ ጦርነት ገጥሞ ንጉሥ ኃይለመለኮት በበሽታ ሊሞት ወታደሮቹ አንድ ቀን ተዋግተው ስለተበታተኑ ቴዎድሮስ በቀላሉ ድል ተቀዳጅቶ የሸዋ ገዥ መርዕድ አዝማች ኃይሉ በማድረግ የኃይለመለኮት ወራሽ ልጅ ምኒሊክ ከሸዋ ወስዶ መቅደላ የቤተሰብ እንክብካቤ ተደርጉለት በክብር እንዲቀመጥ አደረገው። አጼ ቴዎድሮስ ከ1856 ዓ.ም ጀምሮ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ከጫነ ጀምሮ በመቅደላ በእንግሊዞች ተከቦ በ1868 ዓ.ም ራሱን እስካጠፋ ድረስ ኢትዮጵያ ያሳለፈችው ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ የስቃይ ዘመን ነበር።

ለፀመጽ ያልተነሳ ክፍለ ሀገር አልነበረም። በሸዋ የዐመጹ መሪ የነበረው አቢዬቶ ሰይፉ ከ600 ግብረ አበሮቹ ጋራ ተይዘው የቀኝ እጃቸውና የግራ እግራቸው እንዲቆረጡ አደረገ። በትግራይ ደጃዝማች ውቤ ከታሰረ በኋላ የውቤ ልጅ ጓንጉል ጦርነቱን ቀጥሎ ነበር። ቴዎድሮስ ግን ውቤን ወደ ጦር ወስዶ ጓንጉል እጁን ካልሰጠ አባቱ እንደሚገደል ሲነገረው ጓንጉል እጁን ሲሰጥ ሁለቱም አባትና ልጅ በአንድ አምባ እንዲታሰሩ አደረጋቸው። በዚሁም ሞቱ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በትግራይ የጸረ ቴዎድሮስ ጦርነት መሪ የሆነው የደጃዝማች ውቤ የወንድም ልጅ ደጃዝማች ንጉሴ ነበር።

ፀረ ቴዎድሮስ ትግል የተካሔደው ከሁሉ የባስ በትግራይ ነበር። በ1856 ዓ/ም ደጃዝማች ንጉሴ በትግራይ በቴዎድሮስ የተሾሙ ሰዎች በማሸነፍ መረብ ምላሽ፣ መላው ትግራይ፣ ሰሜን፣ ወልቃይት፣ ላስታ በቁጥጥሩ ለማድረግ ችሎ ነበር። አጼ ቴዎድሮስ በመሐሉ በሌላ ክፍለ ሀገር ስለነበረ ጦርነቱ ጋብ ካለ በኋላ በ1861 ዓ.ም ንጉሴን ማሳደድ እንደገና በመቀጠል በመጨረሻ ንጉሴ ወደ ነበረበት ወደ ወልቃይት በመሔድ የንጉሴ ቅርብ ጓደኞች የሆኑ አስረው ከአንድ ወንድሙ ጋር ለቴዎድሮስ ስላ ስረከቡት ቴዎድሮስ ቀስ በቀስ በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲሞቱ አደረጋቸው። ከንጉሴ ተከታዮች ሰባት ሺህ የሚገመቱ ተገድለዋል። በትግራይ የመጨረሻ ፀረ ቴዎድሮስ ዐመጽ መሪ የሆነው በ1865 ዓ/ም ዋግሹም ጉበዜ ለስልጣን ያበቃው ለወደፊቱ አጼ ዮሐንስ አራተኛ የሆነው በዝብዝ ካሣ ነበር።

አጼ ቴዎድሮስ ንጉሴን ማሳደድ አጊዜው ባቋረጠበት ጊዜ በአማራ ጐንደር በልጅ ገራድ የሚመራ ዐመጽ ተነስቶበት ነበር። የአጼ ቴዎድሮስ ሊቀ መንኳስ በነበረው ከእንግሊዙ ቤል ጋር ሆኖ ነበር የዘመተው። ልጅ ገራድ አጼ ቴዎድሮስን ለመግደል ሞክሮ ቤል ሊገድለው የገራድ ወንድም ቤልን ገደለው። በመጨረሻም አጼ ቴዎድሮስ የቤልን ገዳይ

በሽጉጡ በመግደል የጦርነቱ ፍጻሜ ሆነ። 500(አምስት መቶ) እስረኞቹ አብረው ተገደሉ። በጉጃም ፀረ ቴዎድሮስ ፀመጽ መሪ የሆነው በቴዎድሮስ የተሾመው በተድላ ጓሉ ነበር።

ጦርነት ገጥመው ተድላ ጓሉ በተሸነፈበት ጊዜ ስምንት ሺህ እስረኞች በቴዎድሮስ እጅ ገብተው በሙሉ ተገደሉ። በተጨማሪም አራት መቶ ሹማምንቶችና ባላባቶች ተመርጠው ተወስደው ተገደሉ። የዋግሹም ጉበዜና የበዝበዝ ካሣ ምሣሌ በመከተል ምኒሊክም ከመቅደላ ሸሽቶ ሸዋ ገብቶ ስልጣን ለመያዝ በቅቶ ነበር። እነዚህ ሁሉ ጸረ ቴዎድሮስ አመጸኞች ቴዎድሮስን ለመዋጋት ወደ ኢትዮጵያ የገባ የእንግሊዝ ሠራዊት እንደነጻ አውጭ ነበር የተቀበሉት። የቴዎድሮስ ፍጻሜም በደስታ ነበር የተቀበሉት። አጼ ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥቱ በሕይወቱ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በውጭ ሀገር ዜጐች ጠላቶች እንጂ ወዳጆች አላፈሩም።

## 2. አጼ ዮሐንስ

በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የአጼ ቴዎድሮስ የግፍ አገዛዝ ቀርቶ በተለይ በጉራዕ ጦርነት ጊዜ እውነተኛ የኢትዮጵያ አንድነት የታየበት ነበር። የኢትዮጵያ አንድነት መስራች ከቴዎድሮስ ይልቅ ዮሐንስ መሆን ይገባዋል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጸረ ግብጽ ወራሪ ሠራዊትን በአንድነት የተዋጋ በት ጊዜ ነበር። ምኒሊክ ሳይቀር ባለፈው በጉዳጉዲ ጦርነት ከግብጾች ጋር አብሮ ቆሞ የአጼ ዮሐንስ ጦር በጀርባው ለመውጋት ውል አድርጐ የነ በረው በጉራዕ ጦርነት ጊዜ ግን የሕዝብ ግፊት ስለበዛበት ከአጼ ዮሐንስ ጋር ሰመሰለፍ ቃል ገብቶ አነስተኛ ተዋጊዎችም ልኮ ነበር። በግብጾች ላይ በሰሜን በጉዳጉዲና በምስራቅ በአውሳ ጦር ግንባር የተደረጉ ጦርነቶች በሚመለከት ተክለጻዲቅ መኩሪያ «በአጼ ዮሐንስና[1] የኢትዮጵያ አንድነት» በሚለው መጽሐፉ የሰጠው የታሪኩ አገላለጽና ጣሊያኖች ከሚሰጡት አገላለጽ አንዳንድ ልዩነቶች ይታያሉ። በሰሜን ጦር ግንባር የግብጽ ጦር የሚመ ራው በራውፍ ፓሻና በጠቅላይ ሚኒስትሩ የልጅ ልጅ በምክትሉ የዴንማርክ ተወላጅ አንድሩፕ ነበሩ። በምስራቅም በሙንዚንገር ራሱ ነበር። አቶ ተክለ ጻዲቅ ኩሩስ የተባለው የታሪክ ጸሐፊን በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

«በሰሜን ራውፍ ፓሻ በትግራይና በትግሬ ዮሐንስን የከዱት የክርስቲያን መኳንንት ከእስላሞቹ ባላባቶች ጋር አስተባብረው በምስራቅ በኩል የወሎንና የአውሳን እንዲሁም የአዘቦ አሮሞን ባላባቶች ቀስቅሶና ቢቻል ምኒሊክን ጨምሮ ዮሐንስን በሁለት ወገን አዋክቦ በማድከምና በመጣል የግብጽን የበላይ ገዥነት በኢትዮጵያ ሰመመስረት ነበር።

ዳሩ ግን በሰሜን የዘመተው ጦር ጉዳጉዲ ላይ ተመቶ መሪው ኮሎኔል አሬን ዱሩፕ ራሱ በጦር ሜዳ ላይ እንደወደቀ ቀርቷል።

ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኑባር ፓሻ የጉንደትን ውድቀት ገልጾ በዚያው ባለበት በአውሳ ግዛትን አጠባብቆ እንዲይዝ እንጂ ወደፊት እንዳይገሰግስ ከምኒሊክም ጋር ግንኙነት ለማድረግ ጊዜው ምቹ ስላልሆነ እንዲያቀ የው ለሙንዚንገር ደብዳቤ ልኮበት ነበር።

1 ተክለጻዲቅ መኩሪያ:አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት: ገጽ 131





Lord Napier.

Re Giovanni

ሎርድ ናፒር በአጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር ዋና አዛዥ ለአጼ ዮሐንስ ወዳጅ ነበረ።

መንዚንገር ደብዳቤው በፍጹም ሳይደርሰው በሰሜን የዘመተው ጦር መሸነፉንም ሳይገነዘብ በአሳል ሐይቅ በሚገኝበት ቦታ አድርጐ በሀገሩ ባላባት እየተመራ ሲጓዝ ስለ መሸበት ከታጁራ 40 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ከሚገኘው ቀበሌ ከነጓዙና ከነጦሩ አብሮ ሰፈረ። ባላባቱም እነ አሊታ ብሩም አብረውት ነበሩ።

በሕዳር ወር አጋማሽ ላይ የበረሃ ጉዞ አድክሞአቸው ሁሉም በተኙበት ሰዓት ላይ በርከት ያሉ የደንከል ሰዎች በደፈጣ በድንገት ደርሰው ወጓቸው። ወታደሮቹ እንደሚገባ ሳይከላከሉ ብዙዎቹ መንዚንገር ጭምር ተገደሉ፣ በዚህም የሌሊት አደጋ አምልጠው አሊታ ብሩ ወደ ታጁራ በመሸሽ ከሞት ተረፈ።

አብዛኛው ጣሊያኖች ጸሐፊዎች የጉዳጉዲ ጦርነት እና የምስራቁ ጦርነት ለየት ባለ መልክ ይገልጹታል። 1/ አሊታ ብሩ የሚባለው ሰው ተጠቅሶ አይገኝም፣ የሚጠቀሰው ጊዮርጊስ ንጉሤ የተባለው ነው። 2/ ሰሜንና ምስራቅ ጦር ግንባር የተደረጉ ጦርነቶች በተቀራራቢ ቀኖች ቢሆንም በሶስት ቀን የተቀደመው ግን የምስራቅ ጦር ግንባር ነው። 3/ ይህ በመሆኑ ከግብጽ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመንዚንገር ተልኳል የተባለው ደብዳቤ ከተፈጸመው ታሪክ ጋር የሚታረቅ ነው።

ከጣሊያኖቹ ጸሐፊዎች አንዱ[1] ትራቬርሲ የተባለው «ሌት ማረፊያ» በተባለው መጽሐፉ እንደሚከተለው ያቀርበዋል። ኖቬምበር 14 ቀን 1875 ዓ.ም የግብጹ ጦር በጠባቡ የጉዳጉዲ ሰፈር ከማለቁ ሶስት ቀን በፊት የመንዚንገር አሰቃቂ ሞት በደንከል በረሃዎች የአውሣ መንገድ አደገኝነት ያሳያል። ከመሐመድ ግራኝ ወዲህ በእስላሞች ላይ የኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ጥላቻ እንዳለ እየታወቀ በአጼ ዮሐንስ ላይ ምኒልክ ከግብፅ ፓሻ ጋር ምስጢራዊ ስምምነት ማድረጉ ልዩ ከስተት ነው። በዚሁ ስምምነት አደራዳሪ የነበረው ታዋቂው የውጫሌ አስተርጓሚ(TRADUTTORE) በትክክል ግን ከሀዲ (TRADITORE) የነበረው የዮሴፍ ንጉሤ ወንድም ጊዮርጊስ ንጉሤ የተባለው ነው። ሁለቱም የአክሩር ሚሲዮን ተማሪዎች ትግሬዎች ናቸው። መንዚንገር 400 ሱዳናውያን እና ጆርጅ ንጉሤ ሁመት ሎይታ ከተባለው በአጉባት ሱልጣን እየተመሩ ወንድማዊ አቀባበል ከአፋሮች እንደሚጠብቃቸው እየተነገራቸው ከባሕር ወደብ ታጁራ ተነሱ። ከጋርጉሪ ሐይቅና ከኪፋ ተራራ ያለው ሜዳ እንደደረሱ ድንኳን ተከለው ዐረፉ። ብዛት ያላቸው አፋሮች ወዳጅ መስለው ወተት፣ ቅቤ፣ ፍየሎች፣ በሬዎች፣ ለመንዚንገር በገፀበረከት ይዘው ሰፈሩን አጥለቀለቁት። ሌሎችም አፋሮች እንግዶችን ለማየት የመጡ መንገደኞችም ተጨምረውባቸው ነበር። ሱዳኖቹ ልባዊ የወዳጅነት አቀባበል ተደርጎልናል ብለው መሣሪያቸውን አስቀምጠው በሚዝናኑበት ጊዜ አፋሮች ይፈጁአቸው ጀመሩ። አንዳንድ ሱዳኖች መሣሪያቸውን ይዘው በሐይቁ ውሃ ገብተው ብዙ አፋሮችን መግደል ቢችሉም በመጨረሻ እነሱም ተገደሉ። ጆር ጅ ንጉሤ ብቻ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ አይታወቅም ሕይወቱን ማትረፍ ችሏል፣ ወሬውንም ወደ ታጁራ ሄዶ አብስርዋል። አስከሬኖቹ ለጅቦች ምግብ እንዲሆኑ በቦታው ቀርተዋል።

1 Traversi: Let Marefia p.294-296



መሣሪያዎችም በሱልጣን አንፋሪ ትዕዛዝ የመንዚንገር ሽንፈት ምስክር እንዲሆኑ ሳይነሱ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ማንነቱ በዚህ በመንዚንገርም ሞት ጉዳይ ያስመሰከረው ይህ ጆርጅ ንጉሤ ከሞት መዳኑም እንቆቅልሽ የሆነው የምኒልክ ባለሟል ነበረ።

የአንቶኔሊንም ምንጊዜም የሚጠረጠሩ ሰዎች የሚሰበስብ ሁልጊዜ የአጼ ምኒልክ ባለሟሎች ነበሩ። በሌሎችም ከሸዋ ወደ አውሳ ወይም ከአውሳ ወደ ሸዋ የሚመላለሱ ነጋዴዎችና መንገደኞች ጆርጅ ንጉሤ ተዋቂነት ነበረው ። አንድ ትንግርት ነው፣ ግብፃውያን በኢትዮጵያ ላይ በዘመቱ ቁጥር የዚሁ ዓይነት ዕድል የሚያጋጥማቸው። አጼ ዮሐንስ ግብፃውያን ትግራይን ለመያዝ የነበራቸው ምኞት ቅስም ሲሰበር የምኒልክም የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለመጫን የነበረው ምኞት ቅስሙን ጭምር በመስበር ነው።

ሌላው ዝናው የተረሳው የጉራዕ ጦርነት ታሪካችን በአንድ ቀን ጦርነት በሞተው የወታደር ብዛት ከተገመገመ ከሁሉ ቀደምትነት ያለው ነው። በታሪክ ፀሐፊዎች አቀራረብ ልዩነት ቢኖርም[1] ሉካ ደይ ሳቤሊ እንዳቀረበው በጉራዕ ጦርነት በሁለቱ ወገኖች በኢትዮጵያና በግብፅ 50,000 (ሃምሣ ሺህ) ወታደሮች ሞተዋል። ከነሱም ውስጥ አንድ ሶስተኛው ግብፃውያን ሲሆኑ የቀሩት ኢትዮጵያውያን ናቸው። ይህ ማለት የሞቱት የኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥር ከ30,000 በላይ ሲሆን ግብፃውያን ደግሞ ከ15,000 በላይ ነበረ። በዓድዋ ጦርነት ከሞቱት የወታደሮች ብዛት ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል። በ1938 ዓ.ም በኢጣሊያ መንግሥት አማካይነት በሶስት ታላላቅ[2] መጽሐፎች ተከፍሎ በወጣ መጽሐፍ በዓድዋ ጦርነት የሞቱት የወታደሮች ብዛት የመጨረሻ ይፋዊ ግምገማ ተብሎ ታትሞ እንደወጣው የቀለም ወታደሮች ሳይጨምር የሞቱት የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት የመኰንኖች 262 ከተካፈሉት 46 ከመቶ፣ ተራ ወታደሮች 3772 ከተካፈሉት 38 ከመቶ ነበረ። ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱት 6,000 የቆሰሉት 10,000 መሆናቸውን ተገምቷል። ስለዚህ ከተካፈለው 100,000 የሚገመት የኢትዮጵያ ወታደር የሞተው 6 ከመቶ ብቻ ስለሆነ አነስተኛ ቁጥር ነው ለማለት ይቻላል። ጣልያኖች አብዛኛዎቹ የተገደሉት በመሸሽ ላይ እንዳሉ ነበር። በዚህ አሀዝ መሠረት በጉራዕ ጦርነት የሞቱት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ብዛት በዓድዋ ጦርነት ከሞቱት በ5 እጅ ይበልጣሉ ማለት ነው። እንደዚሁም በጉራዕ ጦርነት የሞቱት የጠላት ወታደሮች ብዛት በዓድዋ ጦርነት ከሞቱት በሶስት እጅ በላይ ይበልጣሉ ማለት ነው። የጉራዕ ጦርነት በየዓመቱ ከምናከብረው ከዓድዋ ጦርነት በግዙፍነቱ በጣም የሚበልጥ ነው። በጦርነቱ ከተካፈሉ 70,000 በኢትዮጵያ ወታደሮች ግማሽ የሚጠጉ በጦር ሜዳ ሞተዋል፤ የሞቱት የግብፅ ወታደሮች ግን የኢትዮጵያ ግማሽ ብቻ ነበሩ።

አጼ ዮሐንስ በአገዛዙ ይከተሉት የነበረ የአስተዳደር ዘዴ ከአጼ ቴዎድሮስ ተቃራኒ ነበረ። ተቀናቃኞቹን በማጥፋትና በመግደል ሳይሆን ታማኝነታቸውን በመፅሐፍ ቅዱስ በማስማል ማረጋገጥ ይበቃው ነበረ።

1 Luka Dei Sabelli: Ibd Vol.III p.248

2 F.I.C.I.: Vol. I p.206

በዚሁ መሠረት ምኒልክ በጉራዕ ጦርነት ጊዜ መቅደላን፣ ጎጃምን፣ ቤጌምድርን በመያዝ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ እየተጠራ አጼ ዮሐንስ ሲሸነፍ ወደ ጎንደር በመግባት በዘግጅት ላይ የነበረው ጦርነቱ በአጼ ዮሐንስ ድል አድራጊነት ሲፈጸም አማላጅ ልኮ ከንጉሠ ነገሥቱ ሹመት አግኝቶ ትከሻው ላይ ድንጋይ ጭኖ አጼ ዮሐንስ ዘንድ ቀርቦ ግብር እየከፈለ የሸዋ ንጉሥ ብቻ ተብሎ ለመኖር ስለተስማማ የሸዋ ንጉሥ መሆኑን የሚያፀድቅ ሹመት ከአጼ ዮሐንስ ተቀብሎ በቀላሉ ያለምንም ደም መፋሰስ ለመታረቅ ችሏል። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ አንድነት ተግባራዊ ሆኖ የታየበት ወቅት ነበር። ከምኒልክ ቀጥሎም ለጎጃሙ ራስ አዳል ስሙ ተክለሃይማኖት ተብሎ ተቀይሮ የንጉሥ ማዕረግ ከአጼ ዮሐንስ እጅ ስለተሰጠው የኢትዮጵያ አንድነትና መረጋጋት ተጠናክሮ የታየበት ወቅት ነበር። በመንፈሳዊ በኩልም አጼ ዮሐንስ በማያወላውል መንገድ የቤተክህነት ደጋፊ ስለነበር ለዘመናት በቡድን ተከፋፍለው ሲፎካከሩ የነበሩ የሃይማኖት ክርክሮችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ በቅተዋል።

የካቶሊክ እምነት፣ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንም የሃይማኖት ክርክር እንዳያስነሱ በፖለቲካም ጣልቃ እንዳይገቡ በማሰብ እንደ አባ ኩልቦ ከጐኑ ያስቀምጥ ነበረ። እንደ ካርዲናል ማሣያ የመሣሰሉ ግን ከሀገር እንዲባረሩ አድርገዋል። የሃይማኖት ጉዳይ እንዳልነበረ እንረዳለን። አጼ ዮሐንስ ዘውድ ከጫኑ ጀምሮ ማንም የስልጣን ተቀናቃኙ እንዲገደል ወይም በእስር ቤት ማቅቆ እንዲሞት ያደረገው የለም። የውጭ ሀገር ወራሪዎችን ግብጾች ሱዳኖቹ በተለይ ኢጣሊያኖች ሳያወላውል የሀገሩ ዳር ድንበር ለድርድር ሳያቀርብ በጀግንነት ተዋግቷቸዋል። በኢትዮጵያ ቤተክህነት ዘንድ ፍቅር አትርፏል፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ጥላቻ አላተረፈም፣ የግብፅ ወረራን በማስወገዱ ኢትዮጵያ ከግብፅ ቅኝ ገዢነት ያዳነ እንደመሆኑ መጠን ተከታዩ ትውልድ ተገቢውን ውለታ አልከፈለውም። የአጼ ምኒሊክ የዓድዋ ጦርነት መታሰብያ በየዓመቱ ስናከብር የአጼ ኃይለ ሥላሴ የማይጨው ጦርነት ድል በዘፈኖቻችን ስናስታውስ አጼ ዮሐንስ ግን በጉንደት በጉራዕ እንዲሁም በመተማ የፈጸመው የጀግንነት ሙያ ተገቢው ክብር አልተሰጠውም። በጉራዕ ጦርነት ያለቁ 50,000 የኢትዮጵያና የግብፅ ወታደሮች ያስከተለው ውጤት ኢትዮጵያ የግብፅ ቅኝ ግዛት እንዳትሆን እና በክርስትና ሃይማኖት እምነቷ ፀንታ እንድትኖር አስችሏታል።

ይህ አጼ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ የሰራው ከፍተኛ ውለታ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳያውቀው እየተደረገ ነው። በኢትዮጵያውያን ታሪክ ፀሐፊዎች ስለ አጼ ዮሐንስ የሚቀርበው በክርስትና ሃይማኖት አክራሪነቱ ብቻ ነው። የአጼ ዮሐንስ በመተማ ጦርነት መሸነፍና ውድቀት ምክንያት የሆነው በውስጥ ጠላት የአጼ ዮሐንስን አስተዳደር በማዳከምና ጠላት በሚነዛው ወሬ ምክንያት የጠቅላይ ጦር አዛዥነት ቦታ ለራስ አሉላ በመስጠቱ ፋንታ ለራስ አርአያ በመስጠቱ እንዲሁም ወታደሮቹ ጦርነት ሳይገጥሙ በእግር ጉዞ ብቻ መ ድከማቸውን ነው።

አጼ ዮሐንስ ከሶስት ማዕዘናት ሶስት ጠላቶች ተነስተውበት ነበር። በሰሜን ጣሊያኖች በምዕራብ ማሕዲሶች በደቡብ ምኒልክ። በመጀመሪያ የአጼ ዮሐንስ ሰራዊት በሰሜን ጣሊያኖቹን ለመዋጋት ወደ ሰሜን ዘመተ። ውጊያ ሳይገጥም የባሱ ጠላቶች እስላሞች ተብሎ ፊቱን አዙር ወደ ምዕራብ አመራ፣ ከዚያም የውስጥ ጠላቶች ንጉሥ ተክለሃይማኖትና ንጉሥ ምኒሊክ ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ወደ ጎጃም ተመለሰ፣ ሸዋ ሳይደርስ ግን እንደገና አቅጣጫውን በመቀየር ወደ ሱዳን ሄዶ ሲዋጋ የሠራዊቱ ወኔና ቁጥሩ ወደ ዘመቻ ሲነሳ እንደ ነበረው ሊሆን አይችልም። አጼ ዮሐንስ ድሮ የነበረው ቆራጥና ፈጣን አመራር ቀርቶ ወላዋይ አመራር ማሳየቱ የሚያስገነዝብ ነው። ይኼም ሁኔታ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአሸናፊነት እንዳ ይወጣ አስተዋፅኦ እንደነበረው የሚያመለክት ነው። አፄ ዮሐንስ በጦር ሜዳ በመተማ ሲሞት ከምኒልክ በስተቀር ያዘነለት ኢትዮጵያዊ እንጂ የተደሰተ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ለብዙ ጊዜ ራስ አሉላ ዙፋንህን ሊነጥቅህ ነው እየተባለ ሲነፍስ የነበረ አሉባልታ ሐሰት የጠላት ወሬ ሆኖ ተገኘ። አጼ ዮሐንስ ከመሞቱ በፊት ራስ መንገሻ አልጋ ወራሽ ልጁ መሆኑንና ድጋፉን እንዲሰጠው ለራስ አሉላ ተማፅነዋል። የአጼ ዮሐንስ ሞት ከብላቴንጌታ ኅሩይ አግኝቶ «አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት» በሚል መፅሐፉ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ እንደገለፀው የአጼ ዮሐንስ ሬሳ አንገቱን ቆርጠው ለመውሰድ የመጡ ደርቡሾች[1] «የጌታችን ሬሳ አናስማርክም» በማለት እየተዋጉ ከሞቱት የአፄ ዮሐንስ አሽከሮችና መኳንንቶች 1ኛ. ራስ አርአያ የአጼ ዮሐንስ አጎት 2ኛ. ቢትወደድ ገብረመስቀል ገብረፃዲቅ ቀድሞ የዓድዋ ገዥ የነበረ 3ኛ. ደጃች ተድላ የዘበኞች አለቃ የነበረ 4ኛ. ብላታ ገብረማርያም 5ኛ. አዛዥ ወንድምሁነኝ 6ኛ. አዛዥ ላዕከድራር 7ኛ. መምሬ ዘሚካኤል 8ኛ. መምህር ወልደ አረጋይ 9.መምህር ከንፉ ሐረብ 10ኛ. ቄስ ጎበዝ ሰላማ ይገኙባቸው ነበር። ይህም አፄ ዮሐንስ የውስጥ ጠላቶች እንዳልነበሩት በቂ ማስረጃ ነው።

# 3. አፄ ምኒልክ

አጼ ዮሐንስ በድንገት ሲሞት አጼ ምኒልክ የነገሠው ያለምንም ደም መፋሰስ ያለምንም ተቃዋሚ ነበር። የአጼ ዮሐንስ ዓላማም መጀመሪያ ምኒልክ እንዲነግሥ ቀጥሎም ምኒልክ በሚሞትበት ጊዜ የአጼ ዮሐንስ ወንድ ልጅ አርአያ ሥላሴ እና የምኒልክ ሴት ልጅ ዘውዲቱ ተጋብተው ስለነበረ እንዲነግሡ ነበረ። አርአያ ሥላሴ ስለሞተ ግን ዕቅዱ በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም። ሆኖም እቅዱን የሚያስተባብል ሌላ ዕቅድ ስላልወጣ ምኒልክም በኃይል ሚዛን ከሁሉም የበላይነት ስለነበረው ሌላ የዘውድ ተቀናቃኝ አልነበረውም። ምኒልክ ሲወለድ በሰው የመወደድ ዕድል የነበረው ሰው ነው። አጼ ቴዎድሮስ እንደ ንጉሥ ልጅ በክብር ከመያዙም በላይ ልጁን ድሮታል። አጼ ዮሐንስም ንጉሥ ተብሎ እንዲጠራ ከመፍቀዱም በላይ የዘውድ ወራሽ እንዲሆን ልጆቻቸውም በጋብቻ ተሳስረው ወራሾች እንዲሆኑ ተመኝተውለታል። የጣልያን ሚሲዮናውያንና የጣሊያን መንግሥትም ይወዱት ነበረ። የዓላማቸው አስፈጻሚ እንዲሆን ይተማመኑበት ነበር።

1 አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ:ibd ገጽ 549



ለፄ ምኒልክ እና ጣሊያኖች አማካሪዎቻቸው






ምኒልክ ግን ሁሉንም በማታለል የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ ነበረ። አጼ ምኒልክ ስናስ ታውስ ከሁሉም በላይ ትዝ የሚለን ነገር በዓድዋ ጦርነት በጣሊያኖች ላይ የተቀዳጀው አስደናቂ ታላቅ ድል ነው። በዓድዋ የተገኘው ድል አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድ ዓላማ ለማሰባሰብ በመቻሉ ነው። አጼ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተመሰሳይነት የነበረው በአስተዳደር ለዘብተኝነት ነው። አጼ ምኒልክ ደህና ሹማምንቶችን የመምረጥ ችሎታ ነበረ ው። ስለ ዓድዋ ጦርነት ብዙ ተፅፏል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አድናቆትን አትርፏል። ጦርነቱ በሚካሄድበት ጊዜ በኢትዮጵያውያን መሐከል ሙሉ ወኔና ሕብረት ነበረ። ከድሉ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ለሁለት ተከፍላ ነበረ። አንደኛው ወገን አጼ ምኒልክ በድሉ ተደስቶ ቶሎ ብሎ ወደ አዲስ አበባ ለመመለሥ የቸኮለ ነበረ። ሌላ ወገን ደግሞ በተለይም የትግራይ ሹማምንት የነበሩበት በድሉ በመጠቀም ጣሊያኖችን እስከ ምጽዋ ማባረር ምኞት የነበረው፤ ዓላማውም ሳይሳካለት ስለቀረ በድሉ ማግሥት ያኮረፈ ወገን ነበረ። በዓድዋ ድል በግሉ የተደሰተውና የተጠቀመው አጼ ምኒልክ ብቻ ነው። ጣሊያኖች ተሸናፊዎችም ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሸና ፊዎች አልሆኑም። የኢትዮጵያ የበላይ ጠባቂ (Protectorate) ለማድረግ ባይቀናቸውም በምትኩ ግን በመሬት ይዞታ በኩል የውጫሌው ውል ከሚፈቅድላቸው በላይ ያለ ምንም ደም መፋሰስና ክርክር ለማግኘት ችሏል። ይኸውም አስተማማኝ ወታደራዊ ሰፈር በመገንባ ት የሽንፈታቸውን ለመበቀልና መላውን ኢትዮጵያ በቁጥጥራቸው ለማዋል 40 ዓመት ጠብቀው ቢሆንም ረድተዋቸዋል። አጼ ምኒልክ በ1891 ለዓለም ነገሥታት ለለ የሀገሩ ወሰን ከልል ደብዳቤ ጽፎ ነበር። እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አጼ ምኒልክ ሚያዝያ 14 ቀን 1883 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ለመግለፅ ለኤውሮፓ መንግሥታት በጻፈው ደብዳቤ መሠ ረት ከጣልያን ይዞታ ከአራፋሊ ጀምሮ ወደ ጅግራ ጫዳ፤ ማሕዮ፤ ሐላይ፤ ድግሣ፤ ጉዛ ዓዲባር (ድባርዋ) መረብ ወንዝና አትባራ ወንዝ የሚገናኙበት ቶማት የምትባል ከተማ ይደርሳል። ከዚህም ገዳሪፍ አውራጃ በማጠቃለል በአባይ ዳርቻ የምትገኘው ካርኮርግ የም ትባለው ከተማ ይደርሳል። ከዚህም ነጭ አባይና ሶባት ወንዝ የሚ ገናኙበት ይደርሳል፤ ወደ ሳምቡሩ ሐይቅ ይዞ ልቃል በምሥራቅ ቦረና፤ አርሲ፤ ኦጋዴንን ያጠቃልላል። አብራዋል፤ ጋዳ ቡርሲ፤ ኢሳ ሱማሊያንና አምቦስ ጐሳዎች በማጠቃለል ከጦ ንት ጀምሮ የእኛ ታማኝ የሆነው የመሐመድ አንፋሪ ግዛት የአሳል ሐይቅ ደርሶ ወደ ባሕር ጠረፍ ዘልቆ እስከ አራፋሊ ይቀጥላል። የዚህ የሀገሬ ወሰን ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን እግዚአብሔር ዕድሜ ከሰጠኝ ቀድሞ የኢትዮጵያ ወሰኖች እስከ ካርቱምና ኒያሳ ሐይቅ የጋላ ሀገር ጭምር ለማ ስመለስ እተ ራለሁ። የውጭ መንግሥታት አፍሪካን ለመ ከፋፈል በሚሞክሩበት ጊዜ እጄን አጣምሬ አልቀመጥም። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እስከ ዛሬ እንደ ጠበቃት ለወደፊትም እንደሚጠብቃት ተስፋ አለኝ። ኢትዮጵያንም የውጭ መንግሥታት እንዳይቀራመቷት እርግጠኛ ነኝ። በጥንት ጊዜ የኢትዮጵያ ወሰን ባሕር ነበረ። ኃይል በማጣ ታችን እና የክርስ ቲያኖች እርዳታ ባለማግኘታችን በባሕር በኩል የነበረው ወሰናችን በእስላሞች እጅ ወድቋል። ዛሬ በባሕር በኩል ያለው ወሰናችን በኃይል ለማስመለስ[1] አንሻም።

1 Traversi: ibd p.379




I confini storici dell'Abissinia e le conquiste scioane dal 1882 in poi

በደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ለጥቃቅን መንግስታት መከፋፈል የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ የአፄ ምኒልክ ግልፃ ገብነትና የመልሶ ማዋሐድ ህጋዊ ያደርገዋል።



ነገር ግን ክርስትያን የሆኑ መንግሥታት በጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ብርቱት በባሕር ጠረፍ በኩል ያለው ወሰናችን ባይሆን በአንዳንድ በተወሰኑ ቦታዎች እንደ ሚመለሱልን ተስፋ አለን ብሏል። አፄ ምኒልክ ጣሊያኖች በውጫሌ ውል የተፈቀደላቸውን ወሰን አልፈው መሬት እንዲይዙ ፈቅዶላቸዋል። ጣሊያኖችም ለዚሁ ውለታው የጦር መሣሪያና ገንዘብ ሰጥተውታል። አፄ ዮሐንስ ሲሞት የአፄ ዮሐንስ ወራሾች እንዳ ይነሱበት ጣሊያኖችን አስመራን[1] ቶሎ ብለው እንዲይዙ ይጎተጉታቸው ነበር። የቀሩት ሁሉ ክፍላተ ሀገሮች የምኒልክ ሥልጣን ሲቀበሉ ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ሳይቀበሉ ቀርተው ስለነበረ ጣሊያኖች እንዲከታተሏቸውና የጦር መሣሪያ እንዳይ ደርሳቸው እንዲያደርጉ ጣሊያኖችን ይጎተጉት ነበረ። ጣሊያኖች የሚጠይቁት የውጫሌ ውል እንዲፈርምና ወደ ኢጣሊያ መል ዕክተኞችን እንዲልክ እሺ ብሎ ፈረመ። የኢጣሊያ መንግሥት ከሮም የምኒልክ ሥልጣንና ፍላጎት እንዲያሟላ በምፅዋ ለኢጣሊያ ጦር አዛዥ ጥብቅ ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም፣ የኢጣሊያ ወታደራዊ አዛዦች ግን ሌላ አቋም ነበራቸው። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ በለውጥ ሂደትና በመፈራረስ ስለምትገኝ ችኮላ እንደማያስፈልግ ተቃራኒ ወገኖች እርስ በእርሳቸው በመዋጋ ት እስከሚዳከሙ ጣልቃ መግባት እንደማያስፈልግ በማመን አልተንቀሳቀሱም። አቶ[2] ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ «አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት» በሚለው መፅሀፉ ምኒልክ ጣሊያኖችን አስመራን ቶሎ ብሎ እንዲይዙ እን ደለመናቸው ከመግለፅ ተቆጥቦ የዚሁ ዓይነት ሐሳብ ያቀረ በው አንቶኔሊ መሆኑን በማስመልከት በትግራይ የአፄ ዮሐንስ የዙፋን ወራሾች ብዙ መሆ ናቸውን በማስመሰል ሁኔታው እንደሚከተለው ይገልፀዋል። በአጼ ዮሐንስ ሞት የዙፋን ባ ለንጣዎች መብዛት በጣም የተጠቀመ የኢጣሊያ መንግሥት ነበረ። በዚህ ምክንያት አንቶኔሊ ከሸዋ ለጠቅላይ ሚኒስትር ለክሪስፒ በላከው አስቸኳይ ሪፖርት ውስጥ መደምደ ሚያውን «የትግሬ ተዋጊዎች ከመተማ ተመልሰው ቁስላቸው ሳይድን፣ ኃይላቸው በደከ መበት፣ ሞራ ላቸው በወደቀበት ሰዓት ወደ አሥመራ መገስገስ ነው።» የሚል ቃል ይገኝበ ታል። ይኼንኑ እንዲፈጽም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ምፅዋ ለሚገኘው ለጀኔራ ል ባልዲሴራ ባስተላለፈው ትዕዛዝ ከጀኔራሉ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠው መልስ «እኔ ከምፅዋ ወደ አሥመራ ከመጓዜ በፊት ባላንጣዎቹ በቅድሚያ እርስ በእርሳቸው ቢተላለቁ ይጠቅማል የሚል እምነት አለኝ» በማለት መልስ ሰጥቷል። በትክክል ቃሉ «ደበብ ኃይሉን ለማጠናከር ከዓድዋ እየከዱ ከእነ ራስ መንገሻ የሚመጡትን ወታደሮች እየጠበቀ ነው፣ ወደ ዓድዋ መሄድም ይፈልጋል፤ እኛም በቶሎ ወደ አሥመራ እንድንዘልቅ ጠይቀዋል። ከያለበት የተጠራቀሙ 20,000 የትግራይ ወታደሮች የበለጠ ለሚከፍላቸው ለመዋጋት ተዘጋ ጅተዋል። ነገር ግን እኛ ሰንሄድ የእነሱ የመንገሻና የደበብ መታላለቅ ቢቀድም ይጠቅማል» የሚል ነው። አፄ ዮሐንስ ከመሞቱ በፊት ቀደም ብሎ በምፅዋ የኢጣሊያ ሠራዊት አዛዦች ከረንንና አሥመራን ለመያዝ ከከሃዲዎችና አድርባይ ግለሰቦች ባራ ምባራስ ካፈልና በደበብ በመጠቀም ዕቅድ አውጥተው ነበር።

1. Carlo Rossetti: Storia Diplomatica p.59

2. አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ: ibd ገጽ 563

ጁላይ 1888 ዓ.ም. ባራንባራስ ካሬልን በኢጣሊያ መንግሥት ስም ከረንን ይዞ እንዲያስተዳድር ፈቃድ ተሰጥቶት ነበረ፤ ተሳክቶለት ከረንን ያዘ። በተጨማሪ ደቡብ ሠገይቲ ሆኖ በራሱ የአከለጉዛይ ገዥ ሆኖ ነበረ። የባራምባራስ ካሬል ተመግባይ ሥራ በአሥመራ እንዲፈጽም ከጣሊያኖች የቀረበለት ጥያቄ ሳይቀበል በመቅረቱ ደቡብን ለመያዝና በጣሊያኖች ሥር ሆኖ እንዲሰራ ለማድረግ በጣሊያኖች መኮንኖች የሚታዘዙ 400 የሀገር ተወላጅ ወታደሮች ወደ ሰገይቲ ልኮ ጣሊያኖች መኮንኖች ጭምር ወታደሮቹ በሙሉ ተደመሰሱ። ይህ ሁኔታ ከሆነ ከስምንት ወር በኋላ አጼ ዮሐንስም ከሞቱ 2 ወር በኋላ ባራምባራስ ካሬል የከረን አስተዳዳሪ ጣሊያኖች በምስጢር ከራስ አሉላ ጋራ ተስማምተዋል የሚል ወሬ ስለደረሳቸው ሜይ 29 1889 ዓ.ም. በድንገት ባራንባራስ ካሬልን በማሰር ከረንን ያዙ። ባራንባራሱም ታስሮ ወደ አሰብ ተወስዶ ሞተ። ጣሊያኖች በሰገይቲ ጦርነት ወታደሮቻቸውን የጨረሰባቸው ደቡብ ጋራ ታርቀው ስለነበረ ከረን ለመያዝም ተባባሪ ሆኖ ስለነበረ አሥመራም በጣሊያኖች ስም እንዲቆጣጠር ፈልገው ነበር። ጣሊያኖች ደቡብ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋራ ለመገናኘት ወደ መቀሌ መሄዱንና የጣሊያን ሰላይ ተብሎ ተጠርጥሮ መታሰሩን ሲሰሙ አገስት 3 ቀን 1889 ዓ.ም. አራት ወር ከአጼ ዮሐንስ ሞት በኋላ አሥመራ ሊገቡ ችለዋል።

አጼ ምኒልክ ዓድዋ ላይ በተገኘው ታላቅ ድል ኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንድትሆን አላደረገም። ጠላት ግን በቂም በቀል እንዲዘጋጅ አመቺ ሁኔታዎች በፈለገው መንገድ እንዲፈጥሩለት ተፈቅዶለታል። ጣሊያኖች ሀገሪቷን ከዳር እስከ ዳር ቀዳዳ መውጫ መግቢያ እያጠኑ አስፈላጊ ያልሆኑ ቆንስላዎች በመላው ሀገሪቷ እያቋቋሙ ሰላዮች እየቀጠሩ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች እያከማቹ ለሽንፈታቸው ቂም በቀል ጦርነት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ግን እጆቿን አጣምራ ለማየት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ብቻ በየዓመቱ ታከብር ነበር። አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ በነገሡ ለተከታዮቹ ነገሥታት በተለይ ለአጼ ኃይለሥላሴ በጠላት የተከበበች ሀገር ፀጥታዋ የተናጋ ራሷን ለመከላከል ዐቅም የሌላት ሀገር ነበረ አውርሷቸው ያለፉ።

ኃይለሥላሴ እንደ ምኒልክ ጣሊያኖችን እያታለለ የጦር መሳሪያን በማግኘት መኖር አይችልም፤ ምክንያቱም ጣሊያኖች ካለፈው ጊዜ በቂ ትምህርት ወስደዋል። በአርባ ዓመት የዓለም ስልጣኔ ብዙ ተራምዷል፤ እጅግ የተሻሻሉት የጦር መሣሪያዎችም ተፈልስፈዋል፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የኢጣሊያ ሰራዊት የያዘው የጦር መሣሪያ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከነበረው መሣሪያ በዓይነትም ሆነ በብዛት ከፍተኛ ልዩነት አልነበረውም። ያኔ በዓድዋ ጊዜ የኢጣሊያ ወታደር እንደ ኢትዮጵያ ወታደር ወደ ጦር ሜዳ የመጣው በእግሩ ወይንም በከብት ነበረ፤ ተሽከርካሪዎች አልነበረውም፤ ከአርባ ዓመት በኋላ ግን የኢጣሊያ ጦር የነበረው የጦር መሣሪያ እጅግ ዘመናዊ ነበረ፤ የሚጓዘውም በየዓይነቱ በብዛት በሚቀርቡለት የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች እንዲሁም በጦር አውሮፕላኖች እየተረዳ ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት ግን ከአርባ ዓመት በፊት በዓድዋ ከነበረው የጦር መሳሪያ የተሻለ አልቀረበለትም። ስለዚህ በመሣሪያዎቹ ጥፋት ለሽንፈት አስቀድሞ የተዳረገ ነበረ።



ስለዚህ በዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቀመ ወይንስ ተጎዳ የሚል ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ የተለያዩ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ ቢችሉም በእኔ አስተያየት ግን በድሉ ካገኘው ጥቅም ጉዳቱ ያመዝናል። በጦር ሜዳ በዓድዋ ጦርነት የበለጠ ጉዳት የደረሰባቸው ጣሊያኖች ነበሩ። የሞተ ወታደር ቁጥርም የጣሊያን ይበልጥ ነበር። የጦር መሣሪያም ብዙ ተማርከባቸዋል። የጦርነቱ መነሻ የነበረው የውጫሌ ውል ውድቅ ሆኖ ነበር፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ በውጫሌ ውል ስለማትገደድ ጣሊያኖችን እስከ ምፅዋ ማባረር ትችል ነበር። አጼ ምኒልክ ግን ለኢጣሊያኖች የውጫሌ ውል ከሚፈቅድላቸው በላይ መሬት በችሮታ ሰጣቸው። ምኒልክ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለቀው እንዲሄዱ ፍላጎት አልነበረውም። ለአጼ ዮሐንስ የዘውድ ወራሾች የጦር መሣሪያ እንዳይደርሳቸው ዘብ እንዲቆሙለት ብቻ ነበረ ምኞቱ። ጣሊያኖች ለመበቀል እንደማይፈልጉና መላው ኢትዮጵያን ለመያዝ እንደማይመኙ ገምቷቸው ይሆናል። ጣሊያኖች ተጠናክረው ሰሜን ኢትዮጵያን እንዲቀመጡ በማድረጉ የተጎዳች ኢትዮጵያ ናት። እንደገና እንድትወረር አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላቸው። ዛሬ ከአካሏ ተቆርሶ ተነጥሎ አንድ ጠላት መንግሥት ተቋቋመ። ኃይለሥላሴ ወደ ስደት ሸሽቶ ሲሄድ ማማረርና መርገም የነበረበት ፋሽስት ኢጣሊያ ሳይሆን አባቱ ምኒልክንና በራሱ ዕድል ማማሻኘት ብቻ ነበረበት። በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል መገንጠልና አንድ መንግሥት ማቋቋም የኢትዮጵያ ሕዝብ ማማረርና መርገም ያለበት ከማንም በላይ ምኒልክን ነው።

አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ «አጼ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት» በተሰኘው መፅሀፉ ከዓድዋ ጦርነት ፍፃሜ በኋላ አጼ ምኒልክ ተሸናፊውን የኢጣሊያ ሰራዊት ለምን መረብ አልፎ ተከታትሎ ምፅዋ ድረስ አላባረረውም ለሚለው የብዙዎቹ እንቆቅልሽ ሆኖ የቀረው ጥያቄ ፍፁም መሠረተ ቢስ የሆኑ ምክንያቶች በማቅረብ አግባብ ያልሆኑ ፍፁም ተቀባይነት የሌለው መልስ በመስጠት ፅፏል። ጠላት የተረፈ ኃይሉን አሰባስቦ የመልሶ ማጥቃት እንዳይሞክር ሲባል እንኳን ተሸንፎ ያለ መሪ በመሸሽ ላይ የነበረውን የኢጣሊያ ሰራዊት ለመከላከል እስኪሞክር ድረስ ለጥቂት ቀናት እንኳን እያሳደዱ በድካም፤ በድንጋጤ፤ በረሀብ ተጨንቆ የነበረውን ለምን እንዳልፈጁት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊቀርብ አይችልም። በውጫሌ ውል መሠረት የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ሕጋዊ ወሰን መረብ አልነበረም። ወሰኑ ከላይ የጠቀስኩት ራሱ ምኒልክ ለኤውሮጳውያን መንግሥታት ያስተዋወቀው ነበር። እሱም በአንቀፅ 17ኛው የተነሳ ፈርሶ ለዓድዋ ጦርነት ምክንያት ሆነዋል። የመረብ ወሰን በልዩ ውልና በልዩ ችሎታ ምኒልክ ለኢጣሊያኖች የሰጣቸው ወሰን ነው።

ለአቶ ተክለፃዲቅ አባባል መልስ ለመስጠት ብዙ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል። ከብዙ በጥቂቱ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው ስለሚያስፈልግ[1] ባቀረበው ዘገባ መሠረት ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

1. በጦርነቱ ዋዜማ የኢጣሊያ ጦር አዛዦች ባደረጉት ስብሰባ ቀርቦ የነበረው ክርክር ከሁለት አማራጮች ወደ ኋላ ማፈግፈግና ከማጥቃት ጀኔራሎች በአንድ ድምፅ ማጥቃት በመምረጣቸው ጦርነቱ ሊቀሰቀስ ችሏል።

---
1 F.I.C.I.: Vol. I p.186

አስቀድሞ ለረጅም ጊዜ የተጠና ከመንግሥታቸው የተስማሙበት ዓላማ ግን አልነበራቸውም።

2. የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ባራቴሪ በምስጢር ከሥልጣኑ ተሽሮ ነበር፣ የሚተካው ሰው ባልዲሴራ በሐሰት ስም (PALAMIDESE) ፌብሯሪ 25 በመ ርከብ በመንገድ ላይ ነበር። ፌብሯሪ 23 ከኢጣሊያ ተነስቶ ማርች 4 ምፅዋ ደረሰ። የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው ተተኪው ጀኔራል በመንገድ እንዳለው ነው።

ስለዚህ ጀኔራል ባልዲሴራ ወደ አፍሪካ የሄደው የኢጣሊያ ሽንፈት ለመበቀል ሳይሆን ከጦርነቱ በፊት የነበረው ሁኔታ የጦሩ ጠቅላይ አዛዥነቱን ለመረከብ ብቻ ነበር።

3. ጀኔራል ባልዲሴራ ምፅዋ በደረሰ በማግስቱ ማርች 5 የሚከተለው ቴሌግራም ለመንግሥቱ ልከዋል። «በአጠቃላይ ሁኔታው ከባድ ነው። ከዓዲ ቀይሀ እስከ ዓዲኡግሪ እና አሥመራ ተንቀሳቃሽ ኃይሎች ይገኛሉ። 13 መድፎች፣ 13,000 የኢጣሊያ ወታደሮች፣ 5,000 የሀገር ተወላጅ ወታደሮች ኢንዲጀኒ ሁሉም በድንጋጤ የሚገኙ ናቸው። ከከሳላ የተረጋገጠ ወሬ የለም፣ የሸዋ ጦር (የኢትዮጵያ ጦር) ከጉራዕና አሥመራ መሐል መጥቶ እንደ ሚሰፍር እገምታለሁ። የእነዚህ ቦታዎች ከምፅዋ ጋራ ያለው መገናኛ የላላ ነው፣ በዓዲግራት ያለው ጦር ተከቧል፣ ለአንድ ወር የሚበቃ የምግብ ስንቅ ብቻ አለው። የሰገነይቲ ጦር ሰፈር የመከላከል አቅሙ አነስተኛ ነው። አስ መራ ውሀ ያንሳል። ከነገ ወዲያ ተጨማሪ ጦር ምፅዋ መግባት ይጀምራል። ያለኝ ኃይል በአስመራ አከማቻለሁ። የሰገናይቲና ዓዲኡግሪ እንዳሉ እንዲቆዩ አደርጋለሁ። ከዓዲግራትና ከከሰላ በፍጥነት ለመልቀቅ እሞክራለሁ። ሀ/ የሞቱት ወታደሮች ለመቅበር እንዲፈቀድልን ለ/ ስለ ሰላም ውል ለመ ነጋገር ሐ/ ትግራይ ትልቅ መሆን ለሸዋ አደገኛ መሆኑን ለማስረዳት ሻለቃ ሳልሳ ወደ ንጉሡ ልኬዋለሁ። ዛሬውኑ ወደ አሥመራ እሄዳለሁ» የሚል ነበረ።

4. ከጦርነቱ በፊት የነበረው ሁኔታ ግን ሌላ መልክ ነበረው። አጼ ምኒልክ ሀ/ 17ኛው የውጫሌ ውል እንዲሰረዝ ለ/ ወሰኑ መረብ እንዲሆን ሐ/ የሰላም ድርድር እንዲጀመር የሚል አቋም ነበረው።

ይህ በአጼ ምኒልክ የቀረበው ሀሳብ ግን በኢጣሊያ መንግሥት ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ስለዚህ ፌብሯሪ 8/1896 የኢጣሊያ መንግሥት ለኢጣሊያ ጦር አዛዥ በላከው ቴሌግራም ለሰላም የመቆዳደሪያ ሐሳብ ሀ/ ባለፈው ዓመት በኢጣሊያ ቁጥጥር የዋሉ የዓዲግራትና ዓድዋ መሥመር ለዘለቄታው ለኢጣሊያ እንዲሰጡ ለ/ የውጫሌ ውል ኢትዮጵያ እንድት ቀበል ሐ/ መቀሌና አምባአላጂ በጊዜያዊነት በኢጣሊያ ቁጥጥር ስር እን ዲሆኑ መ/ ለጊዜው ውጊያው ለእኛ ጠቃሚ ካልሆነ በስተቀር መቆም የለበትም ሠ/ የተጠየቀው ተጨማሪ ወታደሮች ይላካሉ ረ/ በዚሁ መሰረት ከምኒልክ ጋራ ለመደራደር ከሚንስትሮች ምክር ቤት ሙሉ ሥልጣን የተሰጠሀ መሆኑን የሚል መመሪያ ተልኮለት ነበር።

5. የኢጣሊያ መንግሥት ሐሳብ ፌብሯሪ 11 ቀን ለአጼ ምኒልክ ሲነገረው ሳይቀበለው በመቅረቱ ማንኛውም የሰላም ንግግር ተቋረጠ።



6. የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ባራቲየሪ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ዕቅድ አውጥቶ ነበር ሐሳቡም ለመንግሥቱ በቴሌግራም አስታውቆ ነበር።

7. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ የባራቲየሪ ቴሌግራም እንደደረሰው በአስቸኳይ የምኒስ ትሮች ምክር ቤት ሰብስቦ ጀኔራል ባራቴሪ ከሥልጣን ወርዶ በጀኔራል ባልዲሴራ እንዲተካ አደረገ፤ ጉዳዩ ግን በምስጢር እንዲጠበቅ ተደረገ።

8. የኢጣሊያ መሸነፍ ማርች 2 በቴሌግራም እንደተሰማ ክሪስፒ ከሥ ልጣን መልቀቅ ተገደደ ውሳኔውም ማርች 4 ፓርላማ ባደረገው ስብሰባ ላይ አሰታወቀ። የጠቅላይ ምኒስትሩ ስልጣን ሩዲኒ ተረከበ። ጀኔራል ሪኮቲ የጦር ሚኒስትሩ ካይታኒ ዱ ሴርሞኔታ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኑ።

9. የሩዲኒ መንግሥት አንዳንዶቹ ወገኖች እንደሚፈልጉት የቅኝ ግዛት ለመሰረዝ ባ ይደርስም ኢጣሊያ በመንፈስም በኃይልም ከዚህ በላይ ለበለጠ ትልቅ ጦርነት ተዘጋጅታ ስላልነበረች ሰላማዊ መንገድ በማስቀደም አስፈላጊ ከሆነ ግን ጦርነቱን ለመቀጠል እንድት ችል ለማንኛውም ወጪ 140 ሚሊዮን ሊሬ ከፓርላማ አስፈቀደ።

10. ስለዚህ በቀድሞ የክሪስፒ መንግሥት ዘማች የኢጣሊያ ሠራዊት ይወጣው ከማ ይችለው ችግር ገብቶ ነበር፤ መንግስቱ ውጊያው ተጠና ክሮ እንዲቀጥል ፍላጎት ነበረው፤ በተከታዩ የሩዲኒ መንግሥት ግን ዘማቹ የኢጣሊያ ሰራዊት በጣም ተጠናክሮ ነበረ። ከፍተኛ ችሎታ ያለው ጠቅላይ ጦር አዛዥም ነበረው፣ ጦርነቱ ለመቀጠል ግን ፍላጎትና ዓላማ አልነበረውም።

11. ድል አድራጊው ሀገር ከፍ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎች የመጠየቅ መብ ት እንዳለው የታወቀ ነው። ተሸናፊ ሀገርም መቀበል የተለመደ አሰራር ነው። ኢትዮጵያም

ሀ/ የጦርነቱ መነሻ የሆነው የውጫሌ ውል አንቀጽ 17ኛው እንዲሰረዝ መጠየቅ መብት ነበራት። ይኸውም የኢጣሊያ መንግሥት ተስማምቶ ተቀብሎታል።

ለ/ በውጫሌ ውል የሰፈረ የኢትዮጵያ ወሰን ላይ እንደተገለጸው አጼ ምኒልክም ለመላው የኤውሮጳ መንግሥታት በይፋ ያስታወቀው በሰሜን ያለው የኢትዮጵያ ወሰን ኢጣሊያ እንድትቀበል መጠየቅ መብቷ ነበር። ባልዲሴራም ኢትዮጵያ ይኼንን መጠየቋ አይቀርም ብሎ በመገመት የኢትዮጵያ ሠራዊት በጉራዕና አሥመራ መሀል ያለው ቦታ ድረስ ይመጣል ብሎ ይጠ ባበቅ ነበር። አጼ ምኒልክ ግን በመብቱ በመጠቀም እስከተባለው ሥፍራ ተሸናፊው ሠራዊት ተከታትሎ እያጠቃ ማሳደድ አላደረገም። ይህ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ጀኔራል ባልዲሴራ አዲስ ተጨማሪ ጦር ከኢጣሊያ የመጣ ብቻ ስለሚኖረው ለሰላምና ለድርድር በዓድዋ ጦርነት የተካፈለ ሰራዊት ከሞላ ጎደል ስለተደመሰሰ ከአጼ ምኒልክ ጋራ በዝቅተኛ ደረጃ ለመደራደር መቅረብ ይገደድ ነበር። ምናልባትም ያለምንም ጦርነት ከምጽዋም ለቆ እንዲወጣ ይገደድ ነበር ወይም እንደ ግብጾችና ቱርኮች በምጽዋ ብቻ ተወስኖ እንዲ ቀመጥ ይገደድ ነበር።

12. ጣሊያኖች የጦርነቱ ሁኔታ ራሳቸው በዚህ ዓይነት ሲመለከቱ አቶ[1] ተክለ ጻዲቅ ግን በመጽሐፉ የጠቀሰው ከሁሉ የበለጠ ደግሞ በኢጣሊ ያኖች ዘንድ ያለው የድርጅት ሁኔታ እስጊ ነበር። ጀኔራል ባራቲየሪ ድል ከሆነ በ4 ቀን ጀኔራል ባልዲሴራ ቁጥሩ 15,000 የሚደርስ አዲስ የጦር ወታደር ይዞ ምጽዋ ደርሶ የዓድዋን ውጊያ ውጤቱን ሰምቶ ድንጋጤም ገብ ርም፤ እንደደረሰበት ቢታወቅም ከዓድዋ ጦርነት የሸሹትን ሰብስቦ እንደ ምንም የጦሩን ቁጥር እስከ 20,000 አድርሶ ከመረብ ባሻገር ያለውን ሀገር ለመከላከል ቆርጦ ይጠባበቅ እንደነበረ ግልፅ ነው ብሉ የገፋው ከእውነት የራቀ ታሪክ ነው።

13. አጼ ምኒልክ ከዓድዋ ጦርነት በፊት በውጫሌ ውል የሌለ በልዩ ውል ኢጣልያኖች እስከ መረብ ድረስ መሬት እንዲያገኙ እንዳረጋቸው ሁሉ አሁንም በነበረው የግል ዓላማ በመመራት በፍቃደኝነት ጣሊያኖች የቅኝ ግዛት ወሰናቸው እስከ መረብ እንዲሆን ፈቅዶ ሰጣቸው። ጦርነቱም በዚህ ዓይነት መንፈስ ነበረ የተደመደመው ወይም ያቆመው። ጣሊያኖችም አጼ ምኒልክን የልቡ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በሰላም ተወዳዳሪያቸው በሻ ለቃ ሳልሳ አማካኝነት በለመዱት የሸዋ ፖለቲካ ስልታቸው በመጠቀም (Poli tica Sciouana) በወቅቱ አራማጅ በመሆን «ትግራይ ትልቅ ስትሆን ለሸዋ አደገኛ ትሆናለች» በማለት በዘኩላቸው ለማስረዳት ሙከራ አድርገዋል። የጣሊያኖች የወሰን ጥያቄ ምኒልክም በፍቃዱ የሚቀበለው በመሆኑም ያለ ምንም ውጣ ውረድ በድርድሩ ወቅት የዚህ ጉዳይ ችግር አልፈጠረም።

14. ጀኔራል ባልዲሴራ ከሀገሩ ወደ አፍሪካ ሲላክ ጦርነት የናፈቀው በጠቅላይ ምኒስትሩ ክሪስፒ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን ተሰጥቶት የነበረው መ መሪያ ጦርነቱን በተጠናከረ መልክ እንዲቀጥል ነበር። ምጽዋ እንደደረሰ ግን ተሸንፎ የተበታተነ ሠራዊት ስለጠበቀው በአዲሱ መንግሥት መመሪያ መሠረት ከራሱ ለመንግሥቱ የሚደረገውን ነገር መጠቆም ነበረበት።

15. አጼ ምኒልክ ስለ ሠላም ለመነጋገር ተልኮ የነበረው ሻለቃ ሳልሳ ወደ ዓዲኡግሪ ተመልሶ መጥቶ ስለነበረ ጀኔራል ባልዲሴራ ማርች 2 ቀን 1896 ዓ.ም. ቅድሚያ የሚሰጠው ስለሰላም መነጋገር ጉዳይ ስለሆነ ለኢ ጣሊያ መንግሥት የሚከተለውን ቴሌግራም ልከዋል። የሰላም ድርድር ለማ ድረግ በሻለቃ ሳልሳ የቀረቡ ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው። 1/ ወሰኑ መረብ እንዲሆን 2/ የውጫሌ ውል አንቀጽ 17ኛ እንዲቀር 3/ በራስ መንገሻ ስር የሚስተዳደር ሀገር ትግራይ የበታች ሹማምንቶች ሹመት ኢጣሊያ የምትስማማበት መሆን እንዳለበት 4/ ከዓዲግራትና ከሌሎች ከመረብ በስተደቡብ በኢጣሊያ ከተያዙ ቦታዎች ኢጣሊያ ለቃመውጣት እንዳለባት። ከዚህ የበለጠ መጠየቅ ስለማይቻል በነዚህ ነጥቦች መሠረት የሰላም ድርድር ለማድረግ እንዲፈቀድልኝ እለምናለሁ የሚል ነበር።

1 አቶ ተክለ ጻዲቅ:አጼ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት: ገጽ 47



ለዚሁ ቴሌግራም የጦር ሚኒስትሩ ቴሌግራሙ በደረሰው ዕለት ከጠቅላይ ሚኒስትር ተማክሮ የሰላም ድርድር ለማድረግ የተፈቀደለት መሆኑን ለጀኔራል ባልዲሴራ መልስ ሊልክ ከአጼ ምኒልክ ብቻ ኢትዮጵያ ከሌላ መንግሥት ስር (Protectorate) እንዳትሆን ማረጋገጫ መጠየቅ እንዳለበት ከገለፀለት በኋላ ይህ ግን ለሰላሙ ድርድር መጓተት ምክንያት መሆን እንደ ማይገባ መመሪያ በመስጠት ፅፈዋል።

16. ጀኔራል ባልዲሴራ በዚሁ ጊዜ ተጨማሪ ጦር ስለተላከለት 43,000 ወታደር ነበ ረው። ይኼም ሆኖ ጀኔራሉ ከሱ በፊት ከነበረው ከጀ ኔራል ባራቲየሪ የበለጠ ድንጋጤ እንደ ነበረው የሚያሳየው የጠበቀውን የኢት ዮጵያ ሠራዊት ከጉራዕና ከአሥመራ መሐል መስፈር ቢወገድለትም ለአንድ ወር ብቻ የሚበቃ የምግብ ክምችት የነበረው በዓዲግራት የተከበበው የኢጣሊያ ጦር በአስቸኳይ ሊደርስለት አልቻለም። ከሁለት ወር በኋላ ነው በልዩ ዘዴ በመ ጠቀም ከበባውን ሊያስለቅቅ የቻለው። የተጠቀመውን ዘዴ በሐሰት በዓድዋ የጦር ግንባር ጦርነት የከፈተ በማስመሰል የንራስ እሉላ ጦር ወደ ዓድዋ ለመሳብ በመቻሉ በአማዳፊ በመ ጓዝ ፀሰንአፊ በኩል ዓዲግራት የተከበበው የኢጣሊያ ጦር ሊያስለቅቅ ችሏል። በየመፅሐፉ በስዕሉ የሚታየው ስለ ዓዲግራት ከተማ ነፃ መውጣት ግን በክሊሜነስ (XIMENES) የተሳ ደፈ ስዕል የኢጣሊያ ወታደር ምስል «ቦድሬሮ» የተባለው የኢጣሊያ የመቶ ዓለቃ ጣሊያ ኖች በጦርነት አሸንፈው በፈረስ እየጋለቡ እንደያዙ በማ ስመሰል የሚያሳይ ስዕል ነው።

17/ ጀኔራል ባልዲሴራ ዓዲግራት ለመድረስ ጥቂት ቀኖች የሚወስ ደው ብዙ ወታደር አሰልፎ 2 ወር ነው የወሰደበት። ምንም ውጊያ ሳያረግ ነበረ የተከበቡ ወታደሮች ማስለቀቅ የቻለው። ጉዞውም የተካሄደው በ4 ደረጃዎች ተከፍሎ ነበር።

1/ በመጀመሪያ ወር ከዓድዋ ጦርነት ፍፃሜ በኋላ በማርች ወር ዘማች ወታደሮች በአ ሥመራና በአካባቢዋ በመከላከል በተጠንቀቅ ማከማቸት 2/ ደረጃ በአፕሪል ወር ከአሥ መራና ጊንዳዕ መስመር እስከ ግይ ሰራው መንቀሳቀስ ነበር 3/ ደረጃ ከአፕሪል መጨረሻ እስከ ሜይ 20 ከዓዲ ቀይህ ተነስቶ ወደ ዓዲግራት መግባት ነበር 4/ ደረጃ ወደ ዓዲ ቀይህ መመለስ ከሜይ 20 እስከ ጁን መጀመሪያ ቀናት ነበረ። ከዓድዋ ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር መረብን ተሻግሮ ጣሊያኖችን ማሳደድ አቅም እንዳልነበረው የገለፀው አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ብቻ አልነበረም። በደርግ ጊዜ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ፕሮፌሰሮች በራ ዲዮና በቴሌቪዥን ይኼንን ሃሳብ ሲያስተጋቡ እንደነበረ የቅርብ ትዝታችን ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ ለማስተባበል ከላይ ከጠቀስኩት መፅሀፍ ሌላ ከኤሚሊዮ[1] ቤላቪታ የተደረሰው «ዓድዋ» የሚለው መፅሀፉ አቶ ተክለ ፃዲቅም በዋ ቢነት የተጠቀሙበት ስለ ዓድዋ ጦርነት የተሰጠዉ አስተያየቶች ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ። 1/ ከዓድዋ ጦርነት ማግሥት የኢጣሊያ ሕዝብ በአደባባይ ወጥቶ «ቪቫ ምኒልክ (Viva Menelik)» እያለ ይጮህ እንደነበረ የተመዘገበ ታሪክ ሲሆን ጣሊያኖች ግን ሀገራቸው ከፈረንሳይ ጋራ ሆነው እውስትሪያን ባሸነፉበት ጊዜ በአውስትሪያ ዋና ከተማ በቪየና አደባባይ «ቪቫ ጋሪባልዲ» «ቪቫ ማዚኒ» እያለ የቪየና ሕዝብ ይጮህ ነበረ ብለው ተፅናንተዋል።

1 Emilio Bellavita: Adua p.304

2/ ጀኔራል ሮቢላንት የተባለው በ1887 ዓ.ም. «በኢት ዮጵያ የሚደረገው ዘመቻ ማንኛውም አደጋ ለመመከት በወታደር፡ በመ ርከቦች፣ በገንዘብ፣ ጠንካራ ድጋፍ ከሌለ ከህገሩም ተባባሪ የሚሆኑ ለመ ፍጠር ካልተቻለ ዘመቻ መሞከር አስፈላጊ አይደለም፡ የአዋ ቂነት ስራም አይደለም፣ የቦታ ርቀትና የመገናኛ ችግሮች እኛ ከምንገምተው በላይ ነው። በኢትዮጵያ መዝመት ከፈለግን የሽንፈት ዝቅተኛ ትንበያ እንኳን እንዳ ያጋጥመን ለማስወገድ አስቀድሞ በሚገባ የተጠና በቂ ዝግጅትና የጦር መሣ ሪያ ያስፈልጋል ብሎ ነበር። 3/ ጀኔራል ማርሴሊ ከዓድዋ ጦርነት ፍፃሜ በኋላ በአንድ የናፖሊ ጋዜጣ የፃፈው በእኔ አስተያየት በኢ ትዮጵያ ላይ የሚደረገው የማጥቃት ጦርነት መተው ያስፈልጋል። ምክንያቱም ኢጣሊያ የምትችለው አይደለም፣ ያላትንም ዓላማ ማላካት አትችልም ብሎ ነበር። 4/ ጀኔራል ባል ዲሴራ «አዲጂ» ከተባለው ጋዜጣ ላይ ከዓድዋ ጦርነት ጥቂት ቀን በፊት በጻፈው «ማስታወስ የሚገባውን በኤርትራ መንገዶች ለለ ሌሉ፡ የዝግጅትም ማነስ፣ የስንቅና ትጥቅ እጥረትም ምክንያት ወዘተ ወደ ፊት ለመግፋት፣ ለማፈግፈግ፣ ለመሰባሰብ ከፍተኛ ችግር አለ» ብሎ ነበር። እንዲሁም በአንድ የ«አንኮና» ጋዜጣ «በኢትዮጵያ በጦር መሣሪያ ጋጋታ እና ብዙ ገንዘብ በማፍሰስ ብቻ መግዛት የሚቻለው ብዛት ያለው ወታደር ከሌለ በለፈው የኢትዮጵያ ደጋ መሬት መኖር አይቻልም፣ ምክንያቱም በጊዜ ብዛት ከጥቃትና መሸነፍ ማምለጥ አይ ቻልም። ስለዚህ ወይንም አዲስ ዘመቻ ቢያንስ ከሀምሣ ሺህ ወታደርና በሁለት መቶ ሚሊዮን ሊሬ ወጪ ወይንም እንደገና ሌላ ጊዜ መዋረድ ይጠብ ቀናል» ብሎ ነበረ። 5/ በሩዲኒ መን ግሥት የጦር ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው ሪኮቲ «እንደገና ጦርነት ማድረግ ከተፈለገ መቶ ሃምሣ ሺህ ወታደርና ግማሽ ቢሊዮን ሊሬ ገንዘብ ያስፈልጋል፣ ከዓዲግራት ለቆ እንዲወጣ ለባልዲሴራ ትዕዛዝ አስተላልፈአ ለሁ» ብሎ ነበር።

6/ ካርዱቺ(Carducci) የተባለው ታዋቂው የኢጣሊያ ፀሐፊ ከዶጋሊ ጦርነት ማግሥት ሲፅፍ የኢጣሊያ ወታደሮች «ኢጣሊያን የሚወሩ ክሮዋቶች» ብሎ ነበር።

7/ ከዚሁ ጥቂት ዓመት በኋላም ጋብርኤሌ ዳኑንሲዮ ሌላ ታዋቂ የኢጣሊያ ፀሐፊ በዶ ጋሊ የሞቱት 500 የኢጣሊያ ወታደሮች «500 አውሬዎች» ብሎ ዘልፏቸው ነበር።

8/ ከዓድዋ ጦርነት ፍፃሜ ሁለት ቀን በኋላ ኢምብሪያኒ የተባለው በኢጣሊያ የፓርላማ አባል፣ ፓርላማ እንዲያፀድቀው ብሎ 19.000 ፊርማ በማሰባሰብ ኢጣሊያ ከአፍሪካ ለቃ እንድትወጣ የሚል ሃሣብ አቅርቦ ነበር። ተቀባይነት ያላገኘውም «ወደ አፍሪካ መሄዳችን አስፈላጊ አልነበረም፣ አሁንም ለቀን መውጣታችን ሐፍረት ነው» የሚል አስተያየት ከክ ሪስፒ ከተሰጠው አስተያየት በመመሬት ብቻ ነው።

9/ የሌሎች ከላይ የቀረቡ አስተያየቶች የጠቀሰ ፌዴርሶኒ የተባለው ራሱ ሲፅፍም «በዓድዋ ጦርነት የተሸነፈው ባራቲየሪ ወይንም ክሪስፒ አይደ ለም። የአንድነቷ ምክንያት ታውቆ ያልነበረች ፈሪ፣ ደካማና ወላዋይ የነበረ ችው፣ ነፃነቷን አንድነቷን ልታገኝ የቻለችው በራሷ ጉብዝና ሳይሆን በአውሮፓ ሰፍኖ በነበረው ውጥረትና እርስ በእርስ ፉክክር እንዲሁም በጥቂት የራሷ ዜጎች ጀግንነት ብቻ በመጠቀም መንፈስ ደካማ የነበረችው ኢጣሊያ ራሷ ናት» የተሸነፈችው በማለት ነበረ የገመገመው።



በዓድዋ ጦርነት ማግሥት ለጀኔራል ባልዲሴራ ሶስት ችግሮች ተደቅኖበት ነበረ:- 1/ የኢትዮጵያ ጦር ከጉራዕና አሥመራ መሐል እንዲለፍር ተገምቶ ስለነበረ አዲስ ዙር ጦርነት መግጠም ተፈርቶ ስለነበረ ዋንኛው ችግር ነበረ፤ 2/ ዓዲግራት ላይ የተከበቡ የኢጣሊያ ወታደሮች ማስለቀቅ 3/ በከሰላ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮችን ከደርቡሾች አደጋ ማዳን። የአ ንደኛውና የሁለተኛው ችግር ባልዲሴራ ያለምንም ደም መፋሰስ ስለተሳካለት የከሰላ ችግር በኢጣሊያ ጦር መኮንኖች የሚመራ በሀገር ተወላጅ ወታደሮች ኢንዲጀኒ ብቻ በተገነባ ጦር ወደ ከሰላ ዘምቶ አራት የኢጣሊያ መኮንኖች ሲሞቱ ሰምንት ቆስለው ከሀገር ተወላጅ ኢንዲጀኒ ወታደሮች 123 ሞተው 271 ቆሰለው ጣሊያኖች ደርቡሾችን ማሸነፍ ችለዋል። አጼ ምኒልክ ጣሊያኖች የነበረባቸው ችግሮች መረጃ የሚያቀርቡለት ብዙ ስለሆኑ የኢጣሊያኖች ችግሮችና ጠንካራ ጎኖች በሚገባ ያውቅ ስለነበረ መረብ ተሻግሮ ጣሊያኖችን ማጥቃት ይሳነዋል ተብሎ አይገመትም። የአጼ ዮሐንስና የአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የቅኝ አገዛዝ ዘመን ስለነበረ በሚቀጥሉት አርእስቶችም እንመለሰበታለን።



ዳ፪ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ

L'imperatrice Taitù (fot. Strazza) Menelic nel 1900

# ምዕራፍ 5

# የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አመሠራረት

## 1. የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መመኘት

ኢጣሊያ አንድነቷን ከመጐናፀፏ በፊት በየጊዜው ወሰናቸው ይቀያየር የነበረ ከ10 ባላነሱ መንግሥታት ተከፋፍላ ነበር የምትተዳደረው። አንዳንዱ ክፍለ ሀገሩዋም በባዕድ መንግሥታት ሥር ይተዳደሩ ነበር። ብዙ ጊዜ ኢ ጣሊያ የኃያላን የኤውሮፓ መንግሥታት የኃይል ሚዛን ማስጠበቂያና ማካካሻ ሁና ታገለግል ነበር። ኢጣሊያ ከነበሩዋት መንግሥታት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ በደቡብ ኢጣሊያ የነበረው የቡርቦን ንጉሣዊ አገዛዝና በሰሜን የነበረው የሳቮያ ንጉሣዊ አገዛዝ ይገኙባቸዋል። በደቡብ ኢጣሊያ የነበረው የቡርቦን ንጉሣዊ አገዛዝ ኤውሮፓ ከሚገኙት ንጉሣዊ ገዢ ቤተሰቦች የተዛመደ ነበር። ይህ ንጉሣዊ ቤተሰብ የስፔን እንዲሁም የፈረንሣይ ዘውድ ጭና ገዝቷል። ዝነኛው የፈረንሣይ ንጉሥ «ፀሐዩ ንጉሥ» ተብሎ ይጠራ የነበረው ሉዊ 14ኛው ቡርቦን ነበር። በዘመናችንም ከሥልጣን ተወግዶ ከቆየ በኋላ ዛሬ ተመልሶ የስፔን ንጉሥ የሆነው የቡርቦን ሐረግ ያለው ቤተሰብ ነው። በሰሜን ኢጣሊያ የነበረው የሳቮያ ንጉሣዊ ቤተሰብ ግን በተወሰኑ የፈረንሣይ፣ የኢጣሊያና የስዊስ አነስተኛ ቦታዎች ለብዙ ምዕተ ዓመታት አነስተኛ መን ግሥት ከመመሥረቱ በቀር ከታላላቅ የኤውሮፓ ንጉሣውያን ቤተሰቦች የተዛመዱ አይደሉም። በዋናው ሀገሩ አሁን የፈረንሣይ ክፍለ ሀገር የሆነችው ሳቮያ ሁና በፈረንሣይ ነገሥታት ተወዳድሮ ወደ ኃያሏ ፈረንሣይ ግዛት ማስፋፋት አልቻለም። ባንድ ወቅት የስዊዝ ንጉሥ ለመሆን አቅዶ ነበር። ነገር ግን ተቀ ባይነት ሳያገኝ ቀረ። በመጨረሻ ኢጣሊያ አንድነቷን ለማግኘት እ ስተባባሪ አጥታ ስለ ነበር ኢጣሊያ በስዊዝ አንፃር ሰፊ ሀገር ብዙ ሕዝብ ያላት ለመሆንዋ ብልጦቹ የሳቮያ ንጉሣዊ ቤተሰቦች•ኢጣሊያ አንድነት ዓላማና ባንዴራ በማውለብለብ የተዋሃደች ኢጣሊያ ንጉሥ ለመሆን በቅቷል። የኢጣሊያ ሠራዊት የጦር መሪከሩ ሳቮያ ነበር። በሀገራችንም የኢጣሊያ ቅጥር «ባለቀለም» ወታደሮች ተሰተጋብቶ ይጠቀሙበት ነበር። የደቡባዊ ኢ ጣሊያ ቡርቦን ንጉሣዊ ቤተሰብ ግን በብልጥነት ባለመጠቀማቸው 1.000 ከሰሜን ኢጣሊያ የመጡ ወደ ዘማቾች ከሥልጣናቸው ሊያባርሩቸዋው ችሏል።

በኢጣሊያ ይገኙ የነበሩ መንግሥታት እንደ ጐረቤቶቻቸው ትንሿ ፖርቱጋል፣ ስፔን፣ ፈረንሣይ ከሀገራቸው ውጭ ቅኝ ግዛት ለመፍጠር አልቻሉም። ከአንድነት በፊት የመጨ ረሻዎቹ ዓመታት ከሀገራቸው ውጭ ለማግኘት ይፈልጉት የነበረ መሬት ለፖለቲካ እስ ረኞቻቸው ማጐሪያ ብቻ ነበር። በ1850 ዓ.ም የቡርቦን ደቡባዊ የኢጣሊያ መንግሥት ለፖለቲካ እስረኞች ማጐሪያ የሚውል መሬት ለማግኘት ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ተዳ ጽፎ ነበር። አንድነታቸውን ካገኙ በኋላም ቢሆን ኢጣሊያኖች የቅኝ ግዛት ምኞት ያደረባቸው ለእስረኞቻቸውና ለገዞተኞቻቸው የሚውል፣ ካገራቸው ራቅ ያለ በረሃማ መሬት፣ ለእስረ ኞች የማምለጥ ዕድል የማይሰጥ፣ በአነስተኛ ጥበቃ ለማኑር የሚቻል ፈልገው ነበር። 1ኛ.



ይህ ሙከራ ግን የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻ አልነበረም። በዚሁ ዓ.ም ደጃዝማች ንጉሴ በአጼ ቴዎድሮስ እጅ ገብቶ ስለተገደለ ለብዙ ጊዜ ሲታሰስበት የነበረው እቅድ ተግባራዊ ሣይሆን ቀረ። ይህ ሙከራ ግን የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻ አልነበረም።

## 2. በብርታኒያ መሪነት የኢጣሊያ

## የመጀመሪያ ወረራ በኢትዮጵያ፣ የምፅዋ ወረራ፣

አፄ ዮሐንስ የኢጣሊያ ወረራን ሲቃወሙ



- IL RE GIOVANNI.



Révérend Père J.-B. COULBEA

ከ1862[1] ዓ.ም ጀምሮ በአንጎላና በሞዛምቢክ የበፈራ፣ የወሕኒ ቤትና የግዞት ቦታዎች ለማቋቋም የኢጣሊያ መንግሥት ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ያደረጋቸው ውይይቶች ጣልያኖች የሚሰጧቸው መሬቶች ጊዜያዊ ሳይሆን ለዘለቄታ እን ዲጠቀሙባቸው ያቀረቡት ጥያቄ በፖርቱጋል በኩል ተቀባይነት ስላላገኘ ሳይሳካ ቀረ። 2ኛ. በአሌውቲኒያን ደሴቶች ከአላስካ አጠገብ ከሩሲያ ጋራ 3ኛ. በፎክላንድ ከእንግሊዝ ጋራ 4ኛ. እንዲሁም ከሱማትራ 5ኛ. ከቬኔዙዌላ 6ኛ. ሰሜን ምዕራብ ቦርኒዬ 7ኛ ዙላ በኢትዮጵያ 8ኛ. ካቢንዳ (ዛየር) 9ኛ. ሞዛምቢክ 10ኛ. አዲሲቷ ጊኒ ወዘተ ጣሊያኖች ለአሰረኞች የሚያገለግል መሬት የመግዛት ጥያቄ አቅርቧል፣ ሆኖም ውጤት ሣያገኙ ቀርቷል። በዘመኑ ብዙ ጣልያኖች ሠራተኞች ያለ ምንም ዕቅድ ገንዘብ (ካፒታል) ሳይኖራቸው፣ ከመንግሥታቸው ምንም እርዳታ ሣይደረግላቸው ወደ አሜሪካ ይሄዱ ነበር።

የሥራ ኮንትራት በሚል ሽፋን በቀድሞ ጊዜ በጥቁሮች ባሮች ተይዘው የነበሩ የሥራ ቦታዎች በጣሊያኖች ተተኩ። ይህ አዲስ የባርነት ዓይነት ሕጋዊነት አገኘ። በዚህ የተነሳ ኢጣሊያኖች ተበሳጭተው ትኩረታቸው ወደ አፍሪካ ሆነ። በአፍሪካም ቢሆን ከሀገራችን ሌላ ያልተያዘ ሀገር አልነበረም። ኢጣሊያ የቅኝ ግዛት መመኘት የጀመረችው ከሌሎች የኤውሮፓ ሀገሮች ዘግይታ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት እስከ 1861 ዓ.ም ለራሷ አንድነትና ነፃነት ስላልነበራት ነው። ኢጣሊያ ካሏት 20 ክፍላተ ሀገሮች ሁለት ብቻ አንድ ላይ ሆነው በሳቮያ ንጉሣዊ ቤተሰብ መሪነት የሳርዲኒያ መንግሥት በሚል ስያሜ ለብዙ ጊዜ ነፃ መንግሥት መሥርተው ሲኖሩ በመጨረሻ ተሣክቶላቸው የኢጣሊያ አንድነት አንኳፀፉዋቸው። የቀሩት ግን እስከ 1861 ዓ.ም ድረስ ግማሽ በባዕድ መንግሥታት ሲገዙ ግማሾቹ ደግሞ ጥቃቅን መንግሥታት ነበሩ። ኢጣሊያ አንድነቷና ነፃነቷን ሣትቀዳጅ የሳርዲኒያ መንግሥት በ1852 እና በ1857 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን ከነበሩት ከኢጣሊያኖች ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ጋራ ደብዳቤ በመፃፃፍ በሀገራችን ላይ የቅኝ ግዛት ለመመሥረት ምኞት ነበራት። የሳርዲኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረውና የኢጣሊያ አንድነት ገምቢ ካቩር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዳሬክተር በነበረው ነግሪ አማካይነት በአሮሞ ሀገር የካቶሊክ ሚሲዮን ኃላፊ የነበረው ለካርዲናል ማሳያ በፃፈው ደብዳቤ ከኢትዮጵያ መሣፍንቶች ከሁሉም ኃይለኛ ከሆነው የንግድና የወዳጅነት ውል በሳርዲኒያ መንግሥት ስም እንዲፈራረሙ ፍላጎታችን ነው የሚል ነበር። ካርዲናል ማሣያም በአባ ሌዮን ዳቫንቸር አማካኝነት ደጃዝማች ንጉሤን በመጠቀም የአብዛኛው ኢትዮጵያ ሀገረ ገዢ መሆኑንና በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ዐምጾ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለመሆን የነበረው ፍላጐት እንዲረዳው ወታደራዊ እርዳታ ከተሰጠው በቀይ ባሕር ዙላ አጠገብ ለሳርዲኒያ መንግሥት መሬት ለመጠት ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ ለካቩር መልስ ይሰጣል። ዘመኑ ኢጣሊያ በሣርዲኒያ መንግሥት መሪነት ነፃነቷንና አንድነቷን ለመቀዳጀት ከባድና መሣኝ ትግል የምታደርግበት ስለነበረ፣ ሁለተኛም ጠቅላይ ሚኒስትር ካቩር 1861 ስለሞት እንዲሁም በዚሁ ዓ.ም ደጃዝማች ንጉሴ በአጼ ቴዎድሮስ እጅ ገብቶ ስለተገደለ ለብዙ ጊዜ ሲታሰብበት የነበረው እቅድ ተግባራዊ ሣይሆን ቀረ።

1 A Gaibi: Manuale dl Storia Politico Militare delle Colonie Italiane p.6



ኢጣሊያ ምፅዋን ወራ በያዘችበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ ጐን ይገኙ ከነበሩ የውጭ ሀገር ሰዎች፤

1ኛ. አባ ኩልቦ ፈረንሳዊው ላዛሪስት ሚሲዮናዊ ከሃይማኖት ሥራው ሌላ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ሐውልታዊ ጽሑፍ ደራሲ የኢትዮጵያ ወዳጅ። ጣሊያኖች ኤርትራን እንደያዙ ፀረ ኢጣሊያ ተብሎ ከኤርትራ እንዲወጣና ተመልሶ እንዳይገባ አገዳ ተደርጎበት የነበረ።[1]

2ኛ. ዶክተር ኒኮላ ፓሪሲስ ግሪካዊ በአጼ ዮሐንስ ጠያቂነት ከግሪክ ንጉሥ የአጼ ዮሐንስ ሐኪም እንዲሆን ተልኮ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር ከ1884 እስከ 1886 በኢትዮጵያ ከኖረ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የአቴንስ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የነበረው በኢትዮጵያ በኖረበት ሁለት ዓመታት ስለ ተመለከተው ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ በሕክምና በማተኩር ኢትዮጵያን በማድነቅ መጽሐፍ ጽፏል። ሀገሩ ከተመለሰ በኋለም የኢጣሊያ ወንድሞቼ እያለ በጋዜጦች ኢትዮጵያን ከመውረር እንዲቆጠቡ ተማጽኖዋል። በጣሊያኖች ዘንድ ግን አሻጥረኛ ፀረ ኢጣሊያ ግለሰብ የአጼ ዮሐንስ አማካሪ እየተባለ ተወቅሷል።

3ኛ. ዶክተር ለዮፓልዶ ትራቨርሲ ለስለላ ከኢጣሊያ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የተላከ። በዓድዋ ጦርነት ምክንያት ከአዲስ አበባ ለቆ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ የተለያየ ሹመት አግኝቶ በኢትዮጵያ የኖረ፤ "ልጥ ግረፊያ" የተሰኘው ስለ ኢጣሊያ የስለላ ተግባር በኢትዮጵያ መጽሐፍ ደራሲ ይገኙባቸዋል።

ፈረንሣውያን ላዛሪስት ሚስዮናውያን የኢጣሊያ ጠላት ተብለው በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ከኤርትራ እንደተባረሩ በአባ ሚኬለ ዳ ካርቦናራ (Padre Michele Da Carbonara) የሚመሩ ትምህርት የሌላቸው ካፑቺኒ ሚሲዮናውያን ጣሊያኖች ተተኩ።

ከመጀመሪያ የኢጣሊያ የምፅዋ ወረራ ጀምሮ እስከ ዓድዋ ጦርነት ጊዜ ድረስ ላዛሪስት ፈረንሣዮች ሐበሾችን በመደገፍ ያራምዱት ለነበረ ተግባር አባ ሚኬለ ዳ ካርቦናራ ከኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በመተባበር አከሽፈዋል ።

አባ ሚኬለ ከሮማ ሲነሳ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ከነበረው ክክሪስፒ ድጋፍ አግኝቷል፤ በኤርትራ ከኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ጋር ተባባሪ ነበረ፤ ከጀነራል ባራቴሪ ጋራ ወዳጅነት ፈጥሮ ነበረ፤ በፈርዲናዶ ማርቲኒ ዘንድ ልዩ አክብሮት ነበረው፤ በማርቲኒ ቦታ የኤርትራ የመጀመሪያ ሲቪል ሀገረ ገዢ የተተካ ሳልቫጎ ራጂ ፍቅር አትርፈዋል፤ ከኢጣሊያ ንጉሥ ኒሻን ተሸልመዋል።[1]

1. F.I.CI p. 56

ኢጣሊያ ምፅዋን በምትወርበት ጊዜ ተዘናንታ ነበረ የገባችው። ሁለት ኃያላን መንግሥታት እንግሊዝና ፈረንሣይ አፍሪካን ለመቀራመት ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ የፈረንሣይ ከምዕራብ አፍሪካ እስከ ምሥራቅ ቀይ ባሕር ድረስ ኩታ ገጠም የሆነ ቅኝ ግዛት ለማድረግ ስትጥር እንግሊዝ ደግሞ በበኩሏ ከሰሜን አፍሪካ ከግብፅ ወይም ከሱዳን እስከ ደቡብ አፍሪካ ኩታ ገጠም ግዛት ለማድረግ በምትጥርበት ጊዜ እንግሊዝ ፈረንሣይን በመቅደም ኢጣሊያን የራሷ መሳሪያና ደጋፊ ለማድረግ አቅዳ ከአሰብ እስከ ምፅዋ ያለውን የባሕር ጠረፍ እንድትይዝ ሁለቱ ሀገሮች ተስማሙ። በዚሁ ጊዜ ኢጣሊያ ኃያሏ ታላቋ ብሪታኒያ ከጎኗ ከማሰለፏም በላይ ከብሪታንያ ድጋፍና ግፊት ስላልተለያት በግብፅ እጅ ያለምንም መከላከያ ኃይል ትኝኝ ወደ ነበረችው ምፅዋ በኮ/ሉ ሳሌታ የሚመራው 802 ወታደሮች የኢጣሊያ ጦር አዝምታ ፌብሯሪ 5 1885 ዓ.ም ያለምንም ደም መፋሰስ በቁጥጥሯ ስር አደረገቻት። ኮ/ል ሳሌታ ከኢጣሊያ ሲነሳ ተሰጥቶት የነበረ ትዕዛዝ በአፋር በረሃ የተገደሉ የኢጣሊያ ዜጎች ለመበቀል ወደ አሰብ መሳኩ እንጂ ምፅዋን እንዲይዝ የተነገረው ሱዳን ሱዋኪም ወደብ ሲደርስ ብቻ ነው። ከጦር መርከቡ አዛዥ ካይኒ ጋራ ሆኖ ምፅዋን በያዘበት ጊዜም ቢሆን የኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ብቻ እንዳይውለበለብ የኢጣሊያና የግብፅ ሰንደቅ ዓላማዎች አንድ ላይ እንዲውለበለቡ ፈቀደ። በምፅዋ የግብፅ ባለስልጣናት ምፅዋን ለመያዝ ጣሊያኖች የመጡ መሆናቸውንና ከመንግሥታቸው ከተማውን ለመያዝ የተሰጣቸው የጽሁፍ ትዕዛዝ ከተነበበላቸው በኋላ ተቃውሞዋቸውን አሰሙ። የኢጣሊያ ወራሪ ወታደሮች ግን ወደ ምፅዋ የዘመቱት ብቻቸውን አልነበረም። ምፅዋ የነበሩት የግብፅ ባለሥልጣኖች ጉዳዩ ያልተነገራቸው ስለነበረ ጣሊያኖቹ አናስገባም ብለው ተኩስ እንዳይከፍቱ በመፍራት «ኮንዶር» የተባለችው አንድ የእንግሊዝ መርከቧን አጅባ ምፅዋ ገብታ ስለነበረ የመርከቡ አዛዥ ጣልታ ገብቶ የግብጾችን ተቃውሞ ለማብረድ በመቻሉ ግብጾችም ወታደሮቻቸው ወደ ሱዳን ዘምተው ስለነበረ በቂ የሰው ኃይል ስላልነበራቸው አድራጎቱ ሕጋዊ አይደለም። ከአቅማችን በላይ የመጣ ኃይል ግን ሳንወድ በግድ ተቀብለናል ብለው ተቃውሞቸውን ካሰሙ በኋላ በተለይ እንደ ሱዳን የግብፅና የኢጣሊያ ጥምር አስተዳደር ይሆን ይሆናል ተብሎ ስለተነገራቸው ጣሊያኖች ከተማዋን እንዲይዙ ፈቅደውላቸው አሰብ በገንዘብ ከተገዛች ልክ 15 ዓመት በኋላ ምፅዋን በቁጥጥራቸው አድርገዋል። በሚቀጥሉት ወራት የፈረንሳይ የጦር መርከቦች ምናልባት ይመጡ ይሆናል ተብሎ እየተፈራ ስለነበረ ጣሊያኖች ከምፅዋ እስከ አሰብ ያሉት የባሕር ወደብ ጠረፎች የዳሕላክ ደሴቶችና አርቂቆም በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ።



በምፅዋና በአካባቢዋ ይዞታቸው ከአጠናከሩ በኋላ ጣሊያኖች ግዛቶቻቸው በአዋጅ «የአሰብ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት» የሚል ስያሜ ቀርቶ «በቀይ ባሕር የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች» የሚል አዲስ ሁለተኛ ሥያሜ ሰጥቷቸዋል። በምፅዋ የኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ከግብፅና ከቱርክ መንግሥታት ሌላ ሩሲያም በሃይማኖት ምክንያት ከኢትዮጵያ ጋራ መቀራረብ ስለነበራት ተቃውማለች፤ ፈረንሳይም በይበልጥ ተቃውማለች። በተለይ በኤርትራና በ ትግራይ የነበሩ የፈረንሳውያን ካቶሊክ ሚስዮናውያን ወረራውን ከመቃወማቸው በላይ ኢትዮጵያ ኤርትራን እንዳታጣ ተሳትፎ አበርክተዋል፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተቆርጣ ለኢጣሊያ እንዳትሰጥ በብርቱ ተቃውሞ አሳይተዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ ምርምር ያካሔዱት ምሁራን ቄሶች ስለነበራቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ከሁሉ በላይ ደግሞ በአጼ ዮሐንስ 4ኛ ንጉሠ ነገሥት ትመራ የነበረች ኢት ዮጵያ ተቃውሞ በማሰማት ብቻ ሳትወሰን እንደሚታወቀው መራራ ትግል አካሄዳለች።

ትራቬርሲ[1] የተባለው የኢጣሊያ ዜጋ «ልጥ ግሪፍያ» በተሰኘው መጽሐፉ ደራሲ ምፅዋ በኢጣሊያ ወታደሮች በተወረረችበት ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ ወደ ሚገኙበት በሥራ ምክንያት ይገኝ ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱም በከባድ ድንጋጤና ቁጣ ተውጦ እንደነበረ ለማየት ችሏል። ሌሎች ፈረንጆችም ነበሩ፤ ከእነሱ ውስጥም

1ኛ. በምፅዋ የፈረንሳይ ም ክትል ቆንስል ለሜይ፤

2ኛ. ታዋቂው የፈረንሳይ ዜጋ ላዛሪስት ሚስዮናዊ አባ ኩልቦና

3ኛ. ዶክተር ፓሪሲስ የተባለው ጣሊያኖች ከልክ በላይ ይፈሩትና ይጠሉት የነበረ የአጼ ዮሐንስ ሐኪም ይገኙባቸው ነበረ።

አባ ኩልቦ ከአጼ ዮሐንስ ጎን መገኘቱ አጼ ዮሐንስ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ይጠላል የሚለውን ወሬ ውድቅ ያደርገዋል። አጼ ዮሐንስ ይጠላው የነበረው ተንኮል የሚሰሩ በኢትዮጵያ አንድነት ያሴሩ የነበሩ እንደ ካርዲናል ማሳያ ያሉት ብቻ ነበር። የአጼ ዮሐንስ ቁጣ በይበልጥ የተጠናከረው የኢጣሊያ ባሕር ኃይል ዋና አዛዥ አድሚራል ካይኒ ምፅዋ ሲገባ ባወጣው አዋጅ ነበረ። በዚሁ የመጀመሪያ አዋጅ ካይኒ የኢጣሊያ ጦር ምፅዋ ሊገባ የቻለው የእንግሊዝ የግብፅና የአጼ ዮሐንስ ወዳጅ ስለነበረ ነው ብሎ ነበር። አጼ ዮሐንስ በተደጋጋሚ ትራቬርሲ የተባለው ጣሊያናዊን እያስጠራ የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ ምፅዋ የመጡበት ምክንያት ይጠይቀው ነበረ። ምንም እንደማያውቅ ብሎ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ሐኪም ወይም ሐገር የሚጎበኝ በመምሰል ሰላይ መሆኑን ጥርጣሬ ስላደረበት ጥያቄ ያበዛበት ነበር። የምፅዋ ወረራ በኢጣሊያ የተቀናጀና የተፈፀመ ሊሆን አይችልም። ጣ ሊያኖች ከዚህ ቀደም የቅኝ አገዛዝ ልምድ የሌላቸው እንደመሆናቸው መጠን ታላቁ የምፅዋ ዘመቻ ማሰብና መፈፀም ከአቅማቸው በላይ ነው።

1 Leopoldo Traversi : ibd p.303

ከዚህ ቀደም በአሰብ የለመዱት በሀገራቸው ውስጥም ተቃውሞ እየገጠማቸው ከባላባቶች በገንዘብ መሬት መግዛት ካልሆነ በስተቀር በጦርነት ለትኝ ግዛት አንድ ሀገር ለመያዝ አጋጥሚቸው አያውቅም ነበር። የምፅዋ ዘመቻ በአፋጣኝ በረቀቀ ዘዴ የታቀደውና ሥራ ላይ የዋለው በእንግሊዞች መሪነት ነው። በወቅቱ ግብጾች ታዋቂው የእንግሊዙ ጎርዶን ፓሻ ያለበት በሱዳን ከማህዲስቶች የተከፈተባቸው ጦርነት ምክንያት በውጥረት ነበሩ። ከባድ ሽንፈት እያገጠማቸው ነበረ። ኢጣልያ ምፅዋን እንድትይዝ በሪንግ ሉርድ ክሬመር በካይሮ ለኢጣሊያ ወኪል የእንግሊዝ መንግሥት ኢጣሊያ ምጽዋን እንድትይዝ ፍላጎቱ መሆኑን ገልጦለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሉርድ ግራንቪልም በጽሑፍ አረጋግጦ ነበረ።[1] በዚሁ መሠረት እንግሊዞች ከአፄ ዮሐንስ ጋራ ተባብረው ማህዲስቶችን ለመዋጋት ያቀረቡት ሐሳብ አጥጋቢ ውጤት ሳያገኝላቸው በመቅረቱ ፊታቸው ወደ ኢጣሊያ አዞሩ። እንግሊዞች የሱዳን ጦርነት የመጀመሪያና ቅድሚያ የሚሰጠው አጣዳፊ ዓላማቸው ሲሆን ጣሊያኖችን ወደ ምፅዋ መርተው ያመጡበት ምክንያት ሩቅ ዓላማቸው ምፅዋንና ቀይ ባሕር ወደቦች በፈረንሣይ እጅ እንዳያወድቁ የቅርብ ወዳጃቸው ኢጣሊያ ዘብ እንድትቆምላቸው ለማድረግ ነበረ። ስለ ምጽዋ ወረራ በኢጣሊያ የቀረበው[2] በኦክቶበር 12 1884 ዓ.ም የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣሊያ መንግሥት ምፅዋ በፈረንሳይ እጅ ከሚሆን በኢጣሊያ እጅ ቢሆን እንደሚፈልግ ጽኑ ፍላጎቱ መሆኑን ከመግለፁም በላይ ምፅዋን ለመያዝም በምፅዋ የተመደቡ የግብፅ ወታደሮች በሱዳን ጦርነት ለመካፈል የተላኩ ስለሆነ ተቃዋሚ ኃይል እንደማያጋጥማቸው አስረድቷቸው ስለነበረ ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ከምፅዋ እስከ አሰብ ያለው የባሕር ጠረፍ እንደ ማንቺኒ አባባል «ለእንግሊዝ መንግሥት ወዳጅነት በሌለው ሀገር እጅ እንዳይወድቅ ለመከላከል በኢጣሊያ ለእንግሊዝ የቅርብ ወዳጅ መንግሥት እጅ ሲሆን የሚመረጥ ስለሆነ» ምፅዋ በኢጣሊያ እንድትያዝ ተወሰነ።

ጣሊያኖችም በበኩላቸው ምፅዋን ለመያዝ በቢያንኪ የሚመሩ ጣሊያኖች በአፋር በረሀ የደረሰው እልቂት በእሱ ምክንያትም በጣሊያን ሥምና ክብር የደረሰው ውርደት ለመበቀል የሚል ሰበብ ስለነበራቸው በኮ/ል ሳሌታ የሚመራ ጦር በመላክ በኢትዮጵያ ወረራቸውን ለመፈጸም ወሰኑ። ኮ/ል ሳሌታ ከኢጣሊያ ሲነሳ የተሰጠው ዋና መመሪያ ወደ አሰብ ሄዶ ስለቢያንኪ እልቂት እንዲያጣራ ነበር። ሆኖም ሌላ ትዕዛዝም ለምላሌ ምፅዋን ለመያዝ ሊደርሰው እንደሚችል አስጠንቅቆት «ጎታርዶ» በተባለው መርከብ ጉዞውን ጀምሮ ጃንዋሪ 31/1885 ዓ.ም ስዊኪም ሊደርስ ከአድሚራል ካይኒ ቨስፑቺ የምትባለው የጦር መርከብ አዛዥ ተገናኝቶ ወደ አሰብ በመሄድ ፋንታ ወደ ምፅዋ እንዲሄድ አዲስ ትዕዛዝ ደረሰው። ሁለቱ መርከቦች ፌብሯሪ 3 ከስዋኪም ተነስተው ፌብሯሪ 5 በ4 ሰዓት 1885 ዓ.ም ምፅዋ ገቡ።

1. Trraversi : Ibd p. 302

2. F.i.c.i : Vol. I p. 84-88



ከሁለቱ ጦር አዛዦች በዕድሜ የሚበልጥ ካይኒ ስለነበረ ምፅዋን ለመያዝ ከግብጾች የተረከበ እሱ ነበረ። ጃንዋሪ 26/1885 ዓ.ም ካርቱም መህዲስች እጅ ወደቀች፤ ጄኔራል ጎርዶንና የግብፅ ወታደሮች በሙሉ መገደላቸውን በዚህ ቀን ወሬ ተሰማ። ይኸም ሆኖ እንግሊዝ ለኢጣሊያ ምፅዋን እንድትይዝ የምትሰጠው ድጋፍ አላቋረጠችም። ራሱ አድሚራል ካይኒ ስለምፅዋ መያዝ ያቀረበው ይፋዊ ሪፖርት እንደሚከተለው ይገልፃል። «መርከቦቻችን ወደ ወደቡ ሲቃረቡ ያልተጠበቀው ጉብኝት ማንነት ለማወቅ የሚሰበሰበው ሕዝብ ይታይ ነበር። ከመርከብ ወርደን ከግብፃዊ ምክትል ሀገረ ገዥ ኢፀት በይ ለመነጋገር ወደ ቤተ መንግሥት የአንድ ፎቅ ሕንፃ አመራን። በንግግሩ እንግሊዛዊው «የኮንዶር» መርከብ አዛዥ ተካፋይ ነበር። የምክትል ሀገረ ገዥ አስተረጓሚ ማርኮፖሉ ቤይ የሚባል ተካፋይ ነበረ። በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ እንደተቀመጥን አድሚራል ካይኒ ከኪሱ አውጥቶ ከኢጣሊያ መንግሥት ምፅዋን እንዲይዙ የተላኩ መሆናቸውን የሚገልፅ ቴሌግራም ካነበበ በኋላ ከመንግሥቱ ትዕዛዝ ደርሶት እንደሆነ ለኢዘት ቤይ ቢጠይቀው አልደረሰኝም በማለት መልስ ሰጥቶ ትዕዛዝ እስካልተሰጠው ድረስ ኢጣሊያ ምፅዋን እንድትይዝ የማይፈቅድ መሆኑን ይገልፃል። አድሚራል ካይኒም በመቀጠል ትዕዛዙ ግልፅ ስለሆነ ግብጾች የሚቃወሙ ከሆነ በኃይል ለመጠቀም እንገደዳለን፤ ከተማዋንም በጦር መርከቦች ትደበደባለች አለ። በዚሁ ጊዜ እንግሊዛዊው «የኮንዶር» መርከብ አዛዥ ጣልቃ በመግባት ብሪታኒያ ኢጣሊያ በምፅዋ የምትወስደው እርምጃ የማትቃወም መሆኗን፤ በካይሮ ስለዚሁ ጉዳይ የሚያውቁ መሆናቸውንና በሁለቱ መንግሥታት መሐከል ንግግሮች የተደረጉ መሆናቸውን ለኢዘት ቤይ ተገልጾ ትዕዛዙ መድረስ በመዘግየቱ ምናልባትም ጠፍቶም ሊሆን ስለሚችል እንዳይቃወሙ፤ ስለ ጉዳዩ ብቻ ለግብፅ መንግሥት እንዲያስታውቅ ብሎ በማረጋገጡ፤ ምክትል ሀገረ ገዢም ከጦሩ አዛዥና ከማርኮፖሉ ጋር በዐረብኛ ከተነጋገረ በኋላ ሰሞታው ለራሱ የግብፅ መንግሥት እና ለኢጣሊያ መንግሥት የሚያሰማ መሆኑን ገልጾ የጦር አዛዥ ተቃውሞውን እያሰማ በኃይል ማነስ ሊቋቋም ስለማይችል ብቻ ከተማዋን ኢጣሊያ እንድትይዝ የፈቀደ መሆኑን የሚል መልስ ለጣቸው። ከቀኑ 9:00 ሰዓት በሻምበል ጋርዲኒ (Gardini) የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ከመርከብ መውረድ ጀመሩ። በአቱምሎ የተመደቡ ማታው ወደ ተመደበላቸው ቦታ ደረሱ። ምሽጉን ባዶ ነበረ ያገኙት። በሞቱምሉ የተመደቡ ግን ሌሊት ነበረ የደረሱ። ስለሁኔታው የማያውቁ የተገኙ የግብፅ ወታደሮች ስለ ጉዳዩ ለማጣራት ወደ ምፅዋ መልእከተኛ ላኩ። በማግስቱ ጠዋት ከሀገረ ገዢው ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ኃይል ለለመ ጣባችሁ ምሽጋችሁን እያስረከባችሁ በጽሑፍ ከጣሊያኖች ብቻ ማስረጃ ተቀበሉ የሚል መልስ ለጣቸው። የጦሩ አዛዥ የሚገኝበት ሕንፃ ጣሊያኖች በሩን በመስበር ገብተው ሕንፃውን ያዙት። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት አድሚራል ካይኒ ለምፅዋ ነዋሪዎች የሚከተለውን መግለጫ አስተላለፈ:-

« የኢጣሊያ መንግሥት የብሪታኒያ፤ የቱርክ፤ የግብፅ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጅ ነው። ከዛሬ ጀምሮ የኢጣሊያ መንግሥት ምፅዋን በቁጥጥሩ አውሏታል። የግብፅ ሰንደቅ

ዓላማ ከኢጣሊያ ሰንደት ዓላማ ጐን ትውለበለባለች። እንደ ወዳጆቻችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉን። እንደ ዘወትር ኑሮዋችሁ ቀጥሉ፤ ለወደፊቱ ትደሰታላችሁ።» የሚል ነበር። ስለ ምፅዋ ወረራ የኢጣሊያ መንግሥትና የእንግሊዝ መንግሥት ብዙ ጊዜ ሲነጋገሩበት የቆዩት ጉዳይ ነው። በተለይ ግን በቢያንኪና ጓደኞቹ በአፋር በረሃ አልቁት በኋላ በኢጣሊያ ሕዝብ ቁጣና ድንጋጤ አሳድሮ ስለነበረ የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በለንደን የኢጣሊያ እንባሳደር ኢጣሊያ በጊዜያዊነት የቀይ ባሕር ወደቦችን ብትይዝ ብሪታንያ ምን ሐሳብ እንዳላት እንዲያጣራ ትዕዛዝ ስለሰጠው አንባሳደሩም ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጠይቆ ያገኘው መልስ 1ኛ. ግብፅ የቀይ ባሕር ወደቦችን ይዛ ለማስተዳደር ኃይል ያንሳታል 2ኛ. ግብፅ ካልቻለች የወደቦቹ የማስተዳደር ኃላፊነት የቱርክ ስለሚሆን የእንግሊዝ መንግሥትም ለቱርክ መንግሥት አሳስቦ እንደነበረ ገልጿል። 3ኛ. ኢጣሊያ ግን ብሪታኒያ የራሷ ግዛት ያልሆነ ለመስጠትም ሆነ ለመከልከል መብት እንደሌላት እንድታውቅላት ትፈልጋለች። ስለሆነም የኢጣሊያ መንግሥት አንዳንድ የቀይ ባሕር ወደቦችን ለመያዝ ፍላጎት ካለው ከቱርክ ጋራ መስማማት እንዳለበት ብሎ ከገለፀ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት በሚመለከት ግን የማንኛውም የቀይ ባሕር ወደብ ከበይሉል እስከ ምፅዋ ኢጣሊያ ብትይዝ ተቃውሞ እንደሌላት ይገልጽና ነገር ግን ምፅዋን በሚመ ለከት ከሆነ ከዚህ በፊት እንግሊዝና ኢትዮጵያ ያደረጉት ስምምነት እን ዲከበር ቅድመ ሁኔታ እንዳለ ዲሴንበር 22 ቀን 1884 ዓ.ም መልስ ሰጥተዋል።

## 3. የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ሕግ አልባ አስተዳደር

ካርሎ ሻንዘር[1] (Carlo Schanzer ) የተባለው ኢጣሊያዊ የፓርላማ አባል በ1912 በደረሰው መጽሐፍ ስለ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር በሕግ አንፃር ባካሄደው ጥናት አስተዳደሩ የኢጣሊያ ሕገ መንግሥት የማይከተል፣ ከሌሎች የኤውሮፓውያን ቅኝ ግዛቶች በማነጣጠርም ሕግ አልባ ሕገ ወጥ መሆኑን በማስረዳት ጽፈዋል።

በአፍሪካ ቅኝ ግዛቶች የነበራቸው ሀገሮች ለምሣሌ ፖርቱጋል፣ ፈ ረንሣይና ብሪታኒያ ጠቅሶ በጻፈው በእነዚህ ሀገሮች የተያዙ ቅኝ ግዛቶች የ ሀገራቸው ቅጥያ መሬት የማይነጣጠል አድርገው ይወስዷቸው ነበር። በግ ዛታቸው የሚኖሩ ሕዝቦችም እንደ ዜጎቻቸው በእኩል ደረጃ ይቆጥሩዋቸው ነበር። የኢጣሊያ ስለ ቅኝ ግዛቶቿ አስተዳደር አቋም ግን ከእነዚህ ሀገ ሮች በጣም የተለየ ነበረ። በኢጣሊያ ሕገ መንግሥት ቁጥር 5 መሠረት ማን ኛውም መሬት ወይም ሕዝብ ከሀገሩዋ ድንበር ውጭ ቢሆንም ከሀገሩዋ ጋራ አጠቃልላ የምታስተዳድረው [illegible] ሀገሮች በሀገሩዋ ባለው በአንድ ዓይነት ሕግ ማስተዳደር ይገባት ነበር። የኢጣሊያ ሕገ መን ግሥት አንቀጽ 5 «ንጉሱ ብቻ የሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን አለው፣ ርእሰ ብሔር ነው፤ የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ ነው፤ ጦርነት ያውጃል፤ ሠላም፣ ወዳጅነት፣ ንግድ ይዋዋላል።

1. Carlo Schanzer : L'acquisto delle Colonie e il dritto Pubblico Italiano



የገንዘብ ወጪ የሚጠይቁ ውሎችና እንደዚሁም በሀገሪቷ የመሬት ለውጥ የሚያመጡ ውሎች ግን በሕዝብ ተወካዮች (ፓርላማ) ካልፀደቀ በሥራ ላይ አይውልም።» በማለት ይደነግጋል። ሆኖም ኢጣሊያ የሕገ መንግሥቷ አንቀጽ 5 ወደ ጐን በመተው ቅኝ ግዛቶችዋ በሚመለከት በተግባር ሌላ አሠራር ትከተል ነበር። አጼ ምኒልክ ለኢጣሊያ ነገሥታት ደብዳቤ መጻፍ ይወድ ነበር። ኢጣሊያ በሕገ መን ግሥታዊ የዘውድ አገዛዝ የምትስተዳደር ስለነበረች በሀገሪቱ ሥልጣን ያለው ጠቅላይ ሚኒስትር እንጂ ንጉሡ አይደለም ብሰን በመገመት አጼ ምኒልክ የኢጣሊያ ንጉሥ እንደ ራሱ ፈላጭ ቆራጭ እየመሰለው ነው ብለን ግምት እንሰጥ ይሆናል። ነገር ግን በኢጣሊያ ሕገ መ ንግሥት አንቀጽ 5 መሠረት ውሎችን በሚመለከት ንጉሡ ብቸኛ ሥልጣን እንደነበረው ያመለክታል። ስለዚህ የአጼ ምኒልክ ለኢጣሊያ ነገሥታት ደብዳቤ መጻፍ አግባብ ያለው ነበር።

ኢጣሊያ አሰብን ከያዘችበት ጊዜ 1882 ጀምሮ ደራሲው መጽሐፍ እስካሳተመበት 1912 ዓ.ም ድረስ በኢጣሊያ ፓርላማ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 5 መሠረት ስለ ኢጣሊያ የመሬት ስፋት መጨመር በየጊዜው ከአ ንዳንድ የፓርላማ አባሎች ጥያቄና ነቀፌታ ሲቀርብ የኢጣሊያ ባለሥልጣናት ይሰጧቸው የነበሩ ማብራሪያዎች በሕግ አንፃር አጥጋቢ አል ነበሩም። በመጀመሪያ የቅኝ ግዛቶች የሀገሪቱ አንድ አካል ናቸው ወይስ አይደሉም ለሚለው አከራካሪ ጥያቄም ግልጽ የሆነ መልስ አልተሰጠውም። የዚሁ ዓይነት ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢጣሊያ ፓርላማ ለክርክር የቀረበው ጁን 26 1882 ነበር። በዚሁ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ማንቺኒ (Mancini) ቅኝ ግዛቶች (አሰብ) በአስተዳደር ቢለያዩም የኢጣሊያ አንድ አካል ናቸው የሚል መልስ ሰጥቷል። የውጫሌ ውል በተደረገ ጊዜ፣ ሜይ 2 1889፣ ወደ ፓርላማ ለክርክር ሳይቀርብ እንዲያውቀው ብቻ ስለተደረገ፣ ማርች 5 1890 አንድ የፓርላማ አባል ፈራሪ (Farrari ) በዚሁ ውል መሠረትና የኢጣሊያ የመሬት ስፋት የተለወጠ ስለሆነ በኢጣሊያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 5 መሠረት ለፓርላማ ቀርቦ መጽደቅ ሲገባው ከሕገ መንግሥቱ ውጭ ነው ውሉ የተፈጸመው የሚል ነቀፌታ አቀረበ። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረ ሰው ዝነኛ የነበረ፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ሽንፈት ስለ ቀመሰ ሥልጣኑ በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ የተገደደ ክሪስፒ (Crispi) የማንቺኒ ተቃራኒ አስተያየት በመሰንዘር የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የኢጣሊያ አንድ አካል ሳይሆኑ በኢጣሊያ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ መሆናቸውን ከገለጸ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል ተቃራኒ ትችቶች ያስከተሉበት ቃላቶች በመጠቀም «ሕገ መንግሥት አንቀጽ 5 የመንግሥት መሬት ነው በሚልበት ጊዜ የሚያመለክተው ስለ ብሔራዊ መንግሥት፤ ስለ ገዥዋ የኢጣሊያ መን ግሥት መሬት ነው እንጂ ከሀገር ውጭ የሚያዙ መሬቶች አይደሉም» በማለት ገልጧል።

ማርች 17 1885 ካይሮሊ (Calroli ) የተባለው የፓርላማ አባል የኢጣሊያ መንግሥት ፓርላማ ሳያውቀው መሬት ማስፋፋት ማድረጉ በመ ውቀስ ብራንካ (Branca) የተባለውም ሌላ የፓርላማ አባል የኢጣሊያ መንግሥት ፓርላማ ሳያውቀው በአፍሪካ የተመደበው ጦር ወጪ በማድረጉ ሂሳ ሰንዝረዋል።

ሜይ 7 1885 የኢጣሊያ ፓርላማ በተሰበሰበበት ጊዜ ተራ የፓርላማ አባል የነበረው ክሪስፒ መንግሥት ፓርላማ ሳያውቀው ወደ አፍሪካ ዘመቻ ማድረጉ ወቅሶዋል፣ ሌሎች የፓርላማ አባላትም በወቀሳ ተካፋይ በመሆን ድምፃቸውን አሰምቷል።

በዚሁ ወቅት የኢጣሊያ መንግሥት የመተማመኛ ድምፅ ጠይቆ በ189 ድጋፍ ለ97 ተቃዋሚና 7 ድምጸ ተዐቅቦ ስላገኘ ባድራጎቱ እንዲገፋበት ብርታት አግኝቷል።

ሜይ 19 እና ሜይ 21 1885 የኢጣሊያ ፓርላማ ባደረገው ስብሰባ ቤካሪኒ(Beccarini) እና ክሪስፒ የተባሉ የፓርላማ አባሎች ወደ አፍሪካ ለተ ላከው የኢጣሊያ ሠራዊት ስለሚደረገው የገንዘብ ወጪ በሚመለከት ፓርላማ ሳያውቀው በመደረጉ ሕገወጥ ነው በማለት ወቀሳ አሰምቷል።

ኢጣሊያ ቀስ በቀስ በምፅዋ አካባቢ ይዞታዋን በምታስፋፋበት ጊዜ በ ኢጣሊያ ፓርላማ የከረረ ክርክር ቢደረግም የኢጣሊያ ሠራዊት ከአፍሪካ ይውጣ ብለው የሚጠይቁ የፓርላማ አባላት ቢኖሩም የኢጣሊያ መንግሥት የሚፈልገው ወጪ ሁሉ የፓርላማ ድጋፍ ለማግኘት ችግር አላጋጠመውም።

ሜይ 28 1888 ፓርላማ ባደረገው ስብሰባ ቤካሪኒ ፣ ሙሲ (Musi) እና ፈራሪ የተባሉ የፓርላማ አባሎች የኢጣሊያ ወታደሮች ከአፍሪካ እንዲወጡ በመጠየቅ ድምፃቸውን አሰምቷል። በማርች 17 1891 በኢጣሊያ ፓርላማ ስለ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 5 ክርክር ተነስቶ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ሩዲኒ (Rudini) የክሪስፒ ሐሳብ በማንፀባረቅ የኢጣሊያ ንጉሥ ፓር ላማን ሳያማክር በሀገሪቷ መሬት ላይ ለውጥ ለማድረግ ይችላል በማለት መልስ ሰጥቷል።

ጁን 11 1891 ሌላ የፓርላማ አባል ፒየራንቶኒ (Pierentoni) ላቀረበው ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትር ሩዲኒ መንግሥት ውሎችን ለማድረግ መብ ት እንዳለውና ለፓርላማ የሚያቀርበው ፓርላማ እንዲያፀድቀው ወይንም እንዲቃወመው ብቻ ነው የሚል መልስ ሰጥቷል።

በ18 90 ሌላ የፓርላማ አባል ስለ ኤርትራ ወሰን ጉዳይ ከኢትዮጵያ ጋር እንደዚሁም በጅቡቲ ጋራ ሜይ 24 1900 ስለተደረጉ ስምምነቶች ጉዳይ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 5 መሠረት አልተፈጸመም በማለት ላቀረበው ነቀፌታ፣ ከኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፕሪኔቲ (Prinetti) መልስ ሲሰጥ ከኢትዮጵያ ጋራ የተደረገው ውል አዲስ መሬት አልተቀላቀለም ፣ ውሉ የተደረገው ኢጣሊያ በይዞታዋ የነበረ መሬት ለማጽደቅ ብቻ ነው፣ ምሳሌም በመጥቀስ ኦክቶበር 1896 የተደረገው የሰላም ውልም ቢሆን ለፓርላማ ቀርቦ አልፀደቀም [redacted] ች ሁሉ የኢጣሊያ ከፍተኛ ባለሥ ልጣኖች የሚሰጧቸው መልሶች ግልጽነት የጎደለባቸው ድብስብስ ያሉ ነበሩ። ኢጣሊያ ለስሙ በዴሞክራሲ የምትስተዳደር ሀገር ነበረች፣ በተግባር ግን አፍሪካን በሚመለከት ከፋሺዝም ያላነሰ ፀረ ዴሞክራሲ አስተዳደር ትከተል ነበር።



ሻንዘር እላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ደራሲ ሌሎች የሕግ ባለሞያዎች ስለዚሁ ጉዳይ በጽሑፎቻቸው የኢጣሊያ መሬት ስፋቱ በመጨመሩ በሕግ አንፃር የደረሱባቸው ግምገማዎችን ከጠቀሰ በኋላ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 5 በመንግሥት ይዞታ የሚገኘው መሬት በሚለበት ጊዜ የቅኝ ግዛቶች መሬቶችም የሚያጠቃልል መሆኑን መወሰድ እንዳለበት በማለት ደምድሟል።

የቅኝ ግዛት የማግኘት ምኞታቸውን ለማጠናከር አሰብ ወደ መንግሥት ይዞታ ከተዛወረች በኋላ፣ ከምፅዋ ወረራ በፊት ሜይ 1883 ጣሊያኖች ከአውሳ ሡልጣን አንፋሪና ከሸዋ ንጉሥ ምኒልክ የንግድና የወዳጅነት ስምምነቶች አድርገዋል።

ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በሰሜን በምሥራቅና በደቡብ የባሕር ጠረፎች በመነሳት ስለፈጸመቻቸው ከበባዎችና ወራሪዎች የሚገልጹ ውሎች ደራሲው ካርሎ ሻንዘር በመጽሐፉ ከገጽ 101 እስከ 212 በሙሉ አውጥቷል። ውሎቹ ለ3 የተከፈሉ ናቸው። ሀ/ አሰብ ለ/ ምፅዋና ኤርትራ ሐ/ ሶማሊያና በናድር የሚል አርእስት ያላቸው ናቸው።

## ሀ/ አሰብ

የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ኤርትራ ለመፍጠር የመጀመሪያ ጥንስስ የሆነችው ስለ አሰብ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ሻንዘር 7 ተራ ቁጥር ቅደም ተከተል ያሏቸው ማስረጃዎች አውጥቷል። በመጀመሪያዎቹ አምስቱ ተራ ቁጥሮች ፕሮፌሰር ሳፔቶ በኢጣሊያ መንግሥት አቀነባባሪነት፣ በሩባቲና ኩባንያ ስም፣ አሰብ አካባቢ ከነበሩ የአፋር ሡልጣኖች የገዛበት ውሎች የያዙ ናቸው። 6ኛ ተራ ቁጥር ሩባቲና ኩባኒያ አሰብን ለኢጣሊያ መንግሥት ሲያስረክብ የተዋዋለበት ነው። 7ኛ ተራ ቁጥር ጁላይ 5 1882 በኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ተዳማዊ ፊርማ አሰብ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆኗን የወጣበት የሕግ ድንጋጌ አዋጅ ነው።

## ለ/ ምፅዋና ኤርትራ

ሻንዘር ስለ ኤርትራ 38 ተራ ቁጥር ያሏቸው ውሎች ደብዳቤዎችና አዋጆች አሳትሞ በመጽሐፉ አውጥቷል።

ኢጣሊያ ምፅዋን በጦር ኃይሏዋ ወርራ ከያዘች በኋላ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የነበረው ለምፅዋ ከተማ ሕዝብ የሰጠው መግለጫ 1ኛ ተራ ቁጥር በመሆን ወጥቷል። የኢጣሊያ ማንነት አጉልቶ በሚያሳይ በዚሁ ሐሰተኛ መግለጫ አዛዡ የኢጣሊያ መንግሥት የብሪታኒያ፣ የቱርክ፣ የግብጽና የኢ. ትዮጵያ ወዳጅ በመሆኑ ምፅዋን በቁጥጥሩ ስር አድርጓል ብሏል።

በ2ኛና 3ኛ ተራ ቁጥር እንደልማዳቸው ጣሊያኖች ሲጀምሩ ሁልጊዜ ማባበያ ገንዘብ በወር 500 ብር በመክፈል ከሐባብ ጐሣ መሪ ጋር ኦክቶበር 9 1885 እና ጁላይ 9 1887 ያደረጉት ስምምነት ነው።

4ኛ ጁላይ 20 1888 ከዙላ ናይብ ለኢጣሊያ መንግሥት ታማኝነቱን ለመግለጽ የደረሳቸው ደብዳቤ ነው።

5ኛ የቤኒ ዓሚር የጐሣ መሪዎች ዲሰምበር 2 1888 ታማኝነታቸው ለኢጣሊያ መንግሥት የገለጹበት ጽሑፍ ነው።

6ኛ አንቶኔሊ ዲሰምበር 9 1888 ከአውሣ ሱልጣን ጋራ መሐመድ አንፋሪ ያረገው ውል ነው። ከአሰብ ወደ ሸዋ የሚወስደው መንገድ በረሃማ እንደመሆኑ መጠን የኢጣሊያ ተጓዦች ደህንነት እንዲጠብቅ የኢጣሊያ መንግሥት ለሱልጣኑ 18.000 ብር ለመክፈል ቃል ገብቷል። በተጨማሪም በየዓመቱ 3.000 ብር ለመክፈል ቃል ገብቷል።

7ኛ. እላይ ጣሊያኖች ከጐሣ መሪዎች እንዳደረጓቸው ውሎች በእኩል ደረጃ ሆኖ የቀረበው ታዋቂው የኢጣሊያ መንግሥት ወኪል ኮንቴ አንቶኔሊና (Antonelli) አጼ ምኒልክ ሜይ 2 1889 በውጫሌ ያደረጉት ውል ዝነኛው የውጫሌ ውል ነው። በዚሁ የተፈጠረች ኤርትራ ቁጥር አንድ ተብላ ልትጠራ ትችላለች፣ ለኤርትራ መፈጠር መሠረተ ድንጋይ ነው።

8ኛ. ለውጫሌ ውል ተጨማሪ በኢጣሊያ ናፖሊ (Napoli )[1] ኦክቶበር 1/1889 ደጃዝማች (ራስ) መኰንን እና ክሪስፒ የተፈራረሙት ውል ነው።

9ኛ. ስለ አሰብ የተደረጉ ስምምነቶችና ስለ ኤርትራ በ8 ተራ ቁጥሮች የተፈጸሙ ውሎች ለኤርትራ መፈጠር ያመቻቹ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ። በዚሁ በ9ኛ ተራ ቁጥር የወጣ ግን ጃንዋሪ 1 1890 በኢጣሊያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ተፈርሞ በቀይ ባሕር አካባቢ የሚገኙ የኢጣሊያ ይዞታዎች በሙሉ በአንድ ስም ተጠቃለው «የኤርትራ ቅኝ ግዛት» የሚል ስም እንዲሰጣቸው የሚያዝ አዋጅ ነው። በዚሁ አዋጅ ኤርትራ ቁጥር አንድ ተፈጠረች። የአዋጁን ፎቶ ኮፒ ተመልከት።

10ኛ. ጁላይ 1 1890 የኢጣሊያ መንግሥት ስለ ኤርትራ ጉዳይ ሕጎችና ድንጋጌዎች ለማውጣት የሚያስችለው በኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ የተፈረመ ተጨማሪ አዋጅ ነው።

11ኛ. የኤርትራ መንግሥት ከሐደንዳዋ ጐሣ መሪ ጋራ በኢጣሊያ ስር እንዲሆን የሚፈቅድ ሰፐቴምበር 4 1890 የተደረገ ስምምነት ነው።

12ኛ. ኦክቶበር 8 1890 ከአፋር የአዶይማራና አሳይመራ የጐሣ መሪዎች በኢጣሊያ ስር እንዲሆኑ የሚፈቅድ ስምምነት ነው።

13ኛ. ኦክቶበር 15 1890 የኢጣሊያ ባንዴራ እየተከሉ የአዶይማራ ጐሣ ከአውሣ በደቡብና በምዕራብ የተካለለበት ውል ነው።

14ኛ. የኤርትራ መንግሥት የኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ፕሮቶክተሬት (Protectorate )ከዓድ እማር 15ኛ. ከሰብደራት 16ኛ. ከሐምራም 17ኛ. ከባሪያ 18ኛ. ከዓድ ሸረፍ 19ኛ .ከማሪያ ቀይ 20ኛ. ከማሪያ ጠይም 21ኛ. ከመንግዕ ቤት አብርሂ 22ኛ. ከመንግዕ ቤት ሻንካ የጐሣ መሪዎች ጋራ ሁሉም ኦክቶበር 20 1890 ውል ያደረገበት ነው።

1. Vico Mantegazza : La Gueerra in Africa p. 145



23ኛ. የአዶይማራና የአሳይማራ የጐሣ መሪዎች ቀደም ብሎ የኢጣሊያ መንግሥት ከአውሣ ሱልጣን ጋራ ያደረገው ውል እንዲቀበሉ ለማድረግ ኖቬምበር 3 1890 የተደረው ውል ነው።

24ኛ. የኤርትራ መንግሥት ኖቬምበር 11 ቀን 1890 ከበጁክ፣ 25ኛ. ከቤት ማላ 26ኛ. ከዓድ ኢከድ የጐሣ መሪዎች ጋራ ለኢጣሊያ ተገዢነታ ቸውን በመቀበል ያደረጋቸው ውሎች ናቸው። በውጫሌ ውል ጊዜ እንደዚሁም ጃኑዋሪ 1 1890 ኤርትራን የፈጠረ አዋጅ ጊዜ ያልነበሩ መሬቶች ከተራ ቁጥር 11 እስከ 26 እላይ የተጠቀሱ ውሎች ስለ ተጨመሩ በት የመሬት ስፋቷና የኗሪ ሕዝብ ቁጥር ጨምሮ ኤርትራ ቁጥር 2 ተፈጠረች።

በተራ ቁጥር 28ኛ. የኢጣሊያና የእንግሊዝ መንግሥታት ስለ ሰሜን ኤርትራ ከሱዳን ጋራ የሚያዋስነው ወሰን የተከለሉበት ኤፕሪል 15 1891 ያደረጉት ውል ነው። ከዚህ ውል በኋላ ኤርትራ ቁጥር 3 ተፈጠረች።

በተራ ቁጥር 29ኛ. ከዓድዋ ሽንፈት በኋላ ኢጣሊያ የውጫሌ ውል ተሰርዞ የኢትዮጵያ ነፃነትን ለመቀበል ተገዳ የአዲስ አበባ ውል ተብሎ የሚጠራ ኦክቶበር 26 1898 (ጥቅምት 17 ቀን 1882) ዓ.ም ሁለቱ ሀገሮች የተፈራረሙበት ውል ሲሆን፣ በዚሁ ቀንም በተራ ቁ. 30ኛ ያለው ስለ ኢጣሊያ እስረኞች መለቀቅ የስምምነት ውል እድርገዋል።

ዲሰምበር 21 1893 ኢጣሊያ እቁርዳትን በጦር ኃይል በቁጥጥሩዋ ባደረገችበት ጊዜ ኤርትራ ቁጥሩ 4 ተፈጠረች።

ጁላይ 17 1894 ኢጣሊያ ከሰላን በጦ ርነት በቁጥጥሩዋ ባዋለችበት ጊዜ፣ ከኤርትራ ጋራ ስትቀላቀል የኤርትራ ገጽታ የመጨመርና የመቀነስ የታየበት ወቅት ኤርትራ ቁ.5 ተፈጠረች።

ካርሎ ቫንዘር ስለ ኤርትራ መፈጠር ሂደት በተራ ቁጥር 31 እንዳ ወጣው ኢት ዮጵያና ኢጣሊያ ጁላይ 10 1900 (ሐምሌ 3 ቀን 1892 ዓ .ም) ስለ ደቡባዊ ኤርትራ ወሰን ጉዳይ፣ መረብ ምላሽ ሁለት አንቀጽ ብቻ ያዘለ አጭር ውል ባደረጉበት ወቅት ኤርትራ ቁጥር 6 ተፈጠረች።

በተራ ቁጥር 32 የወጣው የእንግሊዝና የኢጣሊያ መልክእተኞች በአሻጥር የኩናማ አውራጃ ከኤርትራ ጋር እንድትቀላቀል ሮማ ላይ ዲሰምበር 22 1901 ያመቻቹበት ውል ነው። በተራ ቁጥር 33 የወጣው የ32ኛ ተራ ቁጥር ተቀጣይ ሲሆን አጼ ምኒልክ በአዲስ አበባ የኢጣሊያና የብሪታንያ አምባሳደሮች የኩናማ አውራጃ ከኤርትራ ጋር እንድትቀላቀል ሜይ 15 1902 አዲስ አበባ ላይ ያፀደቀበ ት ውል ነው። በዚሁም ውል መሠረት ኤርትራ ቁጥር 7 ተፈጠረች።

በተራ ቁጥር 34ኛ እና 35ኛ የኢጣሊያና የፈረንሳይ መንግስታት ስለ ደቡብ ኤር ትራ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛትና ጂቡቲ የፈረንሣይ ወሰን ጉዳይ በሮማ የደረሱበት ስምምነት ሲሆን በዚሁ ስምምነትም ኤርትራ ቁጥር 8 ተፈጠረች።

በተራ ቁጥር 36ኛ የተመለከተው ኢጣሊያ በቀይ ባሕር የአፋር የባሕር ወደቦች ተወስና የነበረች60 ኪሎ ሜትር ከባሕር ወደ አፋር መሬት ውስጥ እንድትገባ የሚያስችላት ውል ሁለቱ መንግሥታት ኢጣሊያና ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ላይ ሜይ 16 1908 የደረሱበት ውል ነው። ከዚሁ ውል በኋላም ኤርትራ ቁጥር 9 ተፈጠረች።

ኤርትራ ቁጥር 10 የተፈጠረችው በ1928 ዓ.ም (1935–36) በተደረገው ጦርነትኢጣሊያኖች መላውን ኢትዮጵያ ከተቆጣጠሩ በኋላ ያደረጉት የግዛት ሽንሸና ነው። በዚሁ ጊዜ ትግራይ አፋር ምሥራቅ ወሎ ወዘተ በኤርትራ ግዛት ውስጥ ተከልለው ነበር። ኤርትራ ቁጥር 11 በ1928 ዓ.ም (1935–36) በተደረገው ጦርነት ጣሊያኖች አዲስአበባ ከመግባታቸው 1 ወር በፊት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ኤታ ማጆር ሹም በነበረው ጀኔራል ጋባ የተነደፈው እቅድ አጼ ኃይለ ሥላሴ በኢጣሊያ እጅ እንደሚገባ ታስቦ የተዘጋጀ ስለሆነ በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም።እቅዱ ለኤርትራ ቅኝ ግዛታቸው ከብር ወሰኗ ዓለም አቀፋዊ ታዋቂነት ያለው ባሕር ጣና እንዲደርስ ጦርነቱ በሰላማዊ መንገድ እልባት ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ነበረ። በእቅዱ መሠረትአፋርኛየሚናገሩበትመሬት በሙሉ፣ ትግራይ በሙሉ፣ ወሎ በሙሉ ፣ ከቤጌ ምድር ቋራና አለፋ ከኤርትራ ጋር ተቀላቅሎ በኤርትራ ስም እንዲጠሩ ነበር።

ደሴ በጣሊያኖች አልተያዘችም ነበር፤ የወሎ ሀገረ ገዢ አልጋ ወራሽ አጄ ለጣሊያኖች እንደሚሰጥ እምነት ነበራቸው። አልጋ ወራሽ ግን ደሴን ለቆ ወዳልታወቀ ቦታ ስለሄደ ማርሻል ባዶሊዮ እንዳሰበው አልተሳካለትም። ማርሻል ባዶሊዮ አጼ ኃይለሥላሴ አዲስ አበባን ለቆ በመሄድ ትልቅ ስሕተት እይሰራም የሚል ግምት ነበረው። በዚሁ መሠረት ከኃይለሥላሴ ጋራ ሊደረግ የታሰበው የሰላም ድርድር ተካፋይ እንዲሆን የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር የነበረ ለሶና ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ በባዶሊዮ ተጋብዞ መጥቷል። አጼ ኃይለሥላሴ ያለበት ቦታ ሲታወቅ ባዶሊዮና ለሶና አንድ ላይ ሆነው ያረቀቁት ለኃይለሥላሴ የሚላክ ቴሌግራም መልእክት እንዲያውቀው የተነገረው በሚከተለው ነበረ። «ደሴ እገኛለሁ፤ የእኔ ጦር ብዛት ግርማዊነትዎ ያውቃል። አሁን ወደ አዲስ አበባ ጉዞዬን ስቀጥል ምራሉ የወደቀና የተበታተነ የኢትዮጵያ ጦር የሚያደርግልኝ መከላከል የለም። ለምን የክርስትያን ደም በከንቱ ይፈሳል? ግርማዊነትዎ ስለ ሰላም ንግግር የሚፈልግ ከሆነ እኔ መልእክተኞች ለመላክ ዝግጁ ነኝ። ይሁን እንጂ የግርማዊነትዎን ደኅንነት የአዲስ አበባን ፀጥታ ለመጠበቅ ወደ አዲስ አበባ ማምራቴ የማይቀር መ ሆኑን ግልጽ ይሁንልዎት።» ዱቼ ግን ምን ጊዜም ትክክለኛ መንገድ የሚመርጠው በሃሣቡ ስላልተስማማ የባዶሊዮና የለሶና እቅድ ውድቅ ሆነ። ከዚህ በኋላ ማርሻል ባዶሊዮን ያሳሰበው የነበረ ስለ ሰላም ጀኔሽ የሚደረጉ ን ግግሮች በድል አድራጊነት ወደ አዲስ አበባ እንይገባ እንዳይከለክል ነበር። ለሶና ግን የዚሁ ዓይነት ሃሣብ ምን ጊዜም ዱቼ እንደማይቀበለው ያረጋግጥለት ነበር። ምንም እንኳን ዋና የኤርትራ ገንጣዮች አጼ ምኒልክና ጣሊያኖች ቢሆኑም የዛሬ ትውልድ ገንጣዮች እላይ ከተዘረዘሩ 11 ዓይነት ኤርትራዎች ሀገራቸው ተብላ የተሰጠቻቸው የትኛዋ ኤርትራ እንደሆነች እናት ሀገራችን ብለው እንዲሞቁላት ከጣሊያኖችና ከምኒልክ የተሰጣቸውን ሳያጣሩ በታወረ



እእምሮዋቸው የሚመሩ መሆናቸውን ያሳያል። ኤርትራ አንድ ሀገር ናት ብትባልም ዋና ኤርትራ ወሰኑዋ በውጫሌ ውል የተወሰነው በጣሊያን ንጉሥ ኡምቤርቶ በአዋጅ የጸደቀው ብቻ መሆን ይናገርበታል። ኤርትራ አንድ ጐሣ የሚናገርባት ወይንም አንድ ቋንቋ የሚ ናገር ሕዝብ የሚናገርባት ሀገር አይደለችም። ሌሎች ኤርትራዎች የተቀላቀሉ ናቸው። የመጨረሻዋ ኤርትራ ቁጥር 10 አክራሪ የኤርትራ ብሔርተኞች ይገባናል ከማለታቸው በቀር በአሁኑ አስተዳደር ኤርትራ አይደለችም። ብዙዎች ፈረንጆች በአጠቃላይ የውጭ ሀገር ሰዎች ኢትዮጵያ አንድነት የላትም፣ በጐሣ የተካፋፈለች ናት፣ የብሔረሰቦች ጥርቅም ሞዛይክ ናት ይላሉ።

## ሐ. ሶማሊያና በናድር

ጣሊያኖች በሶማሌ እጃቸው ማግባት ሲጀምሩ አሰብ እንዳደረጉ ሁሉ የሀገሩ ባለባቶች ሱልጣኖች በገንዘብ በመደለል ነበረ። ሻንዘር በ29 ተራ ቁጥሮች አላትሞ እንዳወጣ አዋጆችና ውሎች መሠረት ከመጀመሪያ ተራ ቁጥር 1 የተዋዋሉት ከአቢያ ሱልጣን በየዓመቱ 200 ብር ማሪያ ተሬዛ በመክፈል በኢጣሊያ ስር እንዲሆን በመፍቀዱ ጃንዋሪ 1889 ነበር። ቀጥሎም በተራ ቁጥር 2 ከአቢያና ከሚጁርቲኒ ሱልጣኖች በዓመት 1800 በመክፈል በኢጣሊያ ሥር እንዲሆኑ አፕሪል 7 1889 በመፍቀዳቸው ነው። የኢታላ ተራ ቁጥር 3 ማርች 7 1891 የሞቃድሾ ሱልጣኖች በኢጣሊያ ሥር በወደቁበት ጊ.ዜ ግን ገንዘብ ሳይከፍላቸው ማርች 24 1891 ነበረ።

በተራ ቁጥር 6 በ1692 ኢጣሊያ የበናድር ወደቦች ለመጠቀም የሚያስችላት ውል ከብሪታኒያና ከዛንዚባር ሱልጣን ባደረገችበት ጊዜም ገንዘብ ለሱልጣኑ በመክፈል ነበረ። ሌሎች ስምምነቶች ከባርደሬና ሉግ ሱልጣኖች ጋራ ሲደረጉ ገንዘብ ሳይከፈላቸው የኢ.ጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ራሳቸው በመጠየቅ ነበር።

ኢጣሊያ የሶማሊያ የወደብ ከተሞችን ይቆጣጣር ከነበረው ከዛንዚባር ሱልጣንና ከብሪታኒያ እንደዚሁም ከተለያዩ የበናድር ሱልጣኖች ተዋውላ በእጇዋ ያስገባቻቸው መሬቶች አንድ ላይ ተጠቃልለው በኤርትራ እንደተደረገ ሁሉ አፕሪል 5 1908 በኢ.ጣሊያ ንጉሥ ቪክቶሪዮ እማኑኤሉ 3ኛ ፊርማ በወጣው አዋጅ መሠረት የኢጣሊያ ሶማሊያ የሚል ስም ተሰጥቷቸው በደቡብ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ተፈጠረ። የዚህ አዋጅ ፎቶ ኮፒውን ተመልከት።

በመጨረሻም ኢጣሊያ በሕንድ ውቅያኖስ የወደብ ከተሞችን ይቆ ጣጠሩ ከነበሩ ሱልጣኖች ጋራ እንዳደረገቻቸው ውሎች ሜይ 16 1908 ከአጼ ምኒልክ ጋራ ባደረገችው ውል ወሰኑ ሲከለል ኢጣሊያ ለአጼ ምኒልክ 3 ሚሊዮን ሊሬ በመክፈል ነው።

# ኤርትራና ሶማሊያ መፈጠር

ኢጣሊያ ወደ ሀገራችን ከመምጣቷ በፊት ኤርትራና ሶማሊያ የሚባሉ ሀገሮች አልነበሩም፣ ኤርትራ በትግራይ ተጠቃልላ ትጠራ ነበር።

ሶማሊያ በሚመለከት በኬንያ፣ በደቡብና ሰሜን ሶማሊያ፣ በጅቡቲና በኢትዮጵያ የተለያዩ ጐሳዎች በሱማሊያ ቋንቋ የሚጠቀሙ ቢኖሩም ሶማ ሊያ ተብሎ የሚጠራ ሀገር አልነበረም።

ኤርትራ የተፈጠረችው ስምም የተሰጣት በኢጣሊያዊው ንጉሥ ኡምበርቶ ቀዳማዊ አዋጅ ጃንዋሪ 1 ቀን 1890 ዓ.ም. ነው። ሶማሊያ (የደቡብ ሶማሊያ) የተፈጠረችው ስምም የተሰጣት በኢጣሊያዊው ንጉሥ ኤማኑኤሉ ሶስተኛው አዋጅ አፕሪል 5 ቀን 1908 ዓ.ም. ነው።

የሁለቱ አዋጆች ፎቶ ኮፒ ከካርሎ ሻንዘር መጽሐፍ የተቀዳ ለአንባብያን ቀርበዋል፣ ተመልከት።

ኤርትራ ከትግራይ አንድ አካል ነበረች። በጣሊያኖች ቁጥጥር የዋለው አብዛኛው የሶማሊያ ግዛት ግን በናድር ተብሎ ይጠራ ነበር። ጣሊያኖች ከተለያዩ የሶማሊያ ሱልጣኖች ጋራ የኢጣሊያ ጥገኝነት እንዲቀበሉ ስምምነት ካደረጉ በኋላ በአዋጅ አንድ ላይ ተጠቃልለው የኢጣሊያ ሶማሊያ ቅኝ ግዛ ት ተብለው እንዲጠሩ አድርገው አንድ አዲስ ሀገር ፈጠሩ።

## 4. ስለ ኤርትራ መፈጠርና ስም

ጃንዋሪ 1/1890 የኢጣሊያ መንግሥት በቀይ ባሕር የነበሩት ቅኝ ግዛቶች በሚመለከት በጋዜት ጋዜጣ አዋጅ አውጥተዋል፣ አዋጁ 15 አንቀጾች ያዘለ ነው። የመጀመሪያ አንቀጽ ስለስም መቀየር የሚመለከት በቀይ ባሕር የኢጣሊያ ይዞታዎች ኤርትራ በሚል ስም በአንድ ቅኝ ግዛት ተጠቃለዋል የሚል ነበረ።

ፌብሩዋሪ 6/1891 አጼ ምኒልክና አንቶኔሊ ሶስት ውሎች ተፈራርመው ነበረ። 1ኛ. ስለወሰን ጉዳይ፣ 2ኛ. በውጫሌ ውል አወዛጋቢ የነበረው ስለአንቀጽ 17 ፌብሩዋሪ 8/1891(ጥር 1883) 3ኛ. ስለኢትዮጵያ የተበደረችው የገንዘብ ጉዳይ። እነዚህ ሶስት ውሎች ከተፈ ራረሙ በኋላ አንቶኔሊ አጼ ምኒልክን በአንቀጽ 17 የተመለከተው አታ ለሉኝ ብሎ ወረቀቶቹን ተዶ ባዶ ናቸው ብሎ ስለነበረ አጼ ምኒልክ አንቀጽ 17 ተሰርዟል ብሎ ያስፈረሙት አንቶኔሊ ግን አንቀጹ ማይቀየር ሁለቱ ትርጉሞች ሕጋዊነት እንዲኖራቸው ብቻ ነው የፈረምኩት ብሎ ስላለ ሶስቱን ውሎች ተዶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ሆኖም በይፋ የወጡ ውሎች ስለሆኑ ስለ ወሰን ጉዳይ በሚመለከት ከዚህ በታች ሙሉ ቃል አውጥቶዋል። የገር ማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ መልእክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ስለወሰኖች ጉዳይ በሚመለከት ከዚህ በታች ባለው ስምምነት ደርሶዋል።

ከአዲባር የወሰኑ መስመር ከምእራብ ወደ ምሥራቅ ከአዲባር ወደ ድባርዋ የሚወስደው መንገድ ተከትሎ ይሄዳል። ከድባሩዋና ወደ አዲባር የሚወስደው መንገድ



በስተደቡብ የኢትዮጵያ ናቸው አዲባሮና ወደ ሰሜን የሚገኙ ቦታዎች የኢጣሊያ ናቸው። ከድባሩዋ ተነሥቶ ወደ ሽከቲ ወደ ጐራዕ በአዲ ቀልቦ አዲጊና ኮርባርያ ወሰን ይሆናሉ። ሽከቲ ድርበታ አዲ ጊና ኮርባርያ የኢጣሊያ ናቸው። ቁኩልና ጐራዕ የኢትዮጵያ ናቸው። አዲ ጓንጉል፣ አናደቆ፣ ማዓረባ፣ ሰገነይቲ፣ ሄቦ የኢጣሊያ ናቸው። ድግሣ የኢትዮጵያ ናት። ከድጥግ ወደ ሐላይ የሚወስደው መንገድ በደቡብ ያሉት ቦታዎች የኢትዮጵያ ናቸው። በስተ ሰሜን ያሉት የኢጣሊያ ናቸው። ከሀላይ በማንፋይቶ ወደ ማሀዮ ወደ የፈርአን ዶሮዎች ሜዳ እስከ ማንከበ አራት ሰዓት መንገድ ከአራፋሊ በስተደቡብ የዶለቲ ሸለቆ። ከአዲባር ጋራሻ ከመረብ የሚያገናኘው ካለው መስመር ወሰን ይሆናል። ከዚህ መስመር በስተደቡብ የኢ ትዮጵያ በስተሰሜን የኢትዮጵያ ናቸው። ጋራሻ ከመረብ የሚያገናኘው እስከ ተከዜ የሚ ሄደው መስመር ቢሬ አጠገብ ከመስመሩ በስተምዕራብ የኢጣሊያ በስተምሥራቅ የኢትዮ ጵያ። ስለአወዛጋቢው ጉዳይ የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ጣሊያኖች አሁንም ጥፋተኛው አጼ ምኒ ልክ አይደለም ብለዋል፣ የከሐዲው አስተርጓሚው የግራዝማች ዮሴፍ ንጉሴ ጥፋት ነ ው ብለው በአስተርጓሚው አሣቧቸዋል። (Traduttore ) አስተርጓሚ ሳይሆን ከሐዲው (Traditore ) ነው ብለውታል። በአሁኑ ውልም ሆነ በዋናው የውጫሌ ውልም ወንድሙ ጆርጆ ንጉሴ ከሐዲ ነው ብለውታል። ሁለቱም ትግሬዎች ናቸው፣ በአክሩር የካቶሊክ ሚስዮን ተማሪዎች ነበሩ። ይህ ማለት ደግሞ የ ፈረንሣዊው ቄስ አባ ኩልቦ ተማሪ እንደነበሩ ማለት ነው። ስለዚህ አባ ኩልቦ ደህና ተማሪዎች አፍርተዋል ማለት ይቻላል። ስለ ጆርጅ ንጉሴ ተራቬርሲ «በልፐ ማረፊያ» መጻፉ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ «የግብጺው እስማኤል ፓሻ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ከፍቶ ነበረ። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በታወቀው የሱዊስ ተወላጅ ሙንዚንገር 400 የሱዳን ዜጐች በመምራት ኢት ዮጵያን ለመዋጋት በእስማኤል ፓሻ አቀነባባሪነት ሶስት ቀን ከጉዳጉዲ ጦርነት በፊት በታጁራ በኩል ኢትዮጵያን ለመውረር መክራ ተደርጐ ነበረ። በኢትዮጵያ ታሪክ አዲስ ነገር ሆኖ የታየው ንጉሥ ሚኒልክ በአጼ ዮሐንስ ላይ በማሴር ከግብጹ ፓሻ ሚስጢራዊ ውል ማድረጋቸው ነበረ። የዚሁ ውል አቀነባባሪ ጆርጆ ንጉሴ ነበረ። ከዘመቻም ከሙንዚንገር ጋራ ተካፋይ ሆኖዋል። በአፋር በረሐ ከገቡ በኋላ አፋሮች እንደሰላማዊ ሰዎች መስለው ከተጠጉዋቸው በኋላ ሙንዚንገርና 400 ሱዳናዊያን በሙሉ ሲገደሉ ጆርጆ ንጉሴ ግን ምንም አደጋ ሣያጋጥመው በደህና ወደ ታጁራ ተመልሶ ስለደረሰው አደጋ ዜና ሰጥቶዋል። የአጼ ምኒልክ ታማኞች እንደዚህ ያሉ ሰዎች ነበሩ። ሆኖም በውጤቱ መክሸፍ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ለመጫን ምኞት የነበረው ንጉሥ ምኒልክ ትልቅ ሐዘን ሆኖ ነበረ።»

አክቶበር[1] 28 1898 ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ኢጣሊያና ኢትዮጵያ የሠላም ውል በአ ደረጉበት ጊዜ አንቀጽ 4 ስለወሰን ጉዳይ እንዲህ የሚል ነበረ። «ስለወሰኑ ጉዳይ ሁለቱ ወገኖች ወደ ስምምነት ለመድረስ ባለመቻላቸው ነገር ግን ሣይዘገዩ ለሀገሮቻቸው ሠላም ለመመሥረት ፍላጐት ስላላቸው ከዛሬ ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የገርማዊ የኢጣሊያ

1. Carlo Rossetti: Ibd p. 181

ንጉሥና የግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መልእክተኞች የወሰናቹ ጉዳይ በወዳጅነት መንፈስ ለመወሰን ወደ ስምምነት ደርሰዋል። የወሰኖቹ ጉዳይ እስከሚወሰኑ ሁለቱ ወገኖች አሁን ያለው ወሰን ተጠብቆ በየይዞታቸው እንዲያከብሩና ይህ በመረብ በለሣና ሙና ወንዞች የተከለለ ጊዜያዊ ወሰን እንዳይጥሱ ተስማምተዋል።» ኢጣሊያና ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ ባደረጉት ውል መሠረት ከአንድ ዓመት በኋላ ሣይሆን ከ4 ዓመት በኋላ አዲስ አበባ ላይ ጁላይ[1] 10/1900 ሁለት አንቀጽ ብቻ ያዘለው የሚከተሰው ውል ተፈራርመዋል። በቅድስት ሥላሴ ስም ግርማዊ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ የኢጣሊያ ንጉሥና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በኤርትራ ቅኝ ግዛትና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የወሰን ጉዳይ ከአዲስ አበባ የሠላም ውል ኦክቶበር 26/1896 (ጥቅምት 17 ቀን 1889) ተንጠልጥሎ የቆየውን የወሰን ጉዳይ እልባት ለመስጠት ለላለባቸው ነገሮች ተስማምተው የሚከተለውን ስምምነት አድርገዋል።

1ኛ. ከዚህ ውል ጋራ ተያይዞ የቀረበው ካርታ እንደሚያሣየው ቶማት–ቶድሉክ–መረብ–በለሣ– ሙና ያለው መሥመር በሁለቱ ወገኖች የኤርትራና የኢትዮጵያ ወሰን መሆኑን ተቀብለውታል።

2ኛ. ከቶማት–ቶድሉክ–መረብ–ማይ አንበሣ–ማይፈሜ–ማይመረታ–ማይማሕዮ–የፈርአን ዶሮች ሸለቆ የሚያልፈው መስመር ጀምሮ እስከ ቶማ ት–ቶድሉክ–መረብ–በለሣ–ሙና ያለው መስመር መሐል ያሉት መሬቶች ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ለኢጣሊያ የተሰጡ ስለሆነ የኢ ጣሊያ መንግሥት ለሌላ ሀገር አሣልፎ እንዳይሰጥና ወይንም እንዳይሸጥ ግ ዴታ ገብቶዋል።

በኢጣሊያ ስም ሻምበል ቺኩዲኮላ ፈርሞዋል። በኢትዮጵያ ስም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ፈርመዋል። በውሉ እነጋገርና መንፈስ ሁለት መሥመር የተጠቀሱበት ምክንያት መረዳት በተደራዳሪዎቹ መሐከል ወደ ስምምነት ከመድረሣቸው በፊት የተደረገውን ውጣ ውረድ ከርከር ማወቅ ያስፈልጋል። አጼ ምኒልክ ለድርድር ያቀረበው የወሰን ክልል ሃሣብ ነበረ። ይህ የአጼ ምኒልክ መሥመር በጊዜው የነበረ የዜና ወኪል እንዳማተመው እንደሚከተሰው ነበረ። መሥመሩ ከትግራይ (ቶማት) ተነስቶ መረብ ቶድሉክ ይደርሣል። እስከ ማይ አንበሣ ይቀጥላል። ከዚህም እስከ ምንጩ ሄዶ ወደ መረብ ማይፈሜ ወርዶ ማይ መረታ እስከሚገናኝበት ተከትሎ ይሄዳል። ከማይመረታ ይወጣና ከጕራዕ–ድግሣ–ሐላይ–ማህዮ በስተደቡብ ወ ደ ፈርአን ዶሮዎች ሸለቆ ይወርዳል። ከዚያ ከቀይ ባሕር 60 ኪሎ ሜትር ፖራለል ይቀጥላል። አዲሱ መሥመር እንደ ጕራዕ ድባርዋ–ድግሣ–ሐላይ የታወቁ መንደሮች ወደ ኤርትራ ስለሚያከልል ፌብራዋሪ 6/1891 ከተደረገው ስምምነት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ከሁለቱ ወገኖች ሁለት የተለያዩ ሐሣቦች ቀርበው እንዳሉ ከአንድ ገለልተኛ ስለ ፖለቲካ የማያውቅ ወገን የሚከተለውን ሐሣብ ይቀርባል።

1. Carlo Roesetti : ibd p. 247



ንጉሡ የተባሉት መሬቶችን እንዲያስተዳድር ለኤርትራ መንግሥት እንዲሰጡ በምትኩ ደግሞ የኤርትራ መንግሥት እነዚህ መሬቶች ከአዲሱና ከአሮጌው መሥመር መሐል የሚገኙ ማለት ሠራዬ፣ ሽመዛናና በከፊል አከለጉዛይ ከዚህ ቀደም ለንጉሠ ነገሥቱ ይከፈል ከነበረው ግብር ጣሊያኖቹ ለምኒልክ እንዲከፍሉ። ንጉሡ ከልክ ያለፈ የመግባባት ስሜት በማሣየታቸው ሌላ አስታራቂ ሐሣብ ቀረበ። ይሄውም መሬቶቹ ለዘለቄታ ለኢጣሊያ እንዲሰጡ በግብር መልክ በየዓመቱ ኢጣሊያ የምትከፍለው ገንዘብ በአንድ ጊዜ እንድትሰጥ የሚል ሐሣብ ቀርበላቸው ተቀብለውታል። አጼ ምኒልክ የገረማቸው ነገር ቢኖር ስለጣሊያኖች ተለዋዋጭ አስተሣሰብ ብቻ ነበረ። በአንድ ወቅት ሀገሩን ለቀን እንሄዳለን፤ በሌላ ወቅት ደግሞ በያዙት መሬት ላይ የማስፋፋት ዓላማ ማካሄዳቸው ነበረ። በጣሊያኖች ግምት አጼ ምኒልክ ከልክ በላይ የመስማማት መንፈስ ያሣየበት ምክንያት ማርቲኒ የኤርትራ ሀገር ገዥ የነበሩ ራስ መንገሻ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ በሸፈቱበት ጊዜ እጃቸውን እንዲሰጡ ለማስገደድ ብዙ ወታደሮች ስለላኩባቸው ከጣሊያኖች በኩል ምንም የሚያስፈራቸው ነገር እንደሌለ የሚል እምነት ስላደረባቸው ነው ብሎዋል።[1] ጣሊያኖች ኤርትራ የሚል ስም ሲያወጡ ጃንዋሪ 1/1890 እንዲሁም የውጫሌ ውል ሲፈረም ሜይ 2/1889 የኤርትራ ስፋት እላይ እንደተገለጸው ከአሥመራ በስተደቡብ ሽከቲ ብቻ ይደርስ ነበረ በስተምሥራቅ ሰገነይቲ በስተምዕራብ ከረንን ብቻ ያጠቃልል ነበረ። አብዛኛው አከለጉዛይና ሰራዬ አውራጃ በሙሉ ከኤርትራ ጋራ አልተቀላቀሉም ነበር። እነዚህ ሁለት አውራጃዎች በሕግ ከኤርትራ ጋራ የተቀላቀሉት 10 ዓመት ተኩል የኤርትራ ስም ከወጣ በኋላ ጁላይ 10/1900 ነበረ።

በዚሁ መሠረት እነዚህ ሁለት አውራጃዎች የዋናው ኤርትራ አካል ሣይሆኑ በተጨማሪ በአጼ ምኒልክ ቸርነት ቆይተው በኢጣሊያ በገንዘብ ተሰውጠው የተሸጡ መሬቶች ናቸው።[2] በስተደቡብ በኩል ከላይ እንደተገለጸው ሊያስፋፉ በስተምዕራብ እንደዚሁም በ1893 ዓ.ም. የባርካ አውራጃ፣ በ1894 ዓ.ም. ከሰላን ፣በ1902 የኩናማ አውራጃ፣ በ1908 የአፋር መሬትን በመያዝ የቅኝ ግዛታቸውን ሊያስፋፉ ችለዋል። ኤርትራውያን የሚሞቅላት ሀገራችን ብለው የሚወዷት ኤርትራ ዳር ድንበሯ ከየት ወዴት እንደሆነ ቢጠየቁ የሚሰጡት መልስ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች የቀየሱት ዳር ድንበር ከማሳየት በስተቀር ሌላ የራሳቸው የላቸውም፤ ኤርትራ የተፈጠረችው በውጫሌ ውል ነው፤ በዚህ ውል መሠረትም ዳር ድንበሯ ከሸከቲ አያልፍም ነበር አጼ ምኒልክም የሀገሬ ዳር ድንበር ብሎ ለአውሮጳ መንግሥታት ያስታወቀው ከሸከቲ በስተደቡብ ያለው መሬት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ወደ ኤርትራ የተቀላቀሉ መሬቶች በሕገ ወጥ መንገድ ነው 1ኛ. አከለጉዛይና ሰራዬ አውራጃዎች በሕገ ወጥ መንገድ ከኤርትራ ጋራ እንዴት እንደተቀላቀሉ እላይ ገልጭዋለሁ። 2ኛ. ከሰላ ከኤርትራ ጋር ከተቀላቀለች በኋላ ሥስ አ ፍሪካ አዋቂ ብለው ጣሊያኖች የሚያምኑበት ዘረኛው ጀርመናዊ ስዌ ንፉርት ጠቅላላ ኢጣሊያ ያላት ጦር ሠራዊት በሙሉ እንኳን በኤርትራ ብታሰፍር ከሱዳኖች ወረራ ልትከላከል አትችልም ብሎ ስላስፈራራቸው ጣሊያኖች ተደናግጠው ባጣዳፊ እንግ

1. Carlo Roesetti : ibd p. 248-150

2. Carlo Roesetti : ibd p. 247

ሊዞች ለመረከብ ዝግጁ ሳይሆኑ እየገረማቸው ከሰላን ለቀው ወጥቷል። ከሰላ ኢትዮጵያውያን ዝርያ ያላቸው የሚኖሩባት ከጣሊያኖች በፊት ራስ አሉላ ዘምቶ ድል ተቀዳጅቶ ብዙ ኢትዮጵያውያን የሞቱበት ራስ አሉላ ራሱም የቆሰለባት ከተማ ናት። ኢጣሊያ ለእንግሊዞች ያስረከበቻት በሕገ ወጥ መንገድ ነው፤ ጣሊያኖች በማንኛውም ነገር ጀ ርመኖችን ተከትለው መሄድ ይወደሉ። በሰው ዘር እኩልነት ከሚያምኑ ላቲ ኖች ይልቅ ዘረኝነት ከሚያምኑ ጀርመኖች ጋራ መስማማት ይወዳሉ።

3ኛ. የኩነማ እውራጃ ከኤርትራ ጋራ የተቀላቀለች በአዲስ አበባ የኢ ጣሊያ አምባሳደር ቺኩዲኮላና የእንግሊዝ እምባሳደር ሐሪንግተን በኢትዮጵያ ላይ የፈጸሙት ዓይን አውጣ የማወናበድ ሕገ ወጥ ሰራ ነው። በወቅቱ የእንግሊዝ መንግሥት ግዙፍ የሆኑ እቅዶች አውጥቶ ነበር ከእቅዶቹ መሀከል ከካርቱም እስከ ኡጋንዳ የሚደርስ የባቡር ሀዲድ ለመዘርጋት መሥመሩም ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲገባ ታስቦ ስለነበረ የኢትዮጵያ ንግድ እንቅስቃሴ ከነጭ አባይ ከተገናኘ በቀጥታ ወደ ሜዲተራንያን ባሕር የሚደርስበት መንገድ ነበረው። ይህ በወረቀት የተነደፈ እቅድ በሥራ የሚውል መስለዋቸው ፈረንሳዮች በአዲስ አበባ የነበረ እምባሳደራቸው ላጋርድ ላይ ወቀሳ ሰንዝረውበት ነበር። የእንግሊዝና የኢጣሊያ እምባሳደ ሮች ደግሞ አጼ ምኒልክን ለማስሞኘት በመቻላቸው ከመንግሥቶቻቸው ልዩ ምስጋና አግኝተዋል።

ፈረንሳዮች የነበራቸው ስጋት ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የሚዘረጋው የባቡር ሀዲድ ጥቅም የሌለው ይሆናል በሚል ፍርሀት ነበር። ቪጎኒ (Vigoni) የተባለው በኢጣሊያ የሕግ መወሰኛ አባል የሆነው ሜይ 26/1903 ዓ.ም. በኢጣሊያ ፓርላማ ካደረገው ረጅም ንግግር እና ኩናማን በሚመለከት ያቀረባቸው ጥያቄዎች ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ[1] «ይህ በጣም አስገራሚ የሆነ ውል ተብሎ የማይጠራ ወይንም ለውሉ ትድመ ሁኔታ የማይባል በኢጣሊያ በኩል ማርቲኒ እኘዚያ ቺኮዲካላ ቦድሬሮ የነበሩበት፤በእንግሊዝ በኩል ሬነልሮድ ግለ ችንሐሪኒግተን የነበሩበት ኖቬንበር 22/1901 በሮማ በተደረገው ስብሰባ መጨረሻ ያወጡት መግለጫ የተነጋገሩበት ጉዳይ ስለ ኢትዮጵያና ሱዳን የወሰን ጉዳይ የሚል ሲሆን ስብሰባውም የተካሄደ በማን በምን ምክ ንያት እንደነበረ አይገልፅም፤መልዕክተኞቹ ወደ አዲስ አበባ ሔደ ው ሜይ 15/1902 ዓ.ም. ሻምበል ቺኮዲኮላና ኮ/ሌ ሐሪንግተን ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ጋራ ውል ተፈራርመዋል በዚሁ ውል መሠረት የቅኝ ግዛታችን ፊት ከነበረባት ወሰን ከሥር መሰረቱ ተቀያይሯል፤በእትባራ ወንዝ የነበረን መብት እንድናጣ ተደርጓል፤ ዋና የስብሰባ ዓላማ ይኸው ሳይሆን አይቀርም። የኩናማ አውራጃ በማግኘት ከአትባራ የሚያገኘኝ ሆምራ አጥተናል፤ በዚሁ መሠረት ወደ ከሰላ የሚወስደው የእግር መንገድ እናገኛ አጥተናል። አራት የኢጣ ሊያ መንግሥት ሰራተኞች እና ሶስት የእንግሊዝ መንግሥት ሰራተኞች ልዩ ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ማስረጃ ሳይቀርብ ጉዳዩ ወደ ፓርላማ ቀርቦ ሳይፈተድለት የቅ ኝ ግዛታችን ወሰን የመሬቱ ሰፋት ለመቀየር የሚያደርግ ውል እንዴት ሊያደርጉ ቻሉ?» የሚል ነበር።

1. Carlo Rossetti : ibd p. 266-268



መልስ የሰጠው ተጠባባቂ ሚ ንስትሩ ግን ለሌላ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ለዚሁ ጉዳይ ግን በቂ መልስ ሳይሰጥ ጊዜያዊ ነኝ በማለት አልፎታል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የትግራይ ወይም የጎንደር ሀገረ ገዢዎች ሳይጠየቁ በአጼ ምኒልክ ፍቃድ ብቻ የኩናማ አ ውራጃ በሕገ ወጥ መንገድ ኤርትራ ከታወጀበት ቀን ከ12 ዓመት በኋላ ከኤርትራ ጋራ የተቀላቀለ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

የኤርትራን ስም በሚመለከት አብዛኛው ኢትዮጵያውያን አይጠሉትም። እኔ ብቻ ይመስለኛል የምጠላው። ከጣሊያ የተሰጠ ስም ቢሆንም መጥፎ ስም አይደለም ከቀይ ባሕር የመጣ ነው ይላሉ። ቀይ ባሕር፤ ከመዓሉ በፊት የሐበሻ ባሕር ነበረ ስሙ። ኮንቲሮሲኒ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚለው መጽሐፉ የሚገኘው ማፕ መመልከት ይበቃል። አብዛኛው ኢት ዮጵያውያን ኤርትራውያንም ጭምር ከኤርትራ የበለጠ ስም ምን ተብሉ ሊጠራ ይችላል ይላሉ። በእኔ በኩል የኢጣሊያ ቀኝ ገዥዎች ባወጡልን ስም መጠቀም ራሱ አሳፋሪ ነው። ሌላ ስም ማውጣት ለኢጣሊያኖች እስቸጋሪ እንዳልሆነ ሁሉ በእኛም አስፈላጊነቱን ካመንበት አስቸጋሪ ሊሆን አይችልም።[1] ኮንቲሮሲኒ አቢሲኒያ ከሐበሻ የመጣ ነው የጥንት የገዢ መደ ብ የነበረ የአንድ የትግራይ ጉሳ ስም ነው፤ በኢጣሊያ ሀገር በደቡባዊ ኢጣ ሊያ ከሲሲሊ የባሕር ቦይ እስከ ላመቲኩስ ባሕረ ሰላጤ ብቻ ተወስኖ የነበረ ኢጣሊያ የሚለው ስም በኋላ ግን ለሞላው ኢጣሊያ እስከ እልፕስ እንደ ተስፋፋ ሁሉ በኢትዮጵያም የሐበሻ ስም ከመጀመሪያው ወሰኑ አልፎ በሞላው ኢትዮጵያ ሊሰፋፋ ችሏል ብለዋል። አግአዚያን የሚባሉም በሰሜን ኢትዮጵያ የነበሩ የኢትዮጵያ ጉሣ የግእዝ ቋንቋ የፈጠሩ ናቸው። ኤርትራ በእነዚህ ሁለት ጉሣዎች በሌላም ልትጠራ ትችላለች፤ የኤርትራ ስም ካላስወገድን ምንጊዜም ከኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ተገዢነትና ተዝታ ልንላቀቅ አንችልም። በሞዛምቢክ ማፑቶ የተባለችው ዋና ከተማዋ 500 ዓመት ስትጠራበት የነበረ ስም በመቀየር ነው ስም የተሰጣት፤ በሌላ አፍሪካ ሀገሮችም ብዙ የቅኝ ገዢ ዎች ስሞች ተቀይረዋል።

ኢጣሊያ ኤርትራን የፈጠረቻት በየጊዜው ከኢትዮጵያ እየቆራረሰች በገንዘብም፤ የጦር መሣሪያ በመስጠትም፤ በልዩ ተንኮልም ባጠራቀመቻቸው በተለያዩ ቦታ የተጠራቀሙ መሬቶች አንድ ላይ በማሰባሰብ ነበረ። እነዚህ በብዙ ዘዴ አንድ ላይ የተጠራቀሙ መሬቶች ቅኝ ገዢዋ ኢጣሊያ ኤርትራ ብላ ትጠራቸው ጀመረች። ዛሬ ኤርትራውያን ነን ኢትዮ ጵያውያን አይደለንም የሚሉ ወገኖች ሁሉ የኤርትራዊነት መለያቸው የዘር፤ የቋንቋ፤ የሃይማኖት ወይም የጆግራፊ እቀማመጥ መሠረት የላቸውም። ብ ቸኛ መለያቸው የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ፈለግ ለመከተል ነው።ለኢጣሊያ ቅኝ እገዛዝ አፍቃሪና ተገዢ በመሆናቸው ነው። ኤርትራ ሀገር ያደረገቻት ግፈኛዋ ቅኝ ገዢዋ ኢጣሊያ ናት። ይህ ሀገር ግን በዘር ወይንም በቋንቋ በታሪክ ልዩ የጋራ መለዮ የለውም። ኤርትራውያን ነን የሚሉ ሁሉ የኢጣሊያ የቅኝ አገዛዝ የሚናፍቃቸው ካልሆኑ በስተቀር በጋራ የሚያስተሳስራቸው ሌላ ነገር የላቸ ውም።

1. C.Conti - Rossini Etiopia e genti d'Etiopia p.1

ኤርትራ ጣሊያኖች ይጠቀሙባት የነበረ የኢትዮጵያን ለመያዝ ለነበራቸው ዓላማ ፀረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳ እያደረጉ ለወረራ እንዲዘጋጁባት ነበር። የዛሬ ኤርትራውያን በዚያ መልኩ የኢጣሊያ ፀረ–ኢትዮጵያ አራማጅ ከኢጣሊያ በልዩ ልዩ መንገድ በተማሩት መሰረት ለማራመድ ካልሆነ በስተቀር ለሕዝቡ ነፃነት አመጣንልህ ለማለት አይችሉም። እርግጥ ይህ ሁሉ ሁኔታ የተፈጠረው በኤርትራውያን ብቻ አይደለም። ዋናው ምንጩ ከኢትዮጵያ መንግሥት ነው። ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሳንሄድ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሕዝቡ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲያድርበት ጥረት አላደረገም። ጋብቻ ከአንድ ግለሰብ ማድረግ ጥቅም አይሰጥም። በሕዝቡ ላይ ቅስቀሳ ተደርጎ በኢጣሊያ የተሰጠው የኤርትራ ስም መቀየር የተገባ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ግን እንደ ምኒልክ ያሰበው የነበረ በስግብግብነት ለዘውድ ብቻ ነበረ። ለሌሎች ኢትዮጵያውያን አርአያ እንዳይሆን ተብሎ የተዘጋው የኤርትራ ፓርላማ ለኃይለ ሥላሴ ዘውድ ማዳ ከም እንጂ ማጠናከር አልጠቀመም። ለፀረ–ኢትዮጵያ ኤርትራውያን በውጭ መንግሥታት እየተረዱ ለእነሱም የማይበጅ አፍራሽ ተግባራቸው እንዲያካሂዱ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።

አሁን የፈለጉት ነፃነት አገኘን አሉ። የተወሰኑ ሰዎች ለጊዜው አስደስቷቸው ይሆናል። ዘላቂነት ያለው ሰላምና በህዝቦቿ መስማማት በመመ ስረት መሠረተ ድንጋይ አልተጣለም። ሊጣልም አይችልም። በቀረው የኢት ዮጵያ ክፍል አንዳንድ በጎ ጅምሮች ሲታዩ በኤርትራ ግን የሚታይ ብሩህ ተስፋ የለም። ይህ የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ቡድን ጉድለት ሳይሆን የኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ መኖር እንደማትችል በቂ ማስረጃ ነው። ኤርትራ የራሷ መንግሥት እንድትመሰርት ተኽምራዊ የሆነ የማዕድን ሀብት ክምችት እንደ ነዳጅ መገኘት አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ራሴን እችላለሁ ለማ ለት ዘበት ነው። አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ከኢጣሊያ ወይንም ከአሜሪካ ወይንም ከጀርመን እርዳታ ሲገኝ የሚያመጣ ምንም ለውጥ የለም። አሁንም እርስ በእርስ ጦርነት ገጥመን እናሸንፋለን ብለው የሚያስቡ ኃላፊነት የጎደላቸው ናቸው። ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ግዛት ነው የያዘቻት፣ ኤርትራውያን የአስ ተዳደር በደል ተፈፅሞባቸዋል ወዘተ...ተብሏል። ይኼ ሁሉ ወሬ ግን ቅጥፈት ነው። አብ ዛኛው ኢትዮጵያን ጠልተናል ብለው ከአዲስ አበባ ከሌሎችም ከተሞች ኮብልለው ነፃነት አገኘን ብለው ወደ ኤርትራ ከሄዱ ወይንም ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ከተንከራተቱ ኤርት ራውያን በድህ ነታቸው ተማረው ሳይሆን በንግድ ብዙ ሀብት ያካበቱ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከፍተኛ ደረጃ የነበራቸው ናቸው። ከጥንት ጀምሮ ኢጣሊያ የሸዋ ፖለቲካና የትግራይ ፖለቲካ እያለች ያካሄደችው የሰበካ ጠባሳ ናቸው።

በሸዋ ፀረ–ትግራይ ሰበካ ያካሄዱት ከካርዲናል ማሳያ ጀምሮ ብዙ ናቸው። ሰበካቸውም ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ እስከ ዘመናችን ደርሷል። ዘመኑ የአፄ ዮሐንስ ዘመነ መን ግሥት ነበር። ጣሊያኖች ያሰቡት እንደነበረ[1] ቀንደኛ ጠላታቸው አፄ ዮሐንስ ነው በእንፃሩም ወዳጅ ንጉሥ በሸዋ አግኝተናል፤ ስለዚህ ባለን አቅም አፄ ዮሐንስን ማጥፋት አፄ ምኒ ልክን ደግሞ ማስደሰት አለብን በሚል ዓላማ ነበር።

1. E Bellavita : Ibd p. 83



ከፋፍለህ ግዛ ሁሉም የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። የሸዋ ፖለቲካ በአንቶኔሊ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል። ከምኒልክ ጋራ ለመግባባት ችግር አላጋጠመውም። ሚኒልክ ይፈልገው የነበረ የጦር መሳሪያ ስለሆነ አንቶኔሊ ለምኒልክ የጦር ማግሪያ ለማትረብ ቆርጦ ተነስቷል። ሸቀና ጨርቃ ጨርቅ ለገፀ በረከት ለማበርከት የእቴጌ ጣ ይቱ ወዳጅ ለመሆን በቅቶ ነበር። አፄ ዮሐንስ በሕይወት እስካለ ድረስ የአንቶኔሊ ሐሳብ የሚታወም ጣሊያንዊ አልነበረም። አፄ ዮሐንስ እንደሞተ ግን በምፅዋ የነበሩ የኢጣሊያ ከፍተኛ የጦር አለቆች ከነሱ ውስጥም በተለይ ጀኔራል ባልዲሴራ[1] የኢትዮጵያ ከፍላተ ሀገሮች ያለማቋረጥ እርስ በእርስ እን ዲጣሉ ለማድረግ እቅድ አውጥቶ ነበር። በተለይ በትግራይ በአንድ በኩል የራስ መንገሻ ደጋፊ በመምሰል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የራስ መንገሻ የበታች ሹማምንቶቹ ሁል ጊዜ እያመ ፁበትና እንዳይታዘዙ በማድረግ እቅድ አውጥቶ ነበረ። በመጨረሻ ኢጣሊያ ይህ እቅድ ከግብ ለማድረስ እንቅፋት የሆነበት በውጫሌ ውል መሠረት ኢጣሊያ ምኒልክን ንጉሠ ነገሥት አድርጋ በማወቋ ነበር። በዚሁ ጊዜ ከዚሁ የተለየ ፖለቲካ ማራመድ የመንግሥቱን ፖለ ቲካ መቃወም ይሆናል። በ1890 ዓ.ም. የኤርትራ የሲቪል ሀገረ ገዢ ተብሎ ተሹሞ ጋንዶልፊ የሚባል ተልኮ መጣ። በዚሁ ጊዜ አክለጉዛይና ሰራዬ አውራጃዎች በተግባር የኢጣሊያ ግዛት ሆኖ ነበር፣ በሕግ ግን የኢትዮጵያ መሬቶች ነበሩ።[2] አፄ ምኒልክ ትግራይን የአፄ ዮሐንስ ትውልድ ሀገር የእኔ መሬት ነው ማለቱ ጣልያኖች ያስገርማቸው የነበረ ጣሊያኖች ሕገ ወጥ እነጋገር ብለው ይገምቱት ነበር።[3] ይሄም ጣሊያኖች የፖለቲካ ብስለታቸውና እው ቀታቸው ዝቅተኛ እንደነበረ የሚያስገነዝብ ነው። ጋንዶልፊ የአንቶኔሊ የሸዋ ፖለቲካ በከሸፈበት ወቅት ከመንግሥት ጋር በመስማማት የትግራይ ፖለቲካ ለማራመድ በትግራይ ሹማምንቶች በኩል ሞክሮ ነበረ። በመጀመሪያ የሚታና መሰሎት ነበር። ውል ለመፈራረ ም ተችሎ ነበር። የሰራዬና የአክለጉዛይ አውራጃዎች የኢጣሊያ ግዛት መሆናቸውን ራስ መንገሻ ተቀብሎ ነበር። ይሄም በመረብ በተደረገው ጉባኤ ራስ መንገሻና ጀኔራሉ ባደረጉት ጉባኤ ዲሴንበር 1891 ዓ.ም. በማህላ ቃል ተረጋግጦ ነበር። በዚሁ መሠረት ከ4 ዓመት በፊት ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በጦርነት እንደሚገጉ በኮሎኔል ሳሌታ ታውጀ የነበረ አዋጅ በይፋ ለማስቀረት ምክንያት ሆኖ ነበር። የትግራይ ፖለቲካ ውጤት እንዳይሰጥ እንቅፋት የሆነው ጀኔራል ጋንዶልፊ ለቆ በመሄድና በምትኩ ጀኔራል ባራቲሪ የኤርትራ አስተዳዳሪ ሆኖ በመሾሙ ነበር። በመንግሥት በኩል የአንቶሌኒ ፖለቲካ ስለከሸፈ ገንቢ ሥራ ለማከናወን የተቆጠበበት ወቅት ነበር። አዲሱ ሀገረ ገዢ ባራቴሪ ግን የግሉ የሆነ አስተዳደር ለመመሥረት ችሎ ነበር። በተለይ እዚህ ሳናስታውሰው ማለፍ የማይገባን የትምህርት ጉዳይ ነበረ። ጀኔራል ባልዲሴራ በእነስተኛ ደረጃ የትምህርት መሠረት ጥሎት የነበረ የቀለም ትምህርት ለማስቀ ረት የሙዚቃ ትምህርት ብቻ እንዲሰጥ መደረጉ ነው።[4]

1. E Bellavita : Ibd p. 84
2. E Bellavita: Ibd p. 123
3. E Bellavita: Ibd p. 124
4. E Bellavita: Ibd p. 132

ራስ መንገሻ ደጋግሞ ሌላ የመረብ ጉባኤ እንዲደረግ ጠይቆ ጣሊያኖች ሳይቀበሉት ከቆዩ በኋላ ባራቴሪም ለምክር ወደ ጣሊያን ሀገር ሄዶ በነበረ ጊዜ ስለተፈቀደለት ጉባኤ በሚደረግበት ጊዜ ከኢጣሊያ መንግሥት ስጦታም እንዲሰጠው ስለታቀደ ተልኮለት የነበረው ስጦታ በጉባኤው ቀን ተሰጠው። ባራቴሪ ግን ለመንግሥቱ በላከው ሪፖርት ወይንም ከራስ መንገሻና ከኤርትራ ሀገረ ገዢ ጋራ አንድ ጉባኤና ስምምነት ማድረግ፣ ወ ይም ጉባኤና ስምምነት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጋር ማድረግ ሁለት ስምምነቶች የማድረግ ግን እስከ አሁን በልዩ ልዩ ዘዴ የተሞከረ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል በማለት ጽሑፉን ደምድሞ ነበር።[1] የትግራይ ፖለቲካ ቆይቶ የተጀመረ ቢሆንም በተለይ ጣሊያኖች በዓድዋ ሽንፈት ከገጠማቸው በኋላ በተጠናከረ መልኩ ቀጥሎ ለማይጨው ጦርነት እስከ ተዘጋጁበት ጊዜ ድረስ የሸዋ ፖለቲካ ሲጠፉ የትግራይ ፖለቲካ ወቅታዊ በመሆን በሰሜን ኢትዮጵያ ፀረ–ሸዋ ጥላቻ ለብዙ ዓመታት በሕዝቡ አንጎል እንዲቀረፅ አድርገዋል። ከነፃነት በኋላም ጣሊያኖች ለዘመናት ለኩሰውት የሄዱት ጥላቻ እነ እጼ ኃይለስላሴ ለማጥፋት ባለመቻላቸው ከቁጥጥራቸው ውጭ በመሆን ህገ ረቷ ለ30 ዓመታት እርስ በእርስ ጦርነት ትርጉም የሌለውና ዓላማ ቢስ የሆነ እዙቅት እንድትወድቅ ሆና ቆይታለች። ጣሊያኖች የትግራይ ፖለቲካ እናራምዳለን በማለት ከራስ መንገሻ ጋራ በመረብ ወንዝ እጠገብ ጉባኤ መቀ መጣቸውን ስጦታ ማበርከታቸው ስራስ መንገሻ ከእጼ ምኒልክ ጋራ እንዲጣላ በማድረግ ጉዳት እንጂ አልጠቀሙትም። በእጃቸዉ የገባ የኤርትራ ሕዝብ ግን ፀረ ሸዋ ስበካ በተለያዩ መንገዶች አካሄደው ሕዝቡ በተለይ ለሙጊያው የሚመስምኂቸው ሰዎች በኢትዮጵያ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው እና በታማኝነት እንዲዋጉላቸው መርዘዋቸዋል። የኢጣሊያኖች ስበካ ከትውልድ እስከ ትውልድ ተላልፎ በዘመናችንም ውጤቱ እየታየ ነው።

## 5. የኩናማ አውራጃ ከኢትዮጵያ ተነጥላ ከኤርትራ ጋራ መቀላቀሏ ዝርዝር ሁኔታ

ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በየቀኑ በፃፈው ማስታወሻ የኤርትራ ሀገረ ገዢ በነበረበት ጊዜ በተገኙ ማስረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ኩናማ የሚኖሩበት መሬት ከኢትዮጵያ ነጥቆ ወደ ኤርትራ እንደተቀላቀለ የሚገልፁ ሁኔታውን ፀጭሩ አቀርባለሁ። እንግሊዞችና ጣሊያኖች ስለ ኩናማና ምዕራባዊ ኤርትራ ከሱዳንና ከኢትዮጵያ የሚያዋስናት ወሰን ለማሻሻል ቀደም ብለው ተነ ጋግረውበት ነበር። ማርቲኒ በአፕሪል 1900 ዓ.ም. ወደ ምዕራባዊ ቆላ ኤር ትራ ጉብኝት ያደርጋል። አፕሪል 18 እና 19 ከረንን ይጎበኛል። 21 እና 22 አቆርዳትን ጎብኝቷል። 23 ተኮላይ የቤኒአመር የመጨረሻ መሬት ደርሶ ወደ ባሪያ መሬት ሞጎሮ ይገባል። 26 ቶድሉክ ይደርሳል። 27 ኤይማላ የሚባል ቦታ እንደደረሰ 2 የኩናማ የኢትዮጵያ ግዛት ሰዎች ሁለት ፍየሎች በስጦታ ይዘው ማርቲኒ ጋር ይቀርባሉ። ጨርቅ ስልብስ የሚጠቅማቸው ሰጥቶ ይሸኛቸዋል።

1. E Bellavita: ibd p. 134



በየዕለቱ በሚጽፈው ማስታወሻ እነዚህ ግማሽ እውሬ ኩናሞች በማን ግዛት እንደሆኑ በጣሊያን ይሁን በእንግሊዝ ወይ በሀበሻ ይሁኑ አያውቁም። እንደውነቱ ከሆነ ግን መሬታቸው የኢትዮጵያ አንድ አካል ነው በማለት ጽፈዋል።[1]

ቺኮዲኮላ [2] ለማርቲኒ ቴሌግራም ልኮ «እጼ ምኒልክ የኩናማ አውራጃ /ጋሽና ሰቲት አውራጃ/ ለእኛ እንዲሰጠን ያቀረብኩለት ሐሳብ የሚያስብበት መሆኑን ነግሮኛል» ብሏል። ማርቲኒ ማርች 13 ቀን 1902 ወደ ኩናማ ጉብኝት ማድረግ ስለሚፈልግ ከመቶ እለቃ ፖሌራ ጋራ የአቁርደት እውራጃ ገዢ በጉብኝቱ ወቅት ስለሚያስፈልጉ አጃቢ ወታደሮች ይወያያል። የመቶ አለቃ የሚኼድበት የኢትዮጵያ መሬት ስለሆነ ቢያንስ 200 ወታደሮች እንደሚያስፈልጉ ሐሳብ ስላቀረበ አጃቢዎቹ 1ኛ.የባሻ ገብረ ሕይወት ባንዳ 2ኛ. እርባ ግመሎች 3ኛ. አንድ መቶ አለቃ ጦር እንዲያጠቃልል ይስማማሉ። በጉብኝቱ ወቅት ማርቲኒ አንድ ኢጣሊያዊ ገዳሪፍ ነዋሪ የሆነው ያገኛል። ኩናማ የእኛ ከሆነ የገዳሪፍ፣ የጎንደር፣ የንዓባት ንግድ በዚሁ መስመር ወደ እኛ ግዛት እንደሚሄድ እያጠራጥርም ይለዋል። አፕሪል 13 1902 ማርቲኒ በኩናማ ምድር እንዳለ ግብር ለማስከፈል የመጡ 3 ኢትዮጵያውያን ይገናኛል። እኛ ግብር ለማስገበር ነው የመጣነው፣ ነገር ግን ጣሊያኖችን እንፈራለን ሲሉት ማርቲኒ ኩራት ስለተሰማው እንዲህ ብሎ ይመልስላቸዋል። «እንስማማ እኔ እዚ የመጣሁት ከእጼ ምኒልክ ጋራ ተስማምቼ የንግድ መንገዶች የሚተላለፉበትን ለማጥናት የመንገዶቹ ጸጥታ እስተማማኝ እንዲሆኑ ለማየት ነው። እነዚህ መሬቶች የእኔ ስላልሆኑ ግብር አልቀበልም። እናንተ ግን መብት ካላችሁ መቀበል ትችላላችሁ። እኔ ግን የመንገዶቹ ጸጥታ እንዲከበር ስለምፈልግ ዘረፋ እንድታደርጉ አልፈቅድም። ያለበለዛ እኔ እቤታችሁ መጥቼ እዘርፋችኋለሁ፣ ርህራሄም አላደርግም።»[3] አፕሪል 17 1902 ዓ.ም. ማርቲኒ የኩናማ መሬት ለቆ ወደ አስመራ በሚመለስበት ጊዜ «እነዚህ መሬቶች ካየኋቸው በኋላ ለሀበሻ ልተዋቸው ነውን? አይሆንም» ይላል። ኩናማ ጐሣዎች አሁን እኛ እዚህ መጥተን ከሄድን ሕግ አክባሪዎች አይሉንም፣ ፈሪዎች ነው የሚሉን። ዞሮ ዞሮ ለወደሬት ቢዘገይም ባይዘገይም ኩናማ የእኛ መሆናቸው ስለማይቀር ያላቸው ቅሬታ ማዳመጥ ያስፈልገናል። በሌላ በኩል ግን የእኛ እስካልሆኑ ድረስ እንዴት ተደርጎ ነው ጠባቂ ወታደሮች ልናስቀምጥበት የምንችለው? ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ነው። የባሻ ገብረ ሕይወት ባንዳ በጣም ትንሽ ነው 34 ጠብመንጃዎች ብቻ ነው ያለው። እስብበታለሁ የሚያስችኩል ነገር አይደለም፣ በማለት የወደሬት እቅዱ ይገልጻል።

ኢትዮጵያዊ የኩናማ ሀገረ ገዢ በኩናማ ስለተደረገው «ጉዞ ሽርሽር» ማርቲኒ ወደ ግዛቱ ሲገባ ለምን እንዳልተነገረው ስሞታ አሰምቷል። የተሰጠው መልስ ለበታቹ ሹም ለገሰ እንደተነገረውና ጉብኝቱም የተደረገው በንጉሥ ምኒልክ ፈቃድ መሆኑን የሚል ነበረ።

1. F. Martini : ibd Vol.II p. 148
2. F. Martini : ibd Vol.II p. 484
3. F. Martini : Diario Eritreo Vol.II p. 570

ስለ ኩናማ ጉዳይ ንግግሮች እየተካሄዱ ስለሆነ ማደናቀፍ አያስፈልግም መጠንቀቅ ያስፈልገናል ብሎ ማርቲኒ ይመዘግባል።[1] ሜይ 22 1902 ዓ.ም. ማርቲኒ የዓዲ አቦ ሰዎች ወደ ኩናማ መሬት እየገቡ እንዳይዘርፉ ብሎ ሰበብ በማድረግ ለባርካ ሀገረ ገዢ ወሰኑን ጥሶ እንዲገባ በቴሌግራም ትዕዛዝ አስተላልፎለታል።[2] ሜይ 25 1902 ዓ.ም. ማርቲኒ ሜይ 9 ከቺኮዲኮላ የተላከ ቴሌግራም ይደርሰዋል። ቴሌግራሙም «ምኒልክ ኩናማ ለእኛ እንዲሰጥ አይታወምም» የሚል ነበር። ሜይ 31 1902 ዓ.ም. የአረዛ ሰራዬ ኢጣሊያዊ ገዢ ለማርቲኒ ስለ ኩናማ ጉዳይ አንስቶ ሲጽፍለት አዝማች ገሠሠ የወልቃይት ሀገረ ገዢ ከአ/አበባ ሲመለስ በእኛ ላይ መጥፎ አስተሳሰብ ይዞ ነው የመጣው። በተቻለው መጠን ኩናማ ለእኛ እንዲሆን ይታወማል። ፈረንጆች የፈለጉትን ሁሉ እንዲያደርጉ እንዲፈቅድላቸው ለአፄ ምኒልክ መድኃኒት ሰጥተውታል፤ በተለይም ጣሊያኖች እንተያያለን እያለ ነው፤ ምኒልክ ፈርሞ ይስጣቸው፤ የማደርገውን እኔ አውቃለሁ እያለ ይፎክር ነበረ ብሎዋል። ሜይ 16 1902 ዓ.ም. በተፃፈው ቴሌግራም ቺኮዲኮላ ለማርቲኒ የኩናማ መሬት ለኢጣሊያ እንዲሰጥ አፄ ምኒልክ ፈቅደዋል የሚል ዜና ያበስረዋል። ይሄንን ማረጋገጫ ሲያገኝ ማርቲኒ አሁንም የኩናማ አውራጃ በተግባር በእኛ ስር ስለሆነች የወልቃይት ሌቦች ለዘረፋ ለመምጣት ቢሞክሩ ለእኛ እንደ ስድብ ስለሆነ አንድ ሻንበል ጦር ወደ ስፍራው እንዲሰማራ ብሎ ያዝዛል።

ሜይ 15 1902 ዓ.ም. የተፈራረሙት ውልም ሁለት አንቀጽ የያዘ የሚከተለው ነው። ከአፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በጋራ በመስማማት ሻለቃ ቺኮዲኮላ የኢጣሊያ አምባሳደር በኢትዮጵያ እና ሌተናል ኮሎኔል ሀሪንግተን የእንግሊዝ መንግሥት አምባሳደር የሚከተሉት ነጥቦች ተስማምተዋል።

1ኛ. በኤርትራና በኢትዮጵያ ከዚህ በፊት በውሉ ከቶማት እስከ ቶድሉክ የነበረው መስመር እንደሚከተለው ተስተካክሏል። ኮርእም ሀጋል ከሴቲት ከሚገናኝበት አዲሱ ወሰን ይሄንን ወንዝ የማዕተብ ወንዝ እስከሚገናኝበት ድረስ ተከትሎ ይጓዛል። ታኩራ ተራራ ለኤርትራ በመተው መረብና ማይ አንበሳ እስከሚገናኙበት ድረስ ተከትሎ ይሄዳል፤ ከማዕተብና ከሴቲት መሐል እንደዚሁም ከማይ አንበሳና ከመረብ መሐል ያለው መሥመ ር ከኢጣሊያና ኢትዮጵያ የተውጣጡ መልዕክተኞች አቦታው ተገኝተው የኩናማ አውራጃ ወደ ኤርትራ እንዲሆን በማድረግ ይወስናሉ። 2ኛ. የኤ ርትራና የሱዳን ወሰን በአፕሪል 16 1901 ዓ.ም. በእንግሊዝና በኢጣሊያን መልዕክተኞች የተወሰነ መሆኑ ቀርቶ ከሳብደራት በአቡ ጋመል በኩል ኮርእም አጋር ከሴቲት ጋራ ወደሚገናኙበት የሚሄድ መንገድ ይሆናል።

እላይ የተመለከቱ ስምምነቶች በዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተቀባይነት አግኝቷል። በሥራ ላይ የሚውሉም የእንግሊዝና የኢጣሊያ መንግሥታት ሲያጸድቁት ይሆናል።

---

1. F. Martini : Diario Eritreo Vol.II p. 573
2. F. Martini : Diario Eritreo Vol.III p. 3



**ፊርማ**

ግርማዊ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በራሳቸውና በወራሾቻቸው ስም።

ሻለቃ ቺኮዲኮላ በግርማዊ ቪክቶሪዮ አማኑኤሌ 3ኛ የኢጣሊያ ንጉሥ በራሳቸውና በወራሾቻቸው ስም።

ሌተናል ኮሎኔል ሐሪንግተን በግርማዊ ኤድዋርድ 7ኛ የታላቋ ብሪ ታኒያና የአየርላንድ ንጉሥ የእንግሊዝ የጋራ ብልጽግና ሐገሮችና የባሕር ማዶ ንጉሥ የሕንድ ንጉሠ ነገሥት በራሳቸውና በወራሾቻቸው ስም።

ይኼንን ውል በሁለ~~ት [illegible] ቋንቋዎች~~ የተጻፈ አንድ ዓይነት የሆነ እኩል ዋጋ ያለው ፈርመዋል፤ ማሕተማቸውን አኑረዋል።

አዲስ አበባ ሜይ 15 ቀን 1902 ዓ.ም.።

በውሉ መሠረት ስለሱዳንና ኤርትራ ጉዳይ ከእንግሊዝና ከኢትዮጵያ የተውጣጡ መልዕክተኞች በቦታው ሄደው ምልክት አድርገዋል። በኢትዮጵያና በኤርትራ ወሰን ግን ምልክት ስላልተደረገ በዓዲ አቦ በኩል ምልክት ባልተደረገበት ቦታ በየጊዜው ግጭት ሊፈጠሩ ችሏል። ጁላይ 28 1902 ዓ.ም. ብዙ የሽሬ ሹማምንቶች ለአፄ ምኒልክ የኩናማ አውራጃ ለኢጣሊያ መሰጠቱ በመቃወም ቅሬታቸውን የገለጹ መሆናቸው መረጃ ለማርቲኒ ይደርሰዋል።[1] አፕሪል 16/1903 አምስት ኢትዮጵያውያን በኩናማ መሬት በመገኘታቸው ሊዘርፉን መጥ ተዋል በማለት በጣሊያኖች ታስረው ከነሱ ውስጥም ሁለት ልጆች ናቸው ተብለው ሲለቀቁ 3 ግን ተራ ወንጀለኞች ናቸው ተብለው ወደ ናቅፋ አሰብ ተወሰዱ።[2] ሜይ 2/1903 ሁለት ሌሎች ኢትዮጵያኖች በኢጣሊያን ታስረዋል።[3] ከሽሬ መሪዎች አንድ ደጃዝማች አብርሃ ወልደ እስራኤል የኩናማ አውራጃ ስምምነት አልቀበልም ብሎ በመቃወሙ ማርቲኒ ሜይ 14 ቀን አንድ መቶ አለቃ ልኮ ከአድራጎቱ የማይታገስ ከሆነ ከአፄ ምኒልክ ጋራ ተስማምተን እርምጃ የሚወስድበት መሆኑን እንዲነገረው አድርጓል። የሽሬ አውራጃ መሪዎች ለአንድ ዓመት መከራከራቸው የኩናማ መሬት የትግራይ ሽሬ አንድ ክፍል እንደ ነበረች ያሳያል።

## 6. ሶማሊያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት

በ1885ዓ.ም. ኢጣሊያ በስሜን ኢትዮጵያ በወረረችበት ጊዜ በሶማሊያ ወደቦች የሚጁርቲኒና የኦብያ ሱልጣኖች ነበሩ። በዚሁ ጊዜ በናዲር፣ ኪስማዮ፣ ብራቫ፣ መርካ፣ ሞቃዲሾና ዋርሼክ በዛንዚባር ሱልጣን ቁጥጥር ስር ነበሩ።

---

1. F. Martini : Diario Eritreo Vol.III p.6
2. F. Martini : Diario Eritrao Vol.III p. 160 -166
3. F. Martini : Diario Eritreo Vol.III p. 174

በ1888 ዓ.ም. እና 89 ዓ.ም. ኢጣሊያ ከሚጁርቲኒና ከኦቢያ ሱልጣኖች ጋር የበላይ ጠባቂ ለመሆን ተስማማች። በ1892 ዓ.ም. ከዘንዚባር ሱልጣን በመከራየት ኢጣሊያ የበናዲር ወደቦች እንድታስተዳድር ስምምነት አደረገች። የኢጣሊያ መንግሥት ከፊሎናርዲ ኩባንያ ስምምነት በማድረግ በመንግሥት ስም ኩባንያውን እስተዳዳሪ አደረገው። ኖቬምበር 15/1895 ከፎሌ በሚባለው ቦታ የሶማሊያ ገር ሆኖ ተሹሞ የነበረው ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ በኀይል ንግሥት ታስሮ በነበረው ቼኪ የሚመሩ ጣሊያኖች 20 ኪሎ ሜትር ከሞቃዲሾ ራቅ ብለው ለጉብኝት ሄደው በነበረበት ጊዜ 1/ ራሱ ቼኪ 2/ የመርከብ አዛዥ ማፌይ 3/ የመርከብ አዛዥ ሞንጃርዲኒ 4/ የመርከብ ምክትል መቶ አለቃ ባራልዲ 5/ ደክሬስቶፎሬ 6/ ሳንፌሊቼ 7/ የባሕር ዘብ ጉዞሪኒ 8/ የመቶ አለቆች ቫሮኒ 9/ ጋስፓሪኒ 10/ የመቶ አለቃ ሐኪም ዝሙራሊያ 11/መሐንዲሱ ኩዊሪከቲ 12/ሌሎች 5 ጣሊያኖችና 70 አሽከሮች ከሶማሊዎች በአፋሮች እንደተከሰተ ጥቂት ሱልጣኖች ሀገርን ሊሸጡ ይችላሉ ነገር ግን ሕዝቡን አይወክሉም፤ በነጻነት መኖር የለመዱ የነጮች የበላይነት በሀገራቸው ሲሰፍን ተመልክተው ደማቸው ስለፈላ አሰቃቂ እልቂት ሊፈጽሙ ችለዋል። እላይ የተዘረዘሩት ጣልያኖች በሙሉ ተገደሉ።

በ1905 ሁለት የኢጣሊያ ሻምበሎች 120 አስከሪ ዐረቦች በመያዝ ብዙ የመንግሥት ንብረት የዘረፉ ሱማሊያዎችን ለመቅጣት ወደ ሞቃዲሾ አካባቢ ይዘምታሉ። የዘመቻው መሪ ሻንበል ቦንጀሽኒ ላካባቢው ሕዝብ ዘራፊዎችና የተዘረፉ ንብረቶች በሙሉ ካላቸው እን ዲያወጡ ካላወጡ ግን ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በማስጠንቀቅ የአንድ ሳምንት «አል ቲማተም» ሰጥቶ የአልቲማተም ቀን ሊያልቅ ሲል ወደ ሉግ ጉብኝት አድርጎ ሲመለስ ባይ ዶዋ አካባቢ ሲደርስ በሐበሾች የተዘረፉ ሶማሊዎች እርዳታ የሚጠይቁ እሱ ዘንድ ይመጣሉ። ባለፈው ጊዜ በቼኪ የሚመሩ የነበሩ ጣሊያኖች በድንገት ሳያስቡት በሶማሊዎች ጥቃት ደርሶባቸው ነበረ ያለቁት። አሁን ግን ጣሊያኖች ከሞቃዲሾ የመጡበት ዓላማ ሐበሾችን ለመፈለግ ሳይሆን ዘራፊዎች ሶማሌዎችን ለመቅጣት ነበር። ሐበሾችም በሰፍራው የተገኙት ጠብ ፍለጋ አልነበረም። ሀገሩ የኢትዮጵያ መሆኑን ለማረጋገጥና ግብር ለማስከፈል፤ በሰፈሩባቸው ድን ኳኖች የኢትዮጵያ ባንዲራ እያውለበለቡ በባይዶዋ አካባቢ መሐሳ በተባለው ቦታ ከሞቃዲሾ አንድ ቀን ተኩል የእግር መንገድ ከብቶቻቸውን ይዘው 2500 ተዋጊዎች ታጣቂዎችና 1000 የእርሲና የኡጋዴን ወዶ ዘማቾች ሆነው ለውጊያ ምንም ሳያስቡ በድንኳናቸው ተቀ ምጠው ነበር። ሻንበል ቦንጀሽኒ ሶማሌዎች ለኢጣሊያኖች እርዳታ መጠየቃቸው በዚህ አጋጣሚ ንብረቱንም ሊመልሱ ይችላሉ። እርዳታ ከተሰጣቸውም ከኢጣሊያኖች ጋራ መግባባት ሊፈጠር ይችላል ብሎ በማሰብ የጠየቁት እርዳታ በደስታ ነበር የተቀበለው። ሐበሾች ያሉበት ቦታ በሚገባ ካጠና በኋላ በሐበሾች ላይ ድንገተኛ ጥቃት ፈጽሞ ሊጨርሳቸው ዕቅድ ያወጣል። ዲሴምበር 15 ከጠዋቱ 12 ሰዓት 300 መደበኛ ያልሆኑ ሶማሌ ባንዳ ታጣቂዎች በማስለፍ ጥቃት ካደረሰባቸው በኋላ ሐበሾች ከእልቂት ያመለጡትን ተከታትለው ለመጨፍጨፍ ትዕዛዝ ከሰጣቸው በኋላ ሁለቱ ጣሊያኖች ግራና ቀኝ ተቀምጠው እየመሩ 20 ዐረቦች መደበኛ የኢጣሊያ ታጣቂዎች ወታደሮች በሐበሾች ላይ ድንገተኛ ተኩስ ከፍተው ሳይዘጋጁ



የላፎሌ እልቂት

በላፎሌ የተገደሉ ጣሊያኖች ስም ዝርዝር በአንደኛ መስመር 1/አንቶኒዮ ቸኪ 2/ የመርከብ አዛዥ ማፌይ 3/ የመርከብ ም/መቶ አለቃ ሳንፌሊቼ በ2ኛ መስመር 1/ የመርከብ ም/የመቶ አለቃ ባራልዲ 2/ የመርከብ ም/አለቃ ኦሊቪዬሪ 3 የመርከብ አዛዥ ሞንጃርዲኒ 4/ ሻምበል ሐኪም ስሙራሊያ፡፡ በ3ኛ መስመር 1/ የባሕር ዘብ ጉዞሊኒ 2/ የጉምሩክ ሠራተኛ ኩዊሪጌቲ 3/ የመርከብ የመቶ አለቃ ጋስፓሪኒ 4/ አዛዥ ሮልፎ 5 የመርከብ የመቶ አለቃ ባሮኒ

I Caduti nell'eccidio di Lafolè: al centro: Antonio Cecchi; ai lati: comandante Maffei, sott. di vascello Sanfelice; seconda linea: sott. di vasc. Baraldi, sottocapo Olivieri, comm. Mongiardini, cap. medico Smuraglia; terza linea: g. mar. Guzzolini, funzionario dogana Quirighetti, ten. commissario Gasparini, capo Rolfo, ten. comm. Baroni.



በ1888 ዓ.ም. እና 89 ዓ.ም. ኢጣሊያ ከሚጅርቲኒና ከአቢያ ሱልጣኖች ጋር የበላይ ጠባቂ ለመሆን ተስማማች። በ1892 ዓ.ም. ገንዘብ ለዛንዚባር ሱልጣን በመክፈል ኢጣሊያ የበናዲር ወደቦች እንድታስተዳድር ስምምነት አደረገች። የኢጣሊያ መንግሥት ከፊሎናርዲ ኩባንያ ስምምነት በማድረግ በመንግሥት ስም ኩባንያውን አስተዳዳሪ አደረገው። ኖቬምበር 15/1896 ከፎሌ በሚባለው ቦታ የሶማሊያ ገገር ሆኖ ተሹሞ የነበረው ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ በጌራ ንግሥት ታስሮ በነበረው ቼኪ የሚመሩ ጣሊያኖች 20 ኪሎ ሜትር ከሞቃድሾ ራቅ ብለው ለጉብኝት ሄደው በነበረበት ጊዜ 1/ ራሱ ቼኪ 2/ የመርከብ አዛዥ ማፊይ 3/ የመርከብ አዛዥ ሞንጃርዲኒ 4/ የመርከብ ምክትል መቶ አለቃ ባራልዲ 5/ ደክሪስቶፎሬ 6/ ሳንፌሊቼ 7/ የባሕር ዘብ ጉዞሪኒ 8/ የመቶ አለቆች ቫሮኒ 9/ ጋስፓሪኒ 10/ የመቶ አለቃ ሐኪም ዝሙራሊያ 11/መሐንዲሱ ኩዊሪከቲ 12/ሌሎች 5 ጣሊያኖችና 70 አሽከሮች ከሶማሊዎች በአፋሮች እንደተከሰተ ጥቂት ሱልጣኖች ሀገርን ሊሸጡ ይችላሉ ነገር ግን ሕዝቡን አይወክሉም፤ በነጻነት መኖር የለመዱ የነጮች የበላይነት በሀገራቸው ሲሰፍን ተመልክተው ደማቸው ስለፈላ አሰቃቂ እልቂት ሊፈጽሙ ችለዋል። እላይ የተዘረዘሩት ጣልያኖች በሙሉ ተገደሉ።

በ1905 ሁለት የኢጣሊያ ሻምበሎች 120 አስከሪ ዐረቦች በመያዝ ብዙ የመንግሥት ንብረት የዘረፉ ሱማሊያዎችን ለመቅጣት ወደ ሞቃዲሾ አካባቢ ይዘምታሉ። የዘመቻው መሪ ሻንበል ቦንጆቫኒ ላካባቢው ሕዝብ ዘራፊዎችና የተዘረፉ ንብረቶች በሙሉ ካላቸው እንዲያወጡ ካላወጡ ግን ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በማስጠንቀቅ የአንድ ሳምንት «አልቲማተም» ሰጥቶ የአልቲማተም ቀን ሊያልቅ ሲል ወደ ሉግ ጉብኝት አድርጎ ሲመለስ ባይዶዋ አካባቢ ሲደርስ በሐበሾች የተዘረፉ ሶማሊዎች እርዳታ የሚጠይቁ እሱ ዘንድ ይመጣሉ። ባለፈው ጊዜ በቼኪ የሚመሩ የነበሩ ጣሊያኖች በድንገት ሳያስቡት በሶማሊዎች ጥቃት ደርሶባቸው ነበረ ያለቁት። አሁን ግን ጣሊያኖች ከሞቃዲሾ የመጡበት ዓላማ ሐበሾችን ለመፈለግ ሳይሆን ዘራፊዎች ሶማሌዎችን ለመቅጣት ነበር። ሐበሾችም በስፍራው የተገኙት ጠብ ፍለጋ አልነበረም። ሀገሩ የኢትዮጵያ መሆኑን ለማረጋገጥና ግብር ለማስከፈል፣ በሰፈሩባቸው ድንኳኖች የኢትዮጵያ ባንዲራ እያውለበለቡ በባይዶዋ አካባቢ መሐላ በተባለው ቦታ ከሞቃዲሾ አንድ ቀን ተኩል የእግር መንገድ ከብቶቻቸውን ይዘው፣ 2500 ተዋጊዎች ታጣቂዎችና 1000 የአርሲና የኡጋዴን ወዶ ዘማቾች ሆነው ለውጊያ ምንም ሳያስቡ በድንኳናቸው ተቀምጠው ነበር። ሻንበል ቦንጆቫኒ ሶማሌዎች ለኢጣሊያኖች እርዳታ መጠየቃቸው በዚህ አጋጣሚ ንብረቱንም ሊመልሱ ይችላሉ። እርዳታ ከተሰጣቸውም ከኢጣሊያኖች ጋራ መግባባት ሊፈጠር ይችላል ብሎ በማሰብ የጠየቁት እርዳታ በደስታ ነበር የተቀበለው። ሐበሾች ያሉበት ቦታ በሚገባ ካጠና በኋላ በሐበሾች ላይ ድንገተኛ ጥቃት ፈጽሞ ሊጨርሳቸው ዕቅድ ያወጣል። ዲሴምበር 15 ከጠዋቱ 12 ሰዓት 300 መደበኛ ያልሆኑ ሶማሌ ባንዳ ታጣቂዎች በማሰለፍ ጥቃት ካደረሰባቸው በኋላ ሐበሾች ከእልቂት ያመለጡትን ተከታትለው ለመጨፍጨፍ ትዕዛዝ ከሰጣቸው በኋላ ሁለቱ ጣሊያኖች ግራና ቀኝ ተቀምጠው እየመሩ 20 ዐረቦች መደበኛ የኢጣሊያ ታጣቂዎች ወታደሮች በሐበሾች ላይ ድንገተኛ ተኩስ ከፍተው ሳይዘጋጁ



የላፎሌ እልቂት

በላፎሌ የተገደሉ ጣሊያኖች ስም ዝርዝር በአንደኛ መስመር 1/አንቶኒዮ ቸኪ 2/ የመርከብ አዛዥ ማፈዪ 3/ የመርከብ ም/መቶ አለቃ ሳንፌሊቸ በ2ኛ መስመር 1/ የመርከብ ም/የመቶ አለቃ ባራልዲ 2/ የመርከብ ም/አለቃ ኦሊቪዬሪ 3 የመርከብ አዛዥ ሞንጃርዲኒ 4/ ሻምበል ሐኪም ስሙራሊያ፡፡ በ3ኛ መስመር 1/ የባሕር ዘብ ጉዞሊኒ 2/ የጉምሩክ ሠራተኛ ኩዊሪጌቲ 3/ የመርከብ የመቶ አለቃ ጋስፓሪኒ 4/ አዛዥ ሮልፎ 5 የመርከብ የመቶ አለቃ ባሮኒ

I Caduti nell'eccidio di Lafolè: *al centro*: Antonio Cecchi; *ai lati*: comandante Maffei, sott. di vascello Sanfelice; *seconda linea*: sott. di vasc. Baraldi, sottocapo Olivieri, com. Mongiardini, cap. medico Smuraglia; *terzo linea*: g. mar. Guzzolini, funzionario doganale Quirighetti, ten. commissario Gasparini, capo Rolfo, ten. comm. Baroni.



ተዘናንተው በሚገኙበት ጊዜ አልቂት እንዲፈጽሙ ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል። ፕላኑ እንዳሰቡት የተሳካ ሆኖላቸው ነበር። በኢትዮጵያውያን ሰፈር የከብቱም፣ የሰውም፣ የሴቱም፣ የወንዱም ጩኸትና ለቅሶ ይሰማ ነበር። ያልቆሰሉና ያልሞቱ ኢትዮጵያውያን ሸሽተው ከድንኳናቸው ወጡ። በዚሁ ጊዜ በጣሊያኖች ፕላን መሠረት 300 ሶማሌ ታጣቂዎች ሐበሾችን አባረው ለመፍጀት ሞክረው ነበር። ሐበሾች ግን እንደገና በመሰባሰብ ከሶማሊዎች ጋራ ውጊያ ገጥመው ከግማሽ በላይ በጦር ሜዳ ሲገድሉባቸው የቀሩት አምልጠው ሸሹ። በጣሊያኖች የሚመሩ ዐረቦችም ከኢትዮጵያውያን ጋራ ውጊያ ገጥመው ሁለቱ የኢጣሊያ ሻንበሎችና ከ120 ዐረቦችም 83 ገደሉባቸው። የቀሩት ሸሽተው አመለጡ።[1]

ኢትዮጵያውያን ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር ከሞቃዲሾ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው ባሐሌ የተባለው ቦታ የኢትዮጵያ ባንዲራ ተክለው ወደ ሕንድ ውቅያኖስ ለመድረስ ሞቃዲሾን ለመያዝ ሲታገሉ አጼ ምኒልክ አዲስ አበባ ሆኖ ከኢጣሊያ አምባሳደር ጋራ በመነጋገር ጥፋተኞች ወራሪዎች ጣሊያኖች ሆነው ሳለ ኢትዮጵያውያን እንዲቀጡና ከያዙት ቦታ እንዲመለሱ አድርገዋል። ሉግ የተባለ ለንግድ አመቺ ከተማ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ለወሰን የተስማሙበት ከባሕር 180 ማይል ፓራለል ርቀት ውጭ የምትገኝ በገንዘብ ለኢጣሊያ ይሸጠዋል።[2]

## 7. የመረብ ምላሽ ደቡብ ወሰን የሽያጭ ውል የተፈጸመበት ዝርዝር ሁኔታ፣

የሽያጭ ውል በጣሊያን በኩል ይደራደሩ የነበሩ ሀ. የኢጣሊያ መንግሥት ሊ. በኢትዮጵያ የኢጣሊያ አምባሳደር ቺኮዲኮላ ሐ. የኤርትራ ሀገረ ገዢ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ሊሆን ዋና ተዋናይ ግን ማርቲኒ ነበር። ድርድሩ የተከናወነው ማርቲኒ ሀገረ ገዢ ሆኖ ተሹሞ ኤርትራ ከገባበት ጃንዋሪ 1898 ዓ.ም. ጀምሮ በፊርማ እስከጸደቀበት ቀን ድረስ ጁላይ 1900 ዓ.ም. ነው። የሁለት ዓመት ጊዜ ነው ለማለት ይቻላል። ማርቲኒ የፃፈው የዕለት ሁኔታ ማስታወሻ ብንከታተል ከሜይ 3 1898 ዓ.ም. ስለ ወሰኑን ጉዳይ መከታተል ጀምሮ ነበር። በዚሁ ዕለት ከኢጣሊያ [3] አምባሳደር በአ/አበባ አንድ ገለልተኛ ከራስ መንገሻ ነፃ የሆነ መሬ ት ከመረብ ጀምሮ እስከ ኦክቶበር 1898 ወሰን ውል የተፈጸመው በአነስተኛ ወረዳዎች በመከፋፈል በራስ መንገሻ በቀጥታ የሚታዘዙ በጣሊያኖች ላይ ግን ያልሸፈቱ እየተመረጡ ገዢዎች እንዲመደቡ የሚል ሐሳብ አቅድ አጼ ምኒልክ እንዳለው በቴሌግራም እንዳስታወቀው መዝግቧል። ከዚህም በላይ አጼ ምኒልክ ከዚህኛው መሬት የኢጣሊያ ወዳጅነት እንደሚመርጥ ገልጾልኛል፤ ነገር ግን መሬቶቹ እንዳይሸጡ ለሚቃወሙ የራሱ ሹማምንቶች ራሶች ለመቋቋም አቅም እንደሌለው አጼ ምኒልክ ገልጦልኛል ብለዋል።

1. V. Mantegazza : Benadir p. 248-252
2. V. Mantegazza : Benadir p. 278
3. F.Martini : Ibd Vol I p. 141



ማርቲኒ ጁን 15 ኢጣሊያ የተባሉ መሬቶችን ለቃ የምትወጣ ከሆነ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጠኝና ሌላ ሰው መንግሥት እንዲተካ ብሎ ለሮማ ይጽፋል። ጁላይ 1 ማርቲኒ በኤደን የኢጣሊያ ቆንስል ስለወሰኖች ለመነጋገር ከሸዋ የሚመጣው መልዕክተኛ ወደ ኤርትራ እንዳይላክ በማለት ደብዳቤ ይላክለታል። በጁላይ ወር ስለ ኤርትራ ጉዳይ ለመነጋገር በተለይ ስለወሰኑ ለመነጋገር ወደ ሮማ ሄዶ ኦገስት 24 በቶሪኖ ቤተመንግሥት ከኢጣሊያ[1] ንጉሥ ተገናኝቶ ስለወሰኑ ጉዳይ ያስረዳል። በ25 ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በተነጋገረበት ጊዜ ሚኒስትሩ ያለው ምርጫ የኢጣሊያ ይዞታ በተግባር ላይ ያለው ወሰን ሳይሆን ሕጋዊነት ያለው መሆን እንዳለበት በማስረዳት እንደገና ከሸዋ ጋራ ጦርነትም መግጠም እንደማይፈልግ ይነግረዋል። ሴፕቴምበር 10 ከጀኔራል ባልዲሴራ ጋር [2] ይገናኛል። ጀኔራሉ የሰጠው ምክር ኢጣሊያ ከዓዲ ቀይህ እንድትወጣ ከተገደድክ ወደ ሀገርህ ተመለስ። ዓዲ ቀይህን ካጣን ያልታሰበ አሳዛኝ ችግር ልንወድቅ እንችላለን፣ ለዚህም እርስዎ ምስክርም ኃላፊም እንዲሆኑ አልመኝሎትም። ዓዲ ቀይህን የምንለቅ ከሆነ ከደጋ ኤርትራ በመላው ብንለቅ ይሻላል። ሴፕቴምበር 11 በአንድ የኢጣሊያ ጋዜጣ ማርቲኒ የመረብ የኤርትራ ወሰን ኢጣሊያ እንድትለቅ ብሎ በመከራከሩ ወደ ጦርነት አዘቅት ሊከተን እየሞከረ ነው ወይም ንጉሡ (አጼ ምኒልክ) በቁጣ ለጦርነት እንዲነሳ እያደረገ ነው ብሎ በማውጣቱ ማርቲኒ ሃሳቡን በመግለፅ ረጅም ሪፖርት ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለማቅረብ ያስባል። ሃሳቡን ካልተቀበሉት ግን ወደ ኤርትራ አልመለስም ብሎ ውሳኔ ያቀርባል። የኢጣልያ ንጉሥ ተቀብሎ እንዲያነጋግረው ይጠይቃል። ሴፕቴምበር 22[3] ሪፖርት አቀርበዋል።

ባሻ ጆን በዓድዋ ጦርነት የዓይን ምስክር በትግራይ ይኖር የነበረ እንግሊዛዊ፣ የዓድዋ ጦርነት እሁድ ሊካሄድ ጦርነቱ ባይደረግ ኖሮ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለሰኞ ወደ ኋላ ለመመለስ ከዓድዋ ለቆ ለመሄድ አስቦ እንደነበረ የሚል ከአሥመራ ደብዳቤ ይደርሰዋል። ቶሪኖ ሆኖ በማርቲኒ አስተያየት የትግራይ ችግር የተባባሰ ይመስለዋል። በአጼ ምኒልክ እና በራስ መንገሻ መሐከል ጦርነቱ የማይቀር ነው፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ስለ ወሰኑ መነጋገር እንደማይቻል ያስባል። በቶሪኖ ግን «ይህ ሰራዬ የሚባለው ሀገር መቼ ነው ለኢትዮጵያ የምትመልሱት? ቶሎ በሉ እንጂ!» እያለ የማያሾፍ ሰው የለም። ይሄ ሁሉ የቶሪኖና የሚላኖ የቅኝ ግዛት ጥላቻ የኤርትራ ወታደራዊ አገዛዝ መስተዳድር ሰለቆየች ነው። በማርቲኒ ግን በመጀመሪያ ሲቪል አስተዳዳሪ ነገሮች እንደሚቀየሩ በማለት ራሱን ያመሰግናል። ሴፕቴምበር 26/1896 ቶሪኖ ቤተመንግሥት የኢጣሊያ ንጉሥ የምሳ ግብዣ ተጋብዘዋል። ስለ ኤርትራ ከመነጋገራቸው በፊት ማርቲኒ ከንጉሡ የሚለ ቀወጣቸው የሐሳብ ልውውጦች ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል ወሳኝ ናቸው። ከሆነልኝ ሆነልኝ ካልሆነልኝ ተሸናፊ እንደሆንኩ ማመን አለ [illegible]

1. F.Martini : Ibd Vol I p.238
2. F.Martini : Ibd Vol I p.239
3. F.Martini : Ibd Vol I p.241

ከምላ ግብዣ በኋላ ከአደረጋቸው የሐሳብ ልውውጦች በኋላ ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ
ነው፣ ንግግራችን እኔ እንደምፈልገው ሆኖ አልቋል፡ እኔ ለግርማዊነታቸው የጠየኳቸው
በአጭሩ እንደሚከተለው ነበረ ። ግርማዊ ሆይ ወደ ኢጣሊያ ከመጣሁ ሁለት ወር ሆኖኛል፡
እዚህ ከመጣሁ ጀምሮ እስከአሁን እንከተለው የነበረ ፖለቲካ መቀየር እንዳለበት በስሕተት
ለአጼ ምኒልክ እንመልሳለን ካልናቸው መሬቶች ባለን አቅም ተጠቅመን ለቀን መውጣት
እንደሌለብን ለጠቅላይ ሚኒስትርና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በቃል ነግሬያቸዋለሁ። እውነ
ትህን ነው ብለው መልስ ሰጡኝ። ነገር ግን ቺኮዲኮላ የጀመራቸው ንግግሮች እንዲራዘሙ
ከማድረግ በቀር ሌላ የሚደረግ ነገር እንደሌለ ነው የነገሩኝ። ይሄም የመራዘም እቅድ እኔ
ለውጭ ጉዳይ ሚ ኒስቴር ባቀረብኩት ሪፖርት የታገልኩለት ነው ። የዚህም ኮፒ ግርማዊነትዎ
እንዲላክልዎት ጠይቄያለሁ። ግርማዊነታቸው እዎ አንብቤዋለሁ አሉ፡ ጥሩ ነው ብኋል[1]
ግርማዊነትዎ ግባችን እንዲሳካ የማቀርበው ሐሳብ አቀራረቡን በአዲስ መልክ መሆኑን
አይተው ይሆናል፣ ከኤርትራ ከተለየሁ ሁለት ወር ሆኖኛል። እኔ የምፈልገው የመንግሥት
ሐሳብ ምን እንደሆነ ለማወቅና የማያወላውል መመሪያ እንዲሰጠኝ ነው፡ ውሳኔ በሌለው
አቋም ከተቀመጥን ወይንም ዕድል እንዲመጣው የምንል ከሆነ እኔ ግርማዊነትዎን የምለም
ነው ኀሊናዬ ስለማይቀበለው ከተሰጠኝ ኃላፊነት እንዲያሰናብቱኝ ነው ይላል። ንጉሡም ይ
ህ ሊሆን አይችልም እርስዎ ያውቃሉ፡ ነግሬዎታለሁ። አሁንም እደግምሎታለሁ፡ እኔ በእ
ርሶ ላይ ሙሉ እምነት አለኝ ብቻ ሳይሆን እኔ በሚያደርጉት ትግል ከጎንዎ ነኝ። ሰዎች እን
ደሚሉት እኔ ጦርነት የጠማኝ መሆኔን በይፋ ለመግለፅ ችግር የለብኝም። እንደእ ቢሆን ኖሮ
የኢትዮጵያ ንጉሥ ላቀመሰን ዱላ ብድር መመለስ እወድ ነበር። የቦንፋኒኒ መመረጥ ያልተቀ
በልኩት ከኤርትራ ለቀን እንድንወጣ ደጋፊ ስለነበረ ነው፡ የእርስዎም መመረጥ በደስታ
የተቀበልኩት የዚሁ ተቃራኒ ስለሆነ ነው። ከደጋው ኤርትራ አንወጣም። በእኔ ድጋፍ
መተማመን ይችላሉ ብኋል። ኦክቶበር 1 ማርቲኒ የኢጣሊያ ቆንሲል በኤደን የራስ መኰንን
መልዕክተኞች ወደ አሥመራ ለመሄድ 95 ሰዎች ዘይላ መጥተዋል የሚል ቴሌግራም ይደር
ሰዋል። እኛ ከአጼ ምኒልክ እንጂ ከራስ መኰንን እንደማንነጋገር ለንጉሡም የምንከራከርባ
ቸው መሬቶች ለራስ መንገሻ እንዲሰጡ ብሎ ያቀረበው ሐሳብ እንዳልተቀበልነው ተነግሮ
ታል። ስለሆነም እኔም ስለሌለሁ ወደ ኤርትራ እንዳይሄዱ እንዲያደርግ ቴሌግራም ለቆንሲሉ
ተፅፏል።

ኦክቶበር 2 ማርቲኒ ከኔራዚኒ ጋራ የአ/አበባ ውል ከአጼ ምኒልክ ጋር ስለተፈረመው
ውል ይነጋገራል። እርሶም ያቀረቡትን ሐሳብ መሞከር አይከፋም፣ እኔ የምሆንልዎት አይመ
ስለኝም። እርስዎ አጼ ምኒልክ አከለጉዛይን እና ሰራዬን ለመረከብ የሚጨነቅበት ጉዳይ አይ
ደለም የሚል ስሕተት የሆነ አስተሳሰብ ነው የተነሱት። ነገር ግን አጼ ምኒልክ በከፍተኛ
ደረጃ የሚፈልጋቸው መሬቶች ናቸው። አጼ ምኒልክ ሥልጣን የለውም የሚል ነገርም አያም
ንበትም። በዓለም ካሉ ነገሥታት ከሁሉ ኃይለኛ አጼ ምኒልክ ይመስለዋል።

1. F.Martini : ibd Vol I p.244



የሚያስት የተንቀሳ እምነት ነው በማለት መዝግበዋል።[1] ኦክቶቦር 3 ማርቲኒ ጠዋት
ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ካኔባር ይገናኛሉ። በንግግሩ ኔራዚኒ እና አፒዚያም ነበሩ። በአ/አበባ
ውል መሠረት ለኢትዮጵያ መመለስ የምንገደድባቸው መሬቶች ላንመልስ በመቆየት ካለፈ
ለገ ምን መደረግ አለበት? አጼ ምኒልክ እንዲፈቅድ ለማድረግ በገንዘብ መካስ ያስፈልግ
ይሆናል! ገንዘቡ ግን ከየት ይገኛል? እኔ ከካኔባር ጋራ አልተስማማሁም ስብሰባው ውጤት
አልሰጠም።[2] እኔ አሉና ኔራዚኒ ከሰዓት በኋላ ከጠቅላይ ምኒስትሩ እንድንገናኝና አንድ
ንስማማ ይወሰናል። ከሰዓት በኋላ ማርቲኒ ሚኒስትሩ ጋር ይገናኛል። ሚኒስትሩ ስለሌላ ነገር
ምንም ሳያተኩር ለቺኮዲኮላ በትግራይ ስላለው ሁኔታ ምክንያት የወሰኑ ጉዳይ ለማስተካከል
አሁን ማሰብ ስለሚያስቸግር አሁን ባለው ሁኔታ እንዲቀጥል እና አጼ ምኒልክ መካካሻ
ሊጠይቀን እንደሚችል እንዲያጠና መመሪያ እንዲሰጠው ሐሳብ ያቀርባል። ጥሩ ነው መመሪ
ያዎች ነገ ይፃፋሉ ለፊርማ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይላካሉ። በሚቀጥለው ሳምንት መጀመ
ሪያ በአጋጣሚ የሚገኘው የሚላከው ፖስታ ይላካሉ። በጣም ጥሩ ነው፣ ንጉሡ ቃላቸውን
አክብረዋል። በዚህ ሁሉ የእሳቸው እጅ እንዳለበት ይታየኛል። ለስንብት በሞንዛ ከንጉሡ
ምላ ግብዣ ከ5:30 እስከ 8:00 ሰዓት ቆየሁ፣ በእኔ ላይ ያላቸውን እምነት ገልፀውልኛል።

የማርቲኒ ወደ ኤርትራ መልስ ሆነ። ኖቬምበር 4 አሥመራ ይገባል፡ ኖቬምበር 7
ራስ መኰንን አጼ ምኒልክ በትግራይ ላይ ዘመቻ ይጀምራል፣ ለመንገሻ ኡልቲማተም ይላ
ካል። ራስ መንገሻ ግን "አንተ ምን እንደምታደርገኝ ትፅፍልኛለህ፣ ነገር ግን እኔ አንተ ጋር
እንድቀርብ የምትጠይቀኝ አልመጣም። ምክንያቱም ሴይጣን የሰጠሽኝን ተስፋ ሊያስረሳህ
ይችላል" የሚል መልስ ይልካል።

ዲሴምበር 6 ከቺኮዲካላ ቴሌግራም[3] ለማርቲኒ ይደ ርሳል። መመለስ የሚገባን መሬቶች
በጊዜያዊነት ለእኛ ለመስጠት አጼ ምኒ ልክ ዝግጁ መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ማርቲኒ በዚሁ
ጊዜ የእኔ ፖለቲካ አሸንፏል ይላል። ከእንግሊዞች ጋራ እንደምንስማማ ለምኒልክ ማሳየት
ይሄንን ስለሚፈራ ለእንግሊዝ ኤርትራን አሳልፈን እንዳንሰጥ በመፍራት ከእኛ ጋራ
መስማማት ይፈልጋል። ዲሴምበር 7 ሁለት ቴሌግራሞች ከቺኮዲኮላ ይደርሳሉ፣ በአንደኛው
አጼ ምኒልክ ራስ መኰንንም በትግራይ በኩል የላከ መሆኑን ኔራዚኒ ከመኮንን ጋራ ስለወሰኑ
ጉዳይ እንዲነጋገር እንዲላክ ሲጠይቅ በሁለተኛው ከሁለት ቀን በኋላ ላልተወሰነ[4] ጊዜ
መሬቶቹን ለመሥጠት አጼ ምኒልክ ዝግጁ መሆኑን የሚገልጽ ነበር።በ48 ሰዓት ውስጥ አጼ
ምኒልክ ሐሳቡን ምን አስለወጠው? እንግሊዞችን በመፍራት ይሆናል? ዲሴምበር 8 ካኔቫሮ
ላልተወሰነ ጊዜ ማለት እኛ ወደን እስከምንለቅ ድረስ ማለት እንደሆነ ብሎ የተረጎመው
መሆኑን በቴሌግራም ገልጿል፣ እኔም በእሱ ሐሳብ እስማማለሁ ይኋል።

1. F.Martini : ibd Vol I p. 248
2. F.Martini : ibd Vol I p. 247
3. F.Martini : ibd Vol I p. 286
4. F.Martini : ibd Vol I p. 287

ዲሴምበር 27 ቺኮዲኮላ አጼ ምኒልክ ምንም እንኳን ስለወሰኑ ጉዳይ መልካም አስተሳሰብ ቢኖረውም እኛ በራስ መኮንን ላይ ያለን አስተሳሰብ ግልፅ እስኪሆን ድረስ ለጊዜው የወሰኑ ጉዳይ እንዳለ[1] እንዲቆይ ወስኗል። ለቺኮዲኮላ ከራስ መንገሻ ጋራ ወዳጅነት እንደሌለንና እንዳልነበረን ለአጼ ምኒልክ እንዲላክለት ደብዳቤ አጽፋለሁ። ጃንዋሪ ሁለት 1899 ትግራይ ላለው ራስ መኮንን ምግብ ስለሚያጥረው ምኒልክ ምግብ እንዲላክለት ጠይቆ ነበር። ካኔቫሮ ሀ/ አንድ ቴሌግራም ልኮ የወሰኑ ጉዳይ ቶሎ እንዲያልቅ በቺኮዲኮላ እንዲጉተጉት ይጠይቃል ለ/ በሌላ ቴሌግራም ምግብ ለራስ መኮንን ምንም መስጠት እንደማይችል ሐ/ በሌላ ቴሌግራም ደግሞ ለወሰኑ ጉዳይ የሚጠቅመን ከሆነ ምግብ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን[2] መ/ በሌላ ቴሌግራምም የወሰኑ ጉዳይ የሚያልቅልን ከሆነ በምጽዋ ለኢትዮጵያ በጉምሩክ እከፋፈል ለማሻሻል እንደሚያደርግ ለቺኮዲኮላ እንዲነገረው በመጠየቅ። ጃንዋሪ 7 ኖቬምበር 23/1898 ከአጼ ምኒልክ የተጻፈ ደብዳቤ በትግራይ የሚገኝ የራስ መኮንን ጦር እየዘረፈ ከተመገበ ሕዝቡ እንዳይሸፍት 30,000 ብር ብድር ከተሰጠው ምግቡ ከኤርትራ እየገዛ ስለሚመገብ በምትኩ ግን በከርከር ላይ ያሉ መሬቶች አጼ ምኒልክ በዘለቄታው ለኢጣሊያኖች ለመሥጠት ዝግጁ መሆኑን የሚገልጽ ነው። አጼ ምኒልክ በጣም ብልጥ ነው። አሁን ግን ብልጥነቱ ይጉደዋል። እኛ መሬቶቹ ለዘለቄታ አስቀድሞ ካልሰጠን በእኔ በኩል ምግብ ለሸዋ ጦር መስጠት አንችልም። ጃንዋሪ 10 የትግራይ ቄሶች ለራስ መንገሻና ለራስ መኩንን እርስ በእርሳችሁ ጦርነት ከምትገጥሙ በሐማሴን የሚገኙ-ሃይማኖት የሌላቸውን እሸወጡ እያሉ ይመክሯቸው ነበር። በራስ መንገሻና በራስ መኩንን መሐል ሰላም ሆኗል። ፌብሯሪ 25 ጥር 1 ቀን[3] ነው፤ ዛሬ ከወረኢሉ አንድ ሪፖርት ከቺኮዲኮላ ከአጼ ምኒልክም አንድ ደብዳቤ ደርሶኛል። የአጼ ም ኒልክ ደብዳቤ ለንጉሥ ኡምቤርቶ የእሁኑ ወሰን እስከመረብ ሳይለቅ እንዲቀመጥ የሚለምን ነበረ። ደስ ብሎኛል ስለ ኤርትራ ወሰን ጉዳይ ሁሉም ጥሩ መልስ አግኝቻለሁ። እኔ ባልኖር ወሰኑ ድባርዋ ይሆን ነበረ። ሲጋርድ እና ቫላሶፍ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። የእኛ ወዳጅነት በኢትዮጵያ ጨምሯል። የፈረንሳይና የሩሲያ ቀንሷል። ፌብሯሪ 27 ከበሩ ሜዳ ቺኮዲኮላ ቴሌግራም ልኮልኛል፤ ከአቡነ ማቴዎስ ጋራ በመስማማት የአጼ ምኒልክ የመጨረሻ ማወላወል ለማሸነፍ እየሞከርኩ ነው የሚል ነበር። ሜይ 20 1889 ቺኮዲኮላ ቴሌግራም እንደላከው አጼ ምኒልክ የእናንተ ወዳጅነት ለሁልጊዜ ዘላቂ መሆኑን እርግጠኛ ከሆንኩ ሌላ መሬትም እሰጣችሁ ነበር የሚል ሐሳብ ነበረበት። በቺኮዲኮላ ሐሳብ የወሰኑ ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ቢሆን ለምሳሌ 15–20 ዓመት ወደ ስምምነት ለመድረስ ችግር አይኖረውም ነበረ፤ ላልተወሰነ ጊዜ ከሆነ ግን ንግግሩ ሊራዘም ይችላል። ጁን 23 ሁለት ቴሌግራሞች ከቺኮዲኮላ ተልከውልኛል። ስለወሰኑ ጉዳይ አጼ ምኒልክ ሁለት ሐሳቦች አቅርበዋል።

1. F.Martini : ibd Vol I p. 314
2. F.Martini : ibd Vol I p. 334
3. F.Martini : ibd Vol I p. 538



1ኛ. በጊዜያዊነት መስጠት የራስ መኩንን ጥያቄ ጣሊያኖች ከተቀበሉ የምግብ ጉዳይ

2ኛ. ለሁልጊዜ ለመስጠት በየዓመቱ ግብር ከተከፈለ ኢጣሊያ ከተባሉ መሬቶች መልቀቅ ስለማትፈልግ ካሳ መስጠት ይኖርባታል።[1]

በእኔ በኩል አጼ ምኒልክ ያቀረባቸው እቅዶች ልንቀበላቸው አንችልም። ጁን 25 ማርቲኒ ወደ ኢጣሊያ ለመሄድ ተነስቷል።

ፌብሯሪ 6/1900 ዓ.ም. ማርቲኒ ቺኮዲኮላ አጼ ምኒልክ ምንም ካሳ ሳይጠይቅ ከያዝናቸው መሬቶች ሰራዬ በሙሉና አከለጉዛይ በሙሉ ከሎጎና ሺሜዛና በቀር ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ገልጸውልኛል።[2] አፕሪል 15 በቺኮዲኮላ ቴሌግራም መሠረት አጼ ምኒልክ የወሰኑ ጉዳይ ቶሎ ለመጨረስ ይፈልጋል ነገር ግን ካሳ ይፈልጋል። ይኸውም ለማስመሰል ነው፤ ገንዘቡ ግማሹ በብድር መልክ እንዲሰጠው ግማሹ የቴሌግራፍ መስመር ከኤርትራ ወሰን እስከ አዲስ አበባ ለማስጨረስ ለሚደረገው ወጪ ይውላል። አፕሪል 23 ከአዲስ አበባ ቴሌግራም ይደርሳል፤ አጼ ምኒልክ መረብ– በለሳ– ሙና ለእኛ ለመስጠት ተስማምተዋል። ካሳ ግን 5 ሚሊዮን ሊሬ ጠይቀዋል። ስለዚህ ጉዳይ ግን በጥብቅ በምስጢር እንዲያዝ ይፈልጋል። ቴሌግራሙ ወዲያውኑ ወደ ሮማ አስተላልፈአለሁ። ሜይ 28/1990 ዓ.ም. ከሁለት ዓመት ድካም በኋላ ተላክቶልኛል። ሰራዬ፤ አከለጉዛይና ሽሜዛና የእኛ ናቸ ው፤ አጼ ምኒልክ ለመፈረም ዝግጁ ነው። ይህ ሁሉ የተገኘው በእኔ ድካም ነው ለማለት ይችላሉ፤ እኔ ባልኖር የራስ ወሌ ድንኳኖች መቀሌ ሳይሆን ድባርዋ ላይ ይተከሉ ነበር። ዛሬ ጥሩ ቀን ነው እኔ ደስ ብሎኛል፤ ለፖለቲካ እስረኞች ምህረት አድርጊያለሁ፤ ለስደተኞች እዝግች ሰንጋል ጥምር ምሕረት አድርጊያለሁ በማለት መዝግበዋል።

ጁን 18 «ውሉ በአንድ ሳምንት ውስጥ ይፈረማል፤ የቺኮዲኮላ ቴሌግራም አጼ ምኒልክ የወሰኑ ጉዳይ ያለቀ መሆኑን እንዳረጋግጥልዎት ይፈልጋል ብለዋል። ከገንዘቡ ግማሹ በኢትዮጵያ ብር እንዲከፈለው በእኛ የተሰሩ፤ በዚህ መሠረት ገንዘብ ስለምንሰራለት የተከፈለን ኮሚሽን ያስመሥላል።» በማለት መዝግቧል።

ማርቲኒ ከሮማ ወደ ኤርትራ ከመመለሱ በፊት ዲሴምበር 27 ስለወሰኑ ጉዳይ ተጨማሪ ውል ከአጼ ምኒልክ ጋራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የጁላይ 10 ውል ለማሻሻል ረጅም ቴሌግራም ለቺኮዲኮላ ተልኳል። ለአጼ ምኒልክ የተሰጠው 5 ሚሊዮን ሊሬ ለ11 ዓመት የእኛ ያልሆኑ መሬቶች ይዘናቸው ስለነበረ ሳይከፈል የነበረብን የግብር ዕዳ ሂሳብ እንዲሁም ስለ ደብረቢዘን «ጉልቲ» መክፈል የነበረብን ዕዳ ሂሳብ መሆኑን ለመግለፅ ተጨማሪ ውል ማድረግ ያስፈልጋል። እኛ በምስጢር ልንይዘው ስለማንችል ጥሩ ዘዴ ነው። በዚሁ መሠረት የእኛ ፓርላማ ስለማይገባው ሳናስፈቅድ እንዳልገዛን በማስመሰል ምንሊክም በሹማምንቶቹ ፊት ጉዳዩ እንደማይገባቸው የሚያስመስሉ ሳያስፈቅድ እንዳልሸጠ ለማድረግ ይቻላል።

1. F.Martini : ibd Vol II p. 49
2. F.Martini : ibd Vol II p 64

# ምዕራፍ 6

## ኢትዮጵያ በቅኝ አገዛዝ ዘመን

## የኢጣሊያ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ማግኘት የነበራቸው ሚና

ኢጣሊያ በሀገራችን የቅኝ ግዛት እንድታገኝ ብዙ ጣልያኖች የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደውም ሆነ ሳይወዱ ወሣኝ ሚና ተጫውቷል ፣ ከእነሱ ውስጥም 1/ ጁስፐ ሳፐቶ 2/ ደ ያኮቢስ 3/ ካርዲናል ማሣያ ተከፋይነታቸው በምን ሁኔታ እንደነበር በዚህ በታች ባጭሩ እገልፃለሁ

### ሰፐቶ



ሚሲዮናዊ ሰፐቶ



ፕሮፌሰር ሰፔቶ

ከ17ኛ ምእተ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በየጊዜው በኢትዮጵያ የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ከፊሎቹ የተላኩት ሚሲዮናውያን በመንገድ እንዳሉ ሲሞቱ፣ ሌሎቹ ከሀገር ተባርረዋል ። ዓላማው ተሣክቶለት ለዘለቄታው የካቶሊክ ሃይማኖት ሲመሠርት የቻለው ሳፐቶ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊው አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ[1] እንደሚለው ሳፐቶ ሆነ ሌሎች ሚሲዮናውያን የተላኩት ከኢጣሊያ መንግሥት አልነበረም። ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው አንጋፋ ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ዘመን ኢጣሊያ ገና ነፃነቷን አላገኘችም ነበር። በመሠረቱ ሚሲዮናውያን የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋት የሚላኩ በአንድ

[1] ተክለፃዲቅ መኩሪያ: የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ ገጽ : 55



መንግሥታዊ አካል ሳይሆን በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ ብቻ ሲሆን፣ በሚላኩበት በታ ግን ትብብር የሚያደርጉት ከፈረንሳይ መንግሥት ወኪል ነበር።

በተጨማሪም ሳፐቶ ከባላባቶች ሱልጣኖች ጋር ተነጋግሮና ተስማምቶ ዓሰብን ለኢጣሊያ የገዛ እንደ መሆኑ መጠን፣ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት

መሥራች ተብሏል ። የሳፐቶ አጭር የሕይወት ታሪክና ያከናወናቸው ሥራዎች ከዚህ በታች አቀርባለሁ[1] ። ሳፐቶ በመጀመሪያ ጊዜ ከሀገሩ የወጣው ወደ ሶሪያ ነበር ። የተላከውም የላዛሪስት ሚስዮናዊ በመሆን ነበር። በ1837 ሳፐቶ ለጉብኝት ከሶሪያ ወደ ካይሮ ሄደ። በዚህ ጊዜ ሳፐቶ 26 ዓመት ዕድሜ ወጣት ነበር ። በዚህ ጊዜ አርናልዶና አንቷን ዳባዲ የተባሉ ፈረንሳውያን ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ አስበው ካይሮ ገብተው ስለነበር ፣ዓረብኛ ቋንቋ የሚያስተምራቸው አስተርጓሚም የሚሆናቸው ሰው ለመፈለግ ካይሮ ወደሚገኘው አንዱ የካቶሊክ ገዳም ሄደው ሃሣባቸው ሲገልፁላቸው ያለ ምንም ማወላወል ሳፐቶን ጠቆሟቸው ።3ቱ ሰዎች በዓላማቸው ተስማምተው ዝግጅታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግብፅን ለቀው ጂዳ የገቡ ፋብሪዋሪ 11 / 1838 ዓ ም ነበር። ማርች 3 / 1838 ዓ ም የትግሬይ ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ዓድዋ ደረሱ። ሳፐቶና አርናልዶ ዓድዋ ሲቀሩ አንቷን ግን የተላከበትን ተግባር ለመፈፀም ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ጁማ ጉዞውን በመቀጠል ከፋ ድረስ በመዝለቅ ሥራውን አጠናቀቀ። ወደ ጎንደር ሲመለስ ኢትዮጲያ ከግብፅ ወረራ ራሷን ለመከላከል እንድትችል የክርስትያን መንግስታት እርዳታ እንዲያደርጉላት በመጠየቅ አንድ ደብዳቤ ለፈረንሳይ ንጉሥ፣ ሌላ ደብዳቤ ለእንግሊዙዋ ንግሥት ከጎንደር ቤተ መንግሥት ሹሞች ተጽፎ እንዲያደርስላቸው ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ጉዞውን በመቀጠል ዓድዋ ደረሰ። ሳፐቶም በበኩሉ ተጨማሪ ሚሲዮናውያን ረዳት እንዲላኩለት በመጠየቅ ለሚመለከተው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሹሞች ደብዳቤ አዘጋጅቶ ስለነበር እንዲያደርስለት ለአንቷን በመስጠት ተሰናበተው። የሮም ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ደብዳቤ እንደደረሳቸው ከሚመለከታቸው ክፍሎች ተመካከረው ወዲያውኑ ደ ያኮቢስና ሞንቱዎሪ የተባሉ ሁለት ሚሲዮናውያን እንዲላኩ ስላደረጉ አክቶበር 1839 ዓ ም ወደ ኢትዮጵያ ደረሱ። ከሶስቱ ሚሲዮናውያን ደ ያኮቢስ አላፊ ሆነ፣ የሥራ ክፍፍልም ተደረገ።በዚህ መሠረት ደ ያኮቢስ ዓድዋ፣ ሞንቱዋሪ ጎንደር፣ ሳፐቶ ሸዋ፣ ተመድበው እንዲሠሩ ተደረገ። ሳፐቶ አመዳደቡን ቢቃወምም ትእዛዙን ለመፈፀም ብቻ ወደ ሸዋ ለመሄድ ጎንደር ደረሰ ። ነገር ግን በጠና ታሞ ወደ ዓድዋ ተመለሰ ። ሳፐቶ ምንም እንኳን ሀገሩንና ህዝቡን ከልብ የሚወድ ቢሆንም የተመደበበት ክፍለ ሀገር/ሸዋ/ ስላልወደደው፣ በበሽታም ምክንያት፣ ብዙ መጥፎ ወሬም ስለተወራበት ሀገሩን ለቆ ወደ ኤውሮጳ መመለስ ግድ ሆነበት። እንደገና ወደ ኢትዮጲያ ተመልሶ ሥራውን እንዲቀጥል ቢጠይቅም አልተፈቀደለትም ። ሳፐቶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዓላማ በቤተ ክርስቲያን አለቆች ታፍኖ ቢቀርም፣ በግሉ ግን በሕይወት እስካለ ድረስ ጥረቱ አላቋረጠም ። የሳፐቶ ዓላማ በመጀመሪያ የሀገሩን ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ባሀል ማጥናት ሲሆን የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋትም ከሀገሩ መሪ፣ ለምሣሌ የትግራይ ደጃዝማች ውቤ የሚሲዮናውያን የበላይ ጠባቂ

[1] G Giacchero G. Bisogni: Vita di Giuseppe Sapeto

ዓላማው ተሣክቶለት የደጃዝማች እንዲሆን ማድረግ ነበር።የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማው ተሣክቶለት የደጃዝማች ውቤ ወዳጅነት አትርፎ ነበር። የፈረንሳይ መንግስት ወደ ሩቅ ምሥራቅ የሚጓዙ የንግድ መርከቦች ማረፊያ ጣቢያ እና የንግድ መናኸሪያ የሚያገለግል በቀይ ባህር ወደ ኢትዮጵያ መግቢያዎች ወደብ ተስጥቶት የሚሲዮናውያንና የደጃዝማች ውቤ ወዳጅና የበላይ ጠባቂ እንዲሆን የማድረግ ግን የእንግሊዝ መንግስት የማይቋረጥ ተቃውሞ ያጋጥም ስለነበር፣ በቀላሉ የሚሳካ ነገር አልሆነም። ይህ በሐንጎሉ የነበረው ከግቡ ለማድረስ በግሉ የሞከረው በ1858 ዓ ም በሮም የፈረንሳይ አምባሳደር ለነበረው የፃፈው ረጅም ደብዳቤ ነበር።ሳፐቶ ከእለቆቹ ጋራ ያልተግባባበት ምክንያት በፖለቲካ ውስጥ በመግባቱ ነው ተብሎ ወቀሣ ተሰንዝሮበታል። ይህ ግን ዋናው ምክንያት ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም አለቃውም ቢሆን በባሰ ሁኔታ በፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ነበር። ሌላ የቢሰኝነት የሀሰት አሉባልታ ወሬም ተሰንዝሮበት ነበር። ነገር ግን ይኸም ቢሆን የስም ማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ከእውነት የራቀ መሆኑን ተረጋግጧል። ሳፐቶ ከእለቆቹ ጋር አለመግባባት የተፈጠረውና ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያበቃው ዋና ምክንያት ከአለቃው ጋር በትውልዳቸው፣ በክፍለ ሀገር የተለያዩ ስለሆኑ፣ የተፈጠረ አለመግባባትና፣ በአስተሳሰብም ነበረ፣ በዚህ ምክንያት ነው ቢባል የሚመስል ይሆናል።አለቃው ደ ያኮቢስ የደቡብ ኢጣሊያ ተወላጅ ነው። በኋላ ቀረነት የኢጣሊያ ክፍላተ ሀገሮች የመጨረሻ ደረጃ የያዘች ናት። ሳፐቶ ግን በሰሜን ምዕራብ የምትገኝ የሊጉሪያ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ነው። የሊጉሪያ ሕዝብ እረያን /ነጭ ዘር/አይደለም። በኤውሮጳ አረያኖች ከመስፈራቸው በፊት የነበሩ ከመጀመሪያዎቹ የኢጣሊያ ሰፋሪዎች አንዱ ነው።የኩሽ ወይም የሴም ዘር ሣይሆን እንደማይቀር ይገመታል።ሊጉሪያ በኢጣሊያ ውስጥ ያበረከተችውና የምታበረክተው አስተዋፅኦ በፖለቲካ፣ በኪነ ጥበብ፣ በሥነ ጽሁፍ፡ በእርሻ የምትገኝ ክፍለ ሀገር ናት። የሕዝቡም መዘተ አይደለም። ሊጉሪያ በባህር ዳርቻ የምትገኝ ክፍለ ሀገር ናት። የሕዝቡም ሙያ ባሕርተኛና መርከብ ሰሪ ነው። ኮለምበስ የሊጉሪያ ተወላጅ መሆኑን ብቻ መጥቀስ የሊጉሪያና የሳፐቶ ማንነት ሊያስረዳን ይችላል። ሳፐቶ ወደ ሸዋ ተመድቦ እንዲሰራ ሲታዘዝ ቅሬታ ያደረበት ራሱ በደብዳቤ እንደተገለፀው ሸዋ ከቀይ ባህር ብዙ ርቅት ስላለው ነው።ሊጉሪውያን ከባህር ኑሮ ተለይተው መኖር አይችሉም። ለሳፐቶ ይታየው የነበረ ቀይ ባህር እንደ ሊጉሪያ የመርከቦች መናኸሪያ እንዲሆን ለማድረግ፣ እንደ ኤውሮጳዊት ሀገር ፣በተለይ ካቶሊካዊት ሀገር: እንደ ፈረንሳይ አንድ ወደብ አግኝታ ለንግድ መርከቦቿ አገልግሎት እንዲሆናት እንዲሰጣት ነበር። ይህን በማሰቡ ግን ሃይማኖቱን በይበልጥ ለማስፋፋት እንጂ የሃይማኖት ጉዳይ ችላ ያለበት ጊዜ አልነበረም። ምክንያቱም እንደ ሳፐቶ አስተሳሰብ እንድ ካቶሊካዊት ሀገር በቀይ ባህር የአንድ ወደብ ባለቤት ከሆነች ለራሷ ተጠቅማ የሚሲዮናውያንን መብት ታስከብራለች።

## ሳፐቶና ሩሰል

ደጃዝማች ንጉሤ የትግራይ ገዥ በደ ያኮቢስ ምክር በመታገዝ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለመጫን ቴዎድሮስ ጋር ፍልሚያ

የሚያደርግበት ወቅት ነበር። እንግሊዛዊው ቆንሲል ፕላውድን Plounden አፄ ቴዎድሮስን ሲረዳ ሾሽን በያርድ Chauvin Beillard የተባለው ፈረንሳዊ ቆንስል በደ ያኮቢስ አማካኝነት ደጃዝማች ንጉሤን ይረዳ ነበር። የፈረንሳይ ቆንስልና ደ ያኮቢስ በሰጡት ምክር መሠረት ደጃዝማች ንጉሤ ወደ ናፖሊዮን 3ኛ የፈረንሳይ



ንጉሠ ነገሥት፣ ወደ የሮም ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ 9ኛ መልእክተኞችን ላከ ።አፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ከጫኑ 4 ዓመት ሆናት ነበር። ስለዚህ ቴዎድሮስን አስወግዶ ሌላ ንጉሠ ነገሥት በስልጣን ማውጣት የውጭ መንግሥት እርዳታ ካልታከለበት የማይቻል ስለሆነ መልእክተኞች የደጃዝማች ንጉሤ እና የደ ያኮቢስ ደብዳቤዎችን ይዘው የተላኩት የንጉሤ ዓላማና ተስፋ የንገሥ ነገሥት ዘውድ ስመጫን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ ስመጠየቅ ነበር።መልእክተኞቹ ኖሸምበር 1858 ዓ ም ከኢትዮጵያ ተነሱ። ጃንዋሪ1859 ዓ ም ሮም ገቡ ።በዚህ ጊዜ አስተርጓሚ የሚሆን 3 ቋንቋዎች ዓረቢኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ የሚያውቅ ሳፐቶ ብቻ ሆኖ ስለተገኘ፤ ወደ ርእስ ሊቃነ ጳጳሱ ተጠርቶ መጣ።መልእክተኞቹ ከርእስ ሊቃነ ጳጳሱ ተገናኙ። ነገር ግን ጳጳሱ የመልእክተኞቹ ዋና ትኩረት የጦር መሣሪያ እርዳታ ለማግኘት መሆኑን ስስተረዱ የሞቀ አቀባበል ሣያደርጉላቸው ቡራኬ ሰጥተው አሰናበቷቸው።መልእክተኞቹ ወደ ፈረንሳይ ሀገር አምርተው ፓሪስ ሲገቡ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው። ናፓሊን 3ኛም በታላቅ ስነ ሥርዓት እና ክብር ተቀብሎ አነጋገራቸው። ስጦታዎችም በሁሰቱም ወገኖች ተሰጣጡ። ሳፐቶም ከመልእክተኞቹ ጋር ተገናኝቶ ነበር ።መልእክተኞቹም በተደረገላቸው አቀባበል ተደስተው ነበር። ናፖሊዮን 3ኛ መልእክተኞቹ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ በሚያስናብትበት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ወደ ደጃዝማች ንጉሤ መልእክተኛ እንደሚላክ ቃል ገብቶ ነበር።መልእክተኞቹም በሮም በኩል ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።ሮም ሲደርሱ ከሳፐቶ ተለያይተው ተሰናበቱ። ከዚህም በመቀጠል ቀይ ባህር እንደደረሱ ይጓዙበት የነበረ መርከብ ሰጠመ፣ ከናፖሊዮን 3ኛ ለደጃዝማች ንጉሤ የሚሰጡ ስጦታዎች ሲሰጥሙ መልእክተኞቹ ግን ከመርከብ በደህና ወረዱ። ሆኖም በምድረ በዳ የእግር ጉዞ ስለገጠማቸው የመልክተኞቹ መሪ በውሃ ጥም ሞቶ የቀሩት ሀገሪቸው ደረሱ። ናፖሊዮን 3ኛ ከዚህ ቀደም ለኢትዮጵያውያን መልእክተኞች በገባላቸው ቃል መሠረት ለደጃዝማች ንጉሤ መልእክተኛ ለመላክ ወሰነ። ለዚህም የተመረጠው ሰው ሩሰል የሚባል ነበር። ኦክቶበር 13/1859 የመልእክተኞቹ መሪ ለመሆን የተመረጠበትና መመሪያዎች የያዘ ደብዳቤ ተሰጠው። ሳፐቶም አስተርጓሚ ሆኖ የፈረንሣይ መልእክተኞች አባል በመሆን እንዲሄድ ኦክቶበር 29/1859 አብሮ ሮም ነበረ። ገና ጉዞዋቸው ከመጀመሩ በፊት ሩሰል ስለ ሳፐቶ ሲጽፍ ተራ አስተርጓሚ ከማገልገል ሌላ መብት እንደሌለው ነበር። ሳፐቶ ግን በበኩሉ የሀገሩን ቋንቋው የሚያውቅ እሱ ብቻ ስለሆነ ልዩ ሥልጣን እንዲሰጠው ፈልጎ ነበር። ዲሴምበር 1859 ምፅዋ ሲደርሱ በአለፈው ጊዜ ወደ ፈረንሣይ ሄደው ከነበሩ መልእክቸኞቹ አንዱ አባ እምነቱ መልእክተኞቹን ተቀበሏቸው። ዲሴምበር 28

ቀን 1859 ከምፅዋ ተነስተው ጃንዋሪ 5/1860 ዓ ም ቆሐይቶ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ የሚገልፁ የሀንፃ ፍርስራሾች የሚገኙበት ታሪካዊ መንደር እንደደረሱ ከአቡነ ደ ያኮቢስ የተላከ አንድ ሰው ደጃዝማች ንጉሤ በአፄ ቴዎድሮስ ጦር የተከበበ ስለሆነ ሊቀበላቸው እንደማይችል ነገራቸውና ደ ያኮቢስ ወደ ሚገኝበት ወደ ሐላይ ሄደው እንግዶች በመሆን ተቀመጡ። ብዙ ሣይቆዩ

ግን ዘርአይ በተባለው በአከለጉዛይ የአፄ ቴዎድሮስ ወኪል በሚመራው ጦር እንግዶች የዓረፉበት መንደር ወይም ሐላይ ደርሶ እንደተከበቡ አወቁ። የተኩስ ልውውጥ ተደረገ ። ደ ያኮብስና ሳፐቶ ከሀገሩ ህዝብ ጋር በነበራቸው መግባባት ገንዘብም በመስጠት ደ ያኮብስና የ100 ብር መያዣ ሰጥተው ሐላይ ከመቃጠል፣ የሰው ደምም በከንቱ እንዳይፈስ አደረጉ። ጃንዋሪ1860 ሌሊት የፈረንሣይ መንግሥት መልክተኞች ከሐላይ ሸሽተው ወጡ። ምፅዋ እንደደረሱ ሩስል ባዶ እጁ ወደ ሀገሩ እንዳይመለስ ከደጃዝማች ንጉሤ ወኪል አባ እምነቱ አንድ ውል ተፈራረሙ። በስምምነቱ መሠረት ደጃዝማች ንጉሤ የዙላ ባህረ ሰላጤ ለፈረንሳይ ሲሰጥ የፈረንሣይ መንግሥት ከንጉሤ ጎን የሚሰለፉ የፈረንሣይ ወታደሮች ለመላክ ተስማምተው፣ የፈረንሣይ መልእክተኞች አሁን የቀራቸው ሌላ ተልእኳቸውን ማጠናቀቅ ነበረባቸው። ይኸውም መመሪያ በተሰጣቸው መሠረት ከምፅዋ ጀምረው የቀይ ባህር ምዕራባዊ የባህር ዳርቻ አፍሪካዊው ወደቦች አንድ በአንድ ማጥናት ነበር። ስለዚህ ወደ ደቡብ በማምራት በዶሉልን፣ አሰብን፣ ታጁራን፣ ዘይላን፣ አደንን እና ፔሪንን በማጥናት ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ይህ የቀይ ባህር ወደቦች ጥናታዊ ጉብኝት ለፈረንሣይ ምንም ጥቅም ያመጣላት አልነበረም። ነገር ግን በሩሰል ቸልተኝነትና በሰፐቶ ብልጥነት አሰብን ለኢጣሊያ ለመግዛት ጥንስስ ሃሳብ ለሳፐቶ ያደረበት በዚህ ጉብኝት ነበር። ምክንያቱም ኢጣሊያ አንድነቷን ለማግኘት የተቃረበችበት ነበር። ሩሰል በለአሰብ ጥሩ ወደብ ልትሆን የምትችል መሆንዋን በማስታወሻ ደብተሩ በሰፊው ጽፎ ነበረ። የሚጠጣ ንፁህ ውሃ እንዳላት መንደሮች እንዳላት፣ ለመርከቦች ማረፊያ ምቹ እንደሆነች በሚገባ መዝግቦ ጽፎ ነበር። ሳፐቶ ይህን ሁሉ እይቶ ነበር። ሁለቱ ሰዎች ከሮም ተነስተው እስከ ተመለሱ ድረስ አንድ ቀን ሣይስማሙ በጭቅጭቅ ነበር ጉዞዋቸውን የጨረሱት።በሳፐቶ አባባል ሩሰል ጣሊያኖችን አይወድም "ሩ" በሚል ስድብ ይንቃቸዋል፣ የፈረንሳይ እብሪተኝነት መንፈስ ያሣያል። "ሩ" በሚል ስድብ ይንቃቸዋል፣ የፈረንሳይ እብሪተኝነት መንፈስ ያሣያል፣ ከሱ በታች ያረገኛል ፣ ሀገሩን ይሳደባል፣ በተለይ እኔን አይወደኝም፣ ከሱ በታች ያረገኛል ፣ ሀገሩን ይሳደባል፣ በተለይ እኔን አይወደኝም፣ የማውቀው እኔው ነኝ፣ ስለዚህ ልዩ ክብር ሊሰጠኝ ይገባ ነበር እያለ ቅሬታውን ይገልፅ ነበረ። ሳፐቶ ለፈረንሣዮች ክብር አልሠራም ብሎ እየፎከረ ነበር ወደ ሀገሩ የተመለሰው። ሳፐቶ ከፍተኛ እውቀት ቢኖረውም ከሰው ጋር መስማማት ጠባይ ግን ይጎድለዋል። ከደ ያኮቢስና ከሩሶል ጋር ብቻ ሣይሆን አሰብ ለመግዛት ሲሄዱም ከመርከቡ አዛዥ ጋር በጭቅጭቅ ነበር ጉዞውን የጨረሰው።

# ሳፐቶና አሰብ

ጣሊያኖች ሳፐቶ አሰብን ለጣሊያኖች በመግዛቱ በኢትዮጵያ የጣሊያ ቅኝ ግዛት መስራች ብለው ያስታውሱታል። ነገር ግን ምን ጊዜም የኢትዮጲያ ግዛት መሬት ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት እንዲሆን ሃሣብ አቅርቦ አያውቅም ። ሳፐቶ ስለኢትዮጵያ ታሪክ ጥልቅ ጥናት ያካሄደ ሰው ከአክሱም ፣ አድዋ፣ ጎንደር፣ ላሊበላ፣ ጸሎት። ያገኛቸው የቤተ ክህነት ጽሑፎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግእዝ፣ ስለፍትሀ ነገሥት፣ ስለስንክሳር፣ ሲኖዶስ፣ ወዘተ ሰብስቦ በሀገሩ ቤተ መዘክር ወይም ሙዚዬም እንዲቀመጡ አድርጓል። በአዱሊስ የጠፋ ጽሁፍ አጥንቷል። ኢትዮጲያ የብዙ ሺህ ዓመት ታሪክ ያላት ሀገር መሆንዋን እጥንቶ መስክሯል። ብዙ መጽሐፎች ስለኢትዮጵያ ጽፏል።ሌሎች የሀገሩ



ሰዎች በዚሀ ሙያ ተሰማርተው ጥናት እንዲያደርጉ ተማጽኗል። በትምህርት ደረጃ ከሚሲዮናውያን መካል ከሳፐቶ ጋራ የሚወዳደሩት ወይም የሚበልጡት እንደኩልቦ የመሳሰሉት ፈረንሣውያን ሚሲዮናውያን ብቻ ናቸው። ፈረንሣውያን ከተባረሩት ከ1896 ዓ ም ጀምሮ ሆን ተብሎ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ምሁራን ሚሲዮናውያን አልተላኩም። በዚህም የተነሳ የሀገሩ ተወላጆች በትምህርት የበለፀጉ ሊገኙ አልተቻለም። ሳፐቶ ከፈረንሣይ መልእክተናች ጋር ሆኖ በቀይ ባህር ያደረገው ጉዞ እንደተመለሰ ለጥቂት ጊዜ በፈረንሳይ ብሔራዊ ቤተ መፃህፍት ሥራ ጀምሮ ነበር።በ ኢትዮጵያ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ለሚሲዮናውያን አገልግሎት የሚሆን ቅዳሴ በማዘጋጀት ላይ እንዳለ ይከፈለው የነበረው ደሞዝ ከቤተ ክህነት ስለተቋረጠበት በ51 ዓመት ዕድሜው በ1862 ዓ ም ከቄስነት ሙያው በመልቀቅ ሥራ ለመጠየቅ ባቀረባቸው ማመልከቻዎች መሠረት፣ በኢጣሊያ መንግሥት የአርሻ ሚኒስቴር ስር ሥራ አገኘ። በ1864 ዓ ም በዩኒቨርስቲ የዐረብኛ ቋንቋ አስተማሪ ፕሮፌሰር ሆኖ ተሾመ። ሳፐቶ ከአስተማሪነቱ ሥራ ጎን ለጎን በነበረው የግል ስሜት ተነሳስቶ የስዌዝ ካናል ተሠርቶ ሲያልቅ ለኢጣሊያ ንግድ ስለሚያስገኘው ጥቅም ለጣሊያ ነጋዴዎች ለኢጣሊያ መንግሥት በልዩ ልዩ መንገድ ቅስቀሳ ያደርግ ነበር። በሲዌዝ ካናል ንግድ ሲጀምር የጣሊያ መርከቦች የሚያርፉበት አንድ የንግድ መናኸሪያ የሸቀጣ ሸቀጥና የነዳጅ ወይም ከሰል ማእድን መጋዘን፣ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ለሚመላለሱ መርከቦች ማረፊያ የሚያገለግል ወደብ በቀይ ባህር ማግኘት ከፍተኛ ጠቃሚነት እንዳለው ሣይሰለች ይቀሰቅስ ነበር። በዚሁ ጊዜ በ1865 ዓ ም ኢጣሊያና የሲዌዝ ካናል በሚል አርእስት አንድ መጽሐፍ ደርሷል። ከ1865 ዓ ም እስከ 1869ዓ ም ድረስ በለዚህ ጉዳይ ሣያቋርጥ ማመልከቻዎች ለውጭ ጉዳይ፣ ለባህር ንግድ ፣ ለእርሻ፣ ለኢንዱስትሪና ንግድ ሚኒስቴሮች፣ እንዲሁም ለታላላቅ ነጋዴዎች፣ ለምሁራን ሲጽፍ ቆይቶ ነበር። በ1869 ዓ .ም ግን የሱዌዝ ቦይ የሚከፈትበት ዓመት ስለ ነበረ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ጥረቱን በማጠናከር ሜይ 1869 ዓ ም አንድ ደብዳቤ

ለእርሻ ሚኒስትር ለነበረ ሚንጌቲ (Minghetti) ፃፈ። በደብዳቤው የመረጣቸው ቦታዎችንም ጠቅሶ ጽፎ ነበር። እነሱም 1ኛ/ሐመራ ከቀይ ባህር በስተምስራቅ በእስያ የአንድ ወዳጁ የሆነ ሼክ ንብረት ስለሆነች በ14.000 ብር እንዲሸጥለት ተስማምቶ ስለ ነበር 2ኛ/ ዳመራ ከሐመራ ፊት ለፊት የምትገኘው በምሥራቃዊ ቀይ ባህር በአፍሪካ ምድር። ይህ ሁሉ ለማድረግም ከእሱ የበለጠ ሀገሩን የሚያውቅ ሰው ስለሌለ ኃላፊነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር። አራት ወር ጠብቆ መልስ በላላገኘ ሰፕቴምበር 1869 ዓ ም ለጠቅላይ ሚኒስትር መናብሬያ ቢፅፍ አሁንም እንደማይሆንለት ስለተረዳ ተስፋ በመቁረጥ ጥረቱን ከማቋረጡ በፊት የመጨረሻ ዕድሉ ለመሞከር እስቦ ለኢጣሊያ ንጉሥ ለነበረው ለቪክቶሪዮ አማኑኤል ሁለተኛ ደብዳቤ በመፃፍ ለንጉሡ ቅርብ የነበረ ሰው አማይቶ በጉዳዮ ስላተስማሙበትና ስለወደደው ከንጉሡ ትእዛዝ አስጥልሃለው ፀማልት በማግስቱ በጠቅላይ ሚኒስትር በኩል ጉዳዮ እንደሚያልቅ ተነገረው። በተባለው ቀን ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ሄደ ጥያቄው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ተነገረው። በዚህ ዓይነት ሳፐቶ የረጅም ጊዜ ምኞቱ ወደ ተግባር የሚውልበት

ጊዜ ደረሰ። 14.000 ብር በኢጣሊያ 100.000/መቶ ሺህ ሊሬ/ ስለተፈቀደ በታውን አድሚራል አክቶን ፕሮፌሰር ሳፐቶን ይዞ እንዲሄድ ተወስና ሳፐቶና የመምረጥ ጉዳይ የቴክኒክ ነገር ስለሆነ ኃላፊነቱን ለአክቶን ተሰጠው። ሳፐቶና አክቶን አክቶበር 1869 ዓ ም ከኢጣሊያ ተነሱ። ኖቬምበር 17 የሲዊዝ ቦይ የሚመረቅበት ቀን ነበር።ሳፐቶና አክቶን ከኢጣሊያ ሲነሱ የተነገራቸው ግዥው በኢጣሊያ መንግሥት ስም እንዲሆን ሲሆን በጉዞ እንዳሉ ግን የኢጣሊያ መንግሥት ግዥው ለጊዜው በባለመርከቡ ሩባቲና ኩባንያ ስም እንዲሆን ተስማምተው ነበር። ኖቬምበር 6 ቀን ሳፐቶና አክቶን ኤደን ገቡ። ከኤደን ሶስት ጀምረው በምሥራቅና በምእራብ የባህር ዳርቻዎች እየፈተሹ መጥተው ወደቦች በልዩ ልዩ ምክንያት እንደማይሆኑዋቸው አረጋግጠው ኖቬምበር 13 ቀን 1869 ዓ ም አሰብ ደረሱ። በታውን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ በማግስቱም ውል ረገድ ቦታው ለፈለጉት አገልግሎት ተስማሚ መሆኑን ስላመኑበት የማጁ ሆኑ ያ የመሬት ባለንብረት ከሆኑት ከወንድማማቾቹ ሱልጣን ኢብርሃም በን አሕመድና ከሱልጣን ሀሰን በን አህመድ ንግግር ተጀምሮ ስድስት ሺህ ብር ( ማሪያ ትሬዛ ) በአሰብ የሚገኘው ትንሽ መሬት ለመግዛት ተስማሙ። ለዚህም 250 ብር በመቶ ቀናት ቀብድ ተሰጥቶዋቸው በዲሴምበር 3 ቀን 1869 ዓ ም ጀምሮ ከአሰብ ፊት ለፊት ውስጥ ቀረው ገንዘብ ብር 5750 ለመስጠት ተስማምተው ስለአገኙት የሚገኙ አንዳንድ ደሴቶችም ከአሰብ ጋር ለማቀላቀል አስፈላጊ ሆኖ ከኢጣሊያ ሲመለሱ ከደሴቶቹ ባለቤት የሆነው ሌላ ሱልጣን ለመነጋገር እቅድ አውጥተው ወደ ሀገራቸው ወደ ኢጣሊያ ተመለሱ። መቶ ቀናት ከማለፋቸው በፊት ገንዘቡን ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ ከጨረሰበት በኋላ ግጁውም የሚከናወነው ሌሎች የአውሮጳ ሀገሮች እንደሚያደርጉት

ሁሉ በመንግሥት ስም ሣይሆን በሩባቲና ኩባንያ ስም እንዲሆን የተደረገ መሆኑን ለሳፐቶ ሲነገረው ከመንግሥት ነፃ አገልግሎት ወደ እንደ ኩባንያ ነፃ አገልግሎት በመዛወሬ "መታሞርፎዚስ" ለውጥ ማድረጊ የሚያሣዝነኝ አይደለም ብሎ ከአሌዘ በኋ? ፌብርዋሪ ጉዞውን ወደ አሰብ ቀጠለ። ማርች 9ቀን 1870 ዓ ም አሰብ ደረሱ። መቶ ቀናት ሊያልቅ ሶስት ቀን ይቀረው ነበር። ጣሊያኖች ከመርከባቸው ነዳጅ /ከሰል ማዕድን/ እና ሌላ ቁሣቁስ ማራገፍ ሲጀምሩ ሳፐቶ ለመግዛት ከተዋዋለው የባህር ዳርቻ ውጭ አብደላህ ሻሂም የተባለው ሱልጣን ንብረት በሆነው መሬት በማራገፋቸው ኢብራሂምና ሀሰን ተቋውሞዋቸውን አሰሙ። ሱልጣን አብደላ ሻሂም እንደ ሌሎች ሱልጣኖች መሬቱን ለመሸጥ ፍላጎት ነበረው ጣልያኖቹም ለአሰብ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት መሬቱን ለመግዛት ፈቃደኞች ነበሩ። ስለ ዋጋው የተፈጠረው ልዩነት ብቻ መነጋገር ጀመሩ። ሱልጣን አብደላህ ሻሂም ለሌሎቹ ሱለጣኖች እንደተከፈላቸው 6000 ይከፈለኝ ብሎ ጠይቆ ነበር። በአንድ ቀን ለ10 ሰዓታት ሲከራከሩ ውለው ስላልተስማሙ የሚያስማማቸው ከሱልጣኑ ልዩ ወዳጅነት ያለው ተፈልጎ 210 ብር የደላላነት ተከፍሎት ወደ ስምምነት ሊደርሱ ችላል። በስምምነቱ መሠረት 250 ብር ለቀብድ ከተከፈለው ገንዘብ ሌላ የፊተኛው ውል ተሰርዞ ሦስቱ ሱልጣኖች እኩል የሚከፋፈሉት 8100 ብር ሳፐቶ ሲከፍላቸው የሩባቲና ኩባንያ ወኪያውን ከራስ ሉማህ አላህ ተብሎ ከሚጠራው የባህር ዳርቻ እስከ ጋንጋ ተራራ ድረስ



ያለውን መሬት እንዲረከብ ተስማምተው ተፈራረሙ የኢጣሊያ ባንዲራ ተውለበለበ 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ።

አሁን የቀረው ነገር ከአሰብ ፊት ለፊት ያሉት አንዳንድ ደሴቶች ዋና ዋናዎቹ ለአሰብ ወደብ አስፈላጊ ስለሆኑ ጣሊያኖች ለማጠቃለል ስላሰቡ የደሴቶቹ ባለቤት የራሄይታ ሱልጣን ብርሀን ስለነበር ሳፐቶ ወደ ራሂታ ሂዶ ከሱልጣኑ ከተነጋገረ በኋላ በቀላሉ ሊስማሙ ችሏል። ሱልጣን ብርሃን የጠየቃቸው ነገሮች የሚከተሉት ነበሩ።1ኛ /ሱልጣን መሆኑን በኢጣሊያ መንግሥት በደፋ አዲታወቅለት 2/ከቱርክና ከግብፅ መንግሥት በቀል የኢጣሊያ መንግሥት እንዲጠብቀው 3ኛ በኪራይ መልክ ደሴቶችን ለሩባቲና ኩባንያ ለመስጠት ሲስማማ 100ብር በዓመት የ10ዓመት አስቀድሞ እንዲከፈለው የሚሉ ነበሩ። ነገር ግን ውሉ ሲፈራረሙ ሳፐቶ የከፈለው 100ብር የአንድ ዓመት ብቻ ነበር። ማርች 20ቀን ውሎችን በሙሉ ተጠናቅው ነበር። ሆኖም ሳፐቶ ለወደቡ የሚያስፈልጉ አንዳንድ ነገሮችን ለማከናወን እስከ አፕሪል 25አሰብ ቆይቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ።

ሳፐቶ በ1870 ዓ ም ሀገሩ ሲመለስ ጥሩ አቀባበል የተደረገለት በአነስተኛ ወገን ብቻ ነበር። አብዛኛው ጣልያኖች በማጥላላት ነበር የተቀበሉት። አብዛኛዎቹ የኢጣላያ ጋዜጠኞች፣ መጽሔቶችና የፖለቲካ ሰዎች አሰብ የተቃጠለ ሀገር ነው ሙቀቱም ኃይለኛ በመሆኑ ሰው ሲኖርበት አይችልም እፅዋት አይበቅሉበትም ምድረ በዳ ነው፣የሚጠጣ ውሀ የለውም ወዘተ እያሉ ይፅፉ

ነበር። እንዲያጣራ በመንግሥት የተላከ ኮሚሽየንም ይህንኑ ነው ያረጋገጠው። ሳፐቶ ግን የአሰብን ጠቃሚነት በስብሰባም በጋዜጦችም በመጽሔቶችም ለሀገሩ ህዝብና መንግሥት ለማስረዳት ሣያቋርጥ ለ10ዓመት ተከራክሮዋል ። በመጨረሻ ግን የኢጣሊያ መንግሥት የአሰብን ጠቃሚነት እየተረዳው ስለሄደ አክቶበር 22ቀን 1979ዓ ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረ ደ አምዛጋ ለሳፐቶ እንደ ደብዳቤ ጽፎ ወደ ሮም እንዲመጣ ጠራው። አሰብ 10ዓመት ተረስቶ ከቆየ በኋላ የኢጣሊያ መንግሥት ከሩባቲና ኩባንያ ተረክቦ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት በሚል ስያሜ እንድትስተዳደር ለማወጅ አስቦ ነበር። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ከ10ዓመት በፊት ሳፐቶ አሰብ ፊት ለፊት የሚገኙ ደሴቶች ከአሰብ ጋራ እንዲቀላቀሉ ከሱልጣን ብርሃን ጋራ ጀምሮት የነበረ ንግግር ወደ ፍጻሜ ለማድረስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሳፐቶ በጦር መርከቦች ታጅቦ በ1879 ዓ ም ወደ አሰብ እንዲላክ ተደርጎ ገና ዕለት ክሪስትማርስ 1879ዓ ም አሰብ ደረሱ። ዲሴምበር 29 ቀን 1879 ዓ ም ሳፐቶ ወደ ራሄይታ ሄዶ ከብርሀን ጋራ ተገናኙ። ብርሃን ሃሣቡ ሣይቀየር ለ10 ዓመታት መቆየቱ ጣልያኖች በገንዘብም ማነስ እየገረማቸው ተደሰቱ። የ10ዓመት ሂሣብም ከፈሉት፡ ከ10ዓመት በፊት በአሰብ ተሰርተው የነበሩ አንዳንድ ነገሮች ጣልያኖች በሙሉ ፈራርሰው ነበር ያገኙዋቸው። ለሁለት ወር ተኩል ቤቶቹን የመሥራት፣ የሚጠጣ ውሃ ምንጮችን በመቆፈር ወዘተ ካሳለፉ በኋላ ማርች 15 ቀን 1880 ዓ ም ሳፐቶና ብርሃን ውል ተፈራረሙ።

ከዚህ በኋላ በሱልጣን ብርሀን ጠያቂነት ሳፐቶና ብርሃን አንድ ልዩ ውል ስለ ሱልጣን ብርሃን ለኢጣሊያ ንጉሥ ኡምበርቶ ተገዥነት መሆን ተፈራርመዋል። በዚህ ውል መሠረት ሱልጣን ብርሃን ማንም ሣያስገድደው በፈቃዱ ለኢጣሊያ ንጉሥ አገልጋይ፣ አሽከር፣ ተገዥ ስለሆነ በቅዱስ ቁርዓን ይምላል።1ኛለሩባቲና ኩባንያና ለማንኛውም የሚከተሉት ነገሮች ለመፈጸም ምክንያት ኢጣሊያዊ በሚያዝበት መሬት ለመኖርም ሆነ ለማለፍ በማንኛውም ለመፍቀድ 2ኛ/ባለው ኃይል በአሰብ የኢጣሊያ ይዞታ ከማንኛውም ጠላት መከላከል 3/በአሰብ የኢጣሊያ ይዞታ ዓላማ በአዋሳ በኩል ከኢትዮጲያ ጋራ ንግድ ለማስፋፋት ስለሆነ የመገናኛ መንገድ ከማንኛውም ወረበላ ነፃ እንዲሆን መከላከል። 4ኛ ሱልጣኑ በዐሰብ የሚገኝ የኢጣሊያ ባለሥልጣን ሳያስፈቅድ መሬት ለማንም እንዳይሸጥ እንዲሁም ሱልጣኑ በጠየቀው መሠረት በመሬቱ የኢጣሊያ ጥገኤራ እንዲያውለብልብ። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አገልግሎቶች ለኢጣሊያ መንግሥት የሚሰጥ ስለሆነ ሱልጣን ብርሃን የኢጣሊያ መንግሥት ሠራተኛ እንደመሆኑ መጠን ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄውን ለማስተላለፍ ተቀብላል። አገልጋይ ሆና እንዲታወቅና ለአንድ ተገዥ አሽከር ሊሰጠው የሚገባ ክፍያ ከኢጣልያ መንግሥት እንዲያገኝ ሲጠይቅ ሳፐቶ የሩባቲና ኩባንያ ወኪል

የመጨረሻ ውል በሱልጣን ኢብራሂም ጠያቂነት ነበር። ሱልጣኑ ጣሊያኖች ጥቢቃ የሚያደርጉለት ከሆነና የኢጣሊያ ንጉሥ ተገዥ የበታች ሱልጣን መሆኑን ከታወቀለት ከሳናቦር ደሴትና ከራስ ሉማህ እስከ ኢድ ያለው መሬት ለኢጣሊያ

በስጦታ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ጠይቆ ነበር። ጣሊያኖች ግን የእንግሊዝና የግብፅ የሚጀቀር ተቃውሞ በመፍራት ለመንግሥታቸውም ፖለቲካዊ ችግር እንዳይፈጥሩ በማሰብ እንዳለፉ ውሎች ሳናቦር ደሴት ከራስ ዳርማር እስከ ራስ ሉማህ ያለው የባህር ዳርቻ ብቻ የንግድ ውል ለማድረግ ተስማምተው ተፈራርመው። በአጠቃላይ ሲታይ ሳፐቶ ከኢጣሊያ ህዝብና መንግሥት ፍላጎት ውጭ የአሰብ ግዢ ቀያስና ገዢ ነው። ሳፐቶ አሰብን የገዛው ለኢጣላያ የንግድ መርከቦች ማረፊያ እንድትሆን ከአካባቢው ሀገሮች ኢትዮጵያም ጭምር የንግድ መናኸሪያ እንድትሆን ብቻ ነበር። ይህ ምኞቱና ሃሣቡ በየአጋጣሚ ደጋግሞ የተገለፀው ጉዳይ ነው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የዕድሜው ዘመን የሳፐቶ አስተሳሰብ የአንድ ሊጉሪያዊ አስተሳሰብ ነው፣ ይኸውም የባህር ንግድ ማስፋፋት ነው። አሰብ የእስረኞች ማከማቻ ወይንም የቅኝ ግዛት ማስፋፊያ ጣቢያ ማድረግ ከዓላማው ውጪ ስለ ነበረ ይቃወመው ነበር። ሊጉሪያ ከሎምበስና ሌሎች ባህረተኞች ያፈራች ከፍለ ሀገር ናት።እንደ ሳፐቶ አስተሳሰብ አሰብ የእስረኞች ማረፊያ ቦታ ማድረግ እንደ ኢትዮጵያውያንና ዐረቦች የመሳሰሉት ኩሩና ተጠራጣሪ ህዝቦች ፊታቸውን እንዲያዞሩብን ማድረግ፣ እንግሊዞችም በሚያንገፈግፍ ሥራችን ተደስተው መሣቂያ ያደርጉን ነበር። ሳፐቶ ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ተመኝቶ አያውቅም ፣ አሰብም በኢትዮጲያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ማስፋፊያ ያደረገችው አስተዋጽኦ በጣም አነስተኛ ነው።

የኢጣሊያ መንግሥት የሳፐቶ አስተሳሰብን በመከተል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1881ዓ ም ለሾመው ለአሰብ አስተዳደሪ የሰጠው መመሪያ እንደሚከተለው ነበር። የኢጣሊያ መንግሥት ፍላጎት አሰብ 1ኛ ለውትድርና አገልግሎት 2ኛ/ ለእስር ቤት ቦታ እንድታገለግል አይደለም 3ኛ አሰብ ለንግድ አገልግሎት ብቻ



ለማዋል ጥረት እንዲያደርግ በመግለፅ አደራ እያለ ለዚህም 3 ነጥቦች ለምሣሌነት ተጠቅሰው ነበር። 1ኛ/ነዳጅ /ከሰል ማዕድን/ እና ሌሎች ለመርከቦች አገልግሎት የሚውሉ ቁሣቁሶች ማከማቻ 2ኛ ከአውሮጳ በተለይ ከኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ ወይንም ከኢትዮጵያ ወደ አውሮጳ የሚላኩ እቃዎች የንግድ ማእከል ማድረግ 3ኛ ከዓረብ ሀገሮች ወደ አውሮጳ ወይንም ከአውሮጳ ወደ ዐረብ ሀገሮች የሚደረግ የማስመጣትና መላክ የንግድ እንቅስቃሴ ማእከል እንድትሆን ነበር። የኢጣሊያ መንግሥት ተወካይ ብራንካ ፣ ከዚህ በላይ የተገለፀው መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ፌንሩዋሪ1881 ዓ ም ሥራውን ለመጀመር አሰብ እስከሚገባ ድረስ ሳፐቶ የሚያሰቃየው የነበረ ህመም ተጽቁሞ አሰብ ቆይቶ በዚህ ወር ግን እያዘነ ወደ ኢጣሊያ ተመለሰ።

አሰብ በኢጣሊያ ፓርላማ ፀድቆ የኢጣሊያ ቅኛ ግዛት የሆነችው ጁን 30 ቀን 1882 ዓ ም ሲሆን ከጠቅላላ የፓርላማ አባሎች 239ውስጥ፣ 147 ረቂቁን ሲቀበሉት 72 ተቃውመውታል።

ሳፐቶ ወደ ኢጣሊያ እንደተመለሰ በዩኒቨርሲቲ የዓረብኛ ቋንቋ አስተማሪ ፕሮፌሰር በመሆን የቀድሞ ሥራውን ቀጥሎ ነበር። በ1891 ዓ ም ሳፐቶ በ8(

ዓመት ዕድሜው ታሞ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ በነበረበት ጊዜ ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ ግዛቷን ማስፋፋት በቀጠለችበት ጊዜ በኢትዮጵያ ኢጣሊያ የምትከተለው ፓሊሲ ሃሣቡ እንዲገለጽ ሲጠየቅ በቁጭት የሚሰጣቸው መልሶች መልስ አልባ ከጥያቄው ውጭ፣ ሌላ ጊዜም ስለ ኤርትራ ጥልቀት የሌላቸው የተቃዊሚዎች አስተያየቶች እንዲሁም ስሜታዊ የሆነ የተጋነኑ ከደጋፊዎች የተሰነዘሩ ሃሣቦች አስተያየቱን እንዲሰጥ ተጠይቆ ፈቃደኛ ሣይሆን ቀርቷል። እንደዚሁም ዳኑንሲዮ የተባለው ታዋቂ ኢጣሊያዊ የስነ ጽሑፍ ሰው በዶጋሊ ስለወደቁ የኢጣሊያ ወታደሮች አጥላልቶ ስለ ደረሰው ጽሑፍ ሃሣቡን እንዲገለጽ ተጠይቆ ሳፐቶ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርታል ። የዚህ ዓይነት ዝምታ ከተቃውሞ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ከታገልኩበት ዓላማ ውጭ ነው ብሎ እንደመለሰ ይቆጠራል።

በአጠቃላይ የአሰብ ግዢ የተከናወነው በ5 ጊዜያት ነበር። 1ኛ/ ውል ኖቬምበር 13ቀን 1969 ዓ ም ካንጋ ተራራ እስከ ሉማህ ግዢ የተካሄደበት ፣ገዢ ቢኖር ጁሰፔ ሳፐቶ፣ ሻጮች ሀሰን ቤን አህመድ ኢብራሂም ቤን አህመድ፣ እማኞች መሐመድ አብዲ 2 አህመድ ዓሊ 3 ሰይድ አዋድህ፣ ፀሐፊ አብደላ ቤን ዱራን የተከፈለው ገንዘብ 250 ብር ቀብድ ብቻ።

2ኛ/ ውል ማርች 11ቀን 1870 ዓ ም ከጋንጋ ተራራ ጀምሮ እስከ ባሀር አላሉ የተባለው የባህር ዳርቻና ሉማህ፣ ግዢ የተካሄደበት። ገጅዎች በሩባቲና ኩባንያ ስም ቢኖር ጁሰፐ ሳፐቶ እንድሪያ ቡዘሊና ሻጮች 1/ሱልጣን አብደላ ሻሂም 2/ ሱልጣን ሀሰን ቤን አህመድ 3/ ሱልጣን ኢብራሂም ቤን አህመድ የተከፈለው ገንዘብ 8100 ፣ምሥክሮች1/ አብደላህ ኢደን ፣2 አሊ ከሊ፣3/አራቢዮ አንቲኖሪ 4 ካርሎ ግሮንዶና

3ኛ/ ውል ዲሴምበር 30 ቀን 1879 ዓ ም ከ10 ዓመት በፊት ሳፐቶ ተነጋግሮ ተቋርጦ ቆይቶ የነበረ የሽያጭ ውል ከአሰብ ፊት ለፊት የሚገኙ የዳርማርኪዩ ደሴቶች ከራሄይታ ሱልጣን ጋራ የተደረገው ውል ግዢ ሲኖር ጁሰፐ ሳፐቶ ምስክሮች1ኛ ሻጭ ሱልጣን በረሀን የተከፈለው ገንዘብ 1000 /አንደ ሺህ/፣ ደሊቶች ከራሄይታ ሱልጣን በረሀን የተከፈለው ገንዘብ 1000 /አንደ ሺህ/፣ ምስክሮች1ኛ /አስማን አብደላ ዱራን 2/ ጂያኮሞ ዶሪያ የጀርጆ ልጅ 3/ ኢደዋርዶ በካሪ፣

4ኛ/ ውል ማርች 15 ቀን 1880 ዓ ም ዓሰብ ፊት ለፊት ከራስ ሴንቲያር እስከ ቢዶሉል ሌማ የሚገኙ ደሴቶች በሙሉ አንድም ሣይቀር፣ በተጨማሪ ከራስ ሲንቲያሮ እስከ ራስ ሊማ የሚገኙ የባህር ዳርቻዎች እስከ 4 ማይል ስፋት። ገጅ ፕሮፌሰር ካቫሊየር ጁሰፐ ሳፐቶ፣ ሻጭ ብርሀን በን መሐመድ የራሄይታ ሱልጣን፣ የተከፈለው ገንዘብ 13.000 /አስራ ሶስት ሺህ ብር / ማሪያ ትሬዛ እማኞች1/ ጁሰፐ በንንፌልድ 2/ ጆሊየቲ 3/ ሰይድ ኦሪዳን። የመርከቡ አዛዝ ካርሎ ደ አመዛን ውሉን በፊርማው አረጋግጧል።

5ኛ/ ውል መይ 15 ቀን 1880 ዓ ም የሰናቦር ደሴት እንዲሁም ከራስ ዳርማር እስከ ሉማህ ያለው የባህር ዳርቻ መሬት ስፋቱ 6 ማይል ግዢ ተካሄዷል። ገዢ ፕሮፌሰር ካቫልየር ጁሰፐ ሳፐቶ እማኞች1/ አብደላ መሐመድ 2/ ሰይድ ኦሪዳን

3/ ጁሰፐ ማሪያ ጁሊየቲ 4/ጁህዳር የመርከቡ አዛዝ ካርሎ ዳ አመዛን ውሉን በፊርማው አረጋግጧል።

ሳፐቶ ብዙ ጥንታዊ ጽሑፎች አግኝቷል፣ የኢትዮጵያ በጣም ጥንታዊ የተባለው ፀሎት በሚባለው መንደር በሐማሴን ነበር። ጽሕፈቱ በጣም ጥንታዊ መሆን የተነሳ የተፃፈው በ11ኛው መቶ ክ/ዘመን የሚገመት ነው።በ1878 የምሥራቅ አገሮች ስልጣኔ ምሁራን በፊሬንሴ በተደረገው ጉባኤ ለትርኢት ቀርቦ ነበረ።

2ኛ/ አርጋኖን ለእግዝአብሔርና ለማርያም ውዳሴና ፀሎት የያዘ መፅሐፍ ግልባጥ በደብዳቤ የተሰበሰቡ 6 በበርሊን ይገኛሉ፣

3ኛ/ መፅሐፈ ኪዳን ስለ ኢትዮጵያ ቅዳሴ ሥነ ሥርአት አንድ በዳባዲ አንድ በበርሊን ይገኛል፣

4ኛ/ ቅዳሴ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ጥንታዊ ጽሑፍ በ1878 በፊሬንሴ የተደረገው ጉባኤ ቀርቦ ነበረ፣

5ኛ/ አርጋኖን የማርያም ውዳሴና ፀሎት ጥንታዊ ጽሑፍ አንድ ግልባጥ በበርሊን 4 በፓሪስ ይገኛል፣

6ኛ/ ዜማ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

7እና 8/ ልዮ ልዮ የትዱሳን ታሪኮች ፀሎቶች የያዘ ለየእንዳንድ የዓመት ቀናት ከስንክሳር የተወሰደ አንድ ግልባጭ በፓሪስ ይገኛል

9/ የዮሐንስ ወንጌ



10/ መልእክተ ሐዋርያት



S. ECC. MONS. CATTANEO TRA I GIOVANI CATTOLICI

## ሞንሲኞር ደ ያኮቢስ(1)



የካቶሊክ ሚሲዮናውያን የወንጌል ስብከት ከፈረንሳይ የቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር በቅንጅት ነበር የሚሰሩት። ፈረንሳይ ለሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የበኩር ልጅ ተብላ ትጠራ ነበር። ፈረንሳይ በመላው ዓለም የካቶሊኮች ጠባቂ ተብላ ትታወቅ ነበር። ሚሲዮናውያንም ሮማዊት መስቀል ፈረንሳዊት ባንዴራ እንግበው ይሰራሉ ይባሉ ነበር። ሁሉም ግን ለጥቅማቸው ብቻ ነበረ የሚሰሩት ።የፈረንሳይ መንግሥት ሥራ ለራሱ ፓለቲካዊ ጥቅም እንጂ ለሚሲዮናውያን ዓላማ ደንታ እንደሌው [1] ደ ያኮቢስ ለአለቃው በ18/1845 ዓ ም በፃፈው ደብዳቤ ያስረዳል። በዚሁ ደብዳቤ እንደገለፀው ደጉቲን የተባለው በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል በኢትዮጵያ ለሚገኙ ለካቶሊክ ሚሲዮናውያን ተብሎ ይላክ የነበረው ገንዘብ ለግል ጥቅም ያውለው እንደነበረ፣ ይነግድበት እንደነበረ ፅፈዋል። አሁን በመጨረሻ ከተላከው ገንዘብ 1.300 ብር 800ብቻ እንደደረሰውና ከ1841 ጀምሮ ከተላከው 60.0000 ብር 30.400 ብር ብቻ

[1] 1)Arata Salvatore: Vita Del Beato Giustino De Jacobis

እንደሰጠው ገልጸ ፅፏል። ከ1848 ዓ ም በኋላ በደጉቲን ቦታ የተተኩ ቆንሲሎች ከደጉቲን የተሻሉ አልነበሩም። ሀ/ ሮላድ የተባለ ካቶሊክ አልነበረም ሰ/ ፑዋ የተባለው ከ1850 እስከ 1856 የነበረው ሙስሊም ነበር ሐ/ ደሰይ ሉተራን ነበር። ደ ያኮቢስ ስራ ሲጀምር ሚሲዮኑ በሳፔቶ ተቋቁሞ ስለነበር ችግር አላጋጠመውም።ደ ያኮቢስ ኦክቶበር 13/1839 ዓ ም ምፅዋ ገባ፣ በ29 ዓድዋ ገባ ከጥቂት ቀን በኋላ ከትግራይ ገዥ የነበረ ከደጃዝማች ውቤ ተዋወቀ ስጦታም ሰጠው ከስጦታዎቹ አንዱ ደጃዝማች ውቤ የሚወደው የማርያም ስእል ነበር። ይህ ስእል ዓድዋ የሚገኘው አንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲቀመጥ አደረገው። ደጃዝማች ውቤ በግዛቱ በትግራይ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን እንዲኖሩና እንደልባቸው እንዲንቀሳቀሱ ፈቅዶላቸው ነበር።ደ ያኮቢስ ስራው ሊሳካለት የቻለው በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ለደጃዝማች ውቤ የተሰጠው

ስእል ታእምር ውጤት ነው ብሎ ተርጉሞታል። ዘመኑ ለኢትዮጵያ ታሪክ ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀው ዘመን ነበር።በደ ያኮቢስ የሚመሩ ሚሲዮናውያን ዓድዋ በገቡበት ጊዜ፣ በሳፔቶ አማካኝነት የፈረንሳይ መንግሥትና ደጃዝማች ውቤ ለማቀራረብ ሙከራ ተጀምሮ ነበር። ደ ያኮቢስም በሐሳቡ ተስማምቶበት ነበር። በሌፌብር የፈረንሳይ ባሕርተኞች መኮንን የሚመራው የቦታኒክ አዋቂው ዲዩንና Dillon የዞአሎጂ አዋቂ ፔቲ Petit ያሉበት የፈረንሳይ መልእክተኞች ቡድን ሳፔቶ ከደጃዝማች ውቤ ጋር ስላስታዋወቃቸው ንግግር በተደረገበት ወቅት ደጃዝማች ውቤ በሚከተሉት ነጥቦች ከፈረንሳይ መንግሥት ስምምነት ለማድረግ ሐሳብ አቅርቦ ነበር።

1. ደጃዝማች ውቤ በምፅዋ አጠገብ የምትገኝ አንፊላ የተባለችው ደሴትና የባህር ዳርቻ ወደ ስሜን ምስራቅም ተራራ ጋር ለፈረንሳይ ለመስጠት ሲፈቅድ፤

2. የትግራይ ንግድ ከዚች ወደብ ጋር ይካሄዳል

3. ደጃዝማች ውቤ ለሚሲዮናውያን፣ ለሰላማዊ ሰዎች ፣ሀገር ጎብኝዎች ድጋፍ ይሰጣል

4. ሉዊ ፊሊፕስ ትግራይን ይጠብቃታል ፣ንግድም ያበረታታል

5. በትንሿ ለፈረንሳይ ለተሰጠችው ደሴት ኢትዮጵያውያንም ጭምር የሚማሩበት የእደ ጥበባት ት/ ቤት ይከፈታል።

ሌፌብር ከደጃዝማች ውቤ የቀረበው ሃሳብ ይዞ ለፈረንሳይ መንግሥት ለማቅረብ ዲሴምበር 1839 ወደ ፓሪስ ሄዶ ነበር። የፈረንሳይ ሚንስትር ጊና ግን ለማቅረብ ዲሴምበር ... የእንፊላ ጉዳይ ከእንግሊዝ መታኮር ስላልፈለገ ሃሳቡን ሳይቀበለው በመቅረቱ የአንፊላ ጉዳይ በዚሁ አበቃ፣ ሙከራው በፖለቲካ ምክንያት ያልተሳካ ቢሆንም ለሚሲዮናውያን ግን በተለይ በትግራይ የወንጌል ሰበካቸውን ለማስፋፋት አስተዋጽኦ እንዳደረገ የማይካድ ሃቅ ነው። ደ ያኮቢስ ሁኔታዎች ተመቻችቶለት ስለነበር ስራው ያለምንም ችግር በመቀጠል በመጀመሪያ ቋንቋ ማጥናት ጀመረ፣ ግእዝ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ በአለባበስም እንደ ሀገሩ ሕዝብ ሆነ፣"ከሐጢአት በስተቀር



በማንኛውም ነገር ሐበሻ ነኝ" በሚል መፈክር ከሀገሩ ሕዝብ ጋራ ለመዋሀድ ሞከሯል፣ ሆኖም መፈክሩ ኢትዮጵያውያን ሐጢአተኞች ናችው ወይ የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ምናልባት በደ ያኮቢስ አባባል ካቶሊክ ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞች ናቸው ለማለት ፈልጎ ይሆናል።

የደጃዝማች ውቤና የደ ያኮቢስ ወዳጅነት የሚያጠናክሩ ሌሎች ሁኔታዎች ተከስተው ነበር። ኢትዮጵያ ከግብፅ የምታስመጣው ፖትሪያርክ ለ15 ዐመታት ሳይመጣ ቆይቶ ነበረ። ደ ያኮቢስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዓመት ከጎጃም፣ ከሸዋ፣ ከጎንደርና ከትግራይ ገንዘብ ተዋጥቶ መልእክተኞችን ለመላክ እንዲቻል ለደጃዝማች ውቤ ውክልና ተሰጥቶት ነበር። ኢትዮጵያውያን

መልእክተኞች ቢመረጡም ፣ዐረቦች እያፈኑ የባሪያ ንግድ የሚካሄድበት ከአፋኞቹ ለመከላከል ዋስትና የሚሰጥ አንድ አውሮጳዊ ከመልእክተኞቹ ጋር የሚሄድ ሰው ያስፈልግ ስለነበረ፣ ከተጠቆሙት ሦስት ሰዎች አንድ እንግሊዛዊው ኮፊን ፣አንድ ጀርመናዊ ሺምበርና ደ ያኮቢስ ተመረጡ፣ይህ የውጭ ዜጋ ከኢትዮጵያንውያን መልእክተኞች ጋር ሄዶ ከዓረቦች አደጋ ጠባቂ የሚሆንበት ጉዳይ ለዛሬ ትውልድ ግራ ሊገባን ይችላል። በወቅቱ ግን ይደረግ የነበረ አሰራር ነው። የደ ያኮቢስ የሕይወት ታሪክ ፀሐፊ አራታ ሳልቫቶሬ ይኸን ጉዳይ አንስቶ ሲፅፍ ዓረቦች ኢትዮጵያንን ዝቅተኛ ዘር አድርገው ይገምቷቸው ስለነበር ነው ይላል። ዓረቦች ግን በተፈጥሮቸው ዘረኞች አይደሉም የእስልምና አከራሪዎች ናችው እንጂ። በኢትዮጵያ የባሪያ መሸጥና መግዛት ተየለመደ ነበረ፣ ነግር ግን የዓረቦችና የኢትዮጲያ የባሪያ መያዝ ልምድ ከፈረንጆች በጣም የተለየ ነው ። በዐረቦችና በኢትዮጵያ ባሪያ አብሮ የሚኖር እንድ ቤተሰብ አካል ሲሆን በፈረንጆች ግን ደንበኛ የባርንት ስራ የሚያንፀባርቅበት ነው። ባሪያ እንኳን አብሮ በአንድ ቤት ሊኖር ከጌታው ጋር ሊጠጋም አይችልም: ብዙ ስቃይም ይደርስበታል። ዓረቦች ደግሞ በተለይ ሙስሊም ካደረጉት በኋላ ባሪያ ብሎ አይጠሩትም። ዓረቦች የባሪያ ንግድ የተማሩ ከአሮጳውያን ይሆናል።

ከደጃዝማች ውቤ ለደ ያኮቢስ ጥያቄ ሲቀርብለት ከአንድ ዓመት በላይ ነበረ ዐድዋ ይኖር የነበረው፣ ጥያቄውን ተቀብሎ ነበር ከደጃዝማች ውቤ ቤት የወጣው። በማግስቱ ግን ከመልእክተኞች ጋር ለመሄድ ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች አቀረበ 1/የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ከሮም ጋራ አንድነት የሚፈጥር ከሆነ 2/የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በሀገሩ እንዲሰራ የሚከለከል ሕግ እንዲሻር 3/ መልእክተኞች ከግብፅ የፓትሪያኩ ምርጫ በኋላ ከእኔ ጋር ወደ ሮማ ሄደው ክርእስ ሊቃና ጳጳሱ እንደተዋወቁ። ደጃዝማች ውቤ ፍቃዱን ስላሟላለት ደ ያኮቢስ ለመሄድ ወሰነ። በተለይ ደ ያኮቢስ ያተኩርበት የነበረው ኢትዮጵያውያን ወደ ሮማ መውሰዱና ከጳጳሱ ጋር ማገናኘት ከቻለ ወዲያውኑ ካቶሊክ የሚሆኑ ይመስለው ስለነበር ነው። በየጊዜው ለሕዝቡ የሚደረግላቸው ንግግሮች "ሮማ በወሰድኳችሁ" በማለት ነበር: በንግግሩ መደምደሚያ ይገልፅላቸው የነበረው። ካደረጋቸውም ንግግሮች አንዱ ሮማ ብወስዳችሁ የእናንተ ንግሥተ ሳባ ሰለሞንን ባየች ጊዜ ይሄን ያህል መሆንህን አላውቅም ነበር እንዳለችው ሁሉ እናንተም እንደእሱ ትሉ ነበር በማለት ንግግሩን የጨረሰው።መልእክተኞቹ ተሰባስበው ምፅዋ ሲደርሱ በፈረንሳይ ቆንስላ ጽ/ቤት ፌብሯሪ 16/1841 ዓ ም ባንዲራ ተሰቅሎ ሲውለበለብ ተመለከቱ፣ ይህ ማለት የፈረንሳይ መንግሥት

የካቶሊኮች ጠባቂ መሆኑን ለሁሉም ለማሳየት ነበር። በማግስቱ ፌብራሪ 17 ቀን መልእክተኞች ወደ ኢውሮጳ ጉዞዎቸውን ቀጠሉ። ከዓድዋ ሲነሱ ከሕዝቡ የተደረገለት አሸኛኘት ደ ያኮቢስ እንደ ሀገር ባሕል አልተረጎመውም፣ጥቁር ሕዝብ በነጭ ሰው ያለው የበታችነት ስሜት እንደገለፁ ነበር ግምት የሰጠው። የኢትዮጵያ 50 መልእክተኞች የሚመሩ በአለቃ ሃብተ ሥላሴ ነበረ። በደጃዝማች ውቤ እንደጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የሚያገለግል ሰው ነበረ። ነገር ግን የሸዋ መሳፍንት ዘር የነበረው ሰው ነበር። መርከብ ውስጥ እንደገቡ ደ ያኮቢስ ለመልክተኞች አጭር ንግግር አድርጎ ነበር ። በንግግሩ መጨረሻ ልዑል

ደጃዝማች ውቤ አዝዞኝ ከእናንተ ጋራ እገኛለሁ፣ ነገር ግን እኔ ታዛዥ ባሪያችሁ መሆኔን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ በማለት ደምድሞ ነበር። በመልእክተኞቹ ስም አንዳንዶቹ መልስ ሲሰጡ እየሳቁና እያፌዙ ግልፅ ይሁንልህ አንተ የእኛ ባሪያ ነህ ፣ልዑል የሰጡሁን ትዕዛዝ በሚገባ ካልፈፀምክ ወየልህ በንመለስ እንታያለን በማለት ነበረ የተናገሩ።ደ ያኮቢስ"የምፅዋ አየር ደረቅ ነው፣ በአካባቢ ያሉት መሬቶች ደረቅ ናቸው፣ ከሁሉ የባሰ ደረቅ ግን እጠገቢ ያሉት ሰዎች ልብ ነው"ብሎ ነበር የገመገመው። ጥቂት ቀን አብረው ከተጓዙ በኋላ ግን ከመልክተኞቹ አብዛኛዎቹ 2/3 ይወዱት እንደነበር ገልፀዋል። በጉዞ ላይ እንዳሉ ዓረቦች ደ ያኮቢስ ሲያከበሩ ኢትዮጲያውያንን በክፉ ዓይን ያይዋቸው ነበር ። ባሪያ አድርጎ ለዓረቦች እንዳይሸጣቸው ይፈሩት ስለ ነበር ኢትዮጵያውያን መልእክተኞች ከማንኛውም ሙስሊም ጋር ደ ያኮቢስ እንዳይገናኝ ይከለክሉት ነበር ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው አባቶቻችን ምን ጊዜም የነጮች የበላይነት እንደሚያምኑና እንደሚይቀበሉ ነው።

መልክተኞቹ ካይሮ ሲደርሱ በድብቅም በግልፅም ሃሳባቸውን መግለፅ ጀመሩ ። አብዛኛዎቹ ደ ያኮቢስ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ እንዲስፋ መልእክተኞቹ ወደ ሮም እንዲሄዱ የሚል ደብዳቤ ለግብፅ ፓትሪያርክ የሚሰጥ ደብዳቤ ተቃወሙ ። የግብፅ ፓትሪያርክም ስለ ደብዳቤው ሃቀኝነት ጥርጣሬ አደረበት ደ ያኮቢስ በማይፈልገው መንገድ ለኢትዮጵያ የተሾመ ፓትሪያርክ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ የግብፅ ፓትሪያርክ የኢትዮጵያ መልእክተኞችን መንከባከብ ስላልቻለ ከደ ያኮቢስ ጋር ተስማምተው ወደ ሮም ሲሄዱ 24 ሆነው ነበር። አገስት 12 ሮም ደረሱ ደ ያኮቢስ እንደተመኘው መልዕክተኞቹ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ ዝነኛ ቤተክርስቲያኖችን አስጎበኛቸው ከቅዱስነታቸው ጋር ደጋግመው ተገኛኙ ከሌሎች ካርዲናሎችም ተገናኙ ። ደ ያኮቢስ በርከት ላለ ጊዜ ጉብኝት እንዲቀጥል ቢፈልግም መልዕክተኞቹ ግን በሙሉ፣ በተለይም የመልክተኞቹ መሪ ወደ እየሩሳሌም ለመሄድ ቸኩለው ስለነበረ አንድ ወር ሮም ከቆዩ በኋላ ሴፕቴንበር 12/1841 ዓ ም ከሮም ተነስተው ወደ ናፖሊ አመሩ ። በሀይማኖት ጉዳይ ክርክር ተደርጎ ካቶሊኮች ነስቶሪያኖች እንዳልሆኑ ለመስረዳት ታስቦ የነበረው ዕቅድ ጳጳሱ ጣልቃ በመግባት እንዳይደረግ አገዱ።ደ ያኮቢስ እንደተመኘው ኢትዮጵያውያን ወደ ሮም ሄዱ፣ ጎበኙ ፣አዩ፣ከዚህ በላይ የሚደረገው ማንኛውም ሙከራ ግን አደገኛ ሊሆን ስለሚችል ማቆሙ ይበጃል ተብሎ ከበላይ አካል ተወሰነ። የደ ያኮቢስ ምኞትም በካይሮ እንዳልተሳካ ሁሉ በሮምም አልተሳካም። አራታ ሳልቫቶሬ የደያኮቢስ የሕይወት ታሪክ ፀሐፊ "ሮማ" "ሮማ "የሚለው የደ ያኮቢስ ምኞት እንዳልተሳካ በሚመስል አገላለፅ ነው የደመደመው። ጥቂት ብቻ ካቶሊክ የሆኑ ነበሩ፡ ከእነሱ ውስጥም አባ ገብረ ሚካኤል በአጼ ቴድሮዎስ የተገደለ አማረ በመቅደላ የሞተና አንድ የደ ያኮቢስ የቤት ሰራተኛ የነበረ በመንገድ በበሽታ የሞተ። ሮማ የደረሰ ሰው ካቶሊክ



ይሆናል ብሎ ማመን የዋህነት ሆኖ ቀረ። ኢትዮጲያውያን መልክትኞች ወደ እየሩሳሌም አምርተው እንደደረሱ ኦርቶዶክስ ሆናችሁ ለምን ወደ ሮም ሄዳችሁ የሚል ወቀሳ ከሌሎች ሀገር ዜጎች የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ተከታዮች በተለይ በግሪኮች ብዙ ተቃውሞ ደረሰባቸው ። ጀነዋሪ12 /1842ዓ ም ካይሮ ገቡ ከግብፅ ፓትሪያክ ብዙ ጊዜ ተገናኝተው ከተነጋገሩ በኋላ ፌብሯሪ 14 /1842 ዓ ም

ከካይሮ ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ተነሱ ። አፕሪል 3/1842ዓ ም ምፅዋ ገቡ ፡ ሜይ13/1842 ዓ ም ወደ ዓድዋ ተመለሱ ።የኢትዮጲያ መልዕክተኞች ወደ ግብፅ ወስዶ ለኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ለማግኘት አብረዋቸው እንዲጓዝ ፈቃደኛ ለመሆን ደ ያኮቢስ ያቀረባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ባይፈጽሙለትም ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ የካቶሊክ ሃይማኖት ሰብከት በትግራይ ለማካሄድ ይፋዊ ያልሆነ ፍቃድ ከደጃዝማች ውቤ አግኝቶ ነበር። ጥብቅ የግል ወዳጅነትም ፈጥሮ ነበረ። ብዙ ሰዎች ወደ ካቶሊክ ሐይማኖት ለመሳብ ችሎ ነበር ። ለብዙ ዓመታት የደጃዝማች ውቤ ድጋፍ ባይለየውም ከብዙ አቅጣጫ ግን በደ ያኮቢስ አመራር ላይ ተቃውሞ ነበር ። 1ኛ የቅርብ ረዳቶች ሳፔቶና ሞንትዖሪ ደ ያኮቢስ ከኢትዮጲያ መልዕክተናች ጋር ወደ ግብፅ እንዲሄድ አልተስማሙም ነበር ።

2ኛ በፈረንሳይ ሀገር አለቆቹ ገንዘብ ያባክናል፣ ገንዘብ በመስጠት ሕዝቡ ሐይማኖቱን እንዲቀይር ያደርጋል የሚል ወቀሳ ተሰንዝሮበት ነበር ። ሁለት ጊዜ በ1847 እና 1850 ዓ ም በኢትዮጵያ የካቶሊክ ሚሲዮን እንዲዘጋ ታስቦ ነበረ።

3ኛ ለዘጠኝ ዓመት በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል የሆነው ደጉቲን ከደ ያኮቢስ ጋር የነበረው ያለመግባባት ዋናው ነጥብ ቆንስሉ በምፅዋ አጠገብ ለኢትዮጵያውያን አንድ ትምህርት ቤት ደ ያኮቢስ እንዲከፍት ሲጠይቀው ደ ያኮቢስ ባለመስማማቱ ነበር ።

ትምህርት ቤት እንዳይከፈት ከልከሉ ደ ያኮቢስ ያካባቢው ህዝብ ሀይማኖታቸውን ወደ ካቶሊክ ሀይማኖት እንዲቀይሩ በማድረጉ ደ ያኮቢስ ባለውለታ ተብሎ የሚመሰገንበትና የሚከበርበት ምክንያት አይታይም ።

በአፍሪካ የቀኝ ግዛት ታሪክ እንደታየው ፈረንሳዮችና እንግሊዞች በሄዱበት ትምህርት ቤት በመክፈት ቋንቋቸውን በማስፋፋታቸው እንሆ ዛሬ ፈረንሳይና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የአፍሪካውያን መንግሥታት ይፋዊ የመንግሥት ቋንቋዎች ለመሆን በቅተዋል ። በሀገራችን ግን በደ ያኮቢስ ተቃውሞ የተነሳ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ሳይስፋፋ ቀርቷል። ከደ ያኮቢስ በደጉቲን ላይ የሚሰነዘረው ተቃውሞም ከብዙ በጥቂቱ ለሚሲዮናውያን በተላከው ገንዘብ ይነግድበታል፣ ለሚሲዮናውንያ የተላከ ደብዳቤ ከፍቶ ይፈትሻል ፣በኢትዮጵያ ከነበረው ፓትሪያርክ አቡነ ሰላማ ጋር ይስማማል በ5 ዓመት ለሚሲዮናውያን ከተላከው ገንዘብ 73850 ብር ውስጥ 35.000 ብቻ ለሚሲዮናውያን ሰጥቶ የቀረው ለግል ጥቅም አውሏል ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። በኢትዮጲያ በኩልም ከደጃዝማች ውቤ በስተቀር ደ ያኮቢስ ከሁሉም ተቃውሞ ነበረው ፣በተለይ ከቤተክህነትና ከፓትሪያርኩ አቡነ ሰላማ ። ደጃዝማች ውቤም ቢሆን መጀመሪያ ለፈረንሳይ መንግሥት በላከው ደብዳቤ ምኞቱ በምፅዋ አጠገብ አንድ ወደብ ለፈረንሳይ በማስጠት ለኢትዮጵያውያን የተግባረእድ ትምህርት ቤት እንዲከፈት ነበር። ይህ ሳይሆን በመቅረቱ በኢትዮጵያ ለደ ያኮቢስ ይሰጥ የነበረ መሬት፣ በገንዘቡም ቢሆን ለገዛው በምፅዋ አጠገብ የፈረንሳይ ቆንሲል እንዳቀደው ዓይነት ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ቢሆን ኖሮ ለፈረንሳይኛ ቋንቋ ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ለካቶሊክ ሐይማኖት ጠቀሜታ ሊያመጣ ይችል እንደ ነበረ

እያጠራጥርም ። ደጃዝማች ውቤ ሚሲዮናዊው የጠየቀው ሁሉ ሲያሟላ ደ ያኮቢስ

ግን የውቤ ምኞት ለሟሟላት አነስተኛ ፍላጎት እንኳን አልነበረውም። በ1854ዓ ም ደያኮቢስ በጎንደር በጎጃምና በሸዋ ጉብኝት ለማድረግ የብዙ ጊዜ እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ጎንደር ገባ። ወቅቱ አጼ ቴዎድሮስ ዘውድ ሊጭን የተቃረበበት ነበረ ። አቡነ ሰላማ ከአፄ ቴዎድሮስ ተጠርቶ ከትግራይ ጎንደር ለመግባት የሚዘጋጁበት ጊዜ ነበረ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ምሁራንም በሶስት ቡድን ተከፋፍለው ስለ እየሱስ ክርስቶስ ሁለት ወይንም አንድ ባህርይ ክርክር የተፋፋመበት ጊዜ ነበረ። ደጃዝማች ካሳ (አጼ ቴዎድሮስ) ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አንድነት ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል የሚል እምነት ነበረው ። አጼ ቴዎድሮስ እንኳን ለካቶሊክ እምነት ተከታዮች የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችም ያለአንድ ቡድን፣ የካራ፣ ተከልክለው ነበር ፣ ይታሰሩም ነበር። ደጃዝማች ካሳ ከደ ያኮቢስ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ በጎንደር የሚገኙት ካቶሊኮች እንዳይነኩ ትዕዛዝ እሰጣለሁ የሚል ቃል ገብቶለት ነበር ። በኋላ ግን ዋና ዋናዎቹ ለአንድ ዓመት ታስረው ሲፈቱ አንድ ብቻ ዋና የደ ያኮቢስ ረዳት የነበረው በእስር ቤት በደረሰበት ጉዳት ሲሞት ደ ያኮቢስም ትንሽ እንደታሰረ ተፈትቶ በሱዳን በኩል ከሀገር እንዲባረር ተደረገ ። ሱዳን እንደገባ ግን ባልታወቀ ሁኔታ ተለቆ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ምፅዋ ገባ። በዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ይፈልጉ የነበረ ነገር የጦር መሣሪያ የሚያቀብላቸው ሰው ብቻ ነበረ፣ደ ያኮቢስ ግን ጎንደር ሲገባ ከአጼ ቴዎድሮስ የተጠየቀው አንድ እጥር ደብዳቤ በመፃፍና አነስተኛ ስጦታ በማበርከት ነበር። ስጦታውም ደጃዝማች ካሳ አልተቀበለውም የጦር መሣሪያ ባይሆንም 16 ዓመት በትግሪይ ቢቀመጥ ለኢትዮጲያ ሕዝብ በትምህርትም በልማትም ያበረከተው አስተዋፅ ቢኖር ከደጃዝማች ውቤ ጋር ድጋፍ እንዳልተሰየው ሁሉ አጼ ቴዎድሮስ ድጋፍ እንዲያደርግለት መቻል ነበረበት። ነገር ግን ደ ያኮቢስ ከዚህ ሁሉ ሥራ ሩቅ ስለነበረ ችሎታም አልነበረውም ፍቃደኛም አልነበረም። እሱንና ወደ ካቶሊክ ሐይማኖት የሰወጡ ምእመናንን ከማሳደድ ሌላ በጎ ተግባር ከአጼ ቴዎድሮስ ሊጠብቅ አይችልም ነበረ ። ደጃዝማች ውቤም ቢሆን ለደ ያኮቢስ ያደርገው የነበረው ድጋፍ የቀድሞው ውለታ በማስታወስ፣ እንዲሁም ለወደፊት ከፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ በማግኘት ይረዳኛል ብሎ ተስፋ በማድረግ ይሆናል እንጂ ለካቶሊክ ሃይማኖት ጠበቂ ሆኖ ለመቆም አልነበረም ። ደ ያኮቢስ እንደጠበቀው አቡነ ያዕቆብ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ እንዲሆን ብዙ አስበ የነበረው አልተሳካም ። በ1855 ዓ ም የደ ያኮቢስ ደጋፊ የነበረው ደጃዝማች ውቤ በአጼ ቴዎድሮስ ተሸንፎ ሲታሰር ለካቶሊክ ሚሲዮናውያን ከባድ ውድቀት ሆኖ ነበረ። ነገር ግን ብዙ ሳይቆይ ደጃዝማች ንጉሤ የተባለው በእንጎቱ ቦታ ተተክቶ ትግራይን ለመግዛት የተነሳ ብቅ አለ ። አዲሱ የትግራይ ገዥ ከዳጃዝማች ውቤ ያላነሰ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ደጋፊ ነበረ። ሆኖም 12.000 ከጎንህ የሚቆሙ የፈረንሳይ ወታደሮች ይደርሱልሀል አጼ ቴዎድሮስን አሸንፈህ የኢትዮጲያ ንጉሠ ነገሥት ትሆናለህ የሚል ተስፋ በመስጠት በኢትዮጵያውያን መሀከል እርስ በእርስ ጦርነት ማባባስ በስተቀር ከሁለቱ ወገኖች የተጠቀመ አልነበረም ። ተጠቃሚ የካቶሊክ ሚስዮናውያን ብቻ ሆኑ፤ በጦርነት የደቀቀች ሀገር ስር ሰደው ለመመስረት ችለዋል።

እውነትም አቡነ ያዕቆብ በዐጋሜ ፣ በአከለ ጉዛይና በከረን፣ በቢለን ተወዳዳሪ የሌለው አከራሪ ልዮ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ለመፍጠር ችሏል ።



ልዩ የሚያደርገው ሥነ ሥርዓቱ በሙሉ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሆኖ ፣ ስሙ ብቻ ካቶሊክ ተብሎ ፣ታዛዥነቱ ለሮም ጳጳስ በመደረጉ ነው። ጥቃቅን ነገሮች ብቻ በክርስትና ሃይማኖቶች ልዩነት በማያመጡ እንደ ጋብቻ የመሳሰሉት እጉልቶ በማሳየት ልዩነት ሰመፍጠር ጥረዋል ።

[1]ፔሪኒ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ በእኩሩር የካቶሊክ ሚሲዮን በመጥቀስ አብራርቶ ጽፈዋል ። የካቶሊክ ሃይማኖት አነስተኛ የማስፋፋት ምልክት የታየበት።

1. የኢጣሊያ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ ጥቅም የሚያገኙ እየመሰላቸው

2. በኢጣሊያ እውራጃ ገዥ ተብሎ የተሾመው ደጃዝማች ባሕታ ሐጎስ ወንድሙን ገድሎ ስለ ነበር ካቶሊክ ከሆንክ ሐጢአትህ በሙሉ ይጠፉልሃል ስለተባለ አከራሪ ካቶሊክ በመሆኑና ሌሎችም ካቶሊክ እንዲሆኑ ያስገድድ ስለ ነበር ነው ብለዋል።

3. የእከሩር ካቶሊክ ሚሲዮን የእደ ጥበብ አታስተምርም፣ ሌላ ትምህርት አታስተምርም፣ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚችሉ እንደ እርሻ፣ የእንስሳት እርባታና ሌሎች ጠቃሚ ሞያዎች አታስተምርም።

4. ሃያ የሚያህሉ ልጆች ብቻ ግእዝ፣ ጣሊያንኛ፣ አማርኛ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ ያስተምሯቸዋል፣ ከእነሱም መርጠው ለቄስ ትምህርት ወደ ከረን ይልኳቸዋል።

5. ካቶሊኮች ከእርቶዶክስ የሚሻሉ ቢመስሉ ጋብቻ በማክበር ብቻ ነው ። በሌላ ሁሉ የባሰ ውሸታሞች ናቸው። ሃይማኖታቸው ወደ ካቶሊክ ከሚቀይሩ ሁሉ በራሳቸው እምነት ሳይሆን የኢጣሊያ መንግሥት የሚወዳቸው እየመሰላቸው በተሰይ ሀገረ ገዥው ደጃዝማች ባሕታ እንዲወዳቸው ነበረ ካቶሊክ ይሆኑ የነበረ።

6. መንፈሳዊ ስእሎች በብዛት ከሚታደላቸው በቀር ከካቶሊክ ሚሲዮን አንድም ጥቅም አያገኙም ። ሌላ ነገር ከእርቶዶክስ የሚለያቸው በካቶሊክ ቄሶች ሚስት አያገቡም፣ የእርቶዶክስ ግን ያገባሉ።

7. ስለመሰረታዊ ልዮነቶች ግን እንኳን ተራ ሕዝብ አስተማሪ የሆነው ቄሱም ሊገባው የማይችል ነው ። ስለዚህ ሚሲዮናውያን በሽብር ነው የሚጠቀሙት። ገሐነመ እሳት ትገባለሕ ብለው በማስፈራራት እንዲሁም በሴቶች እንደመሳሪያ በመጠቀም በካቶሊክ ሐይማኖት በጋብቻ መፋታት አይፈቅድም ብሎ በማስተማር ይኸውም ለሴቶች ዋስትና የሚሰጥ ስለሆነ ነው።

8. የቆየ የሃይማኖት ሥነ ሥርዓት ብሔራዊ የሆኑ ባሕሎች፣ የያሬድ መዝሙሮችና ውዝዋዜዎች በፀናጽልና በከበሮ፣ እጣኖች ፣የቄሶች ለዐይን የሚስቡ አሰባበስ ቢከለከሉ ምናልባትም አሁን ካቶሊክ የሆኑት ወደ እርቶዶክስ ይመለሱ ነበረ።

9. የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ደጋፊዎች የነበሩ መሪዎች ደጃዝማች ውቤና ደጃዝማች ንጉሴ ለፈረንሳይ መንግሥት የእደራ ደብዳቤ በመፃፍ ከንቱ ተስፋ እንዲያድርባቸው በማድረግ ለኃያሉ አፄ ቴዎድሮስ ተጋልጠው ተራ በተራ በሚዘገንን ሁኔታ እንዲገደሉ እንዳደረጉ ሁሉ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የቀየሩ ሕዝቦችን ጉዳት ካልሆነ የጠቀማቸው ነገር የለም።

---

[1] Magg. Ruffilo Perini : Mereb - Melasc p 354- 57

10. ደ ያኮቢስ በደጃዝማች ውቤ መገደል ለትግርና ወደ ምፅዋ ስደት ቢዳርገውም ደጃዝማች ንጉሴ ትግራይን በተቆጣጠረ ጊዜ የሚሲዮናውያን ሁኔታ እንደ ቀድሞ በመመለሱ በጦር ሜዳ ዕድል ለትግራይ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ የሚስዮናውያን ዕድል አብሮ በመሄድ ይቃናል በሚል መፈክር ለደጃዝማች ንጉሴ ድጋፍ እንዲሰጥ ለመምሰል ሚሲዮኑን በደብልዋ ለማስፋፋት የቻለበት ጊዜ ነበረ። ደጃዝማች ንጉሴ ለሽንፈት ያበቃቸው የደ ያኮቢስ ምክር በመከተሉ ብቻ አልነበረም፣በደብልዋ በፈረንሳይ ደካማነት ነበር። የሚገርመው ደግሞ የፈረንሳይ መንግሥት የማያደርገውን አደርጋለሁ ብሎ ተስፋ በመስጠት ነበር ። ደጃዝማች ውቤና ደጃዝማች ንጉሴን ለሽንፈት ከማጋለጡ ሌላ በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል መስራች ሆኖ ለዘጠኝ ዓመት አገሩን ያገለገለ ዴጉቲን የተባለው ቆንሲል ስራውን በሚለቅበት ጊዜ ለብዙ ጊዜ የስራ ቅራኔ በነበረው በደ ያኮቢስ ስላከናወናቸው ሥራዎች ግምገማ እንዲደረግለት ከፈረንሳይ መንግሥት መታቀዱ ሌላ የደካማነት ምልክት ነበር ። ሆኖም ካርድናል ማሳያ ስለ ደጉቲን ጥሩ አስተያየት ፅፎ ስለ ነበር ደጉቲን እድገት አግኝቶ ወደ አደን ተዛውሮ ስራውን ቀጥሏል ።ደ ያኮቢስ 22 ዓመት በትግራይ ሲኖር የታሪካችን አሻራ ባሉባቸው ቦታዎች አሳልፈዋል ። መጀመሪያ በዓድዋ ፣ በአክሱም አጠገብ ቀጥሎም በሐላይ በቆሐይቶና ትኩንዳዕ ታሪካዊ ቦታዎች አጠገብ ነበር፣ ግን ስለ ሀገራችንና ሕዝቦቿ ማንነት በቂ ግንዛቤ ሳያገኝ ነው ጊዜውን ያሳለፈው ።ደ ያኮቢስ ስለ ኢትዮጲያ የደረሰው መፅሐፍ የለም፣ በየአጋጣሚው የሚፅፋቸው ደብዳቤዎችና ማስታወሻዎች፣ ስለ ሕዝባችን የሚሰጣቸው አስተያየቶች ኋላ ቀር ምስኪን ጥቁሮች ፣ኔግሮች፣ ባርባሪያን የሚል ብቻ ነበሩ። ስለ ኢትዮጲያ Ethiopian Nation ብሎ የጠራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ያደንቃትም ለብዙ ዘመናት በእስላሞች፣ እምነት የሌላቸው ሕዝቦች ተከባ 1/ የቅዱሳን መጻሕፍት እንክብካባ በመያዝዋ 2/ የጥምቀትና ሌሎች የክርስትና ምልክቶች አክብራ በመያዟ 3/ ጾም በማክበሯ 4/ ምንኩስና በማክበሯ 5/ የማርያምና ተቅዱሳን እምነት ከነ ሥእሎቻቸው ማክበሯ ወዘተ ምክንያቶች ነበረ ። በእንፃሩ ለጥቂት ጊዜ ብቻ በኢትዮጵያ የኖረ ሳፔቶ ስለ ኢትዮጲያ ብዙ መፅሐፎች ደርሷል፣ በተደጋጋሚ ኢትዮጲያን Ethiopion Nation ብሎ ይጠራታል ። የሚያደንቃትም ከክርስትና እምነት ሌላ በሁለ ገብ ከፍተኛ ታሪኳ ነው። በተለይ ሀ/ የግብፅ ሥልጣኔ በኩር ልጅ ለ/ የግብፅና የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች ስልጣኔ ምንጭ ብሎ ይጠሯታል።

ሌሎች ጣሊያኖች ሥለ ኢትዮጵያ ጥሩ አስተያየቶች የሰጡ አሉ ከእነሱ መካከል እንዱ ቢያንኪ የተባለው ተራ ሀገር ጎብኝ አጼ ዮሐንስ ተቀብሎ ባነጋገረበት ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ የሰጠው አስተያየት መጥቀስ ይጠቅማል። ቢያንኪ በሰጠው አስተያየት ስለኢትዮጵያውያን ቆንጅና እንዲሁም ስለአለባበሳቸው ደስ ማለቱ ካደነቀ በኋላ የሚያሳዝነው ግን ከልክ በላይ ኩሩ መሆናቸው ነው፤ይህ ግን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከባሕላቸው የወረሱት ነው።በእስላሞች ላይ ባካሄዱት ጦርነት ባስመዘገቡት ጀግንነት ነው፤ ሁሉም ደግሞ ትልቅ ዘር ነን፣ የንጉሥ ወይም የመሳፍንት ዘር ነን የሚል የዋህ እምነት ያላቸው ናቸው ። አንዳንድ ጊዜ ያሳዝናሉ ሰው የሌለው የማይችለው አድርግልኝ ብለው ወጥሮ በመያዛቸው እንዲሁም በማስመሰል ጠባያቸው የሚያሳዝኑ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን በተለይ

የትግራይ ሕዝብ የእኛ ትኩረትና ወዳጅነት ማግኘት ይገባቸዋል በማለት ጽፈዋል።



# ካርዲናል ማሳያ[1]



በሮም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የጋላ ሀገር ሚሲዮናዊ ሆኖ የተመደበው ፈረንሳዊው አንቷን ዳባዲ ለጳጳሱ በጻፈው ደብዳደቤ መሠረት ነበር ። 35 ዓመት በኢትዮጵያ አሳልፋል ከ1846 እስከ 1880 ። ብዙ ጊዜ ግን እንደ ቱሪስት ሆኖ ነበረ ያሳለፈው። አንቷን ዳባዲ ምንም ችግር ሳያጋጥመው ከኢውሮጳ ተነስቶ በአራት ወር ውስጥ ትግራይን፣ ጎንደርን፣ ጎጃምን፣ ምስራቅ ኢትዮጲያን ወሊጋን፣ ጅማን፣ አጳርጦ ከፋ ደርሶ የፈለገውን ምርምር አካሄዶ ወደ ኢውሮጳ ሲመለስ፣ አቡነ ማሳያ ግን ወደ ጋላ ሀገር መግባት አልቻልኩም በማለት ከ1846 እስከ 1851 ዓ ም ድረስ የቆየው ባሕር ወደቦች ትግራይ ጎንደር ጎጃም ደርሶ አባይን ተሻግሮ ወደ ተመደበበት ሀገር ለመድረስ ሳይችል ተርቶ ራስ ዓሊ ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋራ የወዳጅነት ውል እንድትፈራረም ስለምትፈልግ መልእክት አድርስልኝ ብሎኛል ብሎ ሰበብ በመፍጠር ከአምስት ዓመት በኋላ ወደ ኢውሮጳ ተመለሰ ። ማሳያ የኢትዮጵያ መሬት እንደረገጠ በመጀመሪያ የሚሲዮናዊ ስራ በድብቅ የባሪያ ንግድ ከሚያካሄዱ ሰዎች የጋላ ልጃገረዶችን ካቶሊክ በማድረግ ነበረ ሥራውን የጀመረ ። በአፄ ዮሐንስ ትዕዛዝ ተባርሮ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እንደ ሕይወት ታሪኩ የሚቆጠር 12 ቮሊዩም የያዘ መጽሀፍ ደርሷል። እንዲሁም የሚፅፋቸው የነበሩ ብዙ ደብዳቤዎች ታትመው ወጥተዋል። ካርዲናል ማሳያ ባከናወናቸው ስራዎችና በደረሳቸው ጽሑፎች በሀገሩ ሰዎች አድናቆት ቢያተርፍም ሀገራችን በሚመለከት ከስድብ በስተቀር ቁም ነገር ያለው ፅሑፍ ጽፎ የተወው የለም ። ከ35 ዓመታት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት በአፍሪካ ጉብኝት በማድረግ ነበረ ያሳለፈው ። ቀጥሎም አንድ ዓመት ከስምንት ወር በኢውሮጳ ጉብኝት በማድረግ ነበር ያሳለፈው። በሁለተኛ ዙር ወደ አፍሪካ ያደረገው ጉዞ በም ቀይሮ በግብፅ ፣ ሱዳን፣ ጎንደር ፣ጎጃም ወደ እሮሞ ሀገር ዛሬ ምዕራብ ሸዋ የሚባለው ጉደር አካባቢ ወደ ተመደበበት የሥራ ቦታ በ1852 ሊገባ ችሏል ። ጉጃም እንደደረሰ ረዳት ቄስ ቸዛሬ የተባለው እዛው እስተምጦት የነበረ እንደገና ተመልሶ ከቄሱ

ጋር በተገናኘበት ጊዜ፣ ከቄሱ ጋር ከፍ ያለ አለመግባባት ተፈጠረ ። ቄሱ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ቋንቋ አድናቆት አድሮበት ጥናት በማካሀድ ላይ ሲያገኘው ካርዲናል ማሳያ ግን ይህ ትልቅ ውርደት ሆኖ ተሰማው ።ስለካተሊክ ሐይማኖት

[1] Ettore Cozzani ; Vita Di Gughielmo Massaya

ከፈረንሳይኛ ወደ አማርኛ ተርጉሟል፣ ሥለ ጥምቀት የተፃፈ ከአማርኛ ወደ ላቲን ተርጉሟል፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቅዳሴ ተርጉሟል ። ይሄ ብቻ አይደለም ደብተራ ለመሆንም ሞክሮ ነበረ በማለት ወንጅሎታል። ካርዲናል ማሳያ ከዚህ ወራዳ ሥራ ካላቀቀው በኋላ ምክትሉ አድርጎ ሹመት በመስጠት ወደ ከፋ እንዲሄድ በማድረግ ከጎጃም እንዲርቅ አደረገው ።ካርዲናል ማሳያ በአርሞ ሀገር የሐይማኖት ሰባኪ በጀመረበት ጊዜ ሁለት ሴቶች ባሪያ በመግዛት ነበረ ሥራውን የጀመረው ፣አንዷ ወጣት ስትሆን ከእሱ ጋራ አልዘለቀችም ፣አንዷ ግን እርጊት ታማኝ ሆና ከእሱ ጋራ እስከ መጨረሻ አገልግላለች። ካርዲናል ማሳያ የፃፈው ባለ12 ቮሊዩም መፅሐፍ እንዲሁም በኢጣሊያ መንግሥት የታተመ ባለ ሁለት ትልቅ ቮሊዩም መፅሐፍ የሕይወት ታሪኩ የሚያወሩት ቅደም ተከተል የሌለው ታሪክ ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ግለሰብ በመዝለል ጥቃቅን ነገሮችን ደጋግሞ በማድረግ ነበር። የካርዲናል ማሳያ የሌለው ሞያ አጋና ማትረብ የጀዙ ሲሆኑ ፣ ዋና መሠረት ዓላማቸው ግን አክራሪ የካቶሊክ ሐይማኖት ተከታይ መሆኑን ለመግለፅ ነው ። ሌላ በጽሑፉ የሚያንፀባርቀው ፀረ እስልምና ሃይማኖት፣ ከእስልምና ባለነሰ ሁኔታ ደግሞ ፀረ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ያንፀባርቃል። በተለይ የኢትዮጵያ የሆነ ሁሉ ከማጥላላት የተቆጠበበት ጊዜ የለም። የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፊደል፣ ባሕል፣ ወዘተ ። ከኢትዮጵያውያን የሚወደው አንድ ሰው ብቻ ነበረ እሱም አጼ ምኒልክ ነበረ።

ካርዲናል ማሳያ ገና የኢትዮጵያ መሬት ሳይረግጥ ጅዳ እንደደረሰ አንድ ፈረንሳዊ ዜጋ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ በማየቱ ተቃወሞ በማሰማቱ ዘረኛ ነው በማለት ጣሊያኖች ኮርተውበታል ። አቡነ ማሳያን ተከትሰው ከመጡ ረዳት ቄሶች መካከል እላይ እንደተገለፀው ነዋሪነቱ ጎጃም ተመድቦ የነበረው አባ ቸዛሬ የተባለው ብቻ አይደለም ። ኢትዮጵያን በማድነቅ ከአቡኑ የተለየ አቋም የነበረው ነዋሪነቱ ጎንደር ሆኖ ተመድቦ የነበረው ጁስፔ የሚባለው ቄስም ከአባ ቸዛሬ በባሰ ሁኔታ የኢትዮጲያ ታሪክ ፍቅር ስለአደረበት አቡነ ማሳያ ወደ እርሞ አገር በሄደ ጊዜ ተከትሎት እንዲሄድ ታዞ አልሄድም ብሎ ነበረ ። አቡነ ማሳያ ካደረበት የኢትዮጲያ ፍቅር ለማላቀቅ ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ ያልሞከረው ነገር አልነበረም ፣ ግን አልተቻለም፣ የእርሞዎች መጥፎነት ወሬ በመስማት ፍርሐት ስላደረበት ነው ወይንስ ያ የኢትዮጵያ የተረገመ መንፈሳዊ ቋንቋቸው ግእዝ ይሆናል ከዛች ቦታ እንዳይላቀቅ የሚያደርገው ወይንስ የደብተራዎች ጥንቆላ ነው ብሎ በማለብ በምክርም በግሳፄም ቢሞክር አልታዘዝም ብሎ ስራውን ቀጥሎ ነበር። በመጨረሻ ግን ተፀፀጥትኩ ብሎ ወደ ሮማ ለመመለስ ወሰነ ። ሮማ እንዳገባ ለአለቆቹ ወደ ተመደብኩበት ወደ እርሞ ሀገር ልመለስ ብሎ ጠይቆ ስለተፈቀደለት ስለ ኢትዮጵያ ያካሄደው ጥናት የእጅ ፅሁፍ አስረክቦ በሱዳን በመመለስ ላይ እንዳለ ታሞ ፣ካርቱም ሲደርስ ሞተ። ከላይ እንደተጠቀሰው አባ ቸዛሬ ያለፍላጎቱ ከጎጃም ወደ እርሞ ሀገር እንዲሄድ ከተደረገ በኋላ መጀመሪያ ወደ እናሪያ ሊሙ እንዲሄድ ተደርጎ፣ በኋላም ወደ ከፋ ስለተላከ እዛም እንደደረሰ የከፋ ንጉሠ ነገሥት በታላቅ ክብር ከተቀበለው በኋላ የኦርቶዶክስ ቄሶች ሚስት ስለሚያገቡ ልጁ አደርግሃለው ብሎ በሀገሩ ሥነ

ሥርዓት ሚስት ዳረው፣ 2 ልጆች እስኪወልድ ድረስ ለአቡነ ማሳያ ሳይናገር ቆይቶ፣ አቡኑ ወሬ ስለደረሰው ሦስት ጊዜ ደብዳቤ ፅፎ መልስ ስላጣ ወደ ከፋ ሄዶ ከስህተቱ እንዲታረም ለማድረግ እሰቦ ጉዞውን ሲጀምር ያስደንቀው የነበረው ነገር ካባ ቸዛሬ ጋር እንዲሰራ የተመደበው የአገሩ ተወላጅ እንዲጀና ኢትዮጵያዊ አባ ያዕቆብ ቄስ ምንኩስናው ጠብቆ ሲኖር አባ ቸዛሬ ግን የካቶሊክ



ቤተሰብ፣ ነጭ ዘር ፣ ኢጣሊያዊ ቤተሰብ ፣ ካቸቺን ሆኖ ይህን ከባድ ቅሌት መፈጸሙ ነው ።

አቡነ ማሳያ እናሪያ ሲደርስ አባ ባጅቦ የተባለው የሀገሩ ንጉሥ አቡኑን ወደ ከፋ እንዳይሄድ ምክር ለመስጠት ሞክሮ ነበር ። ነገር ግን ክንቱ ሙከራ ሆኖ ቀረ፣ እንደገና አባ ባደቦ ስለ ከፋ ሁኔታ ለአቡኑ ሲያስረዳ ፣ የከፋ ህዝብና ንጉሥ ሰው መግደል፣ መርዝ መስጠት ልማዳቸው አይደለም ነገር ግን ንጉሡ፣ 7 የንጉሡ አማካሪዎቻችና የአባ ቸዛሬ ሚስት ዘመዶች ከከፋ ከመጡ መልእክተኞች እንደተረዳነው አቡኑ ወደ ከፋ እንዲሄድ ይቃወማሉ፣ ስለዚህ ወደ ከፋ ባይሄድ ይሻላል ብሎ ቢነግረው ሊሰማ ስላልቻለ ሚያዝያ 25 1859 ዓ ም ጉዞው ወደ ከፋ ጀመረ ። አቡነ ማሳያ ገና ከፋ ሳይደርስ ጊራ እንዳለ እንደ አባ ቸዛሬ ለማድረግ ተሞክሮ ነበር፣ ከፋ እንደደረሰም ተመክሯል፣ አቡኑ ግን ምንም እንኳን የ50 ዓመት ጎልማሳ ቢሆንም አልተበገረላቸውም። እከቶበር 2 /1859 ዓ ም ከፋ መሬት ገባ ከንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኞችና ከአባ ያዕቆብ መልእክተኖች ጋራ ተገናኙ፣ ከከፋ ባላባቶች ጋር ከቤተመንግሥት የሚያስፈልገውን ምግብ በማቅረብ፣ ስጦታ በመስጠት ምግብ የሚሰሩለት በማስመሰል ሰመፈተን ቆንጆ ሴቶችን አጠገቡ በማድረግ፣ የተሟላና የረቀቀ አቀባበል ተደረገለት ። በመጨረሻም በወጥመድ ስላልገባላቸው ከአባ ቸዛሬ ጋር አገናኙት። ሁለቱም ተቃቀፉ፣ አባ ቸዛሬ ይቅርታ ጠየቀ፣ ነገር ግን ተወግዞ ስለ ነበረ ከሌሎቹ ካቶሊኮች ጋር መቀላቀል ተከለከለ፣ አባ ቸዛሬ ከካቶሊኮች ጋር ለመቀላቀል የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ተደርጎ ቄሱ አባ ቸዛሬ የበራ ሚፍ ይዞ ቤተክርስቲያን በር ውጭ ተምበርክኮ መቆም ነበረበት። ይኸውም በ10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በአውሮጳ ይደረግ የነበረ ልማድ ነው ። እከቶበር 23/1859 ዓ ም ቄሱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገብቶ ከምእመናን ገንዘብ ለቤተክርስቲያን የሚሆን ቢቀበል ይቆይና አቡኑ ልብስ ጵጵስናው ለብሶ ለቅዳሴው ወደ ቤተክርስቲያን ሲደርስ ቄሱ ልመናውን አቋርጦ ወደ አቡኑ ተጠግቶ ድንጋይ በትከሻው ጭኖ፣ እግሩን ለመሳለም፣ ያጎነበሳል ይኸውም የኢትዮጵያ ባህል ነው ።

ቄሱ በሕዝቡ ፊት ይቅርታ ይጠይቃል፣ አቡኑም ፍትሐት ሰጥቶት በመጨረሻ ተቃቅፈው ይሳሳማሉ ። ሁለቱ የአባ ቸዛሬ ልጆችም ክርስትና ይነሳሉ ከዚህ በኋላ አባ ቸዛሬ ስራውን ቀጥሎ 1000 ሰዎችን ክርስትና አስነስተዋል።ከ4 ወር በኋላ አባ ቸዛሬ በድንገተኛ ሕመም ትኩሳት ታመመ: ኮሶ እንዲሰጠው ጠየቀ፣ ከጎኑ ደም እንዲመጠጥ ጠየቀ። ተደረገለት፣ ከሦስት ቀን በኋላ እንደሚሞት ራሱ ተናገረ፣ በ6ኛ ቀን ዐረፈ።

አቡነ ማሳያ ሌሎች ሚሲዮናውያን ረዳቶቹ ሳይንሳዊ ምርምር ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ምርምር፣ ለአንድ ሚሲዮናዊ አያስፈልግም ብሎ እንደ

ስሚታቸው እንዳይሰሩ እፍና ሲይዛቸው ስለ ሀይማኖታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን ጥናት እንዳያካሂዱ የተረገመ የግእዝ ቋንቋቸው እያለ ሲከለክላቸው፣ ራሱ ግን የሳይንስ ተመራማሪ፣ አዲስ ሀገር አቅኚ፣ ሐኪም፣ ተአምር ሰሪ፣ ከቆሎ ወረቀት መስራት የፈለሰፈ፣ የጠንቋዎች ተመራማሪ በማለት፤ አንዳንዶ የካፈቶ ቃላቶች ከፖርቱጋል፤ ከላቲን፣ ከግብፅ፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተወረሱ መሆናቸውን አግኝቻለሁ ብሎ የሚመፃደቅ፣ ሌሎች ሚሲዮናውያን ግን አንድ ሚሲዮናዊ ወደ ሌላ ሥራ ካዘነበለ የሰው ነፍስን የሚያድንበት ጊዜ መሻማት ነው እያለ ሲቃወም ለራሱ ግን ሁለገብ መርማሪ ለመሆን ይፈልግ ነበር። በምድረ ገጽ ምርምር ጀኖግራፊ በኩልም ወደ ከፋና እርሞ ሀገር ለመሄድ በኢትዮጵያ፣

በሱዳን በኩል አስቸጋሪ ስለሆነ በደቡብ በኩል በዛንዚባር ወደ ከፋ ለመድረስ ይቻላል ብሎ ዕቅድ በማውጣት እድናቆት የኢጣሊያ ቀኝ ገዥዎች በማጋነን አቅርበውለታል። ትንሹ ከፋ ማግኘት ከቻልኩ ድሉ ለሚሲዮናውያን ትልቅ አስተዋፅኦ ነው፣ የካቶሊክ ሃይማኖት በምስራቅ አፍሪካ ማንም ሊነቅለው የማይችል ስር ይሰዳ ነበረ: ወደ አካባቢው ይሰራጭ ነበረ የሚል ምኞት ነበረው። ለዚህም ለሳርዲኒያ መንግሥት እርዳታ ተማፅኖ ነበረ ። በደቡብ በኩል በአባ ሊዮን ዳሽንቼር የሚመራ የሚሲዮናውያን ቡድን በስሜን አቡነ ማሳያ ከከፋ ወደ ወላም በ1860 ዓ ም ፋሲካ ወላም እንዲገናኙ ተስማምተው፣ ዕቅዱ ካልተሳካልኝ የአባ ሊዮን ዳዛንቼር ጥፋት ይሆናል ብሎ ነበር።

ይህ ሁሉ ሕልም ኢትዮጵያ በመጥላት ብቻ የተመሠረተው፣ በታሪክ፣ በባሕል በኩል አዋቂ የተባለበት በከፋ የሚገኝ ስለማንጂዮ ኅሳዎች ያቀረባቸው ዘገባዎች ናቸው። ይልቅ ስለ ከፋ ሕዝቦች ማወቅ ይችል የነበረ ብዙ ዓመት ከእንሱ ጋር የተቀመጠና የተዋለደ አባ ቻዛሬ ነበር።

ስለ ባሪያ ንግድ በከፋና በኦሮሞ ሀገር የነበሩ ሚሲዮናች ብዙ ባሪያዎች እንደ ነበሯቸው አቡነ ማሳያ ከማመኑም በላይ፣ ሚሲዮኑ ይሄንን ስራ የሚያከናውነው በምስጢር እንደነበረና የተገዙ ባሪያዎች በየሀገሩ የሚሲዮናውያን ጣቢያዎች እየተላኩ እየተከፋፈሉ ትምህርት እየተሰጣቸው ክርስትና ይነሱ እንደነበሩ ጽፋል ። አቡነ ማሳያ የባሪያ ነጋዴዎች ባሮች እንዱ ቤት ውስጥ እንደ እንስሳት እያረቡ ይሸጧዋቸዋል ብሎ ሲጠቅስ የሚሲዮናውያን ባሮችም በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ልጆች እንደነበሯቸው ጽፈዋል።

አብነ ማሳያ የአየር ሁኔታ አዋቂ ፣የእፅዋት፣ የከብት በሽታ አዋቂ ነኝ እያለ የሌለውን እውቀት እንዳለው ቢያስመስል የኢጣሊያኖች ያልተቆጠበ ተገቢ ያልሆነ አድናቆታቸውን ገልፀውለታል።

አቡነ ማሳያ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አባ ቻዛሬ በተረከበበት ጊዜ ከከፋ መንግሥት ጋራ አንድ ውል ተፈራርሞ ነበር፣ በውሉም መሠረት ።

1. የአባ ቻዛሬ ሚስት ከዘመዶቿ ጋር እንድትኖር
2. ለጥሎሽ የተሰጧት ባሮች፣ መሬት ወዘተ የእሷ ይሆናሉ
3. ባልና ሚስት ይጠቀሙበት የነበረ የታድሚራ መሬት ባሮች ከብቶች የአባ ቻዛሬ ይሆናሉ፣ አቡኑም እዚህ መኖሪያው ይሆናል
4. ሁለቱ የአባ ቻዛሬ ልጆች ለአቡኑ ይሰጣሉ
5. ክርስቲያን የሆኑ ቄሶች ሁሉ የአርቶዶክስም ጭምር በአቡነ ማሳያ ይታዘዛሉ እንዲሁም ቤተክርስቲያናች በሙሉ ።

ይህ ውል መሠረት በማድረግ አቡነ ማሳያ ለአባ ቻዛሬ እንዳደረገው ሁሉ: ራሱ ዳኛ በመሆን የአርቶዶክስ ቄሶችን መፍረድ ይጀምራል ፡ 1853 ዓ ም እንዱ ጎጃሜ አባ ዳምጡ የተባለው ቄስ በዕዳ ስለተያዘ ከሀገሩ ሸሽቶ የወጣ ጊራ እንደደረሰ አባ መጋል እስላም እንዲሆን ምክር ሰጥቶት ነበር። ከፋ እንደገባም የቄስ ስራ ሳይሆን የጠንቋይ ስራ ይሰራ ነበር። ለሃያ ዓመታት እባለዘር በሽታዎች መጥፎ ስነምግባር ስራዎችን በሕዝብ ላይ እያሰራጨ ከኖረ በሀላ አንድ ቀን፣ ጥምቀት ቀን ሕዝቡ በሚሰበሰብበት ወቅት በንቦች ተነክሶ ሰውነቱ አብጦ ይሞታል። ጓደኛው አባ ወልዱ የተባለው ሌላ ቄስ የሚስቱ ወንድም ነኝ በማለት ንብረቱንና ሚስቱን ይወርሳል፣ አቡነ ማሳያ ራሱ ወደ አቋቋመው ፍ/ቤት ችሎት ጠርቶ ይፈርደዋል፣ የተከሰሰበትም፣ 1ኛ. የክህነት ማዕረግ የለውም 2ኛ. ክርስትናም አልተነሳም 3ኛ. የአንድ ቄስ ባሪያ ስለነበረ እንደ ዝንጀሮ ከጌታው



እንዳንድ ነገር የሀይማኖት ስራና የቄስ ስራ ተማረ፣ በዚህ ምክንያት ቄስ ለመሆን በቃ 4ኛ. አንድ ልጃገረድ ጠልፎ ከወሰደ በኋላ ከዘመዶቿ ጋር ተስማምተው ገንዘብ ከፍሎ ባሪያ አድርጎ ሲኖር አንድ ቀን ከወንድ ተኝታ እጅ ከፍንጅ ስላገኛቸው ሁለቱም በአንድ ጉድጓድ አብረው ተቀብረው በጉንዳኖች ተበልተው እንዲሞቱ በማድረጉ፤ አባ ወልዱ ቄስ ባለመሆኑ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ተላከ፡፡ ይህ ከአንድ አቡን ወይም ቄስ የሚጠበቅ ሥራ አይደለም፣ በፈረንጆች ቃል የአንድ አድቨንቸረር / Adventurer / ስራ ሊባል ይችላል ፡፡ የራሱ ቄሶች እንኳን እንደፈለገ ማድረግ ይችላል የሌላ ሀይማኖት ቄሶች ግን መብት የለውም

አባ ፍስሐ የተባለው የካቶሊክ ቄስ የነበረው ወንጀሉ በሙሉ ሳይዘረዝር በሕዝቡ ፊት እንዲወገድ ብሎ ፈርዶበታል።

አቡነ ማሳያ በቄሶቹ ላይ የፈፀመው ሌላ ሕገወጥ ተግባር የክህነት ማእረጋቸውና ጥምቀታቸውን አጠራጣሪ በማድረግ እንደገና ክርስትና ማንሳት እንደገና ማዕርገ ክህነት መስጠት ነበረ። ይህ የተደረገው አባ ኃይሉና አባ ያዕቆብ የተባሉ አስቀድሞ የአርቶዶክስ ቄሶች የነበሩ በኋላ ግን ሀይማኖታቸውን ቀይረው ካቶሊክ በመሆን ብዙ ዓመታት ከሰሩ በኋላና ብዙ ሰዎች ካጠመቁ በኋላ ነው ። በነገራችን ላይ አቡነ ማሳያ አርቶዶክስ የሚል ቃል ተጠቅሞበት አያውቅም፣ የሚጠቀምበት ቃል"ሄሬቲክ" በማለት "አፈንጋጭ ከእውነተኛ ሐይማኖት የተገነጠለ" በሚል ቃል ነበረ የሚጠቀመው። አቡነ ማሳያ በከፋ በጥሩ ሁኔታ አልነበረም የወጣ፣ ከከፋ ለመውጣት ተከልክሎ ነበር። ሌላ ሕገወጥ ተግባር የአቡነ ማሳያ በከፋ የሚኖር ክርስቲያን ሁሉ ኃላፊ እንደመሆኑ መጠን ከሕጋዊ ሚስት ሌላ ባሪያ ሴት ወዳጅ ያላቸው ወንዶች ሁሉ ባሪያን መሸጥ መስወጥ በክርስትና እምነት የሚከለከል ሕግ በመጣስ እንዲሸጥዋቸው አስገድዶ በአንድ ሚስት ብቻ እንዲወሰኑ ማድረግ ነበረ። አገሰት1861 ዓ ም ከፋ አቡን እንደማያስፈልጋት የሀገሩ ምሁራን ለከፋ ንጉሥ ስለተናገሩ ከሀገር እንዲወጣ ተደረገ ። ጉዞውም በድንገት እንዲጀምር ተገደደ። ምንም ነገር ይዞ እንዲሄድ አልተፈቀደለትም። በታጠቁ ወታደሮች የውሻ ራስ በስጦን ባሮች ተሸክሞት እየተከተሉት፣ ከበኋላው የዝንጀሮ ቆዳ ባርኔጣ በጠንቋይ ደም የተሞላበት በአንድ ድስት እጁ ይዞ ደም እየረጨ ፣ሰው እንዳይጠጋው በአርባ ማንጂዎች ጎሳዎች ተከቦ ነበረ ጉዞውን የሚያደረገው ፡፡ ማንጂዮ የተባሉ ጎሳዎች ሰው ከተጠጋቸው ስለሚረክስ

ሰው አይጠጋቸውም ፡፡ አቡኑ ወደ ጊራ እንዲወስዱት ይጠይቃል፣ አይፈቀድለትም፣ ወደ ጅማ ካካ ወይንም ጅማ አባጅፋር ስመሻገር በግ ይታረዳል: ወደ ውሻው ራሳ ደም ይረጫል፣ ጉጅብ ወንዝ ባለው ድልድይ ደም ይረጫል፣ በመጨረሻ ውሻው ወደ ወንዝ ይጣላል፣ ፀሎት ይደረጋል ፡፡ ወደ ጃንጀሮ ነፃ መንግሥት የካፊቾ ዋናው ቤተመቅደስ የሚገኝበት ይወስዱት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ነበር። ከብዙ ምክር በኋላ አቡኑ ለአባ በካ የጅማ ንጉሥ እንዲሰጥ እሱም ወደ ሰቃ እናሪያ እንዲወስደው ተስማምተው ሴፕቴምበር 1861 አቡኑ አድቨንቸረር በሚያሰኝ ሁኔታ ተባሮ በከፋ የመኖር ማብቂያው ሆነ።

በ1858 ዓ ም አጼ ቴዎድሮስ ወሎንና ሸዋን በተቆጣጠረበት ወቅት ወደ አሮሞ መንግሥታት ዘምቶ ለማስገበር አስቦ ነበረ። አሮሞ ሁሉ ተባብረው ወራሪውን እንዲቋቋሙ ምክር ይሰጣቸው የነበረ አቡነ ማሳያ ነበር።የአጼ ቴዎድሮስ ዘመቻ ሳይደረግ ቀረ።

አቡነ ማሳያ ከከፋ ሲወጣ ወደ ወዳጅ የአሮሞ መንግሥታት ነበረ የመጣው። መጀመሪያ ጁማ ቀጥሎም እናሪያ፣ ከዚህ ኋላ ግን የሚሲዮናውያንና ኤውሮጳውያን አከባሪ የነበረ የእናሪያ ንጉሥ አባ በጊቦ ስለሞተ አዲስ ንጉሥ አባ ቡልጉ ለንጉሣውያን ቤተሰብ መጥፎ ዕድል ታመጣለህ ተብሎ ስለተነገረው አቡነ ማሳያ በሁለት ቀን ውስጥ ከግዛቱ እንዲባረር ተደረገ። በዚህ መሠረት ከፋ ብቻ አይደለም የአቡነ ማሳያ ጠላት: እናሪያም ጠላት ሆነች። በጠቅላላ የአሮሞ መንግሥታት አንድነታቸውን አጠናክሮ ወራሪ የሐበሻ ጦር እንዲከላከሉ ብሎ ለመስበክ አቡነ ማሳያ ያስተባበራቸው ጥሰው ዋና አስተባባሪው የነበረ አባ ባጊቦም ስለሞተ እርስ በእርሳቸው በመዋጋት ሲጀምሩ የሐበሻ ጦር በቁጥጥሩ ሊያውላቸው ችላል ።

ጃንዋሪ መጨረሻ 1862 ዓ ም አቡነ ማሳያ ጋራማራ ገባ። ወደ ኤውሮጳ ለመሄድ ይፈልግ ነበር ።ደች የተረገመች ሀገር ኢትዮጵያ አቋርጦ ለማለፍ ቴዎድሮስንም አቡነ ሰላማን ለማየት ያስጠለዋል፣ ያበጨንቀዋል። የአሮሞ መንግሥታት እንዲተባበሩ በመምከር ያደረገው ሙከራ እንዳይታወቅበት ሕሊናው ይወቅሰዋል ። ለአጼ ቴዎድሮስና ለጎጃም መሪ በግዛታቸው እንዲያልፍ እንዲፈቀድለት ደብዳቤ ይፅፋል። ከሁለቱ ሰዎች ጥሩ መልስ ቢያገኝም ተደብቆ ጎጃም ይገባል። አክቶኸር 1962 ዓ ም ጎጃም ከኢትዮጵያ የተለየ ሀገር እንደሆነች በመገመት እስከ ሜይ63 ዓ ም በጎጃምና በአበሻ ሀገር (ጎንደር) መካከል ለ1 ዓመት ዋሻ ውስጥ እንደ ባህታዊ ሆና ኖርኩ ይላል። ከዚህ በኋላ በድብቅ ኢትዮጵያን አቋርጦ ምጽዋ ለመድረስ ጉዞውን ይቀጥላል። ጎንደር ናጋሌ እንደደረሰ በድንገት በወታደሮች ተከቦ ታስሮ አጼ ቴዎድሮስ ወዳለበት በመወሰድ ጉዞውን ይቀጥላል ። የታሰረበት ምክንያት የአሮሞ መንግሥታት በአጼ ቴዎድሮስ እጅ እንዳይገቡ እንዲተባበሩ ባደረገው ቅስቀሳ እንዳይሆን ብሎ ይጠራጠራል ።ነገር ግን ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ አጼ ቴዎድሮስ አንዳንድ ጥያቄዎችን ከጠየቀው በኋላ አቡኑና ተከታዬቹ በሙሉ እንዲፈቱ አዝዞ አስፈላጊውን እርዳታ ምግብ፣ መጠለያ እንዲሰጣቸው በማዘዝ ያስናብታቸዋል ። አቡነ ማሳያ ከመዓት ያወጣው አምላክ በማመስገን ፋንታ ፀረ ኢትዮጵያ ሐንጎሉ ሲጉላላ የነበረው አስተያየት ለመስጠት ምክንያት ሆኖበታል። ብዙ ደራሲያን ባቀረቡት ምርምር የኢትጵያ ሕዝብ ባሕልና የእጅ ፅሑፎችን በመመርመር ኢትዮጵያ በአሪት ጊዜም በክርስትና ጊዜም የበለፀገ ሥልጣኔ አግኝታ

አታውቅም፣ በሀንጎል ሳይንሳዊ ስልጣኔም ቢሆን እንደ ኤውሮጳዊ ሳይንሳዊ ሥራዎች በጥልቀት ሲመረምር የሚገኘው ነገር ባዶ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር ኢትዮጵያ ሌላ ሳይንሳዊ መጽሐፍ የላትም። ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር ሌላየተጻፈ መጽሐፍ የለም። የኢተዮጵያ ታሪክ የባሕል ብልፅግና አብሮ የመኖር ስነ ሥርዓት ሰፍና ስለማያውቅ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤትም ተመስርቶ አያውቅም ።ኢትዮጵያ በአንድ የተወሰነ ሳይንስ ክፍል ምርምር ያደረጉ ግለሰቦች የሉም፣ ጥቂት የእጅ ጽሑፎች ከምሥራቃውያን የክርስትና ሐይማኖት አባቶች የተቀዱ ናቸው። በሕዝብ ቋንቋ የተፃፈ ካባልስቲክ የዕብራውያን እምነት ፍልስፍና ሌሎችም የጥንቆላና የአስቂኝ ነገሮች ናቸው።

ይህ አስተያየት የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ የውጭ ሀገር ሰዎች ስልጣኔ ያለውን ሕዝብ ለመፍጀት ነው የምትሄዱ ብለው የወቀሷቸው እንደተሰሚነት ያለው ሰው ገለልተኛ የእግዚአብሔር ሰው ማስረጃ ሆኖላቸዋል።

ጁላይ 20 /1863 ዓ ም ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር ተሰናብቶ ጉዞውን ወደ ምፅዋ ይቀጥላል ። ጉዋላ ትግራይ ሲደርስ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ሰዎች ባየ ጊዜ ነፍሳቸው



ካቶሊክ ፣ሥነ ሥርዓታቸው ኤሬቲክ አፈንጋጮች በማለት ደንበኛ ካቶሊክ መሆናቸው ይጠራጠራል ።ትኩንዳዕ ሲደርስ የጥንት ከተማ ፍርስራሶች ባየ ጊዜ የወደቡ ገዥዎች (አዱሊስ) የሰሯቸው ሀንፃዎች ናቸው በማለት አስተያየቱን ይሰጣል። ምፅዋ ደርሶ ስለ ረጅም ጉዞው ጥያቄ ሲያቀርቡለት አጼ ቴዎድሮስ ከእኔ ጋር ተቀመጥ ብሎኝ ነበር እኔ ግን አልተቀበልኩትም ብሎ በሚያወራበት ጊዜ በምፅዋ የነበረ የካቶሊክ አቡን ለምን እንቢ አልክ ለካቶሊክ ሚሲዮናውያን ይጠቅም ነበር ብሎ በጠየቀው ጊዜ፣ የአበሻ ሕዝብ እንደ ሕፃን ነው፣ አንድ ሕፃን ያለቅሳል፣ ይጮሀል አንድን እቃ ለማግኘት፣ እቃውን ካገኘው በኋላ ግን ይወረውረዋል ፣እኔም እንደዚህ ያጋጥመኝ ነበረ ብሎ ከመለሰለት በኋላ አንተ ከእኔ የበለጠ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጠሕ እንዴት ፀባያቸውን አታውቅም ብሎ ይንቀዋል። ይህ በሁለተኛው ጉዞው በአፍሪካ በተመደበበት በጋላ ሀገር የተቀመጠበት ፖለቲካና ሐይማኖት ድብልቅ እየሰራ 10 ዓመት ብቻ ከአሮሞ ሀገር ያሳለፈው ጊዜ ነበር ፣ግን 15 ዓመት የተቆጠረለት 5ዓመት ያሳለፋቸው ግን በጉዞ ነበር

## አቡነ ማሳያና የሳርዲኒያ መንግስት

ከዚህ ጊዜ በኋላ አቡነ ማሳያ በሙሉ ያሰለፈው በፖለቲካ ነው ለማለት ይቻላል። አቡነ ማሳያና የሳርዲኒያ መንግሥት አቡኑ በአሮሞ ሀገር በኖረበት ዘመን የኢጣሊያ መንግሥት ስላልነበረ የሳርዲኒያ ዜጋ ተብሎ ነበረ የሚታወቀው፣ ለሀገሩ መንግሥት በቀጥታ ሆነ ራሱን በወኪሉ ባባሌዮን ዳቫንቸር ፖለቲካ ነክ ሥራዎች እስከ 1859 ዓ ም ድረስ አካሒዷል ። ያከናወናቸው ሥራዎች በጳጳሱ ትእዛዝ በደረሰው የሕይወት ታሪኩ መጽሐፍ ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች እንዲገለፁ አልተፈለጉም ነበር፣ ምክንያቱም የሳርዲኒያ መንግሥት የጳጳሱን ግዛት በኃይል ወስዶ ከግዛቱ ቀላቅሎ አንድ የኢጣሊያ

መንግሥት በመመሥረቱ ሁለቱ መንግሥታት በጠላት ዐይን ይታዩ ስለነበረ ነው።

አቡነ ማሳያ በመጽሐፉ ባይገልፅም በፃፋቸው ደብዳቢዎች ለሀገሩ መንግሥት ያከናወነው ለመረዳት ይቻላል። የመጀመሪያ ደብዳቤ ከአቡነ ማሳያ

የተፃፈው ጃኗሪ15/1857 ነበረ። በመልስም አቡኑ በሚቀጥለው ዓመት ፋብራሪ 1 ቀን 1958 ነበረ ከሁሉም ኃይለኛ ከሆነ የኢትዮጵያ መስፍን ውል ለመፈራረም የሳርዲኒያ መንግሥት ያለው ፍላጎት ሲገልፅለት አቡነ ማሳያ የሚያውቃቸውን ወዳጅነት ያለው ብዙ የአሮሞ መንግሥት አለው፣ ነገር ግን ከነዚህ መንግሥታት ውል ማድረግ ምንም እንኳን ሐብታም ቢሆኑ የባሕር በር ስለሌላቸው ጥቅም የለውም፣ በሐበሻ ሀገር ወደ እነዚህ ሀገሮች ለመግባት በሚካሄዱት የማያቋርጡ ጦርነቶች ምክንያት የማይቻል ነው።

በአበሻ ሀገር በአቡነ ደ ያቆቢስ በኩል መሞከር ይቻላል። መንግሥታችን ትንሽ ጊዜ ከታገስ ግን ሶስት ሚሲዮናውያን ከዛንዚባር ወደ ወላም የሚመጡ ስላሉ ከአባ ሊዮን ግንኙነት ማድረግና አቅድም እንዲሰምር የሳርዲኒያ መንግሥት እርዳታ ማድረግ ይገባዋል። 2-3 ዓመት በኋላ በደቡብ በመጀመሪያ ወደ ወላሞ ከዚያም ወደ ኩሎ መድረስ ይቻላል። ከጉድሩ እስከ ከፋ ያለው መንገድ ተመቻችቷል በሚቀጥሉ ዓመታት አቡነ ማሳያ በቀጥታ ከሳርዲኒያ

መንግሥት ግንኙነት እጸቁም አባ ሊዮን ከሳርዲኒያ መንግሥት በአቡኑ ሥም ይዋዋፍ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ፌንሯሪ 12 ቀን 1859 አባ ሊዮን በቀጥታ ከጠቅላይ ሚኒስትር ካቩር ደጃዝማች ንጉሴ ካሰበት ቦታ ሄዶ በፃፈው ደብዳቤ በአቡነ ማሳያ ትዕዛዝ የሄደ መሆኑን ጠቅሶ ሲፈረም የታሰበው ውል አቅርቦ እንደነበረ ገልፆ ውሉም በደጃዝማች ንጉሴ ተቀባይነት እንዳገኘ ጽፏል ፡፡ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ሰፋሪዎች ምቹ እንደሆነች ገልፀዋል፡፡ ደጃዝማች ንጉሤም ለሣርዲኒያ ንጉሥ ደብዳቤ ፅፎ ነበረ፡፡ ሙከራው ውጤት ሳያገኝ የቀረው በሚስዮናውያን ምንኩሴዎች ችሎታ ማነስ ነው ብለው የተረጎሙት ሰዎች ነበሩ ምክንያቱም ሚሲዮናውያን የተጠየቁት በኢትዮጵያ ከሚገኙት መሳፍንቶች ከሁሉም ኃይለኛ የሆነው ጋር በሳርዲኒያ መንግሥት ስም እንዲፈራረሙ ነበር ፡፡ ከሁሉ ኃይለኛ የነበረ ደግሞ ደጃዝማች ንጉሤ ሳይሆን አጼ ቴዎድሮስ ነበር ፡፡ከሁሉም የሚበልጠው ሚሲዮናውያን ምንክሲዎች ረዳታቸው ንጉሤን በመምረጥ ጠላታቸው አጼ ቴድሮስን ሳያስታውቁ ቀሩ ተብለው ተወቅሰዋል ነገር ግን ወቀሳው ትክክል እንዳልሆነ አባሊዮን አፕሪል 2 1859ዓ ም ለካቩር በፃፈው ደብዳቤ ያሳያል ፡፡በዚህ ደብዳቤ ከደጃዝማች ንጉሴ ከተገናኘ በኋላ ከአጼ ቴዎድሮስም ጋር ተገናኝቶ ለንጉሴ የቀረበው ውል አቅርቦለት ነበር፣ አጼ ቴዎድሮስ ከማንኛውም ኤውሮጳ መንግሥታት ውል ማድረግ ዝግጁ ነበር ሆኖም ስለ ሐይማኖት ነፃነት ከሚሲዮናውያን ጋር አይስማማም፣ በመቀጠልም አባ ሊዮን በደብዳቤው ላይ አጼ ቴዎድሮስ በፖለቲካ በኩል የኤውሮጳውያን አስተሳሰብ ያለው ድንቅ ሰው መሆኑን ገልፆ 60. 000 የሚገመት ጦር የኤውሮጳ መኮንኖች አሰልጣኞች ያስፈልገዋል የአውሮጳ የእጅ ባለሞያዎችም ያስፈልገዋል፡፡ ደፋርና የውትድርና ሙያ ሰላለው ንጉሤ ሊቋቋመው እንደማይችል ጠቅሶ ጽፏል፡፡

## የአቡነ ማሳያ 3ኛ ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ

አቡነ ማሳያ ወደ ሸዋና ወደ ኦሮሞ ሀገር መግቢያ መንገድ በዛንዚባር በኩል የማይታሰብ መሆኑን በተረዳ ጊዜ፣ በምሥራቅ በኩል በዛሬዎቹ ጅቡቲ

ወይንም በሜን ሶማሊያ ለመግባት ለመሞከር አፕሪል 15 /1866 ወደ አፍሪካ ጉዞውን ጀምሮ ምፅዋ ሲደርስ በአቡነ ደ ያኮቢስ ቦታ ተሸሞ የመጣ ከፈረንሳዊው አቡነ ቢል ይገናኛል፡፡ ከአዲሱ አቡን ጋራ ግጭት ይፈጥራል፣ ምክንያቱም አዲሱ አቡን ልክ እንደ ኤውሮጳውያን ለኢትዮጵያውያን ትምህርት ቤት ለመክፈት ይፈልጋል፡፡ አቡነ ቢል ወጣት ኢትዮጵያውያን እንደ ኤውሮጳውያን እኩል አያያዝ እንዲደረግላቸው እንደሚገባ ሲያስብ፣ አቡነ ማሳያ ግን ይህ የማይሆን ነው ብሎ ተቃወመ፡፡ አቡነ ደ ያኮቢስ እንደሚያደርገው ትምህርት መክፈት ጥሩ ታማኝ የሀገሩ ተወላጆች የሃይማኖት ሰባኪያን እንዲሆኑ ማስተማር ብቸኛ ጥሩ ዘዴ ስለሆነ አቡነ ቢል ላቀረበው ሀሳብ የተሳሳተ ነው ለማለት እቅዱ ውድቅ እንዲሆን አደረገው፡፡ በዋና መ/ቤት ተደማጭነት የነበረው አቡነ ማሳያ ብቻ ነበረ፣ እሱ ጥሩ ነው የሚለው ሁሉ ጥሩ ነው መጥፎ የሚለው ሁሉ ደግሞ መጥፎ ነው፡፡ የአቡነ ቢል እቅድ በምፅዋ አጠገብ ለኢትዮጵያውያን ትምህርት ቤት መክፈት ሙከራው የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ሦስተኛ ጊዜ ነው ፣በመጀመሪያ ደጃዝማች ውቤ ለኢትዮጵያውያን ትምህርት ቤት እንዲከፈት የሚል ለፈረንሳይ መንግሥት ያቀረበው ሀሳብ እንግሊዞችን በመፍራት ከፈረንሳይ መንግሥት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፤



ለሁለተኛ ጊዜ በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንሲል በምፅዋ አጠገብ ትምህርት ቤት እንዲከፈት ላቀረበው ሐሳብ ሞንሲኞር ደ ያኮቢስ ኢትዮጵያዊ ስሙ አቡነ ያዕቆብ ከነበረው ዓላማ የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋት ከሀገሩ ሰዎች ማስልጠን ካልሆነ በስተቀር የሕዝብ ትምህርት ቤት መክፈት ከዓላማው ውጭ ስለሆነ ውድቅ ሆኖ ቀረ፣ ሦስተኛ ጊዜ በነፃነት በወንድማማችነት እኩልነት የምትመራ ፈረንሳይ ወኪል የሆነው አቡነ ቢል እንደ ቆንሲል ደግሞ ተመሳሳይ የሆነ በምፅዋ አጠገብ ለኢትዮጵያውያን ት/ቤት እንዲከፈት ያቀረበው ሃሳብ ካርዲናል ማሳያ ኢትዮጵያዊ ስሙ አቡነ መሲያስ እንድ አቡነ ያዕቆብ የካቶሊክ ሃይማኖት ለማስፋፋት ለቄስነት ትምህርት ቤት ለሀገር ተወላጆች ማደራጀትና ማሰልጠን ብቸኛ አማራጭ ነው ብሎ በመውሰድ ውድቅ ስለአደረገው፣ የፈረንሳይ ቋንቋና ባሕል በሀገራችን እንዳይመሰረት አድርገዋል፤ ይኸም ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ትምህርትን በመከልከል ካደረሰብን በደል ተመሳሳይ ነው

በዚህ መሠረት በኢጣሊያ ሚሲዮናውያን ዘረኞች እጅ ልንወድቅ ችለናል፣ ቀጥሎም የኢጣሊያ ቀኝ ገዥዎች ወረው ሊይዙን ችለዋል፡፡ ደ ያኮቢስና ማሳያ ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ማስፋፋት ያደረጉት አስተዋጽኦ የኢጣሊያ ዘረኞች ኮርቶባቸዋል፡፡

ከርዲናል ማሳያ በኦሮሞ ሀገር የካቶሊክ ሃይማኖት የሚሰብክ ወደ ፈረንሳይ ሀገር ወስዶ ማስልጠን እቅድ አወጣ[1] ለዚህም ምፅዋ ከደረሱ ሊሸጡ የተዘጋጁ ባሮች ኦሮሞ የሆኑ እየመረጠ ለመመልመል ነበረ ፡፡ 10 ባሮች ኦሮሞዎችን ገዝቶ

ወደ ግብፅና ፈረንሳይ ሀገር ይልካቸዋል ፤ፈረንሳይ ሀገር ሲደርሱ ከነጮች እኩል ሳይሆን ሰብቻቸው ተይዘው ስልጥነው ቄስ ሆነው ወደ ሀገራቸው ተልከው የካቶሊክ ሃይማኖት ወንጌል ሰባኪያን እንዲሆኑ ነበረ ፡፡ ለዚህም መሬት ተገዝቶላቸው ነበረ፣ ቤትም ተሰርቶላቸው ነበረ ፡፡ ነገር ግን እቅዱ አልተሳካም፣ እቅዱ እንደከሸፈበት የሚያሳይ ከዚህ በኋላ ስለነዚህ የጣቶች ትምህርት ቤት በመጽሐፉ ያለው ነገር የለም፣ እቅዱም እንደሚከሽፍ አስቀድሞ የታወቀ ነገር ነው፣ ምክንያቱም ዘረኝነት ከፈረንሳይ ሀገር ተቀባይነት እንደማያገኝ የታወቀ ነገር ነው፡፡

አቡነ ማሳያ በዘይላ በኩል ወደ ሸዋ ለመግባት ፈልጎ ለንጉሥ ምኒልክ ፈቃድ እንዲሰጠው ጠይቆ መልስ በመጠባበቅ እንዳለ ዘይላ ሄዶ ከሀገረ ገዥው ከኤሚር አቡበከር የጦር መሣሪያ ለማቀበል ሌላም ለመስጠት ወደ ሸዋ እንዲገባ እርዳታ እንዲደረግለት መስማማት ጀመረ ፡፡ በዝግጅት እንዳለ ግን በኤውሮጳ ፀረ- ሐይማኖተኛ፣ ፀረ- ሮም ጳጳስ ከሆነው አቡነ ማሳያ ከሳርዲኒያ መንግሥት ተስማምተዋል የሚል ወቀሳ ተሰንዝሮብሀል የሚል ወሬ ስለደረሰው ይኼንን ለማጣራት ጉዞውን አቋርጦ ወደ ኤውሮጳ ተመልሶ ሚይ 1867 ሄዶ ሮማ እንዳለ የንጉሥ ምኒልክ ወደ ሸዋ እንዲገባ ፈቃድ ይደርሰዋል፡፡

## የአቡነ ማሳያ 4ኛ ጉዞ ወደ ኢትዮጲያ፣

አቡነ ማሳያ 4ኛ ጉዞውን ለመጀመር ሴፕቴምበር 1867 ከማርሰይ ወደ እስክርድሪያ ጉዞውን ጀመረ፡፡ እንግሊዝ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመቻ የሚዘጋጅበት ወቅት ነበረ፡፡ ለንጉሥ ምኒሊክ ከእንግሊዝ መንግሥት የተላከ እንዲያደርስላቸው

[1] Difesa Della Razza A 2 N14

ከእንግሊዞች ደብዳቤ ተሰጥቶት ከአቡበከር ጋር ከጠየቀው አንድ ሺህ ጠብመንጃ ሁለት መቶ ወዲያውኑ እንዲሰጠው ተስማምተዋል ። አንድ 100 ጉዞውን ሲጀምር 100 እንኮበር ሲደርስ። ጠብመንጃዎቹ በፈረንሳይ ቆንስላ ይቀመጣሉ። መነሻ አባቦ ከጅቡቲና ታጁራ መሀል ኦክቶበር 1867 አቡነ ማሳያ ወደ ኦሮሞ ሀገር ለመሄድ እንደሚፈልግ ማስመሰል ፍላጎቱ ግን ሸዋ ለመቀመጥ ነበረ፣ ምክንያቱም ከኦሮሞ ሀገር ተባርሮ ነበረ የወጣ፣ ቢመለስም ችግር እንደሚገጥመው አሳምሮ ያውቅ ነበር ።

ምኒሊክ በቃሉ ወደ ኦሮሞ ሀገር ትሄዳለህ ይለዋል ፣በተግባር ግን ለዓላማው ሊጠቀምበት ስለሚፈልግ እንዳይሄድ እያዘገየው ነበረ። በዚህም ሁኔታ ተስማምተው ሊኖሩ ችለዋል። ምኒልክ ማሳያን የተመለከተ እንደ መንፈሳዊ ሰው ሳይሆን እንደ ፖለቲካዊ ሰው አማካሪ ነበረ። ምኒልክ በሕፃንነቱ ኃይለመለኮት የመጀመሪያ አባቴ አጣሁ ከኀረመስኩ በኋላ ሁለተኛ አባቴ ቴዎድሮስ አጣሁ ፣አሁን እርስዎ ሦስተኛ አባት እንዲሆኑኝ እፈልጋለሁ በማለት ለአቡኑ ሲነግረው ለማስመሰል ያሀል አቡነ ማሳያ እኔ ወደ ኦሮሞ ሀገር እሄዳለሁ ሌላ አባት አቡን ቱረን እተውልሃለሁ ብሎ መልስ ይሰጠዋል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ምኒልክ ይህን ሁሉ የምትመከረኝ በፅሑፍ ብታረግልኝ ብሎ በጠየቀኝ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲጠይቀኝ ሳልጠብቅ የማኪያቬሊ ዓይነት መጽሐፍ አዘጋጀሁለት ብሎ

በመፅሐፉ ያሰፍሯል። ማኪያቬሊ "ፕሪንቺፔ" በሚል አርእስት በደረሰው መጽሐፍ በመጥፎነቱ በዓለም ተዋቂነት ያተረፈው መጽሐፍ፣ አንድ ገዥ ወይም የሀገር መሪ በጭካኔ ዜጎቹን መስተዳደር አለበት፣ ርሕራሄ፣ ደግነት የሞኞች ሥራ ነው ፣በሚል አስተሳሰብ የተመሰረተ መጽሐፍ ነው።

የአቡነ ማሳያ ለምኒልክ የአማካሪነት ተግባር የዚህ ዓይነት ሲመስል፣ ደግነቱ ግን ምኒልክ የማኪያቬሊ ትምህርት በሥራ ላይ አላዋለውም። የአቡነ ማሳያ ሕይወት ታሪክ ፀሐፊ ግን መጽሐፉ በመጥፋቱ ለዓለም ስልጣኔ ትልቅ ሀዘን ነው ብሎታል። ለኢጣሊያ ታሪክ ለዓለም ስልጣኔ መምህር ተብሎ እንደማስረጃነት ሊጠቀስ ይችል ነበር ብሎታል ። አብነ ማሳያ የንጉሥ ምኒልክ አማካሪ በመሆን በየቀኑ ወደ ግቢ እየተጠራ ምክሩንና አስተያየቱን ይሰጥ ስለ ነበረ እንደውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይቆጠር ነበረ። ንጉሥ ምኒልክ ወደ አቡነ ቤት እየሄደ ይመካከሩ ነበረ። የውጭ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥም ሚኒሥትር ነበረ፣ የፍርድ ሚኒስትርም ስለነበረ የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ገብቶ እንደነበር ማለት ይቻላል ።ይህ በመሆኑ የሚሲዮናውያን ቤት በባለ ጉዳዮች ተጨናንቆ ይውል ነበረ ።

ንጉሥ ምኒልክ ግን ከአጼ ቴዎድሮስ በጭካኔ ለማስተዳደር ሥራ መጥፎነቱ አልተማረም። አቡነ ማሳያ ሸዋ እንደገባ መጀመሪያ ሐሳቡ ለሚስዮናውያን መሬት ማግኘት ነበረ። በዚህ መሠረት ራሳቸው ሚሲዮናውያን ፈልገው መርጠው ያገኙት መሬት ፊንፊኔ አካባቢ አስር ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው መሬት፣ ሃያ ገባር ቤተሰቦች የሰፈሩበት ተሰጥቷቸው፣ ቤትና ቤተክርስቲያንን ሰርተው ይኖሩ ነበረ። ይህ ሁኔታ የኢጣሊያ ቀኝ ገዥዎች አዲስ አበባ በጣሊያን ዜጎች የተቆረቆረች ከተማ ብሎ እንዲኮሩባት ምክንያት ሆኖዋቸው ነበረ። የተቆረቆረችውም በ1868 ዓ ም ነበረ። አቡነ ማሳያ በኦሮሞ ሀገር ቀደም ብሎ የመሰረታቸው የሚሲዮናውያን ሰፈሮች ምዕራብ ሸዋ፣ ወሊጋ፣



ጅማ፣ ከፋ፣ ግንኙነት በመፍጠሩ ለምኒልክ ሀገሮቹን ሊያውቃቸውና ወር እንዲያስገብራቸው ምክንያትና መሪ በመሆኑ አቡነ ማሳያ በቁጭትና በሐዘን ያስታውሰው ነበረ።

አቡነ ማሳያ ግን ንጉሥ ምኒልክ ወደ ጋላ ሀገር እንዳልሄድ ከለከለኝ በማለት ወደ ሀገረ ስብከቱ ሳይሄድ ሸዋ በመቀመጥ የምኒልክ አማካሪ ለመሆን መረጧል። ከአጼ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ንጉሥ ምኒልክን ንጉሠ ነገሥት ለማድረግ አቡነ ማሳያ ያልሞከረው ነገር አልነበረም። 1ኛ/ ወደ መትደላ ሄዶ ከእንግሊዞች ጋር እንዲገናኝ ቢጎተጉተው ምኒልክ የአቡኑ ምክር ባለመቀበል ሳይሄድ ቀረ 2ኛ/ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ወደ ትግራይ ሄዶ ከበስበስ ካሳ ጋራ በሚወጋበት ጊዜ ምኒልክ ጎንደርን እንዲይዝና ንጉሠ ነገሥት እንዲባል ቢመክረው ከሚስቱ ከበፈናጋ መለየት ስላልፈለገ ከሸዋ አልተንቀሳቀሰም። በዚህ ምክንያት አቡነ ማሳያ በከፍተኛ ሐዘን ተውጦ ነበረ። አቡነ ማሳያ ንጉሥ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለማድረግ ባይሳካለትም ከኤውሮጳ መንግሥታት ግንኙነት እንዲፈጥር ምክር መስጠት ቀጥሎ ነበረ። በተለይ ከኢጣሊያ መንግሥት የፈጠረው ግንኙነት ወሳኝነት አለው። አቡነ ማሳያ አሁን የሚፈልገው የመጣበት ጉዳይ የሐይማኖት ለመስበክ ሳይሆን የፖለቲካ ሥራ በመስራት ነው ለማለት ይቻላል። ወይንም በፖለቲካ ተጠቅሞ ሐይማኖትን ማስፋፋት ነበር። አብዛኛዎቹ ሰዎች የአጼ ቴዎድሮስ ጭካኔ ሲያወግዙና

ሲያንገበግባቸው አቡነ ማሳያ ግን ደጋፊና የሚያደንቀው ነበር። አድናቆቱም በሁለት ምሳሌዎች ይገልፀዋል 1ኛ ፀረ-ሙስሊም ሃይማኖት በመሆኑ ኢትዮጵያ በሞላ በቁጥጥር አውሎ ወደ ጎንደር ሲመለስ ግማሽ የጎንደር ከተማ የነበረው በጎንደር የእስላሞች መንደር እቃጠለው። ከዚህ በኋላ ወደ ደረታ የምትባለው ጎንደር አጠገብ የምተገኘው መንደር የመሐመድ ግራኝ መቃብር የሚገኝበት በማምራት መንደራቸውን እነዳያወድምባቸው እስላሞች 15.000 ብር ለመስጠት ይሞክራሉ። ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ አልተቀበላቸውም። እስላሞች ገንዘቡን እጥፍ አድርገው በተጨማሪ ለአቡነ ሰላማም ገንዘብ በከፈሉ ጊዜ፣ አቡነ ሰላማ ይህ መንደር እንዳይቃጠል ለአጼ ቴዎድሮስ ምክር ሰጠው ምክንያቱም ገንዘብ በሚያስፈልግበት ጊዜ ገንዘብ ሊያስገኝ ይችላል፤ ደረታን ከማቃጠል ይልቅ ከካቶሊክ ሃይማኖት የሚስማማ ደብረ ሊባኖስ ገዳምንና ንጉሣቸው ኃይለመለኮትን ማውደም ይበጃል ብሎ ይመክረዋል። አጼ ቴዎድሮስ በተሰጠው ምክር ቢገረምም አቡነ ሰላማን እንዲደሰትለት ያሰበው ሥራ 50.000 ብር ተቀብሎ እስላሞችና ክርሲቲያንም በአንድ ላይ ጋብዞ በሬዎች በእጁ እያረደ በሙሉ እንዲበሉ ያደርጋቸዋል፣ የማኪያቬሊ ፕሪንቺፔ መጽሐፍ ለምኒልክ እንደ መመሪያ የሰጠው አቡነ ማሳያ ጭካኔ ያደንቃል እንጂ አያወግዝም ።

2ኛ ምክንያት አቡነ ማሳያ ቴዎድሮስን የሚያደንቀው የራስ ዐሊ ልጅን ህጋዊ ሚስት አግብቶ በመወሰኑና ለሌሎች ሹሞች አንድ ሚስት ብቻ በመያዝ ምሳሌውን እንዲከተሉ በማድረግ ነበር። በዚህ ጊዜ አቡነ ማሳያ ለቴዎድሮስ ከላጋማራ የጻፈው ደብዳቤ እንደሚከተለው ነበር። "እንዴት ጥሩ አጋጣሚ ነበረ ኢትዮጲያን ለማዳን ከእግዝአብሔር የተላከ ነው ከእሱ ጋራ አብሬ ብሰራ ፣ ከእሱ ጎን አልለይም አሊቃዬን አደርገው ነበረ፣ ዝቅተኛ ባሪያው እሆን ነበር፤ ይህ ለማድረግ ግን "ኤሬቲክ "የሆነ ሃይማኖቱን ከድቶ ወደ ካቶሊክ ሐይማኖት መምጣት አለበት።"

አቡነ ማሳያ በአጼ ቴዎድሮስ ያልተሳካለት ዓላማ በምኒልክ ይሞክራል ።አቡነ ማሳያ የሚያሳየው ምኒልክ የቴዎድሮስ ልጅ ሆኖ የሱ የተፈጥሮ ጀግንነት

የደፋርነት የጭካኔ ስጦታ ባለመግሩ ነበር። የእንግሊዝ ጦር ወደ መቅደላ በተጠጋ ጊዜ ምኒልክ በአቶ ኀበና የሚመራ ጦር ወደ በቃው ልኮ ነበር፤ እንግሊዞች መቅደላ በገቡበት ቀን ግን ፋሲካ ሀገሩ እንዲውል በሚል ሰበብ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ጦሩ የተመለሰበት ዋናው ምክንያት ግን ሌላ ነበረ፤ ይህውም ምኒልክ ለአቡነ ማሳያ ቢያካፍለው እንዲህ ብሏል ቴዎድሮስ በአባቱ ሞት በልጅነቱ ወስዶ አሳድጎታል አስተምሮታል አልጋወራሽ አድርጎትም ነበር፤ ምኒልክ ሸሽቶ ሲጠፋ ለቴዎድሮስ ከባድ ሐዘን ነበረ፤ ተቀይሞም ይሆናል ይኼም ምኒልክ ምንጊዜም የቴዎድሮስ ፍቅር እንደነበረው ያሳያል፤ ቴዎድሮስ ይሙት እያለ ነበረ የሚምለው ።እንግሊዞች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ አማካሪዎች ብቻ አልነበሩም ሸዋ ከእንግሊዞች ጋር እንዲተባበር የማይፈልጉ የነበሩ፤ ራሱ ምኒልክ አይፈልግም ነበረ። ቴዎድሮስ ተሸንፎ ሸዋ ቢገባም እንግሊዞችን ፈርቶ ሊከላከል አይደፍርም ነበር። ምኒልክ ከእንግሊዞች ጎን ተሰልፎ ቢሆን ኖሮ እሱ ነበር ንጉሠ ነገሥት የሚሆነው ከአፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ግን ቀግሹም ጎበዜና በሰበሰ ካሳ ለስልጣን ሲሯሯጡ ምኒልክ የአቡነ ማሳያን ምክረ ጆሮ ዳባ በማለት አልተንቀሳቀሰም ።በአቡኑ አነጋገር ከባፋና ጎን መለየት አልፈለገም። ምኒልክ በጦር ሜዳ በጀግንነት ሲፋለም ያልቻለበት ትልቅ ድግስ በማዘጋጀት የበላይነቱን ለማሳየት ሞክሮ ነበር። በድግሱ 300 መቶ በሬዎች ታረዱ፤ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተጋበዙ፤ እሳላፊዎች ብቻ 200 ሰዎች ነበሩ። በሰበሰ ካሳ በመድፍ ሲያሸንፍ እኔ በጠላ ፤ በጠጅ ፤ በገንዝብ አሸንፋለሁ ይል ነበር። ይህ ዘዴ ብዙ አድናቆት ቢያሳድርም ንጉሠ ነገሥት ሊያደርገው አልቻለም ።

ምኒልክ በቀላሉ ሥልጣን ለመጨበጥ ሌላ ዘዴም ሞክሮ ነበር። ግብፅ በሰሜን ኢትዮጵያ በአጼ ዮሐንስ ላይ ወረራ ለማድረግ ትዘጋጅ ነበረ። በምሥራቅም በሙንዚንገር የሚመራ የግብፅ ጦር ውጊያ እንዲከፍት አቅዶ ነበረ ።የምኒልክ ጦርም በደቡብ የአጼ ዮሐንስን ጦር እንዲወጋ ለማቀናጀት ምኒልክ ከግብፆች ጋር እንዲያስማማው ከአቡነ ማሳያ እርዳታ ጠይቆ ነበረ። አቡነ ማሳያ በእስላሞች ላይ ባለው ጥላቻ እጁን ሊያስገባ አልፈለገም። በዚህ ጊዜ ምኒልክ በዘይላ ገዥ በአቡ በክር አማካኝነት ከግብፅ ጦር ስምምነት ሊፈጥር ችሎ ነበር። በዚህ ስምምነት መሠረት 1ኛ ምኒልክ ከደቡብ በወረኢሉ በኩል ደብረታቦር መድረስ ነበረበት 2 ኛ ሙንዚንገር ጋሻ በታጁራ አውሳ ሐይቅ መድረስ ነበረበት 3 ኛ ግብፆች አጼ ዮሐንስ ወደ ደቡብ ሲያመራ ትግራይን ወረው ተከዜን ተሻግረው አጼ ዮሐንስን ከምኒልክ ጦር ጋራ ተቀላቅለው እንዲወጉ ነበረ። ከድሉ በኋላ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ይሆናል፤ ነገር ግን ከጎኑ ሙንዚንገር እንዲቀመጥ ይገደዳል፤ ይህ ቅንጅት በአጼ ዮሐንስ ድል አድራጊነት ስለከሸፈ ምኒልክ እንደገና ወደ አቡነ ማሳያ በመመለስ ለኢጣሊያ ንጉሥ መልዕክተኛ ለመላክ ይወስናል፤ ይኸውም ቀደም ብሎ አቡነ ማሳያ በሰጠው ምክር መሠረት ነበረ። የመልእክተኞቹ መሪ እንዲሆን በምኒልክ የተሾመው አባ ሚካኤል የሚባል ነበር። እንደአጋጣሚ አባ ሚካኤል ከዚህ ቀደም የቤተክህነት ትምህርት ለመማር ወደ ፈረንሳይ ሀገር ማርሰይ የሚሄዱ የኦሮሞ ልጆች ግብፅ ድረስ እንዲወስዳቸው በአቡነ ማሳያ ተልኮ አድርሷቸው ነበር። ከአባ ሚካኤል ጎን አብሮ የሚሄድ የመልእክተኞች አባል አባ ሉዊጂ ጎንዛጋ ላሰር የተባለው ከፈረንሣይ ሀገር ወደ ኢትዮጲያ የኦሮሞ ልጆችን የመለሰ ቄስ ነበረ፤ እንዲሁም የመንፈሳዊ ትምህርት ወደ ፈረንሳይ ሀገር ሄደው ከነበሩ ልጆች አንዱ አብሮ የመልእክተኞች አባል ሆኖ ሄዶ ነበረ። አቡነ ማሳያ በ1872 ዓ ም ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ደብዳቤ ከዚህ ቀደም የኢጣሊያ መንግሥት ሳይመሰረት የሳርዲኒያ መንግሥት ይባል በነበረበት በ1857 ዓ ም



እቡኑ ክፋ ሆኖ ለጠቅላይ ሚኒሥትር ካቩር ከሁሉ ኃያል የሆነው ከኢትዮጵያ መሳፍንቶች በሳርዲኒያ መንግሥት ስም ውል እንዲፈራረም ተጠይቆ እንደነበረ አስታውሶ፤ ነገር ግን የማምለጫ መልስ ያህል ጠቀሞ እንድነበር ጠቅሶ አሁን ግን በሸዋ ስለሚገኝ ንጉሥ ምኒልክም በታጁራ በኩል ከውጭ መንግሥታት በቀጥታ መገናኘት ስለሚችል የኢጣሊያ መንግሥት ፍላጎት ለማሟላት ጊዜው የደረሰ መስሎ ስለታየኝ፤ ንጉሥ ምኒልክ ግንኙነት ለመፍጠር ፅኑ ፍላጎት ስላለው፤ የተላከው መልእክተኛ አባ ሚካኤል የንጉሡ ሃሳብ በሙሉ የሚያስረዳ ይሆናል ብሎ ፅፎ ነበረ ።በመልእክተኞቹ ጉዞ መሠረት በኢጣሊያ መንግሥት እና በንጉሥ ምኒልክ መሀል ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ከተፈጠረ ለሀገራችን ጥቅም የተቻለኝን ያህል ለማድረግ እንደማልቆጠብ ላረጋግጥሎት እወዳለሁ ብሏል። አቡነ ማሳያ ለኢጣሊያ ንጉሥ በፃፈው ደብዳቤ ከልጅነትዎ ጀምሬ የማውቀዎት መሆኔን ለንጉሥ ምኒልክ በገለፅኩለት ጊዜ ደጉ ንጉሥ ከግርማዊነትዎ ጋር ግንኙነት እንዲፈጥርለት ስለጠየቀኝ እኔም ሳይጠይቀኝ ፍላጎቱን ለማሟላት ግዴታ ስላለብኝ ጥሩ ሰው መሆኑን በዚህ ሀገር ከሚገኙ መሳፍንቶች ሁሉ የተሻለና ከፍተኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የምኒልክ መልዕክተኛ ወደ ጣሊያን ሀገር በሚሄዱ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያን ለመያዝ ላደረጉት ትግል እንደ አንድ መሠረተ ድንጋይ የተጣለ አድርገው ነው የሚገምቱት። ይህ የመጀመሪያ ጊዜ የምኒልክ መልዕክተኛ በኢጣሊያ ሀገር ብዙ ውዝግብና ክርክር ፈጥሮ ነበር። ጋዜጠኞች አቡነ ማሳያን አሻጥረኛና ፖለቲከኛ አቡን እያሉ ስሙን ሲያጠፉ አቡኑም የአባ ሚካኤል ስም ማጥፋት ያለው የሌለው ታሪክ ያወራ ነበር።

የምኒልክ ወንድም ነኝ ብሏል ፤አቡነ ሣሳያ ከምኒልክ የበለጠ ስልጣን አለው እያለ ስሙን ያጠፋ ነበረ።አቡነ ማሳያን ያናደደው ደግሞ በተለይ በሮም ከተማ በፀረ ሃይማኖት የሆኑ የፖለቲካ ቡድኖችና ጋዜጠኞች ተከቦ ፀረ ጳጳስና ፀረ ካቶሊክ አቋም በመውሰዱ ነው። አንዳንድ በጳጳሱ አካባቢ የሚገኙ ሰዎችም አቡነ ማሳያ መልእክተኛ ወደ ሮም እንዲላክ ለምና ተባበረ በማለት ጥርጣሬያቸውን ይገልፁ ነበረ። የአባ ሚካኤል ተልዕኮ ከንቱ ሆኖ አልቀረም በአንቲናሪ የሚመራው ከኢጣሊያ ወደ ኢኳቶሪያል ሐይቆች ለምርምር የተላከ ቡድን ወደ ሸዋ እንዲመጣ ምክንያት ሊሆን ችላል። ይህ ቡድንም የመጣበትን ተልዕኮ በመርሳት ሸዋ በመቅረቱ ኢትዮጵያን በቀኝ ግዛት ለመያዝ በእነአቡነ ማሳያ እየተረዳ ለኢጣሊያ ቀኝ ገዥዎች ዋና መሣሪያ ጣብያ ለመሆን አገልግሏል። ብዙ ጊዜ ሲወራ የምንሰማው ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣ ጠላት ሁል ጊዜ ከቀይ ባሕር ነው የሚለው አባባል አጠያያቂ ያደርገዋል። ኢትዮጵያ ለመውረር የተቀነባበረው ባለፈው ምዕተ ዘመን አብዛኛው በሸዋ በሰፈረው የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ወኪሎች አቡነ ማሳያም ጭምር አማካኝነት መሆኑን ግልፅ ነው።

## የአቡነ ማሳያ ሴራ ከሸፈ፤ በሸዋ እርስ በእርስ ጦርነት ተወገደ

አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ጦርነት ይማዘዙበት የነበረ ሁኔታ እንዴት እንደከሸፈ የተገኘው በአቡነ ማሳያ አቀራረብ ነው። እንደ አቀራረቡ በምኒልክ ላይ ሴራ የተፈፀመው በሚስቱ በበፋና የተጠነሰሰ ነበር። ንግሩ1ዋ/

አቀረበለት። አቡኑም ለዚህ መልስ ሲሰጥ እኔ ሸዋ ልኖር የቻልኩ በአፄ ዮሐንስ ፍላጎት ሳይሆን በምኒልክ ትዕዛዝ መሆኑን ገልፆ ይህ ወሬ የሚያወሩት የሁለታችን የጋራ ጠላቶች ናቸው እኔን ፍለጋ እዚህ መምጣት አያስፈልግም፣ እኔ ያለምንም ፍራት አጼ ዮሐንስ ያሉበት መሄድ እችላለሁ ልጆቼን ትቼ መሄድ ግን መሸሽ ስለሚቆጠር ክብሬን ስለሚነካ ለመሄድ ፈቃደኛ አይደለሁም የሚል ነበር ::

ቀጥሎ ምኒልክ በአቡኑ መልስ ስለተደሰተ ይቀመጡ እርስዎን ለመንካት ከመጡ የእኔ እስከሬን ረግጠው ማለፍ አለባቸው ።ነገር ግን አሁን አባታዊ ምክር እንዲሰጡኝ ነው የምፍልገው፣ ቄሶች ሰላም ለማድረግ ይገፋፉኛል

ቤተመንግሥትና መኳንንቶች ጦርንት ለማድረግ ይመክሩኛል፣ አፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የሚመጣ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ለመሳለም ነው የሚሉ ሰዎች ማመን አለብኝ ወይ? ብሎ ይጠይቀዋል ።አቡነ ማሳያ በማያሻማ ሁኔታ ማንነቱን በሚያሳይ መልስ ይሰጣል፣ "የእግዚያብሔር ሰው እንደመሆኔ መጠን ሰላም እንዲሆን እመክራለሁ፣ ነገር ግን ሰላም ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆን አለበት፣ ጉዳዩን የመንግሥት ምክር ቤት ተሰብስቦ መመርመር አለበት፣ ለአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ይፃፍ  ሐሳባቸውን ለማወቅ መልስ ከአገኛችሁ በኋላ ጠይቁኝ ።ነገር ግን ተጠንቀቁ ሰላም ከሆነ እውነተኛ ሰላም መሆን አለበት፣ ሆኖም ሰላም እንዲሰፍን የሚጥር ሁሉ በእኔ ላይ እንደፈረደ ይቆጠራል፣ ሐቀኛ ምክር መሥጠት የእኔ ግዴታ ነው" በማለት ሐሳቡን አጠቃልሎ ገልጾ ወደ ሰፈሩ ፍቅረ ገምብ ይሄዳል።

የጦርነት ስጋት ስለነበረና አቡኑም የሚኖሩበት እንደጦር ምሽግ የተሰራ በመሆኑ የውጭ ሀገር ሰዎች ሁሉ ባፋናም እንዲሁም ብቸኛ የምኒልክ ልጅ/ ሕፃን/ ሌሎችም ከአደጋ ለመከላከል አቡኑ ቤት ይሄዳሉ። ከባፋናም ጋር አንድም ንግግር ሳይለዋወጥ የምኒልክ ልጅ ስለ ትንሿ ሕፃን ግን በየቀኑ በራሱ የተፃፈ ደብዳቤ ለምኒልክ ይልክ ነበር። የሁለቱ ወገኖች የጦር አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበረ፣ ሁለቱም ወገኖች ለማስማማት ቄሶች "ሄሬቲክ" ኤውቲሲያኖች ከአንድ ወገን ወደ ሌላ ወገን ይመላለሱ ነበር። ነገር ግን ውጤት አላገኙም ነበር። የሸዋ ታጣቂዎች የሚያጋጥማቸውን የአጼ ዮሐንስ የአበሻ ጦር ይገድሉ ነበር። አጼ ዮሐንስም ደብረ ማርቆስን የምኒልክ ጦር በመቃጠሉ የምኒልክ የእናት ትውልድ ሀገር ሰላ ድንጋይን በእሳት አቃጠለ፣ በዚህም የተናደደ የአካባቢው ሕዝብ ያገኘው የሐበሻና የጎጃም ወታደርን ሁሉ ፈጀ እንዲሁም በአጠቃላይ በጦር ሜዳ መሸነፍ ጀምሮ ሸዋንና ምኒልክ ሊያድን የሚችል ውሳኔ ተደርሶ ነበረ፣ ነገር ግን ምኒልክ አቡነ ማሳያ በየጊዜ ይሰጠው የነበረው "<u>የማኪያቬሊ</u>" ትምሕርት አልሰማም፣ ሁለቱ ወገኖች የተኩስ አቁም ተስማሙ ሙርኮኞችም ተለዋወጡ፣  የአጼ ዮሐንስ ወታደሮች ሊቼ ሰፍረው መጠበቅ ስለሰለቻቸው የጦር መሣሪያቸውን ለምኒልክ ሰዎች ይሸጡ ጀመሩ፣ የምኒልክ ወታደሮችም ሳይንቀሳቀሱ መቀመጥ ስለሰለቻቸው እያመለጡ መጥፋት ጀመሩ። በዚሁ ዓይነት ሰላም እየተቃረበች መጣች፣ ምኒልክም ሰላም ለመቀበል ወሰነ። የሰላም ንግግር በአጼ ዮሐንስ ሰፈር እንዲሆን ተወሰና ምኒልክ ወደዚህ ሲያመራ እንደ አንድ ነፃ ንጉሥ ሳይሆን ተሸናፊ በመሆን እንደ የበታች ታዛዥ የሰላም ውል ተከናወነ። በሰላም ውሉ መሠረት1ኛ/ምኒልክ  ከአጼ  ዮሐንስ



ግዳመጥ አልፈለገም ነበር። ምኒልክ ወደ ስልጣኑ እንደተመለሰ ከመሸሻና ከአጼ ዮሐንስ ስልጣኑ እንዳይነጠቅበት መጠራጠር ጀመረ። በመጀመሪያ መሸሻ የመሸሸበት የተባለው ቦታ መያዝ አስቦ ነገር ግን ወታደሮች መዋጋት እንደማይፈልጉ ተረዳ፣ ከሁለት ሳምንት ከበባ በኋላ ተመልሶ ወደ ቤቼ እንዲመጣ ተገደደ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡና አማካሪዎቹ መሸሻ እጅ እንዲሰጥ አቡነ ማሳያም ምክር እንዲሰጠው ጠየቁ። አቡኑም አንድ ደብዳቤ ለመሸሻ ፃፈ፣ መሸሻም መልስ ሲሰጥ ለስልጣን ጉጉት እንደሌለው፣ ከአጎቱ ከምኒልክ ጋር ጦርነት መግጠም እንደማይፈልግ፣ ጥቃት ከደረሰበት ግን ለመከላከል እጁን ለባፋና እንደማይሰጥ፣ የሚወዱት ወታደሮችም እንደማይከዱቸው፣ ስለዚህ ለሱና ለወታደሮቹ ምህረት ከተደረገላቸው ሰላም እንደሚያደርግ ገልጾ ጽፋል ።የመንግሥት ምክር ቤት

ተሰብስቦ ባፋና ከቤተ መንግሥት እንድትወጣ ሆና መሸሻ ከሙሉ ትጥቁ ከምሽጉ እንዲወጣ እንዲደረግ ተወስና በፋና ሩቅ ሰፈር ተወስዳ እንድትቀመጥ፣ መሸሻ ግን ደጃዝማች ተብሎ በትልቅ ክብር ሊቼ እንዲገባ ስለተደረገ ለምኒልክ ትልቅ ውርደት ከመሆኑም በላይ መሸሻ ከድሮ የበለጠ ሥልጣኑ አደገኛ መሆኑን ተረዳ ።መሸሻ በታላቅ ክብር ሊቼ ሲገባ ሁለቱ ካቶሊክ አቡኖች አቡነ ማሳያና አቡነ ቶረን በአከባበሩ ሥነ-ሥርዓት ተገኝተው ነበረ። ሥነ-ሥርዓቱ እንዳበቃ ወደ ሚሲዮናች ሄደ፣ የአቡነ ማሳያ እግር መድቆ ቤቱ ሆይ ስላደረኩት ሰላም ደስ ብሎዎታል ወይ ብሎ ቢጠይቀው፣ አቡነ ማሳያ ልጄ አሁን ሂድ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን ስላዮች ስላሉ ሌላ ጊዜ እንነጋገርበታለን በማለት አሰናበተው። አቡነ ማሳያ በፋና ከቤተ መንግሥት በመራቋ ሰላም የሰፈነ ሆና ቢመስለውም ምኒልክ ቃሉን አያከብርም ተብሎ ይጠራጠራል  እንደጠረጠረውም 1/ በሴትዮዋ ችሎታና ተንኮል 2/ ከቤተክህነት ምስጢራዊ ቅንብር 3/ በምኒልክ ደካማነት ባፋና ክብሯ ሳይቀነስ አስተባሰቧን ሳትቀይር የተሰጣትም ሆነ የዘረፈችው መሬት ሳይነካባት ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሰች ።አጼ ዮሐንሥ ለጊዜው ባፋና ከቤተመንግሥት በመባረሯ ወደ ሸዋ

በመግባት እንቅፋት ሆናበት ነበር። የአቡነ ማሳያ ምኞት ባፋና ከቤተመንግሥት ተባርራ እንድትቀር አልተሳካም ከሸፈ ።

አጼ ዮሐንስ በመድፍ ብልጫ ቢኖረው ያለ መንገድ በመድፍ መጠቀም ያስቸግረዋል፣ ምኒልክም በፈረሰኛ ወታደር የበላይነት ነበረው፣ ውጊያውም የሚካሄደው በሀገሩ ስለነበረ ድሉ የምኒልክ ይሆን ነበር። ምኒልክ ግን ባፋና ወደ ቤተመንግሥት ለመመለስ ለአጼ ዮሐንሥ ራሱ መንገድ ከፈተለት። ባፋና እንደተመለሰች አጼ ዮሐንስ በሙሉ ተስፋ ዝግጅቱን ጀመረ ሸዋን ለመውረርም ወሰነ ።

## አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ታሪቁ
## 2ኛ የአቡነ ማሳያ የሸዋ ፖለቲካ ሴራ
## ከሸፈ

አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ተፋጠው በነበሩበት ወቅት ምኒልክ አቡነ ማሳያን ወደ ግቢ ጠርቶ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የሚዘምተው እኔን ፈልጎ ሳይሆን እርስዎን ፈልጎ ነው ይባላል ለምን ወደ ፈንሬኔ አይሄዱም? የሚል

ወ/ሮ ባፌና በጣም ተገክለዋ በመሆንዋ 2ኛ/የቤተክህነት ድጋፉ በመሆንዋ 3ኛ/የአጼ ዮሐንስ ድጋፉ በመሆኑዋ አቡነ ማቴዎስ ምኒልክን ካቶሊክ ለማድረግ የነበረው በውር ዓላማ ዕንቅፋት ነበሩች። ነገሩ ገሐድ የሚያሳየው የአቡኑ ማቴዎስ እጅ እንዳለበት ነው። ከሌላ ገለልተኛ ወገን ቀርቦ ቢሆን ኖሮ በባሰ ሁኔታ ያልተገለፀ የአቡኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ለማወቅ እንችል ነበር። ምኒልክ ከሚስቱ ከባፌና ጋር ለዘመቻ ወደ ወሎ ወረኢሉ ፤ ጎንደር ደብረ ታቦር እስከ ጎንደር ከተማ ጉዞ ያደረጉ ጎዳናው በሚሄዱበት ጊዜ የሸዋ ደህንነት 3 መኳንንቱ እንዲቆጣጠሩት አድርጎ ነበር የሄደው። እነሱም 1/ለምኒልክ በጣም ታማኝ የነበረው እሻቹ ወልደፃዲቅ 2/ ታማኝነቱ አጠራጣሪ የነበረው የአባቱ ወንድም ግርማ 3/ በጣም ወጣት የነበረው ሌላው የአባቱ ወንድም የበዳቱ ልጅ መሸሻ፣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት የነበረው፣ ምኒልክ ልጅ ሳይወልድ ከሞተ አልጋወራሽ ሆኖ የነበረው። በተለይ አበጋዝ ወላዋታን እንዲከታተል አድርጎት የነበረ።

ባፌና ከባሏ ጋር ዘመቻ የሔደችበት ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ መጥመድ ለማከነባት ነበር። ምኒልክ በአባይ ወንዝ ሙላት ወደ ሸዋ የማይመለስበት ሁኔታ ሲፈጠር አንድ በከፊል ሙስሊም በከፊል ሽባ ሆኖ የነበረው የማህል ሥላሴ ልጅ መርዕድ ኃይሉ በመሸዋ ስም ንጉሥ እንዲባል፣ በኋላ ግን አጼ ዮሐንስ ምኒልክን የተማ ሲያሸንፍ ሥልጣን ለባፌና ልጅ እንዲለቅ በተለይ ከቤተክህነት ድጋፍ እየገባበቻት የተልለው ሴራ ነበረ፣ ቀንበሩ ሲበግ መጀመሪያ የተንቀሳቀሰ እሻቹ ወ/ፃዲቅ ነበረ ።

ግርማሜን ለመውጋት አስቦ ነበረ። ነገር ግን በሁለቱ ወገን በኩል ወታደሮች ብዙ እስላሞች በላሉበት እንዋጋም በማለታቸው ከአበጋዝ ወላዋማ በመስማማት መሸሻ አስተማማኝ ቦታ በማስቀመጥ በማከብ በሌላ በኩልም በአቡኑ ማቴዎስ ወደ ካቶሊክ ሐይማኖት እምነት ተስብኮ ስለነበረ አቡኑ ወደሚኖሩበት ወደ ፍቅሬ ገምብ ወስዶ አስቀመጠው። በአቡኑ ቤት ከእሻቹ ወ/ፃዲቅ ጋር ተሰብስበው ከተመካከሩ በኋላ ዓማጺውን መርዕድ ኃይሉን ለመውጋት ወጡ። ጉደብላ ላይ ሚያዝያ 2 1878 ዓ ም በተደረገው ጦርነት በአንድ ፈረንሳይ የጦር አሰልጣኝ የሰለጠኑ የእሻቹ ወታደሮች በባሕላዊ ግላዊ የጦር ስልት የሚጠቀሙ የመርዕድ ኃይሉ ወታደሮች ተሸነፉ፣ አሰልጣኙ ፈረንሳዊም ከሞቱት መሀል ነበር። አሸናፊው መርዕድ እየፎከረ አንኮበር ገባ። ታማኝ ለባል የነበረው ግርማሜ ጣልቃ ገብቶ ጦርነት ከአማፂው መርዕድ ጋር የተም ስለአበአለው ተቃዋሚ አበር ወደ እነዋሪ ወስዶ መሸሻም ከእሱ ጋር አስቀመጠው። ምኒልክና ባፌና ባሉበት ወሬ ሲሰማ ባፌና የቤተሰብ ግጭት ብላ ለምኒልክ በለበሰቸው የምኒልክ ወኪል መሆኗን የሚገልፅ ፅሁፍ ይዛ ወደ ሸዋ መጥታ እነዋሪ ገብታ ከግርማሜ ጋር ተስማምታ ያለው ንብረትና የጦር መሣሪያ ከአንኮበር ወደ መርሐ ቤቴ አከማችታ አስቀመጠችው። መሸሻም ከእሷ ጋር አስተምሮ የአጼ ዮሐንስ በድል አድራጊነት ወደ ሸዋ መግባት እየተጠባበቁ ልጇን ለማንገሥ እቅድ አውጥታ ነበረ ። መሸሻን የሚጠብቁ ወታደሮች ግን ከታሰረበት ገብተው አለቃቸው ባፌናም በገደል ሊወረውሯት ሲሉ መሸሻ በካቶሊክ ትምህርት ያደገ ስለሆነ አስራችሁ ንብረቷን ውሰዱ እንጂ አትግደሏት ብሎ ስለተማጸናቸው ሳይገድሏት ቀሩ። ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ ጥያት ሸኝቶ ወደ ሸዋ ሲገባ ጎዶኑ በፍቅር ታመር ስለነበር ባፌና ስለሚቀጣት ነው ብሎ የባፌናን ክሕደት ጉዳይ አልሰጠውም፣ ግርማሜ ባፌናን ሲይዝ መርድ ኃይሉ በምኒልክ ፊት ያጋልጣት ነበረ። ምኒልክ ግን ግንም



የንጉሥ ሹመትና ዘውድ ተቀበለ ፤ የሸዋና የወሎ 2ኛ/ምኒልክ በየዓመቱ ግብር ለአፄ ዮሐንስ ይከፍላል 3ኛ/ ምኒልክ ከዘይላ ወደ ሸዋ የሚወስደው መንገድ ለሁለት ዓመት ለአውሮፓውያን ዝግ ያደርገዋል 4ኛ/ አጼ ዮሐንስ ደብረ ሊባኖስ ጎብኝቶ ከሸዋ ይወጣል 5ኛ/በሐይማኖት በኩል የደረሱበት ውሳኔ ምስጢር ሆኖ ይቆያል 6ኛ/ ስለ አቡነ ማቴዎስ አጼ ዮሐንስ ሲያነጋግሩት ስለፈለጉ ብቻ አቡኑ አጼ ዮሐንስ ዘንድ እንዲቀርብ ተብሎ ይነገረዋል።

ይህ ውሳኔ ለአቡነ ማቴዎስ እንደ አንድ ተራ የኢትዮጵያ ቄስ ወይንም ጠንቋይ ሳያበረር በዚሁ እንዲነገረው በማድረጋቸው ክብር ይበግተዋል ። ማርች ወር መጨረሻ 1878 ዓ ም ምኒልክ የንጉሥ ዘውድ መጫን አከባበር ሥነ-ሥርዓት ከፈረንሳዊው ፔኩኝ የተባለው ይነገረዋል። ማቴዎስ ከምኒልክ ተጠርቶ

በቦታው ሲደርስ ሥነ-ሥርዓቱ በአንድ ድንኳን ተፈጸም ነበር። ሁለት ሰገነት ወንበሮች ነበሩ: አንዱ ከፍ ያለው ለአጼ ዮሐንስ፣ ሁለተኛ አነስ ያለው ለምኒልክ።

በጭፈራና በእልልታ ታጅቦ ምኒልክ በአዳራሽ ውስጥ ገባ፣ የአጼ ዮሐንስ እጅን ሳመ፣ ማቴዎስ አሳፋሪ ብሎታል። አጼ ዮሐንስ ንግግር አድርገዋል። ምኒልክ እጠገኔ በለጠው መስቀል ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነቱን ይምላል ፡ አጼ ዮሐንስ ለምኒልክ በትክክለኛው ባርኖስ ያለብሰዋል፣ በራሱ ዘውድ ይጭንበታል።"ከእንግዲህ አንተ በኩር ልጄ ነህ "ይለዋል ። ምኒልክ በሰገነት ይቀመጣል ንጉሠ ነገሥቱም ይስመዋል ። መድፎችም ጠብመንጃዎችም ይተኩሳሉ፣ ታላላቅ ሰዎች ወደ ምኒልክ እየተጠጉ እጅን ይስማሉ ። የሁለቱ ወገኖች ሠራዊቶች የተካፈሉበት ግብዣ እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ይቆያል። ምኒልክ ዋጋውን አገኘ በማለት አቡነ ማቴዎስ ሃሳቡን ይደመድማል። ብዙ የሸዋ ሰው ምኒልክ በቄሶች ሴራ በመጥመድ ውስጥ ገባ ተጥግቶ ቢሆን ኖሮ አሁን ንጉሠ ነገሥቱ እሱ ነበረ እያሉ ያወሩ ነበር። የደብረ ሊባኖስ ጉብኝት ካበቃ በኋላ በምኒልክ አማካኝነት አቡነ ማቴዎስ አጼ ዮሐንስ ዘንድ እንዲቀርብ ይጠባበቅ ነበር። በመጨረሻ እንዲቀርብ ተፈቅዶ አንድ ጥልግ ቤት ውስጥ በገባ ቁጥርም ጥበግው እየባሰ ይሄድ ነበረ፣ ጋረጃም ነበር፣ በመጨረሻ በድንኳኑ መሐል ከላይ ተዳዳ ሲከፈት የአቡኑ ገጽን በልጭልጭ አለበት። የት እንዳለ ራሱን ለመቆጣጠር አልቻለም። ለመንቀሳቀስ ሲደፍር በእጁ ተይዞ እንዳይንቀሳቀስ ተደረገ። በዚህ ሁኔታ እሱ ሰው ማየት አይችልም፣ ሰው ግን ማለት ንጉሠ ነገሥቱ ያየዋል፣ ጥያቄው እጭር ነበር

1/ ለምን እዚህ መጣህ? 2/ ሸዋ ውስጥ ምን ትሰራለህ? 3/አሁን ፍላጎትህ ምንድነው? የሚል ነበር ። የአቡኑ መልስ 1.እዚህ የመጣሁት ለግርማዊነትዎ እጅ ለመንሳት ነው 2. ሸዋ ውስጥ ምን እንደምሰራ ንጉሥ ምኒልክ ሊነግርዎት ይችላል፣ እኔ ሚሲዮናዊ ነኝ 3. ስራዬን ለማከናወን እንድችል ነፃነት እንዲሰጠኝ ከመጠየቅ በቀር ከግርማዊነትዎ የምፈልገው ነገር የለም። ስለም በመሰሉት ደስ ብሎዋል ሁራኩም ስጥቻለሁ የሚል ነበር። አጼ ዮሐንስም ጥሩ ነው ወደ ምኒልክ ሰፈር ተመለስ በእሱ በኩል ምን እንደሆነ ሃሳቤ ይነገርሃል በማለት ያሰናብቱታል። ከሁለት ቀን በኋላ አጼ ዮሐንስ ሁለት አዋጆች በማከማት ከሸዋ ወጣ 1ኛ/ ስለ ምኒልክ ባፌና እንደ ንግሥት ተከብራ በሸዋ እንድትቀመጥ 2ኛ/ ስለ ሃይማኖት አሁን ባለው ሁኔታ እስከ አንድ ዓመት ቆይቶ ከአንድ ዓመት በኋላ የሊቃውንት ስብሰባ ተደርጎ ውሳኔ ይደረጋል። በሸዋ ውስጥ የነበረ ፍራፉ

በፋና አሁን ያሰውን የንጉሥ ዘር አሰወግዳ ልጄን እንደምታነግሥ፣ በሃይማኖትም የካራ እምነት ሸዋ በሙሉ እንዲቀበል ይደረጋል የሚል ነበር።

አጼ ዮሐንስ ከሔደ በኋላ ምኒልክና አቡነ ማሳያ ተገናኝተው ተወያይተዋል። አቡኑ ምኒልክን የገሰፀበት ምክንያቶች ጥቂቶቹ 1ኛሸዋ የደብረ ሊባኖስ የሃይማኖት እምነትና የሐበሻ የጋራ እምነት ባሰው ጥላቻ ምኒልክ እንዴት ሊጠቀምበት እንዳልቻለ 2ኛ/ በበፋና የጠላት ሰላይ እንዴት ሊመራ እንደሚችል 3ኛ/ 30.000( ሰላሳ ሺህ )የፈረንሳኛ ጦር በጎጃም በኩንቱ ከማሳለፍ ይልቅ በሸዋ ጠረፍ ቢያስልፍ ኖሮ አጼ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመግባት ባልቻለ ነበር።

ከዚህ በኋላ ከአቡኑ ተሰናብቶ ምኒልክ ወደ ሰፈሩ ይመለሳል፣ የንጉሥ ምኒልክ የዘውድ ሹመት አከባበር እንደተፈጸመ ምኒልክ በበኩሉ ሰሁለት ሰዎች

በሸዋ የራስ ሹመት ማዕረግ ሰጠ እነሱም ራስ ጎበና እና ራስ ዳርጌ ነበሩ። በኢትዮጵያ በአርቶዶክስ ክርስትና እምነት ልዮነት ለሁሉ ጊዜ ተወግዶ፣ አቡነ ማሳያ አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ጦርነት እንዲገጥሙ የነበረው ምኞት ከሸፈ።

# 3ኛየአቡነ ማሳያ ሴራ ከሸፈ፣

በኢትዮጵያ ለዘመናት ሲያወዛግብና ሲያከራክር የሰው ሕይወትን ሲያጠፋ የቆየው በገዳማትና በሃይማኖት አባቶችና ምሁራን መካከል የነበረው ልዮነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ አጼ ዮሐንስ ቆርጦ የተነሳበት ጉዳይ ነበር። አቡነ ማሳያ በ12 ዓመት በሸዋ በተቀመጠበት ጊዜ በልዮነቶቹ ተጠቅሞ በሸዋ የካቶሊክ ሃይማኖት ለመመሥረት ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፤/ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚመራ የሃይማኖት ቡድን ሶስት ልደት የተባለው ከካቶሊክ ብዙ የማይለይ እምነት በመሆኑ 2/ በአብዛኛው በኢትዮጵያ የተስፋፋ ካራ የተባለ ቡድን ነበር 3/ ቅባት የተባለው በጎጃም ደብረ ወርቅ ነበረ፣ ከካራ ጋራ ብዙ የማይለይ ነበረ። አቡነ ማሳያ የአንደኛ ቡድን ደጋፊ ነበር።

የአቡነ ማሳያ ዓላማ ቢሳካ ኢትዮጵያ በሃይማኖት ሳብያ እርስ በርስ ጦርነት አዘቅት ልትወድቅ ትችል ነበር ።ይህ እንዳይደርስ ግን በአጼ ዮሐንስ አስተባባሪ መሪነት በቀላሉ ልዮነቶች ሊወገዱ ችሰዋል። አጼ ዮሐንስ ከምኒልክ ጋር ታርቆ ወደ ሰሜን ከመመለሱ በፊት ስለ ሃይማኖት ጉዳይ የሊታውንት ጉባኤ እንዲጣራ ቃል በገባበት መሠረት በደብረ ታቦር ጉባኤ ተደርጎ ነበር። ከሸዋ 50 አባላት የደብር አለቆች መምህራን፣ ካህናት ያሉበት ከእነሱ መካከልም 30 የደብረ ሊባኖስ አለቃ አሸቴና አለቃ ሣህሌ የተባሉት የአቡነ ማሳያ ተባባሪ የሆኑ በይፋ ካቶሊክ የነበሩ ይገኙበት ነበር። ሌሎች (100)መቶ አባላት እንደ አቡነ ማሳያ አባባል ከጎጃምና ከአቢስኒያ የተወከሉ ነበሩ። ከእነሱም እንደ ደብረ ሊባኖስ መልእክተኞች የጉባኤ ቀን ሲደርስ መጡ። የኢትዮጵያውያን የአእምሮ ብስለት የሚጠራጠር ሰው ቢኖር ይህ የጉባኤ ክንውን በአንክሮ መከታተልና ማጤን ይገበዋል። የደብረ ሊባኖስ እምነት ተከታዮች አርፈው ተቀምጠ ነበር፣ የካራ እምነት ተከታዮች ግን በአውሮጳ የምርጫ ቅስቀሳ ከሚደረገው ያላነሰ ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር። በጉባኤው ንጉሥ ምኒልክና ራስ አዳል ተካፋይ ነበሩ። አቡነ ማሳያና ንጉሥ ምኒልክ በጉዳዩ ተነጋግረውበት በምርጫ የደብረ ሊባኖስ ቡድን እንደሚያሸንፍ ሙሉ በሙሉ ተማምነው ነበር።ነገር ግን ንጉሥ ምኒልክ



የጉባኤ አሠራር ረቂቅ ተንኮል የተሞላበት ሆኖ አገኘው፣ ተሳታፊዎች በ10 በ10 ተከፋፍለው ነበር። ለየአንዳንዱ አንድ በንጉሠ ነገሥቱ የተሾመ ነበረው። ለእያንዳንዱ ጉዳይ የሚያወያዩም የሚመርጡም ለየብቻው ነበር። ወዲያውኑ ውጤቱ ለንጉሠ ነገሥቱ ማስታወቅ ነበረባቸው። በኤውሮጳ ፓርላማ ምርጫ ጥበበኛ አሻጥረኛ የሆነው ሰው እንዲህ ያለ አሰራር ችሎታ ሊኖረው አይችልም። ከ10ሮቹ አለቆች ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኞች የተመረጡ ነበሩ። የመጀመሪያ ቀን ይግባኝ የሌለው ዳኛ ማን እንደሚሆን ምርጫ ተካሄደ ለዚህም አጼ ዮሐንስ ተመረጠ። ሁለተኛ ቀን በኢትዮጵያ የሃይማኖት አንድነት እንዲሰፍን ምርጫ ተካሄደ ለዚህም የነበሩ ተቃዋሚዎች በመደለያና በዘዴ ለማቆም ተችሏል። ሦስተኛ

ቀን የትኛው እምነት መቀበል እንደሚገባ ምርጫ ተካሄደ ዋናው የጉባኤ ነጥብ ነበረ።10 ብድኖች እርስ በእርሳቸው እንዳይገናኙና ውጤትም እንዳይቀባበሉ በጥብቅ ተከለከሉ። ለደብረ ሊባኖስ በሚስጢር ዛቻ ይሰነዘርባቸው ነበረ። ተከለ ፃዲቅ የተባለ የአቡነ ማሳያ ወገን ኮሶ ታይቶኛል ብሎ ከጉባዔ ጠፋ፣ እሸቴ ሌላ የአቡነ ማሳያ ቄስ ከሌሎች ቄሶች ጋራ ሆኖ አመመኝ ብሎ ምክንያት ፈጥሮ ከግባዔው ወጣ፣ ሁለት መምህሮች ተቃውሞ ሊያሰሙ የፈለጉ ተባረሩ። ጉባዔው እንደተፈፀመ ታላላቅ ሹማምንቶች ንጉሥ ምኒልክና ራስ አዳል ባሉበት ውጤቱ በይፋ ተገለፀ ። ኢትዮጵያ በካራ ሃይማኖት አንድ ሆናለች ። ውጤቱን እንዲቀበሉ ሁለት ዓመት ለክርስቲያኖች ሦስት ዓመት ለሙስሊሞች 5 ዓመት ሃይማኖት አልባ ለሆኑ ሃይማኖቱን እንዲቀበሉ የጊዜ ገደብ ተሰጣቸው። ሁለት አለቆች ተቃውሞውን ያሰሙ የነበሩ ተቃውሞዋቸውን ለማቆም ስላልፈለጉ ወዲያውኑ ምላሳቸውን ተቆረጡ ። ስለ አቡነ ማሳያ በጉባዔ ጊዜ ሴብተምበር 18 / 1878 እስከ ሜይ 1879 ዓ ም ምንም ዓይንት ዛቻ ወይንም ጉዳት አልደረሰበትም ነበር።በሃይማኖት ምክንያት ኢትዮጲያውያንን ለመከፋፈል የተውጠነጠነ ሴራ ግን ከሸፈበት።

# አቡነ ማሳያ ከኢትዮጵያ ተባረረ

አቡነ ማሳያ የልብ ወዳጅ ይተማመንበት የነበረ ምኒልክ በችግሩ ጊዜ ሊረዳው ባለመፈለጉ ወይንም ባለመቻሉ ሕሊናው ለሁለት ይከፈላል ወይንም በ "ለሄሬቲኮች" እየተታለለ ነው ወይንም መቶ ጊዜ አታላይ ከእኔ የበለጠ ተንኮለኛ ነው እያለ በጭንቅላቱ እያሰበ እንዳለ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ አንድ ደብዳቤ እንደደረሰውና ከሚሲዮናውያን የበለጠ ሀገራችንን የሚወድ ሰው ስለሌለ ከውጭ መንግሥታት ወዳጅነት ለመፍጠር አፄ ዮሐንስ ወደ ኤውሮጳ ልልካቸው ስለሚፈልግ እንዲላኩልኝ ብለዋል ብሎ ለአቡነ ማሳያ ይነግረዋል። አቡነ ማሳያ በፍርሐትና በጥርጣሬ ይዋጣል። ምኒልክ ግን የንጉሠ ነገሥቱ ሐቀኝነት ሊያስረዳው ይሞክረል ሊያሳምነው ግን አልቻለም፤ ከሁለት ሣምንት በኋላ አቡነ ማሳያ ሌላ ደብዳቤ ከምኒል ይደርሰዋል ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ታቦር ይጠብቃችኋል፣ ጁን አጋማሽ ላይ እንዲደርሱ የሚል ነበረ። ይኼም ሆኖ ተስፋ ሳይቆርጥ አሁንም ከምኒልክ ጋር ለመገናኘት ይጠይቀዋል፣ ይገናኛሉ አቡነ ማሳያ ምኒልክን ለማነጋገር የፈለገው ጥቅም አገኛለሁ ብሎ በማሰብ ሳይሆን ምኒልክ ይኼን ሁሉ ዓመታት አብረው ሲኖሩ ጨዋ ሰው ነበረ ወይ? ወይንም

ሊያታልለኝ ነበር የኖረው የሚለው ጥያቄ በሐንንሱ የሚጉላላ እውነቱን ለማወቅ መልስ ለመፈለግ ብቻ ነበር፡፡የወደኝ ነበረ ወይንስ ያታልለኝ ነበረ፡፡ ብዙ ነገር እስከ ግታ ተጫውተው ተሰነባበቱ፡፡ ቾን 27 ጉዞው ይጀምራል ቾላይ ወረኢሉ ይደርሳሉ እንክት 5/1979 ዓ ም ደብረ ታቦር ደረሱ፡፡ ሚሲዮናውያን ብዙ ክብር የሰጡት አፄ ዮሐንስ ቶሎ ብሎ ተቀብሎ እንዲያስተናግዳቸው ይጠባበቁ ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ቆይተው ወደ ሚያርፉበት ቤት ለማረፍያ ወደ ተዘጋጀላቸው ቤት ተወሰዱ፡፡ በማግስቱ እንክት 6/ 1979 ንጉሠ ነገሥቱ ይፈልጋችኋል ተብለው ሄዱ፡፡ አፄ ዮሐንስ ዘንድ ሶስት ሰዓት ደጅ ከጠኑ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረቡ፡፡ አልጋ ላይ ቁጭ ብሎ፣ እግሩን ተኮራምቶ፣ ሸማ ለብሶ፣ አንድ ክንዱ ትራስ ላይ ተደግፎ አገኙት፡፡ ሚሲዮናውያኑ ለመጠጋት ሞከሩ፣ ግን ተከለከሉ፣ ስፈር እንዳይገቡ ተከለከሉ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ጥያቄውን ጀመረ፤ ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው እነሱም ጠርተውን ነው የመጣነው ትእዛዝዎን እየተጠባበቅን ነው አሉት፡፡

ንጉሠ ነገሥቱም በመቀጠል መልካም ነው ክረምቱ እስኪያልቅ ቅርብ የሆነ መንደር ሆናችሁ ታሳልፉላችሁ ወደ ሀገራችሁ እንደምትመለሱ እስከ ምንገራችሁ ድረስ ተጠባበቁ ብሎ ነገራቸው ሚስዮናውያኖቹ እጅ ነስተው ወደ ተባለው ሥፍራቸው ተመለሱ፡፡ በዚህ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ እስረኞች መሆናቸው ተነገራቸው፣ ወደእስረኖቹ ማንም ሰው ሊጠጋ አይችልም ነበር የሚጠጋ ሰው ሲያጋጥም ይገረፍ ነበር፣ በምግብ በኩል ግን እስረኞቹ ጠግበው ይተርፍ ነበር፡፡ከምን የመጣ ነው ይኼ ሁሉ ቸር መሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ምንጭ ያልመጣ፣ ከምሥራቃውያን የኼሬቲክ ሃይማኖቶች ቆሻሻ ውሃ የጠጣ ሰው የእውነተኛ የእግዚአብሄር መንፈስ መንፈሳዊ ስሜት ሊያድርበት አይችልም፣ ለሰው ለማሳየት ነበረ ማንኛውም የአፄ ዮሐንስ ስራ፡፡ በፖለቲካ ምክንያት ነው፡፡

እንደ ታበሩ ወሬ ስምተናል ብለው አንዳንድ ሰዎች ወደ አቡነ ማሳያ ይመጡ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ አቡኑ ከሞተ በቤተክርስቲያን በክብር ይቀበራሉ ይላሉ አንዳንዶቹ ደግሞ አጼ ዮሐንስ ራሳውን ወደ ገደል እንዲጣል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቷል ብለው ሲናገሩ ይሰማል፣ እኔ ቢጠይቁኝ ግን በአንድ የኼሬቲክ ቤተክርስቲያን ከመቀበር ወደ ገደል ቢጥሉኝ እመርጣለሁ የሚል መልስ እሰጣቸው ነበር፡፡ እናንተ ግን ከሞትኩ በሜካ በአንድ ዛፍ ስር ቅበሩኝ በማለት አቡነ ማሳያ ይሰብካቸው ነበር፡፡ እክቶበር 3/1879 ሌሊት ፀሐይ ሳይወጣ እስረኞቹ ሁሉ ወደ ንጉሠ ነገሥት ጊቢ ተወሰዱ ከቀኑ 6 ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረቡ የመጨረሻ በንብት የተዘቀዘ አቀባበል ነበረ የተደረገባቸው፣ የገቡበት ክፍል ጭለማ ነበር ፡፡ብንጉሡ ላይ የዓመፅ ወንጀል እንደሰራን የሚመስል አቀባበል ተደረገልን ተዝቃዛ የንጉሠ ነገሥት ድምፅ ሰማን ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ የሚል፣ ቀጥሎም ለእንቴ ለራስ አርአያ ጽፌላችኋለሁ ስለ ጉዞዋችሁ ይነግሯችኋል፣ ከጠባቂዎችም ዝቅ ብለን እጅ እንድንነሳ ተገደን ወጣን፡፡ ግማሽ ሰዓት ውጭ እንደቆየን ንጉሠ ነገሥቱ ሹማምንቶችና የውጭ ሰዎችም ያሉበት ብዙ ሰዎች ከነሱም መካከል የነበሩ ሲኖር ቢያንኪና ወንድማማቶች ናረቲ የሚገኙበት ታጅቦ ከግቢ ሲወጣ አየነው፡፡

# አቡነ ማሳያ ተጋለጠ [1]

ጣሊያኖች አቡነ ማሳያን የትኝ ግዛታቸው አባት አድርገው ሲያወዱሱት በወቅቱ አርሞ ሀገር ሄደው የአቡኑን ሥራ የተመለከቱ ጣሊያኖች ሥራውን ለማጋለጥ ነበረ የተገደዱት፡፡ እንደሚታወቀው ከኢጣሊያ የጆኦግራፊ ማህበር

[1] Ettore Cozzani Vita Di Guglielmo Massaia VII P412



የተላኩ 4 አባላት የሚገኙበት በአንቲናሪ የተባለው የሚመራ ምክትል መሪ ግርቲና ሁለት አባላት ቼኪና ኪያሪኒ የተባሉ ያቀፈ ብድን ወደ ኢኳቶሪያል ሐይቆች ለማምራት ሸዋ በአቡነ ማሳያ አማካኝነት ጣቢያ መስርተው ነበረ ፡፡ ከቡድኑ አባላት ሁለቱ ቼኪና ኪያሪኒ ተልእኮዋቸውን ለማከናወን ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተጉዘው አቡነ ማሳያ አቋቁመው የነበሩትን የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ያሉባቸው ቦታዎች ሲደርሱ ከሚሲዮናት እርዳታ እናገኛለን ብለው ይጠብቁ ነበረ፣ ነገር ግን በተገላቢጦሽ ሚሲዮናት በእርዳታ ፋንታ ችግር ነበር የፈጠሩባቸው፡፡ ቼኪና ኪያሪኒ ከከፋ ሀገር በሚል አድራሻ ኢጥሪል 24/1979 ዓ ም ለአለቃቸው በፃፉት ደብዳቤ አቡነ ማሳያን እንደሊሉቱ ደት ምስኪን ሰው ምስኪን ማሳያ ብለው በመጠቀም ፋንታ ብራቭ ጎበዝ ማሳያ ብለው ቢጠሩትም ወደ ፍሬ ነገሩ ሲገቡ ግን ከባድ ትችት ሰንዝረውበታል፡፡ አቡኑ ካደረገው ጥረት ሲታይ ያገኘው ውጤት አነስተኛ ነው ብለውታል፡፡

እንደሚታወቀው በጥንቃቄ ተከፖ ከከፋ ጎበዙ አቡነ ማሳያ እስከ ተባረረ ድረስ የተከናወኑ ነገሮች ብናልፈው አባ ኃይሉ ከፋ አባ ሌዮን በጊራምጋሊዮር ኮቺና በላጋማራ ብቻ ነበረ የተሩ፡፡ ነገር ግን ወይንም ለአቡነ ማሳያ መንገዶች ተዘግተውበት ነበር ወይንም ሮም ሚስዮናቹን ረስታቸዋለች ወይንም እነዚህ ሰዎች በሐገሩ መኖር ተሰናዋቸው ነበር፤ ሚሲዮናት እየወደሙ ሄደው ዛሬ ጠፍቷል ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህ የተነሳ ለሀገር ጎብኚ ሁሉ ችግር መፍጠራቸው አልቀረም፡፡ አቡነ ኮቺና ወደ ከፋ የተመለሰ በላጋማራና ጉድሩ የነበረው 30.000 ብር ግራያ ትራዛ ከነበረው እዳ ለመሸሽ ነበረ፣ ቦታውን የተወው አባ አውጉስ የተባለው ቄስ በአለቃው ዕዳ ተይዞ ተከሶ ያለው ንብረት ሁሉ የለበሰው ልብስ ሳይቀር ተወስዶበታል፡፡ ማንኛውም ነጭ ሰው በእነዚህ ሀገሮች ያለፈ ዕዳውን ለመክፈል ይገደዳል፡፡ የአቡነ ኮቺና መታመምና

አሟሟት በርሃብ፣ በችግር፣ የተነሳ ነበረ፡፡ የበሽታውም ዓይነት አቢታዊ ከመሆኑ የተነሳ ለአንድ ዓመት የአልጋ ቁራኛ በሆነበት ጊዜ ማንም ሰው ሊጠይቀው አይጠጋም ነበረ፣ ከንጉሡም ጀምሮ ሹማምንቶችም ጭምር፡፡

ስለ አባ ሌዮን በጊራና እናሪያ ቼኪና ኪያሪኒ አስታየታቸውን ሲሰጡ የባሪያዎች ባሪያ ሆና ነበረ ይኖር የነበረው አንድ ቁራጭ እንጀራ ለማግኘት የሚስዮናዊ ሥራውን ትቶ በእነዚህ ጨካኖች ሥር ሆና የእንጨረኛ፣ የግምበኛ የአናጢ ወዘተ... ሥራ እየሰራ ይኖር ነበረ፡፡ ከዚህም የባሰ ከባድ ችግር ስላጋጠመው ሀይማኖቱን ከድቶ ሙስሊም እንዲሆን እስከመገደድ ደርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን ክብሩን እያዋረደ ተለማምጦ ሃይማኖቱን ሳይከድ ለመኖር በቅቷል፡፡ ዛሬ እሱ የሰው ሁሉ መሳቂያ በመሆኑ ለእኛም ችግር ፈጥሮብናል፡፡ ምን ያህል ዝቅተኛ ደረጃ ደርሶ እንደነበረ ሊገባው አይችልም፤ ይህ ሁሉ የሆነው የአቡነ ማሳያ ከምኒልክ ጋር በሸዋ ተቀምጦ በነበረ ጊዜ ነው፡፡

የአቡነ ማሳያ ጭፍሮች ሊያስተዳድራቸው የሚገባው በእንዲህ ያለ ችግር ወድቀው ሲገኙ፣ አቡኑ ግን ወደ ተመደበበት ሀገረ ስብከቱ እንዳይሄድ ምኒልክ ከለከለኝ እያለ ለማስመሰል በሸዋ ወርቃማ እስር ቤት የተባለበት ይኖር ነበር፡፡ ወደ አሮሞ ሀገር ተመልሶ ለመሄድ ያልፈለገበት ምክንያት በነበረው የገንዘብ ዕዳ እንዳይያዝ ይሆናል ወይንም የተደበቀ ሌላ ምክንያት ሊኖር ይችላል፡፡

# ልጥ ማረፊያ

የአቡነ ማሳያ ነገር ሲነሳ የልጥ ማረፊያ ማስታወስ ግዴታ ይሆናል። ይህ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የመጀመሪያ ጥንሥሥ የተባለበት ትንሹ መሬት ከንጉሥ ምኒልክ ለማሳያ ለመጀመሪያ ጊዜ ይሰጠው የነበረ ድርጎ ለማስቀረት በመሬቱ እንዲጠቀምበት የተሰጠው መሬት ነበር[1]። ጥቅምም ይሰጠው ነበረ፣ በኋላ ግን የጆዮግራፊ ማህበር አባላት ወደ ሸዋ መጥተው ጣቢያ ሲያቋቁሙ ለእነሱ እንዲሰጣቸው አቡኑ ባሳሰበው መሠረት የተሰጣቸው ነበረ። አቡነ ማሳያ መሬቱን አሳልፎ መሥጠቱ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ድጋፍ ያደርግላቸው ነበር። ያለ አቡኑ ድጋፍ ፣ምክር፣ ሰልጣን፣ ምንም ሥራ ሳያከናውኑ ይመስሉ ነበር /ትራቨርሲ/። አቡነ ማሳያ ለማስመሰል ሚሲዮናዊ ነኝ፣ በፖለቲካ አልገባም እያለ በተደጋጋሚ ይለፈልፋል። ነገር ግን በፖለቲካ ከመግባቱ ብቻ ሳይሆን አለቆቹም እንደፈቀዱለት የሚያስበረዳ ወደ ሸዋ የተላኩ ጣሊያኖች ከመድረሳቸው ፊትም ከደረሱ በኋላም ለኢጣሊያ ጆዮግራፊ ማህበር የፃፋቸው ሁለት ደብዳቤዎች ገልፀዋል። የጆዮግራፊ አዋቂ ተብሎ የተነገረለት አቡነ ማሳያ ከኢጣሊያ ኢትዮጵያ የሚለየን ከኢኳተር ዘጠኝ ድግሪ ሎንጂትዮድ ብሎ ከዘባረቀ በኋላ ደሴምንበር 1876 በፃፈው ደብዳቤ የካቶሊክ ሚሲዮን ድጋፍ እንደማይለያቸው ሸዋ እንደ መእከል እንደሚያገለግላቸው በምኒልክ እግከኝ ነትም በከፋ ሌላ ጣቢያ ሊያቋቁሙ እንደሚችሉም፣ ኢጣሊያም ይህ ሁሉ ክብር ለማድረግ በመብቃቷ ደስታውን ገልጾ ሥራው ግን ያለ ችግር እንደማይከናወን አስጠንቅቋል። በ1877 ዓ ም ልጥ ማረፊያ ለኢጣሊያኖች ምኒልክ ሲሰጣቸው ከኢጣሊያኖች የሚፈለገው የጦር መሣሪያ ማግኘት ነበር። ትራቨርሲ ይህ ከፍተኛ የሆነ ዓላማው፣ አንድ ጥቁር ንጉሥ ሐንጎል ሊደረስበት የማይችል ይመስል የነበረው "በእኛ በጣሊያኖች ትክክ በእኛ ጉዳት የመጨረሻ ውጤት እስከ እገኘንበት ጊዜ ድረስ በማያቋርጥ ጥረት ቀጥሎበታል። እኛ ጣሊያኖች ግን በሸዋ ፖለቲካና በትግራይ ፖለቲካ መላ ጠፍቶብን በሰሜንም በደቡብም የተጠላን ሆነን በተስፋ መፈንጠቅና ተስፋ መቁረጥ ሐዘንንና ደስታ ብዙ እይተን ችግሮች የተፈራረቁበት ወደ ኤርትራ ሱማሊያ ሊቢያ ልንደርስ የቻልንበት ለኢጣሊያኖች ሁሉ የቅኝ ግዛት ስሜት እንዲያድርባቸው የተደረገ ፓሊቲኪዊ ሥራ የመጀመሪያ ጮራ የፈነጠቀው ከልጥ ማረፍያ ነው" በማለት ዘግበዋል ።

ይህ አባባል የሚያሳየው ኢጣሊያ ልጥ ማረፊያ ለሃያ ዓመት ካገኘችው መሬት የሰለላ መረብ በኢትዮጵያ ላይ ለመዘርጋት የተጠቀመችበት መሬት እንደነበረ ነው። ከኢጣሊያ ጆግራፊ ማህበር ተልከው የመጡ ጣላያኖች ሁሉም ሊቃውንት ነበሩ ። አቡነ ማሳያ ግን ኖቬንብር 20 1887 ዓ ም በጻፈው ረጅም ደብዳቤ አሁንም ከኤኳቶር ያለው ሎንጂቲቲዩድ ርቀት ሊነግራቸው ይሞክራል አቡነ ማሳያ በእሮሞ ሀገር የመሰረታቸው ሚሲዮኖች የነበረ ሁኔታ ጉዱ እንዳይታወቅበት ጣሊያኖች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ አልፈለገም ነበር ። ከመጡ በኋላም ወደ ጅማ ከፋ ጉዞዋቸው እንዲቀጥሉ አልፈለገም ነበረ።

---

[1] Leopoldo Traversl: Let marefia



ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣሊያኖች ጋራ የሚያደርገው መመሳጠር አጼ ዮሐንስን እንደሚያስቆጣ ጥርጥር አልነበረውም። በዚህ ጊዜ ነበረ ለምኒልክ አንድ የሮማ አቡን የቤተ ክህነትህ አሌቃ አድርገሀል ሰላም እንዲሆን ከተፈለገ ማሳያን እንድታስረክበኝ እዝዤሃለሁ የሚል ደብዳቤ ከአጼ ዮሐንስ የደረሰው። ምኒልክ አጼ ዮሐንሥን ለመቋቋም መሣሪያ ያስፈልገው ነበር።ይኼንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከኢጣሊያኖች ጋር ተመሳጥሮ ያልወጠነው ነገር አልነበረም ።

1ኛ/ በዚህ ጊዜ በኢጣሊያኖች ምክር አቡነ ማሳያና አንቲኖሪ ለአውሮጳ መንግሥታት የባሪያ ንግድ ለማጥፋት የጦር መሣሪያ እርዳታ ለምኒልክ ያስፈልገዋል የሚል ደብዳቤ እንዲጽፍ አድርገውታል።

2ኛ/ አንቲኖሪም ለዋና መሥሪያ ቤቱ ይኼንን ሐሳብ በመደገፍ ኖቬንበር 11/1878 ዓ ም ደብዳቤ ልኳል።

3ኛ/ ጣሊያኖች የባሮች በሐበሻ ሀገር አሉ ብለው ሲያወሩ የባሪያ ንግድ አባቶች ራሳቸው መሆናቸውን ሳያውቁ ቀርተው አይደለም። ኢትዮጵያ በባሪያ አሳዳሪነት ለዓለም ሲያስታውቋዋት፣ ምኒልክ ለመርዳት የነበራቸው ዓላማ ለማሳካት የሚዶልቱት ተንኮል ብቻ ነበር። የልጥ ማረፊያ ሠራተኞች አቡነ ማሳያና አንቲኖሪ ጣብያው ፀረ-ባሪያ ንግድ ሰበአዊ ተግባር እከናውነዋል እያሉ ይሰብኩ ነበር። ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ እንዲሰራ ለማድረግ ሃሳብ እንደነበራቸው የሚያመለክት ነበር ። አቡነ ማሳያ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ግን፣ እንዲሁም አንቲኖሪ ከሞተ በኋላ ኪያሪኒም ከሞተ በኋላ ሕልውናውን ካገኘው በሦስት ዓመት ውስጥ በይፋ የፖለቲካ ተግባርና የስለላ ማእከል በመሆን በዓድዋ ጦርነት ምክንያት እስከ ተዘጋበት ጊዜ ድረስ ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መመስረት ከፍ ያለ አገልግሎት ሰጥቷል። ብዙ ጊዜ እንደሚነገረው፣ በተለይ በደርግ ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር የነበረው፣ ኢትዮጵያ ወረራ ይሰነዘርባት የነበረ በቀይ ባህር ብቻ ይባል ነበር ። ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው በሰሜን አቅጣጫ ብቻ ወረራ አልተፈጸመባትም። ድምጽ በሌለው መሣሪያ ኢትዮጵያ የተወረረችው ከምጽዋ ወረራ የበለጠ በመሐል ሀገር ከልጥ ማረፊያ ነበር። ጣሊያኖች ልጥ ማረፊያ ሆነው ካከናወኑት ተግባር የተጠቀመው ሚኒልክ ነው በማለት ቁጭታቸውን አሰምተዋል ። ራሳችን በሸጥንለት የጦር መሣሪያ በእኛ ላይ አውሎ ዓድዋ ላይ በጦር ሜዳ ለሽንፈት ዳረገን እያሉ ዘወትር የሚያሰሙት ትችት ነው ። በእንፃሩም እኛ ኢትዮጵያውያን በመሐላችን በመሀል ኢትዮጵያ ወዳጅ መስሎ ጠላት አስቀምጠን ወረራ እንዲካሄድብን እንዲከፋፍሉን ራሳችን መንገድ ሰጥተናቸዋል ብለን ጣሊያኖች እንዳረጉት ሁሉ ስህተታችን ከመማር ፋንታ አቡነ ማሳያና አንቲኖሪ ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ለማቀበል የጀመሩት ሥራ ሌሎችም ልጥ ማረፊያ ተቀምጠው በይበልጥ እንደ አንቶኔሊ የመሳሰሉት ሲጠቀሙበት አደጋ እንደሚያመጣብን አልተገነዘብንም። አንቶኔሌ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በግሉ ነው ይባላል ። ከኢጣሊያ መንግሥት ወይም ከኢጣሊያ ጆዮግራፊ ማህበር ውክልና አልነበረውም ፤ ነገር ግን በግሉ ከዘመዶቹ ለአንቲኖሪ አደራ ተብሎ የገባ ነው ።አንቶኔሊ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገባ በልጥ ማረፊያ ሹመት አልነበረውም፣ ነገር ግን በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የንጉሥ ምኒልክ ባለሟል ለመሆን በቅቷል ። ምኒልክ የሚፈልገው የጦር መሣራያ ስለ ነበር አንቶኔሊም በአስተማማኝ ሁኔታ የጦር መሣሪያ ለማቀበል አስተማማኝ ዕቅድ አውጥቶ ሁሉም ወገኖች እንዲስማሙበት አደረገ ።

1ኛ/የጦር መሣሪያ የሚገባበት መንገድ እንደ ድሮው በሰው እጅ ባለው የባህረ ወደብ ቀርቶ በኢጣሊያ እጅ በሚገኘው በአሰብ በኩል እንዲገባ [illegible] አቅርቦ

የግቡም የኢጣሊያ መንግሥት ፍላጎት ሰላ ነበረ፤ ንጉሥ ምኒልክም ስላተሰማማበት ከአፄ ዮሐንስ ሱልጣን ችግር ቢያጋጥም ራሱ ለመፍታት እንደሚችል ቃል ስለገባለት የጦር መሣሪያ ለምኒልክ ለማምጣት በዐሰብ በኩል ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

2ኛ/ የጦር መሣሪያ በተላኩ የሚያዘበት መንገድ አጣዮቶ ነበረ። ቫቲካን እንደሚያታወቀው የሮም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ከመንፈሳዊ ሥልጣን በተጨማሪ የእንዳንድ የኢጣሊያ ክፍለ ሀገሮች ያተረ የዓለማዊ የመንግሥት መሪ ነበሩ። ይህ ስልጣናቸው ግን የኢጣሊያ መንግሥት በተቋቋመ ጊዜ በኃይል ተነጥቀው ነበር። የአንቶኔሊ አጎት ካርዲናል ሆኖ የሊቀ ጳጳሱ ዋና ጸሐፊ በመሆኑ ምኒልክ የሚፈልጋቸውን ሬሚንግተን ጠመንጃዎች በቫቲካን ግምጃ ቤት ተከማችተው እንደሚገኙ ያውቅ ነበር። በዚህ ዕድል በመጠቀም አንቶኔሊ የጦር መሣሪያዎቹን ሁለት ሺህ ጠመንጃዎችን ለምኒልክ ለመሸጥ ችግር አላጋጠመውም። አንቶኔሊ ማርች 27 ቀን 1881 ዓ ም ከንጉሥ ምኒልክ ጋራ ኮንትራት ተፈራርመው ፍቤሀዐርዌ18 /1881 ዓ ም ወደ ሀገሩ ለመሔድ ከሸዋ ተነሣ። አንቶኔሊ እና አንቲናሪ ባረቀቁት ንባብ ምኒልክ ስለኮንትራቱ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ደብዳቤ እንዲጽፍ አድርገውታል ። በዚህ ደብዳቤም ምኒልክ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጻፈው የኢጣሊያ ቆንስል በሸዋ እንዲቋቋም፣ በዚህ የታም አንቲናሪ እንዲመደብ ጠይቋል።

ንጉሥ ምኒልክ በጠየቀው መሠረት ኦገስት 7/1882 ዓ ም ከኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተጻፈው ደብዳቤ አንቲናሪ በሸዋ የኢጣሊያ መንግሥት ሙሉ ወኪል ባለሙሉ ሥልጣን አንቶኔሊ ምክትሉ አድርጎ ሾመቸው ነበር። ነገር ግን አንቲናሪ በመሐሉ ስለሞተ ኃላፊነቱ በሙሉ አንቶኔሊ ተረከበ። በዚህ መሠረት ይህ ዓመት ሌት ማረፊያ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ድርጅት በመሆን ያገለገለበት ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ ጣልያኖች ከዘይላ ወደ ሸዋ ለማጓጓዝ ይደርስባቸው የነበረ ውርደት በማብቃቱ ተደስተው ይደርስባቸው የነበረ በደል ለመበቀል የቀጠበት ጊዜ ነበረ ። በዚህ በላይ አዲስ መንገድ ትኩረት የሳበው ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር መንገድ የከፈተ በመሆኑ ነው። አንቶኔሊ ጃንዋሪ 29/1882 ዓ ም አንኮበር ሲገባ ንጉሥ ምኒልክ በታላቅ ክብር ነበር የተቀበለው ። ሁለት ጊዜ በአቡነ ማሳያ ሲፈረም የነበረው አውንም በአንቲናሪ ሲፈረም ታስቦ የነበረው በሸዋና በኢጣሊያ መሐል የንግድ ስምምነት አንቶኔሊ ከምኒልክ ጋር ተፈራርመው። አንቶኔሊ ሌት ማረፊያ በሆስፒታል ማከሚያ ሸፋን ስም እንዲሰጣት ባሰበው መሠረት እንደ ሐኪም በኃላፊነት ቦታውን እንዲመራ ተደረገ ። ምኒልክ ወደ ኢጣሊያ መልክተኛ እንዲልክ ቃል ገብቶ ስለነበረ አንቶኔሊ በተደጋጋሚ ቃሉን እንዲያከብር ሲጠይቀውም ለአራት ዓመት ምክንያት በመፍጠር አቆይቶ በ1889 ዓ ም አፄ ዮሐንስ ከሞተ በኋላ በራሱ መኳንንት የሚመሩ መልዕክተኞች እስኪልክበት ጊዜ ድረስ መልዕክተኞቹ እልካለሁ እያለ በአፍ ብቻ ሲያታልላቸው ነበር ። ራስ መኮንን ኢጣሊያ ሲገባ በመጀመሪያ የተቀበለው የሌት ማረፊያ ዋና መ/ቤት ኃላፊ የነበረው የኢጣሊያ ጂኦግራፊ ማኅበር አባላት ነበሩ ።የሌት ማረፊያ መደምደሚያ የነበረው የውጊል ውል

ነበረ። ሌት ማረፊያ የተዘጋው በዓድዋ ጦርነት ምክንያት ነበር ። የሌት ማረፊያ አስተዳደርና የኢጣሊያ መንግሥት ወኪል ባለሙሉ ሥልጣን ደርቦ ይሰራ የነበረው ትራቨርሲ የተባለው ሊሰናበት ወደ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሊቀርብ በምትኩ የመጣ ከሙኒ ፒያና ሥራውን ለመጀመር ባልተለመደ ሁኔታ ነው ዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸው ሊቋረጥ የቻለው። ተሰናባቹ ብዙ ዓመት



በኢትዮጵያ በተቀመጠበት ጊዜ የተደረገለት ትብብር አመስግኖ ለአዲስ የኢጣሊያ ወኪልም ትብብር እንዲደረግለት ለመጠየቅ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ተረካቢውን የኢጣሊያ መንግሥት ወኪል ከበፊቱ የበለጠ የሁለቱ ሀገሮች ግንኙነት እንዲሻሻል የመንግሥቱ ፍላጎት መሆኑን በመግለጽ ንግግሩን ሲጨርስ አጼ ምኒልክ፣ ሌላ ነገር ምንም ሳይናገር 'መቼ ነው ወደ ሀገርህ ተመልሰህ የምትሄደው? ብሎ ጠየቀው። በዚህ ጥያቄ ፒያና ያልተዘጋጀ በመሆኑ ወዲያውኑ ግራ ሳይገባው ግርማዊነትዎ ከፈቀዱልኝ ጊዜ ጀምሮ ነው ብሎ መልስ ሰጠ ።አጼ ምኒልክ በመቀጠል ከዶክተሩ ጋር ለምን አትመለስም፣ ከዚህ የበለጠ አጋጣሚ ልታገኝ አትችልም አለው። ፒያና የዚህ ዓይነት መልስ ይጠብቃል ብሎ ያላሰበው በመሆኑ ምንም ዓይነት መልስ ሳይሰጥ ወደ ሀገሩ የመመለስ ጥያቄ ተቀብሎ ከአዲስ አበባ ወደ ሌት ማረፊያ አመራ። በአጼ ምኒልክ ፊት ለመናገር ያልደፈረው ኮሙኒ ፒያና ዶክተር ትራቨርሲን ሌት ማረፊያ ሲያገኘው አንተ ይህን ሁሉ ዓመት ስትቀመጥ ከሀገር ውጣ ሳይልህ ለእኔ በአንድ ቀን ከሀገር እንድወጣ እንዴት ጠየቀኝ እያለ እየጮኸበት ተናገረው ። አጼ ዮሐንስም ሰው ከሀገር ሲያባርር በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር ። የንጉሠ ነገሥቱ ስም ተቀይሯል የኢትዮጵያውያን ባህል ግን አልተቀየረም። ሌት ማረፊያ ከንጉሡ በመስማማት በግሉ ይተዳደር የነበረው ብቻ በአዲስ አበባ ይኖር የነበረ ኢጣሊያዊ ካፑቺ የተባለውና አንድ የቤፍ የተባለው ኢትዮጵያዊ እንዲረከቡ ተደርጓል ። ካፑቺ ማንኛውም መረጃ ለኢጣሊያ መንግሥት እንዲያስተላልፍ ተነግሮት ነበር ። ምጽዋ ላሉት የኢጣሊያ ባለሥልጣናት ኢትዮጵያ ለጓደኛ ታደርገው የነበረ ዝግጅት ያስተላልፍ ነበር። ሰላይ ተብሎ ተይዞም ታሰረ ፣ ኢርኪውያን ዳኞች ያሉበት ፍ/ቤት ቀርቦ ሞት ተፈርዶበት ነበር ። አጼ ምኒልክ ግን ምሕረት ተደርጎለት በአንድ አምባ ታስሮ እንዲቀመጥ አደረገው። ከጦርነት በኋላ ከጦር እስረኞች ጋር ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች ሌት ማረፊያ ለሳይንሳዊ ምርምር እናውላለን በማለት ይመለስልን ብለው ጠይቀው ነበር፤ ነገር ግን ጥያቄያቸው ተቀባይነት አላገኘም ።

## አንቲናሪ እና አንቶኔሊ

ጣሊያኖች በሌት ማረፊያ ጣቢያ ማእከል መስርተው የሸዋ ፖለቲካ politica Scouna ብለው ይጠሩት የነበረ የስለላ መረባቸው ለመረዳት አንቲናሪና አንቶኔሊ በሸዋ የፈጸሙት ተግባር ገለፃ ካልተጨመረ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ትኝ ግዛት መመስረትና የአቡነ ማሳያ ሥራ የተሟላ ሊሆን አይችልም። ስለቱም ሰዎች የሸዋ ፖለቲካ መስራቶች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። አንቲናሪና አንቶኔሊ የካርዲናል ማሳያ ተማሪዎች ናቸው ። አንቲናሪ እንደ አቡነ ማሳያ የተላከበትን ሳይንሳዊ ተግባር ትቶ ወደ ፖለቲካ ሰው ተለውጦ ከንጉሥ ምኒልክ ጎን ሆኖ በሸዋ ጊዜውን ያሳለፈው በፈታደንነት በወርቃማ እስር ቤት የኖረ ነበር ። የምኒልክ

ጓደኞች ጣሊያኖችን የጦር መሣሪያ አቀባዮች አድርጎ አፄ ዮሐንስን ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለመጨበጥ በነበረው ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ ነበር ። አፄ ዮሐንስም በሸዋ የተቀመጡ ጣሊያኖች ተግባራቸው ስለተረዳ መቃወም አልቀረም። በዚህ መሠረት ዋናው ቆንሮዎቸው የነበረ አቡነ ማሳያ የአፄ ዮሐንስ መቀመጫ ዋና ከተማ ወደ ነበረው ወደ ደብረ ታቦር እንዲላክ አድርጎ ከሀገር አባረረው። ነገር ግን የአቡነ ማሳያ መባረር ለጣሊያኖች ከባድ ችግር አልፈጠረባቸውም፤ ምክንያቱም በእሱ የተተኩት ሰዎች ለምኒልክ

የጦር መሣሪያ በማቀበልና የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሠረት በመጣል በበለጠ ሁኔታ አስፋፍተው ቀጥለውበታል ።

እንደሚታወቀው የውጫሌ ውል የዓድዋ ጦርነት ሊያስከትል ችሏል ። የዘመኑ የኢትዮጲያ መሪዎች በደቡብ ሆነ በሰሜን በቅኝ ገዥነት ኢትዮጵያ እንዳትገባ ፍላጎት እንደነበራቸው የሚያስረዳ ምኒልክ የጦር መሣራያ ጣሊያኖች እንዲያቀበሉት ከመጠየቁም ሌላ ከጣሊያኖች በተሰጣቸው ልጥ ማረፊያ መሬት ላይ በራሱ ኪሣራ የቴክኒክ ት/ቤት እንዲያቋቁሙለት ጠይቋቸው ነበር ። ነገር ግን ጥያቄው ጣሊያኖች ከነበራቸው ዓላማ ውጭ ስለ ነበረ ተቀባይንት ሳያገኝ ቀረ ። ጣሊያኖች ለምኒልክ የሚሰጡት እርዳታ የጦር መሣሪያ ማቀበል ብቻ የተወሰነ ነበር። በአንድ ወቅት ጣሊያኖች የተሰጣቸው የልጥ ማረፊያ መሬት ከሳይንሳዊ ተግባር ወደ ፖለቲካ ከለወጡት በኋላ የባሪያ ንግድ ለመቆጣጠር ሰብአዊ ተግባር ለማከናወን በማስመሰል ሙከራ በሚያደርጉት ጊዜ ምኒልክ የባሪያ ንግድ በሀገሩ ለመዋጋት እንድችል የጦር መሣሪያ እንዲሰጠው ብለው ለዓለም አቀፍ የባሪያ ንግድ አስወጋጅ ሰብአዊ ድርጅት ደብዳቤ እንዲጽፍ አደረጉት። ምኒልክ በግሉ በባሪያ ነጋዴዎች ሰፈር ደፈጣ በማድረግ ሁለት ሺህ ባሮች ነጻ አወጣኋቸው ብሎ በመጥቀስ ስለገለጠ አንቲኖሪ ለምኒልክ የሚሰጥ የጦር መሳሪያ ለሰብአዊ ሥራ እንደሚውል ለማስረዳት ኖቬንበር 11/1878 ዓ ም ለዋናው መሥሪያ ቤት ለኢጣሊያ ጆአግራፊ ማህበር በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል ። ይህ ሰብአዊ ድርጅት ነፃ የሚለቀቁ ሰዎች የሚያርፉበት ያነፃነት መንደር እንዲመሰረት አቡነ ማሳያ ኃላፊ እንዲሆን ሀሳብ ነበረው ። ነገር ግን ከመጀመሪያም የሃሰት ወሬ ስለነበረ ውጤት ሊገኝ አልተቻለም ። የተለቀቁ ባሪያዎች እንኳን በመንደር ሊሰባሰቡ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ሳይመለሱ በግላቸው ነበር በውድም በጎጃም የተከፋፈሉቸው። ቢያንኪ የተባለው ኢጣሊያዊ በሌላ ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ የተላከው ካንቲኖሪ ጋር በባሪያ ንግድ የተነሳ ብዙ ንትርክ እርስ በእርሳቸው ፈጥረው ነበረ ። አንቲኖሪ ምኒልክን በመደገፍ የባሪያ ንግድ የሚካሄደው በኢትዮጵያውያን እስላሞች ብቻ ነው ብሎ ሲከራከር ቢያንኪ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችም በተለይ በሸዋ የባሪያ ንግድ በድብቅ ያካሄዳሉ የሚል አስተሳሰብ ነበረው። ከዚህ የባሰም ያከራከራቸው በሀገራቸው ጋዜጦችና መ/ቤቶች በሰፊው በይፋ የወጣ ጠባቸው ስለ ቺኪ የተባለው ኢጣሊያዊ ነበር ። ቺኪ የኢጣሊያ ጆዮግራፊ ማህበር አባል ነው፣ ቺኪ ከኪያሪኒ ጋር ሆኖ ጣሊያኖች በጆዮግራፊ ማህበር የተላኩበት ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ወደ ኢካቶሪያል ሐይቆች አምርተው ነበር ። ነገር ግን ጌራ ሲደርሱ ባልታወቀ ምክንያት በጌራ ንግሥት ትእዛዝ ታሰሩ። በእስር እንዳሉ ኪያሪኒ ታሞ ሞተ፣ ቺኪ ጓደኛው ሲሞት ወደ ሸዋ ለመመለስ ስለተከለከለ ለአለቃው ለአንቲኖሪ ከእስር እንዲያስፈታው እርዳታ ጠየቀ። ለዚህ ተግባርም ንጉሥ ምኒልክ ፣

ጎጃሙ ራስ አዳል እና አፄ ዮሐንስ ከእስር እንዲያስፈቱት ተጠይቀው ነበር ። ጣሊያኖች የሚያውቁትና ግንኙነት የነበራቸው ከምኒልክ ብቻ ነበር ። በአጼ ዮሐንስ እምነት ደግሞ የምዕራብ ኦሮሞ ሕዝቦች እስከ ከፋ ድረስ ኃላፊነት ያለው ምኒልክ ሳይሆን ራስ አዳል ነበረ ።

ስለዚህ በራስ አዳል በኩል በአጼ ዮሐንስ ትእዛዝ ቺኪ እንዲፈታ ተደርጓል ። የቺኪ መፈታት ምክንያች በማድረግ በአንቲኖሪና በቢያንኪ መካከል ሰፊ ልዩነት ተፈጥሮ ነበር ። ቢያንኪ ንጉሥ ምኒልክ ቺኩን ከእሥር ለማስለቀቅ ጥረት ሳያደርግ በመቅረቱ ወቀሳና ስድብ በሀገሩ ጋዜጦች አሳትሞ ስላወጣ አንቲኖሪም በቢያንኪ ላይ ተቃውመውን በማሰማት ንጉሥ ምኒልክ



በመደገፍ ሁለት ረጅም ደብዳቤዎች ጽፏል ። አንዱ ደብዳቤ ለኢጣሊያ የጅዮግራፊ ማህበር [1], ሌላው ደግሞ ለቺኪ። [2]. በዚህ ደብዳቤ አንቲኖሪ የሸዋ ፖለቲካ ተብሎ የሚጠራ ቡድን ደጋፊ መሆኑን ያንጸባረቀበት ወቅት ነበር ። ቢያንኪ በምኒልክ ላይ የሰነዘረባቸው ወቀሳዎች ለእኔ በሸዋ የምኖር ሊጎዱኝ ይችላሉ ካለ በኋላ ቢያንኪ ምኒልክ ላደረገለት እርዳታ ውለታ ለመመለስ ሲገባው ተገቢ ያልሆኑት ስድብና ማፌዝ መሰንዘር አስፈላጊ አልነበረም ። ቢያንኪ ምኒልክ ላይ ችሎታ የሌለው፣ ሀሰተኛ የባሪያ ንግድ ደጋፊ ወዘተ....ብሎ የሰጠው አስተያየት በሙሉ ከእውነት የራቀ ነው። ለዚህም ማስተባበያ መጥቀስ የሚቻለው የካቶሊክ ሚሲዮን አባቶች እንኳን ሳይቀሩ ከሸዋ ቢባረሩም ከምኒልክ ጋር የወዳጅነት ደብዳቤዎች እየተለዋወጡ ናቸው ። እኔ በጭፍን ዓይን ምኒልክ ደጋፊ አይደለሁም፤ መርሳት የማይገባን ግን ምኒልክ አንድ አፍሪካዊ ንጉሥ መሆኑን ነው።በጎንደር እስር ቤት ሆኖ ከቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት በአክራሪ ደንቆሮች የጎንደር ጸረ ፈረንጆች የቤተክህነት ሰዎች ያገኘው አስተዳደግ በሕይወቱ ላይ ተጽእኖ አሳድሮበት ይሆናል ። ስለዚህ በደም የተወረሰ የዘሩ ጉድለት በተጨማሪ በአስተዳደግ ያገኘው በነሙች ላይ ጥላቻ የማይለቀው በምኒልክ ላይ መደነቅ አያስፈልግም ። ነገር ግን ማየት ያለብን ከእነሱና ከሹማምንቶቹ፣ በተለይም ከእሱና ከአጼ ዮሐንስ ምን ያህል ልዩነት እንዳለ ነው ። ምኒልክ ኩራተኛ አይደለም ፤ ቂም በቀል አያውቅም፣ ሰው መግደል አያውቅም፣ በሀይማኖት አክራሪ አይደለም ፣ ኤውሮጳውያንን ይወዳል፣ የእነሱን ስልጣኔና እንዱስትሪን የሚያደንቅ ነው። በዚህም በኢትጵያ ህዝብ በከፊልም በአጼ ዮሐንስ በተቃራኒ አቋም ይገኛል። አጼ ዮሐንስ ምኒልክ በፖለቲካና በተንኮል ቢበልጠውም በግብረገብነትና በደግነት ግን ከምኒልክ ያነሰ ነው። አጼ ዮሐንስ በኤውሮጳውያን ላይ ጥርጣሬ አለው። በነገሠ ጊዜ ለጥቂት ጊዜ ከኤውሮጳውያን ጋራ ይስማማ ነበረ፣ በኋላ ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከኤውሮጳውያንና ከካቶሊክ ሚሲዮን መጣላት ጀመረ። አጼ ዮሐንስ አቡነ ማሳያ ከሀገሩ ለማባረር ሲፈልግ በማታላያ ዘዴ በመጠቀም ነበር። በካቶሊክ ቄሶች ላይ ጥላቻ እንዲፈጠር የሚያደርግ የኢትዮጵያ ቤተክህነት ነው። በምኒልክ በኩል ግን በቄስ ካቶሊኮችና በኤውሮፓውያን ላይ ያለው ከጥላቻ ውጭ ከመሆኑም በላይ ሲያቀርባቸውና ሲወዳቸው ይታያል በተንኮለኞችና ደንቆሮች የኢትዮጵያ ቤተክህነት አባላት ላይ ብቸኛ ሆኖ በመታገል የሚሸሩበት ሴራ ያከሽፍብባችዋል፣ ይንቃቸዋል፣ ይስቅባቸዋል ። ከእሱ አካባቢ ያሉት የእሱ ሹማምንቶች ግን ከእሱ አስተሳሰብ የራቁ ናቸው።

ብዙ ኤውሮጳውያን አታለውት ሳይቀየም ምህረት ማድረጉ መንፈስ ጠንካራ መሆኑ ያሳያል። አጼ ዮሐንስ ግን ብልጥ ስለሆነ አይታለልም። ምኒልክ የአንድ ደጉ አፍሪካዊ ንጉሥ ምሳሌ ነው ለማለት እንዳሰብኩ ትገምቱኝ ይሆናል፣ ዳሩ ግን አስቀድሚም ተናግሬአለሁ፣ ምኒልክ ጥሩ ጠባይ ቢኖረውም ጉድለትም አለው፣ ከጉድለቶቹ መካከል ነገሮችን ማቅለል፣ ቸልተኝነት፣ እንዲሁም በቀላሉ በአማካሪዎቹ መታለል ናቸው።

የእኛ ሰዎች ወደ ደቡብ ምዕራብ ሲጓዙ በምኒልክ ባንዲራ መታጀብ ሲገባቸው እነሱን ግን ያጅባቸው የነበረ የግብፅ መንግሥት ሰላይ፣ ወኪል የነበረው የሀይማኖት ሰው ሐጂ አማን የተባለው ነበረ ። ምኒልክ ስለ ሐጂ አማን ሲነገረው ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር፣ ነገር ግን እንዲከታተለው የተላከ ሹም በጉቦ ለቀቀው ። ለምኒልክ ግን ሸሸቶ አመለጠ ብሎ ነገረው። ምኒልክ አስፈላጊውን

[1] .Leopolodo Traversl Let Marefia p 181-189
[2] Leopolodo Traversl Let Marefia p 177-181

እርምጃ በዙው በመውሰድ ፋንታ ለምን ለተቃችሁት በማለት ብዙ ከተለመደ ቸልተኝነቱና በጥልቀት ያለማየት ብዙ አበሳ ራሱ እንጂ ምንም አላደረገውም። ሐጂ እማን እንደልቡ በነፃ ስራውን ቀጥሎ ለቼኪና ለኪያሪኒ ሥራቸውን እንዳይተጥሉ ጥና እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

ቼኪና ኪያሪኒ ጉዞዋቸውን ከመጀመራቸው በፊት ምኒልክ አስተድሞ ሥልጣን ያለው ሰው መንገዱ እንዲያመቻችላቸው መላክ ይገባው ነበር። በተለመደ የቸልተኝነቱ ግን ይህን ሁሉ አላደረገም ነበር። ግን ይህ አንዳንድ ሰዎች እንዳወሩት ጎደኝነት አይደለም። ቼኪና ኪያሪኒ ስለደረሰባቸው ስቃይ ምኒልክ ጥፋት የለውም. ምክንያቱም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ናቸው እነዛ መንግሥታት በራስ ጎበና ጦር ዘመቻዎች ወደ እጁ የወደቁት። ቼኪና ኪያሪኒ የሚገኙበት ሁኔታ ብዙ ሰዎች እያወቁ አይናገሩም ነበር። ምኒልክ ግን ምንም አልደረሰበትም ነበር። እጁ የሐንስ ቢጠይቁትም እንደማያውቅ ነበር የነገራቸው። ምኒልክ የቼኪና ኪያሪኒ መታሰራቸው እኔ በደብዳቤ ስነግረው ግርቲኒም የጦር መሣሪያ ስላላመጣ ተናዶ ስለነበረ ወዲያውኑ ለራስ ጎበና ለመጻፍ አልፈለገም፤ ግርቲኒ ቃሉን አላከበረም፤ በግርቲኒ ምክንያት ምኒልክ ብዙ ወጪ አውጥቷል ምኒልክ ብዙ በድብ ደርሶበታል ቢባ ከማለትም አልተመለሰም ።

ይህ የግርቲኒ ጉድለት ግን በቼኪና ኪያሪኒ ላይ ቂም በቀሉ መወጣት አይገባውም ነበር። ቀይቶ ግን እኔ ደጋግሜ ባስረዳሁት መሠረት ስህተቱን አምኖ ፈረሳቸው ጀምሮ ነበረ። ነገር ግን በዚሁ ጊዜ ቼኪ በራስ አዳል እግካኝነት ከእስር ተለቅቆ ነበር ስለዚህ የምኒልክ ዘግይቶ የደረሰ የከንቱ እርዳታ ሆነ ቀረ። ምኒልክ በዚሁ ጊዜ የተፈጥሮ ደግነቱ ወደ ጎን አስቀምጦ የአፍሪካዊ ደመ ግፉትን ስለመረው ከሌሎች የሚለየው ጠባይ ጥቅም ላይ አላዋለም። ወረኢሉ እማኘቼው በቃል ባነጋገርኩት ጊዜም ራስ ጎበና ሳገኘው ትዕዛዝ እሰጠዋለሁ ነበር ያለኝ፤ ሌላ ጊዜም ስለ ቼኪ ጉዳይ እኔን ማግባት አልፈለገም ነበረ ያለኝ፤ በዚህ ጊዜ ልቤ በሐዘን ተሞጠ ። ግን ጥፋቱ የማን ነው?

በቼኪና ኪያሪኒ የተነሳ ምኒልክን ከንመገመ በኋላ ወደ ሌላ ጉዳይ ወደ ቤይሩል እልፍት ጉዳይ በመዝለል በቤይሩል የሞቱት የኢጣሊያኖች ደም እኔ አበቀበለኛቸዋለሁ ብሎ ምኒልክ የተናገረውን በመጥቀስ የኢጣሊያ መንግሥት ትብብር ላለማድረግ ሕፍረት ይሰማኛል እያለ ይህ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የአሰብ ሾዋ መንገድ ይከፈት ነበር። ያቺ ደረቅ የአሰብ ወደብ ከመሐል ኢትዮጵያ በመንገድ ካልተገናኘች ምንም ጥቅም እንደሌላት በማለት አስተያየቱን

አጠቃለሉ ዕፋሉ፤ ተጥሎም ፈረንሳዮች በጅቡቲ በኩል ከአሰብ ጋር የሚያደርጉት ውድድር የኢጣሊያ መንግሥት እንዲያስብበት በማስጠንቀቅም ጽፋሉ። አንቲኖሪ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ታስቦ ስለነበር ወርቃማ በሸዋ የእስር ቤት ኑሮ ለማራዘም ኦክቶበር 1881 ዓ ም አንቲኖሪ የኢጣሊያ ወኪል ሆኖ ቀንሲል ተሹሞ እንዲቀመጥና ለዚህም ስራ ሌላ ሰው መላክ እንደማያስፈልግ ደብዳቤ ለኢጣሊያ መንግሥት ምኒልክ እንዲጽፍ ራሱ አንቲኖሪና አንቶኔሊ አድርገውታል። ኦገስት 7 /1882 ከኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለንጉሥ ምኒልክ የተላኩ ደብዳቤዎች አንዱ ምኒልክ ባቀበው መሠረት የአኒቲኖሪ የቆንስል ሹመት የሚያበስር ነበር። ነገር ግን ኦክቶበር 17/1882 ዓ ም አንቶኔሊ ለኢጣሊያ መንግሥት ሲጽፍ አንቲኖሪ ኦገስት 26/1882 ዓ ም ስለሞተ ባይታሰብ በምትኩ ራሱ አንቶኔሊ ኃላፊ እንዲሆን ተመኘ። በእቡነ ማሲያ ከሆኑ ተባር መለየት በአንቲኖሪ በሞት መለየት ሦስተኛ ሰው የሸዋ የፖለቲካ



መሥራቶችና አራማጆች አንዱ ሳይታሰብ ዕድሉ ተሳክቶለት የቀናውና ስሙ በታሪክ በሰፊው ያስጠራው አንቶኔሊ ሆነ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓድዋ ጦርነት ጊዜ ድረስ አንቶኔሊ ብቸኛ በሸዋ የኢጣሊያ ወኪልና ተዋናይ የሸዋ ፖለቲካ አራማጅ ሆኖ ነበረ ።



# ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ወረራዎችና ጦርነቶች

## ምዕራፍ 7. የሠሐቲና የዶጋሊ ጦርነቶች

### 1. ከዶጋሊ ጦርነት በፊት ሆነ በኋላ የነበረ ሁኔታና ጦርነቱ

ከድሮ ጀምሮ በኢትዮጵያ እርስ በርስ ጦርነት ያልተለያት ቢሆንም ከኢጣሊያ በፊት የነበረው የመገንጠል እንቅስቃሴ አልነበረም። ስለዚህ ኢጣሊያ አሰብን ገዝታ በኢትዮጵያ መሬትና በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ በ1869 ዓ.ም ሀገራችንን ለቃ እስከሄደችበት ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933 ዓ.ም 72 ዓመት ተቆጥሯል። ከ1933 ዓ.ም እስከዛሬ 1990 ዓ.ም ድረስ ደግሞ 67 ዓመት ሆኗል። በድምሩ 139 ዓመታት ተቆጥሯል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ ኢትዮጵያውያን አልቀዋል። ብዙ ንብረት ወድሟል። ሌላ ዓለም በሥልጣኔ ሲራመድ ሀገራችን በሥልጣኔ ወደኋላ እንድትቀር ተገድዳለች። በዚህም የተነሳ በእነዚህ ረጅም ዓመታት ውስጥ ሀገራችን ሰላም አግኝታ አታውቅም። ይህ የሆነበት ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢጣሊያ ሀገራችንን በውረርዋ የተነሣ የተለኮሰባት የማይበርድ እሳት መሆኑን እንረዳለን። ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነት የገጠሙት በራስ አሉላ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦርና በሎሬኔል ደ ክሪስቶፎረስ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር በ1887 ዓ.ም በዶጋሊ ላይ ነው። ሆኖም በበዶሉል ላይ አሩሮች አሥራ አራት ኢጣሊያኖችን የገደሉበት ዐረ ትኝ አገዛዝ አንድ ገድታ ስለሆነ እንደ አንድ ጦርነት ሊቆጠር ስለ ሚችል ከጣሊያኖች ጋር ያደረግነው የመጀመሪያ ጦርነት ልንቆጥረው እንችላለን። ከዶጋሊ ጦርነት አንድ ቀን በፊት የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፓርላማ ተገኝቶ ስለ ራስ አሉላ ያደረጋቸው ዛቻዎች በራስ አሉላ ስር ስለነበሩ የኢጣሊያ ዜጎች ስቀረቡለት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ ለአ ፍሪካውያን የነበረውን ንቀት የተሞላበት አነጋገር በሰነዘረው ዝነኛ ሆነው የሚኖሩ ቃላቶች መልስ ሲሰጥ «በአገሬ ችን ልንረግጣቸው የምንችል እፍኝ የማይሞሉ ዘራፊዎች አጋንኖ ማውራት አስፈላጊ አይደለም» ብሎ ነበር።[1] ራስ አሉላ የሐማሴን ሀገረ ገዥ ነበሩ። ሐማሴን ሲባል ዛሬ የምናውቃት ሐማሴን ብቻ የሚያመለክት አልነበረም። ኢጣሊያ ወደ ኤርትራ ስትገባ ኤርትራ በሙሉ ሐማሴን ተብላ ትጠራለች። ወሰኑም ከሰሜን እስከ ከሰላና የጉበጽ መሬት ይደርሳል። በደቡብ በግዴታ እስከ መረብ ብቻ አልነበረም። በታሪክ እንደምናውቀው ብዙ ባሕር ነጋሢዎች ከመረብ ተሻግረው ሽሬ አድዋ የገዙበት ጊዜ ነበረ። በራስ አሉላ ጊዜ የዚው አይነት ሁኔታ እንደ ነበረ ነው የሚገመተው። ስለ ራስ አሉላ የትውልድ ሀገሩ ብዙ ጊዜ እንደሚባለው ከተምቤን ብቻ አይደለም የሚወለደው በእናቱ እናት ከአከለጉዛይም ይወለዳል።

1 Carlo Zaghi : Le Origini Della Colonia Eritrea p.126



በዶጋሊ ለጦርነት የተገደሉ የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች



Gli ufficiali caduti a Dogali. - *Da sinistra a destra: prima linea:* cap. Longo, cap. Benetti, cap. Paglioli, cap. Di Benedictis, cap. med. Gasparri; *seconda linea:* ten. Fusi, ten. Gattoni, ten. Di Bisogno, ten. Feliciani, ten. Galanti; *terza linea:* ten. Griffo, ten. Sburlati, ten. Comi, ten. Saccani; *quarta linea:* ten. Tirone, ten. med. Ferretto, ten. Cu... (caduto a Saati), sottoten. Dessi; *quinta linea:* sott. Tofanelli, sott. Martello, sott. Lombardini, sott. Bellentani. *Nell'ovale:* ten. col. De Cristoforis.

የሐማሴን ሀገረ ገዥ ሆኖ የተሾመው በ1879 ዓ.ም ነው። ራስ ወ/ሚካኤል በግብጽ እርዳታ የመረብ ምላሽ ሀገረ ገዥ ሆኖ ከአጼ ዮሐንስ ስልጣን ውጭ ለመሆን ብዙ ጊዜ ታግሎ ነበር። ነገር ግን የአጼ ዮሐንስ ታማኝ ቀኝ እጅ የነበረው ሻለቃ አሉላ በኋላም ራስ አሉላ እንግዳሰ ለመጀመሪያ ከአጼ ዮሐንስ ጋር እንዲታረቁ አደረጋቸው። አንድ ላይ ሆነው በጉራን ከግብጽ አስለቀቁ። ለተቀምር 1870 ዓ.ም በአጼ ዮሐንስ ትእዛዝ ራስ ወ/ሚካኤል ታስሮ ወደ አምባ መቀ ተወሰደ። ሻለቃ አሉላም ራስ ተብሎ የሰሜን መስኖችን ወሰቀ ቅርስ ጋሻ ተብሎ የሐማሴን መረብ ምላሽ ሀገረ ገዥ ሆነ። ጣሊያን ምጽዋን በወረረ ጊዜ ኢትዮጵያ በሁለት ግንባር አደጋ ተደቅኖባት ነበር። 1) ምጽዋ ከጣሊያኖች ጋር 2ኛ) በከሰላ ከመሐዲዎች ጋር። ስለዚህ ምጽዋ ወረራ አደገኛ ሆኖ አልታየውም ከተቀመጡም የግብጾች አስተዳደር የተለየ መሆኑ አልታየውም ነበር። በስለዚህ ወደ ከሱዳ ዘምቶ በደርቡሾች ላይ ድል ተቀዳጅቶ በትዝብቱ ላይ አስቀትኛ የመቀለል አደጋ ደርሶበት አሥመራ ሲገባ ጣሊያኖች ከምጽዋ ከተማ አልፈው በተቀሰኙ ደጋ ያለነበረ መሬቶችን መያዛቸው መረጃ ያልደረሰው ስለነበረ ቁጣቸውን ለማ ሳያሳ ሐኪሞቹና መድሃኒቶች እንዲሰበሰብ ለኢጣሊያ ጦር ቶና አቶር መልእክት ላከ ነበረ። ነገር ግን ኢጣሊያኖች የሀገሩ ጉዳዮች ወደቂ በመሆን ከምጽዋ ከገቢያ መሰማማታቸውን በሰማ ጊዜ በኃይለኛ ቁጣና ብስጭት ሐኪሞቹንና መድሃኒቶችን አስፈለጋም ብሎ በንቀና አጼ ዮሐንስ በመመለስ እንዲመለሱ አድርጎ የሀገሩ ጉዳዮች ከገቢያ ከምጽዋ እንዲለቁር በመመልከት ለኢጣሊያ ጦር ቶና አሳሽ ደብዳቤ ጻፈ። ጣሊያኖች ምጽዋን ከወረሩ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ጦርነት ወይም ከፍተኛ ግጭት እንዳን የሚያደርሱ ሁኔታዎች አልነበሩም። በሁለቱ ሀገሮች በመሐከል ሰላም ሰፍኖ ስለነበረ ጣልያኖች የተቆጣው አንድ ኢጣሊያዊ መሐንዲስ ከሰሀ ተደረጉ ለተቋም ንጉሥ ተ/ሃይማኖት አንድ አስቀትኛ ደብዳቤ በርቀት ስለነበረ አውግም ሉል ተለኮ በቁረሙም! ሉል ድብድቤ ሉመ ምሬት ምግል ዝሏን አስተቁር 9/1886 ዓ.ም ምጽዋ ደርሶ በትግራይ በኩል ወደ ጉዞም እንዲደርና እንዲፈ ቅድሰት አሰብ አሉላ ወደቀ ስለነበረ! ራስ አሉላም ከአጼ ዮሐንስ አስፈትዶ በለተፈቀደለት ከሉሉች ጣሊያኖች ጋር ሆኖ ግለት ከሸለቃ ዲያና የኢጣሪ አንድ ዓመት ለጂ ኮማንዴ ጋሪ! የፈረሰኛ የመቶ አለቃ ሜጀሪና በጋዲ ዝሓን ለሀቶች የሊማ ሊያ መድረሮች ተወሰው ሊለምበር 4/1886 ዓ.ም አሥመራ ደረሰው ራስ አሉላ ከነጉሥ ነገሥት ጋር ስለነበረ የራስ አሉላ መንደሮችና መሬቱ ከገቢያ ከፋ የሙቱ አቀባበል አደረጋላቸው።[1] ጀነራሉ 5/1887 ዓ.ም ራስ አሉላ ወደ አሥመራ ተመልሶ መጡ ራስ አሉላ ስለተቀበሉት ዓላማ ተደሰቱ ተቀባይነቱ ከነጄም ለተመለሱ ለአጼም[2] ቤተ ክርስቲያን ትክራሊያኖሽ ብሎ ጓሽን አስጋጅቶ ተሰናብቶ እጅልም ተሰናብተው ከአሥመራ ሲመለሱ ትንሽ ጊዜ ሲተረው ራስ አሉላ ጣልያኖች ዊን እንደያዙ መሰማታቸውን መረጃ ደርሶባቸዋል።

1 Carlo Zaghi: ibid p.122

2 Carlo Zaghi: ibid p.122





ጀነራል ታንክሬዲ ሳሌታ (Tancredi Saletta) በምፅዋ የመጀመሪያ የኢጣሊያ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ ኩሩኝል ሆኖ የኢጣሊያ ዘመቻ መሪ የነበረው የዘመቻው የሐሰት ዓላማ በአፍሪቃ በጂኦፖለቲካ ብሪታኒያ የሚመራ ጣልያኖች የተገደሉ ደም ለመበቀል በሰነዘር ከጣሊያኖች “በአንዲ ጋዜ ተር የአፍሪቃ ሕዝቦች ኢጣሊያ ስለውን ሠረ መሆናን አሳያቸው 2ኛ ለኢውሮፓ ኃያል መሆኗን 3ኛ ለመላ ዓለም ትልቅ መሆናችን አሳያችሁ” በሚል በተ ምኞታቸውን በመግለጽ ነበረ የሸፈቱ።

በዚሁ ጊዜ ራስ አሉላ ማሊምቢን ጠርቶ ጣሊያኖች የግብጾችን ፈለግ ተከትለው ኢትዮጵያን ለመውረር ሃሣብ እንዳላቸው ስጋት ስላደረበት በወዳጅነት[1] መልክ ለጀነራል ጀኔ ከዊዓ እንዲለቅና ምጽዋ ብቻ ሰፍር እንዲቀመጥ እንዲጽፍለት ይለምነዋል። ማሊምቢም ለራስ አሉላ የደረሱት መረጃዎች ሀሰት መሆናቸውንና እሱ በዓይኑ ያየው ግን ጣሊያኖች በምጽዋ ጦር ሰፈራቸው መሆናቸውን ገልጾ ደብዳቤ ለመጻፍ ግን ዝግጁ መሆኑን ነገረው፤ የተጠየቀውን ደብዳቤም ጻፈ።

ራስ አሉላ ለጊዜው ወደ ዓድዋ ጉዞውን እንዳይጀምር ለማሊምቢ ይነገረውና ጣሊያኖች ከዊዓ ተነስተው እንደሆን ለማረጋገጥ ወደ ጊንዳዕ ለመሄድ ይዘጋጃል።ሆኖም ማንኛውም ነገር ቢደርስ ጉዞዎቻቸውን የሚቀጥሉ መሆናቸውን ማረጋገጫ ይሰጠዋል። እሱ ግን የጀነራል ጀኔ መልስ ምን ልባት አትጋቢ ካልሆነ በመፍራት ከእኛ አንድ ሰው ወደ ምጽዋ ሄዶ ከጀነራሉ ጋር እንዲነጋገር ብሎ ሀሳብ ያቀርብለታል።[2] ራስ አሉላ ግን ፒያኖ ነጋዴ ግደሆን የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ሻለቃ መሆኑን ስለሰማ ጃንዋሪ 12/1887 ዓ.ም ዒት መንገደኞቹን ሁሉ ወደ ድንኳኑ ይጠራቸዋል። በጣም በቀዘቀዘ አነጋገር ከአንድ ሰዓት በኋላ በጊንዳዕ በኩል ወደ ሰሐቲ ሄዶ ጣሊያኖች እውነትም ኢትዮጵያን ወረው እንደሆን ለማረጋገጥ እንደሚፈልግ ገልጾ የጀነራሉ መልስ እንደመጣለት ጉዞዎቻቸውን የሚቀጥሉ መሆናቸውን ይነግራቸዋል። ጀነራሉ ግን ራስ አሉላ ከምጽዋ ጣሊያኖችን ለማባረር ከአሥመራ ተነስቶ ወደ ምጽዋ እየገሰገሰ መሆኑን የሚል መረጃ ስለደረሰው ዊዓና ሌሎች ጦር ሠፈሮችን በወታደርና በመሣሪያ ማጠናከር ጀመረ። በዚያው እለት ጊንዳዕ የደረሰው የኢትዮጵያ ጦር እስከ ጃንዋሪ 21 ዊዓን ለቆ እንዲወጣ ዛቻ ያዘለ ደብዳቤ ይጽፍለታል። ጀነራል ጀኔ ግን ወታደሮቹ ወደ ዊዓ የተላኩ ፀጥታ ለማስከበር ስለሆነ ካሉበት እንደማይነሱና እንዲያውም የሚያጠናክራቸው መሆኑን ይጽፍለታል፤ ተጨማሪ ጦርም ከሀገሩ እንዲላክለት ይጠይቃል። በዚሁ ጊዜ ከንቲባ ከፋ[3] የራስ አሉላ ወንድምና ወኪል በራስ አሉላ ትእዛዝ መንገደኞችን አስር ያለ ምግብ ከአሥመራ ወደ ጊንዳዕ አምጥቶ በዝናብና በብርድ ያስቀምጣቸዋል። ጃንዋሪ 17/1887 ዓ.ም ወደ ራስ አሉላ ድንኳን ቀረቡ፤ በሹማምንቶቹ ተከቦ ተቀብሏቸውና ፊቱን አኮማትር ለማሊምቢ እንዲህ ሲል ጠየቀው «የኢትዮጵያ ወዳጅ ነኝ አላልከኝም ነበር?» ማሊምቢም «ምንም አላውቅም» አለ። ራስ አሉላም በቁጣ ገንፍሎ «ለጀነራል ጀኔ ከዊዓ ወታደሮቹን እንዲያስወጣ ፃፍ ነበር ያልኩህ፤ እሱ ግን ሰሁቲን ያዘ፤ አሁንም ከሰሐቲ ወታደሮቹን እንዲያስወጣ ፃፍለት ካልሆነ አንገታችሁን እቆርጣችኋለሁ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ጦርነት እሄዳለሁ፤ ብዙም ግድ የለኝም» አለው።

1. Carlo Zaghi: Ibd p.123
2. Carlo Zaghi: Ibd p.123
3. Carlo Zaghi: Ibd p





የጦር ጀግናው ራስ አሉላ

RAS ALULA.

RAS ALULA.

በዚሁ ጊዜ ፒያኖ «እኛ የመጣነው ለጦርነት ቢሆን ኖሮ ባዶ እጃችንን እንዴት በእርስዎ እጅ እንያዛለን» ብሎ ንግግር ሲጀምር ራስ አሉላ በቁጣ ጉራዴውን በእጅ እየያዘ «ገደም ካላልክ ትገደላለህ» አለው። ሚሊዮቢኒ ቅር እያለው እንደገና ሌላ ደብዳቤ ገፈ «ወታደሮቹ ከተባሉት ቦታዎች ካልተመለሱ ጥንቅቃታችን ተቀርጦ ነው የሚላካቸሁ» ብሎ ጻፈ፤ ከሶስቱ ሹሞች አንዱ መጥቶ ስለአሊልአን ራስ አሉላ ከወገደሮቹ አንዱ አሜቴ የተባለ ወደ ምጽዋ ሄዶ በሁለት ቀን ውስጥ መልስ ይዞ እንዲመጣ ተላከ። ለመጀመሪያው ደብዳቤ መልስ መጣ ሚሊዮቢኒ ጥንቀት ስለደረሰት የራስ አሉላ ወገድም ከንቲባ ከፋ «የሀበተኛ መሳሮች ወሬ እየሰማ ነው እንጂ ኢጣሊያ በፍፁም ጦርነት አትፈልግም ብለህ ለራስ አሉላ ንገርልን» አለው። ራስ አሉላም «አንተ ውሸታም ነህ የሰሐቲ መድፎች ካልተነሱ ከወታደሮቹ ጋር ከምንኩሉና ከሰሐቲ መሐል ባለው መንገድ እንደምደርስ አላደሃለሁ» አለው።[1] ከምንኩሉና ከሰሐቲ መሐከል ያለውም ቦታ ዶጋሊ ነው። ተከሩይ በተባለው የእከሱም ተወላጅ ሰው ሌላ ደብዳቤ ተገፈ። ጃንዋሪ 20/1887 ዓ.ም አሜቴ የተባለው የኢጣሊያ መላደር ይዞት ለሄደው ደብዳቤ መልስ ደረሰ። ነገር ግን ጀነራል ጄኔ ካለፈው ጊዜ ሐሳቡን ስለለወጠ ራስ አሉላ ተናደደ። ለምዕራቦቹ ለያቀቸውና ለያንዳንዳቸው ጠባቂ አደረገባቸው። ማግ ቸውን ካልሲም እንዲያመልጥ አደረጋቸው። ራስ አሉላ ጣሊያኖች እየተሰደቡ በሚገኘው እንዲገኑተቱና ምግባም እንዲደሰጣቸው አዘዘ። በዚሁ ጊዜ ከየአቅጣጫው ብዙ ጦር ወደ ጊንዳዕ መሰብሰብ ጀመረ። ከምጽዋም በቅርብ ጊዜ ውስጥ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀል ግጭት እንደሚኖር የሚሉ ዜናዎች ተሰራጩ። በተሰፋይ ለተላከው ደብዳቤም ጀነራሉ ሀሳቡን ግልጽ አደረገ። ጃንዋሪ 20/1887 ዓ.ም የኢጣሊያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለመሩ ጥና አሻ ራስ አሉላ በአበረቶቹ ላይ አንድ ጉዳት ቢያደርስባቸው የሚከተለው እርምጃ ከባድ እንደሚሆን ለራስ አሉላ እንዲነገረው፤ ተጨማሪ ኃይልም የሚላክለት መሆኑን ግረጋገጡ ለጀነራል ጄኔ ይደርሰዋል። ጃንዋሪ 22/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ጥና አሻ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲጽፍ ከራስ አሉላ ጋር ውግረቱ እንደቀጠለ ነው። ከራስ አሉላ በጣም ኃይለኛ ደብዳቤ ደርሶኛል። የማስፈራሪያ ቃል ግን የለውም።

ራስ አሉላና ወታደሮቹ ሊያጠቁን እየመጡብን ናቸው፤ ምክንያቱም ንጉሡ ከእኛ ጋር መቆራረጥ አይፈልግም። አስረኞቹ በእሱ እንደታሰሩ ናቸው። ራስ አሉላ ግን እንደቆተው የሚፈጽማቸው አይመስልም። እስረኞችን ለማስለቀቅ ራስ አሉላ ፈቃደኛ ካልሆነ በጦር ኃይል ማስፈራራት እንድንችል ወታደርና መሣሪያ ተጨማሪ እንዲላክልን ያስፈልጋል። በወቅቱ ከምጽዋ ብዙ ቴሌግራሞች እዚያ መቃረቡን የሚገልፁ ወደ ሮማ ደርሰው ስለነበረ ጃንዋሪ 24/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኢጣሊያ ፓርላማ ተገኝቶ ስለሁኔታው እንዲያብራራ ጥያቄ ቀርቦለት ሚዛን የጉደለበት የነተተ ቃል «በአገራችን የምንረግጣቸው አራት ዘራፊዎች (እኛን የሚይዙ) ናቸው» ብሎ መልስ በመስጠቱ ሲጠቁበ የሚኖሩ ቃላቶች ሆነው በታሪክ ተመዝግቧል።[2]

1. Carlo Zaghi:Ibd p.25

2. Carlo Zaghi: Ibd p. 126



አምልኮቱ ዓንመላ አምልኮቱ ርብቶ አይመጣቸውም ነበር። የካረብ በረሀ አቋርጣ ዘላ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ደርሳ ርብቶ ላይ ዓንመላ ላይ የምትገኘው ዝናብን ተከትሎ ከደጋው ክፍል ሀገር እየወረደ የሚያርሰው ገበሬ እብቶ ዘመናት ለእፋማን ቅርስና እንበር፤ ከኢጣሊያ የበለጠ ኃያላን የበሉ የምጽዋ ገበሮች ግደበር፤ የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ነፃነት በመሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ምልክት ሆኖ የኖረው፤ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች እንዴት ሊደፍሩት ይቻ ለሚለው ጥያቄ መልሱ እኛ ራሳችን መርተን ስለሰጠናቸው ነው፤ የሚገርመው ግን እሁንም ከስህተታችን ባለመማራችን ነው። በአጠቃላይ የእርስ በርስ ጦርነት እንጂ ብዙዎቹን ጣሊያኖች ጦርነት ገጥመው ያሸነፉበት ወቅት አልነበረም። ይሄም የሚያሳፍረንና የሚያሳዝነን መሆን ይገባናል። ከሀገራችን አልፈን ወደ ሶማሊያ ወደ ሊቢያ ሄደን ለጣሊያኖች ዝናና ክብር ደማችንን አፍሰናል።

በተለይ የኤርትራና የሶማሊያ ተወላጆች በ1928 ዓ.ም (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) የኢጣሊያ ወረራ በሰሜንና ደቡብ ጦር ግንባር ከጣሊያኖች ጉን በግንባር ቀደም ከመሰለፍ አልፎ በደቡብ ጦር ግንባርም ኤርትራውያን ተሰልፈው ተዋግተዋል፤ ሶማሊዎች ግን ከደቡብ ጦር ግንባር በቀር በሰሜን ጦር ግንባር አልተሰለፉም። ወደ ሊቢያም አልተላኩም። በዚህ ብቻ አላበቃም ከዚያን በኋላ በኤርትራ ለሰላሳ (30) ዓመታት የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት በተዘዋዋሪ መንገድ ጣሊያኖች ያስጨፈጨፉን ጦርነት ነው ለማለት ይቻላል። ጣሊያኖች ናቸው ኤርትራውያን ኢትዮጵያን እንዲጠሉዋት እንዲጠሏት መርዝም የሆነ ከደማቸው የማይለቅ ትምህርትና ሥልጠና ነው የሰጡዋቸው። ኢጣሊያ ኤርትራ የምትባል ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ቅኝ ግዛት ይህ ሁሉ በመንደሮቻቸ ላይ ጥላቻና ደም መፋሰስ ሊደርስ አይችልም ነበር። የኤርትራ ችግርና የኤርትራ ጥያቄ የሚለውም ባልተፈጠረ ነበር። የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች እየተባለ ለሁለት እንከፈልም ነበር። ኢትዮጵያን የወረረች ኢጣሊያ ብቻ አልነበረችም። በወቅቱ ከባድም ኃያላን መንግሥታት አንዱ የነበረው ግብፅ የእቴጌን ቁርጥ መንግሥት እንኳን የኢትዮጵያን የባሕር ጠረፎች በቁጥጥሩ አድርጎ በነበረ ጊዜ ወደ መሀል ደጋይቱ ሀገራችን ለመግባት ተደጋጋሚ ያደረገው ሙከራ ሁሉ እርስ በርሳችን ለማጣላት ስለአቻለ አራት መቶ ዓመት በወረራቸችን ቢቆይም ዓላማው አልተሳካለትም። ጎበዝም በተለይ ባለፈው ምዕት ዘመን በኤርትራ፤ በትግራይ፤ በጐንደር፤ በአውሳ መሀል ኢትዮጵያ ውስጥ ዘልቃ ገብታ ሀገራችንን በቁጥጥር ሥር አድርጋ የአባይና የባሕር ጣና ባለቤት ለመሆን የነበራት ምኞት በተመሳሳይ ሁኔታ አልተሳካለትም።

ኢጣሊያ ምጽዋን ወርራ በምትይዝበት ጊዜ ምን ነበረ ዓላማዋ ለሚለው ጥያቄ ኢትዮጵያን ለመያዝ ግረማመጃ ለታደርጋት የቅርብና የራት ዓላማ ነበራት፤ ወይንም የእንግሊዝ መንግሥት ኢጣሊያን ገፋፍቶ ምጽዋንና የቀይ ባሕር ጠረፎችን ከግብጽ አስለቅቆ ወርራ እንድትይዝ ሲያደርግ ኢትዮጵያ እንድትይዝ የመገፋፋት ዓላማ ነበራት ወይ የሚለው ጥያቄ መልሱ ሁለቱ መንግሥታት እንደዚሁ ያለ ዓላማ እንዳልነበራቸው እንረዳለን። በእንግሊዝ መንግሥትና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል የተገፈ ውል ባይኖርም ከምጽዋ መያዝ በኋላ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሲደረጉ በነበሩ መደበኛ የዲፕሎማቲክ ደብዳቤ ልውውጦች

ከጦርነቱ በኋላ ተጠይቆ ሲመልስም «ከጥቂት ቀን በፊት የተናገርኳቸው ቃላቶች ትክክል አልሆኑም። ስለዚህ አሁን ስህተት ተናግርኩ ብዬ ማመን ችግር የለብኝም» ብሏል። ጀንዋሪ 26/1887 ዓ.ም የዶጋሊ ጦርነት ተደረገ። በኢትዮጵያ በኩል ስንት ወታደር እንደ ተካፈለ አይታወቅም። በኢጣሊያ በኩል ግን 540 (አምስት መቶ አርባ ወታደሮችና) ሃምሣ ባሺ ብዙክ ባጠቃላይ 590 በጦርነቱ ተካፋይ ሆነው ነበር[1]። «ባሺቡዙክ» ማለት ከሀገሩ ሕዝብ በጉብጾች ተመልምለው የነበሩ ወታደሮች ወደ ጣሊያኖች የተላለፉ ናቸው። ከአምሥት መቶ ውስጥ አራት መቶ አሥራ ሶስት በግዳው ሲሞቱ የቀሩት በሙሉ ቆስለው የሞቱ መስኗቸው ኢትዮጵያውያን የተዋቸው ነበሩ። ከእነሱም ውስጥ በደረሰባቸው ከባድ ቁስል ጦር ሰፈራቸው ሲደርሱ የሞቱ ነበሩ። ከባሺቡዙክ ግን ማንም ሰው አልቆሰለም፣ አልሞተም፣ አለተዋጉም ማለት ነው። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ጀንዋሪ 25/1887 ዓ.ም በራስ አሉላ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦርና በሻለቃ ቦሬቲ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር መካከል የሰሐቲ ጦርነት ተካሂዷል። በሰሐቲ የተዋጋው የኢጣሊያ ጦር ዶጋሊ ከተዋጋው በሰው ኃይል አነስተኛ ነበረ። ነገር ግን በሶስት መቶ ባሺቡዙክ የተጠናከረ ነበር። በኢጣሊያ የደረሰ ጉዳት ቀላል ነበር።

አንድ መቶ አለቃ በደረሰበት የመቁሰል አደጋ ሞተ። ሁለት የኢጣሊያን ወታደሮች ቆሰሉ። እንደዚሁም ሶስት ባሺቡዙክ ሞቱ። አንድ ቆስሏል። በሰሐቲ ኢጣሊያኖች እንደ ዶጋሊ ዕድል አላጋጠማቸውም ስሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያ ጦር ጠንካራ ተቃውሞ ለመጀመሪያ ስላጋጠመው በሙሉ ኃይል ላያጠቃ ወደ ኋላ አፈግፍጐ ወደ ዶጋሊ አምርቶ በሙሉ ኃይሉ አጥቅቶ የነበረውን የኢጣሊያ ጦር በሙሉ ሊደመስስ ችሏል። የዶጋሊ ጦርነት የምናስታውሰው በጥቂት ሰዓቶች ብዙ የኢጣሊያ ወታደሮች የተገደሉበት የራስ አሉላና የኢትዮጵያውያን ጀግንነት በታሪክ የተመዘገበበት በመሆኑ ብቻ አይደለም። የሰሐቲና የዶጋሊ ጦርነቶች በዓይነ ሕሊናችን በጥልቀት ሊያሳስቡን የሚገባን ትምህርት ሊሰጡን የሚችሉ ሁኔታዎች ገና በእነዚህ ሁለት የመጀመሪያዎቹ ጦርነቶች ተከስቷል። የዶጋሊ ጦርነት ለዘለዓለም ሲያኮራን የሚኖር የሚገባ በኢትዮጵያውያንና በኢጣሊያኖች መካከል ብቻ የተካሄደ ጦርነት ሲሆን የሰሐቲ ጦርነትና ሌሎችም ከሱ በኋላ እስከ 1933 ዓ.ም (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ከኢጣሊያኖች ጋር ያካሄድናቸው ጦርነቶች ሁሉ ግን ጣሊያኖች ብቻቸው የገጠሙን ጊዜ የለም። ግማሾቻችንን እየመለመሉ በገንዘብ እያታለሉ በወንድሞቻችን ላይ ዘምተን ሀገራችንን ወግተን ደማችንን አፍሰስን ወገኖቻችንን ገድለን የሀገራችን መሬትና ሕዝቦቿን በጣሊያኖች በባርነት እንዲገዙ እናስረክብ ነበር። በመሀል ሀገር እንዲሁም በጠረፍ የእኛ ትብብር ባያገኝ ኖሮ ጣሊያን በምጽዋ ገብቶ በጦርነት ለመግጠም ባልደፈረን ነበር፣ የአርበርቡዕ ገደላ ገደሎችና የዓሊ ጌደ፣ የሰያሕ ገደ፣ የሐዳስ ሸለቆዎች ዘልቀው ለመግባት ባልቻሉ ነበር። የጎርሶይ፣ የመተተን፣ የአባ ሐኒ ተራራዎች በምንም ታአምር ለመውጣት ባልቻሉ ነበር።

1. Carlo Zaghi: Ibd p. 128



እንደምንረዳው ኢጣሊያ ግብጽ ከነበራት ይዞታዎች ብቻ እንድትወሰን የሚያስገነዝቡ ነበሩ። የእንግሊዝ መንግሥት የተነሳበት ዓላማ ግቡን ከመታለት በኋላ ወዲያውኑ ራሱን ለማገለል መርጧል። የኢጣሊያ መንግሥት በእንግሊዝ መንግሥት ግፊት በመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የቅኝ ገዢነት ለመያዝ ከታላላቆቹ መንግሥታት ቁጥር በመግባቱ ተደስቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀስ በቀስ በተጠናከረ መልክ ወረራውን ቀጥሎ ፍልሚያው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ብቻ ተወስኖ በ1928 ዓ.ም መላውን ኢትዮጵያ በመያዝ መደምደሚያ መስኗት ነበር። ይህ የተባለው ፍልሚያ በጦር ሜዳ ብቻ ሣይሆን በዲፕሎማሲም ጭምር ስለሆነ ሁኔታውን ለማብራራት አንዳንድ የታሪክ መዝገቦች ማገላበጥ ያስፈልጋል። ምጽዋ በወረራ እንደተያዘች ከአንድ ወር ተኩል በኋላ የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ምጽዋ ዘምቶ በነበረው ጦር ማይዣ ለተባለው በምጽዋ የኢጣሊያ መንግሥት ተጠሪ የኢትዮጵያና የግብጽ ወሰኖች በዝርዝር እንዲያስረዳው በጠየቀው መሠረት ሲኞር ማይዣ ማርች 19/1885 ዓ.ም በፃፈው ማብራሪያ ደብዳቤ እንደሚያስረዳው በምጽዋ አውራጃና በኢትዮጵያ ያለው ወሰን በአጭሩ በሚከተለው አኳኋን ገልጾታል።[1] «ስለ ወሰን ጉዳይ ግብጾችና ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት አመለካከት የላቸውም። ኢትዮጵያውያን ወሰናቸው እስከ ባሀር መሆኑን ራሷ ምጽዋም ወደ ባቸው መሆንዋን ሲያምኑ ግብጾችም ወሰናቸው እስከ ደጋ ሀገር ስር ይደርሳል ብለው ያምናሉ።

በተጨባጭ ግን ባለው ሁኔታ የጀንስቶን ካርታ በመመርኮዝ ሰሐቲ የግብጽ መንደር ለትሆን ዓይለት ግን የኢትዮጵያ መንደር ናት፣ ስለዚህ ወሰኑ መሆን ያለበት በሁለቱ መንደሮች መሀል ነው። ከምጽዋ እስከ ሰሐቲ የአራት ሰዓት የእግር መንገድ ነው። ከሰሐቲ እስከ ዓይለት ደግሞ የሌላ አራት ሰዓት የእግር መንገድ ነው። ስለዚህ ወሰኑ የሚገኘው ከምጽዋ የስድስት ሰዓት መንገድ ላይ ነው። ሞንኩሎ ከምጽዋ የአንድ ሰዓት መንገድ ነው። ሲኞር ኑካርዲ በምጽዋ ነዋሪ የኢጣሊያ ዜጋም ይህንኑ ሀቅ ነው ያረጋገጠልኝ። ማርኩፑሉ በይ የግብጽ ዜጋ የጉምሩክ ሠራተኛም እንግሊዛዊ አድሚራል ሒወት በኢትዮጵያ በእንግሊዝና በግብጽ መሐከል ስምምነት በተፈራረሙበት ጊዜ የዓይለት ጉዳይ በቃል ተነጋገረንበት የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋን በቃል የተስማማንበት ጉዳይ ነበር ብሎ አስረድቶኛል። አድሚራል ሒወት ዓድዋ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ስላደረገው ውይይት Blua Book Abyssainia 1884 page 3 በፃፈው መጽሀፍ እንደገለፀው ንጉሡ (አጼ ዮሐንስ) የግብጽ ወታደሮች የሞንኩሎ ለቀው በሙሉ ወጥተው እንደሆን ብለው ቢጠይቁኝ እነስተኛ ቁጥር ብቻ አሉ ብዬ መለስኩላቸቸው ብሎ መግለፁ ይህ ቦታ ለግብጾች የተፈቀደላቸው የመጨረሻ የወሰን ክልል መሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም በእሁኑ ሁኔታ ዛሬ ዓይለት የኢትዮጵያ ስለሆነች ከንጉሡ ጋር መቆራረጥ ካልተፈለገ ዓይለት ልንይዛት አንችልም። ከምጽዋ በስተደቡብ ከባህር እስከ ተራራዎች ያሉት የሻሆ ጐሣዎች ግብጽ በስም የእኔ ግዛት ናቸው ስትላቸው በተግባር ለኢትዮጵያ ግብር ስለሚከፍሉ የኢትዮጵያ ግዛት ናቸው።

1 Vico Mantagazza: Da Masawa a Saati p. XI

ሌላ ከኢጣሊያ መንግሥት ተልኮ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ለመነጋገር ሬላት አንቶኔሊ ደርሶ ወደ አገሩ ጉዞውን ለመቀጠል ከራስ አሉላ ፈቃድ ይጠብቅ የነበረ ፌራሪ የተባለው መልእክተኛ አንቶኔሊ እንደደረሰ ከአንቶኔሊ (ትግሬ) [1] ብሎ ማርች 23/1888 ዓ.ም ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ደብዳቤ ኢጣሊያ ምጽዋን መያዝዋ በመቃወም አጼ ዮሐንስ ሚደሰሙ እንደት ሊሆን እንደቻለ ብሎ ጥያቄዎች ራስ አሉላ አትርበውለት በሁላን በኩል የሚሀል እስከኞች ለመከላከል መሆኑን ስለገለፁላቸው ቁጣቸው ሊበርድ ችሏል። ከዚህ በኋላ ስለተጠየቀው ሊቸር ፌራሪ አጼ ዮሐንስ ዘንድ በኢጣሊያ መንግሥት ስም ለማደረገው ተልእኮ የኢትዮጵያ ወዳጅ የነበ ረችው ሩሲያ በሊንት ፒተርስበርግ ይወጣ የነበረው ጋዜጣ[2] ጁን 25/1885 ከአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የዜና ወኪል አግኝቶ ያወጣው እትመ እቤ ዮሐንስ ለፌራሪ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በወዳጅነት እንዲኖሩ ከተፈለገ፤ 1ኛ. ከምጽዋ በስተቀር ማንኛውም የተያዘ ግዛት ወደበኋ እንዲለቀቁ 2ኛ. የኢጣሊያ ወታደሮች የኢትዮጵያ መሬቶች ከሆኑ ከአርቂቆ፣ ምንኩሉና አሬቱሊ እንዲለቁ 3ኛ. ኢጣሊያ ከሸዋ ንጉሥ ጋር ያላት ግንኙነት አቋርጣ ሚሲዮናውያን እንዳትልክለት 4ኛ. ኢጣሊያ የንግድ ውል ከኢትዮጵያ ጋር እንድታደርግ በእንዝሩም ንጉሡ ምፅዋ የኢጣሊያ ይዞታ መሆንዋን ያውቁላታል የሚል ነበር።

ስለ ሰሐቲ ጉዳይ በኢጣሊያ ወታደሮች መያዝ በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ከራስ አሉላም ሆነ ከኢጣሊያ ባለሥልጣኖች ደብዳቤ ተለዋውጠውበት ስለነበረ የኢጣሊያ የጦር ሚኒስትር ለሐቲ ኖቬምበር[3] 12/1886 ዓ.ም ለኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ደብዳቤ እንደ ሚከተለው ያብራራል። «በወታደራዊ ጥቅም ስንመለከተው ሰሐቲን ይዘን መቆየት የሚደገፍ አይመስለኝም። ምክንያቱም ራቅ ያለ ስለሆነ ለእኛ ድክመት ሊያመጣብን ይችላል። በሚጢጢክ ይዘን መቆየት ግን እደግፋለሁ። ጠላት አደጋ ለመጣል ቢሞክር አንመልሰው፣ እንግርከው፣ ወይንም እንደመሰለው እንችላለን። ይህ ከተከሰተ ደግሞ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በእስቶቫይ መንቀሳቀስ እንችላለን። ነገር ግን ሰሐቲ በኢጣሊያ ወታደሮች እንይዛትም እንችላለን። ይህ ከሆነ ግን ምሽግና የወታደር ሰፈር መሥራት ያስፈልገናል። ምክንያቱም ድንገት ጠላት አደጋ ቢጥልብን ዘምንኩሉ ወይንም ከምፅዋ እርዳታ እስኪመጣልናቸው መከላከል እንዲችሉ ማለት ነው። ነገር ግን የሁለተኛው የሰሐቲ መያዝ እግራቸው ከራስ አሉላ ጋር የሚያቆያይውን ስለሆነ ብናስወግድ ይመረጣል። ስለዚህ የመጀመሪያ ዘዴ ብንጠቀም የተሻለ ይመስለኛል» ብሎ ሃሳብ አቅርቦ ነበር። በሁኔታው ሁለቱ ሚኒስትሮች ስለተስማሙበት ለጦር አዛዥ በተግባር እንዲያውለው ትእዛዝ ይተላለፍለታል። በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ደብዳቤ የሮማና ሰሐቲ በወታደርና በመድፍ ያጠነከርን ስለሆነ ምንም የሚያስፈራ ነገር እንደሌለ ያረጋግጣል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XVII

2 . Vico Mantegazza: Ibd p. XXIII

3. Vico Mantegazza; Ibd p. XXI



ጀንዋሪ 18/1887 እንደገና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በፃፈው ደብዳቤ የወታደሮችን በሮማና በሰሐቲ መስመር ራስ አሉላ የደነገጠ መሆኑን ገልጾ ከራስ አሉላ ጋር ይገኝ የነበረው ሚሲዮናዊ ከፒያና ማሸዋ የተባሉ ጣሊያኖች ራስ አሉላ እንዳስራቸውና ጣሊያኖች ከተባሉ በታዎች ካልወጡም እንደሚገድላቸው የዛተ መሆኑን ገልጾ፤ ነገር ግን ሊያስፈራራን ለመፈለግ ብቻ እንደሆነ አክሎ አስታውቋል።[1]

ጀንዋሪ 25 የሰሐቲ ጦርነት ተካሄደ። ራስ አሉላ ጣሊያኖች ሰላየሉበት ወደኋላ አፈገፈገ። ወደ ድንገት ተመልሶ እስረኞች በሙሉ እንገታቸውን እንዲቆረጡ አስቦ ነበር። ነገር ግን ፈረንሳዊው ቄስ አባ-ኩልቦ[2] ፍታት ሊሰጣቸው ከሰፈሩ ከአኩሩር መጥቶ ስለነበረ ራስ አሉላን ለምና አስጣላቸው። ቄሱ አባ ኩልቦ ቄስ ብቻ አልነበረም ምሁርም ነበረ። የኢትዮጵያ ሐቀኛ ወዳጅ ነበረ። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ጠቃሚ መጽሀፍ ፅፏል። ጣሊያን ሀገራችን ስትገዛ የማይፈልጉ ተብለው ከሀገር ሲባረሩ በምትካቸው የመጡ የኢጣሊያ ዜጎች ሚሲዮናውያን ግን ከመንግሥታቸው ጋራ ከማደር በቀር በትምህርት ያልበሉ ነበሩ። ምሁራን ኢትዮጵያውያን ቄሶች ለማፍራት ፍላጎትም ችሎታም ያልነበራቸው ነበሩ። ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በ1891[3] በደረሰው መጽሀፍ በኤርትራ ስለነበሩ ሶስት ፈረንሳዊያን ሚሲዮናውያን ላዛሪስት አስተያየት ሰጥቷል። 1ኛ. አቡነ ክፍሌ የመባለው ኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ጳጳስ ሥጋ ሥርዓት የተሞላበት አነጋገር አላቸው ብለው አወድሷቸዋል። 2ኛ. አባ ኩልቦ በመጀመሪያ ጊዜ ጣሊያንን ይቃወም ስለነበረ ከኢጣሊያ ባለሥልጣኖች እንግላ ደርሶበት ነበር፤ አሁን ግለሰቡ አክሩር ነው የሚኖረው፤ እኛው ሔጂ አላገኘሁትም፤ አላየሁትም፤ ስለሱ ምንም ለመናገር አልችልም ብሎ ነበር። 3ኛ. አባ ፒካር የያ አምሥት ዓመት በከረን ዘኖራል። ከሱ ጋር ረጅም ውይይት አድርጊያለሁ። ለማቀርብለት ክርክር ሁሉ በመጀመሪያ ጊዜ ቄስ በመሆን መልስ ሰጠኝ። በኋላ ግን የፖለቲካ ሰው በመሆን የሃይማኖት ሰውነቱ የምቃወም መሆኔን ስለገለፅኩለት ለአንድ ኢጣሊያዊ ዜጋ የፓርላማ አባል ስለሕሊና ነፃነትና ስለ ሃይማኖት ነፃነት ማስተማሩ የገረመው መሆኑን ገለፀልኝ፤ እኔም እንዳ ሳመንኝ አልከደኝም፤ ስለዚህ ይህ ሰው ካወቅኋቸው ሁሉ ከፍተኛ ብቃት ያለው ተናጋሪ ጥል ቅና ቅጽበታዊ መልሶች የሚሰጥ ሰው ሆኖ አገኘሁት ብሎ አስተያየቱን ሰጥቷል። የሁለቱ ሰዎች ማርቲኒና ፒካር አለመግባባት ሲገመገም እውነትም የሚገርም ነው። ሃያ አምሥት ዓመት በአፍሪካ የኖረ አንድ ተራ ቄስ ለአንድ የፓርላማ አባል ስለነፃነት ማስተማር ሲችል ሁለቱ የተቃራኒ የሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ላቲናውያን የሚባሉ ናቸው። እንደደገሙ ከሆነ ኢጣሊያም እንደ ፈረንሳይ በፓርላማና በዲሞክራሲ የምትመራ ሀገር ነበረች። ነገር ግን የፈረንሳይ ዲሞክራሲ ከሀገሩ ሕዝብ የተዋሃደ ስር የሰደደ ስለሆነ ለአንድ ኢጣሊያዊ የፓርላማ አባል ለአንድ የኢጣሊያ ሚኒስትርም ስለ ዲሞክራሲና ነፃነት አንድ ፈረንሳዊ ተራ ሰው ለማስተማር ይችላል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XLI

2 Carlo Zaghi Ibd p. 127

3 F: Martini: Nell' Africa Italiana p.230

የማርቲኒ ፍላጐት ፈረንሣውያን ሚሲዮናውያን ከኤርትራ እንዲባረሩ ከፒካር ፍንጭ ለማግኘት ነበረ። ለምሳሌ እንግሊዝ ይሏቸው ከነበሩ ቅኝ ግዛቶች ዜጐቻቸው ያልሆኑ ሚሲዮናውያን የሚያባርር ቢሆኑ ኖሮ እንዲሁም ፈረንሣዮች ዜጐቻቸው ያልሆነ እሚያባርሩ ቢሆኑ ኖሮ ዛሬ የሚታየው የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ከምላ ጉደል በእኩል ደረጃ መስፋፋት አይታይም ነበር። እነዚህ ሁለት በዲሞክራሲ የሚያምኑ ሀገሮች ግን እንዲህ ያለ እርምጃ አልወሰዱም፤ ኢጣሊያ ብቻ ናት እንዲህ ያለ ግፍ ለመፈፀም የምትችለው። ጉዳዩ የሶስት ፈረንሣውያን ሚሲዮናውያን ጉዳይ አይደለም። ጉዳዩ ዘረኝነት ነው። የዲሞክራሲና ፀረ ዲሞክራሲ ትራኔ ነው። ዛሬም ቢሆን ጣሊያኖች ዲሞክራሲ የተቀበሉት ስለተሸነፉ ሣይ ወዱ በግድ ነው። ሁለቱ አገሮች ስለነፃነትና ዴሞክራሲ ያሏቸው ርእዮተ ዓለም ዲያሜት ራሊዊ ተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብ ነው። ሁለት የተለያዩ ሕዝቦች መሆናቸውን ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ፈርዲናንዶ ማርቲኒ አክራሪ ዘረኛ ነኝ ባይ ነበረ፤ የነጭ ዘር ነኝ ብሎ መቶ ጊዜ ቢያወራ አሪያን ዘር እንዳልሆነ የታወቀ ነው። እንዲሁም ሃምሣ ከመቶ የሚያህሉ ጣሊያኖች ነጭ ዘር አርያን አይደሉም። አባ ፒካር ግን እጣርቼ ዘሩን ባላውቅም ንፁህ ነጭ ዘር አርያን ሣይሆን እንደማይቀር ይታመናል። ነገር ግን እንደ ሀገሩ ሕዝብና መንግሥት በዘረኝነት ስለማያምን ለአንድ ኢጣሊያዊ የፓርላማ አባል ስለ ዲሞክራሲ ትምህርት ሊሰጥ ችሏል። ጀንዋሪ 26/1887ዓ.ም. የዶጋሊ ጦርነት የተካሄደበት ዕለት ነበር። ከጦርነቱ በፊት የተፈፀሙ ሁኔታዎች እላይ እንደገለፅኩ ሆኖ ራስ አሉላ ሣሊምቤኒ እጁን ታስሮ በዓይነ ቁራኛ እየተጠበቀ በአንድ ተራራ ሆኖ የጦርነቱ ተመልካች እንዲሆን አድርገውት ነበር።[1] ራስ አሉላ ስለ ጦርነቱ ውጤት ለአጼ ዮሐንስ ሲጽፍ አምስት ሺህ የኢ ጣሊያ ወታደሮች እና[2] ስድስት ጀነራሎች ተገድለዋል ብሎ ነበር የነገረው። ከአጼ ዮሐንስ በፊት ግን የኢትዮጵያ ድል ዜና የሰማ ንጉሥ ምንሊክ ነበረ። ለሱ ግን (1500) አንድ ሺህ አምሥት መቶ[3] ጣሊያኖች ተገድለዋል ብሎ ነበረ ያበሰረው። ከራሱ ወገን ግን (200) ሁለት መቶ ብቻ እንደሞቱበት የተጋነነ የሣሊምቤኒ ግምት ግን 2000 ኢትዮጵያዊያን በዶጋሊና ሰሐቲ ጦር ነቶች እንደሞቱና እንደቆሰሉ ብሎ ነበረ። ቆይቶ ግን ከአጼ ዮሐንስ ለምኒልክ የተጻፈ ትክክለኛው ለማወቅ ተችሏል።[4] አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ ጣሊያኖች ወደ ሀገራቸው ሪፖርት ሲያስተላልፉ በዶጋሊ ጦርነት የተገኘው ድል ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሸዋ ሰዎችም ጭምር ከልክ በላይ ደስታቸውን እየገለፁ ናቸው ብለዋል።

በእንጦጦ ይገኝ የነበረ ትራቬርሲ[5] የዶጋሊ ድል በእንጦጦ ሲሰማ የነበረው ሁኔታ ለአንድ ጓደኛው በፃፈው ደብዳቤ ብቿከተለው ዓይነት ያብራራዋል።

1. Carlo Zaghi: ibd p.129
2. Vico Mantegazza: ibd p.74
3. Carlo Zaghi: ibd p.145
4. Carlo Zaghi: ibd p.144
5. Carlo Zaghi: ibd p.145



እንደ አንድ መብረቅ ነው ጭንቅላቱ መሀል የመታው፤ ብዙ ድካሞችና ገንዘቦች የፈሰሱባቸው ብዙ አትዶች መክሸፋቸው ብቻ ሣይሆን ሀገሬ በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ገንዘብና ብዙ የሰው ሕይወት ሊጠፋበት የሚችል የጦርነት አዘቅት እንደወደቀች ይታየኛል። አቢሲኒያን 20–30 ሺህ ወታደር አስልፎ ማሸነፍ አይቻልም። ንጉሠ ነገሥቱ (300,000) ሶስት መቶ ሺህ ገደማ ወታደሮች ማሰለፍ የሚችሉ መሆናቸውን ስናስብ የኢጣሊያ ሠራዊት ከተለው ቁጥር (20,000) ሃያ ሺህ እጥፍ ማሰለፍ ይኖርብናል (40–60 ሺህ ወታደር)። የራስ አሉላ ዜና በደረሰበት ዕለት የሐበሾች ደስታ ሸዋዎቹም ጭምር እስከ ማበድ ደርሶ ነበር ንጉሡ ብቻ (ንጉሥ ምኒልክ) ይመስለኛል አዝነው ነበር። ምክንያቱም በጣም ከፍት የሆነ አንጎል ያላቸው ሰው ስለሆኑ እሳቸው ብቻ ናቸው የሁኔታው ከባድነት ሊገምቱ የሚችሉ።እርስዎም ሊገባዎት እንደሚችል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተገኘው ድል ከሀረር ጋራ በማያያዝ አሁንም በዶጋሊ በተገኘው የራስ አሉላ ድል በእነዚህ «ኔግሮች» ጭንቅላት የማይሸነፉ መሆናቸውን የሚል እምነት ሊያድርባቸው ችሏል።

እኛ እርምጃ በምንወስድበት ጊዜ ግን ይህ ሁሉ ደስታቸው ወደ·ት እንደሚገፋፋቸው አላውቅም። እዚህ እኛ ሁላችን ደህና ነን። እኔ እንደሚመስለኝ የሚያሰጋን እደጋም የለም፤ ነገር ግን ከዛሬ ነገ ከሀገር እንድንወጣ ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ይመጣል ብዬ እየጠበቅሁ ነው በማለት ጽፈዋል። እዚህ ላይ ስለ ዶጋሊ ጦርነት ሲነሳ ማስታወስ የሚገባን አንድ ነገር አለ። የጠቡና የጦርነቱ መነሻ ጣሊያኖች በሰሀቲ ጦር ሰፈር ሠርተው ራስ አሉላ ለቀው እንዲሄዱ ደጋግመው ቢለምኗቸው እንለቅም በማለታቸው ነው። ጣሊያኖች በዶጋሊ ጦር ሰፈር አልነበራቸውም! ራስ አሉላ ግን ከጊንዳዕ ከመነሳቱ በፊት ለጣሊያኖች እስረኞች ከሰሀቲ እና ምንኩሉ መሀል ሄጄ እዋጋለሁ ብሞትም ግድ የለኝም ብሎ ሲነግራቸው እንድ ትንቢት ነበር የተናገራቸው። ጦርነቱ እንዲካሄድ በሁሉ ሰው ሲጠበቅ የነበረው በሰሀቲ ነው። እንደታሰበም ጀንዋሪ 25/1887 ዓ.ም. በሰሀቲ ጦርነት ተከፈተ። የራስ አሉላ ጦር ግን መጠነኛ ተቃውሞ ስለአጋጠመው አፈገፈገ።

በዚህ ጊዜ ጣሊያኖች እሸነፍን ብለው ተደሰቱ። የራስ አሉላ ጦር ግን ጦርነት ፈርቶ አልነበረም የሸሸው። የአንድ ትልቅ ጀነራል የጦርነት ስልት ነበር ያካሄደው። ጣሊያኖች ራሳቸው የዚሁ ዓይነት ስልት አድናቆታቸውን ገልፀዋል። የራስ አሉላ ጦር ወደኋላ እይደሰም ያፈገፈገ ወደ ፊት ወደ ምንኩሉ ነበር የገሰገሰው። ወደ ምንኩሉ በሚገሰግስበት ጊዜም ሰሀቲ የነበረው የኢጣሊያ ጦርም እንዳይንቀሳቀስ መንገድ ዘጋበት። ይህ በዚህ እንዳለ ባልታሰበ ሁኔታ ከምንኩሉ ለእርዳታ ወደ ሰሀቲ ይጓዝ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ጀንዋሪ 26/1887 ዓ.ም. ከጧቱ በ2:00 ሰዓት በዶጋሊ ተገናኙ። የራስ አሉላ ጦር በረቀቀ የጦር ስልቱ በመጠቀም ወዲያውኑ ተኩስ አልከፈተም። ወደ ሰሀቲ የሚወስደው መንገድ እስቀድሞ ተዘግቶ ነበር፤ አሁን በጐን ግራና ቀኝና ከምንኩሉ የሚያገናኘው መንገድ ከበባና መዝጋት ተያያዘው።

የራስ አሉላ ጦር ከበባ በሚያደርግበት ጊዜ ገገር ተራራዎችን በቁጥጥሩ እ ውሎ ነበረ። የኢጣሊያ ጦር ሁኔታውን ከተረዳ በኋላ ወደ አንድ ኮረብታ ተሰበሰበ። የተኩስ ልውውጥ

እየቀጠለ ነበር፡ ዋናው ጦርነት የተካሄደው ግን ከበባው ካለቀ በኋላ ነው። የቆየው ለጥቂት ደቂቃ ብቻ ነበር። ከቀኑ 6:00 ሰዓት ጦርነቱ አብቅቶ ነበር። ጣሊያኖች ከሞንኩሎ ለእርዳታ ለሄደው ጦር (ማለት በዶጋሊ ያለቀው) ሌላ ጦር ለእርዳታ ልከው ነበር።

የራስ አሉላ ጦርም ድል አደረኩ ብሎ አልተቀመጠም። ምናልባት በሞንኩሎ ላይም አደጋ ለመጣል ወይም ለሰላ ብቻ ፈጣን ፈረሰኞች ወደ ሞንኩሎ ሲያመራ ለእርዳታ ከሚመጣው የኢጣሊያ ጦር ተገናኙ። ጣሊያኖች ጦርነት ለመግጠም የመጡባቸው መስሏቸው ቦታ ቦታቸውን ያዙ። የኢትዮጵያ ፈረሰኞች ግን በመጡበት አኳኋን ተመለሱ።



Ras Alula.



Tommaso De-Cristoforis

1. ራስ አሉላ 2. ኮሎኔል ዲክሪስቶፎሪስ በዶጋሊ ጦር ግዳ የተገደለ 3. ጀኔራል ጄኔ የጠሚች የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በዶጋሊ ሽንፈት ምክንያት ስራውን እንዲለቅ የተደረገ።



ጀኔራል ጄኔ በምፅዋና አካባቢው ሰፍሮ የነበረ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በዶጋሊ ጦርነት ጣሊያኖች ከደረሰባቸው ሽንፈት በኋላ ከስልጣናቸው ወርዶ ተወቅሶ ወደ ሀገሩ የተመለሰ በሙትኩ የተሾመ ጀኔራል ሳሌታ በምፅዋ የመጀመሪያ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በቅድሚያ ያከናወነው ሥራ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ ሀገሮች መሆናቸውን አዋጅ በማውጣት ነው።



Generale Gené



# 2. ስለ ዶጋሊ ጦርነት የሻምበል ታንቱሪ ሪፖርት

የውጊያው እርዳታ የተላከው የኢጣሊያ ጦር ይመራ የነበረው ሻምበል ታንቱሪ [illegible] ነበር። እሱም ሀሳቡን የሌሉ መሆናቸውንና መንገድ ክፍት መሆኑን ከአረጋገጠ [illegible] ጉዞውን ቀጠለ። ስለሁኔታው ተልእኮ ራሱ የጻፈው ሪፖርት በሚከተለው አኳኋን [illegible]። «ጥቂት[1] ጊዜ በኋላ አንድ ባዶ ግዛን ጉድጓድ የነበረበት አየሁ፤ ፍተሻ ያረጉ [illegible] የሙት ወታደር ነው። አስተርጓሚው ሁለት የአካባቢ ሰዎችን ጠይቆ የእኛ ጦር በሙሉ እንዳለቀና አውንም ኢትዮጵያውያን ብዙ እንደሆኑ ቦታቸውን እንደያዙ መሆናቸውን ነገሩኝ። እኔ ግን የሚጋጋ መሰለኝ፤ ጉዞውን ቀጠልኩ፤ አስተርጓሚው በፍርሀት [illegible] ወታደሮች [illegible] እንደደረሱ ፊት እየሄዱ የሚፈትሹ የነበሩ ወታደሮች የሀበሻ ፈረሰኞች እየገቡ ነገሩኝ። ቦታ ቦታችንን ያዝን። ሶስት ወታደሮች የኢትዮጵያ ፈረሰኞች ወደ ሄዱበት እንዲከታተሏቸው ላክሁ። በዚሁ ጊዜ አስተርጓሚውና ባሺቡዙኮች ጠፉ። የላኳቸው ሶስት ወታደሮች ወደ ሰሁቲ በፍጥነት የሚጓዙ ሶስት አራት የሀበሻ ፈረሰኞች ብቻ እያዩ ተመልሰው ነገሩኝ። እርግጠኛ ለመሆን የመቶ አለቃ ማንቶሪ ከጥቂት ወታደሮች ጋር መንገዱን እንዲፈትሽ ላክሁት። እሱም ተመልሶ ጠላት እንደሌለ፣ የሞቱ ግመልና የጎመል መጫኛ፣ የጥይት ባዶ ሣጥኖች፣ የሥጋ ቁርቁሮች እየሁ ብሎ ተመልሶ ነገረኝ። በቦታው ደጋፍ የነበሩ ሁለት የማግመርታ አረቦችን ይዞ አስርኳቸው። እነሱም ሀበሾች የእኛን ወታደሮች ያጠቁበትን ቦታ አሳዩኝ። በቦታው ስንደርስ በቅርብ ጊዜ ከተቀበሩ ጥቂት የሀበሻ ሬሳ በስተቀር ሌላ ምንም ምልክት አልነበረም። አለፍ ብለን በአንድ ትንሽ ኮረብታ አንድ የቆሰለ የኢጣሊያ ወታደር አገኘሁኝ። እሱም የእኛ ወታደሮች በሙሉ እንደሞቱ ነገረኝ፣ ትንሽ አለፍ ብሎም ሬሳቸው እንደሚገኝ ነገረኝ። የዚሁ አሣዛኝ ዜናም አሳመንኩም። ወደ ነገረኝ ቦታ አመራሁ። በትንሿ ኮረብታ ስር ትልቁን አደጋ ተመለከትኩ። ሁሉም በመስመር ተጋድመው ነበር፤ አንደ አንድ ሰልፍ። የሪፖርቱ የመጨረሻ ቃላቶች አከራካሪ ሆነው [illegible]። በመጨረሻ የኢጣሊያ ወታደሮች ጥይት ስላለቀባቸው በሾንኬ ጨበጣ ውጊያ ነበረ የተዋጉት። በሾንኬ የተዋጉ ወታደሮች በመስመር ሆነው ተጋድመው ሞተው ሊገኙ አይችሉም። በተጨማሪ የዶጋሊ ጦርነት በሚከበርበት ጊዜ እነዚህ ቃላቶች እንዳይደጋገሙ ትዕዛዝ ተላልፎ ነበር።

# 3. ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ጀኔራል ጄኔ ያወጣው ፕሮግራም

ጥንቅሬ 29/1887 ዓ.ም. በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጄኔ ሁለት ሪፖርቶች ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጽፈል። በጽሁፉም የሰነዘረው ሀሳብ በሚከተሉ እንደሚከተለው ነው።

1 F.I.C.I Vol. 1 p.96-98

ስለ ሰሁቲና ዶጋሊ ጦርነቶች ከገለፀ በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት መቋረጡ ገልጦ ከ8–10 ሺህ ወታደሮች የጦር መርከቦችና ሌሎችም እንዲላኩለት ጠይቆ በጃንዋሪ 25 እና 26 በተደረጉ ጦርነቶች በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ፍልሚያ እንገኛለን በማለት ገልጦ አሁን ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው ብሏል። አፋጣኝ እርምጃ ወስደን በጦር ሜዳ ሽንፈታችንን መበቀል ነው። ወታደራዊ ንቅናቄዎች በምናደርግበት ጊዜ በሚከተሉት ሁኔታዎች መታገዝ አለበት። 1ኛ) ሐብብ፣ ቤኒዐምር የመሳሰሉት ወዘተ...ከእኛ ጋር የሚስማሙ ጐሣዎች በእኛ እርዳታና መሪነት በሰሜን በኩል ወደ ኢትዮጵያ መገፋፋት፣ 2ኛ) የሱዳን ደርቡሾች በመረብ በኩል ወደ ዓድዋ በአዝማን ዴግግ አሥራ ሁለት ሺህ ተዋጊዎችም አሉ ስለሚባል ወደ ጐንደር መተማ እንዲያመሩ ማድረግ፣ 3ኛ) በራሱ በሐማሴንም በራስ አሉላ አገዛዝ ያልተደሰቱ ሰላሉ በግልፅ የማይታይ ግን ኃይል ያለው የእስላሞች ወገንም ከሀበሻ ጭቆና ለመላቀቅ ስለሚፈልግ ማደፋፈር። በዚሁ ሁኔታ በጕስና አሥመራን መያዝ እንችላለን። ወደ ከሰላና ካርቱምም የሚወስደው መንገድ አቋርጠን ኢትዮጵያን በእኛ ላይ እቅመ ቢስ ልናደርጋት እንችላለን። ምክንያቱም በሁሉም መንገድ እንዳየነው ከኢትዮጵያ ጋር በሠላም ለመኖር ወይንም ውሉች ማድረግ ጨርሶ የማይቻል ነው። በደጋ ኢትዮጵያ ይዞታችን ማረጋገጥ ከቻልን ተጽእኖ አለው። ጀኔራሉ ሌላ ደብዳቤም ጽፎ ነበር። ሚኒስትሩ ግን ሀሳቡን ውድቅ አድርገውበታል። አሥመራ ውስጥ ሰላዮች ናችሁ ተብለው አራት ጣሊያኖች ታስረው ይገኙ ነበር። ራስ አሉላ እነዚህ ጣሊያኖች እንዲለቀቁ አንዳንድ ከጣሊያኖች ጋር የሚተባበሩ ሰዎችን አሳልፈው እንዲሰጡት፣ አንድ ሺህ ጠመንጃዎች ወደ ራስ አሉላ እንዳይገቡ በጣሊያኖች ትእዛዝ የታገዱበት እንዲላኩለት ጠይቆ ነበር። በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል ጀኔ ለራስ አሉላ ጥያቄ አሟልቶ አንድ ሺህ ጠብመንጃዎችን መላኩ በሰማ ጊዜ ከኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሮቢላንት ማርች 18 ቀን 1887 ለጀኔራል ጀኔ ደብዳቤ ጽፎ አድራጐቱን ተቃውሞ ጀኔራል ጀኔ ከቦታው ተነስቶ በምትኩ የመጀመሪያ ጊዜ ኢጣሊያ ምፅዋን በወረረች ጊዜ የጦር አዛዥ የነበረው ጀኔራል ሣሌታ የተሾመ መሆኑን ይገልፁለታል።[1] የጠብመንጃዎች የሽፋን ምክንያት ሆነ እንጂ ለጀኔራሉ የስልጣን መውረድ ዋና ምክንያት ግን በዶጋሊ ጦርነት መሸነፍ ነው።

ይህም በዶጋሊ ጦርነት ምክንያት በኢጣሊያ መንግሥት ምን ያህል ውዝግብ ተፈጥሮ እንደነበረ ያስረዳል። የደብዳቤው ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው። «የጦር መሣሪያዎች ለራስ አሉላ መስጠትዎን ስሰማ በጣም ነው የደነገጥኩ። በተለይም ስለዚህ ጉዳይ ጥብቅ መመሪያ ተሰጥቶ ስለነበረ ነው። ሁኔታውን ለምኒስትሮች ም/ቤት መቅረብ ስለነበረበት መስሉም ስለታየኝ አቅርቤው የክቡርነትዎ አድራጐት በሙሉ ድምፅ የማይደገፍ መሆኑን አምኖበት ይኸውም ለእርስዎ እንዲነገርዎት ስለታዘዘ ይኸም በሚሆንበት ጊዜ እርስዎ አሁን ባሉበት ስልጣን ለመቆየት የሚታረን በመሆኑ ያስከተለው ውጤትም እርስዎ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረው እንዲሰሩ ስለተወሰነ በጦር ሚኒስትሩ አቅራቢነት ጀኔራል ሣሌታ በቦታዎ ተተክቶ እንዲሰራ ተወስኗል።»

1. Vico Mantegazza,ibd, p.49-50



# 4. ፈረንሣይ፣ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ

የሀገራችን የባህር ወደቦች ለቅኝ ግዛት መያዝ ይፈልጉ ከነበሩ ሀገሮች አንዷ ፈረንሣይ ናት። ስለዚህ ጉዳይ በፈረንሣይ የኢጣሊያ አምባሳደር ማርች 24/1887 ዓ.ም. ለሀገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የፃፈው ደብዳቤ በአጭሩ መጥቀስ ጠቃሚ ይመስላል።[1] በአንድ ግብዣ ላይ አምባሳደሩ የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አነጋግር ስለምፅዋ ወረራ የሰሁቲ የዶጋሊ ጦርነቶች ወዘተ... አንስተው ሲነጋገሩ ፈረንሣይና ኢትዮጵያ የወዳጅነት ውል ለማድረግ እቅድ እንደነበረ አምባሳደሩ ለሚኒስትሩ አስታውሰው ከውሉ ዋና ዋና ነጥቦች፣ 1ኛ) ዙላና አካባቢዋ የፈረንሣይና የኢትዮጵያ ጥምር አስተዳደር እንዲመሰረት፣ 2ኛ) ከኢትዮጵያ ወይንም ወደ ኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴ ከጉሙሩክ ነፃ እንዲሆን፣ 3ኛ) ፈረንሣይ ለኢትዮጵያ ከማንኛውም ሌላ ሀገር ወረራ ዋስትና እንድትሆናት የሚሉ ይገኙባቸው እንደነበረ ሲገልፁላቸው ሚኒስትሩም እቅዱ የቀየና በምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል የቀረበ መሆኑን ገልፀው፣ ነገር ግን የፈረንሣይ መንግሥት ዓላማ ስላልሆነ ቆንስሉ ከእንዲህ ያለ አድራጐት እንዲቆጠብ መመሪያ የተሰጠው መሆኑን ነገሩኝ፣ እኔም በበኩሌ ቆንስሉ ከፈረንሣይ ሚሲዮናውያን ተገፋፍቶ ሊሆን እንደሚችል ከገለጽኩላቸው በኋላ እሳቸውም የፈረንሣይ መንግሥት ለጊዜው ኢጣሊያ በምፅዋ መግባት እምና ተቀብሉታል፣ ምፅዋ በእንግሊዝ እጅ ከምትሆን በኢጣሊያ ቁጥጥር ብትሆን የፈረንሣይ መንግሥት ምርጫ መሆኑን አረጋግጠውልኛል ብሏል።

ብዙ ጊዜ እንደሚነገረው ኢጣሊያኖችን ገፋፍቶ ወደ ሀገራችን ያመጣቸው የእንግሊዝ መንግሥት መሆኑን ነው። ከዚህ በላይ በጠቀስኩት ጽሁፍ ደግሞ የፈረንሣይ መንግሥት ሥጋትም እንግሊዝ ምፅዋን እንዳትቆጣጠር መጣር ብቻ የተወሰነ ስለሆነ ኢጣሊያ ምፅዋን ብትቆጣጠር የፈረንሣይ መንግሥት የማይቃወም መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

በምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል ጽ/ቤት ጉዳዩ በቀላሉ የተፈታ አልነበረም። ለብዙ ጊዜ በሁለቱ ሀገሮች ውዝግብ ሲፈጥር ቆይቷል። ለምሳሌ ከላይ ከተጠቀሰው የሐሳብ ልውውጥ አንድ ዓመት በኋላ አፕሪል 1888 ዓ.ም. ማንቴጋትሣ የተባለው በምፅዋ የCorriere della sera. Illustrazione Italiana መጽሔቶች የዜና ወኪል የነበረው ስለ ፈረንሣይ ቆንስላ የሰጠው አስተያየት እንደሚከተለው ነበር።[1]

«ፈረንሣይ በምፅዋ የቆንስላ ጽ/ቤት ያላት ብቸኛ ሀገር ናት። የምታቀርበው ሰበብም የንግድ ዜጎች መብት ለመጠበቅ ነው የሚል ነው፣ ምክንያቱም የራሷ ዜጋ በምፅዋ አንድ ሰው እንኳ የላትም።

1 Vico Mantegazza,ibd, p.49-50

ሁሉም እንደሚያውቀው በምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል መኖሪያን ሆኖ አይደለም የሚታወቀው። በዶጋሊ የደረሰው ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት በምፅዋ በጣም ሙቀ የሚቀጠሩ ሠራዊቶች በሙሉም ይኖሩ ነበር። ከዶጋሊ ጦር ነት ማግስት ግን ሁሉም ተባረሩ። ይኸውም ማንም ሊገርመው አይችልም። አሉት የታወቁ ሠራዊቶች ግን ለክ እንደ ሌሎች መገደር ሊገኙበው ያለበት ተለወጠ። ተፈለገው ግን በፈረንሣይ ምክትል ቆንስል መኖሪያ ቤት ተገኙ። ምንም እንኳን ቆንስሉ መሸ ሌሎች ያለታረሙ እየፈለገኝ ወደይ የነበረው ቢሆንም የእኛ ጦር አዛዦች እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥበው ነበር። ሁሉም ያውታል ምንም እንኳን ሐበሾች ፈረንሣይ የምትወዳቸው ዜጎች ባይሆኑም በፈረንሣይ ቆንስል ጽ/ቤት ከፍ ያለ የመጠጊያነት አቅዋም ያገኙ እንደ ነበር የታወቀ ነው። ሌላ ቆንስል መርዕ ተቀደር በመሆኑም ሁኔታዎች አለ ተቀየሩም። ገልጾች ጉዳር እንዳይከናወ ብላ ፈረንሣይ የፈጠረችው ክርክር ብቻ ውዝግብ ፈጥሯል። ከዚይ ሌላ የተጠቀሰው ኢጣሊያኖች[1] ጋዜጠኛ አምበት ጦር ተደም ብሎ ፌብሩዋሪ 22/1887 ዓ.ም የሚከተለውን ዜና አሰራጭቶ ነበር። «ዛሬ ጠዋት ከዚህ በፊት በፈረንሣይ ቆንስል ጽ/ቤት እና በሐበሾች መካከል እንደኘ አውገም ቢሆን ይህ የጠየ ሥራ ለመቀጠል የሚያስፈልግ ሆኑስ ክ/ማርያም የተባለው ቄስ እዚህ ምፅዋ ገብቷል። እሱ ደብዳቤዎችን ለመውሰድ በየወሩ ከከረን ምፅዋ ይመጣል። ደብዳቤዎችን እሱ ከመረከቡ በፊት የኢጣሊያ ጦር ዕዝ ከፍቶ ያነባቸዋል። ምናልባት መንግሥታችን በጦርነቱ ምክንያት መስኮ ዝግ ነው ብሎ በአወጀበት ጊዜ አስፈላጊ ቁሬጥቶች አላገኘም። የሃይማኖት ሚሲዮናውያን ቢሆኑም ለአገሪቱ ተገዢ መሆን ነበረባቸው። ስለሆነም ለቄ አስተያየት ማድረግ ባልተገባ ነበረ። ምክንያቱም እንደሚታወቀው ይህ የሃይማኖታዊ ሚሲዮን ከሃይማኖት ጋራ ምንም ግንኙነት የሌለው ተግባር ሲያከናውን ነው የሚታየው። ነገር ግን የፈረንሣይ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ መንግሥታችን ባደረገው ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት ደብዳቤዎችን ለመቀበል በየወሩ አንድ ቄስን ከከረን ወደ ምፅዋ እንዲመጣ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ተደርጓል። «ቄሱ ሐጉስ እዚህ በሚመጣበት ጊዜ እስከሚሄድ ድረስ በወታደር ዕዝ ታብር ይቆያል።

እሱም ሆነ አብረው የሚመጡ ሰዎች ከማንም እንዳይገናኙ ተደርጎ በእጃቢ ወደ መጠበት ይመለሳሉ። ነገር ግን ባለፈው ጊዜ አንድ ጠባቂ ኢጣሊያዊ መኮንን ከአለቃ መሆኑን እያወቀ አንድ የፈረንሣይ ቆንስል አሽከር ከቄሱ ጋር ተገናኝቶ ለማነጋገር ደጋግሞ ሁለት ሶስት ጊዜ በመሞከሩ በኃይልም በመጠቀም ለመከላከል ተገዶ ነበር።»

በሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት ማለት በፈረንሣይና በእንግሊዝ የነበረው ፉክክር ምክንያት የተጎዳን እኛ ነን። ኢጣሊያ እንኳንስ ከሀገሯ ወጥታ ቅኝ ግዛት ልታስተዳድር የራሷን ሀገርም ለማስተዳደር የበቃችው ገና ትናንትና ወደ ሀገሯን ከመምጣቷ በፊት ስለሆነ ሌሎች ሕዝቦች ለማስተዳደር ለማድረግ ችሎታ ያልነበራት የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣሊያ አሳልፎ መስጠት እኛን መጉዳት መገንዘብ ይኖርበታል።

1. Vico Mantegazza: Ibd p. 56



ኢጣሊያ ነገሷን እንድትገኝ ያገኘችው በናፖሊዮን 3ኛ የፈረንሣዮች ንጉሠ ነገሥት 140,000 /መቶ አርባ ሺህ/ ጦር በማዝመት፣ እንዲሁም በእንግሊዝ መንግሥት የዲፕሎማሲ ድጋፍ ነበረ። ኢጣሊያ ግን ውለታዋን ረስታ እነዚህን ሁለት ሀገሮችን በመቃወም መንገድ ታያቸዋለች።

## 5. በኢትዮጵያ ላይ የጀነራል ባለታ የጦርት ዓዋጅ

የዶጋሊ ጦርነት ያስከተለው መዘዝ ቀላል አልሆነም። ጣሊያኖች የሽንፈታቸው ምሬት በሰፊው ተያያዙት። የመጀመሪያ ዙር ፋሽሚያ በግድግ በደረሰባቸው ላይ ሁለተኛ ክፍር ሽንፈት ድረስ አስደረሰም። ጣሊያኖች በአብሬት ተገለሰተው ከአጼ ዮሐንስ ሞት በኋላ ትግራይን በሙሉ ይዘው አምባላጌ ደርሰው ወደ መሀል ሀገር በገሰገሱበት ጊዜ አጼ ምኒልክን አስቆጥቶ የአድዋ ጦርነት እንዲከተል ሆኑ። ኢጣሊያ ከምፅዋ አልፋ ወደ ደጋው የኢትዮጵያ መሬት ማስፋፋት ቀጥላ የዶጋሊ ጦርነት ከከተለ በኋላ በኢትዮጵያ ላይ አጠቃላይ ጦርነት በአዋጅ በማወጅ እንደ ሚታወቀው አጼ ዮሐንስና መላውን ኢትዮጵያን አስቆጥቷቸው ስለነበረው አጼ ዮሐንስ ጣሊያኖችን ከሀገራችን ጠራርጎ ለማስወጣት ከተት ሠራዊት ብሎ ዘምቶ እንዳስበው ሳይሳካለት በመቅረቱ ጣሊያኖች እንዲ እስጨረሱን ማመስገን ሊገባቸው በተቃቀት ግምት የዶጋሊ ሽንፈታቸውን በጦር ሜዳ ስለተበቀሉ ለበለጠ እብሪት ተነሳስተው ሠረራቸውን ቀጥለው አጠቃላይ ደርሰው ጎድጓ ላይ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የተደረገው የጦር ሜዳ ፍልሚያ በኢጣሊያ ተሸናፊነት የመጀመሪያ ዙር መደምደሚያ ሆነ። በዶጋሊ ግዜ የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊቸር ሮቢላንት የኢትዮጵያ ጦር አራት ዘራፊዎች ናቸው ብሎ በመናገር የተሳሳተ ግምት እንደሰጠ ሁሉ በ1891 ዓ.ም ፊርዲናንዶ ማርቲኒ ስለ ኢትዮጵያ የጦርነት ብቃት ሲገልፅ «አቢሲኒያ በአሁኑ ጊዜ በጣም ደካማ ሀገር ስለሆነች ከንጉሦቿ አንዱ ወይንም ንጉሦቿ ሁሉ አንድ ላይ በመሆን በኢጣሊያ ጦርነት አውጀው ሊያሸንፉ የሚችሉ አይደሉም» ብሎ ነበር። ይህ የተሳሳተ አመለካከታቸው ወደ ጎድዋ ጦርነት ሽንፈት አደረሳቸው።

እዚሁ በምፅዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀነራል ባለታ ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ መሆናቸውን አውጆ በአዋጁ ይህን እያጸና በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ሜይ 4/1887 ዓ.ም በሰርኩላር ለአርሲ መንግሥታት የተላለፉ ደብዳቤዎች፣

1ኛ. በምፅዋ አካባቢ የሚገኙት የቀይ ባሕር ወደቦች የተዘጉ መሆናቸውን

2ኛ. በእነዚህ ወደቦች ከሌላ ሀገር ወይንም ከሌላ ሕዝብ ጋራ ንግድ ማካሄድ መከልከሉን

3ኛ. ማንኛውም መርከብ ይህን አዋጅ ጥሶ ቢገኝ በሊሩ መንጃል ተዘግቶ ፍርድ ቤት ቀርቦ ትቀጣለች ብሎ ሊያስታውቅ፣ በዚህ ሰዓትም ሌላ ደብዳቤ በፈረንሣይ የኢጣሊያ

አምባሳደር የተገለው ጀነራል ባለታ ከምፅዋ የፈረንሣይ ቆንስል በኩል በሚከተሉት ነጥቦች የተሰማው መሆናቸውን ይገልጻል።

1ኛ. የፈረንሣይ ሚስዮናች አቡን ከሌሎቹ ትርጉማኖ ሚስዮናች በቀጥታ መገናኘት የሚችለው በምን ምክንያት ሚሲዮናዊ ከቦታ በሚለቅበት ጊዜ ሚስዮኑ ሲዘረፍ ብቻ ነው።

2ኛ. አቡኑ ከሌሎቹ ትርጉማኖች ሊገናኙ የሚችሉ በየሁለት ወር ወይንም በአሥመራ በኩል ከእኛ ኃላፊነት ቁጥጥር ውጭ ሆኖ ነው።

3ኛ. ይህን ስምምነት አቡኑ በአክሱር ትንጫና በኩል ለሌሎቹ ትርጉማኖች ያስተላልፋል። ግንቦት 14/1887 ዓ.ም የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለኢጣሊያ በፈረንሣይ ሀገር አምባሳደር በላከው ደብዳቤ ጀነራል ባለታ በጦር አዛዥ ምክንያት መገናኛ መርሶ የተከለከለ ቢሆንም ለፈረንሣይ ሚሲዮናውያን ልዩ አስተያየት የተደረገ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ቆንስሉ ግን ከቦታው እንዲነሳ ጥረት የተደረገ መሆኑን አስረድቷል። በርግ የፈረንሣይ አምባሳደር ግንቦት 7/1887 ዓ.ም [1] ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በላከው ደብዳቤ በኢጣሊያ መንግሥት አድራጎት ተቃውሞ አሰምቷል።

በምፅዋ እና አካባቢዋ በቀይ ባህር ወደቦች የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀነራል ባለታ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ኢጣሊያ ሙሉ ጦርነት ያወጀች መሆንዋን ከሚገልፁት ሰባት አንቀጾች አንደኛውና ዋነኛው ከሞላ ጎደል ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው።[2]

1. ከኢትዮጵያ ጋር ማንኛውም ግንኙነት ተቋርጧል። ስለዚህ በጦርነት ፍልሚያ የሚገኙ ሁለቱ አገሮች ማንኛውም ዓይነት ንግድ የተከለከለ ነው። ስለዚህ ማንኛውም የንግድ እቃዎች ውርስ ይሆናሉ።

2. ከኢትዮጵያ ጋር ወይንም ከጉንዋ የቆሙ ጉሣዎች ሁሉ ማንኛውም ዓይነት መገናኘ ወይንም መስማማት ለመንግሥት ፀጥታ አስጊ በመሆኑ ከህደት ነው። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሁሉ በሞት ወይንም እድሜ ልክ፣ በግዴታ ሥራ ይቀጣል።

ስለዚህም ማንኛውም ሰው ሆነ ብሉ፣ ሀ/ ለጠላት መጠለያ የሰጠ ወይንም ያሰጠ ለ/ በድብቅ በምፅዋ አካባቢ ጦር ሠፈሮች ማስረጃ ሲፈልግ ወይም ሲሰጥ የተገኘ ሐ/ በማድረግም ሆነ ማድረግ የሚገባው በመቆጠብ የኢጣሊያ ጦር አደጋ የጣለ ወይንም በአንድ ጦርነት ጥሩ ውጤት እንዳይገኝ ያደረገ።

መ/ በሰው ኃይል፣ በገንዘብ፣ በቀለብ፣ በጦር መሣሪያ በጦር ትጥቅ ለጠላት የረዳ በዚሁ ተራ ቁጥር መሠረት ይቀጣል።

3. የውጭ ሀገር ዜጎች በቂ መተዳደሪያ የሌላቸው መሆናቸው የተጠረጠሩ ሰዎች ከሀገር ሊባረሩ ይችላሉ።

1. Vico Mantegazza: Ibd. p. LIV

2. Vico Mantegazza: Ibd. p. LXIII



4. ማንኛውም ሰው በጦርነት የሚገኙ በሁለቱ ሀገሮች መኖሪያ ሊመርጥ አይችልም። ስለዚህ በስምንት ቀን ውስጥ አንድ የመኖሪያ አድራሻ መርጦ ማስታወቅ ይኖርበታል።

5. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይንም ማንኛውም ከኢትዮጵያ ተባባሪ የሚባሉ ጉሣዎች ያልሆነ የኢጣሊያ ጦር ከያዛቸው መሬቶች ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ነዋሪ ቢሆንም ወይንም በማንኛውም ዓይነት በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት የገቡ የተለያየ ፈቃድ ካልተሰጣቸው የኢጣሊያ ጦር ምርኮኛ ይሆናሉ።

6. የኢጣሊያ ጦር የበላይ ዕዝ ተባባሪ ጉሣዎች ብሎ የሚጠራቸው ሁሉ በኢጣሊያ በተያዘው መሬት መኖርና መዘዋወር ይችላሉ። ነገር ግን ከታወቀ የጉሣቸው መሪዎች የተሰጣቸው ፈቃድ መያዝ ይኖርባቸዋል።

7. የውጭ ሀገር ሰዎች /የገለልተኛ ዜግነት ያላቸው/ በተያዘው መሬት መኖር ከፈለጉ በስምንት ቀን ውስጥ መደበኛ የመኖሪያ ፈቃድ ከጠቅላይ ጦር ዕዝ ካላገኙ ከሀገር ይባረራሉ።

## 6. ስለ ራስ አሉላ የተሰጠው አስተያየት

የዶጋሊ ድል የተገኘው በራስ አሉላ የጦር ታክቲክ ልዩ ችሎታ መሆኑን አያጠያይቅም። ምንም እንኳን ራስ አሉላ ተገቢ ክብርና ቦታ ከሀገሩ ባያገኝ ለምሣሌ በሀገር አቀፍ፣ ጉብና በሸዋ፣ አሉላ በትግሬ ተብሰው የተገጠሙና የመሣሰሉት በይበልጥ ቢዳብር የሀገራችን ታሪክ እንደዳበረ ይቆጠራል። በፀረ ኢትዮጵያ የታወቀው የኤርትራ ታላቁ ሀገረ ገዢ የነበረው ማርቲኒ [1] በ1891 ዓ.ም ስለ ራስ አሉላ የሰጠው አስተያየት ከዚህ በታች መጥቀሱ ይጠቅማል። "ይህ ራስ አሉላ የተባለው ቀድሞ የኩበት እበት ሰብሳቢ የነበረው ዛሬ ራስና ቁርኩ ፓሻ በሀገሩ ታሪክ ምናልባት አንድም ምልክት ለማስተላለፍ ያልተጨነቀ በኢጣሊያ ታሪክ ግን አንድ ታሪክ ሠርቷል።

ምስጢራዊ ፍጥረት ነው። ብዙ ሰዎች እናውቀዋለን ይላሉ። ምናልባት ግን ማንም አያውቀውም። ከሚወዳቸው ጋር ቸር ሩህሩህ ነው ተብሎ ይነገርለታል። ጠላቶቹ ግን አንድ ቀን እንኳ የጠላቸው ያስማጸረጥ የሚያላድድ፣ ምህረት የለሽ ነው የሚሉ በእኛ ግዛት ዛሬ የሚገኙ ድር የሚያውቁት ሰዎች የሚሰነዝሩዋቸው አስተያየቶች ናቸው። የተቃዋሚዎች ኃይለኛ ጥላቻ ከመሆኑ የተነሣ ምንም የሰብአዊነት ባህርይ እንደሌለው ይናገራሉ። በወታደራዊ ችሎታም ምንም እንደሌለው ይናገራሉ። 1ኛ. ከዶጋሊ ሌላ በጦር ሜዳ አሸናፊ አልሆነም፣ ይሸውም በጣሊያኖች ስህተት እንጂ በራስ አሉላ ችሎታ እንዳልሆነ ያምናሉ። 2ኛ. በአራማት ዐጋሜ በሥዩምና ስብሐት ተሸንፏል። 3ኛ. ከግብጾች ጋር በአሳፋሪ ሁኔታ ሸሽቷል። 4. በጉራዕ የተገኘው ድል በአጼ ዮሐንስ ብርታት ብቻ ነው፣ ራስ አሉላ ምንም አልተካፈለም። 5ኛ. በኩፊት ሠራዊቱ ካሰጨረሰ በኋላ የአስማን ዲግማ ደርቡሾች ብላታ ንብሩ ራሱን መስዋእት በማድረግ ባያድኑት ኖሮ እሱንም ይገድሉት ነበር። 6ኛ. በመተማ ነገሩ ተስፋ እንደሌለው አይቶ ፊቱን ወደ ኋላ አዞሮ ነው የተመለሰው።

1. F: Martini: ibd p. 147

7ኛ. ጥሩ ክርስቲያንም አይደለም፤ መስቀል በጠብመንጃው ሲያላትም ከእስላሞች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ግን እስላሞች ሲሰግዱ እሱም አብሮ ይሰግዳል።»

በሌላ በኩል ግን ስለ ራስ አሉላ ወታደራዊ ችሎታ በአንድ ኮረብታ ሆኖ የዶጋሊ ጦርነት ይመለከት የነበረው ሻለቃ ፒያኖ አንድ ኤውሮጳዊ የጦር ጀኔራል ራስ አሉላ ለወታደሮቹ ከሰጣቸው ትእዛዝ የተለየ አይሰጥም ነበር፤ በማለት የባለሙያ በከፍተኛ አድናቆት ቃሉን ሰጥቷል። ማርቲኒ ራስ አሉላ ኢትዮጵያ በእሱ የምትመሰል፤ እሱ ብቻ የኢትዮጵያ ተወሬ ወኪል መሆኑን ያምናል። የአጼ ዮሐንስ ልጅ ራስ መንገሻ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ካላስጣን የሀሊና ዕረፍት አያገኝም ብሏል።

## 7. የዶጋሊ ጦርነት በጣልያኖች ላይ ያስከተለው ድንጋጤ

ከሰሐቲና ዶጋሊ ጦርነት ማግሥት ጀንዋሪ 27 ጣሊያኖች ከሰሐቲና ከዊዓ ከሌሎችም ይዞታቸው ከነበሩ ቦታዎች ለቀው ወጥተው በምፅዋ ብቻ ለመቀመጥ ተወስነው ተቀመጡ። ጣሊያኖች ቢያሸንፉም ቢሸነፉም ሁል ጊዜ ስለ ጀግንነታቸው ብቻ ነው የሚያወሩት። ካርሉ ዋጊ በሁለቱ ጦር ሜዳዎች የሁለቱ ሀገሮች ስላሳዩት ጀግንነት ሲፅፍ «በእርግጥ በሁለቱ ጦር ነቶች ለኢጣሊያ ጦር ትልቅ ክብር ተመዝግቧል። ሆኖም ሐበሾችም እንዲኮሩባቸውና አብሬት እንዲያደርጓቸው አስችሏቸዋል። ራሱ ከሰሐቲና ከዊዓ ማፈግፈግ እነሱ በሰጡት ማስጠንቀቂያ ፈርተን ሳይሆን አነስተኛ ቁጥር የነበረው ጦራችን በማሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን ስለአመንበት የተወሰደው እርምጃ ከእኛ ወገኖች ለእነሱ በሚጠቅም ለእኛ ክብር ግን በኃይል የሚጎዳ አመለካከት ተርጉመውታል» ብሏል።

ጣሊያኖች በምፅዋ ተወስነው ሊቀመጡ ለምግባቸው ከባሕር ማዶ ካልሆነ ከኢትዮጵያ ማግኘት ስላልቻሉ ጀኔራል ጄኔ የነበረው አማራጭ አዲስ ተጨማሪ ጦር በመጠየቅ ሽንፈታቸውን መበቀል ያስብ ነበረ። ራስ አሉላ በበኩሉ ጣሊያኖች በማፈግፈጋቸው ተደስቶ ወዲያው የነበሩ የኢጣሊያ እስረኞች እያያዘ ማላላት ጀመረ። በምፅዋ ከኢጣሊያ አሻከርም መጣጥፍ ተደርጎ በጣሊያኖች በጉምሩክ ተወስደውበት የነበሩት አንድ ሺህ ጠብመንጃዎች ስለተመለሱለት ላሹሩ በቀር ሌሎች እስረኞች ተለቀው ምፅዋ ገቡ። ላሹሩ 15,000 ማሪያ ተሬዛ ብር ከፍሎ በአንዱት ከእስር ተለቀቀ። የዶጋሊ ጦርነት በኢጣሊያ ሀገር ከባድ ውጥረት ፈጥሯል ብሔራዊ ሐዘን እንዲባልም ታውጇል።

1. አንዳንድ የፓርላማ አባላት ኢጣሊያ ከአፍሪካ ለቃ እንድትወጣ ሐሳብ ሲያቀርቡ፤

2. ሌሎች ደግሞ በመደበኛ ብቻ ተወስነ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንዲመሠረት ጠይቀዋል።

3. አብዛኛው የፓርላማ አባላት ግን ኢጣሊያ በዶጋሊ የወደቁ የኢጣሊያ ወታደሮች እንድትበቀል ጠይቀዋል።



ለሁሉም ግን ስለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ያስጨበጠ ነበር። ኢትዮጵያ ጣሊያኖች ይገምቷት እንደነበረች አውነተኛ ማንነቷ ለማወቅ ያስቻለው ጦርነት ነበረ። ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የውጭ ጉዳይና የጦር ሚኒስትሮች ከሥልጣናቸው እንዲለቁ ሲገደዱና አዲስ ጠቅላይ ምኒስትር ሆኖ የተመረጠውም ጦርነት የናፈቀው የቅኝ ግዛት የማስፋፋት ደጋፊ የነበረው ክሪ ስፒ ነበር።

## 8. ስለ ሰሐቲና ዶጋሊ ጦርነቶች ከኢጣሊያ መንግሥት የተሰጠ ይፋዊ መግለጫ

ስለ ሰሐቲና ዶጋሊ ጦርነት በወቅቱ በኢጣሊያ መንግሥት የተሰጠው ይፋዊ መግለጫ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነበር።

ጀንዋሪ 22 ስለ ራስ አሉላ ዓላማዎች የሚያስጉ ዜናዎች ይደርሱ ነበር። ራስ አሉላ ብዛት ያላቸው ወታደሮችን አስከትሎ ከጊንዳ ወደ ሰሀቲ ወርዶ እንደነበርና 5 ኪሎ ሜትር ከዚህ ቦታ ርቆ ሰፍሮ እንደነበረ ታውቆ ነበረ።

ሻለቃ ቦሬቲ ይህን ሁኔታ እንደሰማ በ25 ፍተሻ አድርጎ ነበረ። ነገር ግን ወታደሮቹ ከአንድ ኪሎ ሜትር ትንሽ የሚበልጥ እንደተጓዙ የጠብመንጃ ተኩስ ስላጋጠማቸው ወደ ኋላ ተመለሱ። ሆኖም ወደ ደሴት /Desset/ ሸለቆዎችና ወደ ሌሎች አነስተኛ ሸለቆዎች የሚያምሩ የሰሐቲ ይዞታ የሚከቡ በርካታ ወታደሮች መኖራቸውን ማሥረጃ ለመሥጠት ችሏል። ወታደሮቹ ወደ ጦር ሰፈራቸው እንደተመለሱ ኮረብታዎች በኢትዮጵያ ወታደሮች የተሞሉ ነበሩ። ቦሬቲ አደገኛ ከበባ ለማስወገድና ጠላትን ወደ መድፎች ተኩስ ዓላማ ለመሳብ የመቶ አለቃ ኩሞዎ ግማሽ የኢጣሊያ መቶ አለቃ ጦርና ሁለት የመቶ አለቃ ይዞ እንዲወጣ አዘው የመቶ አለቃ ፊዴሪኮ ኩሞዎ ወደ ፊት በሚራመድበት ጊዜ የሸለቆው ዝቅተኛ ቦታቸውን እንደያዙ አንድ መቶ የሚያህሉ ሐበሾች በድንገት ደረሰባቸው፤ ተኩስም ከፈተባቸው፤ ይህ የማጥቃት ምልክት ነበር።

ጠላት ወዲያውኑ ሁሉን ኮረብታዎችን ያዘ፤ የእኛ ሰዎችም በተላከላቸው ሌላ ግማሽ የመቶ አለቃ ጦር እየተረዱ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ምቹ ወደሆነ ቦታ አፈገፈጉ። በዚሁ የመጀመሪያ ግጭት የመቶ አለቃ ኩሞዎ /Cuomo/ ከባድ የመቁሰል አደጋ ደረሰበት። ብዛት ያላቸው ሐበሾች እንደ አውሬ እየጮሁ ወደ ማጥቃት ተንቃነቁ፤ አንዳንዶቹ ከምሽጉ 300 ሜትር ርቀት ደርሰው ነበር። ሆኖም ከእኛዎቹ ወታደሮች ለሁለት ሰዓት የቆየ የጠላ ት ኃይለኛ ተኩሥ በመቋቋም ጠላት ማጥቃቱን እንዲያቆም አስገድደውታል፤ ወደ ኋላ በመመለሥ በመጀመሪያ በሥነ ሥርዓት ሆኖ፤ ቀጥሎ ግን ወደ ሽሽት ተለወጠ በዚሁ ቀን ጠላት የደረሰበት ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ በመውሰዱ ለማወቅ አልተቻለም፤ ከእኛ ወገን ግን የመቶ አለቃ ኩሞዎ /Cuomo/ ጭምር የሞቱ 5 የቆሰሉ 3 ነበሩ።

ማታውን ሁሉም ኮረብታዎች ተለቀው ነበር። ምግብ ትጥቅ እና ተጨማሪ የሰው ኃይል በመጠየቅ ቦሬቲ በላከው ቴሌግራም የውጊያው ዜና የተሰ ማው በምፅዋ ከቀኑ 11 ሰዓት ነበረ። ጀኔራል ጄኔም ሌሊቱ ሥንቅ አጅቦ ወደ ሰሐቲ የጦር ሰፈር እንዲሄድ ለቱና

ኮሎኔል ደ ክሪስቶፎሪስን /Da Cristoforis/ አዘዘው። የአርዳታ ቡድን ጀንዋሪ 26 ከጠዋቱ 11 ሰዓት ከ20 ከመንኩሎ ተነሳ። በመቶ አለቃ ኮሚ የ37ኛው እግረኛ የሚመራ መደ በኛ ያልሆኑ ወታደሮችና መደበኛ የሆኑ አንድ መቶ አለቃ ጦር ከ15ኛ ሻለቃ ጦር ፊት አጥቂ ጦር በመመደብ ነበር። ከቅርብ እርቀት ሁለት መድፎች በበቅሎዎች እየተጎተቱ 20ኛና 41ኛ ሬጂመንት፣ እንዲሁም 6ኛ እና 7ኛ ጦር በ24 በዚሁ ወር ከጣሊያን የመጡ እግረኛ የመቶ አለቃ ጦር ይከተሉ ነበር። እንዲሁም ትጥቅና ስንቅ በበቅሎዎችና በግመሎች የተጫኑ ነበሩ። የደጀን ጦር ግን ግማሽ የመቶ አለቃ የ48ኛው እግረኛ ጦር ነበረ።

ከጠዋቱ 2:30 ሰርጋታብ /Sergatab/ ትንሹ ወንዝ ጦሩ እንደተሻገረ በቅድሚያ የሚገኘው ጦር ሰሐቲ ለመድረስ አንድ ሰዓት የእግር ጉዞ ሲቀ ረው ባሺቡዙኮች በፊት አጥቂ ጦር ጠላት እንዳለ ተመለከቱ። ጉዞውን አቋርጦ ሌቴናኮሌኔሉ ከሻምበል ሚኪሊኒ ጋራ ሆነው የ17ኛ መድፈኛ በፍጥነት ወደፊት አመሩ። ሚኪሊኒ /Micheiini/ ወደ ሰሐቲ የሚሄደው የሻለቃ ቦሬቲ ጦር ለማጠናከር ከመቶ አለቃ ቲሮኒ /Tironi/ እሱም የ17ኛ መድፈኛ ጋራ ሆኖ የመድፈኛ አዝ በሰሐቲ ለመረከብ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት መድፎችን በመያዝ ነበረ።

ሐበሾች በዚሁ ጊዜ በ800 እና 1000 ሜትር ርቀት በቡድን ተከፍለው መሥመር ይዘው ነበረ። የፊት አጥቂ ጦር መድፎችን በመያዝ አፈታቸው ቦታውን ያዘ፡ ቀሪውን ጦር ፊትለፊት በሚገኘው ኮረብታ ቦታውን ያዘ። ተኩሱ ከጠላት ተጀምሮ ብቅ እያሉ እያቋረጡ የሚጠፉ ሰዎች ነበሩ። አጠፋውን የተኩሥ ምላሽ ከመድፎች ይደርስባቸው ነበር። ነገር ግን ለትንሽ ጊዜ ነበረ፣ ምክንያቱም ከመድፎቹ አንዱ ወዲያውኑ ተበላሸ። ሁለተኛውም ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሥራውን አቋረጠ፣ ሁለቱም ተወረወሩ። የጠላት ጥቃት ዓላማ ጥበብ የተሞላበት ለመከበብ ስለነበረ ዋናው የእግረኛ ጦር ወታደሮች በጠላት እንዳይያዝ በሥተኋላ ከነበረ ኮረብታ በመመለስ ቦታውን እንዲይዙ ትዕዛዝ ተሰጣቸው። ይህ እንቅስቃሴ የተካሄደው በቡድን ሲሆን ኃይለኛ ተኩሥና ጩኸት ከሐበሾች እየተካሄደበት ነበር ወደ የተመደበላቸው ቦታ የደረሱ።

የእኛ ወታደሮች በእውነተኛ ጀግንነት አቋም ተኩሥ እየከፈቱ «ቪቫ ሊታሊያ» (Viva L'italia) እያሉ ነበረ በበኩላቸው ይጮሁ የነበረው። ነገር ግን በደረሰባቸው ጉዳት የሰውና የመሣሪያ እጥረት እየተከሰተ ቢመጣም ለቀሩት ጥቂት ወታደሮች በትጥቅ ከፍል የነበሩ ጥይቶች ታደሉ። አዲስ የጠላት ኃይለኛ ጦር ሲመጣ ግን በእጅ መሣሪያ፣ በጨበጣና በጎራዴ፣ የሰው በሰው ትግል ተበሩ የሌለው ትግል ለማድረግ ተገደዱ።

በእኩለ ቀን ገደማ (ከቀኑ 6 ሰዓት) የእኛ ጦር ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ ነበር። ከዚህ በኋላ አሰቃቂ የልብስ ማስወለቅ፣ የወደቁትን ማቁሰል፣ ከሞት የተረፉት ቁስለኞች በመውደቃቸው የሞቱት ስለመሰላቸው ዘርፈው ራቁታቸው እየወጡ ሳይወጉዋቸው በመቅረታቸው ነው። በጦርነቱ መጨረሻ በጣለው ኃይለኛ ዝናብ በጭቃ ላይ ተጥለው እየደሙ መንቀሳቀስ ሳይችሉ መቀመጣቸው ስቃያቸው ምን ያህል እንደነበረ ለመገመት አያዳግትም። አንዳንዶቹ



በብዙ ችግር መንኩሎ ደረሱ። የቀሩት በሻንበል ታንቱሪ (Tanturi)፣ የሚመራ ዱቺ (Duci)፣ ፖርታና (Porta)፣ ሳንቶሮ (Santoro)፣ ያሉበት የ54ኛው የመቶ አለቃ ጦር ከብዙ ሰዓት በኋላ ለእርዳታ መጥተው ለቅሞ እስከ ሚወስዳቸው ድረስ በመሬት ላይ ተጥለው ነበር የቀሩት።

ይህ ሻንበል በ5 ሰዓት በእርሳስ የተፃፈ ወደ ዶጋዓሊ እርዳታ የሚጠይቅ ከኮሎኔል ደ ክርስቶፎሪለ እንደደረሰው ወታደሮቹን ሰብስቦ ወዲያውኑ ተነሳ። እግረ መንገዳቸው ሲጓዙ ባሺቡዙኮች የሐበሻ ሬሣዎች ተመለከቱ። በዚሁ ጊዜ በተጠንቀቅ በመሆን ይዟቸው መጥተው በነበሩ መድፎች ተኩሥ ከፈቱ። ይህ ተኩሥ የጠላት ድምፅ እንዲጠፋ እንዲሸሽ አደረገው። በመቶ አለቃ ታንቱሪ (Tanturi) ወደ ፊት ያሉ ቦታዎች ፍተሻ ሲደረግ መንገዱ ነፃ ሆኖ ተገኘ።

ኩባንያው ወደ ጦር ሜዳ ሲደርስ የእልቂቱ እውነተኛ ገፅታ ሊገነዘብ ችሏል። ከታንቱሪ በ27 ለጀነራል ጄኔ የተፃፈው ሪፖርት የሚከተለው ቃል ተገልጾ ነበረ «ሁሉም ራቁታቸውን ሆኗል፣ በጀርባቸው ተኝተዋል፣ ከባድ ቁስሎች ነበሯቸው፣ በተራ በመሥመር እንደተቀመጡ ተጋገድመው ነበር፣ ምንም ጠብመንጃ፣ ልብስ፣ ባዶ ኮዳም አልነበሩ ቸውም፤ ሁሉም ተወስዶባቸዋል። ሻንበሉ በሌላ ሪፖርቱ ይህ ጀግንነት የተሞላበት የሰው እልቂት በማየት ኩባንያውን ሰብስቦ ለወደቁት ወታደሮች የብረት ሰላምታ አድርጎላቸዋል።

ከ500 በደ ክርስቶፎሪስ ይመሩ የነበሩ ወታደሮች ውስጥ 413 ሞተዋል፤ 86 በከባድና በቀላል ቆስለዋል፡ አንዳንዶቹም በደረሰባቸው ጉዳት ቆይተው የሞቱ ነበሩ ከመኮንኖች ውስጥ 22 ሞተዋል፡ ቆስሎ ሻምበል ሚከሊኒ (Michelini) ብቻ ተረፈ። የመቶ አለቃ ኮሚ ቆስሎ የ37ኛው እግረኛ ጦር በብዙ ችግር ሞንኩሉ ለመድረስ ችሎ ነበር፣ ከዚያም ወደ ምፅዋ ተወሰደ፣ ሆስፒታል መርከብ «ጋልባልዲ» ተኝቶ ፌብሯሪ 3 ዐረፈ። የሞቱት በስፍራው ተቀበሩ። የኮሎኔል ደ ክርስቶፎሪስ አስከሬን ግን ወደ ምፅዋ ተወስዶ ከመቶ አለቃ ኮሚ አስከሬን ጎን ተቀብሯል።

# ምዕራፍ 8
# በአጼ ዮሐንስ የመትመራው ኢትዮጵያ ላይ በጣሊያኖች የተፈጸመበት የማዳከም ስውር ደባ

## የሰር ፓርታል ተልእኮ

### 1. ዝግጅትና ጉዞ

ጁን 30/1887 ዓ.ም በእንግሊዝ ሀገር የኢጣሊያ አምባሳደር[1] ለሀገሩ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲፅፍ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ሣሊስቡሪ ተገናኝቶ ተነጋግሮ እንደነበርና ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ለመኖር የምትፈልግ ከሆነ የእንግሊዝ መንግሥት የሽምጋይነት ሚና ለመጫወት ፍላጐቱ መሆኑን ገልፀውልኛል ይላል። አምባሳደሩ እንደገና ጁላይ[2] 16/1887 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ ከሎርድ ሣሊስቡሪ ጋራ በድጋሚ ተገናኝቶ የተነጋገረበት መሆኑን ይገልፃል። በዚሁ ዕለትም በሌላ የፃፈው ደብዳቤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለንግሥት ቪክቶሪያ አንድ ደብዳቤ መፃፉን ገልጾ አንዳንድ ነገርም በመግለፅ ንጉሠ ነገሥቱ በኢጣሊያ መንግሥት አቋም በሞታ አመልክቶ ከአድሚራል ሒወት የተደረገ ውልም የተጣሰ መሆኑን ገልፀዋል። አምባሳደሩ በሌላ ደብዳቤ ጁላይ[3] 21/1887 ዓ.ም. ከሎርድ ሣሊስብሪ ካደረገው አዲስ ውይይት የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ለአጼ ዮሐንስ ወደ ምፅዋ ባለሥልጣን ልካ ሰላም ብትለምንና ጣሊያን የምትሰጣቸው ትድመ ሁኔታዎችን ጠይታ ቢቀበል ብሪታንያ ልታደርገው የምትችለው ብቸኛ የሽምጋይነት ተግባር ነው። ሣሊስቡሪም በበኩሉ የኢጣሊያ መንግሥት ፈቃድ ከሆነ ብሪታንያ የሽምጋይነት ተግባር ማድረግ ዝግጁ መሆንዋን በግለት ገልጿል። የኢጣሊያ አምባሳደር በለንደን ጁላይ[4] 21 ፣ 28 እና 30 አራት ደብዳ ቤዎች በመጀመሪያ የአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ በኢጣሊያንኛ ተተርጉሞ ልኪያለሁ ይላል። ቀጥሎም አጼ ዮሐንስ ንግሥት ቪክቶሪያ በሽምጋይነት በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል እንድትገባ መጠየቃቸውን የሚል ዜና ከአንድ የዜና ምንጭ ተነግሯል።

ከዚህ ቀጥሎም የመቅደላው ጀግና ሎርድ ናፒየር በእንግሊዝ ፓርላማ ለሎርድ ሣሊስቡሪ መንግሥታቸው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ያለው ጠብ በሽምጋይነት ገብቶ ደም መፋሰስ እንዳይከሰት የአድሚራል ሒወት ውል መጀመሪያ አንቀጽ በተግባር እንዲውል እርምጃ እንዲወስድ ጥያቄ እንዳ ቀረበና ጥያቄም ከቀረበ በኋላ ሎርድ ሣሊስቡሪ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለእንግሊዛውያን ወዳጅ ነበረ።

1 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXIII

2 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXIV

3 Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXV

4. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVI-VII



በሌላ በኩል ደግሞ የኢጣሊያና የእንግሊዝ ወዳጅነት ረጅም ዘመን ያለው ነው። ሆኖም ሽምግልና ለማድረግ ከማሰብ በፊት ተቀባይነት እንዳለው ሳይረጋገጥ የሽምግልና ሀሳብ ማቅረብ ጠቃሚነት የለ ውም ብሏል። ሎርድ ሣሊስቡሪ ኢጣሊያና ኢትዮጵያን ለማስማማት ባለው ጽኑ ፍላጐት ሰር ፓርታል ወደ አጼ ዮሐንስ ለመላክ መወሰኑን ገልጿል። እሱ እስከሚመለስ ግን ጦርነቱ እንዳይጀመር ተማጽኖ በተጨማሪ ለሚከተሉት ሶስት[1] ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት የኢጣሊያ መንግሥት መልስ እንዲሰጠው ጠይቋል። 1ኛ. ኢጣሊያ ያላት የመጨረሻ የመሬት ጥያቄ 2ኛ. ሰሐቲን ለኢጣሊያ ለመልቀቅ ኢትዮጵያ ከተስማማች በሰውጡ ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ስምምነት ውል ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነች 3ኛ. የኢጣሊያ መንግሥት ተጨማሪ ሌላ የመሬት ማስፋፋት የማያደርግ መሆኑን ቃል ይገባ እንደሆን፤፤የኢጣሊያ መንግሥት ግን ለሶስቱ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ሳይሰጥ ቀርቷል። የእንግሊዝ መንግሥት በራሱ አነሳሽነት ሽምጋይ ለመሆን ባቀረበው ሀሳብ መሠረት ወደ ኋላ ሳይል በዕቅዱ ሎርድ ፖርታል[2] የንግሥት ቪክቶሪያ ልዩ መልእክተኛ በመሆን ለአጼ ዮሐንስ የተላኩ ብዙ ስጦታዎች ይዞ የመንገድ ርቀት ወይንም ሌላ ማንኛውም ችግር ሳያግደው ጉዞውን ጀመረ።

የተነሣበትን ዓላማ ግቡን ሳያደርስ ታሪካዊ ተግባሩን አከናወነ። እንደ ሎርድ ሣሊስቡሪ እና እንደ ጀግናው[3] ናፒየር ድጋፍ ያለው ይህ የሎርድ ፓርታል ተልእኮ ለእንግሊዝ ኃላፊነትን ለመወጣት የታላቅነት ምልክት ነበር። ስለዚህ ቀድሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ስጦታዎች ወደ አጼ ዮሐንስ ይዞ በመሄድ ስለ ሁለቱ ሀገሮች ወዳጅነት ለመነጋገር ኢጣሊያዊ ጀነራል ፓትሶሊ የተባለው የኢጣሊያ የንጉሥ ኡምቤርቶ መልእክተኛ በመሆን ወደ ኢትዮጵያ አምርቶ ምጽዋ ደርሶ ነበር። ነገር ግን አጼ ዮሐንስ ይገኙ የነበረበት ከምፅዋ በጣም ሩቅ ቦታ ነው በማለት ጉዞውን አቋርጦ ወደ ሀገሩ ተመልሷል። የተሰጠውም ምክንያት ጀነራሉ በሀገሩ ብዙ ሥራ ስላለው ነው ተብሏል። የእንግሊዝ መልእክተኞች አድሚራል ሒወትና ሎርድ ፖርታል በሀገራቸው ሥራፈቶች መሆናቸው ነውን? በመልእክቱ ንግሥት ቪክቶሪያ ሎርድ ፖርታልን ወደ አጼ ዮሐንስ የላከችበትን ዓላማ ስታብራራ በጉዳዩ ይዞታ ስለነበሩ መሬቶችና በኢትዮጵያ መሬት ወሰን ጉዳይ ኢትዮጲያና ኢጣሊያ ለማስማማት መሆኑን ገልፃለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ሎርድ ሣሊስቡሪ ለኢጣሊያ መንግሥት ሎርድ ፓርታል ከኢትዮጵያ ከመመለሱ በፊት ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ደጋግሞ አደራ ብሎ ሎርድ ፖርታል ኦክቶበር 14/1887 ዓ.ም.[4] ከለንደን ጉዞውን ጀምሮ በ20 አሌክሳንድርያ ግብፅ እንደሚገባ ይጠበቅ ነበር።

1. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVI

2. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVII

3. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVIII

4. Vico Mantegazza: Ibd p.LXXXVIII

ስለ ሎርድ ፖርታል ተልእኮ ጉልቶ የሚታየው የእንግሊዝ መንግሥት በጉ እመለ ካከትና በጉ ተግባር ነው። እንግሊዝ ሀገር ሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች የምታፈልቅ ሀገር ናት። የመቅደላው ጀግና ሎርድ ናፒየር ኢትዮጵያንና አጼ ዮሐንስን በሚገባ የሚያውቅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ምናልባትም በሰብዓዊነት ተነሳስቶ ይሆናል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀከል ሰላም እንዲሰፍን እንዲጥር ሎርድ ሳሊስቡሪን የገፋፋው። በወቅቱ ሌሎችም ከሎርድ ናፒየር ጐን የቆሙ እንግሊዛውያን ሊኖሩ ይችላሉ። የእንግሊዝ መንግሥት ሰር ፖርታልን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ የወሰነው በኢትዮጵያና በኢጣሊያ ያለው ውጥረት አልባት ለማግኘት በማሰብ ነበር። ከባድ ችግሮች አፈታችን ተደቅነዋል፡ ጥረታችን ይሣካል ወይም አይሣካም ብሎ መተንበይ አስቸጋሪ ነው። ካልተሣካልን ግን የኢጣሊያ መንግሥት በእኛ ጉድለት እንዳልሆነ እንዲረዳልን ተስፋ አለኝ በማለት ነበር የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጥረቱን የጀመረ። ጣሊያኖችም በበኩላቸው በሀበሾች በኩል ጥቃት ካልደረሰባቸው ተኩስ እንደማይከፍቱ ለሎርድ ሳሊስቡሪ አረጋግጠውለታል። በእንግሊዝ[1] ወገን ሎርድ ፖርታል ምፅዋ እንደደረሰ ጀነራል ሳሌታ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ መምጣቱን ለራስ አሉላ እንዲነግርለት ተፈልጐ ነበር።[2] ጣሊያኖች ግን ይህን ለማድረግ አልተ ስማሙም። እንዲያውም በራስ አሉላ በኩል ችግር የሚፈጠርበት ስለሆነ ወደ አጼ ዮሐንስ ለመሄድ በራስ አሉላ በኩል ማለፍ አይገባውም። ቀጥተኛ የሆነ አጭር መንገድ ጀነራል ሳሌታ ሊጠቁም ይችላል ብሎ ሀሳብ አቅርቦ ነበር። ይህ የጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ተቃውሞ ምን ያህል ጥላቻ በራስ አሉላ ላይ እንደነበረ ያሣያል። ጣሊያኖች ከልባቸው የእንግሊዝ የሽምጋ ይነት ሚናም እንደማይፈልጉት ያሳያል። ዕቅዱም እንዳይሳካ ፍላጎታቸው መሆኑን ያሳያል። ሎርድ ሳሊስቡሪ ግን መመሪያ እኔ ራሴ ለሎርድ ፖርታል እሰጠዋለሁ በማለት[3] በእጭሩ ዘጋው[4] ኦክቶበር 29/1887 ዓ.ም. ሰር ፖርታል ምፅዋ ደረሰ። በእንግሊዝ መንግሥት በኩል ማጣራት ከሚፈልጓቸው ነገሮች 1ኛ. ሰሐቲ እና ዊዓ ለጣሊያኖች፣ ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ የዐይለት ሜዳ ገለልተኛ እንዲሆኑ አጼ ዮሐንስ እንዲስማሙ ለማድረግ ከተቻለ በጕስም የኢጣሊያ እንዲሆን አጼ ዮሐንስ ከተስማማ በኢጣሊያ በኩል ሌላ የኢትዮጵያ መሬት ለመያዝ እንዳትመኙ ቃል ትገቡ እንደሆን ተብሎ ቢጠየቁ ጣሊያኖች አጥጋቢ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል። በመቀጠልም ሎርድ ሳሊስቡሪ ራስ አሉላ በጣሊያኖች ላይ እልቂት በመፈፀሙ አጼ ዮሐንስ ለኢጣሊያ መንግሥት ማዙን እንዲገልፅ ማድረግም ይቻል ይሆናል። አጼ ዮሐንስ ከዚህ በላይ ከተጠየቀ ግን ጦርነት ይመ ርጥ ይሆናል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. XC

2 Vico Mantegazza: Ibd p.XC

3 Vico Mantegazza: Ibd p.XCI

4 Vico Mantegazza: Ibd p.XCIII-IV



እርግጥ ውጥረቱ በጦርነት ይፈታል ከተባለ ኢጣሊያ ያለ ጥርጥር ድል ትቀዳጃለች። ነገር ግን የምትከፍለው መስዋእትነት በጣም ከባድ ይሆናል። በዚህ ቀን ኦክቶበር 29/1887 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ለመኖር በኢጣሊያ መንግሥት ቅድመ ሁኔታዎች ሆነው የቀረቡት፣ 1ኛ. ንጉሡ አጼ ዮሐንስ[1] ባለፈው ጊዜ በተደረገው ጥቃት ማዙን እንዲገልጽ 2ኛ. ዊዓ እና ሰሐቲ የኢጣሊያ እንዲሆኑ ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ እንድትሆን ሀይለት ሜዳ የኢጣሊያ እንድትሆን ቢያንስ በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት እንድትሆን ወሰኑ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ በመሆን እንዲወሰን። 3ኛ. ንጉሡ /አጼ ዮሐንስ/ ኢጣሊያ የሀባብና ዐሳውርታ ጎሣዎች የበላይ ጠባቂ መሆንዋን እንዲቀበል። 4ኛ. ኢጣሊያ ከብሪታንያ ጋራ ተስማምታ ሰንሀይት እንድትይዝ። 5ኛ. የወዳጅነትና የንግድ ውል በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል እንዲደረግ። ኖቬምበር 9/1887 ዓ.ም. ፖርታል አሥመራ ገብቶ ከራስ አሉላ ጋር ተገናኝተዋል፡ በጉዞ ተደስቷል፣ ራስ አሉላ ጥሩ አቀባበል አድርጎለታል፣ ነገር ግን ራስ አሉላ ሰር ፖርታል ጉዞውን እንዳይቀጥል ከልክሎታል፣ ፖርታልም ተቃውሞ አሰማ፡ ራስ አሉላ ግን አልተቀበለውም። ሆኖም ሶስት ፈጣን ፈረሰኞች ወደ ንጉሡ የሚገኙበት ቦታ ተልከው ትእዛዝ እንዲሰጠው ጠይቋል። በ15 ፖርታል አሥመራ ነበር፣ መታሰር ግን አልታሰረም።

ኖቬምበር 19/1887ዓ.ም ፖርታል በ50 የራስ አሉላ ወታደሮች ታጅቦ ወደ ዓድዋ አጼ ዮሐንስ ወደ አለበት አምርቷል። ፖርታል ከአሻንጌ ሐይቅ አጠገብ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተገናኝቷል።[2] ለጣሊያኖች አሳልፎ መሬት ለመሥጠት ጉዳይ ግን አጼ ዮሐንስ በሙሉ ውድቅ ነው ያደረገበት።

ትንሽ ተስፋ ጭላንጭል የተሰጠው በእስላሞች ደርቡሾች ላይ ከመዝመት ፈንታ ከክርስቲያኖች ጣሊያኖች መዋጋቱ የሚያሳዝነው መሆኑን ገልጸውለታል። ከአድሚራል ሒወት ያደረጉት ውል በጣሊያኖች ተጥሷል ብሏል። በወቅቱም የምፅዋ ወደብ የኢትዮጵያ እንደሆነች ድምፅ አሰምቶ ለጊዜው ብቻ ነበር በግብፅ እጅ እንድትቆይ የተስማማ።

ስለሆነም አጼ ዮሐንስ አንድ ስንዝር መሬት ለጣሊያኖች ከሚሰጥና የሀ ጉሩ ዳር ድንበር ለድርድር ከሚያቀርብ ጦርነት የሚመርጥ መሆኑን በድል አድራጊነትም እንደሚወጣ እርግጠኛ መሆኑን ለሰር ፖርታል ገልፀውታል።[3] ዲሴምበር 26/1887 ዓ.ም ሰር ፖርታል የአጼ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ምጽዋ ተመለሰ። ቢፖርታል አስተ ያየት አጼ ዮሐንስ በጦርነት አቋም መያዙ ብዙ ምክንያቶች አሉ። 1ኛ. ራስ አሉላ የሰጠው የተሳሳቱ መረጃዎች 2ኛ. ብዙ ጦር ሰብስቦና ከሌሎች ሹማምንቶቹ ተመካክሮ ጦርነት ለማድረግ በመወሰኑ 3ኛ. ከዚህ በላይ ራስ አሉላ እንግሊዝና ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለመክፈት ቅንበር እንዳላቸው የሚል ወሬ አሰራጭቶ ስለነበረ።

1. Vico Mantegazza: Ibd p.XCIV-XCV

2. Vico Mantegazza: Ibd p.CVI-CVII

3. Vico Mantegazza: Ibd p.CVII

አጼ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፈው ደብዳቤ ጦርነት እንደማይፈልግ ነገር ግን ከምፅዋና ከምንዝሩ በቀር ሌላ አንድ ክንድ የኢትዮጵያ መሬት ኢጣሊያ አለፋ እንድትቆጣጠር የማይፈቅድ መሆኑንና ጦርነት ቢነሳም እንግሊዝ ከኢጣሊያ ጎን እንደማትሰለፍ ያለውን ተስፋ ገልፀዋል። በሰር ፓርታል አስተያየት ይህ ሁሉ የአጼ ዮሐንስ እጅም በራስ አሉላ ወሬ በመመራቱ ነው። ራስ አሉላ በደምብ አልተቀበሉኝም፤ አሥመራ ላይ ለአሥር ቀን እንደ እሥረኛ ያዙኝ፤ ንጉሡ አስቀድሞ ከራስ አሉላ የተላከ መልእክት ከእኔ ጋር ከመነጋገሩ አንድ ቀን በፊት ባይደርሰው ኖሮ ያቀረብኩለት አንዳንድ ትድመ ውጤታዎችን ይቀበል ነበር። በዚሁ መልእክት ራስ አሉላ ኢጣሊያኖች ወደ ሰሐቲ እየመሩ መምጣቸውን ገልፀውለታል። ከዚህ በኋላ ነው ንጉሡ ስለ እኔ ተልእኮ ጥርጣሬ ያደረበት። ሆኖም እኔ የእንግሊዝ ወዳጅነትና ገለልተኛነት ለማስረዳት ችያለሁ። ከሁለት ወር በፊት ተልእኬ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ሌላ ይሆን ነበር።

## 2. የፓርታል ወደ ምፅዋ መመለስ የአጼ ዮሐንስ እምቢዮች

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የአጼ ዮሐንስ እምቢታዎች ለሎርድ ፓርታል ያሰማው በአንድ ቦታ ተቀምጠው በማከጋር ወይንም በጽሁፍ በአንዱ ደብዳቤ አይደለም። ሰር ፓርታል የሰጣቸው ብዙ አስተያየቶች የራሱ ግምገማ ናቸው። አጼ ዮሐንስ እምቢ ለሀገሬ ስንዝር መሬት አሳልፌ ለጣሊያኖች አልሰጥም ብሎ ሐሳቡን የገለፀው በልዩ ልዩ መንገድ ነው።

ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማንቴጋትሳ ዲሴምበር 30/1887 ዓ.ም ባወጣው እትመ ከእንግሊዝ መልእክተኞች አካባቢ ያገኘሁት ነው ብሎ ያወጣው ዜና በሚከተለው ዓይነት ይገልፀዋል።[1] 1ኛ. በሎርድ ፓርታልና በቢቼስ የሚመራ የእንግሊዝ መልእክተኞች አጼ ዮሐንስ የተቀበላቸው በቀዝቃዛ አቀባበል ነበር። ይኸውም አንደኛ እምቢ ሆነ። 2ኛ. አጼ ዮሐንስ መልእክተኞችን ተቀብሉ ሳያነጋግራቸው ሶስት ቀን ደጅ እንዲጠኑ አደረጋቸው። ይኸውም ሁለተኛ እምቢ ሆነ። 3ኛ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀበላቸው የንግስት ቪክቶሪያ ደብዳቤ የተቀበሉበት ቀን በጣም ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው ያነጋገራቸው። 4ኛ. ንጉሡ ምንም መልስ ሳይሰጥ አሰናበታቸው። 5ኛ. በማግስቱ ጧት አጼ ዮሐንስ ስለ እንግሊዞቹ ሳይጨነቅ ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ። እንግሊዞቹም ተከተሉት። 6ኛ. ለብዙ ቀናት በጉዞ አብረው ቢቆዩም እንግሊዞቹም ወደ ምፅዋ ለመመለስ እንደሚፈልጉና መልስ እንዲሰጧቸው ቢጠይቁም ንጉሡ መልስ ሳይሰጣቸው ዘጋቸው። በአሥራ ሁለተኛው ቀን ብቻ ለአጭር ጊዜ ተቀብሉ ካነጋገራቸው በኋላ አንድ ገፅ ደብዳቤ ለንግሥት ቪክቶሪያ የሚሰጥባቸው እንዲያደርሱት አስጠነቀቃቸው። 7ኛ. ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደላቸው።

1 Vico Mantegazza: ibd p.78



ነገር ግን በሌላ ጊዜ እንደሚደረገው እጅብ ማይሰጣቸው የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎቻቸውን በመመስገን አንድ የመንገድ መሪ ብቻ ሰጣቸው። 8ኛ. በመጀመሪያ ቀን ከንጉሡ የተመለሱ ጉዞ ሲያከናውኑ ሎርድ ፓርታል ዕረፍት ሳያደርግ ጉዞውን ለመቀጠል ፈልጎ ነበር፤ የአካባቢው ሀገረ ገዢ ግን ተቃወመው፤ ፓርታል በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብ ሀገረ ገዢው የወታደሮችን ጠባቂዎች ወደ እንግሊዞች በመደቀን በኃይል በመጠቀም ለማስፈራራት ጉድ ሆነበት ነበር። እንደገና ከንጉሡ ትእዛዝ ተቀብለው ነው ጉዞአቸውን ሊቀጥሉ የቻሉ። 9ኛ. የአጼ ዮሐንስ እምቢ ግለት ምልክት የነበረው ለእንግሊዝ መልእክተኞችም ሆነ ለንግሥት ቪክቶሪያ ስጦታ አለማበርከቱ ነበር።

አጼ ዮሐንስ የሀገሩን መሬት ቆርሰው ለጣሊያን ለመስጠት እምቢ ማለት በሌላ ወቅትም ገልጧል በኢጣሊያና በአጼ ዮሐንስ የተፈጠረው ውጥረት ለማርገብ በንጉሥ ምኒልክና ከታወቀው ወረ ኢትዮጵያ የነበሩት እጅም የነበረው አንቶኔሊ ምክር[1] ንጉሥ ምኒልክ በሽምጋይነት እንዲቀርብ ሀሳብ ቀርቦ ስለነበረ በኢጣሊያ በኩል እንግሊዝ በገና የገኙበት ስለሆነ የሸዋ ንጉሥ ሽምጋይነት አስፈላጊ አይደለም የሚል አቋማዊ የነበረው ሲሆን አንቶኔሊ ፌብሩዋሪ 20 1888 እንደጻፈው ምኒልክ በእንግሊዝ ሽምጋይነት ብቻ ዕርቅ እንዲሆን ስጋት ነበረው ምክንያቱም ከዕርቁ በኋላ አጼ ዮሐንስ[2] የሚዘምተው በምኒልክ ላይ ይሆናል ብሎ በመስጋት ነው። አጼ ዮሐንስም ለሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ኅዳር 12 ቀን 1880 ዓ.ም /ኖቬምበር 21/1887 ዓ.ም/ በጻፈው ደብዳቤ «የእንግሊዝ መንግሥት ለኔ ግታ ሳታውቅ ምፅዋን ለምን ለኢጣሊያ መንግሥት እንደሰጠ አይገባኝም። ከእንግሊዝና ከግብፅ ጋር ያደረግነውን ውል በማፍረስ ጣልያኖች ለእኔ ዜጎች ጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈል ጀመሩ፤ በዚህ ምክንያት ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖች ጋር ሰላም እንዲፈርስ አደረገ፤ እኔ ግን ለራስ አሉላ የፈጸመውን ድርጊት እንዲፈፅም ትእዛዝ አልሰጠሁትም። ዛሬ ሁለቱ የጦር መሪዎቻችን ፊት ለፊት ቀርበው በሚገኙበት ጊዜ ሰላም ለማድረግ የሚቻል ከሆነ እኔ ወደ አንድ ስምምነት ለመድረስ ዝግጁ ነኝ»፤ ብሎ ነበር።[3] ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈው በሌላ ደብዳቤም ደግሞ እንዲህ በማለት ነበር የደመደመው።

«የግርማዊነትዎ ፍላጎት በእኛና በኢጣሊያኖች መሀል ሰላም ለመፍጠር ከሆነ ይህ ሊሆን የሚችለው እነሱ ሀገራቸው ላይ ሲሆኑ እኛም በሀገራችን ስንሆን ብቻ ነው፤ ነገር ግን ዛሬ በሁለቱ ወገኖች ፈረሶች የተጫኑ ስለሆነ ጉራዴዎችም የተመዘዙ በመሆናቸው የኔ ወታደሮች እንደ አሸዋ ብዙ ናቸው፤ ጠመንጃቸውን ይዘው ለጦርነት ዝግጁ ናቸው። ኢጣሊያኖች ጦርነት ይፈልጋሉ። ነገር ግን ኃይል በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነው። የሚፈልጉትን ያድርጉ፤ እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ እነሱን ፈርቼ በአንድ ጉድጓድ አልደበቅም»።

1 Vico Mantegazza: ibd p.CI

2 Vico Mantegazza: ibd p.CVIII

3 Vico Mantegazza: ibd p.CXII

# 3. አጼ ዮሐንስና ሠራዊቱ በዐይለት

አጼ ዮሐንስ ከነበረበት ከመሎ ተነስቶ ሠራዊቱን መርቶ ከምፅዋ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር የሚርቀው ዐይለት እንደደረሰ ከዚሁ መንደር አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ወደሚገኘው በሰሐቲ ሰፍር ለነበረው ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ሶስት ጊዜ ደብዳቤ ጽፏል።

በመጀመሪያ ደብዳቤው ከዐይለት ጦር ሠፈሩ ማርች 26/1888 ዓ.ም ለፋ ያለ ሲሆን ቁም ነገሩ[1] እኔና እናንተ ያልሰለጠኑ ሕዝቦችን አንድ ላይ ሆነን እንድንዋጋቸው ፍላጐቴ ነበር። አንድ አካል ሆነን ተዋግተን እናሸንፍ ነበር። እንግሊዞች ከግብጾች ጋር ያዋዋሉን ውል እናንተ አላከበራችሁም። በውሉ መሠረት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ምፅዋ ላይ የጉምሩክ ቀረጥ መክፈል አይገባቸውም ነበር። በኢትዮጵያ ነገሥታት ሥር የነበሩ በኋላ ግን ግብጾች ይዟቸው የነበሩ መሬቶች በሙሉ ወደ እኔ እንዲመለሱ። ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ሀገር ናት። ስለዚህ ሀገሬን ለቃችሁ ሂዱ፤ እናንተም በራሳችሁ ሀገር ሁኑ። እግዚአብሔር ኃይል ከሰጠኝ እናንተ በአንድ በኩል እኔም በሌላ በኩል በአንድ ላይ ሆነን ያልሰለጠኑት ደርቡሾችን መዋጋት እንችላለን፤ ግዛታችንን በማስፋፋት እናወድማቸዋለን፤ ይህ የተሻለ ነበር፤ እኔ እንደ እናንተ ክርስቲያን ነኝ፤ ወንድማማች ነን፤ የእኛ ያለመግባባት ሌሎች እንዲስቁብን ብቻ ነው የሚጠቅመው። ራስ አሉላ ለእኔ ምንም ሣይፅፍ ያደረገውን አደረገ። እናንተም አልፃፋችሁልኝም፤ የተፈፀመው የሴይጣን ሥራ ነው።

እናንተ ናችሁ ወደ እኔ ሀገር መጥታችሁ የምትወጉኝ፤ እኔ አይደለሁም ወደ እናንት ሀገር የሄድኩኝ። እናንተን ለመዋጋት ወደ ሀገራችሁ አልመጣሁም፤ እኔ የመጣሁት ሀገርህ ተወሯል ስላሉኝ ወሰኖቼን ለመጠበቅ ነው። ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ። ሁላችን በየሀገራችን እንቀመጥ። ሁለተኛ ደብዳቤ የተፃፈው መልስ ስለዘገየበት ማርች 30/1888 ዓ.ም መጋቢት 22 ቀን 1880 ዓ.ም ነበር። በዚሁ ዕለት የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ በሰሐቲ ጦር ሰፈሩ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ከምፅዋ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ከዐይለት የሚከተለው መልስ ለአጼ ዮሐንስ ተሰጠ። «ግርማዊነትዎ ሰላም እንደሚፈልጉና የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ገልፀውልኛል። የእኔ ንጉሥም የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ፍላጐቱ ነው። በሁለ ታችን ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ ግን የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። 1ኛ. ኢጣሊያ የፀሓውርታና የሀባብ ጉሣዎች የበላይ ጠባቂ መሆንዋን ኢትዮጵያ እንድትቀበል 2ኛ. ሰሐቲና ዊዓ እስከ ባህር ጠረፍ የኢጣሊያ መሬቶች መሆናቸውን ኢትዮጵያ እምና እንድትቀበል፤ 3ኛ. ከሰሐቲ ወደፊትም የአንድ ቀን የእግር መንገድ የኢጣሊያ መሬቶች እንዲሆኑ ኢትዮጵያ እንድትቀበል። 4ኛ. ጊንዳዕ የኢትዮጵያ ትሆ ናለች። ዐይለት ከነሸለቆዎቿ ለኢጣሊያ እንዲሆኑ፤ ወሰኑ በሁለቱ ሀገሮች ምልክት ይደረጋል። ግርማዊነትዎ በዚሁ የሚስማሙ ከሆነ ወደ ጦር ሠፈሬ ወደ ሰሐቲ የሚያምኑትን ሰው ይላኩልኝ የሚል ነበር።

1 Vico Mantegazza: ibd p.CXVII



የአጼ ዮሐንስ ሶስተኛ ደብዳቤ አጠር ያለ ነው። «የእናንተ ሀገር ከባህር ሮማ ድረስ ነው። የእኔ ደግሞ ከባሕር ወዲህ እስከ እዚሁ ወደ ኢትዮጵያ በኩል ነው። እሚያጣላን ነገር የለም። አያቶቼ ነገሥታት ይገዙት የነበረ መሬት እንዴት አድርጌ ጽፌ ማህተም አድርጌ ለእናንተ እሰጣለሁ? ክርስቶስ ነው ለኔ የሰጠኝ። የክርስቲያን ደም የሚፈስበት ቦታ የት እንገናኛለን፤ እኔ የምገኘው አንድ ቦታ እናንተም የምትገኙ በሌላ ቦታ ነው። የሚያገናኘን ነገር የለም። ከእንግዲህ የእኔ መልእክተኛ ወደ እናንተ አይሄድም። የእናንተም ወደእኔ እንዳ ይመጣ» የተፃፈው መጋቢት 23/1880 ዓ.ም። የአጼ ዮሐንስ አቋም ግልፅ ነው፤ የሚያኮራን ነው፤ የሚደነቅ፤ በማያወላውል ሁኔታ በኢትዮጵያ መሬ ት ላይ ድርድር አላደርግም ብሏል፤ አንድ ክንድ መሬት አልሰጥም ማለቱ በታሪክ ለዘለዓለም ሊያስመሰግነው የሚኖር ነበር።

ጊዜው በኢትዮጵያ ታሪክ ወሳኝ ወቅት ነበር። የፓርታል ተልእኮ ለምን ከሸፈ ብለን በምናስብበት ጊዜ ብዙ አስተያየቶች ሊሰጡ ይችላሉ። ግብጾችና ቱርኮች ሽንፈት ሊደርስ ባቸው ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምረው ነው ምፅዋንና ቀይ ባህር ወደቦችን የያዙ። ነገር ግን ወደቦቹን ብቻ በመያዝ እስከ ተወሰኑ ድረስ ኢትዮጵያ ከወደቦች ለቀው እንዲወጡላት ለማድረግ በቂ ኃይል ስላልነበራት ልታባርራቸው አልቻለችም። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ በሰላም ይኖሩ ነበር። አልፎ አልፎም ወደ ደጋው ክፍል የኢትዮጵያ መሬትን ለመያዝ ዘል ቀው ገብተው በተገኙ ጊዜ ሁሉ ሽንፈት ተከናንበው ነው ወደ ሰፈራቸው ይመለሱ የነበረ። ጣሊያኖች ግን አመጣጣቸው መላው ኢትዮጵ ያን ለመያዝ ስለነበረ እንደ ግብጾችና ቱርኮች መሆን አልፈለጉም። ይህ የጣሊያኖች የነበራቸው ጽኑ የመሬት መስፋፋት ዓላማ የፓርታል ተልእኮ ሊሳካ ያልቻለበት ዋና ምክንያት ነው። ጣልያኖች የእንግሊዝን ሽምጋ ይነት ይፈልጉ ይመስሉ የነበሩ ጊዜ ለመውሰድ ብቻ ነበረ ለማለት ይቻላል። በሁለተኛ ደረጃም ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ በይፋ ጦርነት በማወጃቸው ነው። ሰር ፓርታልም ጣሊያኖች ይህን አዋጅ እንዲሽሩ ለማድረግ አልሞከረም። በኢትዮጵያ በኩልስ ተልእኮው እንዳይሳካ ምን ጉድለት ተገኘ ለሚለው ጥያቄ ጥፋታቸው ሉርድ ፓታልን አስታራቂ ሣይሆን እንደ ጠላት ከኢ ጣሊያ ጉን የተሰለፈ አድርገው መገመታቸው ነው። የአሰብ ኢጣሊያዊ አስተዳዳሪ የነበረው ሊዋር ሊሞኒ ለኢጣሊያ የጦር ሚኒስትር[1] ጀነዋሪ 4/1888 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የአጼ ዮሐንስ ቃል ነው ብሎ ጠቅሶ ያስተላለፈው ፅሁፍ ማንበብ ይበቃል። አጼ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ሀሳባቸውን ገልጠዋል። «ለእኔ የመጡብኝ ችግሮች ሁሉ ከእንግሊዞች የመጡብኝ ናቸው። እነሱ ውል ለማድረግ ወደ ሀገሬ መጡ ነገር ግን እንደ አንድ ልጅ ነው የተጫወቱብኝ። ዛሬ ከነሱ ጋር ሰላም ነኝ። ነገር ግን በእነሱ እምነት የለኝም። ምን ዓይነት ሀሳብ ይዘው እንደሚቀርቡ ማየት እፈልጋለሁ። ሀሳባቸው ጥሩ ከሆነ እቀበለዋለሁ። ሆኖም ሌሎች አስታራቂዎች ቢሆኑ እመርጣለሁ። ዕቅዳቸው የሚጐዳኝ ከሆነ እታወጣለሁ። እንደ ሩሲያ ወይንም እንደ ፈረንሣይ ያሉ ሀገሮች ሽምጋዮች መጠቀም ይገባኝ ነ በር፤

1 Vico Mantegazza: ibd p.CXI-III

ነገር ግን ከመጀመሪያዋ ሀገር ጋር የጠበቀ ወዳጅነት የለኝም። በፈረንሳይም እምነት የለኝም። ምክንያቱም ንጉሥ የላቸውም። ምንሊክ ሽምጋይ ለመሆን ሁኔታ ካለው በእንግሊዞች በኩል ስለተቻለ እሱ ይገፉበት፤ ካልቻለ እውነት ጦርነት ማድረግ ያስፈልጋል። በጦርነትም ምንም ተቅም እንደማይገኝ እምኖሬ አውቃለሁ። የሚል ነበረ። ስለሁለቱ ሀገሮች የኃይል አሰላለፍ ሚዛን ሰር ፓርታል ከኢትዮጵያ ሲመለስ ያደረገው ሪፖርት መጥቀስ ይበቃል።[1] ሰር ፓርታል እንደ ዮሐንስን ያገኘው ወሎ እሸንጌ ሐይቅ በሆንም ዋና ከተማዋ ግን ጉንደር ደብረ ታቦር /ማምሬ/ ናት ብሏል። ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጣ ጦር ዝግጅቱን አጠናቅቆ ከኢጣሊያ ጋር ጦርነት ለመግጠም ወደ ምፅዋ በመጓዝ ተንቀሳቅሶ እንደነበረ አግኝቼዋለሁ ብሏል። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት የሰው ኃይል ብዛት ከፍ ያለ መሆኑን ገልጿል።

1. የራስ አሉላ ጦር 16,000 ወታደር
2. የራስ ሐጐስ ጦር 20,000 ወታደር
3. የንጉሡ ነገሥት ልዩ ዘብ 5,000 ወታደር
4. የራስ ሚካኤል የወሎ 25,000 ወታደር
5. ራስ ሀ/ማርያም የንጉሡ የወንድም ልጅ እኔ አላየሁትም እንደ ሰማሁት ግን ከራስ አሉላ ጦር ይበልጣል
6. ደጃዝማች መሸሻ 5,000 ወታደር
7. ራስ አርአያ ሥላሴ የንጉሡ ልጅ 40,000 ወታደር
8. ቀኛዝማች ጉበና የበጌምድር ገዢ
9. ቀኛዝማች ብሩ
10. ደጃዝማች ተሰማ
11. ንጉሥ ተ/ሃይማኖት
12. ንጉሥ ምንሊክ

ስለ ወታደሮችም ሲፅፍ በደንብ የተያዙ ናቸው። የደጋው ተራራው ሀገር ተወላጆች ናቸው፤ በየጊዜው የተኩስ ልምድ ያደርጋሉ።

በተፈጥሮም የመቋቋት ችሎታ አላቸው፤ ብዙ ጊዜ ምግባቸውን የሚያገኙት ከሚያልፉባቸው ቦታዎች ነው። አንዳንዶቹ ግን የራሳቸው ስንቅ አላቸው። ጦሩ የሚዘምትበት የአሥመራ አካባቢ በእርሻ ሀብታም ካለመሆኑም በላይ የራስ አሉላ ጦርና የራስ ስብሀት ጦር በመቀለብ ላይ ስለሆነ ተጨማሪ ጦር አይችልም። ስለዚህ እንደተባለው በአሥመራ አካባቢ ጦሩ በሙሉ በሚሰበሰብበት ጊዜ ንጉሡ ሁለት አማራጮች አለው። 1ኛ. ወይንም ለጥቂት ጊዜ ውስጥ ጦሩ ወደ መሀል አገር መመለስ አለበት። 2ኛ. ወይንም ቶሎ ብሎ ወደ ኢጣሊያ ጦር በመጓዝ ፈጣንና ወሳኝ ጦርነት ማካሄድ ይኖርበታል።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. CXV



ንጉሡ ነገሥት የሁለተኛዋ ምርጫ አለቀደም የመረጠ መሆኑን ተገንዝቧል። ስለዚህ ለጣሊያኖች የሚከብዳቸው ተመጣጣኝ የሰው ኃይል ማሰለፍ ያለቻሉ እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ጦር በሰው ኃይል ከ100,000 በላይ ነው። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት በጉራዕ በጉንደት፣ ከቱርኮች ጋር እንዲሁም በቅርቡ በዶጋሊ ከኢጣሊያኖች ጋር ባደረጋቸው ጦርነቶች በችሎታው ስለሚከራራ በልዩ ሞራሉን አሸንፏል ብሎ የወመተ ሠራዊት ነው። በኢጣሊያ በኩል የኢጣሊያ ጦር በ20,000 ወታደሮች የተጠናከረ ጦር ነበር። ከእነዚህ ውስጥ 3,000 ባሺቡዙክ ናቸው። በተጨማሪም 19,000 መደበኛ ያልሆነ የደበበ ጦር ነበሩ። በሌላ በኩልም ጣሊያኖች ከንጉሥ ምንሊክ እርዳታ እንደሚያገኙ ተስፋ ነበራቸው። የእንግሊዝ መንግሥትም ጣሊያኖች በሁኔቱ ከእኛ ጋር ቆመዋል ብለው ያምኑ ነበር። ኢጣሊያ የጦር መሣሪያ የበላይነት ያላት ብትሆንም በወታደራዊ ብቃት በቀየ የጀግንነት ታሪክ ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ጋር እንደማትወዳደር የታወቀ ነው።

ይህ ሰፊ ዝግጅት ፀተደረገበት የዓድዋ ጦርነትን ሊያስቀር ይችል የነበረ ጦርነት፤ ከዓድዋ ጦርነት የበለጠ ለኢትዮጵያ ዝና ሊያተርፍ ይችል የነበረ ለምን አልተካሄደም? ጦርነቱ ተካሂዶ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በአሸናፊነት ትወጣ እንደነበረ በኢጣሊያ ወታደሮች ሰፍና የነበረ የሞራል ውድቀትና ሽብር የሚጠቁም ነበረ። ኤርትራውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ተገንጥለው በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ቀንበር ወድቀው ኤርትራውያን የሚል ስም ተሰጥቷቸው ተረግጠው ሰብዓዊ መብታቸውን ተገፈው እድገ ዘም ነበር። ዛሬ እንደሚነገረው የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች እየተባሉ ሁለት ሀገሮች አይከፈሉም ነበር። በአጼ ዮሐንስ ትመራ የነበረችው ኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀል የተካሄደው ትግል አጼ ዮሐንስ የክርስትና ሃይማኖት እምነት አክራሪ ተከታይ ሆኖ ግትር አቋም ይዞ በመቆየት ሊቀርብ በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በኩል ግን በረቀቀ ተንኮልና ደባ የተመረኮዘ አቋም ነበራቸው። በስነ ልቦና በኩል ፍልሚያው ተመጣጣኝ አልነበረም። ጣሊያኖ ች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቅኝ ግዛታቸውም ለማድረግ ያልሸረቡት ሴራ አልነበረም። ምንም የህሊና ቅሬታ ሳይሰማቸው 1ኛ. የሀበብ ኢትዮጵያውያን እስላሞች 2ኛ. የሰሜርታ ኢትዮጵያውያን እስላሞች 3ኛ. ከክርስቲያኑ የሸዋ ንጉሥ ምንሊክ የጦር ወዳጅነት መስርተው ነበር። 4ኛ. ከእስላሞቹ የሱዳን መሀዲስቶችም የጦር ወዳጅነት እቅድ አውጥተው ነበር። በሥራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት መርተው ወደ ሀገራቸን ካመጧቸው ከእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖች እንዳይታዩ በመፍራት ብቻ ነው። የእንግሊዝ መንግሥት ከሱዳን መህዲስቶች የከረረ ጦርነት ማካሄዱ የሚታወስ ነው። 5ኛ. ጣሊያኖች ከክርስቲያኑ ንጉሥ ተ/ሃይማኖትም ወዳጅነት ፈጥረው ነበር። 6ኛ. ጣሊያኖች በትግራይ፣ በኤርትራ፣ ሸዋ፣ ከፋ፣ ጅማና ወለጋ ከነበሩ የኢጣሊያ ሚሲዮናውያን ቅርብ ግንኙነት ፈጥረው የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን መሣሪያ ያደረጋቸው ነበር። ካቶሊካውያን የነበሩ የፈረንሳይ ሚሲዮናውያን ግን ዓላማቸውን ስለማያፈፅሙ የአገር ሃይማኖት ብቻ ግድም የአገር ገዳም ማኅበር /ቫቲካን/ ከነበሩ የኢጣሊያ ዜጎች ለይተው እየተቀረጹ ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ አደረጋቸው። እጼ ዮሐንስ የጣሊያኖች እረመኔነት ተረድተ ቢሆን ኖሮ ግን ሱዳኖች እስላሞች ስለሆኑ ቀንደኛ ጠላት፤ ጣሊያኖች

ክርስቲያኖች ስለሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ጠላቶቹ እያደርጋቸውም ነበር። ከሱዳኖች ጋር ተወያይቶ ይህ ከባህር ማዶ የመጣ የጋራ ጠላታችን አንድ ላይ ሆነን እናባርር ባለ ነበር። አጼ ዮሐንስ ከመላው ኢትዮጵያ ተወጣጥቶ ኢጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት ምፅዋ አካባቢ የሰፈረ በእሱ የሚመራ 120, 000 የሰው ብዛት እንዳለው ይገመት የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት ብታት እያለው ደርቡሾችን ለመዋጋት ቅድሚያ በመስጠት ወደ መተማ ፊቱን እንዲያዞር ማድረጉ እንቆቅልሽ ሆኗዋል። ጣልያኖች ይህን ማድረግ በመቻላቸው አጼ ዮሐንስን ያስፈሩ ስለመሰላቸው ከነበራቸው የሞራል ውድቀት ሊያንሰራሩ ችሏል። በጦርነት እንዳሸነፉ መስሎ ታይቷቸዋል። የአጼ ዮሐንስ የክርስትና እክራሪነት ውጤት ነው።

Il falso allarme al forte Margherita.

*Essendo stata segnalata la comparsa di una banda di abissini di pozzi di Tata, furono dal forte Margherita sparati alcuni colpi di cannone, che spazzarono immediatamente la via.*





Re Giovanni

በኢጣሊያ ሰፈር ሽብር ሰፍኖ ነበር

አጼ ዮሐንስ

የአጼ ዮሐንስ ጦር ጓይለት ሲሰፍር በጣሊያኖች ላይ ሰፈኖ የነበረ ፍርሐት



# 4. በኢጣሊያ ሰፍሮ የነበረበው ፍርሐት

የመሸነፍ ጽዋ የማያውቅ በጀግናው አጼ ዮሐንስ የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት በትኩስ መንፈስና ኃይል ወደ ምፅዋ ዘምቶ ጣሊያኖችን ከምፅዋ ለማስወጣት በወኔ መጥቶ ነበረ። የኤውሮጳ ታላላቅ መንግሥታት ሣይቀሩ ሥጋት ላይ ሊጥላቸው የነበረ ለአፍሪካውያን ፀረ ቅኝ አገዛዝ እን ቅስቃሴ አገዛና ማነቃቂያም ሊሆን ይችል የነበረ፣ በጀግንነት ብዙ እማይ መሰገነው በአጼ ምኒሊክ ይመራ የነበረው በዓድዋ ጦርነት ካላየው የጦር ጀብዱ የበለጠ ጣሊያኖችን ለማንበርከክ ዕድል የነበረው ዐይለት ደርሶ ፊቱን ወደ ኋላ ለምን እንዳዞረ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አንድ አንቆቅልሽ ሆኖብናል። በእርግጥ የጠላት እጅ ያለበት ነው። 46 መድፎች አሰልፎ የነበረው የግብጽ ጦር በጉራዕ የደመሰሰ አጼ ዮሐንስ ጣሊያንም ከዚህ የበለጠ ኃይል እንደማይኖረው ስለሚገመት በአሸናፊነት የማይወጣበት ምክንያት አልነበረም። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ እንኳን ጣሊያን በዐድዋ ጦርነት ያስለፈቻቸው 56 መድፎች ብቻ ነበሩ። አጼ ዮሐንስ ለሽንፈት የተዳረገው በጦር ሜዳ ተሸንፎ አይደለም። የተሸነፈው በተደቀነበት ከአጼ ምንሊክና ከጣሊያኖች ጥምር የስለላ መረብ ነው።

አጼ ዮሐንስ በዐይለት የመጨረሻ ደብዳቤው ከአሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት በስሐቲ የኢጣሊያ ጦር ሠፈር ይገኝ ለነበረው ለኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ዋና አዛዥ ከፃፈ በኋላ ጦሩን በሙሉ ወደ ኋላ እንዲመለስ አደረገ። ይህ ውሳኔ ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ አሳዛኝ መራራ ትክክለኛ ያልነበረ ውሣኔ መስሎ ነው የሚታየው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ቀን በየዓመቱ የሀዘን ቀን ተብሎ ታስቦ መዋል ነበረበት። በተለይ የኤርትራ ተወላጆች የሆኑ ሁሉ ለጅ ቦች የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ሰጡን ብለው መውቀስ ይገባቸዋል። በጣሊያኖች ግምት አጼ ዮሐንስ ጦርነት መግጠም ያልፈለገበት ምክንያት፣ 1ኛ. አጼ ዮሐንስ ከጣሊያኖች የበለጠ ደርቡሾችን ስለሚጠላ 2ኛ. ጣሊያኖችን ለማሸነፍ እንደማይችል ስለተረዳ 3ኛ. የምግብ እጥረት ስላጋጠመው ነው በማለት በቴሌግራምም በደብዳቤም ደስታቸውን ወዲያውኑ ከምፅዋ ማሰ ተጋባት ጀመሩ። ነገር ግን ስለ ስንቅ እጥረት አጼ ዮሐንስ አስቀድሞ ያሰበበት ስለሆነ ምክንያት ሊሆን አይችልም። ጣሊያኖችን መፍራትም የማይታሰብ ነው። ራስ አሉላ በዶጋሊ ያረዳቸው ጣሊያኖች አጼ ዮሐንስን ሊያስፈሩ አይችሉም። በኢትዮጵያ በሙሉ በወቅቱ ለሠራዊቱ ወደ ኋላ ፊቱን ማዞር የተሰጠ ምክንያት የለም። በንጉሠ ነገሥቱና በጦሩ መሀል የሀሳብ ልዩነት እንደነበረ የተገኘ ፍንጭ የለም። በሌላ ይኹ ያልሆኑ ታሪክ መፃሕፍት ስናገላብጥ ግን አንዳንድ ፍንጮች ለማግኘት እንችላለን። ስለሆነም በረጋ መንፈስ ሲታይ አጼ ዮሐንስ ከዚህ ውሣኔ የደረሰው የደርቡሾችን አደገኛ ሁኔታ ስለተገነዘበ ሊሆን ይችላል። የጎንደር አቢያተ ክርስቲያናት ይቃጠሉ ነበር፣ ክርስቲያኖች ይታረዱ ነበር። የዚህ ሁሉ ሁኔታ የሕዝቡ ብሶት ከእልቂት እንዲያድናቸው በመማፀን ጥያቄ ከጎንደር ሕዝብ በየቀኑ ይደርሰው እንደነበረ የታወቀ ነው። ለዚህ ይሆናል አጼ ዮሐንስ ደርቡሾችን የመጀመሪያ ጠላቶቹ በማድረግ ወደ ኋላ ለመመለስ የወሰነው። ሠራዊቱ 700–800 ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዞ መጥቶ ከምፅዋ 45 ኪሎ ሜትር ብቻ ርቀት

በዐይለት መፍር ኃይሉና ወኔው ግድተነስ ለመጫወት ዓላማ ግይለግሬ እንዲመለስ ግድረን በሙራዊት የምሬል ወድቀት እንደሚያጋጥም አያጠራጥርም።

ስለሆነም አጼ ዮሐንስ ለዚህ ድርጊቱ እኛ የዛሬ ትውልድ ለንወቅሰው አይገባም። እንዲያ በአጼ ዮሐንስ ጊዜ በአሁኑ በመኖናችን በ21ኛው ክፍለ ምዕተ ዘመን ያለን ያምናን ሱዳን ክርስቲያንና እስላም በሃይማኖት ምክንያት ሊፋጁ ይታያሉ። በሱዳን ብቻ አይደለም፤ ከፓኪስታን እስከ ሞሪታኒያ ያሉት ብዙ እስላም ሀገሮች እንደ ኢራን እስላማዊት ሪፐብሊክ በሚል ስም በሀገራቸው መንግሥት መመሥረት የሚመኙ ተቂቶች አይደሉም። ክርስቲያናዊ ሪፐብሊክ ብሎ በመሰየም መንግሥት ለማቋቋም የሚመኝ ክርስቲያን ሕዝብ ግን በመላው ዓለም የለም። በኢትዮጵያ ታሪክ ለለ አጼ ዮሐንስ ተደጋግሞ የሚወሳው የክርስትና ሃይማኖት ክብክብ ላይ አክራሪ መሆን ነው። አጼ ዮሐንስ በግብፅና በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ላይ በፈፀሙት የማያወላውል ጀግንነት ተገቢ ውለታና ክብር አልተሰጣቸውም። ስለ ኤርትራ መፈጠር በምንጽፍበት ጊዜ አጼ ዮሐንስ በመተማ ባይሞት ኖሮ ኤርትራ የምትባል ሀገር አትፈጠርም ነበር። ወይንም ደግሞ በምትኩ አጼ ምንሊክ ግዛቱን ሌላ ንጉሥ ለምሳሌ አጼ ተ/ጊዮርጊስ ነግሦ ቢሆን ኖሮ ኤርትራ የምትባል የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አትፈጠርም ነበር።

በሀገራችን በምፅዋ አካባቢ ወረው በያዙት መሬት ሆነው ለመለፍ ፍላ ግዛ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጦርነት ለመግጠም ይጠባበቁ የነበሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በዶጋሊ ከባድ ሽንፈት ደርሶባቸው ስለነበረ ከባድ የመንፈስ ጭንቀት እንደነበረባቸው በፅሁፉ ሬጣቸው ጣሊያኖች ሊጽፏቸው የነበሩ ጽሁፎች እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይችላሉ።[1] ይህ ሥዕል ቁ. 1 ፎቶ ኮፒ ኢትዮጵያውያን ግድታቸቸው ኢትዮጵያውያን መጠብን ብሎ እንደ የኢጣሊያ ወታደር ማስጠንቀቂያ በለጠፈበት ጊዜ በአንድ ጦር ሠፈር ተወምደው የነበሩ መድፎች በባዶ ተከተሟቸውን ሲያሳ ያሳያል።[2] ማርች 29/1888 ዓ.ም ትሪብና ለተባለው ጋዜጣ በምፅዋ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ሆኖ የዜና ወኪል ጋዜጠኛ ያቀረበው ጽሁፍ የሶስት ቀናት ሽብር በሚል አርዕስት ማርች 26፣ 27፣ 28 ያየውንና የሰማውን ሲገልፅ የኢጣሊያ ወታደሮች ምን ያህል የእንጎል ሽብር እንደነበረባቸው እንደሚከተለው ገልጿል። «ባለፉት (ጦር ግንባር) ወደ ምፅዋ ተመለስኩ፤ በሁለት ሰዓት ነበር፡ አንድ መልእክተኛ እኔ ዘንድ መጣና ጌታዬ ቶሎ ብለው ወደ ሰፈሩ ይመለሱ። ዛሬ ማታ ወይንም ነገ ጠዋት ንጉሡ ይመጣሉ ብሎ ነገረኝ። እኔ ጦርነት እንደማይከፈት ባምንበትም በመጠርጠር ተገፋፍቼ ወዲያውኑ እመለሳለሁ። ሰፈሩ ለመድረስ ግማሽ መንገድ እንደሄድኩ ከሰፈሩ ጦር አዛዥ የማስጠንቀቂያ ደወል ተሰማ። በተጠንቀቅ ሁኑ ተባልን። እኔ በመሰለኝ ምንም ነገር አላየሁም። ወታደሩ ግን ድምፅ ሰምቻለሁ እያለ ከመናገር አላቋረጠም። በየጦር ሠፈሩም ተኩስ ነበር። ባለሩ ተኩስ ተከፍቶ በኋላ ፍራቻ ሁሉም ሰው መሣሪያ መያዝ ጀመረ።

1 G.Piccini: Guerra d;Africa Compapagna 1888 Parte IV p.225

2 G.Piccini: Guerra d;Africa Compapagna 1888 Parte IV p.258



ወደ ሰፈሬ ደርሰን በመጀመሪያ ያገኘሁትን ወታደር ጠየቅሁት፤ ጦርነቱ ሊጀመር አይቀርም ከሰፈሬ ወጣ ብሎ ያለው የጦር መድፈኛ ክፍል ዘንድ ሄጄ ሻምበሉን አነጋገርኩት፡ እሳቸው እጄን ከጨበጡኝ በኋላ እጠብቅዎት ነበር ታዲያስ ቀኑ ደረሰ ወይ ብዬ ጠየኳት «ዛሬስ አያጠራጥርም ጦርነቱ መጀመሩ ነው አሉኝ። ግን ማስጠንቀቂያ ደወል የሰማችሁ ለምንድነው ብዬ ጠየኩት። እርሳቸውም የሀበሻ ኃይል ክፍሎች ተኩስ ተከፍቶ ስለነበረ ነው አሉኝ። መድፈኞችን ተዘጋጅተውን አየን፤ የመሳት ወታደሮችን ለማየት ምክርን እየሰጡን የባሮች የተፈጠረ ድምጽ ካልሆነ ሌላ ድምጽ አላሰማንም። ሌሊት ደረሰ ሁላችንም በድንኳን ውስጥ ማደሩን በመድፎች ስር ተኝተን አደርን ጧት እዛው ቀስ ቀስ ብዬ። ሠራዊቱ ሁሉ እንቅልፍ ያጣ ነው። እኔም በቀኝ እጄ እርሳስ ይዣለሁ፤ በአገሬ ጠቅላይ ተቀምጬ አለሁ! ሹመት ያገኘሁ ቀያለሁ፡ አንድ ፈረስ ታስሮ ተጭኖ ቆሟል፤ ለአምባሳደሮችና ለማስተባበር ተዘጋጅቻለሁ። ፋት የሚያሳይ መንፈር አካባቢውን ሁሉ በመሰለኝ ምንም የለም፤ መረጃ የምጠብቃቸው ሁሉ የተለያዩ ሀሳቦችን ይሰጡኛል። እብዛኛው ንጉሡ ነገሥቱ ወደ ሰፈራችን እንደደረሰ ይነግሩኛል፤ ከ100,000 ሺህ ወታደር ጋር ሰፍሯል፤ ሌሎች ደግሞ ሌላ ይላሉ። ይህ ሁሉ የት ነው። ሁለት ቀን በፊት ምፅዋ ግዛው የምንገኝ አርቲፊ እንደሚሉት ነጋሪዎች በሙሉ ወደ ምፅዋ ሲጓዙ አይቻለሁ። የበረሮች ጉዞ ነበር ያስገረመኝ፤ እንደዚሁ በበትሩ፡ በገመል ነበር የሚሄዱት፤ መተላለፊያ አልነበረም። በረሮች ከቤታቸው ለቀው መሄድ የማይወዱ ሲሆኑ ግድ አንድ አደጋ በእርግጥ እንዳለ ያስገነዝባል። እንደሚባለው የሚገኘው የስዊዲን ሚሲዮን እንኳን ጣይ ቀር በዶጋሊ ጊዜ ያልተነካ ቢሆንም ለቀው መጥቷል። ይህ ሁሉ፡ ሌላም የነበረ ትርምስም ሐሜቶች እየመጡም ብዙ ያደረሱት ውርርድ እስከ ራሱ ብዙ ተርጓሚ አድርሰውኝ ነበር። ብቻ ግን ደስ ይለኛል። ማርች 27 የሌሊት ወይንም የሁለት ማስጠንቀቂያ ዓይነት ሰማን፤ ማታ ለመተኛት ወደ ድንኳኖቻችን ሄድን፤ እንቅልፋችን ረጅም አልሆነም፤ ሰዓት ሰዓት ሲሆን ና እያሉ በአገሬ ጉተቱኝ፤ ማስጠንቀቂያ ተደውሏል፤ ወታደሮች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል አሉኝ። ግቢያችን እንደው ሊገባን ማወቃት አልነበረ የተኛሁ መሰለኝ። በእርግጥም ከ4–5 ኪሎ ሜትር ርቀት ተኩሶች ይሰሙ ነበር። ለምን ሰዓት ቀጠሉና ቆሙ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ተኩስ ተሰማ፤ ዋና ጦር ሠፈር የተቃጠለ መሰለኝ፤ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወታደሮች ወደ ሠፈራቸው እያፈገፈጉ ሲመለሱ አየን፤ ወዲያም ተኩሱ በመሳት ወታደሮች እንደነበረ ተገነዘብን ጥቂት ጊዜ በኋላ ፈረስ እየጋለቡ ሁለት ሰዎች አንድ [illegible] አንድ መቶ አለቃ ወደ እኛ መጡና ማን ነው ተኩስ የከፈተ ብሎ [illegible] ለምን በቦታቸው የሉም ብሎ ጠየቀ። [illegible] ጋር [illegible] በኋላ ወደ [illegible] ነው ብለው መልስ ሰጡት። «ሰማን ላይ ነበር የተተኮሰው [illegible] እንደሆነ፤ [illegible] ፈረሰኞች ላይ» የሚል መልስ ተሰጠው። እሱም [illegible] ፈረሰኞች የምትሏቸው [illegible] ነበርኩ፤ ቢሆንም ቦታቸውን ለቀው የሸሹት [illegible] ነው፤ እነዚህም ወደ [illegible] ቦታ ተመልሰው ቦታቸውን እንዲይዙ [illegible] ይህ ሁሉ [illegible]

የሀሰት ማስጠንቀቂያ ለማስወገድ ማስጠንቀቂያዎች ለወደፊት ያለመኩንናች ትእዛዝ እንዳይሰጡ ብሎ ለሁሉም ትእዛዝ አስተላለፈ። ከአራት ቀን ወዲህ የምንሰማው ሐበሾች በሁሉ ቦታ እንዳሉ ነው፤ የተገኙበት ቦታ ግን የለም። የማራይታ ተራራ ከሩቅ የሚያማይ መነፅር የሐበሻ ጦር ይታያል አሉኝ። እኔም ማራይታ ተራራ ሄጄ አየሁ። እኔ ግን ያየኋቸው የኢጣሊያ ባሺቡዙክ ናቸው ጠብመንጃቸውን መሬት አስቀምጠው። አራት ኪሎ ሜትር ወደ ሀይሰት የሚወስደው መንገድ ባሺቡዙክ ተዝናንተው የነበሩት የጠላት እንቅስቃሴ እንዳልነበረ ምልክት ነው። እኔ ጠቅላይ አዛዡ እንደሚለው ንጉሡ ዐይለት እንዳሉ አልክድም፤ ጦሩም ኃይለኛ መሆኑን አልክድም፡ እማይገባኝ ግን ይህ ሁሉ አጋነው ማውራት ነው። ሐበሾች ምናልባት ይመጡ ይሆናል ልናያቸው ይሆናል፡ ነገር ግን አሁን የሉም ማይናሩ እንዴት አሉ ለማለት እንገደዳለን። አመመን ብለው ከቦታቸው እማይገኙ ወታደሮች እየጨመረ ነው። ለምሣሌ ከ240 ፈረሰኛ ወታደሮች አሁን እቦታቸው የሚገኙት 37 ብቻ ናቸው።

ማርች 8 የእጼ ዮሐንስ ጦር በጉራዕ ግብጾችን ያሸነፈበት ቀን ዋዜማ ነበር። ይህንን ያስታውሱ የነበሩ ጣሊያኖች ቀኑ እንደ ጥንቆላ የሚቀናን ቀን ነው ብለው ሐበሾች ጦርነት የሚከፍቱብን ቀን ሊሆን ይችላል ብለው ፈርተው ስለነበረ እንደ አጋጣሚ አነስተኛ ተኩስ ሲሰማ ሐበሾች ወረሩን ብለው ተሸብረው የዋሉ መሆኑን ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማንቴጋትዛ በዚሁ ዕለት ባስተላለፈው ዜና ጣሊያኖች በሽብርና በፍርሃት እንደነበሩ ያስረዳል። የማስጠንቀቂያ ተኩስ ለመጀመር የተተኮሰው ከአንድ ኢጣሊያ ጦር ሰፈር ነበር። ሽብሩ ከሰሐቲ ጀምሮ እስከ ምፅዋ ተዛመተ። በሰሐቲ ወታደሮች ወደ ሰፈራቸው ገብተው ቦታቸውን ያዙ። በምጽዋ ቀኑ እሁድ ስለነበረ ሰዓቱም 12:00 ሰዓት የመዝናኛ ሰዓት ስለነበረ ወታደሮቹ ወደ ከተማ የሚወጡበት ሰዓት ነበር። ወታደሮቹም፡ ባህር ኃይሉቹም በከተማዋ ተበታትነው ነበር። በዚሁ ጊዜ የማስጠንቀቂያ ምልክት በተሰማ ጊዜ በየቦታው ወታደሮቹ ሲሮጡ ይታዩ ነበር። የታየው አንድ አስጨናቂ ትርኢት ነበር። ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ሁሉም ሂሣብ ማይከፍሉ በለሄዱ ከስረዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ጦር ማይዋጋ ይመለሳል ተብሎ እይገመትም ነበር።

የባቡር ሀዲድ መንገድ ያፈራርሳሉ የሚል ስጋትም ነበረን፤ ነገር ግን ይህ የጥቂት ወንበዴዎች ሥራ እንጂ ብዛት ያለው ጦር ለዚህ ዓላማ እንደማይነሳ ተገነዘብን። ሰኞ ማታ ስንተኛ ማክሰኞ እንወረራለን የሚል እምነት ነበረን፤ በዚሁ እምነት ብዙዎቹ ማይተኙ ነበር ያደሩ። የታይምስ ጋዜጣ የዜና ወኪልም ከእኛ ጋር ነበር፤ ከለሊቱ 6:00 ተኛን፤ ነገር ግን ወዲያውኑ ማስጠንቀቂያዎች ቀሰቀሱን። ማክሰኞ ብዙ አዲስ ነገር አልታየም። ምግባችንን መብላት ስንጀምር ግን አዲስ ማስጠንቀቂያዎች ተሰሙ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ ቀናች አለፉ። አንድ ቀን ግን ሁለት ቡቴቴ ልብስ የለበሱ ሐበሾች ከንጉሡ ተልከናል ብለው ወደ እኛ መጡ። የመጡበትም ጉዳይ ንጉሡ ሰላም እንደሚፈልጉ ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ለመንገር ነበር። የጦሩ ዋና አዛዥ ጥያቄው በቃል ሊሆን አይችልም። ንጉሡ ስለ ሠላም መደራደር ከፈለጉ ደብዳቤ መጻፍ እንዳለባት ተነገሯቸው ወደመጡበት ተመለሱ። በአሁኑ



ጊዜ ዋናው የንጉሡ ጦር በዐይለት ሜዳ እንደሰፈረ ታውቋል። ንጉሡ በሕይወቱ ከአሥመራ ገደላ ገደሎች አልፎ የማያውቅ ለሽርሽር እንዳልመጣ ስለሚገመት የእኛ ወታደሮች ቀንና ሌሊት በተጠንቀቅ እንዲሆኑ ተደረገ። ለሶስት ሌሊት በመደዳ አነስተኛ ተኩሶች ሁለቱ ወገኖች ይለዋወጡ ነበር። ደበበ አሁን ከንጉሡ ጋር ስለሆነ ጣሊያኖች ደካሞች ናቸው የወታደር ብዛት የላቸውም እያለ ያሳምናቸው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ ሹማምንቶች ጦርነቱ ቶሎ እንዲጀመር የትዕግስት ማጣት ሁኔታ ነበር። በተለይ ራስ አሉላ ሰላዮችም ወዶገቦችም በአንድ ቃል እንደተናገሩ በራሱ ሀሳብ ጥቃት ለመጀመር አሻፈረኝ ብሎ ነበር።[1] ንጉሡ ግን አልቸኮለም ነበር። በንጉሡ እና በራስ አሉላ ብዙ ስምምነት እንዳልነበረ የሚያስረዳው ከንጉሡ የተላኩ ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ መልእክተኞች ራስ አሉላ በሰበብ እንዳያስቀራቸው ንጉሡ የላካቸው ራስ አሉላ በሰፈረበት ቦታ ሳይሆን ሌላ ራስ በሰፈረበት ነበር። ረቡዕ አንድ ቄስ ወደ ኢጣሊያ ጦር ሰፈር ርቦኝ ነው የመጣሁ ብሎ ገባ። ሐሙስም እንደዚሁ ሌላ ቄስ መጣ። ሰላዮች እንዳይሆኑ ስለተጠረጠሩ እጃቸውን በብረት ታስረው ወደ ምፅዋ ተወሰዱ። ምግብ ተሰጥቷቸዋል። እንደረሀብተኞች ብዙ በሉ። ጥያቄ ተደረገላቸው፡ ከሁለቱ ቄሶች አንዱን አነጋግሬው ነበር።

ስለጣሊያኖች የባቡር ሀዲድ አደነቀ። ስለ ራስ አሉላ ሲጠየቅ ጣሊያኖችን እጠቃለሁ ብሎ መፈለጉ ዕብድ[2] ነው ብሏል። ስለ ደበብ[3] ተጠይቆ ከንጉሡ ጋር መሆኑ ገልጦ ነገር ግን ሹመት እንዳልተሰጠው ተናግሯል። ራስ አሉላ በደበብ እንደሚቀናም ነግሮኛል። አሁን ሌሎች ሁለት የንጉሡ መልእክተኞች ደብዳቤ ይዘው መጥተዋል። በዚሁ ደብዳቤ ንጉሡ ሰላም እንደሚፈልግ ገልጸዋል፤ ሁለተኛም ደብ ዳቤም ጽፈዋል።

የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ከመንግሥቱ ከተመካከረ በኋላ ሰላም ለማድረግ ንጉሡ የማይቀበላቸው ቅድመ ሁኔታዎች በመጠየቅ ለንጉሡ ደብዳቤ ላከለት። ሰኞ ጠዋት ንጉሡ ለኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ እንደገና ደብዳቤ በመጻፍ በሁለቱ መልእክተኞቹ አማካኝነት ለጊዜው የሰላም ውይይት መቀጠል እንደማያስፈልግ ገልጾ ጻፈ፤ በማግስቱ ማክሰኞ ጦርነቱ ይጀመራል ተብሎ ተፈርቶ ነበር፤ ነገር ግን ጠዋት ሐበሾች ሰፈራቸውን ለቀው እንደሄዱ ታወቀ።

የኢጣሊያ ጦር የነበረው ሌላ ችግር የጦር አዛዦች መቀያየር ነው። ከመጀመሪያ የምጽዋ ወረራ ፌብሯሪ 1885 ዓ.ም. እስከ ማርች 30/ 1888ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ተፋጠው በነበሩበት ጊዜ አራት ጀኔራሎች የጦር አዛዦች ተቀያይረዋል። ይህም የአመራር ድክመት የሚያሳይ ነው።

---

1 Vico Mantegazza: ibd p.264

2 Vico Mantegazza: ibd p.266

3 Vico Mantegazza: ibd p.266

ጠቅላይ ሚ/ሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና የጦር ሚኒስትሩም በዶጋሊ ጦርነት ምክንያት ስራቸውን ለቀቁ።

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁኔታ በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በኩል የነበረውን የመረበሽ ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ሁኔታ ለመረዳት(Tribuna) በተሰኘው መጽሔት በወቅቱ ያወጣው አትመው አነስተኛ ምሣሌ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል። መደበኛ ያልሆነ የኢጣሊያኖች ቅጥረኛ ወታደሮች ባሺ-ቡዙክ በኢትዮጵያ በኩል የነበረ በራስ መተማመን ስሜት ከፍተኛ እንደነበረ ለመረዳት አንድ አነስተኛ ምሣሌ የሚሆን አንድ ባሺ-ቡዙክ ቡድን ኃይለት ድረስ በድንገት ዘልቆ ሄዶ መንደሩን ተቆጣጥር አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ምርኮኛ አድርጎ ወደ ጣሊያኖች በቀረበበት ጊዜ በከፍተኛ ኩራት «የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ» ራስ አሉላ መጥቶ ይበቀለናል ብሎ እንደተናገረ ጽፏል።

የዚሁ ምዕራፍ ቁጭቱ ሲገመገም የሰር ፖርል ተልኮ የተሳካ ነበረ ለማለት ይቻላል፣ የሁለቱ ወገኖች ሀሣብ ዲስፁል፣ ተገቢ ትብብር አላገኘም፣ የእንግሊዝ መልእክተኞች በጣሊያኖች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት አትርፈዋል። እንግሊዞች ገና ከካይሮ ሳይነሱ ጣሊያኖች ለራስ አሉላ የሚመጡ መሆናቸውን እንዲነግሩላቸው ቢጠይቋቸው ጣሊያኖች በኢትዮጵያ በኩል ፈርቶን ነው እማላጅ የላከብን እንዳይላቸው ፈርተው፣ ሣይተባበሩዋቸው ቢቀሩም፣ እንግሊዞች ምጽዋ እንደደረሱ ራሳቸው ለራስ አሉላ መልእክተኛ ልከው በአጭር ጊዜ አስረቅደው ጉዞቸውን መጀመር ችለዋል። ይዘውት የመጡት አስተርጓሚያቸው በኃይለኛ በሐይ ቢሞትባቸውም ንብረታቸው ቢሰረቅባቸውም ጉዞአቸውን አቋርጠው ከመንገድ ተመልሰው እንደገና ጉዞቸውን ጀምረው አሥመራ ሊደርሱ ችለዋል። አሥመራ ከደረሱ በኋላ ወደ አጼ ዮሐንስ ያለበት ወዲያውኑ ለመጓዝ ጠይቀው ራስ አሉላ ግን ንጉሠ ነገሥቱን ሳላስፈቅድ አትሄዱም፤ እውነት እንግሊዞች መሆናችሁን አለመሆናችሁን ብሎ ከለከላቸው። ያለ ውዴታቸው አሥመራ ለ15 ቀኖች ቢቆ መጡም አስረኛ ሆንናል ብለው ተቃውሟቸውን ከማሰማት በቀር ወደ ኋላ ለመመለስ ሳያስቡ የተላኩበት ጉዳይ በደህና ለማከናወን በቅቷል።

በኢትዮጵያ በኩል የአጼ ዮሐንስና የራስ አሉላ ጸረ ኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ወረራ በማያመላውል ሁኔታ አቋም በመውሰድ የተንጸባረቀበት ጊዜ ነበረ። (Crispi) ክሪስፒ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ሲመረጥ ኢትዮጵያንና ኢጣሊያን ለማሥታረቅ ብሪታኒያ ተግባሯን የጀመረችበት ወቅት ነበረ። ከክሪስፒ በፊት የነበረው ጠቅላይ ምኒስትር ዲፕሬቲስ (Depretis) ጣሊያኖች በዓላማ የሚመሩ ባለመሆናቸው በኢትዮጵያ ላይ ምን እርምጃ እንደ ምንወስድ አናውቅም በማለት የእንግሊዝ መንግሥት ሽምጋይነት ለመቀበል ፍቃደኛነቱን ለመግለፅ ዝግጁ አልነበረም። ክሪስፒ ግን ለራሱ ዓላማ እንዲጠቀምበት የእንግሊዝ ሽምጋይነት በደስታ ነበረ የተቀበለው።



የእንግሊዝ ሽምጋይነት መነሻ የሆነው አጼ ዮሐንስ የሒወት ተብሎ የሚጠራ ውል አልተከበረም በማለት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት ነበር። ክሪስፒ ብዙ ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ነበረ የእንግሊዝ ሽምጋይነት የተቀበለው።

(Carlo Zaghi) ካርሎ ዛጊ ዲፕሬቲስ ጥፋተኛ አድርጎ ክሪስፒ ትክክለኛ ነው ብሎታል። የእንግሊዝ መንግሥትም ሽምጋይነት መቅረቡ ከልብ የመነጨ ነው ብሎታል። ጦረኛ ከሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ኢጣሊያ እንዳትጋፈጥ በማሰብ ነው ኢትዮጵያውያንም በሱዳን እንግሊዝ ከደርቡሾች የነበራት ውጥረት እገዛ እንዲያደርጉላት አስባ ነው ብሎታል።

ጣሊያኖች ከእኛ ጋራ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደካሞች ናቸው። ከጥንት ጀምሮ አንድነታቸውን ሊመሰርቱ ለዚሁ ያበቋቸው ሀገሮች ባለውለታ መሆን አልቻሉም። ጣሊያኖች ከጥንት ጀምሮ ምንም የማይጠቅሟቸው ከጀርመኖች ጋራ መቀራረብ ነው የሚወዱ። አሁንም ጀርመኖችን ማድነቅ አላቋረጡም። የጀርመኖች ጭራ ተከትለው ከመሄድ የእንግሊዞች ጭራ ተከትለው መሄድ ይበጃቸው ነበረ። የሚወዱት ከሀገራቸው ተሰደው ወደ አዲስ ሀገሮች ለመስፈር ጥቅም ሊያገኙ ይችሉ ነበረ። እንደዚሁም የፈረንሳይ የእስፔን የትንሿ የፖርቱጋል ጭራ ተከትለው ቢጓዙ በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ ለመስፈር ጥቅም ያገኙ ይችሉ ነበር። የኢጣሊያዊው ክሪስፒ በአፍሪካ የቀኝ አገዛዝ ዓላማ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች እንዲሁም ፖርቱጋሎች ከሚያራመዱት ለየት ያለ ነው፣ የሚለይበትም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገሩን ሕዝብ ፈጅተው፣ ጨርሰው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጣሊዮኖችን ለማስፈር ነበር።

እንግሊዞች ጣሊያኖችን የቀይ ባሕር ጠረፎች እንዲቆጣጠሩት የሚገፋፏቸው ዓላማቸው ምን እንደሆነ ሳይገነዘቡ ጣሊያኖች በሱዳን ወታደራዊ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ፈልገው ይሆናል ብለው ጥርጣሬ ነበራቸው። ይህ አባባል ግን እንግሊዞች አስተባብለውታል፤ ሊሆንም የማይችል ነው ምክንያቱም በጦርነቱ ቢካፈሉም ጥቅም መፈለጋቸው አይቀርም ነበር።

## 5. የሸዋ ፖለቲካና የትግራይ ፖለቲካ

እንደሚባለው ሁሉ ራሳቸው ጣሊያኖች ሸዋ የነበራቸውን ከምኒልክ የተሰጣቸው ትንሿ ልዩ ግረፊያ የምትባለው መሬት የመላው ኢትዮጵያ ገዢዎች ለመሆን የረዳቸው መሆኗን ከተለያዩ ደራሲያን የተጻፉ መጽሀፍቶች ያስረዳሉ። ፕሮፌሰር ካፔቶ ኢጣሊያ አሰብን እንዲገዛ በማድረጉ መላው ኢትዮጵያን ለመያዝ በቅተናል አላሉም ወይንም በእንግሊዝ መንግ ሥት ድጋፍ ምጽዋንና ቀይ ባሕር ጠረፎችን በቁጥጥራችን በማድረጋችን መ ላዋን ኢትዮጵያ ለመቆጣጠር በቅተናል አላሉም፤ ወይንም ሌላ ምክንያት አላቀረቡም። የጠላት ወራሪዎች ኢትዮጵያ ላይ ይመጡ የነበሩ በሙሉ በቀይ ባሕር ጠረፎች ነው ተብሎ በተደጋጋሚ የሚነገረው ስህተት መሆኑን እንረዳለን። ሸዋ በንጉሥ ምኒልክ ተባብሮት ከፍተኛ የኢጣሊያ የስለላ ድርጅት ተዘርግቶበት ነበረ፤ ከወታደራዊ ወረራ የበለጠ ተግባር አከናውነዋል። አሰብን በመግዛት ኤርትራን የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት እንድትሆን መሰረት



Re Giovanni




በትግራይ ፖለቲካና በሸዋ ፖለቲካ ዋና ተዋንያን 1.አፄ ዮሐንስ 2. አፄ ምኒልክ 3. ኮንት አንቶኔሊ



የማለ ፕሮፌሰር ጁሰፔ ሳፔቶ አልነበረም ተቀማጭነቱ ሸዋ የነበረው ካርዲናል ማሳያ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እንድታስፋፋ ከሳፔቶ የበለጠ አስተዋጽኦ አድርጓል ቢባል ስህተት አይሆንም። ካርዲናል ማሳያ ከ1846 ዓ.ም. ጀምሮ 35 ዓመት በኢትዮጵያ ተቀምጧል። በአጼ ዮሐንስ ትዕዛዝ ከኢትዮጵያ ከመባረሩ በፊት እስከ 1880 ዓ.ም. የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ አማካሪና ወዳጅ በመምሰል የትግራይና የአጼ ዮሐንስ ቀንደኛ ጠላት የሸዋና የንጉሥ ምኒልክ እውነተኛ ወዳጅ በመሆን ግልጽ አቋም በመውሰድ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሱ እንዲታታሩ ደክሟል። በንጉሥ ምኒልክ ዘንድ በነበረው ተደማጭነት እንደ አንቶኔሊ የመሳሰሉት ብዙ ጣሊያኖች በሸዋ ተቀምጠው ፀረ ኢትዮጵያ ነጻነትና ጸረ ኢትዮጵያ አንድነት ስራቸውን እንደልባቸው እንዲያካሂዱና እንዲያስፋፉ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥቷል። ሸዋ የተቀመጠበት የመጨረሻ ዓመታት ከንጉሥ ምኒልክ ጎን ተቀምጦ የፖለቲካ ስራ ከማከናወን በስተቀር የመንፈሳዊ ስራ ችላ ብለው እንደነበረ ራሱ በጻፈው መጽሐፍ ገልጧል። ካርዲናል ማሳያ ብዙ ጊዜ የሚመራው በሀይማኖት ነው፣ ምኒልክን ካቶሊክ ማድረግ የደብረ ሊባኖስ ገዳማትን ካቶሊክ ማድረግ ይመኝ ነበር። ነገር ግን በሀይማኖት ብቻ አልተወሰነም አጼ ዮሐንስና ንጉሡ ምኒልክ ጦርነት ቢገጥሙ ምኒልክ አሸናፊ እንደሚሆን እምነት ነበረው። በዚሁ የተነሣ ምኒልክ በአጼ ዮሐንስ ላይ ጦርነት እንዲያስነሳ ከማነሳሳት አላረፈም ነበር። በአጼ ዮሐንስ ላይ በአጠቃላይ በትግሬዎች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበረው፣ ለምሳሌ አንድ ትግሬ የአንድ ልጅ ፍቅር ይዞት በካቶሊክ ሀይማኖት ጋብቻ ለመፈጸም ቢጠይቀው ትግሬዎች እንደ ሰይጣን ስለሚታያ ቸው ትግሬ ልብ አለው ወይ ፍቅር ያውቃል ወይ ብሎ ተችቷል። አጼ ዮሐንስ ከኢትዮጵያ ባያባርረው ኖሮ የውጫሌ ውል በኢጣሊያ መንግሥት ስም ከምኒልክ ጋራ ለመዋዋል ከኢጣሊያ መንግሥት የታጨ ካርዲናል ማሳያ ነበረ። ነገር ግን አይቀጨውም አጎቱን ማሣያ ተክቶ አንቶኔሊ ነው የተሾመው የአንቶኔሊ አጐት በዋናው የቫቲካን መንግሥት ካርዲናል ሆኖ ይሠራ የነበረ ነው ስለዚህ ካርዲናል ማሳያ ሲባረር የአንድ ካርዲናል የወንድም ልጅ ነው የተተካ።

ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ ሁለት ዓይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ነበራቸው የሸዋ ፖለቲካና የትግራይ ፖለቲካ። በኢትዮጵያ ግዛታቸውን በማስፋፋት ማለት ሸዋ ያለው ባለሥልጣንን መደገፍ ወይንም ትግራይ ያለው ባለሥልጣንን መደገፍ። ካርዲናል ማሳያ የሸዋ ፖለቲካ ደጋፊና መስራች ነበረ ለማለት ይችላል። ከርሱ ቀጥሎም እነ አንቶኔሊና አንቲኖሪ ወዘተ ነበሩ። በኢትዮጵያ ወገን የሸዋ ፖለቲካ ደጋፊ አጼ ሚኒልክ ብቻ ነበረ። የትግራይ ፖለቲካ ደጋፊዎች የኢጣሊያ የወታደር ክፍል ነበረ። ነገር ግን በመንግሥታቸው በኩል ተሰሚነት አልነበራቸውም። ምክንያቱም 1ኛ. እስከ መጨረሻ ጊዜ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት በሸዋ የፖለቲካ ሙሉ እምነት አሳድሮ ነበረ 2ኛ. ራሣቸውም ቢሆኑ ራስ አሉላና አጼ ዮሐንስን እያስታወሱ ጠንካራ አቋም አልነበራቸውም ትግራይን ብናጠቃር ከሸዋ የባሰ ጠላታችን ሊሆን ይችላል የሚል ፍራቻ ነበራቸው። ሸዋ ግን የበደለችን ነገር የለም። የሸዋና የትግሬ ፖለቲካ የተፈጠረውና የተጠናከረው ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ነው። አጼ ዮሐንስንና ራስ አሉላን ለማውደም የታቀደ ነው። ቂም በቀላ ቸውን ለመወጣት ነው። ሁለቱም እንደ

አንድ ሰይጣን ሆነው ይታይዋቸው ነበረ።[1] ለምሳሌ በአንድ ወቅት አጼ ዮሐንስ የእርም ህዝብ ተበደለ ባሪያ ሆኖ እየተሸጠ ነው ብሎ ሁኔታ በሚያቀርብበት ጊዜ እሱ አንድ ሰይጣን ሆኖ ለእርም ህዝብ ርህሩህ እንዴት ሊሆን ይችላል እያሉ ያፌዙበት ነበረ።

አጼ ምኒልክ ለነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ለመጣን ዓላማ ለማስፈጸም ካርዲናል ማሳያ አባቱ ብሎ እየጠራ በረቀቀ ዘዴና ብልሀት ከተጠቀመበት በኋላ ለአጼ ዮሐንስ አስረክቦ ወደ ሀገሩ እንዲሄድ አድርጎታል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንቶኔሊን እያታለለ ከተጠቀመበት በኋላ በገዴት ከሀገር እንዲወጣ አደረገው።

ኤንሪኮ ቸሩቲ (Enrico Cerruti) የተባለው የጣልያን ዜጋ በ1869 በአዲስ ጊኒ ሶስት ደሴቶች ነገሮች የኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ሞግዚትነት መቀበላቸውን የሚያረጋግጥ ሶስት ኮንትራቶች ይዞ ወደ ሀገሩ መጥቶ የኢጣሊያ መንግሥት ለመረከብ ስላታተው ሳይሳካ ቀርቷል። ጣሊያኖች ኢትዮጵያ እንደ አዲስ ጊኒ ያለምንም ደም መፋሰስ በመጀመሪያ ሸዋን አጼ ዮሐንስ ከሞተ በኋላ መላዋን ኢትዮጵያን ውል በመፈራረም ብቻ በቁጥጥራቸው ለማድረግ (ፕሮቴክቶሬት) ጉጉት ነበራቸው። በኢጣሊያና በሸዋ መካከል በተደረገው የወዳጅነትና የንግድ ውል በአንኮበር ነበር፤ ቀኑም ግንቦት 14 ቀን 1875 ዓ.ም. (ሜይ 21/1883) ነበረ፤ ተዋዋዮችም ንጉሥ ምኒልክና አንቶኔሊ ነበሩ። በሁለቱ መንግሥታት መካከል እንደ ተደረገ ውል ነበረ። ንጉሥ ምኒልክ ከትሮፒካል አፍሪካ ኢጣሊያን ለማወቅ የሚፈልግና ወዳጅነት የሚፈልግ አፍሪካዊ መሪ እየተባለ እየተወደሰ ስም አትርፎ ነበር። ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋራ መገናኘት ሲጀምር የኢጣሊያ ቪክቶሪዮ ኤማኑኤል ዳግማዊ ይባል የነበረው ንጉሥ ስለሞተ በምትኩ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ሲነግሥ ምኒልክ በዚሁ አጋጣሚ ለአዲሱ ንጉሥ ደብዳቤ ሲጽፍ ሟቹ ንጉሥ የመንግሥቱ ጠባቂ ለእኔም እንደ አንድ አባት በማለት ገልጾ ነበር። በሌላ ደብዳቤው ደግሞ «በሟቹ ንጉሥ የነበረውን ወዳጅነት እርስዎ እንደሚቀጥሉ፤ እንደ አጋጣሚ ጠላት በእኛ ላይ አደጋ ለመጣል ቢሞክር እርዳታ እንደሚያደርጉልኝ ተስፋ አለኝ» ብሎ ጽፎ ነበር። በተጨማሪ «የሟቹ ንጉሥ እርስዎ ተከትለው የእኛ ጠባቂ እንደሚሆኑ እተማመናለሁ» ብሎ ነበር። እነዚህ ደብዳቤዎች አሥራ አንድ ዓመት ከውጫሌ ውል በፊት የተፃፉ ለውጫሌ ውል ቅድመ ሁኔታዎች ያዘጋጁ እንደነበሩ ያስረዳሉ። እነዚሁቸው ሸዋን ወይንም መላውን ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ፕሮቴክቶሬት ለማድረግ አስቀድመው እቅድ እንደነበራቸው የሚገልፁ ነበሩ። ጠላት ተብሎ የሚጠራው አጼ ዮሐንስ መሆኑን ግልፅ ነው። እነዚሁ የኢጣሊያ አማካሪዎች አስተባብለው እሚያንፀባርቁ መሆኑን አያጠራጥርም። ስምንት ወር ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ ሁለት ዓመት ከውጫሌ አስቀድሞ ጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም. (ኦክቶበር 20/1887 ዓ.ም.) የወዳጅነትና የኅብረት ውል የሚል ስያሜ ምኒልክና[2] አንቶኔሊ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈራርመዋል።

1.A. Gaibi Manuale die storia Politica delle Colonie Italiane p.09

2.1 Carlo Zaghi: Ibid p.140



በሁለት መንግሥታት የተደረገው ውል ነው የሚመስለው። ይህ ውል በኢጣሊያና በአጼ ዮሐንስ ጦርነት ቢነሣ ምኒልክ ከኢጣሊያ ጎን እንዲሰለፍ የሚያደርግ መሆኑን ታምኖበት ነበር። ቀደም ብሎም የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለፓርላማ ኦክቶበር 11/1887 ዓ.ም. ለአንቶኔሊ በጻፈው ደብዳቤ የሚከተሉት ነጥቦች ከንጉሥ ምኒልክ እንዲጣሩ ጠይቆ ነበር። 1ኛ/ ምኒልክ እኛ በአጼ ዮሐንስ ላይ በምናደርገው ጦርነት በተግባር ለመተባበር ፈቃደኛ እንደሆን 2ኛ/ የዚሁ ትብብር ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል። 3ኛ/ ትብብሩ ተግባራዊ ካልሆነ ከምኒልክ ጦር ጋሻ የአጼ ዮሐንስ ጦር ወረራ በመጠበቅ በደቡብ እንዲቀሩ ለማስገደድ ወይንም ምኒልክ ፍፁም ገለልተኛ እንዲሆንልን ምስትና ማግኘት እንችላለን ወይ የሚሉ ነበር።[1]

አንቶኔሊ ንጉሥ ምኒልክ የኢጣሊያ መንግሥት ታማኝ መሆኑን ለማ ስረዳት ሲያቅተው በንጉሡ ሙሉ በሙሉ እተማመናለሁ ነገር ግን የንጉሡ ጀነራሎችና ሹማምንቶች ብዙዎቹ የሰሜን ተወላጆች ስለሆኑ ጦርነት ቢነሣ ለአጼ ዮሐንስ እንዳያደሉ ያሰጋል ብሎ ጽፎ ነበር። አንቶኔሊ ሰሜን ብሎ የሚጠራው ትግራይ፤ ወሎ፤ ጎንደር፤ ወዘተ... የሚያጠቃልል ነበር።

በተለይ አቴጌ ጣይቱ እንደ ትግሬ ነበር የሚቆጥሩት፤ ከኢጣሊያ መንግሥት ስለ ምኒልክ ታማኝነት ተጨባጭ ነገር እሳባዮም ተብሎ በሚጠየቅበት ጊዜ ያቀርበው የነበረው ምክንያት ንጉሡ ከኢጣሊያ ጋር እንደሚሰለፍ አልጠራጠርም፤ ነገር ግን በትግሬዎችና የሰሜን ሰዎች ስለተከበበ እንደልቡ ለመሆን ነፃነት የለውም የሚል ነበር። ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው እንደ ትራቪርሲ አሉም ጦርነት ቢነሣ አጼ ዮሐንስ 200,000 ወታደር ማሰለፍ ስለሚችል ኢጣሊያ ወደ 50,000 ወታደር ማሰለፍ ያስፈልጋታል ብሎ ያምን ነበር። 10–20,000 ሺህ ወታደር ማሰለፍ ውድቀት ያመጣብናል ብሎ ተምብየው ነበር። በአጼ ዮሐንስ ጦር ላይ እንዲገጥሙ ኢጣሊያ ያሰለፈቻቸው ወታደሮች 19,182 ብቻ ነበሩ። የጦሩ ጥንካሬ የሚለካው ሊያሰለፍ በሚችለው የመድፎች ብዛት ሲሆን ኢጣሊያ አጼ ዮሐንስን ለመግጠም ያሰለፈቻቸው 48 መድፎች ብቻ ነበሩዋት። አጼ ዮሐንስ ከግብጾች ብቻ የማረኳቸው 24 መድፎች ነበሩት። ከእንግሊዞችም የተረከባቸውም ነበሩት፤ ስለዚህ በጦር መሣሪያም ሁለቱ ወገኖች ኃይላቸው ተመጣጣኝ ነበር። አጼ ዮሐንስን እነጋገረው ወደ ምፅዋ የተመለሱ የሉርድ ፖርታል መልእክተኞች እባሉች ለኢጣሊያ ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያን ለመቋቋም በቂ ኃይል እንዳላዘጋጁ ነገሯቸው ነበር። አንቶኔሊ ምኒልክን ከኢጣሊያ ጎን ለማሰለፍ አጋጠመኝ ብሎ የሚያቀርበው የነበረ ሌላ ችግር አጼ ዮሐንስ የቢተክሆነት ሙሉ ድጋፍ አለው፤ ስለዚህ ነው ምኒልክ[2] ፍራቻ የሚያድርበት የሚል ነበር፤ ይኸውም ለምሳሌ ምክንያት ነው። በተረፈ በም ንሊክ የነበረው ተሰሚነት የተነካ አዲስ አበባ ደኖሩ የነበሩ ሌሎች ኤውሮፓውያን ምኒልክ አይደለም ንጉሥ አንቶኔሊ ነው ብለው ሲወቅሱት፤ እሱ ግን ይኮሩበት ነበር፤ በጣሊያን ዜጎች ማይቀር ተወቅሷል አዲስ አበባ

1 Carlo Rossetti: Ibid p.80

2. Carlo Rossetti storia diplomatica dell' Etiopia Durante Menelik II

ይኖሩ የነበሩ ፈረንጆች ነጋዴዎች ስለሆኑ አንድ ንጉሥ ነጋዴዎችን ማበሳጨት ስለማይገባው ምኒሊክ ከፈረንጆቹ ጋራ እንዳይገናኝ አድርጎት ነበር። በተለይ ገንዘብ ከልክ በላይ በመስጠት ከሁሉም ወገን ከራሱ ዜጎች ማይቀር ተወቅሷል። እሱ ግን ኩራት ስለሚሰማው በአዲስ አበባ አነስተኛ ታዋቂነት ያለው ሰው ቢያገኝ አሥር ብር ከእኔ ያላገኘ አይኖርም እያለ ይኮራበት ነበር። አንቶኔሊ ጁላይ 2/1888 ዓ.ም. ከምኒሊክ ጋር ተነጋግሮ ጦርነት ቢነሣ ከኢጣሊያ ጋር ተሰልፌ እዋጋለሁ ብሎ ነግሮኛል ብሎ ሪፖርት ለመንግሥቱ ይልካል። ምንሊክም [1] ጁላይ 6/1888 ዓ.ም. ለኢጣሊያ መንግሥት ሲፅፍ አጼ ዮሐንስ ሀገሬን ለመውረር እየተዘጋጀ ነው እኔ ግን ለመከላከል ዝግጁ ነኝ። አንቶኔሊ 5,000 ጠብመንጃዎች ፈጥነክተን እንደሚላክልኝ ተስፋ ሰጥቶኝ ነበር። እኔ ሀገሬን በምከላከልበት ጊዜ በከንቱ የፈሰሰ የገር ማቺትዎ ዜጎች ደም እበቀላለሁ። አሁን እኔ የምጠይቀው ጠብመንጃዎቹ ከ10,000 እንዳያንሱ ነው። በዚሁ ቀን ምኒሊክ ለጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ደብዳቤ ሲፅፍ «ለኢጣሊያ መንግሥት ኃያልነቴና ወዳጅነቴ የማሳይበት ጊዜ ደርሷል ብሎ ጽፎ ነበር። የኢጣሊያ መንግሥትም ኃያሉና ወዳጅነቱ ለእኔ የሚያሳይበት ጊዜ ደርሷል» ብሎ ጽፎ ነበር። ኦገስት[2] 11/88 ዓ.ም. አንቶኔሊ ረዘም ያለ ሪፖርት ለመንግሥቱ ልኮ ነበር። አንዳንድ ነጥቦችን ለመጥቀስ የሸዋ ተለፋና የሸዋ ዝንባሌ ወደ ኢጣሊያ መሆኑን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ። የእርእያ ሥላሴ ሞት በምኒሊክና በአጼ ዮሐንስ የነበረው የዝምድና ግንኙነት ተቋርጧል። በሁለቱም መካከል የነበረውም መሀላ ተቋርጧል። ምኒሊክ ለአጼ ዮሐንስ ወታደራዊ እርዳታ የመስጠት ግዴታ የለበትም። ይህ ከዛሬ 10 ዓመት በሁለቱ ወገኖች መሐል የተደረገው ስምምነት አልተጠቀሰም። ስለዚህ አጼ ዮሐንስ መጠየቅ የማይገባውን ነገር ነው የጠየቀ። በተጨማሪም አጼ ዮሐንስ በውለታም አያመሰግንም። የወዳጅነት መንፈስም አያሳይም። ስለዚሁ ጉዳይ የገባበት መሀላ ቃል አላከበረም ምኒሊክም ከመሀላ ቃልነፃ ይሆናል። ምኒሊክ በመወራጨትና ባልተለመደ ሁኔታ ቁርጥ ያለ ውሣኔ በመያዙ አዲስ ሰው ሆኖ ነው ያገኘሁት የኢጣሊያ መንግሥት የማይከዳው መሆኑን እኔ ቃል እንድገባለት ጠይቆኛል። ለንጉሡችን የፃፈው ደብዳቤ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ያላቸው ያልተጣጣመ ሁኔታ በመግለፅ ነው። በተደጋጋሚ የጦር መሣሪያ ይጠይቃል። በዶጋሊ የሞቱ ወታደሮችን ራሱ ለመበቀል ይፈልጋል። ምኒልክ እውነት አይናገርም ብዬ ጥርጣሬ የለኝም። በሚቀጥለው ጥቅምት ወይንም ኅዳር አጼ ዮሐንስ ሸዋን እንደሚወር እርግጠኛ ነኝ። በዚሁ ጊዜ ምኒሊክ ለሁለተኛ ጊዜ ለአጼ ዮሐንስ ሊንበረከክ አይችልም! ይዋጋል። ምኒልክ በቃሉ ይረጋል! በዚሁ አጋጣሚ እኛ ማንጠቀምበት ብንቀር ትልቅ ስህተት ይሆንብናል ብሏል። አንቶኔሊ ጣሊያን ሀገር ሄዶ 4,700 ጠብመንጃዎችና 220,000 ጥይቶች ይዞ [3] ጃንዋሪ 22/1889 ዓ.ም. አዲስ አበባ በገባበት ጊዜ ከፍተኛ አቀባበል ተደረገለት።

1 Carlo Rossett: ibd p.51

2 Carlo Rossett: ibd p.52

3. Carlo Rossett: ibd p.54



ለወደፊት የሚፈረመውን የውል ረቂቅ ይዞ ነበረ የመጣው። ፌብርዋሪ[1] 20/1889 ዓ.ም. አንቶኔሊ ለኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በፃፈው ሪፖርት በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደሚከተለው ያብራራል። የውሉ ረቂቅ በሚመለከት (በውጫሌ የሚፈረመው ውል ማለት ነው።) ችግር የሚያመጣ አይመስለኝም፤ ብቻ ንጉሡ መሬቱን ስለመስጠቱ ጉዳይ የመሬቶቹ ባለቤት እሱ መሆኑን ሳይረጋገጥ ቃል መግባት እንቅፋት መስሎ ይታየዋል። የኢጣሊያ መንግሥት ንጉሡ ነገሥት ለመሆን ሲረዳው ጉዳዩ ወደ ፍፃሜ ሲደርስ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀል ሰላምና ወዳጅነት የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ እርግጠኛ ለመሆን እንደሚፈልግ አስረድቶኛል። ምንሊክ እብዛኛዎቹ የትግራይ መኳንንቶች በአጼ ዮሐንስ መጥፎ አስተዳደር የወደሙችና የደኸዩት ሀገራቸው ኢጣሊያ ብትገዛቸው በደስታ የሚቀበሉ መሆናቸውን አረጋግጠውልኛል።

እነዚህ አጋጣሚ ሁኔታዎች እንዲያመልጡን አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ትግራይ እንዳታንሰራራና እንዳትጠነክር ጊዜ በመስጠት ስህተት ከሠራን እንደገና ለአዲስና አስከፊ ጥቃቶች እንጋለጣለን።

በሸዋ በኩል አንድ ወዳጅ የሆነ ንጉሥ አለን፤ የእኛ እርዳታ ካልተጓደለው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ለማግኘት ጥሩ ዕድል አለው። እኛ አሁን ለምናደርግለት ውለታ በሰፊው ይከፍለናል። በዚሁ ደብዳቤ ላይ የሚታዩ ነገሮች ሀ/ ንጉሥ ምኒሊክ በጣሊያኖች አይዞህ ባይነት የትግራይ መኳንንቶች በንጉሠ ነገሥቱ በአጼ ዮሐንስ መንግሥት ላይ እንዲያምፁ ያኮሞኮሟቸው እንደነበረ ግልጽ ማስረጃ ነው። ይህም በአጼ ዮሐንስ መንግሥት ላይ የተፈፀመው ሴራ የኢትዮጵያ ጦር ጣሊያኖችን ከምፅዋ ጠራርጎ እንዳያወጣ እንዲሁም በመተማ የኢትዮጵያ ጦር መሸነፍ ምክንያት ሆኗል። የትግራይ መኳንንቶች ግን አፄ ዮሐንስን እንዳልከዱት ከመተማ በኋላ በእስክሬኑ ዙሪያ ተሰብስበው የሞቱ ሰዎች በቂ ምስክር ነው። ለ/ አንቶኔሊ ምን ያህል ጥላቻ በትግራይ ላይ እንደነበረው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ይህ ሁኔታ ደግሞ የአንድ ግለሰብ ስሜት ብቻ አልነበረም። የኢጣሊያኖች ሁሉ ጠቅላላ ስሜት እንደነበረ አያጠራጥርም። በአንድ ወቅት አንቶኔሊ ንጉሥ ምኒሊክ ጋር አነስተኛ አለመስማማት ተፈጥሮ በነበረ ጊዜ ምኒሊክ በትግራይ በኩል ወደ ሀገርህ ሂድ ብሎ በተናገረው ጊዜ አንቶኔሊ ይህ የምኒሊክ ሀሳብ የአጼ ዮሐ ንስ ትእዛዝ መሆኑን ስለሚያውቅ እምቢ የሚል መልስ ሲሰጥ እርስዎ የበቅሎዎች፣ ፈረሶች፣ ወርቅና ባሮች ግብር ለአጼ ዮሐንስ ከፍሏል። ነገር ግን የአንድ ነጭ የሆነ ሰው ግብር አይከፍሉትም እኔም በብረት ታስሬ ካልሆነ በትግራይ በኩል ወደ ሀገሬ አልመለስም ብሏል። ይህም አቋሙ በትግራይ ላይ የነበረውን ጥላቻ ሌላ ማስረጃ ነው። በአጼ ዮሐንስ አስተዳደርም ትግራ ይ ተብሎ ይጠራ የነበረው የአሁኑ ትግራይ ብቻ አልነበረም፤ ኤርትራም ጭምር ነበረች። ጣልያኖች የሸዋ ፖለቲካ የሚሉት ይሄ ነው።

1. Carlo Rossett: ibd p.56

# 6. ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የፈጸሙት ተጨማሪ ስውር ደባ

በአዲስ አበባ ይፈፀም የነበረው ማእከላዊ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ወደ ምፅዋ ጎዶም ተንፀባርቋል። ማንቴጋትሣ የተባለው የኢጣሊያ ጋዜጠኛ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ዛሬ ነገ ይፈነዳል ተብሎ ተፈርቶ የነበረው ጦርነት እንዲከታተል ወደ ቦታው ተልኮ የነበረ ከምፅዋ ያስተላልፋቸው የነበሩ ጽሑፎች ብናነብ አጼ ዮሐንስ ከመኳንንቶቹ ጋር በተለይ ከራስ አሉላ ጋር ለማጣላት ይደረግ የነበረ እንቅስቃሴ ምን ያህል ስር ሰዶ እንደነበረ እንረዳለን። ነገሩ በከፍተኛ ምስጢር ይካሄድ የነበረ ስለሆነ ምንግዜም እውነቱን ማወቅ ስለማይቻል በተገኙ አንዳንድ ፍንጮች ብቻ መወሰን ግድ ይሆንብናል። የአጼ ዮሐንስ ጠላቶች በጦር ሜዳ ሊያሸንፉት እንደማይችሉ በሚገባ ስለተረዱ በእጅ አዙር በስነ ልቦና ጦርነት ተጠቅመው ሊጥሉት ችለዋል። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ዲሰምበር[1] 8/1887 ዓ.ም. ባስተላለፈው ዜና «በኢትዮጵያና በኢጣሊያ የሰላም ድርድር እቅድ እንዳለ ስለ ሰላም ድርድሩ በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት አስተያየት ሲሰነዝር «ንጉሡ ነገሥቱ ለጣሊያን መሬት የመስጠት ጉዳይ በአንደኛ ደረጃ ሲሆን ይኸውም አቢሲንያ መስጠት የምትፈልገው የራሷ ያልሆነ መሬት ስለሆነ ከረን ቢሰጠን የተሻለ አማራጭ ነው፣ በዐይለት አካባቢ እሰጣለሁ ቢል የተቃጠለ መሬት ስለሆነ ምንም ጥቅም የሚሰጠን አይደለም። ስለ ሞራል ካሣም ይወራል ይኸውም ራስ አሉላ እንዲቀጣና ከሥልጣን እንዲወርድ የሚል ነው። በእኔ አስተያየት የሰላም ሰምምነት ቢደረግ እንኳን፣ ራስ አሉላ ከሥልጣን ይወርዳል ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ንጉሡ በራስ አሉላ ላይ ሙሉ እምነትና ልባዊ ፍቅር ስላለው ነው።

ሆኖም ሁሉም ነገር ሊሆን የሚችል ነው፣ በሐበሻ ሀገር የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፣ ተወዳጅነት የነበረው አንድ ራስ በአንድ አፍታ ከሥልጣን ተባር፣ የባሰም ዓይኑ ታውር በአንድ አምባ እንዲቀመጥ የሚደረገው የሚያጋጥም ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ለራሱ አይደለም የሚሰጋው፣ ራስ አሉላ የሚታየው የልጁ ቀንደኛ ጠላት እንዳይሆነው በመፍራት ነው» ብሎ ጽፏል።[2] ዲሰምበር 22/1887 ዓ.ም. ጋዜጠኛው ባሰራጨው ሌላ ዜና ደግሞ ራስ አሉላ በራስ ሐጐስ ስር መሆኑን ወሬ መሰማቱ ከገለፀ በኋላ አስተያየቱን ሰፋ በማድረግ እንዲህ ይላል። ከሐበሻ ሹማምንቶች ራስ ሐጐስ በዕድሜ ከሁሉም የሚበልጥ ነው። በንጉሡ ላይ ሐሳቡ ተቀባይነት አለው፣ ንጉሡም ያደምጠዋል፣ ምክሮቹም በሥራ ላይ ያውላል። ራስ ሐጐስ ረጋ ያለ ሰው ነው።

አዋቂ ነው፣ ለንጉሡም ታማኝ ነው፣ የሚነፍሰው ዜና እውነት ከሆነ ከራስ አሉላ የተሻለ ተብሎ መመረጡ ንጉሡ በራስ አሉላ ላይ እምነት እንደሌለውና የትኩላ እርምጃ እንዳይወስድ የሚፈራው መሆኑን ያሳያል።

1. Vico Mantegazza: Ibd p. 56

2. Vico Mantegazza: Ibd p. 58



ራስ ሐጐስን ከላይ በተጠቀሱ ፀባዮች ለዚሁ ደረጃ መመረጡ ያሳያል፣ ነጭ ጢሙ በአንድ ጥቁር ሰው ላይ ራስ ሐጐስ እንደ ኤውሮጳዊ ያስመስለዋል። በሌላ በኩልም ከሌሎች የእሱ ዘር የሆኑ ሰዎች ለየት በማለት በኤውሮጳውያን ላይ ጥላቻ አሳይቶ አያውቅም። ለሚኒ ቢያንኪ ወዳጅ ነበረ። ብዙ አገልግሎቶችም አበርክቶለታል፣ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሀገር ጎብኚዎች እንደ ብራንኪ እና ነራዚኒ ከእርሱ እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ትብብሩን በሚጠይቁበት ጊዜ አገልግሎቱን አበርክቷል። ዲሰምበር 28/1887 ዓ.ም. ነበር ሎርድ ፖርታል ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተነጋግሮ ምፅዋ የተመለሰ። ጋዜጠኛው ጠይቆ እንደተረዳው ሎርድ ፖርታል ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመቋቋም ቢያንስ አሁን ካሏት የጦር ኃይል እጥፍ ማሰለፍ ይኖርባታል የሚል አስተያየት ሰጥቷል። 40,000 ወታደር ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ጀንዋሪ 30/1889 ዓ.ም. በአስተላለፈው ሌላ ዘገባ ስለ ራስ አሉላ ከሥልጣን መውረድ በሚከተለው መልክ ያብራራዋል።

«ራስ[1] አሉላ የበለጠ ሥልጣንና ክብር እንዳይኖረው ትዕግስት የማጣት ሁኔታውም እንዲቀዘቅዝ ለማድረግ ንጉሡ ራሱ አስደናቂ ነገር እያደረገ ይመስላል። ራስ አሉላን ደበብ መግሪያ በማድረግም ቢሆን እየነካካ ይመስላል፣ ስለዚህ ትዕግሥት ማጣት በጭንቅላቱ ስላለ ንጉሡን ያልገመተው አንድ አደጋ ሊጥለው ይችላል። በአሁኑ ሰዓት ንጉሡ ራስ አሉላን በደህና ዓይን አያየውም ይህ የልጁና የራሱ ስውር ጠላት፣ ሊያጠፉ እመቺ ሁኔታ እየጠበቀ ነው፣ ጦርነቱ ጥሩ ውጤት ካላመጣለት የቀረው እድሜው ዓይኑን አጥፍቶ በአንድ ተራራ እንዲኖር ያደርገው ይሆናል። ንጉሡ ጦሩን ራሱ መምራቱ ሹማምንቶች እርሱ ከሌለ እርስ በእርሳቸው እንዳይጣሉ በመፍራት ነው። የጣሊያኖች የስለላ መረብ በአጼ ዮሐንስ ሰፈር ላይ ምን ያህል ስር ሰዶ እንደነበር ስናይ አጼ ዮሐንስ በመተማ በሞቱበት ጊዜ ጥይቱ ከማን እንደተተኮሰ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። ደበብ ስብዙ ጊዜ ሽፍታ ሆኖ ለጣሊያኖች አድሮ ከቆየ በኋላ አሁን ንጉሡ ያለበት ገብተዋል። እሱም ስለ ንጉሡ የሰጠው አስተያየት ጋዜጠኛው ያሰራጨው ዜና እንደሚከተለው ነበር። ንጉሡ እንደ ድሮ አይደለም አካባቢው ያሉት ሁሉ ይጠረጥራቸዋል ይፈራቸዋል። ለአንዱ ሹመት ይሰጣል ለሌላው ይነጥቃል ራሶችም እርስ በእርሳቸው ስምምነት የላቸውም፣ አንዳንዶቹ በትንሽ ገንዘብ ለእኛ እንዲያድሩ ሊገዙ ይችላሉ፣ በንጉሡ ላይ ሊያምጹ ይችላሉ፣ ንጉሡ ማንንም አያምንም። ይህ አስተያየት የተሰጠው ለወ/ር ናረቲ ነው። ኢጣሊያዊ ጋዜ ጠኛ ፌብርዋሪ 10/1889 ዓ.ም. ባሰራጨው ዜና[2] ደበብ በአሁኑ ጊዜ ጣሊያኖችን ከድቶ ከንጉሡ ጋር ታርቆ ተቀላቅሎ ይገኛል። ሀሳቡ እንዲለውጥ ያስደረገው ምን ምክንያት ይሆናል ብለው ጣሊያኖች በሚመረምሩበት ጊዜ ምናልባት ይሆናል ብለው ያመኑበት በራስ ሚካኤል ላይ ቅናት ስለነበረው ብለው ያምኑ ነበር። ጣሊያኖች የወሎው ራስ ሚካኤል ከአጼ ዮሐንስ ከድቶ ወደ ጣሊያኖች እንዲገባ ንግግር ጀምረው ነበረ፣ ውጤቱን ለማሳየት ተቃርቦ ነበር።

1 Vico Mantegazza: Ibd p. 66

2 Vico Mantegazza: Ibd p. 72

ይህ ሁሉ ደግሞ ደቡብ ያውቅ ነበር። በአቢሲኒያ ራስ ሚካኤል ከፍ ያለ ደረጃ ያለው ነው። እሱ ወደ ኢጣሊያ ከገባ ደቡብ ተደግጭነት ያጣል። ንጉሥ ምኒልክ ፌብሩዋሪ 20/1889 ዓ.ም.[1] ለኢጣሊያ ንጉሥ በፃፈው ደብዳቤ። «ግርማዊነትዎ ከምፅዋ በኩል ያለው ወሰን በሚያስቡት ሁኔታ እኔም በሙሉ ተስማምቼበታለሁ። እግዚአብሔር አንድ ቀን እነዛ መሬቶች በእኔ ግዛት ውስጥ ካደረገልኝ የሁለታችን ሙሉ ስምምነትና የልብ ወዳጅነት ለማደፍረስ ምንም አይነት ችግር እንደማይገጥመን ግርማዊነትዎ እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ ብሏል። ንጉሥ ምኒልክ ይህ ሁሉ ውል ሲፈራረም ደብዳቤዎችንም ሲጽፍ የሸዋን ህዝብ አስተያየት ጠይቆ ወይንም ተከትሎ አልነበረም። የሸዋ መኳንንት አንዳንድ ጊዜ ለዘብ ባለ አቋም አንዳንዱም ጠንካራ አቋም በመያዝ ሁሉም ግን ስለወሰኑ ጉዳይ መሬት ለጣሊያን እንዳይሰጥ ተቃሚዎች እንደነበሩ ጣሊያኖች መዝግበውታል።

ከነዚህ የአንቶኔሊና የምኒሊክ ሁለት ዳብዳቤዎች በኋላ ማለት ከፌብሩዋሪ 20 /1889 ዓ.ም. 20 ቀን በኋላ አጼ ዮሐንስ ለሀገሩ፣ ለሀይማኖቱ እየተዋጋ የጀግና ሞት በመተማ ሞተ አንቶኔሊና የኢጣሊያን መንግሥት እቅዳቸው የተሳካላቸው መስኋቸው ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ሊፈርምላ ቸው ተዘጋጅቶ የነበረ ውል ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ እንዲፈርም አረጉት።

## 7. የአጼ ዮሐንስ ታላቅነት

ጣሊያኖች ስለአጼ ምኒልክ አስተያየት ሊሰጡ ከመጀመሪያ ጀምረው እስከሞተ ድረስ የጣሊያን ወዳጅ ነበረ ይላሉ። ወደ ዓድዋ ጦርነት የገፋፋቸው ባለቤቱ እቴጌ ጣይቱ ናት ይላሉ። የ17ኛው የውጫሌ ውል አንቀጽም የአላላተው ግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚው ነው ይላሉ። ስለ አጼ ዮሐንስ ጣሊያኖች የሰጡት አስተያየት ስለ አጼ ምኒልክ ከሰጡት አስተያየት ተቃራኒ ነው። አጼ ዮሐንስ የጣሊያን ቀንደኛ ጠላት እንደነበረ ሲናገሩ፣ ኢትዮ ጵያውያን ነን፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንን እንወዳለን የሚሉ እውነተኛ ኢትዮጲያውያን ካሉ አጼ ምኒልክን አይደለም መውደድ የሚገባቸው፣ ጀግና ሆኖ የኖረ በጀግንነት አንድ ጊዜ ታሉን ሳያጥፍ ለሀገሩ የተሰዋው አጼ ዮሐንስን ነው መውደድና ማክበር የሚገባቸው ብለው ጽፈዋል። ጣሊያኖች እንደዚህ ማለታቸው ብዙ ምክንያቶች ስላላቸው ነው። እኔ ግን እዚህ መጥ ቀስ የምፈልገው ሁለት ለአጼ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ የተጻፈ ደብዳቤዎች ናቸው የአጼ ዮሐንስ ታላቅነት እና የሀገር ወዳጅነት የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸው። እነሱም 1ኛ. ከምጽዋ ወረራ አስር ወር በኋላ ኖቬምበር 26/1885 ዓ.ም.[2] የተጻፈ ሲሆን 2ኛ. ከዶጋሊ ጦርነት 10 ወር በኋላ ኖቬምበር 21/ 1887 ዓ.ም. የተጻፈ ነው።[3] በወርቅ ፊደላት ሊጻፉ የሚገባቸው ቃላቶች ናቸው።

---

1. Carlo Rossett: ibd p.57-58
2. Leopoldo Travarsi:Les Marefia p.306
3. Carlo Rossett; ibd p.47



1. የአንደኛው ደብዳቤ ሙሉ ቃል «የኢጣሊያኖች ጉዳይ በሚመለከት የነርሱ ማጭበርበርና ተንኮል ምንጊዜም አያቋርጥም፣ በመጀመሪያ በሰላም መንገድ እኔጋ መጡ፣ ለንግድ የሚጠቅም መንገድ እንሰራለን በሚል ሰበብም አውሳን ለመያዝ ፍላጎት ነበራቸው፣ እኔ ግን ለዚህም ለሌሎችም ያቀረቧቸውን ሀሣቦች ሁሉ አልተቀበልኳቸውም፣ ወሬያቸውን ሳላዳምጥ ሸኘኋቸው፣ ባደረኩላቸው አሸኛኘት ተበሳጭተው ምጽዋና በጎብ ጾች እጅ የነበሩ አካባቢዎችን ያዙ፣ በምጽዋ ለምሽግ ትላልቅ ጉድጓዶችን ሰሩ። ወደ ሀገራችን እቅጣጫም አንድ ቤት ለበሽተኞች ብለው ሰሩ። የታመሙትን ወደ ሀገራቸው ይልኳቸዋል። ደሀና የሆኑ ያስመጣሉ አንዳንድ ሀገር ጉብኚዎች ሀገሬን ለማጥናትና ወሰናቿን ለማወቅ ቆደም ብለው መጥተው ነበር። እኔ ግን ወደ ኋላ መለስኳቸው ላያቸውም ወሬያቸውም ለመስ ማት አልፈለኩም፣ ቁም ነገር ያላቸው ሰዎች አይደሉም አታላዮዎች ናቸው፣ ነገር ግን እንግሊዞች የሚሰሩብኝ ሥራ መሆን አለበት ጣሊያኖች እዚህ የመጡ። በሀገራቸው የግጦሽ መሬት እና ሳር ስለሌለ አይደለም እዚህ የመጡት። በአብሬተኝነት ትልቅ ለመሆን ነው፣ ምክንያቱም ብዙ ናቸው። ሀብታሞችም አይደሉም። ነገር ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ተዋርደው፣ አዝነው በዓለም ፊት ክብራቸው ዝቅ ብሉ ይመለሳሉ። እነዚህ ሰዎች ሊያስፈ ራሩን የሚችሉ ሰዎች አይደሉም፣ እኛ በአንድነት መቆም አለብን። አንተ ወደ እኔ መምጣት አትችልም ምክንያቱም ሀገሩ የግጦሽ መሬትና እህል የለውም። ስለዚህ ወደ ኦሮሞ አገር በኩሉ በኩል ሁሉም ነገር የሚገኝበት ስለሆነ አብረን ብንሄድ የተሻለ ነው። ለጊዜው አንተ የባህር መንገድ መዝጋት አለብህ። በአውሣ በኩልም ሆነ በጨርጨር ዘይላ በኩል ማንም ሰው ማሳለፍ የለብህም ባገርህ የሚገኙ ሁሉ እንዲሄዱ ታደርጋለህ። በዚሁ አይነት ሁሉም ይዋረዳሉ። እኛ ሁለታችን ሁልጊዜ አንድ ሆነን ከኖርን በእግዚአብሔር ብርታት እንኳንስ እነዚህ ደካማ ጣሊያኖች የሌላ ሀገር ኃይለኛ ዜጎችም እናሸንፋቸዋለን። አዳም በአብሬት ከእግዚአብሔር የበለጠ ትልቅ ለመሆን ፈልጎ የተከሰከሰ ፍሬ እንደቀመሰና ቅጣትና ውርደት እንደደረሰበት ጣሊያኖ ችም እንደዚሁ ያጋጥማቸዋል።»

በደብዳቤው አጼ ዮሐንስ እንደገለጠው ወደ ምዕራብ ሀገሮች ዘመቻ በማድረግ እንደቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት የኢትዮጵያ አንድነት ለማስ ከበር የቀድሞ ዳር ድንበሩዋን ለማስከበር እቅድ እንደነበረው ያሳያል። አጼ ዮሐንስ ራሱ ባይመቸውም የተባለው በህብረት የሚካሄድ ዘመቻ ተግባራዊ ለማድረግ ልጁ አርአያ ሥላሴን ወደ ሸዋ ልኮ ነበር። ነገር ግን በአጼ ምኒልክ ራስ ወዳጅነት ሀሳቡ ሳይሳካ ቀረ።[1]

2. የሁለተኛው ደብዳቤ ሙሉ ቃል። ከኢጣሊያ ንጉሥ ጋራ ወዳጅነታችን ከፍ ያለ መግባባት ነበረን እርሳቸው ስጦታዎችን ይልኩልን ነበረ እኔም ስጦታዎች እልክላቸው ነበር። ቆንስሉ ጆቫኒ ብራንኪ ወደ እኔ መጣ በታላቅ ክብር ተቀበልኩት፣ በመኖሪያ ቤቱ አሳረፍ ኩት፣ እርሱን ለማስደሰትና ለማክበር ሁሉም ነገር አደረግኩ፣ ደስ የማይል በርሱ ላይ የሰራ ሁት ሥራ ያለ አይመስለኝም።

---

1 C.Zaghi: Le Origini della Colonia Eritraa p.65

ከዚያ በኋላም የእንግሊዝ መልእክተኞች መጡና እንዲህ አሉኝ «እኛ ከግብጾች ጋራ ሰላም እንድታደርጉ እንፈልጋለን፤ እነርሱ የያዙት መሬታችሁን ለቀው ይወጣሉ እናንተም በመሬት በራሳችሁ ሀገር ባለቤት ትሆናላችሁ። ምጽዋ የእናንተ ትሆናለች እናንተም በመሬት የጉሙሩክ ቀረጥም ታገኛላችሁ ጠላታችሁን በምጽዋ ማስቀመጥ ትችላላችሁ። በምትፈልጉት መጠን የጦር መሣሪያ ይተላለፍላችኋል» ብለውኝ ነበር። ይህ ለማድረግ የእርስዎ ፈቃድና ማንተም ካለበት የጦር መሣሪያ ንግድ ለእርስዎ ነፃ ይሆናል። ለዚሁ ሁሉ ማካካሻ በማሕዲስቶች ላይ በምናደርገው ጦርነት እርዳታ ታደርጉልናላችሁ፤ መተማና ከሰላ ያሉት የግብፅ ወታደሮች ለቀው እንዲወጡና እስላሞችን ለመዋጋት የእርስዎ ወታደሮች ከእኛ ወታደሮች ጋር ይስማማሉ። እኔ የእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበልኝ ሀሳብ ተቀበልኩ። ሆኖም የእን ግሊዝ ወታደሮች እርዳታ እያስፈልገኝም አልኳቸው እኔ ብቻዬ በእኔ ወታደሮች ብቻ እስላሞችን ልወጋቸው እንደምችል ነገርኳቸው። ስለሆነም የፈለ ክሁትን አደረክሁ። ለእኔ ግያስታውቅ የእንግሊዝ መንግሥት ለጣሊያኖች ለምን ምፅዋ እንደሰጣቸው አሁንም አልገባኝም። ጣሊያኖች በምፅዋ ሰፍረው መጠናከር ጀመሩ፤ ያለ እኔ ፈቃድ እኔ ለሰጠሁ ለማለፈል ገውም የጦር መሣሪያ ሰጡ። ለእኔ ዜጎች ከእንግሊዝ ጋር ባደረግነው ውል መሠረት መክፈል የማይገባቸውን ጉሙሩክ ቀረጥ እንዲከፍሉ አደረጉ። በተጨማሪ ም ወታደራዊ ምሽጎችን በመሥራት ለእኔ ወደ ተመለሱልኝ መሬቶች እያ መጡ ናቸው። በዚሁ ምክንያት ራስ አሉላ ከጣሊያኖች ጋር ሰላም እንዲደፈርስ አደረገ። እኔ ግን ራስ አሉላ ያደረገው ነገርን እንዲያደርግ ትእዛዝ አልሰጠሁትም።

ዛሬ ሁለቱ ሠራዊቶች ጦርነት ለመግጠም ፊት ለፊት በሚገኙበት ጊዜ ሰላም ማድረግ የሚቻል ከሆነ እኔ በበኩሌ ለስምምነት ዝግጁ ነኝ። የኢጣሊያ መንግሥት ለማንኛውም ስምምነት ተቃራኒ መሆኑን ማስረጃ አለኝ። ለትዳሴ የሚያገለግል ነጪት (ወይን ጠጅ) አንኳን ስምምነት ተቃራኒ መሆኑን ማስረጃ አለኝ። ሳይቀር ከምፅዋ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳያልፍ አይፈቅድም። በበኩሌ የኢጣሊያ መንግሥት ሀገሬን በቁጥጥሩ ለማድረግ ካልመጣብኝ፤ ከምፅዋም ሸቀጣ ሸቀጦች እንዲተላለፉ ነፃ ካደረ ገ፤ ሰላም ለማድረግና ወደ አንድ ስምምነት ለመድረስ ዝግጁ ነኝ።

# 8. አጼ ምኒልክ

አጼ ምኒልክ ለእነዚህ ደብዳቤዎች መልስ አልሰጡም። ጣሊያኖቹን እያታለለ ብዙ የጦር መሣሪያ እንደልቡ አግኝቷል። የት እንደዋሉ የማይጠየቅበት ብዙ ሚሊዮን ጥሬ ገንዘብ በልቷል። የተመኘው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭና ለልጆቹ አውርሰዋል። በዚሁ ዓለም የተመኘውን ሁሉ ጊዜያዊ ክብርና ገንዘብ አግኝቷል። ዘላቂ ዘለዓለማዊ ክብርና ጥሩ ዝና ግን አላገኘም። ጊዜ የማይሽረው ዝና ለሀገሩ ያተረፈ አጼ ዮሐንስ ብቻ ነው። አጼ ምኒልክ ጣሊያኖችን ብቻ አይደለም ያታለለ፤ ከአጼ ቴዎድሮስም የአባትነት እንክብካቤ አግኝቷል። እንክብካቤ ካሳደገው በኋላ የራሱን ሴት ልጅ ለሚስትነት ድርታል። በተመሳሳይ ሁኔታ አጼ ዮሐንስም ልዩ አክብሮት ሰጥቶታል። ልጅ አርአያ ሥላሴ የአጼ ምኒልክ ሴት ልጅ ዘውዲቱ እንዲያገቡ አድርገዋል። ሁለቱም ነገሥታት አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ አጼ ምኒልክ



ሥር ስለነበረ 3ኛ. ጎበጽና ቀርከም የቀይ ባሕር ወደቦች በሙሉ የእኛ ናቸው እያሉ የሚከራከሩ ስለነበረ ነው። ስለኤርትራ መፈጠር የተፈጸመው ሽያጭ ግን በግልጽ መን ግሥት የተፈጸመ ስለሆነ ሕጋዊነቱ አያጠራጥርም። ሆኖም ይህ በሀገራችን ታሪክ የተከሰተው ታላቅ ክህደት ኤርትራን ለመገንጠል በቂ ምክንያት ለመሆን ከቶ ባልቻለ ነበረ። የአንድ ግለ ሰብ ክህደት ግለሰቡ ንጉሥም ቢሆን ሕጋዊነቱን የሚያስጠይቅ አልነበረም። የውጫሌ ውል ለኤርትራ መፈጠር መሠረት ድንጋይ የጣለ ስለሆነ ደረጃ በደረጃ ከዚህ በታች መዘርዘር አስ ፈላጊ ነው። ብፁእ ካርዲናል ማሣያስ በኦሮሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተብለው በሮማ ጳጳስ የተሾሙት በ1846 ነበረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ35 ዓመታት በሀገራችን ተቀምጠዋል። በወለጋ፣ በጂማ፣ በሸዋ ሚስዮኖችን መሥርቷል። በ1868 ወደ ሀገራቸው ሄደው ከከረሙ በኋላ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ወደ ኦሮሞ ሀገር ለመሄድ በዐይላ በኩል ሸዋ እንደገቡ ንጉሥ ምኒልክ የፖለቲካ አማካሪው እንዲያደርጋቸው አሰበው የሃይማኖት ሥራቸውም በሸዋ እንዲያከናውኑ ስለፈቀደላቸው እዛቸውም ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙ፤ በአጼ ዮሐንስ ትእዛዝ ከኢትዮጵያ እስከተባረሩበት ጊዜ ድረስ ለ11 ዓመታት በሸዋ ተቀምጠዋል።

ብፁእ ካርዲናል ማሣያስ በሀገራችን ይካሄድ የነበረው እርስ በርስ የሥልጣን ሹክቻ ስለ ኤርትራ መፈጠር ወሣኝ ሚና የተጫወቱ ሰው ናቸው። ንጉሥ ምኒልክ በካርዲናል ማሣ ያስ አማካኝነት ከኢጣሊያ መንግሥት ግንኙነት ለመፍጠር ፍላጐት ስለነበረው በ1872 አባ ሚካኤል የተባሉ መልዕክተኛ ከተላኩ በኋላ የመልዕክተኛውን ስም ማጥፋት ዘመቻ ስለተያ ያዙ ወደ ጣሊያን ሀገርም ደብዳቤ ጽፈው በደህና እንዳይቀበሉት ስላደረጉ የአባ ሚካኤል ተልእኮ ተሰናክሉ ሳይሟላ ቀረ። ነገር ግን የአባ ሚካኤል ወደ ኢጣሊያ ሀገር ጉዞ ጣሊያኖች ወደ ኢትዮጵያ ሸዋ እንዲያተኩሩ ገፋፋቸው። የሌሎች የኢውሮፓ ሀገሮች ፈለግ በመከተል ከ1873 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ ዓመታት ስብሰባ ካካሄዱ በኋላ በ1876 ዓ.ም. የኢጣሊያ የጂኦግራፊ ማህበር የሚል ማህበር መሠረቱ። ከዚህ እያይዘውም የጂኦግራፊ የሕክምና ጣቢ ያ በሸዋ ለመመሥረት ተስማምተው ወዲያውኑ በአንቲናሪ የሚመራው የኢጣሊያ አንድ ቡድን ወደ ሸዋ የሚላኩ አባሎች ተመርጠው ማርች 8 ቀን 1876 ከኢጣሊያ ሀገር ተነስተው ሴፕቴምበር 18/76 ሸዋ ገቡ። ጃንዋሪ 18/77 ካርዲናል ማሣያ በመረጡላቸው «ልጥ ማረፊያ» የተባለው መሬት ለመኖሪያ፣ ለህክምና፣ ለዕረፍት፣ ለምርምር እንዲጠቀሙበት ከንጉሥ ምኒልክ ተሰጣቸው። ይህ ትንሹ መሬት ኢትዮጵያን ጠቅላላ ለመያዝ የረዳን፤ መሠ ረተ ድንጋይ የተጣለበት ቦታ ነው ብለው ጣሊያኖች ይኮሩበታል። እውነትም ይህ ቦታ ሲሰ ጣቸው በእርዕሰቱ ለተጠቀሰው ዓላማ ሣይሆን ለኢጣሊያ መንግሥት ፀረ-ኢትዮጵያ ስለላ ማዕከል በመሆን አገልግሏል። ጣሊያኖች በመጀመሪያ ወደ ሸዋ በገቡበት ጊዜ ብዙ ስጦታ ዎች ለንጉሥ ምኒልክ ከመንግሥታቸው የተላከ ይዘው መጥተው ነበር። ንጉሥ ምኒልክ ግን በተለይ ያተኮረው ጣሊያኖች ለራሳቸው መከላከያ ብለው ይዘዋቸው የነበሩ 150 ጠብመን ጃዎች ነበረ። ጣሊያኖች የተላኩበት ዓላማ ወደ መሐል አፍሪካ ኤኳቶሪያል ሐይቆች ሄደው ለመሰለልና ለማጥናት ነበረ። ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ የንጉሥ ምኒልክ ቀም አሰረዋቸ፤ ከፊል እሥረኞች መሆናቸውን ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። የንጉሡ ዓላማ የንጉ

50,000 ወታደር ሞቷል። 20,000 ከግብፅ ወገን፣ 30,000 ከኢትዮጵያ ወገን። በዓድዋ ጦርነት ግን የሞቱት ወታደሮች 6,000 ከኢጣሊያ ወገን፣ 7,000 ከኢትዮጵያ ወገን ብቻ ነበሩ። የጉራዕ ጦር ነት ተገቢ ክብርና ትኩረት እንዳይሰጠው የተደረገው በቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት ምኒሊክና ኃይለ ሥላሴ ፍላጐት ስለነበረ ብቻ ነው። በደርግ ጊዜ ይህ ሁኔታ እንዴት አልተለወጠም? ግብጾች አፍሪካውያንና ዓረቦች ስለሆኑ ጣሊያኖች ኤውሮጳውያንና ነጮች ስለሆኑ ከፍ ዝቅ የሚያደርግ ልዩ መስኪያ ነጥብ ካልተሰጠ በቀር በሞቱ ሰው ቁጥር ሲታይ ግን ልዩነቱ የጎላ ነው። እንደዚህ በ1928 ዓ.ም. የጣሊያን የመጨረሻ ወረራ የተካሄዱ ጦርነቶችም አጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ እንደተዋጋ ተደርጐ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለማይጨው ጦርነት ብቻ ነው እንዲያውቅ የተደረገ። በምጽዋ የሰፈሩ የኢጣሊያ ጦር መኮንኖችም የምኒልክ ደጋፊ ነበሩ። ጣሊያኖች የንጉሥ ምኒልክ ደጋፊዎች በ1898 (በኢትዮጵያ 1881 ዓ.ም) በምጽዋ አካባቢ ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ጦርነት ለመግጠም ተቃርበው በነበሩ ጊዜ ምኒልክ ለሱሞናዊ ዘር የሆነ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆን የሚገባው መሆኑን ለማስረዳት ይጥሩ ነበረ። በአንጻሩ አጼ ዮሐንስ በአመጽ ያለአግባብ በሥልጣን የወጣ እያሉ ቅስቀሣ ያካሂዱ ነበረ። የአጼ ምኒሊክ ዘር የሆኑ 30 ሰሎሞናዊ ነገሥታት 1270–1632 የነገሱ የስም ዝርዝር ካወጡ በኋላ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ የበለጠ ሰራዊት እንዳለው ለማስረዳትም ይጽፉ ነበረ። ቀጥሎ ምኒልክ የመላው ኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው የኃይለ መለኮት ልጅ መሆኑን ገልጸው ኃይለ መለኮት በአጼ ቴዎድሮስ ተሸንፎ እስረኛ ሆኖ ተወስዶ ከእስር ለማምለጥ በመቻሉ ወደሸዋ ተመልሶ የሸዋ ንጉሥ ተባለ። በ1865 ሁሉም ግዛቶች ከአቢሲኒያ በስተቀር ለመቆጣጠር ችሎ ነበረ። መላውን ወሎ በጦርነት አሸንፈው ተቆጣጥሮ ወደ ጎንደር በመሄድ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ፈልጎ ነበረ። ነገር ግን በመቅደላ አጼ ቴዎድሮስ ሐበሾች በእንግሊዞች ተሸንፈው እራሱን ስለገደለ እንግሊዞች አጼ ዮሐንስን ንጉሥ በማድረጋቸው ምኒልክ ጉጃምን ተቆጣጥሮ ወደ አቢሲኒያ በማምራት ንጉሥ ለመሆን ሲቃረብ አጼ ዮሐንስ በግብጾች ላይ ባደረገው ጦርነት ስለቀናው ምኒልክ እድሉ ለጊዜው አከተመ፣ ለዮሐንስ እጁን ሠጠ። ሆኖም ምኒልክ የሕዝቡና የጦሩ ታማኝነት አለው፣ የኢጣሊያም ወዳጅ ነው። አንድ ቀን ከጣልቃ ገቢው ከአረኛው ዮሐንስ በቅርብ ጊዜ ጦርነት ገጥሞ አሸንፎ የአባቶቹን ዙፋን እንደሚረከብ እያጠራጥርም ብሏል።

## 9. የውጫሌ ውል

ፀቀይ ባሕር በኩል የሀገራችን ለንዝር መሬት አንሰጥም ተብሉ ከፍተኛ ትግል በሚደረግበት ጊዜ በመሐል ሀገራችን ግን ያ የተከበረ መሬታችን፣ የታሪካችን አሻራ የሆነው የሰሜናዊ የሀገራችን መሬት ለድርድር ቀርቦ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በገጸ በረከት ተሸጧል። እሱብን ለኢጣሊያ የሸጡ ሱልጣኖች እንኳን ሕጋዊ አይደሉም፣ በኃላፊነት የሚጠየቁ አይደሉም ተብሏል፣ ምክንያቱም 1ኛ. አሰብ ራሱ በአውሣ ሡልጣን ሥር ስለሆነ 2ኛ. የመላው አፋሮች ሹም አንፋሪ የአውሣ ሡልጣንም በሙሉ በኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት



በሰለሞን ዘር ይወለዱል ብለው በግመን ከምኒልክ ጋራ በጋብቻ የመተሳሰር ፍላጎት ነበር የታወቀውም። አጼ ምኒሊክ በጣም ዕድለኛ ሊባል ይገባዋል። ይሄውም ዕድል በከፊል እያቀረቡ ያቀረበት ዕድል ነው ለማለት ይቻላል። የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ግን የሰለሞን ዘር የለውም ገንዳቸው የኦሮሞ ዝርያ ነው። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የሰለሞን ዘር አመጣጥ ዐይነቱ የሚታወቀው በቀድሞ መሪዎች እንድናውቀው የተሰጠን ታሪክ መንዝ ላይ የቀረው ከአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ከአቤቶ ያዕቆብ የሚወለድ መሆኑን ይገልፁና አንድ ትውልድ ዘለው ከአቤቶ ያዕቆብ የልጅ ልጆች ከሆኑ አንዱ ከአቤቶ ነጋሲ ምስፍና ተጀመረ ይላሉ። ሌሎች ግን አንደሚከተለው ያስቀምጡታል።[1] አጼ እያሱ ቀዳማዊ ሸዋን ለመጐብኘት በመጣ ጊዜ መርድ አዝማች ሹመት ሰጠው። አጼ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት እምነት ተቀብሉ ነበር። አጼ ሱሲኒዮስ በቤተመንግሥቱ አንድ ፋሪስ የተባለው የኦሮሞ ዝርያ ሆኖ የየጁ ተወላጅ ነበር። እሱም እንደ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት ተቀብሉ ነበር። አጼ ሱሲኒዮስና ፋሪስ በግድም በውድም የካቶሊክ የይማኖት ለማስፋፋት ብርቱ ጥረት ቢያደርጉም በሕዝቡ ተቃውሞ አጼ ሱሲኒዮስ ከሥልጣን ሲወርድ ፋሪስም ራስ ሆኖ የወሎ ሀገረ ገዢ ሆኖ ተሹሞ ሄዶ ስለነበረ ራስ ፋሪስ በሞተ ጊዜ አንድ ሴት ልጅ ትቶ ነበር የሞተ። ስነበልት የምትባል ከአጼ ፋሲል ለመሸሽ ከወሎ ወደ መንዝና ግሸን መጥታ አንድ ሀብታም ሰው አግብታ ነጋሲ የተባለውን ልጅ ወለደች። ከነጋሲ ቀጥሎ ያለው ትውልድ ስውጥ የሌለው ቢሆንም መርዕድ አዝማች የተባለው ነጋሲ ማይሆን የሱ ልጅ አብዩ ነው። የትውልዱ ሀረግ 1ኛ. ነጋሲ 2ኛ.ሰባስቴ 3ኛ.አቢዩ /መርዕድ አዝማች/ 4ኛ. አምደእየሱስ 5ኛ. አስፋወሰን 6ኛ. ወሰንሰገድ 7ኛ. ሣህለ ሥላሴ (ንጉሥ) የነገሰበት ዘመን 1813 እያለ ይሄዳል። ነጋሲ ከአጼ ልብነ ድንግል እንደማይወለድ የሚያስረዳን አጼ እያሱ ቀዳማዊ የአጼ ልብነድንግል የልጅ ልጅ ሲሆን እንዴት ከጐንደር ለጉብኝት ወይንም ግብር ለማስከፈል ወደ ሸዋ ሲመጣ ብቻ ከነጋሲ ጋራ ተዋወቀ? ነጋሲ የንጉሥ ዘር ከሆነ እንዴት ሸዋ ተረስቶ ተቀመጠ? ለምን እንደሌሎቹ የመሣፍንት ዘሮች ወደ ወህኒ አምባ አልተወሰደም? የቅርብ ዘመድ ሆነው ተረስተው ሊቀመጡ አይ ችሉም። የምንሊክና የኃይለ ሥላሴ የሰለሞን ዘር መሆናቸው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እሜን ብሎ የተቀበለው ነው። የሌላ ነገሥታት ዝና እንዳይወራ በታሪክ እንዳይመዘገብ ከፍተኛ ጥረት ይደረግ ነበር።

የሀገራችን ታሪክ እንድናውቀው ይደረግ የነበረው ለቀድሞ ነገሥታት በሚያመች ሁኔታ ነበር። የታሪክ ፀሐፊዎችም ለነገሥታቱ ያደሩ ከነገሥታቱ ደመወዝ የሚከፈላቸው ነበሩ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገሩ ትክክለኛ ታሪክ ለማወቅ አልቻለም። በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ከዐረ ቅኝ ገዢዎችና ተስፋፊዎች በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል። ከተካሄዱት ጦርነቶች የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲያውቅ የተደረገው ስለዓድዋና ማይጨው ጦርነት ብቻ ነበር። በታሪካችን ውስጥ ከሁሉ ከባድ ጦርነት የተመዘገበው ግን በጉራዕ የተካሄደው በግብፅና በኢትዮጵያ መሀል የተካሄደው ጦርነት ነው።

---

1 Cecchi: Da Zeila alle fronitere di Caffa V I p 257-58

ው ነገሥት ዘውድ ለመጫን ከአጼ ዮሐንስ ላይ በግልጽ ወደፊት በመገልም የነበረው ሥውር ዓላማ የሚያገለግሉት ጣሊያኖች የጦር መሣሪያዎች እንዲያቀብሉት ነበረ።

ጣሊያኖችም የመጡበት ይፋዊ የሆነ ዓላማ ቢደናቀፍባቸውም ሥውር ዓላማቸው ግን ሀገራቸው ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ስለነበረ በከፊል እሥረኛ መሆን እምብዛም አልጠሉትም። ካርዲናል ማሣያ ራሳ ቸው በይፋ የተሰጣቸውን ሀገረ ስብከት የኦሮሞ ሀገር ቢሆንም በሸዋ ኦሮሞዎች ስላሉ በሸዋ መቀመጣቸው ለተሰጣቸው ተልዕኮ ተቃራኒ እንደማይሆን ይናገሩም ይጽፉም ነበረ። ሐቁ ግን ኦሮሞ ሀገር ለመሄድ ያልፈለጉት 1ኛ. ከ ኦሮሞ የመጡት ተባርረው ስለሆነ መመለስ ስለማይችሉ 2ኛ. ንጉሥ ምኒልክን ካቶሊክ ለማድረግ ተስፋ ስላደረባቸው 3ኛ. በኦሮሞ ሀገር በገንዘብ ዕዳ እንዳይያዙ ነበረ። ምኒልክ በእጁ ብዙ ማስፈራሪያዎች ይዟል። የጦር መሣሪያ እናቀብልም ካሉት በቃል የሰጠኋቸው መሬት በጽሁፍ አልሰጣችሁም፤ ወደ ጂማ ከፋ እንድትሄዱ አልፈቀድላችሁም፤ ከሀገር እባርራችኋለሁ ይላቸው ነበረ። ጣሊያኖች ሌላ ሥውር ዓላማ ስለነበራቸው ከምኒልክ ቃል መውጣት አልፈለጉም። በዚሁ መሠረት ከአባሎቹ አንዱ ሰባስቲያኖ ማርቲኒ የተባለው ዲሰምበር 5/1877 መሣሪያ ለማምጣት ወደ ኢጣሊያ ሀገር እንዲሄድ ተደረገ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ኖቬምበር 1879 ስጦታዎችን፣ ኒሻኖችን፣ ደብዳቤም የወዳጅነት ውል ረቂቅና 210 ጠበመንጃዎችን ይዞ ሲመለስ አንቶኔሊ የተባለው የምኒልክ ወዳጅ ለመሆን የበቃና የውጫሌ ውል አቀነባባሪ የነበረው ለመጀመሪያ ጊዜ አብሮ ወደ ሸዋ መጣ። አንቶኔሊ የጦር መሣሪያ ለአፍሪካ እንዳይሸጥ የሚል ስምምነት በተለይ ብሪታኒያ በጥብቅ ትከታተለው የነበረው በመጣስ ማርቲኒ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እሱን በመተካት ከምኒልክ ጋር የጦር መሣሪያ ንግድ ማድረግ ጀመረ። ሌሎች ሀገሮች በሚቆጣጠሩበት ወደብ መሣሪያ ለማስገባት ችግር ስለሚፈጥር በኢጣሊያ ቁጥጥር ለሆነው በአሰብ ወደብ መሣሪያዎቹ እንዲገቡ አቅድ አውጥቶ ተሣካለት። በቫቲካን ካርዲናል የሆኑ አጐት ስለነበሩት፣ በዚሁ ዝምድና በመጠቀም የሮማ ጳጳስ ከመንፈሣዊ ሥልጣናቸው ሌላ የአንድ ሀገር መሪ ስለነበሩ፣ ከ1860 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ይህ ሥልጣናቸው ስላጡ በቫቲካን 2000 ሬሚንግቶን ጠበመንጃዎች በሽያጭ ለምኒልክ ለማግኘት ስለተስማማ የኢጣሊያ መንግሥት በ1879 ካርዲናል ማሣያ ባለሙሉ ሥልጣን ኢጣሊያን ወክለው ከምኒልክ ጋራ እንዲዋዋሉ የተደረገው ስምምነት ካርዲናሉ ከሀገር በመባረራቸው አንቶኔሊ በቦታቸው እንዲተካ ተደርጐ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ተሾሞአል። ከምኒልክ ጋራም አንድ የወዳጅነትና የንግድ ውል ተፈራርመዋል። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ጣሊያኖች ምኒልክ መልእክተኛ ወደ ጣሊያን ሀገር እንዲልክ ይጐተጕቱት ነበር። ምኒልክ ደግሞ አጼ ዮሐንስን በመፍራት ይሆናል፣ ሁል ጊዜ እሺ እያሉ መልዕክተኛውን ከመላክ ተቆጥበው ይኖሩ ነበረ። ጣሊያኖች ግን በጣም የተቸገሩበት ጉዳይ ነበረ፤ ምናልባትም የውጫሌ ውል ዓይነት ለሸዋ ብቻ ለማስፈረም አስበው ይሆናል። አሁንም ምኒልክ የመልክተኛው ወደ ጣሊያን ሀገር የመላክ ጉዳይ እያረሳሳ ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ በዶጋሊና በበይሉል የሞቱት ጣሊያኖች እኔ አበቀልላቸዋለሁ እያለ ጣሊያኖችን እያታለለ በምስጢር ከጣሊያን መንግሥት 5000 ሬሚንግቶን ጠበመንጃዎች ለማግኘት ውል አደረገ።




ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ አንቶኔሊ ራሱ ተታሎ መንግሥቱን የሚያታልልበት የነበረ ዘዴ ንጉሥ ምኒልክ ገር ናቸው ጣሊያኖችን ይወዳሉ፤ ግዛታቸው ሸዋ በኢጣሊያ የበላይ አስተዳዳሪነት ሥር፤ (ፕሮቴክቶሬት) ለማድረግ ፍላጐት አላቸው (አካባቢያቸው ግን ብዙ ትግሬዎች አሉ) ከጦር አለቆችም ብዙ ትግሬዎች አሉ (ባለቤታቸውም ጣይቱ ትግሬ ናቸው) አብዛኛው የቤተ ክህነት መሪዎች የአጼ ዮሐንስ ደጋፊ ናቸው ወዘተ... በሚል እኑ ጋገር ነበረ ለኢጣሊያ መንግሥት ያስተላልፋቸው የነበረ ሪፖርቶች ዋና ፀረ–ትግራይ የሸዋ ወዳጅ የነበሩ ደግሞ ካርዲናል ማሣያ ነበሩ። አንቶኔሊም ከእሣቸው ተምሮ ፀረ– ትግራይ፣ ፀረ–ኢትዮጵያና የሸዋ ወዳጅ ፖሊሲ አካሄደዋል። ጣሊያኖች ቀንደኛ ጠላታችን ይሉት የነበረ አጼ ዮሐንስ በጀግንነት ለሀገሩና ለሃይማኖቱ እየተዋጋ በጦር ሜዳ መተማ ላይ መጋቢት 1ቀን 1881 ዓ.ም. (ማርች 10/1889) ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። አሁን ለጣሊያኖችና ለንጉሥ ምኒልክ መልእክተኛም ወደ ጣሊያን ሀገር ለመላክ ውልም ለመፈራረም መንገድ ክፍት ሆነላቸው። አንቶኔሊ ብዙ ጊዜ የተመኘው ክብር ያለምንም ውጣ ውረድ ራሱ ማግኘት ፈለገ። ድሮ ይመኘው የነበረ በሸዋ የጣሊያን የበላይነት አስተዳደር (ፕሮቴክቶሬት) ብቻ ነበረ። አሁን ግን ከተመኘው በላይ ማይታሰብ የመላው ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ሥር የበላይነት አስተዳደር አገኘሁ ብሎ ተደስቶ ውሉም የሚፈራረምበት አጼ ምኒልክ ወደ ጣሊያን ሀገር መልዕክተኞቹን ልኮ መሆኑ ቀርቶ አዲስ አበባ ላይም አልተደረገም ፤በወሎ በአንድ አነስተኛ መንደር ሚይ 2 ቀን 1889 በውጫሌ ውሉ[1] ተፈጸመ። ውሉ 20 አንቀጾች ያዘለ ነበረ። ኤርትራን በሚመለከት ግን ሶስተኛ አንቀጽ ብቻ ነበረ። እሱም በሁለቱ ወገኖች ያለመግባባት ለማስወገድ በወሰናቸው ልዩ ቋሚ ምልክት የሚያደርጉ ሁለት የኢጣሊያ፣ ሁለት የኢትዮጵያ መልእክተኞች በተውጣጡ ልዩ ኮሚሽን ይመሠረታል፤ የሚመራበትም በሚከተለው ይሆናል። ሀ/ የደጋ መስመር የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ወሰን ይሆናል ለ/ ካራፋሊ አካባቢ ተነስቶ ሐላይ ሰገነይቲና አሥመራ በኢጣሊያ ወሰን ውስጥ ይሆናሉ። ሐ/ አዲ ንፋስና አዲ ዮሐንስ በቦጐስ በኩል በኢጣሊያ ወሰን ውስጥ ይሆናሉ። መ/ ከአዲ ንፋስ ቀጥታ መሥመር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ የወሰን ምልክት ይሆናል የሚል ነበረ። በዚሁ ጊዜ አንቶኔሊ በደስታ ተውጦ ውሉን መፈረሙን ለሀገሩ መንግሥት ያበስራል፤ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ የቆየው የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ወደ ጣሊያን ሀገር መላክም እልባት ያገኛል። ከዚህ በፊት እንደተደረገው እንደ አባ ሚካኤል ሣይሆን አጼ ምኒልክ የእኅት ልጅና ታማኝ ቀኝ እጅ የነበረው ራስ መኰንን መልዕክተኛ ባለሙሉ ሥልጣን አድርጎ ሸዋ ወደ ኢጣሊያ ይላካል። አንቶኔሊና ራስ መኰንን ኦገስት 21 ቀን 1889 ጣሊያን ሀገር ይደርሣሉ። ራስ መኰንን አክቶበር 1 ቀን 1889[2] ስለወሰኖች ማስተካከያ ከውጫሌ ተጨማሪ ውል ይፈራረሟሉ።

---

1 Carlo Rossetti| Ibd p.41-45

2 Carlo Rossetti/Ibd p.41-45




የትግራይ ድንበር እስከ 1872 (1880)



ይህ ውል በእኔ ፖግብ የውጫሌ ውል አንቀጽ 16ን የሚታረን ነው። ይህ ውልም 11 አንቀጾች ያዘለ ሲሆን ኤርትራን የሚመለከት ግን አንቀጽ 3 ብቻ ነው።

እሱም በአሁኑ ጊዜ በየደጆታቸው ባለው መሬት ወሰኑ እንዲከበር መሠረት በማድረግ የሁለቱ ሀገሮች ወሰናች ማስተካከያዎች ለመወሰን ሜይ 2 ቀን 1889 አንቀጽ 3 በተደረገው ውል መሠረት የኢጣሊያ ንጉሥና አጼ ምኒልክ መልእክተኞቻቸውን ይሾማሉ የሚል ነበረ።

የወደቁት የኢትዮጵያ መንግሥታት መሪዎች ገንጠዮችና ከሐዲዎች እየተባሉ ሲጠሯቸው እንደነበረ እናስታውሳለን፤ ነገር ግን ዋና ገንጣዮች ምኒልክና ጣሊያኖች ናቸው። የዛሬ ግን ገንጣዮች የቅኝ አገዛዝ የእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ርእዮተ ዓለም ደጋፊዎች አፍሪካን ለመቀራመት የመጣው አቅድ በበርሊኑ ጉባዔ የተደነገጉ ውሣኔዎች በተግባር ደጋፊዎች፤ በጣሊያኖች ሰብከት ፀረ–ኢትዮጵያ አቋም ያደረባቸው ቢባሉ አይበዛባቸውም። ይህ ፀረ–ኢትዮጵያና ፀረ–አማርኛ ተናጋሪ ሕዝብ ጥላቻ በሚገት አብዛኛው በኤርትራ ነው ጉልቶ የሚታየው። በአንጻሩም ፀረ–ትግራይ ጥላቻ የሚሰማው በአዲስ አበባ ብቻ ነው፤ በሌሎች ክፍላተ ሀገራት አይሰማም ጣሊያን የረገጡበት ቦታ የሸዋ ፖለቲካ፤ የትግራይ ፖለቲካ እያሉ በሸዋ በስሜን ኢትዮጵያ ተቀምጠው እርስ በርሳችን ለማፋጀት የለኮሱብን እሳት ነው። ገንጣዮች ሌላ ተጨባጭ የሚያጣላን በቂ ምክንያት ሊያቀርቡ አይችሉም።

# ምዕራፍ 9
# ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ወረራዎችና ጦርነቶች
# ክፍል 2
## አከለጉዛይ የጦር አውድማ ሆናለች

### ሀ. ሰገነይቲ

ፊታውራሪ ደበበ የአጼ ዮሐንስ የወንድም ልጅ ነው። ከእዚሁ ተጣልቶ በረሐ ለበረሐ እየዞረ በውንብድና ሥራ የሚተዳደር ነበረ። ጣሊያኖች ይጠቅመናል ብለው በኢትዮጵያ ላይ ደፈጣ ውጊያ እንዲያደርግላቸው ከመለመሏቸው ብዙ ሰዎች አንዱ ነበረ። ከጣልያኖች በሚጣላበት ጊዜ ወይንም በጥርጣሬ በሚያዩበት ጊዜ የአማውርታ ጉሣ ተያዥ ሆነው ያስታርቁት ነበረ። በዚሁ ምክንያት የአማውርታ ጉሣዎች የደበበ ወዳጅ እያሉ ጣሊያኖች ይጠሩዋቸው ነበረ። በዓመት 5,000 ሊሬ ከጣሊያኖች ለደበበ ይከፈለው ነበረ። አገስት 1888 ግን ከጣሊያኖች ጋራ ተጣልቶ ሸፍቶ አስጨንቋቸው ነበረ። መደበኛ አድራሻውም ሰገነይቲ ነው ስለተባለ በወቅቱ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረ ጄኔራል ባልዲሴራ ከምዕዋ ወታደሮችን ልኮ በድንገት አደጋ ጥሎ ደበበን ለመግደል እቅድ አውጥቶ ይሄን እቅድ የሚፈጽምለት ሻንበል ኮርናኪያን (cornacchia) ይመርጣል። 400 ባሺብዙክ ይሰጠዋል። እንደዚሁም 4 የኢጣሊያ መቶ አለቆች አብረው ለዘመቻ እንዲሄዱ ይታዘዛሉ። የዘመቻው ውጤት ግን ከዶጋዓሊ በኋላ በጣሊያን ሕዝብ ላይ የደረሰ ከባድ ሽንፈት ነበረ። ጄኔራል ባልዲሴራ ለሻምበል ኮርናኪያ አገስት 1 ቀን 1888 ዓ.ም. በጻፈለት ደብዳቤ ደበበ በሚገኝበት በሰገነይቲ ድንገተኛ አደጋ በመጣል ደበበን እንዲይዙ ታዟል። በተቻለ ፍጥነት በሐዳስ ሸለቆ በኩል ወደ ሰገነይቲ ዘልቀው ሳይነጋ በሌሊት እንዲደርሱ። ወደሰገነይቲ በሚጓዙበት ጊዜ ምንም ሰው ከእርሰዎ በፊት እንዳያስቀድመ፤ በተለይ አክሩር እንደደረሱ ከአክሩር ወደ ሰገነይቲ ማንም ሰው እንዳይሄድ እንዲከለክሉ፤ ሰላዮች ሊሆኑ ይችላሉ። ደበበን ወይም ተከታዮቹን ለመያዝ ወይንም ለመግደል ከቻለ ተግባርን እንደፈጸመ ምርኮኞቹን ይዘው በፍጥነት ይመለሣሉ። ደበበ በቦታው ካልተገኘ ከእሱ ቤቶች መጋፊያዎችን ከተወሰዱ በኋላ አጠገቡ ላሉ ቤቶች አደጋ የማያመጣ ከሆነ ቤቶቹን እንዲቃጠሉ ያደርጋሉ። ይሄንን ትእዛዝ ተቀብሎ አገስት 6 አክሩር አካባቢ ከቀኑ በ6 ሰዓት ደርሰው እስከሚቀጥለው ቀን ከቀኑ 9 ሰዓት ዕረፍት ያደርጋሉ። ጠዋት አገስት 8 ወደ ሰገነይቲ አምርተው ድንገተኛ ጥቃት ለመፈጸም በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ፤ ደበበ ከአገስት 6 ጀምሮ መምጣታቸውን ሰምቶ እንቅስቃሴያቸውን ይከታተል ስለነበረ፤ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ልጅ ከመንደሩ አስወጥቶ ለውጊያው



ተዘጋጅቶ ይጠባበቃቸው ስለነበረ ተኩስ ተከፍቶ ጦርነት ተካሄዶ በድምሩ 250 ባሺብዙክና አምስቱ የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች ሲገደሉ ሌሎቹ የቆሰሉ ወይንም ያልቆሰሉ ሸሽተው ምፅዋ ገቡ። ደበበ የሰው ኃይል 470 ጠብመንጃ የታጠቁ ተዋጊዎችና 400 ጎራዴና ሻንጃ የታጠቁ ተዋጊዎች ነበሩ። እዚህ ላይ ጣሊያኖች ሶስት ስህተቶች እንደፈጸሙ ይታያል። 1ኛ. ከምፅዋ ሰገነይቲ ለመድረስ አጭሩ መንገድ በሐዳስ ሣይሆን በግሊ ጊዱ ነው። 2ኛ. አክሩር ላይ ከ24 ሰዓት በላይ መቆየታቸው ራሣቸውን በራሣቸው እንደተጋለጡ ይቆጠራል። 3ኛ. ጦርነት ሣይገጥሙ መሸሻቸው። ጣሊያኖች ከዶጋዓሊ ቀጥሎ ከባድ ሽንፈት የደረሰባቸው በሰገነይቲ ጦርነት ነበረ። በሰው ኃይል ሁለቱ ወገኖች ተመጣጣኝ ነበሩ። የሞቱት ሁሉም ጣሊያናውያን ባይሆኑም በሞቱት የሰው ብዛት ሲታይ ግን ከዶጋዓሊ ጋራ የሚተራረብ ነበረ። በደበበ ጦር ላይ የደረሰው ጉዳት በጣም አነስተኛ ነበረ። ተኩስ እንደተከፈተ ጣሊያኖች መሸሽ ስለጀመሩ የተገደሉት አብዛኛው በመሸሽ እንዳሉ ለ5 ሰዓት እያሣደዱ የገደሉዋቸው ናቸው። ከብዙ ሰዓት ሽሽት በኋላ ከኢጣሊያ ጦር መኰንኖች አንዱ ወታደሮቹን እቁም ለመከላከል ሞክሮ ነበረ። ግን አልተሣካለትም፤ ራሱም ተገደለ። ስለዚህ ጦርነቱ በሰገነይቲ ሰም የሚጠራው የተጀመረበት ቦታ በመሆኑ ነው እንጂ ያበቃው የ5 ሰዓት ሩጫ ወደ ምፅዋ በሚወስደው መንገድ ነበረ። ሽንፈት ስለሆነ ከሰገነይቲ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች የሉም።




### ለ. ሐላይ

የአከለጉዛይ ሰገነይቲ ተወላጅ ደጃዝማች ባህታ ሐጎስ የሸፍቶች አለቃ በመሆን ከነራስ አሉላ እና ከጣሊያኖቹ ጋር እየተጣላና እየታረቀ በጉረቤቶቹ አማውርታ ጎሣዎች ሀገር በረየዎች እንዲሁም ዘመዶቹ ባሉበት ሀገር በሐባብ ሳህል በረሃዎች ከኖረ በኋላ በመጨረሻ ለጣሊያኖች ያደረ መስሎ ከአንድ ኢጣሊያዊ መቶ አለቃ ስር በመሆን የአከለጉዛይ አውራጃ ገዢ ሆኖ በጣ ሊያኖች ተሹሞ ተቀማጭነቱ ሰገነይቲ ሆኖ በሚያስተዳድርበት ጊዜ የራሱ የሆነ ዓላማ ነበረው። ዓላማውም አመቺ ጊዜ ጠብቆ ጣሊያኖች በሀገሩ የዘረጉትን አዲስ ስርዓት ለማፈራረስ ነበር። በክሳላ ጦርነት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር አለቆች ከጀኔራል ባራቴሪ

ጀምሮ ከትግራይ እደጋ ይደርስብን ይሆናል ብለው ስጋት ነበራቸው። ነገር ግን በኢጣሊያ ክሕደት የሚፈጽም ባህታ ሐጎስ ይሆናል ብሎ የገመተ ሰው ማንም አልነበረም። ከትግራይ መሪዎች ሁሉ እምነት ተጥሎበት የነበረ ከጣሊያኖች ታላቅ ክብር ያገኘ ነበረ። ለብዙ ዓመታት በበረሃ ከተንከራተተ በኋላ ከራስ መንገሻ በታች በመሆን ወደ ሀገሩ ገብቶ በሰላም ለመኖር እንደሚመርጥ የሁሉ ግምት ነበር። ጣሊያኖች ጀግና ብለው ይተማመኑበት ነበር። እንዲጠቀሙበትም ብዙ ሃሣብ ነበራቸው። ዲሰምበር 15 ባራቴሪ ከረን ሆኖ ስለክህደቱ ወሬ ሲሰማ ማመን አልቻለም ነበር። የከዳበት ምክንያት ጥርጣሬ ያደረባቸው ምክንያቱን በሚመረምሩበት ጊዜ ጣሊያኖች የፈረንሳይ ሳዛሪስት ቄሶች ይሆናሉ የሚል ነበር።

ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በደረሰው መጽሐፍ የተጠቀሰው ፍራንኬቲ የተባለው ከአስመራ በእንድ የኢጣሊያ ጋዜጣ ስለደጃዝማች ባህታ ሐጎስ ያወጣው ዘገባ ከዚህ በታች እቀርባለሁ።

ስለእሱ ታማኝነት (ስለባህታ ሐጎስ) ጥርጣሬ ያለው ሰው ቢኖር እንጎሱ ትክክል አይደለም ይባል ነበር። ስለሆነም እሱ ዓመጽ እነሳ፣ ይኸውም የሆነበት በድንገተኛ ንዴት በደል ስለደረሰበት ለመበቀል አይደለም። በታላቅ ክብር ከበውት ሰገነይቲ በሚኖሩ ነጮች ላይ ለረጅም ጊዜ ክህደትና ጥንቃቄ የተሞላበት ጨካኝ እልቂት ካዘጋጀ በኋላ ነው።

እሱ ከእኛ ከጣሊያኖች ደመወዝ ይቀበል ነበር፣ ውድ ስጦታዎች ከእኛ የተቀበለ በቅኝ ግዛት ለማንም ሐበሻ የማይሰጥ ሥልጣን ከእኛ አግኝቶ የነበረ ዲሰምበር 1894 ዓ.ም. ሐላይ ላይ በወታደር ምሽግ ላይ በሰጠነው መሣሪያ እኛን እየተዋጋ ሞቷል።

ከኤርትራ ስለተባረሩ ተናደው የፈረንሳይ ሳዛሪስት ሚሲዮናውያን ተገፋፍቶ ነው ተብሏል። ሊሆን የሚችል ነው። ባሕታ ሐጎስ ከላዛሪስቶች ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበረው። በአኩሩር ቤተክርስቲያን እንዲሰሩ እርዳታ አድርገውላቸው ነበር። በየጊዜው ይጠይቃቸው ነበር፣ ደብዳቤዎች ይጻጻፍ ነበር። ነገር ግን ለክሕደት የገፋፋው ይህ ብቻ ወይም ዋነኛ ምክንያት ሊሆን አይችልም። የተለመደው ዕስታዊ የማታ ውይይት ወደ ጐን ትቶ የመቶ አለቃ ሳንጉዊኔቲ ካሰረ በኋላ ድል እንደሚቀዳጅ በአጭር ጊዜ እርግጠኛ በመሆን ወደ ሐላይ ባመራበት ጊዜ የሚከተለውን ለአከለጉዛይ ሕዝብ ጥሪ አስተላለፈ። ከነዚህ ከባህር ማዶ የመጡ ሰዎች ነጻ እወጣችሁአለሁ መሬታችሁን ወስደው ባዶ ሊያስቀሯችሁ ይፈልጋሉ። እኔ ከራስ መንገሻ ጋር ተስማምቻለሁ። ራስ መንገሻ ብዛት ያለው ጦር ይዞ ወደዚሁ እየገሰገሰ ነው። እስካሁን ያልተነሳሁ መልስ ከሩቅ ቦታ እጠብቅ ስለነበረ ነው። ጥሪውን ሕዝቡ የተቀበለው በጣም በከፍተኛ ስሜት ነው። ለጥሪው ምክንያት የሆነው ማንም ሰው ሊያስተባብለው የማይችለው ፍራንኬቲ ወደ ኤርትራ ያመጣቸው ኢጣሊያውያን ቤተሰቦች በሰራዬ ከጉዶፈላሲ እስከ ጉራዕ እንዲሁም ትንሹ መሬት ባህታ ሐጎስ ከሚያዝበት በአከለጉዛይ ውስጥ ጉራዕ አጠገብ የእርሻ መሬት ከ25 ሄክታር የማይበልጥ ተሰጥቷቸው ነበር። ይህ ጉዳይ ባህታ አስቆጥቶት ነበር። ሰንዐፌ በራስ መንገሻ ድንኳን የተገኙ ማስረጃዎች ውስጥም የደጃዝማች ቁጣ የሚገልጹ ነበሩ። ሶስት ጊዜ ለአጼ ምኒልክ ደብዳቤዎች ጽፎ ጣሊያኖችን ለማጥቃት እንደሚፈልግ ገልፀዋል፤ ይህ ካልተፈቀደለት ምኒልክ ጣሊያኖችን ሰፋሪዎች መሬት ማግኘት የሚችሉት ከሀገሩ ተወላጅ ሴቶች ሲጋቡ ብቻ እንደሆን ብሎ ለኢጣሊያ



መንግሥት እንዲያማልድለት ገልጾ ነበር። ሁለት ጊዜ እሱም ራሱ አጼ ምኒልክ መልስ እየጠበቀ ስለሆነ እንዲጠብቅ፤ መልሱ እንደመጣ ግን ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚነገረው መሆኑን ጽፎለት ነበር። ምኒልክ ይጠብቀው የነበረው መልስ የውጫሌ ውል ኮሚክ የሆነ የአንቶኔሊ አንቀጽ 17 እንዲሰረዝ ነበር። ባሕታ ሐጎስ የጠየቀው ፈቃድ ይሰጠው አይሰጠው አይታወቅም። ሆኖም የተፈተደ መሆኑን ምልክት የሚሆነው በኩዓቲት ጦርነት ጃንዋሪ 13 እና 14 /1895 ዓ.ም. በከፊል ወይም በሙሉ በሥራ ላይ የዋሉ አጼ ምኒልክ ለራስ መንገሻ 35,000 /ሰላሳ አምስት ሺህ/ ጥይቶች መላኩ ነው። ሰፈራን የሚቃወሙ ሰዎች ይኸውላችሁ የእናንተ ሥራ ምናልባት ለሙከራ የተሰጡ መሬቶች ባይሰጡ ኖሮ ባህታ ሐጐስ አይሸፍትም ነበር፤ ለመንገሻ ዕርዳታ አይሰጥም ነበር። በሐላይና በኩዓቲት ድል ለማግኘት የከፈልናቸው በከንቱ የሰው መስዋዕትነትና ገንዘብ ይቀር ነበር ይላሉ በማለት ጽፈዋል።

ማርቲኒ በበኩሉ ለዚሁ ደብዳቤ መልስ ሲሰጥ ከሰላ ይዞ ማሕዲስችን እሸንፎ የተካ፣ ጋላባት፤ ገዳሪፍ የንግድ እንቅስቃሴ ወደ ምጽዋ እንዲመጣ እስተማማኝ ለማድረግ የማይፈለግ ከሆነ የኢጣሊያ አርሶ አደሮች በሀገራቸው በረሃብ የሚሞቱ በኤርትራ መሬት ተሰጥቷቸው ባለንብረቶች እንዲሆኑ ለማድረግ የማይቻል ከሆነ ይኸና የመሳሰሉት ለማድረግ የማይቻል ከሆነ እኛ ምን ልንሰራ ነው በአቢሲኒያ የተቀመጥነው? «እንዲጀኒ» ተወላጆቹ ከራሳቸው ዘር የሆኑ ዘራፊዎች እንድንከላከልላቸው ነውን? ወ.ዘ.ተ. ብሎ ነበር እስተያየቱን የደመደመው።

ከዚህም ሌላ ደጃዝማች ባህታ ሐጐስ ለከህደት ያነሳሳው በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ ምናልባት የፈረንሳይ ላዛሪስቶችም ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህም በሰንዓፈ በራስ መንገሻ ድንኳን የተገኙ ወረቀቶች ፈረንሳይ በእኛ ላይ የምትፈጽመው መሰናክል ማዕከል እንደነበሩ አሳይቷል። በዚሁ ወቅት ከሚሲዮናውያኑም ሌላ እጅ እንደነበረ የኢጣሊያ ጦር ኃይል መጽሔት አትሞ እንዳወጣው ክሎሸት (Clochette) የተባለው ከፈረንሳይ መኰንኖች አንዱ ለባሕታ ሐጐስ መሸፈት እጅ እንዳለበት ከታመኑ የዜና ምንጮች የተገኘ ብሎ አውጥቶ ነበር።

ባሕታ ሐጐስ በቅርብ ጊዜ ነው ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የቀየረ እንደ ባህታዊ ጸሎት ያዝ ነበር፤ ሰገነይቲ አጠገብ ከሚገኘው የላዛሪስት ቤተክርስቲያን ግንኙነት ነበረው። አንድ የሀገሩ ተወላጅ ኢንዲጀኖ ቄስ የነፍስ አባቱ የነበረው ላዛሪስት፤ ዓመጸኞች በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች ሁሉ ተካፋይ እንደነበረና ባህታ ሐጐስ ወደ ሐላይ በሔደበት ጊዜ አብሮ ይሔድ እንደነበረ ተረጋግጧል። ላዛሪስቶች በእኛ ላይ ይደረግ የነበረ ሴራ ያውቁ እንደነበረ ሌላ ማስረጃ የሚሆነው ሻለቃ ቶሰሊ በባህታ ሐጐስ እና በትግራይ ራሶች የተደረጉ ስምምነቶች በሙሉ ዝርዝር ከአንድ ኢንድጀኖ ላዛሪስት ያገኘው ነው። ይኸውም በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነው።

ከሳንጉዊኔቲ ጋር ፎርናሲዮና አርናልዶ የተባሉ ሁለት በሰገነይቲ የሚኖሩ የቴሌ እፕሬተሮች ታስረው ነበር። የአስተሳሰሩ ሁኔታ ሳንጉዊኔቲ ራሱ ሲያወራ ማታ ዲሰምበር 14

መቶ አለቃው ቡና በሚጠጣበት ሰዓት እንደተለመደው ባሁታ ሐጐስ ወገድሙ ሰንጋልና ሌላ ሹም ሆነው በየተኑ ይጋብዛቸው የነበረ ቡና ይወዱት ስለነበረ ከቡናው የበለጠም ያጠጣ ቸው የነበረ የአልኮል አረቂ ይወዱ ስለነበረ ወደ ቤቱ ገቡ። ቡናም እንዳለቀ ባሁታ ሐጐስ ሰንጋል መቶ አለቃውን ዘለው በእጁ ያዙት። ሳንጉኒቲ (Sanguinetti) ለመከላከል ሞከረ። ነገር ግን ወደ መሬት እንዲዘረር አደረጉት፤ ባሁታም አንድ ጉልበቱ ወደ ደረቱ አጥፎ እንዳይንቀሳቀስ አደረገው። መቶ አለቃው እግዚአብሔር ይቀጣሃል ኢጣሊያ ታላቅ ናት አለው። ባህታ ሐጐስም ኢትዮጵያ የበለጠ ታላቅ ናት አለው።

ዲሰምበር 16 በሻለቃ ቶሰሊ የሚመራ ጦር በጀኔራል ባራቲሪ ትእዛዝ የመቶ አለቃ ሳንጉኒቲ ለማስለቀቅ ማዕረባ ደረሰ። የባህታ ሐጐስ በአከለጉዛይ ከብዙ ጊዜ በጣሊያኖች ላይ የታቀደ አመጽ ሊከሽፍ የቻለው ማዕረባ ላይ ሻለቃ ቶሰሊ በሸረበው ተንኮል ነበረ። ሻለቃ ቶሰሊ ካቶሊክና የኦርቶዶክስ ቄሶች ሽምጋዮች ወደ ሰገነይቲ እየተመላለሱ የታሰሩ ሰዎች ለማስፈታት አዲስ ተጨማሪ ወታደሮች እስኪመጡለት ድረስ እሙቆ እንዲዓተት አደረገው። ሐላይ የሚገኘው ከሻምበል ካስቴላትሲ ከሚመራው ጦርም በቴሌፎን ግንኙነት ፈጠረ። በአጠቃላይ 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ወታደር ሊሰበስብ ችሏል። በ18 ሰገነይቲን ለመውረር ተወሰነ። አመጸኞቹ ግን አልተገኙም፤ ለቀው ሔደው ነበር። በማግስቱ ባህታ ሐጐስ ከ1600 የሚበልጡ ተዋጊዎች ይዞ ወደ ሐላይ አምርቶ በድንገት ደርሶ ሐላይ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮችን ትጥቅ ለማስፈታት አስቦ ነበር። ባህታ ሐጐስ ሐላይ እንደደረ ሰ ወታደሮቹ መሣሪያዎቻቸውን እንዲያስረክቡና በሰላም ወደኋላ እንዲመለሱ እንደሚ ፈቀድላቸው ጠይቆ ነበር። አሁንም የጦሩ አዛዥ ካስቴላትሲ ጊዜ ለመውሰድ በቄሶች ሽም ጋይነት ንግግር ተጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ተኩል ተጓተተ። በ7 ሰዓት ተኩል ባህታ ሐጐስ ሁለት መቶ የምሳ /250/ የነበረው በኢጣሊያ ጦር ላይ ተኩስ ከፈተ። እስከ 10 ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ቆጥሎ ኢጣሊያኖች ከሰገነይቲ ወታደሮች እርዳታ ስለደረሱላቸው በ12 ሰዓት ጦርነቱ አልቆ የደጃዝማች ባልቻ ተዋጊዎች ተበታተኑ። ከጣሊያኖች የሞተ የለም። የሞቱትና የቆሰሉ የቀለም ወታደሮች ኢንዲጀኒ አስከር ብቻ ነበሩ፤ 11 የሞቱ 122 የቆሰሉ የተሸለሙ ግን ጣሊያኖች ብቻ ነበሩ። ጣሊያኖች ስለደጃዝማች ባህታ አስከፊንና ከዓማጺያን ስንት እንደሞቱ ያሉት ነገር የለም። ማንቴጋሳ (Mantegazza) እንደዘገበው ጦርነቱ ሲያልቅ 12 ሰዓት ነበር፤ ቀሉ ብሉ ጨልሞ ነበር ኃይለኛ ጉም እንደነበረ ብቻ ጽ ፍዋል። በጥቂት ቀናት ውስጥ የኢጣሊያኖች ትእዛዝ አክብረው 1200 ታጣቂዎች ጠብመን ጃቸውን አስረክበዋል። ለ300 ታማኝ ተብለው የተገመቱ መሣሪያቻቸው እንዲይዙ ተፈቀደ ላቸው።

ደጃዝማች ሰንጋል የባህታ ወንድም፣ የኩዓቲቱ ተወላጅ ፊታውራሪ ተሰሩ ከ600 ታጣቂዎች ጋር ወደ እንጥጮ ራስ መንገሻ ጋር ሸሽተው ገቡ። ልጅ ገብረመድህን የባህታ ልጅ ሃምሳ የሚገመቱ ሰው አስከትሉ ጫካ ገብቶ በሽፍትነት ተሰማርቷል። ስለደጃዝማች ባህታ አስከፊን የት እንደተቀበረ ጣሊያኖች በጽሁፋቸው ባይናገሩም የቀበረው ታማኝ



ጭፍራው የድግግው ተወላጅ ሰጳር ባሕር መሆኑን ከጊዜ በኋላ ጣሊያኖች ጥቆማ ደርሷቸው ችላ ብለውት ነበር። ከነጻነት በኋላ በእንግሊዝ አስተዳደር ዘመን ሰጳር ባህር ሲሞት ለልላ ሰው በታውን አሳይቶ ስለነበረ ከተቀበረበት ተቆፍሮ ወጥቶ በክብር በሰገነይቲ እንደገና ሥር ዓተ ቀብር ተፈጽሟል።

በሐላይ በደጃዝማች ባህታ ላይ የደረሰው ሽንፈት በኃላፊነት የሚጠይቀው ራሱ ደጃዝ ማች ባህታ ነው። ሁለት ቀን ሰገነይቲ ላይ አንድ ቀን ሐላይ ላይ ጣሊያኖች በጠመዱት ወጥ መድ ውስጥ በመግባት በሃሰተኛ ቄሶች ሽምጋይ መልዕክተኞች በመታለሉ ምክንያት ነው። ባሕታ ሐጐስ የካቶሊክ ሃይማኖት የተቀበለው በቅርብ ጊዜ ስለነበረ ለአዲሱ ሃይማኖት የነበረው ፍቅር ለሽንፈቱ ተጽእኖ እንደሚያመጣ ተፈጥራዊ ሕግ ነው። «ነዋሪት» የሆነ ሰው ሁሉ በአዲሱ ሃይማኖት ምክንያት እምነቱ ከመጠን በላይ አክራሪ ስለሚሆን በቄሶችና በሃይማኖት ላይ ያልተቀጠበ እምነት ስለሚያድርበት ተንኰለኞች የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች ቄሶችን እንደመሣሪያ በመጠቀማቸው ደጃዝማች ባህታን ሊያታልሉ ችለዋል። ይህ ባይሆን ኖር በመሠረቱም የቄሶች ሽምግልና ተንኰል መሆኑን ተረድቶ መቀበል አይገባውም ነበር። ከሆነም ከፍጥነት የተለመደው በሕዝቡ እምነት የተጣለበትም ጀግንነቱ እጣሬ እርምጃ ወ ስዶ ማሳየት ይጠበቅበት ነበር። ወደመጨረሻ ሰዓት ጣሊያኖች ራሳቸው አደገኛ ከሆነ ጀምሮ የመጨረሻ ወሳኝ ጥቃት ለመሰንዘር ጥይታቸው እስከሚያልቅባቸው ይጠብቅ እንደነበረ ጽፍ ዋል። ሕዝቡ ጥሪውን ተቀብሉ ከእሱ ጐን ተሰልፎ ነበር። ጣሊያኖች በመሣሪያ ቢበልጡትም ብቁ የሰው ኃይል ነበረው፤ 1600 ሰው ለ250። ቄሶች ጊዜውን ባይገድሉበት ድሉ የእሱ ነበር። ቄሶች ግን ነፍሱን አድነው ይሆናል፤ ሥጋው ግን በጣሊያኖች ዘረኞች እንድትገደል አድርገዋታል። ይህ በመሆኑ ጣሊያኖችን ለማጥቃት ሌላ (Dogali) የዶጋሊ ዓይነት ሽንፈት እንዲቀምሱ ለማድረግ በራስ መንገሻ እና በአጼ ምኒልክ ተቀነባብሮ የነበረ እቅድ ሊከሽፍ ችሏል።



ራስ መንገሻ ከጠላት ጣሊያኖች ሳይቀር በኩንቲት ባሳየው የጦር ታክቲክ አድናቆት ያገኙ፡፡

Il Gen. Oreste Baratieri.

# ሐ. ኩዓቲትና ሰንዓፌ

ጣሊያኖች ደጃዝማች ባህታ ሐጎስን መደምሰስ በመቻላቸው ራስ መንገሻ የደስታ መግለጫ ልኮላቸው ነበር። ሰላም እንደሚፈልጉም ለመነጋገር አንድ ቄስ ወደ ጀኔራል ባራቴሪ ልኮ ነበር። ጀኔራሉ ግን ኃይሉን ለማሳየት የራስ መንገሻ ዋናው ከተማ ዓድዋን ተቃውሞ ሳይገጥመው ያዘ። ከዚህ በኋላ ራስ መንገሻ ብዛት ያለው ጦር 15 ሺህ የሚገመት በመምራት ወደ አከለጉዛይ ኩዓቲት እያመራ መሆኑን ስላወቀ አስቀድሞ ለመድረስ ዓድዋን ለቆ በመውጣት ከዓድዋና ከመራዩ ተነስቶ ኩዓቲትን ይዞ ጠበቀው። ጀኔራሉ «ጥርጣሬ የሞኝነት ነው፤ መዘግየት አደገኛ ነው፤ ትዕግስት የደካማ ምልክት ነው። የሚል መፈክር በመያዝ በጦር ሜዳ ለመፋለም ይናፍቀው የነበረ ምኞቱን አገኘ። ራስ መንገሻም ጣሊያኖችን እስከ ቀይ ባህር ድረስ በማባረር በሚል ዓላማ ነበረ ወደ ኩዓቲት ለጦርነት የቀረበው። የኩዓቲት ጦርነት ቀላል አልነበረም። ራስ መንገሻ ቢሸነፍም ከጣሊያኖች ሳይቀር በጦር ስልቱ ችሎታ አድናቆት ያገኘበት ወቅት ነበር።

ከጥቂት ወራት በፊት ለአጼ ምኒልክ «ንጉሥ ተብዬ ስምን አልጠራም?» ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ለዚሁ ጦርነት ሊገፋፋው የሚችለው እንዴት እድርጌ ንጉሥ ሳድርግህ ሰፊ ግዛት ከሌለህ? ትልቅ ለመሆን ሞክር። እኔም ፍላጐትህን አሟላልሀለሁ ብሎት እንደነበረ ይነገራል።[1] ለጊዜው የነበረ የኤርትራ ሀገረ ገዢ ጉዳዩን ሰምቶ ደርቡሾችን ለመዋጋት ራስ መንገሻ ከተባበረ በጋላባት መሬት እንደሚሰጠው ሃሣብ አቅርቦለት እንደነበረ ይባላል። ጀኔራል ባራቴሪ የፊት አጥቂ ጦር፤ የግራ፤ የቀኝ፤ የመሐል፤ ተጠባባቂ ጦር በማለት መድቦ 4,000 ወታደር አሰልፎ ዝግጅቱን አጠናቆ ነበር። በሐላይ፤ በኩዓቲትና በሰንዓፌ ወሳኝ ሚና የተጫወተው የመድፈኛ ክፍል ኃላፊ የነበረው በኋላም ለብዙ ዓመታት በአዲስ አበባ የኢጣሊያ አምባሳደር ሆኖ ያገለገለው ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ ወይም ወዳጅ ይዞ በነጮች ፊት ከነጮች እኩል በድፕሎማቲክ ግብዣዎች ሳይቀር እንድትገኝ በማድረጉ ወቀሳና ትችት ከፈርዲናንዶ ማርቲኒ የደረሰበት ቺኮዲኮላ ነበረ።

ጀንዋሪ 13 ጧት በ11 ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ የጣሊያን ጦር ጠላትን ለማጥቃት እንቅስቃሴ ጀመረ። 12 ሰዓት የቺኮዲኮላ ተኩስ በመከፈት ጀመሩ። ሐበሾች ምንም ሳያስቡበት በድንገት ተኩስ ብንከፍትባቸውም በፍጥነት እየተወረወሩ በቡድን እየሆኑ ቁጥራቸው እየጨመረ ገደላማ ቦታዎችን በአስደናቂ የመንቀሳቀስ ችሎታቸው እያቋረጡ በመሐድ ቁጥራቸውም እንዳይታወቅባው እየተደበቁ ገደላማ ቦታዎች እንደጋሻ እየተጠቀሙ ዒላማ እንዳ ይሆኑ እየነቁ በየጊዜው እንዳይታዩ እየጠፉ ወደ ጎድጓዳ ቦታዎች እየገቡ ወደፊት ሲገሰግሱ ይታዩ ነበር። ውጊያው በጨበጣ ሳይቀር እየተፋፋመ እያለ በሰፊው ከበባ እየተሞከረ መሆኑን ከባንዳዎች ተነገረን። ከ3ኛ ባታሊዮን ጦር ከበባውን እንዲያከሽፉላቸው፤ ምክንያቱም በሥፍራው የነበሩ ባንዳዎች እያፈገፈጉ ይገኙ ነበር።ሆኖም የተላከ የሻለቃ ጋሊያኖ ጦር ጉዳት ደረሰበት።

1 Vivo Mantegazza:Ibd p.290



ምክንያቱም የጠላት ጦር የወገን በመምሰል አታሏቸው ተኩስ ካቆሙ በኋላ ከበረጃቸው። ነገር ግን ሌላ ጦር ስለተላከ የደረሰብን ሽንፈት በአነስተኛ ጉዳት ለመወጣት ተችሏል። የጋሊያኖ ኩባንያዎች ጉዳት ስለደረሰባቸው በታቸው ባዶ ስለሆነ መሐል የነበረው የሂዳልጎ ጦር በቦታቸው ተተካ፤ በዚህን ጊዜ የመቶ አለቃ ስካልፋሮቶ (Scalfarrotto) ዓረፈ። የጠላት የመከበብ መከራ አልተቋረጠም ነበር። ከበባውም ይመጣ የነበረው ከምስራቅ በኩል ስለነበረ በም ዕራብ የነበረው ጦር ወደ ምሥራቅ እንዲዛወር አደረከሁ፤ መድፎችም ወደ ምሥራቅ እንዲዛወሩ ተደረገ፤ እኔም በታዬን ወደ ምሥራቅ ቀየርኩ። በዚህ ዓይነት ግን የሶስት ዒላማ ሆንን። ሆኖም የእኛ ወታደሮች ለመመለስ ችለዋል። በዚሁ ጊዜ የመቶ አለቃ ሳንጉዊንቲ የመቶ አለቃ ካስቴላትሲ (Castellazzi) እና ወታደር ቤርቶያ (Bertola) ዓረፉ፤ በታውን እየለቀቅን እና እያስለቀቅን ከበባውን እያከሸፍን እን ደገናም እየተሞከረብን ብዙ ጉዳት ከጠላት ላይ እያደረስን እኛም ጉዳት እየደረሰብን የግልና የቡድን ጀግንነት የታየበት ነበር። በዚሁ ጊዜም ከኩዓቲት ሰሜን ከፍተኛ ቦታዎች የሰፈረ የጠላት ብዛት የነበረው ተኩስ ደረሰብን፤ ግን አደገኛ አልነበረም። ጀንዋሪ 13 እና 14 ያለው ሌሊት ጠላት ቀን ያልቀናው ሌሊት በጨለማ ጥቃት ይሞክር ይሆናል ብለን ስጋት ነበረን፤ ሌሊቱ ግን ተኩስ ሳይሰማ አደርን፤ ጧት 14 ጠላት በኃይለኛ ተኩስ ጀመረ፤ ግን ከባድ ጉዳት አላደረሱብንም፤ በምሥራቅም በምዕራብም አቅጣጫዎች ተኩስ ቀጥለው ነበር። ጀኔራል ባራቴሪ ጦርነቱ እንዲያልቅ አይቸኩልም ነበር፤ የሚጠብቃቸውን ስንቅና ትጥቅ ነበረው። ጠላት ግን ቀኑ በተራዘመ ቁጥር እንደሚከፋው ግምት ነበረው። ስለዚህ ለጀንዋሪ 13 ጠቅላላ የማጥቃት እርምጃ እንደሚወስድ ዕቅድ አዘጋጅቶ ነበረ፤ በ14 ማታ አንድ የኢጣሊያ አስከር አስረኛ ሆኖ የነበረ ለማምለጥ ስለቻለ ጠላት ወደ ኋላ ማፈግፈጉን ገለጸልን። ባራቴሪ በ9 ሰዓት ተኩል ከለሊቱ የጦር አዛዦች ስብሰባ ጠርቶ ጠላትን በሄደበት ለመከታተል ተወሰነ። ከትትሉ ቀጥሎ ከቀኑ 7 ሰዓት ተኩል ትኩንዳዕ አጭር ዕረፍት ሆነ፤ ጉዞውም ቀጥሎ ጠላት ወዳለበት ሰንዓፌ ማታው ሳይጨልም ገባን፤ ሰንዓፌም ብዙ ድንኳኖች ተተክለው አየን፤ ድንኳኖቹ በሩቅ በመድፍ ተደበደቡ። በዚህ ጊዜ ጠላት ተደናግጦ መሸሽ ጀመረ። ማታ በጨለማ ጣልያኖች ሰንዓፌ መግባት አልደፈሩም፤ ሲነጋ ሰንዓፌ ሲገቡ ጣል ያኖች ብዙ ዕቃዎች አገኙ። ጠቃሚ የነበሩ ግን ተረስተው ሳይወሰዱ የቀሩ ከላይ የተጠቀሱ የደጃዝማች ባሕታ ሐጎስ፤ ራስ መንገሻና አጼ ምኒልክ የተጻጻፉባቸው ደብዳቤዎች ብቻ ነበረ የተገኙ።

በደብዳቤዎቹ መሠረት ደጃዝማች ባሕታና ራስ መንገሻ አመጽ ማስነሳት ያሰቡትና ራስ መንገሻ ሊደርስ የሚችለው በዲሴምበር 20 ነበረ[1] በጦር ነቱ የተካፈሉ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት 3934 ነበረ፤ የሞቱት 3 የኢጣሊያ መኰንኖች 2 ወታደሮች 90 ኢንዲጂኒ /ኤርትራውያን/ ፤የቆሰሉት ሁለት የኢጣሊያ መኰንኖች 227 ኢንዲጂኒ /ኤርትራውያን/ ነበሩ። ሽልማቶች ለጥቂቶቹ ልዩ ሽልማቶችና የወርቅ ኒሻን፤ አዛዦች የወርቅ ኒሻን ለ69 ልዩ ልዩ ማዕረግ ላላቸው ጣልያኖች እና ለ19 ኢንዲጂኒ የብር ኒሻን ለ29 ጣሊያኖችና ለ179 ኢንዲጂኒ የነሐስ ኒሻን ተሰጥቷቸዋል።

1 .Vico Mantegazza: Ibd p.324

# አቆርደት እና ከሰላ በጣሊያኖች ተያዙ

## መ. አቆርደት፣[1]

ጣሊያኖች በደጋዓሊ ሽንፈት ከገጠማቸው በኋላ ወደ አፍሪካ ከገቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ድል ዓገኙ አቆርደትን ለመያዝ ዲሴምበር 1893 ዓ.ም በደርቡሾች ላይ ባካሄዱት ጦርነት ጊዜ ነው።

ድሉን የተቀዳጁት ራሳቸው ተዋግተው አልነበረም። የቅጥር ተዋጊ የቀለም ወታደር ወይም «አንዲጀኒ» እያሉ የተሰየየ ስም የሚሰጧቸው ለኤርትራውያን ወታደሮች ተጠቅመው ነው። ከዚሁ ዘመን ጀምሮ ለወደፊት ሀገራችንን ለቀው እስከወጡበት ጊዜ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933 ዓ.ም /1941/ ድረስ ጣሊያኖች የሚጠቀሙት እርስ በእርሳችን ለማጨራረስ ነው። ብቻቸውን ሆነው ጦርነት ገጥመው ድል ያገኙበት ጊዜ የለም።

ጣሊያኖች አቆርደትን ለመያዝ በመጀመሪያ ጊዜ ከደርቡሾች ጋር ግጭት ያደረጉት 1890 ዓ.ም ነው። ስድስት ወር ኤርትራ የሚል ስም ከተሰጠ በኋላ ነው። የተካፈሉት በአንድ ሻምበል ፋራ (Captain Fara) የሚመሩ 250 የኤርትራ አስከሮች ነበሩ። አንድ አስከርና ሁለት ቢኒዓመር ሲቪል ነዋሪዎች ተገድለዋል። በዚሁ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች 1ኛ. ሻምበሉ የሳቮያ የወታደር ኒሻን 2ኛ. ሶስት መቶ አለቆች የብር ኒሻን 3ኛ. አንድ መቶ አሰቃ እና ሁለት አምሳ አለቆች የነሐስ መዳይ ኒሻን። በዚሁ መሠረት የባርካ አውራጃ ኤርትራ ስትመሠረት ያለነበረ ቆይቶ ከኤርትራ በኃይል የተቀላቀ አውራጃ ነው።

ጁን 1892 ዓ.ም ሳራ ቤት ላይ በሻምበል ሂዳልጎና የመቶ አለቃ ስፐሬያፊኮ(Cap. Hidalgo Tenent Spreafico) የሚመሩ ወታደሮች ጦርነት ገጥመው 40 ደርቡሾች ተገድለዋል። ሶስተኛውና ዋነኛው የአቆርደት ጦርነት ዲሰምበር 21 ቀን 1893 ዓ.ም ተካሂዷል። ተካፋይ የነበሩት 42 የኢጣሊያ መኰንኖች 33 ተራ ወታደሮች 2106 ኤርትራውያን ነበሩ። የሞቱት ሶስት የኢጣሊያ መኰንኖች አንድ የኢጣሊያ ወታደር 104 ኤርትራውያን ነበሩ የቆሰሉት አንድ የኢጣሊያ መኰንን እና አንድ ወታደር 121 ኤርትራውያን ነበሩ። በኢ ጣሊያኖች ግምት 1000 ማሕዲስቶች ተገድለዋል። በዚሁ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች፣

1ኛ. ኰሎኔል አሪሞንዲ ሜጀር ጄኔራል ተብሎ ተሾሟል። 2ኛ. ባራ ቴሪ ጄኔራል ባልተካፈለበት ትልቁ የኢጣሊያ ኒሻን ትዱስ ማውሪሲዮ ተሸልሟል። 3ኛ. ሌተናል ኰሎኔል ኮርቴዚ ትልቁ የወታደራዊ ኒሻን ሳቮያ 4ኛ. ለሁለት ሻምበሎች ለአምስት የመቶ አለቆች የኢጣሊያ የዘውድ ኒሻን 5ኛ. ለአንድ ሻምበል የወርቅ ኒሻን 6ኛ. የብር ኒሻን ለአሥር ሻምበሎች ለ 6 መቶ አለቆች ለ10 ባለ ሌላ ማዕረጎች። 7ኛ. የነሐስ ኒሻን ለሁለት ሻምበሎች ለ22 የመቶ አለቆች ለአሥራ ሶስት ባለ ሌላ ማዕረጎች ለሰባት «አንዲጀኒ» የሀገር ተወላጆች።

1. V. Mantegazza: Ibd p.145



በኢጣሊያ ፓርላማ የደስታ ንግግሮች ተደርገዋል። የኢጣሊያ ንጉሥ የዘመቻው አዛዥ ለነበረው ለኰሎኔል አሪሞንዲ የደስታ ቴሌግራም ልኳል። የድሉ ባለቤት የሆነው የኤርትራ ተዋጊ ግን የሞተው እና የቆሰለው ጣሊያኖች እንዲሾሙና እንዲሸለሙ ብቻ ነበር። የነሐስ ኒሻን ያገኙት ሰባት አንዲጀኒ ብቻ ነበሩ።

## ሠ. ከሰላ[1]

ራስ አሉላ ኩፊት በዘመተ ጊዜ በከሰላ አካባቢ የሚኖሩ ሀለንጋ እና ሐደንደዋ የተባሉ ጎሣዎች ዘራቸው ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ጸረ ማሕዲስቶች ስለነበሩ ራስ አሉላን እንደ ነጻ አውጭ ነበር የተቀበሉት። ጣልያኖች ከሰላን በተቆጣጠሩ ጊዜ ከላይ የተቀጠሱት ጉሣዎች ሌሎችም ከሱዳን ጋር ከመኖር ይልቅ ከኤርትራ ጋር መተዳደር ይመርጡ እንደነበር የገልጹላቸው እንደነበረ ገልጸዋል። ማንቴጋትሣ የተባለው ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ በደረሰው መጽሐፍ እንደገለጸው ራስ አሉላ ወደ ኩፊት ሲዘምት 10.000 /አሥር ሺህ/ ወታደሮች ነበረው እስማን ዲግማ 8,000 /ስምንት ሺህ/ ወታደሮች አሰልፎ ነበር። እስማን ዲግማ በአባቱ ቱርክ ሲሆን በእናቱ ግን ከሐደንደዋ ስለነበረ በከፊል ኢትዮጵያዊ ነው። ጦርነቱ ከባድ ነበር፤ ሆኖም ድሉ የኢትዮጵያውያን ሆነ፤ 3,000 /ሶስት ሺህ/ ደርቡሾች ተገደሉ፤ በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው የሰው ጉዳት ባይገለጽም፤ ጉዳቱ መጠነኛ እንደነበረ የሚያስረዳ ከኩፊት መልስ ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ ነው ዶጋዓሊ በጣሊያኖች ላይ ድል የተገኘው። በጉጃም በኩልም ንጉሥ ተክለሃይማኖት 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ የሚገመቱ ወታደሮች በመምራት ገላባትን ከደርቡሾች ለማስለቀቅ በተደረገው ጦርነት ታላቅ ድል ተቀዳጅቶ ነበር። ነገር ግን ደርቡሾች ተጠናክረው መጥተው እንደገና ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር ጦርነት ገጥመው ቤተ ክርስትያኖች እያቃጠሉ ብዙ ሰው ስለፈጁ ጣሊያኖች ለመዋጋት ወደ ምዕዋ ተጉዞ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት አቅጣጫውን ለውጦ ወደ መተማ ለመምራት ተገደደ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እንግሊዞችና ግብጾች ከማሕዲስቶች ለተሰነዘረባቸው ብዙ ጥቃቶች ሽንፈት ስለገጠማቸው ማንኛውም ጦርነት አቁመው በመደራደር ብቻ ይገኙ ነበረ። በዚህ ወቅት ነበረ የሱዳን መሪ ማሕዲ በእንግሊዞች፣ በግብጾች፣ እንዲሁም በንጉሥ ተክለሃይማኖት ባገኘው ድል ተዝናንቶ ሱዳንና ኢትዮጵያ ፀረ ኤሮጳውያን ግንባር እንዲፈጠር ፈልጐ የነበረ። ይህ ለማድረግ ግን አጼ ዮሐንስ የእስልምና ሃይማኖት እንዲ ቀበል ሃሣብ ለአጼ ዮሐንስ አቀረበለት። አጼ ዮሐንስ ግን በተለመደ እቢታው ሣይቀበለው ቀረ። ራስ አሉላ ወደ ከሰላ ዘምቶ የተዋጋ፤ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ወደ ገለባት ዘምቶ የተዋጋ አጼ ዮሐንስም ወደ መተማ ዘምቶ ሲዋጋ የሞተው የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር እንጂ የሰው ሀገርን ወር ለ መያዝ አልነበረም። ሙንዚንገር የተባለው ዜግነቱ ስዊስ ሆኖ የምሥራቅ ሱዳን የቦጐስ እና በምፅዋ በግብጽ መንግሥት ስም ያስተዳደር የነበረ ሰው ነው። ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የነበረው ሰው ነበረ።

1 V. Mantegazza: Ibd p. 203-247

ሆኖም ምሁርና ተመራማሪ ነበረ። ግዛቱ ስለነበረው ከቀይ ባሕር እስከ ዓባይ ያሉ ሕዝቦች ታሪክ አንድ መጽሐፍ ደርሰዋል። ይህ መጽሐፍ ጠቃሚነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው። ከመጽሐፉ ጋራ ተያይዞ የነበረ ማፕ በጣም ጠቃሚነት ስለነበረው የእንግሊዝ መንግሥትና የኢጣሊያ መንግሥት ስለ ቀይ ባሕር አካባቢ በሚካለሉበት ጊዜ ይጠቀስ የነበረ ማፕ ነው። በአጭሩ መጽሐፉ የሚያስረዳው ከመጽዋ ወደ ምዕራብ እስከ አባይ ወደ ሰሜን እስከ ግብጽ ያሉት ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው።

ከዚህ በታች ደራሲው የጻፈው ከጀርመን ወደ ጣሊያንኛ ተተርጉሞ ስላገኘሁት እኔም የጣልያንኛ ፎቶ ኮፒና በአማርኛ ትርጉም ከዚህ በታች የማቀርበው ሰንጠረዥ በሚገባ ያስረዳል። ኢትዮጵያ የሰው መሬት አትፈልግም የራስዋን ደግሞ አሣልፋ አትሰጥም የሚል አነጋገር በዜና ማሰራጫዎች ተደጋግሞ ሲነገር እንሰማለን። ነገር ግን ከሱዳን የከሰላ ክ/ሐገር ወይንም የምሥራቅ ሱዳን ክ/ሐገር የሚገኘው 500 ሺህ እስኩዬር ኪሎ ሜትር ሕዝቡንና መሬቱን አሣልፈን ለሰው ሰጥተን የምንገኘው እንጡራ ሐብታችን ነው። ይህ መሬት ለአራት ዓመት በኤርትራ ውስጥ ኤርትራ ተብሎ እየተጠራ በጣሊያን ቅኝ ገዢነት ቁጥጥር ገብቶ ነበረ። የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ግን ከእንግሊዝ ጋር ተደራድረውበት ሀገሩን ለቀው ስለወጡ አሁን መሬቱ የሱዳን መሬት ሆኗል። ሕዝቡም በመቶ ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያውነቱን ረስቶ ዛሬ ሱዳናዊ፡ ዐረባ ተብሎ ይጠራል። ሕዝቡ ኢትዮጵያዊነቱን እንዲያስታውስ የኢትዮጵያዊ ሁሉ ኃላፊነት ነው።

የከሰላ ጦርነት ጁላይ 17/1894 ተካሂዷል። 56 የኢጣሊያ መኮንኖች 41 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 2526 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስድስት/ ኤርትራውያን የጦርነቱ ተካፋይ ሆነው ውለዋል። በጦርነቱ አንድ የኢጣሊያ መኮንን ሲሞት 25 ኤርትራውያን ተገድለዋል። እንዲሁም 40 ኤርትራውያን ቆስለዋል። ከጦርነቱ በኋላ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለኢጣሊያን ንጉሥ የደስታ ቴሌግራም ልከዋል። የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር የጦር ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጦሩ አዛዥ ቴሌግራም ልከዋል። በከሰላ አዲስ የተሠራ ጦር ሠፈር በባራቴሪ ስም ተሰይሟል። በጦርነቱ ምክንያት የተሰጡ ኒሻኖች 1ኛ. ለጀኔራል ባራቴሪ አንድ ወታደራዊ ሣቮያ ኒሻን 2ኛ. እንዲሁም ለጀኔራል አሪሞንዲ 3ኛ. ለሻለቃ ሂዳልጐ 4ኛ. በሻምበል እስፐራያሌኮ 5ኛ. ለሻምበል ሣልሣ የሻለቃ ማዕረግ አግኝቷል። 6ኛ. ሻለቃ ቱሪቶ የቅዱስ ሞሪሲዮ ላዛር ኒሻን፤ 7ኛ. የመቶ አለቃ ፓቮኒ የዚሁ ዓይነት ኒሻን 8ኛ. የወርቅ ኒሻን የተቀበለ ካርዲዮ ማላቮልቲ /ሻምበል/ 9ኛ. የብር ኒሻን አምስት ሻንበሎች ሁለት መቶ አለቆች አንድ ባለሌላ ማዕረግ አራት የቀለም ወታደሮች፤ 10ኛ. የነሐስ ኒሻን ያገኙ አንድ ሻምበል 11 መቶ አለቆች 1 ምክትል መቶ አለቃ 10 ባለሌላ ማዕረጎች 11 አስከሮች ኢንዲጀኒ ፤ 11ኛ. የምሥጋና ወረቀት የተቀበሉ 8 ሻምበሎች 19 መቶ አለቆች 21 ባለሌላ ማዕረጎች። ከጦርነቱ በኋላ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ለጣሊያን ንጉሥ የደስታ ቴሌግራም ልከዋል። የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር የጦር ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚ/ሮች ለጦር አዛዡ ቴሌግራም ልከዋል። በከሰላ አዲስ የተሠራ ጦር ሠፈር በባራቴሪ ስም ተሰይሟል። ከሰላ ከኤርትራ ጋር እንድትቀላቀል ደማቸውን ያፈሰሱ ኤርትራውያን



ሲሆኑ፤ ጣሊያን ግን እርስ በርሣቸው ተሿሹመውበት በመጨረሻ ሀገሩን ለቀው ወጥተዋል። ይሄ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የፈሰሰበት ከሰላ ጣሊያኖች ለአራት ዓመት እስከ 1897 ይዘውት ከቆዩ በኋላ ያለአንድ በቂ ምክንያት ሜይ 1897 ለእንግሊዝ መንግሥት አስረከበው። የአካባቢው ሕዝበ በተለይ ሐለንጋና ሐደንደዋ የተባሉ ጐሣዎች ከኤርትራ ጋር ለመቀላቀል እንደሚፈልጉ እየገለጹላቸው ከሰላን ለቀው ወጥተዋል።

ጣሊያኖች ከከሰላ የወጡበት ምክንያት በወቅቱ በከሰላ ከዋና ጦር ሰፈራቸው ከምፅዋ ሩቅ በመሆንዋ ነው ብለው ቢናገሩም ሐቁ ግን የወጡበት ምክንያት የደርቡሾች ፍራት ነው። በአፍሪካ በሙኖፎ ስም በጣም ተዋቂ ሰው የነበረው ጣሊያኖች በሐሣባቸው ስለሚስማማ በጣም ይወዱትና ያከብሩት የነበረው ጀርመናዊው ስቫይንፉርት (Schweinfurt) ስለ ከሰላ በጣሊያን ወታደሮች መያዝ ከኢጣሊያ ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ ተደርጐለት በሰጠው አስተያየት፤ የከሰላ በጣሊያን እጅ መውደቅ አስደሣችም ነው በጣም አስጊም ሊሆን ይችላል ብሎ ነበረ። ጠቅሎልም ሐሣቡም በማብራራት ደርቡሾች ተስፋ በመቁረጥ የመጨረሻ ዕድላቸው ከመሞከር የማይመለሱ ናቸው ብሎ ነበረ። በከሰላ መያዝ ከፍተኛ ንዴት ሊያድርባቸው ይችላል። በአውሬነት ፀባያቸው እየተመሩ ወሣኝ ትግል ለማድረግ እን ደሚሞክሩ ይጠበቃል። ከሰላን ከኢጣሊያ ለማስለቀቅ 50 ሺህ እስከ መቶ ሺህ ሰው ሆነው ሊመጡ ይችላሉ። በዚሁ ጊዜ በኤርትራ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮች ለአንድ ቀን እንኳን ተዋግተው የመቋቋም ኃይል አይኖ ራቸውም። አብዛኛው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ማሠለፍ ያስፈልግ ይሆናል። ኤርትራ በሙሉ እንዳትጠፋ ያሰጋል ብሎ ከደመደመ በኋላ ጠያቂው በዚህ ጊዜ ጣሊያኖች አደጋ በሚደርስባቸው ጊዜ ብሪታኒያ እርዳታ አትሰጣቸውም ወይ ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ ስቫይንፉርት (Schweinfu..rt) መልስ ሲሰጥ አይመስለኝም፡ ብሪታኒያ ቀጥተኛ የራ ስዋ ጥቅም ከሌላት እርዳታ አትሰጥም፤ ስለዚህ ጣሊያኖች ከብሪታኒያ እርዳታ እናገኛለን ብለው መጠበቅ የለባቸውም ብሎ ነበረ። ይኼ የስቫይንፉርት (Schwe-infu: rt) አስተያየት ነው ለጣሊያኖች ሽብር ፈጥሮባቸው ከከሰላ ሊወጡ የቻሉት። የስቫይ ንፉርት (Schwe-infu-irt)አክራሪ ዘረኛ ጠባብ አስተሣሰብ የነበረው ሰው ነው፣ ጣሊያኖ ችን ከፍ አድርጎ ማቅረብ ይወዳል። እናንተ ጣሊያኖች ታማኝ የሆኑ ባለቀለም ወታደሮች ለመፍጠር ችላችኋል! እንግሊዞች፤ ፈረንሣዮች እኛም ጀርመኖች እንደ እናንተ ማድረግ አንችልም ብሎ ሐሣብ ሲያቀርብ ጣሊያኖች ሣያመዛዝኑ ሐሣቡን በመቀበላቸው በብዙ ስህተት ሊወድቁ ችለዋል። ዘረኛው ጀርመናዊ ስቫይንትፉርት (Schweinfu irt) ወደ አፍሪካ ይሄደው ሀገሩ ጀርመን በአፍሪካ በሰፊው የቅኝ ግዛት ለማስፋፋት እንድትችል ነው።

ይህን ለማድረግ ግን ከሌሎች ሀገሮች ስለተቀደሙቸ እነሱን ማጥላላት ነበረበት። ጣሊያንም የጀርመን ፈለግ እንድትከተል ስቫይንፉርት ምኞቱ እንደነበረ ግልጽ ነው ስቫይንፉርት በአጭር አስተሳሰቡ የአፍሪካ ጎሣዎች አጥንቶ ይሆናል የወታደር ሙያ ግን ያለው ሰው አይደለም። ሌሎች ሰዎች በትምህርትና ሙያ እስትርራቴጂ በመመርኩዝ ኤርትራን ከማሕዲሶች ወረ ራ ለመከላከል ከሰላን መልቀቅ ሳይሆን ከሰላን ይዞ ማጠናከር

ነው ብሏል። ከከሰላ እስከ አትባራ ያለው መሬት መቆጣጠር ከተቻለ የማሕዲስቶች ወረራ እንዲያከትም ማድረግ ይቻል ነበር። ከዚህ ከተሰቀቀሳቸው ግን ለወረራ መንገድ በመከፈት ምቹ እንዲሆንላቸው ብለው የሚጥሩትን በመከልከት የሽዋይንፉርት አስተያየት የተቃወሙ ነበሩ። ከዋንት ከእነ ባርባሮሳ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ጀምሮ ጀርመኖችና ጣሊያኖች መፈቃቀር ነበራቸው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጀርመኖች የዘረኞች ቁንጮ ሳይሆን እንደ ሌሎች ባርባሪያን ሁሉ የበታችነት ስሜት በበረታቸው ጊዜ ባርባሪያን ንጉሥ መሆን እንደማይችል የሚል እምነት ስለነበራቸው ጀርመናዊ መንግሥት ተብለው መጠራት ትተው ሮማዊ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ይጠሩ ነበር። የጀርመን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሆሊ ሮማን ኢምፓየር (Holy Roman Empire) እየተባለ ይጠራ ነበር። ትልቁ የኢጣሊያ ቋንቋ አባት ዳንቴ አሊጌሪ ለእነ ባርባሮሳ ይገዙላቸው ነበር። ጀርመኖችም በሮማውያን ላይ እንደ አምላክ እምነት ነበራቸው። ጣሊያኖችም በጀርመኖች ላይ እንደ አምላክ እምነት ነበራቸው። በዚሁ መልኩ ነው ጣሊያኖች ለሽዋይንፉርት የተናገረውን ሰምተው የሚያሳፍር ሽሽት ከከሰላ የወጡ። ሽዋይንፉርት ስለ አንዳንድ የአፍሪካ ጎሣዎች ስም ዝርዝር ያውቅ ይሆናል እውቀቱ ግን የአንድ ጀርመናዊ ዘረኛ ሰው ከመሆን አያልፍም የወታደራዊ ሞያ ዕውቀት አልነበረውም።

ዛሬ ከአንድ መቶ አመት በላይ በኋላ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በአፍሪካ ከጣሊያኖች በጣም የተሻለ አመራር ይከተሉ እንደነበረ ለሽዋይንፉርት እና ለጣሊያኖች ሊሆኑዋቸው በተገባ ነበረ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ቢችሉ የቀድሞ ተግባራቸው ቢተገሉ ማስረጃ ደስ ባላቸው ነበር። ዛሬ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በአፍሪካ በቀድሞው ቅኝ ግዛቶቻቸው ወዳጅ የሆነ ሕዝብና መንግሥታት አሏቸው እንጂ ታማኝ ሕዝቦች የላቸውም። ጣሊያኖችና ጀርመኖች ግን በዘረኝነታቸው ሆነ ታማኝ ሕዝብ ወይም ሀገር ሊያፈሩ አልቻሉም።

# ትግራይ ተወረረ

## ሬ. የኢጣሊያ በራሪ ጦር፤ የደብረዓይላ ውጊያ[1]

የኩፍቲት ጦርነት ፍጻሜ ምክንያት በማድረግ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ለባራቲየሪ በላከው የደስታ ቴሌግራም ከእንግዲህ ትግራይ ለኢጣሊያ ክፍት ሆናለች፤ ካሲያዝናት የኛ ስንቁና ይሆናል ብሎ ነበረ። ምናልባት በነዚህ ቃላቶች ተደፋፍረው ጀኔራል ባራቲየሪ ራስ መንገሻን ለመያዝ ያደረገው ድካም ከንቱ ስለሆነበት ትግራይን ለመውረር የተጀመረው፤ የጠብ አጫርነት ነበር። ማርች 18/1895 ባራቲየሪ ትጥቅህን ፍታ ብሎ ትእዛዝ ለራስ መንገሻ ይልክለታል «ኡልቲማቱም»። ነገር ግን ራስ መንገሻ በባሰ ሁኔታ የጣሊያንን እንቅስቃሴ ያሰናክል ስለነበረ ጀኔራል ባራቲየሪ መንግሥትን አስፈቅዶ በኩፍቲት ባገኘው ድል የሚደበገር መስሎት በእብሪት ተነሳስቶ ራስ መንገሻን ተከታትለው ለመያዝ ወስኖ በይፋ ማርች 25 ወሰንን ጥሶ በመግባት ዓዲግራትን ያዘ።

1 V. Mantegazza:Ibd p. 353



በራሪ ጦር ወይንም ተወርዋሪ ጦር የተባለው መንገድ ጠራጊ እስከ መቀሌ አሰማራ። ጣሊያኖች ወደ አፍሪካ ሲገቡ ያገር ተወላጆች ወታደሮች በወገናቸው ላይ አይዋጉም ወይንም ደግሞ ፈሪዎች ናቸው በማለት ለውትድርና ብቁ አይደሉም የሚል እምነት ነበራቸው። በአቈርዳት፤ በከሰላ፤ በሐላይ፤ ከኩፍቲት ከተደረጉ ጦርነቶች ኋላ ግን በተቃራኒ ነጭ ሰው በአፍሪካ ለውትድርና ብቁ አይደለም የሚል እምነት ሊያድርባቸው ችሏል። ስለዚህ አብዛኛው ጦርነቶች የሚካሄዱት ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው በማጋጨት ብቻ ነበር። ጠላትም ከጀርባው እናጠቃዋለን ብለው ጣሊያኖች በሻለቃ ቶሰሊ የሚመራ ተወርዋሪ ጦር አራተኛ ባታሊዮን ኢንዲጀኒ ተብሎ የሚጠራው ወደፊት እየገሰገሰ ራስ መንገሻን ቦታውን እየለዋወጠ የሚሰፍርባቸው ቦታዎች ሊከታተል ከቆየ በኋላ በስተጀርባው የተባለው ቦታ የደረሰ መሆኑን ለጀኔራል ባራቲየሪ አስታውቋል። ራስ መንገሻም ይገኝ የነበረው በደብረ ዓይላ ነበረ። ራስ መንገሻም የበታች ሹማምንቶቹ እንዲከላከሉ በመተው ወደ ያልታወቀ ቦታ ሸሽቶ ሄደ። ጣሊያኖች ደብረ ዓይላ ከነበረው የኢትዮጵያ ጦር ጦርነት ገጠሙ። በጦርነቱ ማብቂያ ጊዜ የኢጣልያ ወገን አስራ አንድ ኢንዲጀኒ ኤርትራውያን ሞቱ፤ 30 ቆሰሉ፤ ከጣሊያኖች የሞተ አልነበረም። ጣሊያኖች ራስ መንገሻ ወደ ሳምሬ ሄዷል ስለተባለ መከታተላቸውን አቁመው ወደ አምባላጀ አመሩ።

በደብረ ዓይላ ጦርነት ምክንያት የተሰጡ ሽልማቶች። አዛዥ ለነበረው ለሻለቃ ቶሰሊ የብር ኒሻን እንዲሁም ለሶስት ሻምበሎች ለሶስት መቶ አለቆች ለአንድ ተራ ወታደር ለሁለት ማዕረግ ያላቸው ኢንዲጀኖች የብር ኒሻል። የነሐስ ኒሻል የተሰጣቸው 13 መቶ አለቆች 6 ባለ ሌላ ማዕረግ ጣሊያኖች እንዲሁም 15 ማዕረግ ያላቸው ኢንዲጀኖች ነበሩ።

ከኩፍቲት ጦርነት በኋላ በቀለም ወታደሮች «በኢንዲጅኒ» ብቻ ተጠቅመው ጣሊያኖች ድል በመቀዳጀታቸው የኢጣሊያ መንግሥት በጣም ስላስደሰተውና ስለጣፈጠው የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ (Mocceni) ለጀኔራል ባራቲየሪ በላከው ቴሌግራም ቢያንስ እስከ 2000 /ሁለት ሺህ / «የኢንዲጀኒ» ወታደሮች እንዲመለመሉ ጀንዋሪ 17 ሐሣብ አቅርቦ ነበር።[1]

በደብረ ዓይላ የተዋጉ ኢትዮጵያውያን በበታች ሹሞች የሚመሩ ነበሩ። 1ኛ. የጓጋሜው ተሰፋይ ዕንግዳ 250 ጠብመንጃዎች 2ኛ. ሌሎች ሁለት ሹሞች 600 ጠብመንጃዎች 3ኛ. ቀኛዝማች ኃይለማርያም 400 ጠብመ ንጃዎች 4ኛ. አዝማች አብርሃ በግንስባ የመቶ አለቃ ቤቲኒ የገደለ 50 ጠብመንጃዎች 5ኛ. ደጃዝማች ዘገየ አባንብሩ የደበበ ወንድም ነበሩ። ቁስለኛ ሆነው ከታሰሩ ቀኛዝማች ኃይለማርያም እና የአከለጉዛይ ተወላጅ ጃፍታ ቀኛዝማች ስብሐት ይገኙባቸው ነበር።[2]

1 Vico Mantegazza:Ibd p. 315

2 Vico Mantegazza:Ibd p. 391

# ሰ/ የአምባአላጄ እልቂት

ጣሊያኖች በነበራቸው አስተሳሰብ ራስ መንገሻ በኩዓቲት በመሸነፉ ጦሩ ተበታትኖ ሥልጣን አልባ በመሆኑ እሱንም ተከታትሎ ለመያዝ የኢጣሊያ ጦር በራሪ ኃይል በመመደብ



ትምክህተኛው ሻለቃ ቶሴሊ ያለ አቅሙ በአምባ አለጄ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋራ ጦርነት ገጥሞ በከንቱ ሰው ያስጨረሰ፡፡


Ras Maconnen.

Maggiore Pietro Toselli.

የሚቋቋመው ኃይል ሊገኝ ባለመቻሉ፤ በራስ መንገሻ ሥር የነበሩ መሬቶች ሁሉ ከኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ከኤርትራ የተቀላቀሉ መሆናቸውን ወሰነዋል። የሸዋ ቤተ መንግሥትም በበኩሉ ራስ መንገሻ ያስተለት ሰው ስለሆነ፤ ሸዋ ለራስ መንገሻ ሲል ጦርነት እንደማያስነሳ ስለሚገመት፤ በሻምበል ፕርሲኮ የሚመራ አንድ በራሪ ጦር ከአምባአላጄ አልፎ እስከ በላኩ ደርሶ ነበር። ከዚህም ሌላ የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች በተሰጣቸው ኒሻኖች በአብሪት ተወጥረው ስለነበር በሌላ ርካሽ የሰው ነፍስ ትክሻ የበለጠ ክብርና ዝና ለማትረፍ ጉጉት ነበራቸው። አንድ ፈረንሳዊ ላዘሪስት ቄስ የኢጣሊያኖችን ሃሣብ በማወቁ ካሐሳይና ኩዓቲት ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ለዛሪስቶች የፈረንሣይ ሚስዮናውያን እየወረሱ ያባርሯቸው ስለነበረ በአንድ ኢጣሊያ ከፍተኛ የጦር መኰንን ግፍና አድራጎት ተናዶ (Ah! c'est la guerre que vous voulez? Eh bien vous l'aurez) ብሎ በመናገሩ[1] ወቀሳ ስለደረሰበት ይቅርታ ለመጠየቅ ተገዶ ነበር። ትርጉሙም እናንተ ጦርነት አይደለም የምትፈልጉ? ታገኙታላችሁ ማለት ነው። ሐቅ ነው የተናገረ ሐሰት አልተናገረም ጣሊያኖች ወደ አምባ አላጄ፤ መቀሌና አድዋ ጦርነቶች እያመሩ ነበሩ፤ ቄሱ የተናገረው እንደ ትንቢት ነበረ፤ ቄስ ስለሆነ ግን ይቅርታ እንዲጠይቅ አደረጉት። ፈረንሳዮች ሲባረሩ በአባ ሚኬሌሌ ዳ ካርቦናራ የሚመሩ ትምህርት አልባ የሆኑ የኢጣሊያ ተወላጅ የሆኑ ካፑቺኖች ለኢጣሊያ ታማኝ የሆኑ፤ ኢጣሊያ ድል ባገኘች ጊዜ የቤተክርስቲያኖች ደወል የሚደውሉ፤

1. Vico Mantegazza:ibd p.356





*Padre Michele da Carbonara,*
Controbattè l'azione dei Lazzaristi francesi che hanno sempre favorito gli Abissini

ዝነኛው አባ ሚክለ ዳ ካርቦናራ እና ረዳቶቻቸው ላዘሪስት የፈረንሣይ ሚሲዮናውያንን የተኩ፡፡



ከድል የሚመለሱ ወይም ወደ ጦርነት የሚሔዱ የኢጣሊያ ወታደሮች ቡራኬ የሚሰጡ ተተኩ። ጣሊያኖች ምኒልክ ለጦርነት ተዘጋጅቶ እንደነበረና ብዛት ያለው ጦር በመምራት ወደ ትግራይ እያመራ መሆኑን ይወራ የነበረ ዜና የሚያስጋቸው እንደነበረ ሊገምቱ አልቻሉም። የአምባአላጂ ጦርነት አስፈላጊ አልነበረም። ጣሊያኖች በአብሪት ተወጥረው ስለነበረ ጣታደራዊ አትግቸውን ሊገምቱ አልቻሉም።

ኖቬምበር 30 አሪሞንዲ ለቶሴሊ ስለጠቅላይ አዛዡ ዓላማ ሊያስረዳው ለማጥቃት አስፈላጊ ባይሆንም ጠላት ወደፊት ከገፋ ግን መቋቋም እንደሚያስፈልግ ገልጾለታል።[1] ዲሴምበር 2 ሻለቃ ቶሰሊ ከራስ መኩንን የሰላም ንግግር እንዲያደረግ ቢጠይቅም፣ አክሎ ግን ለጦርነት የመጣ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሰዋል። ቶሰሊም ወዲያውኑ አንተ እያለ መልስ ሲሰጥ «ሰላም የምትፈልግ ከሆነ ወደፊት መግፋት የለብህም» የሚል መልስ ይልክለታል። ሻለቃ ቶሰሊ ከመቀሌ ወደ አምባአላጂ የተንቀሳቀሰው ኖቬምበር 25 ቀን ነበር የሔደበትም ዓላማ ጠላት ፍለጋ ወይም ደግሞ ከጠላት ጋር ጦርነት ለመግጠም ሳይሆን የእንዳመሆኒ እና አካባቢ ሕዝብ ለመረጋጋት እና ቀደም ብሎ አምባአላጂ ይገኝ ለነበረ ለሻምበል ፐርሲኮ ጦር እገዛ ለማድረግ ነበር። ኖቬምበር 26 አምባአላጂ ደረሰ። በ27 ወደ በላጉ ለምርቶ የኢትዮጵያ ጦር ወደፊት እየገፋ መሆኑን ማስረጃ አገኘ። በ28 ይኸንኑ የሚያረጋግጡ ሌሎች ማስረጃዎች አገኙ። በዚሁ ዕለት ጣሊያኖች ከበላጉ ወደ አምባአላጂ ተመለሱ። ከ29 እስከ ዲሴምበር 5 ለአንድ ሳምንት ምንም አዲስ ነገር አልተለፈጠረም። በዚሁ ጊዜ ሻለቃው ለመከላከያ ብቻ ያስብ ነበር። አምባአላጂም በጠላት እንደማትወረር እርግጠኛ በመሆን ግምት ነበረው። ተጨማሪ ጦርም አሪሞዲ እንደሚልክለት ተስፋ ነበረው። ዲሴምበር 5 ሻለቃ ቶሰሊ ድፍረት የተሞላበት ፍተሻ ለማድረግ በሉታና ተካ ማርያም የተባሉ ተራራዎች ጠላት ሰፍሮባቸው እንደሆነ ለማወቅ ሔዶ በጠላት ጦር እንዳልተያዙ አረጋግጦ ተመለሰ። በኢትዮጵያ በኩል የኃይል ሚዛን በሚገባ የሚያውቁ ከመሆኑም በላይ ኢጣሊያ በአምባአላጂ የነበራት ጦር ዝርዝር ማስረጃ ስለነበራቸው የሻለቃ ቶሰሊ ከባድ ድፍረት እያስገረማቸው ነበር ዲሴምበር 6 ቶሰሊ በጦርነቱ ዝግጅት በማድረግ ብቻ አሳለፈው። ዲሴምበር 7፣ 12 ሰዓት ተኩል ከኢትዮጵያ በኩል ተኩስ ተጀመረ። ብዙ ሳይቆዩ ጣሊያኖች አንድ መቶ አለቃ እግሩ ላይ ቆሰለባቸው፣ ወደ አቅራቢያ ቤተ ክርስቲያን ተወሰዶ በ3 ሰዓት የግራ ጦር ግንባራ ቸው ማፈግፈግ ግድ ሆነበት። በ4 ሰዓት የቀኝ ጦር ግንባራቸው በራስ መንገሻና በራስ አሉላ ጥቃት ደረሰበት፣ በ5 ሰዓት ገደማ አጠቃላይ መሸሽ ጀመሩ። የመሸሹ[2] ሁኔታ በአጣዳፊ፣ አሳፋሪ፣ አስቃቂ ሁኔታ ነበር። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ዲሴምበር 3 ራስ መኩንን ስለ ሰላም ለመ ነጋገር በመጠየቅ ለጀኔራል ባራቴሪ ደብዳቤ ልኮ ነበር።

1 Vico Mantegazza: ibd p. 227

2 Vico Mantegazza:ibd p.435-439



ጣሊያኖች ግን በግ ፈዝ በጣሊያንና ኢትዮጵያ በጦርነት ፍልሚያ ስለማይገኙ ስለሰላም ንግግር ማድረግ አጼ ምኒልክ ስለቶየ እስመግባበት ለመነጋገር እስፀ ካልሆነ በስተቀር ለመንገሻ[1] ብሎ ጦርነት አይገጥምም ብለው በመገመት ትኩረት ሳይሰጡት ቀሩ። ከሞት የተረፉት አንዱ የሆነው የመቶ አለቃ ፓጂላ (Pagella) ሲያወራ ከቶሰሊ ጋር ሆኖ በሚሸሹበት[2] ጊዜ በነበረው ትርምስ ሁለቱም ተጠፋፉ። በዚሁ ጊዜ በሚሸሹበት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ከባድ እልቂት ደረሰበት። ሻለቃ ቶሰሊም ይከታተሉት በነበሩት ኢትዮጵያውያን ተገድለው ይሆናል ብሎ ገምቷል። አምባአላጂ ላይ ጣሊያኖች ጦርነት የገጠሙት ከ60,000 /ስልሳ ሺህ /የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋራ ሲሆን እንደ ዶጋሊ (Dogali) ክብር አልተሰጠውም ካለ በኋላ የአምባአላጂ ተዋጊዎች ጥፋታቸውን በመስመር ሆነው ስላልሞቱ ነው ወይ? በማለት በግፈዝ ጽፈዋል።

ከኢትዮጵያ ወገን የተገኘው ሌላ ዜና የኢጣሊያኖቹ እስከሬኖች እንሰትው ከቀበሩት አንድ ባለስልጣን እንዳረጋገጠው ጣሊያኖቹ በሙሉ ራቁታቸውን ነበሩ፣ ልብሶቻቸውን የተወሰዱባቸው ከራሳቸው ኢንዲጆኒ ወታደሮቻቸው ነበር ብሏል። ሻለቃ ቶሰሊ ራቁቱን ነበር፣ የእጅ ጓንት ግን ነበረው። ቶሰሊ የቆሰለው በአንድ ጥይት ደረቱን በስቶ የወጣ ነበር፣ በጎራዴም ቀኝ ጉንጩ ላይ ቆስሏል፣ ግራ እንገቱ ላይ እንደገና በጎራዴ ቆስሏል፣ በሌላ ክፍል ገላውም በሻንጃ ቆስሎ ነበር። ከሻለቃው እስከሬን ዙሪያ 13 የኢጣሊያ ወታደሮች እስከሬኖች ወድቀው ይገኙ ነበረ። 14 ጣሊያኖች ከውጊያ ቦታቸው ሸሽተው ወጥተው በአንድ ቦታ ተገኝተው ሲሞቱ የዶጋሊው የሻለቃ ታንቂሪ ዓይነት የጽሑፍ ገለጣ የሚመሳሰል ነው። ተዋጊዎቻቸውን አስጨርሰው ራሳቸው ብቻ አንድ ላይ ሆነው ከሞት ለማምለጥ ሲሞክሩ ሞተው መገኘታቸው ከዶጋሊ የባለ በመስመር ተለልፈው እንደሞቱ ይቆጠራል። ከጦርነቱ በኋላ የሻምበል ታንቂሪ ዓይነት ወደ ሥፍራው ተልኩ ቢሆን ኖሮ በጦርነቱ ተካፋይ ከነበሩት ጣሊያኖቹ ግማሾቹ በአንድ ቦታ በውጊያ ቦታ ሳይሆን በመሸሽ ላይ እንዳሉ በደረሱበት ቦታ ሲያገኛቸው ከዶጋሊ ያላነሱ ታላቶች ጽፎ ለታሪክ ያስቀር ነበር። ስለዚህ በአምባአላጂም እንደ ዶጋሊ ከጣሊያኖች ግማሽ በመስመር ሆነው ሲሞቱ ሁለት የተማረኩ፣ ሶስት ሸሽተው ያመለጡ ናቸው። 13 የተባለም በስህተት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ከሻለቃ ጋር የተቀበሩት ጣሊያኖች ከሻለቃው ጭምር 14 ሳይሆኑ 20 ነበሩ ፤ በጦርነቱ የተካፈሉ ጣሊያኖች 30 እማይደርሱ እንደነበረ ሲታወስ አንድ ላይ ያልተቀበሩ ቢኖሩ ከሶስት ወይም ሁለት አይበልጡም። የአምባአላጂ እልቂት እንዴት እንደ ዶጋሊ ክብር አልተሰጠውም የሚለው ጥያቄ ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ በአምባአላጂ የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች ከ30 አይበልጡም በዶጋሊ የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች 500 ነበሩ። በዶጋሊ ጣልያኖች በቀለም ወታደሮች ኢንዲጆኒ አልተጠቀሙም ጥቂት የነበሩ አልቆሰሉም አልሞቱም። በአምባአላጂ ግን ከተካፈሉት 2450 ወታደሮች 2420 «ኢንዲጆኒ» ነበሩ ከእነሱ ውስጥም 2000 የመቁሰልና የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል።

1. Vico Mantegazza:ibd p.420

2. Vico Mantegazza:ibd p.434

300 በደህና የተመለሱ ሊሆኑ የቀሩት 120 የት እንደደረሱ አይታወቅም። ጣሊያኖች ግን ያሳዘናቸውና የተጨነቁበት ስለራሳቸው ዜጋ የሆኑ የሞቱ ከ25 የማይበልጡ ብቻ ነበር። ስለኢንዲጀኒ የሞቱና የቆሰሉ ግን እንኳን ሊያዝኑላቸው ሰው እንደሞተ አልመሰላቸውም። ሻለቃ ቶሰሊ ጣሊያኖች ብሔራዊ ጀግና በኢጣሊያ ሕዝብ ከፍተኛ ዝና ያተረፈ በኢትዮጵያውያንም ከፍተኛ ክብር የተሰጠው እንጎሉ ከፍት የሆነው የማደራጀት ችሎታ ያለው፣ ብስለት ያለው ወዘተ ያልተባለለት ነገር የለም። ሐቁ ግን ተቃራኒ ነው ጨዋኝ ቅኝ ገዢዎች ከሚባሉ ጣሊያኖች አን ዱ ነው። 1ኛ. ከመቀሌ ወደ አምባአላጂ በተነሳበት ዕለት አንድ ከሐዲ የሚለው ኢትዮጵያዊ በሜዳው ፈጣን ፍ/ቤት ችሎት አደረኩ ብሎ ወዲያውኑ ተረሽኖ እንዲገደል ፈረደበት። 2ኛ. ራስ መኮንን በተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ ቢያደርጉለት እሬቱ ያለው ብዛት ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት በዕብሪት ተነሳስቶ ጦርነት መግጠም በመድፈሩ በሺህ የሚቆጠሩ የንፁሀን ደም ማስጨረሱ ወንጀለኛ ነው። 3ኛ. ታማኝ የነበ አስተርጓሚው የአዘጋ ተወላጅ የሰጠው አስተያየት ስለቶሰሊ ያለው አድናቆት ቢገልጽዎ ወደ ዋና ጉዳዩ ሲገባ «ትንሽ ተኩስ አንለዋወጥ ነበርን» ራስ መኰንንም የኢትዮጵያ ጦ ዋና አዛዥ እንደልማዱ ደብዳቤዎች ይጽፍ ነበር። ሻለቃም መልስ ይሰጥ ነበር። ራስ መኮን አምባአላጂ የንጉሡ መሬት ስለሆነ እንድትለቅ ብሎ ሲጽፍለት ሻለቃም እኔ ወታደር ነኝ ወደኋላ መመለስ አልችልም አንተ መጀመሪያ ተመለስ በኋላም እኔ ወደ ኋላ እመለሳለሁ»። በዚሁ ጊዜ ሁለቱ ንጉሦች ነገሩን በሰላም ይፈቱታል። የተያዙ ቦታዎች አይለቀቁም በጠላት ፊትም ወደ ኋላ መመለስ አያስፈልገም[1] ብሎ መልስ ሰጥቷል። ራስ መኰንን ብቻ ሳይሆን አጼ ምኒልክም ሰላም ፈላጊ እንደነበረ ጣሊያኖች ራሳቸው የመሰከሩት ነው።[2] 4ኛ. ቶሰሊ የጦር ስልት አዋቂ ቢሆን ኖሮ ለማሸነፍ ባይችልም በነበረው የጦር መሣሪያ የበላይነት እስከ ማታ ለመከላከል ቢችል ሌሊት በሽሽት ሳይሆን በስነ ስርዓት ወደ መቀሌ ሰመመለስ ይችል ነበር። ሻለቃ ቶሰሊ ግን ጥቂት እንደተዋጋ ወደ ሽሽት ነው ያሰበው። አሽናፊ ጦርም በሁኔታው ተቀጥሮ እያሳደደ ሊጨርሳቸው ችሎዋል። ተጠባባቂ ሆኖ ተመድቦ የነበረ በመቶ አለቃ (Ricci) ሪቺ የሚመራው የአስከሮች ኢንዲጀኒ ጦር ወደ ፊት ወደ ውጊያ ገብቶ እንዲዋጋ ያደረገው በ3 ሰዓት ነበረ፣ 2 ሰዓት ጦርነቱ እንደተጀመረ። የመቶ አለቃውም በጦር ሜዳ ላይ ሞተ፣ ከነበሩት መቶው /100/ ወታደሮቹም አምስት ብቻ በሕይወት ተረፉ[3] 5ኛ. በማታ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ቶሰሊ ባስተላለፈው ቴሌግራም ብዙ ብዙ ናቸው የሚያነዱት እንጨት እስከ እድማስ ይታየኛል። በሶስት አቅጣጫዎች የተሰለፉ ሌሎች የሚነዱ እንጨቶች የተየዘበራረቁ ሆነው ይታያሉ የሚል ነ በረ። በዚሁ ጊዜ በኢጣሊያ ሀገር ግን የቅኝ ግዛታቸው ኤርትራ ያንዣበባት የጦርነት አደጋ ዜና ሳይሰማ ሙሉ በሙሉ ሰላም የሰፈረነበት አድርገው ያሳዩ የነበረ ይህ ሁሉ እያወቀ ጦርነተ መግጠሙ የብዙ ሰው ሕይወት ለከንቱ ለሞት የዳረገ ወንጀለኛ ይባላል እንጂ ጀግና ሊባል አይችልም።

1 F.I.C.I : ibd p.157

2 Vico Mantegazza: ibd p.337

3 Vico Mantegazza: ibd p.438



6ኛ. ጣሊያኖች ኢንዲጀኒ እንዲሞቱላቸው የሚፈልጓቸው ወታደሮች ነፍሳቸው እንኳ ላቸው የአንድ ሕፃን ነው እያሉ ሲያፌዙባቸው ይታዩ ነበር። 7ኛ. በአምባአላጂ የሞቱና የቆሰሉ የሰው ቁጥር የተሰያዩ ሰዎች የቀረቡ የተለያዩ ናቸው። ፍቺ እንዳቀረበው[1] እንደሚከተለው ነው። ከሞት የተረፉ ሶስት የኢጣሊያ መኰንኖች አንድ የተማረከ፣ ከኢንዲጀኒ ተዋጊዎች የሞቱና የቆሰሉ ሁለት ሺህ ነበሩ። በጦርነት ተካፋይ የነበረ የቶሰሊ ጦር በአጠቃላይ ሁለት ሺህ አራት መቶ አምላ ነበረ።

## ቀ. የመቀሌ ከበባ

ጣሊያኖች የመቀሌ ምሽግ የሰሩሩት በታሪካዊ መቃብር ቦታ አራት ማዕዘናት የነበሩ ው ጥንታውያን ታሪካዊ መቃብሮችን እየቆፈሩ አጥንቶችን እያወጡ ነበር። የመቀሌ ምሽግ ዳይሰቀቅ የተደረገው የኢጣሊያ የባላይ መኰንኖች ከአምባአላጂ ሽንፈት በኋላ ስብሰባ ርገው ባሳለፉት ውሳኔ መሠረት Giuseppe Galliano.



Maggiore Giuseppe Galliano.

ትምክህተኛው ሻለቃ ጋሊያኖ በአስተያየት ከመቀሌ ከበባ በክብር እንዲወጣ ተደርጎ ዳግም በጦርነት እንዳይካፈል ቃል የገባበትን በማጠፍ በዓድዋ ጦርነት ተካፍሉ በጦር ሜዳ ታምር ይሰራል ተብሎ ሲጠበቅ በመሸሽ ላይ እንዳለ በኢትዮጵያ ወታደሮች ተገድሎ የዘዲኑን ዋጋ ያገኘ

ራስ መኰንን

ሻለቃ ጋሊያኖ የምሽጉ ኃላፊ ሆኖ የቀረው በፍላጎቱ ነበር። ጣሊያኖች በመቀሌ ተከበው ለመቅረት ተጨባጭ ዓላማ አልነበራቸውም የመቀሌ ምሽግ ቢለቀቅ ጀኔራል አሪሞንዲ ያቀረባቸው ምክንያቶች 1ኛ. በወታደሮችና በሀገሪቷ የሞራል ውድቀት ያስከትላል። 2ኛ. እዚያው የተከማቹ ስንቅና ትጥቅ ለማውደም ጊዜ እናገኝም ነበር። ይዘነው ለመሔድም የመጓጓዣ ችግር ነበር።

1 F.I.C.I.

እነዚህ ምክንያቶች ግን ሰንካላ ምክንያቶች ነበሩ። 3ኛ. በተለይ ሶስተኛ ምክንያት ምሽጉ በእጃችን መሆን ለመደራደር የሚሰነዝርባቸው የማጥቃት እርምጃ አንዱ ለማድረግ ታላቅ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚለው ተጨባጭነት የሌለው ከንቱ ጎራ ነበረ። ምክንያቱም አለቃው ዋና አዛዥ እንኳን ለማጥቃት ዕርምጃ የሚውሰድ የነበረው ሃሣብ ወደ ኋላ ወደ ዓዲቀይሀ ለማፈግፈግ ነበር። ዲሰምበር 22 በራስ መኮንን የተላከ አንድ መልዕክተኛ ከአንድ ደብዳቤ ጋር ወደ ሻለቃ ጋሊያኖ ደላካል። ጥያቄውም እንደተለመደው «በንጉሥ ነገሥቱ ስም ይህን መሬት ለቀህ እንድትሔድ እጠይቅሃለሁ ይህን ካላደረክ ግን ጦርነት ለማድረግ ታስገድደኛለህ የክ ርስቲያን ደም በከንቱ ሲፈስ ያሳዝነኛል» የሚል ነበር። ሻለቃ ጋሊያኖም አንተ እያለ የሰጠው መልስ «የእኔ ንጉሥ እዚሁ እንዲህን አዞኛል እኔም ከዚህ አልንቀሳቀስም የፈለከውን አድርግ የማስጠንቀቅህ ግን እዚህ ከእኔ ጋር ምርጥ ጠብመንጃዎችና መድፎች እንዳሉኝ ነው። ሌሎች የተላኩ መልክተኞችም የዚሁ ተመሳሳይ መልስ ነበረ የተሰጣቸው። ጃንዋሪ 3 አንድ ኢጣሊያ አስከሬ በራስ መኮንን አሽረኛ የሆነው የመቶ አለቃ ስካላ (Scala) ልዩ ሠራተኛ የነበረው የራስ መኮንን አዲስ ደብዳቤ ይዞ የመቶ አለቃ ቤርቲኒ ወይም ሌላ መኮንን ለመነጋገር እንዲላክለት የሚጠይቅ ተልኮ ነበር። ነገር ግን ሻለቃ ጋሊያኖ ከሱው የማይቀጥረው የእሱ አስከሬ የነበረው መልዕክተኛ ሆኖ ሊመጣበት ተናዶ ሌላ ትልቅ ሰው አንተ ምን እንደምትፈልግ የሚነግረኝ ላክልኝ እኔም እልክላለሁ የሚል ነበር መልስ የሰጠው ራስ መኮንን አቶ ጊዮርጊስ የተባለው ከ8 የሸዋ ተወላጆች መልዕክተኞች ልኮ ጦርነት የምትፈልግ ከሆነ በአግባብ ለአንተ ጓደኞች የደረሰባቸውን አስታውስ የአንተ ወንድሞችን በመከተል ትልቅ እሆናለሁ ብለህ የምትፈልግ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ እሳይሃለሁ የሚል ነበር።

ለዚህም ጃንዋሪ 7 ሻለቃ ጋሊያኖ የላከው መልስ በደብዳቤ እንደጠላት መስሎህ ነው የጻፍክልኝ እኔ ግን ወዳጅ ሰው ይመስለኝ ነበር አንተ በእኔ መንግሥት ላይ ጦርነት አደርጋለሁ ካልክ እግዚአብሔር የፈቀደው ይሆናል። እኔ ግን የወታደር ግዴጄን እፈጽማለሁ የሚል ነበር። ከጃንዋሪ 8 ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ጦር የማጥቃት እርምጃ ጀመረ፤ በተለይ ጃንዋሪ 10 እና 11 የራስ መኮንን ጦር ኃይለኛ ጥቃቶች ሰነዘረ፤ ከዚህ በኋላ ከበባውን ብቻ በማጠናከር ተወሰነ። የኢጣሊያ ጦር ውሃ በማጣቱ ለችግር ተጋለጠ። ጃንዋሪ 18 ለጭና አሰሽና ሀገሬ ገብ የላከው ቴሌግራም ውሃ ስለሌለን ለመቋቋም አልቻልኩም። ምሽጉን ትተን እንወጣም ነገር ግን ትንሹ የመቀሌ ምሽግ ግዴጄን ይፈጽማል፤ ታላቅ ክብር ተጎናጽፎ ይሞታል። ጉረኛው ሻለቃ ጋሊያኖ በአንድ በኩል ከምሽጉ ለቅቄ አልወጣም እያለ በሌላ በኩል ጃንዋሪ 9 ቀን የበታች ሹማምንቶችን ሰብስቦ እየተጣጋ ከምሽጉ እንደሚወጣ የሚል ሃሣብ ሲያቀርብላቸው «ቪቫ ኢታሊያ» እያሉ ነበረ ሃሳቡን የተቀበሉት። በመሐሉ ግን ከባራቴሪ የተላከ መልዕክተኛ ከአጼ ምኒልክ በፌልተር አማካይነት የተደረደረው ስምምነት በመቀሌ ምሽግ የሚገኙ የኢጣሊያ ወታደሮች መሣሪያዎቻቸውን እንደያዙ እንዲወጡ ደህንነታቸውን እስከ ዓዲግራት ድረስ እንዲጠበቅ ለዚሁ ማካካሻ ግን የኢጣሊያ ጦር እንደ የሰላም ንግግር ለመጀመር መቀበል እንዳለበት የሚል ነበር። የኢጣሊያ ጦር ጃንዋሪ 22



ከምሽጉ ለቆ ወጣ፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተፈላጊ የነበረው የሰላም ንግግር መጀመር ግን ምናልባት የውጫሌውን ውል እንዲሰረዝ ለማድረግ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ በልዩ ልዩ ምክንያት በተለይ የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሰሜን በመገፋቱ ተረስቶ ቀረ።[1]

ጃንዋሪ 8 ነበረ የውሃ ምንጭ በሐበሾች እጅ የገባ ። ሐበሾች ከባድ ጥቃቶች ከሰነዘሩ በኋላ መሬት በመሬት እየተንፉቀቁ የውጭ መከላከያ ድረስ ዘልቀው ደርሰው ጉዳት ቢያደርሱም ራሳቸውም ጉዳት ስለደረሰባቸው አጼ ምኒልክ በምሽጉ ያሉ ኢጣሊያኖች በውሃ ጥም እጃቸው መስጠታቸው ስለ ማይቀር በኃይል መምከር ቀርቶ የከበባው ቁጥጥር ብቻ እንዲጠናከር አዘዙ። በኢጣሊያ የወታደራዊ አታሼዎች ለኢጣሊያ አድናቆታቸውን ገልጸዋል። እንደ ተለመደው የጀርመን ትጉሠ ነገሥት ጉልየልሞ 2ኛ ታላቅ ኒሻን ለሻለቃ ጋሊያኖ ሸልመውታል። የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ የማዕረግ እድገት በጦር ሜዳ መሆ ፈቅደውለታል። አጼ ምኒልክ ይጠይቀው የነበረ 1ኛ. ወሰኑ ቀድሞ ወደነበረው መረብ፤ በለሳ፤ ሙና እንዲሆን 2ኛ. የውጫሌውን 17ኛው አንቀጽ እንዲሰረዝ 3ኛ የሰላም ንግግር እንዲጀመር ሲሆን የጣሊያን መንግሥት ግን ይህ የአጼ ምኒልክ ሃሣብ ሊቀበለው እንደማይችልና እንደማይፈልግ በመግለጽ ለጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ፌብሯሪ 8 በላከው ቴሌግራም 1ኛ. የዓዲግራትና ዓድዋ አካባቢ የኢጣሊያ እንዲሆኑ 2ኛ. የውጫሌውን ውል አጼ ምኒልክ እንዲቀበል 3ኛ. መቀሌና እምባአላጂ በጊ ዜያዊነት በኢጣሊያ አስተዳደር እንዲሆኑ በዚሁ መሠረት ንግግር ለማድረግ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተፈቀደለት መሆኑን የሚል ነበረ። ይህ የኢጣሊያ መንግሥት ሃሳብ ፌብሯሪ 11 ለአጼ ምኒልክ ሊገለጽለት ማንኛውም ንግግር ሊቋረጥ ችሏል። ጠቅላይ ምኒስትር ክሪስፒና የጦሩ አዛዥ ቴሌግራሞች ይለዋወጡ ነበር። ክሪስፒ ሀገሪቷ የምትጠብቀው ደንበኛ ድል የሐበሻ ጉዳይ ለአንዴም ለሁል ጊዜ እንደሚያልቅ እንዲደረግ ሲጠይቀው ባራቴሪም ከኢጣሊያ የሚላኩ ተጨማሪ ወታደሮች በዓዲግራት ከአሰባሰብኩ በኋላ የሸዋ ወታደሮችን ብቻቸው ወይንም ከሌሎች ጋራ ተሰብስበው እንደማወድማቸው ሙሉ እምነቴ ነው በማለት ነበረ ይመልስለት የነበረው።

ጣሊያኖች የውጫሌ ውል ከሚፈቅድላቸው በላይ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው በቂ ወታደራዊ ኃይል አልነበራቸውም ራሱ ባራቴሪ ጃንዋሪ 7/ 1896 ዓ.ም. ለመንግሥቱ በላከው ሪፖርት ብዙ ችግሮች በተለይ ለነጭ ወታደሮች ቁጥር እንዳሉ እንዲሆኑ ከገለፀ በኋላ በራሴ ብዙ እምነት ስላለኝ አይደለም ተጨማሪ ወታደሮች የማልጠይቀው ለሀገሪቷ አዝኜ አይደለም። ነገር ግን ስንቃቸው ለማደራጀት ስለማልችል ነው ብሎ ነበር። በመንግሥት አባላት ማሕከል ከፍ ያለ ልዩነት ነበረ። ጠቅላይ ሚኒስትር ችግሮቹን ሁሉ መወጣት መቻል አለብን ብሎ ሲከራከር ሌላው ግን በድፍን ተጨማሪ ወታደ ሮች እንዲላኩ የሚቃወም ነበር። በዚሁ ጊዜ ከክሪሲፒ መንግሥት አባል ሩዲኒ ሁኔታው በማክረር እንደሚከተለው ገልጧል።

1 F.I.C.L: Ibd p.164

በኢትዮጵያ ደጋዎች የነጭ ወታደር መጠቀም ቀላል ነገር አይደለም፤ ዝግጅት ያስፈልጋል፤ ይኼንን ለማድረግ ደግሞ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም የበጋት ጉዳይ እንደ እንዲጀና ወታደር ነጭ ወታደር ቶሎ አሽከሚችሁ ወደ ጦር ሜዳ መላክ አትችሉም። ስለዚህ ነው ጀነራል ባራቴሪ መንግሥት የሚልክለትን የነጭ ወታደር እንዲላክለት ያልፈለገው፤ ይህ ሁኔታ ለእኛ እንደማስጠንቀቂያ ነው። እኛ ልጆቻችን ለድል የሚያበቃቸው እስፈላጊውን ሁሉ ላናሟላላቸው በገልካቸው ለሚደርስባቸው ሁሉ በኃላፊነት እንጠይቃለን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለሟሟላት ደግሞ ብዙ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው ብሎ ነበር።

## በ. የዓድዋ ጦርነት፤

የዓድዋ ጦርነት ሽንፈት ማስቀረት ይቻል ነበረ እየተባለ ብዙ ተተችቷል። ጀነራል ባራቴሪ ወደ ኋላ ወደ ዓዲ ቀይሕ ማፈግፈግ አስቦ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ፌብሯሪ








፣: P. Antonelli.

አፄ ምኒልክ እና ጣሊያኖች አማክረዋቸውም የኢጣሊያ ክፍተለ ግዛ ያሸዋ ፖለቲካ አራማጆች።







Menelic all'apogeo della sua potenza

በዓድዋ ጦርነት ተፋላሚዎች



Generale Oreste Baratieri



Regina Taitù.



Ras Maconnen.

25 ቴሌግራም ከላከለት በኋላ ግን ያላመነበት ጦርነት ከፍቶ ለሽንፈት ተዳርገዋል። ስለዚህ ለሽንፈቱ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት ባራቲሪ ሳይሆን ክሪስፒ ነው የሚሉ ወገኖች ብዙ ናቸው። ይኼንን ወቀሳ ያስጣ አብዛኛውን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጀነራል ባራቲሪን ለመፍረድ በአስመራ ተሰይሞ የነበረው የጦር ፍ/ቤት ነው። ጀነራል ባራቲሪ ገና ከሜይና ጁን ወራት 1895 ዓ.ም ጀምሮ በመኸር ወራት ከምኒልክ ጋራ ጦርነት እንደሚኖር ለመንግሥቱ ያስጠነቅቅ ነበር። ዳሩ ግን በየጊዜው የሚልካቸው ደብዳቤዎችና በሚልካቸው ቴሌግራሞች ወደ ሀገሩ እንዲመለስ እና በሌላ ሰው እንዲተካ ደጋግሞ ከመጠየቅ ሌላ ስለ ሀገሩ ችግር ወይንም በሰላማዊ መንገድ ወይም በጦር ሜዳ ለመፍታት የነገሩ ሁኔታ በተጨባጭ በማገናዘብ በደረሰው ወታደር ይጨመርልኝ ስንቅና ትጥቅ ይጨመርልኝ ከማለት በቀር በተግባር የመጨረሻ መፍትሔ የሚሆን ሐሳብ ለመንግሥት ሊያቀርብ አልቻለም። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ሌሎችም የበኒ አባሎች ኢጣሊያ የምትፈልገው የማያዳግም ታላቅ ድል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታ መሆኑን በተደጋጋሚ ይገልጹለት ነበር። ለምሳሌ ጁን 7 ባራቲሪ በፃፈው ደብዳቤ «መንግሥታችን ከአጼ ምኒልክ ጋራ ሰላም ለማድረግ የሚቻል መሆኑን እምነት እንዳለው አላውቅም ወይንም ለምምከር አቅድ እንዳለው አላውቅም፤ አጼ ምኒልክ ሁኔታው እንደሚያመቻቸው የእኛ የመስፋፋት ዓላማ ያሰፈራቸዋል፤ ምናልባትም የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት ሰላም ቢደረግ ፈላጊው ይሆናል። እኛ በጦርነት አሸንፈን የያዝናቸውን መሬቶች ለመመለስ እንችላለንን? እኛ ብዙ ባሪያዎች ከወላጅ ይዞ የተመለሰ ሽፍታ ጋራ የሰላም ንግግር ማድረግ እንችላለንን?» ብሎ ፅፎ ነበር። [1] ጁን 22 በላከው ሌላ ቴሌግራም የሥራ መልቀቂያ ለመጠየቅ የበታሁት የምጠይቀው ነገር ስለማይፈጸምልኝ ነው ካለ በኋላ አሁን የምጠይቀው ያሉኝ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት እንዳለ እንዲሆን፤ የኢንዲጄኒ ወታደሮች ብዛት እንዲጨምር ነው ብሏል። [2] ባራቲሪ ለመመካከር ወደ ኢጣሊያ ተጠርቶ 1000 የኢንዲጄኒ ወታደሮች እንዲመለመሉ 700 የመንገኛ ከብቶች እንዲገዙ ተፈቀደለት [3] ባራቲሪ የጦርነት ደመና የሚያንዣብብ መሆኑን ስለተረዳ መንግሥት ላያስፈቅድ የሸዋ ጦርን ለማውደም 7ኛ እና 8ኛ ባታሊዮን እንዲጀኒ መልምሎ አቋቁሞ ነበር። ምክንያቱም በአፋጣኝ አንድ እርምጃ ካልተወሰደ ኢጣሊያ በአንድ ትልቅ ጦርነት አዘቅት ልትወድቅ ትችላለች። በዚህ ጦርነት በአሸናፊነት እንደምንወጣ ባያጠራጥርም የሚጠይቀው ወጪ ለመገመት ግን አዳጋች ይሆናል። ሁለት መንገዶች ከፊታችን ተደቅኗል ሰላምና ጦርነት። እኔ በሰላማዊ መንገድ ችግሩ ለመፍታት አመርጥ ነበር።

ነገር ግን በቀጥታ ከንጉሡ ነገሥቱ ሆነ ወይንም አንድ ራስ ለምሳሌ ራስ መኮንን ሥልጣን እንዲይዝ አድርገን፤ ኢትዮጵያ የውጫሌ ውል እንድትቀበል የቅኝ ግዛታችን ወሰን ከመቀሌ በስተደቡብ እንዲሆን ለማድረግ መምከር ያስፈልጋል።

1. E.Bellavita Ibd p. 193

2. E.Bellavita Ibd p. 194

3. E.Bellavita Ibd p. 197



በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ 4ቱ የኢጣሊያ ብሪጋዴር ጀነራሎች
ዳቦር ሚዳና አሪሞንዲ በጦር ሜዳ የተገደሉ
አልበርቶኔ በዓድዋ ተማርኮ አዲስ አበባ እስረኛ ሆኖ የቆየ ኤሌና ከዓድዋ ጦር ሜዳ በሸሸበት ጊዜ የቆሰለ



I QUATTRO GENERALI BRIGADIERI DI ADUA.
Gen. Vittorio Dabormida (medaglia d'oro). 2. Gen. Giuseppe Arimondi (medaglia d'oro).
Gen. Matteo Albertone 4. Gen. Giuseppe Ellena
(Civica Raccolta delle Stampe - Milano).

[1]ለዚሁ ፕላን የኢጣሊያ መንግሥት መልስ ባይሰጥም በተለይ በአሪሞንዲ የሚመራ የወታደሮች አስተሳሰብ ግን ከደብረ ዓይላ ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ችግር የራስ መንገሻ ጦር ተሸንፎ ተበታትኖ እንዲስቀረን ሁሉ የሸዋ ጦርም በድፍረት ወደ ደቡብ ገስግሠን የምኒልክ ጦር ሳይደራጅ ደርሰን ድምጥማጡን ልናጠፋው እንችላለን የሚል እምነት ነበራቸው[2]። ይህ ግን ጣሊያኖች በሕልማቸው እንደታየያቸው የሚገመት እንጂ ወታደራዊ አቅማቸው የሚፈቅድላቸው አልነበረም።

ሻለቃ ቶሰሊ ወደ አንባአላጂ መሄድ የቻለው ለወታደራዊ ግደጅ ታዞ ሳይሆን ራሱ በተደጋጋሚ ለጀነራል አሪሞንዲ በጠየቀው መሠረት ነበር[3]።

የኢጣሊያ መንግሥት በወቅቱ የነበረው የኢኮኖሚ ችግር ለጦር ዝግጅት ገንዘብ መጨመር ስላልቻለ ከአጼ ምኒልክ ጋራ ለመስማማት ይዞታውን ማጥበብ ነበረበት። ይህ ባለመደረጉ ጣሊያኖች የስራቸውን ውጤት አገኙ። ጣሊያኖች በደረሰባቸው አሳፋሪ ሽንፈት የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ቡድን ጉድለት አይደለም ኃላፊነቱን የምትወስደው መላው ሀገሪቱ ናት።

ራስ መኰንን ከአጼ ምኒልክ የሠላም ንግግር እንዲያደርግ ታዞ ወደ ትግራይ ሲሄድ ባራቴሪ በፈልተር አማካኝነት በቀጥታ የሰላም ንግግር እንዲደረግ ደብዳቤ ሲደርሰው ዲሴንበር 3 የራስ መኰንን ደብዳቤ እንደደረሰው በጀነራል አሪሞንዲ በኩል ባስተላለፈው ቴሌግራም ለንግግሩ ለሻለቃ ቶሰሌ ሙሉ ስልጣን የሰጠው መሆኑን ከገለፀ በኋላ ንግግሮች በጥንቃቄ መከናወን እንዳለባቸው አስጠንቅቆ ንግግር ይደረግ የሚለው ሐሳብ የማታለያ ዘዴ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩልም የሰላም ንግግር ውጤታማ የሚሆነው እኛ ኃይላችንን ስናሳይ ብቻ ነው ብሏል።[4]

ዲሴምበር 3 ባራቴሪ የሰላም ንግግር እንዲደረግ በቀጥታ ለራስ መኰንን በጀነራል አሪሞንድ አማካኝነት ደብዳቤ ፅፎ ነበር፣ ደብዳቤው ግን ጦርነቱ ስለተጀመረ ለራስ መኰንን አልደረሰውም። ችግሩ ባራቴሪ ስለ ንግግሩ ጥርጣሬ ሲኖረው አሪሞንዲ ግን አያምንበትም ነበር፣ ሻለቃ ቶሰሊም በባሰ ሁኔታ አያምንበትም ነበር።[5]

ዲሴምበር 3 ራስ መኰንን በቀና መንፈስ ከሻለቃ ቶሰሊ የጻፈለት ደብዳቤ የሰጠው መልስ የአብሪተኛ በባዶ ጉራ ምልክት ነበረ።[6]

1. E.Bellavita Ibd p. 206
2. E.Bellavita Ibd p. 206
3. E.Bellavita Ibd p. 206
4. E.Bellavita Ibd p. 212
5. E.Bellavita Ibd p. 214
6. E.Bellavita Ibd p. 214



ዲሴምበር 6 ከምሽቱ 12 ሰዓት ሻለቃ ቶሰሊ ለጀነራል አሪሞንዲ በጻፈው ደብዳቤ «ራስ መኰንን ትላንት በጻፈው ደብዳቤ እኛን ለማስፈራራት ሐሰት የተናገረ ይመስለኛል፣ ንጉሡ ዓዘቦ የደረሰ አይመስለኝም። ንጉሡ አሻንጌ ደርሷል ብሎ ራስ መኰንን ሐሰት የተናገረ ይመስለኛል። የራስ ስብሐት ሁለት ሰላዮች ንጉሡ አሻንጌ እንደሚገኝ አረጋግጧል። ምናልባትም አልደረሰ ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በበኩሉ በኖቬንበር ወር «ትግራይ ከእንግዲህ ከኤርትራ ጋራ ተቀላቅሏል» እያለ ጉራውን ያሰማ ነበር።

ጀነራል አሪሞንዲ ባራቴሪ ባይከለክለው በኢትዮጵያ ተዋጊዎች ባለው ንቀት የቶኑጣ ወደ ደቡብ ገስግሶ ሳስታን በኢጣሊያ ቁጥጥር ለማድረግ አስቦ ነበር። የሚላኖ «ራዲካልስ» የሚባሉ ፀረ ቅኝ አገዛዝ አቋም የነበራቸው ወገኖች እንደ ሚርካቴሊ የተባለው ከዕንጣሉ በደብረ ዓይላ ጦርነት እስረኛ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አነጋግሮ ያገኘው መልስ «ይህ ጦርነት ቀላል ነው፣ ዋናው ጦርነት ከአንድ ወር ከ12 ቀን በኋላ ታገኙታላችሁ» ብለው እንደተናገሩ ዘግበዋል። በተለይ የዓይባ ቀኝአዝማች ኃይለማርያም የተናገረው ቃል ብሎ የወጣው «ሸዋ ለጦርነት ዝግጁ ነው። ጦርነቱም ኃይለኛ ነው የሚሆነው» የንጉሡ ወታደሮች ሁሉም ጠብመንጃ ታጥቀዋል ብዙ ጥይትም መድፎችም አሏቸው «ብዙ ጊዜ የጦር ልምምድ ያደርጋሉ» ብለዋል።[1]

የኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብላንክ ኖቬንበር መጨረሻ «በኤርትራ ሁሉ ነገር ደህና ነው ሰላም ሰፍኗል» ብሎ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒም ኃላፊነት በጐደለው አነጋገር «በአፍሪካ ጦርነት እንደኛ ትልቅ ሀገር የሚያሰጋው አይደለም» ብሏል።[2]

ሻለቃ ቶሰሊ ከአቅሙ በላይ የሆነ አደጋ አንዣብቦ እያየ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ሲገባው ጦርነት እገጥማለሁ ብሎ መሞከሩ ጀግንነት አይባልም በራሱና በሌላ ሰው ሕይወት የተጫወተ ወንጀለኛ ነው። ወደ አምባአላጂ የሄደው በፍቃዱ ነው። አሁንም ከአንባላጂ ለቆ ለመውጣት የሚከለክለው ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያ ሠራዊት ብዛት ከመቶ ሺህ በላይ ነው የሚለው አባባል የኢጣሊያ መንግሥት የተጋነነ ነው ብሎ አልተቀበለውም ነበር። እንደዚሁም ጀነራል ባልዲሴራ ባራቴሪን ለመተካት ወደ አፍሪካ ከመሄዱ በፊት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለማሸነፍ የሚያስፈልጋት የወታደር ብዛት ተጠይቆ 40.000 ያስፈልጋታል ብሎ የሰጠው አስተያየት የተጋነነ ነው ብሎ አልተቀበለውም ነበር።

ጣሊያኖች እኛን አንጎላችን የአንድ ሕፃን ልጅ ነው ብለው ሲገምቱን ራሳቸው በተለመደው የክህደት ፀባያቸው ራስ መኰንን ግዛቱን ሐረር ትቶ ትግራይ በሚገኙበት ጊዜ ሐረር በወታደር አልተጠበቀችም ብለው በመገመት በዘይላ የእንግሊዝ ሶማሊያ በኩል ሐረርን ለመውረር አስበው ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ግን ከፈረንሳይ መንግሥት ጋራ መጣላት ስለማይፈልግ ጥያቄያቸውን ሳይቀበለው ይቀራል።

1. E.Bellavita Ibd p. 225
2. E.Bellavita Ibd p. 227

እንደገና ከመቀሌ ከበባ በኋላ[1] ጥያቄያቸውን አሻሽለው በሶማሌላንድ ሳይቆዩ ለማለፍ ብቻ ብለው ይጠይቃሉ። አሁንም የእንግሊዝ መንግሥት ሳይቀበላቸው ይቀራል። ወእንግሊዝ ሳይፀንላቸው ሊቀር በፈረንሳይ ግዛት በጅቡቲ በኩል ለማለፍ እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃሉ። የፈረንሳይ መንግሥት ጣሊያኖች ከጀርመኖች ጋራ የሚያስተሳስራቸው ብትሪፕል አሊያንስ። እንዲወጡ ቅድመ ሁኔታ ስለጠየቃቸው ሕልማቸው ሳይሳካላቸው ይቀራል።

በመጨረሻም በአሰብ በኩል ለመግባት እቅድ ያወጣሉ ይኸንን ዘመቻ የሚመራ በችሎታው በጣም የተመሰገነ ኰሎኔል ፒታሉጋ (Pittaluga) የተባለው ተመርጦ ከተወና በኋላ ችግሩን ሊወጡ ባለመቻላቸው ውድቅ ሆና ቀርቷል። እነዚህ ሁሉ እቅዶች ሲሞከሩም ጥሩ ውጤት ሊያመጡ እንደማይችሉ የታወቀ ነው። ተሞክሮ ቢሆንም በራሳቸው ወታደሮች ሳይሆን እንደልማዳቸው በእንዲጀኒ ኤርትራውያን ተጠቅመው ኢትዮጵያን ፊት ለፊት ሲያቅታቸው በጀርባዋ ሊወጓት ነበር። ስለዚህ የዓድዋ ድል ድርብ ድል ነው። ይህ ሁሉ እቅድ የወጣው ደግሞ በትልቁ ጠቅላይ ሚኒስትራቸው በክሪስፒ ነው። ከመቀሌ ከበባ የተለቀቁ ወታደሮች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ እንጂ እንዳይዋጉ የሚል ቃል በውሉ ላይ ገብቶ ነበር፣ ነገር ግን ቃላቸውን አላከበሩም። ጣሊያኖች ከመቀሌ ሲለቀቁ ንግግር እንዲደረግ ቃል ገብተው ነበር። ነገር ግን ቃላቸውን አላከበሩም። እጼ ምኒልክ ከተለቀቁ ወታደሮች ዘጠኝ መኰንኖችና አንድ ባለሌላ ማዕረግ በመያዣ ይዞ አቆይቷቸው ነበር። ከትንሽ ቀን በኋላ ግን ከእቴጌ ጣይቱ የተላኩ መልእክተኞችና አንድ የእጼ ምኒልክ ደብዳቤ ይዘው ስለ ሰላም ንግግር እንዲደረግ የሚጠይቅ ወደ ጀኔራል ባራቴሪ ተልከው ነበረ። በዚሁ ጊዜ ጀኔራል ባራቴሪ ሻለቃ ሳልሳን ወደ እጼ ምኒልክ ስለንግግሩ ጉዳይ ለማወቅ ላከ። እሱም ሲመለስ እጼ ምኒልክ እርግጥ ሰላም ይፈልጋል ነገር ግን ጦርነት የሚፈልጉ ወገኖች ስላየሉ ምንም ማድረግ አልቻለም የሚል መልስ ይዞ ሲመጣ ባራቴሪ ፌብሯሪ 13 ለእጼ ምኒልክ የፃፈው ደብዳቤ «ስለ ሰላም ለመነጋገር የቀረቡት ቅድመ ሁኔታዎች የውጫሌ ውል እንዲሰረዝ የኢጣሊያ ባንዲራ ያውለበለበበት ቦታዎች ለኢጣሊያ እንዳይሆኑ ለማድረግ ተቀባይነት የለውም። የሚሉ ስለሆነ እርሶን ለማስደሰት ስለ ሰላም ለመነጋገር ሻለቃ ሳልሳን ላኩሎት። ትክክለኛ ነገር ለእኛም ለእርሶም የሚሳካ መስሎኝ ነበር። አሁን ስለሰላም ንግግር ጉዳይ አብቅቷል። ሁላችን የመሰለንን ለማድረግ ነፃ ነን» የሚል ነበር። ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ደጋግሞ ሰላም መፈለግ የደካማነት ምልክት ነበረ የተረጎሙት። በዚሁ መሠረት ኃላፊነት በጎደለባቸው ውሳኔዎች ብዙ ሕዝብ በከንቱ እንዲያልቅ አድርጓል።

ፌብሯሪ 28 የኢጣሊያ ጀኔራሎች ስብሰባ ተቀምጠው ዋና አዛዥ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ጠይቀዋቸዋል። ሀ/ ከወጣት ጀኔራሉ አልቤርቶኔ ተጀመረ። ወደ ኋላ ማፈግፈግ የማልቀበለው ነው ወደ ኋላ ማፈግፈግ እንደ ተሸነፍን ይቆጠራል ጠላት እንዲያጠቃን መጋበዝ ነው በማለት ንግግሩን ጨርሷል ለ/ ሁለተኛ ተናጋሪ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ነበረ ወደ ኋላ ማፈግፈግ የወታደሮችና የሀገሪቷ ሞራል ይነካል፣ ከጋጠመ ማጥቃት ይመረጣል ብሏል።

1. E. Bellavita Ibd p. 257



ሐ/ ሶስተኛ ተናጋሪ ያቀርደቱ ጀግና ብለው የሚጠሩት ጀኔራል አሪሞንዲ ነበር፣ ለቅኝ ግዛታቸው ኢውሮጳውያን በቁጥር አነስተኛ ሆነው ነበር ሁል ጊዜ የተዋጉ የእኛም እንደዚሁ ነው። የተሻለ መግሪያና መለዋወጫ ስላለን፣ የኢጣሊያ ወታደሮች ጀግንነትና ዲሲፒሊን፣ የመተኮስ ችሎታቸው የቁጥራቸው ማነስ ይተካል። ጊዜ ማባከን አያስፈልግም ጥሩ አጋጣሚ እያመለጠን ነው፣ ጠላት በአምባአላጂና በመቀሌ ያገኛቸው ድሎች ተዝናንቶ ወደ ኋላ ለመሸሽ ነው የሚያስበው። በዚሁ ዓይነት ጦርነቱ በጠላት አሸናፊነት በእኛ ተሸናፊነት አለቀ ማለት ነው። የጠላት ወታደሮች ቁጥራቸው 80.000 እንኳን ቢሆኑ ስንት ናቸው በጠብመንጃ የታጠቁ? ከ50 ወይም 60 ሺህ አይበልጡም። ሰላዮች ማጋነን ይወዳሉ። እንደሚታወቀው ብዙ የሐበሻ ወታደሮች ምግብ እናመጣለን ብለው ወደ ተምቤን ሄደው ወደ ሀገራቸው ይሄዳሉ እንጂ ወደ ጦር ሜዳ አይመለሱም። ሁሉም እንደሚያውቀው የሸዋ ሰዎች ጥሩ ወታደሮች አይደሉም ፈሪዎች ናቸው፣ የሴት ፀባይ አላቸው። ቆርጠን እያጠቃን ወደ ዓድዋ ብንገሰግሥ ፈጥነው ሸሽተው ይጠፉ ነበር። ወሳኝ ድል እንኳን ባናገኝ ጠላት እንዲሸሽ በማድረጋችን በከፊል እንዳሸነፍን እራሳችንን እንቆጥራለን። ስለዚህ ድል ለመቀዳጀት ወደ ዓድዋ ወደ ፊት መሄድ ይገባናል ብሏል። መ/ ጀኔራል ኤሊና ከኢጣሊያ በቅርብ ጊዜ የመጣ እንደመሆኑ መጠን እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ አጥቅተን ታላቅ ድል መቀዳጀት አለብን ባይ ነበር።

ስለዚህ የጀኔራል አሪሞንዲ ንግግር ሙሉ በሙሉ ደጋፊ ነበር። ጀኔራል ባራቴሪ ሰላዮች በአንድ ቃል እንደተናገሩት የኢትዮጵያ ጦር ወደ አክሱም ሄዷል፣ ራስ ወሌ ሞቷል፣ እጼ ምኒልክ ታሟል የሚሉ ስለሆነ ወደ ዓድዋ ለመንቀሳቀስ ወስኛለሁ ብሎ ነገራቸው። ፌብሯሪ 29 ማታ በ3:00 ሰዓት ከሳውራ ወደ ዓድዋ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ሲንቀሳቀሱ ጣሊያኖች 20.120 ወታደሮች ነበሯቸው የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው በሶስት ጦር ግንባር ተከፋፍሎ ነበር።

ማርች አንድ ቀን 1896 ዓ.ም. በእኛ መጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. የአንደኛ ጦር ግንባር የግራ ጦር ግንባር በጀኔራል አልበርቶኔ (Albertone) የሚመራ የኢንዲጀኒ ብርጌድ ነበር።

ሁለተኛ ጦር ግንባር የመሀል ጦር ግንባር በአቀርደቱ ጀግና የሚል ቅፅል የተሰጠው በጀኔራል አሪሞንዲ (Arimondi) የሚመራው የኢጣሊያኖች ብርጌድ ነበረ።

ሶስተኛ ጦር ግንባር የቀኝ ጦር ግንባር በጀኔራል ዳቦርሚዳ (Dabormida) የሚመራ ብርጌድ ነበር።

አራተኛ ብርጌድ የደጀን ጦር ከጀኔራል አሪሞንዲ በስተኋላ የተሰለፈ በጀኔራል ኤሊና (Elena) የሚመራ ብርጌድ ነበር።

የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል ባራቴሪ (Barattieri) ነበር የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀከል ነው ለማለት አያስደፍርም። ጦርነቱ የተካሄደው በአንድ ወገን በኢትዮጵያ ወታደሮች በሌላ ወገን የኢጣሊያ ወታደሮችና ጭፍሮቻቸው

የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች መካከል ነበር። የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች በጣሊያኖች አስተዳደር ወታደሮች ሊባሉ አይችሉም፤ ትልቅ ክብር እንደተሰጣቸው ይቆጠራል። መደበኛ ከሆኑ አስከር ይባላሉ፤ መደበኛ ካልሆኑ ባንዳ ይባላሉ፤ ከተት የሚባሉም ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ጥምር ተዋጊዎች ነበረ ከኢትዮጵያ ጋራ ጦርነት የገጠሙት። ብዛታቸው በአማካኝ ግማሽ ጣሊያኖች ግማሽ እንዲጂኒ ነበሩ። ከዚህ በፊት የተደሩጉት ጦርነቶች ለምሳሌ በአምባላጂ በኲዓቲ፤ በኢትዮጵያዊያንና በኢንዲጂኒ ኤርትራውያን መሐከል የተደረጉ ጦርነቶች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ጣሊያኖች በመሪነት አዋጊዎች ብቻ ነበሩ። በዓድዋ ጦርነቱ የተካፈሉ የኢጣሊያ ጀኔራሎች የደረሰባቸው ዕድል በጣም አሳፋሪ ነው። ጀኔራል አልበርቶኒ በኢትዮጵያ ሠራዊት ተማረከ፤ ጀኔራል አሪሞንዲና ጀኔራል ዳቦርሚዳ በጦር ሜዳ ተገደሉ፤ ጀነራል ኤሊና በሽሽት ጊዜ ስለቆሰለ ወዲያውኑ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ዋና አዛዣቸው ብቻ ነበረ ያልሞተና ያልቆሰለ።

ጦርነት በመጀመሪያ የገጠመ የኢንዲጂን ብርጌድ ነበሩ። ሁለት ሰዓት ሳይሞሉ ብዙ ጉዳት ስለደረሰባቸው የኢትዮጵያ ሠራዊትም ለመቋቋም ስላልቻሉ በብዛት ወደ ኋላ ሲመለሱ ያገኛቸው አንድ በጀኔራል አሪሞንዲ ብርጌድ ውስጥ የአንድ ሬጂመንት አዛዥ የነበረው ኰሎኔል ብሩሳቲ የሚባለው የኢጣሊያ ወታደሮች ገና ተኩስ ሳይሰሙ ለሁለት ሰዓት በኋላት የተቃጠሉ እንዲጂኒ ተዋጊዎች በአብረተኛና የንቀት መንፈስ ተነሳስቶ ወደ ጦር ግንባር ሊመልሳቸው ሞከር አልተቻለውም። ጡሩምባ እያሰማ እንዲቆሙና እንዲሰበሰቡ ቢያዛቸው እንዲጂኒ ብቻ ሳይሆኑ ትጥቅ አልቀበናል የቆሰሉትን እናመላልሳለን እያሉ አለቆቻቸው መኰንኖች ጣልያኖችም ጭምር አልታዘዙትም። ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ ግን የራሱ የኢጣሊያ ወታደሮችና ራሱ ኮሎኔሉም በባሰ ሁኔታ ሲሸሹ ይታዩ ነበር። በመቀሌ ከበባ አዛዥ የነበረው ሻለቃ ጋሊያኖ ጀግና ተብሎ ታምር ይሰራል ተብሎ ሲጠበቅ ብዙ ሳይዋጋ ተገደለ በሶስቱ ጦር ግንባር የተደረጉ ትንቅንቅ ውጊያዎችና የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዴት አድርጎ በአስደናቂ ሁኔታ ሊያሸንፍ እንደተቻለ ሰፊ አርእስት እንደመሆኑ መጠን የዚሁ ጽሑፍ ዓላማ ስላልሆነ አልፈዋለሁ። ራሳቸው ጣሊያኖች እንደመሰከሩት አብዛኛው ሰው የሞተባቸው በጦር ሜዳ ሳይሆን በሚሸሹበት ጊዜ ነበር።

የጀኔራል አልቤርቶኒ የኢንዲጂኒ ብርጌድ የተዋጋው ከጠዋቱ 12 እስከ 4 ሰዓት ሲሆን ይሽን ያህል ጊዜ የመሰደቡትን ፊታአውራሪ ገበየሁ በጦር ሜዳ ቆስሉ ስለ ሞተ በመሀከሉ ጦርነቱ በኢትዮጵያ በኩል ጋብ ብሎ ስለነበረ ነው። የጀኔራል አሪሞንዲ ብርጌድ ጦርነት የጀመረው በ4 ሰዓት ተኩል ነበረ። በ6:30 ብርጌድ እንዳልነበረ ሆኗል።

ጀኔራል ኤሊና ወታደሮቹ ከጀኔራል አሪሞንዲ ጦር ጋር ተቀላቅለው እንዲዋጉ ቢደረጉም እሱ ግን እንደ አጋጣሚ ዋና አዛዥ ጀኔራል ባራቴሪ ፍተሻ በሚያደርጉበት ጊዜ ሙሉ ቀን በአንድ ሾላ ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ስላገኘው ጦርነቱ ያለቀ መሆኑን እና የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ኋላ በመመለስ እየሸሸ መሆኑን ስለነገረው ከቀኑ 7 ሰዓት ከሌሎች ጦር መኰንኖች ጋር በመሆን ሸሽተው ማምለጥ ችለዋል።



የጀኔራል ዳቦርሚዳ ብርጌድ ጦር እስከ ቀኑ 4:30 የሌሎች ብርጌዶች ዕድል ሳይየሰማ ከቆየ በኋላ በዚህ ሰዓት የተኩስ ድምጽ ተሰማ። በ5 ሰዓት ተኩሱ እየጨመረ መጣ ከቀኑ ከ9 ሰዓት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ትእዛዝ ተሰጠ። የኢትዮጵያ ጦር ጣሊያኖች እንደሚሏቸው «ሸዋውያን» እያሳደዱ ይፈጁቸው ነበር። ደግነቱ ግን የኢትዮጵያ ጦር በመሸሽ የነበሩ ጣሊያኖችን ለመግደል አላተኮሩም፡ ከሞቱት ወታደሮች ንብረት መዝረፍ ብቻ ነበር የተያያዙት። በዚሁ ጊዜም ኃይለኛ ዝናብ መጣል ስለጀመረ ተኩሱ ሊቋረጥ ችሏል። ከዚያም መሽቶ ስለጨለመ ውጊያው ሊቋረጥ ችሏል። ማርች 4 ቀን በእኛ መጋቢት 26 ቀን ከቀኑ በ8 ሰዓት ከጦር ሜዳ የሸሹ የኢጣሊያ ተዋጊዎች 300 ሆነው ዓዲቀይህ ገቡ።

ባራቴሪ ማርች 3 ቀን ጠዋት ከዓዲቀይህ የጦር ሠራዊቱ ብዙ ቁጣና ተቃውሞ ያስከተለበት ታሪካዊው አወዛጋቢው የተባለው ረጅም ቴሌግራም ለኢጣሊያ መንግሥት ላከ። የቴሌግራሙ ሙሉ ቃል ትርጉም እንደሚከተለው ነው። «ቅዳሜ ወደ ዓድዋ የሸዋውያን የፊት ይዞታዎችን በነበሩት እርምጃ ወሰድኩ። ስለዚህ እርስ በእርሱ የሚገናኙ ብሪጌዶች በሶስት መሥመሮችና ሌላው ብርጌድ ደጀን በማድረግ ወደ ፊት ገሰገስኩ። የቅኝ ክንፍ ዳቦርሚዳ 6 ባታሉዮን ነጮች 4 መድፎች አንድ ባታሊዮን ሚሊሻ ነበረው። የመሀል ክንፉ አሪሞንዲ 5 ባታሊዮን ነጮች የኢንዲጂኒ ተዋጊዎች 2 መድፎች ነበሩት። የግራ ክንፍን አርቤርቶኒ 4 ባታሊዮን እንዲጂኒና አራት መድፎች ነበሩት። ደጀን ጦር ኤሌና 6 ባታሊዮን ነጮች አንድ እንዲጂኒ 2 መድፎች ባለ ፈጣን ተኩስ ነበሩት። ሁለቱ የግራና የቀኝ መሥመር ወታደሮች ከሳውሪያ ጦር ሰፈር እስከ ዓድዋ ሰላሽ ሜዳ ድረስ ያሉት መንገዶች ተከትለው መራመድ ነበረባቸው። የመሀል መስመር ጦር በመሀል መንገድ እየተጓዘ ግንኙነት መፍጠር ነበረበት። የደጀን ጦርም በዚሁ መሥመር ነበረ የሚናጓዘው። መነሻ የጨረቃ ብርሀን በመጠቀም ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ነበር። የመጀመሪያ ግብ በቀኝ የረቢ አርእየኒ ኮረብታ ለመያዝ፤ በግራ የኪዳነምህረት ኮረብታ ለመቆጣጠር ነበረ። እነዚህ ፓራለል መንገዶች የግራና የቀኝ የሚያርቆባቸው ለአንድ ልዩ ዓለት የተሰራ ወደ ላይ የሚወጣ ተራራ የራዮ ተራራ ለሁለት ተከፍሏል። ነገር ግን ከሱ ውጭ ወደ ምዕራብ መገናኛዎች ቀላል ናቸው እርስ በእርሱ ይታያሉ። አፕራሲዮኑ እንደታሰበው ተከናወነ። ጠዋት ኮረብታዎች ከጠላት ነፃ ስለነበሩ በአንድ ጊዜ ተያዙ። እኔም እስከ ረቢ አርእየኒ ኮረብታ ድረስ መጥቼ ስለነበረ ሁኔታው ተነገረኝ። ይህ በዚህ/ቅንዳለ በ1 ሰዓት በግራ በኩል ከኪዳነ ምህረት አልፎ ወደ ዓድዋ አቅጣጫ ከፍ ያለ ተኩስ እንደተመለከትኩ ለአልበርቶኒ ጦር የተሻለ እርዳታ እንዲያደርግና ከእሱ ጋራ በቅንጅት ለመሥራት እንዲችል የዳቦርሚዳ ጦር ወደፊት እንዲራመድና ወደ ማርያም ሸዊቶ ቦታ እንዲይዝ አደረኩ። የአሪሞንዲ ጦርን ወደ ረቢ አሪየኒ ኮረብታ ጠራኋቸው። በአንድ ሰዓት ተኩል ትንሽ ጊዜ በኋላ ምናልባት ከእኛ በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ወደ አባገሪማ የሚተኮስ መድፍ ተሰማ። የግራ መሥመር ጦር ጦርነት ገጥሞ ነበረ፤ ነገር ግን ከተወሰነለት ቦታ በጣም አልፎ ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ከአልበርቶኒ የተላከልኝ ማስታወሻ የቀረቶ ባታሊዮን ከኮረብታው ወደ ዓድዋ አቅጣጫ ተልኮ ነበር። ኃይለኛ ጦርነት ገጥሞት እንደነበረ እሱም ያለው ኃይል በሙሉ በስራ ላይ በመዋል ከጦርነቱ የቀረቶ ባታሊዮንን ለማላቀቅ

ምክር እንደነበረ በማለት ሁኔታውን በመዘርዘር እንዳወቀው አድርጎ ነበር። በዚሁ ጊዜ በመጀመሪያ በበርሳሊየሪ ጦር በኋላም በቀረው ጦር አልበርቶኔን በመደገፍ ከኪዳነምህረት ኮረብታ ፊት ለፊት የሚገኘውን አንድ ከፍተኛ ቦታ እንዲይዝ ለአሪሞንዲ ብርጌድ ትእዛዝ ሰጠሁ። እንደዚሁም ሁለት ባለፈጣን ተኩስ መድፎች ወደዚሁ ሁለቱ ባለፈጣን ተኩስ መድፎች ወደዚሁ እንዲዛወሩ አደረግሁ። በዚሁ ወቅት ወደ ዓድዋ የሚወስዱ ከፍ ያሉ ቦታዎች ከፍተኛ ውጊያ ይካሄዱ ነበር።

ዳቦርሚዳ ወደ ግራ ድጋፍ እንዲሰጥና በቀጥታ አርቤርቶኔን እንዲረዳ ትዕዛዝ ላኩሁ። ትዕዛዙ መድረሱን አላውቅም። ብዛት ያላቸው የጠላት ተዋጊዎች ከግራና ከቀኝ ወደ ከፍተኛ ቦታ ሜዳች ብቅ ማለት በመጀመራቸው የአልቤርቶኔ ጦር ቀስ በቀስ ማፈግፈግ ጀመረ። እንዲያውም ማፈግፈግ ቆሞ እንዲጂናች ወደ ፊት ገፍቶ ነበረ፤ /ፋታውራሪ ገበየሁ ሲሞት/ እኔም የዳቦርሚዳ ጦር ይሆናል ብዬ ግምት አደረብኝ ምክንያቱም እውነቱን ለማየት አንድ ተራራ ይከልለኝ ነበር። በዚሁ ወቅት ከከፍተኛ ቦታ ሜዳች ብዛት ያላቸው አንድ ላይ ተሰብስበው ይወርዱ በነበሩ ጠላቶች ባለፈጣን ተኩስ መትረየሶች ተኩስ ይከፈት ነበር። አርበርቶኔ አሪሞንዲ ከያዘው ቦታ በታች ጠንካራና ተስማሚ ወደ ኮረብታ የሚወርደው ቦታ አፈገፈገ። ይሄውን ቦታ ለማጠናከር በተጠባባቂ ተመድቦ የነበረው የሻለቃ ጋሊያኖ ባታሊዮን ቦታውን ያዘ። ነገር ግን የጠላት ተኩስ ብታት ያለው ባይሆንም የእኛ ይዞታዎች በጣም ምቹና ገደር ቢሆንም ወታደሮቹ በቡድን በሚመጡበት ጠላቶች ባዶ ቦታ አንገሎች በመጠቀም ዘተራራ ስር ቦታ ይዞ የነበረ ሁለት ዐርሳሌሪ ባታሊዮኖች በፍጥነት ወደ ኋላ እንዲመለሱ አደረጋቸው። እንደዚሁም የቡሩሳቲ ሬጂመንት ባታሊዮኖች ቦታውን ለቀቁ። የተጠባባቂ ደጀን የነበሩ የኤሊና ባታሊኖችም ለመቋቋም አልቻሉም። ወደ ኋላ የሚሸሹ እያደና ገሩዋቸው ነበረ። በዚሁ ጊዜ ጠላቶች በታላቅ ድፍረት ወደ ያዝነው ቦታ እየመጡ በውስጣችን እየገቡ በቅርብ ሆነው በመኩንኖቹ ላይ እያተኮሩ ይተኩሱ ነበር።

ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው ማፈግፈግ ለማቆም ምክርም ትዕዛዝም ሊሰራ አልቻለም። በቀሩት ቦታዎችም ለማሰባሰብ መኩንኖች ያደረጉት መከራ ከንቱ ሆኖ ቀረ ምክንያቱም ወደ ፊት የሚገፉ ጠላቶች እና ጥቂት ከበታች ተኩራርተው የሚጋልቡ ሸዋውያን ፈረሰኞች ሁሉም ነገር እንዲበታተን ለማድረግ በቂ ሆነው ነበረ። ከዚህ በኋላ እውነተኛ እልቂት ይደርስብን ጀመር። ወታደሮች ያለ መጣሪያ ከተገኘን እንሰለብም የሚል እምነት ስለነበራቸው እንደ እብዶች መጣሪያቸውን ትጥቃቸውን ይወረውሩ ነበር። ሁሉም ምግባቸውና ሉቦርዶ የውኃ ልብሳቸውን ይወረውሩ ነበር። እኔ ከጀኔራል ኤሊና ከኮሌኔል ስቴቫኒና ከብሩሳቲ ጋራ ሆነን ወደ ኋና ስፈራቸው ወደ ላውራ እንዲያመሩ ያደረግነው መከራ ከንቱ ሆኖ ቀረ። ሁሉም ወደ ሰሜን ወደ ሰፈ መንገድ ፊታቸውን ያዞሩ ነበር። ሌሊት ቆመን የማፈግፈጉ ስርዓት እንዲኖረው ሞክረን ነበረ። ነገር ግን በእንደዚህ ያለ ግዜ በሚፈጠረው በሐዘብ ለአመገባበት የተነሳ ለሁለት ተከፈልን ግማሾቹ ከኮ/ሉ ስቴቫኒ ብሩሳቲ ጋራ ወደ ማይግባይኔ ሲያመሩ ሌሎች ከእኔ፤ ጀኔራል ኤሊና ቫሌንዛኖ ጋራ ሆነን ወደ ዓዲቀይህ መጣን። ስለ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ብርጌድ ምንም ወሬ የለኝም እንደዚሁም ስለ ጀኔራል አርቤርቶኔ።



ጀኔራል አሪሞንዲ ተቃራኒ ወሬዎች ይሰማሉ። የሽፈታችን መጠን በትክክል ለማወቅ አልቻልኩም። በጦርነት የተካፈሉ የነጭ ባታሊዮን ወታደሮች እንደገና ለማደራጀት ያስቸግ ይቻል መስሎ ነው የሚታየኝ። የአንዳጃኔ ተዋጊዎች ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ተበታት ነዋል፤ በነጮች ወታደሮች አሁን ምክንያት ጥፋተኞች የተነሣ መጠን አለበት። ሁሉም ሽፍቶችና የመስኩ ጠላቶች ነፍስ ዘርፏል። የማይበገር የመከላከያ ሠራዊት የተያዙ በሽፍቶች የተከበበ የግዴግራት ምሽግ ለቆ እንዲወጣ ግዜዝ አደገኛ ይመስለኛል። ዛሬ ሌሊቱን ወደ ሰገነይቲና አስመራ ለመሄድ ፍላጎት አለኝ። ለጊዜው ላምቤርቲ ነገ ጠዋት አስመራ ስለሚመጣ የቅኝ ግዛት መንግሥት ይረከባል እና ከሚኒስትሩ ይገናኛል [1]

ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች እስከ ምፅዋ እንዲመለሱ ለምን አልተደረገም ወይንም ለውጫሌ ውል መሠረት ወደ ተፈተደላቸው አጼ ምኒልክ ለሌውርዷ መንግሥታት የሀገሩ ዳን ድንበር ብሎ ወደ አስታወቀው ወሰን ለምን እንዲመለሱ አልተደረገም ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚችል ማስረጃ የለም። ጣሊያኖች እንደገና በሚሉት ማስረጃዎች [2] የኢትዮጵያ ሠራዊት እስከጉራዕ ዘልቆ መሀል በኢጣሊያ ቀኝ ግዛት ለመግባት እቅድ ነበረው። በዓድዋ በተደረደገው ስብሰባ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ሠራዬና ወደ አከለጉዛይ እንዲገባ ተወስኖ ነበር። ማርች 3 ደጃዝማች በንጋል የባሕታ ሐጎስ ወገድም ከዓድዋ ተነስቶ ወደ በለሳ እንዲሄድ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። ማርች 6 የሸዋ ጦር ወደ እንጢጮ ተንቀሳቅሶ ነበር። በዚሁ ቀን ባልዲሴራ ወደ ሮማ የላከው ቴሌግራም ሁኔታው ከባድ ነው፤ ያለው ሠራዊት 15.000 የኢጣሊያ ወታደሮች እና 5000 አንዳጃኔ በጦርነት የተደናገጡ ናቸው። የሸዋ ጦር ምናልባት ከጉራህ እና አስመራ መሀል ለመከፈር እየመጣ ነው። ማርች 6 ደጃዝማች አርአያ ዳዕር ተከሉ ይዞ ነበር፤ የበለሳ መሥመር አዝማች አበራ ሐጎሥ ተፈፀኖ በአንድ የንጉሡ ፊታውራሪ ተይዞ ነበረ። ራስ ስብሐትም ማይመረት በመያዝ እስከ ዶንገሎ ድረስ ዘልቆ ከዓዲግራት የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርጎ ነበር። በአከለጉዛይ መሉ የንጉሡ ጦር ወደ ፊት መግፋት ለማመቻቸት ዓመጸኞች ተንቀሳቅሰው ነበር።

ጣሊያኖች ሲያሸንፉ እንበሶች ሲሆኑ ሲሸነፉም ግልፎች ነው የሚሆኑት። ከዓድዋ ጦርነት በፊት ከአጼ ምኒልክ፤ ከራስ መኰንን፤ ከእቴጌ ጣይቱ፤ በተደጋጋሚ ይቀርብላቸው ለነበረ ስለ ሰላም ጥያቄ በእብሪት ውድቅ ሲያደርጉ ቆይተው አሁን ግን የሰላም ንግግር ፈላጊዎች እነሱ ሆኑ። ለዚሁም ሻለቃ ሳልሳ ሶስት ጊዜ ወደ አጼ ምኒልክ ተላከ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሠራዊት ፈረስ ማይ ከተሰበሰበ በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ሳይንቀሳቀስ ተቀምጦ ማርች 20 ቀን ቀስ በቀስ ወደ ሀገሩ መመለስ ጀመረ። አጼ ምኒልክ ወደ ጉራዕ ሳይዘልቅ ወደ ሸዋ የተመለሰበት በቂ ምክንያት ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል አጼ ምኒልክ ልክ 7 ዓመት ከዓድዋ ጦርነት በፊት አጼ ዮሐንስ በመተማ በሞተ ጊዜ ማለት ማርች 10 ቀን 1889 ዓ.ም. በእኛ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. አጼ ምኒልክ ማርች 26 ቀን 1889 በእኛ

1. E. Bellavita ibd p. 392-393

2.E. Bellavita ibd p. 418

መጋቢት 18 ቀን 1881 ዓ.ም. ለኢጣሊያ ንጉሥ ደብዳቤ ፅፏል የጻፈውም ደብዳቤ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው። ከዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ፣ የሐረር፣ የከፋና የጋላ ሀገሮች ንጉሥ ለኢጣሊያ ኃይለኛ እና ወዳጅ ንጉሥ ኡምቤርቶ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. በመተማ አንድ ልዩ አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጥሯል። ንጉሡ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ ከሠራዊቱ በሙሉ ጋራ ሆነው ወደዚያው ሄደው ስለነበረ ከደርቡሾች ጋራ ተዋግተው ተሸንፈው ቆስለው ሞተዋል። ለጊዜው የእኔ መልእክተኞች ወደ ግርማዊነትዎ እስኪመጡ ድረስ እኔም ከአንቶኔሊ ጋራ ስለምልካቸው እና ለግርማዊነትዎ በሆዱ ያለው ሁሉ እስኪምገልፅልዎት ድረስ ግርማዊነትዎ በምፅዋ ለሚገኙ ጀኔራሎች በትግራይ በኩል የሚገኙት ሽፍቶች የሚናገሩትን እንዳይሰሟቸው እና የጦር መሣሪያ እንዳይገባ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉላቸው እለምንታለሁ። ከዚሁ ዜና በኋላ ሁሉም ለኢትዮጵያ ዘውድ መብት እንዳላቸው ለማስጣት ይፈልጋሉ። የግርማዊነቶ ወታደሮች አስመራ ገብተው አጠንክረው እንዲይዙ። በዚሁ በኩል መንገዶቹ እንደተያዙና በመካከሉ ጦር እንዲጠናከሩ እንዲያደርጉ እለምናዎታለሁ። ይህ ሁሉ ነገር ለግራማዊነቶ ለመናገር የሚያስደፍረኝ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከብዙ ዓመት ጀምሬ እመኘው የነበረ ዘውድ መብትም ያለኝ ስለሆነ ሊሰጠኝ ነው የኢትዮጵያም ሰላምና ዕረፍት ሊሰጣት ስለሆነ ነው[1] አጼ ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ወደ ሸዋ ሲመለስ ለትግራይ ሹሞች ከጣሊያኖች ጋራ ያላቸው ችግር ራሳችሁ በራሳችሁ ተወጡ እንደማለት ይቆጠራል እነሱም ደካማ ነበሩ ሁሉም በራስ መንገሻ የሚታዘዙ አልነበሩም።

አጼ ዮሐንስ ከሞቱ ከአራት ቀን በፊት ቀንደኛ የትግራይ ጠላት የሸዋ ፖለቲካ አራማጅ አንቶኔሊ ከአዲስ አበባ ለኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር የፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ብሎ ነበር ንጉሥ ምኒልክ አብዛኛው የትግራይ ሹማምንቶች በአጼ ዮሐንስ መጥፎ አስተዳደር የደከመ ሀገራቸው በኢጣሊያ ቢያዝ ደስታቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ አጋጣሚ ሁኔታ በዝምታ ማለፍ አያስፈልገንም። ምክንያቱም ትግራይ እንደገና ነፍስ እንዲዘራና እንዲጠናከር ጊዜ በመሥጠት በስህተት መውደቅ እንችላለን። ይሄም ቀን ከመጣ ለጨካኝ እና አዲስ የትግራይ ገዛት ልንጋለጥ እንችላለን በሸዋ በኩል አንድ ወዳጅ የሆነ ንጉሥ አለን[2] ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሀገሩ ሲመለስላቸው አፎይታ አግኝተው እስረኞቻቸውን ለማስለቀቅ ነበረ ሐሳባቸው። በኢትዮጵያ የተማረኩ የኢጣሊያ እስረኞች 1700 ነበሩ። በመንገድ በድካም፣ በበሽታ ስለሞቱባቸው ተለቀው ወደ ሀገራቸው በሚሄዱበት ጊዜ የተቆጠሩ 1300 ብቻ ነበሩ።

ስለ ሐስረኞችም ስለ ሰላም ንግግርም ወደ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ መልዕክተኛ ሆኖ የተላከው ሻለቃ ነራሲኒ የሚባለው ነበር። ሴፕቴንበር 10/1886 ዓ.ም. በዘይላ በኩል ሐረር ገብቶ ራስ መኮንን የደመቀ አቀባበል አድርገውለታል። በኦክቶበር ሻለቃ ነራሲኒ ከኢትዮጵያ ጋራ ስምምነት የተደረሰ መሆኑን ለመንግሥቱ ሲገልፅ ስለ አጠቃላይ ሰላም በሚመለከት።

1. Carlo Rossetti Ibd. p. 59

2. Carlo Rossetti Ibd. p. 57



1ኛ. ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በጦርነት እንዳልሆኑ፣

2ኛ. የውጫሌ ውል ውድቅ እንደሆነ፣

3ኛ. የኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነትና ሉዐላዊነት ኢጣሊያ ትቀበላለች፣

4ኛ. የወሰኑ ጉዳይ አሁን እንዳለ መረብ፣ በለሳ፣ ሙና ሆኖ ከዚሁ የሰላም ውል ከአንድ አመት በኋላ በወዳጅነት እንዲወሰን፣

5ኛ. የመጨረሻው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ለሌላ መንግሥት እሳልፎ እንዳይሰጥ በራሱ ፍቃድ መልቀቅ ከፈለገም ለኢትዮጵያ ብቻ እንዲመልስ የሚሉ ነበሩ፣

## ምርኮኞችን በሚመለከት

1ኛ. ምርኮኞች ነፃ እንደሆኑ በዘይላ በኩል ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ወደ ሐረር እንዲሰበሰቡ፣

2ኛ. የኢጣሊያ ቀይ መስቀል በጂልዱላ እንዲረከባቸው፣

3ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት ምርኮኞችን ለመቀለብ ያወጣው ውጪ የኢጣሊያ መንግሥት እንዲከፍል ማርች 26 ቀን 1898 ዓ.ም. በፊርማቸው አፅድቀዋል። በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ ፖርላማ ኖቬንበር 30 ቀን 1896 ባደረገው ስብሰባ ሙሉን አፅድቋል። በኢጣሊያ ፖርላማ አባል በሆነው ኢምብሪያኒ የሚመሩ ከኤርትራ ለቀን እንውጣ የሚሉ ወገኖች ነበሩ። ሐሳባቸው ግን 26 ደጋፊ ሲያገኙ 53 ታአቅቦ ድምፅ በ184 ተቃውሞ ውድቅ ሆኖባቸዋል። በዚሁ ተስፋ ሳይቆርጡ የቅኝ ግዛት ተቃዋሚዎች የሶሻሊስቶች መሪ ኢምብሪያኒ እማካኝነት አለከራኖች ከፍተኛ ወጪና ውርደት ብቻ ነው ኢጣሊያ የምታተርፈው በማለት ከኤርትራ ለቃ እንድትወጣ ለማድረግ ሞክሮ ነበር።

2 .ሁለተኛ ወገን ከመንግሥት በኩል ከበሳ ደጋ በሙሉ ብቻ ለቆ በምፅዋና አርቂቆ ብቻ እንዲወሰን ሐሳብ ቀርቦ ነበር።

3. ሌላ ወገን በነ እስተሳሰብ እለን የሚሉ አሁን ያለው ወሰን እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ኢጣሊያ ከማንኛውም መስፋፋት ተቆጥባ ለደረሰባት ሽንፈት እበቀላለሁ ብላ ሳታስብ ከአቢሲኒያ ጋራ በሰላም እንድትኖር

4. አነሉተኛ ወገን በወታደር ክፍል የሚደገፍ ለጊዜው ብቻ ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ተቀብላ ከአቢሲኒያ ጋራ ሰላም እንድትመሠርት ቀስ በቀስ በኤርትራ እየተጠናከረች ሐዳ በሚሰጢር ለዘመቻ ተዘጋጅታ ከፍተኛ ጦርነት አካሂዳ የደረሰባትን ሽንፈት እንድትበቀል የሚሉ ነበር። ማርች 5 ቀን 1897 ዓ.ም. የኢጣሊያ መንግሥት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሩዲኒ እማካኝነት ስለ አፍሪካ ልዩ ልዩ ሀሳቦችና ዕቅዶች ያስራጫል። አፕሪል 14 1897 ከፓርላማ አቦሎች ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ይቀርባሉ ከመንግሥትም ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ አፕሪል 22 ወደ ድምፅ መስጠት ይተላለፋል።

1ኛ. ኢጣሊያ ኤርትራን ለቃ እንድትወጣ የሚጠይቅ በከፍተኛ ተቃውሞ ውድቅ ይሆናል፤

2ኛ. የኦክቶበር 26 የሰላም ውል ቁርጡ እስኪታወቅ ድረስ ፖርላማ ስለ አፍሪካ ጉዳይ ክርክሩ እንዲያዘገይ የሚለውን በድምፅ ብልጫ ውድቅ ይሆናል።

3ኛ. መንግሥት ስለ አፍሪካ ባወጣው ፕላን ፖርላማው ይስማማል የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት ያገኛል። እንደገና ስለ አፍሪካ ጉዳይ ዲሴንበር 16/1897 ኢጣሊያ ከአፍሪካ ለቃ መውጣት አለባት ከሚሉ ወገኖች በፖርላማ ግያቄ ቀርቦ 81 ድምፅ ደጋፊ ሲያገኝ 172 ተቃውሞ ስለገጠመው ውድቅ ይሆናል። ይህውም ስለ አፍሪካ የመጨረሻ ክርክር ይሆናል። ስለ ከሠላ ጉዳይ ግን የኢጣሊያ መንግሥት ደርቡሾችን በመፍራት እንዲሁም የመንግሥት ወጪውን ለመቀነስ የእንግሊዝ መንግሥት እንዲረከበው በመለመን ለእንግሊዝ አስረከባት። በአንፃሩ ግን የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ ቀደም በደርቡሾች የደረሰበት ሽንፈት ከምንም ሳይቆጥር ምንም እንኳን ያልተዘጋጀ ቢሆንም ዲሴንበር ወር 1897 ከኢጣሊያኖች ሊረከብ ችሏል። አንዳንድ ጣሊያኖች ከከሰላ ለቆ መውጣት ለሀገራቸው ከዓድዋ ሽንፈት የበለጠ ውርደት ነው ብለውታል።



La liberazione di Adigrat: arrivo del ten. Bodrero sotto le mura del forte (disegno di Ximenes)

ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች ዓዲግራት ውስጥ የተከበቡ

ወታደሮቻቸውን ባሻገር ያስለቀቁ መሆናቸውን

የታወቀ ሊሆን በሮል አድራጊንት የገቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ይህ

ስእል አመላቷል።



# የዓድዋ ጦርነት የሞቱና የቆሰሉ በሁለቱ ወገኖች

1. ከሁሉ አከራካሪ የሆነው በዓድዋ ጦርነት የሞቱ የኢጣሊያ ወታደሮችት ነው።[1] በ1938 በኢጣሊያ መንግሥት የታተመው መጽሐፍ ኢጣሊያኖች ብቻ በሚመስከት በጦርነቱ እየተካፈሉ ወታደሮች 11.430፤ 553 የጦር መኰንኖች 10.877 ተራ ወታደሮች፤ ያልሞቱና ያልተማረኩ 4555፤ ከእነሱ ውስጥም 265 የጦር መኰንኖች፤ 4290 ተራ ወታደሮች ነበሩ። የሞቱና የተማረኩ ኢንዲጀኒ ሳይጨምር 7043 ሲሆኑ ከእነሱም 288 የጦር መኰንኖች፤ 6755 ተራ ወታደሮች።

በመጨረሻ የተደረጉ ጥናቶች ግን የሞቱና የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች 262 (46 ከመቶ)፤ 3772 ተራ ወታደሮች (38 ከመቶ) እንደበሩ ተረጋግጧል ካለ በኋላ ስለ ኢንዲጀኒ ወታደሮች የሞቱና የቆሰሉ ለማወቅ እንዳልተቻለ ገልጦ ሆኖም የደረሰባቸው ጉዳት ከባድ ስለነበረ በአማካኝ በጦርነቱ ከተካፈለው የደረሰው ጉዳት 50 ከመቶ ሊሆን እንደሚችል ገልጧል።

1406 አስካሪ ምርኮኞች የቀኝ እጃቸውና የግራ እግራቸው ተቆርጧል 6 አስካሪና 30 የኢጣሊያ አስር አለቆችና ተራ ወታደሮች ተሰልቧል። በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው ጉዳት የሞቱ 6000፤ የቆሰሉ 10.000 ተገምቷል ብሎ ገልጿል።

2ኛ. አልቤርቶ ፖሌራ[2] በደረሰው መጽሐፍ በመግቢያ ላይ እንደተገለጸው የኢጣሊያ ሠራዊት 286 የጦር መኰንኖች 6.600 ተራ ወታደሮች በጦር ሜዳ ተገድሎበታል 1700 አብዛኛው የቆሰሉ ተማርኳል። በኢትዮጵያ የደረሰው ጉዳት 17.000 ነው ብሏል።

3ኛ. አ ብሮንዞዎሊ በደረሰው መጽሐፍ[3] የኢጣሊያ ሠራዊት በጦርነቱ ከተካፈሉ 9.837 ተራ ወታደሮች 3.772 በጦር ሜዳ ሞቷል (38 ከመቶ) በላይ እንዲሁም በጦርነቱ ከተካፈሉ 571 የጦር መኰንኖች 262 (46 ከመቶ) በጦር ሜዳ ሞቷል። የኢንዲጀኒ ወታደሮች የሞቱና የቆሰሉ አይታወቅም ሆኖም የደረሰባቸው ጉዳት ከባድ ስለነበረ በአጠቃላይ ኢጣሊያ ካሰለፈቻቸው ወታደሮች በአማካኝ (50 ከመቶ) የሞቱና የቆሰሉ ናቸው ተብሎ ተገምቷል። በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ጉዳት በትክክል ባይታወቅም የሞቱ 6.000 የቆሰሉ 10.000 መሆናቸውን ተገምቷል ብሏል።

4ኛ. ሉካ ዴይ ሳቤሊ[4] በደረሰው መጽሐፈ የኢጣሊያ ሠራዊት ከሞቱበት 6.000 ወታደሮች 4.600 ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች ሲሆኑ 268 የጦር መኰንኖች ነበሩ የቆሰሉ ከ500 በላይ የበሩ የተማረኩ 1.700 ነበሩ።

1.Fici p. 206

2. Alberto Pollera La guerra di Adua XII

3. A Bronzuoli Adua p. 67

4. Luca Dei Sabelli La Storia Di Abissinia Vol.3 p.422

በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው ጉዳት የሞቱት 7.000 ነበሩ የቆሰሉት 10.000፤ 2.000 ቆይተው ሞቷል ብሏል። አጼ ምኒልክ በኤርትራውያን ኢንዲጀኒ ላይ የሚሰጠው ቅጣት ራሱ ጣልቃ መግባት አልፈለገም አቡነ ማቴዎስ ፍርድ እንዲሰጡ መብት ሰጧቸው በዚሁ መሠረት በአቡኑ ትዕዛዝ ወዲያውኑ የቀኝ እጃቸውና የግራ እግራቸው እንዲቆረጡ ተደረገ።

በዚሁ ዘገባ የሚታየው አዲስ ነገር በሌሎች ታሪክ ፀሐፊዎች ያልተገለጠ የቆሰለኞች ቁጥር ነው። በማንኛውም ጦርነት የቆሰለኞች ቁጥር ከሚሞቱ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ የታወቀ ነው በዓድዋ ጦርነት ግን ባልተለመደ ሁኔታ ቁጥራቸው ከሞቱት በጣም ዝቅ ብሎ መገኘቱ ጣሊያኖች የሞቱት በሽሽት ላይ እንዳሉ መሆኑን ያሳያል።

5ኛ. ታዋቂው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ- ሮሲኒ[1] በጻፈው የኢጣሊያ ጦር ቁጥሩ ከ17.000 ትንሽ ያነሰ ነበረ ከእነሱ ውስጥም 6.400 ኢንዲጀኒ ነበሩ ብሏል። 4.900 ነጮች ወደ አንድ ሺህ የሚጠጉ ኢንዲጀኒ ተገድለዋል ብሏል። ሌላ አንድ ሺህ የሚጠጉ ኢንዲጀኒ ተማርከው አንድ እግራቸውና አንድ እጃቸው ተቆርጧል ብሏል። ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ የሰላም ውል ሲፈራረሙ ኦክቶበር 1896 ኢጣሊያ 1580 ምርኮኞች ተመልሰውላታል፤ ከኢትዮጵያ ስለቀለባቸው የተደረገላቸው ወጪ መካካሻ ኢጣሊያ 10 ሚሊዮን ሊሬ ከፍላለች።

6ኛ. ኮራዶ ዞሊ[2] በደረሰው መጽሐፍ በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ በኩል የሞቱና የቆሰሉ 16.000 ነበሩ። ከኢጣሊያ የሞቱና የቆሰሉ 8.000 ነበሩ ምርኮኞች 1.800 ሲሆኑ ግን ደርሶባቸው ከነበረ ቆሰልና በሽታ ስለሞቱባቸው ከእሥር ተለቀው የተመለሱ ትንሽ ከ1.800 የሚበልጡ ነበሩ።

7ኛ. ካርሎ አናራቶኔ[3] በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች 80.000 ብቻ ነበሩ። በኢጣሊያ በኩል በጦርነቱ የተካፈሉ የጦር መኰንኖች 551 ተራ ወታደሮች 10.550፤ ኢንዲጀኒ፤6.790 ነበሩ። የሞቱ 4.600 ጣሊያኖች ከእነሱ ውስጥም 2ጀነራሎች፤ 2 ኰለኔሎች፤ 267 የጦር መኰንኖች፤ 2000 ኢንዲጀኒ። የቆሰሉ ተማርከው እጃቸውና እግራቸው የተቆረጡ ኢንዲጀኒ ጭምር 2000 ነበሩ። የኢጣሊያ ምርኮኞች 1.752 ነበሩ ከእነሱ ውስጥም 150 የጦር መኰንኖች ነበሩ፤ ነገር ግን ከጦርነቱ አንድ ወር በኋላ አፕሪል 7 አጼ ምኒልክ ምርኮኞቹ 2400 እንደነበሩ ለሻለቃ ሳልሳ አስታውቀውት ነበረ። በኢትዮጵያ በኩል በጦርነት፤ በረሃብና በበሽታ የሞቱ የቆሰሉ በአጼ ምኒልክ 20.000 ወታደር እንደሚገመት ዘግቧል።

---

1. Conti- Rossini Etiopla e genti d'Etiopla
2. Corrado Zoli CronacheEtiopichep. 187
3. Carlo Annaratone In Abissinia p.346



# የዛሬ ዘመን የሸዋ ፖለቲካ አራማጆች

ጣሊያኖች እና አጼ ምኒልክ ሊያስማማቸው የቻለ ነገር ሁለቱም በአንድ የጋራ ጠላት በአጼ ዮሐንስ ላይ የጠብመንጃቸው አፈሙዝ ያነጣጥሩ ስለነበረ፤ የጠላቱ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል ጽንሰ ሀሳብ በመመራት ነበረ።

አጼ ዮሐንስ እንደ አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ አንድነት ለድርድር የማያቀርብ ስለነበረ፤ የጣሊያኖች ፍላጐት የማያሟላ ቀንደኛ የኢጣሊያ ጠላት ነበረ። ቃሉም አንድ ቀን ሳያጥፍ ነበረ በጦር ሜዳ በጀግንነት የሞተው።

አጼ ዮሐንስ ለአጼ ምኒልክም የሥልጣን ተቀናቃኝ በመሆኑ ብቸኛ ባለጋራ ነበረ።

ከዚህ በላይ እንቲኖሪ በጻፈው ደብዳቤ እንደተገለጸው በፀረ አጼ ዮሐንስ የቅኝ ገዥነት ዓላማቸው፤ ኢትዮጵያን በቁጥጥራቸው ለማዋል የነበራቸው ፍላጐት እውን ለማድረግ፤ እንደ ፖለቲካ መሣሪያ ሊጠቀሙበት ቢመክሩም፤ ጣሊያኖች አጼ ምኒልክን በእኩል ደረጃ አያዩት አልነበረም። የሚደራደሩት «ምንም ቢሆን ጥቁር ንጉሥ መሆኑን መዘንጋት የለብንም» እያሉ ዝቅ አድርገው ይመለከቱት ነበር። እምዩ ምኒልክ ግን በየዋህነቱ ለኢጣሊያ ንጉሥ በላከው ደብዳቤ የመንግሥቴ ጠባቂ (የሸዋ መንግሥት) እያለ ይጽፍለት ነበር፤ ካርዲናል ማሳያንም አባቴ እያለ ይጠራው ነበር።

በዘመናችን፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ 100ኛ ዓመት በሚከበርበት ወቅት፤ ከጥንት ከአንቲኖሪ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሸዋ ፖለቲካ አራማጆች በአዲስ አበባ አቆጥቁጠው ይታያሉ። የዓድዋ ድል መታሰቢያ 100ኛ አመት በሚመለከት መእሕድ የበዓሉ አከባበር፤ ጦርነቱ በተካሄደበት በዓድዋ ሳይሆን በአዲስ አበባ መከበር አለበት ብሎ በመጠየቅ የካቲት 10 ቀን 1988 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ለሕዝብ ጥሪ ሲያስተላልፍ በአዲስ አበባ በየመንገዱ ከተሰጠፉ ጹሑፎች ውስጥ የሚከተሉት ቃላቶች ይገኙበታል።

«የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀጥቅጠው ለመግዛት የዘመቱ ቅኝ ገዥዎችና ለዚያ ለረከሰ እምነታቸው እውነት ያሰለፉቸው ጥቁር ባንዳዎች ከነጭ ሰው በፊት እኛ እንሙት ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱ ሁሉ የሀፍረት ማቅ ከንብንባቸውን ለምንግዜም ከራሳቸው ሊያወርዱት በማይችሉበት ሁኔታ ዓድዋ ላይ ታሪክ ተሰርቷል። ይህ ታሪክ መሪ ያኢትዮጵያ ሕዝብ እና እምዩ ምኒልክ የማይነጣጡ ናቸው።

የዘመናችን የታሪክ ክህደት ምንጩም በዓድዋ ጦርነት ወቅትና ከዚያም በፊት ሆነ በኋላ በኢትዮጵያ ጠላትነት የምናውቃቸው ባንዶቹ እንቅስቃሴ ውጤት ነው።

ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የእድገት ጎዳና የመሩንን፤ ባቡር፤ ስልክ፤ ፖስታ፤ የውሃ ቧንቧ፤ መኪና የመሳሰሉትን ስናወሳ እምዩ ምኒልክን ማስታወሳችን አይቀሬ ነው።

ከቅኝ ገዢዎች ጋር የተደረገው ጦርነት በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጮች በጥቁር መንግሥት ጦር ድባቅ ተመተው የተሸነፉበት የዓድዋ ጦርነት ሲሆን ኢትዮጵያና እምዩ ምኒልክ የጦርነቱ ውሉ ሲሆን ደግሞ የኢጣሊያን መሪዎችና ሽንፈታቸው ከእነርሱም ጋር

ተሰልፈው የታሪክ ሞት የሞቱ ከሳባት ሺህ በላይ የሆኑ ባንዶች ከቶውኑ የማይነጣጠሉና የማይዘነጉ ናቸው።»

ይህን መግለጫ ያቀረበው መላው አማራ ሕዝብን እንወክላለን የአጼ ምኒልክ ደጋፊዎች ነን ከሚሉ ወገኖች ነው። ነገር ግን ይህ ስሜት የመላው አማራ ሕዝብ ስሜት አይደለም፤ መላው የአማራ ሕዝብን ከማይወክሉ ከጥቂት ግለሰቦች የመነጨ ስሜት ነው። ለአንድ መቶ ዓመት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሲከበር የኖረው፤ በተለይ በአፍሪካ ደረጃ ወንድር የ100ኛ ዓመት ለማክበር በምንዘጋጅበት ዋዜማ አጼ ምኒልክ በአድዋ ጦር ሜዳ ኃያል አውሮጳዊት መንግሥት ነኝ የምትለው ኢጣሊያን በማሸነፍ ነው እንጂ ሰባት ሺህ ባለቀለም ከጣሊያኖች ጉን የተሰለፉ ኢትዮጵያውያን ባንዳዎችን በመግደሉ ያሳየው ጀግንነት በሚል መፈክር አውለብልበን አይደለም። ኢትዮጵያውያን ሁላችን በተለይ የዓድዋ ድልን በምናከብርበት ጊዜ እርስ በእርሳችን መወቃቀስ ባልተገባ ነበር። ይህ በመእህድ የወጣ መግለጫ ከአንድ ታላቅ የፖለቲካ ቡድን የማይጠበቅ ርካሽ ጥራዝ ነጠቅ ወቀሳና ተራ ስድብ ግን መልስ ሊሰጠው ይገባል። ስለባንዳዎች ወይንም ከኢጣሊያ ጉን ተሰልፎ የገዛ ሀገሩን የመውጋት ጉዳይ ከተነሣ የመጀመሪያ ባንዳ፤ የባንዳዎች ቁንጮ ራሱ ምኒልክ መሆኑን የማይካድ ሀቅ በመሆኑ ጥቂት ታሪካዊ ክንውኖች መጥቀስ ይቻላል።

1ኛ. በሰሜን ኢትዮጵያ የጣሊያኖች ማንነት በማይታወቅበት ጊዜ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት አጼ ምኒልክ በሸዋ የኢጣሊያኖች ወዳጅነት መስርቶ ነበረ። ስለዚህ ምኒልክ የመጀመሪያ ባንዳ ነው።

2ኛ. በዶጋሊ የሞቱ የኢጣሊያ ወታደሮችን በአፋር በርሀ የሞቱ የኢጣሊያ ትኝ ፕሮ ዎችን እኔ አበቀላችኋለሁ። ከእናንተ በፊት እኔ ልሙትላችሁ ብሎ በተደጋጋሚ ለጣሊያኖች የገለጸላቸው ወዳጃቸው የነበረ ምኒልክ ነው።

3ኛ. ምኒልክ የሀገሩ ዳር ድንበር ጉዳይ ለአውሮጳ መንግሥታት ለማስታወቅ በጻፈው ደብዳቤ አሥመራን እና ምጽዋን ለጣሊያኖች በመሸጥ የጣሊያኖች መሬት መሆናቸውን በማመን በሰሜን የኢትዮጵያ ወሰን ከቺከቲ (20 ኪሎ ሜትር ከአስመራ) በስተደቡብ መሆኑን ገልጸዋል።[1]

4ኛ. አጼ ምኒልክ የሀገሬ ወሰን ነው ብሎ ያመነበትን በማጠፍ ጣሊያኖች ከጉናቸው የሚያሰልፉቸው ባለቀለም ወታደሮች ለመመልመል ያስፈልገናል ብለው በጠየቁት መሠረት አይበቃችሁም ብሎ እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ያለውን መሬት ጨምር ሰጣቸው። ቀሃሉም በውሜሌ ውል የሌለ የኩናማ መሬትም ሰጣቸው።

5ኛ. ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ጣሊያኖችን አባሮ መሬቱን ለመመለስ መብትና ኀይል ሲኖረው ይኼንን ማድረግ አልፈለገም። ይኸውም ሌላ የምኒልክ ክህደት ነው።

6ኛ. በጉዳ ጉዱ (ጉንደት) ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ትጭናለህ የሚል ሀሰት ተስፋ ከጉባዔውያን ሲሰጠው ምኒልክ ፕሽምበር 1876 ዓ.ም. ከጉባዔች

1. Traversi : Let Marefia p. 379



እስላሞችጋራ ተስማምቶ አጼ ዮሐንስን ለመውጋት ተዘጋጅቶ ነበረ። ግብጾች በሰሜን ኖ በምሥራቅ ጦር ኀምባሮች ስለተሸነፉ ግን እትዱ ሳይላካ ቀረ

በታሪክ የሀፍረት ማቅ የተከናነበ በከሀዲነት ከታሪክ የማይፋቅ እላፋሪ ተግባር በመ ስራት ያለፈ የሀገሩን ሕዝብና መሬት የሸጠ እምዬ ምኒልክ ነው እንጂ እንደ እቃ የተሸጡ ጭቁን ሕዝቦች አይደሉም። ባንዳም ተብሎ መጠራት የሚገባው ሚኒልክ ብቻ ነው። ባንዳ ሆኖ በጣሊያኖች ያልተቀጠረ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም አይገኝም። የገታት ሕሊና ማነስ ስለሆነ ለጣሊያኖች የሚቀጠሩት ሰዎች ሥራና ደመወዝ ከማግኘታቸው በቀር እርቀው ማየ ት የማይችሉበት ጸመን ይኖሩ የነበሩ ናቸው።

በዘመናችን የታሪክ ክህደት ምንጩም፤ ዋና ባንዳ አድርገን የምናውቀው ምኒልክ ብቻ ነው። ይኸም ሆኖ ስህተት በመስራቱ ከመውቀስ እልፈን የነበረበት ዘመን ስንመለከት በጠላ ትነት እንመለከተውም። የኤርትራ ነፃ ሀገር መፈጠርም የምኒልክ ክህደት ያመጣው ውጤት ነው። ለዚህም ሌላ ማንም ሰው በኃላፊነት አይጠየቅበትም። ምኒልክም የክህደት ተግባር የፈጸመበት ምክንያት ከሀገሩ ከኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት ዘውድን ለመጫን ፍላጎቱን ስለሚ ያስቀድም ነበር። የሸዋ መኳንንት፤ እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ መኳንንት የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ሲሸጥ ከመቃወም አላቋረጡም ነበረ። ምኒልክ ግን በሥልጣኑ እፍኖ ዝም አሰኛቸው።

የምኒልክ ደካማ ጉን ስናስታውስ ጠንካራ ጉንም ማስታወስ ያስፈልገናል። በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ምኒልክ መላው ኢትዮጵያን ለአንድ አላማ፤ በአንድነት ማሰለፍ መቻሉ፤ ለድል መብቃቱ፤ ለኢትዮጵያ አስደናቂ የጀግንነት ክብርና ዝና ማትረፉ ከጠንካራ ጉኑ አንዱና ዋነኛው ነው። ምኒልክ በለዘብተኝነት ሀገርን የማስተዳደር ችሎታም ነበረው። ምኒልክ በዘመናችን የእሱ ደጋፊዎች ነን የሚሉ እንደሚያስቡት የጉሳ ጥላቻ አልነበረውም። ሁለቱ የአጼ ምኒልክ ታማኝ ሚስቶች ጣይቱና ባፉና የሰሜን ኢትዮጵያ ተወላጆች ነበሩ። ጣሊያ ኖች በየጊዜው በዘመኑ ያቀርቧቸው የነበሩ ሪፖርቶች ችግር እንደፈጠረባቸው ብለው በተደ ጋጋሚ ከመግለጽ ያላቋረጡት ጉዳይ ምኒልክ ከሾማቸው መኳንንቶች ብዙዎቹ የሰሜን ኢት ዮጵያ ተወላጆች እንደነበሩ ነው የሚያስገነዝበን። በዚሁ ምክንያት ጣሊያኖች እንደሚሉት የሸዋ ፖለቲካቸው ለማራመድ ምኒልክን ሃሳብ በማስቀየር፤ በየጊዜው እንቅፋት ያጋጥማ ቸው እንደ ነበረ ነው የምንረዳው።

በመእህድ መግለጫ መሠረት በዓድዋ ጦርነት የተሸነፉና የሞቱ ከጣሊያኖች ወገን የእምዬ ምኒልክ ወዳጆች ስለሆኑ ቁጥራቸው ስንት እንደነበሩ ሳይጠቀስ ከባንዶዎች ወገን የታሪክ ሞት የሞቱ ከሰባት ሺ በላይ የሆኑ ባንዳዎች ናቸው ይላል። አባባሉ ግን ፈጽሞ ከእው ነተኛ ታሪክ የራቀ፤ ልብ ወለድ ነው። በዓድዋ ጦርነት የሞቱና የቆሰሉ በኢጣሊያ ወገን ራሳ ቸው ጣሊያኖች ቁጥራቸው እንዳወጡት፤ የሞቱ ጣሊያኖች ሰባት ሺ ሲሆኑ ከአንዲጀኒ (ባን ዳዎች) ስንት እንደሞቱ ራሳቸው ጣሊያኖች በትክክል ሊያውቁት አልቻሉም። የዚህ ዝርዝር ከዚህ በላይ ተገልጧል።

የመአሕድ መግለጫ እውነት ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦር ሜዳ ጦርነት የገጠሙቸው ከኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ጋራ መሆኑ ቀርቶ የኢጣሊያ ተዋጊ ወታደር ያልተሳተፈበት ከኢጣሊያ መሪዎች እና ከኤርትራውያን ጋራ ብቻ መሆኑ ነው።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፣ እንዲሁም የኤውሮጳ ታሪክ ፀሀፊዎች፣ በመአሕድ ውስጥ ከተሰገሰጉ ጥቂት ግለሰቦች በስተቀር ኢትዮጵያ በአጼ ምኒልክ መሪነት በዓድዋ ጦር ሜዳ ድል የተቀዳጀችው በአምስት ጀኔራሎች የሚመራ በኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ላይ መሆኑን በሚገባ ያውቃል። ከጣሊያኖች ጐን ተሰልፈው ስለሞቱ ባንዳዎች ከዳተኛው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢጣሊያኖች ወዳጅ አጼ ምኒልክ የሀገሬ ሰዎች አይደሉም ብሎ ለጣሊያኖች እንደ እቃ የሸጣቸው አሳዛኝ ሞት ሞቱ ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀዘኑን ሊገልጽላቸው የሚገባ ናቸው እንጂ ከጣሊያኖች አብልጠ በጠላትነት የሚያያቸው አይደሉም። የመአሕድ መግለጫ የሚያስገነዝበን አሁንም ጣሊያኖች የእጅ አዙር ቅኝ ገዢነታቸውን እያራመዱብን የሚገኙ መሆናቸውን ነው። ድሮ ኢትዮጵያውያንን እርስ በርሳቸው ለማፋጀት በይፋ የሸዋ ፖለቲካ፣ የትግራይ ፖለቲካ ብለው ይጠሩት ነበረ። ዛሬ ዓላማው ሳይቀየር ስም ብቻ በመቀየር የኢትዮጵያን ሕዝብ በማይወክሉ በጥቂት ግለሰቦች አማካይነት ጣሊያኖች ቀድሞ የሰመዱት የጠላትነት ሥራቸውን እያራመዱብን ይገኛሉ። ከእነ አንቶኔሊ ጀምሮ በሸዋ ፖለቲካ ተኮትኩተው ያደጉ የልጅ ልጆች በሸዋ እንዳሉ ሁሉ በሰሜን ኢትዮጵያም በትግራይ ፖለቲካ ተኮትኩተው ያደጉ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም ግን አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉሳ አያምንም።

ፖስታ፣ ባቡር፣ መኪና፣ ወዘተ...ወቅቱ ሰሰፈቀደ በዳግማዊ ምንሊክ መጀመራቸው ለምኒልክ ልዩ ውለታ የሚያሰጠው አይደለም። ይልቁንስ በስልክ ስም ምኒልክን የሚያስወቅሱ ሁኔታዎች በወቅቱ ተፈጥረው ነበረ። ከአሥመራ ወደ አ/አ የተዘረጋው የስልክና የቴሌግራም መስመር ስለላ ለማድረግ ስለሚመቻቸው ከምኒልክ የበለጠ ጣሊያኖች ነበረ እንዲዘረጋ የፈለጉት። በየጣቢያው በኢትዮጵያ መሬት በስልክና ቴሌግራም ሥራ የኢጣሊያ መንግሥት በጣሊያኖች ሠራተኞች ብቻ እንዲካሄድ አጥብቆ ይፈልግ ነበረ። የዋሁ ምኒሊክ ግን ጣሊያኖች ወዳጆቼ እንደመሆናቸው መጠን እንደበጉ አድራጊዎችና አሰልጣኞች በመቆጠር፣ ከጣሊያኖች ጐን ኢትዮጵያውያን ረዳት አፐሬተሮች (ሰልጣኞች) በየጣቢያው እንዲመደቡ አድርጉ ነበረ። እነዚህ ኢትዮጵያውያን በጣሊያኖች የማይፈለጉዋቸው ስለነበረ ብዙ ጊዜ በመሐከላቸው ጭቅጭቅ ይነሳ ነበረ። አንዳንዶቹ በጣሊያኖች ተከሰው ወደ ምኒልክ ለፍርድ ቀርበው ከባድ ቅጣትና ጥቃት ይደርስባቸው ነበር። ጣሊያኖችም ማስቀጣት በመቻላቸው ይደሰቱበት ነበር።



# ስለ ዓድዋ ጦርነት ከኮንቲ–ሮሲኒ የቀረበ

ስለ ዓድዋ ጦርነት ኮንቲ–ሮሲኒ ሰፋ ያለ ካቀረባቸው ዘገባዎች ወደ ኤርትራ ቅኝ ግዛታቸው በተናጠል ሸሽተው በደህና የገቡ 258 የጦር መኰንኖች፣ 4.666 ነጭ ወታደሮችና ወደ 4000 የሚጠጉ ኢንዲጀኒ ነበሩ። የቆሰሉ 461 ጣሊያኖች ከእነሱ ውስጥም 30 የተሰለቡ፣ 552 ኢንዲጀኒ ከእነሱ ውስጥም 6 የተሰለቡ፣ እግራቸውና እጃቸው ከተቆረጡ ሌላ።

የተገደሉ 289 መኰንኖች 4600 የኢጣሊያ ወታደሮች፣ ከአንድ ሺ ብዙ የማይበልጡ ኢንዲጀኒ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነው በመሸሽ ፍጥነት ስላላቸው ነው። ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ የእግር ከባድ ጉዞ 7 የጦር መኰንኖች፣ 70 ተራ ወታደሮች ሞተዋል።ምርኮኖች 1900 ወደ ሸዋ (አዲስ አበባ) ያመሩ፣ 170 በትግራይ የቀሩ ከእነሱ ውስጥም በአዲስ አበባ 54 መኰንኖች፣ በትግራይ 6 የጦር መኮንኖች ነበሩ። ከእስር በመንገድ ያመለጡ 235።

ምርኮኖች ከአዲስ አበባ ወደ ሀገሩቸው የተመለሱ 1580።

በፈታውራሪ ለማ የሚታዘዙ ወታደሮች በደጀዝማች በሻህ ሞት የተናደደ ተማርከው በእጃቸው ከገቡ ወታደሮች 70 ነጮችና 230 ኢንዲጀኒ ጨፍጭፈው በመግደል ግፍ በመፈጸማቸው ፈታውራሪ ለማ በአጼ ምኒልክ ትእዛዝ ታስሮ ወደ እንድ አምባ ተልኳል።

አስካሪ የተማረኩ 800 የሚጠጉ ነበሩ። ከእነሱም ብዙዎቹ ሊማረኩ የቻሉት የቆሰሉ ወይንም በሸሽት ጊዜ የዘገየ ኢጣሊያዊ አለቃቸው ትተን አንሄድም በማለታቸው ነው። ከእነሱ ውስጥ በአቡነ ማቴዎስ ትእዛዝ የግራ እግራቸውና የቀኝ እጃቸው የተቆረጡ በትክክል ስንት እንደ ሆኑ ባይታወቅም በእግር ጉዞ አድርገው በየመንገዱ በበሽታ፣ በድካም፣ በረሃብ ከሞቱት ሌላ ትንሽ ከ400 የሚበልጡ አሥመራ ገብተው የሕክምና እርዳታ አግኝተዋል።

ስለ ኢትዮጵያ ጦር የሞቱና የቆሰሉ ለማወቅ አስቸጋሪ ስለሆነ ኮንቲ ሮሲኒ ከተለያዩ ሰዎችን የተለያዩ አስተያየቶች አውጥቷል።

1. ኮንቲ ሮሲኒ በግሉ ካገኛቸው መረጃዎች የሞቱ 7000 የቆሰሉ 10.000 ነበሩ። ተመሳሳይ ቁጥር (Berkeley) እና (Keller) የተባሉ ዘግበዋል።
2. በአዲስ አበባ የፈረንሣይ ወኪል ከጻፈው ደብዳቤ የሞቱ የኢትዮጵያ ወታደሮች 3867 እንደነበሩ ገልጧል።
3. ሌሎች ምንጮች የሞቱ ከ4000 እስከ 5000 እንደሚደርሱ አውጥቷል።
4. ከሩሲያ በኩል የተገኙ ዘገባዎች የሞቱ 4000 የቆሰሉ 6000 ነበሩ።
5. አቡነ ማቴዎስ የሞቱ 4500 እንደነበሩ ገምቷል።
6. አጼ ምኒልክ ለፈረንሣይ ሪፑብሊክ ፕሬዝዳንት በላኩት ደብዳቤ የተገደሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች 5000 እንደነበሩ ገልጧል።

7. (Augusto Wylde) የሞቱ ከ5000 እስከ 6000 ፤በከባድ የቆሰሉ 8000 እንደሚደርሱ ገምቷል።

8. ግራዝማች የሌፍ እስረኛው ሆኖ ለነበረው ለጀነራል አልበርቶኒ እንደነገረው የሞቱ 8000 ከእነሱ ውስጥም 2000 ከጦርነቱ በኋላ ባሉት ቀናት፤ የቆሰሉ 10.000 እንደነበሩ ገምቷል።

9. ለንጉሠ ነገሥቱ ቅርብ የሆነ ሌላ ሰው የሞቱ 12.000 የቆሰሉም 12.000 መሆናቸውን ለጀነራል አልቤርቶኒ ገልጾለታል።

ኮንቲ ሮሲኒ በድሉ ኢትዮጵያ ያልተጠቀመችበት መኖሩን ዘግቧል። በዓድዋ ጦርነት ማግሥት 15 ወይንም 20.000 የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ኤርትራ ቢገቡ ተበታትነው ይገኙ ከነበሩ ኢጣሊያ ወታደሮች ተቃውሞ ሳይገጥማቸው ምፅዋ አርቂቆ ለመድረስ ባይችሉም ሳብርጉማ ዲግዲጋታ ተራራዎች ለመድረስ ይችሉ ነበረ፤ ለጀነራል ባልዲሴራ ችግር መፍጠር ብቻ ሳይሆን ለለዘለቄታው ኢጣሊያ ከኤርትራ እንድትወጣ የምትገደድበት ሁኔታ ይፈጠር ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት ጉዳት ቢደርስበትም ጦርነቱን ለመቀጠል ከፍተኛ ስሜት ነበረው፤ ለመዝረፍ ካልሆነ ተጨማሪ ኃይል እሬቱ እንደማያጋጥመው ይተማመን ነበር። በአዲስ አበባ የሰላም ውል በሚደረግበት ጊዜ አጼ ምኒልክ ለኢጣሊያ መልእክተኛ ነራዚኒ እንደነገረው የትግራይ መሣፍንቶች የኤርትራ ወኪሎች እስከ ሰሐቲ ድረስ ጦርነቱ እንዲቀጥል ይገፋፉኝ ነበር ብሎ ገልጾለታል።

ይኸን ቢደረግም በቂ ተቃዋሚ ኃይል ሲያጋጥም በድል አድራጊነት ይከናወን እንደነበረ ገልጾለት ነበር። ዕቅዱ በተግባር ማዋልም ተሞክሮ ነበር። መረጃ ሰብሳቢዎች ወደ ሰሜን ተልከው ምቹ መንገዶችና ውሃ የሚገኙባቸው ቦታዎችን እንዲጠቁሙ ተልከው ነበረ። አዝማች ሰንጋል በጽሑፍ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ዓድዋ ላይ የሰራዬና የአከለጉዛይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋራ ካልተባበሩ ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ማስጠንቀቂያ አዋጅ ሲለግ ለኢጣሊያ ታማኝ የሆነው የሰራዬ ሕዝብ በብዛት ወደ ጣሊያኖች በመሰደዱ በሐልሐል መጠለያ ተዘጋጅቶለት ነበር። ደጃዝማች ሐጎስ ተፈሪ አዝማች አበራ፤ ከንጉሡ ጦርም አንድ ክፍል ወደ ጉራዕ በሚወስደው መንገድ በበለሳ ወንዝ ሰፍረው ነበረ። በጀርባቸው ራስ ስብሐት ማይ መረት እስከ ዶንጎሎና ገለባ ሰፍሮ ነበረ። ደጃዝማች አርአያ ሌላው የወራረው መስመር ከዳዕሮ ተከለ እስከ መረብ ይቆጣጠር ነበር። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ከእንጢጮ ወደ ሐማሴን መንቀሳቀስ ጀምሮ እንደነበር የኢትዮጵያ መንግሥት የሰጠው መግለጫ አረጋግጧል። ትክክለኛ ወሬዎች ለጣሊያኖች ሊደርሱ የቻሉት በኢትዮጵያውያን ታስሮ የነበረ ማርች 3 የተለቀቀ የደምበላሱ ከንቲባ ማና ነበረ። ከንቲባው በተናገረው መሠረት የኢትዮጵያ ሠራዊት ጦርነቱን ለመቀጠል ወስና ነበር የተመረጠው የወረራ መስመርም በለሳ ማይ ሰራው ጉራዕ ሲሆን ስለዚህ መስመር አዝማች ሰንጋል ትክክለኛውን መረጃ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ከዓድዋ መነሻ ቀን ማርች 4 ወይንም 5 እንዲሆን ተወስኖ ነበር። ጣሊያኖች ከጦር ሰፈራቸው እንደማይወጡ የሚል እምነት ነበረ የኢትዮጵያ ጦርም



ጥቃት እንደማይፈጽምባቸው ሆኖ በወረራ እንደተያዘ ይቆጠር ነበር፤ ጣሊያኖች ድንገት ከጦር ምሽጋቸው ከወጡ ግን ውጊያ እንደሚከፈትባቸው ተወስኖ ነበር። ነገር ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ደቡብ የመልስ ጉዞ ጀመረ። እምዬ ምኒልክ ለነራዚኒ እንደገለጹለት ለዚሁ ውሳኔ የደረሰ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ በማሰብ ነው ብሏል። የመንገድ ችግርና የውሃ እጥረት እንዳለ ተወርቶ ነበር፤ ይህ ሁሉ ግን ሐሰት ነው። የውሃ እጥረት ሊያጋጥም የሚችለው የምኒልክ ጦር በሙሉ ሴቶች የቤት ሠራተኞች የጋማ ከብቶች ጭምር ቢንቀሳቀስ ብቻ ነው። አንድ ጠንካራ ጦር ብቻ ቢንቀሳቀስ ግን ችግር ሊፈጠር አይችልም ነበር፤ ምክንያቱም ከአንድ ወር በኋላ 42.000 የነበረው የባልዲሴራ ጦር ምንም ችግር ሳያጋጥመው ነበረ የሰፈረበት።

## Nel 1890 nasce la Colonia Eritrea, mentre Menelich fa il doppio gioco.

Già comandante di una brigata nella spedizione del gen. San Marzano, Antonio Baldissera un bravissimo ufficiale padovano di origine austriaca che aveva combattuto contro i piemontesi nel '59 aveva assunto nel 1888 il comando delle truppe e poi il Governo della Colonia.

Toccò dunque a Baldissera raccogliere l'appello di Menelich ad estendere l'occupazione militare verso il Tigrè. Il primo passo fu Cheren, in Eritrea, trampolino verso l'Asmara.

Per occupare l'Asmara, Baldissera aveva chiesto a Roma altri quattro Battaglioni Indigeni, 1700 nazionali, una batteria, e almeno 500 muli. Ma i piani di Crispi erano diversi, fondati sulla politica del *divide et impera*, cioè sullo sfruttamento delle rivalità tra i ras abissini dello Scioa e del Tigré.

Gli ultimi giorni di maggio del 1889, due colonne italiane muovono su Cheren, dove la banda del *barambaras* Kafèl presidia il fortino. La banda viene disarmata e, lasciata a Cheren una piccola guarnigione, i nostri rientrano a Massaua.

In giugno vengono occupate Sabarguma e Ghinda. Il 2 agosto tre colonne si arrampicano verso i prati dell'Asmara, a 2350 metri d'altezza, trascinando i cannoni sull'orlo dei burroni; il giorno dopo Baldissera si installa all'Asmara nel palazzo di ras Alula. Da qui, il governatore militare lancia il suo proclama: «Coltiva, o coltivatore. Commercia, o commerciante. Non temere. Chi governerà è il Governo d'Italia... Io sono venuto per arricchire e per proteggere il paese, non per distruggere...».

Sembra l'inizio di un'era di pa-

## Menelich invoca Baldissera




**Il Negus Menelich**

*Divenuto Negus d'Abissinia nell'89, Menelich (nella foto) incoraggia Baldissera a occupare tutto il Tigrè.*

# ምዕራፍ 10

## ኤርትራ፣ በቋንቋ፣ በጐሳ ወዘተ

የአንድ ሀገር የአንድነት መለያ ወይንም መመዘኛ ነጥቦች ቋንቋ፥ ጐሣና ሃይማኖት፥ ለብዙ ጊዜ አብሮ መኖር፣ ባሕል የአለባበስ፥ የአመጋገብ ተመሳሳይነት፥ የመሬት አቀማመጥ ኩታ ገጠምነት ወዘተ ናቸው።

ቋንቋ የአንድ ሕዝብ ማንነት ብቸኛ መለያ ሆኖ ሊወሰድ አይችልም። ትግሪኛ፥ አማርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ አፋርኛ፥ ሶማሊኛ ወዘተ ተናጋሪዎች የቋንቋ አንድነት የሚያሟሉ ቢሆኑም የጐሣ (ዘር) አንድነት ግን አያሟሉም። ለመላ ኢትዮጵያ ምሳሌ ብዬ የጠቀስኳቸው የሳሆ ወይንም ዓሳውርታ ተናጋሪ ሕዝብና በኒ ዓመር የሚባሉ ናቸው። ሳሆ አንድነታቸው የተመሠረተው በቋንቋ ነው በዘር ግን ከዚህ በዝርዝር እንደሚቀርበው ከ21 ጐሣዎች የተውጣጡ ናቸው። ሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ የሚኖርበት የመሬት ስፋት በጣም አነስተኛ ነው፥ ከአንድ ወረዳ ያነሳ ነው። በተቃራኒ በኒ ዓመር የሚባሉ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው (ትግሬና በጃ)፣ በአንድ መጠሪያ ስም አብረው የሚኖሩ ግን ለብዙ መቶ ዓመታት ብቻ ሳይሆን ምናልባት ለብዙ ሺህ ዓመታት ነው። የቀድሞ ቅኝ ገዢዎቻችን ጣሊያኖች የቋንቋ አንድነት ቢኖራቸውም የዘር አንድነት የላቸውም፥ የተለያዩ ቋንቋዎች ነበሩዋቸው አሁንም አልጠፉም ዲያሌክት እየተባሉ ይጠቀሙበታል በብዛት ተሰራጭቶ ኢጣሊያ ቋንቋ ለመሆን የበቃ የአንድ የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር የቱስካና በተለይም የዋና ከተማዋ ፊረንስ ቋንቋ ነው።

የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የካም ዘሮች መለያ የሆነው በጐሣ ስለሚያምኑ ለእርስ በእርስ ጦርነት ተዳርገው ይታያሉ። የአፋር ሁኔታም ከሶማሌዎች ጋራ ተመሳሳይ ነው። በተቃራኒ በጐሣ አንድነት የማያምኑ ኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው። አንድነታቸው የተመሠረተው ከባንቱ የወረሱት፣ በካም ዘሮች ሁሉ የሌለ የዕድሜ ክልል አንድነት የጋዳ አስተዳደርና የቋንቋ አንድነት ነው፣ የጐሣ አንድነት ግን አያሟሉም። ትግሪኛና አማሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ የቋንቋ አንድነት ካልሆነ የጐሣ አንድነት የላቸውም።

የሃይማኖቱ መለዮ ጉዳይ በሀገራችን ጐልቶ የማይታይ ቢሆንም በውጭ ሀገር ለምሳሌ ሕንድ፣ ፓኪስታን፣ ባንግላዲሽ የተለያዩበት በቋንቋ ወይንም በጐሣ አይደለም በሃይማኖት ብቻ ነው። እንደዚሁም ሱዳን በጦርነት የምትታመሰው በሃይማኖት ምክንያት ነው በአውሮጳም በሰሜን አየርላንድ እንደዚሁም በቦሲኒያ የሚደረገው ውጊያ በሃይማኖት ምክንያት ብቻ ነው፣ የዘር ወይንም የቋንቋ ጥያቄ የለም። ኤርትራ ሀገር የሚያደርጋት ማንኛውንም መመዘኛ አታሟላም። ኤርትራ የምታሟላው ለኢጣሊያ ቀኝ ገዢዎች ጥቅምና ዓላማ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት እንደ ጦር ሰፈር ጣቢያ እንድታገለግላቸው ብቻ ነው። ከጣሊያኖች ሌላ ኤርትራ እንደ ሀገር መፈጠር አጼ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ እንዲጭን ከጫኑ በኋላም እንዳይነጠቅ አገልግሎት እንድትሰጥ ለግሉ ተጠቅሞባታል። ኤርትራ ባትፈጠር ለዘውድ ሥልጣን ተፎካካሪዎ ትግራይ አትዳከምም ነበር ከአጼ ዮሐንስ ሞት ብኋላ አጼ



ምኒልክ ሥልጣን ቢጨብጥም ከትግራይ ብርቱ ተቃውሞ ይገጥመው እንደነበረ አያጠራጥርም። በዚሁ መሠረት ጣሊያኖች ኤርትራን ይዘው እንዲቀመጡ ረድቷቸዋል አደፋፍሯቸው ከጣሊያኖች ገንዘብ በማግኘት ተጠቅሟል።

የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ተዋርደው ከሀገራችን ሲወጡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ እንድትዋሐድ አመቺ ሁኔታ ስለተፈጠረ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ተሰጧት በፌዴሬሽን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ ተዋሕዳ በነበረችበት ጊዜ አጼ ኃይለሥላሴ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሕዝብ እንደ ኤርትራ ጥያቄ እንዳያቀርብ በመፍራት የዲሞክራሲ ጥያቄ እንዳያቀጠቅጥ በመፍራት ለግሉ አገዛዙ ብቻ በማሰብ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ሙሉ አንድነት በማወጁ፣ በውጭ መንግሥታት እየተረዱ የኤርትራ ገንጣዮች እንዲደራጁ አደረጋቸው። ስለዚህ የቀድሞ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ኤርትራ እንድትቋቋም ያደረገው ከጣሊያኖች ጋራ በመመሳጠር አጼ ምኒልክ ሲሆን የአዲሲቷ ነፃ መንግሥት ኤርትራ እንድትቋቋም መሠረት የጣለው ለግሉ የዘውድ ስግብግብነት አጼ ኃይለሥላሴ ነው። ሁለቱም በከሐዲነት በታሪክ ተጠያቂ ናቸው።

በኤርትራ የሚኖረው ሕዝብ ግን በቋንቋ፥ በታሪክ፥ በዘር፥ በሃይማኖት፣ በባሕል ወዘተ ከቀሩት ኢትዮጵያውያን የሚለይበት አንድም ነገር የለም። ይህ የሁሉ ኢትዮጵያውያን እምነት የሆነው አባባል ትክክለኛው መሆኑን ለማስረጃነት ኤርትራ በዘር በቋንቋ በሃይማኖት ከዚህ በታች በዝርዝር አቀርባለሁ።

የኤርትራ ሕዝብ እንደ ሶማሊያ የጐሣ ግጭት ባይኖርም በጐሣ የተከፋፈለ ነው። ከዚህ በታች በዝርዝር የሚቀርበው ግን በመጀመሪያ በቋንቋ አከፋፈል ሲሆን ለእያንዳንዱ የጐሣ አከፋፈልም ይቀርባል። ትግሪኛ ተናጋሪ ከሆኑ 3 አውራጃዎች (አከለጉዛይ፣ ሐማሴንና ሠራዬ) በማስቀደም ፖሌራ 1 በደረሰው መጽሐፍ እንደዚሁም በሕዝቡ አፈ ታሪክ መሠረት በማድረግ አቀርባለሁ።

## አንደኛ የአከለጉዛይ አውራጃ የጐሣ አከፋፈል

በአከለጉዛይ አውራጃ የሚኖረው ሕዝብ ለመጀመሪያ ለሁለት ሊከፈል ይችላል የምናብ ልጆችና ከምናብ የማይወለዱ። ከምናብ የሚወለዱ እንደገና ለ4 ይከፈላሉ። አከለጉዛይ፣ ሽመዛና መረታ።

### ሀ. የአከለ ልጆች የሚከተሉት ናቸው

1. ፀንዓ ደግለ 4. አከራን ወዲ አከለ
2. ሐደግቲ 5. መስሐል ወዲ አከለ
3. ደቂድግና 6. ዘርኢሞሲ

### ለ. የጉዛይ ልጆች ወይም ደጉዛይ የሚከተሉት ናቸው።

1. ዓረት 4. ደረጨን
2. ዝባውንቲ 5. መጽሔ
3. ደቂ ዘርኢ ሠናይ 6. ሐዳድም ጨዓሎ

7. ደቂትሕዝታ

## ሐ. የሽመዛና ልጆች የሚከተሉት ናቸው።

1. ዝባን 3. እንዳዳሼን

2. አንሩፍ ላዕላይ

አግሩፍ ታሕታይ 4. አምበሰት

## መ. መረታ ሰበን መረታ ቀይሕ

በአካለጉዛይ የምናብ ልጆች 63 ከመቶ ናቸው

## በአከለጉዛይ የምናብ ልጆች ያልሆኑ የሚከተሉት ናቸው

1. ተድረር ከበለው ቤተ የሚወለዱ ሰለስተ ደቂድራር ይባላሉ።

2. ከሌላ ቦታ ፈልሰው የመጡ እንዳሐጺንና ሮብራ ወረደ ምህረት ከሚባለው የዛጉዌ የአጼ ይትባረክ ልጅ የሚወለዱ፤

3. ደቂ ንብረ አዲ ማቶም እገላ ሐምስ አግነ የአጼ አምደ ጺዮን (ተጉለት) ልጅ የሚወለዱ እንደዚሁም ኢዳ የሚባሉ በአሳውርታ የሚገኙ።

4. ደጊዔን፤ ገጊዔን ወገራ ከአንካላ ደንከል የሚወለዱ

5. እንጋናእ በሐማሴን የሚገኙ ጨዋ ከተባሉ የሚዛመዱ ከጠላት ከመከላከል በጥንት ጊዜ በነገሥታት የታሉ ..

# ሁለተኛ የሐማሴን የጉሣ አከፋፈል

ሐማሴን ሲባል በኢትዮጵያውያን ዘንድ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መረብ ምላሽ ከሞላ ጎደል የዛሬዋ ኤርትራ ያመለክት ነበር። በአፈ ታሪካችን ታሪክ መሠረት አንበሳ (ዓይን ሳባ) ቀዳማዊ ምኒልክ የተወለደበት ሀገር ነው። እንዲሁም ማይበላ ንግሥተ ሳባ ውሀ ጠምቷት ውሃ የጠጣችበት ቦታ ነው። የሐማሴን ትርጓም በአንድ ሃብታም የበለው ሴት ደግ፣ እንግዶች ተቀባይ የነበረች የተሰጠ የአዘን እማት (የእዘን እማች) ማለት ነው ተብሏል። ሌሎች ደግሞ ከመሐዛ ጥንታዊ መሐዛ የአክሱም ገባር ሕዝብ በንጉሥ ኢዛና ጽሑፍ የተጠቀሰ የመጣ ነው ይላሉ።

ምዔን መሐዛ የሚባል አሁንም በአከለጉዛይ አውራጃ ኩዓቲት አጠገብ የአውራጃው የሀገር ባሕል ሕግ የተደነገገበት አንድ ትንሽ ወንዝ ይገኛል።

ምናብ አንደኛ በ950 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ቀዳማዊ ምኒልክን ከእየሩሳሌም አጅቦ የመጣ ሲሆን ከእሱ በኋላ ከ5–15 ትውልድ ተቆጥሯል። ወደ ንጉሥ ሜርኒ ለመድረስ እስከ ሜሮኒ ድረስ ምናብ ይኖር የነበረ በደንብያ (ጎንደር) ነበር። ሜሮኒ ወደ ሐማሴን በመምጣት ፋሉቅ፣ ማሉቅ፣ ሜሉቅ ተወለዱ።

«የሜሮኒ ከደንቢያ ጉንደር ደምበዛን መፍለስ በትክክል የሚያስታውሱት የእሱ ልጆችና የልጅ ልጆችም የማያጠራጥር ስለሆነ እስከ እሱ ያለው ሀረግም ትክክል መሆኑን መወሰድ አለበት።»



ተስፋ ጺዮን የአቴሼም ልጅ ይኖር የነበረው በአጼ ሱሲኒዮስ ዘመነ መንግሥት (1607–1632) ስለሆነ ሜሮኒን በዘጠኝ ትውልዶች ስለሚቀድመው ሜሮኒ ወደ ደንቤዛን የመጣበት ዘመን በ1300 አጋማሽ መሆን አለበት።

የደንቤዛን መንደሮች የሚከተሉት ናቸው

1. ዓዲ ተከለ ዛን 2. ማጋርካ 3. ሹማንጉሥ ላዕላይ 4. ሹማ ንጉሥ ታሕታይ

5. አፍደዩ 6. ጨርሺ 7. ዓዲ አኮሉም 8. ጋሺናሽም

9. ሐየሎ 10. ጉሬታት 11. ዘንገረም 12. ደቂ ዘሩ

13. ደታ መሀረ 14.ደቂ ንብሩ 15. ዋራ 16. እና ናላይ።

ጨርሺ ውስጥ ከአገው ላስታ የመጡ አንደ ብሌን ይገኛሉ።

በሹማ ንጉሥ ታሕታይ ከተምቤን የመጡ ይገኙባቸዋል። በዘንገሬም ከአክሱም የመጡ ይገኙባቸዋል።

ደቂቴሽን መንደር ስሙ ያገኘው ከአቴሽን የሀዝባይ ልጅ ነው። ከልጆቹ 3 ቡሮህ መርቆርዮስ ዛርቶናይ በአባታቸው መንደር በዓዲ ቆንጺ ሰፈሩ ሌሎች ግን

ሀ. ተስፋ ጺዮን የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን ዓዘጋና ፀዐዘጋ ቆረቆሩ፡

ለ. ገብረ ክርስቶስ ፃዕዳ ክርስቲያን

ሐ. ራውያ ወቂ ድባ

መ. ያዕቆብ ዓዲ ያዕቆብ

ሰ. ሙሳ ዓዲ ሙሳ

የተስፋ ጺዮን አራት ልጆች ምናብና ዘራይ ዓዘጋ ደረሳቸው፡ ታከለና ኢጋብ ጸዐዘጋ ደረሳቸው

## የደቂቴሽን ተወላጆች የሚከተሉት መንደሮች ናቸው።

1. ገጀረት 2. ጎዳይፍ 3. ዓዲ ሰግዶ 4. ወቂ ዱባ 5. ቁሸት

6. ፃዕዳ እንባ 7. ዳዕሮ ተሙሉስ 8. እና ጉዶ 9. አዲ ለሰን

10. ፃዕዳ ክርስቲያን።

## የምናብ ዘርዓይ (ሐዘጋ) መንደሮች የሚከተሉት ናቸው

1. አብነይና ሹም ጊሚሮ ከምናብ የሚወለዱ

2. ዓዲ ሽማግሌ፡ ዓዲ መረኒ፡ ዓዲ እሰፈዳ፡ ዓዲ ሃብትሉስ እና ሐዘጋ ከዘርአይ የሚወለዱ

3. ዓዲ በደል፡ አመትዱ፡ ኮልኮሌ፡ ኢያዐ፡ አደና ቅልቅል ከሩቅ ቦታ የመጡ፡

4. ዓዲ ያዕቆብ በፍላንቱ ከምናብ ዘርአይ የተቀላቀለ።

ከሁሉ የላቀ መንደር ብዛት ያለው የደቂ ዘርአይ ነው። የሐዘጋ መሬ በመሆን ከታኪለ ኢጋብ (ፀዓዘጋ) ለሥልጣን ተወዳድረዋል።

ታከለ ኢጋባ (ፀዓዘጋ) ከደቂተሺም ሌላ ከፍል እስከ አከለጉዛይ ሐማሴን፡ ሰራዬ እስከ ወልቃይት ግዛቱን አስፋፍቶ ነበር። በፍላጎታቸው ከፀዓዘጋ የተቀላቀሉ ደቂ ምናብ መንደሮች 1. ዓዲ ቆንጺ 2.ዓዲ ሙሣ 3. ዓዲ ገብሩ 4. ዓዲ ተክላይ 5. ዓዘጋ ናቸው።

ዓዲ ቆንጺ የደቃተሺም ምናብ ዘርአይ እና ታከለ ኢጋባ ዋና ከተማ ነበረች

## ደቡብ ካርነሺም

አስር መንደሮች አሏት እነሱም– 1.እንባ ደርሆ 2. በለሳ 3. መድረጽዮን 4. ኩዓጺዮን 5. ገረሚ 6. ምድሪ ዛውል 7. መስፍንቶ 8. ፀሐፍላም 9. ደቂ ጴጥሮስ 10. ዓዲ አረጊት

## ሰሜን ካርነሽም

1. ዓዲ አጺዮን 2. ወቂ 3. ዓዲ ሻቃ 4. ዛግር 5. ደከሰብ 6. ጉዋንተባ 7. ዓዲ ሐንዳ 8. ዓዲ ጂን 9. ደፈረ ነገደ ሰዊ ይባላሉ።

ከተንቤን እና ከአሸርጋለ የመጡ በገራሚ፡ በለሳ፡ ኩዓጽዮን (ደቡብ ካርነሺም) የሰፈሩ ናቸው።

ከዓጋሜ የመጡ ዓዲ ጺዮን (ሰሜን ካርነሺም) መድረጽዮን (ደቡብ ካርነሺም) ደፈረ ዛውል ደቂ ዮሴፍ ናቸው። በተጨማሪም ዓዲ ሻቃ ዋቂ እንዲሁም ዛውልም የሰፈሩ ናቸው።

ዛግር ከዓዲ አቦ የመጣ ከባሪያዎቹ ጋራ አቢ የተባለ የሰፈረበት ነው። መስፍንቶ የመጀመሪያ ኢትዮጵያን የገዙ የካም ዘር አጋበስ አባቡ አሩዌን ጎድሉ 400 ዓመት ሲገዛ የነበረና የነገሠ ነው ይባላል።

ደከሰብ ከመደባይ ታቦር (ዓዲ አቦ) መጥተው የሰፈሩ

ፀሐፍላም ከድባርዋ የመጡ

ደቂ ጴጥሮስ ከዓዲ ተከለዛን የመጡ

ዓዲ አረጊት እና ጉዋንተባ ከአስገደ (ጽንዓደግለ) በጂንና ዓዲ ሐንዳ

በቶፋይ ከአካለጉዛይ የመጣ የሰፈረበት። በእንባ ደርሆ የካርነሽም ዋና ከተማ ብዙ ጐሳዎች ይኖራሉ፡ ገዛ ደገ ከመስፍንቶ እንወለዳለን ይላሉ። አገሙ ለዊ እንደዚሁም ገዛ ሐም ዚየገና ኩዓጽዮን ግሮቶም የሚባሉም እና ሌሎችም ከምናብ ደቃቱሽም ዘርአይ ታከለ ኢጋባና ከደምቤዛን ጋራ እንወለዳለን ይላሉ።

ገዛ ኩዓዮን ከኩዓጽዮን የመጡ እነሱም ከአካለጉዛይ ጽንዓ ደግለ የመጡ ናቸው። በእምባ ደርሆም ከፍተኛ ሥልጣን ስለነበራቸው የካርነሽን መሪ ከእነሱ ብቻ ይመረጥ ነበር። በ1600 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ቢዝሙት የሚባለው ኃይለስ ጉዋዳድ አስገደ እና ሂላል የሚባሉ 4 ልጆች ነበሩት። አስገደ ከወንድሞቹ ጋራ ስለተጣላ ዓዲ ንፋስ የተባለ መንደር ቆረቆረ። የካርነሽም አንድ ክፍል ነበር አሁን ራሱን የቻለ ሆኗል። ዘሮቹ ተባዝተው ከእነሱ እንዱ ሂቢስ የሚባለው የሐባብ፡ ዓድ ተማርያም ዓድ ተክለስ ምናልባትም በጂግ የሚባሉ ባላባቶች ሆነዋል።

ቢዝሙት የራሱ ወገኖቹን ለማጠናከር እዛዝ የተባለው ከእንክላ ትግራይ አስመጣ። እሱም እንባደርሆ ከሰፈረ በኋላ የበላይነት አገኘ። ከነገደ ያሁዳ እወለዳለሁ በማለቱም



በሌሎች ጎሳዎች የመሪነቱን ሥልጣን ያዘ። ካርነሽም በፀዐዘጋ ሥር በነበረበት ጊዜ ከእነዚህ አንዱ በኪት የተባለው የወረዳው መሪ በመሆን የከንቲባ ሹመት አገኘ። ምክንያቱም ከአስገደ የምትወለድ ወ/ሮ ጎበዙ አግብቶ ስለነበረ እነሱንም እወክላለሁ ብሎ ለመናገር ችሎ ነበረ። የአስገደ ተወላጆች ግን አላአግባብ ስልጣናችን ተነጠቅን የዓዲ ንፋስ መሪ መሆን የሚገባን እኛ ብቻ ነን በማለት ስለተቃወሙ አጼ ቴዎድሮስ ዓዲ ንፋስን ኡሽቴ ጉልቲ አደረገው ማለት ራሱን የቻለ ግብር በቀጥታ ስንጉሡ ብቻ የሚከፍል። ይህ ደንብ አሁንም ይሰሩበታል የአስገደ ልጆች ስለዚሁ ግን በደቡብ ከርድኔሽም በሰሜን ከርዲኔሽም አዲ ንፋስ በማለት ሹመቱን ተከፋፍለውታል።

## ራሳቸውን የቻሉ (ራስ ገዝ) መንደሮች

እነሱም 1ኛ/ አስመራ ከተማ ሐዳሙ ጭምር እንዲሁም 2. ዓዲንፋስ 3. ዓዲ አበይቶ 4. ቤት መካ የተባሉ መንደሮች ናቸው።

በጥንት ጊዜ አሥመራ አራት ጐሳዎች የሚኖሩባት አንድ መንደር ነበረች። እነሱም 1ኛ/ አሥመራ ከዓሳውርታ ተራራዎች የመጡ የሩበን ጎሳ የሆኑ 2/ ስራንስር አንዳንዶቹ ከሰመሐር ዓድሳውራ የመጡ ሲሉዋቸው ሌሎች ደግሞ ዓዲጺዮን ከአጋሜ የመጡ የዮሴፍ ነገድ ይሏቸዋል 3/ ሹላሌ ከአከለጉዛይ የመጡ 4/ ግሮቶም አንዳንዶቹ ከሰምሐር የመጡ ሲሏቸው ሌሎች የአገው ዘር የሆኑ እንደ ዓዲ አቢዮቶ ያደርጉአቸዋል።

## ሰሐርቲ

ከነገደ ስምኦን የሚወለዱ ተመሳሳይ ካላቸው ከሰባት የትግራይ ቤተሰቦች ከላስታ የመጣ ሌላ ቤተሰብም ሁሉም አገው ስለሆኑ ስስሚዛመዱም ተስማምተው የሚኖሩ ሾብሀተ ሰሐርቲና የላስታ ከዱዱ ተብለው ይጠራሉ። ሰባት መንደሮች አሏቸው። 1. ሀሉት 2. አዲ አውሻ 3. ዞጊብ 4. ዓዲ እሕደሮም 5. ዓዲ አራዳ 6. አምበይቶ 7. ቆዳዱ። ከእነሱ ዘር በሐማሴን፤ በሠራዬ፤ በአከለጉዛይ ተበታትነው ይገኛሉ።

## ሰለስተ ውቅርቲ

ከነገደ ሰዊ እንወለዳለን ይላሉ፤ ነገር ግን ከውቅሮ አምባ ሰመይቲ ከትግራይ የመጡ ናቸው፤ ስለዚህ ከአምባ በማይቲና ከጎረቤቱም ከሀሀይሌ ትግራይ በዘር ይቀራረባሉ። ሦስት መንደሮች ብቻ ነበሩ። 1. ውቅሮ 2. ዓዲዛመር እና 3. ዝባን አገብ።

## ላምዛ

ከአንድ ንጉሥ ትብጠት የተወለዱ ናቸው። ስለዚህ የይሁዳ ነገድ ናቸው። ወረደ ምህረት የተባለው ንጉሥ ወይም መሥፍን ወደ አከለጉዛይ ስለመጣ ዓዲኢክሊ በተባለው ቦታ ሰፈረ። በዚሁ ጊዜ አንድ የመረታ ሴት አንድ ላም ለማበርከት እፊቱ ቀረበች። ንጉሡ

ከላሟ ቀንጆ ልለዝበረች ልጅቷን መረጠ። ከዚሁ ግንኙነት አንድ ወንድ ልጅ ተወለደ። ነገር ግን ሌሎች ላምዛ ለምዘታይ የላም እረኛ ማለት ነው ይላሉ። የላምዛ ሰዎች ግን በ7 ቤተሰብ የተከፈሉ ከትግራይ ዐራ የመጡ መሆናቸው ያምናሉ። እነሱም:- ላምዛ፣ ዓዲካ፣ ዓዲ አብዛማት ፣ እና እዲዘናፍ እቋቋሙ። መራዋ፣ ዓዲ ቀይሕ፣ ዓዲ ቀሺ፣ ዳንባ፣ ዓዲ አከሉ፣ ኮርባቲ፣ እና እዛዩ የተባሉ መንደሮች ግን ከአክለጉዛይ፣ ከጨዋ፣ ከምናብ ዝርአይ እና ከአማዲር የመጡ ያቋቋማቸው ናቸው። በበኩላቸው የላምዛ ሰዎች በሰሐርቲ፣ ሎጎ ጨዋ እና ሌሎች የሐማሴን መንደሮች እንደዚሁ በአክለጉዛይ፣ በሰራዬ፣ ሰፍረው ይገኛሉ በተለይ በድባርዋ፣ ገዛለምዛ የተባለ ትልቅ መንደር አለ።

## ሎጎ

ከመሀከላዊ መንግሥት ፀጥታን ለማስከበር የተላኩ ወታደሮች ተዋልደው ተባዝተው የተመሰረቱ ናቸው። በመጀመሪያ ጊዜ ወደ መረታ አከለጉዛይ የመጡ ከቋራ ነው ይባላል። ብዙ ግፍ ስለሰሩ ሕዝቡ ቤቶች ተገፋፍቶ ሁሉንም ጨረሳቸው። ርጉዝ ሴቶች ሳይቀሩ። አንድ ርጉዝ ሴት ብቻ አምልጣ ወደ ሽከቲ ሸሽታ ትሔዳለች። ወንድልጅ ወልዳ ተስፋ ጊዮርጊስ ነኪ የሚል ስም ተሰጥቶት የሎጎ አባት ለመሆን በቅቷል። ይህች ሴት ላምዛንም የወለደች ናት። ስለዚህ ሎጎና ላምዛ ዘመዳሞች ናቸው እንደገና በመብዛታቸው ከእነሱም ወደ አከለጉዛይ መጥተው ሎጎ ሳርዳ መሠረቱ፡ የቀሩት በጽልማ በሰፋ በደቡባዊ ሐማሴን ሰፈሩ።

በ1450 አጼ ዘረአ ያዕቆብ ተነስቶ የነበረ የሀይማኖት ክርክር ለማብረድ ወታደሮች ወደ መረብ ምላሽ ልኮ ነበር። ወታደሮች ወደ ተመደቡበት ሲደርሱ የነገደ ይሑዳ ነን ብለው ይናገሩ ስለነበሩ በግራኝ ጦርነት ምክንያት ከቤተመንግሥት ጋራ ወደ ሰሜን የመጡ መሆናቸውን ይገመታል። በዚሁ ምክንያት ጨዋ ተብለው ከሎጎ ጋራ እና በሌላ ቦታም እንዲሰፍሩ ተደረጉ። በሰራዬ ሎጎ ጨዋ የዕልማና የበፋ ወረዳዎች ሰፍረዋል። ከበላ ጨዋ ተብለው የሚጠሩት መንደሮች በሐማሴን ሰፍረዋል። ሎጎ ሳርዳ በሚባሉ በሽመዛናና በአካለ ጉዛይ ሰፍረዋል።

## ሸብዓተ ዓንሰባ

1. ደቂ ነአምን እና 2. ዓዲ ዮሐንስ ከአማራ (ጎንደር) የመጡ ናቸው 3. ሞላዘናይ ከሸዋ 4. ደቂ ዳንሺም 5. ደርስነይ ከሽመዛና አከለጉዛይ 6. ደቂ ሻሐይ ከዓላውርታ 7. ደቂ ዓንዱ ከትግራይ የመጡ ናቸው።

## ሦስተኛ የሠራዬ አውራጃ የጕሳ አከፋፈል

በ2ኛ አጋማሽ የ13ኛ ክፍለ መቶ ዘመን የዛግዌ ስርወ መንግሥት በወደቀበት ጊዜ አገው ዘር የሆኑ የሰሎዋ አሞተጂር ከተባለው ይወለዳሉ በሚባሉ በወረ ሰናዝጊ በተባለው መሬት አዲሶቹ የአማራ ገዢዎች በመፍራት ወደ ሰራዬ መጡ አትከሙ መልጋ ተብለው እየተጠሩ ቀደም ብለው የነበሩ ነዋሪዎችን በማጥፋት ወይንም በማዋሀድ ሀገሩን ሁሉ



ተቆጣጠሩት። እነዚህ አትከሙ መልካ የይሁዳ ዘር ናቸው። መሪያቸው ዋሬ ሰናዝጊ ሦስት ልጆች ነበሩት። ሀ/ ማይ ለ/መልጋ ሐ/ ተስፋ

ተስፋ ከታናሽ ወንድሞቹ ሳይስማማ ስለቀረ ወደ ምዕራብ በኩል ሄዶ ሰፈረ ልጆቹም ደቂ ተስፋ ተብለው ሀገራቸው ሆነ። ለማይ ዋናው ሰራዬ ደረሰው፣ መልጋ፣ ቁሐየንና መራጉዝ ደረሰው።

## 2ኛ. የቢለን ቋንቋ ተናጋሪ

ከገብሬ ታርካ ነገድ ከላስታ የመጣ የሚወለድ ከታኩቴ የሐማሴን የመጡ እነሱም የአገው ትውለ ዘር ስላላቸው በቦጎስ ከረን አካባቢ የሰፈሩ በ1530 ዓ.ም. ነው። ቋንቋቸውም ከአገውኛ የሚዛመድ ነው። የቢለን ቋንቋ ተናጋሪ ከላስታ ወደ ከረን አመጣጥ በማስመለከት እጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘር አንድነት የሚያስገነዝቡን ሁኔታዎች እናገኛለን። አልበርቶ[1] ፖሌራ ስለ ቢሌን እና አገው ሕዝብ አስተያየት ሲሰጥ ጉዳዩን በትክክል በማስቀመጥ እንደሚከተለው ፅፏል። «ከአገው ፈልሰው ወደ ኤርትራ በመጡበት ጊዜ ቢሌኖች የዘራቸው ምንጭ አገው ሳይጠፋ የቀረ ናቸው። ወደ ሰሜን ባደረጉት ጉዞ ብዙ ምልክቶች በመላው ኢትዮጵያ ይታያሉ፤ በጎጃም የአገው ምድር ሰባት ጎሳዎች ይገኛሉ፤ እንደዚሁም በቋራ፤ በደንቢያ፤ በጌምድር፤ ወገራናት ሰሜን፤ አብዛኛው የትግራይና የዐጋሜ ሕዝብ፤ በዛጉዌ ዘመን መንግሥት ጊዜ ከአገው ጋራ የተቀላቀለ ነው። እንደዚሁም ከመረብ በለሳ በስተ ሰሜን በደጋ የሚገኝ ሕዝብ በተለያዩ ጊዜያት ከላስታ፣ ከቋራ፣ ከደምቢያ፣ ከትግራይ፤ ከዐጋሜ እየፈለሰ የመጣ ስለሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አገው ሕዝብ ግንኙነቱ የተቃረነ ነው። ይህ ሁኔታ ትክክለኛነቱ የሚረጋገጥ አሁንም የዓላውርታ ሰዎች ክርስቲያን ሐበሾችን ቢለን ብለው ይጠሯቸዋል። አንድ የአጼ ዐምደ ጺዮን ሚስት (1322–1342) የኤርትራ አገድ ከልል በ1322 ትገዛ የነበረች ስሟ ቢለን ሳባ ነበረች። የዚሁ ክፍለ ሀገር አንድ ሀገረ ገዢ ከብዙ 10 ዓመታት በኋላ እሱም ቢለን ሰገድ ተብሎ ይጠራ ነበር። 100 ዓመት በኋላም የሰራዬ ሀገረ ገዥ ቢለን ሰገድ ነበረ ስሙ። የቢለን ሰዎች፤ በተለይ የመገረብ መንደር ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ምንም እንኳን ትግሪኛ በሚናገሩ የተከበበ የአገው ቋንቋ የማይናገር ቢሆንም በማያጠራጥር ሁኔታ ከአገው መምጣቱ የሚያስታውሱ የአገውኛ ስም ቦታዎች አሉት። የሰራዬ ሕዝብ በሙሉም ከአገው መምጣቱ አይተናል። የግእዝ ቋንቋ ወደ ትግሪኛ የተቀየረው የአገው ሕዝብ በውስጡ በመግባታቸው ነው። የአገው ሕዝብ ባዶ መሬት ያገኙ እንደ ቦጎስ ግን የአገውኛ ቋንቋቸው ሳይቀየር ተመሥርቷል። በዚሁ ምክንያት ከዚህ በላይ ትግሪኛ ተናጋሪ ከሆኑ ሕዝቦች ቢሌኖች ዝመድናቸው የተለዩ ሳይሆኑ በዘራቸው በኩል እንደተለጣፈ መሆናቸውን ያስገነዝበናል፤ ስለዚህም ነው ከትግሪኛ ተናጋሪ ጋራ በዚሁ ዝርዝር ሊቀርቡ የቻሉ በዛሬ ዘመን ቢሌኖች ከቋንቋቸው ሌላ ትግሬ የበለጠ የተስፋፋ ቋንቋ ይናገራሉ። ስለዚህ የትግሬ ቋንቋ እየተስፋፋ ቢሄድ የቢሌን ግን እየጠፋ እንደሚሄድ ይታመናል።

1. Alberto Pollera: Le Popolazini Indigene Dell' Eritrea

ከዚህ በላይ የተጠቀሰ ታሪክ ከባሕላችንና ከአፈ ታሪካችን የሚስማማ ሲሆን ከደቡብ ዓረቦች ከሳባውያን የዘር ዝምድና እንዳለን ግን ባሕላችን የማይቀበለው ነው። በዚሁ መሠረት አገው ከሴማዊ ነገድ ይሁዳ ጋራ ምንም ግንኙነት የላቸውም የኩሽ ወይንም የካም ጉሳ ናቸው የሚለው አባባልም ውድቅ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም ሰለሞን ከነገደ ይሁዳ አንዱ ነው እንጂ እሱ ብቻ አይደለም ነገደ ይሁዳ።

## 3ኛ የትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ

ከአጠቃላይ የኤርትራ ሕዝብ ትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ 50 በመቶ የትግሬ ተናጋሪ 27 በመቶ ነው። የትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ የሚኖርበት መሬት ከምፅዋ በስተደቡብ ከደህላክ ደሴቶች እስከ ከሰላ ሲሆን በቤጃና በፉንግ ወራሪዎች ተከበው ተርተው ባሕላቸውና ቋንቋቸው የቀየሩ አሉ። እንዲሁም በደቡብ አፋር ሳሆ ሕዝቦች የተሻለ መሬት ፍለጋ ወደ ሰሜን ስለሚንቀሳቀሱ። ከደጋ ትግሪኛ ተናጋሪም ወደ ትግሬ ተናጋሪ ሄደው የገቢ መደብ የሆኑ አሉ። የዛሬ ትግሬ ተናጋሪ የሚከፋፈሉ በታውን በያዙ ባላባቶች ስለሆነ በዚህ መሠረት ተከፋፍለው እንመለከታቸዋለን።

አራት ጉሳዎች ከአንድ ነገድ እንወለዳለን የሚሉ በቋንቋ ግን የማይገናኙ 1ኛ/ ቀርን ሐሶ፣ 2ኛ/ የሳሆ ቋንቋ የሚናገሩ 3ኛ/ መንሳዕና ማሪያ የትግሬ የሚናገሩ ናቸው።

ሁሉም ከዓረብ መጣን የሚሉ ሲሆኑ በዘር አቆጣጠር ይለያያሉ።

## 1. መንሣዕ

ከኮረይሽት የመሀመድ ነገድ ከዘድ የሚባው የመጣነው። ቀርና በ1300 ዓ.ም ነው ሲሉ ዋናው የሐረጋቸው ስም አያውቁም የወለዳቸው ሶስት ልጆች ብቻ ይዘረዝራሉ። በዚህ መሠረት ከመንሳዕ በኩል የሚተርበው የዘር ሐረግ ከዘድ የነብዩ መሀመድ ጎሳ 1ኛ/ ሐሶታይ ሐሶ ያፈራል 2ኛ/ ቀርናይ ቀርና ያፈራል 3ኛ/ መንሳዓይ መንሳዕ ይወልዳል 4ኛ/ማርያያይ ማሪያ ይወልዳል።

በቀርና የሚቀርብ የዘር ሐረግ ግን ስሙን የሚያውቁት የሐረጋቸው አባት ሦስት ልጆች ወልዷል 1ኛ/ጋራብሶ ማሪያዓዩና ማሪያን የወለደ 2/ ሐሳይ ሐሶ የወለደ 3/ አማር ቀር ቀርዓና መንሳዕ የወለደ። የአፈ ታሪክ እንደሚለው መንሳዕና ማሪያ ከሌሎች ሁለት ወንድሞቻቸው ተለይተው አዲስ መሬት ለመፈለግ ወደ ሰሔን ተጉዘው ወደ ሃይጋት የመንሣዕ ተራራዎች አረፉ። ከዚያም ወደ ኤርታ አመሩ። የማሪያ ተራራዎች። ማሪያ በኤሮታ መቀመጫው ማድረግ ሲመርጥ ማንሣዕ ግን ወደ ሀይጋት ተራሮች በመመለሥ መቀመጫው (ሀገሩ) ማድረግ መረጠ። መንሣዕ የመሪ ወገን ሽማግሌ ሲሆኑ በስራቸው (ትግሬ) የሚባሉ ወደው እገሊጋይ የሚሆኑ ወይንም በግድ ወይም ተድዋ ባሪያ የነበሩ ከደጋ ወይም ከቤጃ የሚመጡ ያጠቃልላል።

የማሪያ ሹም ሬቲ የተባለው ከሁለት ሚስቶች በ1700 ዓ.ም ሁለት ልጆች አንድ ቀይ አንድ ጥቁር ይወልዳል። በዚሁ ምክንያት ማሪያ ቀይና ማርያ ጥቁር እየተባሉ ይጠራሉ። ወደ እሁኑ አገራቸው የመጡበት በ1500 ዓ.ም መሆኑ ይታመናል።



## 2. አልገደን ሰብደራት

ከሱደን ከሰላ የሚዋሰኑ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው። ደንበኛ አገሊያን ትግሬ መሆናቸውን የሚያረጋግጠው ምንም እንኳን በቁጥር አነሰተኛ ሲሆንም በሌላ ጉሳ ሲከበቡም የትግሬ ቋንቋቸውን እጥብቀው ይዘው ቆይተዋል፤

## 3. ሐለንጋ

የከሰላ እውራነጀ ወይንም ተካ ነዋሪዎች ናቸው። ከሰራየ የመጡ ናቸው ይባላል። ከደቂ ተስፋ ሰራዩ ወረዳ መርቆሬዮስ የሚባል ገዳም ተመዝግበ እንደሚገኘው ድሩይ ወይንም ዶሪ የተባለው ባሕር ነጋሽ የብሔር ሰገድ ልጅ የድባሩዋ ባሕር ነጋሽ አባ እልዋሪስ በ1520 ዓ.ም በስልጣን ላይ ያገኘው ወደ ኑባ ዘሐይ ወደ የምትጠፋበት ድረስ ዘመቻ ለማድረግ ሰላሰበ ወደ መረብ ወንዝ ወረደ። ከእሱ በኋላ ነጋች የተባለው ወንዝ ሄደ። ዘመቻው የተሳካ እልነበረም ምክንያቱም ከእነሱ ጥቂት ብቻ ወደ ሰራየ ተመለሱ መሪውም ሞተ፤ ተከታዮቹ ግን የሄዱበት አላማ ከግቡ ሳያደርሱ እንመለስም በማለት በመሪያቸው የወርቅ በትር «ሐለንጋ ወርቁ» ተሰየሙ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ነበሩ። ነገር ግን በቤጃ ስለተሸነፉ ምንም እንኳን ከሰራየ መምጣቸው ቢያስታውሱም ቤጃ መናገር ግድ ሆኖባቸው ነበር። ግሕዲሶች ብዙ ጉዳት አደረሱባቸው። ጣሊያኖች ከሰላን ለእንግሊዞች ሲሰጧት ሐለንጋ በቦታው ቀሩ። ብዙዎቹም አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረው የዓረብኛ ቋንቋ መናገር ጀመሩ። እራስ እሉላ ወደ ከሰላ ዘመቻ ባካሔደበት ጊዜ ሐለንጋ እንደ ነጻአውጪ ነበረ የተቀበሉት፣ ጣሊያኖች ከሰላን ሲይዙ ከወገኖቻቸው ጋር በመቀላቀላቸው ተደስተው ነበረ።

## 4. ሳሄል

የሳሔል የገንት ነዋሪዎች አስፋዳ አልማዳ ሐፉራ የሚባሉ ጉሳዎች ነበሩ። ከአክለጉዛይ ዕንዓደግሌ ዓዲ ንፉስ ይኖሩ የነበሩ ጎሳዎች በ1600 ዓ.ም አራት የእምነት ልጆች ጋይለስ፣ ጋዳት፣ አስገደ እና ሄሰል መገባባት የጎድልባቸው ስለነበረ አስገዴ ወደ ሳሔል በመሄድ አዲስ ሀገር ቀረቀረ። ስማቸው የተጠቀሱ የሳሄል ቀደምት ነዋሪዎች አስፋዳ፣ አልማዳ እና አፉራ በማግባባትና በኃይል ሌሎችም የግእዝ ዝርያም ሆነ የቤጃ በእሱ ስር እንዲሆኑ አደረጋቸው። ሐቢብ የአስገደ የልጅ ልጅ መፍለስና ተበሳ ማርያም ይወልዳል። ተበሳ ማሪያም ከወንድሙ ጋራ መኖር ሳላልፈለገ ከሮራ አስገደ በመውረድ ወደ ሰብካ ግዳ ይሰፋራል፤ ጎድ ተማሪያም ይመሠርታል። ከሁለት የመፍለስ ልጆች አንዱ ተክለስ እንደተማርያም ከሮራ አስገደና ዐንሰባ መሀከል ያለው ሀገር በገርገር ግዳ ሰፍር ከዓድ ተክለስ በስተ ምዕራብ ይመሠርታል። የመጀመሪያው ልጅ ኤብቴስ ከሮራ አስገደ በስተምስራቅ እስከ ቀይ ባሕር ይሰፍራል ሐባብ በመባል ይታወቃል። አፈ ታሪክ እንደሚለው አስገደ ወደ ሣሔል ሲመጣ አንድ ቄስ የነፍስ አባት ነበረው ጀቢብ ሩክ (ዘራብሩክ) የሚባል። ሌላ ተከታይም ነበረው። እንዲሁም ሐምዳይ የተባለ የሐሶ ተወላጅ አሽከር ነበረው። ቄሱ አልወለደም ጀቢብ ሩክ በዐንሰባ ተቀምጦ የቢትጁክ (በጁክ) ጉሳዎችን መሠረተ። እምዶይ ከጌታው ሳይለይ ብዙ ልጆች በመውለድ

ዓድ ሐምዶይ የተባሉ (ሐደምዶይ) አብረው ኖሩ። ቤት አስገደና ሐሸንዶይ ክርስቲያን ገበሬዎች ነበሩ በእነሱ ስር የነበሩ ትግሬዎች ግን እስላሞችና አረኞች ነበሩ።

## ዓድ ሼክ

የእስልምና ሃይማኖት ሰባክያን (ሲክ) ከነብዩ መሐመድ ዝምድና ያላቸው ናቸው። ከመካ የመጡ ሸሪፍ ሁሉን ተብለው እንደ ሹመት የሚጠሩ ነበሩ። ነገር ግን የሸሪፍ ሁሉን ሐቀኛ ተወላጆች ስለማይቀበሏቸው ሼክ ሁሉን ብቻ እየተባሉ (መምህር መሪ ሽማግሌ) እየተባሉ በግዜል የሚኖሩ ናቸው።

## ዓድ ፃውራ

ከሌሎች የግዜል ነዋሪዎች የሚለዩበት በእኩልነት በዲሞክራሲ የተመሰረተ በሀገር ሽማግሌዎች እየተመሩ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ነው። የአንድ ዘር ትግሬ በሀብትና በገድ ተማርኮም መገኘታቸው እውነተኛ ትግሬ ግእዝ ያሰኛቸው ነበር፤ ነገር ግን እነሱ ከሺግር መጥተው የተባለ ዓረብ እንወለዳለን ይላሉ። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው።

## ዓድ ሙዓሊም

ስማቸው የአስተማሪዎች ጉሳ ማለት ነው፤ ማለት የእስልምና የሃይማኖት የዓረብኛ ቋንቋ አስተማሪዎች። ይህ ጉሳም የመደብ ልዩነት ሳይኖረው በእኩልነት የሚተዳደር ነው። አነስተኛ ጉሳ ነው ከዓረብ መጣን ቢሉም የሚጠቀሙበት ቋንቋ ትግሬ ነው።

## ቤት ማላ

ከዓረብ ከነቢዩ መሐመድ እንወለዳለን የሚሉ ማላ የሚባለው አባታቸው የኤርትራና ሱዳን ጠረፍ ይኖር ነበር። ግማሽ በኤርትራ ግማሽ በሱዳን ይኖራሉ፤ ቋንቋቸው ቤጃ ነው፤ በቋንቋቸው መሠረት ቤጃ ናቸው እንጂ ዓረብ አይደሉም። በአሰፋፈራቸው ብቻ ከሳሖል ጉሳዎች ተመድበዋል።

## ራሻይዳ

በዘር በቋንቋ ባይገናኙም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዓረብ ሀገር የመጡ ማለት በ1870 ዓ.ም.፤ በአሰፋፈራቸው ብቻ በሳሖል የሚመደቡ ከስዋኪም እስከ አኪክ የሚኖሩ ግማሽ በሱዳን ግማሽ በኤርትራ ይኖራሉ የዓረብኛ ቋንቋቸውን ሳይረሱ በዘርም ከአካባቢ ሕዝብ ሳይደባለቁ ይኖራሉ። ድሮ የባሪያ ነጋዴዎች ነበሩ።

## 5. ሰምሐር

ከአርቂቆ እስከ ሰብታ የሚኖሩ የተለያዩ ዘር ሲሆኑ በቋንቋ ግን የመጀመሪያ ነዋሪ የትግሬ ቋንቋ በልጦ ይታያል።

ከአጠቃላይ ሕዝብ 65 ፐርሰንት ትግሬ 10 ፐርሰንት አረብኛ 5 ፐርሰንት አፋር 14 ፐርሰንት ሳሆ 2 ፐርሰንት ሌሎች ናቸው። የገጠር በሙሉ ትግሬ ሲሆን በከተሞች ሌሎች ይገኛሉ። ናይብ በአርቂቆ ሆነው በቱርክ ሹመት የተሰጣቸው ናቸው። የቤጃ ጉሳ ናቸው።



ከአዶሊስ መውደቅ በኋላ ወደብ የነበረች። አረቂቆ በትግሬ ዱኮና ትባላለች ምናልባት በጥንት ጊዜ የዝሆን ጥርስ ንግድ ይካሄድባት የነበረ ይሆናል። ቱርኮች 1557 ምፅዋን ሲይዙ ናይብ ግምሩክ እያስከፈሉ ሀብታም ነበሩ። ቱርኮች ሲመጡ ለደጋሬዎችና ተታራኒዎች ለሁለት ተከፈሉ። ተታራኒ ባሕር ነጋሽን የሚደግፍ ነበር። የቱርኮች ደጋፊ ወገን ናይብ አደረገቸው። ባሕር ነጋሽም በቱርኮች ላይ ዘመቻ ለማድረግ አቅም ስለሌለው አልሞከረም። ቱርኮች በናይብ በኩል የውስጥ ጉሳዎች ለመቆጣጠር ቻሉ። ሀባብ፤ ሰምሐር፤ አሳውርታ፤ አፋር፤ መንሣዕ፤ በጉስ፤ ማርያ፤ ቢኒ ዐመር። ክርስቲያን በሚኖርበትም ከእስላሞች የሚያገኙ ሰዎች እየላኩ «ጉልቲ» ማግኘት ችሏል። ግብሮች በቱርኮች ሲተኩ ከናይብ ሌላ ሲርዱር ሳርዳር በሚል ስም የወታደር አለቃ ሾመ። እነሱም ቤትሳርዳ ይባሉ ነበር። ከእነዚህ ወታደሮች ከፊል መደበኛ የሆኑ ሌሎች ያልሆኑ ከናይብ ሰራተኛ፤ ባሪያ፤ ደንገጡሮችና፤ ይዞ ዘመዶች፤ የተውጣጡ ሲመሰረቱ መሪዎቻቸው «ኬኪያ» ይባላሉ። ቤተሰቡም የኬክያ ይባላሉ። እነዚህ መደበኛ ያልሆኑ ወታደሮች አስከር ይባሉ ነበር። የእነሱ አለቆችም ጀሪቼ ይባሉ ነበረ። ስራቸውም በዘር የሚተላለፍ ስለሆነ ቤት አስከር ቤት ጀሪቼ ተባሉ። በዚህ ዓይነት ናይብ፡ ብለው ቤጃ ሕዝቡን በተሰየ የከተማ ሕዝብ ለመቆጣጠር ችሎ ነበር።

## የገጠር ነዋሪዎች

1. ዓድ ሀ ድብልቅ ዘር ቋንቋ ትግሬ ከዓይለት እስከ መንግዕ የሚኖሩ
2. ዓድ ሹማ ድብልቅ ዘር ቋንቋ ትግሬ
3. ዓድ አሸር ዋና መሬታቸው ዓሳውርታ ቢሆንም ድብልቅ ዘር ናቸው ቋንቋቸው ትግሬ
4. ናባራ ድብልቅ የሰምሀር ዘር ቋንቋቸው ትግሬ
5. እፍሌንዳ ድብልቅ ሐይንዳዋ ቤጃ ቋንቋ ትግሬ
6. ዋሪያ ሐደንደዋ ቤጃና ድብልቅ ቋንቋ ድብልቅ
7. መስጣሊት ድብልቅ ጉሳ ቋንቋ ትግሬ በዘር የሚከተሉት ጉሳዎች ይኖራሉ።
1. ዓድ ቺካኒ ከዒዳ አሳውርታ የመጡ
2. ቤት ሼክ ደርቡሽ ሱዳናውያን
3. ቤት ሼሬፍ ዓረቦች
4. ዓድ ሳርጓል፤ቤት ከኪያ፤ ዓድ ሻግራይ፤ ዓድ ሐመድ ፈጋች፤ ዓድ ሚደይ፤ ዓድ ሺሚቲ ዓድ አሳባላ፤ ዓድ ጀመል ሁሉም ቤጃ ናቸው።
5. ዓድ ሐሬክ፤ ዓድ ሼክ መሐመድ፤ ዓድ ጋለዳ የአዶሊስ
6. ዓድ ሼክ ሳዓይድ የመስሊላት
7. ዓድ ሶስንጌ፤ ዓድ ሳይሙ ዓድ የሚባ ዓረብ
8. ዓድ ሐንድ ዘለንድ
9. ዓድ ጨምብሉ ዓርምቴ አልዋናውያን

10. ዓድ ባሻናክ በዝናውያን

11. ዓድ ሳሉእ ዓድ ሸራፋይ ቱርከ፡ ሌሎችም እሉ ሁሉም በትግሬ ቋንቋ ይግባባሉ።

እቱምሎ ሞቱምሎ ሌሎችም ከተሞች ልክ እንደ አርቂቆ ናቸው።

## 6 በኒ ዐመር

ትግሬና ቤጃ ቋንቋ ተናጋሪዎች የጥንት ነገዳቸውን አያውቁም 16ኛው ክፍለ ዘመን አሚር በን ኩኑ ከተባለው የሳዓውዲ ዓረብ ተወላጅ በስዋኪም በኩል ገብቶ ወደ ባርካ መጥቶ ይገዛቸው በነበረ ይጠራሉ። ከዚህ በኋላ ከባርካ ወደ አርቂቆ መጥተው የአረቂቆ ቤጃን ናይብ ጎሳ በመዋለድ የመሠረቱ ናቸው። ቤኒ ዓመር ማለት የአሚር ልጅ ማለት ነው። በሰራዊ እገውጎሳ በመዋለድ የመሠረቱ ናቸው። ቤኒ ዓመር ማለት የአሚር ልጅ ማለት ነው። በሰራዊ እገው ጎሳ አትክሙ መልጋ ወረው ሥልጣን በመያዛቸው የቤጃ የበላይነት እንደ አከተመ ሁሉ በበኒ ዓሚርም ፋንግ ወረው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመያዛቸው አከተመ። የግብፅ እገዛዝ በ1840ዓ.ም ፋንግ በማባረር ቤጃዓሊን ከሱዳን የመጡ የመሪነት ስልጣን እንዲይዙ አደረጉ ናኘታን ይባላሉ። እነሱም የአባ ቢደ ጎሳ ናቸው። የናኘታን ዋና መሪ ዲግላል ይባላል። ሹመቱ ከፋንግ የተወረሰ ነው። ዲግላል መቀመጫው አቆርዳት አጠገብ ደጋ የተባለ ቦታ ነው። የሁለቱ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሳይጣሉ አብረው የሚኖሩ ከብዙ መቶ ዓመታት ምናልባትም በብዙ ሺህ የሚቆጠር ዓመት ነው። ሆኖም ትግሬ ተናጋሪ ንፁህ ትግሬ አይደሉም በተለይ ከአገልጋዮቹ ውስጥ ከሁሉም ቅልቅል ናቸው የቤጃም አሉባቸው። እንዲሁም የቤጃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቤጃ ብቻ አይደሉም ከሁሉ ቅልቅል ናቸው። በተለይ ከአገልጋዮች የትግሬ ዘርም አሉባቸው። የቤጃ ሕዝብ በሄደበት ቋንቋውን ረስቶ የሌላ ቋንቋ በመያዝ ነው የሚኖረው። ስለዚህ የቤጃ ቋንቋ በቤኒ ዓመር ባርካ በስተቀር በሌላ አካባቢ ጠፍቷል። የጥንት ግብፃውያንም ቋንቋቸውን በብርቅነት ማጥናት የሚፈልግ ሁሉ ዕድል ይሰጣል። የጥንት ግብፃውያንም ከቤጃ ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ። በኒዓመር በብዙ ንዑስ ክፍል (138) ይከፈላሉ። እነሱም እንደገና እስከ ቤተሰብ ድረስ ይከፋፈላሉ። የትግሬ ክፍል ዋና መሠረቱ ከሐማሴን ከመጡ የተገነባ ነው።

## 7. የደሴቶች ነዋሪዎች

የደሴቶች ጥንት ነዋሪዎች ግእዝ ትግሬ መሆናቸው የሚያስረዳ ምንም እንኳን በዓረቦች በየጊዜው ቢገዙም አሁንም የደሴቶች ነዋሪዎች ቋንቋ ትግሬ ነው። ከደሴቶች ነዋሪዎች ውስጥ 65 ከመቶ ትግሬ ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው። 20 ከመቶ ዓረቢኛ የሚናገሩ 14 ከመቶ አፋር የሚናገሩ ሌሎችም በጣም ጥቂት እንደ ሱዳኖች አሉ። ደሴቶቹ 122 ናቸው። ነገር ግን ሰው የሚኖርባቸው በጣም ጥቂት ናቸው።

## 4 የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪዎች፤

ሳሆ ወይንም ዓሳውርታ ቋንቋ የሚናገሩ በቋንቋ አንድነት እንጂ በዘር ግን የተለያዩ መሆናቸውን ከዚህ በላይ ገልጨዋለሁ።



1. የሳሆ ሀገር ቀደምት ነዋሪዎች ዶባ የተባሉ ከየጁ፡ ራያ፡ ወጀራትና ከአፋር መሐል ሰፍረው በሁለቱ ወገኖች ላይ ዘረፋ እያካሄዱ ይኖሩ የነበሩ ናቸው። አሁን ዘራቸው ጠፍቷል። ዶባ የዓሳውርታ ቋንቋና ዘር ዋና መሠረት መሆናቸውን ይገመታል።

2. ሌላ ቀደምት ነዋሪዎች ካቦታ የተባሉ ናቸው ከኤርቶ አፋሮች የሚዛመዱ ናቸው። በነዚህ ሁለቱ ጕሳዎችና በአጋዚያን የሳሆ ቋንቋ ተፈጠረ። አብዛኛው ግን ከአፋር ጋራ የተዛመደ ቋንቋ ነው።

3. ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ ከመንሳዕና ከማሪያ አንድ ጕሣ የሆኑ ቶርዓና ሐሶ የተባሉ ከዚህ በፊት ገልጫለሁ። ምክንያቱ በትክክል የማይታወቅበት ቶርዓና ሐሶ ሳሆ ቋንቋ ተናዎሪ ናቸው። እንደ ሚገመተው በጥንት ዘራቸው ግእዝ ነበር ከሰመሀር ጕሳዎች በጉርብትና ስለሚኖሩ ግን የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ሆኑ። ሆኖም በተጨማሪ የትግሬ ቋንቋም ይናገራሉ።

4. እምሰት አሣውርታ ጎሣዎች የሚባሉ ከእማር እሱር እንወለዳለን የሚሉ ናቸው። ከክርስቲያን የደጋ ሰዎች በአሰባበስም በመልክም የሚመሳሰሉ ናቸው። ከአፋሮች ኤርቶ ዝምድና አለን ይላሉ። እንዲያውም ስማቸው የመጣው ከእማር እሱን ሳይሆን ከአሳ ኤርቶ አሣያማራ አንድ ወገን መሆኑን ይገመታል።

5. ከእምስት አሳውርታ ተለይተው ብቻቸውን የሚኖሩ ኤንጋገ ሰናፈ የተባሉ ናቸው።

6. ኤዳ በአከለጉዛይ ከደቂ ገብሪ፡ ደቂ መኮን፡ እገለ ሐጼን የሚዛመዱ ናቸው።

7. ኢደፈር የኢዳ ልጆች ከኢዳ ፈልሰው ከብዙ ትግሬና ሳሆ ተናጋሪ ጎሳዎች ስለተቀላቀሉ ድብልቅ በመሆናቸው ቋንቋቸው ሳሆና ትግሬ ነው።

8. ባራዶታ እነዚህም የኢዳ ዘመዶች ይባላሉ። ከእና ዶቆ መንደር አከለጉዛይ ጋር ይዛመዳሉ ይባላል። ስለዚህ በሁለቱ አመጣጣቸው ከደጋ ክርስቲያን እንደሆኑ ያስረዳል።

9. አላባት እሬ ከጕንደር የመጡ በውትድርና ወይንም የሰው ነፍስ በማጥፋት ለመደበቅ የመጡ።

10. ሚኒፈሬ ፀጥታ ለማስከበር ከማእከላዊ መንግሥት የተላኩ ወታደሮች በሰንዐፌ አካባቢ ሀገርን የቆረቆሩ ናቸው።

11. ደብሪ መላ በማርያም ደብር የታሰበሰቡ ክርስቲያን እና እስላሞች ናቸው ከደጋ ከተለያዩ የክርስቲን መንደሮች የመጡ ቢሆንም የሚናገሩት ቋንቋ ግን ሳሆ ነው።

12. አፋር ዝርያ ያላቸው ቋንቋቸውን ትተው ሳሆ የሚናገሩ ራዛማሬ የሚባሉ

13. ሽለሱዋ የሚባሉ የአፋር ዝርያ ያላቸው ቋንቋቸውን ትተው ሳሆ የሚናገሩ

14. እንቲለ ሼክ እሬ ከእውሳ ወደ ማሆ የመጣ የሃይማኖት ሰባኪ ሁለት ወንድሞቹ በአፋር ይኖራሉ አፋርኛ ይናገራሉ የሼክ እሬ ዘሮች ግን ሳሆ ቋንቋ ብቻ ይናገራሉ።

15. ቤት ካሊፋ ከአዱም ባኮ ከነብዩ መሐመድ የተላኩ ሰባት መልዕክተኞች አንድ

ነን የሚሉ ናቸው በውስጣቸውም ሱዳናውያን አፋሮች ደሳም አሳውርታ ጉሳዎች ያቀፉ ናቸው። ዋና ነዋሪነታቸው አዱሊስ ነው ቋንቋቸው ሳሆ ነው።

16. ቤት ሼክ መሐመድ ዘራቸው በሰምሀር በሙሉ የተሰራጩ ናቸው። ዋና ነዋሪነታቸው አዱሊስ ነው ቋንቋቸው ሳሆ ነው።

17. ቤት ቃዲ ነዋሪነታቸው አዱሊስ ድሆና ለአምስት አሳውርታ ጎሳዎች ዳኞች ለመስጠት መብት ያላቸው።

16. ቤት ሼክ ማሕሙድ በሰምሀር ጉጣዎች ተሰራጭተው የሚኖሩ

19. ቤት ሰዋካል ከብዙ ዘር ትልትል ናቸው ነዋሪነታቸው አፍታ ነው

20. አብደላ ሳናአ ሰንንዓሬ የሚኖሩ ከሰነዓ መጣን የሚሉ ከእነሱ ዓዲ ጉልቲ እና ደባር አከለጉዛይ ይኖራሉ።

21. ኢርብ ወዓጋሜ አውራጃ የሚኖሩ ናቸው።

በአጠቃላይ አሳውርታ ተናጋሪ ሕዝቦች 42 ከመቶ ከደጋ ክርስቲያን አውራጃዎች የፈለሱ ወይንም የኢትዮጵያ ወታደር የነበሩት በ6–7–8–9–10–11 ተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ናቸው 29 ከመቶ የአምስት አሳውርታ ጉሳዎች በአራተኛና አምስተኛ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት ናቸው 10 ከመቶ በ3 ተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ናቸው የቀሩት ሌሎች ጉሳዎች ናቸው።

# 5 የአፋር ቋንቋ ተናጋሪዎች

እንደ ሀገራችን ምሁራን አቀራረብ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ አፋር፣ አጋዱን፣ ሴሚውያን ከመካከለኛ ምስራቅ የመጡ ናቸው። አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ[1] የሀገራችን የተለመደ አፃፃፍ ብሎ እንደፃፈው ዮቅጣን የሴም ልጅ ልጅ 13 ልጆች ይወልዳል። ከእነዚሁ 6ቱ ሳባ አባል፣ አፋር፣ አቢማር፣ ማሺሳ ከወንድሞቻቸው ተለይተው ከመካከለኛ ምስራቅን ሀገር ትተው ወደ የመን መጥተው ተቀመጡ። በየመን ባሉ የሕንድ ነገሥታት እየወጉ ሲያስቸግሯቸው በ1808 ከክርስቶስ ልደት በፊት የመንን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ተሻገረው መጡና ሦስቱ ነገዶች ሳባ በትግሬ አባል በአፋር አፋር በወጋዴን ተቀመጡ። እንደመጡም መጀመሪያውኑ 6 ዓመት ለካም ነገድ ንጉሠ የራእአሬ ገብረዋል። በዚህ መካከል የሕንድ ንጉሥ ራማ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ራእአሬን ወግቶ አሸንፎ መንግስትን ቀማው፣ ሕዝቡንም እንደ ባሪያ ይገዛው ጀመረ። ከዚያ ጊዜ እነዚህ ሦስቱ የዮቅታን ልጆች ነገደ ዮቅጣን ከያሉበት ተሰባስበው ራማን ወግተው ሠራዊቱን አሸንፈው እሱንም ገደሉና ሕዝቡንም ከባርነት ነፃ አወጡት። ከዚያም እነዚህ ነገደ ዮቅጣን ነገደ አግአዚያን (ነፃአውጪዎች) የሚል ስም ወጣላቸው ይባላል። ይሁን እንጂ የመንግሥቱን መሪነት ወደ ነገደ ካም ሳይመለስ ነገደ ዮቅታን ተዋግተው ያደኑትን ሀገር ለራሳቸው ያዙት ማለት ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነገደ ዮቅጣን በነገደ ካም ተተክተው ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል።

1. ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኖብያ፣ መሮዌ ዛጉዌ



ይህ አባባል ለሴምና ለካም ነገዶች የሚከፈሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያናጋ ይሆናል። ስለ አፋር መፅሐፍ የጻፈው ኢጣሊያዊ[1] ፀሐፊ ከኢትዮጵያውያን ምሁራን የተገኘ መሠረት ብሎ ዋቢ ቢጠቅስም ከላይ ከአቶ ተክለ ፃዲቅ የተገለጸው በመቀያየር የአፋር ቅድመ አያት አፋር የዮቅታን ልጅ መሆኑን በመውሰድ አፋር የሚል ስም የመጣ ከአፋር ነው ይላል።

አፋሮች ለአዶ ኢያማራ ነጭ ሰዎችና ለአሣ ኢያማራ ቀይ ሰዎች ይከፋፈላሉ አፋሮች ከአዶ ኢያማራ የሚወለዱ የሚከተሉት ናቸው። 1. ሄዳና በብዙ ቦታ ተበታትነው የሚኖሩ ከሐድራ መት የመጡ። 2. በለሱዋ ከየመን ጋይራና ቅድመ አያታቸው በይሉል ላይ ከወረደ በኋላ ሉዋን

በተባለው ቦታ ከአድ በስተደቡብ ምዕራብ ስለሰፈሩ በለሱዋ የሱዋ ክልል ተባሉ 3. ዱና ቅድመ አያታቸው ኢብራሂም ከሆዳይደ የመጣ ከተወለዱ 4. አንካላ ከዓረብ የመጡ ተበታትነው በዓሰብ በይሉል ደሴት የሚኖሩ በተለየ ግን በቡሬ

አካባቢ የሚኖሩ 5. ሐዋኪል በሐዋኪል ደሴት የሚኖሩ 6. ገዲምተ የአዶ ኢያማሬ አንድ ክፍል አፍረራ ሐይቅ፣ ዳታ ዓሊ ተራራዎችና አሊ ዳብ

ሜዳ ይኖራሉ። 7. ዶዳ የአዶ ኢያማራ አንድ ክፍል፣ በሚሌ አካባቢና በወደቦች ይኖራሉ። 8. በርሐቶ ሁሉም በራሶሊ የሚኖሩ 9. ሃይማሜሌ በማር ጉባላ ከሀሰብ ደቡብ የሚኖሩ 10።ፕስይታ የበለሱዋ አንድ ክፍል 11 ሸይከሐ የሐይማኖት መሪዎች ከእነሱ አንድ ክፍል በዓሳውርታ የሚኖሩም አሉ የነብዩ መሐመድ ቤተሰብ ናቸው።

የአፋር ሕዝብ ሲነሳ ብዙ ሰው ትዝ የሚለው ዓሰብን የሸጡ የአፋር ሱልጣኖች ነው። ነገር ግን ጥቂት ግለሰቦች የአፋር ሕዝብ ሊወክሉ አይችሉም። የአፋር ሕዝብ ፀረ ኢጣሊያ ቀኝ አገዛዝ ትግል አካሄዷል። በ1875 ዓ.ም በሙዚንገር የሚመሩ ሱዳንያዊያን ያደረሰው ጥፍጩፋ ይታወሳል። ጣሊያኖች አሰብ ከያዙ በኋላ ወደቡ ከኢትዮጵያ መሐል ሀገር ግንኙነት ካልፈጠረ ጥቅም ሊሰጣቸው እንደማይችል ስለተረዱ መንገዱ መቀየስ ጀመሩ። የአሰብ ቀኝ ግዛታቸው ዋና ፀሐፊ የነበረው ጁሴፔ ማርያ ጁሴቲ ይሄን ተግባር ለማከናወን ትዕዛዝ ይሰጠዋል። በሙቶ አለታ ቢሊዮሬ ባሕርተኞች ወታደሮች በመታጀብ ከቤይሉል ወደ ጉዋሌማ ሜዳ አፕሪል 1881 ጉዞውን ይጀምራል። ሜይ 25 ቀን ሌሊት የቢሩ ሱልጣን ታማቂዎች ሳይታቁ ይከታተሉት ስነበሩ ጣሊያኖች በሙሉ ተጨፈጨፉ። በጠቅላላ 17 ጣሊያኖች ነበሩ። የአውሳ ሱልጣን ለንጉሥ ምኒልክ «አውሮጳውያን ግዛቴን ያለፉበት ጊዜ የለም እኔም ምንግዜም አልፈቅድም» ብሎ ነበር። ቃሉን አከበረ

እልቂቱም በእሱ ትብብር እንደተፈጸመ አያማራጥርም። ዘብ ቆሞ የነበረ ብቻ ለመከላከል ሞክሮ ከአፋሮች ውስጥ አንድ ሊገደል ሌሎች ጣሊያኖች በእንቅልፍ እንዳሉ ጥቂቶቹን አፋሮች ብቻ በማቁሰል በሙሉ ነበር የተገደሉት።

1. Franchetti ; Nella Dancalia Etiopica

ሌሎች ጣልያኖች በበቢያንኪ የሚመሩ ሁለት ሌሎች ጓደኖና መናሬ ታዋቂ የነበሩበት በመጀመሪያ ወደ አጼ ዮሐንስ ከሔዱ በኋላ ከትግራይ አፋርን አቋርጠው ወደ ተይ ባሕር እንዲዘልቁ በአጼ ዮሐንስ ፈቃድ እንዲሰጣቸው አግኝረው የመረጡት መንገዱ አደገኛ መሆኑን ቢነገራቸውም ጉዞቸው ቀጥለው እነሱም እንደ ተድዋዎቹ ጣሊያኖች ወደ ጉዋሊማ ጅረት አመርተው በብሩ ሱልጣን ግዛት ኦክቶበር 7 በ1880 በአፋሮች ተጨፈጨፉ። አፋሮች መዋታቸው ያውቁ ነበር። ነገር ግን ማንም ጣሊያኖቹ እንደተገደሉ የሚናገር አልነበረም። ሁለት ወር ቆይተው የኢጣሊያኖች መሪ የነበረ አፋር በመቀሌ ታስሮ ሲጠየቅ ብቻ እንደሞቱ ታወቀ።

በ1908 ዓ.ም ስለ አፋር ወሰን ክልል ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ያደረጉት ስምምነት ከተደረጉት ሦስት ተከታታይ ስምምነቶች አንዱ ነው። የመጀመሪያ ኦክቶበር 26 ቀን 1896 ከዓድዋ ጦርነት በኋላ የአዲስ አበባ የሰላም ውል በሚል ስያሜ የተደረገው ውል ስለ ወሰን ጉዳይ ከአንድ አመት በኋላ በሁለቱ ወገኖች በስምምነት እንዲወሰን የሚል ነበር። የወሰኑ ጉዳይ ግን በስምምነት በፊርማ የፀደቀው ከ4 ዓመት በኋላ ጁላይ 10/1900 ዓ.ም. ነበረ። በስምምነቱ መሠረት ቶማት ቶድሉክ መረብ በለሳ ሙና መስመር የኤርትራና የኢትዮጵያ ወሰን ይሆናል። ከአጼ ሚኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለኢጣሊያ የተሰጠው መሬት የኢጣሊያ መንግሥት ለማንም እንዳይሸጥ ወይንም አሳልፎ እንዳይሰጥ ይደነግጋል። 3ኛውና የመጨረሻው ሜይ 16 1908 በኢጣሊያና በኢትዮጵያ የተደረገው ስምምነት የሚመለከት ነው። ጣሊያኖች በጥቂት የቀይ ባሕር ወደቦች ተወስነው የነበሩ ይዞታቸው ከቀይ ባሕር ወደ ውስጥ 60 ኪሎ ሜትር በማስፋፋት ከአሳውርታ እስከ ፈረንሳይ ጅቡቲ ግዛት ፓራለል መስመር እንዲሆን ወስኗል።

ጃንዋሪ 1929 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ ቀናት 5000 ዘራፊዎች በኢጣሊያ ዳንካሊያ ገብቷል የሚል ወሬ አስመራ ስለደረሰ የኤርትራ መንግሥት ዘራፊዎችን ለመቋቋምና ወሰኑን ለመጠበቅ በሚል ሰበብ ወታደሮች ወደ ቦታው ለመላክ ይወስናል። ለአካለጉዛይ አውራጃም ጥበቃውን እንዲያጠናክር የፖታሽማእድን ወደ እለበት ወደ ዳሎል በአስፈላጊው ጊዜ ለመሄድ ተጠባብቆ እንዲቀመጥ ትዕዛዝ ተነገረው። ብዙ ጊዜ የኢትዮጵያ አፋሮች ዘረፋ እየፈጉ ወደ ኢጣሊያ ደንከል ስለሚገቡ ለአክለጉዛይ አውራጃ መደበኛ ያልሆኑ ታጣቂዎች እንዲመለምል ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። በተቻለ መጠን ሁሉም የውሀ ቦታዎች ሁሉም የመገናኛ ግዴታ መንገዶች እንዲይዙ ትእዛዝ ተሰጠቶታል። ይህ እንቀስቃሴ የተከናወነው የኢትዮጵያ እነስተኛ ሰሞታ የአነስተኛ የወረዳ ገዥ በቀር ያለ ምንም ችግር ነበር። በመጨረሻም ያስከተለው (ያመጣዋ) ውጤት የወሰን ማስተካከያ በሚል ስም ጣሊያኖች የሚፈልጉት መሬት ለመውሰድ ነበረ ኮራዶ ዞሊ ካርታ ቁ 2 ሁኔታውን ይገልጻል።



# ባርያና ኩናማ ቋንቋ ተናጋሪ
## 6ኛ የኩናማ ወደ ኤርትራ መቀላቀል

ስለኩናማ ከኤርትራ ጋራ መቀላቀል ወደ ውሣኔ የተደረሰበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ትክሻና ኪሣራ በእንግሊዝና በኢጣሊያ የተቀነባበረ ደባ መሆኑ በወቅቱ የተደረጉ ውሎችና ስምምነቶች በማገለባበጥ ግልጽ ሊሆንልን ይችላል። ተጨማሪ ማስታወሻ ተብሎ የቀረበና በእንግሊዝና በኢጣሊያ በኢትዮጵያ መሐከል ሜይ 15/1902[1] አዲስ አበባ ላይ የተደረገው ስምምነት የሚከተለው ነበረ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታት ዳግማዊ ምኒልክ፣ ሻለቃ ቺኮዲኮላ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ አምባሣደርና ሌቴናል ኮሎኔል ሐሪንግቶን የእንግሊዝ መንግሥት አመባሣደር በሚከተለው የጋራ ስምምነት የደረሱበት የሚከተለው ነው።

1ኛ/ በኢትዮጵያ በኤርትራ መሐል የወሰን ውል ቶማት ቶድሉክ መሥመር የነበረው በጋራ ስምምነት እንደሚከተለው ይስተካከላል። የኮር ኤም–ሀገር ከሴቲት ጋራ ከሚገናኝበት ጀምሮ አዲሱ ወሰን ይህንኑ ወንዝ ተከትሎ ከማአተብ የሚገናኝበት ይደርሣል። ወንዙን ተከትሎ ሄዶ አላ ታኩራ የሚባለው ተራራ ወደ ኤርትራ ትቶ ማይ አንበሣ፡ መረብ በሚገናኝበት ይደርሣል። የኩናማ ጉሣ ከኤርትራ ጋራ እንዲቀላቀል ማይ ማአተብ ከሴቲት ጋራ እና ማይ አንበሣ ከመረብ ጋራ የሚያገናኝ መሥመር የኢትዮጵያና የኢጣሊያ መልእክተኞች በሥፍራው ተገኝተው ይወስኑታል።

2ኛ/ ከሱዳንና ከኤርትራ ያለው ወሰን ኤፕሪል 16/1901 በእንግሊዝና በኢጣሊያ መልእክተኞች የከለሉት መሆኑ ቀርቶ ከሰበደራት በአቡ–ጋመለ ኮር ኡመ ሐጋር ከሴቲት ጋራ የሚገናኙበት ያለው መሥመር ይሆናል። ወደ ስምምነት ለመድረስ የተቻለው በአንድ በኩል የእንግሊዝ መንግሥት የአትባራ ወንዝ ውሃ ለራሱ ብዎ እንዲሆን ፍላጉት ስለነበረው የኢጣሊያ መንግሥትም የከሰላ መሬቶች በማጣቱ ከአትባራ ወንዝ ጋሪ አዋሣኝ መሆን ጥቅም ስለማይሰጠው ኤርትራ ቀኝ ግዛቱ ግን ከጉንደር ኩታ ገጠም መሬት እንድትገናኝ ፍላጐት ስለነበረው የእንግሊዝ መንግሥት በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር በእንግሊዝና ግብፅ ሱዳንና በኢትዮጵያ ያለው ወሰን በውይይት ላይ ስለነበሩ በዚሁ መሠረት ኮሎኔለ ሐሪንግቶን የሱዳን ወሰን ከአትባራ ወንዝ እንዲሆን በስተምሥራቅ እንዲዘልቅ ከዳግማዊ ምኒልክ አወንታዊ መልስ አግኝቶ ስለነበረ ከላይ በተጠቀሰው ቀደም ሲል በሮማ ኖቬምበር 22/1901 እንግሊዝና ኢጣሊያ ተፈራርመው ነበረ። ከላይ የጠጣው ውልም የእዚሁ ቅጥያ እንደሆነ እንረዳለን። የውሉም ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነው።

በእንግሊዝና ግብፅ ሱዳን ግዛት ያለው ወሰን ለማጓጓላት ከአቡ ጋመል ተነስቶ (የታልቦት ኮሊ ካርታ ተመልከት) በልዩ መልእክተኞቻቸው የመሬቱ ውጣ ውረድ መሠረት

1. Carlo Rossetti Ibd. 257,258,259

በግድረግ ምልክት የግድረግ ኮር ሰም ሀገር ከሰቲት የሚያገናኘው ወደ ደቡብ አንድ መሥመር እንዲሄድ ተስማምቷል።

በዚህ መሥመር ወደ ምሥራቅ ያለው መሬት ንጉሡ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ የሱዳን መሬት መሆኑን ስላመኑበት በእግቸው ፈቃድ ወደ ኤርትራ ተቀላቅሉዋል። ከዚህ መሥመር በስተምዕራብ ፖራለል ከቀጣት መሥመር ቀጰሉክ በስተሰሜን ያሉት መሬቶች ኢጣሊያ ለሱዳን ትሰጣለች። በዚሁ ስምምነት መሠረት ከሰቲት ወደ መተማ የሚወስደው የወሰን መሥመር ናጋራና ከጐንደር ወደ ኤርትራ የሚወስደው የንግድ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀል ወደ ምዕራብ ይገፋል። በኢትዮጵያ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ነገረፈጆች ከማእተብ ቀድሉክ መሥመር ወደ ምሥራቅ ያለው መሬት ለኢትዮጵያ በመስጠት የኢትዮጵያ ወሰን ስለሰፋ በምትኩ ወደ ኤርትራ የኩናማ ጐሣ መሬት እንዲቀላቀል እስከ መረብ የሚያደርስ መሬት አጼ ምኒልክ እንዲለቅድ ለግድረግ ጥረት ግድረግ ይናርባቸዋል። ለዚሁም ውይይቶች ከአንድ የተወሰነ ጊዜ በኋላ አልባት የማያገኙ ከሆነ የኢጣሊያና የእንግሊዝ መልእክተኞች የሱዳንና የኢትዮጵያ ወሰን በሚመለከት ቀድሉክ እምበሬጋ ወይንም ማእተብ ገበን፣ አባር መሥመር መሠረት በግድረግ በርም ውይይት ይቀጥላሉ (ታልቦት ኮሊ ማፕ ተመለከት) በሱዳንና በኤርትራ በሚመለከት ከቀድሉክ ቀጣት በስተሰሜን ያለው መሬት ለውጥ ሣይደረግ እንዳለው የቆያል። ለዚሁ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ስምምነት የንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድ እስከሚታወቅ ድረስ ሚስጢር ሆኖ ይቆያል።

ፊርማ

ማርቲኒ ኬኔልረድ

አኘዚያ ኀይችን

ቺኮቴላ ሐሪንግቶን

ቦድረር

ይህ በኢጣሊያና በእንግሊዝ መካከል የተደረገው ስምምነት ዐጼ ምኒልክ ከተፈጸመ ሥውር ደባ መሆኑን ከሚያሣዩ ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ/ ስምምነታቸው ለጊዜው በሚስጢር እንዲያዘ ማለታቸው ተንኮል እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።

2ኛ/ በአንድ ፓራግራፍ የኢጣሊያና የእንግሊዝ መልእክተኞች ኩናማ ጐሣ ከኤርትራ ጋራ እንዲቀላቀሉ አጼ ምኒልክን ለማግባባት መጣር አለባቸው ይላል።

3ኛ/ በሌላ ፓራግራፍ ደግሞ ኩናማ ጐሣ ያሉበት መሬት የሱዳን መሬት መሆኑን አጼ ምኒልክ አምነውበታል ይላል።

4ኛ/ በሌላ ወገን ደግሞ የኢጣሊያ ፓርላማ ግንቦት 26/1903 ባደረገው ስብሰባ ከፖርላማው አንድ አባል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስለዚህ ስምምነት ጉዳይ ላቀረበው ጥያቄ



ሚኒስትሩ ሲመልስ እንዲህ ብሎ ሐሳቡን አብራርቷል። ብዙ ለእንግሊዝ ብዙ ለመን ከእንግሊዝ ግን ምንም አላገኘንም የሚለው አነጋገር ትክክል አይደለም ወደ ኤርትራ የተጠቃለለው ግምበ መሬት ከእንግሊዝ የተሰጠ ነው። የቅኝ ግዛታችን ለሌ ያደረገው መሬት የኩናማ ወረዳ እና የአካባቢው መሬት ከኢትዮጵያ ያገኘው ነው። ከእንግሊዝ ጋራ ሆነን በመተባበራችን ነው። ከላይ የተደረጉ ስምምነቶች የሚያስረዱ ኩናማ ጐሣ የሚኖሩበት መሬት የኢትዮጵያ መሬት እንጂ የሱዳን አለመሆኑም። እንግሊዞችና ጣሊያኖች ኩናማ የሚኖሩበት መሬት የኢትዮጵያ መሆኑን ሳያውቁ ቀርተው አይደለም አጼ ምኒልክ የሱዳን መሆኑን አምነውበታል ብለው ስበብ የፈጠሩት ነው።

ባሬያና ኩናማ በቋንቋ ቢለያዩም በባሕል ተመሳሳይ ናቸው። የሚለያያቸው የታወቀ ወሰን የላቸውም፤ በወሰናቸው የሁለቱ ቅልቅል የሆኑ ዝርያዎች ይታያሉ። ከጥንት ጀምሮ በጉርብትና ተስማምተው በመካከላቸው የጎላ የቋንቋ ልዩነት ሳይፈጠር ይኖራሉ። ከሌሎች ጐረቤት ጎሳዎች ግን የወሰን ግጭት በየጊዜው ይፈጥራሉ። ድሮ ባሬያ አሁን ቢለን የሚሉበት መሬት ይኖሩ ነበሩ። አዲሶች መጤዎች ሲመጡባቸው ግን በታወነ ለተወ የቢሌኖች የበሎች (ትግሬ) ከመሆን በፍላጎታቸው አሁን ወደ አሉበት ሲመጡ በመሉ አለመጠም ግንቦች ቢሌን በሚኖርበት የቀሩ «ሰብ መድሬ» ተብለው ይጠራሉ ማለት የጥንት ባለ መሬቶች። በባሬያ መሬት መጥቶ ለመኖር የሚፈልግ ሁሉ ከለከል የለውም። በዚህ ምክንያት በመሐከላቸው ከትግሬ፣ ከበለው፣ ከቢኒአመር፣ ከጎንደር፣ ከቢሌን፣ ከማርያ፣ ወዘተ የመጡ ጎሣዎች አሉ። በኩናማ ግን ከወሰናቸው አካባቢ ከአሁን በቀር የዘር ቅልቅል አይታይባቸውም።

የኩናማ መሬት በ1902 ዓ.ም በሕገወይ መንገድ እንዴት ከኤርትራ ጋር እንደተቀላቀለ እላይ እንደተገለጠው ሲሆን ጣልያኖች ግን በዚህ አላበቁም።[1] ኮሬዶ ዞሊ በ1929 ዓ.ም የኤርትራ ሀገረ ገዥ የነበረው በደረሰው መፅሐፍ እንደገለፀው ጣልያኖች ተጨማሪ መሬት በዚህ ዓመት ምህረት ወሰን ማስተካከያ በሚል ሰበብ ከኩናማ አውራጃ መውሰዳቸውን እንደሚከተው ያብራራል። ኢፕሪል 6/1929 ዓ.ም ከሌሊ አባ የተነሱት ታጣቂዎች ከጋሽና ሰቲት የኤርትራ ግዛት ሰሜናዊ ክፍል ዘለቀው በመግባት ዘረፋ በማካሄዳቸው የኢሬነይ የኤርትራ ታጣቂዎች ተከታትለው ለማጥቃት በኢትዮጵያ መሬት ውስጥ በመግባት አባረዋቸዋል። የኤርትራ መንግሥት ሐሳቦች ከጋሽና ሰቲት ከጎብሳማይ ፎቹ ወደ ምዕራብ ያለው መሬት የራሳቸው እንደሆነ ብለው ይወስዱት እንደነበረ ተረድቶ ነበር። ይህ የማይመስል የስሁተት አስተሳሰብ ዝቅተኛና ከፍተኛ ጥቃበሁ ያሉት የኢትዮጵያ መሬቶች የተቀበሉት ነበረ።

---

1. Corrado Zoli Ibd. p. 275,276,277

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በስንቅና ትጥቅ አቅርቦት ችግር ምክንያት የኤርትራ ፀጥታ አስከባሪዎች ከቦታው ለቀው ነበር።

የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ባለስልጣኖች ከተባለው ቦታ ስልጣናቸውን የማያሳዩበት ስለነበር የሽፍቶች መሰብሰቢያ ሆኖ ነበር።በዚህ ቦታ ቤት ሰርቶ ይቀመጥ የነበረው ጋሎ የተባለው አንድ ሽማግሌ ኩናማ ኤርትራዊ በፈጸመው ወንጀል በኤርትራ መንግሥት በሕግ የሚጠየቅ ነበር። በአንድ የትግራይ ባለስልጣን እውቅና ተሰጥቶት የፈትውራሪ ሹመትም አግኝቶ ነበር። ይኸውም የሆነበት መሬቱ በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ መሆኑን ለማስረዳት ግብርም ለመሰብሰብ ነበር።

በዚሁ የተነሳ የአስመራ መንግሥት መሬቱ በቋሚነት እንዲይዝና ወሰኑ በፀጥታ አስከባሪዎች እንዲከበር በማድረግ ለባርካ ጋሽና ሰቲት አውራጃ ሀገረ ገዥ ትዕዛዝ ያስተላልፋል። በዚሁ አርምጃ ተደናግጦ ጋሎ የኢጣሊያ ግዛት እቀበላለሁ ብሎ ይቅርታ ጠይቆ እጁን ይሰጣል ጀንዋሪ 1929። በኤርትራ መንግሥት ተቀባይነት ያገኛል። ይህ ግን በአዲስ አበባ የሺሬ የኢትዮጵያ ባለ ስልጣኖች ሊዋጥላቸው አልቻለም። የኢጣሊያ ቅሚያ እያሉ በሰላም አልተቀመጡም። የኤርትራ መንግሥትም ይዞታውን እያጠናከረ በአዲስ አበባ ለኢጣሊያ ኢምባሲ አስታውቆ ነበረ። የኤርትራ መንግሥት በወሰደው እርምጃ ራሱ የምዕራብ ትግራይ አገረገዥ ራስ ስዩም መንገሻ ተቃዋሚን ያሰማል። ተቃውሞው ግን ከአንገት በላይ እንደሆነ የሚያስረዳ በ1930 ዓ.ም. አፕሪል ወር በአስመራ ባለፈበት ጊዜ በቤተ መንግሥት የቁርስ ግብዣ በተደረገለት ጊዜ ጣሊያኖች እርምጃውን መውሰዳቸው ትክክል ነው ብሎ ነበር። ሆኖም ትንሽ ጊዜ ቆይተው በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ራሱ ንጉሡም የትግራይ አውራጃና ወረዳ መሪዎች ያሰሙት ተቃውሞ ሲደገፉ ይታዩ ነበር። በዲፕሎማቲክ መንገድም ተቃውሟቸውን ቀጥለው ነበር። ነገር ግን የአስመራ ባለስልጣኖችና የኢጣሊያ መንግሥቶች ባሳዩት ጠንካራ አቋም ነገሩ ተረስቶ ቀርቷል። (ካርታ 2) ተመልከት

# ዘርና ቋንቋ የአንድ ሀገር መለኪያዎች

ኢትዮጵያውያን በቋንቋ በኩልም እንደ ነገዳችን አንድ ግንድ ቋንቋ ነው ያለን። ይኸውም የኩሽ ግንድ ቋንቋ ነው። የሴም ቋንቋ ተናጋሪ የሚባሉ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ ክፍል በዘር ሳይሆን አንዳንድ የሴም ቃላት በመውሰዳቸው ወይንም ስላላቸው የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ሊባሉ አይገባም። የዘራችንም ሆነ የቋንቋችን አከፋፈል ያደረጉልን ኤውሮጳውያን ናቸው። ኤውሮጳውያንም ስህተት ሊፈጽሙ ይችላሉ። ከስህተታቸው እንዲታረሙ ማድረግ የእኛ ኃላፊነት ነው። እንግሊዞች ብዙ የላቲን ቃላቶች ወርሰዋል። ግን ላቲኖች አይባሉም። ጣሊያኖች፤ ፈረንሣዮች፤ ስፓኒሾችና ፖርቱጋሎች ከእንግሊዝ ተመጣጣኝ ትንሽ የሚበልጥ የላቲን ቋንቋ ቃላቶች ስለወሰዱ ላቲኖች ተብለው ይጠራሉ፤ ላቲኖች ግን አይደሉም። አጠራራቸው የመጣ በቋንቋ ነው እንጂ በዘር አይደለም። የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ተብለው የሚጠሩ ኢትዮጵያውያን ትክክለኛ አጠራርና አመዳደብ አይደለም። እንደ እንግሊዞች መሆን አለብን። እኛ ካለን የሴም ቃላቶች እንግሊዞች ያላቸው የላቲን ቃላት ይበልጣሉ። የኢትዮጵያውያን ቋንቋ ግንዱ መሠረቱ የኩሽ ቢሆንም፤ በመሐከላቸው ብዙ ልዩነቶች አሉ። በእኛ ፍላጐትና ስሜት ሳይሆን በኤውሮጳውያን አላግባብ አመዳደብና አከፋፈል ሴማውያን ተብለው የሚጠሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በጥንታዊው ኩሻዊ ስማችን አግአዝያን ተብለው መጠራት አለባቸው። አንዳንድ የሴም ቃላትም እንደወለድን ወይንም እንዳለን አይካድም።

ነገር ግን ይህ ቋንቋችን የሴም ቋንቋ ነው ለማለት አያሰኝም፤ ቃላቶች ቢኖረንም ከሌላ የወረስነው ሳይሆን የራሳችን የአግአዝያን አባቶቻችን ነው። ቋንቋችን ግንዱ የኩሽ ቋንቋ መሆኑ መዘንጋት የለብንም። የግእዝ ቋንቋ ሴማውያን ተብለው የሚጠሩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አባት ነው። ሕዝቡም አግአዝያን ይባላል። አግአዝያን ዐረቦች አይደሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ መፍለቂያቸው ጣቢያቸውና ሀገራቸው አከለጉዛይ[1] ነበረ ነው የሚባለው። ጥንታዊው አግአዝያን ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ በአከለጉዛይ ተጀምሮ ከዳበረ በኋላ ነው ማእከሉ ወደ አክሱም ተዛውሮ ሊቀጥል የቻለው። አክሱም ዋናው ትግራይ፤ የትግራይ እናት ወይንም የኢትዮጵያ እናት ተብላ ስትጠራ አከለጉዛይ ደግሞ ጥንታዊቷ ትግራይ[2] የትግራይና የኢትዮጵያ እናት ትባላለች። ወደ ባሕር ጠረፍ ቅርብ ስለሆነ ፊደሉችም ሥልጣኔም ወስደው ከሌሎች የኢትዮጵያ የኩሽ ቋንቋዎች ግእዝ ቋንቋ የበላይነት ተቀዳጅቶ የሥነ ጽሁፍና የቤተ መንግሥት ቋንቋ እንዲሆን አድርገውታል። ስለዚህ እኛ ጥንታዊው ስማችን አግአዝያን ትተን ሴማውያን ተብለን መጠራት ማክተም አለበት። የኩሽ ቋንቋዎች ለሶስት ይከፈላሉ።

1ኛ/ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው የኢትዮጵያ የኩሽ ቋንቋዎች 2ኛ/ ጠፍቶ የቀረው የጥንታውያን ግብጾች የኩሽ ቋንቋ 3/ የማግሬብ ሀገሮች በርበር የኩሽ ቋንቋ። የጥንታውያን ግብጾች የኩሽ ቋንቋበ ዐረብኛ ቋንቋ ተውጦ ጨርሶ የጠፋ ሲሆን፤ የማግሬብ ሀገሮች በርበር ቋንቋም በዐረብኛ ቋንቋ ተውጦ በመጥፋት ላይ ይገኛል። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን በዘርም በቋንቋም እስከ አሁን ያልተበረዝን ያልተከለስን ስንሆን የሌሎች የኩሽ ቋንቋዎች የደረሰ ዕጣ እንዳይደርስብን መጠንቀቅና መከላከል አለብን። የኩሽ ዘር ዋና ሠፈሩ በምሥራቅ አፍሪካ ይሁን እንጂ ከመላው አፍሪካ ጥቁር ሕዝብ ተቀላቅሎ ይገኛል። በተለይ ምሥራቃዊውና ደቡባዊው አፍሪካ በከፊል ኩሻውያን ሊባሉ ይችላሉ። ዛሬ ንጹህ ነጠር ዘር የለም። ከኩሻውያንም ከሌሎች ዘሮችም ተቀላቅለው ጠፍቷል።

1. Conti - Rossini : Etiopia e Genti d' Etiopia p. 127 ,34

2. G. Sapeto Etiopia p. 214

ከኩሽ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ብዙት ያለን እኛ ስለሆን የኩሽ ቋንቋ ኢትዮጵያዊ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። እግአዚያን ከደቡብ ዐረቦች ፊደላት ቢወስዱም አባቶቻችን ከእሱ በፊት በነበራቸው የግዕዝውያን ፊደል መጠቀም እኛሽለው የራሳቸው ፊደል ፈጠሩ እንጂ እንዳለ አልተቀበሉትም። አባቶቻችን ያቀረቡን ምናልባት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው የተሟላ ፊደል ነው። እንኳን እኛ ሌሎች አፍሪካውያን ሊጠቀሙበት የሚገባ ነው። ደቡብ ዓረቦች ፊደል የተማሩት ከግሪኮችና ከፊኒቃውያን ነው፤ ራሳቸው ፊደል ፈለማሪያን አልነበሩም። ፊደሉች መበደር የተለመደ ነው፤ በእኛ ብቻ አልተጀመረም። ላቲኖች ከግሪኮች ነው ፊደል የተማሩት፤ ግሪኮችም ከፊኒቃውያን ነው፤ ፊኒቃውያንም ከግብጻውያን ነው የተማሩት። ከባሕል ግንኙነት ሌላ ግን የደቡብ አረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ገብተው ተዋለደው የሴም ኢትዮጵያውያን ቋንቋ ተናጋሪዎች ፈጠሩ ብሎ ማመን ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። በሌላ እርእሰት እንደ ገለጽኩት ፊደል ወደ ኢትዮጵያ የገባው በደቡብ ዓረቦች አይደለም። የኢትዮጵያ ንጉሥ አፈላስ ነው ያስገባው።

1ኛ በኢትዮጵያውያን አፈ ታሪክ ከእሥራኤል እንወለዳለን ብለው የሚያምኑ ኢትዮጵያውያን አሉ። ከዐረቦች እንወለዳለን የሚሉ ግን ከእስልምና የይማኖት ለማገናኘት ካልሆነ በስተቀር አይገኙም። 2ኛ/ በዘር በአንትሮፖሎጂ በኩል ሴም ተብለው ከሚጠሩ ኢትዮጵያውያንና ከሌሎች ኩሽ ተብለው ከሚጠሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ የተረጋገጠ ነገር ነው። ይህ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በቋንቋ ካልሆነ በመልክ እርስ በርሳችን አንለያይም። ብዛት ያላቸው የደቡብ ዓረብ ሕዝቦች ወደ ሀገራችን ፈልሰው ገብተው ቢሆኑ ኖሮ እና ከኩሽ ሕዝብ ተዋለደው ልዩ ሕዝብ ፈጥረው ቢሆኑ ኖሮ ይህ የተደባለቀ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ካልተደባለቁ የኩሽ ጎሣዎች በመልክ ተለይተው ይታወቁ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴማውያን ተብለን ብንጠራም በግዴታ ዓረቦች እንዳልሆን መታወቅ አለበት። ብዙ ባሕሎችና ልማዶች የወረስናቸው ከዓረቦች ሳይሆን ከእሥራኤላውያን ነው። ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑ የሚከተሉት ነገሮች መጥቀስ ይቻላል። 1ኛ/ የታቦት አከባበር 2ኛ/ በጸናጽልና ከበሮ የቤተክርስቲያን ዜማ እንደዳዊት ዘማሪዎች ማዘውተር። 3ኛ/ የቅዱስ ዮሐንስ የመጀረሪያ ዓመት አከባበርና የቅዱስ ሩፋኤል በዓል አከባበር ከእሥራኤላውያን ተመሣሣይ መሆኑ። 4ኛ/ የሩፋኤል ቀን ገንፎ መብላት፤ 5ኛ/ ቢጋብቻ በቀላሉ መፋታትና ብዙ ሚስት ማግባት 8ኛ/ ብዙ ዓይነት ጋብቻዎች መጠቀም 7ኛ/ የወንድም ሚስት ማግባት 8ኛ/ ግርዝ በ8ኛው ቀን እንደሙሴ ሕግ መከተል። 9ኛ/ ክርስትና በአርባ ቀን ለወንድ በሰማኒያ ቀን ለሴት ልጅ መከተል 10ኛ/ የክርስትና ስምና የመጠሪያ ስም በሁለት ስም መጠቀም 11ኛ/ የሚበሉና የማይበሉ እንስሶች መለየት 12ኛ/ የወንድ ስሞች እንደ ኤርሚያስ የሴፍ፤ ያዕቆብ፤ ሚናስ፤ አብራያስ አብርሃም በተለይ በአክሱም አካባቢ የሚዘወተሩ ሲሆኑ፤ የሴት ስም ግን የለም፤ ምክንያቱም ከንግሥት ማክ



ቀዳማዊ ምኒልክ አጅበው የመጡ ከአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች በሙሉ ወንዶች ነበሩ ሴቶች ወደ ኢትዮጵያ አልገቡም።

እግአዚያን የአገው ዛጉዌ ስርወ መንግሥት እስከ ተመሠረተ ድረስ 937 ዓመተ ምሕረት ግእዝ የጋራ ቋንቋ ሲናገሩ ቆይተው ነበረ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ግን ግእዝ ለሶስት ቋንቋዎች ተከፋፈለ። አማርኛ፣ ትግሬና፣ ትግሬ፤ ግእዝ የቤተክህነትና የሥነ ጽሁፍ ቋንቋ ብቻ ሆነ፣ ቀጥሎ አማርኛ ንጉሡ ብዙ ሰው አስከትሎ ወደ ሸዋ ስለሄደ ይህ ቋንቋ ግእዝን ተከትቶ ቀስ በቀስ የቤተ መንግሥትና የሥነ ጽሁፍ ቋንቋ ሆነ። የዛጉዌ መንግሥታትም አማርኛ እንደ መንግሥት ቋንቋ ተጠቅመውበታል። የአማርኛ አመጣጥ በዚህ ዓይነት ሲሆን፤ ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ ቋንቋችን ነው እንጂ የባእድ ቋንቋ አይደለም። የመግባቢያ ቋንቋ ሲኖረ. ን ኩራቱ ለሁላችን ነው። እንደሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የጋራ የመግባቢያ ቋንቋ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሣይኛ፣ በፖርቱጋልኛ ከምንጠቀም በራሳችን ቋንቋ በአማርኛ ብንጠቀም ለእኛ ትልቅ ዕድል ትልቅ ኩራት ነው እንጂ ጭቆና አይደለም።

ሌሎች ቋንቋዎች የመነጋገሪያ ቋንቋ ብቻ ሆኖ ተወስና ነበረ። ባለፈው ምእተ ዘመን ሚሲዮናውያን ወደ ሀገራችን ሲገቡ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ በትግርኛ ስለተረጎሙት በሥነ ጽሁፍ ሊሰፋፉ ችሎዋል። እነ አጼ ዮሐንስና ራስ አሉላ በጽሁፍ በአማርኛ ነበረ የሚጠቀሙት። ከእነሱ የበለጠ ደግሞ ለትግራይ ሕዝብ ለትግርኛ ቋንቋ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆርቋሪ አልተወለደም። እሁንም ቢሆን እግአዚያን እንደነበርን ጊዜ ሁሉ የጋራ ቋንቋችን በቤተክርስቲያን የተወሰነ ሆና ነው እንጂ ግእዝ ነው። ግእዝን ተከቶ አማርኛ የጋራ ቋንቋችን በሚሆንበት ጊዜ እኛ የጠላታችን ቋንቋ ብለን ብንታወም ማሊያናች እነ እንቶኔሊ በእንጉላችን ያስቀረጹልን ስሜት ነው እንጂ መሠረት የለውም። የትግርኛ ቋንቋ ሌሎችም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እስከ ዘመናችን ድረስ የሰነ ጽሁፍ ቋንቋ አልነበራቸውም። በኢትዮጵያ በሥነ ጽሁፍ የዳበሩ ቋንቋዎች የሉንም። አማርኛም የዳበረ ሥነ ጽሑፍ የለውም። ስለዚህ አማርኛ ብቻ በማዳበር ሌሎች ቋንቋዎች ግን ቢጠፉ ለሀገራችን አንድነት አስተዋጽኦ አለው። ከሌሎች ሀገሮች ምሳሌ መውሰድ እንችላለም። ለምሳሌ የእርሚን ቋንቋ ከራሱ ከሩሲያኛ ቋንቋ የበለጠ ጥንታዊነት ያለው በሥነ ጽሁፍ የዳበረ ስለሆነ ቋንቋቸው ቢጠፋ ለመላው ዓለም ጉዳት ነው። የአማርኛ ቋንቋ የፈጠሩ የሰሎሞናዊ ዘር የነበሩ አክሱም የነበሩ ንጉሡና ብዙ ተከታዮቹ የዛጉዌ ስርወ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ ከአክሱም ተነስተው ነው ሸሽተው ወደ ሸዋ የሄዱ፤ እግአዚያን ናቸው፤ ዓረብኛም የአፍሪካ ቋንቋ አይደለም። በሀገራችን የዓረብኛ ቋንቋ ማስፋፋት መሞከር ራሳችን በራሳችን ማንነታችንን ማጥፋት ስለሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በየትም ቦታ መቃወት ያለበት ጉዳይ ነው። ቋንቋችን ዓለማቀፋዊ ከሆነ ከዐረብኛ ቋንቋ መወዳደር ስለሚይችል በጊዜ ብዛት እንደ ሱዳናውያን ጥቁር የዐረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ እንሆናለን።

ኮንቲሮሲኒ ታዋቂው ኢጣሊያዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ( Storia d' Etiopia) በሚለው መጽሐፉ ስለ ደቡብ ዓረቦች በሰሜን ኢትዮጵያ ገብተው መስፈራቸው በሰፊው ጽፎ ነበረ። በሌላ ( Etiopia e Genti d' Etiopia ) በሚለው መጽሐፉ የዓረብ ዘር ምልክት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ እንደማይታይ ሲያስረዳ የዘር በአንትሮፖሎጂ በኩል የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች አንድ ዓይነት የኩሽ ዘር ናቸው ካለ በኋላ በመቀጠል እንዲህ በሎ ጽፏል። «ዓረቦች በምፅዋ፣ አሰብ፣ በሶማሊያ ወደቦች፣ በመሐል ሀገር የንግድ ቦታዎች ይገኛሉ። በኤርትራ ሣህል አንድ አነስተኛ ጐሣ ራሻይዳ የሚባሉ አሉ። በቀድሞ ጊዜ ከሀገሩ ሕዝብ ተዋህደው የጌታ ወገን የሆኑ እንደ ዓድ ሸራፍ በቤጃ ጐሣዎች ውስጥ አሉ። ተመሣሣይ ሁኔታ በሶማሊያ ሚጁርቲኒያ ይገኛሉ። በዛሬ ትውልድ ከማህራ የፈለሱ ለምሣሌ ሬር ማህሙድ ሣልህ ሌላ፤ ዐረብ ናቸው የሚባሉ መምህራን ተብለው ይጠሩ የነበሩ በአትባራ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ዛሬ ግን ከመሕዲሶች ጦርነት ምክንያት በሙሉ ሣያልቁ አይቀሩም።» በዚሁ ዓይነት በኮንቲሮሲኒ አስተሣሰብ ከምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ የሴም ዘር ነን የሚሉ ቢኖሩ ምንም ማስረጃ የላቸውም፤ እሥራኤላውያን ነን የሚሉ በጐንደር የሚገኙ ፈላሾች የሚያምኑት በዘር ሣይሆን በሃይማኖት ብቻ ስለሆነ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት አይቻልም። ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ በዘርም ሆነ በቋንቋ ሴማውያን ወይም ዐረቦች አይደሉም። በኢትዮጵያ ትልቁ ችግራችን ዘርና ቋንቋ መለየት አለመቻላችን ነው። በአሁኑ ወቅት ብሔርና ብሔረሰቦች ተብለው የሚጠሩ ቋንቋ የሚያመለክት ነው ዘር የሚያመለክት አይደለም። ብሔር ወይም ብሔረሰብ ስንለ በዘር አንድ የሆኑ ወይንም በቋንቋ አንድ የሆኑ ምን ለማለት እንደምንፈልግ ግልጽ አይደለም። ኤርትራ ብሔር፤ ትግራይ ብሔር፤ አማራ ብሔር፤ ኦሮሞ ብሔር እንደሌለ ግልጽ መሆን አለበት። እኛ ደግሞ አውሮፓውያንን ተከትለን ትልቅ ክብር እየመለለን የብሔረሰቦች ሙዘዩም ነን እያልን ራሣችን በራሣችን እንጠራለን። በሰሜን ኢትዮጵያ ማእከል አባት ሆኖ የሚታየው የአገው የኩሽ ዘር ነው። በዘመናችን ይህ በላስታ፣ በቤጌምድር፤ ደምቢያ፤ ቋራ፤ በጐጃም አገው ምድር ይኖራል። አገአዚያንም አገው በኢትዮጵያ ታሪክ ውሣኝ ሚና የተጫወቱ ሕዝቦች ናቸው። አገአዚያን ራሣቸው የአገው አንድ ክፍል ሣይሆኑ እንደማይቀሩ እተማመናለሁ። አንድ ሕዝብ ብሔር ወይም ብሔረሰብ የሚያሰኘው አንድ ዓይነት ቋንቋ በመናገሩ አይደለም። አገው ናቸው የሚባሉ ትግሪኛ የሚናገሩ በአበርገለ፤ ሰለዋ፤ በራያ፤ ይገኛሉ። አማርኛ የሚናገሩ የአገው ዘሮች በላስታ፤ በሌላም ቦታ አሉ። በከረን አገው መጣይ ቢሌን ቋንቋ ይናገራሉ፤ ሌሎችም አሉ፤ በሀገራችን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ብሎ መጥራት አግባብ ያለመሆኑን የሚያስረዳ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ሁለት ምሣሌዎች በኤርትራ ውስጥ ብቻ መጥቀስ ይቻላል። 1ኛ/ የቢኒዐመር ጐሣ ተብሎ የሚጠራ በቋንቋ አንድ አይደሉም። በዘርም አንድ አይደሉም። ግማሹ ቤጃ ቋንቋ ይናገራሉ። ግማሹ ትግሬ ቋንቋ ይናገራሉ። በሁለቱ ቋንቋዎች ተናጋሪ



የሚኖረው ሕዝብ ወገን ለይተው ተጣልተው አያውቁም። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚኖሩም በሺ የሚቆጠሩ ዓመታት ነው። 2ኛ/ የዐሣውርታ ጐሣ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ብሔረሰብ ተብለው ይታወቃሉ ነገርግን አሣውርታ በአንድ አነስተኛ ቦታ የሚኖሩ አነስተኛ ሕዝብ ሆኖ አንድ ቋንቋ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ አንድ ዘር አይደሉም። በዘር በኩል ከትግራይ፤ ከአማራ፤ ከኦሮሞም፤ አፋር ሶማሌ፤ አገአዚያን ከቀርከ ከዓረብ እንዲሁም በትክክል የማይታወቁ 21 ዘሮችም ቅልቅል ናቸው። አበሻና አጋአዚያን የተባሉ ጥንታውያን የኢትዮጵያ ጎሳቸው ባሕላቸውና ቋንቋቸው ከሰሜን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መስራጨቱ ታሪካዊ ሐቅ ሲሆን በእንፃሩ ግን ብዙዎች ኢትዮጵያውያን እንደሚመሥላቸው ሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ ወይም ከዓረብ ሀገር የፈለሱ አይደሉም። በዘር በኩል ከተመለከትነው የኢትዮጵያ ጎሳዎች አብዛኛዎቹ የፈለሱት ከመሐል ኢትዮጵያ ነው ወደ ሰሜን የሰፈሩት። በዘመናችን ወደ ተፈጠረው ወቅታዊ ጉዳይ ወደ ኤርትራ ስንገባ በኤርትራ አንድም ጎሳ የሩቅ ቅድመ አያቶቹ ሀገር ኤርትራ ናት የሚል የለም። ሁሉም ከጎንደር፤ ከትግራይ፤ ከሸዋ፤ ከላስታ መጥተው አሁን ባሉበት እንደሰፈሩ በአፈ ታሪክ ከአባቶቻቸው እንደ ተማሩ ያምናሉ። ዛሬ ይሄንን የሚክዱ ቢኖሩ ታሪካቸው የአንድ መቶ ዓመት መሆኑን አምነው የሚቀበሉ ኤርትራን ለመገንጠል እንዲመቻቸው ሰው ሰራሽ ታሪክ ለመፍጠር የሚፈልጉ፤ የእጅ አዙር የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ናፋቂዎችና ወኪሎች መሆን አለባቸው፤ ወይንም ደግሞ አክራሪ እስላሞች ታሪካቸውን ደምስሰው ሌላ ሃይማኖታዊ ታሪክ መፍጠር የሚፈልጉ መሆን አለባቸው።

ኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበሏ በፊት የሙሴ ሕግ ትከተል እንደነበረ የሚያስተምሩ ሙሁራን የሚያረጋግጡት ነው። በኤርትራ በተለይ በሦስቱ የክርስትና ሐይማኖት ተከታይና የትግሪኛ ተናጋሪ የሆኑ የአውራጃ ሕዝቦች ከእስራኤል ቅድመ ክርስትና መዛመዳቸውን ያምናሉ። እንደሚታወቀው ንግሥተ ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ወደ እየሩሳሌም ሄዳ ቀዳማዊ ምኒልክን በመውለዷ ምኒልክም ሲያድግ ወደ አባቱ ሄዶ ከታዋወቀ በኋላ በንጉሥ ሰለሞን ንጉሠ ጽዮን ብሎ ሰይሞ ወደ ሀገሩ በሚመለስበት ጊዜ ከ12ቱ ነገደ እስራኤል አንዳንድ ምኒልክን አጅበው እንዲሄዱ ስለተደረገ በተለይ አብዛኛውን የአከለጉዛይና የሐማሴን ሕዝብ የወለደ ከቢኒያም ነገድ ስለነበር በ950 ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ገባ። እነዚህ ሕዝቦች ደቂምናብ (የምናብ ልጆች) ወይም የብንያም ልጆች እየተባሉ እንሆ እስከዛሬ ይጠራሉ። የአንዳንድ ነገደ እስራኤል የተለየ ምን ነበረው፤ ለምሳሌ ይሁዳ የንጉሥ ዘር ሲሆን ቢኒያም ደግሞ የጦር አዛዥ ነበር ለዊ የቤተክህነት ወዘተ... ከትውልድ ወደ ትውልድ በአፈ ታሪክ በተላለፈው መሠረት ከምናብ ነገድ ከብዙ ትውልድ በኋላ ሜሮኒ በደምቢያ ጎንደር ተወለደ። ሜሮኒ ትልቅ ሰው ሲሆን ወደ ደምቤዛ ሐማሴን መጥቶ ፋሉት፤ ግሉት፤ ሜሉት ወለደ። በደምቢያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ቤተ እስራኤልና አገው ነበሩ። ስለዚህ የምናብ ዘር አገው እንደሆነ ይታመናል። ፋሉት በሐማሴን

ቀርቶ አብዛኛውን የሐማሴንን ሕዝብ ያፈራ ሲሆን ማሉትና ሚሉት ደግሞ ወደ አከለጉዛይ ሄደው የአከለጉዛይን ሕዝብ አብዛኛውን ወልደዋል። ከማሉት ልጆች አከሌና ታከለ ይወለዳሉ። ታከለ ጉዛይና ፲ ልጆቹን ይወልዳል። በዚሁ መሠረት የአከለ ጉዛይ አውራጃ በአከሌና በጉዛይ ትጠራለች። ሚሉትም መረታ ሰበና መረታ ተደሀ በመውለድ በአከለጉዛይ ውስጥ በእነዚህ ሁለት ልጆች ስሙን ያስጠራል።

ንጉሥ ሰርፀ ድንግል የእስራኤልን ሃይማኖት ለማጥፋት ከ1578–1578 ዓ.ም. በፈላሾች ላይ ዘመቻ አድርጎ ነበር። ከዚሁ እልቂት ለማምለጥ ብዙዎቹ ሃይማኖታቸውን ወደ ክርስትና ለውጠው ወደ የማይታወቅበት አገር ሄደው አዲስ ኑሮ ለመመስረት በትተዋል። በኤርትራ ከአግሬ የመምጣታቸውን ምክንያት ሳይገልፁ በተለይ ከደምብያ መጣን ይላሉ። ስለዚህ እነዚህ ጎሳዎች ወደ ክርስትና ሃይማኖታቸውን የቀየሩ የፈላሻ ጎሳዎች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ይገመታል። እነሱም ዛሬ በሐማሴንና በአከለጉዛይ እንዲሁም በሳሃል የሚኖሩ የምናብ (ቢኒያም) ልጆች ናቸው የእነሱ ጎሳዎች በጎንደርና በትግራይ እንዳሉ ያምናሉ።

እስካሁን በተነገረው ታሪክ መሠረት በአጠቃላይ ከኤርትራ ሕዝብ 95 ከመቶ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገሮች ፈልሰው የመጡ ናቸው። በቋንቋ ከሕዝቡ 50 ከመቶ ትግርኛ ተናጋሪ ተብለው የሚታወቁ በዘር ግን የተለያዩ የሆኑ ናቸው። 27 ከመቶ ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ፣ ነገር ግን ዘራችን ትግሬ ነን የሚሉ 23 ከመቶ ብቻ ናቸው የቀሩት 4 ከመቶ ትግሬ ቢናገሩም የዘራቸው አቆጣጠር ግን የተለያየ ነው። 5 ከመቶ ቢለን፣ 5 ከመቶ ሳሆ፣ 5 ከመቶ ቤጃ፣ 4 ከመቶ ኩናማና ባሪያ፣ 4 ከመቶ አፋር ናቸው። ከመሐል ሀገር እንዳልመጡ መናገር የሚችሉ ቤጃ ብቻ ናቸው።

የዚህ አይነት ዘርና ቋንቋ ያለው ሕዝብ ኤርትራ የተለየ ሀገር እንደሆነ ኤርራውያን የተለየ ዘር እንዳላቸው የሚታገሉለት ዋናዎቹ ገንጣዮች እነ አጼ ምኒልክና ጣሊያኖች ከአንድ መቶ አመት በላይ ከበከቧቸው መርዝ ለላልተላቀቁ ነው። አጼ ምኒልክ ቢሞትም ደጋፊዎቹ በአዲስ አበባ ሊኖሩ ይችላሉ።


ይህ ባይሆን ኖሮ አጼ ሚኒሊክ ከሕደት በሚገባ ማጋለጥ በተገባ ነበር። ጣሊያኖች ቆሙንም ቢሆን አይተኙልንም። በአጼ ምኒልክ እና በነ አንቶኔሊ፣ ማርቲኒ፣ ቺከዲኮላ፣ ግራዚኒ፣ ኮሊ ፊርማ ብዙ ዓይነት ሀገራችሁ ናት ብለው የሰጧቸው ለኤርራውያን መቀበሉ እንደ ውርደት ነው። ኤርትራዊ ነኝ ብሎ የሚኮሩ ሰዎች ከኢጣሊያ እልቂት የተረፉ እሱንም በኢጣልያ የቀኝ አገዛዝና ዘረኝነታቸው የሚሰማሙና የሚደሰቱ ናቸው። በምዕራፍ 5 እንደገለፃኩት የኤርትራ አፈጣጠር ትክክል መሆኑን አምነው የሚቀበሉ፣ በ2ኛ ክፍል በዚሁ መጽሐፍ እንደገለፃኩት የኢጣሊያ የዘረኝነት አገዛዝ ትክክል መሆኑን አምነው የሚቀበሉ መሆን አለባቸው። አጼ ምኒልክ ለኢጣሊያ ቀኝ ገዢዎች መሸጡ የሚሰማሙና የሚደሰቱ መሆን አለባቸው።



አሁንም ሌላ የሽያጭ ውል ተፈራርመው ከአሁኗ ኤርትራ የምትበልጥ ወይም የምታንስ ሀገራችሁ ናት ብለው ቢሰጧቸውም ከዚህ የተለየ እጣም ሊኖራቸው አይችልም ማለት ነው። ብዙ ኤርትራዎች ነበሩ አጼ ምኒልክ ፊርማ የሰጣቸው ከነሱም ውስጥ የመጨረሻ ተስማምተው ተፈራርመውበት ሀገራችሁ ናት ብለው የሰጧቸው መቀበል በጣም አሳፋሪ ነው። ኤርትራዊ ነኝ ተብሎ መጠራትም ራሱ አሳፋሪ ነው። በጣሊያኖች ቀኝ ገዢነት ትምህርት የተማሩ በመሆናቸው ግን ሀፍረት አይሰማቸውም።

የኢትዮጵያ የታሪክ ቦታዎች ተብለው የሚቀርቡ በሰሜን በኩል ከወሎ ላሊበላ፣ ከትግራይ አክሱም ሐውልት፣ ጎንደር ከተማና ጣና ሐይቅ ብቻ ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ግን የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ናቸው። ረዘም ያለ ታሪካችን የሚገልፁ የሚገኙት በኤርትራ ክፍለ ሀገር ናቸው። እነዚህ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የታሪክ ቦታዎች የማፕ ንድፍ ተብሎ የቀረበው በታዋቂው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊው ኢጣሊያዊው ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ነው። መፅሐፉ የታተመው በ1925 ዓ.ም ኤርትራ ከተፈጠረች ከ35 ዓመት በኋላ ነው። በማፕ የተመለከቱ ቦታዎች ከአክሱም ጀምሮ እስከ ሰሜን ኤርትራ ታርፋ የሚደርሱ ናቸው። ታሪካዊ ቦታዎች የተሟሉ ናቸው ለማለትም አይቻልም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋራ ከተቀላቀለችበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ በኩል የተደረገ ሙከራ የለም። እኛ አፋችን ከፍተን ኤርትራ ብለን የምንጠራው የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር አንድ የውጭ ሀገር ሰው ያውም ኢጣሊያዊ ባወጣው የማፕ ንድፍ በተገቢ ስሙ ሰሜን ኢትዮጵያ ብሎ ሰየመው እንጂ ኤርትራ ብሎ አልጠራውም። እነዚህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቦታዎች ተብለው የቀረቡ በክፍለ ሀገር የተከፈሉ አልነበሩም። ቦታዎችን በመመልከት ግን 8 ብቻ በትግራይ ክፍለ ሀገር አክሱም ከተማ አካባቢ ሲገኙ 38 በአከለጉዛይ አውራጃ ይገኛሉ የቀሩት 37 በቀይ ባሕር ምፅዋ አካባቢ፣ በሰራዬ፣ በሐማሴን፣ በከረን፣ በሣሂል፣ በባርካ አውራጃዎች የሚገኙ ናቸው።

እነዚህ ታሪካዊ ቦታዎች በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረቶች ናቸው። የኤርትራ ሕዝብ የራሱ እድል በራሱ ይወሰን መገንጠል ቢሰፈልገው ይገንጠል ማለት እነዚህ የታሪክ ቦታዎችና ሀውልቶች በኤርትራ ሕዝብ የተሰሩ የኤርትራ ሕዝብ ንብረቶች ብቻ መሆናቸውን አምነን መቀበላችን ያስመስላል። አንዳንድ የውጭ ሀገር ሰዎች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ሁሉ የተሰሩ ስልጣኔ ነክ ነገሮች አፍሪካውያን አይደሉም የሰሯቸው ከውጭ ሀገር የመጡ ሰዎች ናቸው የሰሩዋቸው የሚሉ ልግዳዊ አመለካከቶች አሉ። በእኛ በኩል ግን ምንም እንኳን አንዳንድ ባለሙያዎች ከውጪ ሊመጡ ቢችሉም በኢትዮጵያ ያለው ታሪክ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰራነው ብለን እናምናለን። እነዚህ ብዙ ታሪካዊ ቦታዎችና ሐውልቶች በወቅቱ ለነበረው ሕዝብ የሚያገለግሉ እስከ ሆኑ ድረስ የሰዎች ቅሪት ዘራቸው እንዳለ ወይንም ተከልሶም ቢሆን ለትውልድ ተላልፎ ወደ ዘመናችን ይደርስ ነበር። ነገር ግን የዚህ ዓይነት ምልክት ዛሬ ምንም አይታይም። ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ






ያሉት ኢትዮጵያውያን መልካችን አንድ ነው። ከዚህም ሌላ ከዚህ በላይ እንደገለፅኩት ሬደላችን ለቋንቋችን እንደሚስማማ አድርገው የፈለሰፉት ንፁህ ኢትዮጵያውያን ቋንቋውን በሚገባ የሚያውቁ መሆን አለባቸው። ይህ ባይሆን ኖሮ እንከን በሌለበት ሊፈጥሩት ባልቻሉ ነበረ።

ከኢትዮጵያውያን መካከል የትኛው ክፍለ ሀገር ነው የሰራው የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በትግራይና በኤርትራ ተመዝግበው የሚታዩ ሐውልቶች በዛሬዎቹ ኤርትራውያንና ትግሬዎች ብቻ የተሰሩ አይደሉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ይወዳል። ለምሳሌ የኦሮሞ ሕዝብ ብንወስድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ወደ መሀል ኢትዮጵያ የመጣ፤ 400 ዓመት ገደማ ነው። በጥንት ጊዜ የኦሮሞ ሕዝብ ማሐል ኢትዮጵያ ይኖር እንደነበረና በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ደቡብአዊ አፍሪካ ወይንም ደቡብአዊ ኢትዮጵያ ፈልሰው ከቆዩ በኋላ እንደገና ወደ ነበሩበት ሀገር ተመልሰው መምጣታቸው ነው የሚያሳየን እንጂ አዲስ ሕዝብ እንደመጣ መገመት የለብንም። ይህ ባይሆን ኖሮ በቋንቋ ካልሆን በቀር በመልክና በፀር ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የማይለዩ በመሆናቸው በቀላሉ ባለተደባለቁና ባልተዋሀዱ ነበር። በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ሐውልቶችና የታሪክ ቦታዎች የተሰሩበት ዘመን የኦሮሞ ሕዝብ ምናልባት በሰሜን ኢትዮጵያ ይኖር ነበር። በኤርትራ የሚኖረው ሕዝብ ከመቶ አስር አይሆንም የጥንት ነዋሪ ናቸው የሚባሉ ሌላው ሁሉ ከሌላ ቦታ መጥቶ የሰፈረ ነው።

ስለዚህ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የታሪክ ቅርሶች የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረቶች ናቸው እንጂ የአንድ የተወሰነ ክፍ/ሀገር አይደሉም። የሀገራችን ነፃነት ተጠብቆ የኖረው በአንድ የተወሰነ ክፍል ሕዝብ ብቻ አይደለም በመላው የሀገሪቷ ሕዝብ ትብብር ነው። ስለዚህ የሀገራችን ቅርሶች የጋራችን ስለሆነ በጋራ መጠቀም የሁሉ ኢትዮጵያውያን ኃላፊነት ስለሆነ ሳይደፈር ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ግዴታ አለብን። በአጼ ምኒልክ የሚመሩ የአማራ ነፍጠኞች የኦሮሞ ሀገርን ወረው ይዘው በጭቆና ገዙት እየተባለ የሚነገረው ተቀባይነት የለውም። የኦሮሞ ሕዝብ በ16 ክ/ዘመን ጀምሮ ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነስቶ የማስፋፋት አካሂዶ የሸዋ ለም መሬት ከአማራ ሕዝብ አስለቅቆ በመያዝ የአማራ ሕዝብ በተራራዎች ብቻ እንዲሰፍን አድርገዋል። በኋላም ወሎን ይዞ ወደ ትግራይ ገብቶ በጎንደር የነበረው ማእከላዊ መንግሥት በሥልጣን ከተካፈለ በኋላ ከሀገሩ ሕዝብ ተስማምቶ ተዋህዶ እስከ 19 ምህተ ዘመን ማብቂያ በዚህ ዓይነት ወረራ ቀጥ ተረጋግቶ ነበረ። በአጼ ምኒልክ ዘመን መንግሥት በስተደቡብ ምዕራብ የቀረው የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋራ አንድ ላይ እንዲቀላቀለ ኦሮሞ ዝርያ በነበራቸው በነ ራስ ጎበና የመጀመሪያ ራስ በሸዋ ሆነው የተሾመው እየታገዘ አጼ ምኒልክ ዘመቻ አድርጎ ኦሮሞዎችን በቁጥጥሩ ማድረጉ መጥፎ ስም ሊሰጠው አይችልም። የአማራ መልስ ማጥቃት ዘመን ተብሎ መጠራት ይቻል ይሆናል ወይንም ደግሞ ዘመነ አጠራር በሰሜንና መሐል ሀገር ከአማራና ከትግሬ ተቀላቅለው በሰላም ይኖሩ የነበሩ

ኦርዋምችና በስተ ደቡብና ምዕራብ ብቻቸውን ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎች ለማቀላቀል የተደረገው ዘመቻ ብለን ብንጠራው እንችላለን።

ስለ ታሪካዊ ቦታዎችም ሆነ ስለ ሌላ ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኤርትራ ጋራ እኩል መብት ለመናገርም ድምጽ መስጠትም መብት አለው። ስለዚህ በማንኛውም መመዘኛ ተቀባይነት የሌለው የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ እጁን አጣምሮ ማየት ከእውነተኛ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም። ታሪካዊ ቦታዎች የኢትዮጵያ ንብረቶች ናቸው የኤርትራ ንብረቶች ብቻ ሊባሉ አይችሉም። የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ንብረት ስለሆኑ የውጭ ሀገር ማለት የኤርትራ ናቸው ኢትዮጵያ አይመለከታትም በማለት ጥበቃ ከማድረግ ችላ ማለት ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው፡ በመጪው ትውልድ የሚያስወቅስ ነው።



Notizie sui popoli che abitano l'Africa Orientale tra il Mar Rosso ed il Nilo.

| PAESI | ABITANTI | ORIGINE | LINGUA | MESTIERI | RELIGIONE |
|---|---|---|---|---|---|
| 1° Isole di Dahlak | Dahalaki | Etiopi in maggioranza, con mescolanza di arabi. | Tigrè | Pescatori e marinai. | Islamismo |
| 2° Isole di Dessè | Dankali | Venuti da Buri. | Saho | Id. Id. | Id. |
| 3° Isole di Massaua | Massauini | Venuti da tutte le parti. Il fondo è etiope. | Tigrè | Commercianti e marinai. | Id. |
| 4° Samhar | 1) Teroa | Chiamano sè stessi arabi, fratelli dei Mensa e dei Marea. | Saho | Pastori. | Id. |
| | 2) Beduini: a) nei villaggi Otumlo, Zaga, Emberemi, Ailet, Asus, Gumhod. b) sotto tende, Az [illegible], Mascialit ecc. | Sono in maggioranza Etiopi venuti dagli Habab e dai popoli dell'Anseba consanguinea della razza subordinata degli Habab. | Tigrè | Pastori e in parte agricoltori. | Id. |
| | | | | | Id. |
| | 3) [illegible] che abitano il capoluogo (Archico). | Il fondo della popolazione è Beit [illegible] che si trovavano a nord del Samhar. | Id. | | |
| 5° Paese degli Habab | Habab divisi in tre stirpi Az Temariam, Az Tekles, Az Hibdes, composti di: a) nobili b) sudditi. | I nobili sono venuti dall'Abissinia in epoca posteriore ai sudditi che sono anch'essi di origine etiopica. | Id. | Pastori. | Islamismo (da circa 60 anni) |
| 6° Sahel (costa del mare fino ad Akik) | Beni Amer che constano di: | Mista. | | | |
| | 1° Nebtab (di stirpe Giallin) nobili. | Arabi. | | | |
| | 2° Soggetti. | Etiopi, parenti dei soggetti presso gli Habab. | | | |
| 7° Paesi dell'Anseba a) Mensa | 1° Beit Abrehe. 2° Beit [illegible]. (Il fondo della popolazione è etiope con nobiltà imparentata con quella dei Marea e dei Teroa, la quale dev'essere di origine arabica). | Etiopi come i soggetti degli Habab. | Id. | Agricoltori e pastori, abitazioni fisse. | Cristianesimo |
| b) Bogos | 1° Beit Tarke (nobili). 2° Soggetti. | Agau di Lasta. Etiopi aborigeni. | Bilen. Il Tigrè viene capito | Id. Id. | Cristiani, pochi Maomettani |
| c) Bejuk | Beit Zere Barak. | Come gli Habab. | Tigrè | Id. Id. | Id. Id. |
| d) Beit Takue | Beit Takue. | Etiopi. La nobiltà immigrata recentemente dall'Hamasen. | Bilen e Tigrè | Id. Id. | Islamiti da circa 30 anni |
| e) Marea | Rossi e neri. | La nobiltà parente con quella dei Mensa, si dice d'origine araba. I soggetti sono etiopi. | Tigrè | Id. Id. | Islamiti da circa 40 anni |
| 8° Baraka | 1° Nobiltà (Nebtab e [illegible]). | Di discendenza arabi. | Tigrè e Bedauie | Pastori. | Islamiti |
| | 2° Soggetti. | Etiopi e Bedgia. | Id. | Id. | Id. |
| 9° Paese dei Barea | 1° Nera. | Di dubbia origine. | Lingua speciale | Agricoltori. | Islamiti e Deisti |
| | 2° Mogoreb | Di dubbia origine. | | | Id. |
| 10° Paese dei Baza | Kunama. | Di dubbia origine. | Id. | Id. | Deisti |
| 11° Algheden | Algheden, in due villaggi. | Il fondo della popolazione è come nel paese dei Baza; vi si trova mescolanza di Etiopi della stirpe [illegible]. | Tigrè | Agricoltori e pastori fissi. | Islamiti |
| 12° Sabderat | Sabderat, in due villaggi che si stanno di fronte. | Il fondo della popolazione è Marea, con varie mescolanze, specialmente di Etiopi. | Id. | Id. Id. | Id. |
| 13° Taka o Gash | 1° Halenga, abitanti specialmente in Chatmia, Hellet, Sceriff, Kassala, [illegible], Dabbah. | Abissini di [illegible]. | Tigrè, parlano anche bedauie ed arabo. | Id. Id. | Id. |
| | 2° Hadendoa. | Bedgia. | Bedauie | Agricoltori e pastori [illegible]. | Id. |
| | 3° Popolo misto di Beni Amer, [illegible], Arabi e Turchi. | Di varie origini. | Varie lingue | Agricoltori, commercianti, soldati, ecc. | Id. |

ሙንዚንገር በግብጽ መንግሥት ስም ከአባይ እስከ ምፅዋ ያለው መሬት አስተዳዳሪ በነበረ ጊዜ ስለ ምሥራቅ አፍሪካ ጥናት በሚል አርእስት በደረሰው መጽሐፍ ስለ ኗሪ ሕዝቦች በሰንጠረዥ ያወጣው የሚከተለው ነው።

| የሀገሩ ስም | የሕዝቡ ስም | ዘር መሠረቱ | ቋንቋ | ሥራ | ሃይማኖት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. ዳሕላክ ደሴት | ዳህላካውያን | አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዓረቦች የተቀላቀሉበት | ትግሬ | አረኞች ባህርተኞች | መስሊም |
| 2. የደሰት ደሴት | ደንከላውያን | ከዐፋር የመጡ | ሳሆ | ” | ” |
| 3. የምፅዋ ደሴት | ምፅዋውያን | ከሁሉ ቦታ የመጡ መሠረታቸው ኢትዮጵያውያን | ትግሬ | ነጋዴ ባሕርተኛ | ” |
| 4. ሰምሀር | 1 ቀርዓ | ራሳቸው ዓረብ ነን ይላሉ የመንሳዕና የማሪያ ወንድሞች | ሳሆ | አረኞች | ” |
| | 2 በዱዋን ሀ/በአቶምሉ ዓ.ገ ኢምበረሚ እሱስ ገሞሀድ ለ/ዘድንጉን እዝ ሸግ ማሻሊድ ወዘተ | አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ከሐባብና ከዓንሰባ የመጡ | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | ” |
| | 3ድኩና ዋና ከተማ አርቂቆ የሚኖሩ | አብዛኛው በለው ከሰምሀር በተሰሚን የመጡ | ትግሬ | አረኞች | ” |
| 5. ሐባብ | 1ዓድ ተማርያም 2.ዓድ ትክሌስ 3.ዓድ ሂብደ ስ ለጨዋና ለአገልጋዮች የሚከፈሉ | ሁሉም የኢትዮጵያ ዘር ናቸው | ትግሬ | አረኞች | ከ40 ዓመት ወዲህ እስላሞች |
| 6. ሳሆል | ሀ.ቢት ዓመር የጨዋ ዘር ነብታል ሻሊ ሲአገልጋዮች | ድብልቅና ዓረቦች | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | እስላም |
| 7. ዓንሰባ ሀ.መንሳዕ | 1ቤት አብርሄ ቤት ሻካን ኢትዮጵያውያን፣ መረዮች ዓረቦች | ኢትዮጵያውያን | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | ክርስቲያን |
| ለ. ቦጎስ | 1ጨዋቤት ተርከ 2.አገልጋዮች | ከአገው ዓለታ ኢትዮጵያውያን ጥንት ኗሪዎች | ቢለን ትግሬ | አረኞች አረኞች ገበሬዎች | ክርስቲያን ጥቂት እስላም |
| ሐ.ቢጁክ | ዘራብሩክ | እንደ ሐባብ ኢትዮጵያውን | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | ከ20 ዓመት ወዲህ |
| መ. ቤት ተክሌ | | ኢትዮጵያውያን ጨዋዎች ከቅርብ ጊዜ ከሐማሴን የመጡ | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | እስላሞች ከ20 ዓመት ወዲህ እስላሞች |
| ሰ. ማሪያ | ቀይ ጠይም | ጨዋዎች እንደ መንሳዕ ዓረብ ነን የሚሉ አገልጋዮች ኢትዮጵያውያን | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | ከ40 ዓመት ወዲህ እስላሞች |
| 8. ባርካ | ሀ/ጨዋዎች (ነብታብ) በለው ለ/አገልጋዮች ኢትዮጵያውያንና በጃ | ዓረብ ነን የሚሉ ኢትዮጵያውያንና በጃ | ልዩ ቋንቋ | ገበሬዎች | እስላሞችና ልዩ ሃይማኖት |
| 9. ባሪያ | ሀ/ነሬ ለ/ሞጎሬብ | ዘሩ አጠራጣሪ | ” | ” | ” |
| 10.ባዜ | ኩናማ | ” | ” | ” | ” |
| 11.አልገደን | አልገደን ሁለት መንደሮች | ኢትዮጵያውያንና በለው ድብልቅ | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | እስላሞች |
| 12.ሰብደራት | ሰብደራት ሁለት መንደሮች | አብዛኛው ማሪያ ሲሉች አብዛኛው ኢትዮጵያውያን የተቀላቀሉበት | ትግሬ | አረኞች ገበሬዎች | እስላሞች |
| 13.ተከ ወይንም ጋሽ | 1.ሐለንጋ በትግሚን ሆለት ሽሬፍ ከሰላ እብሬት ደባህ | የሰራዩ ሐበሾች | ትግሬ እንዲሁም በደኒና ዓረብኛ ይናገራሉ | አረኞች ገበሬዎች | እስላሞች |
| | 2.ሐደንደዋ | በጃ | በጃኒ | አረኞች ገበሬዎች | እስላሞች |
| | 3.የቤኒ ዓመር ሻሊን | ዓረብና ቱርክ ድብልቅ | ድብልቅ | ገበሬዎች ነጋዴ ወታደር ወዘተ | እስላሞች |

# ምዕራፍ 11

# ለማይጨው ጦርነት ዝግጅት

## ኢትዮጵያ ለማይጨው ጦርነት ያደረጋቸው ዝግጅት

ጣሊያኖች ለጦርነቱ 40 ዓመታት ሲዘጋጁ የኢትዮጵያ ለጦርነቱ ዝግጅት ምን ይመስል እንደነበር አሁንም የምናገረኘው ከጣሊያኖች ራሳቸው ነው። ጄኔራል ፍሩሺ በደረሰው መጽሐፍ ኢትዮጵያ ለጦርነት የተዘጋጀችው 3 ዓመት ጦርነቱ ከመፈንዳቱ በፊት ነው ብሏል። ዲሴምበር 1934 ‹1927 ታህሣሥ› ኢትዮጵያ የነበሩዋት ጠብመንጃዎች አንድ ሚሊዮን የሚገመቱ ነበሩ፤ ጥይቶችም 150 ሚሊዮን ነበሩ። ከቅረብ ጊዜ ወዲህ ለኢትዮጵያ የሚቀርቡላት የጦር መሣሪያዎች እየጨመሩ በመሄዳቸው ለኢጣሊያ አስጊ ሁኔታ ሊፈጥሩባት እንደሚችሉ ስጋት ነበር። የእንግሊዝ ጋዜጣ ደይሊ ኤክስፕርስ ጃኑዋሪ 1935 እንደጻፈው የጦር መሣሪያ አቅራቢዎች የኢትዮጵያ መፊት አጥለቅልቀዋት ነበር፣ የሚቀርቡ መሣሪያዎችም ዘመናዊ ጦርነት የሚፈለገው ሁሉ ፀረ ጋዝ ማስክ ጭምር የጦር ተሽከርካሪዎች፣ ነዳጅ፣ ፀረ ታንክ፣ ፀረ አረዮፕላን ያካተቱ ነበር፣ በጂቡቲና በእንግሊዝ ሶማሊላንድ በኩል ያለ ማቋረጠ ይገቡ ነበር ብሏል። በርክክቡ አንዳንድ ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ራሱ በባቡር ጣቢያ ተገኝቶ ይመለከት ነበር። መሣሪያዎች የሚመጡባቸው ሀገሮች በልጂዬም፣ ጀርመን፣ ቼኮዝሎቫኪያ ወዘተ ነበሩ። በመጨረሻ በሀገሮቻቸው ግፊት የጦር መሣሪያ አቅራቢ ነጋዴዎች ከኢትዮጵያ ትዕዛዝ አለመቀበል ተገደው ነበር። በዚሁ ጊዜ በኮንትሮባንድ መልክ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ታገኝ ነበር። ለንጉሠ ነገሥቱ እንቅልፍ ነስቶት የነበረ የጦር መሣሪያ አቅርቦት ጥያቄ በተለይ ከበታች ሹማምንቶች ነበር። ለዚህም ምሳሌ የሚጠቀሰው የቆራኺይ ደጃዝማች አፈወርቅ ነበር።

የመኪና መንገድ የተፈጠረው በደቡብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ነበር። በመሬቱ አስቸጋሪነት ምክንያት ከሁሉ ተረስቶ የቀረው የሰሜኑ ክፍል ነበር። ዘመናዊ ወትድርና መገንባት ሌላ የተደቀነ ችግር ነበረ። ንጉሠ ነገሥቱ የሚኩራባቸው የክቡር ዘመበኛ ጦር ለሰልፍ የሚያገለግሉ ዓይነት ብቻ ናቸው፤ ብዛት የላቸውም። የዚሁ ዓይነት ሠራዊት በብዛት ማፍራት ያስፈልጋል። ብዛት የላቸውም። የዚሁ ዓይነት ሠራዊት በብዛት ማፍራት ያስፈልጋል። አሰልጣኞች የበልጂዬም ተወላጆች የጦር መኰንኖች ናቸው። በወለታ የኢትዮጵያ የጦር መኰንኖችን ለማሠልጠን ኃላፊነት የተሰጣቸው የስዊድን ተወላጆች ናቸው። 100 ሰልጣኞች፣ 60 ከተፈሪ መኰንን ት/ቤት 40 ከዳግማዊ ሚንልክ ት/ቤት የተመረጡ የመጀመሪያዎቹ ነበሩ።



በጦርነቱ ጊዜ እንደ ድሮ ጊዜ ከሕዝብ እየዘረፉ መብላት ለማስቀረት ዘመቻው የሲቪል ጉተራዎች ተሰርዟል። የፕሮፓጋንዳ ሥራ ያተኩር የነበረው በመጪው ትውልድ የሀገር ፍቅር በማስተማር፣ እንዲሁም በኦጋዴን አካባቢ ሕዝቡ በጣሊያኖች ላይ ታምኖ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር እንዲሰለፉ ለማድረግ ነበረ።

ራስ ሙሉጌታ የጦር ሚኒስትር ጁን 29.1935 «ግተን» ለተሰኘው ጋዜጣ ባደረገው ቃለ ምልልስ፣ 4 ወር ጦርነቱ ከመፈንዳቱ በፊት ለጊዜው ኢትዮጵያ 350.000 ወታደሮች አላት፤ ከ15 እስከ 30 ቀን ውስጥ 800 እስከ 900ሺህ ቁጥራቸው ሊደርስ እንደሚችል ብሉ ተናግር ነበር። ጁላይ ወር 1935 የኢትዮጵያ የጦር መሣሪያዎች ወደ ኤርትራና ሶማሊያ ድንበር ሲጉርፉ ታይቷል። በዚህ ጊዜ 25.000 ወታደሮች በደቡብና ምሥራቅ ጦር ሰፈሮች ሰፍረዋል፤ 4000 የጠረፍ ጠባቂዎች ተመድበዋል። የኢትዮጵያ የጦር ስልት በ3 ደረጃ የተከፈለ ነበረ። በመጀመሪያ ኤርትራን በማጥቃት 2ኛ ሶማሌን የማጥቃት ዓላማ፣ 3ኛ የመከላከል። ጣሊያኖች ባገኙዋቸው መረጃዎች መሠረት በ1932፤ 500.000 የኢትዮጵያ ጦር በኤርትራ ድንበር እንዲሰማራ 10.000 በሶማሌ ድንበር እንዲሰፍር ታስቦ ነበር። በኋላ ግን የኢትዮጵያ መንግሥት የሳቡን ቀይር ዋናው ትኩረት ወደ ሶማሌ አደረገ።

ከወልወል ግጭት በኋላ የመጀመሪያ የወታደሮች እንቅስቃሴ የታየው ወደ ሶማሌ ነበረ፤ ቀጥሎም ወደ ኤርትራ እንቅስቃሴ ታይቷል። በሐረርጌ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በእንግሊዝ ሶማሊላንድ በኩል የሚያገኘው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ስለታመቀ የማጥቃት እርምጃ እንደሚወስድ ታስቦ ነበር። ኢትዮጵያ መልሶ ማጥቃት ካልሆነ ለፖለቲካ ሲባል ራሷ ወረራ መጀመር አትችልም ስለተባለ ዕቅዱ በተግባር ሊውል አልቻለም። በኢትዮጵያ አጠቃላይ የወታደር ምልመላ ክተት ጥሪ የታወጀው ሴፕተርበር 1935 (መስከረም 1928) ነበር፤ አንድ ወር ጦርነቱ ከመንፈንዳቱ በፊት፤ ጣሊያኖች ግን ለጦርነቱ ዝግጅታቸው ያጠናቀቁበት ወቅት ነበር። በደቡብና ምሥራቅ ጦር ግንባር 25.000 የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ወደ 60.000 ከፍ ብሏል። ከእነሱ ውስጥም 18.000 በሐረርጌ 12.000 በባሌ 32.000 በሲዳሞ በረና ነበሩ። በኦጋዴን በረሃ መንደሮች ተበታትነው የነበሩ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ቁጥራቸው አልጨመረም። በሰለጠኑ ሀገሮች አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ጦርነት ሲከፍት መክፈቱን በይፋ መግለጽ የተለመደ ሲሆን እብሪተኞች ጣሊያኖች ግን ወሰኑን ጥሰው ሊገቡ በድንገት ነበር።

ኦክቶበር 3 1935 (መስከረም 23 ቀን 1928) ጣሊያኖች የሶማሌን ኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው ሲገቡ ባልተጠበቀ ሁኔታ ኢትዮጵያ ለጦርነቱ ሳትዘጋጅ ነበር። በኦጋዴን የሰፈሩ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ባስቸኳይ ከበላይ አካል እርዳታ የሚያገኙበት ዕድል አልነበራቸውም፤ ችግራቸው ራሳቸው በራሳቸው ብቻ መፍታት ነበረባቸው[1]።

1. General L.Frusci - In Somalia Sul fronte meridionale tavola 7 p. 65

ከማፕ እንደሚታየው በየጣቢያው የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ነበር። ጣሊያኖች ለወደፊት ለሚጠብቃቸው ከፍተኛ ጦርነት የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ሰፈሮች እንደ ጦር ልምምዶች ተጠቅመባቸዋል። የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ግን እጃቸውን ሳይሰጡ ለተፈፀመባቸው ወረራ ሳይደነግጡ ጣሊያኖች ባልጠበቁት ባስደናቂ ሁኔታ አቅማቸው በፈቀደ መጠን፣ ከአቅማቸው በላይ፣ ተቋቁሟቸዋል። አንዳንዶቹ ለመጥቀስ ያህል የመጀመሪያ የኢጣሊያ ወረራ ዒላማ ከሆኑ ውስጥ ኦክቶበር 4 ዶሎ ብዛት ባላቸው፣ ለኢጣሊያ ወታደሮች ስትወረር ጣሊያኖች ከፍተኛ የመከላከል ውጊያ ከኢትዮጵያውያን ወታደሮች ጠረፍ ጠባቂዎች ደርሶባቸዋል።

በተደረገው ውጊያ ከኢትዮጵያ ወገን 8 ሲሞቱ 20 ቆስሏል 86 ተማርከዋል፣ የጣቢያው አዛዥ የነበረው ግራዝማች መኩሪያ ተሰማ ብዙ ጊዜ ቆስሎ እጁን ሳይሰጥ እየተዋጋ ተገድለዋል። ጨካኙ ፋሽስት ማርሻል ግራሲያኒ በክብር እንዲቀበር አድርገዋል። እንደዚሁም በዚሁ ቀን ኦክቶበር 4 ገርሎ ጊቢ ከጧቱ 11 ሰዓት በድንገት በጣሊያኖች ስትወረር 150 የነበሩ የኢትዮጵያ ተከላካዮች ጣሊያኖች እንዳያመልጡ አንደ ጦር ልምምድ ከበባ ቢያደርጉባቸውም ኢጣሊያዊ ኰሎኔል ማለቲ (Maletti ) ያወጣው የጦር ልምምድ ውጊያ አከሽፎበታል። የኢትዮጵያ የጣቢያ ጦር መሪ ግራዝማች በላቸው በጦርነቱ ሲገደል፣ ከ20 ያላነሱ ሌሎች ወታደሮችም ሲገደሉ አብዛኞዎቹ ግን ወደ ጫካ ገብተው ለማምለጥ ችሏል።

ሺላቦ ለመያዝ ጣሊያኖች ዝናብና ጭቃ ስለሆንባቸው ድንገተኛ ጥቃት ሊያደርሱ አልቻሉም። 50 ብቻ የነበሩ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ሰፈራቸውን ለተው ወደ ቀራሄይ ሄደው ከኢትዮጵያ ጦር ጋራ ሊቀላቀሉ ችሏል። ዲጥሬይ ወይንም ተፈረ ከተማ 250 የኢትዮጵያ ወታደሮች የሰፈሩባት ነበረች። ብዛት ያላቸው የመጡባቸው ወራሪ የኢጣሊያ ወታደሮችን በመቋቋም ከፍተኛ ውጊያ ተካሄዶ 30 በጦር ሜዳ ሞቷል፣ ጣሊያኖች ማርከናል ካሏቸው 41 ኢትዮጵያውያን መካከል 23 ሶማሌዎች 8 አማራ 10 ልጆች ሴቶች ነበሩ። በአጋዴን ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች የሰፈሩባት ቀራሄይ 19 በምብ ጣይ አሬዮፕላኖች ተጠቅመው ጣሊያኖች በአየር ደበደቧት። የጦሩ አዛዥ ቆስሎ ባስጊ ሁኔታ በመሆኑ የኢትዮጵያ ጦር ጣሊያኖች ሳያውቁ ምሽጉን ለቆ ወጥቷል። ኖቬምበር ወር በቀራሄይ ጦርነት ለመግጠም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ዝግጅት አጠናቅቀው ይጠባበቁ ነበር። ኖቬምበር 4 ቀን በ12 ሰዓት ለስለላ የተላኩ የኢጣሊያ የጦር አሬዮፕላኖች ቀራሄይ የኢትዮጵያ ወታደሮች እንዳልሰፈሩባት ያረጋግጣሉ። ማርሻል ግራዚያኒ ኢትዮጵያውያን የኢጣሊያ አሬዮፕላን ድብደባ ፈርተው በምሽጋቸው ተደብቀው እንዳይሆኑ ለማረጋገጥ በታንክ የታገዘ ጦር ወደ ቀረሄይ እንዲሄድ አዘዘ፣ በራሱ የኢታማዦር ሹምም ጄኔራል ፒዞሪዮ ( General Pizzorio) የሚመራ ልኮ ኢትዮጵያውያን ቀራሄይን ለቀቃቸውን ከተረጋገጠ በኋላ አሳድዶ መደምሰስ እንዲካሄድባቸው አዘዘ።



ኖቬምበር 6 ቀራሄይ በጣሊያኖች ስትያዝ ሰው አልባ ነበረች፣ ሆኖም ጣሊያኖች ብዙ የጦር መሣሪያ መድኃኒቶች፣ ነዳጅ፣ ቡና፣ ስኳር፣ በርበሬ፣ ማርከናል ብለዋል።

በደቡብ ጦር ግንባር ለተሰለፉ በአንድ ጦር አዛዥ የሚመሩ 100.000 የኢጣሊያ ወታደሮች የተፋለሟቸው ኢትዮጵያውያን በአንድ አዛዥ የማይመሩ፣ የተበታተኑ፣ ቁጥራቸው ኢትዮጵያ ወታደሮች እላይ እንደተገለጠው በጣሊያኖች በሚገባ ይታወቅ ነበር፣ ቁልጭ አድርገው በማፕ አስቀምጧቸዋል።

በሰሜን ጦር ግንባር ለተሰለፈ በአንድ ጦር አዛዥ የሚመሩ 400.000 የኢጣሊያ ወታደሮች የተፋለሟቸው ኢትዮጵያውያን በአንድ አዛዥ የማይመሩ የተበታተኑ፣ የቁጥራቸው ግምት፣ እላይ እንደተገለጠው በጣሊያኖች በሚገባ የታወቀ ነበረ። ባዲሊዮ ባደረሰው መጽሐፍ እንደገመተው በመጀመሪያ የቴምቤን ጦርነት የተካፈለው የኢትዮጵያ ወታደር የተሰጠው ከፍተኛ ግምት ብዛት 20.000፣ በአንደርታ 80.000፣ በ2ኛ የቴምቤን ጦርነት 30.00፣ በሽሬ ከ30 እስከ 50.000፣ የማይጨው 50.000 ነበረ።

በኢትዮጵያ ላይ ይደረግ የነበረ የሥለላ ሥራ ሁሉ ዋና ሰፈሩ ኤርትራ ውስጥ ነበረ።

በ1925 በኤርትራ የኢጣሊያ ጦር ኃይል ኢትዮጵያ 580.000 ጠብመንጃዎች፣ 193 መድፎች እንዳሏት ገምቷል።

የኤርትራ ቅኝ ግዛት ገዢ የነበረው ኮራዶ ዞሊ ( Corrado Zoli) ባደረገው ጥናት ኢትዮጵያ 541.000 ጠብመንጃዎች፣ 205 መትረየሶች፣ 136 መድፎች እንዳላት ግምት ሰጥቶ ነበር።

በ1934 ጣሊያኖች በደረሳቸው መረጃዎች ኢትዮጵያ 800.000 ጠመንጃዎች፣ 900 ቀላል መትረየሶች፣ 280 ከባድ መትረየሶች፣ 224 መድፎች 7 የንጉሡ የግል ንብረት ታንኮች፣ 7 ሌሎች ታንኮች ከእነሱ 5 በሐረር አጋዴን ጦር ግንባር የተመደቡ ነበሩ.[1]

## የኢጣሊያ ዝግጅት ለማይጨው ጦርነት

የዓድዋ ሽንፈት ለመበቀል ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር ያረገችው ዝግጅት በጣም ሰፊ ነው። ለወረራው የተደረገው ዝግጅት ማእከል የነበሩ፣ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዢ ወረራ ማመቻቸት እንደመረማመጃ ጣቢያ አገልግሎት የነበራቸው፣ ኢትዮጵያን በሰሜንና በደቡብ የከበቡዋት የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ኤርትራና ሶማሊያ በኢትዮጵያ ካቋቋመቻቸው 6 ቆንስላዎች ሦስቱ አንጋፋዎቹና ዋናዎቹ የዓድዋ፣ የጉንደርና የደሴ የሚመሩ በኤርትራ ቅኝ ገዢዎች ነበሩ። እነዚህ ቆንስላዎች ሲቋቋሙ በንግድ ድርጅት ሽፋን ነበረ፣ በኋላ ግን የበለጠ መንግሥታዊ ድጋፍ እንዲኖራቸው ቆንስላዎች ተባሉ። በደብረ ማርቆስና በሐረር የነበሩ የኢጣሊያ ቆንስላዎች በኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚታዘዙ ነበሩ። የአሩሲ፣ (ማጋሎ) ቆንስላን የሚቆጣጠሩ በሶማሊያ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ነበሩ።

1. Alessandro Lessona verso l' Impero p.70

የኢጣሊያ ጎላግ በቆንስላዎች አማካኝነት ለፌ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት፣ ሕዝቡ የኢጣሊያ ወረራ ደጋፊ እንዲሆን ለማድረግ፣ የፊሰን መንግሥት እንዲጠላ ማድረግ ነበረ።

ጦርነቱ ሊጀመር ከአንድ ዓመት ያለፈ ሲቀረው የኢጣሊያ ቆንስላዎችና በበታቸው የተሰማሩ የኢጣሊያ ሰላዮች ስራቸውን እንዲያጠናክሩ በተሰጣቸው መምሪያ መሠረት ኢትዮጵያ ለተወላጆች ከተፈለጸ፦ 1. በኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የሚገኙ ትግሬ፣ ሶማሌ፣ ሐረር 2. በጎንደርና በጎጃም 3. በአፋር፣ በራያና በወሎራት 4. በደቡብ ኢትዮጵያ ጋላና ሲዳማ ቅስቀሳዎች እንዲካሄድ ተደርጓል።

ቆንስላዎች ቀዉዳት ትስታ የሰጠው ምክንያት፣ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የተረገጡ ለጦርነት ከተቶ ጥሬ እቃች እስከተኛ ብቻ ያለው ሕገወ ጥሬውን ተቀብሎ መንግሥ ነው። ለ ዘመን 1927 (እስከ 1935) ጣሊያኖች በጅማ፣ ሶዶ፣ ወላይታ፣ ሀረር፣ ሰሜን ለቀምት፣ ጎሬ፣ ነቀምት፣ ጎባ፣ ጋርዱላ፣ ሞቱ፣ እንደራጃ (ሐንጋ)፣ ማጂ፣ ጋምቤላ፣ ደምቢዶሎ መቱ... የፕሮፓጋንዳ ጣቢያዎች አቋቁመው፣ በቂ ገንዘብ እየከፈሉ፣ ለዎች እየቀጠሩ ሥራቸውን ያከናውኑ ነበር።[1]

ጣሊያኖች ታዋቂ የኢጣሊያ ጎላፊዎችም በአለፍና ትስታ ሥራቸው ተካፋይ እንዲሆኑ አድርገዋቸው ነበር። በዚሁ መሠረት የአፋር አዋቂ ነው የተባለ ፍራንኬቲ ዋና በፈረስ በደቡብና ጎዳና ያደረገው፤ እፋርፊያና ወጀራት የሚያጠያይል ቀጠና የውኃ መሬ ነበር፤ ትስተባውንም ያቀረበው በአሜሪካ ሰለማን ላይ ነበር። በጎደርና በጎጃም የተደረገው የትስታ ዘመቻ የተመራው ጋስፓሪኒ (Gasparini) በተባለው የኢርትሪያ ቅኝ ግዛት ገዢ ነበር። የኢጣሊያ ቆንስላዎች በኢትዮጵያ፣ በአለፈራቸው የሥልል ድርጅቶች፣ ተጉተኛ ያለሆን፣ ወረራ አድራጊዎች እንጂ ቆንስላዎች ተብለው ሊጠሩ አይችሉም ነበር።

## የጎንደር የኢጣሊያ ቆንስላ የሥለላ ሥራ

ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ከከፈተቻቸው ቆንስላዎች ከፍተኛ ጠቃሚ የጎንደር ቆንስል ነበር። የ1928 ዓ/ም ጦርነት ከመፈንዳቱ 3 ዓመት በፊት ጀምሮ በጎንደር ቆንስል የነበረው ራፋኤል ዲ ላውሮ (Raffaele Di Lauro) በደረሰው መጽሐፍ በጎንደር ያለው የነበረ ስራ ይዘረዝራል።

1. Raffaele Di Lauro Tre Anni in Gondar p. 41



ኢውሮጳውያንን የሚጠይመሩ ኢትዮጵያውያን ኢውሮጳ ወደገኙ እንዲሰለኑ ደርሶ የነበሩ ፕሮቶ ሸዋውያን ብቻ ናቸው በማለት ቀረ ሸዋ የገጠ ጉግ በማስመሰል የኢጣሊያ የተለመደ ከፍተኛ ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ይስፋፋል።[1]

የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች የኢጣሊያ ለም መሬትን ለማግኘት የማይጠገብ ምኞታቸው በማስመሰልኩት በሰሜን ጎንደር ብቻ አንድ ሚሊዮን ከሚገኘው ህዝብ ውስጥ ጉን 2 ሚሊዮን ጣሊያኖች ማስፈር እንደሚቻል ይገልጻል።[2]

ጣሊያኖች በቅኝ ግዛታቸው ለአፍሪካውያን ዳኞች አይመደቡም ነበረ። ዋና ሀገር ገዥ እንደ የጠ/ሚ/ቤት ዳኛ የአውራጃና የወረዳ የኢጣሊያ ተስተዳዳሪዎችም እንደ አውራጃና ወረዳ ዳኞች ሆነው ይሰሩ ነበር። በጎንደር የኢጣሊያ ቆንስል ኢትዮጵያ እንደ ከፊል ቅኝ ግዛት ስለሚቆጥራት በኢትዮጵያውያን መካከል የዳኝነት ሥራ ያከናውን ነበር። መለስ መልደሚካኤል በተባለው ኢትዮጵያዊ ቆንስ በአንድ ወደ ኢትዮጵያ ለሳይንሳዊ ምርምር የመጣ፣ በጎንደር የተገኘው የፈረንሣይ ዶክተር ክርክር ተነስቶ ነበር።[3]

ቆሱ በ120 ብር የገዛው ፍሪያው የነበረና ከቤት ወፍት ከመጣ ብሎ ዓመት የሆነው ፈረስ የተባለው ነበረበ፣ በፈረንሣዮች ተቀጥር ሲሰራ ሻንበ ጊዜ ፍሪያው እንዲመለስለት ወይንም 120 ብር እንዲከፈለው በማለት ክስ ያቀርባል።

የፈረንሣዮች ዶክተሩ መሬ ግሪዮል (Griaule) የተባለው ሰው መለስ የተቀጠረው በሱዳን መሬት ከመሆኑም በላይ በእሱ ጊዜ ሽፍታ ስለሞት፣ ቢርያ መሆንም አለመቻም ስለነበረ፣ ለሙሉውን ለማትረፍ አልችልም ብሎ መልስ ይሰጣል። ለዳኝነት ሁለቱ ወገኖች ተከራካሪዎቹ ወደ ኢጣሊያ ቆንስል ያቀርባሉ። ቆንስሉም በሙሉ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ዳርቻ መብቷን ለማስከበርትና የኢትዮጵያ ስም ለማጥፋት ታደርገው ከነበረ ፕሮፓጋንዳ አንድ አካል በመሆኑ ዳኝነቱን ለማየት ፈቃደኛ በመሆን ሥራውን ጀመረ። ቆንስሉ የሁለቱ ወገኖች ሃሳብ ከሰማ በኋላ ቆሱ መለስን ፍሬንሳዊ በማድረግ ፈረንሣዮችን ከመንጂል ነፃ በማድረግ ፍርድ ሰጥቶ ይለያቸዋል።

ዲ ላውሮ በጎንደር ቆንስል ሆኖ በተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር የምትዘጋጅበት ስለነበረ ኢትዮጵያ ሲል በመቁጠት፣ ኢትዮጵያን ለማድከም ከሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያውያን ከፍለት ህዝቦች ህዝብ በዳሪዮ ጦርነት ተካፋይነታቸው አስለተኛ ስለነበረ የምትቀየረው ሁሉንም ለማስፈራራት በኢጣሊያ ላይ ጥላቻ የላቸውም በሚል ቅስቀሳ በመቀጠል፣ ለእነዚህም የሚሰጥጥ ልዩ ትስታ በጎንደር ልዩ መሥሪያ ነበረው።

1. Raffaele Di Lauro: ibd p. 185

2. Raffaele Di Lauro: ibd p. 185

3. Raffaele Di Lauro: ibd p. 185

በዚህ መሰረት በ1933 ዓ/ም ከታዋቂው ሀገረ ገዢ ከነበረው ከደጃዝማች አያሌው ብሩና ከባለቤቱ ጋር ለመተዋወቅ ወደ ወገራ ይሄዳል። ግብዣና ስጦታ ከተለዋወጡ በኋላ ቆንስሉ ወደ ጎንደር ሊመለስ ሲል አንድ ቀን ማታ ወደ ደጃዝማች ቤት ለግብዣ ተጠርቶ ሊሄድ፤ የኢጣሊያ ኃይለኛ ወይን ጠጅ ይዞ ሄዶ ስለነበረ ደጃዝማች አያሌው በርከት አድርጎ ጠጥቶ ስለነበር የሙሶሊኒ ፎቶ ግራፍ በቤቱ ግድግዳ እንዲለጥፈው እንዲሰጠው ከመጠየቁም በላይ ለሙሶሊኒ ጤንነት በመመኘት ብርጭቆውን እያነሳ ሲጠጣ አምሽቷል። ከዚህም ሌላ ደጃዝማች አያሌው ፋሽስት ለመሆን ፍላጐት እንደነበረው ገልፀውልኛል በማለት ቆንስሉ ዘግቧል።[1]

ኢጣሊያ በጐንደር ቆንስላ አማካኝነት ታካሄደው የነበረ ፖሊሲ ዘረ ሸዋ ነበረ። ሕዝቡ ለሁለት ለመከፋፈል ትሞክር ነበር፤ አንደኛው የገዢ መደብ የሸዋ ሰው ጨቋኝ፤ ሁለተኛ ጭቁኑ በጐንደር አማራ ጣሊያንን የሚወድ፤ ቆንስሉ ሸዋውያን የገዢ መደቦች ብሎ ይጠራቸው የነበረ የተማሩ ሰዎች ሁሉ፤ ወጣቶችና አስተማሪዎች ነበር። ቀንደኛ የጐንደር የኢጣሊያኖች ጠላት የሸዋ ሰው የሆነው በጐንደር ማዘጋጃ ቤት ሹም ነበረ፤ ከንቲባ ደስታ ምትኬ ይባላል። እንደዚሁም ማንኛዉም ወታደር ኢጣሊያን የማይወድ አድርጎ ይገምተው ነበር። የከንቲባው ዋና መጥፎነት ጠባዩ ኤርትራውያን ወንድሞቻችን እያለ በየአጋጣሚ ንግግር ማድረጉ ነው።

ጣሊያኖች ይጠቀሙባቸው ካሰቡት የሥለላ ዘዴዎች አንዱ ጐንደር ከኤርትራ ጋር ለማቀራረብ ንግድ ማስፋፋትና መንገድ መስራት ነበረ። የኢጣሊያ ቆንስል ከኤርትራ ኡምሐጀር እስከ ደብረታቦር ንግድ ለማስፋፋት መንገድ ለመክፈት በሚል ሽፋን ጥያቄ ለማቅረብ አንድ ደብዳቤ ለደብረታቦር አውራጃ ገዢ ለነበረ ደጃዝማች ወንደወሰን ካሣ ፅፎ ነበር። የተሰጠው መልስ ግን የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳይጠየቅና ሳይፈቅድ ጉዳዩ እንደማይፈቀድለት የሚል ነበረ። የኢጣሊያ ቆንስል ይህ አቋም የሸዋ መንግሥት ማእከላዊነት ለማጠናከር፤ የቀድሞ የሀገር ተወላጆች በአስተዳደር እንዳይሳተፉ በመከልከል የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቡ ባሕልና ማንነቱን አጥፍቶ ሸዋን ለማድረግ የሚሸረበው ሴራ ነው ብሎ ተችቶታል።

በጐንደር የኢጣሊያ ጠብ አጫሪነት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በኢጣሊያ ቆንስል ግቢ ውስጥ በአንዳንድ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጥቃት ተፈጽሞ አንድ የቆንስላው ዘበኛ ከሞተ በኋላ ነበረ። ይህ የሆነበት ጦርነቱ ከመጀመሩ አንድ ዓመት በፊት መሆኑ ነው፤ ማለት፤ ኖቬምበር 5 ቀን 1934 (ጥቅምት 27 ቀን 1927) ዓ.ም.። በጐንደር የኢጣሊያ ቆንስል እምነት ሕዝቡም ሆነ ቤተክህነት ኢጣሊያን ይወድ እንደነበረ ነው። ሀገረ ገዥዎች ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣና ደጃዝማች አያሌው ብሩም በእጁ አስገብቷቸው እንደነበረ የሚል ነበር።

1.Raffaele Di Lauro: Ibd p. 118



ፀረ ኢጣሊያ አቋም የነበራቸው 1ኛ የጎንደር ከተማ ከንቲባ 2ኛ አስተማሪዎች 3ኛ ተስፋዬ የተባለው የጎንደር ብጅሮንድ ብቻ ነበረ። በተለይ ከንቲባ የሀገር ፍቅር ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ በየጊዜው በሚያሰማቸው ንግግሮች የተቀደሰ የኢትዮጵያ መሬት በወራሪዎች አናስነካም እያለ ይቀሰቅስ ነበር። “የኢትዮጵያ አንበሳ ከዚህ ቀደም ወራሪውን የኢጣሊያ አሞራ አንድ እግሩን ሰብሮት ነበር። የኢጣሊያ አሞራ ግን ከደረሰበት ጉዳት ሳይማር ቀርቶ ሰለሞናዊውን ትልቁን የኢትዮጵያ አንበሳ ነገር በመጫር ሲፈልገው ይታያል። አንበሳው አንድ ቀን በሰላም ለመኖር የማይፈልግ የማይጠግብ የአሞራውን ክንፍ ለመስበር የሚገደድበት ጊዜ ይመጣል” እያለ ንግግር ያደርግ ነበር። ለጎንደር ህዝብ ኢጣሊያን እንዲጠሉ ያነቃቃቸው ነበር።

በጎንደር ተለምዶ የነበረ የሮማውያን የእጅ ሰላምታ መስጠት ለማስቀረት ይጥር ነበር። ዕንባ እየተናነቀው ወንድሞቻችን ኤርትራውያን እያለ ንግግር ከማድረጉም በላይ ከጣሊያኖች የከዱ ኤርትራውያን ከጎኑ ለማሰለፍ በትቶ ነበር። በጎንደር የኢጣሊያ ቆንስል ውስጥ የሚሰሩ ኤርትራውያን ላይ ከባድ ሰበካ እያካሄደ ስለነበር ቆንስላው በዓሳውርታዎች ብቻ እንዲጠቀም ተገዶ ነበር። በጎንደር የኢጣሊያ ቆንስላው ላይ የተፈፀመው ጥቃት ይመራ የነበረው 1/ የጎንደር ከተማ ከንቲባ 2/በአስተማሪዎች 3/በልጅ ተስፋዬ የጎንደር ከተማ ብጅሮንድ 4/በላይ ገ/እግዝአብሔር በሚባለው እንደቆንስሉ አባባል በድሮ ጊዜ የባሪያ ነጋዴ የነበረው ማጅራት መቺዎችን በማስከተል ነበር። በጥቃቱ ቸኮል ታዬ የተባለ በኢጣሊያ ቆንስላ ዘበኛ የወገራ አማራ ተወላጅ ተገደለ። የኢጣሊያ ቆንስል ሀገር ገዢው ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣን ወንጀለኞቹ እንዲቀጡ አስፈቅዶ በቆንስላ ግቢ ውስጥ ራሱ ከሳሽ ራሱ ዳኛ በመሆን የራሱን የሆኑ እማኞች አስቀምጦ ራሱ የመረጣቸውን ምስክሮች በራሱ ችሎት ቃላቸውን እንዲሰጡ አድርጓል። ከቀረቡ 20 ምስክሮች 13ቱ ኢትዮጵያውያን 4ቱ ኤርትራውያን 2ቱ ጣሊያኖች አንዱ ፈረንሣዊ ሚስዮናዊ ነበሩ። የነበሩ ሦስቱ እማኞች 1/ትሪቡዚዮ ዶመኒኮ (Tribuzio Domenico) 2/ባራምበራስ ዓምደሚካኤል ተስፋማርያም ማዕረባ የተወለደ 3/አቶ አፅፋሃ ወ/ሚካኤል ሠገነይቲ የተወለደ ነበሩ። ተከሳሾቹ ወንጀለኞች ቆንስሉ ሸዋውያን ብሎ የሚጠራቸው ቁጥራቸው 50 ነበሩ። ጫማቸው አውልቀው ባርኔጣ ካላቸው አውጥተው ወታደሮቹ ጠብመንጃ በቀኝ ትከሻቸው እንደያዙ እያጎነበሱ ሦስት ጊዜ ለኢጣሊያ ሠንደቅ ዓላማ ሠላምታ እንዲሰጡ ተበየነባቸው። እንደ ሀገሩ ባህል በትከሻቸው ድንጋይ እንዳይጭኑ ቆንስሉ ልዩ አስተያየት አደረገላቸው። ከንቲባው ለኢጣሊያ ባንዲራ ሠላምታ በሚሰጥበት ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጡት ኒሻኖች ደረቱና አንገቱ ላይ እንዲለጥፋቸው ተደርጓል።

ሸዋውያን ወደ መሬት ሲያጐነብሱ የኢጣሊያ ባንዲራ ሲሰቀል በሥነ ሥርዓቱ ተካፋይ የነበሩ ሦስት ጣሊያኖች ለባንዲራው የሮማውያን ሠላምታ ሰጡ። በቆንስላው ግቢ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ሴቶች የደስታ ዕልልታ አሰምተዋል። በመጨረሻም ሸዋውያን በበጎቲ ባው እየተመሩ በኢጣሊያኖች ላይ እየዛቱ፣ በመደሰታቸውም እየሳቁባቸው ከቆንስላው ግቢ ወጡ።

የግድ ሚስት ሰባቱ ልጆቿ በኢጣሊያ ባንዲራ ስር ለኢጣሊያ እንደሚዋጉ ገለጸች። ከዚህ ጊዜ በኋላ በእኛ በጣሊያኖችና በሸዋዎች መሐከል ሊደፈን የማይችል የጠላትነት ጉድጓድ ተቆፍሯል። ባገሩ በጣሊያኖችና በአገሬው የቸኩል ሀገር ሰዎች መሐከል በደም የተፈተነ የጋራ ጀግንነት ኃይለኛ ፍቅርና አንድነት ተመስርቷል በማለት አክራሪ ፀረ ኢትዮጵያ አቋሙን ገለጢል። ጦርነቱ ሊፈነዳ ተቃርቧል፣ የኢጣሊያ ቆንስል ያከናወነው የ3 ዓመት ስራው ሲገመገም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሕዝቡ ስሜት ወርንት ፈላጊ አልነበረም በማለት ደምድመዋል። ቆንስሉ ወደ ሀገሩ ከመመለሱ በፊት ደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ በቆንስሉ መጥተ ተጋብዘዋል፣ ቆንስሉም ወደ ደጃዝማች ቤት ሄዶ ምሣ ተጋብዘዋል፣ ሌሎች ከፍተኛና ዝቅተኛ ሹማምንቶችም ቆንስላ እየመጡ ቆንስሉን ያነጋግሩ ነበር።

ራስ ካሣም ቆንስሉን በየጊዜው ያነጋግረው ነበር። ራስ እምሩ ባይቀርቡ ከጐጃም ቁሊገሬም ለኮሌኛል ብለዋል፣ እንደዚሁም ደጃዝማች አያሌው ብሩ አንድ ደብዳቤ እንደፃፈለት ገልፀዋል። ከንቲባው ራሱ ቆንስላው ድረስ መጥቶ ምሣ ተጋብዟል። በወቅቱ የት/ቤት በዓል ስለነበረ ቆንስሉ ተጋብዞ መጥቶ ነበር፣ ደጃዝማች ወንድወሰንም ተካፋይ ነበረ። በበዓሉ መጨረሻ ከንቲባው ተማሪዎች ሕይወታቸው ለሀገራቸው መስዋዕት እንዲሰጡና ደማቸውን እንዲያፈሱ ምክር በመስጠት ንግግር አድርገዋል። ደጃዝማች ወንድወሰን ግን ንግግሩን ግዲመን ጠልቶ ያንቀላፋ ነበር ብሎ ፅፏል።

በመጨረሻ ጊዜያት በኢጣሊያ ቆንስላ ጊቢ ሕክምና የሚሰጥበት ቦታ ሕዝቡ እንዳይጠጋ ተከለከለ። ሸዋውያን ሹማምንቶች ጦርነት የተቃረበ መሆኑንና ኢትዮጵያ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት ድጋፍ እንዳላት የሚል ወሬ ያሰራጩ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱ ንግግር ኮፒ ጐንደር እንደደረሰ ከንቲባው በደስታ ብዛት ጠብታሪዎቹ ወታደሮችን ከኢጣሊያ ጋር ጦርነት እንገጥማለን እያሉ ብዙ ጥይቶች ወደ ሰማይ ይተኩሱ ነበር። በዚህ ወቅት ኢጣሊያ እንደ መሶሊኒ ጠንካራ መሪ ባይኖራት ኖሮ፣ ኤርትራውያን ወንድሞቻችንን ከኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ቀንበር ነፃ እናወጣቸዋለን እያሉ ከጐንደር በወሎ በኩል በደጃዝማች አያሌው ብሩ፣ ከሸሬ በራስ ሥዩም ጦር ኤርትራ ወረራዎች ይደርሱበት ነበር።

መሶሊኒ ግን ሳይቀድሙት ቀደማቸውና የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ ኤርትራ መግባት ጀመሩ። ኢትዮጵያውያን ብሪታንያ የሰጣቸው ቃል ትጠብቃለች የሚል ተስፋ ነበራቸው፣ የኢጣሊያ አምባገነን መሪ መሶሊኒም በሕዝብ ዐመጽ እንደሚገለበጥ ተስፋ ነበራቸው።



መስከረም 1928 ዓ.ም. «ሴፕቴምበር 1935» ንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡ ለጦርነት እንዲዘጋጅ የሚል አዋጅ በጐንደር ከተማ ከ30 የሚበልጡ ነጋሪቶች ድምፃቸውን እያጐሰሙ አሰሙ። በጐንደር ከተማ እደባባይ 2000 የጋሻ የሸዋ ወታደሮች ተሰብስበው የከንቲባን መምጣት ይጠባበቁ ነበር። የጐንደር አቡንም ወደ ጦር ግንባር ለሚዘምቱ ወታደሮች ቡራኬ ሰጧቸው። ከንቲባ ባደረገው ንግግር ከሚከተሉት ቃላቶች ይገኙባቸው ነበር «በባዕድ ቅኝ አገዛዝ የሚማቅቁ ውድ ወንድሞቻችን ኤርትራውያን ምን ጊዜም እንረሳቸውም፣ በቅድስት ሥላሴ ኃይል ተማምነን የተሸከሙት የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር እንደሚደመሰስ አረጋግጥላችኋለሁ።» ከንቲባው ነጋዴዎችን ለስብሰባ ጠርቶ ማንኛውም ንግድ ከኤርትራ ጋር እንዳይደረግ አስጠነቀቃቸው። በመጨረሻ ቆንስሉ ሀገሩን ለቆ እንዲወጣ ከኢጣሊያ መንግሥት ትዕዛዝ ስለተሰጠው፣ የቆንስላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለፈረንሳዩ ቆንስል አስረክቦ በሱዳን በኩል ከኢትዮጵያ ወጣ።



26. Degiac Uond Uossen, figlio di ras Cassa.

ከጀግኖች የልዑል ራስ ካሣ ልጆች በአርበኝነት ትግል ዘመን በጣሊያኖች በጭካኔ ከተገደሉት አንዱ ደጃዝማች ወንድወሰን

አራት ጣሊያኖች 52 ኤርትራውያን ሆነው በተሰነይ በኩል የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ወደሆነችው ወደ ኤርትራ ገቡ። ተጓዦቹ በኢትዮጵያ መሬት የኢጣሊያ ባንዲራ እያውለበለቡ በሚሄዱበት ጊዜ ከኢትዮጵያ መሬት ሳይወጡ የኢጣሊያ ወታደሮች ጦርነቱን በመጀመር በትግራይ በኩል የኢትዮጵያ ግዛት ድንበር ጥሰው ገብተው ነበር። ይኼ ሁሉ ሲከናወን የአፄ ኃይለ ሥላሴ አቋም ወላዋይ ነበር። በአንድ በኩል በኢጣሊያ ቆንስላ ስለተፈፀመው ድርጊት ይቅርታ እንዲጠይቅና ወንጀለኞችም እንዲቀጡ ሲፈቅድ በሌላ በኩልም ለሹማምንቶች ለቤተ ክህነት ለወታደሮችና ለቀድሞ ጀግኖች ሁሉ «አንድ ትልቅ ጠላት ኢትዮጵያን ለመውረር» የተነሳ መሆኑን የሚል መልእክት ያስተላልፍ ነበር።

አፄ ምኒልክ ጣሊያኖችን እያታለለ የጦር መሣሪያን ከጣሊያኖች እጅ እየተቀበለ የሀገሩን ጥቅም ለማስከበር ችሎ ነበር። ጣሊያኖችም በአፄ ምኒልክ ቢታለሉም ለጊዜው እነሱ እደፈለጉት መላው ኢትዮጵያን ለመቈጣጠር ባይቀናቸውም በአፄ ምኒልክ ድጋፍ ክፈል ኢትዮጵያን (ኤርትራን) በቁጥጥራቸው ለማለገባት በቅተዋል። ከኢትዮጵያ መሬት ቆርሰው ወለደው ኤርትራ ብለው የሰየሙዋት ቅኝ ግዛት ለመፍጠር በቅተዋል። ጣሊያኖች በዚሁ መሬት ሠፍረው ለ40 ዓመት ተዘጋጅተው መላው ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር እንዲችሉ በማመቻቸት ኢትዮጵያ እንደገና ለጠላት ወረራ ዳርጓት አልፏል። አፄ ኃይለ ሥላሴ ግን በሐሰተኛ የቈንስላ ሽፋን የኢጣሊያን የስለላ ድርጅቶች ኢትዮጵያ እንድትወረርና እንድትጋለጥ በመፍቀድ ጣሊያኖች ወረራቸውን እንዲያካሄዱ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ከስደት መልስም ጣሊያኖች በዓድዋ ሽንፈታቸው ቂም በቀል ተነሳስተው በኢትዮጵያ ላይ የፈፀሙት ግፍ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሊገነዘብ አልቻለም።

ክድሉ ማግበት ጀምሮ ግፈኞች ዘረኞች ጣሊያኖች ምንም ግፍ እንዳልፈጸሙ ተቈጥረው ተንደላቅቀው በኢትዮጵያ መሬት እንዲኖሩ ሲፈቅድ አንዳንድ ሐቀኛ አርበኞች ግን ላይደላቸው እየተሰቃዩ ሲያልፉ፤ አንዳንድ የዲሞክራሲ አስተዳደር እንዲመሠረት ይፈልጉ የነበሩ የሀገር ወዳጆች ከሥልጣን አግልሏቸዋል። በአንፃሩ ግን አንዳንድ ባንዳዎች ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን እንዲይዙ አድርጓቸል።

ለምሳሌነት የተጠቀሰው በጐንደር የኢጣሊያ ቈንስላ ተግባር በሌሎች ክፍላተ ሃገሮች የነበሩ የኢጣሊያ ቈንስላዎች ተግባር ከጐንደር ያላነሰ ስለላ እንዲያካሄዱ ሙሉ ነፃነት ተሰጥቶዋቸው እንደነበረ እንገነዘባለን። በጐንደር የነበረው የኢጣሊያ ቈንስል በደረሰው መጽሐፍ እንደገለጸው የጐንደርን ሕዝብ እወዳለሁ እያለ ደጋግሞ ጽፏል። የጐንደር ሕዝብ በቁንጅና፣ በሥነ ሥርዓት አክባሪነት፣ በጽዳት፣ በሥልጣኔ፣ በእንግዳ ተቀባይነት ከኤርትራና ከትግራይ ሕዝብ ይበልጣል በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል። የጐንደር ሕዝብ እንግዳ ተቀባይነት ከጣሊያኖች ያለገኘለት ውጤት በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ሥር በወደቀበት ዘመን ታይቷል። ከጣሊያኖች የተዘጋጀለት ድግስ ውርደትና ባርነት ብቻ ነበር። ኤርትራውያን



በስማቸው እንዲጠሩ ሲፈቀድላቸው የጐንደር ሕዝብ ግን ጐንደሬ ነኝ፣ አማራ ነኝ ብሉ እንዳይጠራ ተከልክሉ እንዲጀና ተብሉ ብቻ እንዲጠራ ተደርጉ በመጨረሻም እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ መሬቱን ለጣሊያኖች እየለቀቀ ከምድር ገጽ እንዲጠፉ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ዓላማ ነበር።

የኢጣሊያ ቈንስላዎች ሥራ ውጤት አልለጠም ለማለትም አይቻልም። ጣሊያኖች እንደተመኙት ማንም ተዋጊ የኢትዮጵያ ጦር ሳይገጥማቸው እየዘፈኑ አዲስ አበባ እንዲገቡ ባይሳካላቸውም ራስ እምሩ በጦርነቱ ጊዜ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ (የጐጃም ሕዝብ በጣሊያኖች ላይ ለመዝመት ፍቃደኛ አለመሆኑን) በመግለጽ የጻፈው ደብዳቤ የኢጣሊያ የስለላ ድርጅቶች ጥረት ሙሉ በሙሉ እንዳልከሸፈ እንረዳለን።

# በትግራይ የኢጣሊያ የስለላ ሴራ

ጣሊያኖች በዐድዋ የደረሰባቸው አሳፋሪ ሽንፈት ለመበቀል መሪያቸው ራሱ የጦርነቱ መጀመር ለማብሰር ባደረገው ንግግር ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለመጀመር 40 ዓመት እንደተዘጋጀች ገልጿል። በሌላ በኩል ግን ጣሊያኖች ለጦርነት እንዳልተዘጋጁ በማስመሰል በጐንደር የኢጣሊያ ቈንስላ ላይ ያደረሰው አደጋና በኦጋዴን ወልወል በተደረገው የወሰን ግጭት ተደምሮ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል ለተደረገው ጦርነት መንስኤ ሆኗል በማለት ለጦርነት ምንም ዝግጅት ያላደረገች ኢትዮጵያ ላይ ጠብ አጫሪነት በመለጠፍ በመላው ዓለም ዜናውን አሰራጭተው ለማወናበጃ ተጠቅመውበታል። በሁለቱ ቦታዎች የደረሱ አደጋዎች ግን ሆን ተብሎ በኢጣሊያ የስለላ ድርጅቶች የተቀነባበሩ የጠብ አጫሪነት ድርጊቶች መሆናቸው ለማንም ግልጽ ነው። በጐንደር የኢጣሊያ ቈንስላ የፈጸመው የስለላ ሥራ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሲመስል ዐድዋ ላይ የነበረው የኢጣሊያ ቈንስላ የስለላ ሥራ ከጐንደር የባሰ እንጂ ያነሰ አልነበረም። ትግራይ ምን ጊዜም ለኢጣሊያ ወረራና ጥቃት ግንባር ቀደም ቀማሽ እንደመሆንዋ መጠን በዚሁ ወቅትም ጣሊያኖች ትኩረታቸውን ያሳረፉባት ክፍለ ሃገር ነበረች። ከጦርነቱ በፊት የነበሩ ዓመታት ለምሥራቅና ለምዕራብ ተብላ ተከፍላ በትልቁ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጆች ትስተዳደር ነበር። የምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ገዥ የነበረው ተቀማጭነቱ መቀሌ ሆኖ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ራስ ጉግሳ ነበር፤ በኋላም እሱ በበሽታ ሲሞት ልጁ ኃይለ ሥላሴ ተተከቶ ነበር። የምዕራብ ትግራይ ሀገረ ገዥ የነበረው ተቀማጭነቱ ዐድዋ ላይ ሆኖ ሌላ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ራስ ሥዩም ነበር።

በትግራይ የጣሊያኖች የስለላ ዒላማ ወድቀው የነበሩ በጣሊያኖች ሳይቀር «ለጀንዳሬ» ተብሉ ይጠራ የነበረው የዝነኛው የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጆች በማይታመን ሁኔታ በጣሊያኖች

ተሰብስው የጣሊያኖች ባንዳ ሊሆኑ ችለዋል። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ የጉግሣ ነገሥት የአፄ ኃይለ ሥላሴ ልጅ የዘበወርቅ ባል ነበር፤ የእርእሶ ሥላሴ የአፄ ዮሐንስ በኩር ልጅ የልጅ ልጅ ነበር። እርእሶ ሥላሴም የአፄ ምኒልክ ልጅ የንጉሠ ነገሥታት ዘውዲቱ የመጀመሪያ ባለቤ ነበረ። ይህ ሁሉ የንጉሥታት ዝምድና ያለው ሰው ሀገርን በመክዳት የፋሺስት ኢጣሊያ ባንዳ በመሆን በታሪክ ተመዝግቧል። ጣሊያኖች ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ሊያታልሉ የቻሉት እቴ ተከለሃይማኖት መኩሪያ እንደጻፈው የመላው ትግራይ ገዥ እናደርጋለን በማለት አልነበረም። ከኢጣሊያ ድል በኋላ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ቦታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስተተን እናስቀምጣለን! የአፄ ዮሐንስ ዝና እንደገና ታድሶ ሊፈጠር የሚችለው በኢጣሊያ እርዳታ ብቻ ነው በሚል የሐሰት ስብከት ነበር በመታመኛቸው እንዲገባ ያደረጉት። በእጃቸው ካስገቡት በኋላ ግን ኀፈኞቹ ጣሊያኖች እንኳንስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሊያደርጉት ትግቁን በሙሉ አስፈትተው የአንድ የኤርትራ ምክትል ወረዳ የሺመኛና 100 ሰው የማይሞሉ ባንዳዎች አዛዥ ሹመት ሰጥተው የመንገድ መሪ እንዲሆን አደረጉት። የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ክህደት ብቻው ተነጥሎ የሚታይ ክስተት አይደለም፤ የአባቱ የራስ ጉግሣና የሚስቱ ዘበወርቅ እጊጊት ድራማ ትራጀዲ እሱም ተያያዥ እንዲሆን ጣሊያኖች በሕክምና ሽፋን የፈፀሙት ሴራ ውጤት ነው። ራስ ጉግሣ ለብዙ ጊዜ በመቀሌ በሕመም ይሰቃይ ስለነበረ ዐድዋ የሚገኘው የአጉቱ ልጅ ራስ ሥዩም (ምናልባት በጣሊያኖች የተቀነባበረ ሴራ ሊሆን ይችላል) ፒየር ሎኮ (Piero Locco) የተባለው ኢጣሊያዊ ሐኪም ከዓድዋ ወደ መቀሌ ሄዶ ሕክምና እንዲያደርግለት ለጣሊያኑ ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ጥያቄ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር የመጨረሻ ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት ስለነበረ ዓላማቸውን በሥራ ላይ ለማዋል የተመቻቸ ሁኔታና ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። ራስ ጉግሣ የሚያሰቃየው በሽታ በሳንባ ነቀርሳ ነበር።[1] በዘመኑ ለሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚሰጥ ህክምና አልነበረም። በወቅቱ የኢውሮጳውያን ሐኪሞች የነበራቸው እምነት ግን የሰሜን ሀገር አየር ለበሽታው ፈዋሽነት ጠቃሚነት አለው ይባል ስለነበረ፤ ራስ ጉግሣ በጣሊያኖች ምክር በአሥመራ በኩል ወደ ስዊስ ሀገር ሄዶ ለመዳን ፍላጎት አድርጎበት ነበር። ቢተከሆነት ራስ ጉግሣ ወደ ስዊዝ እንዳይሄድ እያለ ብርቱ ተቃውሞ ሲያደርግ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ግን እንዲሄድ ሲፈቅድ በኤርትራ ቆይታ ሳያደርግ በቀጥታ ወደ ግብጽ እንዲያመራ ነበር ትዕዛዝ የሰጠው። የኢጣሊያኑ ሐኪም ዓላማውና የተሰጠው ተልእኮ ከሕክምና ይልቅ በፖለቲካ ያዘነበለ ስለነበረ፤ ራስ ጉግሣም በበሽታ ድካም ስለነበረ የሐኪሙ ጥረት ራስ ጉግሣን ሳይሆን ለጣሊያኖች ፕሮፓጋንዳ ጥቅም ሲባል ወደ ኤርትራ መሬት ለማድረስ ብቻ ነበር። በዚሁም መሠረት በመንገድ ላይ እንዲሞትበት በታሪክ እስከ ኤርትራ መሬት እንዲወሰድ አደረ።

1. Arnaldo Cipolla Abissinia in Armi p.186



የሐኪሙ ትእዛዝ በታሪክ የመዘከም ከቤተ ክህነትና ከሕዝቡ ብርቱ ተቃውሞ ስላነጠመው ራስ ጉግሣ ለመዳን ለነበረው ጉጉት ለማክበር ሲል በበቅሎ ጀርባ ወጥቶ በእጃቢዎች ተከቦ ከባዱ ጉዞ ከመቀሌ ለመቀጠል ተሰማራ። በዚሁ ጊዜም የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሚስት ዘበወርቅ የሰባት ወር ነፍሰ ጡር የነበረች ታመመች። ባለቤ ጣሊያኑ ሐኪም በሕክምና እንዲረዳት ይለምነዋል። ጣሊያኑ ሐኪም የልዕልቲቱ የበሽታ ዓይነት በእንግሊዝኛ ቃል ኒዩሞኒያ (Pneumonia) መሆኑን ለባለቤ ይገልጽለታል። በሐኪሙ ግምት ትክክል ሊሆን የሚችል ቢሆንም ከራስ ጉግሣ የተላለፈባት የሳንባ ነቀርሳ ሊሆን የሚችል ነበር። ሁለቱም በሽተኞች በሕክምና ለመርዳት የነበረው ዕድል በዚያን ጊዜ እንኳንስ በዐድዋና በመቀሌ በሌላ በሰለጠኑ ሀገሮችም በጣም ውስን ነበር። ቄሶች ሐኪሙ የሰጣት መድኃኒት እንዳትወስድ ከለከሏት። በተለይ የነፍስ አባትዋ ከሸዋ የመጣ ቄስ ሐኪሙ ጣሊያናዊ በመሆኑ እሱ የሚሰጣት መድኃኒት እንዳትወስድ ከለከሏታል፤ አፄ ኃይለ ሥላሴም በእሱ የሚሰጠ እንደሚሰጣት አርግጠኛ ነኝ ብሎ ያምራ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ግን በስልክ ተጠይቶ ሐኪሙ የሚሰጣት መድኃኒት እንድትቀበል አስተያየቱን ሰጥቷል። ጣሊያኑ ሐኪም ባለቤትዋ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና ቄሶች በጥርጣሬ ሲመለከቱት ራስ ጉግሣ ግን ቢሐኪሙ እምነት ነበረው። በዚሁ ጊዜ ሐኪሙ ከአዲስ አበባ ሌላ ሐኪም እንዲላክ ብሎ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት የንጉሡ ግብፃዊ ሐኪም በአሮፕላን ከሁለት ወር በኋላ ተላከ። እሱም ጣሊያኑ ሐኪም ሕክምናው እንዲቀጥል ብቻ ከማድረግ ሌላ እርዳታ አልሞከረም። ከትንሽ ቀን በኋላ ግን ዘበወርቅ ባለቤትዋንና ቤተክህነትን እየተቀበች ዐረፈች። አስከሬንዋ ልዩ አሮፕላን ተልኮ ወደ አዲስ አበባ በሚወሰድበት ጊዜ ራስ ጉግሣ በሽታ የጠናበት በሞት አፋፍ የሚገኝ የነበረ ቢሆንም. በአሮፕላን ማቢያ ተገኝቶ የአስከሬኑ አሸኛኘት ተካፋይ ነበር። በሌላ አሮፕላን ተሳፍሮ ባለቤትዋም ወደ አዲስ አበባ ለቀብር ሥነ ሥርዓት ሄዷል። የልዕልት አስከሬን ወደ አዲስ አበባ እንደሄደ ራስ ጉግሣ የአስተዳደሩ ኃላፊነት ለልጁ ሰጥቶ ጉዞውን በበቅሎ ወደ ኤርትራ አመራ፤ በአስራ ሰባት ቀን ጉዞም ዓዲግራት ደረሰ።

ራስ ጉግሣ በጉዞ ጊዜ ሁል ጊዜ ለጣሊያኑ ሐኪም ያካፍለው የነበረ [illegible] ጣሊያ ጋር ለመቀራረብ ያለው ፍላጎት በመግለጽ ነበር። ለኢጣሊያ መንግሥት እጁን ለመስጠት ፍላጎት እንዳለው ይገልጽለት ነበር። ይህ አስተሳሰብ ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣበት ነው፤ ምክንያቱም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፀረ–ኢጣሊያኖች አቋም ነበረው ብሎ ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛና ደራሲ ቺፖላ (Cipolla) ጽፏል። ጣሊያኖች ስለ ቤተሰቡ ያላቸው በጐ አመለካከት ለላየ ነው ሃሳቡን ቀይር የአፄ ዮሐንስ ቤተሰብ ! ለአፄ ምኒልክ እንደ ቀና ሁሉ! ከጣሊያኖች ጋር በመስማማት ብቻ ነው ሥልጣን መያዝ የሚችለው በሚል ግምት የደረሰ። የትግራይ ሕዝብ ግን በራስ ጉግሣ አስተሳሰብ እንደማይስማማ ማስረጃ ሆኖ ቢጠቀስ የአጉቱ ልጅ ራስ ሥዩም በአንድ ወቅት የሰጠው ምክር የመላው ትግራይ ሕዝብ አስተሳሰብ በአጭሩ

የሚገልጽ ነው። «በእግዚአብሄር እጅ እንደወደቅህ እየመሰለህ ለምን በጣሊያኖች እጅ ትወድቃለህ?» በማለት ምክሩን ለግሷል።

ዓዲግራት እንደደረሰ ራስ ጉግሳ በጣም ስለደከመ በሐኪም ትእዛዝ እረፍት ሆነ፤ ሕዝቡም ወደ መቀሌ እንዲመለስ ከመጠየቅ አላረፈም ነበር። የሐኪሙ ጥረት ኤርትራ ቅኝ ግዛት ለማድረስ የድካሙ ዋጋ ሹመት ከኢጣሊያ መንግሥት ለማግኘት ነው እንጂ ስዊሥ ሀገር የሚደርሰ በሽተኛ ይዞ ይጓዝ እንደነበረ ሕሊናው ያውቅ ነበር።በመጨረሻ ግን ራስ ጉግሳ የኤርትራ ወሰን ሊደርስለት እንደማይችል ግልጽ እየሆነ መጥቷል፤ ቀስ በቀስ እየደከመ ይሄድ ጀመረ። ይኸም ሆኖ ግን ራስ ጉግሳ ሐኪሙ በሚሰጠው መድኃኒት እንደሚድን ከንቱ ተስፋ ነበረው። ሐኪሙ ግን ራስ ጉግሳ ጉዞውን ለመጠቀል ዐቅም እንደሌለው ተረዳ። ለቅርብ ዘመዶችና አጃቢዎች ብዙ ቀን በሕይወት እንደማይኖር ነገራቸው። እነሱም ወደ መቀሌ የመልስ ጉዞ በቃሬዛ እንዲጀመር ሐኪሙ ለራስ ጉግሳ እንዲነግረው ቢጠይቁት ለመናገር ስላልፈለገ ራሳቸው መናገር ግድ ሆነባቸው። ራስ ጉግሳም ጉዳዩን ስለተረዳ ወደ መቀሌ ለመመለስ የፈቀደ መሆኑን ገለጸላቸው። ሁሉም መቀሌ በሕይወት እንደማይደርስ ገምት ነበራቸው። ራስ ጉግሳ ብቻ ተስፋ ባለመቁረጡ ዶክተሩን አስጠርቶ መቼ ነው ወደ አስመራ ጉዞ የሚጀመረው ብሎ በጠየቀው ጊዜ ለጊዜው ዕረፍት እንዲያደርግ ብሎ ሲነግረው ለዘለዓለም ዕረፍት ማለትህ ነው? ብሎ መልስ ሰጠው። ከዚያ በኋላ እያዘነ ወደ መቀሌ ጉዞውን ለመቀጠል ተስማማ። ጣሊያኑ ሐኪምም ወደ ኤርትራ በማምራት ለሦስት ወር አንድ ላይ ከኖሩ በኋላ ተለያዩ። ራስ ጉግሳ ራሱ ሊፈጽመው ያተደ ክህደት ልጁ እንዲፈጽመው መገፋፋቱ ግልጽ ነው። ስለዚህ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ ነው ክህደት የፈፀመው ራሱ የክህደቱ አመንጪ አይደለም።

በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ እላይ እንደተገለጸው ለሁለት ጉራ የእጌ ዮሐንስ የልጅ ልጆች ተከፍላ ትገኝ ነበር፤ 1ኛ ራስ ሥዩም ለማእከላዊ መንግስት ታማኝ በኢጣሊያኖች ላይ የማይታረቅ ጥላቻ የነበረው 2ኛ የራስ ጉግሳ ልጅ ከሃዲው ኃይለ ሥላሴ የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ደጋፊ። የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ክህደት ከሁሉ የከፋ፤ የኢትዮጵያ ስም በዓለም ፊት ያጠፋ ፤ኢትዮጵያ በዓለም ፊት በሀፍረት እንድትሸማቀቅ ያደረጋት የኢጣሊያ የስለላ ድርጅት ውጤት ነው። ሌላ ተራ ሰው ኢትዮጵያዊ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ባንዳ ቢሆን ባላስገረመ ነበር። የጀግናው የእጌ ዮሐስን 4ኛ የልጅ ልጅ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ተባባሪ መሆን ግን ለማመን የሚያዳግት ዜና ነው። ዋናው የክህደት ምንጩ ግን ከወጣቱ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሳይሆን ከአባቱ ከራስ ጉግሳ ነው። እቶ ተክለ ፃድቅ በጻፈው ታሪክ እንደ ገለጸው አፄ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ክህደት መረጃ ይደርሰው ነበር። የአባቱ የራስ ጉግሳ ክህደትም የአፄ ኃይለ ሥላሴም ሆነ ለአፄ ምኒልክ ይደርሳቸው እንደነበረ አያጠራጥርም። ስለዚህ ክህደቱ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በጐጃሙ ራስ ኃይሉ ላይ



እንደተደረገ ሁሉ ከሥልጣን አውርደው መታሰር ሲገባቸው የኢትዮጵያ ስም በመላው ዓለም በመጥፋቱ ሁለቱ ነገሥታትና ሌሎችም የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች በኃላፊነት የሚያስጠይቃቸው ይሆናል።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ከነፃነት በኋላ በእስር ቤት በመማቀቅ ክህደቱን በሞት ሕይወቱ ከፍሏል፤ለክህደት ያበቁት ከኢጣሊያም ሆነ የኢትዮጵያ ወገን ወቀሳ አልደረሰባቸውም። በተለይ 40 ዓመት ተዘጋጅተን ልናጠፋችሁ መጥተናል ብለው የሚፎክሩ ጣሊያኖች አፄ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ ሀገሩ ሲመለስ በይቅርታ አልፏቸዋል። በይቅርታ የሚታለፍ ግን ወጣቱ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ነበር፤የገፈፏች የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች አልበሩም።

## በጐጃም የኢጣሊያ ቈንስላ

የኢጣሊያ የስለላ ዒላማዎች ከሆኑ የኢትዮጵያ መሪዎች አንዱ የጐጃሙ ሀገረ ገዥ ራስ ኃይሉ ነበረ። ከጣሊያኖች ጋር ግንኙነት የፈጠረው ጉጃም ከሚገኘው የኢጣሊያ ቈንስላ፤ እንደዚሁም አዲስ አበባ በኢጣሊያ ኤንባሲ በኩል ብቻ ሳይሆን ራይሞንዶ ፍራንኬቲ በተባለው የኢትዮጵያ አፋር ግዛት ለማጥናት በሚ.ል.ሹሩን ለስለላ ሥራ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ሰፊ ድጋፍ ያገኘው ነበረ። በጣሊያኖች እምነት ራስ ኃይሉ በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ጣሊያኖችን በተዘዋዋሪ ለመርዳት ብሎ ከአፄ ምኒልክ ጐን ለመሰለፍ አልፈለገም። ራስ ኃይሉ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1922 ዓ.ም 90.000 ብዛት የነበረው ወታደር ነበረው።

ሠራዊቱም በማእከላዊ መንግሥት ላይ ዓመጽ ለማስነሳት የሳብ እንደነበረውና የጦር መሣሪያ ግን ስለሚያጥረው ከኤርትራ ጣሊያኖች የጦር መሣሪያና ገንዘብ እንዲልኩለት ይጠባበቅ ነበር። ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ከማእከላዊ መንግሥት የተሰጠው ተደጋጋሚ ትእዛዝ ችላ በማለት ከዘገየ በኋላ፤ የጐንደር ሀገረ ገዥ ከነበረው በማእከላዊ መንግሥት ላይ ዐምጾ ከነበረው ከራስ ጉግሳ ወሌ ለማበር የነበረው ዓላማ ራስ ጉግሳ ተሸንፎ በመገደሉ ስለከሸፈበት የኢጣሊያ ኤምባሲም በሰጠው ምክር መሠረት ወደ አዲስ አበባ አምርቶ እጁን ለመንግሥት ሰጠ። ራስ ኃይሉ የግሪጎሪያዊ ዘመን አቆጣጠር 1927 (በኢትዮጵያ 1919 ዓ.ም)በራይሞንዶ ፍራይንኬቲ አማይነት ለኢጣሊያ አንባ ገነን መሬ ለመሰሊኒ ባለ ወርቅ ጐራዴ በሚሰጢር ሲልክለት ጐራዴው በኢትዮጵያ የታወቀ ስለነበረ ኃይለ ሥላሴ እንዲያውቀው በርማ ከተማ መንገድ መሶሎኒ ታጥቆ እንዳይሄድ አደራ በማለቱ የኢጣሊያ ጸሐፊዎች በማፈዝ ገልጸውታል። ራስ ኃይሉ አዲስ አበባ እንደሄደ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ አልተፈቀደለትም። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከማወጁ በፊት ጣሊያኖች ሁሉም

የኢትዮጵያ ሀገር ጀግኖች እንደ ደጀኖቻቸው ኃይለ ሥላሴ ለማድረግ እንደ ሊያደርጉትም
በደል የነበረው የኢጣሊያ ፋሽስት ወታደር ሲያገኙ የነው ሀገር ገዥ አቤል አለቃ ወራሽ
በመሆኑ ጣሊያኖች ያደረጉት መከራ ሊቋቋሙት አልቻሉም። ሆኖም ራስ በኢትዮጵያ ምድር
ላይ እንዲያገኙ በማድረግ እንደ መሪያቸው ሊመቱሙቸው ችለዋል። ከራስ መሪዎች
ለማሸነፍ መንግሥት ከማይታወቁ ከበሩ እንዲ ከጉዳዩ የራስ ኃይሉ ልጅ እንዳልቸ የነበረ
ግዛትና አለቃ ደጀኖቻቸ አለሩ ነበሩ። ሌሎች የራስ አሉ መሪዎች እባይ ወዲ የደጀኖቻቸ
አበራ የመንደም ልጅና ገብሬ ተድላ የተባሉ በሕዝብ ተደግፈው የነበሩትም ነበሩ። የፈረር
ሀገር ገዥ የነበረውም ለቁል መንገን ስለነበረ ጣሊያኖች ለከሁደት የሚተባበሩቸው
አልነበሩም።

በእነዚህ ሊታይ ታፍራና ተከብራ በውጭ ሀገር ስምችለምብም የማት ታወቅ
የነበረች ኢትዮጵያ በአንድ ኃይለ ሥላሴ ቸልተኝነት ለኢጣሊያ ወረራ ተጋለጠና ተመቻችታ
እንደነበረች እንረዳለን። በወረራ ወቅት ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ በልጣ የተገኘችው በጦር
መሳሪያ ብልጫ ብቻ ሳይሆን በሰው ኃይል ግዝፈት ሚሊዮን ከነበረው የኢጣሊያ ጦር
ኢትዮጵያ አንድ ሚሊዮን ሊገኝት ከኢጣሊያ ጦር በቁጥር በጣም ያነሰ ነበር።

ከስደት መልስ በኋላ እነ ኃይለ ሥላሴ የኢምፔርያል ንጉሣዊ አገዛዝ ለምድ የተሰጠ
እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ የነበረው ረጅም ንጉሣዊ አገዛዝ ተስ በተስ ወደ ሕገ
መንግሥታዊ አገዛዝ እንዲተካ ባለመፍቀዱ የራሱና የመራቾቹ ልጆቹ ጥቅም ከመታጉም
በላይ የመንግሥት ለውጥ በኃይል በመጣ እንደ ከፍተኛ ምክንያት ሆኗል፤ ይኸም ለሀገሪቱ
ጥቅም ሳይሆን ጉዳት ነው ያስከተለው። የሚያስረዳን የሆኑት ታሪኮችን ስንከተል ነው።
የኢትዮጵያ መሬት የነበረው ንጉሣዊ አገዛዝ ተመቻች በሌላ አስተዳደር ሲተካ ያመጣው
መጥፎ አለታየም! ለውጡም የመጣው በሕዝብ ጥያቄ ሳይሆን በጥቂት ግለሰቦች ስለነበረ
እስከአሁኑ አመጣጡ ነው።

# የሙከራ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ

ጣሊያኖች ደግሞ ኢትዮጵያን ከመውረር ሊቆጠቡ የቻለው ለምንድን
ቁሊርቀኛ ፋሺስታዊ አገዛዝ በጣም ዘመን ነበር። ፋሺስታዊ አገዛዝ የሕዝብ አረመኔያዊ
ሰዎችን እየተረዳ ሰማይን በመከተል ጣሊያኖች የሌላቸው መሬት ትና የኃይል ሚዛን አጋና
እያዩ 1000 ዓመታት በላይ በመንግሥትነት የኖሩ ከታላቋ ብሪታንያና ከፈረንሳይ እኩል
እንዲሆኑ እንዲያውም የሮማውያን ልጆች ነን እያሉ በማለት እንደሚበልጡዋቸው
ሊስብቸው በብር ዘመን ነበር። የዐድዋ ጦርነት ሽንፈት ያስከተለባቸው ድንጋጤ ምን
ጊዜም ሊያገጥመ በማይችለው ውርደት ስለነበሩ ለዚህም በቀል ጦርነት ለመክፈት ጣሊያኖች
ቆቅ አልነበሩም። ሆኖም በራሳቸው ወታደሮች ሳይሆን በቅጥር ግብታቸው ባለተለም






Il Ras Gugsa Olié. — [illegible]

ወታደሮች የሚተማመኑ ጥቂት ግለሰቦች በተለይ በኤርትራ ብዙ ዓመት የኖሩ ጣሊያኖች በአነስተኛ ኃይል ኢትዮጵያን ወረው ለመያዝ እምነትም ፍላጐትም የነበራቸው ነበሩ። በ1922 ዓ.ም (1929–30) በኤርትራ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች አማካይነት በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ በማእከላዊ መንግሥት ዐመጽ እንደ ተነሳና የእርስ በርስ ጦርነት እንዳለ በማስመሰል ሐሰት ወሬ በሚነዙበት ወቅት የኤርትራ ሀገረ ገዥ የነበረው ኮራዶ ዞሊ እንደጻፈው ኢጣሊያ የቅኝ ግዛትዋ ኤርትራን ጸጥታ ለማስከበር በሚል ሰበብ በአነስተኛ የጦር ኃይል ጣልቃ በመግባት ትግራይንና አግራን፣ ሰሜን ኢትዮጵያን፣ ጐንደርን፣ ወሎንና ላስታን የሚያ ጠቃልል በአመፅ ለማነሳሳት ቀጥሎም ሸዋንና የቀሩት የኢትዮጵያን ክፍላተ ሀገሮችን አሸንፎ ንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣን አውርዶ የኢትዮጵያ ግብቲያ ለማፋጠን ይቻል ነበር ካለ በኋላ ይኼን ለማድረግ ምክንያት ሆኖ መቅረብ ያለበት 1ኛ ኢትዮጵያ ከጐረቤት ግዛቶች ጋር የገባችበት ውሎች የማታከብር በመሆኗ 2ኛ ያሉባት የውስጥ ብጥብጦች ለጐረቤት፣ለኤርትራ አሳሳቢ እየሆኑ በመምጣታቸው የኢጣሊያ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ሕጋዊ ያደርገዋል ብሎ ነበር። የቀረበው ሃሳብ አዲስ አበባ ከሚገኘው የኢጣሊያ ኢንባሲም ሆነ ከኢጣሊያ መንግሥት ድጋፍ ስላላገኘ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። የኢትዮጵያ የኢጣሊያ ወረራ ሥጋት መኖሩንና ለመከላከል አነስተኛ ዝግጅት ማድረግ የጀመረችው ጦርነት ከመጀመሩ ሁለት ዓመት በፊት ብቻ ነበር፤ በዚሁ ጦርነት ሊጀመር ሲል ለሀገሩ እውነተኛ ተቆርቋሪ የኢጣሊያ ሃቀኛ ጠላት ብለው ጣሊያኖች ያምኑበት የነበረ ራስ እምሩ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በጻፈው ደብዳቤ ከኢጣሊያ ወረራ ለመከላከል እንዲቻል ኢትዮጵያ ቢያንስ ሁለት ዓመት ጊዜ እንደሚያስፈልጋት ብሎ ነበር። ኢጣሊያም ለም የኢትዮጵያ መሬትን ለመውረር እንደ ዐድዋ ጦርነት ጊዜ ሽንፈት ሳይገጥማት ምን ያህል ወታደር ማሰለፍ እንደሚያስፈልጋት ግምገማ አድርጋ ደፍራ ጦርነቱን ለመጀመር 40 ዓመት ፈጅቶባታል። ወደ መጨረሻ ግን ጣሊያኖች ኢትዮጵያም የመከላከያ ኃይሏን ማደራጀት መጀመሯን ስለተረዱ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛታቸውን ለማድረግ አሁን ካልቻሉ አጐራባች ቅኝ ግዛቶቻቸውንም ጭምር የሚያጡበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ስለተገነዘቡ «አሁን ወይንም ምንጊዜም» በሚል መፈክር ተነሳስተው ለመውረር ዝግጅታቸውን ማፋጠን ተያያዙበት።

ኢትዮጵያንም ለመውረር ምን ያህል የጦር ኃይል እንደሚያስፈልጋቸው ግምገማ ማድረግ ስለነበረባቸው ኢትዮጵያ ምን ያህል የሰው ኃይልና መሣሪያ እንዳላት ለማወቅ የተጠቀሙበት ዘዴ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ እንደመጣ በማስመሰል እርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ አድርገው ኃይሏን ለመገምገም ነበር። በዚሁ መሠረት በኤርትራ ቅኝ ግዛታቸው ሀገረ ገዥ ኮራዶ ዞሊ አቀነባባሪነት ሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ ጐንደርና ወሎን የሚያጠቃልል በማይታይ ጠላት እንዲዘምቱ የጦር አውድማ አደረጓት።





...... በጣሊያኖች ግምት የዘቢጥ ጦርነት
ጉግሣ ወሌ ወደ ዘቢጥ ጦርነት ሲነሱ



Il Ras [illegible] quando partiva per la rivoluzione che gli [illegible]
Il seguito dei suoi preti e dignitari.

ማሊያኖች የኢትዮጵያ መንግሥትን እያታለሉ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ብጥብጥ እንዲነሳ ማድረግ የቻሉት የአፋሮች ዕንባ ጠባቂ በመምሰል አፋሮች ከደጋ የትግሬዎችና የወሎ ከፍላተ ሃገሮች የከብት ዘረፋ፤ የሰው መግደል እየደረሰባቸው ነው ብለው ወሬ መንዛት የጀመሩ ከአንበት 1928 ዓ.ም ጀምሮ ነበር። በዚህ ጊዜ የወጀራት ሰዎች ወደ በሩ የአፋር ሱልጣን ግዛት ዘልቀው ንብረቱ ብዙ ከብቶችን ሰርቀው ስምንት አፋሮችን ገድለዋል የሚል ዜና ያሰራጫሉ። የመጀመሪያ ኢላማቸው የሆነው የኢትዮጵያ ባለሥልጣን የአንጻ መሆኒ፡ ጨርጨር፡ ተሩ፡ በሩ፡ ሀገረ ገዥ የነበረ ደጃዝማች አበራ ተድላ ነበር።[1]

በዚህ ዓመት አክቶበርና ኖቬምበር ወር 2000 ሺህ የሚሆኑ የደጋ ሰዎች ዘራፊዎች 8000 ከብቶችን ሰርቀው ሲያመልጡ ከደጃዝማች አበራ ጦር ጋር ተጋጭተው ከሁለቱ ወገኖች 500 ሰዎች ሞቷል የሚል ወሬ ማሊያኖች ባሰራጩት ዜና በመመሪት የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት ዘራፊዎችን ለመግታት ብሉ በተኛዝማች ፍትረ ማርያም የሚመራ ጦር ከወሎ ወደ ሥፍራው ይላከል፤ በዚሁ ጊዜም የምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ገዥ የነበረው ደጃዝማች ጉግሳ አርአያ በሸፍትነት ስለተጠረጠረ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ታዘዘ።[2] ሌሎች ብዛት ያላቸው ዘራፊዎች ከራስ ጉግሳ አርአያ ጋር ደጃዝማች አበራ ተድላ ከዋግ ሹም ከበደ ጓንጉል ግዛቶች እየተነሱ ወደ አፋር ዘልቀው ዘረፋና ግድያ እየፈጸሙ የሚል ወሬ ያሰማል። ማሊያኖች ዓላማቸው ተሳካላቸው። በማሊያኖች ዝርፊያና ግድያ የተፈጸመ ናቸው፤ ብሎ ያስመሰከረ ሲያናፍሱ፤ በኢትዮጵያ ወገን እዚ ኃይለ ሥላሴም ሆነ ሌሎች ሹማምንቶች ሀገሩ ሰላም እንደሆነና የሚወሩ ዝርፊያዎችና ግድያዎች ድርም የተለመዱ ናቸው እያሉ መልስ ይሰጡ ነበር። ደጃዝማች አበራ ተድላ የሚያደርገው ሲያጣ፣ ወቀሳ ሲበዛበት በሁኔታው የሌሎች ሹማምንቶች ትብብርና እጅ እንዳለበት ስለጠረጠረ በአዲስ አበባ ለሚገኘው የኢጣሊያ ኤምባሲ ጽሕፈት ለገነው እንዲያስረዱ ይለምናል።[3]

ማእከላዊ መንግሥት ራስ ጉግሳ አርአያ በግዛቱ ዝርፊያውን ለመቆጣጠር ባለመቻሉ 5000 ሺህ ብር ይቀጣል። ለአፋር ሕዝብ ተቆርቋሪ የሚመስሉ ማሊያኖች የበሩ ሱልጣን ለተፈጸመበት ዝርፊያ እጁ በመመለስ የተመሰፈበት ከብቶች በሙሉ እንዲመለሱ ብለው ወሬ ያሰራጫሉ። ራስ ጉግሳ አርአያና ዋግ ሹም ከበደ ከዘራፊዎች ጋር ውስጥ ለውስጥ የሚተባበሩ መሆኑን እንደሚጠረጥሩት ለደጃዝማች አበራ ተድላ ላይ ለመንግሥት ክስ ያቀርባሉ።[4]

1.Corado Zoli Ibd p.278

2_Corado Zoli Ibd p.256

3_Corado Zoli Ibd p.257

4_Corado Zoli Ibd p.258



የራስ ከበደ መንገሻ አቲከም የቢታች ሹም በሚመሩ 500 ወታደሮች ከሽፍቶች ጋር ውርትት ገጥመው ወታደሮቹ አብዛኛው የተገደሉ መሆናቸው ወሬ ሲሰማ ሌሎች 5000 ዘራፊዎችም ወደ አፋር የገቡ መሆናቸውን ሰምተናል በማለት የኢጣሊያ ትኝ ገዥዎች የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው የታወቀው የጨው ማዕድን ወዳለበት ዳሉል ዲሴምበር 1929 ይገባሉ። የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እኳን የሚወሩ ዝርፊያዎች የተለመዱ ናቸው ብሎ ቢያምንም ወሬውን ቢያስተባብልም በማሊያኖች ግፊት ከወሎ ተልከው የነበሩ በፊታውራሪ ፍትረ ማርያም የሚመራ ዘራፊዎችን ለመግታት የተሰማራው የመጀመሪያው ዘመቻ ተልእኮውን አልተሟላም በማለት በደጃዝማች አበበ ዳምጠው የሚመራ ጀንዋሪ 1928 ዓ.ም 2ኛ ዙሮች ጦር ከወሎ ወደ አላማጣ ኮረም ተላከ። ማሊያኖች ብዙ ዘራፊዎች በአፋር በደንበራቸው እንደተደረጉና ከወታደሮቻቸው ጋር እንደተፈጠሩ ይገልጹ ነበር።

ራስ ጉግሳ አርአያ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ የሚል ትእዛዝ በተሰጠው መሠረት ፌብሯሪ 1929 ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ከባለቤቱ ጋር ወይዘሮ ሻሸወርቅ በኤርትራ አለፏል። ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ዘራፊዎች ወይም በመንግሥት ያመጺ ወገኖች ሲያጣ ለሚፈጠረው ረብሻ በኃላፊነት የሚጠየቀው ደጃዝማች በላይ የዋግ ሹም ከበደ ጓንጉል ልጅ መሆኑን ተርጓሚውን ስለገለጸ ደጃዝማች በላይ በቁጥጥር ስር ውሎ ማርች 10 ቀን 1929 ወደ አዲስ አበባ ይወሰዳል። በዚሁ ጊዜ ማሊያኖች በዳሉል የሚገኙ ማሊያኖችና አፋር ኤርትራ ዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ በሚል ሰበብ ሀገሩን በቁጥጥራቸው አውለው ለገነው በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ቢያስታውቁም ምንም ተቃውሞ ሳያሰማ ይቀበለዋል። በዚሁ ተደፋፍረው ማሊያኖች የኢትዮጵያ አፋር ዳሉል የሚያጠቃልል አንድ አዲስ ወረዳ አፋር አስተዳደር ያቋቁማሉ።[1] ማርች 30 ደጃዝማች አበራ ተድላ ወደ አዲስ አበባ ይጠራል። የምሥራቃዊ የትግራይ ሕዝብ በሙሉ በአስተዳዳሪዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን በማእከላዊ መንግሥትም ቁጥር የለመዐ መሆኑን ማሊያኖች ባሰራጩት ዜና መሠረት ንጉሡ አፕሪል 1 ቀን 1929 በወሎ የጁ የኮተት ጥሪ ያዛል። ደጃዝማች አበበ ዳምጠው የአንጻ መኮኒ አስተዳደር ከደጃዝማች አበራ በሚዜያዊነት ይረከባል፤ ዋግ ሹም ከበደም ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ መቀቀ ሰለነበረ ጃዝማች አበበ የዋግ አስተዳደርም ይረከባል።

በአጠቃላይ 1ኛ ዋግ ሹም ከበደ ጓንጉል 2ኛ ደጃዝማች አበራ ተድላ 3ኛ ራስ ከበደ መንገሻ አቲከም በአካባቢው የሰፈነው ውጥረት በኃላፊነት ስለሚያስጠይቃቸው ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ቀርተው ነበር። የአመጺ ማእከል ዘራል ስለነበር ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ወደዚያ አመራ። ይሁን እንጂ ከሀገሩ ሕዝብ ጋር አክብሮት ግንኙነት ከመፈጠሩ በቀር በአካባቢው ሰላም ለማምጣት ያደረገው አስተዋጽኦ አልነበረም።

1_Corrado Zoli Ibd p.274

ሜይ 1929 ዓ.ም የሁለተኛ መቀጣጫ ዘመቻ ተቋርጦ ዘቡል ሳይደርስ አፄ ኃይለ ሥላሴም ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ወደመጣበት እንዲመለስ ትእዛዝ ያዘዋል። ሜይ 29 ጣሊያኖች ከያዙት የኢትዮጵያ መሬት በፈቃደኝነት ይወጣሉ። በዚሁ ቀን ራስ ጉግሳ አርአያ ከአዲስ አበባ ተመልሶ ስለነበረ በግዛቱ በሙሉ የከተት አዋጅ ያሰማል። ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ጁን 18 ከማይጨው ተነስቶ ከአምስት ወር በኋላ ምንም ሳያከናውን ወደ ደሴ ይመለሳል፤ ወታደሮቹም ይበታተናሉ።[1] አፄ ኃይለ ሥላሴ ዋግ ሹም ከበደ ጓንጉልን ወደ ግዛቱ እንዲመለስ ፈቀዱለት። ጁን 23 ታማኙ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው የተላከበትን ግዳጅ ማከናወን ስላልቻለ ከሥልጣን ወርዶ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ መጣ። ኦገስት 1929 ራስ ጉግሳ ወሌ የነበረው ስፋት ተቀንሶ የየጁ ሀገረ ገዥ እንዲሆን ብቻ ተላከ።

በወሎ የንጉሡ እንደራሴ የነበረው ደጃዝማች ሥዩም ደስታ በሀገሩ ፀጥታ ማስፈን ባለመቻሉ ከሥልጣን ወርደው ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ መጣ፤ በምትኩም የወሎ ግዛት ለ ቃጣቱ የንጉሡ ልጅ አስፋው ወሰን ተሰጠ በሞግዚትነትም ደጃዝማች እምሩ ተሾሙ።

ራስ ጉግሳ ወሌ 1ኛ የየጁ ጦር 2ኛ በአካባቢው ያለው የራስ ካሣ ጦር 3ኛ በአካባቢው ያለው የራስ ጉግሳ አርአያ ጦር የበላይ አዛዥ ሆኖ ስለተሾመ ወደ ቆቦና ዘቡል አመራ።

ራስ ጉግሳ አርአያም ከንጉሡ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ኦክቶበር 1 ቀን ወደ ደቡብ ምሥራቅ ግዛቱ አመራ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ የጉንደሩ ታማኝ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ወደ እንዳ መኮኒ እንዲያመራ ያዘዋል። ተመሳሳይ ትእዛዝም ዋግ ሹም ከበደ ጓንጉል ወደ ምሥራቃዊ ግዛቱ እንዲያመራ ትእዛዝ ይደርሰዋል።

ራስ ጉግሳ ወሌ የአመፁ ማእከል ወደተባለው ወደ ዘቡል ያመራል። ራስ ጉግሳ አርአያም ወደ ግዛቱ እንዳይገባበት ተቃውሞ ያሰማል። ይሁን እንጂ ራስ ጉግሳ ወሌ ወደ ዘቡል በመጠጋት የደጃዝማች አበራ ወንድም ደጃዝማች አርአያ ተድላ የጩርጩር ገዥ አድርጎ ይመድበዋል።

በዚሁ ወቅት ራስ ጉግሳ ወሌና ደጃዝማች አበራ ተድላ ከየጁና ከራያ አመፆኞች ግንባር ፈጥሯል የሚል ወሬ ይሰማል ይኸውም ለራስ ጉግሳ ወሌ ከማእከላዊ መንግሥት ማቋረጥ መሠረት ይሆናል።[2]

ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከግዛቱ ዳባት ተነስቶ ላስታ እንደደረሰ ሁኔታው ውዥንብር ያለበት መሆኑን ስለተረዳ ጉዞውን መቀጠል አልፈለገም።

1. Corrado Zoli Ibd p.281

2. Corrado Zoli Ibd p.280



ፊታውራሪ በዛ በላስታ የራስ ካሣ እንደራሴ ከራስ ጉግሳ ወሌ ጋር ስላልተስማማ ዋጃ ቆቦ ከመጣ በኋላ ተመልሶ ወደ ላስታ ሄደ። የቆቦ ሕዝብ አካባቢም ራስ ጉግሳ ወሌ ወደ ሀገራቸው ከመድረሱ በፊት ሸፍተው ነበር። ኖቬምበር ወር 1929 ዓ.ም ንጉሡ ሁለቱ ራስ ጉግሳ ታማኝነታቸው አጠራጣሪ እንደነበረና ውጥረቱን ለማርገብ እንዳልቻሉ ተገንዝበ ነበር፤ እምነቱ በደጃዝማች አያሌው ብሩ ብቻ አድርጎ ነበር። ራስ ጉግሳ አርአያ ወደ ወጅራት እንዲሄድ ታዘዘ። ራስ ጉግሳ ወሌ በውሃ እጥረት ምክንያት ከዘቡል ለቆ ኖቬምበር 6 ለመሄድ ተገደደ፤ በዚሁ ጊዜ የተሰጠው ግዛት የጁ መሆኑ ተነገረው፤ ከቤጌምድር ግዛቱ የተነሳ መሆኑን ተነገረው፤ ከዘራፊዎች የተቀበለውን መሣሪያ ለፊታውራሪ እንዲያስረክብ ቢታዘዝ ፍቃደኛ ስላልነበረ ከማእከላዊ መንግሥት የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ።

ደጃዝማች አያሌው ብሩ በአካባቢው የነበረው ሁኔታ ውዥንብር የሞላበት ከመሆኑም ሌላ የፀጥታ ሁኔታም እንደተወራ ከባድ እንዳልነበረ ተረዳ።

ጣሊያኖች እንደልማዳቸው ዝርፊያውና ግድያው እንዳለ ነው እያሉ ያወሩ ነበር፤ ወደ ኤርትራ ደብዳቤዎችን የሚያመላልሱ የራሳቸው የፖስታ ሰራተኞች ይዘረፉና ይደበደቡ እንደ ነበረ ዜና ከማሰራጨት አልተቆጠቡም።

አፄ ኃይለ ሥላሴም በጣሊያኖች ወጥመድ በመግባቱ የእነሱን ፈለግ በመከተል ጣሊያኖች እንደተመኙት ሰላምን ሰማምጣት ከማእከላዊ መንግሥት ጦር መላክ እንደሚያስፈልግ በሚል ግምገማ ደረሰ፤ ለዚሁም ዘመቻ አንድ ሐኪም እንዲላከለት ለጣሊያኖች ይጠይቃል የተላከለት ሐኪም ግን በመንገድ ስለዘገየ በተካሄደው የዘቢጥ ጦርነት ተካፋይ ሳይሆን ወደ ኤርትራ ተመለሰ። የመንግሥት ሹማምንቶች ቁጥጥራቸውን ሲያላሉ ዘራፊዎች ቢንቀሳቀሱም የቀናው ግን የአውሳ ሱልጣን ነበር። ዘራፊዎችን አባሮ የተዘረፈውን ንብረት በሙሉ ማስመለስ ችሎ ነበር። አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሁለቱ ራስ ጉግሳ የትኛው እንደሚሸፍት ወይም ሁለቱ እንደሆነ ግልጽ አልሆነለትም ነበር። በዚሁ መሠረት ራስ ጉግሳ አርአያ ከተላከበት ሀገር ዲሴምበር ወር 1929 ወደ መቀሌ እንደተመለሰ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ እንዲሄድ እንዲዘጋጅ ተነገረው።

አዲስ አበባ ያለው የመንግሥት አካል በጣሊያኖች የሚናፈሱ ወሬዎች ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ያስቸግሩ ይሆናል፤ በይፋ ግን ሽፍትነት እንዳልተከሰተና የሚወሩ ዝርፊያዎች በየዓመቱ የሚከናወኑ እርስ በርስ ዘረፋ አያልፍም የፖለቲካ ምልክትም የላቸውም እያለ ያልተሟገተበት ጊዜ አልነበረም። ሆኖም በጣሊያኖች ወሬ ተሰ[illegible]ቶ ጠቅላላ በመላው ሀገሪቱ የጦር አዋጅ ከተት ማወጁ ምን ያህል በጣሊያኖች ስብከት ተወናብዶ በእነሱ ወጥምድ እንደገባ ያሳያል። ጣሊያኖች ባደረጉት ፕሮፓጋንዳ መሠረት በራስ ጉግሳ ወሌ የሚገዛ ሀገር የቤጌምድር ሌላ ምሥራቅ ትግራይ፤ ዋግ ፤ ላስታ፤የጁ፤ ራያ በማእከላዊ መንግሥት አምፆ ነበር። ኮራዶ ዞሊ ካርታ (4) ተመልከቱ፡

ጦርነት ቢነሳ የማእከላዊ መንግሥት ያለው አቅም ለመገምገም እንዲረዳቸው በጣሊያኖች ጉትጎታ ቢሆን ኃይለ ሥላሴ ወይም ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴር የሚመራ ከመላ አገሪቱ የተውጣጣ ጦር ወደ ሰሜን እንዲዘምት ተወሰነ። ጦሩ የተመራው ግን ጣሊያኖች እንደተመኙት በንጉሡ ሳይሆን በደጃዝማች ሙሉጌታ ነበር የተውጣጣም ከማእከላዊ መንግሥት ነበር። የግሉ ጦር ሠራዊት የነበረው ንጉሥ ራስ ተፈሪ ግን አንድ ወታደር፡ አንድ የጦር መሣሪያ፡ አንድ ጥይት እንኳን በዘመቻው ተካፋይ አላደረገም።

1 ደጃዝማች አያሌው ብሩ ወደ ዙሪያ፡ ራያ፡ ቆቦና ቃሊም እንዲያመሩ ታዘዘ

2 ራስ ጉግሳ አርአያ ወደ ማይጨው፡ ጨርጨር፡ ላስታ እንዲያመሩ ታዘዘ

3 ዋግ ሹም ከበደ ጎንተል ወደ ኮረም አላማጣ እንዲዘምት ታዘዘ

ቀደም ብሎ የደጃዝማች አበራ የነበሩ የእንዳ መኮኒ ጨርጨር ግዛቶች ለራስ ጉግሳ አርአያ ተሰጡ።

በደጃዝማች ሙሉጌታ የሚመራ ጦር ከአዲስ አበባ እንደተነሳ ከላይ የተጠቀሱ ሶስት ከፍተኛ ሹማምንቶች በስልክ እርስ በርሳቸው ተነጋገረው ተስማምተው በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ውጥረት የራስ ሙሉጌታ ማእከላዊ መንግሥት ጦር እርዳታ ሳያስፈልጋቸው በቻቸው ለማርገብ እንደሚችሉ ለንጉሡ አስታውቀው ከፌብሯሪ 12 እንዲጀምሩ ያስፈቅዳሉ።

በ1930 ደጃዝማች ሙሉጌታ ወረኢሉ በደረሰበት ወቅት ሶስቱ እላይ የተጠቀሱት ሹማምንቶች ግዳጃቸውን በሚገባ ስለተወጡ የማእከላዊ መንግሥቱ ጦር ዘመቻ አስተደዋ እንደታቀደው ወደ አሸንጌ ማምራቱን ትቶ የመጣበትን ቢላግ ቀደር በራስ ጉግሳ ወሌ ላይ እንዲዘምት ታዘዘ።

ከዚበታው የመጣ ደጃዝማች ሙሉጌታ ጠቅላይ አዛዥ የሚመራ ጦር ደሴ እንደተሰበሰበ ወታደሮች አመጻቸው በሚመስል መልክ ተቃውሞ በማሰማት «ማንን ጠላት ለመዋጋት ዘምተን ነው የመጣን» ብለው በጠየቁት ጊዜ ደጃዝማች ሙሉጌታ ከራስ ጉግሳ ወሌ ጋር ለመዋጋት መሆናቸው ነገራቸው።[1]

የዘማች ሠራዊት መሪዎች ራስ ጉግሳ ምን ጥፋት እንዳመጣ፣ የይግባኙን ቀደር እንደሆን፣ ንጉሥ ለመሆን ፈልጎ እንደሆን ብሎ በመጠየቅ ደጃም ቢሆን ንጉሡ የግል ሠራዊቱም ንጉሡ ራሱም በጦርነቱ ተካፋይ መሆን እንደሚገባው የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር። ጣሊያኖች ብለው ለራሻ የሌ ጠሩት ጦርነት ሠሰን የሆን ከለለ መሆን ቀርቶ በቢልፊሮ ደረጃ የተከሰተ የመሰው ሰሜን ኢትዮጵያ የሚያጠቃልል በመንግሥት ላይ የተሰበረ አመፅ እንቅስቃሴ ነበር።

1.Corrado Zoli : Etiopia d'Oggi p. 180




እንደ ፀደዋ ጦርነት በሆኑ ለግድ መሠረት የጦርነቱ መሪ ንጉሥ ተፈሪ መኮንን እንዲሆን ፍላጐት ነበራቸው። ቀደም ብሎ ግን ሆኖች ሠራዊት የተገነቡተ ኃላፊ በምሥራቅ ወሎና ትግራይ የነበሩ ኀመኛቸውን ለመደምሰስ መሆኑን ተገንዝቦት ነበር። ጠላት በለመኑ፣ እን ደተባለው የኃላ ንጉሥ ባለመኑ ተደብቆ የቆየው የዘመቻ ኃላፊ ገደ በመውጣት ጦሩ በራስ ጉግሳ ወሌ ላይ ፊቱን አዙሮ እንዲዋጋ ተደረገ። ይኸ የውጭ ጠላት ባለበት፣ በጣሊያኖች የተቀነባበረ የከተት ጥሬ ኢትዮጵያ ጦርነት ቢነሳበት ለፍተኛ ምን ያህል ወታደር፣ ሰንግ ያህል ጊዜ ማሰለፍ እንደምትችል ለማወቅ የታቀደ መሆኑን ትራያዪቢ በግድ ዘግቧል።[1]

በአሳዛኝ ሁኔታ በወቅቱ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ኃይለ ሥላሴም ጭምር ጠላት ባዘጋጁላቸው መሥመር እየተሽከረከሩ የኢጣሊያን ቅኝ ገዥ ምኞች በሚፈልጉት መሠረት ሆነው ለመረሬ እንደትጋለጡና እንደትመቻች አድርገ ጊታል። ራስ ጉግሳ ሳይወድ በግድ ለአመጽ እንደተነሳ እንፈረዳለን። ኃይለ ሥላሴና ልጅ እያሱ ከመታወቃቸው በፊት እነ ምኒልክ በሞት ቢለዩ እነ ምኒልክን ተክተው የንጉሡ ነገሥትን ዙፋን ይዋርሱ ተብለው በዕጩነት በተመለከቶች ይታሰቡ የነበሩ ራስ መኮንንና ራስ ጉግሳ ወሌ ነበሩ። ራስ መኮንን እንደሞተም በተለይ የአቴጌ ጣይቱ ድጋፍ ስለነበረው ራስ ጉግሳ ብቸኛ እጩ ሆኖ ቀርቶ ነበር። ከዚህም ሌላ የእነ ምኒልክ ልጅ የዘውዲቱ ባል ነበር፣ ይኸም ራሱ ንጉሥ ለመሆን እንዲመኝ መብት ይሰጠዋል። የእነ ምኒልክ ወራሽ ልጅ እያሱ ቢሆን ተተኪ ሚስቱ የነበረች ዘውዲቱ ሆና እልጋ ወራሽ ኃይለ ሥላሴ ቢሆን ራስ ጉግሳ ወሌ ተቃውሞ አላሰማም።

ንጉሡ ነገሥት ባይሆንም እንደ ንጉሥ ሚካኤል፣ ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የንጉሥ ማዕረግ እንዲሰጠው ፍላጐት ሊኖረው ይችላል፣ የሚገባውም ነበር። የበጌ ምድር ጠቅላይ ገዥ ሹመት በመሆንም ለንጉሥ የሚያስከብር ትሬታ አለ ነበረውም። ለገልጽ ንጉሥ ያጋገረው ከበጌምድር ጠቅላይ ገዥ ተሹር የትውልድ ሀገሩ የጁ፣ ስሜቱ ተቀንሶ፣ የውራጃ ገዥ እንዲሆን በታዘዘበት ጊዜ ብቻ ነው። በትልቁ የኢጣሊያ ወረራ 1928 ዓ.ም ‹1935–36› በጠላት ላይ ያለ ተካፈሉ የኢትዮጵያ አርበኞናኖች ለመጀመሪያ ጊዜ በራስ ጉግሳ ላይ በተደረገው ጦርነት ከመንግሥት ኃይል እንድ ሲሶ ብቻ በነበረው በራስ ጉግሳ ተካፋይ በመሆን በቦምብ ደብድቧል። ፈረንሳዊ የአሪዮፕላን አብራሪ ለድሉ ስላደረገው አስተዋፅኦ 1000 ብር ተሸልሟል፣ በዘመኑ ትንሽዬ ሲተመን ብዙ ነው።

ፌብሯሪ 22 የደጃዝማች ሙሉጌታ ጦር ደሴ ሲገባ የንጉሥ ተፈሪ መኮንን እንደራሴ የነበረው ራስ እምሩ፣ በደሴ የኢጣሊያ ቆንስል፣ ሐኪም የኢ ጣሊያ ሠራዊት ጀኔራል ከነበረው እናሬቶኒ ጋራ ተቀበሉት።

1. Corrado Zoli Ibid p.176




ጣሊያኖች የኢትዮጵያ የወታደር ብዛት ለማወቅ ያደረጉት ጥናት በየዓይነቱ አስራሟቸውታል፡፡



ማርች 22 የማእከላዊ መንግሥት ጦር ዘቢጥ ይደርሳል። አሰላለፉም ‹ካርታ ቁጥር 5 ይታያል› ማርች 22 አራስ ጉንሳ ወሌ በጦር ሜዳ ቁመር ደንጂ ይሰፍራል።

ማርች ወር ራስ ጉግሳ አርአያ በጦርነቱ ሳይካፈል ከማይጨው ተነስቶ መቀሌ ይገባል።

ማርች 28 በራስ ጉግሳ ወሌ ላይ አሬዮፕላኖች ቦንብ ይጥላሉ። በዚሁ ዕለት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የሚያስቃያት በሽታ የነበረ የስኳር በሽታ ይብስባታል።


የኢትዮጵያ መንግሥት በማይታይ የኢጣሊያ የስለላ ወጥመድ ገብቶ እንደነበረ ያስረዳል። ጦርነቱ ጣላት በሌለበት ነው፣ የተካሄደውም ማርች 31 ጧት ነበር። ‹ካርታ ቁጥር 6› ተመልከት ጣሊያኖች የፈለጉትን አግኝተዋል ለወደፊት በኢትዮጵያ ላይ ያሰቡት ወረራ ስለኢትዮጵያ የጦር ክተት ጥሪና ምልመላ አስተማማኝ መረጃ አግኝተናል በማለት ተደስቷል። ይኸ በ1922 ዓ.ም ‹1928–29› የተጠራው ከፊል ክተት በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ከተደረገው ተመሳሳይነት አለው።[1] ለወደፊትም ለብዙ ዘመናት እንደማይለወጥ ብለው ገምተዋል፣ ከዚህ የተለየ እንደማይሆን ጣሊያኖች ባደረጉት ጥናት ለማረጋገጥ በመቻላቸው ተደስቷል።

1ኛ የመጀመሪያ ክተት አዋጅ የተጠራው በሲዳማ ቦረና ዲሴምበር 6 ቀን 1929 ነበር፣ እንደዚሁም በወለጋ፣በጅማ፣ወላሞ፣ ወዘተ በዚሁ ጊዜ እንደነበረ ይታመናል። ወረኢሉ የደረሱም ፌብሯሪ 12 1930 ነበረ፣ ይህ ማለት ሁለት ወር እና 6 ቀን በኋላ መሆኑ ነው። በደጃዝማች ብሩ የሚመራ ጦር ግን ወረኢሉ የደረሰው ማርች 10 1930 ነበረ፣ሶስት ወር ከ4ቀን በኋላ። በደጃዝማች መኩሪያ የሚመራው ጦር ወረኢሉ የደረሰው ፌብሯሪ 26 ሁለት ወር ከሃያ ቀን በኋላ። ደጃዝማች መሸሻ ወረኢሉ የደረሰው ፌብሯሪ 28–2 ወር ከ22 ቀን። ደጃዝማች አትፍርስ ወረኢሉ የደረሰው ፌብሯሪ 26 ሁለት ወር ከሃያ ቀን በኋላ ነው።

2ኛ ለሸዋና ትግራይ ክተት የታወጀው ዲሴምበር 28 1929 ነበረ እንደዚሁም ለሐረር ለአርሲና ለደቡብ ምስራቅ በዚሁ ቀን ሳይሆን አይቀርም።

የደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ ጦር ወረኢሉ የደረሰ ፌብሯሪ 18 ሲሆን አንድ ወር ከሁለት ቀን በኋላ ነው። የደጃዝማች ከፈተው ጦር ወረኢሉ የደረሰው ፌብሯሪ 24፣ አንድ ወር ከ27 በኋላ ነው። ልጅ አባ ወዳጆ ወረ ኢሉ የደረሰው ማርች 15 ሲሆን ሁለት ወር ተኩል በኋላ መሆኑ ነው። ምሥራቅ ትግራይ ዋግ ጦር ሜዳ የደረሰው ፌብሯሪ 5 ነው አንድ ወር ከስምንት ቀን በኋላ ነው። ሰሜን አማራ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ትእዛዝ የደረሰው ሴፕቴምበር 30 ቀን ሲሆን የፌብሩዋሪ 20 ላስታ ገብቶ ነበረ ፣ 20 ቀን በኋላ። ራስ ጉግሳ ወሌ ትእዛዝ የደረሰው ሴፕቴምበር 17 ሲሆን ኦክቶበር 10 የጁ ደርሶ ነበር፣ ሃያ ቀን በኋላ።


1. Corrado Zoli ibd p.363






የወሎ ጦር በተለያዩ ቀናት ወደ ጦር ሜዳ ተቀላቅሏል። በጦርነቱ የተካፈሉ የሰው ኃይል የመግሪያ ሰንጠረዥ ኮሎኔል ዞሊ ባወጣው መሠረት ያደረገው ጥናት ትክክለኛነቱ ስለሚያምንበት የሚመለከተውን ክፍል እንዲ ጠቀምበት ተገደናል። ጥሬውን የተቀበሉ ሹማምንቶች የሚከተሉት ናቸው።

| | ስም | ክፍለ ሃገር | ወብመዝዎች | መድፎች | መትረየሶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደጃዝማች መሉጌታ | አዲስ አበባ | 2800 | 5 | 7 |
| | – ረዳት | – – | 300 | 0 | 0 |
| 2 | – ብሩ | ደቡብ ምዕራብ ሲዳማ | 12000 | 1 | 10 |
| 3 | – መኩሪያ | – – | 2000 | 0 | 4 |
| 4 | – መሸሻ ወልዴ | ከምባታ | 2500 | 0 | 1 |
| 5 | – ደበብ | ደቡብ ምዕራብ | 600 | 0 | ? |
| 6 | – አተፍርስ ናና | | 1000 | 0 | 0 |
| 7 | ልዑ ረዳት | ደቡብ ምዕራብ | 150 | 0 | 0 |
| 8 | ልጅ አባ ወዳጆ | – ምሥራቅ ሐረር | 400 | 0 | 0 |
| 9 | – | – ረዳት | 300 | 0 | 1 |
| 10 | ቀኛዝማች ፍቅረ ማርያም | መሀል ወሎ | 1500 | 0 | 4 |
| 11 | ደጃዝማች እምሩ | ወሎ | 2000 | 0 | 0 |
| 12 | – አበበ ዳምጠው | – | 300 | 0 | 2 |
| 13 | – ወንዶሰን ካሣ | ሸዋና ላስታ | 5000 | 0 | 4 |
| 14 | – ተሰሩ | ሉጋዋቦ | 400 | 0 | ? |
| 15 | – አድማሱ | አማራ ሳይንት | 2000 | 0 | ? |
| 16 | ራስ ጉግሳ ወሌ | መሀል አማራ | 10000 | 2 | 10 |
| 17 | ደጃዝማች ክፈተው | ኤፍራታ | 300 | 0 | 3 |
| 18 | ? | አምባሰል | 750 | 0 | 0 |
| 19 | ደጃዝማች አያሌው ብሩ | ሰሜን አማራ | 3500 | 0 | 5 |
| 20 | ራስ ጉግሳ አርአያ | ምሥራቅ ትግራይ | 5000 | 2 | 9 |
| 21 | – ሥዩም | ምዕራብ – | 600 | 3 | 7 |
| 22 | ዋግ ሹም ከበደ ጓንጉል | ዋግ | 1600 | 0 | 1 |
| | ድምር | | 54900 | 13 | 67 |




1. Operazioni del Ras Gugsa Araiè.
2. Operazioni del Ueghacium Chebbedè Guangùl.
3. Operazioni del Degiacc Afaleù Burrù.
4. Operazioni del Degiacc Mulughetà (esercito imperiale).
5. Operazioni del Degiacc Burrù.
6. Avanzata del Ras Gugsa Oliè



ከዚህ በላይ የተጠቀሱ በሙሉ በጦርነቱ አልተካፈሉም፣ በመሃሉ የተበታተኑ ብዙ ናቸው፣ በጦርነቱ ከተካፈሉ የተበታተኑ ይበልጣሉ።

ይህ ድምርና ጥናት ግን የሚያመለክተው የከፊል ምልመላ ነው። ሙሉ ክተት ቢደረግም ከእውነት የማይርቅ ለማወቁ አስቸጋሪ አይሆንም። ኢትዮጵያ የምታሰልፈው የሰው ኃይል መቁጠር አስፈላጊ አይሆንም፤ መቁጠር የሚያስፈልገው ሀገሪቷ ያላት የመሣሪያ ብዛት ነው። በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው የመሣሪያ ብዛት በሚገባ ይታወቃል፣ በቂ ማስረጃ አለ። በሌሎች ክፍላተ ሀገርም ግምት መውሰድ አያስቸግርም ካለ በኋላ ኮራዶ ዞሊ ከተከዜ በስተምሥራቅ እና በስተምዕራብ ብሎ ለሁለት በመክፍል ለእያንዳንድ ቀጠና የድምሩ በሰንጠረዥ በዝርዝር ይገልፃል። ሰንጠረዡም እንደሚከተው ያጠቃልለዋል።


| ክፍላተ ሀገሮች | ጠብመንጃ | መድፍ | መትረየስ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ከተከዜ በስተ ምሥራቅ | 89.100 | 4 | 24 |
| 2ኛ ከተከዜ ማዶ | 77.500 | 6 | 21 |
| 3ኛ ሸዋና ደቡብ ኢትዮጵያ | 100.000 | 6 | 30 |
| 4ኛ ማእከላዊ መንግሥት | 250.000 | 120 | 130 |
| ድምር | 541.600 | 136 | 205 |

ከዚህ ግምት በመነሳት ነው ኢጣሊያ በማይጨው ጦርነት 500.000 ተዋጊዎች ያሰለፈችው።

ይህ ሁሉ ኢትዮጵያ ብዙ ዓመት ከወረራ በፊት ለጠላት ተጋልጣ እንደነበረች የሚያስገነዝበን ነው። ጣሊያኖች በይፋ ባይገዙዋትም እንቅስቃሴዋ በቁጥጥራቸው እንደነበረ ያሳየናል። ራስ ጉግሳ ወሌ መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም (ማርች 31 1930) በጦር ሜዳ ሲገደል ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የቀድሞ ባለቤቱ ሚያዚያ 24 (ኤፕሪል 22) በድንጋጤ አረፈች።

ንግሥቲቱ ከቀድሞ ባለቤትዋ ጋር የተፃፃፉቻቸው ደብዳቤዎችና የተለዋወጠቻቸው ኤሉግራሞች በጠላት ሳይቀር አድናቆት አግኝተዋል የንግሥቲቱ የቀድሞ ባለቤትዋ ከሞት ለማትረፍ ያደረገችው ጥረት ደግነትዋን ሃቀኛ ፍቅሯን በጉልህ አሳይቷል። ንጉሥ ተፈሪ ጋር በሥልጣን አለመጋፋቷን የበሳልነቷ ምልክት ተብሎ አድናቆት አግኝቶላታል።

መጋቢት 25 (ኤፕሪል3) የዘውድ አማካሪዎች ተሰብሰበው ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ንጉሠ ነገሥት እንዲሆን ወሰኑ። በማግስቱ ኃይለ ሥላሴ በሚል ስም በይፋ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነ።






ራስ ጉግሳ እርሱ በጦርነት ተካፍሎ አልነበረም፤ መጋቢት 26 (አፕሪል 4) የራስ ጉግሳ ወሬና የንጉሡት ነጋሪት ዘመቻ ምት ሳይሰማ የቀኛዝ ኃይለ ሥላሴ መንገሥ ሳይሰማ የድል አድራጊ የጦር መግለጫ ወጣች እያሰማ መቀሌ ገባ። ራስ ጉግሳና ራስ ሥዩም ወሬ የደረሳቸው በደቂቃ በሚገኘው የኢጣሊያ ቴንስላ አማካኝነት ነበር። ለኢትዮጵያ በመላእክት የሚታይ ሀገር ቴንስል በኩል ዜና እንዲደርሳቸው መደረጉ አስገራሚ ነው።

በግድ እንደሚታየው በጦርነት ጊዜ ግን በግን እንደሚተኩስ ለመለየት አስቸጋሪ ነው።

# የጣሊያኖች ቂም በቀል በአፋሮች ላይ

ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ለመረራቸው እንዲመቻቸው እርስ በርስ ጦርነት እንድትታመስ ያደርጉት የነበረው ለራሳቸው ጥቅም ሲሆን ፕሮፓጋንዳ የሚያደርጉት የነበረው ግን ከደጋ ኢትዮጵያውያን አፋሮች ይደርስባቸው የነበረው በደል እዛቸቸ እያስመሰሉ ነበር። የኢጣሊያ ዓላማ ለአፋሮችም ሆነ ለደጋ ሰዎች እኛኝ መሆን ሳይሆን ሁለቱ ጠላቶቻቸው ለሆኑ እርስ በርሳቸው እንዲተላለቁ ለማድረግ ሲጥሩ እንደነበረ የሚያሳይ ነው።

ጣሊያኖች በወደቁ የደረሰባቸው ሽንፈት ለመበቀል አመቺ ጊዜ ይጠብቁ እንደነበሩ ሁሉ በአፋሮችም በተለይ በቢሩ ሱልጣን ግዛት በጁሊየቲ የሚመራ የኢጣሊያ ሀገር ለማጥናት የመጣ ቡድን እንደደረሰም በቢያንኪ የሚመራ ሌላ የኢጣሊያ አጥኚ ቡድን በአፋሮች የተገደሉባቸው ለመበቀል አመቺ ጊዜ ይጠባበቁ እንደነበረ የታወቀ ነው።

ለማስረጃ የሚጠቀሰው ለኢጣሊያ በጐ ነገር ከማይመኙኝ ወገን ሳይሆን ራሳቸው ጣሊያኖች በጻፉት ማስረጃ ነው። ገና የተፈጸመው የኤርትራ ሀገረ ገዥ በነበረው በጉሪዚያ ሲሆን መረጃም የሚተርከው ራሱ ከጻፈው መጽሐፍ ነው።[1]

ኢጣሊያና ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በአፋር ያለውን ወሰን በመካከል ከቀይ ባሕር እስከ 60 ኪሎ ሜትር ያለው መሬት የኢጣሊያ እንዲሆን ተስማምተው ነበር። ይኽ ስምምነት ግን የአፋር መሪዎች እንደ ጣሊያኖች አባባል አያውቁትም ነበር። በ1929 ዓ.ም ኢጣሊያ በመረቀት ብቻ የተሰጣት መሬት ለመቆጣጠር ወሰነች። የቢሩና የአውሳ ሱልጣኖች ተቃውሟቸውን ለኤርትራ መሪዎች አሰሙ፤ የተሰጣቸው መልስ አሉታዊ ነበር። ደጀዝማቾች መሐመድ ያሲን የቢሩ ሱልጣን ወደ ወሉ ሀገረ ገዥ ትርብ አለታውና ወደ ጉንዶ ነጋሪት ሄዶ ስለሁኔታው ሲያስረዳ፣ የአስተዳደሩ ድጋፍ አግኝቶ ነበር የተመለሰው። ሆኖም ውሳኔ ጉዳት ጉድት አልተፈጠረም ነበር።

---

1.Corrado Zoli Cronache Etiopiche p. 196-198

በ1930 አገሰት ወር በድንገት ደጃዝማች መሐመድ ያሲን 30 ተዋጊዎችን በመምራት ሄደረም የተባለ በኤርትራ የሚገኘውን ጉሣ አጥቅቶ ብዙ የቀንድ ከብቶችን ዘርፎ ፤ በግጭቱ ከኢጣሊያ ወገን አንድ ተዋጊ ሞተ፣ ሶስት ቆስሏል። የደጃዝማች ያሲን እህት እንደአጋጣሚ ሀብብ ትገኝ ስለነበረ ለመያዣ በጣሊያኖች ታስራ እንድ መልእክተኛ ወደ ሱልጣኑ ተልኮ ስለፈፀመው ሥራ ሲጠየቅ ደጃዝማች መሐመድ ያሲን ለኤርትራ ሀገረ ገዥ በሰጠው መልስ ለተፈፀመው ድርጊት ሁሉ በኃላፊነት ራሱ ተጠያቂ መሆኑን ገልጾ የፈፀመውን ወገኖቹ ወደ

ኤርትራ ግዛት በመሄዳቸው ባጠፉት ጥፋት ያደረገው ቅጣት መሆኑን የሚል ሲሆን፣ ለወደፊትም መሬቱ ካልተመለሰለት ተመሳሳይ ቅጣት ከማድረግ እንደማይመለስ ገለፀላቸው። ጣሊያኖች የቢሩ ሱልጣን የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ብቻው እንዳልነበ የሚል ግምገማ ደርሰናል የሚል ሰበብ ፈጠሩ። ለዚህም ማስረጃ የሆናቸው ከዘራፊዎች ውስጥ የደጋ ሐበሻ ሰዎችና የታጁራ የፈረንሳይ አፋሮች ተቀላቅለው በመገኘታቸው ነው። የኤርትራ ሀገረ ገዥ የሱልጣኑ መልስ እንደደረሰው በዚሁ ዓመት ሴፕቴምበር ወር እንደገና 500 የቢሩ ታጣቂዎች 15 ተዋጊች ብቻ የነበሩዋት ዋዲ የተባለችው የኤርትራ አፋር መንደር አጥቅተው ከወታደሮቹ ግማሹ ሲገደሉ ግማሹ ተማርከው ተወሰዱ። ከወራሪዎችም እንዳንዶቹ እስከ በይሉል 50 ኪሎ ሜትር ከአሰብ ርቃ የምትገኘው የወደብ ከተማ በመድረስ ዘረፋ ፈጽመው ቤቶችንም አቃጥለው ወደ መጡበት የኢትዮጵያ ግዛት ለመመለስ ችለው ነበር። ደጃዝማች መሐመድ ያሲን ባገኘው ድል ተኩራርቶ እንደገና በሴፕቴምበር ወር አጋማሽ 400 ታጣቂዎች በመምራት ሄዳረም የተባለ የኤርትራ አፋሮችን ጉሳ ለመዝረፍ ወስን አቋርጦ መጥቶ ነበር። ዳሩ ግን ጣሊያኖች ተደራጅተው ይጠብቁ ስለነበረ 15 ሰዎችን ገድለውበት 20 በማቁሰል ከባድ ጉዳት ስላደረሱበት ወደ መጣበት እንዲመለስ አድርገውታል። እንደገና ጣሊያኖች መልሰው በማጥቃት እንደ ሀገሩ ልማድ በሚል ሰበብ ሰፊ ዘመቻ ለማድረግ ወስነው ኦክቶበር 1930 የኤርትራውያን ተዋጊዎች የቢሩ ታጣቂዎችን በድ ንገት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ገብተው ከዘረፉ በኋላ በሰዎች ላይም ከባድ ጉዳት በማድረስ የሚሸሹትን እስከ ኪሪፎ ‹Chirifo› የሱልጣኑ ዋና ሰፈር ድረስ በማባረር ለማንታ የሱልጣኑ ዋና ምሽግ በመድረስ ነ ሠሁ ጉዳት አደረሱ

---

1 Corrado Zoli : Croiache Etiopiche p.79



መንደሩን አቃጥለው፣ያሏቸውቢቶችን አቃጥለው አወደሟቸው። ሱልጣኑና 150 ተከታዮቹም ተገደሉ።

በዚሁ ጦርነት ሴቶችም ተገድለዋል። ከሞቱትም መሀል ታዋቂዋ የሱልጣኑ እህት አማካሪውና አደፋፋሪው የነበረችው፣እንዲሁም ሁለት ሴት ልጆቹ ተገድለዋል፤ ከጣሊያኖቹ ወገን የሞቱት በምንት የቆሱ አስር ነበሩ። ከሱልጣኑ ቤተሰቦች ጉሳ የሱልጣን ዙፋኑት የሚገባቸው አንድ የወንድም ልጅና አንድ ባላባት የሱልጣኑን ሥራ የማይደግፍ የነበረ ብቻ ሳይሞቱ ቀርተው ነበር። በጦርነቱ ጊዜ ደሴ ይገኝ የነበረ ሌላ የሱልጣኑ ያጉት ልጅ መሐመድ እዮ የተባለም ሳይገደል በሕይወት ተረፈ፣ ሱልጣን የሚሾመው ከእነሱ ቤተሰብ ስለሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት መሐመድ እዮን የቢሩ ሱልጣን አድርጐ ከመሾም በቀር በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ፣ በኢትዮጵያ ዜጐች ላይ፣ ደጃዝማች ማዕረግ ያለው ከፍተኛ ባለሥልጣን ያሉበት ሰዎች ላይ የተደረገው ጭፍጨፋ በተፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል በጣሊያኖች ላይ ያሰማው ተቃውሞ አልነበረም።

ፍራንኬቲ በዳንከሊያ በ1929 ዓ.ም‹1921 ዓ.ም› ስላደረገው ጉዞ በደረሰው መጽሐፍ ውስጥ በግልጽ ተጠቅሶ እናገኛለን። አንድ ዓመት ከዐቢይ ጦርነት በፊት በባሮን ራይሞንዶ ፍራንኬቲ የሚመራ የኢጣሊያ ቡድን በኢጣሊያ መንግሥት ሙሉ ፍቃድ በኢትዮጵያ ዳንካሊያ ነዳጅ ማዕድንን ጥናት አድርጐ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለማስታወቅ በሚል ሰበብ ከአሰብ ቤይሉል በኩል ዳንካሊያን አቋርጦ፣ ማይጨው ደርሶ፣ ተመልሶም ወደ አሰብ በመሄድ ጉዞ አድርጐ ነበር። ዘመኑ በአካባቢው በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ውጥረት የሰፈነ ነበር፣ እርስ በርስ ጦርነት የሚካሄድበት፣ የደጋ ኢትዮጵያውያን ዘራፊዎች ወደ አፋር ክልል እየሄዱ በአፋሮች ላይ በደል ይፈጽሙሉ እያሉ ጣሊያኖች ወሬ የሚያናፍሱበት ነበር። በራስ ጉግሳ ወሌ ላይም የዐቢይ ጦርነት የተካሄደበት ወቅት ነበር። ቡድኑ ጉዞውን ለመጀመር ኖቬምበር ወር 1928 አሰብ ገባ። ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከንጉሥ ተፈሪ መኰንን ወደ ዳንካሊያ እንዲሄድ የተሰጣቸው ፍቃድ ነበራቸው። የአውሳ ሱልጣን ፍቃድ የተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽ ግዛቱ ብሉ የሚቆጣጠረው በጋሐሬ ምሽግና ባቡር ሃዲድ መስሬያቸውን በመቃወም የጻፈላቸውን ደብዳቤም ይዟል። ቡድኑ ከአሰብ ወደ ጋሐሬ ሄዶ ሰፈረ። ቡድኑ የነበረው የሰው ብዛት 105 ነበር፤ 70 የቅኝ ግዛቶቻቸው ወታደሮች ሲሆኑ የቀሩት አስተርጓሚዎች የመንገድ መሪዎች ባለ ግመሎች ወዘተ ነበሩ። የያዙት መሣሪያ ብዛት ከመትረየስና ከሽጉጥ ሌላ 87 ጠብመንጃዎች ነበራቸው፣ ብዛት ያላቸው ጥይቶችም ይዘዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጣቸው ፍቃድ ግን 50 ጠብመንጃዎች ብቻ ነበር። ሁሉም ኖቬምበር 30 ገሐሬ ተሰብስበው ነበር። ጣሊያኖች የሚያልፍበት በደጃዝማች መሐመድ ያሲን ግዛት ሲሆን፣ 50 ዓመት በፊት [1]ጣሊያኖች የተገደሉት በደጃዝማች መሐመድ ያሲን አባትና አጉት

የሚመሩ አፋሮች መሆናቸውን ጣሊያኖች አረጋግጠዋል። በባርኔ ራይሞንዶ ፍራንኬቲ የሚመራ ቡድን ዓላማው ሳይንሳዊ የግል ምርምር ለማድረግ ቡድን ሳይሆን በአሰብ የኢጣሊያ አውራጃ ገዥ፣ በኤርትራ ሀገረ ገዥ የሚደገፍ በመሆኑ የቢሩ ሱልጣን የኢጣሊያኖች ዓላማ የሳይንስ ምርምር ለማድረግ ሳይሆን የፖለቲካ ዓላማ እንዳላቸው በትድሚያ ተርጣሬ ስላለበት ተቃውሞውን ማሰማት ጀመረ[1]።

የቡድኑ መሪ ከሱልጣኑ ጋር በግል ለመነጋገር ያደረገው ሙከራ አልተሳካም። ሼክ ጀማል ኢዲን የተባለው በጣሊያን ዳንካልያ ግዛት ቃዲ የነበረው ለደጃዝማች ያሲን የሚስቱ ወንድም በመሆኑ ወደ ደጃዝማች ቢላክም ከኢትዮጵያ መንግሥት ትእዛዝ ስላልደረሰው ጣሊያኖችን ሊቀበላቸው እንደማይፈልግ ፣ ሊያያቸው እንደማይፈልግ፣ በኃይል ለማለፍ ቢሞክሩም እንደሚቃወማቸው ገለጠላቸው። ሸኩና የመንገድ መሪ የነበረው መሐመድ እስማን ቡሉሉስ የተባለው ከመንግሥት የተሰጣቸው ፍቃድ ይዘው ለማሳየት ቢሄዱም ሱልጣኑ ወረቀቶቹ የተጭበረበሩ ይሆናሉ በማለት አልተቀበላቸውም። የደጃዝማች መሐመድ ያሲን ተቃውሞ ለጣሊያኖች ጉዞቸውን ከመጠቀል የሚያግዳቸው አልነበረም። ጣሊያኖች ለሶስት ወር ሳይንቀሳቀሱ ያገዳቸው ከአሥመራና ከአሰብ በሚሄዱበት አካባቢ ዘራፊዎች ስላሉ ጉዞቸውን እንዳይቀጥሉ ይሰጣቸው የነበረ ትዕዛዝ ነበር። ለቡድኑ የደረሱ መረጃዎች ከተሰሙ አነስተኛ ዝርፊያዎች በቀር ልዩ ክስተት እንደሌለ በሚገባ ተገንዝቦ፣ የሚነፍሱ ዜናዎች በጣም የተጋነኑ መሆናቸውን ስለ ተረዳ ጉዞውን እንዲቀጥል ከመጠየቅ አላቋረጠም።[2] ይኸውም የኢትዮጵያ መንግሥት አቋም ነበር። በሌላ በኩል ደጃዝማች መሐመድ ያሲን ከቅርብ አለቆቹ ባደረጋቸው ግንኙነቶች እርግጥ የኢጣሊያኖች ቡድን እንደሚመጣ ደብዳቤ ቢጻፍም እርዳታ እንዲሰጣቸው አይልም፣ እንዲያውም ከትትል እንዲደረግባቸውና እርዳታ እንዳይሰጣቸው ብለው አስረድተውት ነበር። ደጃዝማች ራሱ ነጭ ሰው ወደ ግዛትህ ከመጣ ትጠቃለህ ብሉ አንድ ጠንቋይ አስጠንቅቆኛል እያለ ከመናገሩም በላይ ከጣሊያኖች ወደ እሱ የተላኩ የሚስቱ ወንድም ቃዲውና መሐመድ ኡስማን ቡሉሉስ ጣሊያኖችን ለማስፈራራት የሌለው የጦር ኃይል አለኝ በማለት እንዲጽፉ አድርጓቸዋል። ከዚህ ሌላ ደጃዝማች መሐመድ ያሲን ጣሊያኖች ጉዞቸውን ከመቀጠላቸው በፊት አሰብ ላይ ብዙ ሰው የተገኘበት ባለሥልጣኖች ባሉበት ስብሰባ አድርገው ባባቱ የተገደሉ ጣሊያኖች እንደሚበቀሉዋቸው ተግምሰው እሱንም ሊገድሉት የግሉ ስለሆነ እንዳይጠጋቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ ይደርሰው ነበር።

---

1. Raimondo Franchetti :Nella Dancalia Etiopica p.72'

2. Raimondo Franchetti Ibd p.74



ጣሊያኖች በሰፈሩበት በጋሐረ ሥራ ፈተው አልተቀመጡም በየቦታው እየተዘዋወሩ ሀገሩን እያጠኑ በሚገኙበት ወቅት የአሰብ አውራጃ ገዥ ዲሴምበር 29 ከቦታው እንዳይ ንቀሳቀሱ ጥብቅ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣ የተሰጡ ምክንያቶች ከዚህ በፊት ተደጋግመው የተነገሩዋቸው አስደንጋጭ ሐሰተኛ የፈጠራ ወሬዎች ከዘራፊዎችና ነፍሰ ገዳዮች እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ነበር።[1] ለዚሁ አስደንጋጭ ዜና ምክንያት የሆነው ከገሬፎ ሼክ ጀማል ኢጂን አልፎ ይገኝ የነበረው ሐበሾች የደጋ ብዙ ሰዎች የቢሩ ሱልጣን ግዛት ብዙ ከብቶችን ዘርፈዋል ብሉ ያስላስተላለፈ ሲሆን፣ የቡድኑ መሪ ግን ሩቅ ቦታዎች ድረስ ደጋሬ የሆኑ አፋሮች አግኝቶ ስለነበር የሚያስፈራው ነገር እንደሌለ ለማረጋገጥ ችሎ ነበር። የአሰብ ገዥ ግን ባገኛቸውን ወሬዎች መሠረት በማድረግ የኢጣሊያ ግዛት ወሰኖችን በወታደሮች አጠናክር ነበር። ተዘረፉ የተባሉ ከብቶች የደጃዝማች መሐመድ ያሲን ንብረት ስለነበሩበት ደጃዝማች ተከታትለው በማጥቃት የተዘረፉትን ከብቶች ማስመለስ ችሎ ነበር። በዝርፊያ የተደረጉ ውጊያዎች 6 ደንከሉች 17 ዘራፊዎች ሞተዋል ተብሉ የተወራም የሞቱት ሰዎች ቁጥር 3 ብቻ እንደነበረ ተረጋገጠ። ዘራፊዎቹን ይመራ የነበረም በአንድ አፋር በነፍስ ገዳይነት ወደ ደጋ ወጀራት ሀገር ሄዶ ይኖር የነበረ መሆኑ ታወቀ ‹አንዳዊታ የተባለው›። በዚሁ ጊዜ የቡድኑ መሪ ግመሉችን ለመግዛት ከኤርትራ መሪዎች ለመገናኘት እንዲያመችው የኤርትራ ባለሥልጣናት ጣልቃ ሳይገቡበት በራሱ ሃሳብ እንዲንቀሳቀስ እንዲፈቀድለት በመጠየቅ ወደ አሰብ ሄዶ ነበር፣ ነገር ግን የማይታረቅ የአስተሳሰብ ልዩነት ስለነበራቸው የጉዞው አስፈላጊነት ማቋረጥ የሞራል፣ የኢኮኖሚ ውድቀት እንደሚያስከትል ባለሥልጣኖቹ ሊረዱ ባለመቻላቸው ጋዘን እየተሰጣው፣ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ በገና ዋዜማ ዲሴምበር 22 ወደ ደፈገሐሬ መጥቶ በዓሉን ከጭፍሮች የቡድኑ አባላት ጋር በደስታ አሳለፈ ሁሉም ጉዞውን ለመጠቀል አስፈቅዶ ይመጣል ብለው ይጠባበቁ ነበር። ሆኖም ተስፋቸው ከንቱ ሆነ። ደጃዝማች መሐመድ ያሲን ስላደረገው ዘመቻ የመጨረሻ ወሬዎች እንዳስረዱ በግጭቱ የተተኮሱ ጥይቶች ሶስት ብቻ ነበሩ፣ አንድ ጥይት ከዘራፊዎች ፣ ሁለት ከደጃዝማች፣ ሌላ ውጊያ የተካሄደው በጩበጣ ነበር። ደጃዝማች 800 ግመሎች ከዘራፊዎች ነጥቀው እንዲሸጥላቸው ጣሊያኖች ቢጠይቁት ግመሉቹ አብዛኛው አክስታይ ጸቃ፣ ወተት የሚሰጡ ስለሆነ ለመሸጥ እንደማይፈልግ ነገራቸው። ፍራንኬቲ በተመሳሳይ ጥያቄ ዲሴምበር 27 እንደገና ወደ አሰብ ሄደ። መሐመድ ኡስማን ቡሉሉስ የሚባለው ወደ ሱልጣኑ ተልኮ የነበረው የመንገድ መሪ ታስሮ ተይዟል ተብሎ ሲታሰብ እሱ ግን የነበረው ወደ ገሐሬ ተመልሶ መጣ። ሱልጣኑ ከገሬፎ በቀር በግዛቱ ጣሊያኖች እንዳያልፉ ፈቅዷል ብሎ ነገራቸው፣ በሌላ ቦታም ለመገናኘት ዝግጁ መሆኑን ነገራቸው።

---

1 Raimondo Franchetti Ibd p.82

ዘራፊዎች ገና በዓላቸውን ለማክበር ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ስለነበረ ባሮኔ ፍራንኬቲ ወደ ኤርትራ ገዥ ቴሌግራም ልኮ «እኔ የሳኳቸው መረጃ የሚሰጡኝ ሰዎች በቢሩ ግዛት ውስጥ ሁለት ቡድኖች 500 እና 300 አባሎች ያሉዋቸው ዘራፊዎች በስተቀር ሌሎች ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። ከዐድዋና ከደሴ የሚተሳለፉ ወሬዎች የተጋነኑ ናቸው የቢሩ ሥልጣንም በግዛቱ ለማለፍ ፈትዶልኛል ስለዚህ በአሰብ አውራጃ ገዥ በኩል ያስተላለፉልኝ አገዳ እንዲነሳልኝ፣ ከዚህ በላይ መዘግየት ለጉዟችን እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ብሎ ነበር። ተጓዦቹ እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ ይከለከሉ የነበሩት 1ኛ በአካባቢው ፀጥታ የለም 2ኛ የቢሩ ሥልጣን ፍቃድ አልሰጠም በማለት ነበር። አሁን ሁለቱ ምክንያቶች የተወገዱ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ የቡድኑ መሪ በቴሌግራም በጠየቀው መሠረት ሁኔታዎች እስኪጣሩ ድረስ እንዲጠብቁ የሚል ነበር።

ዋናው ችግር ሆኖ የተገኘው ተጓዦቹ ለነበራቸው የከብቶች የመኖ እጥረት ነበር። ብዙ ግመሎች ይሞቱባቸው ስለነበር ሳር ወደ ሚገኝበት ቦታ እንኳን ለመንቀሳቀስ ሊያስቡ ነበር።

በዚህ ጊዜ የምሥራቅ ትግራይ ገዥ ራስ ጉግሳ አርአያ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ በምፅዋ በመርከብ ተሳፍሮ ፌብሯሪ 21 አሰብ ደርሶ ነበር። የቡድኑ መሪ ፍራንኬቲ ወደ አሰብ ሄዶ ራስ ጉግሣን በማነጋገር በእርሱ ሥር የሚተዳደረው ለቢሩ ሱልጣን ደብዳቤ እንዲፅፍለት ቢጠይቀው ቀዝቃዛ አቀባበል ነበር ያገኘው። አሰብ ሆኖ ለበታች ሹሞች ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቸግረው ሊያስረዳ ቢሞክርም ባሮኒ ፍራንኬቲ ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሄው የኤርትራ ሀገረ ገዥ መሆኑን ማወቅ ስለተሳነው ወይም ደፍሮ መናገር ስላቃተው በጣሊያኖች የተፈጠረው ችግር የመስዋዕትነት ቀማሽ በነበረው ራስ ጉግሣ ላይ ቁጣውን አወረደበት። በሥነ ሥርዓቱ አነጋገር ትቶ በዛቻ አነጋገር ደብዳቤ ለሱልጣኑ ካልሰጠኸኝ ተጓዦቹ ያለ ፈቃድ ጉዞአቸው የሚቀጥሉ ስለሆነ ለሚደርሰው ሁሉ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን ብሎ እየዛተ ሌላ አስተርጓሚ ሊያስተረጉመው ያልፈለገ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የሆኑ ቃላቶች በሚስቱ ፊት ንቀት የተሞላበት ሲያወርድበት ራስ ጉግሣ ደብዳቤ ለመፃፍ ተገደደ። ግን ከአዲስ አበባ ማረጋገጫ ካልተላከ ለባሮኔ ፍራንኬቲ እንዳይሰጠው ለጊዜው ለባራምባራስ በየነ መርሻ እጅ እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር። ማረጋገጫ ግን ስላልተላከ ደብዳቤው ሳይሰጠው ቀረ።

ከአሥመራ የሚመጡ መመሪያዎች ሁኔታዎች እስኪጣሩ ድረስ ጠብቁ የሚል የተለመደ አነጋገር ነበር፣ ተጓዦቹ ግን ከዚህ በላይ ከጠበቁ ከብቶቻቸው እንደሚያልቁባቸው ተረዱ። ባሮኔ ፍራንኬቲ ከኢጣሊያ ባለሥልጣኖች ተገናኝቶ ጉዞውን እንዲጀምር እንዲፈቀድለት ማርች ወደ አሰብ እንደገና ሄደ። ጻፉ ግን ሳይቀናው ቀረ። ስለሆነም ትዕግስቱ ስላለቀ አሰብ ሆኖ ለማርች 2 ሁሉም ግመሎች ጋሀሬ እንዲሰበሰቡ



ማርች 3 ጉዞውን እንጀምራለን ‹የሚል ቴሌግራም ላከ› 3 ወር በከንቱ ከጠበቁ በኋላ ከጋሐረ ጉዞውን የሚጀምሩበት ጊዜ የቡድኑ የለው ብዛት ጣሊያኖች ከ12 ሁለት ሰው ሊቀነስባቸው ጨምሮ ነበር። ሌሎቹ ግን ወታደሮች 111 ፣ ግመሎች 100፣ ግመሎችን የሚነዱ 33፣ በቅሎች 16፣ መሪዎች 7፣ ድምር 151። ጣሊያኖች 10፣ ድምር 161። ጠብመንጃዎች 115፣ መትረየስ 1። እግረ መንገዳቸው ባለቤት የሌለው ግመል አግኝተው ወስደው ተጠቀመውበታል።

ማርች 3 ዋአረ ይደርሳሉ፣ ማርች 4 ሊደሐ ኤላ፣ ማርች 5 ግብሬ፣ ማርች 6 አሹላ፣ ማርች 12 ደራብ፣ ማርች 16 አውራ 20 ኡራኩር አፍራራ ሐይቅ ጉን የሚገኙ ጣሊያኖች ሐይቅ ጁሊየቲ ብለው የሰየሙት ይደርሳሉ።

ከአፍራራ ሐይቅ ወደ ጉሮብሎ በሚጓዙበት ጊዜ የሚጠጣ ውሃ ችግር ነበር፣ በየቀኑ ውሃ ተለክቶ ለጣሊያኖች 10 ሊትር፣ በቀን ለኢንዲጀኖች 5 ሊትር በቀን ይሰጣቸው ነበር። ለተወሰኑ ቀናት ግን ለኢንዲጀኖች 2 ሊትር በቀን ብቻ ታደላቸው። ሁለት ኢንዲጀኖች በውሃ ጥም ሲሞቱባቸው በመንገድ ደክመው ሲቀሩ አስከሬናቸውን ፍለጋ ለመሄድ አልሞከሩም። አፕሪል 15 ኡረርቲ የዘራፊዎች መገናኛ የተባለው ቦታ ደረሱ። ከዚሁ ጊዜ ባሮኔ ፍራንኬቲ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ወደ ማይጨው ሲያመራ የቀሩት ሁሉ ወደ አሥመራ ለመመለስ በመቀሌ በኩል ጉዞአቸውን ቀጠሉ 8 ቀን በኋላ ኢጣሊያዊ የማይጨው ስልከኛ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው አቀባበል አድርገውለት ማይጨው ገባ። የፍራንኬቲ ዓላማ አሁንም ዳንካሊያን አቋርጦ በመጣበት ወደ አሰብ መመለስ ሲሆን ከኢትዮጵያ ባለሥልጣናትና ከኤርትራ ሀገረ ገዥ ግን ከዓላማው እንዲታቀብ ምክር ይጉርፍበት ነበር። ሜይ 3 የላከለት ደብዳቤ በደንካሊያ ላይ ያለው ሁኔታ የተባባሰ ስለሆነ ደጃዝማች ሥዩም ‹በወሎ የንጉሡ እንደራሴ› ደጃች አበበ በዘመቻ ማይጨው የሚገኘው ባንድ ቃል ወደ ተሩና ዳንካሊያ እንዳይሄድ የሚቃወሙ በመሆናቸው በኢጣሊያ መንግሥት ስም በመቀሌ በኩል ወደ ኤርትራ ቅኝ ግዛት እንዲመለሱ ትእዛዝ ለመስጠት እንደዳለሁ የሚል ነበር። ፍራንኬቲ ግን እንዲህ ያለ ቴሌግራም ከቡር ሀገረ ገዥ ያረቀቀው አይመስለኝም ቢሮ ቁጭ ብለው ያሉት ቢሮክራቶችና በሰፍራው ከሕዝቡና ከተፈጥሮ ተቀላቅሎ የሚውል ሰው ያላቸው አስተያየቶች የተለያዩ ናቸው። በዚሁ መንፈስ በመ ነሳት ክቡርነትዎ የላኩልኝ ቴሌግራም አስገርሞኛል። ምክንያቱም እኔ ከማደርገው የሚጣጣም አይደለም። ደጃች ሥዩምና ደጃች አበበ መቃወማቸው አዲስ ነገር አይደለም። ለስድስት ወር ነው እንዲህ ያለ ንግግር የማዳምጠው። ደጃች ሥዩም ከቻለ ወደ ቆላ ክፍል ይውረድ ከሁለት ወር በፊት ጀምሮ ደጃዝማቾች ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እትድ ነበራቸው። ደጃች አበበ በድንገት እዚህ መጥቶ በሕዝቡ ላይ እርምጃ በመውሰዱ በሕዝቡ የተጠላ ሆንዋል። ከሩቅ ሆኖ የዚህ ሀገር ሁኔታ መፍረድ አስቸጋሪ ነው ትክክለኛ ያልሆኑ የሚደርሱ መረጃዎች

መሠረት በማድረግ ድንጋጤ እንደሚፈጥር ይገባኛል። እኔ ምኞቴ የጀመርኩት ጉዞ ግቡ እንዲደርስ ሊሆን ከሁሉም በላ ስምምነት ለመፍጠር እሞክራለሁ። ፈታውራሪ ይግዛው የደጃዝማች እበራ ልጅ በግዛቱ ምንም ችግር እንደማይገጥመኝ አረጋግጦልኛል። እሱ ወደም እጐቱ ፈታውራሪ ገብሬ እስከ ተሩ ይሸኙኛል። በቀረቦታ ከልዩ ልዩ ኃላፊዎች በቀጥታ ተገናኝቼ ለመስማማ ት እቅድ አለኝ። ይህ ጉዞ በርግ ለማደራጀት ሊታቀድ በዳንካሊያ ብዙ ዘራፊዎች እንዳሉ ይታወቅ ነበር። እኔ የዚህ ሀገር ሕዝብ መንፈስ በሚገባ አውቀዋለሁ፤ ሆን ብሎ በነጮች ላይ የተደራጀ ጥቃት ይፈፀማል ብሎ ማሰብ አይቻልም ፤ለጥቃትን ግጭቶች የኔ እጀቢ ወታደሮች በቂ ናቸው የሚል መልስ ልኮ ነበር። ሜይ 7 ቀን ድንገት ለሚደርስብኝ ማንኛውም ጉዳት በኃላፊነት የምጠየቀው ራሴ መሆኔን ዛሬ ፈርሜያለሁ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ነው ያስፈረሙኝ። ይህ የማደርገው ብዙ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ምንም ጉዳት በማደርገው ጉዳይ እንደማይደርስብኝ ስላረጋገጡልኝ ነው። በቀረቢታ ተገናኝቼ የማነጋገራቸው ሰዎች የመጨረሻ ማረጋገጫ ይሰጡኛል። እስከ ተሩ ከእነሱ ማረጋገጫ ካለገኘሁ አልቀጥልም። ከእነሱ ውስጥ እስከ ተሩ ድረስ የሚሸኙኝ ካላገኘሁ ስለ ሁኔታው ያልተነገራቸው አንዳንድ ዘራፊዎች ቢያጋጥሙኝም ምንም አደጋ ላያደርሱብኝ ራሴ መከላከል እችላለሁ።

ሜይ 9 300 ፈታውራሪ ይግዛውና ገብሬ ሰዎች እያጀቡኝ ከማይጨው ተነስተው ወደ ቆርበታ ገቡ፡ አሁንም ከአስመራና ከሮም ጉዞውን እንዳይሞክር ቴሌግራሞች ይጉ ርፍለት ነበር።ይህ ሁሉ በጣም ያላዘነው ነበር፤ ዘራፊዎች ራሳቸው ይኸን ያህል አስፈሪ መሆናቸውን አይገምቱም፡ ቅኝ ግዛታችን ሥንመሠርት ፍርሃት ስለነበረብን ሽንፈት የደረሱብን በማለት የቀድሞ ቀኝ ግዛት ምሥረታቸው (አመሰራረታቸው) ያተቻል። በፈታውራሪ ገብሬ አማካይነት ከአንድ አባይ ውቤ የተባለ ታዋቂ የዘራፊዎች መሪ የሆነ ተዋወቁ። ፍራንኬቲ ፍላጐቱን ከገለፀለት በኋላ አባይ ውቤ ከአንድ ፈረንጅ ሳይቀር ጀግንነቱ በመታወቁ ተደስቶ ከሱ ጋር ከሄደ ምንም አደጋ እንደ ማያጋጥመው ማለት፡ እለከፈለገበት ቦታ ድረስ እንደሚሸኘው ገለጸለት።ሜይ 12 ጉዞ ተጀመረ ፈታውራሪ ገብሬ 50 ታጣቂ ዎች አስከትሎ ይሸኘኝ ነበር።ከ3ሰዓት ጉዞ በኋላ ፈታውራሪ ይግዛው ተሰናብቶን ተመለሰ።ቀጥሎም ቀጠሮውን አክብሮ አባይ ውቤ ከዘራፊዎች ጋር ሆኖ ምርጥ ምርጥ ፈረሶች በመንገድ ላይ ይጠብቀን ነበር። 6ሰዓት ዕረፍት ሆነ። ፊት አውራሪ ገብሬና አባይ ውቤን ኮኛክ ጋበዝኳቸው።ትንሽ እንደተጓዙ ፈታውራሪ ገብሬንና ሌሎች አብረው ይጓዙ የነበሩ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ አደረኳቸው፤አባይ ውቤ ብቻ ቀረ።ቀጥሎም አባይ ውቤም ተመለሰ፡ ወደፊት ካስፈለገ በ24ሰዓት ውስጥ 3000 ዘራፊዎች ፈረሰኞች ሰብስቦ ሊያቀርብ እንደሚችል ነገረው።ከዚህ በኋላ የሚያጋጥሙት አደጋዎች ወጂራት ዘራፊ ዎች ሳይሆኑ በአየሩ የሙቀት ሁኔታና የሚጠጣ የውሀ እጥረት



ብቻ ነበር።ከአፋሮች ጋር አነስተኛ ግጭቶችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ ለዚሁ ግን ራሳችን ለመቋቋም ተዘጋጅተናል በማለት ተዝናንቶ ጉዞውን ቀጥሏል።ሜይ 22 ኢገሬሬ የሚባል ቦታ ሊደርሱ ጣሊያኖች የተገደሉበትና የተቀበሩበት ቦታ መሆኑን አፋሮቹ ነገሩት ቦታውን ሊያገኙት የቻሉት ኢብራሂም የተባለው የመንገድ መሪ በእኩባቢው ያገኛቸው አፋሮች በመጠየቅ ነበር።ኢብራሂም ለሕይወቱ ስለፈራ ተሰናብቶ ወደ ሀገሩ ለመሄድ ጠይቆ ተፈቀደለት፤ 30ብር ተሰጠው፤ ከስጋቱ አላመለጠም፤ በማግስቱ ተገደለ። አስከሬኖች ተቆፈረው ተገኙ ሆኖም አመድ ሆነው ነው የተ ገኙት፤ የቻሉትን ለቅመው ወሰዱ በኢጣሊያ ባንዲራ ጠቀለሉት።አቦታው ከነበሩት የብረት ሰሳምታና ፋሺስታዊ ሰላምታ ተደርጐላቸው አፋሮች እንዲወሩት ከዚሁ ቦታ 4–5 ሰዓት መንገድ የእግር ጉዞ በቢያጊ ይመሩ የነበሩት ሌሎች ጣሊያኖች የተገደሉበት ፍራንኬቲ ሄዶ ለማየት ፈልጐ ነበር።ከመቀሌ ወደ ማይጨው ተመልሰው የመልስ ጉዞ ከፍራንኬቲ ለማድረግ ወይቀው ከተፈቀደላቸው ሁለት ጣሊያኖች አንዱ ታሞ ስለነበር ፍላጐቱ ሊሳካለት አልቻለም። በበቅሉ ለመሄድ ስላልቻለ በአራት ወታደሮች ሸክም ነበር የተጓዘው።አስከሬን አንሸከመም ብሎ እቢ ለማለት የሞከሩ ወታደሮች በዱላ ተገርፈው እንዲሸከሙ ተደርገዋል። ጁን 1 ቀን በአሰብ የኢጣሊያ ኮሚሳሪዮ (አውራጃ ገዥ)የሚመራ ሐኪም ያለበት የኢጣሊያ የኢንድጂኒ ወታደሮች አስቀድመው መልክተኛ መሠረት አስፈላጊ ነገር ይዘው ደረሱ ለትሁሉም ፈነጠቁ በማግስቱ ጪት ዋዲ የሚባል ቦታ ሲደርሱ የመኪና መንገድ ተሰርቶ አንድ ካሚዮን መኪና ተዘጋጅቶ ስለነበር ተሳፍረውን በማታ አሰብ አደረሳቸው። ጁን 10 በአሰብ የሚኖሩ ጣሊያኖች በተገኙበት በካቶሊክ ቤተክርስቲያን አጥንታቸው ተለቅሞ ከዛሬ 40 ዓመት በላይ በዳንካሊያ ለተገደሉ ጣሊያኖች ፀሎት ፍትሀት ተደረገላቸው።

በዚሁ ቀን ክቡር የኤርትራ ሀገረ ገዥ ኮራዶ ዞሊ የሚባለው ቴሌግራም ልኳል በዳንካሊያ ያለምንም አደጋ ስላደረጉት ጉዞ በተለይ አጥንታቸው የሚያኮራውን በደንካሊያ የሞቱ ጣሊያኖች በመገኘታቸው ደስታዬን እገልጽሎዎታለሁ። የጆሊየቲ ቡድን ዘማቾች አጥንት በክብር በምጽዋ ቤተክርስቲያን ለጊዜው እንዲያርፍ አደርጋለሁ፤ እርስዎ ወደ እናት ሀገራችን ይዘውት እንዲሄዱ ከመንግሥት ትዕዛዝ እጠባበቃለሁ።

# ምዕራፍ 12

# የማይጨው ጦርነት

በመጨረሻ ጊዜ ጣሊያኖች መላው ኢትዮጵያን ወረው በያዙበት ጊዜ ያካሄዱት ጦርነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሰሜኑ ብቻ የማይጨው ጦርነት ተብሎ ይታወቃል። የኢጣሊያ የመጨረሻ ወረራ እንደ ዓድዋ በአንድ ቀን፣ በአንድ ጦር ግንባር በአንድ ሰው መሪነት አልተካሄደም። በአራት ጦር ግንባሮች በተለያዩ ቀናትና ወራት፣ በተለያዩ የጦር መሪዎች ነበር የተካሄደው። በተካሄደበት ጊዜ ቅደም ተከተል ብንሄድ ማርሻል ባዶሊዮ የኢጣሊያ ጦር የሰሜን ጦር ግንባር ዋና አዛዥና የደቡብ ጦር ግንባርም የበላይ አዛዥ የነበረው በደረሰው መጽሐፍ፣እንዲሁም አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ በደረሰው መጽሐፍ ጦርነት ስለተደረጉበት ቀናት ልዩነቶች ይታያሉ።

1ኛ/ የመጀመሪያ ጦርነት በራስ ካሣና በራስ ስዩም የጦር አዝማቾች የተመራው የተካሄደው በቴንቤን፣ አንደኛው የቴንቤን ጦርነት ተብሎ የሚጠራው፣የቱካሄደበትም ጥር 11/12/13 ቀን1928 ዓ/ም በአቶ ተክለፃዲቅ ግን ጥር 14 ቀን፣በኤውሮጳውያን ጃንዋሪ 20/21/22 ቀን 1936 ዓ/ም ነበር።

2ኛ/ጦርነት የተካሄደው ጣሊያኖች የእንደርታ ጦርነት ብለው የሚጠሩት አቶ ተክለፃዲቅ የአንባ አራዳም ጦርነት ብሎ የሚጠራው በራስ ሙሉጌታ የጦር ሚ/ሩ አዝማችነት የሚመራው በእንደርታ እምባ አራዳም ተራራ ሲሆን የተካሄደበትም ከየካቲት 2 እስከ የካቲት 11/1928 ዓ/ም በአውሮጳውያን ከፌብሯሪ 10 ቀን –19ቀን 1936 ዓ/ም ነበር።

3ኛ/ ጦርነት የተካሄደው በራስ ካሣና በራስ ስዩም የጦር አዝማችነት ነው፣ የተካሄደው በተምቤን፣ሁለተኛው የተምቤን ጦርነት ተብሎ የሚጠራው፣የተካሄደበትም የካቲት 19/20 እና21ቀን 1928 ዓ/ም በኤውሮጳውያን ፌብሯሪ 27/28/29 ቀን 1936 ዓ/ም ነበረ።

4ኛ/ ጦርነት የተካሄደው በራስ እምሩ መሪነት በሽሬ የካቲት 21/22/23/24 ቀን 1928 በአውሮጳውያን ፌብሯሪ 29 ማርች 1/2/3 ቀን 1936 ዓ/ም ነበር።

5ኛ/ አምስተኛውና የመጨረሻው ጦርነት የተካሄደው በአፄ ኃይለሥላሴ መሪነት በማይጨው፣ጣሊያኖች የአሸንጌ ሐይቅ ጦርነት ብለው የሚጠሩት፣የተካሄደበትም በመጋቢት 23/24/25 እና 26 ቀን 1928 ዓ/ም በአውሮጳውያን አፕሪል 1/2/3/4 ቀን 1936 ነበረ።






ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት

የማይጨው ጦርነት ጀግና



ማርሻል ባዶሊዮ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ዘማች የኢጣሊያ ሠራዊት ዋና አዛዥ



ራስ ሙሉጌታ የመከላከያ ሚኒስትር የእንደርታ ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ዋና አዛዥ

የእንዳርታው ጀግና ራስ ሙሉጌታ



የኢጣሊያ መንግሥት አስተድዋ ባወጣው እቅድ መሠረት ጦርነቱ መጀመር የነበረበት መስከረም ወር 1929 ዓ/ም ፀአውሮጳውያን ለሴፕቴንበር 1936 ዓ/ም ነበረ። ነገር ግን የኢጣሊያ መንግሥትና የኢጣሊያ ፋሽዝም መሪ ዱቼ ሙሶሊኒ ጦርነቱ በኦክቶበር 1935 ዓ/ም ተቀምት 1928 ዓ/ም እንዲጀመር ትእዛዝ ስለተሰጠ በትእዛዙ መሠረት ጊዜው ማፋጠን ግድ ሆነ፤ምናልባት የኢጣሊያኖች መሪ ጊዜው እንዲተድም ያደረገበት ከዓድዋ ጦርነት 40ኛው ዓመት እንዲገጥም በማሰብ ይሆናል። በሰው ኃይል ኢጣሊያ 10 ዲቪዝዮኖች የጣሊያን ወታደር በኤርትራ፤ 1 የሶማሊያ 5ዲቪዝዮን የኢጣሊያ ወታደር በተጠባባቂ በኢጣሊያ ሀገር ዝግጁ እንዲሆን ተደርጎ 100.000 የቀለም ወታደሮች 50.000 ከኤርትራ 50.000 ከሶማሊያ እንዲመለመሉ ተደርጓል።[1]

ዱቼ ኦክቶበር 3/1935 የመረብ ወሰን እንዲጣስ ትእዛዝ ሰጠ። በማርሻል ባዶሊዮ ወታደራዊ ግምት በዲሴንበር ወር መጀመሪያ ላይ ብቻ ከአዲግራት መቀሌ ለመዝለቅ ታስቦ ነበር። ነገር ግን ከላይ የመጣ ትእዛዝ አሁንም ጊዜው እንዲፋጠን ስለታዘዘ ወደ መቀሌ ዘልቆ ለመግባት ከኖቬንበር 3 እስከ 8 እንዲሆን ተወሰነ።ወረራው እንዲፋጠን ያስቻሉበት ምክንያቶች ሀ) የኢትዮጵያ ጦር ተሰብስቦ ከደሴ በስተደቡብ ይገኝ ስለነበረ ለ) ከሃዲው ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳ የኢጣሊያኖች እገዛ ተቀብሉ ትግራይ ከጣሊያኖች ጋራ ተባብራለች ሕዝቡ ልዩ ድጋፍ ባይሰጥም ገለልተኛ እንዲሆን አደርጋለሁ ብሉ ተስፋ ስለሰጣቸው ነበር። ሁኔታው በዚህ ዓይነት እንዳለ ነው ማርሻል ባዶሉዮ የጦር እዛዥነቱ ስልጣን ከማርሻል ደቦኖ የተረከበው። መቀሌ የሰፈረው 100.000 የኢጣሊያ ወታደር አስፈላጊ አልነበረም። ብቻውን የተገለለ ሆኗል። ስንቅና ትጥቅም ለማመላለስ ችግር ፈጥሮ ነበር።

## የመጀመሪያ ግጭቶች

ዲሴንበር 15 ተን 1935 ዓ/ም 1000 የሚሆኑ የኢጣሊያ ባንዳዎች ለሰላ ብቻ ወደ ደንጉሩና የተባለው ቦታ ደርሰው እስከ ተከዜ ለመዝለቅ ተልከው የነበሩ፤ ተልእኳቸውን ሳተው በራስ እምሩ ወታደሮች በድንገት ስለተከበቡ፤ጥሰው ለመውጣት ባደረጉት ውጊያ 9 የኢጣሊያ መኰንኖች፤ 22 የኢጣሊያ ወታደሮች ፤370 ኤርትውያን ሞተው ወይም ቆስለው ከሞት ያመለጡ ወደ እንዳሥላሴ ማታውኑ ገብተዋል።[2] አቶ ተክለፃዲቅ 400 የኢጣሊያ ወታደሮች ሞተው ተገኝተዋል ብለዋል።[3]

1. Badoglio : La Guerra d'Etiopia p. 14
2. Badoglio : La Guerra d'Etiopia p. 45
3. ተክለፃዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ኃይለሥላሴ ገጽ.174/





ራስ ካሣ የተምቧን ጦርነት ጀግና
ራስ ሥዩም የተምቧን ጦርነት ጀግና

የተምቧን ጦርነት ጀግና ራስ ሥዩም






አቡላ ራስ ካሣ እና አቡላ ራስ ሥዩም የተምቧን ጦርነቶች የኢትዮጵያ ጦር የጦር መሪዎች

Capi etiopici non fortunati:



Ras Cassa.

ዲሴምበር 20 በእምባፀለፌ ዓቢይ ዓዲ አጠገብ በተደረገው ጦርነት 13 የኢጣሊያኖች ከእዚህ ፀለሬ ማፈግፈግ ግድ ሆኖባቸው ነበር።

በምዕራብ ጦር ግንባር በሽሬ 12.000 የሚደርስ የኢጣሊያ ጦር ወደፊት እያጠቃ እንዲገሰግስ ታዞ፤ ዲሴንበር 25 ቀን 1935 ዓ/ም ስለቅለቃ አልፎ እፍጋጋ ሲደርስ ከራስ እምሩ ጦር ተዋግቶ ጉዳት አድርሰውበት ሊከታተላቸው ስላአልቻለ 10 ቀን አቦታው ከቆየ በኋላ ተመልሷል። የተሰሉና የሞቱ 7የጦር መኮንኖች 14 የኢጣሊያ ወታደሮች 122 ኤርትራውያን ነበሩ።

የመጀመሪያዎቹ ግጭቶች በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተደመደሙ።

## ሀ) የመጀመሪያ የቴምቤን ጦርነት

የመጀመሪያ ቀን ጥር ወር ማይ መረታ ወንዝ አጠገብ ከባድ ጦርነት ተደርጎ፤ በጨበጣ ውጊያ ሳይቀር ተካሄዶ፤ ገዥ ቦታዎች አንዱ ወገን ሲነጥቅ ሌላው ወገን ሲመልስ ከዋሉ በኋላ በቀኑ መጨረሻ ጣሊያኖች እንደቀናቸው ነው የገመገሙት። የሁለተኛው ቀን ዋሪየው በሚባለው ቦታ በመሸገው የኢጣሊያ ጦር ኃይሉን ለማሳየት ያህል ከምስራቅ በመገስገስ ላይ የነበረው ሌላ የኢጣሊያ ጦር በቀላሉ የሚገናኝ መስሎት ከሰፈሩ ራቅ ብሎ በመሄዱና ደብረ እምባ ደርሶ በመስፈሩ ኃይለኛ ውጊያ ከኢትዮጵያ ጦር ስለገጠመው ወደ ኋላ እያፈገፈገ ሄዶ እስከ ጦር ሰፈሩ ዋሪዬው ሲደርስ፤ እያሸነፈ በመሄድ የተደሰተ የኢትዮጵያ ሠራዊት እየተከታተለው ነበር።

በዚሁ ጊዜ ዋሪዬው ያለው የኢጣሊያ የ ጦር ሰፈር ዙሪያው በአደገኛ ሁኔታ ስለተገኘና የያዘውን መሬት ለቆ ወደ መሀል ጦር ሰፈሩ ለመሰባሰብ ተገዶ ነበር። ይኼም የኢትዮጵያ ጦር ወደ ዝባን ደስና፤ደንበላ የሚባሉ ቦታዎች ለመዝለቅ ከኢጣሊያኖች ይዞታ በስተጀርባ ሆኖ ለመዋጋት አስችሎት ነበር። የኢትዮጵያ ጦር የዋሪየው ጦር ሰፈር ዞሮ አልፎ ወደ ሐውዜን በመዝለቅ መቀሌ ከሰሜን የሚያገናኙትን መስመር ለመቁረጥ ያስችለው ነበር። ይህ ቢሳካ ደግሞ ጦርነቱ ሌላ መልክ ይይዝ ነበር። ቀኑን ሙሉ ይህ የዋሪየው ይዞታ መከበር በቀር ድል የኢጣሊያኖች እንደነበረ በመገመት ማርሻል ባዶልዮ እንደሚቀናው ተስፋ ቢያደርግም የባሰም ሊመጣ ይችላል ብሎ በማሰብ ዕድል ካልቀናው ግን በመቀሌ የሰፈረው 70.000 የኢጣሊያ ጦር ወደ ኋላ ለመመለስ አስቦ ነበር። ነገር ግን በ3ኛ ቀን፤ጥር 3ቀን የኢትዮጵያ ጦር ጥቃቱ አልገፋበትም።መንቀሳቀሱም ስላቆመ ተፈጥሮ የነበረው አደጋ ሊወገድ ችሏል።

እቶ ተክለፃዲቅ በኢትዮጵያ ወገን የደረሰው ጉዳት 1000 የሞተው 2000 የቆሰለው ሲገምተው በኢጣሊያ ወገን 1500 ሞተው የተማረኩም እንደነበሩ ጽፏል። ማርሻል ባዶልዮ






ራስ እምሩ የሽሬ ጦር ግንባር አዋኸ

Ras Immeru.



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ማይጨው ... ጦር ግንባር ከአዲስ አበባ ሲነሱ

(fot. Associated Press - Londra)
Hailé Selassié in calzature sportive parte per il fronte

በመጽሐፉ ከኢጣሊያ ወገን 60 የጦር[1] መኮንኖች 605 የኢጣሊያ ወታደሮች 417 ኤርትራውያን መሞታቸውን ጽፏል።[2] በኢትዮጵያ ወገን ግን ከአዲስ አበባ የተሰጠ መግለጫ መሠረት በግድረግ የራስ ካሣ ጦር 8000 ሰው እንደተገደሉበት ይኸውም ከኢጣሊያኖች ይበልጥ እንደነበረ ይገልጣል።

የአቶ ተክለሃዋርያት መኩሪያና የማርሻል ባዶሊዮ በአጠቃላይ የጦርነቱ አቀራረብ ተመሳሳይ ቢሆንም የአንድ ግንባር የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ከሌላ የጦር ግንባር እርዳታ እንዳይደርስለት ጣሊያኖች አደናቅፈዋል በማለት አቶ ተክለሃዋርያት የገለፁት ግን የማርሻል ባዶሊዮ አገላለጽ በተቃራኒው የገለፀው ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ ለመረዳዳት ሐሳቡም ፍላጎትም እንዳልነበራቸው ብሎ በመገረም ደጋግሞ ጽፏል። በዓድዋ ጦርነት ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው በአንድ መሬ ተሰባስበው ተዋግተው እንዳሸነፉ ሁሉ ጣሊያኖችም ለምስቱ ጦር ግንባር በመከፋፈላቸው ለከባድ ሽንፈት እንደተጋለጡ ሁሉ በአሁኑ ጦርነት ደግሞ የተገላቢጦሽ ሆኖ ጣሊያኖች በአንድ ጦር አዛዥ ስር ሆነው ተዋግተው ሲያሸንፉ የኢትዮጵያ ጦር ባአራት ጦር አዛዦች በመመራት ለአራት ጦር ግንባር በመከፋፈላቸው ባያሸንፉም ባላቸው አቅምና ጀግንነት እንዳይዋጉ ተደርጓል።

ማርሻል ባዶሊዮ የመጀመሪያ የቴምቤን ጦርነት ባደረገው ግምገማ በዓድዋ ጦርነትም ተካፋይ ሆኖ ስለነበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀግና ዘር መሆኑን፤ አሁንም እንደ ድሮ ጀግንነቱ 40 ዓመት በፊት በዓድዋ ጦርነት እንደነበረ እንዳለ ነው ብሎ መስክሯል፤ የተፈጥሮ ጀግንነቱ አሁንም አልተለወጠም ብሏል። አፄ ኃይለሥላሴ ብዙ ጥሩ ችሎታ ሊኖረው ይችላል የጀግንነት መንፈስ ግን የለውም ብሏል።

የራስ ካሣ ሠፈርም የሰፈረው የኢጣሊያ ጦር ሰቆጣ ዞር አልፎ ወደ መቀሌ የሚወስደው መንገዱ ለማቋረጥ በሚያስብበት ጊዜ፤ ራስ ካሣ ለንጉሡ እርዳታ እንዲላክለት በሚጠይቅበት ጊዜ ንጉሡ ለራስ ሙሉጌታ ትእዛዝ አስተላልፎ በአፋጣኝ በጥቂት ሰዓቶች እንዲደርሱ ለማድረግ ስለማን በማጣቱ ከኮረም የ6 ቀን የእግር ጉዞ እርዳታ እንዲላክለት ብሎ መልስ ሰጠው።

የኢትዮጵያ ወታደር ጀግንነት ቢኖረውም አዛዦች አልነበሩትም። ጉድለቱ ከሁሉ የባሰ የንጉሡ ነው ብሏል። የመገናኛ ራዲዮ የነበራቸው በጠላት እየተጠቀምኩ ለእኔ ብቻ ነበር የሚያገለግለው ብሏል።

የመጀመሪያ የቴምቤን ጦርነት ያበቃው በኢትዮጵያ የበላይነት ነበር።

1. ተክለሃዋርያት መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ኃይለሥላሴ ገጽ.170
2. Badoglio : La Guerra d'Etiopia p. 68-70



ዝነኛው የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኢጣሊያ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ በማውገዝ በመንግሥታት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ንግግር ሲያደርጉ።



Il Ministro inglese Anthony Eden




የኢትዮጵያ መልእክተኛ ተክለሐዋርያት በመንግሥታት ማሕበር ጠቅላላ ጉባኤ ንግግር ሲያደርጉ



(Arch. ... - Parigi)

Il rappresentante dell'Etiopia, Teclé Hawariate, si accinge a parlare nella seduta dell'11 settembre a Ginevra



አቶ ተክለሐዋርያት እና ፈረንሣዩ በመንግሥታት ማሕበር ለኢትዮጵያ ጥብቅና የቆመ ጋስቶን ዥዝ ከባለቤቱ ጋራ

L'ora del sì alla Società delle Nazioni . Da sin. a destra: Teklé Hawariate, l'avvocato Gaston Jèze e Madame Jèze

## ለ) የእንደርታ ጦርነት

ማርሻሉ ባዶሊዮ ባጠጣው እቅድ መሠረት የተካሄደው ጦርነት ነው። እቅዱ ምንም እንቅፋት ሳይገጥመው ተፈጽሟል። ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም የነበራቸው የወታደር ብዛት ራስ ሙሉጌታ ከነበረው 80.000 ወታደር ግማሽ ብቻ ነበረ፣ የስጠው ውጤት ግን ከሁሉ ዝቅተኛ ነው። የኢጣሊያ ጦር ወደ አንባ አራዳም በሚገሰግስበት በአንደኛ ሁለተኛ ሦስተኛ ቀን ምንም ተኩስ ሳያጋጥመው ነበር የተጓዘው። በአራተኛው ቀን ፌብራሪ 13ቀን ተራራውን በግራና በቀኝ ለመከበብ ይገሰግስ የነበረው የኢጣሊያ ጦር በቀኝ በኩል በጠመንጃና በመትረየስ ከፍተኛ ተኩስ ገጠመው ነገር ግን ጣሊያኖች አጠፋውን በመመለስ የመጣባቸውን ጥቃት ሊመለሱ ችለዋል።

ሌላ ተቃውሞ ቢያጋጠማቸውም ለቀኑ የታቀደው ግባቸውን ሊያከናውኑ ችለዋል። ፌብራሪ 13 እና 14 ቀን ዝግጅት ለማድረግ ዕረፍት ሆነ። ስድስተኛው ቀን ፌብራሪ15 ቀን አንደኛና ሦስተኛ የኢጣሊያ የኮር ወታደሮች ከተራራው በስተደቡብ ተገናኝተው ከበባውን የሚያከናውኑበት ቀን ነበረ።ፌብራሪ 13 ፣14፣ 15 ከባድ ጦርነቶች እየተካሄዱ ከቆዩ በኋላ አንደኛው ኮር ተራራውን ለመከበብ የተወሰነለት ቦታ ለሳልደረሰ የኢትዮጵያ ጦር ሜዳውን በመልቀቅ ሸሽቶ ወደ አንባ አላጂ፣ በሉዋ ሊያመልጥ ችሏል።

ፌብራሪ 16 የኢጣሊያ ጦር እየተከታተለ እያጠቃቸው ነበር። 17፣ 18፣ 19 ጣሊያኖች በጦር አይሮፕላኖች እየተከታተሉ ይወጓቸው ነበር ጣሊያኖች በኢትዮጵያ የነበራቸው የጦር አይሮፕላኖች ብዛት 300 ይደርሱ ነበረ። 546 በረራቸው አድርገው 396 ቶን ፈንጂዎች ጥለዋል። 30.000 መትረሶች ተኩሰዋል። በእንደርታ ጦርነት ጣሊያኖች የደረሰባቸውን ጉዳት 36 የጦር መኮንኖች 821 የኢጣሊያ ወታደሮች 145 ኤርትራውያን ነበረ። በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው ጉዳት በኢጣሊያኖች ግምት 20.000 ወታደሮች ነበር። ራስ ሙሉጌታ ፌብራሪ 15 ቀን ከጦር ሜዳ ተደብቆ ወጣ፣ ወታደሩም የራስ ሙሉጌታ መጥፋት ሲሰማ ሁሉም መሸሽ ጀመረ። ራስ ሙሉጌታ በራያና አዘቦ ተገድሏል።ራስ ካሣና ራስ እምሩ ስለ እንደርታ ጦርነት አልተጨነቁም፣ማርሻል በማርሻል ባዶሊዮ ሂስ (ታሰንዝሮባ) [1] በአንደኛው የቴምቤን ጦርነት ጊዜ ራስ ካሳ እርዳታ ስላልደረሰው ስሞታ ሰንጉሡ ዓት አልተቆጠበም። የደረሰበት ሽንፈትም በራስ ሙሉጌታ ያሳበበ ነበር። አንድ መድፍ እንኳን ቢላክለት ቀረዶውን ያለው የኢጣሊያ ጦር በግሙደም ለሚቀጥለው ሁሉ መንገድ ከፋች ይሆን ነበር ብሏል።[2]

---

1. Badoglio : Ibd p. 112

2. Badoglio : Ibd p. 118



ከሐዲዎች ራስ ጉግሣ አርአያ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ





(Associated Press)
Degiac Hailè Selassiè Gugsa (genero del Negus) fa atto di sottomissione alle autorità italiane in Adigrat (12 ottobre 1935-XIII)

ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት

Ras Gugsa Araia discendente diretto di Re Giovanni



Il Console d'Italia e il cap. med. del Consolato ricevuti solennemente nella tenda reale di Ras Hailù. Al centro il Ras (1929).



Ras Hailù, ex signore del Goggiam tenuto per molti anni prigioniero dal Negus

## ሐ) ሁለተኛ የቴምቤን ጦርነት

ጦርነቱ የተካሄደው በወርቅ አምባ አካባቢ የኢጣሊያ ጦር ከሰሜንና ከደቡብ እየገሰገሰ በመከበቡ ከዓቢይ ዓዲ በስተምዕራብ ከበባው እንዲጠናቀቅ ነበር። ፌብሯሪ 27 ሌሊት የሁለቱ ተፋላሚዎች ጫፎች ከብዙ ትንቅንቅ ውጊያ በኋላ በኢጣሊያ ወታደሮች ቁጥጥር ሆነ፤ በዚሁ ቀን ልዩ ጀብድ የሰሩ ኤርትራውያን ነበሩ። ፌብሯሪ 28 እቅዱ በኢትዮጵያ ጦር ተይዞ ወደ ሚገኘው ወደ ደብረ አምባ መገስገስና መቆጣጠር ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ባለፈው ቀን በደረሰበት ጉዳት የተዳከመ ቢሆንም የተፋፋመ ውጊያ በማድረግ ጦር አሪዮፕላን በመታገዝ በደቡብም ወደ ምዕራብ ከበባው ሳይደረግበት ለማምለጥ ችሎ ነበር። በ29 ከበባውን የሚያካሄዱ የኢጣሊያ ወታደሮች ሦስት ኪሎ ሜትር ከዓቢይ ዓዲ ቢገናኙም የተከበቡ የራስ ካሣና የራስ ስዩም ወታደሮች በማይታዩ በታዎችና ጉድጓዶች እየተደበቁ ከሞትና ከመታሰር እያመለጡ ውጊያውን ቀጠሉ። ገሚሱ እየተዋጋ ወደ ደቡብ መንገድ ይከፍት ነበር። ገሚሱም ከመታሰር ሞት እየመረጠ ይዋጋ ነበረ።በዚሁ ጊዜም ባዶሊዮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘር የወረሰው ጀግንነት እንዳለው በማለት በአድናቆት መሰከሮለታል።[1] ከማርች 1 እስከ ማርች 6 ቀን ጣሊያኖች የማፅዳት ዘመቻ ቀጥለውበት ውኋል። ብዙ ሰውም ገደሉ ብዙ ሰውም ማርከዋል አሪዮፕላኖችም ያለማቋረጥ ፈንጂዎች ይጥሉ ነበረ።

በኢጣሊያ በኩል የደረሰው ጉዳት 34 የጦር መኮንኖች 359 የኢጣሊያ ወታደሮች 188 ኤርትራውያን ነበሩ። በኢትዮጵያውያን በኩል 8000 ወታደሮች እንደ ሞቱና እንደቆሰሉ ተገምቷል

ራስ ካሣና ራስ ስዩም ከጦርነቱ እምልጠው ከንጉሡ ጦር ተቀላቅለው እንደገና ተዋግተዋል።

## መ) የሽሬ ጦርነት

በራስ እምሩ በሚመራ ጦር ላይ የዘመቱ ሁለት ሙሉ የኢጣሊያ ኮር ወታደሮች ነበሩ፤ ሁለተኛና አራተኛ የሚባሉ።የራስ እምሩ ጦር በመጀመሪያ ከጣሊያኖች ጋራ ያደረገው ግጭት በእንዳባጉና ሳይታሰብ የኢጣሊያ ጦርን ከበው ጉዳት ካደረሱ ባኋላ ወደፊት ገፍተው 25 ኪሎ ሜትር ከአክሱም ደርሰው ነበር። በወቅቱ ጣሊያኖች መቀሌን ሲይዙ ራስ እምሩም ወደ አስመራ ይገሰግሳል ተብሎ ተፈርቶ ነበር። ምናልባት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ይኸ እቅድ ሊኖር ይችላል። በኋላ ግን ራስ እምሩ አብዛኛው በመከላከል ነበረ ያዘነበለው። ማጥቃቱም በድንገት ሳይታሰብ ነበር ያካሄድ የነበረው።

1.Badoglio : ibd p. 133







Olol Dinle, Sultano di Gheledi
Medaglia d'argento

የኦጋዴን ከሐዲ ኦሎል ዲንለ የገለዲ ሱልጣን ከጣሊያኖች የብር ኒሻን የተሸለመ

Il Duce e il Sultano Aba Giobir Abdullà del Giimma

የጂማ ከሐዲ አባ ጆቢር ከዱቼ ጋር

ራስ እምሩ የነበረው ችግር ለብዙ ዓመታት በጐንደርና በጎጃም የነበሩ የኢጣሊያ ቆንሲላዎች ብዙ ሰበካ አካሄደው ነበር [1]።በዚሁ ምክንያት ለምሣሌ ጎጃሞች ከሀገራቸው ውጭ እንዋጋም በማለት አድመው እንደነበረ ራስ እምሩ ለንጉሡ የፃፈው አንድ ደብዳቤ ያስረዳል። [2]የኢጣሊያ አንባገነን መሪ ዱቼ ጦርነቱ እንዲጣደፍ ያዘዘው በዓድዋ 40ኛው ዓመት የበቀል ድል ለኢጣሊያ ሕዝብ ለማስማት ጓጉቶ ስለነበረ ነው። የሽሬ ጦርነት እንቅስቃሴ የተጀመረው የሁለተኛ ኮር አንድ አካል የሆነው ወደ ሰለቅለቃ በሚጓዝበት ጊዜ ማርች 1ቀን የዓድዋ ድል ነበር ‹በእኛ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ/ም›

ሳይታሰብ ኃይለኛ ጥቃት ከኢትዮጵያ ጦር ተሰንዝሮበት ከፍተኛ ጉዳት ስላደረሰ፤ በዚሁ ቀን የዓድዋ መታሰቢያ ቀን የሙቱት የኢጣሊያ ነጭ ወታደሮች በሌሎች ጦር ግንባሮች በአንድ ቀን ከተገደሉት ወታደሮች ብዛት ነበሩቸው። በዚሁ ምክንያት ራስ እምሩ የነበረው ጦር ጣሊያኖች ከፍ አድርገው በመገመት ስጋት ስላደረባቸው የኢጣሊያ የኮር አዛዥ ጦሩ የመከላከል አቋም ይዞ በተጠንቀቅ እንዲቆም ስላደረገው ጦሩ በቀኑ የተመደበለት ግብ ሳያደርስ ቀረ።

ለሚቀጥለው ቀን የሚደረገው ግስጋሴ አንድ ቀን እንዲዘገይ ከጠቅላይ ጦር አዛዥ ፍቃድ ጠይቆ ተፈቀደለት። የኢትዮጵያ ጦር ግን ከጦርነቱ በኋላ ግንኙነቱን ከጣሊያኖች ጋራ አቋርጦ ወደኋላ ተመልሶ ነበረ። ማርች 2ቀን ሦስት የኢጣሊያ ዲቪዚዮኖች ጉዞቸውን ወደፊት ቀጠሉ። ከ7 ሰዓት እስከ11 ሰዓት ከባድ ተቃውሞ አጋጥሟቸው ነበረ።ሆኖም ጣሊያኖች በአረዮፕላኖች እየታገዙ መልሶ በማጥቃት መሰሏቸው። በዚሁ ቀንም የኢጣሊያ ጦር የተመደበለት ግብ ሳያደርስ ቀርቷል። ማርች 3 የኢትዮጵያ ጦር ወደ ኋላ ማፈግፈጉን ቀጠለ። ተከዜ ወንዝ በሚደርስበት ጊዜ የኢጣሊያ ጦር አሬዮፕላኖች ቦምብ ናዳ ያወርዱበት ነበር። የኢጣሊያ ጦር ችግር ሳይጋጥመው ቢጓዝም የኢትዮጵያ ጦር በፍጥነት በመሸሹ ለመገናኘት ሳይችል ቀረ። በዚሁ ዓይነት የሽሬ ጦርነት ፍፃሜ ሆነ። በጣሊያኖች የደረሰው ጉዳት 63 የጦር መኮንኖች 894 የኢጣሊያ ወታደሮች 12 ኤርትራውያን ነበሩ።በኢትዮጵያ የደረሰው ጉዳት 400 የሚገመቱ ወታደሮች ነበሩ። በአሬዮፒላኖች የደረሰው ጉዳትም የሞቱና የቆሰሉ 300 የሚገመቱ ነበር። በማርሻል ባዶሊዮ ግምት ራስ እምሩ አመጽ ወደሰፈነበት ወደ ጎጃም ሸሽቶ ገብቷል ብሏል። አቶ ተክለ ፃዲቅ ግን ራስ እምሩ ወደ አሸንጌ ሄዶ ከንጉሡ ጦር ጋራ ተደባልቆ ተዋግቷል ብሏል።የራስ እምሩ ጦር ጣሊያኖችን ለጦር ነት በማስገደድ እንጂ ሳይገደድ፤ ራሱ ጥቃት በመፈጸም እንጂ ሳያስበው ጥቃት ሳይደርስበት በነበረው በትክክል የማይታወቅ ከ25000 እስከ 50000 የተገመተው አነስተኛ የሰው ኃይል የጦር ስልት በተሞላበት ጀግንነት ተዋግቶ ግዳጁን ፈጽሟል።

1. Lessona : ibd p. 113

2. Badoglio : ibd p. 173



# ሰ) የአሸንጌ ሐይቅ ጦርነት የማይጨው ጦርነት

ያለፉ ጦርነቶች ሲካሄዱ የንጉሡ ጦር ከደብረ ሲና ከቆቦ መሃል ይገኝ ነበር። የንጉሡ ጦር ከ30.000 እስከ50.000 የሚገመት ማርች 21 ከአሸንጌ ሐይቅ በስተሰሜን ሰፍሯል። ንጉሡ የማሸነፍ ዕድል እንደሌለው እያወቀ የተዋጋው ዋና ጦርነት በንጉሡ የሚመራው ነው የሚል የቆየ የኢትዮጵያ ባሕል ስላለ በሹማምንቶችና በሕዝቡም ጭምር ምክር ተገፋፍቶ ነው።

ጣሊያኖች በንጉሡ ጦር ሰፈር ማርች 26 ሰብሰባ ተደርጎ አንዳንድ ሹማምንቶች ግን የጦርነት መግጠም ደጋፊዎች እስከ አሁን ለራሱ ዘውድ በተደረጉ ጦርነቶች እጁን ካማጥር መቆቀመጡን እያጋለጡ ስለሳቁበት፤ በወሳኝ ጉዳዮች ግልጽ አቋም መውሰድ የማይወድ ኃይለሥላሴ የማጥቃት ጦርነት ለመፈጸም ተገድዶ እንደነበረ መረጃ ደርሷቸው ነበረ። ማርሻል ባዶልዮ ትልቁ የማጥቃት እርምጃ የሚወሰድበት ቀን ለኤፕሪል 6 እንዲሆን ወስኖ ነበረ።ንጉሡ ለራስ እምሩ ማርች 23 ቀን በፃፈው ደብዳቤ ራስ ሙሉጌታን በማመልከት ከት፤ሰሙን ሳይጠቅስ፤በሚገባ ሳይዋጋ ብዙ ጉዳት ሳይደርስበት ተሸነፈ። ይኼውም የኢትዮጵያ ሠራዊት በመላው አውሮጳ ያለው የጀግንነት ዝና እንዲጠፋ አድርጎታል በማለት ጽፏል። ኤፕሪል 1ቀን በ11ሰዓት ከ45 ደቂቃ ከኢትዮጵያ ተዋጊዎች የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ እሉበት ተጠግተው መጡ፤ በዚሁም ተኩስ ተጀመረ። ንጉሡ በመካንንና በሆራ ተራራ ቅዳሜ 28 ማርችና ሰኞ 30 ማርች የማጥቃት እርምጃ እንደሚጀመር ለእቴጌ አስታውቆ ነበር።እንደተለመደውም ቴሌግራሙ ተጠልፎ ለኢጣሊያኖች ይደርስ ነበር። ኤፕሪል 1 ቀን ጠዋት የተጀመረው የኢትዮጵያ ማጥቃት ያተኮረው ኤርትራውያን ወደሉበት ምሥራቃዊ መካን ጦር ግንባር ነበረ። ምናልባት ደካማ ጉን ይሆናል ብሉ በማስ ብ፤የበለጠ ወደ ምሥራቅ በመዞር የጨበጣ ውጊያ ሳይቀር ኃይለኛ ጦርነት ተካሄዷል። ከቀኑ በ10 ሰዓት እንደገና በምስራቅና በምዕራብ አቅጣጫ ጥቃት ሞከረዋል። በ11 ሰዓት የኢትዮጵያ ጦር በሁሉም አቅጣጫ ማፈግፈግ ሲጀምር ጣሊያኖች በመድፍና በመትረየስ አሬዮፕላኖች ይደበድቡት ነበር።በቀኝ በኩል ጣሊያኖች ያስታጠቋቸው ራያና አዘቦ ይወጉት ነበረ። ጣሊያኖች እንደሚሉት በሸዋ ገርዎች በነበራቸው ጥላቻ ለኢጣሊያኖች ከፍ ያለ እርዳታ አድርጓል ብሏል። ሐቁ ግን ራያ ጣሊያኖችን ለመርዳት ያነሳሳቸው በዘር ጥላቻ ወይም በድሮ ገርዎቻቸው ጥላቻ ወይንም ጣሊያኖችን በመውደድ ሳይሆን በኋላ ቀር ሰውን መስለብ ባሕላቸው ፍላጎታቸውን ለማርካት አመቺ ሁኔታ ስለፈጠረላቸው ብቻ ነው። ጣሊያኖች ባዘዙዋቸው መሠረት በንጉሥ ላይም ተንኩል መክረው ነበር።

ነገር ግን በንጉሡ ክቡር ዘብ ከሽፏል። ጣሊያኖች ያቤ፦ ከዳቸው 3000 ጠብመንጃዎች ብቻ ነበረ ራሳቸው በዘረፉት መሣሪያ ግን እስከ7000 ደርሰው ነበር። ማርሻል ባዶሊዮ እንዳለፉት ጦርነቶች የኢትዮጵያ ወታደር የክቡር ዘበኛም ቁጥር ቢታላቅ ወኔ እንደተዋጋ በአድናቆት መስክሯል።የኢትዮጵያ ጦር ሽሽቱ እንዳይታወቅበት ዝናብ እየጠላ በነበረበት ወቀት አፕሪል አንድ ቀን ይተኩስ ነበረ። ከአፕሪል አንድ ቀን ጀምሮ በተከታታይ ቀናት ኤፕሪል 2–4 ጣሊያኖች በወታደሮችም፣በራያ አዘቦችም በጦር አሪዮፕላኖችም እያሳደዱ የንጉሡ ጦርን ይወጉት ነበር። በጣሊያኖች የደረሰው ጉዳት 68 የጦር መኮንኖች 332 የኢጣሊያ ወታደሮችና 873 ኤርትራውያን ሲሆን፣ከኢትዮጵያ ወገን የተረጋገጠው 8000 ወታደሮች ነበር።

## ማጠቃለያ

በኢጣሊያ ወረራ በተደረጉ ጦርነቶች በዘፈን ለሕዝብ እንደሚነገረው ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የማይጨው ጦርነት ተብሎ መጠራት የለበትም። በአራት ጦር ግንባር የተደረጉ ጦርነቶች ናቸው። ለእያንዳንዱ ለሠራው ሞያ ምስጋና ይገባዋል እንጂ ሌሎች የሰሩት ሞያ ሁሉ ለንጉሡ መስጠት የለበትም። ንጉሡ በነበረው መሣሪያ ብልጫ የበለጠ መስራት ይገባው ነበር ወይንም ውጤት በማያመጣበት ሁኔታ ይገኝ ስለነበረ ለይሉኝታ ጦርነት ከመግጠም ተቆጥቦ ወደውጭ ሀገር ሄዶ እንዳደረገው ለውጭ ወዳጅ መንግሥታት አቤቱታውን ማሰማት ቢቀጥል በተመረጠ ነበር። ማይጨው የተዋጋ ጦርም ጉዳት ሳይደርስበት ለደፈጣ ውጊያ የሚዋጋ አንድ የተደራጀ ኃይል በአርበኝነት የሚዋጋ ተንቀሳ ተዋጊ ኃይል፣ አደራ በማለት ትቶ ቢሄድ የሚመረጥ ነበር።

ስለሆነም በደረጃ ሲገመገም በጦርነቱ የበለጠ የተዋጋ የጦር ግንባር በድምሩ 1982 የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል ወይም በማቁሰል የተገኘን ጦር ግንባር ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ጀግኖች ልዑል ራብ ካሣና ራስ ስዩም፣ በእነሱ የሚመራ ጦርም ሲሆን፣ ሁለተኛ ደረጃ ጀግና በድምሩ 1513 የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል ወይንም በማቁሰል የሸሬ ጦር ግንባር ስለሆነ ሁለተኛ ደረጃ ጀግና ራስ እምሩ እና በስሩ የተዋጉ ወታደሮች ይሆናሉ።

ሦስተኛ ደረጃ በድምሩ 1273 የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል ወይንም በማቁሰል የማይጨው ጦር ግንባር ለሆነ ሦስተኛው ደረጃ ብቻ ለንጉሡና በስሩ የተዋጉ ወታደሮች ይደርሳቸዋል። የመጨረሻ 4ኛ ደረጃ ጀግና በድምሩ 802 የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል ወይንም በማቁሰል የእንደርታ ጦር ግንባር ስለሆነ 4ኛ ደረጃ ራስ ሙሉጌታና በእሱ የሚመሩ ወታደሮች ያገኛሉ።



ስለዚህ ዘፈኑም ቢሆን በዓድዋ፣በቴምቤን፣በሽሬ፣ በማይጨው፣ በእንደርታ ወዘተ ተብሎ ቢስተካከል ትክክለኛ ፍርድ ይሆናል።ከነዚህም ሌላ በጉራዕ ተብሎ ከዓድዋ በፊት ቢጨመርም ለሀገሩ ትልቅ የኸግንነት ሙያ ለሰራው ሌላ ንጉሥም ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። በጣሊያኖች ላይ የተጎናፀፍነው የመጀመሪያ የዶጋሊ ጀግኖች መርሳትም መቅረት ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል፣ የሌላ መብት የሚቀንስ ነው። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመችው የመጨረሻ ወረራ ማሸነፍዋ ሲያንሳት ነው እንጂ አይበዛባትም። ከነበርዋት የወታደሮች ብዛት የመሣሪያ ብዛትና ዓይነት ብልጫ ኢትዮጵያ የጦር አሪዮፕላን ስላልነበራት ኢጣሊያ እንደምታሸንፍ ጥርጥር አልነበረም።

## 15. የደቡብና የምሥራቅ የጦር ግንባሮች

ስለደቡብ ጦርነት ግንባር ግራዚያኒ እንዲሁም አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የደረስዋቸው ምጽሐፎች ዋቢ በማድረግ አቀርባለሁ። ግራዚያኒ በአክራሪ ፋሽስትነትና በጭካኔው የታወቀ ነው። የጦርነቱ ማብቂያ በኋላ ፀኢጣሊያ ማርሻል፣የነገሌ መስፍን የሚል ማዕረግ አግኝቶ ነበር። ማርሻል ግራዚያኒ የደቡብ ጦር ዋና አዛዥ ነበር።በአዲስ አበባ ግራዚያኒን ለመግደል ሙከራ በተደረገበት ጊዜ 30,000 ኢትዮጵያውያን የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጥቶ ያስፈጀ ነው።


የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ስሁለት ጦር ግንባር ተከፍሎ ነበር።

1ኛ) የደቡብ ምዕራብ በሊዳሞና ቦረና የተሰለፈው በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው 45,000 ወታደሮች ብዛት የነበረው እንዲሁም በባሌ የሰፈረው የደጃዝማች በየነ መርዕድ ድጋፍ ነበረው፣8000 ወታደር ብዛት የነበረው የሚያጠቃልል ነበር።

2ኛ) የምሥራቁ ከፍል በሐረርና በኦጋዴን የሰፈረው በደጃዝማች ነሲቡ ዛማኑኤል የሚመራው 30,000 ወታደር ብዛት የነበረው ከነሱ የተሰለፉም ሀ) ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው ለ) ደጃዝማች ሀብተሚካኤል በሳሳበኔ የሰፈሩ ሐ) ደጃዝማች አበበ ዳምጠው በይጋሚዳ ሰፍረው የነበሩ የሚያጠቃልል ነበር።

ጣሊያኖች አሰልፏቸው የነበረ ወታደር ብዛት 100,000 ይደርሱ እንደነበር የኢትዮጵያ ወታደር በሰው ብዛትም ከኢጣሊያኖች ከጎማሽ የሚያንስ ነበር። ከኢጣሊያ በኩልም ምንም እንኳን ምሥራቅ መሃልና ምእራብ ብለው ቢጠሩም የሚጓዙበት አቅጣጫ በምሥራቅ ወደ ጅጅጋ ሐረር ድሬዳዋ አዲስ አበባ አቅጣጫዎች በደቡብ ከዶሎ ነገሌ ይርጋለም፣ ሞጆ አዲስ አበባ አቅጣጫ በመያዝ በመውረር ነበር።

የሰሜንና የደቡብ ጦር ግንባሮች ሲገመገሙ የኢትዮጵያ በሜን ጦር ግንባር



ማርሻል ግራዚያኒ የደቡብ ጦር ግንባር የኢጣሊያ ዋና አዛዥ

Ras Destà Damtù

የአርበኞች ቁንጮ ራስ ደስታ ዳመጠው በገፊኞች ጣሊያኖች በጭካኔ ተገድለዋል፡፡



ሀ) 400,000 የኢጣሊያ ወታደሮች የተሳተፉበት ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል የነበረው የወታደር ብዛት የኢጣሊያኖች ግማሽ ከመሆኑም በላይ ለአራት የተለያዩ የጦር አዛዦች የተከፋፈሉ ነበር።

ለ) ሰሜን ኢትዮጵያ በሌላ አርእስት እንደገለጽኩት ለብዙ ዓመታት ኢጣሊያኖች ቆንስላዎች አማካኝነት የፕሮፓጋንዳ ዒላማ ሆና ስንብታለች።

ኢትዮጵያም የቆንስላዎች ሥራ አትቆጣጠርም ነበር።

ሐ) የደጃዝማች ኃይለሥላሴ ክሕደት በኢትዮጵያ ላይ ጉዳት ሳያደርስ አልቀረም።

መ) ጣሊያኖች በያዝዋቸው መሬቶች ሁሉ ወዲያውኑ ባንዳዎችን ለመመልመል ችግር አላጋጠማቸውም።

ሰ) ትግራይ ለጣሊያኖች ወረራ ክፍት በመሆኗ በብዛት ከኢጣሊያ ለመከዳት ፍላጎት የነበራቸው ኤርትራውያን የኢጣሊያ ወታደሮች ዕድል ሊያገኙ አልቻሉም።

ረ) የጦር መሣሪያ እጥረት ነበረ። የውጭ ሀገር የወታደራዊ አማካሪዎች አልነበሩም። የዚህ ተቃራኒ በደቡብ ጦር ግንባር ሀ) የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት ተመጣጣኝ ነበር።

ለ) የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገሮች ለኢጣሊያ ፕሮፓጋንዳ የተጋለጡ አልነበሩም። ሐ) ከሃዲ ግለሰቦች አልተከሰቱም። መ)ጣሊያኖች በደቡብና ምሥራቅ ባንዳዎች ለመመልመል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረላቸውም። ሰ) በደቡብ ኢትዮጵያውያን ይዞታቸውን የለቀቁ ጠላት ከላያለባቸው ካልሆነ በስተቀር ወደው የለቀቁበት ጊዜ የለም። ኢትዮጵያውያን ከወሰናቸው ጀምሮ በሚገባ ጣሊያኖችን ተቋቁመው ተዋግተዋቸዋል። ጣሊያኖች አስቀደመው ስለነቁባቸው ነው እንጂ ኢትዮጵያውያን በሁለቱ ጦር ግንባሮች በምስራቅና በደቡብ ጥቃት ከመፈፀም ወደ ሶማሊያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ለመግባት አቅድ ነበራቸው። በደቡብ አቶ ተክለፃዲቅ ዝርዝር ስማቸው እንዳወጣው ብዙ ከኢጣሊያ የከዱ ኤርትራውያን ነበሩ። ብዙ ሶማሌዎችም ከኢጣሊያኖች የከዱ ነበሩ። ረ) በደቡብና ምሥራቅ ጦር ግንባር የኢትዮጵያ ሠራዊት በቂ የጦር መሳሪያ ነበረው፤ የውጭ ሀገር የጦር አማካሪዎችም ነበሩት።

በደቡብ ሆነ በሰሜን ኢትዮጵያውያን ይጎድላቸው የነበረ የጦር አሪዮፕላኖች ብቻ ነው። ለጦር አሪዮፕላኖችም መቋቋም አያዳግታቸውም ነበር። ሊቋቋሙት ያልቻሉት በዓለም የተከለከለ መርዛማ ጋዝ ብቻ ነበር።እሱንም ጠቅላይ የጦርመሪ ቢኖራቸውም ለመቋቋም አያዳግታቸውም ነበር። በዚሁ የተነሳ ለሽንፈት ተዳረጉ። በጦርነቱ ያሳዩት ጀግንነት ግን ከዓድዋ ጦርነት ጊዜ የበለጠ ነበር። ጠላትም በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ማካከል እርስ በእርስ መከፋፈል ሊፈጥር አልቻለም፤ ትብብራቸው በጣም ጥሩ ነበር። ከ100,000 ለጦርነት ከተሰለፉ የኢጣሊያ ወታደሮች ግራዚያኒ እንደፃፈው 3239 ብቻ ጉዳት



የኦጋዴን ጀግና የኢትዮጵያ ዋና አዛዥ ደጃዝማች ነሲቡ



ደርሶባቸዋል። የሞቱት 1299፣የቆሰሉት1910። ከእነዚህ ውስጥ ስንት ጣሊያኖች እንደ ነበሩ እና ስንት ባለቀለም ወታደሮች እንደነበሩ አልገለፀም። ሆኖም ግንባር ቀደም ይሰለፉ የነበሩ ባለቀለም ወታደሮች ስለነበሩ ከሞቱና ከቆሰሉት አብዛኛው ባለቀለም ወታደሮች እንደ ነበሩ ይገመታል። በምሥራቅና በደቡብ ጦር ግንባር የተካሄዱት ጦርነቶች በአራት ደረጃ የተከፈሉ ነበሩ።

ሀ) ጣሊያኖች የጠሩፎች ማስተካከያ ብለው የሚጠሯቸው ጦርነቶች ለ)የቆራኺ ጦርነት ሐ) የገናሌ ጦርነት መ) የኦጋዴን ጦርነት።

## ሀ) የማስተካከያ ውጊያዎች

የማስተካከያ ውጊያዎች ጣሊያኖች በታላቋ ከተማቸው ‹ሚላኖ ፕላን› ብለው ነበረ የጠሩት። ለሦስት ክፍል የተከፈሉ ነበሩ። ምዕራብ መሃልና ምሥራቅ። የምዕራብ ጦር ግን ባር የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ ዶሎንና አካባቢዋን ለመያዝ ነበረ።የኢጣሊያ ጦር ኮሎኔል ሚኬሊ(Micheli) የሚመራ ነበር። በጦርነቱ የተካፈሉ 1ኛ አንደኛ ጉሩፕ (ቡድን) የወሰን ጠባቂ የነበሩት ባንዳ ዱባት 2ኛ) ሦስተኛ ጉሩፕ የዐረብና የሶማሌ ወታደሮች ሦስት ባታሊዮንና በግመል ጀርባ የተጫነ አንድ መድፍ። 3ኛ አምስተኛ የዓረብና ሶማሌዎች ጉሩፕ፤ ወታደሮች ሦስት ባታሊዮኖች በደጀን ነበሩ። ኮ/ሚኬሊ ኦክቶበር 4 ቀን ጦርነቱን ሲከፍት የአንደኛውን ጉሩፕ አካል የሆነውን በኰሎኔል ፕሪጂዮቲ የሚመራ ጠዋት በ11:15 ነበረ ተኩስ የተጀመረው። የኢትዮጵያ ሁለት የጠረፍ ከተሞች ዶሎና አዶ ተይዘው ተቃጠሉ። 50 የኢትዮጵያ ወታደሮች ተማረኩ፤ አዛዥ ግራዝማች መኩሪያ ተስማ እየተዋጋ በጀግንነት ዐረፈ። ግራዚያኒ በወታደራዊ ክብር እንዲቀበር አደረገ፤ አካባቢውም በሙሉ ጣሊያኖች ተቆጣጠሩት።

በመሐል ግንባር የዋቢ ሸበሌ ግዳጓ መሬት ለመያዝ ነበረ። የጣሊያኖች ዓላማ ቀላፎና ሺላቦ ለመያዝ ነበር የኢጣሊያ አዛዥ ጀነራል ፍሩሺ ነበር።በጦርነቱ የተካፈሉ 1ኛ የሙስታሂል ሁለተኛ ጉሩፕ ዱባት። 2ኛ የፈርፈር 4ኛ ጉሩፕ ዱባት። 3ኛ የሁለተኛ የዐረብና ሶማሌዎች ጉሩፕ 3 ባታሌኖች። 4ኛ የሱልጣን ኦሎል ዲንሌ መደበኛ ያልሆነ 500 ተዋጊዎች 7ኛ የደጀን በሶማሌ የነበሩ ኤርትራ ወታደሮች በሙሉ 4 ባታሊዮኖች የሚያታልል ነበር። የጣሊያኖች እቅድ ከሺላቦና ቀላፎ ሌላ ደገሀቡር ወይንም በኢትዮጵያ አጠራር ተፈሪ በር ለመቆጣጠር ነበር።

ኦክቶበር 14የአራተኛ(4ኛ) ጉሩፕ ዱባት ከፈርፈር ወደ ሸላቦ በመምራት ተኩስ ከፈተ፤ሸላቦ ደርሶ ተመለሰ። ኦክቶበር 17 ቀን ግራዚያኒ ዳፐሬይ ለመያዝ ትእዛዝ በለሰጠ ከሶማሊና ምሥራቅ በሻለቃ ቶሻ የሚመራ ዱባት ጦር፤ ከደቡብና ምሥራቅ የሱልጣን

አሎል ተዋጊዎች፣እንደዚሁም በከባድ መሣሪያ የታጠቁ በሻለቃ ፔሮኒ የሚመሩ ኢጣሊያኖች።

ሌላ በመቶ አለቃ ማሪዮ የሚመራ ንዑስ ግሩፕ ድንገት ቀላፎን እንዲይዝ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። ጣሊያኖች በአቶ በሻህ የሚመሩ 500 የኢትዮጵያ ወታደሮች እንዳሉ የሚል መረጃ ደርሷቸው ነበር። ከከተማዋ ምሽግ አጠገብ የሱልጣን አሎል ዲቄሌ ተቃራኒ የሆኑ በመሐመድ ቦዲል የሚመሩ የኢትዮያ ሶማሌዎች ሰፍረው ነበር። ጀነራል ፍሩሺ አክቶበር 18 ከተማዋ እንድትያዝ ወሰነ። ጣሊያኖች በጦር አውሮፕላኖች እየተረዱ ሁለተኛ ግሩፕ ባንዳና የሱልጣን አሎል 500 ታጣቂዎች በውጊያው ሊሳተፍ ኢትዮጵያውያን ወደ ቀላፎ እየሸሹ ስለነበረ ጣሊያኖች የመሐመድ ባዲልን ጎሳ የሚኖሩበትንገላዲ ድረስ እየተከታተሎዋቸው ሄደው ሱልጣን አሎል ገላዲ ገብቶ መሐመድ ባዲልን ገደለው፣ ወደ ቀላፎ ሄዶም ከመቶ አለቃ ማሪዮ ጋራ ተቀላቀለ። ጣሊያኖች ቀላፎን በመያዛቸው የውሂብ ፓሻ (የደጃዝማች ነሲቡ አማካሪ) ፕላን በኢጣሊያ ሶማሌ ግዛት ውስጥ ለመግባት የኢትዮጵያ ጦር የነበረው ፕላን አከሸፏል በማለት ተደሰተውበታል። ይህ ፕላን ጣሊያኖች ባገኟቸው ማስረጃዎችና የሰው ምስክሮች የተረጋገጠ ነው ብለዋል። በምስራቅ ሶማሊያ ጦር ግንባር መሪሐን ጉሳ የሚኖሩበት ነው። የኢጣሊያ ተዋጊዎች በኮሎኔል ማሊቲ Malliti የሚመሩ። 1ኛ የዓረብና የሶማሌ ግሩፕ 3 ባታሊያኖች። 2ኛ ሦስተኛና አምስተኛ ባንዳ ጉሩፕ፣ ሌሎችም ባንዳዎች የተካፈሉበት ነበሩ። በኢትዮጵያ በኩል በግራዝማች አፈወርቅ የሚታዘዙ ጦር ነበሩ።የኢጣሊያኖች እቅድ የገርሎ ጉቢ የኢትዮያን ጦር ሰፈርን ለመያዝ ነበር። የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ቀብሪደሃር ይ እንዲመለሱ ተወስኖ ነበር። ዳሩ ግን ጣሊያኖች በድንገት ስለደረሱባቸው ወደ ጫካ በተበታተኑበት ጊዜ ብዙ ጉዳት ደረሰባቸው። ከምቱትም መሃል የጦር ሰፈሩ አዛዥ የነበረው ግራዝማች በላቸው ነበረ። በገርሎ ጉቢ የ‹ሚላኖ ፕላን› ያበቃል። በጦርነቱ የተካፈሉ በሙሉ ሶማሊያዎችና ዓረቦች ነበሩ።ከሱልጣን አሎል ጉን የሚቀመጥ አንድ ኢጣሊያዊ የጦር መኮንን ኢጣሊያኖች አስቀመጡበት፣ ምክንያቱም በሥልጣኑ ተጠቅሞ ከባለአንጣዎቼ ሶማሊያዎች ጋራ ከመዋጋት ተቆጥበው በኢትዮጵያ ወታደሮች ብቻ ውጊያው እንዲቀጥል ለማድረግ ነበር።

## ለ) የቆራኼይ ጦርነት፣

የቆራኼይ ጦርነት ‹የጎሪትስያ ፕላን› የሚል ስም የተሰጠው በምስራቅ በኩል በኮሎኔል ማሌቲ የሚመራ ከገድሎ–ጉቢ ተነስቶ ነበረ። በደቡብ በኩል በጄኔራል ፍሩሺ የሚመራ ከፈርፈር የሚነሳ ሲሆን በኢትዮጵያ በኩል ግራዝማች አፈወርቅ ተጨማሪ ወታደሮች ስለተላኩለት ሦስት ሺህ ወታደሮች ነበሩት። ከነሱ ውስጥም 100 ወታደሮች



ከጣሊያኖች ከድቶ የመጣ የሁመር ላማንተር ወታደሮች ነበሩ። ይህ የተጠናከረ ጦር ቀድሞ ወደ ደጋሐቡር እንዲያፈገፍግ አፈወርቅ የተሰጠውን ትእዛዝ በመለወጥ ተጨማሪ ሌላ ጦርም ስለሚላክለት እዚያው እንዲቆይና እንዲከላከል ትእዛዝ ደርሶት ነበር። ሀ ክፍል የሚባለው በጄኔራል ፍሩሽ የሚመራው 2ኛ ሁለተኛ የዓረብና የሶማሌ ጉሩፕ 2ኛ የባንዳ ጉሩፕ (ቡድን) 5ኛ አንድ ባታሊዮን የኢጣልያ ሦስተኛ አግረኛ 4ኛ ሌላ ግሩፕ ከፖሎሪታና ዲቪዝዮን (5ኛ የታንከኛ የኢጣልያን ቡድን ለ ቡድን ክፍል የሚባለው በኮሎኔል ማሌቲ የሚመራው ፊት እኖቲ ጦር ሁሉም እግረኛ 6ኛ አንደኛ የዓረቦችና የሶማሌዎች ቡድን ለ) 3ኛ የባንዳ ቡድን በኢጣሊያ ታንኮች የሚረዱ የጦር ሰፈር ኖቬንበር 7 ቀን 1935 ዓ/ም በጦር አውሮፕላኖች በምብ ድብደባ ምክንያት የኢትዮጵያ ወታደሮች ሰፈሩን ለቀው ወጥተዋል። የደረሰባቸው ጉዳት ሊታወቅ አልተቻለም። ጀግናው ግራዝማች አፈወርቅ እግሩ ላይ ስለቆሰለ ወደ ደጋሐቡር በሚጓዙበት ጊዜ በመንገድ ዓረፈ። የኢትዮጵያ ጦር ከጦር ሰፈሩ ለቆ የወጣበት ምክንያትም አዛዡ ግራዝማች አፈወርቅ ስለቆሰለ ነው ብለው ኢጣሊያኖች ተርትመውታል።

## ሐ) የጋናሌ ጦርነት

ግራዚያኒ እንደጻፈው የኢጣሊያ ጦር ግንባር በተቋቋመበት ጊዜ አክቶበር 3 ቀን 1935 ዓ/ም ጣሊያኖች የራስ ደስታ ጻምጠው ጦር በሲዳሞ በረና፣ የደጃ ዝማች በየነ መርዕድ ጦር በባሌ ሰፍረው እንደሚገኝ መረጃ ደርሷቸው እንደነበረ ገልጧል። ነገር ግን ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመሩ የታወቀ ነገር አልነበረም። በአዲስ አበባ የነበረው የኢጣሊያ ኤምባሲ ግን በገናሌ ወይንም በዋቢ ሸበሌ በኩል የኢትዮጵያ ወታደሮች ሶማሌያን ሊወሩ እንደሚችሉ ሴፕተምበር አጋማሽ ላይ አስጠንቅቆ አክቶበር አጋማሽ ላይ በልዩ የሰለላ ድርጅት በኩል የሁለቱ ጦሮች እንቅስቃሴ መረጃ ቢደርስም ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመሩ አልታወቀም ነበር። ራስ ደስታ አክቶበር 25 አዶላ ደርሶ ነበር። በ28 የደራ ደርሶ ስለዶሮና ሉባ ከአንድ ከኢጣሊያ የከዳ ግለሰብ መረጃ ያሰባስብ እንደነበረ ጣሊያኖች አወቁ። ራስ ደስታ በምስራቅ በደጃዝማች ነሲቡም ጭምር በደቡብም በአንድ ጊዜ ማጥቃት እንዲጀመር ለንጉሠ ነገሥቱ ሃሣብ አቅርቦ ነበር። ራስ ደስታ አርናንድ ፍሪር የተባለው ከቤልጅግ ጦር ሠራዊት አንድ አማካሪ ነበረው። በዚሁ ወቅት የወሰን ማስተካከያ ግጭቶች ተካሄደው የዱባት የኢጣሊያ ጦር የሼጋ ጉዶ በተባለው የቦረና መሬት ለስለላ ዓላማ ገብቶ መደበኛ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ጦር ዳዋ ወንዝ አካባቢ እንዳገኘ አመልክቶ ተመልሶ ነበር።ቀጥሎም የስለላ አውሮፕላኖችም በነገሌ አካባቢ የኢትዮጵያ ወታደሮች ድንኳኖች አይተው ተመልሰው ነበር። ጣሊያኖች ከደሎ በስተ ምዕራብ ከዶሎና መልካ ሪዮ መሃል በኩል የዳዋ ወንዝ አቋርጠው ለማለፍ ምቹ ስለሆነ የራስ ደስታ ጦር በዚህ በኩል አልፎ የዶሎ በስተጀርባ ወደሉግ ብቻ ሣይሆን ወደ

ባይዳዋና ባርደራ ዘልቆ ገብቶ ወረራ መፈፀም እንደሚችል ተፈርቶ ነበር። በዚህ በኩል በኢጣሊያ በኩል ቦታው መከላከያ አልነበረውም።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን ከኬንያ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ልዩ ልዩ እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ጣሊያኖች ግምት ነበራቸው። ይህ ካልሆነም ከዶሎ በስተምሥራቅ በኩል ወደ ሉግ አምርቶ ከመቋድሾ ያሉት መገናኛዎች ማቋረጥ እንደሚችል የት የተባለ ችው ትንሿ ከተማ ለመያዝ ወደ ወጂትና ባይደዋ የኢትዮጵያ ጦር ማምራት እንደሚችል ወይንም ወደቀላፎ ማምራት እንደሚችል ተፈርቶ ነበር። ጣሊያኖች በቆረኼይ ጦርነት ማገስ ት ጀምረው ማንኛውም የጦር መሣሪያና ወታደር ወደ ምዕራብ ጦር ግንባር አካማችተው መከላከያ አበጅተው ነበር። ኖቬንበር10 ጣሊያኖች ሙሉ ዝግጅት አጠናቀው 28.000 ወታደሮች በቦታው አስፍረው ነበር።ከእነሱም ውስጥ ግማሽ ጣሊያኖች ስለሆኑ ለምግባቸው፡ ለሚጠጣ ውኃ፡ ለነዳጅ፡ ለሕክምና፡ መጓጓዣ በየብስ ብቻ ሳይሆን በጀልባዎችም ለብዙ ቀን የሚበቃ ተዘጋጅቶ ነበረ።

የኤርትራውያን ጦርም ወደ እዚሁ እንዲዛወር ተደርጎ ነበር። በሶማሌ የኢጣሊያ ዋና አዝ ሰፈር ወደ ባይደዋ ተዘዋውሮ ነበር። ሁለት የእዙ ወረዳዎች ኰ/ል ሚኪሌ ዶሎ ላይ ኮሎኔል ማርቲኒ እዱር ላይ እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር። ኖቬንበር14 ራስ ደስታ የኢትዮጵያ ጦር ነገሌ ላይ እንደተሰበሰበ ወይንም በመሰባሰብ ላይ እንዳለ ጣሊያኖች መረጃዎች ደርሷቸው ነበር።ራስ ደስታ በዳዋ ወንዝ በኩል በፊታውራሪ እደሙና በፊታውራሪ ታደመ በፊት አጥቂ ጦር እየተረዳ ዲሴንበር 8 ወደ ሶማሊያ ጠረፍ በኢጣሊያ ግራ ክንፍ በኩል እንደሚደረስ ተገምቶ ነበር።የባሌ ጦርም በዋቢ ወንዝ በኩል እንደሚደርስ ተገምቶ ነበር።ዳሩ ግን ራስ ደስታ የደጃዝማች ነሲቡ ጦርም አንድ ላይ ሆኖ እንዲያጠቃ ብሎ ለንጉሡ የጠየቀው በስራ ላይ ሊውል አልቻለም። ኢትዮጵያውያን ሌሊት ብቻ ይጓዙ ስለነበረ በልብሳቸውም ቀለም እየተቀቡ እንዳይታዩ ያደርጉ ስለነበረ ፣ የያዙዋቸው ከብቶች በጫካ እየደበቁ እንዳይታዩ ያደርጓቸው ስለነበረ የሰላይ ጦር አሮፕላኖች ሊያዩዋቸው አልቻሉም ነበር። መረጃዎች ሊገኙ የቻሉት በሰዎች ስላለና ለራስ ደስታ ራዲዮ መልእክቶች ጠለፋ ብቻ ነበር። ኖቬንበር 20 ብቻ የኢትዮጵያ ጦር አመጣጥ አቅጣጫ ለማወቅ ጣሊያኖች ችሉ ነበር ይኸውም ፊልቱ በኀልማኛ ዶሎ ሲሆን ለ4 ፊት አጥቂ ጦር የተከፋፈሉ ነበር። 2 ክፍሎች በገናሌ 3ኛው በዋቢ ወንዝ፣ 4ኛ በሸበሌ ወንዝ ዋና ጦር ኖቬንበር11–12 ከነገሌ ተነስቶ አቅጣጫው በፊልቱ በጉል ማኞ በኩል ወደ ዶሎ እንደሚያመራ ታወቀ። የዳዋ ወንዝ ግን ጣሊያኖች ምንም እንቅስቃሴ አልነበረውም ብለው ገምተውት ነበር።ቀጥሎ ግን ጣሊያኖች 2000 የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደሰፈሩበት አረጋገጡ። በዚህ መሰረት ዲሴንበር4 የኢትዮጵያ ለ4የተከፈሉ የፊት አጥቂው 1000 ወታደር የሚገመት በዋቢ ወንዝ ወደ ወደ ላግ ሺግዲ የሚያመራ 2ኛ 2000 ወታደር ያሉበት በገናሌ ወንዝ ወደ መልካ ዲዳ



የሚያመራ 3ኛ ከገናሌ ፊልቱ ዋና መንገድ ይዞ 2000 ወታደር ብዛት የነበረው ጦር ወደ ባተል ማኞ የሚያመራ 4ኛ) 1000 ወታደር የነበረው በዳዋ ወንዝ በኩል ወደ ሰደይ የሚያመራ በአጠቃላይ የራስ ደስታ ጦር 35.000 ወታደሮች ነበሩት።

ስለደጃዝማች በየነ መርዕድ ጦር ምንም የታወቀ ነገር አልነበረም። በዚሁ ቀን ዲሴንበር4 ግራዚያኒ «ሉዲኔ ፕላን» የተባለው የጦርነት እቀድ ያወጣል። ግራዚያኒ ሰላዮች የሰጡኝ ማስረጃ ብሎ ያመነበት ከዚህ በፊት እንግሊዞች ለኢጣሊያኖች ወደው የሰጧቸው ከጁባ ምላሽ መሬት መልሰው እንዲወስዱት ከሐበሾች ጋራ ተስማምተዋል የሚል ወሬ ስለሰማ የዳዋ ወንዝ ውኃም ቀንሶ ስለነበረ የኢትዮጵያ ጦር ዳዋን ተሻግሮ በምእራብ ዳዋ በኩል ወረራ ይፈጽማል የሚል ስጋት ስላደረበት መከላከያ ማጠናከር ጀመረ።

ዲሴንበር 12 ራስ ደስታ በፈልጡ እንደነበረና ጦሩ በሦስት አቅጣጫዎች ከፋፍሎ እንደነበረ ተዘግቧል። 1) በግሪኩ ሙላ ሳባ የሚመራ 3000 ወታደሮች የነበረው ዳዋን ወንዝ ተከትሎ የሚጓዝ 2) እዶ በሚወስደው መንገድ የሚጓዝ 3) ገናሌ ተከትሎ የሚጓዝ። ከሁለተኛና ሦስተኛ ቀድሞ በፊታውራሪ አደመ የሚመራ የፊት አጥቂ ጦር ተሰልፎ ነበር። ጣሊያኖች ለገኙን ባሏቸው መረጃዎች መሠረት ሦስቱ የራስ ደስታ ጦር ክፍሎች ዓላማቸው ዲሴንበር 24–25 ከዶሎ በስተ ምዕራብ ተገናኝተው የዳዋ ወንዙን ሰብረው ለመግባት ዓላማ እነደነበራቸው ጣሊያኖች ይገምቷቸው ነበር። በዚሁ ጊዜም የኢጣሊያ የሰው ስላለና የራዲዮ ጠለፋ አገልግሎት የሐረርጌ በደጃዝማች ነሲቡ የሚመራ ጦርም በማጥቃቱ ተካፋይ እንደሚሆን ራስ ደስታና ደጃዝማች ነሲቡ በራዲዮ መገ ናኛ ተለዋውጦበት ቴሌግራምም ጣሊያኖች ለመጥለፍ በመቻላቸው መረጃ አግኝተው ነበር። ዲሴንበር 14ቀን የኢጣሊያ የፊት አጥቂ ጦር በአረሬ ገናሌ መስመር ለመውረር ያደረገው ሙከራ ከኢትዮጵያውያን ኃይለኛ ተቃውሞ ስለገጠመው ወደ ኋላ ለመመለስ ግድ ሆኖበትነበር። የጦር አሮፕላኖችም በነገሌ ቦምብ ለመጣል ያደረጉት ሙከራ የፀረ አሮፕላን ጥይቶች ተከፍቶባቸው ነበረ። ግራዚያኒ የኢትዮጵያ ጦር ከኬንያ መሬት እልፎ ጥቃት ይፈጽማል የሚል ስጋት ስለነበረው ለኬንያ እንግሊዛዊ ሀገረ ገዥ ቴሌግራም ልኮ የዚሁ ዓይነት እድራጎት እንዳይሞከር በናይሮ ቢ የኢጣሊያ ቆንስል በኩል እንዲነገረው ጠይቋል። ዲሴንበር 19 ዋናው የኢትዮጵያ ጦር አረሬ ደርሷል። ሙላ ሳባ ከመልካ ራዮ ሁለት ቀን የእግር መንገድ ደርሷል። በሁለቱም መስመሮች መካከል በየብስ ግንኙነት ነበራቸው።በዚህ ወቅትም ጣሊያኖች የመከላከያ ስራ እያጠናከሩ ነበር፤ 54 ኪሎ ሜትር በሽቦ አጥረዋል።

በ150 ሰራተኞች መድፎችና መትረየሶች ተጠምዷል።ይህ በእንዲህ እንዳለ ደጃዝማች በየነ መርዕድ ወደ ደቡብ ያመራ ስለነበረ፤ጣሊያኖች ራዲዮ መጥለፍ መረጃ ለማግኘት ስለተቸገሩ፤ ምክንያቱም ደጃዞማች በየነ የራዲዮ መገናኛ ስላልነበረው፤ ግራዚያኒ ዋና የኢጣሊያ ትጥረኛ በነበረው በእሉል ዲጋሌ በመጠቀም የደጃዝማች በየነ መርዕድ ጦር

በጦርነቱ ለመካፈል እንዳይችል አድርገውታል። ጣሊያኖች ይፈልጉት የነበረው የመጀመሪያ ዓላማቸው የደጃዝማች በየነ ጦር ዋቢ ወንዝ፣ ወይንም ዋቢ ሸበሌ ይሁን ለማወቅ መረጃ ለማግኘት ነበር። ማርሻል ግራዚያኒ በመጀመሪያ ጊዜ በምስጢር ኖቬምበር19 ከሱልጣን ኦሎል ጋራ ተነጋግረው ኦሎል እስከ ኤሚ ድረስ ሰላለ እንዲያደርግ ሃሣቡን ገልጾለት ነበር። እንደገና ኖቬምበር 25 ተገናኝተው ተነጋግረዋል። ኦሎል 1000 ተዋጊዎች ነበሩት። ዲሴምበር 2 ኦሎል ከቀላፎ ተነሳ፣ ዲሴምበር17 ኦሎል 300 ኪ/ሜ ከቀላፎ ቡር ካላ፤ በተባለው ቦታ ደረሰ፣ስለ በየነ መርዕድ ጦር መረጃ ለማግኘትም ችለዋል። ዲሴምበር 23 ከኢትዮጵያ ተዋጊዎች ጋራ ውጊያ ፈጥረው ጥቂት ሰዎች ማርኮ የዳጃዝማች በየነ የወታደር ብዛት 5000 ይደርስ እንደነበረና ወደዚሁ እየገሰገሱ መሆናቸውን የሚል መረጃ ያገ ኛል።ኦሎልም ውጊያ እንዳይገጥም በቅድሚያ የተነገረው ወደ ጎን በመተው የጦር አሪዮፕ ላኖች ብቻ እርዳታ ጠይቶ ለጦርነት ይዘጋጃል። ዲሴምበር 26 ተኩስ በኢትዮጵያውያን ላይ ይከፍታል፣ እስከ ጠዋቱ ይቀጥላል፣ አውሮፕላኖቻቸው በጦርነቱ ተካፋይ ነበሩ። ሊጨልም ኢትዮጵያውያን ማጥቃት ያቆማሉ። ከተካፈሉት 19 በአውሮፕላኖች አንዱ በፀረ አውሮፕላን ጥይት በኃይል ስለተመታ በድንገተኛ ማረፊያ እንዲያርፍ ሲገደድ ሌሎችም አውሮፕላኖች ተመትተው ከባድ ጉዳት ስለደረሰባቸው ለወደቀው አውሮፕላን በኢትዮጵያ ጦር ዳግም እንዳይተኮስበት ይጠብቁት ነበር። ኦሎልም ከባድ ጉዳት ደረሰበት። ከነበሩት 1000 ተዋጊዎች 300 ከዱት፣ስለሞቱት አልተገለፀም። በኢትዮጵያ በኩል የደረሰው በኢጣሊያኖች ግምት 1000 ወታደሮችር ነበር። ማታ ሁለቱ ተፋላሚዎች ወደ የሰፈራቸው ተመለሱ። ደጃዝማች በየነ መርዕድ ቆስሎ ስለነበረ እስከ ኢሚ ተመልሶ በጦርነቱ መካፈል ለማቆም ተገዷል። እንደዚሁም ኦሎል የድካሙ ውጤት የማየት እድል ሳይችል ቀርቷል።

የተገኘው ጥቅም ለሁለቱ ወገኖች እኩል ሊሆን ይችላል። ጣሊያኖች ግን የተመለከቱት ስለራሳቸው ባስገኘላቸው ጥቅም ብቻ ነበር። በመደበኛ በዱባት ወታደር ሳይጠቀሙ በኦሎል መደበኛ ያልሆነ ተዋጊዎች ብቻ ብዙ የተነረለት የባሌ የኢትዮጵያ ጦር ከጦርነቱ ውጪ ለማድረግ ለመብቃታቸው ብቻ ተደስተዋል።

## በምሥራቅ ጦር ግንባር

ከሳሳባነህ ቡላለህና ደገሐቡር መሃከል 6000 የኢትዮጵያ ጦር ሰፍሮ ነበር፣ 1000 ወታደርም በዱከን ሰፍረው ነበረ።ወደፊት የዘለቀ አነስተኛ ጦርም በቢርኩት ሐማንለይ እና ሐረር ዲገር ይገኝ ነበር። ይህ ሁሉ ወደ መሃል ኦጋዴን ገብቶ ወራሪ እንዲያካሄድ ለኢጣሊያኖች ስጋት ፐፈጥርባቸው ነበር። የጦር አይሮፕላኖች በቦምብ መጣላቸውን አሳቋረጡም ነበር በነገሌ አንድ አውሮፕላን ወድቆ ተከስክሶ አንድ የኢጣልያ መቶ አለቃ ያኮቡቺ የተባለው ሕይወቱን አጥቷል። በጅጅጋ አንድ አውሮፕላን ወድቆ ውስጡ የነበሩ ጣሊያኖች ነጮች አንድ መቶ አለቃ ሚኒቲ የተባለውና ረዳቱ የሃምሳ አለቃ ዛርኒ ጉዳት



በደረሰባቸው በተናደዱት ሶማሊያዎች ተገድለዋል። ከዚህ በኋላ ጣሊያኖች «የእኛ የጦር አሪዮፕላን ነጂዎችን እንገታቸውን ቆርጧችኋል በምትኩ የሚገባችሁ ታገኛላችሁ» የሚል ወረቀት ከሰማይ ከበተኑ በኋላ መርዛማ ጋዝ በመጣላቸው ከባድ ድንጋጤ በሕዝቡ ላይ አስከትለዋል።

## ዋናው ጦርነት ከመጀመሩ በፊት የነበረው ሁኔታ

የኢትዮጵያ ጦር ምንም እንቅስቃሴ አያሳይም ነበር።ወደ ኋላ ለመመለስም አዝማሚያ ነበረው። የቤልጂጉ ወታደራዊ አማካሪም ላቀረበው ሪፖርት የኢትዮጵያ ጦር ከማጥቃት ቆጥበው ወደ መከላከል እንዲወስን ካሰጠነቀቀ በኋላ ጣሊያኖች ስለሚጥሉዋቸው የጋዝ ቦምቦች ምክር ሲሰጥ:-

1ኛ) ከ1ሰዓት በፊት ቦምብ ወደ ተጣለበት ቦታ አለመጠጋት

2ኛ) ቦምብ የተጣለበት ቦታ በአፈር መሸፈን

3ኛ) በቦምብ የተቃጠለ አፈር በእጅ አለመንካት፣ ማሽተትም እንደማያስፈልግ፣ ማሽተቱም ሞት እንደሚያስከትል አስጠንቅቀዋል።

ለማጥቃት የተዘጋጁ የኢጣሊያ ወታደሮች 14 ሺህ ነበሩ፣ከእነሱም አንድ ሦስተኛ ጣሊያኖች ነበሩ፤ የቀሩት ኤርትራውያንና ሶማሌዎች ነበሩ።

ራስ ደስታ ዲሴምበር 29 መልካ ዲዳ፣ ከዶሎ 60 ኪ/ሜ ርቀት ሰፍር ነበር። ድንኳኑ ከሰሜድንቶይ መስቀል ድንኳን አጠገብ ነበር። የኢጣሊያ አውሮፕላኖች ቦምብ በሚጥሉበት ጊዜ በቀይ መስቀል ድንኳን ይጠለል ነበር። በስሕተት የኢጣሊያ ጦር አይሮፕላኖች የስዊዲን ቀይ መስቀል ሆስፒታል ሲመቱ በግራዚያኒ አባባል የኢትዮጵያ መንግሥት የዓ ለም ሕዝብ ስሜት ለመቀስቀስ ሙከራ ያደርግ ነበር። ግራዚያኒ በራስ ደስታ ጦር ላይ የማጥቃት እርምጃ ለመውሰድ ለበላይ አለቆቹ በሚጠይቅበት ጊዜ ዱቼ በሐሳቡ ከመስማማ ቱም በላይ በማንኛውም ዓይነት መሣሪያ ተጠቀም ብሉታል፣ በመርዘኛ የጋዝ ቦምብ ማለቱ ነው።ለዘመቻው ዋናው አዛዥ ለባዶሊዮም ግራዚያኒ ያቀደውን እንዲፈቀድለት ቴሌግራም አስተላልፈዋል፤ የቀኝ ግዛቶች ዋና ፀሐፊም ግራዚያኒ ስምምነቱን ገልጾለታል። በገናሌ ጦርነት ዋዜማ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት 85 ሺህ ደርሰው ነበር፣ ከእነሱም 49.378 ጣሊያኖች 35.713 አንዲጂኒ ወታደሮች የማጥቃት መጀመር እለባቸው ካሰ በኋላ ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የበርጎንዞሊ ጦር (የኢንዲጂኒ ጦር) ነው ብሏል።ኤርትራውያን በደጀን ይቆማላ ብሏል። ቀጥሎም በዳዋ ወንዝ ከተሰለፈው ከጀኔራል አጎስቲኒ ጋራ እንዲቀላቀሉ አድርገዋል። በበርጎንዞሊ ጦር ውስጥ የአንደኛ ቡድን ባንዶች ሁለተኛ ሦስተኛ የሶማሌና የዓረብ ቡድኖች የሚያጠቃልል ነው።

ጃንዋሪ 14 ራስደስታ በተሽከርካሪ በሚሸሹበት ጊዜ የኢጣሊያ የጦር አውሮፕላኖች ቦምብ ሊጥሉበት ሞክረው ተሽከርካሪው በመደበቁ ሊያገኙት አልቻሉም።በኤርትራ ወታደሮች ውስጥ ከባድ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በአንድ ተንኮለኛ ፕሮፓጋንዳ ከጠላት የተላኩ ሰዎች ተታልለው ከራሳቸው ውስጥም በክርስትና ሃይማኖት ሰበብ ተሰብከው 80 አስከሮች ሌሊት ጃንዋሪ 16 ከድተው ወደ ኬኒያ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል። ሌሎች ከዳተኞች እንዳይከሰቱ እየተፈራ ነው።ጄኔራል አንስቲኒ ወዲያውኑ ኤርትራውያኑ በጃርሶ በኩል ወደ ኋላ እንዲመለሱና ከኬኒያ ጠረፍ ከጓደኞቻቸው ከዳተኞች እንዳይታለሉ ያደርጋል። በሚመለሱበት ጊዜ ግን ሌሎች 700 አስከሮች ወታደሮች ሁሉም ኮፕቶች ክርስቲያኖች ከጣሊያኖች ጠፍተው ወደ ኬንያ ይገባሉ። በኤርትራውያን ላይ ከእንግዲህ ምንም መተማመን አያስፈልገም[1]፤ በሰላይ አይሮፕላኖች አማካኝነት ዋናው የኢትዮጵያ ጦር ሰፈር በነገሌ የተሰባሰበ መሆኑን ስላወቁ ጣሊያኖች ወደፊት እየገሰገሱ እግረ መንገዳቸው የሚያገኟቸውን አነስተኛ ተዋጊዎችን እያባረሩ በሚጓዙበት ጊዜ በመልካ ገርሲ 600 ኢትዮጵያውያን እና 50 አስከሮች ኤርትራውያን የተቀላቀሉባቸው መኖራቸው አወቁ።

ጣሊያኖች በድንገት ደረሱባቸው፤ በታተኑዋቸው ከባድ ውጊያ በጨበጣ ውጊያ ጥምር ተካሂዶ ጉዳት አደረሱባቸው። ከሁለት ሰዓት ውጊያ በኋላ ጨምሪያ ምርኮው ወታደር ትንም ማርከዋል። ጃንዋሪ 18 ጣሊያኖች ከነገሌ 100 ኪሎ ሜትር ርቀት ደረሰው ነበር።ጃንዋሪ 19 ኢትዮጵያውያን ነገሌን ለቀው እየወጡ መሆናቸውን አወቁ።ወደፊት በሚገሰግሱበት ወቅት ፈረሶች፤የቀንድ ከብቶችና ወታደሮችን ማረኩ። ከመልካ ገርሲ በስተምሥራቅ ዱባት ተዋጊዎች ኤርትራውያን ከዳተኞች ካሉባቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች ውጊያ ይገጥማሉ። የጦር አይሮፕላኖች ያለማቋረጥ በነገሌና በሌሎች ቦታዎች ቦምብ እየጣሉ ነበሩ። «ዱቼ» በየቀኑ የደስታ ቴሌግራም ለግራዚያኒ ይልክ ነበረ። ጃንዋሪ 20 ጣሊያኖች አስቀድመው ነገሌ እንዲገቡ የወሰኑበት ቀን ነበር። በአውሮፕላን ስለላ አድርገው ነገሌ ሰው አልባ ሆኖ ነበር። የኢትዮጵያ ወታደሮች ለቀው ወደ ዋደራ ሄዱ።

24 አሪዮፕላን ቦምብ በሚጥሉበት ጊዜ አንድ አሪዮፕላን ተመቶ ይወድቃል። ኢትዮጵያውያን በጫካ ተደብቀው የጣሊያኖችን ምምጣት ይጠባበቁ ነበር። ጣሊያኖች ነገሌ አካባቢ እንደደረሱ ተኩስ ከፈቱባቸው። የ10ኛ ቦታሊዮን አሽከሮች ወደ ዛፎች ጫካ ሂደው ውጊያ ይገጥማሉ ጣሊያኖች ወደ ከተማ መሐል ይገባሉ። ዋናው የኢትዮጵያ ጦር ሰፈር ተበታትነዋል። ግለሰብ ተዋጊዎች ብቻ በጫካ ሆነው ተኩስ ይከፍቱ ነበር። ዋናው የኢትዮጵያ ጦር ምናልባትም ራስ ደስታ ጨምር ከነገሌ 70 ኪሎ ሜትር የምትርቀው ዋደራ ተሰባስበዋል።

1. Graziani Fronte Sud p. 246



ጄኔራል በርጎንዞሊ ተከታትሎ ማጥቃት ይወስናል። ነገሌ በመያዙዋ ጣሊያኖች የገናሌ ጦርነት እንዳለቃ ቆጥረውታል። መንገድ ሁሉ በኢትዮጵያ ወታደሮች አስከሬን የተሞላ ነበር።

1000 ገደማ አስከሬን ተቆጥሯል። ከሞቱት መሐከል የራስ ደስታ ልዩ ፀሐፊ የነበረው ሥዩም ረታ የተባለው ይገኝበት ነበር።

በጄኔራል አግስቲኒ ጦር ግንባር በኩል መላ ላባ እና ሐሰን ገባላ ከራስ ደስታ ጋራ ተሰልፈው ሲዋጉ የነበሩ ወደ መጋ እየሸሹ ናቸው። የጦሩ ግማሽ እንግሊዞች መልካም አቀባበል እያደረጉላቸው ወደ ኬኒያ ገብተዋል። ራስ ደስታም ይርጋለም ገብቷል። ጣሊያኖች ወደ መጋና ዋያሌ አለላ በሚያደርጉበት ጊዜ ጃንዋሪ 29 የኢትዮጵያ ወታደሮች በኤርትራውያኑ ከዳተኞች የተደራጁ አግኝተዋል። እንዲሁም ፌብሯሪ 2 መልካ ጉባ በተባለው ቦታ ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ ወታደሮችና ኤርትራውያን ከዳተኞች ውጊያ ማካሄዳቸውን ገልፀዋል። ጄኔራል አግስቲኒ በመልካ መሪ ዘራፊዎችና ኤርትራውያን ከኬኒያ መሬት እየተነሱ ጉዳት እያደረሱ መሆናቸውን ግራዚያኒ በመጽሐፉ ላይ ገልጿል።

## መ) የኦጋዴን ጦርነት

ጣሊያኖች የኦጋዴን ጦርነት ብለው የሚጠሩት የምሥራቅ ጦር ግንባር ጦርነት በመባል ነበረ፤ምክንያቱም፤ ከኦጋዴን ጀምረው ሐረርና ድሬደዋን ለመቆጣጠር የሚያጠቃልል ነው። የገናሌ ጦርነት የተባለውም የደቡብ ጦር ግንባር መባል ነበረ። የኦጋዴን ጦርነት ለመጀመር ከጦር መሣሪያ ሌላ፤ የሊቢያ ዲቪዚዮን ወደ ሶማሊያ እንዲላክ በተለይ የኤርትራ ወታደሮች እየከዱ ከኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር በመሰለፋቸው አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የቅኝ ግዛቶች ሚኒስቴር ጋራ በመነጋገር እንዲላኩ አድርጓል።

የሊቢያ ዲቪዚዮን በፌብሯሪ ወር ሶማሌ ገባ። 270 የኢጣሊያ ጦር መኮንኖች 600 የኢጣሊያ ወታደሮችና 8000 የሊቢያ አስከሮች ወታደሮች የሚያጠቃልል ነው።

በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ኩራ አስከ ተባለው ከቀብሪ ደሐር 100 ኪ/ሜትር ርቀት ወደሚገኘው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ዘልቀው ገብተው ከባድ ጦርነት አካሄደው 40 ዱባት ተገድለዋል። ጣሊያኖች ግን የሞቱት ዱባት በመሆናቸው ክብደት አልሰጡትም።

ጄኔራል ወሂብ ፓሻ በኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ስም የኢጣሊያ አውሮፕላን ስለፈፀመው የቦምብ ድብደባ ስሞታ ለማቅረብ አንድ የኢያጣሊ[2] ሶማሊይዊ ተመላሽ የነበረ አሁን ግን የኢትዮጵያ መሪዎች ባልደረባ በሆነው አማካኝነት መልእክት ልኮ ነበር። ግራዚያኒ ግን 1ኛ የኢጣሊያ ቀኝ ግዛት ተመላሽ በመሆኑና ፈርሞው የደጃዝማቾች እሴቱ የማይመስል በመረዳት መልእክተኛው ወደ ጣሊያ ሰፈር እንዲገባ በማድረግ ለተያዘው መልስ አለመስጠት

ይሞርጣል። ቶይቶ ግን ግራዚያኒ ለጄኔራል ውሂብ መልእክተኛው ተመልሶ ያልተላከበት ምክንያት ለማስረዳት በቴሌግራም አስታውቀዋል

ከሮማና ከባዶሊዮ የኦጋዴን ጦርነት ቶሎ እንዲጀመር ለግራዚያኒ ጥያቄ ሊቀርብለት ስለነበረ የጠየቀው ሁሉ ስላልተሟላለት ለአፕሪል ወር ታስቦ የነበረው ግራዚያኒ ለማርች 15 በአውሮፕላን ጂጂጋን በመደብደብ እንዲጀመር ወሰነዋል።የሊቢያ ዲቪዚዮን በሙሉ ሙስታሂል ሰፈረ፤ አንድ ባታሊዮን ግን የባንዳ ሶማሌዎች ቦታ ለመሸፈን ቀላፎ ሰፈረ። 4 ባታሊዮን ኤርትራውያን የነበሩት ፈርሰው በእስላሞች ብቻ የተዋቀረ አዲስ የኤርትራውያን ባታሊዮን ከሊብያ ዲቪዚዮን ጋር ይጠቃለላል።

ማርች 5 በሱማሊያ የኢጣሊያ ወታደር ብዛት 96.000 ደርሶ ነበር። ከእነሱ ውስጥም 55.000 ጣሊያኖች 41.000 ኢንዲጂኒ ነበሩ። የየብስ ውጊያ የሚጀመርበት ግራዚያኒ ለአፕሪል10 እንዲሆን ወሰነ። በዚህ መሠረት የሊቢያ ዲቪዚዮን በጄኔራል ናሲ ስር ሆኖ ከሙስታሂል ወደ ዳናን ተዛውረው ለውጊያ እንዲዘጋጁ ተደርገዋል። ከዳናን የሚነሳ ጦር ጄኔራል አጎስቲኒ የሚመራ ሊሆን ነው፤ የመሐል ጦር ከተብሪ ደሐር የሚነሳ በጄኔራል ፍሩሺ የሚመራ ነበር። በዚሁ ጊዜ ማርች 10 ቀን በሶማሊያ የኢጣሊያ ጦር ብዛት 100.000 ደርሶ ነበር። የጦር አውሮፕላኖች 67 የነበር 89 ደርሰው ነበር፤ ከእነሱም ውስጥ 60 በቶረኸይ ሰፍረው ነበር። በየብስ ማጥቃት የሚጀመረበት ግራዚያኒ አንደገና ለአፕሪል 15 እንዲሆን ወሰነ። በመጨረሻ ዱቼ ለ 4–5 ቀን እንኳን ተድሞ እንዲጀመር ብሎ በጠየቀው መሠረት የየብስ ጦርነት ሁለት ቀን በመቅደም ግራኪዚያኒ ለኤፕሪል 13 ቀን እንዲጀመር ይወስናል።

በጄኔራል ናሲ የሚመራ ጦር ሀ) ናሻራ የተባለው መደበኛ ባንዳዎችና የእሎል ዲገለ ባንዳዎች እንዲሁም የሁሰን አይላ ጎሳንዎች የሚያጠቃልል ነበር ለ) የሊቢያ የጦር ዲቪዚዮን በሁለት አቅጣጫ ደገና ግለይኮ ሰጋገ ደጋሙዶ 2) ቢርጎት ዱኩን–ሲጋግ–ደጋግዶ አቅጣጫዎች የሚጓዙ።

የጄኔራል ፍሩሺ የመሀል ጦር 7 ባታሊዮን እንዲጂኒ ያቀፈ ነው የቀብሪ ዳሀር ዋራን ዳብ–ሐማገላይ–ሳሳበነሁ–ደገሐቡር መስመር የሚጓዝ።

የጄኔራል የጎስቲኒ ጦር የቀኝ ክንፍ የፖሊስና የሚጂርቲኒያ ባንዳዎች ያቀፈ ነበር፤ ከዋርዳር አዶ–ኩራቲ–ጋጉት ጋድ–ቡላለህ ደገሐቡር ይጓዝ የነበረ።

የኢጣሊያ አግረኛ ጦር ዲቪዚዮኖች ተቨረ (Tevere)በሙቅ ሀገር የሚኖሩ ጣሊያ ኖች የተካባ እና ፔሉሬታና በተጠባባቂ ሆነው መጓጓዣ መኪናዎች ከተገኙ የሚንቀሳቀሱ።

በኢትዮጵያ በኩል ለ100.000 የኢጣሊያ ወታደሮች በምሥራቅ ጦር ግንባር በደጃዝማች ነሲቡ የሚመሩ ወታደሮች ብዛት 30.000 ብቻ ነበሩ። ሆኖም የኢትዮጵያ



ሠራዊት በነበረው አቅም ለመከላከል ሞክረዋል፤ ተፋልመዋል ጂያና ጉበ፤ ሐማንሌይ ቢርጉት፤ ጉኑጋዶ የመጀመሪያ መከላከለያ ተሰርተው ነበረ፤ መንገዶች በሙሉ ኃይለኛ መከላከያዎች ጦር ሰፈሮች ተሰርቶባቸው ነበር።

በዳጃዝማች አበበ ዳምጠውና በመኩንን እንዳልካቸው የሚመራ የኢትዮጵያ ጦር ከዳናን 40 ኪሎ ሜትር የሚርቀው ጂያና ጎበ በተባለው ቦታ ላይ ደርሰው ነበር። በጄኔራል ናሲ የሚመሩ የሊቢያ ተዋጊዎች አፕሪል 13 በኢትዮጵያ ጦር ላይ ማጥቃት ጀመሩ። አፕሪል 14በሌሎች ጄኔራሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ጦርም የማጥቃት እንቅስቃሴ ጀመሩ። ሁለት ቀን ከባድ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ ጣሊያኖች ሊያሸንፉ ችለዋል።2000 የኢትዮጵያ ወታደሮች ሞተዋል ብዙ የጦር መሣሪያ ተማርከዋል። የተማረከው ወታደር ጥቂት ነበር ምክንያቱም እንደ ሊቢያ ወታደሮች ልማድ በማለት ብቻ ግራዚያኒ በመግለፅ ፅፎል[1] የሊቢያ ወታደሮች መግደል እንጂ ማመረክ አያውቁም ማለት ነው።

ስዚሁም ነበር በተደጋጋሚ ለበላይ አካል ሊቢያውያን ወታደሮች እንዲላኩለት የጠየቀው።ግራዚያኒ እንደመሰከረው የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ቀኑን ሙሉ በአስገ ሁኔታ ሊዋጉ ውለው ሊጨልም ብቻ ማፈግፈግ ጀምረዋል። ብዙ አውሮፕላኖች ተመትቷል ሁለት ተቃጥሏል ግን የወደቁት በኢጣሊያ ይዞታ በነበረ መሬት ነው ግራዚያኒ የኢትዮጵያ ወታደሮች የተመሩት በታወቁ ጀግኖች ነው ብሏል። «ዱቼ» የደስታ መግለጫ የሊቢያ ወታደሮች በተቀዳጁት ድል ለግራዚያኒ ቴሌግራም ልኳል።

## የቢርጎት ጦርነት

አፕሪል19 በጀናርበ የተሸነፉ የኢትዮጵያ ወታደሮች እስከ ቢርጎት ድረስ ጉን ለጎን ከኢጣሊያ ወታደሮች ጋራ ከተጓዙ በኋላ ቢርጉት ላይ የውሃ ጉድጓድ ተቆጣጥረው ይዘው ከነበሩ በጄኔራል ናሲ ከሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ላይ ተኩስ ከፍተው ከጠዋቱ 10 ሰዓት ከ45 ደቂቃ እስከ ማታ 12:00 ሰዓት ሲዋጉ ውለው በመጨረሻ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሊበታተኑ ችለዋል፡ በዚሁ ቀን ጄኔራል ቨርሜ (Verme) ሙሉ ቀን ተጉዞ ማታ ደርሶ ቢርጎት ላይ ለሚገኘው የጀነራል ናሲ ጦር እርዳታ አድርገዋል። ግራዚያኒ እንደተለመደው የሞቱና የቆሰሉ ወታደሮች ሳይጠቅስ በማለፉ ለኢጣሊያኖች ግን ብዙ እንዳልቀናቸው ያሳያል። አፕሪል 20 የሊቢያ ዲቪዚዮን ከበርኩት እስከ ዳኩን ደርሰዋል።

ጄኔራል ግራዚያኒ ጄኔራል ቨርመን ከሰጋግ ወደ ደጋሙዶ እንዲቀጥል ትእዛዝ ይሰጠዋል። ከዚያም ውደ ደገሀቡር ጉዞውን እንዲቀጥል ዝግጁ እንዲሆን ይነገረዋል።

1. Graziani : Ibd. p. 312

ጀኔራል ፍሩሺና አጐስቲኒ ግን ባሉበት እንዲቆዩ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። አፕሪል 24 ከደንበሩር የመጣ 2000 የወታደር ብዛት ያለው የኢትዮጵያ ጦር በደጋ መዳ ጉድጓድ የሰፈረው የኢጣሊያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ለመፈፀም ሞክረው ግን ዱባትና የኤርትራ ባታሊዮን ወደ መጣበት እንዲመለስ አድርገውታል።

በቢርጉት ውጊያ አፕሪል 25 የኢጣሊያ የመሐል ክንፍ አዛዥ ጀኔራል ፍሩሺ በቢርጎት ያለው የሀበሻ ጦር ይዞታ በሚገባ ሰልሎ አጥንቷል ጠንካራ ምሽግ እንደሆነ በሚገባ ተረድቶ ነበረ ይሁን እንጂ የሀበሻ መከላከያ ምሽግ ለመደምሰስ በቂ ኃይል እንዳለው ይተማመን ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ፊታውራሪ ሚሊዮን በምስራቅ ከነበሩት የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ታዋቂነት አልነበረውም፤ እሁንም በቢርጉት የሰራው ጀብድ የሚያስታውሰው ሰው የለም። ግራዚያኒ ጠንካራ የጦር መሪ ተሰሚነት ያለው መሆኑን በደረሰው መፅሐፍ መስክሮለታል።በቢርጎት የሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ኢጣሊያ ከነበራት መጣሪያ የሚወዳደር ባይሆንም ብዙ መጣሪያ ነበረው የተሰሩት ምሽጎች በአይሮፕላን ሊያዩዋቸው እንዳይችሉ የተሰሩ ነበሩ፤በከባድ መጣሪያም እንዳይመቱ የተሰሩ ነበሩ። ጦርነቱ የተጀመረው አፕሪል 24 ጠዋት በ1:00 ሰዓት ከኢጣሊያ ውጪ የሚኖሩ ጣሊያኖች የተውጣጡ ወታደሮች ሁለት ባታሊዮን ነበረ። የተጀመረውም ከቢርጉት በምሥራቅ ነበር፤ ዓላማውም ጉማር የተባለው ተራራ ለመቆጣጠር ነበር። ከኢጣሊያ ውጪ የሚኖሩ የኢጣሊያ ወታደሮች የተራራ ዝቅተኛ ቦታዎች ለመያዝ በቅተው ነበር፤ሆኖም በደረሰባቸው ከባድ ጉዳት የሀገሩን ሙቀትም ለመቋቋም ስላቃታቸው ውጊያውን አቆሙ፤ የእንዲጂኒ ወታደሮች በቦታው ተተክተው ውጊየውን እንዲቀጥሉ ተደረገ። ከ4:ሰዓት ጦርነት በኋላ የኢንዲጂኒ ወታደሮች ከምሽጉ ሆነው እያነጣጠሩ ስለፈጁቸው ወደ ፊት ሊገሰግሱ አልቻሉም የኢጣሊያ መድፎችም በብዙ ትግል በኋላ መከላከያውን ለመስበር ችሎ ነበር።

ከሰዓት በኋላ ውጊያው ቀጥሎ ውኃል የጨበጣ ውጊያም ይደረግ ነበር፤ አውሮፕላኖች እርዳታ ለማድረግ አልቻሉም ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች ይዋጉ የነበሩት ተቀራርበው ስለሆነ ወገን ለይተው ቦምብ ለመጣል ችግር ነበረባቸው፤ ቦምብ ቢጥሉም የኢትዮጵያ ተከላካዮች በጉጓድ ሆነው ይተኩሱ ስለነበር ሊያገኟቸው አልቻሉም።

በቀኝ በኩልም የእንዲጀኒ ወታደሮች መጀመሪያ 6ኛ ባታሊዮን በጣሊያኖች ተተካ ቀጥሎም ሶስተኛ ባታሊዮን ስድስተኛን ተካ ከባድ ማጥቃት ቢሞክሩም የኢትዮጵያ ተከላካዮች ወጥረው ስለያዝዋቸው ወደ ፊት መግፋት ሳይችሉ ቀሩ።በ11 ሰዓት 6ኛ ባታሊዮን እንዲጂኒ እንዲሁም 2ኛ ሁድን ባንዳ በውጊያ ቢካፈሉም ኢትዮጵያውያን አልተበገሩም። ጀኔራል ፍሩሺ በዚሁ ጊዜ ወታደሮቹ ካሉበት እንዳይለቁ በበማድረግ



የጀኔራል አጎቲኒ እርዳታ ይጠይቃል። ማታ ውጊያው የቆመ መስሎ ነበር ለሊቱ ግን እንደገና በማገርሸት ቀጠለ።

የኢትዮጵያውያን ፊት የነበሩት 4000 ወታደሮች ሌላ 1000 ጨመረላቸው፤ ከጦር ሰፈር እየወጡም ጣሊያኖችንን ለማባረር ሞክረው ነበር። ጣሊያኖች ግን የእጅ ቦምብ በመወርወር ሊያከሽፉ ችለዋል። ግራዚያኒ ጀኔራል ፍሩሺ ም ጀኔራልአጎቲኒ እንዲረዳው ያቀረበው ጥያቄ አልተቀበለውም ምክንያቱም በጎኑ ጋዱ ሌላ ውጊያ ለማድረግ እየተዘጋጀ ስለነበረ ነው።

ግራዚያኒ የፍሩሺ የመሐል ክንፍ ጦር ብቻው ካስፈለገም ዕረፍት ካደረገ በኋላ የኢትዮጵያ ተከላካዮችን ለመደምሰስ መቻል እንዳለበት ነገረው። ለማግስቱ አፕሪል 25 ቀን1936 ዓ/ም በመድፎች ኃይለኛ ድብደባ በኋላ ሁሉም ባታሊዮኖች ማጥቃት ሲጀምሩ የኢትዮጵያ ጦር ከዋና ምሽጉ ለቆ ሲወጣ ጣሊያኖች ተከታትለው በሚሸሸው የኢትዮጵያ ጦር ላይ ጉዳት እንዳያደርሱበት በመከላከል የተመደቡት ወታደሮች ስለነበሩ በሥነ-ሥርዓት በእርጋታ ከጦር ሰፈሩ ሊወጣ ችሏል። በዚሁ ጊዜ የሚሸሹ ኢትዮጵያውያንን ለማሳደድ የጀኔራል ናሻ የግራ ክንፍ ጦር ተካፋይ ሆኖ ከቢርጉት እስከ ሐማንሳይ ድረስ ተከታትለው ማጥቃት ቀጠለ።

ባልተለመደ ሁኔታ ግራዚያኒ በመጽሐፉ በሁለቱ ወገኖች የደረሰ ጉዳት ገልጾዋል[1] በኢትዮጵያ በኩል ከ600 ወታደሮች የሚበልጡ ሞተዋል ወይንም ቆስለዋል። በኢጣሊያ በኩል በሁለቱ ቀኖች የሞቱት አስር የኢጣሊያ መኰንኖች የኢንዲጂኒ ወታደሮች ይመሩ የነበሩ፤ እንደዚሁም ሁለት በውጭ ሀገር የሚኖሩ ጣሊያኖች ሲሞቱ የቆሰሉት ዘጠኝ፤ የኢጣሊያ እንዲጂኒን የሚመሩ መኰንኖች አንዱ ከኢጣሊያ ወጭ የሚኖሩ ጣሊያኖች 9 የኢጣሊያ ወታደሮች፤የኢንዲጂኒ ወታደሮች የቆሰሉና የሞቱ በትክክል ቁጥራቸው አይታወቅም መስለኝ ከ600 መቶ የሚበልጡ ነበሩ ብሏል። በድምሩ 31 ጣሊያኖች የሞቱና የቆሰሉ ከ600 የሚበልጡ አንዲጀኖች አብዛኛው ከሶማሌና ዓረቦብ ድብልቅ የነበሩ ባታሊያኖች ስለዚህ 5% ያነሱ ብቻ ጣሊያኖች ሲሆኑ የቀሩት እንዲጂኒ ነበሩ ከሰሜን ጦር ግንባር የባሰ ጦርነቱ የተከሄደው በኢንዲጂኒ ወታደሮች ብቻ ነበረ። የተማረኩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ጥቂት ነበሩ፤ እነሱም ቆስለው ወድቀው የተገኙ ብቻ ነበሩ።

---

1.Graziani : Ibd. p. 323

# የጉኑ ጋዱ ጦርነት

የጉኑ ጋዱ ጦርነት በኢትዮጵያ በኩል ማን እንደነበረ የጦር መሪ ግራዚያኒ በመፅሐፍ አልጠቀሰውም፣ የወታደሩ ብዛት ግን በግምት ከ1000 እስከ 1500 ነበረ። በኢጣሊያ በኩል በሁለት ኮሎኔሎች በአራት ሻለቆች በ2 ሻንበሎች የሚመሩ አብዛኛው ተዋጊዎች ባንዳዎች ነበሩ። ጣሊያኖች በሰሜንና በደቡብ መውረር ጀመሩ። ቦታው በአንድ ወንዝ አካባቢ ጥቅጥቅ ያሉ ዛፎች የተሸፈነ ነበር። ጦርነቱ በመድፍ ድብደባ በ1:30 ሰዓት ተጀመረ በሁለት ሰዓት እስከ 2:30 የጦር አውሮፕላኖች ቦምብ ይጥሉ ነበረ። ከዚህ በኋላ ጣሊኖች በ2 ጄኔራሎች እየተመሩ ወደ ምሽጎች እየተጠጉ መጡ። ኢትዮጵያውያን የማይታዩ እርስ በእርሳቸው ውስጥ ለውስጥ የሚገናኙ በጥበብ የተሰሩ ጉድጓዶች ተደብቀው በቅርብ ርቀት በሚመጡባቸው የኢጣሊያ ባንዳዎች ከፍተኛ ተኩስ ያወርዱባቸው ነበር። በሰሜን በኩል አጥቂ የነበረ ሌ/ኮሎኔል ቺስተርኒ (Cisterni) የባንዳ ተዋጊ ወደ ፊት መግፋት ስላቃተው ጄኔራል አጎስቲን የሻለቃ ሻዳላ የባንዳ ጦር በተጨማሪ ተቀላቅሎ እንዲያጠቃ አዘዘው። ሆኖም ወደ ፊት ገፍተው ምሽጉን መክበብ አልቻሉም። ከባድ ውጊያ ቀጥሎ ጣሊያኖች ከ5 ሰዓት በጃረር ወንዝ ጉዳጓዶች ብቅ አሉ። ቀኑን ሙሉ ከጉድጓዶች አንድ በአንድ ለማስለቀቅ ጦርነት ሲያካሂዱ ሰሊት የተከላካዮች አብዛኛዎቹ በወንዙ ተሻግረው ወጡ ሌሎች ወደ ቡላህ አቅጣጫ ወጡ። ጠዋት አፕሪል 25 ቀን ጣሊያኖች አሰሳ ቀጠሉ። ግራዚያኒ እንደተረከው የኢትዮጵያ የጦር አለቆች ተዋጊዎችን በቦታው እየተዋጉ እንዲሞቱ እንጂ ከቦታው ለቀው ወደ ቡላለህ እንዳይሸሹ ትእዛዝ ሰጥተዋቸው ነበር። ከሸሹ እንደሚገደሉ ተነግሯቸው ነበር፣ ወይንም ደግሞ እንዳይሸሹ በብረት እግራቸውን ይታሰሩ ነበር።

ጣሊያኖች በሌላ ከባድ መሣሪያ ሲያቅታቸው በእጅ ቦምብና ቤንዚን እየረጩ ጉድጓድ ውስጥ ቀርተው በሚዋጉ ኢትዮጵያዊያን በእሳት ፈጅዋቸው። በጣሊያኖች ግምት በጉድጓ ዶች በቤንዚን የተቃጠሉ ኢትዮጵያውያ ከምሽግ ውስጥ ሲወጡ ጣሊያኖች እንዲያዩዋቸው መንገዱን ለቀው ወደ ሜካ ገቡ። ቆይተው ግን አንዳንዶቹ በውሃ ጥምና በረሐብ ደክመው በዚሁ ሜካ ውስጥ በኢጣሊያኖች እጅ ገቡ። አፕሪል 25 በዚህ ግንባር ተሰልፈው የተዋጉ የኢጣሊያ ተዋጊዎች ብዛት 38.000 ይደርስ ነበረ፤ ከእነሱ ውስጥም 15.000 ጣሊኖች ነበሩ።

ቀደም ብሎ ግራዚያኒ በላከው ቴሌግራም ባልተሟላ ማስረጃ የደረሰው ጉዳት በገራ ዳጋ ሜዳ የሞቱና የቆሰሉ 50 ወታደር ያሀል 15 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖችና 4 ተራ ወታደሮች 200 ኤንዲጂኒ ብሎ ነበረ። በጉኑ ጋዱ የሞቱና የቆሰሉ 1 ሻምበል የሞተ እና 5 ተራ ወታደሮች ሞተዋል። የቆሰሉ ሶስት የኢጣሊያ መኰንኖች 4 ባለ ሌላ ማዕርጎች 30 የኢጣሊያ ወታደሮች እና 20 ዱባት ብሎ ነበር። ነገር ግን አፕሪል 26 እስከ 3:00 ሰዓት ድረስ በተገኙ የመጨረሻ መረጃዎች መሠረት ባጠቃላይ በኢጣሊያ በኩል 1ኛ በጂናግቦ 2ኛ ጉኑ ጋዱ 3ኛ በቢርጉት ጦርነቶች ባለ ሌላ ማዕረጎችና ተራ ወታደሮች ጣሊያኖች የሞቱት 27 የቆሰሉት 47 ነበሩ። እንዲጂኒ የሞቱና የቆሰሉ 1387 ነበሩ። ስለዚህ ከሰሜን ጦር ግንባር በባሰ ሁኔታ ጦርነት የተካሄደው አፍሪካውያን እርስ በእርሳቸው ነበረ፤ ጣሊያኖች የሞቱም ሆነ የቆሰሉት ቁጥር 5% የሚጠጋ ነበር።

አፕሪል 29 ሳሳባነህና ቡላለህ በጣሊያኖች እጅ ወደቁ። ጣሊያኖች ሳሳባነህን ቡላለህንና ደጋሐቡር ጠንካራ የኢትዮጵያ ምሽጎች የተገመተ በጦርነት ለመያዝ በሚዘጋጁበት ጊዜ አፕሪል 28–29 ሌሊት በተገኙ ማስረጃዎች የኢትዮጵያ ጦር ሰፈሩን ለቆ መውጣቱን ጣሊያኖች ስላወቁ ግራዚያኒ ጄኔራል ናሲ ደገሐቡርን እንዲያዝ ጄኔራል ፍሩሺ ሳስባነህን ጄኔራል አጎስቲኒም ቡላለህን እንዲይዝ አዘዛቸው።

ከደጋሐቡር መያዝ በኋላ ግራዚያኒ አፕሪል 30 ባደረገው ቴሌግራም በኢጣሊያ የደረሰው ጉዳት 50 የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች የሞቱና የቆሰሉ። 2000 (ሁለት ሺ) የኢጣሊያና የኢንዲጂኒ የሞቱና የቆሰሉ አድርሶታል። የደጃዝማች ነሲቡ ጦር የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የነበረው የአውሮጳውያን አማካሪዎች የነበሩት በሚገባ የሰለጠነ ጦር በሚገባ የተመገበ የቅንጦት መጠጦችን እንደ ኮኛክ ይቀርቡለት የነበረ እስከ መጨረሻ አቅሙ ተዋግቶ 5000 ሰው ጉዳት ደርሶበታል።ጣሊያኖች በኢትዮጵያ የወታደራዊ ምሽጎች ፀረ ፋሽዝም ጋዜጦች ደብዳቤዎች አግኝተዋል። ደጃዝማች ነሲቡና የቅርቡ ጄኔራል ውሂብ ፓሻ ሸሽተው ወደ ጅጅጋ እያመሩ ሄዱ።

ጅጅጋ ሜይ 6፤ ሐረር ሜይ 8፤ ድሬደዋ ሜይ 9፤ በጣሊያኖች ተያዙ። ሜይ 5 የሰሜን የኢጣሊያ ጦር አዲስ አበባ የገባበት ቀን ገራዚያኒ ጄኔራል ናሲን ወደ ሐርሆ እንዲያመራ ያዘዋል። ድሬዳዋ ሲገቡ መጀመሪያ ለመግባት ዕድል እንዲሰጣቸው ከኢጣሊያ ውጭ የሚኖሩ ጣሊያኖች ነበር፤ ከአዲስ አበባ የመጣ የሰሜን ጦርም ከእነሱ ቀጥሎ ገባ።

ግራዚያኒ ጦሩን በመምራት ድሬዳዋ ለመግባት ፈልጎ ነበረ። ነገር ግን የጅጅጋ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ጉብኝት በሚያደርግበት ጊዜ ሕይወቱን ለማጥፋት በጣሉበት አደጋ በጉድጓድ በመግባቱ በመላ ገላው ትጥቅጥና ቁስል ስለደረሰበት በሥነ ስርዓቱ ሳይካፈል ቀርቷል። በዚሁ በግራዚያኒ ላይ የተፈጸመው የመግደል ሙከራ፤ አዲስ አበባ ላይ እንዳደረጉት ሁሉ አካባቢው በነበረው ሕዝብና በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጣሊያኖች ምን አጠፉ እርምጃ እንደወሰዱ ግራዚያኒ በመጽሐፉ የገለፀው ነገር የለም።

በአጠቃላይ በሰሜን ጦር ግንባር የሞቱና የቆሰሉ ኤርትራውያን 2005 ጣሊያኖች 3103 ፤270 የጦር መኰንኖች 2833 ተራ ወታደሮች፤ በድምሩ 5108 ነበሩ።

በደቡብ ጦር ግንባር ማርሻል ግራዚያኒ በደረሰው መጽሐፍ የሞቱና የቆሰሉ በደረናው 2150 ብሎ ጽፈዋል። ጀኔራል ፍሩሺ ግን በዝርዝር በማውጣት ያነሰ ቁጥር ነው የመዘገበው። የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች የስም ዝርዝራቸው ሳይቀር በማውጣት የሞቱ 61 የቆሰሉ 81 ብሎ አውጥቷል።

## የኢንዲጀኒ ዝርዝር በማዕርጋቸው እንደሚከተለው አውጥቷል።

| | የሞቱ | የቆሰሉ |
|---|---|---|
| ሹምባሽ | 5 | 7 |
| ቡሉቅባሽ | 19 | 66 |
| ሙንጣዘ | 34 | 111 |
| አስካሪ መደበኛወታደር | 118 | 454 |
| ዛፕቲየ(ፖሊስ) | 21 | 1 |
| ሽሞች (አዛዦች) | 42 | 1 |
| የባንዳ ሹሞች | 10 | 38 |
| ምክትል ሹሞች | 41 | 61 |
| ዱባት (ባንዳ መደበኛ ያልሆኑ | 2 | 32 |
| ያልተመደቡ | 38 | 54 |
| ድምር | 432 | 1055 |
| ጣሊያኖች | 81 | 81 |
| | 513 | 1136 |

### ድምር 1649

በሰሜንና የደቡብ ጦር ግንባር የሞቱና የቆሰሉ 3492 ኢንዲጀኒ 3265 ጣሊያኖች በድምሩ 6757 ነበሩ፡ ይኸውም በማርሻል ግራዚያኒ የተሰጠው ቁጥር ሳይሆን በጀኔራል ፍሩሺ የተሰጠው ቁጥር በመውሰድ ነው።



# ምዕራፍ 13
## የኢጣሊያ ቂም በቀል

40 ዓመት ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች የሽንፈታቸውን ቂም በቀል የተወጡት በልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች አፈጻጸም፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ የቀድሞ የጦር አውድማዎች በማክናወን ነው።

ማሪዮ አፕሉስ Mario Appellus የተባለው ኢጣሊያዊ በደረሰው መጽሐፍ[1] ‹የኢጣሊያ ቂም በቀል አወጣጥ በሚገባ አብራርቶ ጽፏል።

አክቶበር 3 1935 ከጧቱ 11 ሰዓት የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ለብዙ ጊዜ ዝግጅቱን አጠናቀው በመረብ የኢትዮጵያ ወሰን ጥሰው በመግባት ጦርነቱን ጀመሩ። የመጀመሪያ ጥሰው የገቡት ወታደሮች ኤርትራውያንና ባለ ጥቁር ሸሚዝ Camicce Nere የሚባሉ ፍሺስቶች ነበሩ። ኤርትራውያን መዋጋት ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈለጋሉ፣ ጥቁር ሸሚዞች ኢጣሊያን ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈልጋሉ። የመጀመሪያ የተገኙ የትግራይ ነዋሪዎች ሮማዊ ሰላምታ እየሰጡ የኢጣሊያ ወታደሮችን ተቀብሏቸዋል። የትንሽ መንደር ነዋሪዎች ማር፣ ዶሮዎች፣ እንቁላሎችና ወተት ያቀርባሉ፣ ትልቅ መንደሮች ፍየሎችና በሬዎች ያቀርባሉ።

1ኛ በአድዋ ጦርነት ምክትል መቶ አለቃ የነበረው፣ በዓዲግራት ተከበው የነበረው፣የኢጣሊያ ጦር አባል የነበረው፣አሁን ጀነራል የሆነው ሳንቲኒ በሚመራው የኢጣሊያ ጦር ምንም ተኩስ ሳይሰማ አዲግራት በጣሊያኖች እጅ ወደቀች።

2ኛ አምባ አውገር የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች አነስተኛ ተኩስ ከፍተው ወደ ኋላቸው ሸሹ። ጀኔራል ፒርሲዮ–ቢሮሊ ‹Pirzio -Biroli› የአካባቢው የኢጣሊያ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ከፍ በማድረግ መፈክር በማሰማት አክቶበር 5 ቀን 1935 ዓ.ም የአንባ አውገር በኢጣሊያ መያዝ በሚከተለው ያከብረዋል።

ጀኔራሉ ‹Seluto Al Re› ለንጉሡ ሠላምታ ሲል፣

ወታደሮቹ ‹Viva Il Re› ንጉሡ ለዘላለም ይኑር ብለው ይመልሳሉ

ጀኔራሉ ‹Saluto al Duce› ለዱቼ ሠላምታ ሲል፣

ወታደሮች ‘A Noi›ለእኛ ይላሉ

3ኛ ዐድዋ በቀኝ በኩል መረብ የተሻገሩ በጀነራል ማራቪኛ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ግን አክቶበር 3 መረብ እንደተሻገረ ተኩስ ገጠመው።

1.Mario Appellus : I L Crollo Dell' Impero del Negus

በደቡብ ጦር ግንባር ማርሻል ግራዚያኒ በደረሰው መጽሐፍ የሞቱና የቆሰሉ በደፈናው 2150 ብሎ ጽፈዋል። ጄኔራል ፍሩሺ ግን በዝርዝር በማውጣት ያነሰ ቁጥር ነው የመዘገበው። የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች የስም ዝርዝራቸው ሳይቀር በማውጣት የሞቱ 81 የቆሰሉ 81 ብሎ አውጥቷል።

## የኢንዲጆኒ ዝርዝር በማዕርጋቸው እንደሚከተለው አውጥቷል።

| | የሞቱ | የቆሰሉ |
|---|---|---|
| ሹምባሽ | 5 | 7 |
| ቡሉቅባሽ | 19 | 66 |
| ሙንጣዝ | 34 | 111 |
| አስካሪ መደበኛወታደር | 118 | 454 |
| ዛፕቲየ(ፖሊስ) | 21 | 1 |
| ሽሞች (አዛዦች) | 42 | 1 |
| የባንዳ ሹሞች | 10 | 36 |
| ምክትል ሹሞች | 41 | 81 |
| ዱባት (ባንዳ መደበኛ ያልሆኑ | 2 | 32 |
| ያልተመደቡ | 38 | 54 |
| ድምር | 432 | 1055 |
| ጣሊያኖች | 81 | 81 |
| | 513 | 1136 |

### ድምር 1649

በሰሜንና የደቡብ ጦር ግንባር የሞቱና የቆሰሉ 3492 ኢንዲጆኒ 3265 ጣሊያኖች በድምሩ 6757 ነበሩ፡ ይኸውም በማርሻል ግራዚያኒ የተሰጠው ቁጥር ሳይሆን በጄኔራል ፍሩሺ የተሰጠው ቁጥር በመውሰድ ነው።



# ምዕራፍ 13
## የኢጣሊያ ቂም በቀል

40 ዓመት ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች የሸንፈታቸውን ቂም በቀል የተዋጡት በልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች አፈጻጸም፤ በተለይ የኢትዮጵያ የቀድሞ የጦር አውድማዎች በማክናወን ነው።

ማሪዮ አፔሉስ Mario Appellus የተባለው ኢጣሊያዊ በደረሰው መጽሐፍ[1] ‹የኢጣሊያ ቂም በቀል አወጣጥ በሚገባ አብራርቶ ጽፏል።

ኦክቶበር 3 1935 ከጧቱ 11 ሰዓት የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ለብዙ ጊዜ ዝግጅቱን አጠናቀው በመረብ የኢትዮጵያ ወሰን ጥሰው በመግባት ጦርነቱን ጀመሩ። የመጀመሪያ ጥሰው የገቡት ወታደሮች ኤርትራውያንና ባለ ጥቁር ሸሚዝ Camicce Nere የሚባሉ ፍሺስቶች ነበሩ። ኤርትራውያን መዋጋት ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈልጋሉ፤ ጥቁር ሸሚዞች ኢጣሊያን ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈልጋሉ። የመጀመሪያ የተገኙ የትግራይ ነዋሪዎች ሮማዊ ሰላምታ እየሰጡ የኢጣሊያ ወታደሮችን ተቀብሏቸዋል። የትንሽ መንደር ነዋሪዎች ማር፡ ዶሮዎች፡ እንቁላሎችና ወተት ያቀርባሉ፤ ትልቅ መንደሮች ፍየሎችና በሬዎች ያቀርባሉ።

1ኛ በአድዋ ጦርነት ምክትል መቶ አለቃ የነበረው፤ በዓዲግራት ተከበው የነበረው፤ የኢጣሊያ ጦር አባል የነበረው፤ አሁን ጄነራል የሆነው ሳንቲኒ በሚመራው የኢጣሊያ ጦር ምንም ተኩስ ሳይሰማ አዲግራት በጣሊያኖች እጅ ወደቀች።

2ኛ አምባ አውገር የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች አነስተኛ ተኩስ ከፍተው ወደ ኋላቸው ሸሹ። ጄኔራል ፒርሲዮ–ቢሮሊ ‹Pirzio -Biroli› የአካባቢው የኢጣሊያ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ከፍ በማድረግ መፈከር በማሰማት ኦክቶበር 5 ቀን 1935 ዓ.ም የአንባ አውገር በኢጣሊያ መያዝ በሚከተለው ያከብረዋል።

ጀኔራሉ ‹Saluto Al Re› ለንጉሡ ሠላምታ ሲል፤

ወታደሮቹ ‹Viva Il Re› ንጉሡ ለዘላለም ይኑር ብለው ይመልሳሉ

ጀኔራሉ ‹Saluto al Duce› ለዱቼ ሠላምታ ሲል፤

ወታደሮች ‘A Noi› ለእኛ ይላሉ

3ኛ ዐድዋ በቀኝ በኩል መረብ የተሻገሩ በጀነራል ማራቪኛ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ግን ኦክቶበር 3 መረብ እንደተሻገረ ተኩስ ገጠመው።

1.Mario Appelius : I L Crollo Dell' Impero del Negus



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከይፋ ሲወርዱ

(fot. Associated Press - Londra)
Hailè Selassiè scende, a Caifa, dall'incrociatore «Enterprise»



እንደተለመደው መንገድ የሚፈትሽ የፊት አጥቂ ፊት አውራሪ ጦር ባንዲ ናቸው። በመቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ ደጋፊ ‹Morgantini› የሚመራ ባንዳ ራማ ላይ ተኩስ ተከፈተበት፤ የመቶ አለቃው አፈቱ ላይ በጥይት ተመቶ Viva l'Italia እያለ ሲሞት የመጀመሪያ ኢጣሊያዊ በጦር ሜዳ የሞተ ሆነ። ከባንዳዎች ምን ያህል ሰው እንደሞተና እንደቆሰለ አልተገለጠም። ጣሊያኖች በዐድዋ የነበረው በራስ ሥዩም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ተቃውሞ ገጠማቸው፤ ታማኝ የኤርትራ ወታደሮችና ባንዳዎች እያስቀደሙ በእግረኛ የኢጣሊያ ነጭ ወታደሮች እየታገዙ ኦክቶበር 4 እና 5 በዳዕር ተክሌ እና አካባቢው ውጊያ ሲካሄድ ቆይቶ ኦክቶበር 6 ዐድዋ በጣሊያኖች እጅ ስትወድቅ በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ለሞቱ ጣሊያኖች በአንድ መታብር ሐውልት የሚቆመው ቀደም ብሎ የተጻፈው «በዐድዋ የሞቱ በድል አድራጊዎች ተበቅሏል። በሚል የመታሠቢያ ጽሑፍ በማቆም ዐድዋ ለዘለዓለም ኢጣሊያዊት አድርገናታል ብሏል። ኦክቶበር 14 የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረው ዴ ቦኖ በጦር ሹማምንቶቹ ታጅቦ ዐድዋ ገባ፡ በዐድዋ የሞቱ ጣሊያኖች ፋሺስት ኢጣሊያ ስለተበቀለቻቸው በሠላም መተኛት ይችላሉ በማለት ንግግር አሰምተዋል።

ወደ ትግራይ የገባው የኢጣሊያ ጦር 100.000 ብዛት ነበረው። ኦክቶበር 16 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ትሆናለህ ብለው ጣሊያኖች ሀገሩን እንዲከዳ ያደረጉት የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የአፄ ኃይለ ሥላሴ አማች የምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ገዥ የነበረው በአንድ ተራ ኢጣሊያዊ ሥር ሆኖ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የዐጋሜ ገዥ አድርጉ ሾሙት።

ኦክቶበር 23 ለወደፊት የዴ ቦኖ ቦታ የሚረከብ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ሹመት ያገኘው ማርሻል ባዶሊዮ ለሥራ ጉብኝት ዐድዋ ድረስ መጥቶ ስለነበረ ጦርነቱ ወደ ፀተደረገበት ቦታ በመሄድ ድምጹን ከፍ በማድረግ ‹በዐድዋ የሞታችሁ ሁሉ› ብሎ ይጠራል።

የተሰበሰቡ ጀኔራሎች–ወታደሮች በተጠንቀቅ ቆመው በሙታኑ ስም ሆነው «አቤት»Presente ብለው መልስ ይሰጣሉ።

በዐድዋ ጦርነት የተሳተፉ እንደገና ዐድዋ በኢጣሊያ ሥር የተሳተፉ ኤርትራውያን በፈረስ ሆነው የብረት ሰላምታ ያቀርባሉ። በዚሁ ዐይነት የዐድዋ ቲም በቀል አከባበር ተፈጽሟል።

በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ጣሊያኖች ወታደሮቹን ሲገድሉ የነበሩ የትግራይ ነዋሪዎች አጆች አሁን የኢጣሊያ ልጆች ወደ ዐድዋ በሚመለሱበት ጊዜ ለኢጣሊያ ባንዲየራ ሮማዊ ሠላምታ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።



Fot. Keystone - Londra

Una signora inglese offre fiori ad Hailé Selassié, al suo arrivo a Londra!

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በለንደን ሲደርሱ ከአንድ እንግሊዛዊት ወይዘሮ እንኳን ደህና ገቡ በማለት የአቅፍ አበባ ሲበረከትላቸው



መቀሌን ለመያዝ የተሰጠው ትዕዛዝ ኖቬምበር 2 ነበር፤ ኖቬምበር 3 ከጧቱ 12 ሰዓት ከዕዳጋ ሐሙስ ከሀዲው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሀገሩን ሥለለቀቀላቸው ውጊያ የሌለው ጉዞ ወደ መቀሌ ይጀምራሉ። የፊት እጥቂ መንገድ ጠራጊዎች ኢንዲጀኖች ‹ኤርትራውያን› ባንዳና መደበኛ ነበሩ። ኖቬምበር 5 ገሬዓልታ ላይ ከኢትዮጵያ ትንሽ ተቃውሞ ገጠማቸው ው፤ ሆኖም በቀላሉ እንዲሸሹ አደረጓቸው ኖቬምበር 8 ጣሊያኖች መቀሌ አካባቢ ሲደርሱ አሬዮፕላኖቻቸው መቀሌ ውስጥ የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደ ነበሩ ተመልክተው ተመ ለሱ። ግፈኞች ጣሊያኖች መቀሌ ሲገቡ የግማሽ ትግራይ አዛዥ የነበረው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የአንድ ምክትል ወረዳ፤ የጄመና ዋና አዛዥ በማድረግ የፊት እጥቂ ለጣሊ ያኖች መንገድ ጠራጊ በማድረግ ኖቬምበር 9 ቀን ምንም ውጊያ ሳይገጥማቸው መቀሌ ገቡ።

መቀሌ 1888 ዓ.ም ‹1896› ጣሊያኖች ከ40 ዓመት በፊት ግለት ጃንዋሪ 6 1896 ዓ.ም ምሽግ ሰርተው ጦር ሰፈር መሥርተው የነበረው የአንድ ሻለቃ ጦራቸው በአፄ ሚኒልክ የሚመራው በኢትዮጵያ ጦር ተከቦ እንደነበረ ያስታውሳሉ። በከበባው ጊዜ የተከበቡ ጣሊያኖች እጃቸውን እንዲሰጡ ከኢትዮጵያውን ተጠይቀው ፍቃደኞች ስላል ነበሩ ወደ ምሽጉ ገብው ለመግባት ለሁለት ቀን ኢትዮጵያኖች ሞከረው ስላልተሳካላቸው በእቴጌ ጣይቱ የጦር ታክቲክ በመመራት በሶስተኛ ቀን ጣሊያኖች ውሃ የሚቀዱበትን ቦታ እጥቅቶ ለመያዝ የሞከረው የኢትዮጵያ ጦር ስለተሳካለት፤ ጣሊያኖችን መልሶ ለማጥ ቃት፤ምንጩን ለመያዝ ስላልሞከሩ፤ ጣሊያኖች የሚጠጡበት ውሃ አጡ።

አፄ ምኒልክ ጣሊያኖች በውሃ ጥም በከንቱ ሰው እንዳያልቅ እጃቸውን እስከሚሰጡ ድረስ በኃይል የማጥቃት እርምጃ እንዳይደረግ አዘዙ። ጃንዋሪ 10 ጣሊያኖች ከነበራቸው የተጠራቀመ ውሃ ሊጋግ ከብቶች እንዳይበጥ አገዱ። ጃንዋሪ 11 ለመጠጣት ካልሆነ ለሌላ ነገር እንዳ ይጠቀሙ አገዱ፤ በ12 ለእያንዳንዱ ወታደር በቀን አንድ ሊትር ብቻ ውሃ እንዲታደል አደረጉ። በ15 ግማሽ ሊትር ብቻ በቀን እንዲታደል ተደረገ። በ18 ሩብ ሊትር ብቻ በቀን እንዲታደል ተደረገ። በ20 ጣሊያኖች የነበራቸው ውሃ ጥቂትና ጭቃ የተቀላቀለበት ነበር። ቁስለኞቻቸው በውሃ ማጠብ ስላልቻሉ ከውሃ ጥም ሌላ ቁስላቸው በስብሶ ይሞቱ ነበር፤ ያልሞቱም በውሃ ጥም ይሰቃዩ ነበር። ጣሊያኖች በተደጋጋሚ ከጦር ምሽጋቸው መሳሪያ ቸውን እንደያዙ በሰላም እንዲወጡ ከአፄ ምኒልክ የቀረበላቸው ጥሪ ሳይቀበሉ ከቀሩ በኋላ ከበላይ አለቆቻቸው ስምምነት ስለደረሰ ጃንዋሪ 21 ቀን ምሽጋቸውን ለቀው በክብር መውጣታቸው በከፍተኛ ኩራት ያስታውሱታል።

ኤርትራውያን የቅጥር ወታደሮች፤ የኢጣሊያ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች፤ ታዋቂ ሰዎች፤ ባለሥልጣኖች፤ የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች፤ ሌሎችም በበዓሉ ተካፋይ እንዲሆኑ ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች በተገኙበት ግፍ የማይሰማቸው ጣሊያኖች ከሐዲው ደጃዝማች ኃይለ



Negus Hailé Selassié giunge a Southampton il 3 giugno 1936-XIV (Int. Associated Press - Londra)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በእንግሊዝ ሀገር አቀባበል ሲደረግላቸው



ሥላሴ ጉግሳ በመቀሌ ከተማ የኢጣሊያ ባንዲራ እንዲተከል አደረጉት፤ ልዩ ልዩ መዝሙሮችና ብሔራዊ መዝሙር እየዘመረ አንድ ኢጣሊያዊ ኰሎኔል ድምጹን ከፍ በማድረግ «ሻለቃ ጋሊያኖ» ብሎ ይጠራል።

ሁሉም ሺህ የሚቆጠሩ የተሰበሰቡ ወታደሮች አቤት presente በማለት መልስ ይሰጣሉ።

እንደ ገና ኰሎኔሉ «በ1896 ዓ.ም የሞታችሁ ወታደሮች» በማለት ሲጠራ፤

ሁሉም ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች አቤት ‹presente› የሚል መልስ ይሰጣሉ።

በመጨረሻም በተለመደው የኢጣሊያኖች መፈክር፤

ለንጉሡ ሰላምታ Saluto Al Re ብሎ አዛዥ ሲጮህ ወታደሮች Viva Il Re ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር የሚል ጩኸት ከወታደሮቹ መልስ ይሰጣል። Saluto Al Duce ቢ ሰላምታ ለዱቼ የሚል ጩኸት አዛዥ ሲያሰማ ወታደሮች፣ ጀኔራሎች፣ሲቪሎች በአንድ ላይ A Noi ለእኛ በሚል ጩኸት መልስ ይሰጣሉ።

በዚህ ዐይነት የመቀሌ በጣሊያኖች እጅ መውደቅና ከ40 ዓመት በኋላ የቀድሞ የሽንፈታቸውን ቂም በቀል ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።

# አምባ አላጂ

በጀኔራል ሞንታኛ Montagna የሚመራ የኢጣሊያ ጦር ፌብሯሪ 28 1936 ዓ.ም አምባ አላጂን ጣሊያኖች በተቆጣጠሩ ጊዜ እንደተለመደው መፈክር በማሰማት ነበር ቂም በቀላቸውን ያሰሙት።

ጀኔራሉ «ሻለቃ ቶዜሊ» Maggiore Toselli ብሎ ሲጠራ ወታደሮች በሻለቃ ቶዜሊ ስም አቤት Presente ብሎ ይመልሳሉ።

ቀጠሉም ጀኔራሉ «የክብርና የመስዋእትነት የጦር ጓዞቹ» ብሎ ሲጠራ፣

ወታደሮች በሙታኑ ስም አቤት Presente በማለት መልስ ይሰጣሉ።

የቀድሞ የአምባላጂ ጦርነት የቂም በቀል መታሰቢያ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ተከብሯል።

በተምቤን፣በእንደርታ፣ በሽሬ፣ በማይጨው ላይ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ያደረጓቸው ጦርነቶች ኢጣሊያኖች ድል ሊቀዳጁ የቻሉት 1ኛ ባሰማሩዋቸው ወታደሮች ብዛት 2ኛ በነበራቸው የጦር መሣሪያዎች ብዛትና ጥራት 3ኛ በነበራቸው በአሬዮፕላኖች የበላይነት 4ኛ በአንድ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ብቻ ስለሚመሩ ነበር። ኢትዮጵያውያን ለኢጣሊያ የጦር አሬዮፕላኖች አይበገሩም ነበር፤ ጣሊያኖች ለነበራቸው የጦር መሣሪያ ብልጫም በጀግንነታቸው

ሊደቋቁሙት ይችሉ ነበር፤ ኢትዮጵያውያን ይጉድላቸው የነበረ ማእከላዊ ጠቅላይ እዝና ተመጣጣኝ ያልሆነ የወታደር ብዛት ነበር።

ኢጣሊያ በሰሜን ጦር ግንባር ብቻ 400.000 ወታደር ስታሰልፍ የኢትዮጵያ ወታደር ግን ከዚህ ቁጥር ግማሽ ነበር። የኢጣሊያ ወታደር በአንድ ሰው ሲታዘዙ የኢትዮጵያ ወታደሮች ግን በሰሜን ጦር ግንባር እርስ በርስ የማይገናኙ፤ በአራት ቦታ ተበታትነው ነበር የተዋጉት፤ በደቡብ ጦር ግንባርም በሦስት ቦታዎች ተከፋፍለው ነበር። ስለ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ጠላት ራሱ መስክሮላቸዋል። ኢትዮጵያውያን በዘመናዊ የውትድርና ተደራጅተው የመዋጋት ብቃት የላቸውም የሚለው ኤውሮጳውያን የነበራቸው አመለካከታቸውም ትክክል ሆኖ አልተገኘም። ንጉሡ በተካፈለበት በማይጨው ጦርነት በዘመናዊ ውትድርና የተገነባ የክቡር ዘበኛ ሠራዊት በባህላዊ ከተደራጁ በሌሎች የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠላት በመመከረው መሠረት በበለጠ ተዋጋ እንጂ ያነስ አልነበረም። በጣሊያኖች ግምት ንጉሡ ባገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ድጋፍ ለማግኘት በተወሰነ ቦታ አሸናፊ ቢሆንም ድል ለመጐናጸፍ ጥር ነበር። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ :Appelius በደረሰው መጽሐፍ የማይጨው ጦርነት ለሁለት ይከፈላሉ 1ኛ የኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ጦር በነጮች ጣሊኖች ክፍል መካን በተባለው ቦታ ያደረገው የማጥቃት እርምጃ 2ኛ በጣሊያኖች ላይ የተደረጉ ማጥቃት ውጤት ስላልሰጠ የኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ጦር የመካን ጥቃቱን በማቆም ኤርትራውያን ሠፍረውበት ወደ ነበረ ወደ ማይጨው ከፍተኛ ጥቃት ሰነዘረ። በተለይ ከሌሎች ክፍሎች ተለይቶ ርቆ ሰፍሮ ይመስል የነበረው 10ኛ የኤርትራ ባታሊዮን ላይ ጥቃቱን አጠናከረ። በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የተመኘውን አገኘ፡ ኢትዮጵያውያን በወጥመዱ ገቡለት። ድል ያለ መስዋዕትነት አይገኝም በሚለው መፈክር በመከተል የኢጣሊያ ጠቅላይ አዛዥ 10ኛ የኤርትራውያን ባታሊዮን ለአጠቃላይ የኢጣሊያ ድል ሲባል መስዋዕት እንዲሆን ስለወሰነ አንድ ሜትር ወደ ኋላ ሳያፈገፍግ እስከ መጨረሻ እንዲዋጋ ወሰነ። ኤርትራውያን ብቻ ሳይሆኑ ጣሊያኖች የጦር መኰንኖችም መስዋዕት እንዲከፍሉ ስለተወሰነ አብዛኞዎቹ በጦር ሜዳ አለቁ። ከሞቱት መሃል 1ኛ የባታሊዮኑ አዛዥ ኰሎኔል ሩጀሮ Rugero 2ኛ በውጭ ሀገር (ፈረንሳይ) ይኖር የነበረ ወዶ ዘማቹ ሻምበል ታራንቲኖ Tarantino 3ኛ የክፍለ ጦሩ (ዲቪዚዮን) ኢታ ማጆር ሹም ኰሎኔል ሮንዘቲ Ronzetti 4ኛ አብዛኛዎቹ ጣሊያኖች የበታች የጦር መኮንኖች ።5ኛ የጥምር 10ኛና 5ኛ የባታሊዮን አዛዥ ኮሎኔል ኮርሲ Corsi የመቁሰል አደጋ ብቻ ደረሰበት።

ከኢትዮጵያ ወገን ከ30.000 የክቡር ዘበኛ ጦር ሌላ በማይጨው የተካፈሉ የሚከተሉት ነበሩ።



1 ሊ.ጋባ ጣሰው 8500 ወታደር
2 ራስ ከበደ 2000.–
3 ራስ ጌታቸው 4000 –
4 ደጃዝማች አደፍርስ 7000 ወታደር
5 ፊታውራሪ ብሩ ምኒልክ 2000 –
6 ፊታውራሪ አሸናፊ 5000 –
7 ፊታውራሪ ነጋሽ 2000 –
8 የፖስታ ሚኒስትር 1500 –
9 ቀኛዝማች በየነ በላይነህ 3000 ፈረሰኞች
10 ቀኛዝማች በለው 900 ወታደሮች
11 ፊታውራሪ አስራት ወ/ገብርኤል 2000 ወታደሮች
12 ሊቀምንኳስ ኃ/ ማርያም 2000 –

ከጣሊያኖች ወገን በአጥቂ የኢትዮጵያ ጦር ላይ ከሩቅ እንጣጥረው የሚተኩሱ መድፎች ስለነበራቸው፤ 10ኛ የኤርትራውያን ባታሊዮን ብቻውን የተገለለ አልነበረም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ተዋጊዎች ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርሱባቸው ችለዋል።! 5000 የኢትዮጵያውያን አስከሬኖች ተቆጥረዋል፤ በዚህ መሠረት ከቀኑ መጨረሻ የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት እያካሄደ መሆኑን እያስመሠለ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ግድ ሆነበት።

የኢጣሊያ የስለላ አሬፕላኖች የኢትዮጵያ ጦር ማፈግፈግ በማመልከታቸው በወታደሮች ብዛት ከኢትዮጵያ ጦር አራት ጊዜ የሚበልጠው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በሙሉ የመልሶ ማጥቃትና ማሳደድ ጀመረ። የኢጣሊያ ጦር አሬፕላኖችም ያለማቋረጥ መደብደብ ተጠሉ። ጣሊያኖች የነበራቸው ፍራቻ የኢትዮጵያ ጦር ደቤ ላይ ተሰብስቦ ሌላ የጦርነት ዙር ይገጥመናል የሚል ነበር፤ ይኸውም በጥቂት ቀናት ውስጥ አዲስ አበባ ለመድረስ የነበራቸው ዓላማ በመጠኑም ቢሆን የሚያሰናክል ስለነበረ ዐላማቸው ብርቱ ጥረት አድርገው የኢትዮጵያ ጦር ተበታትኖ እንዲቀር ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ብቃት ያለው መሪ ቢኖረው ጣሊያኖች ከማይጨው ጦርነት በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ለመግባት ባልቻሉ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ግን መሪ በማጣቱ ብቻ ተበታትኖ ቀረ። ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሽቶ ወደ እየትውልድ ሀገሩ በሚያደርገው ጉዞ ብዙዎቹ በኢጣሊያ የጦር አሬፕላኖች ተፈጁ። በኢትዮጵያ ጎራ የነበረው ስሜት በሚመለከት የንጉሡ ወታደራዊ አማካሪ የነበረው ሩሲያዊ ኮሎኔል ኮኖቶፍ የተባለው በሩሲያ ቋንቋ የጻፈው ማስታወሻ በመጠኑ ገልጾታል። ማስታወሻው የተገኘው ጣሊያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ በአንድ ቦታ ተጥሎ ተረስቶ ነበር። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ በደረሰው መጽሐፍ ከሩሲያዊ

ቋንቋ ወደ ፈረንሳይኛ በአልጋ ቦሬኒ ተተርጉሞ የነበረው ወደ ጣሊያንኛ ተተርጉሞ አውጥቶታል። ማስታወሻ የሚያወራው በሦስት ሳምንት ጊዜ ንጉሥ ነገሥቱ ተዳማሚ ኃይለ ሥላሴ ከማይጨው ጦርነት ሽንፈት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ስላደረገው ሽሽት ነው። በግሉ ንጉሡ በጦርነቱ ወቅት ያሳየው የጀግና ሰው ስሜት ነበር፤ በጦርነቱ ጊዜ በጦር ሜዳ ይገኝ ነበር፤ መድፈኛ ክፍል ተገኝቶ ራሱም መድፎቹን ይተኩስ ነበር። የማዘዝ ችሎታ ግን ዜሮ ነበር በማለት ተችቷል። ሠራዊቱም የተዋጋው ያለ እቅድ በዘፈቀደ ነበር ብሏል። የጣሊያኖች ጀግንነትን ያደንቃል፤ የኢትዮጵያ ሹማምንቶችና ንጉሡ ስለጣሊያኖች ጀግንነት የሰጡት አስተያየቶች ይጠቅሳል፤ በሚሸሸው የኢትዮጵያ ጦር ሙሉ ህገ ወጥነትና ብጥብጥ ለፍኗል። ኮረም አካባቢ ንጉሡ ጦርነት ለመግጠም አስቦ ነበር። ንጉሡ በተሰበሰቡበት በአንድ ዋሻ ውስጥ የጦር ስብሰባ ምክር ቤት በተደረገ በስብሰባው መጨረሻ ንጉሡ የነበሩት ጥይቶች፣ ሽጉጦች ፣ ብርድ ልብሶች ፣መጠጦች፣ የቆርቆሮ ምግቦች ለወታደሮቹ አደላቸው፤ በጦሩ ላይ ውዥንብሩ ከፍተኛ ነበር። በጦር ሜዳ ውስጥ በየሚሄደው በየሸን ተረሩ የሚሸሹ ሹማምንቶች፣ወታደሮች በቅሎች፣ አህዮች ብቻ ይታዩ ነበር። ንጉሡ አንድ ሌሊት ያደረበት በማግሥቱ በጣሊያኖች እጅ ይወድቅ ነበር። ኮሉኔሉ ከንጉሡ ጋር ተጠፋፋ፣ማታ ግን ኮረም ላይ ተገናኙ። ራስ ጌታቸው ቆስሉ በመንገድ ቀረ፤ ቀኑ ቅዳሜ ነበር ኮረም ላይ የነበረው ብጥብጡ ተባብሶ በቃል ተነግሮ በማይቻል ሁኔታ ነበር። ጣሊያኖ ች ምናልባት በአሮፕላን ሊመለከቱት ቦታ ለመያዝና ውጊያ ለመግጠም ወደኋላ የሚያ ፈገፍግ ሠራዊት ይመስላቸው ይሆናል። ኮረም ላይ ንጉሡ በተዘጋጀለት በአንድ ዋሻ ነበር ያደረው፤ ዋሻው በወታደሮች የተሞላ ነበር።

እያንዳንዳዱ ወታደር በመሣሪያ እያስፈራራ ያገኘውን ሁሉ ይዘርፍ ነበር። ንጉሡ በወታደሮቹ ከመዘረፍ አላመለጡም። እሁድ ቀኑን ሙሉ ከንጉሡ ጋር ከተጠፋፋ በኋላ ማታ ከአንድ ተራራ በኮረም አጠገብ ተገናኙ። ከሩቅ አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ኮረም ጣሊያኖች እንደገቡ ይታየን ነበር፤ ብዙ አልነበሩም። ከ2000 አይበልጡም። ንጉሡ አንድን ንግግራቸው ፈልጉ ሹማምንቶቹ ግን ተዋጊ ወታደሮች እንደሌላቸው ነገሩት። ንጉሡም ይኼ የሚታየው ሁሉ ወታደር አይደለም ወይ? ብሉ ይጠይቃል።ሹማምንቶቹም የሚሸሹ ወታደሮች ናቸው ይሉታል፤ ቀጥሉም ንጉሡ አቁሟቸው ብሉ ትእዛዝ ለመስጠት ይሞክራል። «ግርማዊ ሆይ የማይቻል ነው» ብለው መልስ ይሰጣሉ። ንጉሡም ለምን ብሉ ይጠይቃል፤ የንጉሡ ልዩ ጸሐፊ ወ/ጊዮርጊስ ምክንያቱም ውሾች ናቸው፤ በእነሱ ላይ ጥይት መተኮስ በተገባ ነበር በማለት ንዴቱን ለንጉሡ ይገልጽለታል፤ በመጨረሻ ንጉሡ ምግብ ለመብላት ይጠይቃል «ግርማዊ ሆይ አይቻልም» ይሉታል፤ «ችሉ ብለን ካልሸሸን ራያ አዘቦ በጣሊያኖች ጦር መኮንኖች የሚመሩ ከእኛ ከአንድ ኪሎ ሜትር የሚገኙ ይማርኩናል» ብለው ያስረዱታል።



ለንጉሡ በቅሉ ከኮረምም የተዘጋጀ ይቀርብለታል። ንጉሡም ወዲያውኑ በቅሉ ጀርባ ወጥቶ «ወደ ቆቦ እንሂድ» ይላል «ግርማዊ ሆይ አይቻልም ከጣሊያኖች ጋር የሚተባበሩ መንገዱ በራያ አዘቦ ተቋርጧል» ሲሉት ንጉሡ «እንግዲያውስ ወደ ላሊበላ እናምራ» ብሉ ትእዛዝ ይሰጣል። እየጋለቡ ቀንና ሌሊት ተጉዘው ላስታ ሲደርሱ ሀገሩና ሕዝቡ ስለጦርነቱ ምንም የማያውቁ ሰላም የሰፈነበት አዩ።

ራስ ሥዩም ከኮረም ከጥቂት የትግራይ ወታደሮች ጋር ወደ ሀገሩ አመራ። ንጉሡ ወደ ትግራይ ተመልሶ የደፈጣ ውጊያ ጦርነት እንዲቀጥል ቢመክረው በ61 ዓመት እድሜ ሽፍታ አልሆንም ብሉ መልስ ሰጠ። ራስ ሥዩም ከሰሜን ትግራይ ወደ ደቡብ፣ተንቤን ከሰሙ እያፈገፈገ ሲመጣ ምንም አይደለም ራስ ካሣ ሲደርስ የተደራጀ ምንም የማይጎድለው ጦር ስላለው ነገሩ ይቀየራል እያለ በተስፋ ይናገር ነበር። ራስ ካሣ ራሱ ተሸንፎ ተንቤንን ለቆ ሲሄድ የሁሉም ተስፋ በዘመናዊ መሣሪያ ተታጥቆና የሰለጠነ ከምርጥ የኤውሮጳ ጦር ሠራዊት የማያንስ ያልተነካ ወደ ንጉሡ ጦር ነበር ተስፋቸው፤ በንጉሠ ነገሥቱ ሁሉም እምነት ነበራቸው። አሁን የሚታየው ግን ንጉሡ በመሸሽ ላይ እንደሚገኝ ፣ ብቻው ከሠራዊቱ ተለይቶ፣ጥለውት የሸሹ፣ በየሜካው ለመደበቅ የተገደደ፣ የራሱ ዜጎች ሳይቀር የሚተኩሱበት ሁኔታ ነው። ከሹማምንቶቹ አንዱ ብሪታንያ ምን እያደረገች ይሆን ብሉ ለኮሉኔሉ ሲጠይቀው፣ሌላው ሹም ጃፓንስ ምን እያደረገች ነው ብሉ ይጠይቀዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ራሱም ጣሊያኖች አዲስ አበባ ድረስ ለመሄድ ሃሳብ ይኖራቸው ይሆን? ብሉ ከጠየቀ በኋላ መልስ ሳይሰጠው ይኼን ለማድረግ ልናግዳቸው እንችልም ብሉ ራሱ ይመልሳል። ንጉሡ ከኮረም ላሊበላ የደረሰው በሁለት ቀን ጉዞ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ወደ ላሊበላ የመጣበት ምክንያት ከጠላት ጦር ለመደበቅ ይሁን ወይንስ ከንጉሣት ቄሶች ምክርና ቡራኬ ለመቀበል ይሁን ማንም ሊያውቀው አልቻለም። ንጉሡ በአንድ ቤት ውስጥ ሲገባ ከሁለት ቀን በኋላ ነው የወጣ። ንጉሡ እንደወጣ ኮሉኔሉ በተገኘበት የጦር ስብሰባ ተደርጉ ሁሉም የስብሰባው ተሳታፊዎች ሀገሪቷን ከውድቀትና ሽንፈት ለማዳን እንደማይቻል ተረድተው ነበር። በወቅቱ በስብሰባው ሁሉም የቀድሞ ጠላቶች ወዳጅ ሆነው ነበር፤ ራስ ጌታቸውም በስብሰባ ተገኝቶ ነበር። ንጉሡ በኀዘን ተውጦ ነበር።

የኮሉኔሉ ማስታወሻ የተጻፈበት የወሩ ቀኑን አይጠቅስም፣የሚጠቅሰው የሳምንቱን ቀናት ብቻ ነው። ከላሊበላ ተነስተው ደሴ አካባቢ ሲደርሱ ንጉሡ ጣሊያኖች ወደ አዲስ አበባ የሚያደርጉትን ጉዞ ለማወቅ ያስባል። አንድ ደጃዝማች መሬት ሰጥተን ለምሳሌ እጋዴን ከጣሊያኖች ጋር ዕርቅ ለማድረግ እንችልም ወይ? ብሉ ለንጉሡ ይጠይቃል፤ መልስ አልተሰጠውም። እሁድ ማታ ንጉሡ በምን ቅድመ ሁኔታ ኢጣሊያ ሰላም ለማድረግ ትቀበል ይመስልሃል? በማለት ለኮሉኔሉ ጠየቀ። በግልጽ ለመናገር

ከፈቀደልኝ «ግርማዊ» ሆይ አሁን ሙሶሊኒ ባገኘው ወታደራዊ ሚዛን ካልሆነ በስተቀር ሌላ ሰላም አይቀበልም፣ ቢቀበል እንኳ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ተቢታትና መንግሥት እልባ ሆና ስለምትገኝ ኢጣሊያ ከየትኛው መንግሥት ልትደራደር ትችላለች» ብሎ መልስ ሰጠው ። ማክሰኞ መቅደላ ስንደርስ ንጉሡ ለ24 ሰዓቶች ቆይታ ለማድረግ ፈልጉ ነበር፣ ሀገረ ገዥው ግን የሀገሩ ሕዝብ በንጉሡ ላይ አደጋ ለመጣል ሃሳብ እንዳለው ለንጉሡ ነገረው።

በችኮላ ብዙ ስንቃችንን ትተን ለቀን መሄድ ተገደናል። በአንድ ትልቅ ሸንተረር እንደደረስን ከሀገሩ ሕዝብ ትልቅ ጥቃት ደረሰብን፣ ብዙ ወታደሮች ሞቱብን፣ ንጉሡም ከአደጋ ሊያመልጥ የቻለው በዕድል ነው። ደሴ በጣሊያኖች እጅ ወደቀች የሚል ዜና ስንሰማ ከእኛ 35 ኪሎ ሜትር ወደ ምትገኝ ወደ ወረኢሉ ለማምራት ሞከርን፣ ሆኖም ወረኢሉም በጣሊያኖች እጅ ወድቃለች የሚል ሌላ ዜና ሰማን። ንጉሡ ጣሊያኖች በእግራቸው ከንፍ አላቸው ልበል የሚል አስተያየት ሰጠ። ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ቀይረን ቀንና ሌሊት በመጓዝ ወደ ፊት ለማምራት ወሰን። ንጉሡም ቶሎ ብለን ካልተራመድን ጣሊያኖች ከኛ በፊት አዲስ አበባ ይገባሉ አለ። ብዙ ሕዝብ በሚኖርባቸው መንደሮች ለማለፍ እንቆጠብ ነበር ምክንያቱም ሕዝቡ የመንግሥት ንብረትና የታላላቅ ሰዎችን ቤት ይበርፍ ነበር። ሮቡዕ 21ኛ የሽሽት ቀን የኢጣሊያ ዝቅ ብለው የሚበሩ የጦር አሪዮፕላኖች አይተውን በቦምብ ሊጥሉብን ሊጀምሩ ጥቅጥቅ ባለ ደን በመግባት ሕይወታችንን ለማትረፍ በቅተናል፤ ጣሊያኖች ግን ደኖችን ሳይቀር በአሪዮፕላን ይደበድቡ ነበር።

ሐሙስ ፍቼ ስንደርስ አምስት መኪናዎች ይጠብቁን ነበር። በቅድሚያ ንጉሡ በእጁ ሰላምታ ሰጥቶን በአንደኛው መኪና ውስጥ ገብቶ ወደ አዲስ አበባ ጉዞውን ቀጠለ።

ከደሴ አዲስ አበባ ለመድረስ ጣሊያኖች አስር ቀን ብቻ ነው የፈጀባቸው። ጦርነቱ አብቅቷል፤ ከሁሉ የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ክፍል የሚወክሉ ተካፋይ የሚሆኑበት የሰልፍ ጉዞ ነው። ሰልፉን ከሚመሩ ባለሥልጣኖች መካከል የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ከማርሻል ባዶሊዮ ሌላ የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ለሶና እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ ሆኖ የተሾመው የሮማ ከተማ ከንቲባ የነበረው ቦታይ ‹Botai› የተባለው ይገኙባቸው ነበር። ሕዝቡ ጣሊያ ኖች በሚያልፉበት እንቁላሎችን፣ዶሮችን፣ በጉችን፣ ፍየሎችን፣ በሬዎችን ስጦታ እያበረከተ ይቀበላቸው ነበር። በአንዳንድ ቦታ በሽዋ ሕዝቡ በጭፈራ ሲቀበላቸው የኢጣሊያ ወታደሮች ይገረሙ ነበር። ምክንያቱም በዐድዋ ያሸነፉን የማይበገሩ ጀግኖች የሸዋ ቁዎች ነበሩ ፤ የኢጣሊያ ቀንደኛ ጠላቶች ሸዋውያን ናቸው ተብለው ተሰብከው ስለነበረ የኢጣሊያ ወታደሮች የት ነው የሚገኙት እነዚህ ሸዋውያን ጠላቶቻችን እያሉ በአይናቸው ለማየት ጓጉተው ነበር። ከገዥ መደብ ከተባሉ ከሸዋውያን ጥሩ አቀባበል ሲደረ ግላቸው ኃይለ ሥላሴ ሸዋውያንም ጭምር እንደማይወዱት የተገነዘቡ መሰላቸው። አዲስ አበባ ለመድረስ ጓጉተው ጣሊያኖች ሌሊት እንቅልፍ አልነበራቸውም፤



የምግብ ፍላጉትም አልነበራቸውም። የመኪና መንገድ እየሠሩ ኤርትራውያን በእግራቸው ጣሊያኖች በመኪና በ‹1600 መኪና ዎች› እየተጓዙ «አዲስ አበባ የማናት ብሎ ሊጠይቅ አንድ ቡድን ሌላ ቡድን «የኛ ናት» ብሎ መልስ ይሰጣል። እንደገና «አቢሲኒያ የማን ናት»ብሎ ሲጠይቅ የመጀመሪያ ቡድን ሌላ ቡድን ደግሞ «የኛ ናት» የሚል መፈክር እያሰሙ ወደ አዲስ አበባ ይጓዙ ነበር።

ኃይለ ሥላሴ ከ20 ቀናት ሽሽት በኋላ አዲስ አበባ እንደገባ ጣሊያኖች መረጃ ደርሷቸዋል። ያለው ገንዘብና ንብረት በባቡር እየጫነ ወደ ጅቡቲ እየተጓዘ መሆኑን ደርሶ ውበታል። በአዲስ አበባ የነበረው የእንግሊዝ አምባሳደር ለሁለት ሰዓት ከንጉሡ ጋር ተገናኝቶ ዋና ከተማዋን ወደ ወሊጋ አዛውሮ ጦርነቱን እንዲቀጥል የሚል ሃሳብ ለኃይለ ሥላሴ አቅርቦ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ግን አወንታዊ ወይም ደግሞ አሉታዊ መልስ ሳይሰጥ የአዲስ አበባ ጅቡቲ ባቡር አስተዳደር ዲርክተር ሙሴ ጀርባል ‹Gerbal› በአቃቂ ባቡር ጣቢያ ልዩ ባቡር ለንጉሡ እንዲዘጋጅለት አዝዞ ከግቢ የቀረቡለት 4 መኪናዎች ተሳፍሮ ወደ አቃቂ ለመሄድ በባቡር ተሳፈረ። ከምሽቱ 3 ሰዓት ወደ ግቢ መጥቶ የኃይለ ሥላሴን ውሳኔ ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብ የእንግሊዝ መረጃ ክፍል ኃይለ ሥላሴ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ጦርነት ገጥሞ ለመከላከል እንደሚሞክር ለሕዝቡ ንግግር ያሰማ ይሆናል የሚል ግምት ነበረው። ቀጥሎም እስከ መጨረሻ የደረጣ ውጊያ እንደሚቀጥል ይደረጋል የሚል ግምት ነበረን። የኃይለ ሥላሴ እቅድ ግን ወደ ጅቡቲ ለመሸሽ ብቻ ነበር።

ጣሊያኖች እንደ እስራኤሎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሬት እንደ ደረሱ ይመስላቸው ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ሱቆች፣ መኖሪያ ቤቶች ፣ ኤምባሲዎች ላይ ዝርፊያዎች ይካሄዱ ስለነበረ። የፈረንሳይ አምባሳደር ቢሮ ውስጥ እንዳለ በበራሪ ጥይት እጁ ላይ ቆስሎ ስለነበረ በራዲዮ ስልክ ከጣሊያኖች ግንኙነት አድርጉ ቶሎ ብለው አዲስ አበባ ካልገቡ በከተማዋ የሚገኙ ነጮች በሕይወታቸው የሚያሰጋ አደጋ እንደነበሩ ገልጾላቸው ነበር።ሜይ 4 በእግር የሚጓዙ ከኤርትራውያን ክፍለ ጦሮች 1ኛ ብርጌድ አዲስ አበባ ደረሶ ከአንጦጦ ተራሮች ዙሪያ ተሠማሩ። ሜይ 5 ጠዋት በመኪናዎች የሚጓዙ የኢጣሊያ ወታደሮች ክፍለ ጦሮች አዲስ አበባ ሲደርሱ በማርሻል ባዶሊዮ መሪነት በሰልፍ ከተማ ውስጥ ገቡ። የሰልፉ ተካፋዮች ከማርሻሉ ሌላ 2 የኮር አዛዦች ጀኔራሎች፣8 የዲቪዚዮንና የብርጌድ ጀኔራሎች፣ የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር፣ የሮማ ከተማ ገዥ ይገኙባቸው ነበር።

የውጭ ሀገር ኤምባሲዎች ከዘራፊዎች ራሳቸውን ለመከላከል ተደራጅተው ነበር። የእንግሊዝ ኤምባሲ በ150 የሕንዳውያን ወታደሮች ይጠበቅ ነበር። በፈረንሳይ ኤምባሲ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የ17 ዜግነት ያላቸው ነጮች ተጠልለው ነበር።በዚሁ ጊዜ

ኤርትራውያን ወታደሮች ባዙር ማቢያ፣ ጉምሩክ፣ የወታደር መሬሮች፣ ባንክና የከተማ ዋና ዋና መግቢያ በሮች እንዲቆጣጠሩ ሲታዘዙ በማርሻል ባዶሊዮ የሚመሩ በመኪና የሚጓዙ የኢጣሊያ ወታደሮች ሰልፈኞች ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ግቢ አመሩ። ጣሊያኖች በጀርመን፣ በፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ቱርክ ፣ ቤልጂየም ኤምባሲዎች ደጃፍ ሲያልፉ እንደ ነፃ አውጪዎች በጭብጨባ አቀባበል ተደረገላቸው። በእንግሊዝ ኤምባሲ ደጃፍ ሲያልፉ ግን ጭብጨባ አልነበረም።

በማርሻል ባዶሊዮ የሚመሩ ጣሊያኖች ታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ይሰቀልበት የነበረው የኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለበት። 10.000 የኢጣሊያ ወታደሮች ግቢ ውስጥ ገብተው በአራት ማዕዘን ይቆማሉ፤ ለባንዲራቸው ወታደራዊ ሰላምታ ይሰጣሉ።[1]

ጣሊያኖች የተለመደው መፈክራቸውን ማሰማት ይጀምራሉ።

ማርሻል ባዶሊዮ የሥነ ሥርዓቱ ታላቅነትና ታሪካዊነት ይሰማው ነበር።

ማርሻሉ «ለንጉሡ ሰላምታ» Seluto Al Re ብሉ በከፍተኛ ጩኸት ሲያሰማ

ዙሪያው ያሉ ወታደሮች በአንድ ድምፅ በመጮህ «ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር» Viva Il Re በማለት ይመልሳሉ።

ማርሻሉ «ለዱቹ ሰላምታ» Saluto Al Duce በማለት ጩኸቱን ሲያሰማ

ወታደሮቹ «ለኛ» A Noi ብለው ጩኸት ያሰማሉ

ይህ መፈክር ለሦስት ጊዜ ይደጋገማታል።

በዚህ ዓይነት አጭር ሥነ ሥርዓት የኢጣሊያ በዐድዋ ጦርነት ሽንፈት በማይጨው ጦርነት ቂም በቀል ድል አድራጊነት ተደምድሟል።

በዋናው ጦር አዛዥ በማርሻል ባዶሊዮ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ከደሴ አዲስ አበባ ሲያመራ ፤ በሌላ ኢጣሊያዊ ሌተና ጀኔራል ስታራቺ የሚመራ የኢጣሊያ ጦር የኢትዮጵያ መሰዮ የአባይ ምንጭ የሆነው የጣና ሐይቅ ሲቆጣጠር ለወታደሮቹ «በዱቼ ስም የጣና ባሕርን ተቆጣጥረናል» የሚል መፈክር አሰምቷል ።[2] በዚሁ ጊዜ በጐርጐራ አድፍጠው የነበሩት የኢትዮጵያ ታጣቂዎች ተታውሟቸውን ለማሰማት ተኩስ ከፈቱባቸው። ጣሊያኖች ተደናግጠው ቢፈልጓቸውም ሊያገኟቸው አልቻሉም። ጣሊያኖች በጐርጐራ ተራራ ባንዲራቸውን ተከሉበት።

1. Mario Appelius : Il Crollo dell'Impero dei Negus p.193

2.Luca Dei Sabelli Storia Di Abissinia v 1v p.245



በዚሁ ጊዜ ሌተናል ጀኔራል ስታራቺ ከተሰበሰቡ ወታደሮች «ዛሬ በጦርነት ማእበል የተከበረ ፋሲካ 14ኛ የፋሺስት ዘመን በንጉሡ ስም፣ በዱቹ ስም በጐርጐራ ከፍተኛ ተራራ የኢጣሊያ ባንዲራ ተከያለሁ። የጣና ባሕር ውሃዎችን እንደገና ሊነጥቁን የሚመጣ ማንኛውም ጠላት ለመከላከል በቀይ ደማችን እንደምንደመስሰው ቃል እንገባለን፤ እናንተስ ቃል ትገባላችሁ?» ብሎ በጩኸት ባሰማበት ጊዜ «እንምላለን» የሚል ድምጽ ከወታደሮች ተሰማ።

ወዲያውኑ በአንድ ም/መቶ አለቃ አማካኝነት ከሁሉም ክፍለጦሮች የተውጣጡ ወታደሮች ወደ ጀኔራሉ ፊት ቀረቡ፣ ም/መቶ አለቃውም «በጦር ጓደኞቼ ስም ባንዲራችን የተከልንበት ከፍተኛ የጐርጐራ ተራራ የሙሶሊኒ ተራራ ተብሎ እንዲጠራ እለምናለሁ» ብሎ ሲጠይቅ፣ ጀኔራሉም «እንደጠየቃችሁ ይሆናል» የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል። ከማይጨው ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር በጥላን የሚመራ ጠቅላይ አዝ ስላልነበረው፣ የሚያዋጋ የጦር አዛዥ በማጣቱ፣ ተበታትኖ ቀረ ! ስኢጣሊያ ጦር አሬዮፕላኖች የእሳት እራት ሆነ። ለዚሁ የዳረጓቸው የኢትዮጵያ መሪዎች በከሐዲነት ያስጠይቃቸዋል። ከማይጨው እስከ አዲስ አበባ የኢጣሊያ ሠራዊት በማርች እየተጓዘ በአንድ ወር አዲስ አበባ ገባ። ጠቅላይ ጦር አዝ ቢኖረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ቢያንስ ለአንድ ዓመት ጣሊያኖች አዲስ አበባ እንዳይገቡ ለማድረግ ይችል ነበር። ጣሊያኖች ራሳቸው ተቃውሞ እንዳያጋጥማቸው ስጋት ነበራቸው፤ በተለይ በጣርማ በር ለመከላከያ አመቺ በመሆኑ እነሱተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ሊገታቸው እንደሚችል ፈርተው ነበር።[1]

# ታላቅዋ ብሪታንያና ኢትዮጵያ

በወቅቱ ታላቅዋ ብሪታንያ ልዕለ ኃያል መንግሥት ነበረች። ብሪታኒያ ጣሊያ ዘዓለም ባሕርና ውቅያኖሶች ለሚደረግ ጉዞ ለመቆጣጠር ኃይል ሳይኖራት ዐሠሩ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮችዋ ከሀገርዋ 4.000 ኪሎ ሜትር ርቀት ማዝመቷ ዘማች ሠራዊትዋ መንገዱም ቢዘጋበት በእልቂት ከመጋለጥ ሌላ አማራጭ የለውም የሚል አስተያየት ትሰነዝር ነበር።[2] ኢጣሊያ ለጦርነቱ መነሻ እንዲሆናት የወልወል ግጭት ብላ ፈጠረች። ለግጭቱ በመንግሥታቱ ማህበር የተሰየመው አስታራቂ ኮሚቴ ለኢትዮጵያ ጥብቅና የቆመው ፈረንሳዩ ሕግ አዋቂ ወልወል በማን ግዛት እንደምትገኝ በመጀመሪያ ይወሰን ብሎ ባቀረበበት ጊዜ ጣሊያኖች ኮሚቴው ተግባሩን እንዲያከናውን የተፈጠረው መሰናክል ነው ብለው ውድቅ አደረጉት። ወልወል የሚገኘው በ100 ኪሎ ሜትር የሚቆጠር በኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

1. Mario Appelius : Il Crollo dell'Impero dei Negus p.193

2. Luca Dei Sabelli Storia Di Abissinia v 1v p.245

ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ስም ለማጥፋት ቋም ነገር የሌለው በስድብ ብቻ የተሞላ አንድ ሪፖርት ለዓለም መንግሥታት ማህበር አቀረቡ። ስለጣሊያኑ ሪፖርት ክርክር የአምስት ሀገሮች አጥኚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ክርክር በሚደርግበት ጊዜ ያልተጠበቀ የድራማ መልክ የሚያሳይ ነገር ተፈጠረ። ታላቅዋ ብሪታንያ ከዚህ በፊት በመንግሥታቱ ማህበር ዝቅተኛ የመካፈል አቋም የነበራት ከሥር መሠረቱ በመቀየር በመንግሥታቱ ማህበር ላይ ከፍተኛ ተካፋይነቷን ለማሳየት የመንግሥታቱ ማህበር ደምቦች በደምብ መከበር እንዳለባቸው ገልፃ ደምቦች በሚጣሱበት ጊዜ የትም ቦታ ድጋፏን ለመስጠት ዝግጁ መሆንዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ከማድረጓም በላይ ሆም ፍሊት Home Fleet የተባለው የብሪታንያ ባሕር ኃይል በሚዲትራንያን ባሕር አሰማራች። ይኸውም ሆኖ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሚኒስትር ‹ማፌይMafey› ለሀገሩ መንግሥት ባቀረበው ሪፖርት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የም ታሳየው የበላይነት የግዛት ማስፋፋት በአካባቢው ለሚገኙ ለእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ጥቅም የማይጐዳ መሆኑን ገልጦ በኢጣሊያ የግዛት ማስፋፋት ብሪታንያ ጥቅም ልታገኝ እንደምትችል የሚል እምነት ሰንዝሮ ነበር። ከዚህ በኋላ ግን የዚህ ዓይነት ፖሊሲ ደጋፊ የነበሩ ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተቀይረው ፀረ–ኢጣሊያ የማስፋፋት ዓላማ ያላቸው ‹በል ዊን እና ሳሙኤል ሆር› ተተኩ። ብሪታንያ አቋሟን ለመንግሥታቱ ማህበር በመግለጽ እንደዚሁም እንደ ማስፈራሪያ የባሕር ኃይሏ ‹ሆም ፍሊት› በሚዲትራንያን ባሕር በማሰማራት ብቻ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ያለው ግጭት እልባት ያገኛል ብላ ገምት ነበራት። ከኢጣሊያ አርቆ መገመት የሚችል መንግሥት ቢኖር የእንግሊዝ ማስጠንቀቂያ በቂ ነበር።

ሆኖም ይህ ሁሉ በኤውሮፓ የጦርነት አደጋ ማንዣበብ ስለሚያስከትል በዕብሪት ትክሻቸው ያበጠ ጣሊያኖች ሊገታቸው አልቻለም። በዓለም መንግሥታት ማህበር ያለው ጉዳይ የእንግሊዝ መንግሥት ኃላፊ መልዕክተኛ የነበረው ኤደን ‘Eden› ጁን 24፣ 25 በሮም ጉብኝት አድርጎ ታላቅዋ ብሪታንያ ኢትዮጵያ በዘይላ በኩል የባሕር በር እንድታገኝ ስታደርግ ኢትዮ ጵያም ለኢጣሊያ ኦጋዴን እንድትሰጥ ነበር። ይህ የባሕር በር ለኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ለማግኘት ብዙ ጥቅም ይሰጣታል በማለት ኢጣሊያ የምድር በረሃዎች ሰብሳቢ አይደለችም በማለት ጣሊያኖች ሳይቀበሉት ቀሩ። የፈረንሳይ መንግሥትም ኢትዮጵያ በዘይላ በኩል የባሕር መውጫ ካገኘች በጅቡቲ በኩል ያለው ንግድ ይወድቃል በማለት ጥርጣሬ አድርባት ነበር። በእንግሊዝ ፓርላማ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባደረገው ንግግር ኢጣሊያ የመስፋፋት መብት እንዳላት ብንቀበልም በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ብዙ ሐሰ ሊደረግ እንደሚቻል ብንቀበልም፣ ይህ ሁሉ ግን በእርቅ የሚፈቱ ናቸው እንጂ ወደ ጦርነቱ አዙትት የሚወስዱ አይደሉም ብሎ ነበር። የእንግሊዝ አቋም በኢትዮጵያ ጉዳይ በዚሁ አላበቃም። ስለ ኢትዮጵያ በ 1906



እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ኢጣሊያ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ግምገማ ለማድረግ ሦስቱ ሀገሮች አገስት 16 1935 በፓሪስ ተሰበሰቡ። ፈረንሳይ ለጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት መብት እንዲታወቅላቸው ስምምነት እንዲደረግ የሚል ሐሳብ ብታቀርብም እንግሊዞቹው መልዕክተኛ ኤደን ግን ከፍተኛ ተቃውሞ አሰማ። የኢጣሊያ መልዕክተኛም ባሮኔ አሎይዚ የቀረበለት ሐሳብ ውድቅ አደረገው።

ስለዚህ ስብሰባው ያለምንም ውጤት ተሰትኖ በማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ለክርክር እንዲቀርብ ተደረገ። የመንግሥታቱ ማህበር ጠቅላላ ስብሰባ በእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ተጀመረ። ሚኒስትሩ ያለምንም ማወላወል የእንግሊዝ መንግሥት የማህበሩ ውሎችና ደንቦች እንዲከበሩ ድጋፉ ይሰጣል ሆኖም የማህበሩ ውሎች በኢትዮጵያ ጉዳይም በሥራ ላይ መዋል አለባቸው በማለቱ በተለይ ፈረንሳይን የሚነካ ነበር። የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ላቫል ‹Laval›ቀደም ብሎ ወደ ሮም ተጉዞ በኢትዮጵያ በጣሊያኖች ጣልቃ ገብነት የግዛት ማስፋፋት ሙሉ መብት ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። በሌላ በኩልም 1ኛ የዓለም ጦርነት ፈረንሳይ ከጀርመን የወሰደቻቸው መሬቶች በሚመለከት የእንግሊዝ ድጋፍ ያስፈልጋታል።

በዚህ መሠረት ላቫል ‹Laval› ከእንግሊዝ ወዳጅነት ወይንም ከጣሊያን ወዳጅነት መምረጥ ነበረበት። በሀገሩ ውስጥም የተቃዋሚዎች ከፍተኛ ግፊት ስለነበረበት ላቫል የመንግሥታት ማህበር ውሎች በኢትዮጵያ ጉዳይም በማህበሩ መድረክ እንዲከበሩ መቀበል ግድ ሆነበት። በዚህ በፊት ተቋቁሞ የነበረው የ5 ሀገሮች ኮሚቴ ተብሎ የሚጠራው በጠቅላላው ጉባኤ የቀረበው ሪፖርት ኢትዮጵያ አስተዳደርዋ ለማሻሻል ሁለገብ ድጋፍ ከውጪ መንግሥታት እንደሚያስፈልጋት እምኖ ይህ ድጋፍ ግን ከአንድ መንግሥት ብቻ ‹በኢጣሊያ› መከናወን የለበትም፣ በብዙ መንግሥታት በጋራ መሰጠት አለበት በማለቱ የኢጣሊያ ቁጣ አስከተለ። የኢጣሊያ ቁጣ በይበልጥ የገነፈለው የኢትዮጵያ መልእክተኛ አክቶበር 5 1935 ኢጣሊያ ወራሪ ተብላ እንድትወገዝ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤ ሲቀበለው ነው። ጣሊያኖች በእብሪት ተነሳስተው ኤውሮጳ አንድ ጥንታዊት ፣ የሰለጠነች ኤውሮጳዊት ሀገር ኢጣሊያን አግልላ ለአንድ ያልሠለጠነች ጥቁር አፍሪካዊት ሀገር የባሪያ አሳዳሪ ሀገር ድጋፏን በመስጠት ለኤውሮጳ የውድቀት ምልክት ነው ብለው ቁጣቸውን በመግለጽ ወረራቸውን ገፉበት።

ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ሜይ 2 ማታ ንጉሡ አዲስ አበባን ለቀ በባቡር ወደ ጅቡቲ ተጉዞ በ23.30 ‹ከማታው 5 ሰዓት ተኩል› ድሬዳዋ ገባ። ሜይ 3 ቀን ከቀኑ 14 ሰዓት ‹ከቀኑ 8 ሰዓት› ጅቡቲ ገባ። በማግሥቱ ሜይ 4 17.30 ‹ከቀኑ 11.30› ኢንተርፕራዝ በተባለው በአንድ የእንግሊዝ የጦር መርከብ ተሳፍሮ ወደ እየሩሳሌም አምርቷል። በጅቡቲ የነበረው ሳልቫቶሬ አፓንተ ‘Salvatore Apante›

የተባለው የአንድ የኢጣሊያ ጋዜጣ መኪል የኃይለ ሥላሴ ጉዞ ዝርዝር አውጥቷል[1]፡ኃይለ ሥላሴ ጅቡቲ ሲደርስ ንብረቱ የኢጣሊያ የሆነው ምግብ ቤት ተሰብስበው ጣሊያኖች Facetta Nera ፋቼታ ኔራ የሚል ዘፈን በሽከላ ተቀርጾ ያሰሙ ነበር። ተጠንቀቁ እኛ ፋሺስቶች ነን እያሉ ጩኸታቸው ያሰሙ ነበር። በእንግሊዝ ጦር መርከብ ከኃይለ ሥላሴ ጋር የተጓዙ 116 ሰዎች ቤተሰብና ባለሥልጣኖች ነበሩ። በፓለስታይን የክብር አቀባበል ተደርጐላቸዋል። ትንሽ ቀን ከሰነበቱ በኋላ ጁን 3 ቀን ኃይለ ሥላ ሴ ታላቅ አቀባበል ተደርጐለት እንግሊዝ ሀገር ገባ። ለኃይለ ሥላሴ የተሰጠው ታላቅ ክብር በግሉ የተሰጠ አልነበረም ፡ ለኢትዮጵያ ነፃነት ክብር የተሰጠ ነበር። ከ5 ዓመት በኋላ ዓለምን በእጁ የጨበጠች መስሏት የነበረ አብሪተኛዋ ፋሺስት ኢጣሊያ 2ኛ የዓለም ጦርነት በእንግሊዝ የጋራ ብልጽግና ሀገሮች ወታደሮች ተሸንፋ ተዋርዳ ከኢትዮጵያ ለቃ ስትወጣ ኃይለ ሥላሴም ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሥልጣን ሲይዝ ከእንግሊዞች የተደረገለት እርዳታ ተገቢ ውለታ የከፈለ አይመስልም፡ ውለታቢስነቱ ኃይለ ሥላሴን ብቻ የሚያስወቅስ አይደለም ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚያስወቅስ ነው። ከነፃነት መልስ በኋላ ኢትዮጵያ በእንግሊዞች አማካሪዎች እርዳታ በዲሞክራሲ አስተዳደር ብትመሠረት ለእን ግሊዞች ውለታ መመለስ ብቻ ሳይሆን የታየው በደርግ ሥር ነቀል ለውጥ አይከሰትም ነበር። የራሱ የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አገዛዝም አይደፈርም ነበር። በ1928 የኢጣሊያ ወረራ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የመጣባት ጠላት ከአቅሟ በላይ ተዘጋጅቶ መሆኑ ባይካድም ኢትዮጵያም ለመከላከል ያደረገችው ጥረት ከአቅሟ በታች ነበር። የኤውሮጳ የውትድርና ጠበብት እንደገመቷት ሆና ያልተገኘችበት ምክንያት በሕዝቧና በወታደሮቿ ድክመት ሳይሆን በነበሩ መሪዎች ችሎታ ማነስ የመሪነት ኃላፊነታቸው በሚገባ ሊወጡ ባለመቻላቸው ነው። ዓላማ ብለው ይዘውት የነበረ በትግራይ ጦርነት በመግጠም ዕድላቸውን አይተው ሲሸነፉ መበታተን ብቻ ነበር የተወሰነ።

# የኢትዮጵያ ጦር መሪ አልነበረውም

የኢትዮጵያ አሰላለፍ ራሱ ለጠላት የሚመች ነበር። እርስ በርስ በሙሬት ኩታ ገጠም እንዲሁም በመገናኛ የማይገናኝ ጠቅላይ እዝ የሌለው በመላው ሀገሪቱ በሰሜን ጦር ግንባርም ሆነ በደቡብ ሠራዊቱ ተበታትኖ ሰፍሯል ፤ ሽንፈትና ማፈግፈግ ሲያጋጥምም ተጠባባቂ ጦር አልተዘጋጀም። በመጣሪያ ማነስ የወታደር ብዛት ኃይል ማነስ የባሰ ሁኔታ ነበር። ይህ ሁኔታ ነበር ወደ ሽንፈት የዳረጋቸው፤ ራስ እምሩ ሪድዮ መገናኛ አልነበረውም።

1. Ficl v3 P.78



የኢትዮጵያ መሪዎች ይለዋወጧቸው የነበሩት ቴሌግራሞች ሁሉ በጣሊያኖች እየተጠለፉ እንደ ማስረጃ ያገለግሉዋቸው ነበር። እነዚህ ቴሌግራሞች በወቅቱ ኢትዮጵያ ጠቅላይ እዝ አልባ ብቻ ሳትሆን መንግሥት አልባ እንደነበረች ያሳያሉ። ፌብሩዋሪ 12 1936 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከደሴ ለራስ ካሣ በላከው ቴሌግራም «ጣሊያኖች በ12 ሰዓት ዉስት በራስ ሙሉጌታ ላይ ጥቃት ሰንዝረዋል፤ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ስለሚገኙ በስተ ጀርባቸው ምርጥ ጦር ልከህ ጥቃት እንዲፈጸምባቸው ካደረግህ ወደ ራስ ሙሉጌታ የዘመተ ጦራቸው ሊቀንስ ይችላል ወይም መቀሌን መያዝ ያለ ተከላካይ ወታደር ከተገኘች የሚል ነበር።ይህ ቴሌግራም ለራስ ካሣ የደረሰው ፌብሯሪ 15 ከምሽቱ 2:30 ሲሆን በዚሁ ጊዜ ግን ራስ ሙሉጌታ ተሸንፎ የእንደርታ ጦርነት አብቅቶ ነበር።

ፌብሯሪ 19 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከደሴ የራስ ሙሉጌታን መሸነፍ ዘግይቶ እንደሰማ ራስ ካሣና ራስ እምሩ ወደ እምባአላጂ እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። ይህ በተግባር ሊውል የማይችል ትእዛዝ ነው ምክንያቱም ከሽሬና ከተንቤን እስከ አምባ አላጂ ያለው ርቀት ብዙ ከመሆኑም በላይ ጣሊያኖች ከተንቤንና አምባ አላጂ መሀል ያለው መሬት ሁሉ በቁጥጥራቸው አውለውት ስለነበረ ትእዛዙ ተጨባጭ ሁኔታ ያልተገነዘበ ነበር።

ፌብሯሪ 20 ራስ ካሣ ለንጉሡ ቴሌግራም ሲልክ ጣሊዮኖች እርስ በርሳችን እንዳንተጋገዝ አድርገውናል ካለ በኋላ በአጠቃላይ በውኸብር እንደሚገኙ የሚያሳይ የሚተከተው ዕቅድ ለንጉሡ ሃሳብ ያቀርባል።

1ኛ አፋቴ ያለውን ጠላት ማጥቃት ምናልባት ከራስ እምሩ ጋር ለመቀላቀል፤

2ኛ በጀርባዬ ያለውን ጠላት ማጥቃት ከራስ ሙሉጌታ ጋር ለመቀላቀል ፡መሸነፉን ስለማያውቅ፤

3ኛ የከበብነውን ጠላት እሱም የከበበን እየተዋጋም መጠባበቅ።

አፄ ኃይለ ሥላሴም የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ስላልተገነዘበ አዲስ ትእዛዝ ይሰጣል። ራስ እምሩ ወደ መከላከል ያዘንብል፤ ጥቃት ከደረሰበት ይከላከል፡ ሌላው ቢቀር ጊዜ ለመውሰድ። ራስ ካሣ በቂ ኃይል ካለው ይዋጋ፡ ጣሊያኖችን ከያሉበት ከራስ ሙሉጌታ ጋር ተቀላቅሉ ይዋጋ።

በተጨማሪ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፌብሯሪ 20 በላከው ቴሌግራም ከደሴ ተነስቶ ወደ ሰሜን ማይጨው ጉዞውን እንደቀጠለ አስታውቋቸው ነበር።

የራስ ሙሉጌታና የራስ ካሣ ሠራዊት ሳይበታተንና ሳይሸነፍ ከንጉሡ ሠራዊት ጋር ለመቀላቀል ቢችል ኖሮ ጣሊያኖች ከባድ ችግር ይገጥመናል ብለው ነበር። ችሎታ ያለው በጠቅላይ ጦር አዛዥ የሚመሩ ጣሊያኖች ግን የኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይሰባሰቡ በተለያዩ ቦታዎች ጦርነት ገጥመው አስቀድመው ባወጡት እቅድ መሠረት አሸንፏቸዋል።

ሌላ ቴሌግራም ራስ ካሣ ለንጉሡ በላከው በጣሊያኖች ተከቦ እንደሚገኝና ያለው ዕድል ወደ ዐድዋ ጥሶ መውጣት ነው ብለዋል። ንጉሡም ፌብሯሪ 25 በሰጡት መልስ ወደ ዐድዋ ጥሶ መሄድ ትክክል መስሎ እንደማይታየው ጠቅሶ በቀድሞ ትእዛዝ መሠረት ወደ አምባ አላጂ እንዲያመራ በድጋሚ ትእዛዝ ሲሰጡ ይኸውም ያለበት 1ኛ አማካሪዎች ስለነበሩት 2ኛ በዚሁ አካባቢ በጣሊያኖች ላይ ጉዳት ለማድረስ ስለማይቻል ነው ብሏል። ይኸ ሁለተኛ ነጥብ ደፈጣ ውጊያ የሚመስል ስለሆነ ጣሊያኖች አስግቷቸው ነበር። ጣሊያኖች ይፈሩት የነበረው ኢትዮጵያውያን በደፈጣ ውጊያ እንዳይጠቀሙ ነበር። የኢትዮጵያ መሪዎች ግን ጣሊያኖች በሚፈሩት ውጊያ እንዳይጠቀሙ ለጣሊያኖች የሚመች የፊት ለፊት ጦርነት ነው የመረጡት። ይኸም ሆኖ ደጀን ጦር ተጠባባቂ ጦር አልነበረም። አስተሳሰባቸው ልክ እንደ ዐድዋ ጦርነት በአፄ ምኒልክ ጊዜ ለመሆን አዝማሚያ ሲኖረው ልዩነቱ ግን በዐድዋ ጊዜ ጦሩ የሚታዘዘው በአንድ ሰው ነበር የሚጓዘውም በአንድ መስመር ነበር።

በ1928 ጦርነት ሠራዊቱ የሚመራው ከበላይ አስተባባሪ ሳይኖረው በብዙ ጦር አበጋዞች ከደቡብ ወደ ትግራይ በብዙ አቅጣጫዎች ይጓዝ ነበር። ይህ የታክቲክ ጉድለት ለመገመት ውትድርና አዋቂ መሆን አያስፈልግም። ፌብሯሪ 27 እና 28 የተንቤን ጦርነት በተጧጧፈበት፣ አምባአላጂም በጣሊያኖች እጅ በገባበት ወቅት ራስ ካሣ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በላከው ቴሌግራም አምባአላጂ የሚገኘው የኛ ጦር ጣሊያኖች ከመቀሌ በጦር መኪናዎች ወደ እኛ መጥተው እንዳይወጉት በመድፍ ተኩስ ከፍተው ለማጥቃት እንዳይሞክር በማለት ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ቀጥሎም ራስ ካሣ በስተጀርባ የሚመጣ ሠራዊት ጦር እንደሰካና ፊት ለፊት በሚመጣው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ላይ ለመግጠም እንደተጓዘ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ካስታወቀ በኋላ አፄ ኃይለ ሥላሴም ስሎዋ ወይንም አምባ አላጄ ላይ በጀርባው የሚገኘው ራያ አስተማማኝ ስለማይሆን ተንቤን ላይ እንዲሰለፍ ምክንያቱም በጀርባው የሚገኘው ዋግ አስተማማኝ ነው ብሎ ምክሩን ይለግሳል።

ራስ እምሩ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በላከው ቴሌግራም አብዛኛው የጎጃም ወታደሮች ከድቷል ፤ በትውልድ ሀገራቸው ካልሆነ ለመዋጋት አይፈልጉም ሕዝቡ ሁሉ ከመጠን በላይ ለሀገረ ገዥው ለደጃዝማች አያሌው አክብሮት የለውም ፤ ይተኩስበታል ብሏል። ራስ እምሩ ለወታደሮቹ ያደረገው ንግግር ግን «እናንተ በምዕራብ ጦር ግንባር የምትገኙ ወታደሮች ካሸነፋችሁ በአሥመራ ፡በምጽዋ፡ በሮማ ባንዲራዎች በጥቁር ቀለም ይውለበለባሉ በእንዳ ጽዮን በአክሱም ቅድስት ሥላሴ የድል ጸሎት እናከብራለን» ብሏል። በማይጨው ማርች 26 የጦር ሜዳ ስብሰባ ተደርጎ አንዳንድ ተካፋዮች የኢትዮጵያ ጦር ወደኋላ ማፈግፈግ እዳለበት ሃሳብ ቢያቀርቡም ማወላወል ዋና ጠባዩ የሆነ ንጉሡ ግን ጥቂት ከተማከረ በኋላ የማጥቃት ደጋፊ የሆኑ አሸሙርተኞች ስለበዙበት ለማጥቃት ወሰነ። በኃይለ



ሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከማይጨው ወደ ደሴ ወይንም ከደሴ ደቡብ ሊያፈገፍግ ብዙ ተጨማሪ ጦር ያገኝ ነበር። ጣሊያኖችም ከባድ ጦርነት ይገጥመናል ብለው ፍርሐት አድሮባቸው ነበር። ይህ ሁኔታ እንዳይደርስ ንጉሡ እንደ ቀድሞ ነገሥታት እንዳይዋጋ ይሸሻል የሚሉ በጣሊያንኛ፣ በትግርኛ፣ በአማርኛ የተፃፉ በራሪ ወረቀቶች ጣሊያኖች ይበትኑ ነበር።

የተሸነፈችው ኢትዮጵያ መሪ አልባ ሆና በደፈጣ ውጊያ ኢጣልያን የሚቋቋሙ ወገኖች አልተሰባሰቡም ነበር

ማርሻል ባዶሊዮ ከማይጨው ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ስለተበታተነ ደሴን ለመያዝ የሚቻለው ሳይሰበሰብ በፍጥነት ገስግሰው ደሴን መያዝ ሲቻል ብቻ ነው ብሎ ወታደሮቹ በፍጥነት ተጉዘው ደሴን እንዲይዙ አደረጋቸው። ከደሴ መያዝ በኋላ የውትድርና ጠበብት ኢትዮጵያ ሊኖራት ስለሚችል እቅድ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰነዝሩ ነበር። አንዳንዶቹ ንጉሡ ጠቅላላ ክተት አውጆ ከኖና ከተማዋን ለመከላከል ሐሳብ እንዳለው ብለው ነበር። ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከደሴ በስተደቡብ ጣሊያኖችን መመከት የተዘጋጁ ይሆናል የሚል ሐሳብ ነበራቸው። ጣሊያኖች ግን የኢትዮጵያ ጦር አንድ ጊዜ ከተሸነፈ እንደገና የማንሰራራት ጠባይ የለውም፣ ተጠባባቂ ጦርም በደቡብ እንደሌለ ብለው ደምድመዋል። የንጉሡ ከንቱ ተስፋ በመንግሥታቱ ማህበር ብቻ ያተኮረ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ከማይጨው አዲስ አበባ እንደገባ ከእንግሊዝ አምባሳደር ተገናኝቶ ተነጋግረዋል፤ እስከ መጨረሻም እንደሚከላከል ይገልጽ እንደነበር ጋዜጦች ወደ ለንደን ያስተላልፏቸው ከነበሩ ቴሌግራሞች ለመረዳት ይቻላል፤ ሐሳቡን የቀየረው የመጨረሻ ደቂቃ ነበር።

ኃይለ ሥላሴ ጅቡቲ ሲደርስ ብቻ የጠበቀው ቀዝቃዛ አቀባበል ነበር። ከጦር ሜዳ ሸሽቶ መምጣቱ ያልተደሰቱበት ብዙ መሆናቸውን ለመገመት ወታደሮቹ ለመዋጋት ዝግጁ ሆነው እያሉ ስለነበረ ነው።

ከንጉሡ ጋር የመጡ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች እንደ ሚያወሩት ንጉሡ ከእንግሊዙ አምባሳደር ባርተን ጋር ከተነጋገረ በኋላ የዘውድ አማካሪዎች ስብሰባ አድርገው እስከ መጨረሻ ለመዋጋት ወስነው ነበር። በኋላ ግን ከሌሎች ሰዎችም ተገናኝቶ ከተነጋገረ በኋላ፣ ከነዚህ ውስጥም የፈረንሳዩ አምባሳደር ቦዳር ጋር ከተነጋገረ በኋላ ንጉሡ ሌላ ውሳኔ ወሰዱ። ንጉሡ ሹማምንቶችን ሰብስቦ በሰሜን የሚደረግ ነገር የለም ወደ ደቡብ መሄድ ያስፈልጋል ብሎ ነገሯቸዋል።

ንጉሡ ቤተሰቡን ጅቡቲ አድርሶ ወደ ጦር ሜዳ እመለሳለሁ ብሎ ይናገር ነበር። ለፈረንሳይ ባለሥልጣኖችም ልጆቹ ለኢጣልያ ቁንስላ እንዳያስረክቧቸው ይማጸን ነበር። ፊታውራሪ ብሩ በሌሎች የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ስም ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ

እንዲመለስ ምክር ለመስጠት ሞክሮ ነበር፤ ኃይለ ሥላሴ ግን እየሳቀ ስለሌላ ጉዳይ እንነጋገር የሚል ብቻ መልስ ሰጧል። ኃይለ ሥላሴ መመሪያ እንዲሰጣቸው ይጠባበቁ የነበሩ ባለሥልጣኖች ኢየሩሳሌም ድረስ ከመጣችሁ እንገናኛለን የሚል መልስ ይሰጣቸው ነበር። ብዙዎች ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በቂ ገንዘብ አልነበራቸውም። ልጆቹና ጥቂት ቅርብ ዘመዶች ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም ቀሳፈሩ። ራስ ደስታ ዘይላ ገብቷል ዛሬ ጅቡቲ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቅ ነበር ፤ ነገር ግን ሳይመጣ ቀረ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ግን ከሀገር አልወጡም። ከኢትዮጵያ መውጣት ያልፈለጉትና ከኢጣሊያ ጋር ውጊያ መቀጠል ከፈለጉ ራስ እምሩ ይገኙበታል።

በሽሬ ጦርነት ከተሸነፉ በኋላ የቀሩት ታማኝ ወታደሮችን ይዞ ራስ እምሩ ወደ ጉሬና ምዕራብ ወለጋ መጥቶ ሰፍሮ ነበር። በጉሬ የነበረው የእንግሊዝ ቆንስል ወደ ኡጋንዳ ጥገኝነት ቢፈቅድለትም ራስ እምሩ ግን አልተቀበለውም ፤ ወደ ጅማና ወደ ሐይቆች በመዝ ለቅ ከራስ ደስታ ጋር በትንጅት መዋጋት አቅዶ ነበር። ግራዚያኒ ግን ወደ ሱዳን እንዳይገባ፣ ወደ ጂማ እንዳያመራ ፤ ወደ ለቀምት እንዳይመጣ፤ በራስ እምሩ ላይ ከበባ አደረገበት። ራስ እምሩ ወደ ጂማ እያመራ ነበር። ኖቬምበር 12 1936 በኰ/ማልታ የሚመራው የኢ ጣሊያ ጦር በጉጀብ ጥቂት የራስ እምሩ ወታደሮችን አግኝቶ ደምስሷቸዋል። ሌላ የኢጣ ሊያ ጦር በኰሎኔል ፕሪንቼቫለ የሚመራው ዋናው የራስ እምሩ ጦር ከጅማ ደቡብ ምዕ ራብ አግኝቶ ሙሉ ቀን የቆየ ከባድ ጦርነት ገጥሟል።

ራስ እምሩ ጦሩ ጉዳት ስለደረሰበት ከቦንጋ ወደ ሰሜን ምሥራቅ አፈገፈገ። በዚህ እንዳለ ራስ እምሩ በሦስት አቅጣጫ በሦስት ኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደ ሮች የተከበበ መሆኑን ሲያውቅ በጉጀብ ወንዝ የተሰራው ድልድይ ለማቋረጥ ሲሞክር ጣሊያኖች ውጊያ ስለከፈቱበት እጁን ለመስጠት ግድ ሆነበት። ተይዞ ወደ ቦንጋ፣ ወደአዲስ አበባ፤ ከዚያም ወደ ኢጣሊያ ተወስዶ በእስር ቆይቷል። ችሎታ ያለው ሐቀኛ ጠላታችን ተብሎ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ማግሥት ከእስር ተለቆ በክብር ወደ ሀገሩ ተመል ሷል[1]።

በሰላሌ አካባቢ ኦክቶበር 20 1936 ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ከአንድ የኢጣሊያ ብርጌድ ጋር ጦርነት ገጥሞ ተገድሏል፤ ከሱ ጋርም 1000 አርበኞች ሞተዋል[2]። ደጃዝማች ወንደሰን ካሣ ተከዜ አካባቢ አንድ የኢጣሊያ ባንዳ ዲሴምበር 10 1936 ዓ.ም ከማረከው በኋላ ጣሊያኖች ወዲያውኑ ገደሉት።

---

1. F.l.o.l v3 p.440

2. F.l.o.l v3 p. 452



ፍቼ አካባቢ ሁለቱ ሌሎች የራስ ካሣ ልጆች አበራና አስፋወሰን የራስ ኃይሉ ባንዳ ተካፋይ በሆኑበት በአምስት አቅጣጫዎች ከከበቡዋቸው በኋላ ዲሴምበር 21 1936 እጃቸውን ሰጥተው ምህረት እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም አነስተኛ ተኩስ ተደርጐ ከተማረኩ በኋላ በጥይት ተደብድበው ተገድለው በፍቼ አደባባይ አስከሬናቸውን ሰቅሏ ቸዋል። በማግሥቱ በግድያው የተካፈሉ 14 ሺህ የኢጣ ሊያ ወታደሮች በፍቼ ከተማ ሰልፍ አሳይተዋል[1]።

የካቲት 12፣ ፌብሯሪ 1937 በየዓመቱ የምናከብረው በአዲስ አበባ የተፈፀመው የንጹሃን ደም ጭፍጨፋ ጣሊያኖች እንደሚከተለው ያቀርቡታል። ሽፍቶች በገጠር ሽንፈት ስለደረሰባቸው በአዲስ አበባ ከተማ ተሰግስገው የነበሩ የካቲት 12ቀን ከቀኑ 6 ሰዓት የንጉሡ እንደራሴ ማርሻል ግራዚያኒ ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ለድሆችና ለቤተ ክህነት ሰዎች ስጦታ በሚሰጥበት ጊዜ ወንበዴዎች ፈንጂዎችን በመወርወር የመግደል ሙከራ ፈጽ መው ራሱ ህገረ ገዥውና የንጉሡ እንደራሴ በብዙ ፈንጂዎች ፍንጣሪዎች ቆስለው ስለነበረ፣ ይህ የክህደት ሥራ የከተማዋ የፀጥታ ሁኔታ ሊያናጋ አልቻለም ሁሉም አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ወንበዴዎች ከመቅጽበት በማያዳግም ሁኔታ ተደምስሷል። ጣሊያኖች የጠረጠሩዋቸው የሚያስጨንቋቸው የነበሩ የራስ ካሣ ልጆች እና የደጃዝማች ፍቅረ ሥላሴ እጅ እንዳለበት ነበር።

የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ለጣሊያኖች እጃቸውን ለመስጠት በዲሴምበር 1936 በአዲስ አበባና በሌሎችም ክፍላተ ሀገሮች ቀጥለው ነበር። ጀንዋሪ 1937 የእጅ መስጠት መሀላ ሥነ ሥርዓት በአዲስ አበባ ተፈጽሞ ነበር።

ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማሪዮ አፐሊዩስ ‹ Mario Appelius› እንደሚከተለው ያቀርባል። የክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያሉበት 200 የሚደርሱ የቀድሞ ሹማምንቶች በአዲስ አበባ ተሰብስበው ነበር። በስብሰባው ከነበሩ የጐጃሙ ራስ ኃይሉ፣ አቡነ ቂሪሎስ፤ ራስ ሃብተ ሚካኤል፤ ደጃዝማች አያሌው ብሩ 11 ፊታውራሪ 20 ቀኛዝማች፤ ብዙ የቤተ ክህነት አለቆችና ሙስሊሞች ይገኙበት ነበር። ከንጉሡ እንደራሴ ጐን ሁሉም የኢጣሊያ ባለሥልጣናት ተገኝተዋል። የዘብ ጠባቂዎች ጉራዴያቸውን እንደመዘዙ ሱማሌዎች ቆመው ነበር። አንድ በአንድ ሁሉም እጁን ለመስጠት የቀረበ የቀድሞ ባለሥልጣን ለማሃላ የተዘጋጀ ቃል እየደገመ ከኢጣሊያ ንጉሥ ሌላ ንጉሥ እንደማ ያውቅ ይናገር ነበር። የጐሬ ገዥ የነበረ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ በንጉሡ ነገሥት ምኒ ልክ፤ በልጅ እያሱ፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፣ በንጉሡ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ያገለገለ ባደረገው ንግግር እስካሁን እጄን ያልሰጠሁ ግዛቴ በኢጣሊያ ወታደሮች ስላልተያዘ ነበር ፤ ከእንግዲ ሕይወቴ እስካለ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ታማኝ በመሆን አገለግላለሁ።

---

1. F.l.o.l v3 p.453

እግዚአብሔር በርግ ሥልጣኔ ኢትዮጵያ እንድትስተዳደር ያድርግልን፤ ረጅም ዕድሜ ለኢጣሊያ ንጉሥ፣ ለዱቼ፣ ለንጉሡ እንደራሴ ግራዚያኒ ብሏል። ሌሎችም ንግግር አድርገዋል። በመጨረሻ ማርሻል ግራዚያኒ በአደረገው ንግግር ዛሬ እጃቸውን የሰጡ ማዩ ደስታ ይሰማኛል፤ እስከዛሬ ያጠፋችሁ ሁሉ ይቅርታ ተደርጎላችኋል። ብዙ የሃሰት ወሬ ይሰማሉ፤ ለምሳሌ ደጃዝማች ሃብተ ማርያም በመካላችሁ ያልተገኙበት ምክንያት ከእኛ ጉን ሆና በመጀመሪያ በለቀምት ሽፍቶቹን ለማሳደድ ከተካፈለ በኋላ በራሱ ባንዳዎች በተመላላይ ሥራ ወደ ጅማ ሄዶ ስለነበረ ጤንነቱ ስለተጉሳቀለ ዛሬ በዚሁ ስብሰባ ባይገኝም ከ15–20 ቀን በኋላ በመካላችሁ ይገኛል። ሁላችሁም ማወቅ የሚገባችሁ የኢጣሊያ መንግሥት ሃሰት እንደማይናገር ነው። ታላቅ መንግሥት ሃሰት አይናገርም። ስለ ራስ ኃይሉም ሃሰት ይወራል።ስለ ራስ ካሣ እጎጊትም የሃሰት ወሬ ይወራሉ[1]።

ራሥ ኃይሉ ከምዕራብ ከኩሉኔል ቤሊ ጋር ወደ ሬቹ በራስ ካሣ ልጆች ላይ እንዲዘምት የላኩት እኔ ነኝ። ራስ ኃይሉ በመጀመሪያ የራስ ካሣ ልጆችን ደርሶባቸው ተኩስ አልከፈተባቸውም፤ ጠርቶ ልትዋጉ የምትፈልጉ ከሆነ፤ ወንዶች ከሆናችሁ ግጠሙን፤ እጃችሁን ለመስጠት የምትፈልጉ ከሆነ ልንቀበላችሁ ዝግጁ ነን አላቸው። የራስ ካሣ ልጆች ዝም ብለው ሲሄዱ ተኩስ ከፈተባቸው። ራስ ኃይሉ ግዳጅን የፈፀመው የራስ ካሣ ልጆችን በመማረክ ለጣሊያኑ መንግሥት አሥረከባቸው። እሱ ግን በአንድ የኢጣሊያ ጦር መኮንን ሥር ሆኖ የአንድ ባንዳ አዛዥ ብቻ ነበር። ከእናንተ ብዙዎቹ ወግተውናል እጃቸውን ሲሰጡ ግን ይቅርታ አድርገንላቸዋል። አንድ ጊዜ ይቅርታ ተደርጎላቸው እንደገና ሲቃወሙን ከተገኙ ግን ይቅርታ አይደረግላቸውም። የዚሁ ጥሩ ምሳሌ የራስ ካሣ ልጆች ናቸው። ወደ እኛ እንዲመጡ ብዙ ጊዜ ጥሪ እንዳደረግንላቸው ታውቃላችሁ ፤ እነሱ ግን ጥሪያችንን አልተቀበሉም። ራስ ኃይሉ፣ ራስ ሥዩም ፤ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ደብዳቤ ጽፈውላቸው፤ ነገር ግን ምንም ውጤት አልተገኘም። በዚህ አጋጣሚ ራስ ኃይሉ ስለፈፀመው ውለታ ላመሰግነው እወዳለሁ።

"ጃዝማች ሃብተ ማርያምም ለኢጣሊያ መንግሥት እጁን እንዲሰጥ ያደረገው ራስ ኃይሉ ነው። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ሰላም ሰፍኗል። የቀረን ያ የተረገመው ራስ ደስታ ብቻ ነው። ራስ ደስታ ለመንግሥት እጁን ለመስጠት እንደማይፈልግ ገልጾ ነበር፤ እኔ ራሴም ደብዳቤ ጽፌለት ነበር ፤ ደብዳቤውም በእጁ ደርሷል። ለእንደዚህ ያለ ሰው ይቅርታ ማድረግ ይገባልን? የማይቻል ነው። ራስ ደስታ በገዛ እጁ የሞት ፍርድ ፈርዷል። በቅርብ ጊዜ የኢጣሊያ ፍትሐዊ ሕግ በሰይፍ ለዘለዓለም ይቀጣዋል። ደጃዝማች በየነ መርዕድም አለ። ከሰባት ወር ጀምሮ ባላባቶች ፤ ሹማምንቶች ፤ቤተዘመዶች ጦር መግፊያን አስተምሮ ለኢጣሊያ መንግሥት እጁን እንዲሰጥ መክረውታል።

1. F.Lol v3 p.486



እሱ ግን ውጊያ መርጧል። እሱም በቅርብ ጊዜ ይደመሰሳል። እነዚህ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው በጦርነት የተሰማሩ፤ ከዚህ በኋላ ግን በመላው ኢትዮጵያ ሰላም ይሰፍናል። ኢትዮጵያ ወደፊት በንጉሣችን ሥም በዱቼ ስም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ለንጉሣችን ሰላምታ Saluto Al Re ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር Viva Il Re ሰላምታ ለዱቼ Saluto Al Duceለእኛ A Noi እያሉ 200 የተድሞ ሹማምንቶች በጣሊያንኛ ድምፃቸውን አሰምተዋል።

## የራስ ደስታ ዳምጠው መያዝና አሟሟት

ጦርነቱ አልቆ ጣሊያኖች የፖሊስ አሰሳ ብቻ እንደተጠለ ይናገሩ ነበር። ፀረ ኢጣሊያ የኢትዮጵያውያን አርበኝነት ከማቀጣጠል አልተቆጠቡም ነበር። ከእነሱ ውስጥ ራስ ደስታ፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ ደጃዝማች በየነ ፤ደጃዝማች ሽመልስ ነበሩ። እነሱ ከነበሩበት ከወላሞ ተነስተው ዋና ከተማዋንም ለማጥቃት እቅድ ነበራቸው። ማርሻል ግራዚያኒ ግን ፋታ አልሰጣቸውም። ጣሊያኖች ብዙ ጀኔራሎች ኮሎኔሎች የተካፈሉበት በፌብሯሪ ከፍተኛ ዘመቻ አካሄዱ።

ፌብሯሪ 20 በተደረገው ጦርነት ደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ በጃዝማች በየነ መርዕድና ሌሎች የበታች ሹማምንቶች በጦር ሜዳ ሲገደሉ ራስ ደስታ ብቻ ለማምለጥ ችሉ ነበር። ነገር ግን ቱቺ በተባለው ኢጣሊያዊ የጦር መኮንን የሚመራ የትግሬዎች ባንዳ ፌብሯሪ 27 ቀን ደርሶበት ተማርኮ በጥይት ተደብድቦ ተገድሏል። ከራስ ደስታ ሞት በኋላ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በኢጣሊያ ቁጥጥር ሥር እንደዋለች ይቆጠራል ብለው ጣሊያኖች ይፎክሩ ነበር። ማርዮ ማሣይ ‹Mario Masai› የተባለው ኢጣሊያዊ የCorriere Di Napoli ወኪል የራስ ደስታና ሌሎችም አሟሟት ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጾታል።

ራስ ደስታ ዳምጠው የሞተው እያለቀሰ ነበር። በሶማሌ እነጋገር ራስ ናክ ማለት ራስ ሴት ይሉታል፤ በአማርኛ ወይዘር ደስታ ይሉታል። ጦሩ በነገሌ ሲሸነፍ ከንጉሡ ስድብ ሲደርስበት አልቀረም፤ ልጅ ሥዩም የእህቱ ልጅና ባራምባራስ ፈለቀ የራሱ ዋና ፀሐፊ የነበረው እንደመሰከሩበት ማርሻል ግራዚያኒ አርባ ጉጫ ከሸና Vina አካባቢ የሰፈረው የመጨረሻ ጦሩ ጥቃት ፈጽሞበት ሲበታተን አልቀረም። ራስ ናክ የሺምበር መጨረሻ እጁን ለመሥጠት ታስቦ 47 ዓመት በኢትዮጵያ የኖረው ሲኖር ካስታኛ ‘Castagna› ሲላክበት አልቀረም። በኢጣሊያ የጦር መኮንን ቱቺ የሚመራ ያደጃዝማች ታከለ መሃኛ ባንዳዎችና በሌላ የኢጣሊያ የጦር መኮንን ፒና የሚመራ ብረት ለበስ የሶማሌ ወታደሮች ተይዞ በማካ ወደ ጦር ፍርድ ቤት ሲቀርብም አልቀረም። «እኔ አልተዋጋሁም» እያለ

ደጋግሞ ይናገር ነበር። እውነቱ ነው አልተዋጋም ተኩስ ሲሰማ የኢጣሊያ ወታደሮች ያልደረሱበት ቦታ መሸሸ ነበር ሥራው፤ ወራዳና ጨካኝ ግለሰብ የሲዳሞና የቦረና ጦር በሚያዘበትም ጥቂት ሺህ ሼፎች መሪ በነበረበትም ጊዜ። ዛሬ የአማራና ለ50 ዓመታት ዋና ከተማዋ የባርያ ንግድ ምንጭ የነበሩ የጉራጌ ዘር ድብልቅ ነው። ተፈሪ ፈረንቱን ስለሚያውቅ ከኮናሌ ጦርነት ሽንፈት በኋላ ጀግናው ምርጥ ሽፍታው ገብረ ማርያም ከጎኑ አስቀመጠበት።

ራስ ደስታን የማሳደድ ተግባር አላፊነቱን በቀጥታ ራሱ ማርሻል ግራዚያኒ ወሰደ። በባሌ አገረኛ የጀነራል ጀሉዞ ጦር ሲከታተለው በሰማይ አሬዮፕላን ሲያጠቁት ወደ የተራራውና ጫካው እየሸሸ ከደጃዝማች በየነ ተቀላቀለ። ግራዚያኒ በባሌ በረሃዎች ፋታ አልሰጣቸውም፤ በምሥራቅ የጀ/ናዚ ጦር፤ በሲዳሞ የጀ/ጀሉዞ ጦር ፤ በጉራጌ የጃ/ጋሊና ጦር እንዲሁም በወላሞ፤ በከምባታ፤ በሐይቆች ሌላ ጦር ተሰማርቷል፤ የጦር አሬዮፕላኖችም ተካፈለዋል። በዚሁ ጊዜ የንጉሡ እንደራሴ ማርሻል ግራዚያኒ ከሰሜን የሊቢያ ዲቪዚዮን እንደዚሁም የሶማሌ ባታሊዮች ከደቡብ ለጥቃት ያሰማራል፤ በተጨማሪም ከኢሚ ዱባትና ሊቢያውያን ወደ ላይኛው ዋቢ ሲመድብ በየነ መርዕድ በባሌ ለመኖር የማይቻል ስለሆነበት ሽፍቶቹ ባሌን ለቀው ወደ ምዕራብ ጉራጌና ከንባታ ለመሄድ ግድ ሆነባቸው ፤ ሌላ አማራጭ ማምለጫ አልነበራቸውም። ገብረ ማርያም፤ ደስታና በየነ መርዕድ ወደ ዋቢ ምንጭ ሲሸሹ አራት ባታሊዮን ሊቢያውያን ሊይዙዋቸው ተቃረቡ፤ ጦርነት ተደረገ በውጤቱ ግን ሽፍቶቹ አልተያዙም እሱሉ በተባለው ቦታ መንገድ ዘግተው ወደጃቸው የሞከሩ ብረት ለበስ ጦርና ሱማሌዎች አላገኙዋቸውም፤ ሦስቱ አምልጠዋል። የማርሻል ግራዚያኒ ትእዛዝ ቀጥሉ ፋታ አልሰጣቸውም፤ ሰላም የሰፈነበት ሀገር በራስ ደስታ አለመያዝ መደፍረስ የለበትም ፤ ስንቅ አሬዮፕላኖች ያቀርቡላችኋል የሚል ነበር። ናታስና ቀሞ የተባለው ተቃር በዋል ጋሊና ወደ ጉራጌ ነው፤ ዛምበን ሆሳዕና ነው፤ ከበባው ተጠናከረ። ናታለና ቁሞ መሪዎቹ ያሉበት መደበቂያ አግኝተው ተኩስ ይከፍታሉ ከውስጡ ተቃውሞ ይገጥማቸዋል። ገብረ ማርያም እየተዋጋ ወደቀ ፤ በየነ መርዕድ ተማርኮ ከአጭር የጦር ፍርድ ቤት በኋላ በጥይት ተደብድቦ ተገደለ። ራስ ደስታ እንደልማዱ አሁንም የመጀመሪያው ተኩስ ሲሰማ በቅሎውን በኃይል እየጋለበ ይሸሻል ከእሱ ጋርም ፊታውራሪ ካሣ ነበር። ከዝዋይ በስተምዕራብ ወደ አዳሚቱሉ ምናልባት ወደ ጉራጌ ሀገር ዘመዶቹ ወደሚገኙበት። ራስ ደስታ ቀንና ሌሊት ይሸሻል፤ ገብረ ማርያም እንደሞተ አያውቅም፤ በተለይ በቶቺ የሚመራው ደጃዝማች ተክለ መሸሻ የትግሬዎች ባንዳ እንዲሁም በፒና የሚመራው የሱማሌ ታጣቂዎች እግሩ የረገጠውን እንደሚከታተሉት አያውቅም። ራስ ደስታ ጉራጌ ሀገር ደርሷል ፤ ያመለጠ መስሎት ነበር። ጧት ፌብሯሪ 25 1937 ባደረበት ቤት ተኩስ ይሰማል። ፊታውራሪ ካሣና የነበሩ ጥቂት ወታደሮች



እንደተከበቡ አወቁ፤ እስከ መጨረሻ ጥይቶቻቸው ተታኩሰው የጀግና አሟሟት ለራስ ደስታ አስተምረው ወደቁ። ራስ ደስታ እጁን ወደ ላይ አውጥቶ ከቤት ይወጣል፤ እጁን ይሰጣል፤ ጣሊያኖች ሕይወቱን የሚያተርፉት መስሎት ተስፋ ያደርጋል። ራስ ደስታ በኢውሮጳ መዲናዎች ሲጎበኝ የነበረ ልዑል ራስ ደስታ አይደለም፤ ጢማም፤ ቡቲቲ ጨርቅ የለበሰ በድንጋጤና በፍርሃት የአንድ ጥቁር ሰው ፊት ቢጫ ሆኗል። ራስ ደስታ ይቅርታ ይጠይቃል፤ መሬት ወድቀው ሰላምታ ያልሰጡ ይገርፍ የነበረ፤ ስለ ኢጣሊያ ፍትህና ሥልጣኔ ለማውራት የሞከረ ሁሉ ያስርና ይገድል የነበረ፤ ሜይ 1936 የኢጣሊያ ጦር መኮንኖች በእጁ የወደቁ አስከሬኖች ይቆራርጥ የነበረ፤ ዛሬ ለእያንዳንዱ ኢጣሊያዊ ወታደር እጅ ይነሳል ፍትሐዊ የኢጣሊያ ጦር ፍ/ቤ ት በሜካ ጦር ሜዳ ችሎት የወታደር አሟሟት ክብር ሰጥቶታል[1]።

ጣሊያኖች በራስ ደስታ ላይ ከመጠን ያለፈ ጥላቻ ያደረባቸው ባንዳነቱም በራስ እምሩ ላይ አክብሮት መስጠታቸው አሁንም የኢጣሊያኖች ፍትህ አልባነት የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር ለሀገራቸው የተዋደቁ።

ከሜይ 1936 እስከ ማርች ለ10 ወር ጣሊያኖች 45 የጦር መኮንኖች 207 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 1200 እንዲጀኒ ወታደሮች ሞተውባቸዋል[2]።

በአጠቃላይ ጦርነቱ በይፋ ከመጀመሩ 3 ወር በፊት በጁላይ 1935 ጦርነቱ ካለቀ 2 ወር በኋላ ድረስ የሞቱ ጣሊያኖች 2911 ሲሆን እስከ ጁላይ 31 1939 ድረስ የሞቱ ጣሊያኖች 4915 ደርሰው ነበር ፤ ከኢንዲጀኒ ሌላ።

እላይ ስሙ የተጠቀሰው ካስታኛ ስለተባለው ኢጣሊያዊ አርናልዶ ቺፖላ ታሪኩ አውጥቷል። ካስታኛ በዐድዋ ጦርነት ከታሰሩ የኢጣሊያ ወታደሮች አንዱ ነበር ፤ የምሕንድስና የበታች መኮንን ነበር። ከአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ መንገዶች፤ ድልድዮች ፤ ቤቶች፤ እየሰራ ከነገሥታትና ከሹሞች ተስማምቶ ይኖር ነበር። አንድ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ብዙ ልጆች ወልዷል። እንደ አራት ረጅም ጢም የነበረው ካስታኛ በጦርነቱ ወቅት ፈረንጆች ሀገር ለቀው ይወጡ ስለነበረ አጼ ኃይለ ሥላሴ «አንተ ካስታኛ ከኛ ጋር መቀመጥ የምትመኝ ይመስለኛል። የኢጣሊያዊነት ምንም የቀረህ ነገር የለህም። ብሉ ቢጠይቀው «የኢጣሊያዊነት ልብ ነው የቀረኝ» ብሉ መለሰለት።

የኢጣሊያ አምባሳደር ጦርነት ሲጀመር ሀገር ለቆ ሲወጣ ሲኞር ካስታኛ ሊሸኘው በባቡር ጣቢያ ተገኝቶ ነበር። አምባሳደሩ ታዲያ ምን አሰብህ ብሉ ለካስታኛ ይጠይቀዋል። ከዚህ ሀገር ለቅቄ መውጣቱ የማይቀር ነው፤ ለኔ ቀላል ነገር አይደለም ለመሄድ፤ ለሚስቴ ፤ ለልጆቼ፤ ለቤተሰቤ ማሰብ አለብኝ።

1. F.I.o.I v3 p. 472-74

2. F.I.o.I v3 p. 476'

ሆኖም አይጠራጠሩ እመጣለሁ። ምንም እንኳ ለ 40 ዓመት በኢትዮጵያ ተቀምጬ ሕይወቴን ለእነዚህ ሰዎች መስዋዕት ባደርግም እኔ ኢጣሊያዊ ነኝ አልረሳውም። አምባሳደሩም ካስታኛ ከኔ ጋር ከዚህ ሀገር ብትወጣ ይሻልሃል ይለዋል። ካስታኛም እንደዚህ ነው? ይለዋል።

አምባሳደሩም አዎ እንደዚህ ሆነህ ይለዋል። አንድ ሻንጣ ሳልይዝ ያለ ገንዘብ ከቤተሰቦቼ ሳልሰናበት በግለት መልስ ይሰጠዋል። አምባሳደሩም ትክክል ይለዋል። ካስታኛም ሲኞር አምባሳደር ይኼ የማይቻል ነው ብሎ መልስ ይሰጠዋል። አምባሳደሩም ካስታኛ ወይንም ዛሬ ከእኔ ጋር ወይንም ምን ጊዜም ከዚህ ሀገር አትለቅም ይለዋል። ካስታኛም ሲኞር አምባሳደር አረጋግጥልሃለሁ ብሎ መልስ ለመስጠት በሚሞክርበት ጊዜ ባቡሩ ሊነሳ ነበር አንባሳደሩ ምልክት በሰጠው መሠረት አንድ የኤምባሲ ሠራተኛ ወደ ባቡሩ ገፍቶ ያስገባዋል! ሌሎችም ጣሊያኖች ከባቡር ውስጥ ሆነው እየሳቁ በጢሙ ይስቡታል። ከአንድ ደቂቃ በኋላ ባቡሩ ተነሳ ካስታኛም ከአምባሳደሩ ጐን ተቀመጠ ጅቡቲ እንደደረሱ ቪንቼና ካስታኛ ወደ ሞቃዲሾ ሄደ ካስታኛ የማረሻል ግራዚያኒ ዋና ጽ/ቤት ሎግ የማስታወቂያ ክፍል ተመድቦ ይሰራ ነበር። ካስታኛ አንድ ቀን «ክቡር ሆይ ከፈቀዱልኝ እኔ ብዙዎችን ራስ ደስታ ወዳሉበት ሄጄ እዚህ ላምጣው። ከልጅነቱ ጀምሮ ነው የማውቀው። አባቱ በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ሞቷል! የኃይለ ሥላሴ ቲገን ምሳሌ እንዲ ከተል ሳልረዳው እችላለሁ» ብሎ ለግራዚያኒ ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ነገር ግን ግራዚያኒ ውድ ካስታኛ እርስዎ ከእኛ ጋር ቢቀመጡ የተሻለ ነው ምክንያቱም እርግጠኛ ነኝ 40 ዓመት በኢትዮጵያ ቢቀመጡም ከራስ ደስታ የሚያገኙት አቀባበል ለሕይወትዎ የሚያሰጋ ነው ብሎ መልስ በመስጠት እንዳይሄድ ከለከለው።

ጣሊያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ ግራዚያኒ ሶማሊያ ሀገር ሆኖ ያልፈቀደለት ካስታኛ ራስ ደስታ ወደሚገኙበት ጫካ ሄዶ እጁን እንዲሰጥ! መልእክት እንዲያደርስለት ቢልክ ውም ውጤት አላሰጠም።



# ምዕራፍ 14

# ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አስተዳደርና የአርበኝነት ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ታሪክ

ወራሪ የኢጣሊያ ሠራዊት ከኤርትራ ተነስቶ ማይጨው ለመድረስ የ200 ኪሎ ሜትር መንገድ ከ6 ወር በላይ ጊዜ ፈጅቶበታል። እንደዚሁም በደቡብ ጦር ግንባር ከሶማሊያ ተነስቶ ኦጋዴን ለመያዝ ከማይጨው ጦርነት በኋላ ግን አዲስ አበባ ለመድረስ 600 ኪሎ ሜትር አንድ ወር አልፈጀበትም እንደዚሁም በደቡብ ጦር ግንባር ከኦጋዴን ድሬደዋ ለመድረስ አንድ ወር አልፈጀበትም። ሁኔታው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደተሸነፈና እንደተደመሰሰ ኢትዮጵያም እንዳበቃላት ያስመስል ነበር። ሐቁ ግን ጣሊያኖች በአጭር ጊዜ አዲስ አበባ ሊገቡ የቻሉት ኢትዮጵያ መንግሥት አልባ ሆና ስላገኙዋት ሠራዊቱም ጠቅላይ እዝ ስላልነበረው በዓለም መንግሥታት መድረክ ለፕሮፓጋንዳ ስነ ልቦና እንዲጠቀሙበት ጦርነት ሳይገጥማቸው ተሽለኩልከው አዲስ አበባን መቆጣጠር ቻሉ እንጂ በድል አድራጊነት አልገቡም። “ዱቼ” ስለ ሁኔታው ስላልተረዳ አዲስ አበባ ከተያዘች በኋላ ወራሪ የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገሮች ዘመቻውን ወዲያውኑ እንዲቀጥል ትእዛዝ ያስተላልፍ ነበረ። ሆኖም በስፍራው ያሉት የጦር አለቆች ግን የክረምት ዝናብ ምክንያት በማቅረብ ጨርሶ እንደማይቻል ስለገለጹለት እንደ ነገሩ ሁኔታ አስፈላጊውን ውሳኔ ራሳቸው እንዲወስዱ ለመፍቀድ ተገደደ። በዚሁ መሠረት ወደ ምዕራብና ደቡብ ክፍላተ ሀገሮች ወረራ ለ5 ወር እንዲዘገይ ተደረገ። ስለዚህ የመጀመሪያ አንድ ዓመት የኢጣሊያ አገዛዝ ታሪክ በክረምት 5 ወራትና ከክረምት ፍጻሜ በኋላ ያሉት 7 ወራት ለሁለት ይከፈላል።

ከማይጨው ጦርነት ሽንፈት በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት በደቡብ ጦር ግንባርም ሽንፈት ስለገጠመው ተበታትኖ እየሸሸ ወደ እየቤቱ ይመለስ እንደነበረ የጣሊያኖች ግምት ነበረ። በዚሁ ጊዜም የኢጣሊያ ሠራዊት በተሽከርካሪዎች ይጓዝ ስለነበረ በእግሩ የሚጓዘውን የኢትዮጵያ ወታደር በመቅደም ከተጠበቀው በላይ በፍጥነት አዲስ አበባ ገብቶ ለመላው ዓለም ድል ተቀዳጀሁ ብሎ ቢያበስርም የኢትዮጵያ ሠራዊት ግን ተበታትኖ ተሸነፍኩ ብሎ የኢጣሊያ ድል አምኖ እንዳልተቀበለ ገሐድ እየሆነ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በጦር ሜዳ የተሸነፈው መሪ በማጣቱ ነው። አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ከወደቀች በኋላም በጣሊያኖች ወራሪዎች ላይ ውጊያውን የቀጠለው በአንድ መሪ ቁጥጥር ተደራጅቶ አልነበረም፤ በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍሎ በተፈጥሮ የወረሰው የሀገር ፍቅር ስሜት ባንዳንድ ቆራጥ የቀድሞ መሪዎቹ ሥር ተሰባስቦ ነበረ። ኢትዮጵያውያን በአዲስ መንፈስ ውጊያውን መቀጠል የውጭ መንግሥታት እጅ እንዳለበት የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው። ከኢትዮጵያ አጐራባች ቅኝ ግዛት ያላቸው መንግሥታት ኢጣሊያ ደካማ በመሆኑዋ ስለ የኢትዮጵያ ግዛት ለመቆጣጠር ዐቅም የላትም ብሉ በመገመት የኢትዮጵያ መሬት ከኢጣሊያ ጋራ ለመቀራመት ፍላጎት እንደነበራቸው ጣሊያኖች እንደደረሱበት ገልጿል። የኢትዮጵያውያን በጣሊያኖች አገዛዝ ላይ ለውጊያ በማነሳሳት እርዳታ ሰጪ ሆነው በመቅረብ የኢትዮጵያ መሬት ለመከፋፈል ፍላጎት የነበራቸው መንግሥታት እንደነበሩ!

ጣሊያኖችም ደካሞች በመሆናቸው እርዳታ ለመቀበል ይገደዱ እንደነበረ ዘግቧል። በጣሊያኖች አባባል በዚሁ መንፈስ ነበረ በምዕራብ ኢትዮጵያ በጉሬ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመው። በጂቡቲ በሶማሊላንድ ፀረ ኢጣሊያ አገዛዝ በኢትዮጵያ በደተኞች መሐል ቅስቀሳ ይካሄድ ነበረ። የዚህ ሁሉ ዓላማ ጣሊያኖችን በማዳከም ኢትዮጵያን ለመዘፋፈል ነበረ።

ጣሊያኖች ግን የነበራቸው ዓላማ የውጭ መንግሥታት ዕቅድ ውድቅ በማድረግ ብቻቸውን የኢትዮጵያውያንን ተቃውሞ ለማውደም ነበረ።

ጣሊያኖች አራት ቀን አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ሜይ 9 ቀን 1936 ስለ ኢትዮጵያውያን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ባደረጉት ግምገማ የሚከተለው ነበረ።

## በበጌ ምድርና ጐጃም

1. ፊታውራሪ መንገሻ በጋላባት አካባቢ
2. ደጃዝማች ባሄል በባሕር ጣና አካባቢ
3. ራስ እምሩ በደብረ ማርቆስ
4. ደጃዝማች አያሌውና አድማሱ ብሩ በጋይንት አካባቢ
5. ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ በበጌምድርና ዘጐጃም
6. ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ በላሊበላ

## በሸዋ

7. ደጃዝማች አበራ ካሣ በፍቼ
8. ራስ ከበደ በኢፍራታ
9. የሽፍቶች ቡድን በጣርማ በር
10. ፊታውራሪ ፍቅረማርያም በጂሩ
11. ፊታውራሪ አስቻናፊ በሰላሌ
12. ደጃዝማች ባልቻ እና መታፈሪያ በደብረብርሃን መንገድ ግራና ቀኝ

## አዲስ አበባ

በከተማዋ ሰላም ሰፍኖዋል፤ ራስ ኃይሉ በጉለሌ ይገኛል። በከተማዋ ዙሪያ ግን ብዙ ሽፍቶች ነበሩ፤ ተለይተው የታወቁ በሰላሌ በእቃቂና ቡልጋ ያሉ ናቸው። ከእነሱ ውስጥ ባራምባራስ አበበ የፖሊስ አዛዥ የነበረ እና ብላታ ታከለ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሹም የነበረ ይገኙባቸዋል። በመናገሻም የታጠቁ ቡድኖች ታይቷል።

## ሲዳማ አርሲ ባሌ

13. ራስ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች ገብረማርያም ደጃዝማች መኩንን ወሰኔ በኬንያ በኩል ከእንግሊዞች ጋራ ግንኙነት ያላቸው።
14. ደጃዝማች በየነ መርዕድ ብጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ደጃዝማች ተፈራ

## ሐረር

15. ብዙ ሽፍቶች በጨርጨር ጋራሙለታና ከንዱዶ ሰፍረው ይገኛሉ እጃቸው ለጣሊያኖች ለመስጠት የገለጡ ራስ ኃይሉና ራስ ሥዩም ናቸው፤ ገና እጃቸውን ለመስጠት በማወላወል ላይ የሚገኙ ደጃዝማች አያሌው ብሩና ራስ ከበደ መንገሻ ናቸው።

አዲስ አበባ በኢጣሊያ እጅ እንደወደቀች የኢጣሊያ መንግሥት ጦርነቱ እንዳለቀ ሰላም እንደሰፈነ ግምት አድርጎበት ነበር። በሰፍራው የነበሩ የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ግን አዲስ አበባ በመግባታቸው ኢትዮጵያን እንዳልተቆጣጠሩ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። የኢጣሊያ ሠራዊት



በአስጊ ሁኔታ እንደሚገኝ ለመንግሥታቸው ለማስረዳት ብዙ መጣር ነበረባቸው። የተደቀኑባቸው ችግሮች ለመቋቋም ብዙ ትግል ማድረግ እንደሚቀርባቸው ስለተረዱ ከአርበኞች አደጋ ለመከላከል ለአስፈላጊ እርምጃዎች ቢወሰዱም ቀላል አልነበረም። የጣሊያኖች የመጀመሪያ ስጋት ያደፈጡ በየቦታው የነበረ የኢትዮጵያ አርበኞች በአንድ መሪ እንዳይታዘዙ ሲሆን፣ የሁሉም መሪ ይሆናል ብለው የጠረጠሩት ራስ እምሩ ነበረ።

የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ከወሰዷቸው እርምጃዎች ዋንኛው ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል ነበር። ለዚሁም በከተማዋ መሃልና በዙሪያዋ ብዙ ወታደሮች ማስፈር ተገደው ነበር። ለጣሊያኖች ተደቅኖባቸው የነበረ ሌላ ችግር የመገናኛዎች ደኅንነት መጠበቅ ነበረ። ስጋት ወድቀው የነበሩ መገናኛዎች ከአዲስ አበባ ጅቡቲ የተዘረጋው ባቡር ሐዲድና ከአዲስ አበባ ደሴ መንገድ ነበረ። ይህ ሁሉ ለማከናወን ከሞቃዲሾና ከሌሎች ቦታዎች ተጨማሪ ወታደሮች እንዲላኩ አድርገዋል። ጣሊያኖች የስንቅ ችግር ለመፍታት የተሻለ ሆኖ ያገኙት ከውጭ በሶማሊያና በጅቡቲ ለማስገባት፣ ከሀገር ውስጥ የገበያ አቅርቦት አናሳ ስለነበረ ወደ ገጠር እየሄዱ ከገበሬዎች በመዝረፍ ይጠቀሙ ነበረ። ሌላ ቅድሚያ የሚሰጠው አስጊ ሁኔታ ብለው የገመቱት በሐረርጌ የሰፈሩ አርበኞች ለመደምሰስ ነበረ። ይኸንንም ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴ ከጦር ኃይል በተጨማሪ አርበኞችን ለመከፋፈል በመቻላቸው ነው። ገና በኢጣሊያ ያልተያዙ ክፍለ ሀገሮች፣ በተለይ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመበት በጉሬ አካባቢ ለመዝመት የዓለም ዜና ማሰራጫዎች ኢትዮጵያ በሙሉ በጣሊያኖች እንዳልተያዘች የሚያናፍሱት ዜና ለማስቀረት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነበረ። የአስተዳደር መዋቅር መዘርጋት የወታደር ቁጥር መቀነስ ቀላል ሥራ አልነበሩም።

የኢትዮጵያ አርበኞች ትግል ለመጀመሪያ ጊዜ ያበሰረው በምሥራቅ ሐረርጌ ከሐረር ጅጅጋ ባለው መንገድ ነው። ሜይ 14 ቀን 1936 ማለት 9 ቀን አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ አርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው 6 ሰዎች ሞተው 2 ቆስለውባቸዋል፤ ሁሉም ኢንጂኒ ነበሩ። ከኢትዮጵያ ወገን በውጊያ ከሞቱ ሌላ የተማረኩ 6 ወታደሮች በጣሊያኖች ተረሽነው ተገድለዋል። የተማረኩ ወታደሮች የተገደሉበት ምክንያት ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር በላከው ቴሌግራም እንደገለጠው የኢትዮጵያ መንግሥት የተደመሰሰ ስለሆነ ማንኛው ወታደር እጁን ለኢጣሊያ ባለሥልጣናት ከሰጠ ምህረት እንደሚደረግለት እጁን የማይሰጥ ግን እንደ ተራ ሽፍታ ዘራፊ ተቆጥሮ እንደሚገደል ለባላባቶችና ለወታደሮች በአዋጅ የተነገራቸው ስለሆነ ወታደሮቹ ሊገደሉ ችሏል ብሏል።

## በሐረርጌ የነበሩ የኢትዮጵያ አርበኞች

1ኛ. በከንዱዶ የነበሩ በፊታውራሪ በዳዶ የሚመሩ ሲሆኑ
2ኛ. በጋራሙለታ የነበሩ በፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ ናቸው።
3ኛ. በስተምዕራብ በጨርጨር የነበሩ በፊታውራሪ ግሊዮን የሚመሩ ናቸው፤
የ3ቱ የኢትዮጵያ አርበኞች ቡድኖች የወታደር ኃይል ብዛት ከ10 እስከ 15.000 መሆናቸውን ተገምቷል።

በኢጣሊያ በኩል ከተሰለፉት:-

1. የሊቢያ ዲቪዚዮን 1ኛ ሬጂመንት III - V ባታሊዮኖች
   3ኛ ሬጂመንት II - X "
   4ኛ ሬጂመንት VIII - IX "
2. ዓረብ ሶማል ቅይጥ ጦር 1ኛ ሬጂመንት I-III-VI "
   2ኛ ሬጂመንት II-IV-V "

3. ኤርትራውያን XLV ባታሊዮን ነበሩ፡፡

ከአጋዴን ጦር ግዳ ሸሽተው ወደ ሐረርጌ የተሰበሰቡ የኢትዮጵያ ወታደሮች በጣሊያኖች ግምት በድንጋጤና በፍርሐት የሚገኙ መስሏቸው ጦራቸው ወደ ባሌ ያበየን መርዕድ ጦር ወዳለበት ለማዝመት የመጀመሪያ እቅዳቸው ነበረ ፡፡ ሆኖም በጨርጨር ጋራሙለታና ኮንዱዶ የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ባደረጉዋቸው እንቅስቃሴዎች ራሳቸው ጣሊያኖች ተደናግጠው ወደ ባሌ ለመዝመት የመጀመሪያ ዕቅዳቸው ተይረው ወደ ባሰ ዘመቻ ክረምት ከመግባቱ በኋላ እስተላለፈው ሙሉ ኃይላቸው በሐረርጌ እንዲያውሉ ተገደዱ፡፡ ዕቅዳቸው ለማስቀየር ያስገደደዋቸው ሁኔታዎች 1ኛ ሜይ 13 ቀን 1936 በሐረርና ጅጅጋ መንገድ በአርበኞች የደረሰባቸው ጥቃት 2ኛ ሜይ 14 በቀርሳ በፊታውራሪ መንገሻ የሚመሩ አርበኞች በደረሰባቸው ጥቃት 3ኛ ሜይ 28 ከአርበኞች ጋራ የተደረጉ ግጭቶች 4ኛ በሚኢሶና አሰበ ተፈሪ መሐከል ባለው መንገድ በደረሰባቸው የደፈጣ ውጊያ ነበረ፡፡ በዚሁ መሠረት መላው ሐረርጌ በአደጋ የወደቀ መሆኑን ሊገነዘቡ ችሏል፡፡ ጁን ወር መጨረሻ በሶስት ቦታ የተከፈሉ በጨርጨር ጋራ ሙለታና ኮንዱዶ የተደራጁ የኢትዮጵያ ወታደሮች መኖራቸውን ተገነዘቡ፡፡ በዚሁ መሠረት ጣሊያኖች ዓብዱላ ኮንዱዶ የሰፈሩት የኢትዮጵያ አርበኞች ለመደምሰስ በ[illegible]ም ቢርና ኮምቦልቻ መሐከል 4 ባታሊዮኖች አሰፈሩ፤ ጋራሙለታ የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ለመደምሰስ በቃር አካባቢ 4 ባታሊዮኖች መድበው አሰፈሩ፡፡ እንደዚሁም ጨርጨር የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ለመደምሰስ በቀርሳ 4 ባታሊዮኖች አስግሩ፡፡ ተጠባባቂ 2 የሊቢያ ባታሊዮኖችም ተመድበዋል፡፡

## ሀ/ ኮንዱዶ

ጣሊያኖች ሐረርጌን አደጋ ላይ እንድትወድቅ አድርገዋል ከተባሉ በአንዱ ቡድን በኮንዱዶ የሰፈረ የኢትዮጵያ አርበኞች ቡድኑ ላይ ዘመጀመር የዘመቻ ጥቃታቸውን ጀመሩ፡፡ የኮንዱዶ ውጊያ የቆየው ከአንድ ወር በላይ ከጁን 22 እስከ ኦገስት 29, 1936 ዓ.ም. አርበኞቹ ጁን 22-23-24-25 በተደረጉ ውጊያዎች ጉዳት ቢደርስባቸውም ንጉሡ ነጋሦት ይመለሳሉ የሚል ወሬ ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ሔዛው ከሚኖሩ የኢትዮጵያ ስደተኞች ዜና ያደርሳቸው ስለነበረ እንደገና ሊደራጁና ሊጠናከሩ ችሏል፡፡ ሲጋሬ እና ሞሊስ በተባሉ ቦታዎች አርበኞች እንደገና በተቋቋመበት ኦገስት 17 ቀን ውጊያዎች ተደርገው እንደገናም ጁላይ 21 ወደ ሲጋሬ ከሚያመሩ አርበኞች ጋራ ጣሊያኖች ውጊያ ስለገጠሙ ጉዳት ስላደረሰባቸው ሲጋሬም በጣሊያኖች እጅ ስለወደቀች በፊታውራሪ በሐይደ የሚመሩ አርበኞች ወደ ሰራርታ አፈግፍገው ሲሰፍሩ ብዙዎቹ ለጣሊያኖች እጃቸው ለመስጠት ተገደዱ፡፡ በዚሁ በሳረርታ አርበኞች ከመሸጉበት ለማስለቀቅ ከኮምቦልቻ 9ኛ የሊቢያ ባታሊዮን 6ኛ የሶማል ባታሊዮን ከሲጋሬ 3ኛ እና 4ኛ የሶማል ባታሊዮኖች እንደዚሁም ከሰሚን ዱባትና ሌሎች ባንዳዎች በማሰማራት ጁላይ 28 እና 29 የሰራርታ ከበባ ለማጠናቀቅ ጣሊያኖች ዕቅድ አውጥተው ነበረ፡፡ በፊታውራሪ በሐይደ የሚመሩ የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ከጣሊያኖች ወረራ በሌሊት እየተሰገሰጉ እምልጠው ጋራ ሙለታ ከሚገኙ አርበኞች ሊቀላቀሉ ችሏል፡፡[1]

[1] Governo Generale Stato Maggiore AOI. II Primo Anno dell' Impero VI testo p 64



## ለ. ጋራሙለታና ጨርጨር

ከአጋዴን ጦርነት በኋላ የተመለሰው የኢትዮጵያ ከራስ መኮንን ጊዜ ጀምሮ ወታደራዊ የተፈጥሮ ምሽግ አቀማመጥ ያለው በጋራሙለታ የሰፈሩ በፊታውራሪ ሽመልስ የሚመሩ ቁጥራቸው 4.000 የሚገመት ነበረ፡፡ በጨርጨር የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች በፊታውራሪ ግሊዮን የሚመሩ ነበረ፡፡ ጋራሙለታን ለመያዝ የተመደበው የኢጣሊያ ጦር 2 ሬጂመንት 4 ባታሊዮን ሊቢያውያን ነበሩ፤ አንድ ሬጂመንት ዓረብ ሶማል ወታደሮችም ተጠባባቂ ረዳት ከጨርጨር የመጡ ዓለመያ ሰፍረው ነበረ፡፡ ጁን 29, 1936 ውጊያው ተጀመረ፡፡ ጣሊያኖች በአርበኞች መሐከል ክፍፍል እንዲፈጠር ስላደረጉ፤ ፊታውራሪ ግሊዮን 1000 ወታደር አስከትሎ እጁን ለጣሊያኖች ሲሰጥ ከፊታውራሪ ሺመልስ ጦርም አንዳንዶቹ እጃቸው ሰለሰጡ ቁልቢ ጁላይ 6 በጣሊያኖች ተያዘች፤ ጁላይ 13 ጨለንቆ ተያዘ ጁላይ 21 ደደር በጣሊያኖች እጅ ወደቀ፤ ጁላይ 19 ጉራዋ ዋናው የአርበኞች ምሽግ ተያዘ፡፡ ፊታውራሪ ሽመልስ ሸሽቶ ወደ ምዕራባዊ ጨርጨር ሄደ፡፡ ጣሊያኖች ጋራሙለታ በሙሉ የተቆጣጠሩ መስሏቸው ነበረ፤ ነገር ግን ፊታውራሪ በሐደ 3000 ወታደሮች አሰባሰቦ ኦገስት 4 እና 5 በጣሊያ ጥቃት ሲጀምር በክረምት ኃይለኛነት ምክንያት ጣሊያኖች ሊዘምቱበት ስላልቻሉ ክረምት እስከሚያልቅ መጠበቅ ግድ ሆነባቸው፡፡ ፊታውራሪ በሐደና ሽመልስ ጣሊያኖች በክረምት መነቃነቅ አቅቷቸው በመቆማቸው በመጠቀም ጦር ሰፈሮችና ባቡር ሐዲዶች ላይ በጣሊያኖች በየጊዜው ጥቃት ከመፈጸማቸው በላይ ንጉሡ ሊመለስ ነው እያሉ ቅስቀሳ ያካሄዱ ነበር፡፡ በጉራዋ አሰሚያ ኩርፋቸሌ ደሉ የነበሩ የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮች ሴፕተምበር 11 ኦክቶበር 1 እና 2 ጥቃት ደርሶባቸዋል፤ በጋልዲቱ የነበረ ጦር ሰፈር ሴፕተምበር 6 እና 10 ኦክቶበር 1 እና 2 ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡ በኮንቮይ የሚጓዙ የኢጣሊያ መኪናዎች ላይ አርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃት አድርሰዋል ከሁሉ ከባድ የነበረው ሴፕተምበር 28 የተደረገው ጥቃት ባስከተለው 9 ሰዓት የቆየው ውጊያ ነበረ፡፡ ኦክቶበር መጀመሪያ ግን አርበኞች አቅማቸው እየታደከመ በመሄድ ላይ ይገኝ ነበር፡፡

## ሐ. በጨርጨር

1/ በቁልቢ ኦገስት 14 እና 20 ሴፕተምበር 27 አርበኞች ጥቃት ፈጽመዋል፤ 2/ አሰበ ተፈሪ ሴፕተምበር 26 3/ ጨለንቆ ሴፕተምበር 1-27-28 እና ኦክቶበር 2 4/ ዱር ኦገስት መጨረሻና ኦክቶበር 2 5/ ዋራቢሊ ሴፕተምበር 15 እና 16 6/ ቁኔ ኦገስት 30 7/ የኮንቮይ መኪናዎች ኦገስት መጨረሻ እንደዚሁም ሴፕተምበር 18 እና 20 አርበኞቹ ጥቃት አድርሰዋል፡፡ ኦክቶበር ወር የክረምት ዝናብ በመቀነሱ ጣሊያኖች ዘመቻቸውን በመጀመሩ የአርበኞች ኃይል እንዲዳከም አድርገዋል፡፡

ከሜይ እስከ ኦክቶበር በተደረጉ ውጊያዎች በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት

| | ኮንዱዶ | ጋራሙለታ | ጨርጨር | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| የሞቱ ጣሊያኖች | 1 | 1 | 11 | 13 |
| የሞቱ ኢንዲጂኒ | 62 | 6 | 218 | 286 |
| የቆሰሉ ጣሊያኖች | - | 1 | 16 | 17 |
| የቆሰሉ ኢንዲጂኒ | 113 | 11 | 316 | 445 |
| | | | ጠቅላላ ድምር | 761 |

ከአርበኞች ወገን በጦር ሜዳ የተገደሉ 1303 ተማርከው የተረሸኑ 39።

## ለ. ሸዋና አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ሠራዊት መሪ በማጣቱ ጣሊያኖች ምንም ተቃውሞ ሳይገጥማቸው ከትግራይ አዲስ አበባ ሊገቡ ችሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ጣሊያኖች አዲስ አበባን መቆጣጠራቸው አሜን ብሎ እንዳልተቀበለው ራሳቸው ጣሊያኖች መስክረዋል። ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በሰሜን ሸዋ በባቡር ሐዲድ በምዕራብ አዲስ አበባ ወዲያውኑ ጣሊያኖችን ለመፋለም የአርበኞች እንቅስቃሴ የታየው ሁሉ ዓላማው ጣሊያኖችን ከአዲስ አበባ ለማስወጣት ነበረ[1]።

ከአዲስ አበባ ጣሊያኖችን ለማስለቀቅ አዲስ ፍልሚያ የጀመረው በትግራይ ተሸንፎ የተበታተነ የኢትዮጵያ ጦር እንደገና ተደራጅቶ አልነበረም፤ በኃይለሥላሴ ጊዜ ስጦርነት የከተት ጥሪ በቂ ቅስቀሳ ሳይደረግለት ስለቀረ በጦርነት ያልተሳተፈ አዲስ ኃይል ነበረ፣ የጦር መሪዎቹም ሁሉ አዲሶች ነበሩ። ኢትዮጵያ የተሸነፈችው በጦር መሣሪያ ብዛትና ዓይነት ማጣት ብቻ አልነበረም። እብዛኛው ኢትዮጵያ ለሽንፈት የተዳረገችው መሪ በማጣቷ ነው። ከማይጨው ሽንፈት በኋላ እስከ አዲስ አበባ ደጀን ጦር ባለማደራጀቱ ጣሊያኖች እየዘፈኑ አዲስ አበባ ሊገቡ ችሏል። የኢትዮጵያ ለጦርነት ማሰለፍ የምትችለውና የሚገባት የወታደር ብዛት ኢጣሊያ ከምታሰልፈው እኩል ወይንም የበለጠ መሆን ሲገባው ኢትዮጵያ ግን በወታደር ቁጥር ብዛትም ከኢጣሊያ ወታደሮች ቁጥር ግማሽ ብቻ ነበረ ያሰለፈችው። ይህ ሁኔታ ከአመራር ጉድለት ጋራ ተዳምሮ ኢትዮጵያ ለሽንፈት ዳርጓታል። ባንጻሩ ግን ይህ ሁኔታ ቢሟላ ኖሮ የጦር አሪዮፕላኖች የታንኮች ማነስ ሊተካው ይችል ነበር። እርስ በርሳቸው እስተባባሪና ገንዘብ ወዘተ.. ያልነበራቸው አርበኞች ከኃይለሥላሴ ዘመን የበለጠ በሕዝቡ ቅስቀሳ ያደርጉ እንደነበረ በባቡርና በመኪና መገናኛዎች እደጋ እየጣሉ ስንቅና ትጥቅ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ ችግር ፈጥረውባቸው እንደነበረ ጣሊያኖች መስክሮውላቸዋል።

# ሜይና ጁን ወራት 1936

ሀ/ ምዕራብ ጣሊያኖች በጥቂት የወታደር ጥበቃ በሰላም መኖር አልቻሉም የነበሩዋቸው ጦር ሰፈሮች ማጠናከር ወይንም መዝጋት ተገድደው ነበር፣ አንድ የኤርትራውያን ብረጌድ አስማርተው ነበረ።

ለ/ ባቡር ሐዲድ

ለጥበቃ የተሰማሩ የኢጣሊያ ነጭ ወታደሮች ነበሩ። ሜይ 16-20-22-23 ጣሊያኖች ከአርበኞች ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል።

ሐ/ ሰሜን ሸዋ

ከምዕራብና ከባቡር ሐዲድ የባሰ ሁኔታ አዲስ አበባ ከተያዘች አንድ ሳምንት ሳይሞላ የአርበኞች እንቅስቃሴ ይታይበት ነበር። ጣሊያኖች የወታደሮቻቸውና የንብረታቸው ደሕንነት ለመጠበቅ በሕዝቡ ጭፍጨፋ ያካሂዱ ነበር። በሚያዝያ ወር 1928 (1936) በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራ የኢትዮጵያ ጦር ተበታትኖ ወደ አዲስ አበባ የሚወስደው ገደላ ገደል ለመከላከያ የሚመች

(1) Governo Generale, AOI II ibd VI p 81



መንገድ ለጣሊያኖች የለቀቀላቸው፣ ሕዝቡም በሆታና በእልልታ ተቀበለን እያሉ ሲዝናኑበት የነበረ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ በግንቦት ወር በቂ ትጥቅ ያልነበራቸው አርበኞች በሚመላለሱ ጣሊያኖች ላይ በየቦታው ባቋቋሙት ጦር ሰፈራቸው ሳይቀር ጥቃት ይፈጽሙባቸው ነበር። ሜይ 11 ቀን ከደሴ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዝ አንድ የጦር አሪዮፕላን ንብረት የጫነ የመኪና ኮንቮይ ሜይ 13 ቀን ሮቢ ሲደርስ በሰላይ ጦር አረዮፕላኖች አርበኞች ጥቃት ሊፈጽሙብት ይጠባበቁት እንደነበረ ጣሊያኖች ስለደረሰበት ጉዞውን አቋርጦ ለመከላከያ በተጠንቀቅ እንዲቆም ተገዶ ከአዲስ አበባ በሜይ 19 ኃይለኛ አጃቢ ጦር ሲላክላት ብቻ ጉዞውን ሊቀጥል ችሏል። ከእሱ በፊት ያለው ሌላ ኮንቮይ ግን ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከባድ ጉዳት ደርሶበት ነበር[1]።

## ኮሮማሽ

ሜይ 22 ቀን ጣሊያኖች በኃይለሥላሴ ዘመን የጦር ሰፈር የነበረ ኮሮማሽ የተባለው ቦታ በሸና አካባቢ ለመያዝ በጀመሩብት ጊዜ ብርቱ ተቃውሞ ከአርበኞች ወገን ገጥሞዋቸው ነበረ፣ ጣሊያኖች ግን ብዙ ትግል ተቋቁመው ይዞታቸውን ሊያቆዩ ችሏል።

## የመንዲዳ ውጊያ

የኢትዮጵያ አርበኞች የበላይ ጠቅላይ አዛዥ ሳይኖራቸው ሃገራቸው በሀገር ፍቅር ተነሳስተው አዲስ አበባ በጠላት ከተያዘች ማግሥት ጀምሮ እንቅስቃሴያቸው በጣም አስገራሚ ነበረ። ሆኖም በመሐላቸው ጀግኖች እንደመኖራቸው መጠን ከሐዲዮች የእንቅስቃሴያቸው መረጃ ለጠላት የሚያስተላልፉ ነበራቸው። የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ ኃላፊ የነበረው ኮሎኔል ትራኪያ ዘደነባ፣ ዋዩ፣ ጨርቆስ የሰፈሩ አርበኞች በመንዲዳ የፈረንሳይ ሳዛሪስት ሚሲዮንን ለማጥቃት አርበኞች ሃሳብ እንዳላቸው ሜይ 3 ቀን መረጃ ይደርሰዋል። የአርበኞች ዓላማም የኢጣሊያ ወታደሮችን ለውጊያ በመጋበዝ ጥቃታቸው እስከ ደብረብርሃን ለመዝለቅ እንደነበረ መረጃ ይደርሰዋል። ኮሎኔሉ አርበኞች ሳይቀድሙት በመቅደም ሜይ 31 ቀን በአንድ ኮሎኔል የሚመሩ ሁለት ባታሊዮን ጦር ወደ መንዲዳ ይልካል፤ ከዚያም አርበኞ ወደ ሰፈሩበት ወደ ዋዩ ሄደው ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ይከፍታሉ።ጁን 2 ተጨማሪ ሌላ ኮሎኔል አንድ ባታሊዮን በመምራት ተልኮ በመንገድ ትኩስ ስለገጠመው በማግሥቱ ጁን 3 ብቻ ቦታው ሊደርስ ችሎዋል። ጁን 6 ጣሊያኖች ተልእኮዋቸውን ፈጽመው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ደብረብርሃን ሲመለሱ ሚሲዮናውያንም መንዲዳን ለቀው ወደ ደብረብርሃን መጡ። አርበኞች 1000 እግረኛ 400 ፈረሰኛ ተዋጊ ነበራቸው። በውጊያው በጣሊያኖች ግምት አርበኞች 100 ወታደር ሞተውባቸዋል። ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 4 የቆሰሉ 36 ነበሩ ሁሉም ኢንዲጀኒ።

(1) Governo Generale, AOI ibd VI Testo p 90

## የአንኮበር ውጊያ

የመንዲዳ ውጊያ በደብረብርሃን የነበረው የጣሊያኖች ጦር ሰፈር በአርበኞች ጥቃት እንዳይደርስበት አስወግዷል። ለጣሊያኖች የደረሱዋቸው መረጃዎች አርበኞች መንዲዳንና ደብረብርሃንን ከወረሩ በኋላ ወደ አንኮበር በማምራት እዛው የነበረ የጣሊያ ጦር አንስተኛ ስለነበረ የጦር ሰፈሩን ለመቆጣጠር እቅድ ነበራቸው። አሁንም ሳይቀደሙ የአንኮበር ጦር ሰፈራቸው ለማጠናከር አንድ ባታሊዮን ላኩ። ከዚህም በተጨማሪ ጁን 7 ሌላ ባታሊዮን በላኩበት ጊዜ 400 የተገመቱ የኢትዮጵያ አርበኞች በየመንገዱ ተኩስ ይከፍቱባቸው ስለነበር፣ በጦር አሬዮፕላን እየተረዱ እየተከላከሉ አንኮበር ሊገቡ ችሏል። አንኮበር በነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈርም ላይ በተደጋጋሚ ተኩስ ይከፈትበት ነበረ። በውጊያው አርበኞች 200 ሰዎች ሞቶባቸዋል። ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 11 የቆሰሉ 19 ነበሩ ሁሉም ኢንዲጂኒ።

## የሸዋ ወታደራዊ መከላከያ ኃይል

ለአዲስ አበባ የስንቅ አቅርቦት አሳሳቢነት በመገንዘብ ጣሊያኖች በብዙ የአስተዳደር ክልሎች ይታዘዙ የነበሩ የአዲስ አበባ ዙሪያ ክፍሎች ሰፋት ያለው መሬት የሚሸፍን የሸዋ መከላከያ ኃይል በሚል ስያሜ አቋቋሙ።

## በጁላይ ወር

ከጁን 2 ጀምሮ በክረምት ወራት ምክንያት ያልተያዙ መሬቶችን ለመቆጣጠር ማድረግ የነበረባቸው እንቅስቃሴ ስለተቋረጠ፣ ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል ብቻ ተወስነው ነበረ። በዚሁ መሠረት በሸበ የታጠሩ፣ ሙሉ ትጥቅና ስንቅ ያላቸው የመከላከያ ጦር ሰፈሮች በአዲስ አበባ ዙሪያ ለእያንዳንዱ ጦር ሰፈር አንድ ባታሊዮን በመመደብ ተቋቋሙ። ሆኖም ጁላይ 14 ቀን የሸዋ መከላከያ ልዩ እዝ ፈርሶ የአዲስ አበባ ጸጥታ ለመከላከል በማእከላዊ መንግሥት ስር እንዲሆን እንደገና ተዋቀረ።(1)

## ምዕራብ ሸዋ

በወሊሶ የነበረው የጦር ሰፈር ተጠናከረዋል። ጨሊሞ ሰፍሮ የነበረው የኤርትራ ባታሊዮን ለባንዳዎች ለቆ ወደ አዲስ ዓለም እንዲዛወር በመደረጉ፣ ባንዳዎች ከአምቦ ከመጡ አርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው፣ ጦር ሰፈሩ በአርበኞች እጅ ወድቀዋል። ሌሎች ወደ አዲስ ዓለም ለዝውውር ይጓዙ የነበሩ የኢጣሊያ አስካሪ ወታደሮች በመንገድ ተኩስ ተከፍቶባቸዋል።

## ወልመራ

ከወሊሶና አዲስ አበባ መሐከል ያለው መንገድ ጣሊያኖች 200 አርበኞች ታይቷል የሚል መረጃ ስለደረሰባቸው፣ ወሊሶ ጦር ሰፈር የነበረውና

(1) Governo Generale AOI ibd p 60



ከአዲስ አበባ የተላኩ ወታደሮች ጁላይ 24 በአርበኞች ላይ ተኩስ ከፍተው የተገደሉባቸውና የቆሰሉባቸው 18 ነበሩ ብሏል፣ ከአርበኞች ወገን የደረሰው ጉዳት አልተገለጸም።

## በባቡር ሐዲድ ውጊያዎች

በባቡር ሐዲድ አርበኞች አደጋ እንዳይጥሉ ለመከላከል ጣሊያኖች የታጠቁ ባቡሮች አቋቁመው ነበር። ጣሊያኖች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ቢያደርጉም አርበኞች አዲስ አበባ ለጣሊያኖች ስንቅና ትጥቅ እንዳይደርሱ ለማድረግ የሐዲድ ብሎኖችን እያወለቁ ይወስዱ ነበር፣ የስልክ ሽቦችን፣ የውሃ መስመሮችን ያቋርጡ ነበር። ጁላይ 6 አርበኞች ከሞጆ አቃቂ ያሉ ቦታዎች ሁሉ መገናኛዎች እንዲቋረጡ አድርገው በኢጣሊያ ወታደሮች ጦር ሰፈሮች ላይ ጥቃት ፈጸሙ። አድአ ላይ አንድ ባቡር ሐዲድ ወልቆ በመነሳቱ መንገዱን ስቶ ወጣ። በባቡር ውስጥ ከወታደሮች ሌላ ሲቪሎች ሴቶችና ሕፃናት ጣሊያኖች ነበሩ፣ አንድ ጀኔራልም ነበረ። አርበኞቹ ባቡሩን ከበው ተኩስ ከፈቱበት፣ ጣሊያኖች በጀኔራሉ እየተመሩ ተከላከሉ፣ ጣሊያኖች እርዳታ ስለደረሰላቸው ሊከላከሉ ችሏል። የአርበኞቹ ጥቃት ስለተቃለለ ማታ በ2 ሰዓት የተወሰኑ ጣሊያኖች ወደ አዲስ አበባ አመሩ ሌሊት በጭለማ የባቡር ሐዲድ ተከትለው ከሔዱ በኋላ መንገዱ ጠፋባቸው፣ ሊነጋ ዱከም ሲደርሱ በአርበኞች እንደተከበቡ አወቁ፣ ጉድጓድ ውስጥ ገብተው ለመከላከል ሞክረው ከሞት እንደማይተርፉ ስላወቁ እሊታቸው Viva Il Re Viva Il Duce እያሉ እንዲሞቱ ምክር ሰጣቸው። ከመስመር የወጣ ባቡሩን ለማንሳት ሐዲዱን ለመጠገን ከአዲስ አበባ የተላከ ሌላ ባቡር ጣሊያኖች የተገደሉበት ቦታ ዱከም ሲደርስ ባጋጣሚ አንድ ሸሽቶ ያመለጠ ጣሊያን እና አንድ በከባድ የቆሰለ ሌላ ጣሊያን ስላገኘ ከእነሱ ስለ ተገደሉ ሌሎች ጣሊያኖች ሁኔታ ታወቀ። በአድአ የተከበቡ ጣሊያኖች ከሞጆ እርዳታ ስለተላከላቸው ከአደጋ ሊድኑ ችሏል። የሞቱ ጣሊያኖች 4 የጦር መኰንኖች 64 ተራ ወታደሮች የቆሰሉ 3 የጦር መኰንኖች 34 ተራ ወታደሮች ነበሩ። በአድአ ጥቃት የፈጸሙ የኢትዮጵያ አርበኞች ቁጥራቸው 2000 እንደነበሩ ተገምቷል፣ መሪዎቻቸው ማን እንደነበሩ አልተገለጸም።

ቦታውን የሚጠብቁ ከድሬዳዋና ከአዲስ አበባ ተጨማሪ ወታደሮች ተልከዋል። ከድሬዳዋ የተላኩ ጁላይ 8 ከናዝሬት እንዳለፉ ሐዲዱ ተበላሽቶ ስላገኙት ከአርበኞችም ተኩስ ስለተከፈተባቸው ለ3 ሰዓት ከተታኰሱ በኋላ ወደ ናዝሬት መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል። በሌላ መጓጓዣ (በመኪና) በማግስቱ ጉዞዋቸውን ቀጥለዋል። ለማግሥቱ ከድሬዳዋ ሌላ ግማሽ ባታሊዮን ጦር ወደ ስፍራው ተላከ።

ከአዲስ አበባ ጁላይ 7 ሁለት ሻለቃ ወታደሮች ተላኩ፣ ነገር ግን መንገዱ ዝግ ሆኖ ስላገኙት አርበኞቹም ተኩስ ስለከፈቱባቸው ጉዞዋቸውን መቀጠል ሳይችሉ ቀርተው አቃቂ ሲደርሱ ቆሙ። ከሰዓት በኋላ ከአዲስ አበባ የተነሳ በጀነራል ጋሊና የሚመራ አልፏቸው በመሄድ ዱከም ሲደርስ የተገደሉ የጣሊያኖች ሬሳ አግኝቶ እንዲቀበሩ አድርጎ ጁላይ 8 ጉዞውን ወደ ሞጆ ከመቀጠሉ በፊት በ10 ኪሎ ሜትር ከመንገድ ገራና ቀኝ የሚገኙ መንደርተኞች ላይ ለጣሊያኖች ግድያ ተባብራችኋል በማለት የበቀል ጭፍጨፋ ፈጽሟል።

ጁላይ 9 ቀን የጦር አሬዮፕላኖች ከድሬዳዋና ከአዲስ አበባ እየተነሱ አርበኞች አሉበት የተባሉ ቦታዎችን በቦምብ ሲደበድቡ ውለዋል። ጁላይ 10

ጀኔራል ጋሊና ከሞጆ እስከ አዳማ ያለው ቦታ ሲያስስ ውሎዋል፡፡ ጁላይ 12 የባቡር ሐዲድ ተጠግኖ ሥራውን ቀጥለዋል፡፡ ጁላይ 13 ግራዚያኒ ጀኔራል ጋሊና በሕዝቡ ላይ ጭፍጨፋ በማድረጉ ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና ሲገልጽለት "ክቡር የመንግሥት መሪ እኔ በሰጠሁህ መመሪያ የእሱ ትእዛዝ አክብረህ ምንም ርህራሄ ሳታደርግ ሁሉን በውምብድና የተካፈሉ በማውደምህ አድናቆቱን ያቀርብልሃል፡፡ በዚሁ ተግባር ቀጥል፣ የባቡር ሐድዲ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአካባቢው የሚገኙ ሁሉ በማጥፋት ነው" የሚል ቴሌግራም በማስተላለፍ ነው፡፡ ጀኔራል ጋሊና ከአቃቂ አዳማ ያለው መሬት በሙሉ የበላይ ኃላፊ እንዲሆን ተሰጠው፡፡ ጀኔራል ጋሊና የሚያዛቸው 1482 ወታደሮች 492 የጋማ ከብቶች 41 ቀላልና ከባድ መትረየሶች 2 መድፎች ነበሩት፣ ሽፍቶች መሸገውበታል ወደ ተባለው ጁላይ 20 ቀን ከሞጆ ተነስቶ ወደ ደቦ ኪዳዮና ቦካን ተራራ አሰሳ ለማድረግ ሞከረ፤ ሆኖም ተኩስ ስለተከፈተበት በጨበጣ ውጊያ ብቻ በመንገዱ ለማለፍ ችሏል፣ የሸንኮራ ነዋሪዎች ሽፍቶች ተብለው ተጨፈጨፉ፡፡ ሌሊቱ በአካባቢው በአደረበት ጊዜ በሕዝቡ የሚደገፉ በአርበኞች ጥቃት ደረሰበት ጁላይ 21 በየረርና ቡልጋ ብዛት ያላቸው አርበኞች የሰፈሩ መሆናቸው መረጃ ስለደረሰው የተሰጠውም ተቀዳሚ ተግባር የባቡር ሐዲድ ፀጥታ ለማስከበር ብቻ በመሆኑ፣ ወደ የረርና ቡልጋ ለሌላ ጊዜ ይተላለፍ ብሎ ወደ ሞጆ ተመለሰ፣ የባቡር ሐዲድ በአደጋ ላይ ስለሚገኝ ወደ ሞጆ እንዲመለስ የሚል ትእዛዝም ደረሰው፡፡ እግረ መንገዱ ወደ ሞጆ ሲመለስ ከአርበኞች ጥቃት ይደርስበት ነበር፣ በጦር አሬዮፕላኖች እየተረዳ ብቻ እየተከላከለ ጁላይ 23 ወደ ሞጆ ሊመለስ ችሏል፡፡ የደረሰበት ጉዳት የሞቱ 4 የቆሰሉ 24 ነበሩ፡፡ ጣሊያኖች የባቡር ሐዲድ መስመር የተጠናከረ መከላከያ እንዲኖረው አደረጉ በየ 60 ኪሎ ሜትር አንድ ባታሊዮን ጦር እንዲመደብበት አደረጉ፡፡

## ሸዋ ሰሜን ምሥራቅ

በተደጋጋሚ አዲስ አበባ ከአርበኞች ጥቃት እንደሚደርስባትና እንደምትወረር የሚሉ ወሬዎች ይሰሙ ስለነበረ በኩሉኔል ትራኪያ የሚመሩ ሁለት ባታሊዮኖች ከሰሜን ሸዋ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ የዐመፁ መሪ ደጃዝማች አበራ እንደሆነም ተወርቷል፡፡ ዓላማቸውም በመጀመሪያ የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮች በቅርብና ሩቅ የሚገኙትን ማጥቃት ቀጥሎም ለጣሊያኖች እንቅስቃሴ የሚያግዳቸው የክርምት ወራት ወቅት በመጠቀም ዋና ከተማዋን መውረር ነበረ፡፡ በክረምት ጭቃ ምክንያት ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ ለጦር ሰፈሮች በቂ ስንቅ ሳይታደላቸው ለትራፊክ ዝግ ሆኖ ነበር፡፡ ጁላይ 4 ወደ ደብረብርሃን ይጓዝ የነበረው አንድ የኢጣሊያ ጦር ወርቁ ሚካኤል በተባለው ቦታ ከአርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው ስለተከበቡ ከበባውን ለማስለቀቅ ለእርዳታ ባለተሽከርካሪ ሌላ ባታሊዮን ወደ ስፍራው ሲላክ፣ የተከበበ ጦርም እርዳታ መላኩ ሲያውቅ ራሱ የከበቡትን አርበኞች ለማባረር ችሏል፡፡

ጁላይ 19 በሁሉ ጦር ሰፈሮች ጥቃት ከአርበኞች ይደርሳል ተብሎ እንደተወራ በተግባር ለማየል ተጀምሮ ነበር፡፡ በደብረብርሃን አካባቢ ሜሜ ወንዝ ላይ አርበኞች ተሰባስበው ስለታዩ የጦር አሬዮፕላኖች ባደረሱባቸው ጉዳት ብቻ ሊበታተኑ ችሏል፡፡ አርበኞች ጁላይ 19 እና 20 በአንኮበር ጦር ሰፈር ጥቃት ለማድረስ ሞከረው የኢጣሊያ ወታደሮች ስለተከላከሉ መልሰዋቸዋል፡፡ ጁላይ 20 ኮርማሽ ላይ የሚገኘው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር አርበኞች ወረው ለመያዝ ለ 3 ቀን የቆየው ተኩስ ተካሂዷል፡፡ የኢጣሊያ



ወታደሮች በመከላከል ድነዋል፡፡ አንኮበር የነበረው የኢጣሊያ ጦር ከጦር ሰፈሩ ወጥቶ በአካባቢው የነበረው የአርበኞች ተዋጊዎች ከቦ እልቂት ማድረስ ችሏል፡፡ በሸዋና ኮርማሽ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ግን ዕድሉ ብዙ አልቀናውም፣ በ2000 አርበኞች ከባድ ጥቃት ስለደረሰበት ጉዳት ደርሶበት ለማፈግፈግ ተገዶ ነበር፣ በጦር አሬዮፕላኖች እርዳታ ብቻ ለመከላከል ችሏል፡፡ ጁላይ 21 እና 22 5ኛ, 10ኛና 4ኛ ባታሊዮኖች ለእርዳታ ስለተላኩ ብቻ በአካባቢው ሰላም ሊሰፍን ችሏል፡፡ ወደ ስፍረው ተልከው የነበሩ መኪናዎች ግግሾቹ ተበላሽተው ግግሾቹ በጭቃ ተውጠው በመንገድ ቀሩ፣ የአርበኞች ጥቃትም በሸዋ ቀንሶ ወደ አዲስ አበባ ጥቃቱን በማተኮር ቀጠለ፡፡ በአርበኞች የደረሰው ጉዳት በጦር ሜዳ የሞቱ 709 ተማርከው የተገደሉ 110 በኮርማሽ ጦር ሰፈር ለተገደሉ ሙሶሊኒ ኒሻን ሰጥተዋል፡፡ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በሰሜን ሸዋ የተደረጉ የአርበኞች ጥቃት የጣሊያኖች ኃይል ከአዲስ አበባ ውጭ እንዲሰማሩ በማድረግ አዲስ አበባን ለመውረር የታለመ ነበረ፣ ለዚሁም ብዙ የአርበኞች መሪዎች ከደጃዝማች አበራ ካሣ ስምምነት ፈጥረው እንደነበረ ታውቋል፡፡ በጣሊያኖች በኩል የአርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃቶች ከመከላከል በስተቀር በአርበኞች ጥቃት ለመፈጸም ታግደው እንደነበረ አምነዋል፡፡ ሆኖም የተቃጡባቸው ጥቃቶች ሁሉ ለማክሸፍ ችለናል ብሏል፣ አርበኞች እና ደጋፊዮቻቸው ሲደመሰሱ፣ ታማኝ ሆነው ከጣሊያኖች ጉን የተሰለፉም ኒሻን አግኝቷል ብሏል፡፡ የዚህ ዓይነት ውጊዮዎች እንዳይከሰቱ ግራዚያኒ ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ በክረምት ወራት በሙሉ ለትራፊክ ዝግ እንዲሆን ትእዛዝ አስተላልፈዋል፣ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች በአጃቢዮች ብቻ እንዲጓዙ ተደርገዋል፡፡ የመኪና መንገድ በመቋረጡ የጦር አረዮፕላኖች ስንቅ ያመላልሱ ነበር፡፡

## የአዲስ አበባ የመከላከያ ሁኔታ

ዋናው እዝ የፒያሳ እዝ ይባላል፡፡ የመከላከያ ጣቢያዎችና ምሽጎች ተቋቁሟል፣ የማስጠንቀቂያ ደወሎች ተቋቁሟል፡፡ ከተማዋ ለ3 ተከፍላለች፣ እያንዳንዱ ክፍል ብዙ ንኡስ ክፍል አለው፡፡ ወደ ከተሟ በሚያስገቡ መንገዶች በየ 50-100 ኪሎ ሜትር የወታደር ሰፈር ተቋቁሟል፡፡ በከተማ ዙሪያ የጦር ሰፈሮችና ምሽጎች ተቋቁሟል፡፡ በከተሟ ዋና ክፍሎች የወታደር የመሰብሰብ የመከላከያ ጦር ተሰርቷል፡፡ ተንቀሳቃሽ የወታደር ኃይል በከተሟ በሙሉ ተመድበዋል፡፡ በከተማ ዙሪያ የተሰሩ የወታደር ሰፈሮች ባንድ ቦታ ብቻ መቀመጥ መወሰን የለባቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ገጠር እየሄዱ አሰሳ ማድረግ የመንግሥት ኃይል ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከተማዋ ለምሥራቅ፣ ምዕራብ ደቡብ ተብላ ነበረ የተከፈለችው የፖሊስ ኃይል መደበኛና ልዩ የፖሊስ ኃይል ነበረው፡፡ ልዩ የፖሊስ ኃይል የሚንቀሳቀሰው የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ ነበር፡፡ በከተሟ ዙሪያ በየ5-10 ኪሎ ሜትር የፖሊስ ኃይል ተቋቁሟል፡፡ የሙከራ ደወል እየተደወለ ልምምድ በየጊዜው ይደረግ ነበር፡፡ ለአማራ መንግሥት በአባይ በኩል ደጃዝማች አበራን ለማስፈራራት ጭምር ወደ አዲስ አበባ ወታደር ለመላክ ዝግጁ እንዲሆን ትእዛዝ ተሰጥቶታል፡፡ መድፎች በየቦታው በተጠንቀቅ ተተክለዋል፡፡ የአሬዮፕላን ማረፊያ እና ከእንግሊዝ ኤምባሲ በላይ በእንጦጦ መከላከያ ምሽጎች ተሰርቷል፡፡ ወደ አዲስ አበባ የሚያስገቡ መንገዶች ፍተሻ ያለማቋረጥ በፈረሰኞች ጭምር ይካሄድ ነበር፡፡ ከሐረር ታንኮች ወደ አዲስ አበባ እንዲላኩ ተደርገዋል፡፡ እንደዚሁም ተሸሬ ዲቪዚዮን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደርገዋል፡፡ በኩረምና ደሴ መሐል ቀርቶ የነበረ በጀኔራል ተሲቶሬ የሚመራ የላባውዳ ዲቪዚዮን 10.000

የወታደር ብዛት የነበረው ከሜይ 16 ጀምሮ እስከ ጁን 30 ድረስ ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ተደርገዋል። በየጊዜው ሰልፍ በማድረግ ሕዝቡ ኢጣሊያ ኃይለኛ የመከላከያ አቅም እንዳላት ለማሳየት ይደረግ ነበር። ጣሊያኖች የነበራቸው ዋና ስጋት አርበኞች በአንድ አዛዥ እንዳይጠቃለሉ ነበረ። በመጀመሪያ የጠረጠሩት ራስ እምሩ ነበረ፤ አሁን ደግሞ የሚጠረጥሩት ደጃዝማች አበራ ካሣ ነበረ። በዚሁ የተነሳ በክሊዲው ራስ ኃይሉ ተጠቅመው ደጃዝማች አበራ እንዲገደል አድርገዋል።

## የሙሉ ውጊያ

በእንጦጦ መስመር በሙሉ የሰፈሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ጁን 29,1936 ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡና በምትካቸው ባንዳ እንዲሰፍሩበት በማሰብ በቀረበው ሃሳብ ስለተስማሙበት ጁላይ 10 ወደ አዲስ አበባ ጉዞውን ሲጀምሩ ከጀርባውና ከጐኑ የደጃዝማች አበራ ካሣ ወታደሮች ናቸው የተባሉ ቁጥራቸው 500 (አምስት መቶ) የሚደርስ ወታደሮች በጣሊያኖች ላይ ተኩስ ከፈቱባቸው። ጣሊያኖች ቦታቸውን ይዘው ሙሉ ቀን ተታኰሱ፤ በማግስቱም ሙሉ ቀን ውጊያው ቀጥሎ ዋለ። አርበኞች ጥቃታቸው እየጨመረ ነበር፤ ማታ ግን በጭለማ ተጠቅመው ኃይለኛ ዝናብም ይጥል ስለነበረ ጣሊያኖች ከከበባው አምልጠው አዲስ አበባ ገቡ፤ ከአዲስ አበባም አንድ ባታሊዮን የኢንዲጂኒ ጦር ለእርዳታ ተልኮላቸው ነበር። በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የሞተ አንድ የጦር መኰንን 29 ወታደሮች የቆሰሉ 2 የጦር መኰንኖች 44 ወታደሮች የጠፉ 3 ከአርበኞች የሞቱ ከ300 እስከ 400 ተገምቷል።

## የአዲስ አበባ ውጊያ

በተቀነባበረ በብዙ አቅጣጫዎች አዲስ አበባን ወረው ለመያዝ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይወራ የነበረ ስላልተሳካ አሁን በአሬዮፕላን ግረፊያ ብቻ በደጃዝማች ባልቻ ለመጀመር ተዘጋጅቷል። ከአሬዮፕላን ጣቢያ የሚጠብቁ የኢጣሊያ ወታደሮች ከቦታው ለቀው ወደ ሌላ እንዲሰማሩ ለማድረግ ለጥቃታቸው እንዲመቻቸው የማስመሰል ጥቃት በባቡር ጣቢያ ለማድረግ ሞክረው እዛው ለጥበቃ የተሰማሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ስለከሸፈ እቅዳቸው ሳይሰራላቸው ቀርቷል።

ለጣሊያኖች በደረሱዋቸው መረጃዎች ደጃዝማች አበራ አዲስ ወታደሮችን በመመልመል ላይ እንደሚገኝ ወደ እንጦጦም እንደ ተጠጋ ያመለክታሉ። ከአዲስ ዓለም በስተሰሜን የረር አካባቢ፤ ሶዶ ጉራጌ፤ ቱሪ ዋጫጫ ተራራ፤ አቃቂ፤ ለገዳዲ ብዙ አርበኞች እንደሚገኙ የሚደርሱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከተማዋን ለማጥቃት የተዘጋጁ አርበኞች የሚከተሉ ናቸው። በሰሜን አበራና አስፋወሰን ካሣ ወንድማማቾች አፈንጉሥ እረጋኛ መስፍን ስለሺ ወዘተ.. ከምዕራብ አፈ ንጉሥ አጥናፌ ወልደጻድቅና ሌሎችም ከደቡብ ከዝቋላ ቀኛዝማች በቀለ ወልደገብርኤል ከምሥራቅ ከሸንኩራ ደጃዝማች ፍቅረማርያም ብጅሮንድ ለጥይበሉ ወዘተ የአርበኞች የሰው ብዛት ከ8 እስከ 10.000 ሺህ የሚገመቱ ነበሩ። ጋሻና አግራ ትራኔያቸው ትተው የተስማሙ ይመስላሉ። ደጃዝማች አበራ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ከውጭ ሀገሮች ወኪሎች የቀድሞ ኢምባሲዎች ግንኙነት ፈጥሮ ነበር። የአስጊ ሁኔታ ዜናዎች ይሰራጩ ነበር። የአርበኞች እቅድ በመሪ ደረጃ ይታወቅ ነበር። ደጃዝማች አበራ ከአዲስ አበባ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ምሥራቅ በሁለት አቅጣጫዎች



ጥቃት በመፈጸም ሁለቱ ወረራዎች በታላቁ ቤተመንግሥት ይገናኙ ነበር፤ ጥቂቶቹም በእንጦጦ ከኢጣሊያ ወታደሮች ውጊያ እያደረጉ ይቆዩ ነበር። አፈንጉሥ አጥናፌና ደጃዝማች ባልቻ ከመሚጫ ተራራና ከቱሪ የአሬዮፕላን ጣቢያ ወረው እንዲይዙ ተመድበው ነበር። ደጃዝማች ፍቅረማርያም ለዚሁ ተግባር ከምሥራቅና ከደቡብ ምሥራቅ ለእርዳታ ይሰማራ ነበር። ለጁላይ 20 እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ወረራ እርም ትብብር ባለማድረጋቸው ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ተደርጎ የክረምት ወቅት እስከሚገባ ጣሊያኖች መንቀሳቀስ በማይችሉበት ጊዜ፤ አሬዮፕላን ጣቢያ አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ ይጠባበቁ ነበር። ጁላይ 16 ግራዚያኒ በጀነራል ተሲቶሬ የሚመሩ አራት የኤርትራ ባታሊዮኖች በከተማዋ ዙሪያ ከሙሉ ትጥቃቸው እንዲሰማሩና ለጁላይ 20 ዝግጁ ሆነው እንዲቀመጡ ለጀነራል ተሲቶሬ ትእዛዝ ይሰጣል። በዚሁ ጁላይ 20 የኤርትራ ባታሊዮኖች በሰልፍ ሆነው በግራዚያኒ ተጐብኝቷል። የኤርትራ ባታሊዮኖች VII, VIII, XVI, XX የተባሉ አራት ነበሩ። የአዲስ አበባ መከላከያ ዝግጅት በግራዚያኒ አገላለጥ።

አዲስ አበባ መከላከያ ለሁለት ባለ አንድ ብሪጌድ ወይንም ለአራት ባለ አንድ ሬጂመንት የተከፈለ ነው። የአዲስ አበባ ዙሪያ በ9 ጦር ሰፈር ጣቢያዎች የታጠረ ነው። ለእያንዳንዱ ጣቢያ አንድ ባታሊዮን ጦር ተመድበዋል፤ በሽቦ ያልታጠረ አቃው በሙሉ ስላልደረሰ ነው። በተጨማሪ 4 ተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች አሉ።

### የአዲስ አበባ (ፒያማ) ጦር አዛዥ ስለ መከላከያ የሰጠው መግለጫ

1. አዲስ አበባን ለመከላከል አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ሀ/ የዙሪያ ስፋት (ርዝመት) ብዙ በመሆኑ (39 ኪሎ ሜትር) ለ/ ቦታው ሜካ በመሆኑ
2. አርበኞች ወደ ከተማ ሰርጎ እንዳይገቡ በተለይ በሌሊት ለመከላከል አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ከአንድ ወታደር ጣቢያን ወደ ሌላው ያለው ርቀት ከ3 እስከ 4 ኪሎ ሜትር ነው። ስለዚህ ከመንገድ ውጭ የሚገባና የሚወጣ ሰው ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ነው።
3. አርበኞች ሳይታዩ ተደብቀው ከመንገድ ውጭ ወደ ከተማዋ መግባት ይችላሉ።
4. የመከላከያ ጣቢያዎች ባሉበት ወደ ከተማ መግባት ከሞከሩ በመከላከያ ሠራዊት ተኩስ ያልቃሉ።

በሸዋና በባቡር ሐዲድ ያለው ሁኔታ ግራዚያኒ ጁላይ 22 ቀን በሚከተለው ቴሌግራም አብራርቶ ገልጾታል። ባለፉት ጥቂት ቀናት የአርበኞች (ሽፍቶች) እንቅስቃሴ ከባቡር ሐዲድ ወደ ደብረሲና ደብረብርሃን ሸዋ አዲስ አበባ መንገድ መስመር ተዛውረዋል። እንደዚሁም በአዲስ ዓለም ወሊታ መስመር አስጊ እንቅስቃሴ ታይቷል። ይህ ሁሉ ፕላን ከሐበሻ ሐንጎል የመነጨ አይመስልም። እቅዱ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉት የመከላከያ ጣቢያዎች ለማውደምና ከተማዋን ለመቆጣጠር ነው።

ከዚህ ቀጥሎ የዕለቱ ሁኔታ እገልጻለሁ፡-

1ኛ. መሐል አዲስ አበባ (ፒያማ) ምንም ነገር የለም።

2ኛ. ምዕራባዊ አዲስ አበባ በደረሱን መረጃዎች አፈ ንጉሥ አጥናፌ አዲስ ዓለምን ለማጥቃት ተንቀሳቅሰዋል። ለማገኘውም አስፈላጊ ጥንቃቄ አድርገናል።

3ኛ. ሰሜን ምሥራቅ ክፍል የኮርማሽ ጦር ሰፈር ትናንት ቀን 6 ጊዜ ከአርበኞች ጥቃት ደርሶበት 6ቱን ጊዜ ተከላክሎ መልሰዋል። የወታደሮች

እርዳታ ተልኮለታል ከ X ባታሊዮን፡፡ ወደ ምኒልክ ግቢ ገብተው የነበሩ ሽፍቶች (አርበኞች) እንዲባረሩ ተደርጎ ነበር፣ ተመልሰው ግን ቦታውን ተቆጣጥረውታል፡፡ ስንት የሜን ኮንቮይ ወደ ደብረብርሃን ያመራ የነበረ ዛሬ ተኩስ ተከፍቶበታል ቁጥራቸው 1000 ከሚደርሱ አርበኞች አጃቢዎች በሚገባ ተከላከለዋል፣ ሆኖም አሁንም በውጥረት ይገኛል፡፡ ከሸዋ የወታደር ኃይል እርዳታ ተልኮለታል፣ ሌላ የኤርትራ ባታሊዮን ባሬ ሌሊት በስፍራው ይደርሳል፡፡

4ኛ. ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ ጀነራል ጋሊና ከሸንኩራ ወደ ሞጆ በሚያመራበት ጊዜ ከአርበኞችና ከነዋሪዎች ገበሬዎች ተኩስ እየተከፈተበት ነበር፡፡ በተደረጉ ተኩሶች 5 አስካሪ ሞቷል 18 ቆስሏል፡፡ በየቦታው በገበሬዎች ላይ አስፈላጊው ቅጣት ተፈጽመዋል፡፡

5ኛ. ባቡር ሐዲድ አገልግሎት የታጠቁ ፋርጎኖች በመቋቋማቸው ስራው ቀጥሏል፣ በጂቡቲ 12 ሺህ ቶን ተከማችቷል፡፡

6ኛ. የጦር አሬዮፕላኖች የአየር ንብረትና የነዳጅ እጥረት ቢያጋጥማቸውም በምብ ከመጣልና ስንቅ ከማቀበል አላቋረጡም፡፡

መረጃዎች እንደሚደርሱን ከሆነ በጁላይ መጨረሻ ሳምንት አርበኞች በአዲስ አበባ ወረራ ይፈጽማሉ፡፡

ራስ ኃይሉ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ትናንት አንድ ደብዳቤ እንደደረሰው ደጃዝማች አበራ የአርበኞች እንቅስቃሴ መሪ መሆኑን አስተባብሎ በቅርብ ቀን ውስጥ እጁን ለጣሊያኖች እንደሚሰጥ ገልጿል፡፡ ትክክለኛ ሁኔታ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፣ ጊዜውን ጠብቀን ለማንኛውም ተዘጋጅተን እንገኛለን፡፡

ከተማዋን ከጠላት ለመከላከል ከተመደቡ 9 በዙሪያዋ የተቋቋሙ የወታደር ሰፈሮች ሌላ ተንቀሳቃሽ የፖሊስ ኃይል አደጋ ሲደርስ ደወል የሚያሰሙ ይኖራሉ፡፡ 50 አባላት ያላቸው በመኪና ሆነው ሌሊት በዋና ዋና መንገዶች ጥቃት ለደረሰበት ክፍል እርዳታ የሚሰጡ ይኖራሉ፡፡ የከተማ ዘበኞች የመሥሪያ ቤቶች ድርጅቶች ድንገት ጥቃት ቢደርሳቸው ራሳቸው መከላከል እንዲችሉ፡፡ ጁላይ 27 በቁጥር 217 (Allegati) በተደረገው ሪፖርት ሬጅም የወታደሮች አሰፋፈርና ዝርዝር ወጥቷል ወረራ በተፈጸመባቸው ቀናት ጁላይ 28-29-30 በተግባር በውጊያ ተካፋይ የነበሩ የኢርትራ ባታሊዮኖች VII VIII - XVI እና እንጦጦ ሰፍረው የነበሩ ባንዳዎች ብቻ ነበሩ፡፡

## ጁላይ 28 - 29- 30 ቀናት በአዲስ አበባ ከተማ

ከብዙ ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የአርበኞች አዲስ አበባን የመውረር ዘመቻ ጁላይ 28 ቀን ሟት ተጀመረ፡፡ ከበላይ በሰቀ መንገድና ጉጃም መስመር ጉለሌ መንገድ መሐል የአርበኞች ሰርጎ ገቦች ይታያሉ፡፡ በዚሁ ጊዜ አስቀድሞ ተዘጋጅቶ በተጠንቀቅ የነበረ ወታደር ቢንቀሳቀስም ግንባር ቀደም ሆኖ በተግባር በውጊያ ተዋናይ የነበረ ግን በጀነራል ተሲቶሬ (General Tessitore) የሚመራው VII እና VIII የኤርትራ ባታሊዮኖች እንደዚሁም በእንጦጦ የሰፈረው በኩሎኔል ዲ ማርቲኖ (Di Martino) የሚመራ ባንዳ ጦር ብቻ ነበረ፡፡ VII ተቃውሞ ሳያጋጥመው ሲጓዝ VIII ግን ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተበት፣ ሆኖም ብዙ ሳይቆዩ መሸሽ ጀመሩ፡፡ በሚሸሹበት ጊዜ ከእንጦጦ ከባንዳዎችና ከጣሊያኖች መድፈኛ ክፍል አርበኞች እልቂት ደረሰባቸው፡፡ በግምት እንደሚታየው የአርበኞች ቁጥር 4000 ነበረ፡፡ በዚሁ ዓይነት በምዕራብ ሰርገው ገብተው የነበሩ አርበኞች አበቃ፡፡ XVI ባታሊዮን ኢንዲጀኒ በራስ መኰንን ቤት እንዲሰፍር ተደርጎ የነበረ ከእነሱ ውስጥ ወደ ሾላ ሰአሰላ ፈረሰኞች



የተላኩ 300 የሚገመቱ አርበኞች አጋጥሟቸው ምንም ተኩስ ሳይከፍቱ ወደ ራስ ጌታቸው ቤት በጫካ ሲጓዙ በኦኪፒንቲ (Occhipinti) ከሚመራ ባንዳ ተጋጩ፡፡ በማግሥቱ ጁላይ 29 በደቡብ ምሥራቅ በራስ ጌታቸው ቤት አካባቢ ብዛት የነበራቸው አርበኞች ሰፍረውበት የነበረ ለመቋቋም VII እና VIII ባታሊዮን ኢንዲጀኒ ተሰማራ፡፡ በጫካ በተጠንቀቅ ሆነው ከነበሩ አርበኞች ሙሉ ቀን ውጊያ ሲካሄድ ዋለ፡፡ አርበኞች በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ ነበሩ፣ የኤርትራ VII እና VIII ባታሊዮኖች ከሩቅ በመድፍ እርዳታ የሚያደርጉላቸው ጣሊያኖች ነበሩዋቸው፡፡

በወለታና በሞጆ የሚገኙ የኢጣሊያ ጦሮች አስፈላጊ ከሆነ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ተነግሮዋቸው ነበር፡፡ ጀነራል ጋሊና የኤርትራውያን የሚያዝዝ ከሞጆ ወደ አቃቂ እንዲጠጋ ተደረገ፡፡ ጁላይ 29 ከሰዓት የአርበኞች ኃይል ሳላልተዳከመ በሰሜን በጀነራል ተሲቶሬ የሚመሩ የኢንዲጀኒ የኤርትራ ወታደሮች በደቡብ በጀነራል ጋሊና (General Gallina) የሚመሩ የኢንዲጀኒ የኤርትራ ወታደሮች በአርበኞች ላይ ተባብረው ጥቃት እንዲፈጽሙ ተደረጉ፡፡ ጁላይ 30 ሟት አርበኞችን በወጥመድ አስገብተው ለመፍጀት ነበር፡፡ አርበኞች ግን የጣሊያኖች ዓላማ ስለተረዱ ሌሊት ቦታውን ለቀ ሄዱ፣ ስለዚህ የኢጣሊያ ጦር ከቀኑ 5 ሰዓት ከበባው ፈጽመው በቀበና ወንዝ ሲገናኙ ማንም ጠላት አላገኙም፡፡ በእነዚሁ ቀናት ሁሉ የጦር አሬዮፕላኖች ተካፋይነ ታቸው የጉላ ነበረ፡፡

በጣሊያኖች የተገደሉ 3 ጣሊያኖች 16 አስካሪ የቆሰሉ 3 የጦር መኰንኖች 2 ተራ ወታደሮች 62 አስካሪ ነበሩ፡፡ የአዲስ አበባ ወረራ በዚሁ ዓይነት ከሸፈ፡፡ በዚሁ ጊዜ ነበረ አቡነ ጴጥሮስ ከወራሪዎች አርበኞች ተቀላቅለው የተያዙና ከሌሎች አርበኞች አንድ ላይ የጦር ፍ/ቤት ቀርቧል ተብሎ በመርካቶ ገበያ ላይ የተረሸኑ፡፡

ስለ አቡነ ጴጥሮስ መረሸን ግራዚያኒ ጁላይ 29 ለቅኝ ግዛት ሚኒስትር በሳብ ቴሌግራም ከቀኑ 11 ሰዓት ተኩል መረሸናቸውና ሕዝቡ በጭብጨባ ፍርዱን (ሀ)-እንደተቀበለው ገልጸዋል፡፡ በዚሁ ቀን Allegati 224 በላከው ሌላ ቴሌግራም አቡነ ጴጥሮስ በራስ ኃይሉ ተይዘው ወዲያውኑ ለመንግሥት አስረከቧቸው ከደጃዝማች አበራና አስፋወሰን ተባበሪ መሆናቸውን ተከሰው አምነው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት መረሸናቸውን ገልጧል፡፡ በAllegati ቁ 225 ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ከ4ቱ የኢትዮጵያ አቡኖች አንዱ የነበረው የአቡነ ጴጥሮስ መረሸሖ በሕዝቡ ድንጋጤ አሳድረዋል፤ ይኸም በማድረግ ያለው የኢጣሊያ ቆራጥ የፖለቲካ አመራር ነው ብሏል፡፡ ግራዚያኒ ጁላይ 31 ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም በጁን 2 እስከ ጁላይ 31 በሸዋ የሞቱና የቆሰሉ የጦር መኰንኖች 12 የቆሰሉ 9 የጠፉ አንድ፣ የኢጣሊያ ተራ ወታደር የሞቱ 71 (ሰባ አንድ) የቆሰሉ 70 የጠፉ 9፡፡ ኢንዲጀኒ የሞቱ 104 የቆሰሉ 277 የጠፉ 1፡፡

## የኦገስትና የሴፕተምበር ወር ውጊያዎች

ለራስ ኃይሉ በወለታ መንገድ አሰሳና በአጥፊዎች ላይ አስፈላጊ ቅጣት ለመስጠት መምሪያ ተሰጥቶታል፡፡ ኦገስት 2 VI ባታሊዮን ኢንዲጀኒ ከከተማዋ በስተሰሜን ለአሰሳ በተሰማራበት ጊዜ ከአንድ አነስተኛ የአርበኞች ቡድን ተጋጭቶ ሁለት ሰዓት የቆየ ውጊያ በኋላ አርበኞች 24 ተገደለባቸው ሸሽቷል፡፡ በዚሁ ጊዜ በአካባቢ መንደሮች ቤቶቹን በማቃጠል ቅጣት ፈጽሟል፡፡

ሕዝቡን ለማስፈራራት በከተማዋ የወታደራዊ ሰልፍ በየቀኑ ቀጥሏል፡፡ በከተማዋ ዙሪያ ያሉት የጦር ሰፈሮች ተጠናክረዋል፡፡ ይኸም ሆኖ በከተማዋ

ዙሪያ የአርበኞች ቡድኖች ሲዘዋወሩ ይታዩ ነበረ፡፡ በከተማዋ ደቡብ ምሥራቅ ደጃዝማች ባልቻ ሕዝቡን ይቀሰቅስ ነበረ፡፡ በአቃቂም በብጅርገድ ፍቅረሥላሴ የሚመሩ አርበኞች ይታዩ ነበር፡፡ ከመስቀል በዓል በፊት ጠቅላላ ጥቃት ይፈጸማል የሚል ፍራቻ በተግባር አልታየም፡፡

## በቁሪና በመጫጫ ተራራዎች አሰሳና ውጊያ

ኦገስት 26 ቀን VIII ባታሊዮን ኢንጂጂኒ ለአሰሳ ወደ ቁሪ ተራራ በተሰማሩበት ጊዜ 1000 የሚደርሱ የደጃዝማች ባልቻ ወታደሮች በተኩስ ስለተቀበሏቸው ውጊያ ተካሄደ፡፡ 1 የኢጣሊያ ጦር መኰንን ሲሞት 15 ኢንጂጂኒ ተገድለዋል፡፡ 40 ኢንጂጂኒም ስለቆሰሉባቸው ሸሽተው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ድር አሬዮፕላን ማረፊያ ለመመለስ ተገደዋል፡፡ እስከ ጦር ሰፈራቸው እያሳደዷቸው ይመጣሉ ብለው ፈርተው ነበር፡፡ ግራዚያኒ በማግስቱ ጄኔራል ጋሊና እንዲሁም ጄኔራል ተሲቶሬ ሰፈሩን በመድፍ ከደበደቡ በኋላ አሰሳ እንዲያካሂዱ አድርገዋል፡፡ ሴፕተምበር 1 ቀን ወደ ቁሪ ተራራ የጣሊያ ወታደሮች ለአሰሳ ሲሄዱ አነስተኛ ተኩስ ብቻ ነው ያጋጠማቸው፣ 2 ኢንጂጂኒ ብቻ የቆሰሉ ነበሩ፡፡

## ምዕራብ አዲስ አበባ

ምንም እንቅስቃሴ ባያሳዩም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ በአፈ ንጉሥ አጥናፌና በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች ሰፍረውበት ነበር፡፡ ጣሊያኖች በኦገስት ወር በኰሎኔል በሊ (Colonel Belly) አማካኝነት በአርበኞች ላይ አሰሳና ሕዝቡን በመሰብሰብ ሥራ ያካሄዱ ስለነበረ ወደ ጣሊያኖች የሚገቡ ሹማምንቶች ነበሩ፣ ሕዝቡም የኢጣሊያ ባንዲራ ይጠይቅ ነበር፡፡ በተለይ ብዛት ያለው ባንዳ በራስ ኃይሉ ተቋቁሞ በዚሁ መስመር ተሰማርቶ ነበር፡፡ ጣሊያኖች አምቦ ድረስ ቁጥጥራቸውን ለማስፋፋት ቢያስቡም የደጃዝማች ባልቻ አርበኞች ያሰጉዋቸው ስለነበረ በኦገስት ወር ወደፊት ለመሄድ አልደፈሩም ነበር፡፡ ሴፕተምበር 13 በግራዝማች ኃይለሥላሴ ተክሉ ባንዳዎች አማካኝነት በ200 የራስ ኃይሉ ባንዳዎች እየተረዱ ወደ ፊት በመግፋት በጡጫጫ ተራራ የደጃዝማች ባልቻ አርበኞችን ማጥቃት አካሄዱ፡፡ ደጃዝማች ባልቻም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋራ ሸሽቶ አመለጠ፡፡ ከአሰሳ መልስ ባንዳዎች በሜታ አቦ ሕዝብ ላይ ከአርበኞች ጋራ ስለተባበረ የበቀል እርምጃ ወሰዱባቸዋል፡፡ ሴፕተምበር 15 ኰሎኔል በሊ ከራስ ኃይሉ ባንዳዎች ጋራ በመሆን ወደ አዲስ ዓለም በልቶ በመሄድ ሕዝቡን ይሰብክ ነበረ፡፡ ሴፕተምበር 17 አፈ ንጉሥ አጥናፌ እጁን ለጣሊያኖች ሰጠ፡፡ ወደፊት ጉዞውን በመቀጠል የኰሎኔል በሊ ጦር ኦክቶበር 5 ከፍ ያለ አቀባበል ተደርጎለት አምቦ ገባ፡፡

## ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ ክፍል

ኦገስት 1 ቀን በአርባ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ጥቃት ይደርስበታል፡፡ ኦገስት 5 ከአዋሽ ወደ አንኮበር የሰፈረው የኢጣሊያ ወታደር ስንቅ ለማመላለስ ጭነቱ በግመሎች ሆኖ አጃቢ ወታደሮች ለመመደብ ታስቦ ነበር፡፡ ነገር ግን እቅዱ ብዙ ችግር ስላጋጠመው፣ የጦሩ አዛዥም ከቦታው ስንቅ ለማግኘት እቅድ ስላወጣ፣ ለወታደሮች የሚሰጠው ስንቅም በመቀነሱ ችግሩ ሊፈታ ችሏል፡፡

በባቡር ሐዲድ አነስተኛ ግጭቶች በየጊዜው ያጋጥሙ ነበር፣ በተለይ በመልካ ጂሉ ብዙ አርበኞች ነበሩ፡፡ ከአዋሽ እስከ አቃቂ ያለው መስመር ጥቃት ይደርስበታል የሚሉ መረጃዎች ይደርሱ ነበር፡፡

ጄኔራል ተሲቶሬ ከአዋሽ አንኮበር በግመሎች የሚጓጓዝ ስንቅ ለማጀብ የተሰጠው መመሪያ አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ትእዛዝ ሲሰጠው እግረ መንገዱ በባቡር ሐዲድ አካባቢ በሚገኘው ሕዝብ ላይ ሥነ ሥርዓት ለማስከበር ቅጣት እየሰጠ እንዲመጣ በተጨማሪም በቦታው ስንቅ ማግኘት ይቻል እንደሆነ ጥናት እንዲያደርግ መመሪያ ስለተሰጠው፣ በዚሁ መሠረት ኦገስት 15 ከመልካ ድሉ ተነስቶ 16 መታሐራ ገባ፡፡ ከአርበኞች ጋራ ተኩስ ያጋጠመው ነበረ፣ ከሁሉ የሚጠቀሰ ኦገስት 20 በፋንቲ የተደረገው ግጭት ነው፡፡

## ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

አዲስ አበባ ላይ የተደረገው ወረራ ከከሸፈ በኋላ በደጃዝማች አበራ ባደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ አርበኞች በሰላሌ፣ ዋዩ፣ መንዲዳና ኮርማሽ ጊዳዎች ሰፍረው ይገኙ ነበር፡፡ ሌሎችም አነስተኛ ቡድኖች ተጉለት፣ መንዝ፣ አንኮበርና ደብረሲና ሰፍረው ነበር፡፡ በተለይ ሸዋና ኮርማሽ አካባቢ የነበሩ አስጊ ነበሩ፡፡ እነዚህ ቡድኖችን ለመደምሰስ አስፈላጊ ነበረ፣ ሁልጊዜ በአየር ኃይል እየተረዱ ወታደሮች ሊያጠፏቸው ሞክረዋል፡ ያደረጉት በአርበኞች ላይ ዘመቻዎች የሚጠቀሱት በመርቆሪዮስ ኦገስት 24፣ እንጎለላ ኦገስት 25፣ በሙሽ ሸለቆ ሴፕተምበር 5፣ ደብረሲና ሴፕተምበር 5 እና 6 ናቸው፡፡

## የአርበኞች እቅድ

የአርበኞች ዓላማ አዲስ አበባን ለመያዝ ነው፡፡ በክረምት ወራት መያዝ ካልቻሉ ሳዘለዓለም የጣሊያኖች ባሪያ ሆነው እንደሚቀሩ እቅድ ነበራቸው፡፡[1]

ታክቲካቸው ግልጽ ነው፣ ወደ አዲስ አበባ የሚያመሩ የመገናኛ መንገዶች በማቋረጥ ከተማዋን ማገለል፡፡ በከተማ ዙሪያ የተሰሩ የጦር ሰፈሮችን ማውደም፡፡ ከተማዋን ወረው ነዋሪ ሕዝብ በጣሊያኖች ላይ እንዲነሳና ተባባሪያቸው ሆኖ እንዲያምፅ ማድረግ ነበረ፡፡ የዚሁ ዓይነት የጦር ስልት ግን ኢትዮጵያውያን ራሳቸው ሊያቅዱት የሚችሉ አይመስልም ነበረ፣ ከፍተኛ እንጉል ያላቸው የጦርነት ልምድ ያላቸው ሊዘጋጅ የሚችል እቅድ ነው፡፡ እቅዳቸው ግን በኢጣሊያ ወታደራዊ ችሎታ ከሸፎባቸዋል፣ ጣሊያኖች የአርበኞች ዓላማ በየቀኑ መረጃ ማግኘት በመቻላቸው የበላይነት አግኝቷል፡፡

## ሐ. ምዕራባዊ ሶማሊያ

### ግንቦት (ሜይ) በነገሌ የኢትዮጵያ አርበኞች ድል፡፡

ጣሊያኖች በዋናው ጦርነት ከከፍተኛ የጦር መኰንኖች ማንም የሞተ ወይንም የቆሰለ አልነበረም፡፡ አዲስ አበባ ከተያዘች 2 ሳምንት በኋላ ግን ሜይ

---

(1) Governo Generale AOI ibd Testo VI p 138

19, 1936 ከነገሌ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የነበረው ጀነራል በርጎንዞሊ (General Bergonzoli) አርበኞችን ለማዳን ባደረገው አሰሳ ባስከተለው ጦርነት ራሱ ጀነራሉ ተገድሰዋል፡፡ ጀነራሉ በአርበኞች ላይ በነበረው ንቀት በእብሪት ተነሳስቶ፣ ጦርነት እንዳይከፍት ከአለቃው ከግራዚያኒ የተሰጠውን ትእዛዝ በመጣስ፣ 9ኛ የዓረብ ሶማል ባታሊዮን ወታደሮችን በመምራት የደጃዝማች ገብረማርያም የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሰፈረበት ዘልቆ ሊገባ ከፊት ለፊትና ከጐን ሳያስበው ተኩስ ተከፍቶበት ከባድ ውጊያ ከተደረገ በኋላ ጀነራሉ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ትእዛዝ ቢሰጥም ባስጊ ሁኔታ ይገኝ ነበር፡፡ የኢጣሊያ ጦር ከባሰ አስከፊ ሁኔታ ሊድን የቻለው ከቦምብ ጣይ አሬዮፕላኖች ባገኘው እርዳታና በተላከለት ብረት ለበስ ጦር ከዋናው ጦር ሰፈሩ ከነገሌ እንዲገናኝ በመደረጉ ነው፡፡ በተደረገው ውጊያ 3 የኢጣሊያ ጦር መኮንኖች ተገድሏል፡፡ (አንድ ሻምበል 2 የመቶ አለቆች) 4 የረሰቡት ያልታወቀ /አንድ ሻምበል 2 የመቶ አለቆች አንድ ም/የመቶ አለቃ) 2 የቆሰሉ ከእነሱ አንዱ ራስ ጀነራሉ ነበረ፡፡ ጀነራሉ አስጊ ሁኔታ ስለነበረ ወደ ነገሌ ሆስፒታል ተወስዶ ተኝቷል፣ በቦታው ሌላ ጀነራል ተተክቷል፡፡ ኢንዲጂኒ የሞቱና የደረሰበት ያልታወቀ 121 የቆሰሉ 55 ነበሩ፡፡

## ሰኔ /ጁን/ 1. መጋ በጣሊያኖች እጅ መውደቅ

ጁን 25 ጣሊያኖች በብዙ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ባንዳዎች እየተረዱ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋራ ከፍተኛ መከላከያ ከገጠማቸው በኋላ መጋን ተቆጣጠረዋል በውጊያው ጣሊያኖች 2 ኢንዲጂኒ 4 ሞቷል፡፡ የቆሰሉ 5 የጦር መኮንኖች፣ 13 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች፣ 10 ኢንዲጂኒ ነበሩ፡፡

## 2. ጣሊያኖች ሞያሌን ተቆጣጠሩ

ሞያሌ ሰፍረው የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች 200 ብቻ ነበሩ፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጣሊያኖች መቋቋም ስለማይችሉ ነጭ ሰንደቅዓላማ በከተማዋ ተክለው የጣሊያኖች መምጣት ይጠባበቁ ነበር፣ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች ወደ ከተማዋ ሲገቡ ተኩስ ተከፍቶባቸዋል፡፡ ጁን 30 ሞያሌ በጣሊያኖች እጅ በወደቀች ዕለት በተደረገው ውጊያ 2 ሲሞቱ 6 ቆስሏል፡፡ ሁሉም ኢንዲጂኒ Allegato ቁ 143፣ ውጊያው የቆየው ለአንድ ሰዓት ነው፡፡

## 3. የጃባሲሬ ውጊያ

ጁን 16 ጃባሲሬን ለመያዝ አስቀድመው የተላኩ ባንዳዎች ነበሩ፣ ሆኖም ድንገተኛ አደጋ ለማድረስ ሲሞክሩ ኃይለኛ መከላከል ከአርበኞች ስለገጠማቸው ባንዳዎች ሸሽተው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡ ጣሊያኖች ለባንዳዎች እርዳታ ቢመጡም አርበኞቹ ከበው ሊደመስሱዋቸው ሞክረው ነበር፣ ሆኖም ብዙ መትረየስ የነበራቸው ሌሎች ጣሊያኖች ስለመጡላቸው ከከበባ ቢድኑም፣ አሁንም አርበኞች አዲስ የመጣባቸው ጦርም ከበው ለመደምሰስ ሞክረው ነበረ፣ ጣሊያኖች መልሰው ማጥቃት ቢሞክሩም የአርበኞቹ ግፊት ለማቆም አቅቷቸው ነበር፡፡ በኋላ ግን ጣሊያኖች ከባድ መድፎችን አስመጥተው ስለተጠቀሙ ሉተነዘበ ጣሊያኖች መውጫ ስለከፈተላቸው ጣሊያኖች ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ችሏል፣ ከአዲስ ያዞታቸው ጣሊያኖች አዲስ መልሶ ማጥቃት አካሂደው አርበኞችን ሊያባርሩ ችሏል፡፡





ሲልቪያ ፓንክኸርስት ለኢትዮጵያ ነፃነት ተሟጋች በቢሮዋቸው ውስጥ እንዳሉ።

በተደረገው ውጊያ አንድ የኢጣሊያ የመቶ አለቃ ሉፖ (Lupo) ዘጁን 16 የተገደለ ጁን 17 አስክሬኑ ተገኝቷል። 24 ዓረብ ሶማል አስካሪና ዱባት ተገድለዋል፤ 33 ቆስሏል፤ 10 ጠፍቷል። ውጊያ የቆየው ለ 8 ሰዓት ነበረ። Allegati ቁ 227, 258, 259። ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋራ ከዱተኞች ኤርትራውያን ተቀላቅለውባቸው ነበረ። Allegati 258

## የሴፕተምበር ወር ሁኔታዎች

በዋቤ ሸበሌ (ጀስትር) ጣሊያኖች ብዙ ተቃዋሚ አላጋጠማቸውም። በፖለቲካ ቅስቀሳ በኩል ቆንስል ሆኖ አርሲ በነበረው ሻለቃ አጎስቲኖ /Mqggiore Agostino/ ተጠቅሟል። እንደዚሁም በውትድርና ባንዳ ጋናለ ዶሪያ 2 ባንዳ ባለ 3 ባንዳ ጀስትር ብለው አቋቁመው በሰየሟቸው ባንዳዎች ተጠቅሟል። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ የነበሩዋት ቆንስላዎች በምን ዓይነት ሰዎች ይመሩ እንደነበሩና ምን ዓይነት ስራ ያከናውኑ እንደነበሩ ለመረዳት እንችላለን። በሴፕተምበር ወር ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ አርበኞች አዲስ አበባ ትወረራለች የሚል ወሬ ይናፈስ ስለነበረ ግራዚያኒ ሴፕተምበር 1 ቀን 1936 ለጀኔራል ሳንቲኒ Santini የሶማሊያ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደርና ለጀኔራል ጀሎዞ Geloso የጋላና ሲዳማ መንግሥት አስተዳዳሪ ስለዚሁ ጉዳይ Allgati ቁ 291 ቴሌግራም ሰልኮ ግልባጭም ለአማራ ክልላዊ መንግሥት አስተዳዳሪ ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ Pirzio - Biroli ለሐረር ክልላዊ መንግሥት አገዥ ጀኔራል ናዚ General Nasi እንደዚሁም ለኤርትራ ክልላዊ መንግሥት አስተዳዳሪ ጉዞኒ Guzzoni አስተላልፎ ነበር። ባስተላለፈው በዚሁ ቴሌግራም በባሌና በሲዳሞ የሚገኙ በየነ መርዕድ ገብረማርያም ለጣሊያኖች እጃቸውን ለመስጠት እንደሌላቸውና በአዲስ አበባ ላይ በሚደረገው ወረራ እንደሚካፈሉ ተደጋጋሚ ወሬ ስለሚሰማ ይኸንን አውቀው በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ነው። ንጉሡም በቅርብ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ መሆኑን፤ ብዛት ያለው ጦር ራስ እምሩ በወለጋ ሰፍሮ እንደሚገኝ፤ ራስ ጌታቸውና ደጃዝማች መኩንን ከካይሮ ወደ ጎሬ እየመሩ መሆናቸውን ስለሚወራ በሸዋ ያሉት የቀድሞ መንግሥት ሹማምንቶች እንደ አበራ ካሣ የመሳሰሉ እጃቸውን ለጣሊያኖች ለመስጠት ሃሳብ የነበራቸው በሚነፍሱ ወሬዎች ተወናብደው እጃቸውን ከመስጠት እንዲቆጠቡ እንዳደረጋቸው ይገልጻል። ስለዚህ 1ኛ ሶማሊያ የሚገኘው አየር ኃይል ወደ አዲስ አበባ የሚወስዱ መንገዶች እንዲቆጣጠር 2ኛ ጀኔራል ጀሎዞ ከአርበኞች ጋራ ግንኙነቱ እንዳያቋርጥ፤ ምናልባት ወደ ሰሜን የሚያመሩ ከሆነ በስተጀርባቸው እንዲወጋቸው። 3ኛ ጀኔራል ናዚ ከአርሲ ከሶማሊያ ወደ ባሌ ወታደራዊ ዘመቻ እንደሚካሄድ ቀደም ብሎ በታቀደው መሠረት ዝግጅቱን እንዲያፋጥን የአማራ ክልላዊ መንግሥትም ለወደፊት ወደ ምዕራብ ወደ ወለጋ የሚደረገው ዘመቻ ተካፋይ እንደሚሆን በማለት ለሁሉም መመሪያ አስተላልፈዋል።

## መ. የአማራ ክልላዊ መንግሥት

ጣሊያኖች ሲገቡ በላስታ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ የሰፈረበት በስተቀር ተቃውሞ አላጋጠመንም ብሏል። ሌላ ቦታ አርበኞች አሉበት እየተባለ ሲወራለት የነበረ ወረኢሉ ነበረ። እንደተባለውም ኦገስት 20 አርበኞቹ በጣሊያኖች ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሞክረው በቦታው የሰፈረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ተባርረው 81 ሞቶባቸዋል፤ ከነመሣሪያቸው የተማረኩ አርበኞች



ተረሸነዋል። በአማራ ክልላዊ መንግሥት ጣሊያኖች በየቦታው ባንዳዎች አሰልጥነው አሰማርተዋል። ስለ ወረኢሉ ውጊያ ግራዚያኒ ዝርዝር ሁኔታ ባስተላለፈው ቴሌግራም ከጣሊያን ወገን 1 አስካሪ ሲሞት 11 ቆስሏል ከእነሱም 3 በከባድ የቆሰሉ ነበረ። በውጊያው ከጣሊያኖች ጎን ተካፋይ ከነበሩ የአካባቢ ነዋሪዎች 6 ተገድለዋል። 18 ቆስሏል። ከአርበኞቹ 81 በጦር ሜዳ ሲገደሉ የተማረኩ 8 አርበኞች 4 በወረኢሉ 4 በደሴ በስቅላት ተገድለዋል ብሏል Allegato ቁ 269

## ላስታና ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ፀረ ኢጣሊያ አዝማዝ እንቅስቃሴ የተካሄደበት በላስታ ነበረ። በደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ አማካኝነት ከጁን ወር ጀምሮ ደጃዝማች ወንድወሰን በይፋ ለጣሊያኖች እጁ እንደሰጠ ነበረ የሚታወቀው Allegato 104. ይሁን እንጂ በተግባር ሕዝቡ ፀረ ጣሊያኖች ለዓመፅ ለማነሳሳት ቅስቀሳ ያደርግ ነበረ፤ ወደ ጣሊያኖች እንዲቀርብ የተደረገለት ጥሪም በሽታ ምክንያት እየፈጠረ አልቀረበም። ጣሊያኖችም የበሽታም ሰባብ በማድረግ በዚሁ በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በማሰብ አንድ ሐኪም ከሰቆጣ ወደ ሙጃ እንዲላክለት ሲፈቅዱ ደብዳቤም እንዲላክለት ይወስናሉ። ከሚላከው ሐኪም ብዛት ያላቸው ከነ ሙሉ ትጥቃቸው የኤርትራ አስካሪና የላስታ ባንዳ አብረው ይሄዳሉ Allegato 235 ደጃዝማች ወንድወሰን ግን ከላሊበላ ለቆ ሄዶ ነበረ። በኦክቶበር ወር ብቻ ጣሊያኖች በደጃዝማች ወንድወሰን ላይ መውሰድ ስላለበት እርምጃ 9 ጊዜ ደብዳቤዎች እርስ በርሳቸው ተለዋውጠዋል (12-7-18-21-24-29-30) በላስታ ባንዳና በነዋሪ ሕዝብ መሐል ግጭት ስለተፈጠረ ሻለቃ ካፋሮ (Maggiore Cafaro) የኤርትራ 24ኛ ባታሊዮን በሙሉ ይዞ ከሰቆጣ ወደ ላሊበላ እንዲሄድ ትእዛዝ ይሰጠዋል። ኦገስት 24 ከሰቆጣ ተነስቶ ሻለቃ ካፋሮ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ወደ ላሊበላ በመሄድ ፋንታ ኦገስት 27 ሌላ የደጃዝማች ወንድወሰን ተባባሪ ኃይሉ ከበደ ከቦ ለመያዝ ሞክሮ ነበረ። በኋላ ግን ኦገስት 29 ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ከበባውን አምልጦ ሸሽቶ ስለጠፋ ሻለቃ ካፋሮ ጉዞውን ወደ ላሊበላ ቀጥለዋል። ሰፕተምበር 7 ቀን የኢጣሊያ ጦር ሰፈር በላሊበላ የ24ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ 450 ወታደሮች በድንገት በአርበኞች ይከበባል። በሻለቃ ካፋሮ የሚመሩ የ24ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን ላይም ከአርበኞች ጥቃት ይፈጸምባቸዋል። ጥቃት የተፈጸመባቸው ሁለቱ ቡድኖች በራድዮ ግንኙነት የነበራቸው የጦር አረዮፕላኖች ስንቅ ትጥቅ በመላክ በቦምብም አርበኞችን በመደብደብ እርዳታ ጠይቀው ነበር። ደጃዝማች ወልደሥላሴ የተባለው የኢጣሊያ ባንዳ መሪ ሰፕተምበር 8 ሻለቃ ኡጎሊኒ (Maggiore Ugolini) ባዘዘው መሠረት 300 ባንዳዎች በመምራት ከሰቆጣ ወደ ቢልባላ ጊዮርጊስ ያመራል። ከአሥመራና ከመቀሌ የሚነሱ የጦር አረዮፕላኖች ሰፕተምበር 8 ስንቅና ትጥቅ በማቀበልና የቦምብ ድብደባ ሲያደርጉ ውለዋል። ከሰዓት በኋላ አርበኞቹ ኃይለኛ በቢልባላ ጊዮርጊስ በተከበበ የኢጣሊያ ባታሊዮን ላይ ጥቃት ፈጽመው ውጤት አላገኙም። ከአርበኞቹ ጋራ የኤርትራ አስካሪ ከዳተኞች ይገኙባቸው ነበር። ኦክቶበር 9 አርበኞች እንደገና በቢልበላ ጊዮርጊስ ላይ ጥቃት ፈጽሟል፤ ይህ ጥቃት ግን ለመሸሽ እንዲመቻቸው ያደረጉት ይመስል ነበር። አርበኞች በአሬዮርላን ጉዳት ስለደረሰባቸው ተበታትነው ደጃዝማች ወንድወሰንም አምልጦ ከደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ለመገናኘት ወደ ትክዜ ሄዷል። ሻለቃ ኡጎሊኒ ከደብረታቦር፤ ደጃዝማች ወልደሥላሴና ሌሎች ባንዳዎች በተጨማሪም 25ኛው የኢጣሊያ ኢንዲጂኒ ባታሊዮን እንደዚሁም በመኪና የሚጓዙ ባለጥቁር ሸሚዝ (ፋሺስት) የኢጣሊያ ወታደሮች ከሞራ

ፀለምቲ ደጃዝማች ወንድወሰንን ለመያዝ ተሰማርቷል በተለይ በአርበኞች ላይና ደጋፊ በተባለው ሕዝብ ላይ በአሬዮፕላን የሚደርሰው ጉዳት አስከፊ ነበረ፡፡ የደጃዝማች ወንድወሰን ሁኔታ ያባብሰው የነበረ ነዋሪዎች የአሬዮፕላን ድብደባ በመፍራት በመንደራቸው ለማስጠጋት አይፈልጉም ነበረ፡፡ በሰፕተምበር ወር መጨረሻ ደጃዝማች ወደ ጣሊያኖች ለመምጣት እንዲፈቀድለትና ይቅርታ እንዲደረግለት በማለት ደብዳቤ ለሻለቃ ኡጎሊኒ ይጽፋል፡፡ ወዲያውኑ ወደ ደብረ ታቦር በመምጣት እጅ እንዲሰጥና ምህረት ተደርጎለት ወደ አዲስ አበባ የሚላክ መሆኑን የሚል መልስ ይላክለታል፡፡ ደጃዝማች ግን አልቀረበም፣ ምክንያቱም በወቅቱ ንጉሡ በእንግሊዞች እየተረዳ ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ነው የሚል ዜና ይናፈስ ነበር፡፡ በሰፕተምበር ወርም ስለ ደጃዝማች ወንድወሰን ጉዳይ ጣሊያኖች እርስ በርሳቸው 17 ቴሌግራሞች ተለዋውጧል፡፡

## የግራዚያኒ ደብዳቤ ለደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ

እንደምን አለህ፣ እኛ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን ታመህ ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ እንደቀረህ ሰምተናል በቶሎ ድነህ እንደምትመጣ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ የጠራንህ ልንተዋወቅህ ፈልገን ነው፣ እንደዚሁም ያንተ እዚህ መምጣት ወንድሞችህ አበራና አስፋወሰን ለመንግሥት እጃቸው እንዲሰጡ ለማደፋፈር ይረዳ ይሆናል ብለን በማሰብ ነበረ፡፡ እኛ አንተ እንድትረዳልን የምንፈልገው የሚነፍሱ ወሬዎች ሐሰት መሆናቸውና እግዚአብሔር ከፈቀደው ማንም ሊለውጠው እንደማይችል ነው፡፡ ለሌሎች እጃቸውን ለሚሰጡ ሁሉ እንደምናደርገው ጥሩ አቀባበል አዘጋጅተንልህ ነበር፡፡ ራስ ሥዩም ከእኛ ደብዳቤ ጋራ አንድ ደብዳቤ ጽፎልሃል፡፡ ስለ እኛ በጎ አስተሳሰብ ዋስትና ሊሰጥህ ይችላል፡፡ ስለዚህ ምንም መፍራት የለብህም፡፡ ያንተ ወላዋይነት ወደ አዲስ አበባ መምጣት በሽታ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በእኛ አለመተማመን እንዳለህ ጥርጣሬ አድሮብናል፡፡ ወንድሞችህ መንግሥትን እጅ ለመንሳት ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጡ ነግረውናል፡፡ አንተም ብትገኝ የቤተሰቦችህ ታማኝነት ተረጋግጦ ለሁላችሁ የሚጠቅም ነበር፡፡

አዲስ አበባ ሰፕተምበር 2 ቀን 1936 ዓ.ም. Allegato 292

ሰፕተምበር 8 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ በተደረው ውጊያ 3 ጣሊያኖች ቆስሏል፤ ኤርትራውያን የሞቱ 2 የቆሰሉ 11፡፡ ከአርበኞች ጋራ የተሰለፉ የድሮ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ነበሩባቸው፡፡ Allegato N 306 ሰፕተምበር 9 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ በተደረገው ውጊያ የሞቱ 2 የቆሰሉ ከኤርትራውያን የሞቱ 10 የቆሰሉ 16፡፡ በላሊበላ የተደረገው ውጊያ ኤርትራውያን የሞቱ 5 የቆሰሉ 2፡፡ የላስታ ባንዳ 2 ሲሞቱ 8 ቆስሏል፡፡ ጠቅላላ ድምር 46 Allegato ቁ 307 ሻለቃ ካፋሮ ሰፕተምበር 11 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ መንደር አካባቢ የነበሩ መንደሮች በሙሉ አቃጥሏል፤ የተማረኩ አርበኞችም በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል፡፡ Allegato ቁ 312፡፡

ከሰፕተምበር 14 ቀን ጀምሮ በሸፈቱ መንደሮች ላይና በአርበኞች ላይ የበቀል እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆናቸውን በአሬዮፕላን የተበተኑ በራሪ ወረቀቶች አማካኝነት ጭምር ተገልጸዋል፡፡ Allegato ቁ 315፡፡ ደጃዝማች ወንድወሰን ሰፕተምበር 30 ቀን ለሻለቃ ኡጎሊኒ በላከው ደብዳቤ እጁን ለመስጠት እንደሚፈልግና ይቅርታ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግሥት አገኘ በሰጠው መልስ፣ ይቅርታ እንድንሰጥህ ከፈለግህ፡፡ 1ኛ ወዲያውኑ እጅህ እንድትሰጥ 2ኛ አስካሪ ከዳተኞች እንድታስረክብ 3ኛ በላስታ የሚገኙ መሣሪያዎች እንዲያስታውቅ የሚጠይቁ ቅድመ ሁኔታዎች በማቅረብ ነው፡፡ ግራዚያኒ ግን ከአማራ ክልላዊ መንግሥት ኃላፊ ለተላከለት ቴሌግራም



ደጃዝማች እንዲያሟላ የተሰጡት ቅድመ ሁኔታዎች ውድቅ በማድረግ ከደጃዝማች ወንድወሰን የሚጠየቀው ቅድመ ሁኔታ ቶሎ ብሎ እጁን እንዲሰጥና ወደ አዲስ አበባ በአሬዮፕላን እንዲመጣ ፈቃደኛ እንዲሆን ብቻ ነው በማለት አሻሽሎለታል፡፡

በሁሉ አካባቢ የሚደረጉ ውጊያዎች በሙሉ ለመጥቀስ አስቸጋሪ ነው፡፡ በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ ጁላይ 20, 21, 22, 23 በኮሎኔል ትራኪያ የሚመሩ ጣሊያኖች በአርበኞችና በሕዝቡ የፈጸሙት ጭፍጨፋ የሚጠቀስ ነው፡፡ በተባሉት ቀናት ውጊያዎች ከተካሄዱ በኋላ ጁላይ 24 እና 25 ውጊያዎች ጋብ ሲሉ ጣሊያኖች ሰላማዊ ሰዎችን መቅጣት ይጀምራሉ፣ 50 የተማረኩ አርበኞችም ተረሽነዋል፣ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ 1000 ከብቶች ተዘርፈው ለነበራቸው የስንቅ እጥረት ተጠቅመውባቸዋል፣ 100(አንድ መቶ) አሰሳ ሲያደርጉ የያገኟቸው ሰላማዊ ሰዎች ሰላይ፣ ከዳተኛ ፣ መሣሪያ ይዞዋል በሚል ሰበብ ተረሽነዋል በውጊያ የተገደሉ አርበኞችም 709 ነበሩ ብሏል፡፡ ከጣሊያኖች 2 ም/መቶ አለቆች ተገድሏል፣ አንድ ሻምበል፣ አንድ ም/የመቶ አለቃ፣ 3 ባለ ጥቁር ሸሚዝ ወታደሮች 2 ሹፌሮች ጣሊያኖች፡፡ ከኢንዲጂኒ ኤርትራውያን የሞቱና የቆሰሉ 63 ነበሩ፡፡ Allegato N 214 ጀነራል ትራኪያ ሪፖርት እንዳደረገው፡፡ በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ በኮሎኔል ጂኖ ፑቺ ዳ ፊሊካያ Colonel Gino Pucci Da Filicaya የአንድ ባታሊዮን አዛዥ የሚመሩ ጣሊያኖች ባደረጉት አሰሳ በአንድ መንደር ቁጥራቸው ያልተገለጠ ሰዎች ተረሽነዋል ብሏል፤ በሌላ መንደርም ቤቶችን ለማቃጠልና የተያዙ መንደርተኞች ለመግደል አንድ ሰዓት ጊዜ ፈጀብን ይላል፤ የተቃጠሉ ቤቶች ቁጥጥርና የተረሸኑ የሰው ብዛት አልተገለጠም፡፡ በሌላ መንደርም ሩፋ በሚባለው ወንዝ አካባቢ ብዙ ቤቶች ተቃጥሏል፣ 50 ሰዎች ተገድሏል፣ ብዙ ከብቶች ተዘርፈዋል፡፡ በአሰሳ ዘመቻ ወደ ጦር ሰፈራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከነበሩዋቸው መኪናዎች 37 በየመንገዱ ለመተው ተገደዋል፡፡ እግረመንገዳቸው፣ በጣሊያኖች ላይ ተኩስ ከፍተው ነበረ ተብለው የተጠረጠሩ የመንደሮች ቤቶች ሁሉ አቃጥለዋል፣ 1000 ከብቶች፣ በሬዎች፣ በጎች፣ ፈረሶች፣ በቅሎች ተዘርፈዋል፡፡ Allegato ቁ 216

ይህ ሁሉ ለወደፊቱም በኢትዮጵያውያን ላይ ተሸንፈው እስከ ወጡ ድረስ የሚፈጽሙት ወንጀል ትክክለኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው፡፡ የኖም በወንጀላቸው አልተጠየቁም፣ እንደ በጎ አድራጊዎች ተቆጥረው ነው ከሀገራችን የወጡ ጣሊያኖች በክረምት ወራት ጭቃ ምክንያት እንዲሁም አርበኞች በሚያደርሱባቸው የማያቋርጥ ጥቃት በሰሜን ሸዋ ለወታደሮቻቸው ስንቅ ለማቀበል ችግር ስለነበራቸው ከሕዝቡ እየዘረፉ ለምግባቸው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ለወታደሮቻቸው የሚሰጣቸው ምግብም ለመቀነስ ተገድደው ነበር፡፡ የምግብ ቅነሳ በሚያደርጉበት ጊዜ ግን ለጣሊያኖችና ለኤርትራውያን እኩል አልነበረም፡፡ የራሲዮናቸውም እንደሚከተለው ነበረ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ፎርኖ ዱቄት ተጨማሪ | ለጣሊያኖች 400 ግራም | ለኤርትራውያን 300 ግራም |
| 2 | ፎርኖ ዱቄት | 100 ግራም ፓስታ ካልተሰጣቸው | X |
| 3 | ሩዝ በፓስታ ፋንታ | 150 ግራም | X |
| 4 | ዕንጨት | 1500 | 1000 |
| 5 | ስኳር | 25 | 40 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ሻይ | X | 15 |
| 7 | ቡና ጨው | 20 | X |
| 8 | ጨው | | 15 |

አስካሪ እንጀራ ስለሚመርጡ በቀን 1000 ራሲዮን ፎርኖ ዱቄት መቆጠብ ተችሏል፡፡ ነሐሴ 26 1946 በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች ከወሚሜ ተራራ ወደ አዲስ አበባ የድር አሬዮፕላን ማረፊያ ሲያመሩ ስለታዩ፣ ከጣሊያኖች ጋራ ውጊያ ፈተረው፣ ከጣሊያኖች ወገን 15 አስካሪ ሲሞቱ 40 ቆስሏል፡፡

# ከክረምት ወራት በኋላ የኢጣሊያ 2ኛ ዙር ዘመቻ ያልተያዙ የምዕራብና የደቡብ ክፍላተሀገሮች ለመቆጣጠር

በዋናው ጦርነት ጊዜ እንደተከሰተው አሁንም አርበኞች የሰው ብዛት አልነበራቸውም፡፡በጣሊያኖች ግምት ወደ ምዕራብና ደቡብ ክፍለተሀገሮች ዘመቻ ለማድረግ በሚዘጋጁበት ጊዜ ቁጥራቸው ከ30.000 አይበልጡም ነበር፡፡ የኢጣሊያ ሠራዊት ግን 339.000 የወታደር ብዛት ነበረ፡፡ ከእነሱ ውስጥም 249.000[1] ኢንዲጄኒ 90.000 ጣሊያኖች ነበሩ፡፡




## በየወሩ የተከናወኑ ውጊያዎች

### ኦክቶበር ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

ዋናው ዓላማ የመኪና መንገዱን ለመጠበቅ ነበረ፡፡የባቡር ሐዲድን ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል በ3 ጀነራሎች የሚመሩ ጀነራል ማሪዮቲ ጋሊና ተሲቶሬ (Mariotti, Gallina Tessitore) ወታደሮች ተሰማርተው ነበረ፡፡ በደቦኪዲዮ 3ቱ ጀነራሎች በ3 አቅጣጫ ባደረጉት ዘመቻ ኦክቶበር 26 ታዋቂ የአርበኞች መሪ የነበረው ደጃዝማች ፍቅረማርያም ተከበው ሊገደሉ ችሏል፡፡

በምዕራብ በኰሎኔል በሊ የሚመራው ጦር ኦክቶበር 4 ቀን አምቦ ገብተዋል፣ ኦክቶበር 16 በኰሎኔል በይትሮኪ የሚመራ ቡድን በአሬዮፕላን የለቀምት አሬዮፕላን ማረፊያ በናያ አርፈዋል፣ ባንዳ ለማቋቋም ሙከራ አድርገዋል፡፡ 1ኛ ብረጌድ ኦክቶበር 12 ከአዲስ አበባ ተነስቶ ኦክቶበር 24 ለቀምት ገብቷል፡፡

[1] Governo Generale A.O.I ibd testo VII p 14



ሐረር የጋራሙለታ ጨርጨር ከአርበኞች ለማጽዳት ተሞክረዋል ወደ ባሌና አርሲ ለመዝመትም ዝግጅት ተጠናቅቀዋል፡፡
ሲዳማ ኦክቶበር 2 የአየር ድብደባ በጀባሴረ ተፈጽመዋል፡፡
አማራ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣን ለመያዝ ከደብረታቦር ከደሴ ከላሊበላ በ3 አቅጣጫ ወደ ተከዘ ዘምተው ከዘው እንዲይዙ ተዘጋጅቷል፡፡

## ኖቬምበር ወር

ዘሸዋና ዘቡር ሐዲድ ብዙ አነስተኛ ግጭቶች ከአርበኞች ጋራ ይከሰቱ ነበር፡፡
በምዕራብ ኖቬምበር 5 በኰሎኔል ፕሪንቺቫለ (Colonel Princivalle) የሚመራ ጦር በአንድ እስላም ባለበት እየተመራ ከአዲስ አበባ ወደ ጂማ ለመሄድ ተነስቷል፣ ሌላ ጦር በጀኔራል ተሲቶሬ የሚመራ ወደ ለቀምት ለመሄድ ኖቬምበር 6 ከአዲስ አበባ ተነስቷል ኖቬምበር 11 በኰሎኔል ማልታ የሚመራ ጦር ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ጊምቢ ተነስቷል፡፡ ሌላ ቡድን የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች እየተረዳ በአሬዮፕላን ወደ ሰዩ ተጉዘዋል፡፡ ሌላ ጦር በሚላኖ የሚመራ ኖቬምበር 16 ከአዲስ አበባ ተነስቶ (X ብርጌድ) ወደ ለቀምት አምርቷል ራስ እምሩን ለመያዝ ኖቬምበር 24 በኰሎኔል ሚላኖ የሚመራ ጦር ከለቀምት በወለጋ ባንዳ እየተረዳ ወደ ጂማ አምርቷል፡፡
የሐይቆች ቀጠና በጀነራል ጀሎዞ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ሰሜን ለመግፋት ያደረገው እንቅስቃሴ በራስ ደስታ ኃይሎች ስለታገደ፣ ሰርዳታ በሻለቃ ቱቺ (Tucci) የሚመራ ጣሊያኖች የትግሬዎች ባንዳ ያካባቸው ራስ ደስታ በሰተጀርባው ለመውጋት ግራዚያኒ አሰማሩ፡፡
ሐረር የባሌ ዲቪዚዮን ጨርጨርን ከአርበኞች ለማጽዳት ቀጥሎ የፊታውራሪ በለዩ ኃይሎች ለመክበብ ሞክሮ እንዲበታተኑ አድርገዋል፡፡
አማራ በደጃዝማች ወንድወሰን ላይ ከበባው እየተጠናከረ ነበረ፣ ከደሴ ወደ ደባ ለመግለቅ ዓላማ የነበረው ከኰሎኔል ቶሴቲ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር ከአርበኞች ከባድ ውጊያ ሰላጋጠመው ወደ መጣበት እንዲመለስ ተገዷል፡፡

## ዲሰምበር ወር

ሸዋ ጣሊያኖች ፊቼን ተቆጣጥረዋል ዓላማው የራስ ካሣ ልጆች አበራና አስፋወሰንን ለመያዝ ነበረ፡፡ በአምስት አቅጣጫ ብጀነራሎችና በኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በትራኪያ ጋሬሊ ናታሌ ኮስታ Tracchia Garelli Belly Natale - Costa የሚባሉ ዲሰምበር 21 ከበው ከማረኳቸው በኋላ ከዳተኞች ሸፍቶች ተብለው በጥይት ተገድለዋል፡፡
<u>ምዕራብ ሸዋና ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ</u>፡፡ በጀነራል ማሪዮቲ የሚመራ የኢጣሊያ ጦር ተልእኮ ቢቾን ለመያዝ ነበረ፡፡
<u>የራስ እምሩ መያዝ</u>፡፡ በ 3 ጀነራሎችና ኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ማልታ፣ተሲቶሬ፣ ፕሪንቺቫለ የተባሉ ዲሰምበር 11 ደጃዝማች ታዬ ጉሉላቴ ተያዘ፣ ዲሰምበር 12 ቢተወደድ ወልደጻዲቅ ተያዘ ዲሰምበር 15 ራስ እምሩ ተያዙ፡፡ ዲሰምበር በአሬዮፕላን የተላኩ 100 ሰው ብዛት ያላቸው ወታደሮች ጋምቤላን ተቆጣጠሩ፡፡ ከአማራ የተላኩ ሌሎች ወታደሮች ዲሰምበር 24 ቤን ሻንጉልን ተቆጣጠሩ፡፡
<u>ሐይቆች</u> ዲሰምበር 1 ቀን ይርጋዓለም ተያዘች
<u>ሐረር</u> ወደ አርሲ ለመዝመት ተጀምረዋል፡፡

አማራ ሌሎች ተጨማሪ ወታደሮች በማሰማራት በተከዜ የነበረ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ ዲሰምበር 10 ተይዞ ተረሽነዋል፡፡

## ጀነዋሪ ወር

<u>ሸዋ</u> ሰላሌን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ቀጥለዋል፡፡ ምሥራቅ ሰሜን ሸዋ በአርበኞች የታመሰች ስለነበረ ጣሊያኖች ብዙ ወታደሮች አሰማርተው ከመንዲዳ በስተሰሜን እምብርትራ በተባለው ቦታ ሰፍረው ከነበሩ በአበበ አረጋይ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሟል፡፡ ሸዋ ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ በአርበኞች አሰሳ ቀጥሏል፡፡
<u>ምዕራብ</u> የክፍለ ሀገሩ አውራጃዎች የመቆጣጠር ቀጥለዋል፡፡
ቤንሻንጉል ዲሰምበር 31 አሶሳ ተያዘች፡፡
ሐይቆች ራስ ደስታ እጅን ለጣሊያኖች እንዲሰጥ የተደረገው ሙከራ ስለከሸፈ ከጋላና ሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሁለት ጀነራሎች ከአርሲ የተውጣጡ ባንዳዎች ከአዲስ አበባ የተላኩ የትግራይ ባንዳዎች የተከፈሰቡት ራስ ደስታን ለመያዝ በግራዚያኒ ራሱ የሚመራ ዘመቻ ተካሄደ ራስ ደስታ ደጃዝማች ገብረማሪያምና በየነ መርዕድ ሁለት ጊዜ ከተከበቡ በኋላ ሁለት ጊዜ ለማምለጥ ችሏል፡፡
<u>ሐረር</u> የሊቢያ ዲቪዚዮን አዋሽ፣ ሚኤሶ፣ አዳማ በሰፈሩ አርበኞች አሰሳ አካሄዷል፡፡ XL የአማራ XX የኤርትራ XXX VIII የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች ወሩ በሙሉ ምዕራባዊ አርሲ ለመቆጣጠር ተሰማርቷል፡፡
<u>አማራ</u> በሸፍትነት የተሰማሩ ለመደምሰስ ተባባሪ ሕዝቡን ለመቅጣት የጣሊያኖች አሰሳ ቀጥሏል፡፡ ከሁሉ የሚጠቀሱ በባሌል ደስታና በወብነህ ተሰማ የሚመሩ አርበኞች ላይ በአም ሐጀር ጉንደር መንገድ የተደረጉ ውጊያዎች ናቸው፡፡

## <u>ፌብሩዋሪ ወር</u>

<u>በአሰልቱ ሸዋ አጠገብ</u> ፌብሩዋሪ 15 በግርማ ስንቡ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ጣሊያኖች ውጊያ አካሄዷል፡፡ በመገር ከታዋቂው በአርበኞች መሪ ኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ አርበኞች ጋራ ፌብሩዋሪ 10, 15 እና 18 ጣሊያኖች ውጊያ አካሄዷል፣ ከነበረው ቦታ ለቆ ወደ ሙሉ እንዲሄድ አድርገውታል፡፡ በተጉለት በጀነራል ትራኪያ የሚመሩ የኢጣሊያ ጦር አርበኞች ጋራ በጣርማበርና አምባ በተርጌ ላይ፣ ፌብሩዋሪ 24 ውጊያ አድርገው አርበኞች ወደ ዘንደጉርና ሰላ ድንጋይ አፈግፍገዋል፡፡
<u>ባቡር ሐዲድ</u> በአርበኞች ላይ አሰሳ አላቋረጠም፡፡
<u>አዲስ አበባ</u> በግራዚያኒ ላይ ፌብሩዋሪ 19 (የካቲት 12) ከውጭ በመጡ ሰዎች አማካኝነት ነው የተባለለት የመግደል ሙከራ ተፈጽመዋል፡፡ ሁኔታው የኢጣሊያ ርእዮተ ዓለምና ጽንሰ ሐሳብ ባላባቶችና የቀድሞ ሹማምንቶች እንዲቀበሉ አስተማማኝ የመሳብና የማዋሐድ ይደረግ የነበረ መልካም ሥራ ለአንድ አፍታ እንዲስተጓጉል አድርገዋል፡፡
<u>ምዕራብ ጋላና ሲዳማ</u>፡፡ ከቦታው የተውጣጡ ባንዳዎች ተቋቁመዋል፣ ከአረበኞች ጋራ ውጊያ አካሄዷል፡፡
<u>ሐይቆችና ጉራጌ</u>፡፡ ጣሊያኖች ከብዙ የአርበኞች ቡድኖች ጋራ ውጊያ ገጥሟል፡፡ ፊታውራሪ ሺመልስ በዎባኒ ተራራ ሰፍሮ ስለነበረ ፌብሩዋሪ 1 ከሻሸመኔ ጦር



ተልኮበት ከባድ ውጊያ ተደርጎዋል፡፡ ከብዙ ትግልና ክትትል በኋላ ፊታውራሪ ሺመልስ ደጃዝማች ገብረማርያምና ራስ ደስታ (ፌብሩዋሪ 24) ተገድለዋል፡፡
<u>ሐረር</u> ብዙ አነስተኛ ግጭቶች ከአርበኞች ቡድኖች ጋራ
<u>አማራ</u> በአም ሐጀር ጉንደር መንገድ አሰሳ ቀጥሏል፡፡

## <u>የማርች ወር</u>

<u>ሸዋ</u>፡፡ ጀነራል ትራኪያ ማርች 1 ጉር ሥላሴ 10 ሰላ ድንጋይ ተቆጣጥረዋል በመገር 21 ከኃይለማርያም ማሞ ጋራ ውጊያ ተካሄዷል፡፡ በእንሳሮ አሰሳ ተካሄዷል፡፡ 28 በአደባይ በአበበ አረጋይ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ተካሄዷል፡፡
<u>ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድና ጉራጌ</u>፡፡ ከባቡር ሐዲድ ዝዋይ ወልቂጤ ወዙተ ኤርትራውያንና ዓረብ ሶማል ባሉበት ሰሬ አሰሳና ትጥቅ ማስፈታት አካሄዷል፡፡
<u>ጋላ ሲዳማ</u>፡፡ ሰሬ አሰሳ ተካሄዷል፡፡ ማርች 19 አርበኞችን አባርረው ጣሊያኖች ማጂን ተቆጣጠሩ፡፡ ማርች 31 ቀን ከአርበኞች ጋራ ውጊያ አካሄዶ ኩሉን ተቆጣጠረ፡፡
<u>ሐረር</u> ታማኖ በተባለው ቦታ ማርች 2 ጣሊያኖች ከአርበኞች ጋራ ውጊያ አካሄዷል፡፡ ከዚሁ ውጊያ በኋላ ብዙ አርበኞች ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ተሰዷል፣ ብዙ እጃቸው ሰጥቷል፡፡
<u>አማራ</u> አንቶ በተባለው ቦታ ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ አሰሳ ተካሄዷል፡፡
<u>ኤርትራ</u> ዐሰሬ ዘባር በተባሉ ቦታዎች (ትግራይ) ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ አሰሳ አካሄዷል፡፡

## <u>አፕሪል ወር</u>

<u>ሸዋ</u>፡፡ በአባዳይ የነበሩ አርበኞች በጣሊያኖች አፕሪል 4 ጥቃት ተሰንዝሮባቸው ከ5 እስከ 11 ጣሊያኖች አሰሳ ሲያካሄዱ ሰነበቱ፣ በእንሳሮ አንደዚሁ፣ 19 እና 20 ወደ ፍቼ በሚመለሱበት ግን ከአርበኞች ተኩስ ስለተከፈተባቸው የአንኮበር አካባቢ ነዋሪዎች መግረፍን ለማስረከብ ስላልፈለጉ ቅጣት ደርሶባቸዋል፡፡
<u>ያጋላና ሲዳማ</u>፡፡ ከልል በኩሉ ኮንታ ጋርዱላ አሰሳው ቀጥሏል፡፡
<u>ሐረር</u> 1000 የፊታውራሪ በሐደ አርበኞች ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ አምርቷል፣ ተሰደዋል፡፡ XXX VIII ባታሊዮን ይከታተሏቸው ስለነበር ዘሁድን ተከትፍለዋል፡፡ ፊታውራሪ በኮንዱዶ ይገኝ የነበረ ሶማሊላንድ እንዳይገባ ለመከልከል አንድ ባታሊዮን ተልኮለታል፡፡ በጋራሙለታ የቀሩት አርበኞችን ለማደን አንድ ባታሊዮን ተመድበዋል፡፡ XXX VIII ዓረብ ሶማል ባታሊዮን አርበኞችን ይከታተል የነበረ ከከባድ ውጊያ በኋላ አርበኞች እንዲበታተኑ አድርገዋቸዋል፡፡ ብዙ አርበኞች በሐደ ያለበት ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ለመግባት ችሏል፡፡
<u>አማራ</u> ሰሬ አሰሳ በአርማጭሆ አካባቢ ተደርጎዋል፡፡

# የ 7 ወሮች ከክረምት በኋላ ክንውኖች በዝርዝር

በአጭሩ በየወሩ የተገለጹ ክንውኖች በቀጠና በመከፈል በዝርዝር ይቀርባሉ ቀጠናዎች የሚከተሉት ናቸው። ሀ/ ሸዋ ለ/ ባሁር ሐዲድ ሐ/ አግሬ መ/ምዕራብ ሰ/ሐይቆች ረ/ ጨርጨርና አርሲ ሠ/ባሌ ቀ/ ሰሜ

## ሀ. ሸዋ

ሸዋ ዋና ፀረ ኢጣሊያ ትግ አገዛዝ ማእከል ሆኖ ነበር፤ በተደጋጋሚ ጣሊያኖች አርበኞችን ለመደምሰስ ቢሞክሩም አልቻሉም። የአርበኞች ቁጥር በጣሊያኖች ግምት ከ9 እስከ 10,000 የሚደርስ ነበረ፤ በቡድን የተከፈሉ ነበረ።

1ኛ. በራስ ካሣ ልጆች የሚመሩ በሰላሌ
2ኛ. ከአዲስ አበባ አዲስ ዓለም መንገድ በፊታውራሪ ዘውዴ አስፋው የሚመራ።
3ኛ. በደብረብርሃን አካባቢ በአበበ አረጋይ የሚመራ፤ የዚሁ ክፍል እስከ ደብረሲና ይደርስ ነበረ
4ኛ. ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ እስከ ባቡር ሐዲድ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ ነበሩ።

የኢጣሊያ አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር።
1ኛ. የዋናው ከተማ ጥበቃ ቡድን
2ኛ. ምሥራቅ ሰሜን ደሴ አዲስ አበባ መንገድ ጥበቃ ቡድን በጄነራል ማሪዮቲ (Mariotti) የሚመራ
3ኛ. ከአዲስ አበባ አዲስ ዓለም መንገድ በኮሎኔል ባሊ የሚመራ የባቡር ሐዲድ ጥበቃ የተመደበ

ከሸዋ ሮቢ እስከ አዲስ አበባ ፋታ ሳይሰጡ ከጣሊያኖች ጋራ ሲዋጉ የነበሩ አርበኞች በአበበ አረጋይ የሚመሩ ነበሩ። በዚሁ መስመር የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ኃላፊ ጄነራል ትራኪያ ነበረ። ጄነራሉ አርበኞቹን መቋቋም ስላቃተው ከደሴ ከሱ ጦሩ ተጠርቶ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ሌላ ጄነራል Mariotti ስለነበረ አግረ መንገዱን አርበኞቹን ለማውደም ይረዳዋ የሚሰሙ የመንደሮች ቤቶች ለማቃጠል እንዲተባበረው September 14 ለግራዚያኒ ልመና ያቀርባል። [1] ሰፕተምበር 17 ግራዚያኒ ጄነራል ትራኪያ (Tracchia) በጠየቀው መሰረት ጄነራል ማሪዮቲ (Mariotti) እንዲተባበር ያዝዛል።[2] ሁለቱ ጄነራሎች የኢንዲጂኒ ጦር (የኤርትራውያን) አዛዦች ናቸው፤ ጄነራል ትራኪያ የ II የኤርትራ ብሬጌድ አዛዥ ሲሆን ጄነራል ማሪዮቲ የIX ብሬጌድ የኤርትራ ኢንዲጂኒ አዛዥ ነበረ።
ጄነራል ማሪዮቲ ለእርዳታ እንዲቆይ የተፈቀደለት ለ10 ቀን ብቻ ነበረ። ወደ ደብረሲና የሚወስደው መንገድ በአርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃት ተቋርጦ ደብረሲና

[1] Governo Generale A.O.I Allegati N 8 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegati N 12-19-117



የጣሊያኖች ሰፈር ተከቦ ያለ ግንኙነት ይገኝ ነበረ። የጄነራል ማሪዮቲ ተልእኮና በቦታው የሰፈረ አርበኞች ለመደምሰስ ነበረ።

አርበኞች በተኩለት፤ አራምባ፤ ዋዩ፤ ቆላ፤ ሸኖ ሰፈረዋል። ተኩለት የሰፈረው የአርበኞች ቡድን 1000 የሰው ብዛት የነበረው ሰፕተምበር 25 የጅብረ ሲና የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ያጠቃል። ከደሴ የሚመጣ የጄነራል ማሪዮቲ ጦር ሰፕተምበር 26 ከደብረሲና 8 ኪሎ ሜትር ብቻ ርቆ ይገኝ ነበረ። በ27 ቀ ጄራል ማሪዮቲ ጦር ከአርበኞች ተኩስ ይከፈትበታል። በዚሁ ጊዜ ጄነራሉ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ምንም እንኳን አርበኞች የጣሊያኖች እስከረ ብዛት አይተው የሸሸ ቢሆኑም 3 ባታሊዮኖች ኤርትራውያን ተከታትለው አርበኞችን ብቻ ሳይሆን ያገኙት ሰው ሁሉ ለመጨረስ ለቀቋቸው 45 አርበኞች ተገደሉ፤ በደብረሲና አካባቢ 100 ቤቶች ተቃጥለዋል፤ የአካባቢ መንደሮች በሙሉ እንደወደሙ ይቆጠራል፤ በደብረሲና የሰፈሩ የኢጣሊ ወታደሮችም ከጦር ሰፈራቸው መጥተው ቤቶችን ለማቃጠል ተካፍደ ነበሩ፤ የቀንድ ከብቶች ተዘርፈዋል፤ በእኛ የደረሰ ጉዳት ወደፊት ይገለጻል፤ የጦር አሬዮፕላኖች በምብ የሚጥሉበት ቦታ ምልክት ሰጥቻለሁ፤ የአካባቢው መንደሮች ሹም ከጣሊያኖች ጋራ ሆኖ ቤቶችን ለማቃጠል ተካፍለዋል፤ ሁለት ቀን ሰረፍት አድርገን ቤቶችን ሙሉ በሙሉ ለማቃጠል ይቀጥላል ብሏል። ጄነራሉ ከደሴ ሰፕተምበር 12 ተነስቶ 4 ባታሊዮን ኤርትራውያን (ወይንም ኢንዲጂኒ) በመምራት ኦክቶበር 16 አዲስ አበባ እስገባበት ጊዜ ድረስ ስላደረጋቸው ውጊዎች ረጅም ሪፖርት አቅርበዋል።

1. የደብረሲና ውጊያ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ነበረ። ከኢጣሊያ ወገን የደረሰው ጉዳት የሞቱ ኢንዲጂኒ 4 የቆሰሉ 9 የጠፉ 1 ነበሩ።
2. ሰፕተምበር 29 አርበኞችን ፍለጋ በደብረሲና አካባቢ ሰሜን ምሥራቅ በተደረገው አሰሳ፤ አብዛኛው በአካባቢው የነበሩ ቤቶች ተቃጥሏል፤ 150 አርበኞች ተገድለዋል። ብሏል። ከኢጣሊያ ወገን አንድ መቶ አለቃና አንድ ም/መቶ አለቃ ቆስሏል፤ ከኢንዲጂኒ 12 ተገድለዋል 33 ቆስሏል።
3. ኦክቶበር 4 በደብረሲና አካባቢ ጉድጓምባ ማክፋድ በተባሉ ቦታዎች ብሬጌዱ አሰሳ አድርጎ ሰፈሩ ሰላም የሰፈነበት መሆኑን አረጋግጧል። ብሬጌዱ ኦክቶበር 6 ከደብረ ሲና ተነስቶ ኦክቶበር 7 ደብረብርሃን ይገባል።
4. ኦክቶበር 9 በጫጫ አካባቢ ተኩስ ተከፍቶበት ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ የተገኙ ቤቶች (ቀከሎ) በሙሉ ተቃጥለዋል፤ 20 አርበኞች (ሽፍቶች) ተገድለዋል፤ ከጣሊያኖች ወገን ምንም ጉዳት አልደረሰም ብሏል።
5. ኦክቶበር 10 በዋዩ በተደረገው ውጊያ 188 አርበኞች (ሽፍቶች) ተገድለዋል። ብሎ ቆስሏል። ከጣሊያኖች ወገን አንድ የመቶ አለቃ ቆስሏል፤ ከኢንዲጂኒ 2 ተገድለዋል፥ 7 ቆስሏል። 250 ቤቶች (ቀከሎ) ተቃጥለዋል፤ 400 የቀንድ ከብቶች፤250 በጎች 30 ፈረሶች ተዘርፈዋል።
6. ኦክቶበር 11 በደነባ በተደረገው ውጊያ 50 አርበኞች ተገድለዋል። ከጣሊያኖች ወገን አንድ መቶ አለቃ ቆስሏል፤ ከኢንዲጂኒ አንድ ሲሞት 7 ቆስሏል። በድምሩ 453 አርበኞች ተገድለዋል፤ ከጣሊያኖች 4 የጦር መኮንኖች ሲቆስሉ ከኢንዲጂኒ 19 ተገድለዋል 66 ቆስሏል።

እስካሁን ጣሊያኖች ለአገዛዛችን ያስጉናል ብለው በወጥመዳቸው አስገብተው የገደሏቸው ወይንም በወጥመዳቸው በማስገባት ላይ የሚገኙ የራስ ካሣ ልጆችና እነ ራስ እምሩ ራስ ደስታ ወዘተ ነበሩ። እነሱን ካጠፉን ኢትዮጵያን በሰላም እንገዛለን የሚል ተስፋ ነበራቸው። አሁን ግን ከዚህ በፊት ያልታወቁ የአርበኞች መሪዎች ብቅ ማለት ጀመሩ፤ ከእነሱ አንዱም አበበ አረጋይ ነው። በአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ትግ አገዛዝ አበበ አረጋይን ለማጥፋት ሳይሞክሩ ቀርተው ሳይሆን ሰላቃታቸው በድል አድራጊነት ሊወጣ

ችሏል። ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ የተቃ ኃላፊ ጀነራል ትራኪያ (Trocchia) ስለ አበበ አረጋይ ጽፈዋል[1]። የጀነራል ትራኪያ 2ኛ ብረጌድ ኢንዲጂኔ 6 ኤርትራውያን ኢንዲጂኔ ባታሊዮኖች ያቀፈ ወንዥራ ብረጌድ ነው፤ 2,17,18, 4,9 እና 21 ባታሊዮኖች/ እሱ የሚያደርገው የማጽዳት ዘመቻ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረሲና በመጓዝ ነው። ሚሚ ከመድረሱ በፊት ኦክቶበር 9,1936 ከአርበኞች ከፍተኛ ተኩስ ተከፍቶበት ሆኖም አርበኞቹ በታቸው ለቀው ስለሄዱ መንገዱን ሊቀጥል ችሏል። ኦክቶበር 10 ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ተካሂዶ 190 አርበኞች ተገድለዋል ብሏል፤ ለማግስቱም ደነባ ላይ ኦክቶበር 11 ሌላ ውጊያ ተካሂዷል፤ የደረሰው ጉዳት አልተገለጠም። ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ የሚሰሩ የኢጣሊያ ሲቪል ሰራተኞች ደኅንነት ለመጠበቅ የጀነራል ትራኪያ 2ኛ ኢንዲጂኔ ብረጌድ በቂ ሆኖ ስላልተገኘ፤ የጀነራል ማሪዮቲ 9ኛ ኢንዲጂኔ ብረጌድ እርዳታ በቂ ስላልሆነ በጀነራል ተሲቶሬ (Tessitore) የሚመራ 7ኛ ኢንዲጂኔ ብረጌድ ኦክቶበር 11 ጠዶ በታው ተልኮ ነበር፤ ነገር ግን ደጃዝማች ፍቅረማርያም አዲስ አበባን ለማጥቃት አቅዷል የሚል ወሬ ስለተሰማ ጀነራል ተሲቶሬ ከሰንዳፋ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ትዕዛዝ ተሰጠው። ጀኔራል ማሪዮቲም ወደ አዲስ አበባ ቶሎ እንዲመጣ የተደረገው በዚሁ ምክንያት ነው። 2ኛ ብረጌድ መንዲዳ ማዚያ በማድረግ ወደ እንኮበር፤ ሞቦቢክ የእያራራ ሸለቆ፤ ሰምበለት፤ አሰልቱ፤ የነገ ሸለቆ በመሄድ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ መቀጣጫ ፈጽሟል፤ የመንደርተኞች ባንደዎችም ተካፋይ ነበሩ። ለጣሊያኖች ብዙ ያስቆጣቸው ከደሴ ወደ አዲስ አበባ ይጓዝ የነበረው በጀነራል ፓዎሊኒ (Paolini) የሚመራ በአንድ የኢጣሊያ ነጭ ዲቪዢዮን ኦክቶበር 18 ቀን ሸዋ አካባቢ አርበኞች ያደረሱት ጥቃት ነው። በውጊያው አንድ የጦር መኮንን ቆስሏል፤ ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች 3 ሞቷል፤ የቆሰሉ 8 ከእነሱ ውስጥም 4ቱ በከባድ ነበረ። አንድ ኢጣሊያዊ ወዛደር መንገድ የሚሰራ በድንጋጤ ሞቷል፤ አንድ አስካሪም ሞቷል፤ አንድ ሲቪል ሾፌር ቆስሏል። ከአርበኞች 200 ተገድለዋል፤ ከ100 ቤቶች (ቱኩል) በላይ እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፤ ኤርትራውያን ወታደሮች ባስቸኳይ ሌሊት ተጉዘው ወደ ስፍረው እንዲደርሱ ግራዚያኒ ትእዛዝ አስተላፈዋል።[2] በገጠር የሚሰማራ የኢጣሊያ ጦር ሰሚያስፈልገው ሰንቅ ሁሉ ከሚያርፍበት ቦታ ይጠቀም ነበረ። [3] ከውትድርና ተግባር ሌላ በሕዝቡ ላይ የግሳብ ቅስቀሳ ይደረግ ነበር፤ በታቃራኒዮች ላይ ከባድ ቅጣት ይፈጸም ነበር። ከጣሊያኖች ጋራ ለሚስማሙ ርሕራሔ የተሞላበት አያያዝ የደረግላቸው ነበር፤ ከእነዚህ ውስጥም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ከጣሊያኖች ጉን ተሰልፈው በታማኝነት ተዋግቷል።[4]። በሸዋ የነበረው ሁኔታ በአጠቃላይ ሲታይ ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ አርበኞችን ለማራቅ የተደረገ ቢሆንም አርበኞች ግን አልጠፉም ነበረ።

## ለ. ባቡር ሐዲድ

ምዕራባዊ ክፍል ከአዋሽ እስከ አዲስ አበባ ያለው መስመር በሚመለከት ነው። በዚሁ አካባቢ በየረር ደቦኮዲዮ ቦካን እንዲሁም በዙቋላ ጋለታ ሲሪዩ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ አርበኞች በአየለ አባ ግርባ የሚመሩ

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegati 25-29-45 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegati N119 V II
[3] Governo Generale A.O.I ibd Testo p 74 V II
[4] Governo Generale A.O.I ibd Testo p 74 V II



ናቸው። ሌላ የአርበኞች መሪ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ጉን ሆኖ የሚንቀሳቀስ በባቡር መስመር የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮችና በዋናው ማእከላዊ ባቡር ሐዲድ አዲስ አበባ ጥቃት የሚፈጽም ደጃዝማች ፍቅረማርያም ነበረ። ያስማቋረጥ ጥቃቶች ይፈጸሙ የነበሩ የሚቀጠሉ የሚከተሉት ናቸው።

1. ኦክቶበር 2 በዱከም ሚሻ 3 ኪሎሜትር ከዱከም በአንድ ባቡር ላይ የተደረገው ጥቃት ነው።
2. ኦክቶበር 10 ከአቃቂና ዱከም መሐል
3. ኦክቶበር 10 አዳማ አዋሰ እና ሞጆ ተብለው በሚጠሩ የኢጣሊያ ባንዳዎች ላይ በዙቋላ ለመፈተሽ ሄደው የነበሩ ከአንድ ሺህ አርበኞች ተኩስ ስለተከፈተባቸው ሸሽተው ወደ ሰፈራቸው ስለተመለሱ ግጭቱ ተወግዷል።
4. በዱከም ወንዝ አጠገብ በዱከምና መልካ ጂሉ ኦክቶበር 12 ቀን በአርበኞች የተሰነዘረው የኢጣሊያ ሚኒስትሮች የሚጓዙባቸው በ2 የታጠቁ ባቡሮች ነበረ። ሆኖም በባቡሮች የነበሩ አጃቢዮች ተኩ በታዎች በመያዝ ተከላከለው አርበኞች ወደ የረር ተራራ እንዲሸሹ አድርገዋቸዋል፤ በባቡሩም ያለ ችግር ጉዞውን ቀጥሏል። ከሰዓት በኋላ ለመቀጣጫ በሕዝቡ ላይ በተደረገው ጭፍጨፋ የ2ኛ ባቡር አጃቢዮች ተካፋይ ነበሩ። አርበኞች ሬት ለሬት ፍልሚያ ስላልፈለጉ ሸሽተው አምልጠዋል፤ 200 ሰዎች ሞተባቸዋል። ከኢጣሊያ ወገን 5 የሞቱ ጣሊያኖች 20 የቆሰሉ ነበሩ፤ ከኢንዲጂኔ 1 ሞቷል 3 ቆስሏል። ለማግስቱ ኦክቶበር 13 በጀነራል ሚስኪ (Mischi) 650 ጣሊያኖች 4 መድፎች ያላቸው በሕዝቡ ላይ ትጣቱ ቀጥለዋል። በዙቋላ አካባቢ 800 የንጉሡ የጋማ ከብቶች ይገኛሉ ስለተባለ ለጣሊያኖች ያደረ ቀኛዝማች ታደሰ ለማረጋገጥ ወደ ስፍራው ይላካል። ቀኛዝማች ከብቶቹ ገበሬዎች ተከፋፈሉባቸው መኖራቸው ካረጋገጠ በኋላ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ገበሬዎች ከብቶቹን ካልመለሱ ቅጣት እንደሚፈጸምባቸው ብሉ አስጠንቀቃቸው። ለፍተሻ ወደ ዝቋላ ተልከው ከነበሩ ባንዳዎች 2 ሲሞቱባቸው 8 ቆስሏል አንድ ም/መቶ አለቃና የአዳማ ባንዳዎች አዛዥ ቆስሏል፤ በዝቋላ አጠገብ የሚገኙ 500 ቤቶች /ቱኩል/ በጦር አሪዮፕላኖች እንዲደበደቡ አንድ ሻላቃ ሃሳብ አቅርቦ ለማግስቱ ኦክቶበር 11 ተደብድበዋል። ጀነራል ሚስኪ ኦክቶበር 13 ሕዝቡንና አርበኞቹን ለመቅጣት በተሰማራበት ጊዜ 2 የኢጣሊያ ወታደሮች ተገድለው የተቆራረጡ አግኝቷል።
5. አርበኞች ከማጥቃት አላቋረጡም። ከአዳማ ሞጆ መሐል ያለው መንገድ አርበኞቹ ባደረጉት አደጋ ባቡሩ ከሐዲድ በሰወጣ ጀነራል ኦክቶበር ሚስኪ ሌላ ጥቁር ሸሚዞችና (Camicie Nere) እና የሞጆ ባንዳዎች ወደ ስፍራው አሰማርቷል። መማሪያ የያዙ ተይዘዋል፤ የተረጋገጡ 50 አርበኞች ተገድለዋል፤ ከአርበኞች 100 ሰዎች ሞቷል። ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 7 ጣሊያኖችና አንድ ባንዳ ከቆሰሉ 19,14 ጣሊያኖች ነበሩ። አሁን አርበኞች ሰሉራቁ አካባቢው ሰላም ነው፡
6. ይህ ተደጋጋሚ በባቡሮች የደረሰው ጥቃት የኢጣሊያ ክብር የሚቀንስ ሆኖ ስለታየው ማርሻል ግራዚያኒ አርበኞችን ማጥፋት አስፈላጊ በመሆኑ ጀነራል ጋሊና ኦክቶበር 16 ወደ ቦታው እንዲላክ ሲያደርገው ከራሱ ወታደሮች ጭምር ይዞ ወደ ባቡር ሐዲድ እንዲሰማራ ሲያደርገው የሰጠው መመሪያ የወሚሚ መናገሻ፤ ሱልልታ፤ የረር ተራራዎች በወታደር እንዲያዙ በተለይ በየረር ተራራ በማተኮር። የጀነራል ማሪዮቲ ወታደሮችም በባቡር ለመጀመሪያ ጊዜ ከሄደ በኋላ በየረር ተራራ እንዲሰማራ ትእዛዝ ተሰጠው። ግራዚያኒ በጀነራል ጋሊና የሰጠው መመሪያ በየረር ደቦኮዲዮ፤ ዝቋላ የሚገኘው አርበኞችን ለመደምሰስ ለማውደም ጥብቅ የሆነ በሕዝቡ

መቀጣጫ እንዲፈጸም ጀነራል ጋሊና የግራዚያኒ ትእዛዝ ለመፈጸም ተዘጋጅቷል፣ ለዚሁም በደቦኪዬ በነበረ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ አርበኞች ላይ ዘመቻ ለመጀመር ይወሰናል።

## የደጃዝማች ፍቅረማርያም መገደል

ጥቅምት 22 ግራዚያኒ የሚከተለው መመሪያ ለጀነራል ጋሊና ላከሟል።

1ኛ. ለዘመቻው ያወጣኸው ፕላን አንብቤዋለሁ፣ ይሁን እንጂ አልተስማማሁበትም

2ኛ. ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ የተሰጠዎት ኃላፊነት ቋሚ መሆኑን መውሰድ አለበዎት፣ ኃላፊነትዎም ብቻዎ መውጣት አለበዎት፣ ከሌሎም ለብዙ ንኡስ ክፍል መከፋፈል የለበትም፣ በአንድ አዛዥ ብቻ ሲመራ ሥራው የተቃና ይሆናል።

3ኛ. በስርዎ ሥር የሚሆኑ 1ኛ ተቨረ ዲቪዮን 2ኛ. የማሪዮቲ ብሬጌድ ባለ 4 ባታሊዮኖች ኢንዲጂኒ 3 የታጠቁ ባቡሮች፡፡ ዲቪዚዮን ተቨረ ከሁን በፊት እንደነበረው በቋሚ ቦታ መሰፈር አለበት፡፡ የማሪዮቲ ባታሊዮኖች በአዛዦቻቸው እየተመሩ ተንቀሳቃሽ ኃይል በመሆን ሩቅ ቦታዎች ለመቆጣጠር ሆኖ ዓላማውም የአርበኞች ቡድኖች ለማውደምና ባቡር ሐዲድ መስመር የሚገኙ መንደሮች ለማጥፋት ነው።

4ኛ. በዚሁ ባቡር ሐዲድ በቹረናይካ እንደተከሰተው ተመሳሳይ ነው፣ ዘመር አዛዦች እሻቸው የሰጡና ሽፍቶች እየተባሉ ለሁለት ክፍሎ የማየት አዝማሚያ እየታየ ነው፡፡ ይህ በቹረናይካ ለባሊያኖቹ መጥፎ ውጤት የሰጠ እንቅስቃሴያችን ያሰናከለ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ መወገድ አለበት፣ ሁሉም ምንም ልዩነት ሳይደረግ እንደ ሽፍቶች መቆጠር አለባቸው ምክንያቱም እሻቸው የሰጡ አመፂ ሁኔታ እየጠበቁ እንደገና ሽፍቶች ይሆናሉ።

5ኛ. አርበኞች (ሽፍቶች) የተከማቹባቸው ቦታዎች የረር፣ ዙቋላና ደቦኪዬ ተራራዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች እየተረዱ ነው ወደ ባቡር ሐዲድ እየመጡ መስመሩን እንዲቋረጥ እያደረጉ አሻጥር የሚሰሩብን፡፡ ስለዚህ በእነዚህ የሽፍቶች ማእከሎች ዘሚገባ ሰርጎ መግባት ያስፈልጋል፣ ወንበዴዎችና ኗሪ ሰዎችን ያለ ምንም ርሕራሔና ምሕረት ማውደም ያስፈልጋል።

6ኛ በእነዚህ ቦታዎች የጦር አሬዮፕላኖች፣ የማውደም ሥራ ፈጽሟል፣ ነገር ግን ሥራቸው የወታደሮች የማውደም ሥራ ካልተጨመረበት የተሟላ ሊሆን አይችልም።

7ኛ. በአሁኑ ወቅት ከቡርነትዎ የማሪዮቲ ብሬጌድ ኢንዲጂኒ ማማሻ በጦር ሰፈር እያስተመሟቸው ይታያል፡፡ ይህ አሰራር መታረም ያለበት ነው፣ ሁሉም የኢንዲጂኒ ወታደሮች ተንቀሳቃሽ መሆን አለባቸው፣ ወደ ዓማፂያን ሰፈሮች ሰርጎ መግባት አለባቸው እነሱ ብቻ ሳይሆን በጀነራል ሚስኪ የሚመሩ የተቨረ (Tevere) ዲቪዚዮን ወታደሮችም ከጦር ሰፈሮች ውጭ መሰማራት ይችላሉ፡፡ ይህ ካልሆነም ለጀነራል ሚስኪ ሌሎች ወታደሮች ሊመደቡለት ይቻላል፣ በዚሁ ዓይነት ከጀነራል ማሪዮቲ ጋራ ሆኖ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል።



8ኛ. ከቡርነትዎ እንደሚያውቁት በአንድ ቦታ ብቻ ትኩረት ከሰጠን ሽፍቶቹ በሌላ አካባቢ ጥቃት ሊፈጽሙ ስለሚችሉ መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚሁ ሁሉ አየር ኃይል ተገቢ ወሳኝ ትብብር ሊያደርግ ይችላል።

9ኛ. እላይ በገለጹኩት መሠረት የበላይ ኃላፊነት በእኔ ሆኖ የእርስዎ ልምድ ያለው የቆ የቅኝ ተዋጊዎች ችሎታ ያከሉበት ማረጋገጫ ስለሚወስዱት ውሳኔዎች እንዲያስታውቁኝ እጠይቀዎታለሁ፡፡ የዚሁ ኮፒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትርና ለመንግሥት መሪ ለዱቼ መላኪ ልኬያለሁ[1] በትእዛዙ መሠረት ጀነራል ጋሊና ለባቡር ሐዲድ ከሁሉ እስከ የነበረው የደጃዝማች ፍቅረማርያም አርበኞች የሰፈሩበት በደቦኪዬ ለመጀመር ወሰነ፡፡

ጥቅምት 25 ዘመቻው ተጀመረ፡፡ ጀነራል ማሪዮቲ ከመሰንቺ ጋር 2ኛና 21ኛ 2 ባታሊዮኖችን በመምራት ሻለቃ ላናቲ 2 ባታሊዮኖች የ9ኛ ብሬጌድ 17ኛና18ኛ ከአላስ ወደ ደቦኪዬ አመሩ፡፡ ሁለቱ ቡድኖች እገሬመገንገኛቸው መንደሮችን እያቃጠሉ ግታው ደቦኪዬ ሲደርሱ ደጃዝማች ፍቅረማርያም ወደ በሚገ ወደ በካን የተዛወረ መሆኑን ሰማው ቀድሞ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ደጃዝማች ወደአለበት ወደ በካን ለማገሥቱ አመሩ፡፡ እስከ እጆሬ ድረስ ሀገሩ በረሃማ ስለሆነ ወንበዴዎቹን ያስተናግዱ መንደርተኞች እያወደሙ ብቻ ማሪዮቲ ከመሰንጨቲ ሻለቃ ላኑቲ Lanuti ከአላስ፣ ሁሉም የ9ኛ ብሬጌድ ባታሊዮኖች ጥቅምት 26 ሟት ወደ በካን አመሩ፡፡ ከእጆሬ እንዳለፉ ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተባቸው፡፡ ከባድ ውጊያ በጨበጣ ሳይቀር ተደረገ፡፡ ደጃዝማች ፍቅረማርያም በዚሁ ውጊያ ተገድለዋል፣ ከእሱ ሌላ ነጋ ድራስ በገልጦ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ፣ ግራዝማች ግተቡ፣ አቶ መኩንን እንደዚሁም ደባ የተባለው ነጋዴ ለደጃዝማች ፍቅረማርያም የባቡር ሐዲድ ቡሉኖች መፍቻ ያቀበል ነበረ የተባለው በዚሁ ውጊያ ተገድለዋል፡፡ ከአርበኞች የተገደሉ 600 ነበሩ፡፡ ከቆሰሉ ባሻ አምፋና ሌሎች ነበሩ፣ በሕዝቡ ላይ የደረሰ ጉዳት በጣም ብዙ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ቤታቸውን ትተው በየእቅጣጫው ተበታትነዋል[2] ከጣሊያኖች ወገን ሁለት ጦር መኮንኖች ሲሞቱ 3 ቆስሏል፣ 10 ኢንዲጂኒ አርትራውያን ሞቷል 43 ቆስሏል፣ ጣሊያኖች ተደብቷል፡፡ የበካን ውጊያ እንዳበቃ የማሪዮቲ ብሬጌድ ወደ ባልቴ በማምራት በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች እንዲደመሰሱ ግራዚያኒ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ የኢጣሊያ 9ኛ ኢንዲጂኒ ጦር ወደ ባልቴ በሚጓዙበት ጊዜ አርበኞች አላጋጠሟቸውም ሆኖም እግረ መንገዳቸው የባልቺ መረናዮስ ሽንኩራ መንደሮች ቤቶች እንዲቃጠሉ አድርገዋል፡፡[3] ማርሻል ግራዚያኒ የማሪዮቲ ብሬጌድ ወደ ባልቺ እንዲያመራ ትእዛዝ ሲሰጠው ደጃዝማች ባልቻ ይገኛል ስለተባለ እሱ እንኳን ቢሸሽ ቤቱና ያካበቢ መንደሮች እንዲወድሙ ብሏል፡፡[3] ለዝቋላ አቡን ለአንድ አርበኛ እንኳን መጠለያ ከሰጠ ያለ ምህረት ቤተክርስቲያኖችን ገዳምን እና መነኩሴዎችን በሙሉ እንዲገወድማቸው በእኔ ስም ንፍለት ብሏል፡፡

በበካን ውጊያ ጣሊያኖች ደጃዝማች ፍቅረማርያምን በመገደላቸው ድል ተቀዳጅተናል ብለው እርስ በርሳቸው ይመሰጋገኑ ነበር፣ በመጀመሪያ 300 አርበኞች ገድለናል ብለው መግለጫ ከወጡ በኋላ ቆይተው ግን የተገደሉ አርበኞች 600 ነበሩ ብሏል፡፡ ሆኖም አርበኞች አለቃቸው ጥቅምት 26 ቢገደልባቸውም 3 ቀን ባልሞላ ጊዜ ጥቅምት 29 ቀን በጨፈጊርሚ 6 ኪሎ ሜትር ከጨፈዶንሳ ተሰባስበው መታየታቸው ታክቲካዊ ማረጋገጥ እንጂ

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 136 V II
[2] Governo Generale A.O.I Testo p 234 V II
[3] Governo Generale A.O.I Testo N 96 V II
[3] Governo Generale A.O.I Allegato N 179 V II

ሽንፈት እንዳልገጠማቸው ያሳያል፡ ገድለናል ያሉዋቸው 600 አርበኞችም ተዋጊዎች ሳይሆኑ ሴቶችና ሕፃናት የአካባቢ መንደሮች መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ጀኔራል ጋሊና ቦታ የቀየሩ አርበኞች እየመሰሳሉ፣ አሁንም የ9ኛ ኢንዲጂኒ ብርጌድ አንድ ባታሊዮን ያሰጠኝ ብሎ አስፈትዶ ከአካባቢው የተውጣጡ ባንዳዎችም በመጠቀም በባልቺና በየረር ለ2ኛ ዙር ውጊያ ይዘጋጃል፡፡ በዚሁ መሠረት በ4 ጀኔራሎች የሚመሩ ወታደሮች መደበኛና ባንዳ ወደ የረር ተራራ ኦክቶበር 30 ይሰማራሉ፡፡

1. ጀኔራል ቶሊተረ ከአዲስ አበባና ከለንዳፋ
2. ጀኔራል ቲራባሲ (Tirabassi) ከራዲዮ ማዚያ
3. ጀኔራል ግሪዮቲ ከባልቺ
4. ጀኔራል ጋሊና ቀኛ አዝማቹ ራሱ ከአዳስ (አድአ)

የዚሁ ዘመቻ ዓላማ ተዋጊውን ጠላት ለማግኘት ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ሽብር ለመፍጠር የኢጣሊያ ኃይለኛነት ትልቅነት ለማሳየት፣ አልገዛም ብሎ አርበኞችን የሚረዳ ሕዝብን ለማጥፋት፣ በግልጽ ባወጡት ሰትድያ ሕዝቡን ዘመግደል ቤቶቻቸውን ለማቃጠል ንብረታቸውን ለመዝረፍ ነበረ፡፡ አየር ኃይልም ተካፋይ ነበረ፡፡ ጀኔራል ግሪዮቲ ብቻ ያከናወነው ተግባር ጣሊያኖች ዘትልቅ ኩራትና ጀግንነት ሲገልጹ ኦክቶበር 30 ጨፈዶጎላ እንደደረሰ 2 መንደሮች አቃጥለዋል ብብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሽፍቶችን ረሽነዋል፣ 150 ከብቶችን ዘርፈዋል ብሏል፡፡ (1) ጀኔራል ጋሊና ራሱ ስለፈፀመው ጀብድ ለግራዚያኒ ሲያስታውቅ በጨፈዶጎሳ፣ ጨፈገርግ፣ አፋ፣ አፍክ፣ ለባኒ ዘመንደሮች ሰሬው ጭፍጨፋ ማካሄዱን፣ ብዛት ያላቸው የቀንድ ከብቶችን ዘርፎ ለባንዳዎች ማከፋፈሉን ከጥቂት አርበኞች ጋራ ግጭት ማድረጉንና 5 መግደሉን ጽፈዋል፡፡(2) ጣሊያኖች ጭግረያ ከታጠቁ አርበኞች ጋራ ጦርነት ገጥመው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ገድለናል ሲሉ ከእነሱ ወገን አስር የማይሞሉ ሞተዋል ሲሉ የማይታመን ነው ጣሊያኖች ይገድሉ የነበሩ መሣሪያ የሌላቸው ሰላማዊ ሰዎች ሴቶችና ሕፃናት ነበሩ፡፡ ግራዚያኒ የአርበኞች መናኸሪያ ብሎ ትኩረት የሰጠበት ቦታ ዝቋላ ነበር፡፡ ግራዚያኒ ወደ ዝቋላ ሕዝቡን እንዲጨፈጭፍና ያሰማራቸው ወታደሮች ወትሮው እንደሚያደርገው ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን አልነበሩም፣ ደፋሮች ተብለው ቅጽል የተሰጣቸው በአለቃቸው በጀኔራልና ቆንስል ተብሎ የሚጠራ ጀኔራል ሚስኪ (Gen. Mischi) የሚመሩ ባለ ጥቁር ሸሚዞች የኢጣሊያ ፋሽዝም ልዩ ወታደሮች የተሰጠ ዲቪዚዮን አባሎች ነበሩ፡፡ ጀኔራል ሚስኪ ለቅርብ አለቃው ለጀኔራል ጋሊና ያቀረበው ሪፖርት(3) ከሞጆ ኖቨምበር 14 1936 ስላደረገው ዘመቻ ባለ ጥቁር ሸሚዝ ፋሽስቶች ብቻቸው አልዘመቱም አዲስ ሞጆ አዳግ የሚባል ስም የነበራቸው ባንዳዎች አብረው ዘመተዋል፡፡

1. ኖቨምበር 9 በአንድ ኢጣሊያዊ የሚመሩ ባንዳዎች ወደ ወምበርና ኩተማ የሚባሉ መንደሮች ልክ አሰሳ ባደረጉበት ጊዜ ከሕዝቡ ተቃውሞ አላጋጠማቸውም አርበኞች አላገኙም ጥይቶች በውስጣቸው ተገኝቷል የተባሉ የ3 ያልተያዙ አርበኞች የአንድ ቄስ ቤት እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፡፡ ኖቨምበር 10 ደፋሮች ባንዳዎች ጂዳ ወደ ተባለው መንደር ሄደው እንዲፈትሹ አደረገ ሕዝቡ የተለመደ የእርሻ ስራው ሲያካሄድ አገኙት የጦር አረዮፕላኖች ግን አካባቢውን በቦምብ ይደበድቡ ነበር ሕዝቡ ከኢጣሊያ ወታደሮች ከጦር አረዮፕላኖች የበቀል እርምጃ ሳይወስድባቸው ለመኖር ከፈለጉ ማድረግ

(1) Governo Generale A.O.I Allegato N 205 V II
(2) Governo Generale A.O.I Allegato N 213 V II
(3) Governo Generale A.O.I Allegato N 329 V II



የሚገባቸው ነገራቸው፣ አንድ ጨዋ የታጠቀ ሰው ስለተገኘ በባላባቱም አደገኛ ሰው መሆኑን ስለነገራቸው ተረሸነ፡፡ ባንዳዎች ፍተሻ እንዲያደርጉ ታዝዘው መግቢያ የተገኘባቸው ቤቶች ተቃጥለዋል፡፡ ሌሊት ኖቨምበር 12 ባንዳዎች ለፍተሻ ተልከው ቹካላ እና ዓሬካ ቡታ ወንድማማቾች የተባሉ እንዲይዙ ታዝዘው አንዱ ብቻ ተገኘ፣ ሕዝቡ በሰጠው ጥቆማ ተገደለ፡፡ ዞረ ኢጣሊያ ትዕቀት ያደርጋል የተባለ መምሬ ግጥ በሌሊት ተይዞ ታሰረ፣ በተደረገው ተኩስ ሁለት አርበኞች ተገደሉ ሌሎች ቆስለው ሸሽተው አመለጡ፣ መንደሩ አርበኞች የተገኙበት እንዲቃጠል ተደረገ፡፡ በገበያ ቀን መምሬ ግጥ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በጥይት ተገደሉ፡፡ ለኢጣሊያ ታማኝ የነበሩ ሁለት ባላባቶች ለሁለት መንደሮች ተሾሙ፡፡ ቢሬዩ ጢቾ ጣሊያኖች ገለታ የተባለው ቦታ አርበኞች አሉበት ስለተባለ፣ 600 የነበሩ አርበኞች ኖቨምበር 19 ቀን ባንዳ አዳማን ልከው እንዲዋጉ አድርገው 100 አርበኞች ሲገደሉ ከባንዳዎች 20 ተገድለው 30 ቆስሏል፡፡ የደፋሮች "Arditi" ፋሽስቶች ዘመቻ አንድ ሰው ሳይዋጉባቸውና ሳይቃወሟቸው በወኪሎቻቸው በባንዳዎች ተዋጋን ብለው ወደ ሰፈራቸው ተመልሰዋል፡፡

ቢሬዩ ጢቾ፡፡ ጣሊያኖች በሲሬዩና ጢቾ አርበኞች የተሰበሰቡበት ነው ውጊያ ይገጥመናል በሚል ጥርጣሬ ነበረ የተጓዘ፣ አርበኞች ግን ደፋሮችና የአዳግ ባንዳዎች ሲመጡባቸው ትንሽ ተኩስ ከፍተው ለቀቁላቸው እንደዚሁም የ9ኛ ኢንዲጂኒ ሲመጡባቸው ያለ ውጊያ ለቀቁላቸው ሲሬዩን ሕዝቡም ተከትሉዋቸው ሸሽቶ ለቀዋል፡፡

በበቀለ እና አባመርሳ የሚመሩ አርበኞች በበኩላቸው፣ ጣሊያኖች ጢቾን በያዙበት ቀን ዲሰምበር 3 በአሩሲ በነበረው የጣሊያኖች ጊዜያዊ ጦር ሰፈር ጥቃት ፈጽመባቸው ሸሽተው ወደ አዳግ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል፡፡ አረዮፕላኖች ግን ባገኙት ድል እንዳይኩሩ በቦምብ ደብድበዋቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ጣሊያኖች በባቡር ሐዲድ መስመር ሰላምና መረጋጋት የተፈጠረ መሰሏቸው ነበር፡፡

# ሐ. አማራ

ጎጃም፡፡ አንድ ቡድን የኢጣሊያ ደጋፊ 2 ቡድኖች ተቃዋሚ ከተቃዋሚ ዘለቀና ስበሐቱ ይገዙ ናቸው፡፡

በላስታ ቤጌምድር በደጃዝማች ወንድወሰን የሚመሩ ናቸው፡፡

በዲባና ወረኢሉ በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች ነበሩበት፡፡

## የደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ መያዝና መገደል፡፡

ደጃዝማች ወንድወሰን በጣሊያኖች ለመያዝና ለመገደል የበቃው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለጣሊያኖች እጄን እሰጣለሁ ብሎ በማስማቱና ንግግር በማድረጉ ነው፡፡ ጣሊያኖች ደጃዝማች እጄን እሰጣለሁ ማለቱ ሐሰት መሆኑን ተረድተናል ሆኖም እንቅስቃሴውን ለመከታተል እንዲመቸን ከበን ለመያዝ እንዲመቸን ንግግርችን እናካሄድ ነበር ብሏል፡፡ ጣሊያኖች በ3 አቅጣጫዎች ከበባ አድርገውበታል፣ 1ኛ ከደሴ 2ኛ ከሰቆጣ 3 ከደብረታቦር፣ እያንዳንቸው ከ1000 በላይ የሰው ኃይል ነበራቸው፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግሥት መሪና የክልሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሚል ሹመት የነበረው ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ ደጃዝማች ወንድወሰን በልዩ ልዩ ዘዴ

በጣሊያኖች ወጥመድ የገባ መሆኑንና ለማምለጥ የማይችል መሆኑን በሳወቀ ጀግንነቱንና የጦር ታክቲኩን ለማሳየት በጣሊያኖች ጦር መኮንኖች የሚመሩ ታማቂዎች ለመውጋት ወደ ደብረታቦር መጣ። በ3 አቅጣጫዎች የዘመቱ ደጃዝማች ወንድወሰንን ለመያዝ የተሰማሩ ታማቂዎች ከበባቸውን አጠናቅቀው ተገኝተዋል። ይሁን እንጅ ከበባውን ለማጠናከር አስተማማኝ ለማድረግ ጣሊያኖች 2 አዲስ ተጨማሪ ተዋጊዎች አሰማርቷል። ከወልዲያና ከላሊበላ የመጡ ባንዳዎች የደጃዝማች ቅርብ ተባባሪዎች ለመያዝ ችሏል። የ5ኛ ዲቪዚዮን ባለጥቁር ሸሚዝ ፋሽሲቶችና የኤርትራ ራያ ጋላ ሌሎች የባንዳ ቡድኖችም በዘመቻው ተካፋይ ሆነው ነበር የደሴው በአመዲ ዓሊ የሚመሩ ባንዳዎችም ተካፋይ እንደሆኑ ታውቆ ነበር።

በዚሁ ጊዜ ግራዚያኒ ደጃዝማች ወንድወሰን እንደሚያዝ ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ ስለነበረ ኖቬምበር 9 ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ ዋና ጊዜያዊ ሰፈሩ ወደ ደብረታቦር ያዛወረ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በዚሁ ቀን ደጃዝማቹ እንደተያዘ ሕግ ፊት ሳይቀርብ እንዲገደል የነገረው መሆኑን ገለጸዋል። ኖቬምበር 10 ከደሴ ተነስቶ የዘመቱ በሻምበል ፋሬሉ (Farello) የሚመሩ የወሎ ባንዳዎች በ1ኛ ተራ ቁጥር አላይ የተጠቀሱ በተከዜ ወንዝ በአንድ ዋሻ ይገኝ የነበረ ደጃዝማች ወንድወሰንን በቁጥጥራቸው ሊያውሉ ችሏል፣ ወዲያውኑ ተረሽነዋል። የዘመቻው አዛዥ ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ በየቀኑ የሚያስተላልፏቸው ከነበሩ ቴሌግራሞች የኖቬምበር 13[1] ቴሌግራም ግራዝማች አበጥ ደጃዝማች ወንድወሰን ቀኛማች ሹመት ሰጥቶ የነጥላና መከት ገዢ አድርጎት የነበረ በጣሊያኖች ቁጥጥር ስር እንደዋለ አንድ የኢጣሊያኖች መረጃ አቀባይ ከስፍራው ወደ ላሊበላ የመጣ ደጃዝማች አሬዮፕላኖች በጣሉት ቦምብ ታፋው ቆስሎ በዓይኑ እንዳየው መመስከሩ [2] ታማቂዎች ከዳተኞች እንደተረሸኑ በደረጃቸው እነሱም የተድሞ አስካሪ መረዝጊ ወልዴ የ19ኛው ባታሊዮን ግዲ ተይዞ ወረዳ እንዲሁም የ17ኛ ባታሊዮን ባልደረባ የነበረው የተድሞ አስካሪ የግዲ ኳላ ወረዳ አባል የነበሩ ናቸው። ይህ ጣሊያኖች ከእነሱ የከዱ እየለቀሙ በጭካኔ የመግደል ሁኔታ በታማኞች ኤርትራውያን መሐል እንዴት ጥቂት እንክርዳዶች ተገኙ ብለው ንዴታቸውን በጊዜው ያሳዩት የነበረ ነው።

ከደሴ ጀኔራል ሪካርዲ (General Riccardi) ደሴምበር 11 ቀን 1936 ወደ አዲስ አበባ ባስተላለፈው ቴሌግራም በሻምበል ፋሬሉ (Farello) የሚመሩ የወሎ ባንዶች ደሴምበር 10 ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከተከዜ በአንድ ዋሻ አንድ ቀን የፈጀ ከባድ ከበባ በኋላ ደጃማዝች ወንድወሰንን የያዙ መሆናቸውን ገልጿል። ጀኔራሉ በዚሁ ቀን በሌላ ቴሌግራም ደጃዝማቹ የተገደለ መሆኑን አለመሆኑን አላውቅም ካልተገደለ በትእዛዙ መሠረት እንዲገደል ለሻምበል ፋሬሉ እነግረዋለሁ ብሏል። እንደገና በዚሁ ቀን ዲሴምበር 11 ቀን በላከው ሌላ ቴሌግራም ደጃዝማች ወንድወሰን ዲሴምበር 10 ከምሽቱ 3 ሰዓት ተኩል የተገደለ መሆኑን ገልጿል።

ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ በበኩሉ ወደ አዲስ አበባ በዚሁ ቀን ዲሴምበር 11 ቀን በላከው ቴሌግራም በደጃዝማች ወንድወሰን እንደተደረገ ሁሉ በደጃዝማች ከበደ እና በአቡነ ይስሐቅም እንዲፈፀም አስፈላጊውን ትእዛዝ አስተላልፌያለሁ ብሏል። እንደዚሁም በተድሞዎቹ የኢጣሊያ አስካሪ ከዳተኞች ርሕራሔ እንዳይደረግ ትእዛዝ ሰጥቻለሁ ብሏል። በዚሁ ቀን በጀኔራል ፒርዚዮ

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 315 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 639 V II



ስለ ደጃዝማች ወንድወሰን መገደል ባጠጣው መግለጫ ለተካፈሉ ሁሉ ምስጋናውን አቅርቧል።

1. ለፋሽስቶች መጀመር ሰላለበት ለ1ኛና 5ኛ ባለጥቁር ሸሚዞች
2. ለባለ ጥቁር ሸሚዞች አንደኛ ግሩፕ የኤርትራ
3. ለኢንዲጂኒ 10ኛ 24ኛ እና 25ኛ ባታሊዮኖች
4. ለአየር ኃይል
5. ለስታ ቤጌምድር ወሎ በለሳ ሰሜን ሕዝብ
6. ለኤርትራ ዘገሬ ገዥ ያአላማጣ ራያ ጋላ ባንዳ በመፋተዶ.

## የዶባ ውጊያዎች፣ አበበ አረጋይ

ባንዳንድ የዘታች ሹሞች አማካኝነት እንደ አበበ አረጋይ የመሣሰሉት የራስ ካሣ ልጆች የፈጠሩት ሰፊ የሽፍትነት እንቅስቃሴ በዶባ እንዳለ ብለው ጣሊያኖች ስለተገነዘቡ፣ ሽፍቶችን ለመደምሰስ ከደሴ በአምባሰል ባንዳ እየተረዳ ኮሎ/ቶስቲ (Tosti) የሚመራ 6ኛ ኢንዲጂኒ ብሪጌድ ኖቬምበር 16 ሽፍራው ይልካሉ። ሆኖም በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች በቀላሉ የሚገኙ ሆነው አልተገኙም። የጣሊያኖች ዶባ ዋና ጦር ሰፈር አድርገው አካባቢውን ሁሉ ለመቆጣጠር የነበራቸው ዓላማ በአርበኞች ብርቱ ተቃውሞ ሊሳካላቸው አልቻለም፣ በዶባ ጦር ሰፈር ተወስኖ እንዲቀመጡ ተደረጉ።

በሌላ የአማራ አካባቢም ደጃዝማች ወንድወሰን ቢገደልም በዘመቻ በባዚል ደስታ የሚመሩ፣ ከእም ሐጀር ጎንደር የሚወሰደው መንገድ በውብነህ ተሰማ የሚመሩ አርበኞች ስለነበሩ፣ ጣሊያኖች አርበኞችን ማጥፋት ስላልቻሉ የአርበኞች ደጋፊ የተባሉ ነዋሪዎች ፌብርዋሪ 1937 ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር። የአርበኞች ዋና ምሽግ የነበረው በአርማጭሆም ተመሣሣይ ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር።

ወደ ዶባ ስለ ዘመቱው በኮሎኔል ቶስቲ የሚመራ ስለ ኢንዲጂኒ 6ኛ ብሪጌድ ጦር ኖቬምበር 26 የደሴ ወታደራዊ እዝ ጀኔራል ሪካርዲ እንዳወጣው ቀኛዝማች አበበ አረጋይ 6 መትረየስ አንድ መድፍ 2000 ተዋጊዎች እንዳሉት ገልጸ፣ ውጊያም ተካሂዶ ከጣሊያን ወገን አንድ አስካሪ ሲሞት፣ አንድ የጦር መኮንንና 6 አስካሪ ቆስሏል፣ ከአርበኞች ወገን 100 ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካባቢው ሕዝብ አርበኞችን ይረዳል ስለተባለ፣ አካባቢው በጦር አሬዮፕላኖች እንዲደበደብ ብሏል። ከዚህም ሌላ ኮሌኔል ቶስቲ አርበኞችን ለመቋቋም ኃይል ስለሚያንሰው፣ በደሴም በቂ ወታደር ስለሌለ፣ ከአዲስ አበባ 40 የጦር መኮንኖች፣ 43 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 1832 ኢንዲጂኒ ወታደሮች 928 የጋማ ከብቶች ወደ ዶባ እንዲላኩ የሚል ሃሳብ አቅርቦ ነበር። ግራዚያኒ ግን ለወደፊት በስፍራው ሰፊ ዘመቻ ለማድረግ እቅድ ስላለው ለጊዜው ወታደሮች መላክ አስፈላጊ አይደለም ብሎ ሃሳቡ ውድቅ አደረገው[1]። የጦር አሬዮፕላኖች በአርበኞች ላይ ባደረጉት ድብደባ፣ ከአርበኞች ተተኩሶባቸው በተደጋጋሚ ተመትቷል ብሏል።

## ጎንደር

የአማራ ክልላዊ መንግሥት መሪ ጀኔዋሪ 27, 1937 ለአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት[2] የውቤ ተሰማ ሚስት ተይዛ እንደታሰረች፣ በመረባት አካባቢ

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 468 VII
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 1021 V II

መንደሮቹን ማቃጠል ዘመቻ ተግለዋል ብሏል፡፡ የተቃጠሉ ቤቶች የጦር መሣሪያ ነበራቸው ብሏል፡፡ ሕዝቡ ውብነህ እጁን ለጣሊያኖች እንዳይሰጥ እየገፋፋው ይገኛል፡፡ 57 ሰዎች በጥርጣሬ ተገድለዋል፡፡ የእግራ ቁስቋም ሕዝብ ብዙ በሉግ ሐጀር ጉንደር የደረሱ ግጭቶች ተጠያቂ ሆኖ ስለተገኘ ተደምስሰዋል፤ የምሽግ ቦታዎች ተገኝቷል፤ የአንድ ኢጣሊያዊ የተገደለ መታወቂያ ወረቀት ተገኝቷል፡፡ ሕዝቡ መኖሪያውን እየለቀቀ ወደ ምዕራብ እየተሰደደ ነው፡፡ በአቸፈር ባቢል ደሴታ ለመያዝ ሙከራ ተደርገዋል፡፡ ተራራ ዮሐንስ የተባለው መንደር ክባቢል ደሴታ ተባባሪ በመሆኑ እንዲወድም ተደርገዋል፡፡

በአርማጭሆ በአንድ ባታሊዮን ኢንዲጂኒና በባንዳ አማካኝነት አካባቢውን ለመቆጣጠር በተደረገው አሰሳ አንዳንድ ቦታ ሕዝቡ ወታደሮችን በደስታ ተቀብሎዋቸዋል፤ መሣሪያም አስረክበዋል፡፡ በማይተባበሩ መንደሮች ያስርጎራሉ የማቃጠል ስራ ተካሂዷል፡፡ 2 ጭቃ ሹሞች 3 ወንበዴዎች (አርበኞች) ተገድለዋል ብሏል፡፡[1]

# መ. ምዕራብ ክፍለተ ሀገሮች

የምዕራብ ክፍላተ ሀገሮች ለመቆጣጠር ጣሊያኖች የተጠቀሙበት በሚሲዮናዊ አባ ቦሬሎ አማካኝነት ነው፤ ይኸውም ግራዚያኒ በፕተምበር 28, 1936 ለአባ ቦሬሎ (Padre Borello) በጻፈለት ደብዳቤ በግልጽ ያስረዳል[2]፡፡ ስፕተምበር 29 የኮሎኔል በሊና የራስ ኃይሉ ባንዳዎች አምቦን በቋሚነት ይይዛሉ፡፡ ኮሎኔል በሊና ራስ ኃይሉ ጦርና ከደጃዝማች ሃብተማርያም ጋራ እና ከአባ ቦሬሉ ግንኙነት በመፍጠር ሕዝቡን ወደ ጣሊያኖች ለመሳብ የፖለቲካ ስራ ያካሂዳሉ፡፡ የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ ለቀምት በሚዘምትበት ጊዜ አባ ቦሬሉ የኢጣሊያ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ በመሆን ያገለግላል፤ ባላባቶች የቀድሞ ሹሞችን ያስተባብራል፤ ቋሚ መኖሪያው ለቀምት ያደርጋል፡፡

1. በአሬሮፕላን የራዲዮ መገናኛ ማሺን እና ሠራተኛው ይላካል
2. በአሬሮፕላን ለአባ ቦሬሉና ለደጃዝማች ሃብተማርያም የሚያገለግሉ የጦር መሣሪያዎች በተለይ ለአባ ቦሬሉ የሚያገለግሉ ባንዳዎች ለማቋቋም አስልጣኞች የጦር መኮንኖች ይላካሉ፡፡
3. የማሪያ ተሬዛ ብር ለአባ ቦሬሉና ለደጃዝማች ሃብተማርያም በአሬሮፕላን ይላካሉ፤ ሌላም ማንኛውም አስፈላጊ ሁሉ ይላካሉ፡፡

አባ ቦሬሉና ደጃዝማች ሃብተማርያም የሚያከናውኑት ተግባር በእምነ ቷወስና አይቀርም በሁሉ አቅጣጫ መሆን አለበት፤ በተለይ ከጐሐንስና ከሆሣዕና ወንድማማቾች ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል፤ በኃይልም ቢሆን ክንፈ ያሉትን መንግሥት እንዲቋቋሙ፤ ግራዚያኒም ደብዳቤ አጽፍላችኋለሁ ብሏል፡፡ ወለጋና ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለ ደም መፋሰስ በጣሊያኖች እጅ እንዲገቡ ወሳኝ ሚና የተጫወተው ኢጣሊያዊ ሚሲዮናዊ አባ ቦሬሉ (Padre Borello) የተባለው ነው፡፡ በአባ ቦሬሉ አማካኝነት ሚያዝያ 5/ሚያዝያ 27 አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ እንደወደቀች በጁን ወር 26 ሰኔ 19, 1928 በጦር አሬሮፕላኖቻቸው አማካኝነት ቡቀ ጥናትና ዝግጅት ሳያደርጉ ጣሊያኖች በከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው አማካኝነት በለቀምት አሬሮፕላን ማቢያ ለማረፍ ያደረጉት ሙከራ በጥቂት ለሀገር ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ከሸፈባቸው በለቀምት አሬሮፕላን

(1) Governo Generale A.O.I. Allegato N. 260 V II

(2) Governo Generale A.O.I. Allegato N. 21 V II



ማቢያ ያረፉ ጣሊያኖች በሙሉ ተገድለዋል፡፡ ኦክቶበር ወር በአባ ቦሬሉ አማካኝነት እስተማማኝ ሁኔታ በለተፈጠረላቸው ጣሊያኖች እንደገና በተሳካ ሁኔታ በለቀምት አሬሮፕላን ማቢያ ለማረፍ ችለው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በራሳቸው ሙሉ እምነት አልነበራቸውም፡፡ 1/ ካሬ የነበረው ፊላ እምሩ ወደ ለቀምት እየገሰገሰ ነው የሚል ወሬ ይሰማ ነበር፡፡ 2/ በመጀመሪያ የጣሊያኖች ወደ ለቀምት በሬራ ጣሊያኖችን ፈጅቷል ተብለው የሚጠረጠሩ የቀድሞ በወለጋ የጦር መኮንኖች ማስወገጃ የሰለጠኑ ያሉባቸው 300 የኢትዮጵያ የጦር መኮንኖች በለቀምት አካባቢ አሉ የሚል ወሬ ይሰማ ስለነበረ አሁንም ጣሊያኖች ፍራት ነበራቸው፡፡ 3/ ደጃዝማች አበራ ካሣ ከሰላሌ ከራስ እምሩ ጋራ ለመገናኘት ወደ ለቀምት አምርቷል የሚል ወሬም ይሰማ ነበር 4/ ፊታውራሪ ሃብቴ እና ገብረወልድ የተባሉ እያንዳንዳቸው 30,000 ጦር በመምራት ጣሊያኖችን ለመዋጋት ከጎሬ ወደ ለቀምት እየገሰገሱ ናቸው የሚል ዜናም ከጂቡቲ ተሰራጭቶ ነበር፡፡ 5/ ከንጉሡ የተላኩ በሕዝቡ ላይ ቅስቀሳ እያካሄደ ነው የሚል ወሬም ተሰምቶ ነበር፡፡

## New times and Ethiopia News

ኦገስት 22 ቀን 1936 በእርእሰት የተጠቀሰው ጋዜጣ ስለ ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ የሚገልጽ ጽሑፍ አውጥቷል[1]፡፡ ሻምበል ብርሬል የተባለው እንግሊዛዊ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቀይ መስቀል ኃላፊ የነበረ ነው፡፡ Capitain Brophil ሻምበል ብርሬል ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ጉብኝቶ ከልሉ በዓለም መንግሥታት ሞግዚትነት እንዲስተዳደር የሚል አስተያየት ነበረው፡፡ ምዕራባዊ የኢትዮጵያ መንግሥት መኖር በእንግሊዝ ፓርላማና የጋዜጠኞ ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ስታንሌይ ጂቮንስ Prof. Stanley Jevons ኢትዮጵያን የሚደግፍ ማሕበር የክብር ፕሬዚዳንት የሆኑ ከሻምበል ብርሬል አንድ ደብዳቤ ይደርሰዋል፡፡ ስለ ምዕራብ ኢትዮጵያ በትክክል መናገር ይቻላል፤ ምክንያቱም በኢጣሊያ ሠራዊት ገና አልተያዘም፤ ስለ ሌሎች ክፍላተሀገሮች የሚደርሱን ዜናዎች የተምታቱ ናቸው፡፡ የምዕራባዊ ኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ የሆነችው ጎሬ ናት፡፡ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በጎሬ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋቁሞ ይገኛል፡፡ መንግሥቱ የሚመራው በራስ እምሩና በደጃዝማች መስፍን እየተረዳ በቢትወደድ ወልደጻድቅ ነው፡፡ ቢተወደድ ወልደጻድቅንና ራስ እምሩን አነጋግሬያቸዋለሁ፤ ሁሉም የነገሩኝ ከእግራም ሆነ ከጋላ የተውጣጣ ሠራዊት ለመመልመል ተስፋ አላቸው፤ ነገር ግን የጦር መሣሪያ የላቸውም፡፡ በየአጋጣሚ ይቀርብልኝ የነበረ ጥያቄ የመንግሥታቱ ማሕበር እርዳታ ሊያደርግላቸው ይችል እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚሁ ዓይነት ተስፋ ካለ ኢትዮጵያ በማኀበሩ ሞግዚትነት ስር እንድትሆን ብለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የጊዜያዊ መንግሥት አባላት ከንጉሡ ነገሥቱ ያለ ማቋረጥ በራዲዮ ግንኙነት አላቸው፡፡ ሌሎች የጊዜያዊ መንግሥት አባላት 1/ ነጋድረስ ወልደሰማያት 2/ ነጋድረስ ብረሃን ሥላሴ 3/ ፊታውራሪ በፈቃዱ 4/ ልጅ ይልማ ድሬሳ 5/ ፊታውራሪ ዮሐንስ ጆቴ 6/ የደጃዝማች ሃብተማርያም ወኪል ናቸው፡፡ ምዕራብ ኢትዮጵያ ምን ያህል ጊዜ በሰላም እንደምትኖር አይታወቅም የዝናም ወቅት (የክረምት) እንዳለቀ፤ ጣሊያኖች ወደፊት ገፍተው ምዕራብ ኢትዮጵያን ከያዙ እንደ ሌሎች ክፍላተ ሀገሮች ምዕራብ ኢትዮጵያም ወደ ሥርዓተ

(1) Governo Generale A.O.I. ibd Allegato N 57 VII

አልበኝነትና ሰቃይ እንዳትወድቅ ያሰፈራል፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ (በእንግሊዝ ሀገር) በመንግሥታቱ ማኅበር ውስጥ ምዕራብ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ስር እንዳትወድቅና በከንቱ የንፁሐን ደም ማፍሰስ እንዳይደርስ ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልተደረገ የሚመጣው ውጤት በጣሊያኖች በሚጣል ቦምብና በጋዝ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የንፁሐን ሕዝብ ሞትና የዚሁ ስም መሬት መውደም ይሆናል፡፡ የመንግሥታቱ ማኅበርም ምዕራብ ኢትዮጵያ በራሱ ሞግዚትነት ስር እንዲስተዳደር ባለማድረጉ በኃላፊነት ያስጠይቀዋል፡፡ የኢጣሊያ ወይራት መግፋት እንዲቆም አድርጉ! የመንግሥታቱ ማሕበርም ቶሎ ብሎ እንዲንቀሳቀስ አድርጉ፡፡ የአማራና የጋላ ሕዝብ በእንግሊዝ ሕዝብ ያላቸው እምነት ስሜት የሚቀሰቀስ ነው! እርዳታ ሳይደረግላቸው ከቀረ ከፍተኛ ወንጀል ይሆናል ወዘተ ብሏል፡፡

## ምዕራብ ኢትዮጵያ (ወለጋ) ያለ ደም መፋሰስ በኢጣሊያ እጅ መውደቅ

እላይ የተጠቀሰው ደብዳቤ ጣሊያኖች እላትመው ሲያወጡ የሰጡት ትችትና ማስተባበያ የለም፡፡

ሰፕቴምበር 7, 1936 አባ ቦሬሉ ለግራዚያኒ ያቀረበው ቁ 9 ሪፖርት በቁ 7 Allegati ታትሞ ወጥቷል፡፡ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከተቆጣጠሩ ጀምሮ በየጊዜው ለግራዚያኒ ደብዳቤ ሪፖርት ይጽፍ ነበር፣ በአማካኝ በወር 2 ጊዜ፡፡ በዚሁ ሪፖርት አባ ቦሬሉ ስለ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም ስለ ለቀምት የነበረው ሁኔታ ለግራዚያኒ በሰፊው አስረድቷል፡፡ የጻፋቸው ሪፖርቶች ሁሉ ለማወቅ ቢቻል በሚሲዮናዊው ስለተፈጸመው የስለላ ስራ የበለጠ ግንዛቤ እናገኝ ነበር፡፡ ስለ ደጃዝማች ሃብተማርያም ለጣሊያኖች ታማኝነት አስረድቶ ግራዚያኒ ደብዳቤ እንዲጽፍለት ተማጽኖዋል፣ እንዲሁም ለ2ኛ ጊዜ ጣሊያኖች በለቀምት አሮፕላን ማቢያ ቦታ ስለሚያርፉበት ሁኔታ ኮሎኔል በይስትሮቺ Baistrocchi በአየር እየጣለለት ይሰጡት ስለነበሩ መመሪያዎችና ግንኙነቶች ጽፏል፡፡

ሰፕቴምበር 27 ግራዚያኒ አባ ቦሬሉ ባሳሰበው መሠረት ለዳጃዝማች ሃብተማርያም ለፊታውራሪ ሞሳ ጂጂቶ ለሌሎችም ባላባቶች ስለ ኢጣሊያ መንግሥት ታላቅነት በማውራት ደብዳቤ ጽፈዋል፣ ሰፕቴምበር 30 (መስከረም 20, 1929 ዓ.ም.) ደጃዝማች ሃብተማርያም መልስ ሰጥቷል፡፡ ኮሎኔል ባይስትሮቺ ሰፕቴምበር 29 የለቀምት አሮፕላን ማረፊያ ደኅንነት ካረጋገጠ በኋላ ከአባ ቦሬሉ ከተሰማማ በኋላ ኦክቶበር 2 ከግራዚያኒ አስፈቅዶ በለቀምት አሮፕላን ማረፊያ ቦታ በደኅና ማረፍ ችሏል፡፡

ኦክቶበር 2 ግራዚያኒ በለቀምት የኢጣሊያ አሮፕላን ያረፈ መሆኑን ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ለሶና (Lessona) በላከው ቴሌግራም ከአባ ቦሬሉ የተላከለት ሪፖርት በማስተላለፍ ነው፡፡ አባ ቦሬሉ በዚሁ ሪፖርቱ ካወሳቸው ብዙ ጉዳዮች ስለ ቀኛዝማች በለው የአፄ ኃይለሥላሴ ልዩ ባለሟል ከኢየሩሳሌም ተልኮ ለቀምት መሰንበቱ ገለጸዋል፡፡ ኦክቶበር 14 ቀን 1936, 14 የጦር አሮፕላኖች ከፍተኛ የአየር ኃይል ባለሥልጣኖች ያሉበት ለቀምት አሮፕላን ማረፊያ አርፈው ውለው ማታ ሁሉ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል፡፡ ይህ ዕለት ለቀምት በኢጣሊያ ቁጥጥር ስር መሆኑዋን ቢቆጥሩትም ፀጥበስ የሚገዝ የኢጣሊያ ሠራዊት ለቀምት እስከሚደርስ በዜና ማሰራጫዎች ለመግለጽ ተቆጥበዋል፡፡ ጣሊያኖች የመጀመሪያ ሥራቸው በለቀምት ባንዳዎች ማቋቋም ነበር፡፡



## ለቀምትን ለመያዝ የኢጣሊያ የአየር ወረራ ከሸፈ

ጣሊያኖች አዲስ አበባ እንደተቆጣጠሩ መሶሊኒ ምዕራብና ደቡብ ክፍላተ ሀገሮች ሳይውል ሳያድር ኢጣሊያ እንድትቆጣጠራቸው ፍላጎት ነበረው፡፡ ግራዚያኒ ግን ይህ በየብስ የማይሞከር መሆኑን ስለተረዳ፣ የሙሶሊኒን ፍላጎት ለሟሟላት ሌላ ዕቅድ ይፈጥራል፡፡ በአባ ቦሬሉ አማካኝነት በለቀምት ደጃዝማች ሃብተማርያም የኢጣሊያ ደጋፊ መሆኑን ማረጋገጫ በማግኘቱ፣ ቅኝ ግዛቶች ለመያዝ የሚደረጉ ጦርነቶች ድፍረት ከታከለበት ሁሉ ነገር የሚቻል ነው በሚል አስተሳሰብ፣ በአየር ወረራ ተደርጎ፣ ከደጃዝማች ኃብተማርያም በማስማማት፣ የመጀመሪያ የኢጣሊያ የጦር አሮፕላኖች ለቀምት እንዲያርፉ የባንዳ ተዋጊዎች በማቋቋም፣ ከደጃዝማች ሃብተማርያም ታማኞች ጋር ተሰልፈው ሀገሩን እንዲቆጣጠሩ ከተደረገ በኋላ መደበኛ የኢጣሊያ ጦር በአየር ወደ ለቀምት ማጓጓዝ ነበር፡፡ ለዚሁ ተግባር የተመረጡ የመጀመሪያዎቹ የኢጣሊያ የጦር መኮንኖች የሚከተሉት ነበሩ፡፡ 1. የአየር ኃይል ጀኔራል ማልዮኮ (Magliocco) 2 ሎካቴሊ (Locatelli) 3. ኮሎኔል ካልደሪኒ (Calderinil) የኢጣሊያ ሠራዊት የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ የነበረ በአዲስ አበባ የኢጣሊያ ኢምባሲ ወታደራዊ አታሼ የነበረ 4 የኮንሶላታ ሚሲዮናዊ አባ ቦሬሉ ለብዙ ዓመታት በለቀምት ኗሪ 5 መሐንዲስ ፕራሶ (Prasso) 6 ከኢትዮጵያ ወገን የኢጣሊያ ተባባሪና ደጋፊ ልጅ ደረጀ የቢትወደድ መኩሪያ ደምሰው የአርጆ ሀገረ ገዥ ልጅ፡፡

በወለጋ የጦር ት/ቤት የተመረቁ 150 ኢትዮጵያውያን ጦር መኮንኖች በሰፈራው የሚንቀሳቀሱ በደጃዝማች ነሲቡ ልጅ የሚመሩ መኖራቸውን ስለሰማ ግራዚያኒ የኢጣሊያ ጦር አሮፕላኖች በለቀምት ከሚያርፉ በእርግጥ እንድያርፍ ፈልጎ ነበር፡፡ አባ ቦሬሉ ግን ከሌሎችም የዘመቻ አባላት ድጋፍ በማግኘቱ በለቀምት እንዲያርፉ መረጠ፡፡ ጁን 25 አቡነ ሳንታ (Monsignor Santa) በለቀምት ተተክሎ የሚውለበለብ የኢጣሊያ ባንዲራን ከግራዚያኒ መኖሪያ ቤት ተገኝቶ ባርኮታል፡፡ ጁን 26 አሮፕላኑ በ8 ሰዓት ለቀምት ዐረፈ፡፡ ደጃዝማች ሃብተማርያም በአየር በተወረወረ መልእክት አማካኝነት ስለተነገረው ሰውና ለጭነት የጋማ ከብቶች ወደ አሮፕላን ማቢያ ልኮ ነበር፡፡ ጣሊያኖች በአሮፕላን ማቢያ ለማደር ወሰኑ፣ ከግራዚያኒ ጋራ በራዲዮ ግንኙነት አድርገው እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት ድረስ ደኅና መሆናቸውን ይገልጹ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ግንኙነታቸው ተቋረጠ፣ ምን እንደደረሰባቸው አልታወቀም፡፡ ጁን 26 ሁኔታውን ለማጣራት ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ተልኮ 3ቱ አሮፕላኖች የተቃጠሉ መሆናቸውን አይቶ ተመለሰ፣ ከዘመቻው አባላት ከሞት የተረፈ አባ ቦሬሉ ብቻ ነበረ፡፡ አንድ የአሮፕላን ሠራተኛ ቆስሎ ከሞት አምልጦ በፊታውራሪ ሞሳ ቤት ተደብቆ የነበረ አርበኞች ተከትለው ከፍተው ገደሉት፡፡ ደጃዝማች ሃብተማርያም ግን ጣሊያኖች በለቀምት ከተማ በቀል ይወስዳሉ በሚል ፍራቻ ከለቀምት ሸሽቶ ወጥቶ ነበር፡፡ የነገሩ ማብራሪያ የተገኘው አባ ቦሬሉ ጁን 30 በጻፈው ሪፖርት ነው፡፡

3 ወር በኋላ 27 ሰፕቴምበር ኮሎኔል ባይስትሮቺ በለቀምት ለማይ በረራ ያደርጋል፡፡ ኦክቶበር 2 በአሮፕላን ማቢያ ወርዶ ከአባ ቦሬሉና ደጃዝማች ሃብተማርያም ጋራ ይገናኛል፡፡ ኦክቶበር 8 በአባ ቦሬሉ ፊትና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በለቀምት ግቢ የኢጣሊያ ሰንደቅዓላማ ይሰቅላል፡፡ ኦክቶበር 11, ሁለት አሮፕላኖች አርፈው የራዲዮ ተከኒሺያኖች በለቀምት እንዲቀመጡ ይመደባሉ፡፡ ከዚሁ ቀን ጀምሮ በየቀኑ የኢጣሊያ ጦር አሮፕላኖች ወደ ለቀምት ይመላለሳሉ፡፡ ኦክቶበር 14 ጣሊያኖች ለቀምት

በቁጥጥራቸው መሆኗን ለማለት እንዲችሉና የመጀመሪያ ዓላማቸው ባንዳዎች ማጽዳት እንዲችሉ 13 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች 23 ተራ ወታደሮች ለቀምት ያሳርፋሉ። ጥቅምት 24 ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ይገሰግስ የነበረው አገሬኛ የኢጣሊያ ጦር 1ኛ 6ኛ 8ኛ የኤርትራውያን ኢንዲጀኒ ባታሊዮኖች እንደዚሁም 3ኛ መድፈኛ ኢንዲጀኒ በኰሎኔል ማሌታ እየተመሩ ለቀምት ገቡ። በዚሁ ቀን አንድ የኢጣሊያ ጦር አሬፕላን ወደ ሰዮ በመብረር ለጆቴ ልጆች ወንድማማቾች ከአማራ የባርነት አገዛዝ ኢጣሊያ ነፃ እንድታወጣቸው የሚል መልእክት ወትንዋል።(1) ከዚህ በኋላ ጣሊያኖች ጊዜያዊ አስተዳደራቸው በባላባቶች መስርተው ለአያንዳንዱ ባላባት 200 ብር ደጃዝማች ሃብተማርያም 1500 ብር (ማሪያ ተሬዛ) ደመወዝ ፈተዱላቸው። ለቀምትን ለመያዝ ተመድቦ የነበረው የራስ ኃይሉ ባንዳና የኰሎኔል ቤሊ (Belly) ጦር ነበረ፤ ደጃዝማች ሃብተማርያም ግን የጣሊያኖች ባንዳ ታማኝ ቢሆንም ደጃዝማች ሃብተማርያም አማራ ነኝ እንዳታመጡብን በማለት ስለተቃወመ በኰሎኔል ማሌታ የሚመሩ ኢንዲጀኒ ኤርትራውያን ወታደሮች ለዚሁ ተግባር ተተኩ። የኰሎኔል ማሌታ ጦር ወደ ለቀምት እየገሰገሰ መሆኑን ደጃዝማች አበራ ካሣ ወንድሞቹ አምቦን ለመያዝ ሃሳብ እንዳላቸው የሚል ዜና ለጣሊያኖች መረጃ ስለደረሳቸው ግራዚያኒ አምቦን የተቆጣጠሩ የኢትዮጵያ አርበኞች በአስቸኳይ የኰሎኔል ጦርን እንዳይወጉ ወደ ለቀምት ጉዞውን እንዲያፋጥን የሚል ትእዛዝ ስለሰጠው በ2 ቀን የመጨረሻዎቹ 100 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍን ተገዶ ነበር። ለዚሁ ጀብድም ከመሶሊኒ የደስታ ቴሌግራም ተልኮለታል።

ግራዚያኒ ጥቅምት 28 ኢጣሊያ ከአንድ የውጭ ሀገር ዜጋ የተላከ ቴሌግራም በደረሰው መሠረት የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች በዩብዶ ሰፍረው ከራስ እምሩ የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመቋቋም ዝግጁ ናቸው። እንደዚሁም በጊምቢ የሚገኙ የደጃዝማች ሃብተማርያም ወታደሮች ለዚሁ ዓላማ ተዘጋጅተው ይገኛሉ ካለ በኋላ እናንተ ጣሊያኖች በምትሰጧቸው መመሪያ መሠረት የጎሬ ወሌቶችን ለማውደም ዝግጁ ነን ብሏል።

## የግራዚያኒ ጥላቻ በአማራ ሕዝብ ላይ

ለቀምት በጣሊያኖች እጅ ከወደቀች በኋላ ግራዚያኒ ኖቬምበር 3 በአርጆና በወርባ የሚኖሩ አማራ የራስ እምሩ ደጋፊ መሆናቸውን የሚል መረጃ ይደርሰዋል። ቀደም ብሎም ኰሎኔል ማሌታ ጥቅምት 28-31 የራስ እምሩ ደጋፊ የተባሉ ቡድኖች ለመደምሰስ 8ኛ 2 የኢንዲጀኒ ባታሊዮን እና 300 ሰዎች ያሉበት የለቀምት ባንዳ ወደ አርጆ ልኮ የአካባቢው ገዢ የነበረው አበበ ብሩ ከእነቤተሰቡና 25 ባለሟልመንኛ ተከታዮቹ በግዲታ እጃቸው ለጣሊያኖች እንዲሰጡ መገደዳቸውን የሚገልጽ ሪፖርት ለግራዚያኒ ይደርሰዋል።

የዚህ ሁሉ ምክንያት በማድረግ ግራዚያኒ ለኰሎኔል ማሌታ በላከው ቴሌግራም አበበ ብሩ ወደ ለቀምት ተወስዶ ከዚያን ወደ አዲስ አበባ ባስቸኳይ በአሬፕላን እንዲላክ ብሎ ካዘዘው በኋላ፤ ስለ አማራ የሆኑ ሰዎች በሚመለከት(2) "አማራመንግዶችሁ የምታገኙት አማራ ሁሉ መፍጀት እንደሚያስፈልግ እምነቱ መሆኑን ይገልጽለታል። ምክንያቱም ኰሎኔሉ አበበ ብሩ ከተያዘ በኋላ ለቀሩት አማሮች የዚሁ ዓይነት ተግባር እንዳይፈጽሙ እናስረዳቸዋለን፤ እንመክራቸዋለን ብሎ ሪፖርት አቅርቦ ስለነበረ ለአማሮች

---

(1) Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 149 V II

(2) Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 239 V II



ለማስረዳት መሞከር ከንቱ ድካም መሆኑን ይገልጽለታል። ስለ አማሮች ጉዳይ ኰሎኔሉ በጥሞና እንዲያስብበት አንድ የዓረቦች ተረት ይጠቅስለታል። የዓረቦች ተረት "አንድ እባብ በመንገድ ካገኘህ ሳትነካው ልታልፈው ትችላለህ አንድ አማራ ካጋጠመህ ግን ሞንቅላቱን ጨፍልቀው" የሚል መሆኑን ገልጾ፤ ተረቱን ከመከተል ሌላ አማራጭ እንደሌለ መመሪያ ይሰጠዋል።



በመሪያ ያዘዟቸውትን አማራ ሁሉ ግደሉ ብሎ ትእዛዝ በመስጠት የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመ በሊቢያም ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመ ጨካኙ ማርሻል ግራዚያኒ

## የጂማ፣ ሳዮ፣ ዩብዶ መያዝ

ጣሊያኖች ለቀምት ከተቆጣጠሩ በኋላ ሳዮም በጆቴ ልጆች ወንድማማቾች አማካኝነት በእጃቸው እንደገባ ስለሚቆጠር ወለጋ በሙሉ እንደተቆጣጠሩ ይገምቱ ነበር። ሳዮ ከጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ኃይሎች ጥቃት ለመከላከል የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች የነበራቸው 5000 ተዋጊዎች፡፡

ሀ/ 2500 በፊታውራሪ የሐንስ ስር ሆነው ከራስ እምሩ ከአደራ ዩብዶ የሚመጣ ጠላት ለመከላከል ተሰማርቷል።

ለ/ በፊታውራሪ ሆሣዕና የሚመሩ 600 ታጣቂዎች ከጎሬ የሚመጣ ጠላት ከቢትወደድ ወልደጻድቅ ጥቃት ለመከላከል ተሰማርቷል።

ሐ/ 1000 ታጣቂዎች በልጅ እስራኤል ሆሣዕና የሚመሩ ከቤን ሻንጉል የሚመጣ የጠላት ጥቃት ለመከላከል ተሰማርተው ነበር።

በቤን ሻንጉል የነበረ ሁኔታ የቆየ እርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ካልሆነ የኢጣሊያ ግዛት ለመጋፋት አልነበረም። በማየ እንደሚታየው ጣሊያኖች እንዳወጡት፡-

ሀ/ አጦር! ጉድሩ! ጉራጌ! ከምባታ! ወላሞ! ናኖ የአርበኞች ቡድኖች ቢኖሩም የኢጣሊያ አገዛዝ ደጋፊ ተብለው የገመቷቸው ነበሩ።

ለ/ በጅማ ዐከንቲባ ጠናጋሻው የሚመሩ 2000 አርበኞች ይቆጣጠሩት ስለነበረ ውጅንብር የሰፈነበት አካባቢ ሆኖ ነበር፤ ሆኖም ለጣሊያኖች ባደረ በአባ ጆቢር አማካኝነት ጣሊያኖች ሀገሩን ለመቆጣጠር ብዙ ችግር አላጋጠማቸውም።

ሐ/ የጉማ! ሊሙ እናሪያ! ከፋ! ጊሚራ ሕዝብ አቋም የታወቀ አልነበረም፤ ምክንያቱም የእነዚህ ወረዳዎች ሀገረ ገዢ የነበረው ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ በይፋ እጁን ለጣሊያኖች ሰጥቻለሁ ቢልም የጎሬ የጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ውክልና ተቀብሎ ነበር።

መ/ ኢሉባቦርና ግጂ ለጣሊያኖች በገልጽ የሚቃወሙ ነበሩ። የኢጣሊያኖች ዋና ዓላማ ራስ እምሩ ወደ ጂማ እምርቶ አካባቢውን ተቆጣጥሮ ከራስ ደስታ ጋራ እንዳይገናኝ ለማድረግ ነበረ።

# ወደ ጅማ ጉዞና የጅማ የደጃዝማች ባልቻ መገደል

ከአዲስ አበባ በየብስ ጅማን ለመያዝ ኃላፊነት የተሰጠው በአባ ጆቢር እየተረዳ ኩሉኒል ፕሪንቺቫለ ነበረ። ዘማች ሠራዊቱ የተዋቀረው በአሰላዎች ብቻ ነበረ።

ሀ/ 45ኛ ባታሊዮን ከ10ኛ ብሪጌድ የተወሰደ
ለ/ 1000 የአባ ጆቢር ባንዳዎች
ሐ/ መድፈኛ ክፍል ከ7ኛ ብሪጌድ የተወሰደ መሳሪያዎች

ድምር 200 ሁሉም አገረ መንገዳቸው ሌሎች ወደዘማቾች የሚቀላቀሉበት ኖቬምበር 4 ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ሆነ። አገረመንገዳቸው የደጃዝማች ባልቻ አርበኞች የሰፈሩበት ይደርሳሉ። ኩሉኒል ፕሪንቺቫለ አርበኞችን ለማጥቃት በቻለቃ ርሊ (Ralle) የሚመሩ 500 ታጣቂዎች ይመድባል። ከባድ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ አርበኞቹ ይሸነፋሉ፣ ደጃዝማች ባልቻ ተማርከው ይረሸናል። ኖቬምበር 10 ጊቤ ይደርሳሉ፤ ኖቬምበር 12 አባልቲ ይደርሳሉ። ኖቬምበር 14 ኩሉኒል ፕሪንቺቫለ ጅማ ለሚገኘው ከንቲባ ጋሻው ጠና እጁን እንዲሰጥ ደብዳቤ ይልክለታል፤ ለማስፈራሪያም በጅማ ሰማይ ላይ የኢጣሊያ ጦር አሪዮፕላኖች እንዲበሩ በጠየቀው መሠረት 26 አሪዮፕላኖች በጅማ ብቻ ሳይሆን በጎሬ፣ ጋምቤላ፣ ደምቢዶሎ፣ ሰዶ፣ ዋርቀ የማስፈራሪያ በረራ ያደርጋሉ። ኖቬምበር 18 ጣሊያኖች ጅማ ገብተው በሱልጣኑ (አባ ጁፋ) ቤተመንግሥት ባንዲራቸው ተከለው ይውለበለባል።

## የሳዩ ወረራ በአየር

ጣሊያኖች በየብስ አድካሚ የእግረኛ ወታደራዊ ዘመቻ በፊት በአየር ኃይል ወታደሮቻቸውን ዘለቀምት አውርደው እንደተቆጣጠሩዋት ሁሉ ሳዮን (ደምቢዶሎ) ለመቆጣጠር በዚሁ ዘዴ ተጠቅሟል። ኖቬምበር 11 ቀን 9 የኢጣሊያ አየር ኃይል አሪዮፕላኖች ሳዮ፣ ዐረፉ፣ የፈታውራሪ ሆማሀና ታጣቂዎች በታላቅ ክብርና ደስታ ተቀበሏቸው። ግራዚያኒ ኖቬምበር 15 ለጆቴ ልጆች ዮሐንስና ሆማሀና በጻፈው ደብዳቤ የጋላ ሕዝብ ከሐበሻ ባርነት ነፃ ይወጣል እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ነፃ ሰዎች ትሆናላችሁ፣ በታላችሁ እንድትረጉ ብሎም አስጠንቅቋቸዋል[1] ጣሊያኖች ሳዮ እንደገቡ እንደልማዳቸው ባንዳ ማቅጠር ጀመሩ። በኩሉኒል ማልታ የሚመራ 1ኛ ኢንዲጂኒ ብሪጌድ ከለቀምት ወደ ቦብዶና ጊምቢ ሲንቀሳቀሱ በጀኔራል ተሲተሪ የሚመራ 7ኛ ኢንዲጂኒ 7ኛና 16ኛ ባታሊዮኖች ፈረሰኛ ያቀፈ ብሪጌድ ዘለቀምት ብቻቸውን ለመተካት ኖቬምበር 6 ቀን ከአዲስ አበባ ተነሳ ኩሉኒል ማልታ ኖቬምበር 14 ጊምቢ ደረሰ። የአርጆ ባላታ ድሬሣ መኮንን የተባለው ለጣሊያኖች እጁን ሰጥቶለሁ ካለ በኋላ ለጣሊያኖች ደጋፊዎች ለማግኘት ቅስቀሳ እንዲያደርግና ባንዳ እንዲመለምል ተነገረ፣ እሱ ግን ከራስ እምሩ በምስጢር ሲስማማ ስለተገኘ ኩሉኒል ማልታ አንድ ባታሊዮን ኢንዲጂኒና ባንዳ ልኮ ተይዞ እንዲታሰር አድርገዋል፣ የአርጆ አካባቢም ትጥቅ አስፈትተዋል። በኩሉኒል ሚላኖ የሚመራ 16ኛ ብሪጌድ ኖቬምበር 15 ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ ለቀምት ለመሄድ ተጓዟል። ከባላታ ድሬሣ ጋራ 6 የዘታች ሹሞች 29 ተዋጊዎች ሕዝቡ መሣሪያ እስኪያስረክብ እንደ መያዣ ታስረው ወደ ለቀምት ተወሰዷል።

---

[1] Governo Generale A.O.I.ibd Allegato N. 333 V II






የሸሬ ጦርነት ጀግና ራስ እምሩ በሱዳን በስደተኝነት ለመኖር በእንግሊዞች የተሰጠው ዕድል ሳይቀበል በጣሊያኖች ላይ ጦርነት በመቀጠል ስለመረጠ 500 ወታደሮች በመምራት በጎልጊያ ላይ እንዳለ ብዙት ባላቸው የኢጣሊያ ጦር የተከበበ መሆኑን በመቀ ሕዝቡን በከንቱ ከማስጨረስ ለጣሊያኖች እጁን ለመስጠት መርጦ ወደ ኢጣሊያ ሀገር ተወስዶ ታስሮ ከዛዬ በኋላ የ2ኛ ዓለም ጦርነት [illegible] ተመልሰዋል።



Ras Immirù



ሲልቪያ ፓንከርስት እንግሊዛዊት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመችው የወታደራዊ ወረራን በመቃወም (New times and Ethiopia News) የተባለው ሣምንታዊ ጋዜጣ መስራችና ሥራ አስኪያጅ የኢትዮጵያ ሐቀኛ ወዳጅ

10ኛ የኰሎኔል ሚላኖ ብሪጌድ በ54ኛ፣ 55ኛ እና 56ኛ ባታሊዮኖች እንዲሁም በ10 ቡድን የኢንጂነር መድፈኛ የተገነባ ነው። ጣሊያኖች የራስ እምሩ እንቅስቃሴ ቀን በቀን ይከታተሉት ነበር። በመጨረሻ የደረሳቸው መረጃ ተከለአብ የተባለው 1000 ታጣቂዎች ያሉት ከጅማ ተባርሮ ኖቬምበር 24 ወደ ኮሳ ሄዷል፣ ከእሱ ጋራም ከጉቲባ ጠናጋቸው፣ ብላታ ተክለሐዋርያት ይገኙበታል።

## የራስ እምሩ ከበባና መያዝ

አሁን ራስ እምሩ ያለበት ከሞላ ጐደል ስለታወቀ ከቦ ለመያዝ ጣሊያኖች ያደረጉት እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ይመስላል።

ሀ/ የኰሎኔል ማልታ ጦር ወደ ጎሬ ያመራል ኖቬምበር 19

ለ/ ከአዲስ አበባ በኰሎኔል ግራሲ (Grassi) የሚመራ 18ኛና 12ኛ የኤርትራ ባታሊዮን ወዘተ ያሉበት ኃይለኛ ጦር ለግጠናከሪያ ወደ ጅማ ይላካል።

ሐ/ ከለቀምት 7ኛ ብሪጌድ በጀኔራል ተሲቶሬ የሚመራ ወደ ዲደሳ ተጉዞ ኖቬምበር 19 ከአባ ጆቢር ተዋጊዎች እንዲቀላቀል

ኖቬምበር 26 ጎሬ በኰሎኔል ማልታ ጦር ወደቀች። የጎሬ አቡነ ሚካኤል አመመኝ ብሎ ወደ ኰሎኔል ማልታ አልተረበም በተደረገው ግጣሪያ ግን እንደሸሸ ተረጋግጧል፣ ኣያመልጥም ብሏል። በሻላቃ ቺሪኖ (Cirino) በተደረገው ክትትል አባ ሚካኤል፣ ቀኛዝማች ይነሱ እና 50 ታጣቂዎች ተማርከዋል።

ኖቬምበር 30 ታዬ ጉሉላቴና ቢተወደድ ወልደጻድቅ ከራስ እምሩ ጋራ ነበሩ። ራስ እምሩ በኤርትራውያን ከዳተኞችና በቀድሞ የወለጋ የጦር መኰንኖች እየተረዳ ጦርነቱን ለመቀጠል ፍላጎት የነበረው ሲሆን ታዬ ጉሉላቴ ግን እጅን ለጣሊያኖች ለመስጠት ያዘነበለ ነበር። በራስ እምሩ ላይ ከበባ ለግጠናከር ሀ/ ኰሎኔል ማልታ ከጎሬ ወደ ቦንጋ መዝለቅ አለበት ለ/ ፕሬንቺቫለ ከጅማ ወደ ቦጋ ሐ/ ተሲቶሬ ከለቀምት ወደ ጉግ ዲደሳ። ራስ እምሩ ዲሴምበር 4-9 አጋሮ እንደነበረ ተረጋግጦ ነበር፤ ኖቬምበር 8 ራስ እምሩ ወደ ጌራ ከፉ ለመሄድ ቦሌ የሚባል ቦታ እንደሚገኝ ለጣሊያኖች መረጃ ይደርሳቸዋል። ዲሴምበር 11 ታዬ ጉሉላቴ ከኰሎኔል ማልታ ቀርቦ እጅን እንዲሰጥ ተጠርቶ ከደጃዝማች አርአያና ከነጋ ድረስ ተሰግ እሽቴ ጋራ ሆኖ ቀርቧል። ዲሴምበር 12 ቢተወደድ ወልደጻድቅ ቀርቦ እጅን ሰጥቷል፣ ወደ ቦንጋ ተወስዷል፣ ሁሉም ያስረከቡት መሣሪያ እየተቆጠረ መሆኑን ኰሎኔል ማልታ ለግራዚያኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም ገልጸዋል። ቦንጋ በጣሊያኖች የተያዘችው ዲሴምበር 10 ነበር።

ኰሎኔል ፕሬንቺቫለ ኖቬምበር 12 ከጅማ ተነስቶ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ራስ እምሩ ወዳለበት በሚሄድበት ጊዜ ከራስ እምሩ ጦር አንድ ክፍል በድንገት ጊዮቾ በተባለው ቦታ ላይ ተገናኝቶ ከባድ ውጊያ ይገጥመዋል፣ በውጊያው በራሱ በራስ እምሩ ነበረ፣ የውጊያ ዝርዝር ኰሎኔሉ በሰፊው ድፍ አቅርበዋል። በውጊያው ሚዳ የታይፕ ማሽኖች፣ ስለ ውትድርና ትምህርታዊ መጽሐፎች፣ የግል ደብዳቤዎች ተገኝቷል። ከጣሊያኖች ወገን አንድ የጦር መኰንን ሲሞት 7 ቆስሏል 47 ኢንጂነር ሲሞቱ 108 ቆስሏል። ስለሞቱ አርበኞች አልተጠቀሰም ሆኖም በደፈና የተማረኩ ተገድለዋል ብሏል። የራስ እምሩ ወታደሮች በከዳተኞች ኤርትራውያንና በቀድሞ በወለጋ የጦር መኰንኖች ግስልጠኛ ተማሪዎች የተገነቡ ናቸው ብሏል። ራስ እምሩ ወደ ኩሉ እምልጦ እንዳይገባ መንገድ እየዘጉበት ነበር፣ ለግግሥቱም በተደረገው ውጊያ ብዙ የተማረኩ አርበኞች ተገድለዋል፣ ሴቶችና ሕፃናት በነፃ ተለቀዋል፣



ከጣሊያኖች ባንዳዎች የሞቱ 3 የቆሰሉ 6 ነበሩ፣ ከአርበኞች 20 ተገድለዋል ብለዋል።

ዲሴምበር 15 ቀን ጣሊያኖች ራስ እምሩ ወደ ቸሪክ እያመራ መሆኑን መረጃ ይደርሳቸዋል። በዚሁ ጊዜ ጣሊያኖች በፍጥነት ገስግሰው ወደ ቸሪክ ወንዝ ያመራሉ፣ ከራስ እምሩ ፊት አጥቂዎች ተገናኝተው ውጊያ ይገጥማሉ፣ ዋናው የራስ እምሩ ጦር በ200 ሜትር ርቀት ይገኝ ነበር። የራስ እምሩ ጦር ለውጊያ ተዘጋጅቶ የነበረ፣ ብዛት ያላቸው የኢጣሊያ ተዋጊዎች በግየቱ ዲሴምበር 16 ከጣሊያኖች ጋራ ለመነጋገር ይጠይቃል።

በመጀመሪያ ራስ እምሩ ወደ ሱዳን እንዲሄድ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ነበር፣ ሆኖም ጣሊያኖች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እጅን እንዲሰጥ ስለጠየቁት፣ እጅን እንዲሰጥ መቀበል ግድ ሆነበት።

ዲሴምበር 16 ከሰዓት በኋላ የእጅ መስጠትና ትጥቅ ግስፈታት ተካሄደ 5000 ወታደሮች እጃቸው ሰጡ 1800 ጠበመንጃዎች 39 መትረየሶች ሁሉም ዘመናዊ በደኅና ሁኔታ ተማረኩ። ዲሴምበር 18 ራስ እምሩና ከፍተኛ ሹሞች ወደ ቦንጋ ተወሰዱ፣ ከመታሰር ለግምለጥ የሚሞክሩ አርበኞች እየታደኑ ነበር። ጣሊያኖች ራስ እምሩ የነበረው የወታደር ብዛት ይገምቱት የነበረ ከ1500 ያነሰ ነበረ። ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚንስትር በላከው ቴሌግራም ራስ እምሩ እየተዋጋ ተይዞ ቢሆን ኖሮ ወዲያውኑ እንዲረሸን ትእዛዝ እሰጥ ነበረ። በተያዘበት ሁኔታ ግን ራስ ደስታም እጅን እንዲሰጥ ግበረታቻ እንዲሆን እንዲያዝ ብቻ ተደረገ። ራስ እምሩ ከተማረከ በኋላም አምልጦ እንዳይሸሽ ይጠረጥሩት ነበር።

## የጋምቤላ መያዝ

90 አስካሪና 2 የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች በአዲስ አበባ ጋምቤላን እንዲቆጣጠሩ ስለተመረጡ እስከ ላሮ በአሬሮፕላን ተወስደ በእግር እስከ ጋምቤላ ተጉዘው ዲሴምበር 17 ጋምቤላ ደረሱ። በቦታው 50 ባንዳዎች ነበሩ፣ ተጨምሮባቸው 200 ሆነዋል። በዚሁ ቀንም የተለያዩ እቃዎች የጫኑ አሬሮፕላኖች ከአዲስ አበባ ጋምቤላ ደርሰዋል፣ የጉምሩክ ሰራተኞችም አስፍረው ነበር።

## የበንሻንጉል መያዝ

በቤን ሻንጉል የነበረ ችግር ከአንጃዎች እርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ብቻ ነበር ጣሊያኖች የሚነካ አልነበረም፣ አንጃዎቹ 1/ የጆቴ ወንድሞች 2/ ሸክ ኢል ሆገሊ 3/ ደጃዝማች መብራቱ ነበሩ።

ለሻክ ኢል ሆገሊ ከንጉሡ የበጊ ግዛት ቀድሞ የጆቴ የነበረው ይሰጠዋል። ደጃዝማች ጆቴ በድንገት ይሞታል፣ 4 ልጆቹ ወደ ሸዋ ለግዞት ይወሰዳሉ፣ ሁለቱ በእስር እንዳሉ ይሞታሉ፣ አንዱ በእንክብር ሲላው በአዲስ አበባ። እዚ ኃይለሥላሴ ሀገሩን ለማረጋጋት ያልሞቱት ሁለት የጆቴ ልጆች በመጀመሪያ ያጊዳግ ወረዳ ቀጥሎም የእሻ ወረዳ ግዛት ይሰጣቸዋል። በጣሊያን ወረራ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን ሲወርድ የጆቴ ልጆች የአባታቸው ግዛት የነበረ መሬት እንዲሰጣቸው ለሸኩ ይጠይቃሉ። እሱ መሬቱን ለማስረከብ ሳይሆን ግብር ከመክፈል ብቻ ፈቃደኛ ነበረ። የጆቴ ልጆች ሀሸኩ ሐሳብ ስላልተስማሙ በደጃዝማች መብራቱ እርዳታ የበጊ ወረዳ ግዛት ወረው ይያዛሉ፣ ሸኩ ሀገሩን ለቆ ሩቅ ቦታ ይሰፍራል፣ (ጎሃ የተባለው ቦታ)። ደጃዝማች መብራቱ ከሸኩ

ያለው ቅራኔ እንደሚከተለው ነው፡፡ የሙስታፋ አባት ፊታውራሪ መሐመድ የቤን ሻንጉል አካል ቢሆንም ራሱ የቻለ አንድ አነስተኛ ግዛት በእኩል ደረጃ ከሌሎች የወረዳ ግዛቶች ነበረ፡፡ ፊታውራሪ መሐመድ እስረኛ ሆኖ ወደ አዲስ አበባ ሲወሰድ ግዛቱ ለሸከ ኢል ሆገሊ ይሰጣል ደጃዝማች ሙስታፋም ለመቀበል ይገደዳል፡፡

ከጣሊያኖች ጋራ ያለው ሁኔታ የጆቴ ልጆችና ደጃዝማች ሙስታፋ ምዕራብ ወለጋ በጣሊያኖች እጅ እንዲገባ ያደረጉት እርዳታ ከፍተኛ ስለሆነ ለጣሊያኖች ባለውለታዎች ናቸው፡፡ ሸከ ኢል ሆገሊ ወኪሉን አዲስ አበባ በመላክ እጁን እንዲሰጥና የኢጣሊያ መንግሥት ጥያቄውን እንዲቀበለው ከመከተትከት አላረፈም ነበር፡፡

ቤን ሻንጉልን ለመያዝ የተሰማራ የኢጣሊያ በጀነራል ደላ ቦና Della Bona የሚመራ ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ የጠረፍ መሬቶች የእንግሊዝ መንግሥት ትሸቀዳድሞ እንዳይዛቸው ፍራት ነበራቸው፡፡ የጣሊያኖች ወደ ቤን ሻንጉል ዘመቻ የተጀመረው ደሰምበር 24 ቀን ነበር፡፡ አባይን አቋርጠው ጀነዋሪ 4 በልፎዲዮ ይደርሳሉ ጀነዋሪ 5 አፎዱ፣ ጀነዋሪ 22 አሶሳ፣ 31 ቦጊ ወዘተ..

## የጉራፋርዳ በጣሊያኖች መያዝ

የወርቅ፣ የብርና የብረት ማእድን አላት የተባለች የጉራፋርዳ ወረዳ ደጃዝማች ታዬ ጉሉላቴ ለእንግሊዞች ለመስጠት ተስማምቶ እንደነበረ ጣሊያኖች መረጃ ደርሰዋቸው ነበረ፡፡ ከዚህ በመነሳት ጣሊያኖች ተሽቀዳድመው ለመያዝ ወሰኑ፡፡ በጣሊያኖች ስም ማገባር ተደም ዘማች የነበረው ለጣሊያኖች ያደረ ባንዳ ቀኛዝማች በቀለ ሲሆን ደሰምዘር 22 ከግራዚያኒ በአሬዮፕላን በተወረወረለት ትእዛዝ መሠረት በታላቅ ደስታ ትእዛዙን ስለተቀበለ ደሰምበር 25 ጉራፋርዳን ለመቆጣጠር ችሏል፡፡ የራስ እምሩ ያልተያዙ አርበኞች በየሜካው እያሳደደ እንዲለቅም ትእዛዝ ተሰጥቶት የነበረ ሌላ የጣሊያኖች ባንዳ ፊታውራሪ መሺት የተባለው ለቀኛዝማች በቀለ ጣሊያኖች እርዳታ እንዲሰግሩ አደረጉት፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ጉራፋርዳን እንዲይዙ የተመደቡ መደበኛ የኢጣሊያ ተወጊዮች ሲገቡ የቻሉ፡፡

በዚሁ ዓይነት በምዕራብ ኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ለፍነዋል ብለው በማሰብ ጀነራል ጀሉዞ ጅማ ዋና ከተማ በማድረግ የጋላና ሲዳማ ከልላዊ መንግሥት መሪና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሚል ሹመት የነበረው ፌብሩዋሪ 14,1937 በጅማ ስራውን ጀመረ፡፡ በዚሁ ጊዜ በአርበኞችና በጣሊያኖች የነበረ አሰላለፍ የሚከተለው ነበረ፡፡

## የአርበኞች አሰላለፍ

1. ሊሙ ቦቶር ተራራዎች በብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበረ የሚመሩ
2. በኩሉ ኮንታ በደጃዝማች ድንቄ የሚመሩ
3. በጋሞና ጋርዱላ በደጃዝማች ወልደማርያም የሚመሩ የራስ ደስታና የበየነ መርዕድ የተቀላቀሉባቸው
4. ቡርጂና ዶሉ ተራራ በፊታውራሪ ታደመ የሚመሩ

የጣሊያኖች አሰላለፍ ከጥቂት የምሕንድስና የከባድ መሣሪያና የጦር መኮንኖች በስተቀር በኢንዲጂኒ አስካሪና በባንዳዎች የተገነባ ስለሆነ



በጣሊያኖችና በኢትዮጵያውያን የሚደረገው ጦርነት ሳይሆን በኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ጦርነት መልክ ነበረው፡፡

1. በቤን ሻንጉል ሀ/ 22ኛና 28ኛ ኢንዲጂኒ ባታሊዮኖች ለ/ ባለ ግመል 3ኛ ባንዳ ሐ/ ምዕራባዊ ቆላ ቡድን ባንዳ መ/ የጣሊያኖች ምሕንድስና፡፡
2. ጎሬና ደምቢዶሎ ጦር ሰፈሮች ሀ/ 7ኛና 16 ኢንዲጂኒ ባታሊዮን ለ/ 7ኛ መድፈኛ ጣሊያኖች ሐ/ ምሕንድስና ጣሊያኖች
3. ለቀምት ሀ/ 54ኛ፣ 56ኛ ኢንዲጂኒ ባታሊዮኖች ለ/ ምሕንድስና ጣሊያኖች ሐ/ መድፈኛ ጣሊያኖች
4. ኖኖ ሀ/ ክ1ኛ ብሬጌድ አንድ ሻለቃ ኢንዲጂኒ ለ/ መድፈኛ ጣሊያኖች ሐ/ ባንደ በሊ መ/ ባንዳ ራስ ኃይሉ
5. ጅማ ሀ/ 12ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ለ/ 45ኛ ባታሊዮን ሙስሊም ሐ/መድፈኛ ጣሊያኖች መ/ ከባድ መድፈኛ ጣሊያኖች ሰ/ ታንከኛ ጣሊያኖች ረ/ የሮሌ (Rolle) ባንዳ ሠ/ የሙስሊም ፕሩኔቲ (Prunetti) ባንዳ
6. ከፋ ጊሚራ ሀ/ 1ኛ፣ 6ኛና 8ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ለ/ የምሕንድስና ጣሊያኖች ሐ/ መድፈኛ ጣሊያኖች መ/ የገብረመድኀን ባንዳ የከበደ ባንዳ ረ/ የበቀለ ባንዳ ሠ/ የመሺት ባንዳ ቀ/ የመሮኔ Merone ወለጋ ቡድን ባንዳ
7. ሶዶ ሆሣዕና ሀ/ 25ኛ፣ 17ኛ ኢንዲጂኒ ባታሊዮኖች ለ/ የምሕንድስና ጣሊያኖች
8. ጉራጌ ዙዋይ 10ኛ፣ 11ኛና፣ 12ኛ የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች፣ ባንዳ ቱፎ
9. ሻሸመኔ 9ኛ ባታሊዮን ዓረብ ሶማል
10. ሀገረ ማርያም 7ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት
11. የጠረፍ ማልካ መራና ቡተፋኒያ ጠባቂዮች 1ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት

እላይ በተጠቀሱ ቦታዎች ሁሉ ጣሊያኖች ከፌብሩዋሪ 28 ጀምሮ እስከ አፕሪል 26, 1937 አነስተኛ ውጊያዎች በማካሄድ ይዞታቸውን አጠናከረዋል፣ ይሁን እንጂ በባኮና በሮዶልፍ ሐይቅ እንዲሁም በስተፋኒያ ሐይቅ አሰላ የተካሄደ በመዩ ወር ነበረ፡፡

# ሰ/ ሲዳማና ሐይቆች

## ሀ/ መጀመሪያ ዙር ኦክቶበር ዲሰምበር 1936

ሳደ Sade ዲሊ አጠገብ

ኦክቶበር 19 በሳዳ ውጊያ 2 የኢጣሊያ መኮንኖች ሲሞቱ 10 ቆስሏል፡፡ ተራ ወታደሮች 5 ሲሞቱ 27 ቆስሏል፡፡ ኢንዲጂኒ 37 ሲሞቱ 119 ቆስሏል፡፡ ኖቨምበር 6 ስለ አርበኞች ጣሊያኖች የደረሳቸው መረጃዎች የሚከተሉት ነበረ፡፡

1/ደጃዝማች ገብረማርያም ከ1500 ወታደሮች ጋራ ከተፈሪ ኬላ እስከ ዲላ በሚርጎ ወንዝ አካባቢ የጣሊያኖች ወደፊት መግፋት ለማደናቀፍ ሰፍረዋል፡፡

2/ ፊታውራሪ ታደመና ተሰማ 500 ተዋጊዮች ቡሌ ሰፍረዋል፡፡

3/ በይርጋ ዓለም 300 ከዳተኞች ኤርትራውያን ሰፍረዋል፡፡

## ቡሌ

ደሰምበር 12 በጀነራል ናቫሪኒ የሚመራ ጣሊያኖች ከፊታውራሪ ተሰማ ከሚመሩ አርበኞች ግጭት ያፈጠራል። በጣሊያኖች ግምት 50 አርበኞች ሞቷል፣ ከጣሊያኖች ወገን 2 ሲሞቱ 20 ቆሰሏል (ኢንዲጂኒ)

## ራስ ደስታ

ደሰምበር 4 ቀን ራስ ደስታ በሻምበል ቱቺ አማካኝነት ለሕይወቱ ዋስትና ከተሰጠው እጁን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን አስታውቆ ነበር። ራስ ደስታ እጁን እንዳይሰጥ የሚቃወሙ 1ኛ ደጃዝማች ገብረማርያም 2ኛ ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ነበሩ። ግራዚያኒ ጦሩን በሙሉ ይዞ ከገባ ለራሱ ለሕይወት ዋስትና ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ገለጸለት፤ ራስ ደስታ እጁን ለመስጠት ስለዘገዩ ግራዚያኒ በጀነራል ጀሉዞ አማካኝነት ደሰምበር 31 ራስ ደስታ እጁን እንዲሰጥ 7 ቀን ብቻ ጊዜ እንዲሰጠው ከዚሁ ጊዜ በኋላ ግን ምህረት እንደማይደረግለት እንዲነገረው ያዛል። ራስ ደስታ ግን ጣሊያኖች የማይቀበሉት ቅድመ ሁኔታ ለመልእክተኛ ካስታኛ አማካኝነት በማቅረብ እጁን ሳይሰጥ ቀረ።

ጀነራል ጀሉዞ በቴሌግራም እንደገለጸው በተለያዩ ቦታዎች ከኦክቶበር 15 እስከ ወሩ መጨረሻ በተደረጉ ግጭቶች በጣሊያኖች ወገን የደረሰው ጉዳት 2 ጦር መኮንኖች ሲሞቱ 12 ቆሰሏል፣ ባሌ ሌላ ማዕረግ የሞተ የለም የቆሰሉ 6 ተራ ወታደሮች ጣሊያኖች የሞቱ 10 የቆሰሉ 55 ነበረ። ኢንዲጂኒ የሞቱ 104 የቆሰሉ 197[1]

በሌላ ሪፖርት ጀነራል ጀሉዞ በሰፕተምበር 10 እስከ 15, 2 የጦር መኮንኖች ቆስሏል፣ 3 ባለ ሌላ ማዕረግ ቆስሏል፣ ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች 29 ቆስሏል፤ ኢንዲጂኒ የሞቱ 19 የቆሰሉ 69 መሆናቸውን ገልጸዋል። እንዲሁም ከሰፕተምበር 15 እስከ 30 የሞቱ የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 11 የቆሰሉ 13፣ ኢንዲጂኒ የሞቱ 8 የቆሰሉ 12 መሆናቸውን ገልጧል።

በተለያዩ ውጊያዎች ከኖቬምበር 6 እስከ ደሰምበር 16 በጣሊያኖች ላይ የደረሱ ጉዳቶች

| ቀንና ወር | የጦር መኮንኖች | | ጣሊያኖች | | ኢንዲጂኒ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሞቱ | የቆሰሉ | የሞቱ | የቆሰሉ | የሞቱ | የቆሰሉ |
| ከ1እስከ 15 ኦክቶበር | - | 2 | 7 | 31 | 19 | 69 |
| ከ15እስከ30 ” | 7 | 12 | 16 | 35 | 104 | 197 |
| ከ1እስከ15 ኖቬምበር | - | 4 | 3 | 4 | - | 8 |
| ከ15 እስከ 30 ” | 4 | - | 2 | 20 | 5 | 23 |
| ከ1እስከ15 ዲሴምበር | - | 1 | - | - | - | 29 |
| ድምር | 8 | 16 | 28 | 90 | 128 | 326 |

በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት አልተገለጸም ግን ከባድ ነበረ ብሏል።

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato 221 V II



## ለ/ 2ኛ ዙር ከጀነዋሪ 1 ፈብሩዋሪ 15

ጀነዋሪ 5, 1937 የአርበኞች አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር።

1. ዋናው የራስ ደስታ ጦር በአርባጉጉ ከሸና ሰፍር ይገኛል፤ በቀድሞ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያንና በደጃዝማች ገብረማርያም የተከበበ ስለነበረ እጁን ለጣሊያኖች ለመስጠት ነፃነት አልነበረውም፤ ሞራሉ ወድቆ ነበር።
2. ደጃዝማች በየነ መርዕድ 2000 ወታደር (ባሌ ጎባ) የሰፈረ
3. ደጃዝማች መኩንን ወሰኔ 2000 ወታደር በሶዶ ወላሞ የሰፈረ
4. በደጃዝማች ገመዳ ሚስት የሚመሩ ከአርሲ የመጡ ከምባታ የሰፈሩ
5. በፊታውራሪ ታደመ የሚመሩ በደሉ ተራራ አካባቢ የሰፈሩ

የአካባቢው አማራና ጉራጌ ሕዝብ የራስ ደስታ ደጋፊ ነበረ የአርሲ እርሞ የጣሊያኖች ደጋፊ ነበሩ። በሻምበል ቱቺ የሚመራ ትግራዩ ደጃዝማች ተከሉ ባንዳ የአርሲ እርሞች 5000 (አምስት ሺህ) ታጣቂዎች ድጋፍ አቅርበዋል።

ጣሊያኖች የነበሩዋቸው ወታደሮች የሚከተሉት ነበረ።

1. ወደ ክፍሉ የሚያመሩ በሻምበል ቱቺ የሚመሩ የትግራይ ባንዳዎች፣ 5000 እርሞች ወዶዘማቾች ባንዳዎች የተቀላቀሉበት
2. በሀገረማርያም 4 ባታሊዮኖች ዓረብ ሶማልና መድፈኞች ጣሊያኖች እንዲሁም 1ኛና 12ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት
3. በዲላ አንድ ባታሊዮን ባለ ከባድ መሣሪያ ጣሊያኖች
4. በሆሉ 1ኛ ልዩ ቡድን
5. በጀቢ ተራራ የሰፈረ የሊቢያ ዲቪዚዮን
6. በሀረርጌ የሰፈሩ በጀነራል ናሲ የሚመሩ ወታደሮች በደቡብ ምዕራብ በራስ ደስታ ላይ ዘመቻ እንዲካፈሉ ተደርገዋል።

የማጥቃት እርምጃ የሚጀመረው ለጀነዋሪ 20 እንዲሆን ተወስኗል። ዘመቻው የሚመራው ወደ ደቡብ የመጣው በራሱ በማርሻል ግራዚያኒ ነው።

ከእርሞ አርሲ ሌላ ጣሊያኖች 3000 (ሶስት ሺህ) ሲዳማ ተዋጊዎች አሰማርቷል። በተጨማሪም 1 ባታሊዮን አማራ 1 ባታሊዮን ኤርትራውያን በዘመቻው ተካፋይ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ሻምበል ቱቺ 600 (ስድስት) ሌላ የሲዳማ ተዋጊዎች ወዶዘማቾች ድጋፍ አግኝቷል።

በራስ ደስታ ላይ የሚደረገው ዘመቻ ይህ ሁሉ የተጠቀሰው የወታደር አገረኛ ኃይልና 50 አፊሮፕላኖች ያለማቋረጥ የሚጥሉት ቦምብ አልበቃም ብለዋቸው ጣሊያኖች ወላሞን ለመቆጣጠር ባቡር ሐዲድ መስመር ከሚቆጣጠሩ ተቀንሰው በጀነራል ግሪሮቲ የሚመሩ የ9ኛ ብሬጌድ ክፍል በጀነራል ጀሉዞ ስር እንዲሆን አድርገዋል።

በአርባጉጉ የሰፈሩ የራስ ደስታ ወታደሮች ብዛት ከ4 እስከ 6 ሺህ የሚገመት ብቻ ነበሩ።

ከጀነዋሪ 7 እስከ 27, 1937 በተለያዩ ቦታዎች በተደረጉ ውጊያዎች ከአርበኞች 1000 (አንድ ሺህ) ተገድለዋል። ከጣሊያኖች ወገን 2 የጦር መኮንኖች ተገድለዋል 3 ቆስለዋል የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 3 ቆስሏል ኢንዲጂኒ 93 ተገድለዋል 119 ቆስሏል። 6000 ጠበመንጃዎች 37 መትረየሶች ተማርከዋል።

የሞቱና የቆሰሉ መጥቀስ ብቻ የተደረጉ ውጊያዎች ክብደትን አያሳዩም በተለይ በሕዝቡና በአርበኞች ላይ የደረሰው ጉዳትና ሲታይ አያሳይም። በሕዝቡና በአርበኞች ላይ ጣሊያኖች ያደረሱት የነበረ በደል ለመረዳት ማርሻል ግራዚያኒና የኢጣሊያ ጀነራሎችና ኮሎኔሎች በየቀኑ ይለዋወጡባቸው የነበሩ ብዙ ቴሌግራሞች እንዳንዶቹ ማገለባበጥ ያስፈልጋል።

ግራዚያኒ ለሚፈጽመው ወንጀል የደሴታ መገለጫ ሲልከላቸው እነሱም የሚደረግላቸው ማበረታቻ ክብርና ኩራት ይሰማቸው ነበር። ግን ብዙ ሰው እንደገደሉ ውድድርና ፉክክር ነበረ የያዙት

ማርሻል ግራዚያኒ ለጀነራል ትራኪያ ዲሰምበር 15,1936 የሰጠው መመሪያ የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ ለማስከበር ትጥቅ የማስፈታት ተግባር ሙሉ በሙሉ መሆን እንዳለበት ነው፤ ወንበዴዎችንም ወይንም የተጠረጠሩ ወንደቤዎችንም ለማውደም ሙሉ በሙሉ መሆን እንዳለበት ነው[1]

ጀነራል ትራኪያ ዲሰምበር 25 እጃቸው ከሰጡ መሐከል ወይዘሮ ብዙነሽ ሃብተሥላሴ የደጃዝማች አሰፋወሰን ካሣ ሚስት ነበረች ብሏል። ቀጥሎም ትጥቅ ስለማስፈታቱ ተግባር ከዲሰምበር 9 እስከ 26 5የከባድ መትረየስ 36 ቀላል መትረየስ 3340 ጠብመንጃዎች፣ 1 ታንክ፣ 65,000 ጥይቶች ተማርከዋል ብሏል።

ሻምበል ቱቺ ከአርሲ ሰዎች ጋራ ባለው መልካም ግንኙነት ዲሰምበር 31 ባደረገላቸው ጥሪ መሠረት 3,000 አርሲ ወደ እሱ ሲቀርቡ 800 ጠብመንጃ የታጠቁ በእሱ ስር እንዲሆኑ ፈቅዷል። የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች በሚልኳቸው ቴሌግራሞች አርበኞችን ሽፍቶች ብለው ሲጠሩዋቸው አርሲ ከጣሊያኖች ጉን ሆኖ ወዶዘማቾች አርበኞች ብለው ይጠሩዋቸው ነበር።

በሻምበል ቱቺ ስር የሚገኙ አርሲ ራስ ደስታን ለመከታተል 1000 ከአዳሚቱሉ ጀነዋሪ 2,1937 ተንቀሳቅሏል በዚሁ ቀን ኮሮሌ ደርሰዋል፤ ከቀኛዝማች ወልደጻድቅ ጉሙት አድርገው ቀኛዝማች ወደ ሸሬ ሰለሸሸ ሸሬ በአየር እንዲደበደብ ጠይቀዋል፤ እነሱም ጀነዋሪ 3 ወደ ሸሬ ያመራሉ። ሻምበል ቱቺ ጀነዋሪ 3 ሌሎች 80 አሮሲ አሮሞ መሣሪያ የታጠቁ አርበኞቹን ለመዋጋት ስለጠየቁ እቀበላቸዋለሁ ብሏል።

ጀነራል ጀሉዞ ለግራዚያኒ ጀነዋሪ 3,1937 ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ 10 ኪሎ ሜትር ከአርባ ጉግ እንደሚገኝ እጁን እንዳይሰጥ ዋናው ተቃውሞ የሚያጋጥመው ከቀድሞ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያን መሆኑን ገልጸዋል፤ በተለይ የካሳታኛ ተልእኮ ከከሸፈ በኋላ እየተከታተሉት ይገኛሉ ብሏል[2]።

ጀነዋሪ 4 ሻምበል ቱቺ 156 የታጠቁ አርሲ ከእሱ ጉን ሆነው አርበኞቹን ለመዋጋት ጠይቋል ብሏል ሆኖም ለጊዜው አልተቀበልኳቸውም ብሏል። ሌሎች የሲዳማ ተዋጊዎች በግራዝማች መንገሥቱ የሚመሩ ከእሱ ጉን ሆነው አርበኞቹን እንዲዋጉ የጠየቁት መሆናቸውን ሻምበል ቱቺ በቴሌግራም ገልጧል። ጀሉዞ ጀነዋሪ 6 ብዛት ያላቸው መረጃ ሰጪዎችና ባንዳዎች በራስ ደስታ ዙሪያ ተሰማርቷል፤ መንገዶቹ ሁሉ በጠባቂዎች ታጥረዋል፤ በአየርም ቦታው ያለማቋረጥ እየታደበደበ ነው ብሏል። አርበኞች ካካ በሚባል ተራራ ይገኛሉ። ሻምበል ቱቺ ጀነዋሪ 6 ባስተላለፈው ቴሌግራም ባገኛቸው መረጃዎች መሰረት በከዳተኞች ኤርትራውያንና በሐበሾች ጠብ ተነስቶ ከሁለቱ ወገኖች 6 ሞቷል ብሏል።

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 773 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 847 V II



ጀነራል ጀሉዞ ጀነዋሪ ባስተላለፈው በሌላ ቴሌግራም ራስ ደስታ ዋራሉ ወድቆ ይገኛል ወደ ኬንያ ለመሸሽ ሃሳብ አለው ሆኖም የቀድሞ አስካሪ ከዳተኞቹ እና ደጃዝማች ገብረማርያም እንዳይሸሽ እንደ እስረኛ እየጠበቁት ይገኛሉ፤ ባንዳ አርሲ ከራስ ደስታ ወታደሮች ግጭት እየፈጠሩ ይገኛሉ የአየር ኃይልም ድብደባ እያካሄደ ይገኛል[1]።

ጀነዋሪ 8 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ ከአርባጉግ የለቀቀ መሆኑን አስካሪ ከዳተኞች ሸሽቶ እንዳያመልጥ እየተከታተሉት መሆኑን ገልጸዋል[2]።

ጀነዋሪ 9 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ፊታውራሪ ተሰማ እና ገረመው ወደ ጣሊያኖች ሄደው እጃቸው ለመስጠት አስበው ነበር ነገር ግን ከዳተኞች አስካሪ ተኩስ በመክፈት ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ አደረጉዋቸው[3]።

ጀነራል ጀሉዞ ጀነዋሪ 10 እና 11 ባስተላለፋቸው ቴሌግራሞች የራስ ደስታ አርበኞች ከኢጣሊያ ባንዳዎች እንደተጋጩና የዳዋ ከዳተኞች ኤርትራውያን ተካፋይ እንደነበሩ ገልጧል[4]።

ጀነዋሪ 12 ግራዚያኒ ለጀራል ባስተላለፈው ቴሌግራም የሲዳማ ፀዎች ለወደፊት ጥሩ አስካሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለጊዜው ጨቤን ይዘው ወደ ራስ ደስታ እንዲዘምቱ ማድረግ እንደሚቻል፤ ለዚሁም ከሸባዲና ባላባት ለሚሰ ዋራሞ ስምምነት እንደፈጠረና ባሉት 3000 ተዋጊዎች በቡሺራ ላይ እንዲሰማሩና ከበስተኋላው የኢጣሊያ መደበኛ ድጋፍ እንዲያደርጉለት ትእዛዝ ሰጥቶ፤ ሌሎች ባለባቶችም የእሱ አርአያ እንዲከተሉ መጣር እንደሚያስፈልግ እና ለማደፋፈሪያ በሕይወትም ሞቶም ራስ ደስታን መያዝ ለቻለ ሁሉ ገንዘብ እንደሚከፈለው እንዲነገራቸው በማለት መመሪያ ሰጥቷል። ጀነራል ጀሉዞም መልስ ሲሰጥ በትእዛዙ መሠረት እፈጽማለሁ ብሏል።

ጀነዋሪ 14 ጀነራል ጀሉዞ ለግራዚያኒ በላከው ቴሌግራም ራስ ደስታ በሬት አጥቂ ወታደሮቹ በከዳተኞች የተጠናከሩ ዛሬ የኢጣሊያ ዓረብ ሶማል ወታደሮችን አጥቅቶ በተደረገው ውጊያ ሁለት አስካሪ ሞቷል አንድ የኢጣሊያ ሶር መኰንን እና 5 አስካሪ ቆስሏል። ከራስ ደስታ ወገን የሞቱ ብዙ ናቸው ከእነሱ ውስጥም የኢጣሊያ ቡሉክባሽ የነበረው[5] ከዳተኛ አስካሪ ከራስ ደስታ ግራዝማች ሹመት ከንጉሡም ቀኛዝማች ተሰጥቶት የነበረ ተገድሏል ብሏል። ራስ ደስታ የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን በፍጥነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ ፈረሶች ዘርፎ አድሏቸዋል ብሏል።

ጀነራል ናዚ ጀነዋሪ 16 ባስተላለፈው ቴሌግራም ሊቢያውያን ወታደሮች ሰላ ካራ በተባለው ቦታ (ሐረርጌ) የተማረኩ 9 አማሮች የገደሉ መሆናቸውን ገልጧል።

ጀነራል ጀሉዞ ጀነዋሪ 17 ባስተላለፈው ቴሌግራም አርበኞች በጣሊያኖች ተኩስ እየከፈቱ እንደሚሸሹ ገልጦ ደጃዝማች ገብረማርያም እና የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ ከጣሊያኖች ጋራ በግጭት የተካፈሉ እንዳይሸሹ ይጠብቁዋቸዋል ብሏል።

ጀነራል ጀሉዞ ጀነዋሪ 20 ባስተላለፈው ቴሌግራም ወደፊት የሚገሰግሱ ወታደሮቹ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ እየገጠማቸው መሆኑን ገልጦ አርበኞቹ

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 866 V II
[2] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 874 V II
[3] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 882 V II
[4] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 887-893 V II
[5] Governo Generale A.O.I. Allegato N.909 V II

የሚመሩ በገራዝማች በቀብዞ እና በሰለባ እንዲሁም በሌላ ኤርትራዊ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ ከፍተኛ ጥቃት የሚፈጽሙበት ወቅት ነው፡፡ ጃንዋሪ 20 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም አርበኞች ባጣዳፊ ሸሽተው እየመለሱ መሆናቸውን ገለጠ ብዛት ያላቸው በጌዳ የተባሉ ሴቶችና ሕፃናት ወደ ጣሊያኖች እየተጠለሉ መሆናቸውን አስረድቷል፡፡ በሌላ ቴሌግራምም በዚሁ ዕለት አንድ ኖርወይ ተወላጅ ሐኪም ከራስ ደስታ ጋራ እንደሚገኝ ገልጧል፡፡ ከራስ ደስታ ጋራ ደጃዝማች ገብረማርያምና ጥቂት የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ እንደሚገኙ፣ ቀኛዝማች ፀጋ ጣሊያኖችን እየተቋቋመ መሆኑን ገልጧል፡፡

ሻምበል ቱቺ ጃንዋሪ 20 ባስተላለፈው ቴሌግራም አርሲ አሮሞ ወደዘማቾች 5000 ከአዳሚቱሉ የተነሱ መሆናቸውን ከእነሱ ውስጥም 1500 ጠብመንጃ የታጠቁ 2000 ፈረሰኞች እንደነበሩ ሌሎች 500 ባንዳም አብረው እንደዘመቱ ገልጧል፡፡

ጃንዋሪ 21 ጀነራል ኩበዱ (Cubeddu) ባስተላለፈው ቴሌግራም ከአርበኞች ከፍተኛ ውጊያ ተደርጎ 57 አርበኞች እንደሞቱ ከእነሱ ወስጥም ከዳተኞች የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን እንደነበሩባቸው ገልጧል፡፡ከጣሊያኖች ወገን አንድ ኢጣሊያዊና 14 ኢንዲጀኑ ሲገደሉ አንድ ኢጣሊያዊና 16 ኢንዲጀኑ ቆስሏል ሁሉም ከባንዳ፡፡ 1000 ጠብመንጃዎችና 12 መትረየሶች ተማርከዋል[1]፡፡

ጀነራል ጀሉዞ ጃንዋሪ 23 ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ ቺሬ በተባለው ቦታ ይገኝ እንደነበረ አረጋግጧል፣ የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ የሚገኙባቸው 500 አርበኞች እሱ ጋራ እንደነበሩ ገልጧል፡፡ ጃንዋሪ 24 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ከጦር ሜዳ የሚሸሹ ማየት አስደናቂ ስለሆነ በፊልም ቢቀረጽ ጥሩ ነበር ብሏል፡፡

## ጃንዋሪ 28 የነበረ ሁኔታ

ጣሊያኖች በአርበጎና፣ ከሻና፣ ቺሬ፣ ጋዮ ባደረሱባቸው ጥቃቶች አርበኞች ተበታትነው እንደገና ተደራጅተው ባለ የነበሩ የጀዝማች በየነ መርዕድም ጣሊያኖች ባደረሱባቸው ጥቃት ከቦታቸው ለቀው ኮር ከርዱቡተባለው ተራራ ሰፍረው ስለነበረ፣ ሁለቱ ቡድኖች በዚሁ ቦታ ተቀላቅለው ይገኙ ነበረ፡፡ ከዚህም አርበኞች ወደወላሞና ጉራጌ ለማምራት ሃሳብ ነበራቸው፡፡ ጣሊያኖች፡-

① ከአርባጎማና ከሸና ጀነራል ጀሉዞ

② ከቦርሊ፣ ጉራምባ ወንዶ ሻምበል ቱቺ

③ ከሻሸመኔ በዶዶላ የሰፈሩም የፓስኮሊኒ ጦር ነበረ፡፡

አርበኞች ከሁቢ እና የባና መሐል ወደ ወላሞና ከምባታ እንዳይዘልቁ ጣሊያኖች በብ ቆመው ይጠብቁዋቸው ነበር፡፡ ጃንዋሪ 31 አርበኞች በራስ ደስታ እየተመሩ ወደ ጀደብ ተራራዎች ተጠግተው የነበሩ በጣሊያኖች ጥቃት ደርሶባቸው ከፍተኛ ውጊያ ተካሄዶ ጉዳት ደረሰባቸው፣ አርበኞች በአየርም ከፍተኛ ድብደባ ይደርስባቸው ስለነበረ ተበታትነው ከጣሊያኖች ከበባ እልቂት ሊያመልጡ ችሏል፡፡ ምርኮኞች አርበኞች በውጊያ የተካፈሉ በብዙ ሺህ

(1) Governo Generale A.O.I. Allegato N. 972 V II



የሚቆጠሩ እንደነበረ የደረሰባቸው ጉዳትም በ600 የሚገመት እንደነበረ መስክረዋል፣ ፊታውራሪ ሽመልስ በውጊያው እንደተገደለ መስክረዋል፡፡

ከፌብሩዋሪ 2 ጀምሮ ጣሊያኖች አርበኞች በሄዱበት ሲከታተሉዋቸው ነበረ፣ ፌብሩዋሪ 8 ጠዋት ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ በጣሊያኖች ግምት ① 200 አርበኞች ተገደሉ ② 250 ተማረኩ ③ 350 ጠብመንጃዎችና 3 መትረየሶች ሲያዙ ④ 300 የአርበኞች ቤተሰብና አሽከሮች ተማረኩ ⑤ ብዙ መቶ የሚቆጠሩ ከብቶች ተያዙ የቀሩት አርበኞች ተበታተኑ፡፡ ጣሊያኖችም መከታተል አቁመው አርበኞች እስኪሰበሰቡ መጠበቅ መረጡ፡፡

## 3ኛ ዙር ውጊያ የፌብሩዋሪ ወር ሁለተኛ አጋማሽ

አርበኞች ወደ ሰሜንና ወደ ጉራጌ ደጋፊያቸው የነበረ ወገን መሸሻቸው ለየካቲት 12 አዲስ አበባ ላይ ግራዚያኒን ለመገደል የተቃጣ ሙከራ የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ብለው ጣሊያኖች ግምት ወስደው ነበር፡፡ የመግደል ሙከራ ቢሳካ በሚፈጠረው ውዥንብርም ተጠቅመው አርበኞች ወደ አዲስ አበባ ለመግባት ይችሉ ነበረ፡፡ ምናልባት በዚሁ ምክንያትም ከመግደል ሙከራ በኋላ በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ እንደመብረቅ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም አዲስ አበባ መግባታቸው ዜና ተሰምቶ ነበር፡፡

በዚሁ ጊዜ በአርበኞች ላይ የነበራቸው የፍርሐት ስሜት የተነሳ በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበሩ ወታደሮቻቸው በቀር ከሞላው ኢትዮጵያ የነበሩዋቸው ወታደሮች በአስር የሚቆጠሩ ጀነራሎችና ኮሎኔሎች የሚመሩ ወደ ዙዋይና ጉራጌ በገር አዘመቷቸው፡፡

በዚሁ መሠረት፡-

1. ጀነራል ናሻሬኒ ከሐይቆች አካባቢ
2. ዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች
3. ባንዳ ፔሊዛሪ (Pellizzari)
4. ባንዳ ቱቺ
5. ከሐረርጌ የሊቢያ ዲቪዚዮን በጀነራል ኩበዱ የሚመሩ
6. ምዕራብ ባቡር ሐዲድን ይጠብቁ ከነበሩ ወታደሮች አብዛኛው ዋና አዛዥ ጀነራል ጋሊና ሜምር
7. ከሰሜን ሸዋ በጀነራል ትራቢያ የሚመሩ
8. በባቡር ሐዲድ የነበሩ የጀነራል ናታሌ፣ ቶስቲ ወታደሮች
9. ባንዳ ክሪኒቲ (Criniti)

ግራዚያኒ ከሰሜን የሚዘምቱ ጣሊያኖች ጀነራል ትራቢያ ኮሎኔል ቶስቲ በጀነራል ጋሊና ስር ሆነው እንዲዘምቱ፣ ጀነራል (ቆንስል ሚስኪ) ብቻ አቦታው እንዲቀር አደረገ፣ በፋሬ አቅጣጫ ወደ ከምባታ እንዲንቀሳቀሱ አደረገ፡፡ የምዕራብ ኢትዮጵያ ጦርም በተጠንቀቅ እንዲቆም ተደርገዋል፡፡

## ፌብሩዋሪ 11-15

በአዳሚቱሉ እና በመቂ የነበሩ አርበኞች ጣሊያኖች እንቅስቃሴያቸውን እንዲከታተሏቸው ነበር፣ እንደዚሁም ከዙቋላ ወደ ጉራጌ የሚወስደው መንገድም ባንዳ ሞጆና ባንዳ አዳማ የተባሉ የአርበኞች እንቅስቃሴ እንዲከታተሉ ተደረገ፡፡

## ፌብሩዋሪ 16 እና 17

በኰሎኔል ናታሌ የሚመራ፣ በኰሎኔል ሸማከን የሚመራ፣ እንደዚሁም በጄኔራል ሚስኪ የሚመራ የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች ያሉባቸው የሻምበል ቱቺ ባንዳና የፐሊዛሪ ባንዳ የሚያጠቃልል ከመቂ በስተሰሜን አርበኞች ይገኙበታል ቡተባለ ቦታ ሰፈሩ።

## የመቂ ውጊያ

አርበኞችን ከበናል ብለው ጣሊያኖች በሚተማመኑበት ሰዓት አርበኞች ከከበባው ለመውጣት በጣሊያኖች ላይ ጥቃት ፈጸሙ፤ ከባድ ውጊያዎች ተካሄዱ። የአርበኞች ጥቃቶች ዋና ዓላማ የጣሊያኖች ጥበቃና ትኩረት አሳስተው ለማምለጥ እንዲችሉ ነበረ። አርበኞች ዕቅዳቸው ተሳክቶላቸው 12ኛ ባታሊዮን ዓረብ ሶማልና ባንዳ ፐሊዛሪ መሐል ከጥበቃ ነፃ ቦታ አግኝተው ወደ ጉራጌ ሀገር ለማምለጥ ችሏል። የሻምበል ቱቺ ባንዳዎች አርበኞችን በየሄዱበት እንዲከታተሉቸዋውና ወደ ቡታጅራ እንዲያመሩ ታዘዙ። አርበኞች የሚገኙበት ጎጀቲ መሆኑን ስለተሰማ ሁሉም ወደ ጎጀቲ በመገስገስ 1200 ከሚሆኑ አርበ ኞች ጋራ ውጊያ ገጥመው እንዲበታተኑ አደረጉዋቸው።

## ፌብሩዋሪ 20

የናታሌ ጦር ጎጀቲ እንደደረሰ ራስ ደስታ በዚሁ አካባቢ እንደሚገኝ የሚል መረጃ ያገኛል። በዚሁ ጊዜ አንድ ባታሊዮን ጦር ፊት ለፊት አጥቂ ሌላ ባታሊዮን በቀኝ አጥቂ በማሰማራት ውጊያ በአርበኞች ላይ ይከፍታል፤ አርበኞችም በኃይል እየተከላከሉ ከዋሉ በኋላ ጭለማ ይለያቸዋል። በዚሁ ቀን ውጊያው ጀግናው ደጃዝማች ገብረማርያም ተገደለ፤ ደጃዝማች በየነ መርዕድም ተማረከ ፡ አየር ኃይል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይህ የጣሊያኖች ድል ለአዲስ አበባው የመግደል ሙከራ ተገቢ የሆነ የበቀል እርምጃ ነው ብለው በመገምገም በጣም ተደስተውበታል፤ ራስ ደስታ በሽሽት አምልጧል።

## ፌብሩዋሪ 21

በዚሁ ቀን ጣሊያኖች ከጎጀቲ በስተምዕራብ አርበኞቹን በመፈለግና ሕዝቡን በመጨፍጨፍ አሰልፈዋል። የቱቺ ጦር ወደ ሸርሸራ ሰፍሮ መስካን የራስ ደስታ እናት ትውልድ ሀገር ድረስ በመሄድ እያሰሰ ነበር።

ኰሎኔል ናታለ እና ጀኔራል ጋሊና በሰሜናዊ እና ደቡባዊ ጉራጌ እያሰሱ ይሄዱ ነበር።

## ፌብሩዋሪ 22 እና 23

ጀኔራል ጋሊና ፌብሩዋሪ 22 ሞሎሁን ነበረ በ23 ቶሊ ደርሶ ነበረ። ሻምበል ቱቺ ፌብሩዋሪ 23 ራስ ደስታ ከ40 ተከታዮቹ ጋራ ሆኖ ወደ ኢዣ እንደሄደ መረጃ ያገኛል። በዚሁ ጊዜ የእሱ ባንዳዎች አንድ ሌሊቱን በመጓዝ ወደ ስፍራው ደርሶ ሳይነጋ ራስ ደስታ ያለበት ቦታ እንዲከብብና ራስ ደስታን እንዲይዝ ትእዛዝ በመስጠት ያሰማራል። ጀኔራል ጎሊና ወደ ቶሊ አቅጣጫ



ያመራል የኰሎኔል ናታሌ ጦርም በሰፊው ከበባ ለማድረግ ወደ ሆሆ ያሰማራል። ከዚህም ከቶሊ ወደ ደመራስ፣ ወልቂጤ፣ እገር፣ ጉመር፣ አርባ መዝለቅ ነበረባቸው።

## ፌብሩዋሪ 24

በዚሁ ቀን ጠዋት ራስ ደስታ የመሸገበት በባንዳ ቱቺ ተከበበ፤ አጭር ውጊያ በኋላ ራስ ደስታ ተማረከ ምህረት እንዲደረግለት [illegible] ከሰዓት በኋላ ግን ተረሸነ። ከፌብሩዋሪ 25 እስከ ማርች 4 ጀኔራል ጋሊና እና ኰሎኔል ናታለ የተበታተኑ የራስ ደስታ ጦር ፍለጋ ከቶሊ ደመራስ፣ ወልቂጤ፣ እጃ ጉመር አርባራጌ ተሰማርተው ከቆዩ በኋላ ወደእየምድብ ስራቸው ተመለሱ። ጣሊያኖች የራስ ደስታ መያዝ በየካቲት 12 ከተደረገው የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ እያያዘውታል፤ የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ [illegible] ደስታ መገደል ተበቅለናል ብሏል። የጀኔራሎችና የኰሎኔሎች ጋጋታ ተቀት አርበኞችን ለመዋጋት ነው። ጣሊያኖች የእግዚአብሔር ፍርድ ተፈጽመዋል እያሉ ጉራቸው ያሰሙ ነበረ፤ ይሁን እንጂ ትግሉ ቀጥሉ ጣሊያኖች ተሸንፈው ከአፍሪቃ ከሀገራችን ወጥቷል።

ፌብሩዋሪ 1 ቀን ጀኔራል ናዚ ባስተላለፈው ቴሌግራም ኰሎኔል ፓስኮሊኒ ተከታትሉ አርበኞችን እንዲያጠቃ ባዘዘው መሠረት አብታ በተባለው ተራራ ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ ከተማረኩ ሰዎች ከደጃዝማች በየነ መርዕድ ፊታውራሪ በሐደና ግራዝማች ደምሴ ጋራ ይኖሩ የነበሩ ሴቶች ይገኙባቸው ነበር። እነሱ በሰጡት ቃል በአርበኞች የደረሰ ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ እንደነበረ ገልጧል። እንደዚሁም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አርበኞች ከጣሊያኖች እየሸሹ ወደ ወላሞ ለመሄድ እየሞከሩ መሆናቸውን ገልጧል።

ከአርበኞች ወገን ከሞቱ መሐከል 8 ሹሞችና 50 ኤርትራውያን ከዳተኞች እንደሚገኙባቸው ተናግረዋል።

ፌብሩዋሪ 1 ቀን ጀኔራል ናዚ ባስተላለፈው በሌላ ቴሌግራም ኰሎኔል ፓስኩሊኒ (Pascolini) ከአርበኞች ጋራ ከባድ ውጊያ አድርጎ እንደነበረና የአርበኞቹም ብዛት በብዙ ሺህ የሚቆጠር እንደነበረ ከተማረኩ ሰዎች ለመረዳት እንደተቻለ፤ አርበኞችም ይመሩ የነበሩ በራስ ደስታ በደጃዝማች ገብረማርያምና በደጃዝማች በየነ መርዕድ እና በፊታውራሪ ሽመልስ እንደነበረ ገልጧል።

በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት በትክክል ባይታወቅም ከፍተኛ ነው ብሏል፤ በጣሊያኖች ወገን የደረሰው ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ አንድ መቶ የሚጠጉ ነበሩ። ከቆሰሉ መሐል አንድ የኢጣሊያ የጦር መኮንን ብቻ ነበረ።

እላይ ስለተጠቀሰው ውጊያ አስመልክቶ ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጀኔራል ናዚ ያልገለጠው የተማረኩ ሴቶች የተገደሉ መሆናቸውን ገልጧል[1]።

ፌብሩዋሪ 3 ግራዚያኒ በየባኖ ስለተደረገው ውጊያ አስመልክቶ ባስተላለፈው ቴሌግራም[2] በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ 200 የሚጠጋ ነበረ 4 የጦር መኮንኖች ተገድለዋል 4 ቆስሏል። በአርበኞች የደረሰ ጉዳት እንደ አንድ ቱራ ነው ብሏል። ይህ ኰሎኔል ፓስኩሊኒ ያደረገው ውጊያ ነው። በዚሁ ቀን በዚሁ አካባቢ ናዚ ሻምበል ቱቺ ከአርበኞች ጋራ ስላደረገው

---

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 1046 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 1047 V II

(አርበኞች) ከመኖታቸው በላይ መሪዎቻቸው ደጃዝማች በየነ መርዕድ ጎበረግርያም የተገደሉ መሆናቸውን፣ ራስ ደስታ ቆስሉ ሸሽቶ ያመለጠ መሆኑን አብራርተዋቸዋል። ለጣሊያኖች ተፋቻ ያሳየ የጎጀቲ መንደር ተገቢውን ቅጣት የደረሰበት መሆኑን ገልጧል። ፌብሩዋሪ 23 ጄነራል ጋሊና ቶሊ መንደር ደርሶ በመንደሩ ሕዝብ እንዳላገኘ ገልጧል፣ ራስ ደስታ 2 ቀን በፊት 3 ሰዓት በእግር መንገድ ርቆ የሚገኘው ከጊ ከሚባለው መንደር ደርሶ መንደሩን እንዳቃጠለው ገልጧል እንድ ባታሊዮን ጦር አጋማይ ወደሚባለው መንደር ልኮ ጎበረግርያም የሚኖርበት ስለሆነ ስለ ራስ ደስታ የት እንደሚገኝ መረጃ ለማግኘት በመንደሩ ሕዝብም የመቀጣጫ ጭፍጨፋ ለማካሄድ ነበር፣ የተገኙ መረጃዎች ግን የተለያዩና ተቃራኒ ነበሩ ብሏል። ከዚና አጋማይ የተባሉ መንደሮች የሸፍቶች ቤተሰቦች መኖሪያ ስለሆኑ እንዲወድሙ ተደርገዋል። ራስ ደስታ ባለፈው ምሽት 4 ሰዓት በዚሁ ከጊ መንደር እንዳለፈና ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ እንደሄደ፣ ፊታውራሪ ታደሰ 30 ተዋጊዎች ጋራ አብሮ እንደነበረ፣ ራስ ደስታ በተቅማጥ ይሰቃይ እንደነበረ፣ የጎበረግርያም ሚስት 100 ታጣቂዎች አስከትላ ቶኮር ወደ ተባለው 3 ቀን እግር የሚርቅ መንደር እንዳመራች፣ ቺምባላ ቱቺ መስክን የራስ ደስታ እናት የቀድሞ መኖሪያ ድረስ በመዝለቅ ያገኘው ነገር እንዳልነበረ፣ ለማግስቱ ጠዋት ሐቦ ወደ ተባለው ቦታ አርበኞች ያመሩበት ነው ስለተባለ እስካሁ እንደሚልክ ገልጧል።

ፌብሩዋሪ 24[1] ከዋናው መሥሪያ ቤት ከአዲስ አበባ በኢታ ማጆር ስም ለሁሉ የጦር ክፍሎች የተላለፈው ቴሌግራም ፌብሩዋሪ 19 (የካቲት 12) እየቱሪ የመግደል ሙከራ በኋላ ሽፍትነት የሚገኙ መሪዎች ሁሉ ከሽመልስ በኋላ በየነ መርዕድ በኋላም ጎበረግርያም ዛሬም ራስ ደስታ በቺምባላ ቱቺ ጦር ተማርኮ ስለተገደለ የእግዚአብሔር ፍትሕ ፍርዱን ሰጥቷል ብሏል።

በዚሁ ቀን ፌብሩዋሪ 24, 1937[2] ከመትር ለየት ያለ ረጅም የራግርት ቴሌግራም ግራዚያኒ ለዱቼ ሙሶሊኒ በላከው ዱቼ ሆይ በማለት ይጀምራል ከራስ እምሩ መያዝ በኋላ የመጨረሻው የተቃዋሚዎች መሪ ራስ ደስታን ለማመሪያም በዐጡኝ ትእዛዝ መሠረት፣ እኛን በሰላም እንዲሰጥ የተደረገ ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ከበርንትዮ እኛን በሰላም እንዲሰጥ 7 ቀናት ጊዜ እንዲሰጠውና ተጐ ካለፈ በኋላ ግን ምህረት እንደማይደረግለት በሰጡኝ መመሪያ መሠረት የተሰጠው ጊዜ እንዳለፈ እኔ ራሴ በራስ ደስታ ላይ የሚደረገው ዘመቻ ለመምራት ወደ ይርጋጨፌ ሄጄ ነበር። በአርባጉግና ከሸና በተደረጉ ውጊያዎች የገላ ዶል 1ኛ መቻበሊያ በሚከበርበት ጃንዋሪ 20-21-22 ራስ ደስታ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶበት 500 ጠበመንጃዎች 30 መትረየሶችና 4 መድፎች ተማርከው ነበር። ደጃዝማች በየነ መርዕድ በነበረበት በባሌ ከፍተኛ ጥቃት ከጣሊያኖች ስለደረሰበት ወላም በጣሊያኖች ያልተያዘ ስለመሰለው ወደ ወላም ለማምራት በማሰብ ከጣሊያኖች ጦር ተበቃ እምልጦ በየባና ለማለፍ ችሎ ስለነበረ ራስ ደስታ ያለበትው ድጋፍ ለማግኘት ችሎ ነበር። በዚሁ ጊዜ በራስ ደስታ ላይ እንደዚሁም በደጃዝማች ጎበረግርያም ላይና ሲከተሉት በነበሩት የዓዋ ከሓተኞች ኤርትራውያን፣ ከእነሱ ጋራ በተቀላቀለው የበየነ መርዕድ ኃይለኛ ጦር ላይ ፣ በጄነራል ናዚና በጄነራል ጄሎሶ የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በማምራ ጥቃት እንዲፈጽሙባቸው አዘዝኩ። በስከተለው ከባድ የየዓና ውርጎቶች ከትልቁ የሊቢያ ዲቪዚዮን ብቻው 7 የጦር መኰንኖችና

---

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1155 V II
[2] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1156 V II






ራስ ደስታ በጫካ በቡታጀራ ከመገደሉ ጥቂት ሰዓት በፊት

(fot. «Illustrazione Italiana»)

Ras Destà, subito dopo la cattura,
viene interrogato davanti al Tribunale di guerra



ራስ ደስታ የተገደለበት
አጠገብ የሚገኘው ዛፍ

Buttagerà — L'Albero presso cui fu ucciso Ras Destà

ሰለ ውጊያ ባስተላለፈው ቴሌግራም በአርበኞች የደረሰው ጉዳት 60 ተገድሏል፣ ከባንዳ ቱቺ የሞቱ 22 የቆሰሉ 23 ነበሩ። በኩሉኔል ፓስኮሊኒ ጦር ላይ የደረሰው ጉዳት በትክክል እንደሚከተለው ነበረ ብሏል። 3 የጦር መኮንኖች ተገድለዋል 5 ቆስሏል የኢጣሊያ ተራ ወታደር የቆሰለ 1 ኢንዲጄኒ የተገደሉ 100 የቆሰሉ 138። በዚሁ ቀን ናዚ ባስተላለፈው ቴሌግራም የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች የስም ዝርዝር ከገለጸ በኋላ ከሊቢያ የሞቱ 53 የቆሰሉ 102፣ ከባንዳ የሞቱ 47 የቆሰሉ 36 መሆናቸውን አስረድቷል።

ከዚህ በላይ ስለተጠቀሱ ውጊያዎች አስመልክቶ ግራዚያኒ ፌብሩዋሪ 5 ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጄነራል ናዚ ያልገለጸው የተማረኩ ሰዎች (ሴቶች ቤተሰቦች ጭምር) የተገደሉ መሆናቸውን ገልጿል።[1]

ፌብሩዋሪ 20 ኩሉኔል ናታለ ባስተላለፈው ቴሌግራም የራስ ደስታ ተዋጊዎች ከጎጂቲ በስተደቡብ እንደሚገኙ ከማረካቸው ሰዎች ባገኛቸው መረጃዎች ለማወቅ መቻሉን ገልጾ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም ወደ ስልጤ እያመሩ መሆናቸውን፣ ደጃዝማች መርዕድ ሚስቱ ቆስለው ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ሃሳብ እንዳላቸው አብራርቷል።

ፌብሩዋሪ 20 ኩሉኔል ናታለ ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ከጎጂቲ መንደር በስተሰሜን ውጊያዎች እየተካሄደ መሆናቸውን፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድ ፊታውራሪ ተሰማ ወልደጊዮርጊስ፣ ቀኛዝማች በላይነህ ዲሉ፣ ቀኛዝማች ደባብሀ አካሉ የተማረኩ መሆናቸውን ገልጿል። በውጊያው ተካፋይ የነበሩ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም መቁሰላቸው አለመቁሰላቸው ለማረጋገጥ አልቻልኩም ብሏል። በተገኘው ድል ተጠቅሜ አርበኞቹን ለማሳደድ 2 ባታሊዮን ጦር እንዲላኩልኝ እለምናለሁ። በሁለቱ ወገን የደረሰ ጉዳት ለወደፊት አገልጻለሁ፣ በጎጂቲ በስተሰሜን ራስ ደስታ ሊገኝበት ስለሚችል በአየር እንዲደበደብ እለምናለሁ ብሏል።

ፌብሩዋሪ 21 [2] ኮሉኔል ናታለ ባስተላለፈው ቴሌግራም ትናንት በጎጂቲ የተካሄደው ውጊያ ውጤት እየሰጠ ነው፤ በአሁኑ ሰዓት ትናንት ጦርነቱን ይመራ የነበረው የደጃዝማች ገብረማርያም ሞት እያረጋገጥኩሁ ነው። የደጃዝማች ገብረማርያም የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አስከሬን ፎቶግራፍ አስነሥቼ ደጃዝማች በየነ መርዕድ፣ ፊታውራሪ ተሰማ፣ ደጃዝማች ተክሉ፣ እንዲሁም የአርመን ዜጋ የሆነች ሴት ሁሉም በአንድነት ደጃዝማች ገብረማርያም መሆኑን አረጋግጠው መስክረዋል።

ፌብሩዋሪ 21 ጄነራል ጊስኪ ባስተላለፈው ቴሌግራም የበየነ መርዕድ ልጅ ተሰልቦ በመንገድ አግኝቶ እንደሰበሰበው ገልጿል፣ በጣሊያኑ ፐሊዛሬና በግራዝማች ጋሰባ የሚመሩ ባንዳዎች አሰሳ አድርገው 200 ሰዎች መያዛቸውን ከእነሱ ውስጥም 60 ባለመማረያ እንደነበሩ ገልጿል። እስካሁን በተደረገው አሰሳ 635 ሰዎች ለውጊያ ብቁ የሆኑ ከ1200 የሚበልጡ ሴቶች ሕፃናት ሽማግሌዎች ተማርከዋል። ከአርበኞች ወገን የደረሰ ጉዳት የሞቱ 300 ሰዎች ናቸው፣ ከጣሊያኖች ወገን የደረሰ ጉዳት ገና አልተረጋገጠም ብሏል።

ፌብሩዋሪ 22 ጄነራል ጋሪቦልዲ ከአዲስ አበባ ለተለያዩ የጦር ክፍሎች በላከው ቴሌግራም በኮሉኔል ፓስኮሊኒ PASCOLINI የሚመሩ ተዋጊዎች ባካሄዱት ውጊያ ፊታውራሪ ሽመልስ ተገድለዋል። በሐይቆችና በጎጂቲ በናታለ ቱቼ ፐሊዛሬ የሚመሩ ወታደሮች እንደዚሁም በጄነራል ጊስኪ የሚመሩ 12ኛ ግሬብ ሶማል ወታደሮች ባደረጉዋቸው ውጊያዎች በብዙ መቶ ሽፍቶች

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N. 1059 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N. 1138 V II



300 ወታደሮች ተገድለዋል። ከዚህ በኋላ ከብዙ ቦታዎች ባገኘናቸው መረጃዎች የሽፍቶች (አርበኞች) መሰብሰቢያ ጉራጌና ከምባታ መሆናቸውን ስለታወቀ በእነዚህ ቦታዎች እንድናተኩር ተደረገ። በዚሁ መሠረት ከጄነራል ጋሊናና ጄነራል ጊስኪ እንደዚሁም ኩሉኔል ናታሌ በሞጆ ለስብሰባ ተቀምጠን በሁለት አቅጣጫ ወደ ጉራጌና ከምባታ እንዲዘምቱ አደረግሁ። የዚሁ ታክቲክ ውጤት ሙሉ በሙሉ የተሳካ ስለሆነ ኩሉኔል ናታሌ በጎጂቲ ባካሄደው ጦርነት በየነ መርዕድን በቁጥጥሩ ስር በማዋል እንዲረሸን ከማድረጉም በላይ ገብረማርያም ተገደኛ የኢጣሊያ ጠላት ነው፣ በ1931 የኢትዮጵያ ጦር በመምራት ሶማሊያን ለመቆጣጠርና ለመያዝ እቅድ ነበረው። የጎጂቲ ጦርነት ይመራ የነበረው በራስ ደስታ ነበረ፣ እሱ ግን አምልጦ ለመሸሽ ችሎ ነበር ሆኖም በጉበዙ ሻምበል ቱቺ የሚመሩ የደጃዝማች ተክሉ ፀትገራይ ባንዳዎች ተማርኮ ወዲያውኑ በጥይት ተደብድቦ እንዲገደል ተደርገዋል። በዚሁ ወቅትም በሕይወቴ ላይ የመግደል ሙከራ የተቃጣበት ነበር፣ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም ተበሩ በመቁረጥ ወደ ሰሜን በሚሸሹበት ጊዜ አዲስ አበባን ለመያዝ እየገሰገሱ ነው የሚል ወሬ በአዲስ አበባ ይናፈስ ነበረ። ዱቼ ሆይ ይህ የሕሊና ዕረፍት የሚሰጠን ድል ለክቡርነትዎ እያበረከትኩ፣ ከእንግዲህ በምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር፣ በሸዋ በሚፍጨረጨሩ ተቃዋሚ ኃይሎችን ለመደምሰስ ብቻ እናተኩራለን የክቡርነትዎ ፍጹም ታማኝ በማለት ሪፖርቱን ደምድሟል። በዚሁ ቀን ፌብሩዋሪ 24 ሻምበል ቱቺ ለግራዚያኒ በላከው ቴሌግራም ዛሬ 24 ከጠዋቱ 12 ሰዓት የእኔ ተዋጊዎች ራስ ደስታ ዳምጠው ማርከዋል፣ ክቡር የመንግሥት መሪ (ሙሶሊኒ) በሰጡት ትእዛዝ መሠረት በምሽቱ በ11፡30 በጥይት ተደብድቦ ተረሽኗል ብሏል።

በዚሁ ቀን ሻምበል ቱቺ ዝርዝር ማብራሪያ ሲሰጥ ራስ ደስታ ወደሸሸበት ከእኔ ባንዳዎች በቂ ኃይል ልኬ ሙሉ ሌሊት ተጉዘው ራስ ደስታ ከ5 ሹሞች ሌሎች አርበኞች ይገኙበት ወደነበረ ምሑር ደርሰው ባንዳዎች ሌሊቱ መንደሩን ከበበው ከአጭር ውጊያ በኋላ ውጊያን በማቆም እጃቸውን ለባንዳዎች ይሰጣል። በዚሁ ውጊያ ፊታውራሪ ካሣ ባራምባራስ ተሰማ ልጅ ረጋ ፀሐፊው ኢልያስና 20 አርበኞች ተገድለዋል፣ ሌሎች የራስ ደስታ ተከታዮች አርበኞች የቆሰሉ ወደ እኔ ድንኳን እየመጡ ይገኛሉ። ከእኔ ባንዳ ጉዳት አልደረሰም፣ 2 መትረየስና 40 ጠብመንጃዎች ተማርከዋል። ከመረሸኑ በፊት ራስ ደስታ በደጃዝማች ተክሉ መሸሻ እንደተያዘ የሚል ጽሑፍ አስፈርሚያለሁ ብሏል[1]።

## ረ. ጨርጨር አርሲ

መጀመሪያ ዙር ብለው ጣሊያኖች የጠሩት በጨርጨርና ጋራሙለታ በፊታውራሪ በሐደና ፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ አርበኞች ላይ ብዙ ወታደሮች ከማሰማራታቸው በላይ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጀግኖች ወደ ጣሊያኖች የገቡ በቀድሞ ጀግና በፊታውራሪ ጊሊዮንና በሌሎች መሪዎች ባንዳዎች ሳይሆን አርበኞች የሚል መጠሪያ በጣሊያኖች የተሰጣቸው እየተረዱ ነበረ። ዋናዎቹ የአርበኞች መሪዎችና ተዋጊዎች በጣሊያኖች ሳይገደሉ ወይንም ሳይማረኩ ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ ችሏል። የጣሊያኖች ዋና ዓላማ የባቡር ሐዲድ ለትራፊክ አስተማማኝ ለማድረግ ነበር። በአርሲ የሰፈሩ አርበኞች

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1159 V II

ከሠርሠር ጋራሙለታ የሸሹ በፊታውራሪ በሐደና ሺመልስ የሚመሩ እንደዚሁም በስፍራው የነበሩ በልጅ አበበ ዳጋፋር የሚመሩ ነበሩ፣ ጉት በሚባሉ ተራራዎች ከገለምሶና ጨለል መሐል የሰፈሩ 6000 የሚያጠቃልል ነበረ፡፡ ቀተሉ ግን በጣሊያኖች ተሰብኮ ልጅ አበበ ደጋፋር ወደ ጣሊያኖች ከመግባቱም በላይ ከጉናቸው ተሰልፎ አርበኞችን እንዲዋጋ በጠየቀው መሠረት ተፈቅዶለት ባንዳ ሆኖ ነበር፡፡ 2ኛው የአርበኞች ቡድን ቢራቆ በጢቾ ይገኝ የነበረ ነው፤ 5000 ተዋጊዎች ነበሩት ከየረር ውጊያ ሸሽተው ወደዚሁ ቦታ የሰፈሩ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ አርበኞች ከጣሊያኖች በደረሰባቸው ጥቃት በማምለጥ በፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ 1000 በፊታውራሪ በሐደ የሚመሩ 4000 ወደ ሲዳሞ በማምራት ከራስ ደስታና በየነ መርዕድ ጦር ሊቀላቀሉ ችሏል፡፡

በደሰምበር መጨረሻ ጣሊያኖች የአርበኞች መፈራረስ ምልክት በማለት ደስ ያሰኛቸው ተፈጠረ፡፡ በፊታውራሪ ሺመልስና በቀለ አየለ አርበኞች ከፊታውራሪ ወሊሺ አርበኞች ያለመግባባት ተፈጥሮ ግጭት ተፈጥሮ ፊታውራሪ ወሊሺ ለጣሊያኖች እጁን ሰጥቷል፡፡

## ሠ. ባለ

አርበኞችን ለማጥፋት የተዘጋጁ ጣሊያን ወገን የሚከተሉ ነበሩ፡፡

1. 11ኛ የአማራ ባታሊዮን በደዳቻና ሳያማና መሐል
2. 38ኛ የሶማል ባታሊዮን በሸዳላና እንቾራ መሐከል
3. የምሥራቅ አፋሲ ጦር ሀ/37ኛ የአማራ ባታሊዮን ለ/4ኛ የሶማል ባታሊዮን እና ሐ/ ዱባት ከእንቾራና መአቡል ቃሲም መሐል
4. የሠርሠርና ግራሙለታ ጦር 5ኛ ሀ/ የሶማል ባታሊዮን ለ/ ዱባት ሐ/ የ1ኛ ባታሊዮን በከፊል ከአቡል ቃሲምና መልካ ጊልኪ መሐል
5. በጦር ሰፈሮች (ጊልከይ፣ ግልካ ቲቢ እግጋሎ) የሰፈሩ
6. ባሂቱ ባንዳ ከጊኘር በስተምሥራቅ
7. ዳሎ ባንዳ በማእከላዊ መንግሥት የሚታዘዝ

በአርበኞች ወገን የተሰለፉ የሚከተሉት ነበረ

1. በፊታውራሪ ሻለቃ አሰፋው የሚመሩ አብዛኛው የቀድሞ የኢትዮጵያ መደበኛ ጦር 1700 ወታደር 50 መትረየሶች የነበራቸው በጉሬ አካባቢ ሰፍረው ነበር፡፡
2. በፊታውራሪ በሐደ የሚመሩ 1200 በማኮና አካባቢ
2. በፊታውራሪ ተሰማ የሚመሩ በጥቂት መቶ የሚገመቱ ከጊኘርና ማላጎ መሐል የሰፈሩ
4. በቀኛዝማች ተዘራ የሚመሩ በጥቂት መቶ የሚገመቱ በዓራብሊግ ተራራ የሰፈሩ
5. በባራምባራስ አለምሴ የሚመሩ 300 በኢጀርሳ የሰፈሩ

### ሀ/ የጉሬዱ ውጊያ ፌብሩዋሪ 22-23

ውጊያው በሻለቃ አሰፋው የሚመሩ አርበኞች ፌብሩዋሪ 22 ሌሊት በጀኔራል ኩበዱ የሚመሩ የኢጣሊያ ጦርን በማጥቃት ተጀመረ፡፡ ሲነጋ መልሶ ማጥቃት አካሄደው፤ ከቀኑ 6 ሰዓት ከአርበኞች የተሰነዘረባቸው ሌላ ጥቃትን በመመለስ በአሬዮፕላኖች እየታገዙ 2 ሰዓት የቆየ ውጊያ ተካሂዶ አርበኞችን ሊያባርሩ ችሏል፡፡ አርበኞች 150 ወታደሮች ተገድሉባቸዋል፡፡



### ለ/ የታማሞ ውጊያ

ማርች 2 ሌሊት አርበኞች በታማሞ ተራራ ሰፍረው እንደሚገኙ ስለታወቀ የጀኔራል ኩበዱ ጦር በዋት ጉዞውን ጀምሮ ከቀኑ 10 ሰዓት የአራብሊግና ታማሞ ተራራ ደረሰ፣ ቦታው በአርበኞች እንደተያዘ ተረጋገጠ፡፡ የአርበኞች ተዋጊዎች ብዛት 2200 ነበረ፣ 50 መትረየሶች ነበራቸው፡፡ 7ኛና 9ኛ የሊቢያ ባታሊዮን ከካባድ ውጊያ በኋላ ታማሞን ሲቆጣጠሩ አርበኞች በማፈግፈግ አምልጠው ከቦታው ለቀዋል፡፡ አርበኞች 500 ተገድሉባቸዋል፣ ከሞትም መሐከል ፊታውራሪ ተፈራ ይገኝበታል፡፡

### ሐ/ የዋራ ቆምቦ ውጊያ

በኮሎኔል በሪዮ (Berio) የሚመራ ሌላ የኢጣሊያ ጦር ወደ ጊኘር እያማራ የነበረ ማርችን ዋራ ቆምቦ ወንዝ ደርሶ ከወንዙ በስተግራ የሰፈሩ አርበኞችን ጥቃት ሰነዘረ፣ ከባድ ውጊያ ተካሄዶ አርበኞች ወደ ጊኘር አፈገፈጉ አርበኞች መልሶ ማጥቃት አካሂደው ነበር ጣሊያኖችም ተከላከሉዋቸዋል፡፡ ከአርበኞች የተገደሉ 200 መሆናቸውን ተገመቷል፣ ከሞቱት መሐከል ግራዝማች እምሩ ይገኝበታል፡፡ በዚሁ ቦታ ጣሊያኖች ወድቆ የተከሰከሰ የራሳቸው አሬዮፕላኖች ስብርባሬ አገኙ፡፡ የሰፈሩ ሰዎች እንደመሰከሩ የግራዝማች እምሩ አርበኞች በአሬዮፕላኑ ውስጥ ከነበሩ ጣሊያኖች ውጊያ ገጥመው 4 ጣሊያኖች ሲገደሉ 5ኛ ተማርኮ ከፊታውራሪ በሐደ ጋራ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ እንደተወሰደ ተናግረዋል፡፡

### መ/ የጉሬ ውጊያ

በጀኔራል ኩበዱ የሚመሩ ጣሊያኖች ታማሞን ተቆጣጥረው ከሰነበቱ በኋላ ማርች 5 ወደ ጉሬ አመርተው አቢናስ ተራራ ሲደርሱ ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተባቸው፡፡ አርበኞች በሻለቃ አሰፋው የሚመሩ የፊታውራሪ በሐደ የተቀላቀሉባቸው ነበሩ፡፡ በጨበጣ ሳይቀር ከባድ ውጊያ ተካሂደ አርበኞች ከጉሬ ለቀው ወጥተዋል፡፡ በአርበኞች የደረሰው ጉዳት የተገደሉ 200 ነበሩ፡፡

በዚሁ በባሌ የሚደረገው ውጊያ የተደመደመ መሆኑን ገምቷል፡፡

ከፌብሩዋሪ 22 እስከ ማርች 14 በባሌ በተደረጉ ውጊያዎች የደረሱ ጉዳቶች ከሁለቱ ወገኖች የሚከተለው ነበረ፡፡

### ሀ/ ከአርበኞች

1. በጦር ሜዳ የተገደሉ 1000 የሚጠጉ
2. ተማርከው የተገደሉ 500
3. የተማረኩ ባለታዮት 3000

የተማረኩ የጦር መሣሪያዎች 8.500 ጠብመንጃዎች 53 መትረየሶች መድፎች 3

### ለ/ ከጣሊይኖች

1. የጦር መኩንኖች የተገደሉ 3 የቆሰሉ 3
2. ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች የተገደሉ 2 የቆሰሉ 3

3. ኢንዲጀኒ የተገደሉ 56 የቆሰሉ 138

## ሰ/ የአርሆ ውጊያ

በባሌ ከተጠቀሱት ውጊያዎች በኋላ ጣሊያኖች አርበኞችን በማሳደድ ላይ ይገኙ ነበሩ። አፕሪል 11 38ኛ የሶማል ባታሊዮን በአርሆ አጠገብ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከከባድ ውጊያ በኋላ ከአርበኞች ወገን ከመቶ የሚበልጡ ተገድለዋል፤ ከጣሊያኖች ወገን 2 የጦር መኰንኖች ሲቆስሉ 15 አስካሪ ተገድለዋል 50 ቆስሏል። በፊታውራሪ በሐይደ ተማርኮ ተወስዶ የነበረ ኢጣሊያዊ የአሬዮፕላን አብራሪ በውጊያው ተገድለዋል። ፊታውራሪ በሐይደ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ገብቷል።

በዚሁ ዓይነት የባሌ ውጊያ ፍጻሜ ያገኘ መሆኑን ጣሊያኖች ገምቷል።

ስለ ጉሬዶ ሌሊት በ22 ፌብሩዋሪ የተደረገው ውጊያ ጀኔራል ናዚ ባደረገው ሪፖርት 2 ባለ ጥቁር ሸሚዝ የኢጣሊያ ወታደሮች ተገድለዋል፤ 1 ቆስሏል 2 ሊቢያውያን ተገድለዋል። በጥዋቱ ውጊያ አንድ የጦር መኰንን ሲቆስል ሊብያውያን አንድ ተገድሎ 6 ቆስሏል። በጥሻ ሆነው የኢጣሊያ ጥቃት የሞከሩ ሁሉ ተማርከው ተገድለዋል። ጣሊያኖች አርበኞችን በሚያሳድዱበት ጊዜ አንድ መቶ አለቃ በከባድ ቆስሏል አንድ 50 አለቃ በቀላል ቆስሏል። ከ1ኛ እግረኛ ሊቢያውያን 1 ሲሞት 8 ቆስሏል፤ ከ4ኛ እግረኛ ሊቢያውያን 1 ሲገደል 11 ቆስሏል፤ ከአርሞ አርበኞች (ባንዳ) 2 ሲገደሉ 5 ቆስሏል የተማረኩ 30 አርበኞች ተገድለዋል።

በዋራ ቆምቦ በተካሄደው ውጊያ የተማረኩ 15 ምርኮኞች ተገድለዋል። 2 ጣሊያኖች ቆስሏል። 13 ኢንዲጀኒ ሊቢያውያን ሲገደሉ 25 ቆስሏል። እጃቸውን ለመስጠት የቀረቡ ከጊኘር የመጡ ፊታውራሪ ተሰማና ቀኛዝማች ግዛው አብረው ከቀረቡ አርበኞች ጋራ ተገድለዋል።[1] ጀኔራል ኩበዱ አሰሳ በሚያደርግበት ጊዜ 20 አርበኞችና ሌሎችም ቤቶቹ ሕፃናት ተማርከው ተገድለዋል። በተጨማሪም ግራዝማች ይልማና 40 የተማረኩ ወይንም እጃቸው የሰጡ አርበኞች ተገድለዋል።[2] ማርች 5 በጉሬ በተካሄደው ውጊያ ጀኔራል ናዚ ባደረገው ቴሌግራም መሠረት 2 ጣሊያኖች የጦር መኰንኖች ተገድለዋል፤ አንድ ባለ ሌላ ማዕረግ ቆስሏል። 31 ኢንዲጀኒ አስካሪ ሊቢያውያን ሲገደሉ 80 ቆስሏል። 3 ባንዳ ተገድለዋል።

በምዕራብ ባሌ የዳሎ (Dallo) ባንዳ አዛዥ የተማረኩ 29 የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ተገድለዋል[3]።

ማርሻል ግራዚያኒ ማርች 13 ለጀኔራል ናዚ በላከው ቴሌግራም የኢጣሊያ እምባገነን መሪ ዱቼ ሙሶሊኒ በግራዚያኒ በኩል ጀኔራል ናዚ በመፈጸም ላይ ያለው ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ መደሰቱን የላከለት መሆኑን ገልጾ እሱም በበኩሉ በቃል እንደነገርኩህ ሁሉ በመፈጸም ላይ ያለኸው ተግባር ትምህርት ሰጪና ወሳኝነት ያለው ብሏል[4]። አርሆ አፕሪል 11 ስለተደረገው ውጊያ ግራዚያኒ እንደገለጸው 2 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች ቆስሏል 15 አስካሪ ተገድሏል 50 ቆስሏል ብሏል። ጀኔራል ናዚ በበኩሉ ስለዚህ ውጊያ በላከው ቴሌግራም ብዛት ያላቸው አርበኞች ቆስለው ወይንም ሳይቆስሉ የተማረኩ

(1) Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1171 V II
(2) Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1172 V II
(3) Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1174 V II
(4) Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1192 V II



ተገድለዋል። በተጨማሪም ጣሊያኖች አሰሳ በሚያደርጉበት ጊዜ የማረኩዋቸው የሚሸሹ 26 አርበኞች ተገድለዋል።

## ቀ. ሰላሌ

በኖቬምበር መጨረሻ በሸዋ የነበሩ ዋናዎቹ የአርበኞች ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው።

1. በሬቹ ወንድማሞቹ አበራና አስፋወሰን ካሣ፤ ልጅ መስፍን ስለሺ።
2. በግንደበረትና ሙገር ዘውዱ አስፋው
3. ወጫሌ (ከዱበር ወንዝ በስተሰሜን፤ የአበራ ካሣ የበታች ሹሞች
4. ደነባ ወደ ወረኢሉ በሚወስደው መንገድ አበበ አረጋይ.

አበበ አረጋይ በጣሊያኖች የተሾሙ አስተዳዳሪዎች እየሻረ የራሱ ይመድብ ነበረ።

በሸዋ አርበኞችን ለማጥፋት የተመደቡ የኢጣሊያ ወታደሮች ሀ/ በደብረብርሃን ለ/ በአዲስ አበባ ሐ/ በአምቦ መ/ በደብረማርቆስ ሰ/ በደብረሲናና ደባ ሰፈረው ነበር። ጣሊያኖች በሚስጢር የተያዘ "F" ብለው የሰየሙት ፕላን አውጥተው ነበር። ለዚሁ ዘመቻ 1. በባሌ 2. ትራኪያ 3. ጋሬሊ 4. ቶስቲ 5. ናታሌ 6. የአልፒን ባታሊዮን 7. የወንዝ ጠባቂ ቡድን ተዘጋጅተው ነበር።

ከአርበኞች መሪዎች ድፍረትና ንቃት የተሞላበት እንቅስቃሴዎች ይወስድ የነበረ አበበ አረጋይ ነበረ። ጀኔራል ትራኪያ የአርበኞች መሪ የአበበ አረጋይ ጦር ለመደምሰስ በመንዲዳ ብቻ በመወሰን የኢጣሊያ ኃይል የማሳየት እርምጃ እንዲወሰድ ጠይቆ ስለተፈቀደለት፤ ጀኔራል ትራኪያ 1ኛ 3ባታሊዮኖች ኤርትራውያን፤ 2ኛ የደብረብርሃንና የሸዋ ባንዳዎች 3ኛ ከባድ መሣሪያዎች በመያዝ ወደ መንዲዳ አመራ። በጀኔራል ቶስቲ የሚመራ ጦርም የኢጣሊያ ኃይል ለማሳየት ወደ ደነባ አመራ። ጀኔራል ትራኪያ ዲሴምበር 9 መንዲዳን ሲቆጣጠር በአበበ አረጋይ ቤተሰቦችና ንብረቶች ላይ የበቀል እርምጃ ወሰዷል። በዋብስ የሚደረገው ጥቃት በአየር ኃይል የተደገፈ ነበር። አርበኞች ጣሊያኖችን ሳይገጥሙ ወደ ሩቅ አፈገፈጉ። ከዚህ በኋላ አርበኞች በቀላሉ የማይበገሩ መሆናቸውን ስላወቀ ግራዚያኒ የ"F" ምስጢራዊ ፕላን በሥራ ላይ እንዲውል ትእዛዝ በመስጠት 1. ትራኪያ 2. ቶስቲ 3. ጋሬሊ 4. በሊ 5. ናታሌ የሚመሩ ጦሮች አሰማራ።

ዘመቻው የሚመራው ራሱ ግራዚያኒ ነበረ፤

1. በትራኪያ ቶስቲ የሚመሩ ወታደሮችና የደብረብርሃንና የሸዋ ባንዳዎች ያሉባቸው በሁለት መስመሮች ከደነባ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ መራመድ ነበረባቸው።
2. በጋሬሊ የሚመራ ጦር ከእንጦጦ ወደ ሰሜን እንዲያመራ
3. በበሊ የሚመራ ጦር የራስ ኃይሉ ባንዳ ያለበት ከአምቦ ወደ ሰሜን ምሥራቅ እንዲያመራ
4. በናታሌ የሚመራ ጦር ከየኪተል (ጉጀም) አባይን በ[illegible] ተሻግሮ በአባና ኢዳቦ ወደ ሩቅ ማምራት ነበረበት።

በዚሁ መሠረት አርበኞቹ በሁሉም አቅጣጫ ስለተከበቡ ማምለጫ አልነበራቸውም፤ በሬቹ ተሰባስበው ነበረ።

ደሰምበር 19 በጉር ወንዝ ዘውዴ አባኮራን እና ዘውዴ አባፋርዳ የተባሉ አርበኞች በጣሊያኖች ላይ ተኩስ ይከፍታሉ፣ ሆኖም በጣሊያኖች መደበኛና ባንዳ ወታደሮች ተባርረዋል።

በመቱ ዋሻ በሰፈሩ አርበኞች ላይ ጣሊያኖች ጥቃት ፈጽመው 150 አርበኞችን፣ ገድለው በመንደሩ ላይ የበቀል እርምጃ መቀጫ ወስደዋል፤ ደብረሊባኖስን ተቆጣጥረዋል እንደዚሁም ፍቼን ተቆጣጠሩ። ግራዚያኒ ለወታደሮቹ የሰጠው መመሪያ በአሁኑ ሰዓት የዘመቻ ዓላማ 1. አበራ ካሣን ለመያዝ 2. ፍቼን ባስተማማኝ መቆጣጠር 3. አካባቢውን በሙሉ ማጽዳት የሚል ነበረ።

# የራስ ካሣ ልጆች መያዝና መገደል የአረበኞች ትግል አላደከመውም

ደጃዝማች አበራና አስፋወሰን በደጋሞና፣ በሰላሌ ተራራዎች ይገኙ እንደነበረ ጀነራል ትራኪያ ስላወቀ ከበባውን በማጥበብ ሊይዛቸው ችሏል። የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ከግራዚያኒ ጀምሮ ከልክ በላይ ተደስቷል። የግዛታቸው ማእከል በሆነው በፊቼ ከተማ አደባባይ አዲስ አበባን ለማጥቃትና ለመያዝ፣ የአዲስ አበባ ደሴ መንገድ ለማቋረጥ ትእዛዝ ይሰጡበት በነበረው የራስ ካሣ ልጆችን በመግደላቸው የአርበኞች ትግል ያበቃለት መሆኑን መሰሏቸው ከመጠን በላይ ተደስተው ደስታቸውን ይገልጹ ነበር።

ደሰምበር 21 ቀን ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ ባደረገው ቴሌግራም ከምሽቱ 12 35 አበራና ወንድወሰን ካሣ በፊቼ አደባባይ የተረሸኑ መሆናቸውን ገልጿል። አርበኞች በጦር ሜዳ የሞቱ 60፣ ተማርከው የተገደሉ 53 ነበሩ፣ ኢጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት 4 የተገደሉ 31 የቆሰሉ ናቸው ብሏል። ግራዚያኒ ለጀነራል ትራኪያ ባስተላለፈው ትእዛዝ ትጥቅ የማስፈታት ሂደት እንዲከናወን፤ ሽፍቶችን ወይንም ሽፍቶች (አርበኞች) መሆናቸውን የተጠረጠሩ ሁሉ ለማጥፋትም ሙሉ በሙሉ እንዲካሄድ አደራ ብሎ ማንኛውንም እርምጃ ተወስዶ የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ አስተማማኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው፣ ይህ ሁሉ ተግባር ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እምነት የሚጣልበት ነው። ጀነራል ትራኪያ ሕዝቡ በኢጣሊያ ኃይለኛነት እንዲያምን ለማድረግና ለማስፈራራት በዘመቻው የተካፈሉ 14,000 የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ወታደሮች በፊቼ ሰልፍ እንዲያደርጉ አዝዞ፤ ወታደራዊ ሰልፍንም ጉብኝቷል። በሰልፍ ሕዝቡና ቤተክህነቱ ደንግጧል፣ ብዙ የቀድሞ ሹሞች እጃቸውን ሰጥቷል ብሏል።

ጣሊያኖች ጥላን "F" ሙሉ በሙሉ ግቡን መትቷል ብሏል። ሆኖም የራስ ካሣ ልጆችንመግደል ምንም እንኳን ከፍተኛ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት የነበሩ ቢሆኑም፤ የአርበኞች የትጥቅ ትግል አላዳከመውም። ጣሊያኖች ራሳቸው የአርበኞች መሪዎች ብለው የጠቀሷቸው ያለመያዛቸውና ያለመገደላቸው የጣሊያኖች ግምት ስሕተት መሆኑን እንረዳለን።

ደሰምበር 24 ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም በባራምባራስ ዘውዴ አባፋርዳ የሚመሩ አርበኞች ከፊቼ ዘመቻ ወደ ሸኖ የተመለሱ ከጣሊያኖች ባንዳዎች ጋራ ውጊያ እንደተካሄደ ገልጿል።

በ1937 ጀነዋሪ መጀመሪያ ጣሊያኖች ራሳቸው አርበኞች እንዳልተደመሰሱ አምነዋል። ከፊቼ እስከ አባይ ድረስ ሰፍረው ይገኙ የነበሩ



አርበኞች 1. በኃይለማርያም ማሞ 2. በዘውዴ አባኮራን 3. ዘውዴ አባፋርዳ 4. ዘውዴ አስፋው 5. መሰፍን ስለሺ የሚመሩ ነበሩ።

በሸኖ ቆርማሽ፣ ተጉለት፣ መንዝ ሰፍረው ይገኙ የነበሩ የምሥራቃዊ ክፍል የተባሉ እንደ ቀድሞ በአንድ መሪ (አበራ ካሣ) አይመሩም፣ ሞራላቸው ወድቀዋል በማለት አሁንም ጣሊያኖች የተሳሳተ ግምት በአርበኞች ላይ ነበራቸው፣ ምክንያቱም ድሮም በአንድ መሪ የተጠቃለሉ አልነበሩም።

በጀነራል ቶሰቲ የሚመሩ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢ ወታደሮች ከፊቼ ዘመቻ በኋላ ጀነዋሪ 4 ከፊቼ ተነስተው ጀነዋሪ 6 ኢያርሶ ሲደርሱ በጎርጂ ሸለቆ በፊታውራሪ ዘውዴ አባኮራን የሚመሩ አርበኞች ላይ ጥቃት ፈጽመው 98 አርበኞች ተገድለዋል፣ ከጣሊያን ወገን የደረሰ ጉዳት አልተገለጸም። እንደዚሁም በዚሁ ቀን ጀነዋሪ 6 የቀኛዝማች ይርጉ፣ ቀኛዝማች ገብረመስቀልና ፊታውራሪ ተሰማ የኢጣሊያ ባንዳዎችና ጀነራል ትራኪያ በቴሌግራም ለግራዚያኒ እንደገለጠው ከአርበኞች ጥቃት ተፈጽሞባቸው 20 አርበኞች ተገድለዋል ብለዋል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከራስ ካሣ ልጆች ግድያ በኋላ የአርበኞች ትግል የመቀነስ ምልክት እንዳልነበረ ነው።

ጣሊያኖች መሣሪያ እንዲያስረክቡ ትእዛዝ የሰጧቸው መንደሮች ትእዛዙን አላከበሩም ብሏቸው በመንደሮች ላይ ጭፍጨፋ ቢፈጽሙም ውጤት አላገኙም።

ጀነራል ትራኪያ ከአባይና ጃማ ጃርሶ መካከል 2ቱ ቀኛዝማች ዘውዴ ይገኛሉ ስለተባለ ለጀነራል ቶሰቲ አካባቢውን አሰሳ አድርጎ እንዲይዛቸው ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር።

ሌላ የኢጣሊያ ኰሎኔል ለአሰሳ የተሰማራ ማርቲኔሊ (Martinelli) በዚሁ አካባቢ (ኢዳቦ) በኃይለማርያም ማሞ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን 40 ተገድሰዋል ብሏል። ከጣሊያኖች 5 አስካሪ ኢንዲጄኒ ኤርትራውያን ተገድሰዋል፣ 7 ቆሰሏል አንድ የኢጣሊያ መቶ አለቃ ቆስሏል። ጀነራል ትራኪያ ደሰምበር 19 ከኃይለማርያም ማሞ ጋራ ስለተደረገው ውጊያ ተጨማሪ ሲሰጥ ኃይለማርያም ከነበሩት 200 ተዋጊዎች 50 ብቻ አስካሪ ቁዳተኞች ያሉባቸው ተከትለውት ሲሸሹ ሌሎች ግን ገበሬዎች በግዴታ ከእሱ ጉን ሆነው እንዲዋጉ የተደረጉ ስለነበረ አልተከተሉትም።

በሸዋ ሰሜን ምሥራቅ የነበሩ አርበኞች ከራስ ካሣ ልጆች መገደል በኋላ እንደ ቀድሞ ሰፍረው ይገኛሉ እነሱም።

1/ በተጉለት በወልዴ ተሰማ የሚመሩ
2/ በመንዝ በደጃዝማች አውራሪስ የሚመሩ
3/ በአንኮበር አካባቢ በባራምባራስ ይልማ የሚመሩ
4/ በእስልቱ በጅማ ሰምበቴ የሚመሩ

በእነዚህ አርበኞች ላይ የደብረሲና አንኮበር ደብረብርሃን ባንዳዎች አሰማርተባቸው ነበር፤ ከባራምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ጀነዋሪ 11 ቀን መታሰርና መገደል ጣሊያኖች ውጤት አላገኙም።

በሸዋ በላምና መረጋጋት ለማስፈን የተደረጉ ውጊያዎች ሰላሌና ምሥራቅ ሸዋ የሚሸፍን ከኖቨምበር ወር መጨረሻ እስከ ጀነዋሪ ወር እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል።

ከጣሊያኖች የሞቱ 140 የቆሰሉ 159 ከአርበኞች የሞቱ 574 የቆሰሉ በትክክል አይታወቅም ተማርከው የተገደሉ 271 እጃቸው የሰጡ፦

1/ 6 ደጃዝማቾች
2/ 33 ፊታውራሪ
3/ 89 አነስተኛ ሹሞች

4/ 13 ወይዛዝርት የታሰሩት ሹሞች በመዶች

## ለ. በሸዋ ሰላምና መረጋጋትን ለመፍጠር ጣሊያኖች የፈጸሙት ተግባር።

የተደረገው ሙከራ ጣሊያኖች ለ2 ወር ፌብሩዋሪ፣ ማርች፣ ኤፕሪል ይዘልቃል። ይሁን እንጂ ዋረታቸው ከደሴ አዲስ አበባ ያለው የመኪና መንገድ ጥበቃ ማድረግ ብቻ የተወሰነ ነበረ፤ መንዝ፣ መርሐቤቴ፣ ሞረድ የመሳሰሉ አካባቢዎች ለመግባት እንኳን እንዳልሞከሩ ራሳቸው ጣሊያኖች አምነዋል።

ሸዋ በጣሊያኖች ላይ የማይታረቅ ትራኔ እንዳለው ለመገንዘብ ችለናል ብሏል።

## 1. ፌብሩዋሪ

አርበኞቹ እየተጠናከሩ ከመሔድ በቀር ጣሊያኖች እንደተመኙት አልጠፉም

1. ከፊቼ በስተምዕራብ በሙገር ሸለቆ ልጅ ኃይለማርያም ማሞ እና ባራምባራስ ዘውዱ አባተርጓ ሰፍረዋል።
2. ከደብረብርሃን በሰሜን እና በስተምዕራብ በአንኳር ለጣሊያኖች ተገርኑቱ አስተማማኝ ያልሆነ አንድ ምስሌኔ በውር ቀስቃሽነት በድብቅ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ ነበረ።
3. በሞረድ፣ ዋዩ ጅሩ በአበበ አረጋይ የሚመራ የማይበርድ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ ነበረ።
4. በተጉለት ዐመፀኞቹ አነስተኛ ቢሆኑም የቀድሞ መንግሥት አደገኛ ሹሞች ነበሩባቸው።
5. በሸና ኮርማሽ አካባቢ በአለልቱ በአደገኛ ሽፍታ በጅማ ሰምበቴ የሚመሩ አርበኞች ሰፍረዋል።
6. ከሞፈር በስተሰሜን በመንዝ ደጃዝማች አውራሪስ በግልጽ ሽፍታ ባይሆንም ምግብና የጦር መጠለያ ለአርበኞች እያቀበለ ከሽፍቶች ጋራ ግንኙነት ነበረው።

የኢጣሊያ ትኝ ገርዮች ወታደሮች በደብረብርሃን፣ ደብረሲና አንኮበርና ሸና ኮርማች፣ መንዲዳ፣ ሺዋንጉርት ፊቼ ጦር ሰፈሮቻቸው ተወስነው ይቀመጡ ነበር።

የደጃዝማች አውራሪስ ልጆች ለጣሊያኖች ያደሩ ለጣሊያኖች እጃቸው የሰጡ ስለነበረ በመንዝ የነበረ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ በእነሱ አማካኝነት በፖለቲካ መፍትሔ ይገኝበታል የሚል እምነት ነበራቸው።

ጣሊያኖች በቅድሚያ በሙገር፣ በአለልቱ በጅሩ ሞረድ ዋዩ ያስቸግሩ የነበሩ አርበኞችን ለመደምሰስ እቅድ አውጥተው በ2ኛ ጊዜ ደግሞ በተጉለት የነበሩ አርበኞችን ለማጥፋት ሃሳብ ነበራቸው።

## የኢምበርተራ (ዋዩ) ውጊያ፣ የአበበ አረጋይ ጦር መከበብ

በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች በጃማና ሞፈር የሰፈሩ መሆናቸውን የሚል መረጃ ስለደረሰባቸው ጣሊያኖች ከበባ አድርገው ሊደመስሱት በማሰብ



1. በፊቼ መንዲዳ 6ኛ ብርጌድ 2. በዣማ እና ፀጋ ወደብ 11ኛ ብርጌድ ከመንዲዳ ዋዩ የሰፈሩ ተመድበው ከደጃዝማች አውራሪስም እንዳይገናኙ ጥበቃ ያደርጉ ነበር። የአበበ አረጋይ አርበኞች ወደ ደነባ በሚጓዙበት ጊዜ ጊንደ ኮሬ በተባለ ቦታ በጣሊያኖች የጀነራል ቶስቲ ጦር ተኩስ በመክፈታቸው ለጣሊያኖች የአካባቢው ሕዝብ ለመፍጀት ምክንያት ሆኖላቸው ነበር። ጀነራል ትራቢያ ሪፖርት እንዳደረገው በተጉለት ጀነዋሪ 30 5አርበኞች በሕዝቡ ላይ ዘረፋ ለመፈጸም የሞከሩ ተረሽነዋል ብሏል። በአንኮበር አካባቢ ጀነዋሪ 3 ጣሊያኖች ያገኟቸው የአርበኞች ቡድኖች አባርረው 30 ቤቶችን አቃጥለዋል። በጊንደ ኮሬ ተኩስ ከከፈቱ አርበኞች አንድ በጦር ሜዳ ሲገደል 2 ተማርከው ተገድለዋል፤ የጊንደ ኮሬ መንደር በጣሊያኖች ላይ ተኩስ በመክፈቱ ተደምስሰዋል። ኮሎኔል ቶስቲ አበበ አረጋይ ወደ እምበርተራ ይገኛል ስለተባለ ጀነራል ትራቢያ ከመንዲዳና ከፊቼ ወታደሮች በማስመጣት ከምዕራብና ምሥራቅ መውጫ ዘግቶ ሲጠባበቅ ኮሎኔል ቶስቲ እምበርተራ በመዝለቅ ውጊያ ገጥሞ አርበኞች ግን ለማምለጥ ችሏል፤ በጣሊያኖች ግምት ከአርበኞች .100 ተገድለዋል።

## የእምቡር ውጊያ (አለልቱ)

በጅማ ሰምበቴ የሚመሩ አርበኞች በምሽጋቸው በእምቡር ሰፍረው እንደሚገኙ ጣሊያኖች ስለደረሰበት በመልከኞቻቸውና በምስሌኔዎቻቸው አማካኝነት ዝብሬዎች እንዲዘምቱባቸው አደረጉዋቸው።

በእምቡር (አለልቱ) የሰፈሩ አርበኞችን ለመደምሰስ ጣሊያኖኛ በ3 አቅጣጫ ወታደሮቻቸው ለውጊያ አሰማርቷል።

1ኛ 5ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ እና የሸና ባንዳዎች በሰሬው ከበባ እንዲያካሄዱ፣ ከሸና አለልቱ፣ ዉሬ ማርያም የሚያመሩ

2ኛ ሬት ለሬት የሚገጥሙ በሁለት መስመር የተሰማሩ ባለጥቁር ሸሚዝ ፋሽስት ወታደሮች ከሸና ኮርማሽ ዉሬ ማርያም የሚያመሩ በኮቺና ባርበሪኒ የሚመሩ (Coci Barberini). ሁሉም በጀነራል ጋቲ ቆንስል የሚመሩ (Console Generale Gatti) ጠዋት ፌብሩዋሪ 11 ቀን በአርበኞች ምሽግ ላይ ጥቃት ፈጸሙ፣ ከሁለት ሰዓት የፈጀ ውጊያ በኋላ አርበኞች በሌሊት ዉለግ ተገን በማድረግ ሊያመልጡ ችሏል።

በአርበኞች የደረሰ ጉዳት 225 ተገድለዋል፣ ግርማ ሰንቡቴ ራሱም ቆስሏል። ፌብሩዋሪ 18 ጣሊያኖች በአካባቢው ሰላም መረጋጋት አስፍረናል ብለው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ሸና ተመለሱ። ከጣሊያኖች ወገን 2 ባለጥቁር ሸሚዝ ቆስሏል፣ 6 አስካሪ ሲገደሉ 15 ቆስሏል።

በሙገር አካባቢ በፌብሩዋሪ 10 ውጊያ የተገደሉ አስካሪ ሲቢያውያን ራሳቸው የተቆራረጠ ያልተቀበሩ ፌብሩዋሪ 16 ቀን ተገኝቷል።

ፌብሩዋሪ 18 በኢጣሊያ ጦር ላይ ጥቃት የፈጸመ ተማርከዋል፤ በዚሁ ቀን በፊታውራሪ አለሙ የሚመራ ባንዳና በአርበኞች ግጭት ተደርገዋል አንድ ባንዳና አንድ አርበኛ ተገድለዋል። 2 በአለሙ የተማረኩ 5 በአር አካባቢ ሕዝብ ከኃይለማርያም ማሞ ጉን ተሰልፈው ተዋግቷል የተባለው የተማረኩ በምሽት በፊቼ ተገድለዋል።

# የሙገር ውጊያዎች

በኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ አርበኞች አልተደመሰሱም ስለነበረ ፌብሩዋሪ 10 ጣሊያኖች በ11ኛ ብሪጌድ ጥቃት ፈጸሙባቸው፤ ይሁን እንጂ ከተከላከሉ በኋላ ለማፈግፈግ ችሉ ነበር። ጣሊያኖች አርበኞች ምንም አልተነኩም በማለት የአገር መንደርተኞችም ለጣሊያኖች ረድታችኋል በመባል ከአርበኞች ጥቃት ይደርስባቸው ስለነበረ፣ ጣሊያኖች በኮሎኔል ጋሬሊ የሚመሩ የፈታውራሪ ዓለሙ ኢገርሳ ባንዳዎች አስገሩባቸው። አርበኛ አፈግፍገው ወደ ሙሉ መንደር ሊሄዱ ችሏል። ጣሊያኖች እንዳመኑት 11ኛ በቦታው ሊያሰፍን የቻለው ሰላም ጊዜያዊ ብቻ ነበረ፣ በግራዚያኒ ትእዛዝ መሠረት ጣሊያኖች ሙሉ በሙሉ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን አልቻሉም።

ፌብሩዋሪ 10 ስለተደረገ ውጊያ ጀነራል ትራኪያ ባስተላለፈው ቴሌግራም 300 ቤቶች እንዲደመሰሱ ተደርጓል ብሏል። በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት 4 ሲሞቱ 12 ቆስሏል፣ ከአርበኞች 55 ተገድለዋል፣ ጣሊያኖች አርበኞችን በሚያሳድዱበት ጊዜ ሌሎች 200 ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደርጓል። ከኢጣሊያ ወገን 4 ሞቷል 12 ቆስሏል.

ጀነራል ትራኪያ ፌብሩዋሪ 20 ባደረገው ቴሌግራም የኢጣሊያ የባንዳ መሪ ዓለሙ በሙገር ሸለቆ በኃይለማርያም ማሞና በዘውዴ አባፋርዳ ጥቃት አካሄደ ከጣሊያኖች ወገን 5 ቆስሏል ከአርበኞች በጦር ሜዳ የተገደሉ ብዙ ነበሩ የተማረኩ 6 ከምሽቱ በ12 ሰዓት በፊቼ አደባባይ ተገድለዋል።

ጣሊያኖች በፌብሩዋሪ ወር ያካሄዱት ውጊያ ሲገመገም በጅማ ሰምቦቴ የሚመሩ አርበኞችን እንዲበታተኑ አድርገናል፣ በኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ ከሙገር ወደ ሙሉ እንዲሸሹ አድርገናል፣ በአበበ አረጋይ የሚመሩ ከጅሩ ለዳባ እንዲሸገሩ አድርገናል፣ በሰላሌ ቋሚ ባይሆንም ጊዜያዊ ሰላም እንዲሰፍን አድርገናል፣ በዋዩ ደነባ ከአርበኞች ግጭት ነፃ እንዲሆን አድርገናል። በዚሁ መሠረት የደሴ አዲስ አበባ መንገድ በስተምሥራቅ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኗል በማለት በዚሁ ለማድረግ ያቀዱት ግቡን መትቷል ብሏል። ሆኖም ጣሊያኖች እንዳመኑት በእምበርተራና በእምቡር ያሸነፍናቸው አርበኞች ወደሞፈር አካባቢ ሸሽተው ሄደው፣ ጣሊያኖችን ለማጥቃት በተለያዩ መሪዎች ሥር ሆነው በተለይም በአበበ አረጋይ በሰላ ድንጋይ አካባቢ ይገኙ ነበር።

የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ ምክንያት ጣሊያኖች ያደረጉት የሕዝብ ጭፍጨፋ በመፍራት የሸሹ ሁሉ በደብረሊባኖስ ገዳም ከመጠለላቸው በላይ በሙሉ በእንሳርና በተጉለት ከነበሩ አርበኞች በመቀላቀላቸው የአርበኞች ትግል ነፍስ እንዲዘራና ብርታት እንዲያገኝ ረድቷል። በሌላ በኩልም ለጣሊያኖች በደረሱዋቸው መረጃዎች መሠረት በራስ ደስታ ትእዛዝ መሠረት እነዚህ እየተጠናከሩ የመጡ የአርበኞች ቡድኖች ወደፊት አዲስ አበባን ለመያዝ ለሚደረገው ዘመቻ የሰሜን ጦር ግንባር ሠራዊት ሊሆኑ ይችላሉ።

# 2 የማርች ወር ውጊያዎች

## ሀ/ በተጉለት ውጊያ

በተጉለት ከተሰበሰቡ 3000 አርበኞች 200 የወታደር ደምብ ልብስ የለበሱ የቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደሮች ነበሩ 20 ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ነበሩ። የአርበኞች ዓላማ በጠርማ በር የመኪና መንገድን



ማስናከል ነበር፣ ጥቃታቸውም በሥራ ላይ በማዋል ለመጀመር አስበው የነበረ ለፌብሩዋሪ 25 ነበር።

የአርበኞችን ዓላማ ለማክሸፍ የጣሊያኖች ሰሜን ምዕራብ ሸዋ እዝ ያወጣው እቅድ፦

1. አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ የመኪና መንገድ ትራፊክ እንዳይቋረጥ ማድረግ
2. የአርበኞች በጣሊያኖች ላይ የሚፈጽሙት ግፊት ለመከላከል እስከ ሞፈር ማባረር
3. የአርበኞችን ኃይል መበታተንና ማውደም
4. በጣሊያኖች ላይ ጥላቻ በሚያሳዩ የተጉለት መንደሮች ከባድ ቅጣት መፈጸም የሚያጠቃልል ነበረ።

ለዚሁ ተግባር ጣሊያኖች ያሰማሩዋቸው ወታደሮች የሚከተሉት ነበሩ።

1ኛ በኮሎኔል ጋይቢ (Gaibi) የሚመራ ጠንካራ የፊት አጥቂ ጦር 4ኛ እና 5ኛ ባታሊዮኖች እንዲሁም 6ኛ መድፈኛ ያቀፈ ነበረ።

2ኛ ዋናው ጦር ሀ/ 5ኛ የቅኝ ግዛት ባታሊዮን ለ/ 3ኛ መድፈኛ ሐ/ 358ኛ እና 220ኛ የጥቁር ሸሚዞች ፋሺስት ወታደሮችና አብሮዋቸው የሚጓዝ መድፈኛ "ቺሬኔ" (Cirene)

3ኛ እላይ ከተጠቀሱ የጦር ክፈሎች ተቀላቅለው የሚዘምቱ ሀ/ የደብረሲና ለ/ የደብረብርሃን ሐ/ የአንኮበር መ/ የሸና ሰ/ በማለሰብ ሹሞች የሚመሩ ባንዳዎች ይገኙበት ነበር።

ፌብሩዋሪ 22 የኢጣሊያ ዘማች ሠራዊት ጉዞውን በመጀመር የዚንጀር ጊቤ ወንዝ አሰሳ አካሄደ 23 በጣርማበር አካባቢ አንድ ኃይለኛ የአርበኛ ቡድንን አባረረ። በ24 እምባ በተርጌን ተቆጣጥሮ ከባድ ቅጣት ከመፈጸሙ በላይ በጅብ ዋሻ አካባቢ ያገኛቸውን 200 አርበኞች እንዲበታተኑ አድርገዋቸዋል።

ፌብሩዋሪ 25 በ3 አቅጣጫ የመጣ የአረበኞች ቡድን ጠርማበርን ለመያዝ የሞከሩ ብዙ ሰው ተገድሉባቸው ጣሊያኖች ተከላከለው መልሰዋቸዋል። በ26 እና 27 በአካባቢው ሰፊ አሰሳ አካሂዷል በ28 አርበኞች ጉዳት ስለደረሰባቸው ወደ ዘንደጉርና ሰላ ድንጋይ አፈገፈጉ።

ጣሊያኖች ለዘመቻ ሲነሱ የሚገጥሟቸው የአርበኞች ስም ዝርዝር ጀነራል ትራኪያ እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

1. በአንኮበር አካባቢ የነበረ ሀ/ ልጅ አየለ ኃይሌ ለ/ ልጅ ደስታ ሃብተሥላሴ ሐ/ ፈረደ እንዳርጌ
2. በዋዩና ደነባ በራምባራስ አበበ አረጋይ በቦታው ከነበሩ ባራምባራስ በቸሀ፣ ቢሻ ወልዴና ተሰማ፣ ልጅ ይግዛው ወዘተ ጋራ ተቀላቅሏል።
3 በመንዝ የደጃዝማች አውራሪስና ልጆቹ።

ጀነራል ትራኪያ እንደገለጸው[1] በጅብ ዋሻ በተደረገው ግጭት ከጣሊያኖች ወገን አንድ ባንዳ ቆስሏል። ከአርበኞች አንድ በጦር ሜዳ ሲገደል ሌላው ተማርኮ ተገድለዋል። የተገደለው ምርኮኛ ከመገደሉ በፊት በ24 በእምባ በተርጌ በተደረገው ውጊያ አርበኞች 35 እንደሞቱባቸውና ብዙ እንደቆሰሉባቸው ተናግረዋል። በደብረብርሃን 4 ዘራፊዎች(አርበኞች) ተረሽነዋል።

በሬቺ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ እንደገለጸው የኃይለማርያም ማሞ አርበኞች ባለፉት ቀናት በጋሬሊ (Garelli) በሚመራ የኢጣሊያ ጦርና በዓለሙ

---

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 1162 V II

በሚመሩ ባንዳዎች ጉዳት ደርሶበት የነበረ ከአዲስ አበባ የፈለሱ ስለተቀላቀሉበት 400 ተዋጊዎች በማግኘት ጥንካሬ አግኝቷል ብሏል፡፡

ማርች 1 ቀን ጣሊያኖች ጉር ሥላሴን ተቆጣጠሩ ይኸም የመኪና መንገድ ለመቆጣጠር አስተማማኝ ያደርገዋል ብሏል፡፡ ማርች 6 ቀን በአምበር ሸለቆ ከነበሩ 400 አርበኞች ውጊያ ተደርጎ አርበኞች 10 ተዋጊዎች ሞተውባቸዋል፡፡

ጣሊያኖች አርበኞችን እውድመናል እንዲበታተኑ አድርገናል ካሉ በኋላ አክሉም ብዛት ያላቸው በሰላ ድንጋይ ተሰባስበው ስለሚገኙ በእነዚህ አርበኞች ላይ የከፍሉ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ጠሩን አዝምቶ ማርች 9 ሰላ ድንጋይን ለመያዝ ወሰነ፣ በሁለት አቅጣጫ በቀኝ ዋና ጦር ግንባር በኮሎኔል ጋይቢ የሚመራ ሰላ ድንጋይን ለመያዝ በግራ[1]ኮሎኔል ፑቺ (Pucci) የሚመራ እምቢሲን ለመያዝ ማርች 10 ሰላ ድንጋይ ተያዘ፣ በአርበኞች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሰዋል፤ ከ11-14 በአካባቢው አሰሳ ተካሄዷል፣ 100 አርበኞች ተገድለዋል፣ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት በመሰፈኑ የሰላ ድንጋይ ሳህሊት ደብረ ምጥማት ማርያም ቤተክርስቲያኖች እሻቸውን ሰጥቷል፡፡

ጀነራል ትራኪያ ማርች 10 ባስተላለፈው ሪፖርት ሁለቱ ኮሎኔሎች በሚዘምቱበት ጊዜ የበላይ አዛዥ ስለነበረ፣ ከኮሎኔል ጋይቢ ጉን ሆኖ የዘመተ ታማኝ የኢጣሊያ የደብረሲና ባንዳ አዛዥ የነበረ በጣሊያኖች ፊታውራሪ ሆኖ የነበረ በጦርነቱ ተገድለዋል ብሏል፡፡ ከቀኑ በ8፡30 ተጠባባቂ የኢጣሊያ ወታደሮች ከአርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው 3 ወታደሮች ቆስሏል፣ በ11 ሰዓት ሰላ ድንጋይ ተያዘች፣ አካባቢው ሁሉ እቃውን ይዞ ስለሸሸ ሰው አልባ ሆኖ ነበረ፡፡ ሁሉም ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፣ ከ25 ኪሎ ሜትር የበለጠ መሬት አንድ ቤት እንኳን ቆሞ ያልተቃጠለ አይታይም ነበር፡፡ ከአርበኞች 30 በጦር ሜዳ ተገድለዋል 7 ተማርከው ተረሽነዋል፡፡ ከጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 5 የቆሰሉ 10 ነበሩ፡፡

ማርች 23 ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ በላከው ሌላ ሪፖርት ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ በሙሉ ወድሟል፣ 40 መንደሮች ወድመዋል፣ ከ4,000 የሚበልጡ ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፡፡ በጣሊያኖች ወገን የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 31 የቆሰሉ 30 ነበሩ፡፡ ከአርበኞች በጦር ሜዳ የተገደሉ 212 ተማርከው የተገደሉ 396 ነበሩ፤ ተጉለት የሚገባት ቅጣት አግኝታለች ብሏል፡፡[1]

## 3. የእንሳሮ ውጊያ

በእንሳሮ ሰፍሮ የነበረ ሰሎር ዐመጽ ከግራዚያኒ የመግደል ሙከራ በኋላ ገሀድ የወጣው ከአዲስ አበባ ከአልቄት ለማምለጥ ሲሉ መጥተው ሲቀላቀሉበት ነው፡፡[2]፡፡ በእንሳሮ የነበሩ አርበኞች ለማውደም የተሰጠው ለኮሎኔል ጋሬሊ ነበረ፤ ትጥቅ ለማስፈታትም የሚያጠቃልል ነበረ፡፡ ብዙ ሰዎች የኢጣሊያ ወታደሮች በሚመጡበት ጊዜ ወደ ሽፍትነት ተሰማርቷል፡፡ በዚሁ የተነሳ ጣሊያኖች አሰሳ ማድረግና ሰው መግደል ጀመሩ፡፡ ፀጋ ወደብ በተባለው ወንዝ ከአርበኞች ጋራ የተደረገው ግጭት የሚጠቀስ ነው፡፡ ማርች 21 በተደረገው ግጭት አርበኞች ተበታትነዋል፡፡ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ሲመለስ ታይቷል፣ የኢጣሊያ ወታደሮችም ወደ ፍቼ ተመለሱ፡፡

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N. 1209 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Testo N. 371 V II



ጀነራል ትራኪያ ማርች 21 ስለ እንሳሮ የጻፈው ሪፖርት ኮሎኔል ጋሬሊ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ እንዲመለስ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እንዳለቀ የእንሳሮ አካባቢ መንደሮች ወደ ቤታቸው ያልተመለሱ ቤቶችና መንደሮች እንዲወድሙ አርገዋል፣ በአርበኞች አሰሳ በሚደረግበት ጊዜ 15 አርበኞች በጦር ሜዳ 12 ተማርከው ተገድለዋል፡፡ በጣሊያኖች ላይ የደረሰ ጉዳት የሞተ 1 የቆሰለ 2 ነበሩ፡፡

አርበኞቹ ጣሊያኖች በሚመጡበት ጊዜ ፀጋ ወደብ ወደ ተባለው ቦታ ሸሽተው ሄደው ስለነበረ ሊፈልጓቸው በመጡ ጣሊያኖች ላይ ተኩስ ከፈቱባቸው፡፡ ከአጭር ውጊያ በኋላ ሸሽተው አመለጡ፣ 22 አርበኞች ተገድለዋል፡፡ ከአርበኞች መሪ አንዱ የነበረው ሽቴዱ ዱሬ ተማርኮ ተገድለዋል፣ 750 ከብቶች በጣሊያኖች ተዘርፈዋል፡፡ ፊታውራሪ እምባው የተባለ ከጣሊያኖች ጐን ነኝ ሲል የነበረው ከግራዚያኒ መግደል ሙከራ በኋላ፣ የጦር መሣሪያ ለያዙ ሰዎች ሁሉ በፀረ ኢጣሊያ ትግል እንዲዘጋጁ ምክር ይሰጥ እንደነበረ ተረጋግጧል፡፡ የእሱ እህትም ፊታውራሪ መርከያ ከደብረሊባኖስ ሸሽተው የመጡ መጠለያ የሰጠ እንዲሸሽ ድጋፍ በመስጠቷ ተይዛ ታስራለች፡፡[1]

## 4. የሙገር ውጊያ

ከግራዚያኒ የመግደል ሙከራ በኋላ 300 ከአዲስ አበባ የሸሹ ወደዚሁ አካባቢ መጥተው ነበር፡፡ ማርች 12 ኃይለማርያም ማሞ የእህል ስንቅ ለመግዛት ወደ ሙገር መምጣቱ ጣሊያኖች መረጃ ስለደረሳቸው፣ ማርች 14 11ኛ ብሪጌድ ወደ ስፍራው ላኩ፣ ማርች 15 እና 16 ጣሊያኖች አርበኞችን ወደ ሙሉ በማሳደድ ላይ ነበሩ በሕዝቡ ላይም ኃይለማርያም በመደገፋቸው ከባድ ቅጣት ፈጽመዋል፡፡


ማርች 15 ጀነራል ትራኪያ ስለ ሙገር ውጊያ የላከው ሪፖርት ኃይለማርያም ማሞ በእንቅልፍ እንዳለ በድንገት ተገኝቶ ሆኖም የግል ንብረቱ እንኳን ሳይሰበስብ ለማምለጥ ችለዋል፣ አርበኞች 21 ሰዎች ተገድሉባቸዋል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን 3 ቆስሏል፡፡ በታማኙ በጣሊያን ባንዳ በፊታውራሪ ዓለሙ እየተረዳ የአካባቢ ሕዝብ አርበኞቹን ለማሳደድ ተባብረዋል፡፡ ጉልቶዮን ተወላጅ የጣሊያን አስካሪ የነበረና የኪዳ ቸፈራ ባሕቱ የተባለ፣ በሬቺ ጊሪ የሆነው የራስ ካሣ ሚኒስትር የነበረ ደጃዝማች ወርቅነህ ለጣሊያኖች እጁ በሰጠው ተይዘዋል፣ በሬቺ ለኢጣሊያዊ ሀገረ ገዥ ስላስረከበው ከብሩ አባተ ጋራ በአደባባይ ተገድለዋል[2]፡፡

አበበ አረጋይ ከተጉለት ወደ ሞቱ ሄዷል፣ ከእሱ ጋራ በተደረገው ግጭት የኢጣሊያ የባንዳ መሪ ተገድሏል፡፡

ማርች 16 ጀነራል ትራኪያ በሰጠው ሪፖርት በሰላ ድንጋይ በአበበ አረጋይ አርበኞችና በጣሊያኖች ባንዳዎች መሐል ተኩስ ልውውጥ ተደርጎ ከሁለቱ ወገኖች አንዳንድ ሰው ተገድለዋል፡፡ በሙገር የአርበኞች እንቅስቃሴ ቀጥለዋል፡፡ ምንም እንኳን በግርግ ግብለጊዮርጊስ ከሚመሩ አርበኞች ከዳተኞች ኤርትራውያን ካሉባቸው ጋራ ከባድ የጠብመንጃና የመትረየስ ተኩስ ቢያጋጥምም ጣሊያኖች እንተኒ የተባለ መንደር ለመያዝ ችለዋል፡፡ ፊታውራሪ ግብለጊዮርጊስ የግርግ አባት የኃይለማርያም ማሞ አጎት ነው፡፡ አርበኞች ከሞቱባቸው 9 ሰዎች አንዱ የአስካሪ ልብስ የለበሰ ከዳተኛ ኤርትራዊ ነበረ፡፡

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N.1204 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N.1193 V II

# የኢትዮጵያ አስተዳደር አከፋፈል በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን




ጣሊያኖች የኢትዮጵያ መሬትን ቈርሰው ኤርትራ ብለው እንደሰየሙት ሁሉ መላዋን ኢትዮጵያ በተቈጣጠሩበት ጊዜ የኢትዮጵያ ስምን አጥፍተው በርዘው ኢጣሊያዊት ምሥራቅ አፍሪካ AOI የሚል መጠሪያ ነበረ የሰጧት።



የአካባቢ መንደሮች ተደምስሰዋል። አርበኞቹ ሲሸሹ ኃይለኛ ተኩስ በጣሊያኖች ላይ ይተኩሱ ነበር።

# 3. የአፕሪል ወር ውጊያ

ጣሊያኖች በሸዋ ሰላምና ማረጋጋት ለማስፈን ያደረጉት ጥረት ግቡ እንዳልመታ ማመን ጀምረዋል። ጣሊያኖች እንደተመኙ እየተዳከሙ የመጡ አርበኞች አልነበሩም በተገላቢጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ የመጡ ጣሊያኖች ነበሩ፤ ባንፃሩም እየተጠናከሩ የመጡ አርበኞች ነበሩ። ጣሊያኖች እንዳመኑ በአንድ አካባቢ አርበኞችን ደምስሰናል አጥፍተናል ብለን ወደ ሌላ አካባቢ ለተመሳሳይ ተግባር ስንሰማራ፤ ቀደም ብለን ከአርበኞች ያፀዳነው አካባቢ በተጠናከረ መልኩ አርበኞች የሰፈሩበት የአርበኞች መናኸሪያ ሆኖ እናገኘዋለን በማለት አርበኞችን በማጥፋት ስቅዳቸው እንዳልተሳካላቸው ይገልጹ ነበረ[1]። ጣሊያኖች አርበኞችን ለማጥፋት ያደረጉት ኃይለኛ ሙከራ እንዳልተሳካላቸው የሚያሳይ ምልክት በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረ ጀኔራል ትራኪዮ ተሸሮ በጀኔራል ማለቲ (Maletti) መተካቱ ነው።

የአርበኞች ድፍረት ለመግታት አዲሱ የጦር አዛዥ የወሰደው እስቸኳይ ጊዜያዊ እርምጃ ሁኔታዎቹ እስከሚጣሩ ድረስ ደብረሲናንና የአዲስ አበባ ደሴ የመኪና መንገድን ደኅንነት ለመጠበቅ ኮሎኔል ጋይበ ከፍተኛ ጦርን በመምራት ወደ ስላ ድንጋይ በመላክ ነበር። ማርች 29 ጣሊያኖች ከሞፈር ወንዝ ባሻገር ሰፍረው ለ3 ተከፍለው አርበኞች ጥቃት ለመፈጸም እንደተዘጋጁ መረጃ ይደርሳቸዋል። 1ኛ የተኛ መንዲዳን ለማጥቃት 2ኛ ማዕከለኛ በአበበ አረጋይ የሚመራ ከሁሉ ኃይለኛ ከሁሉ የሚያሰጋ ከሁሉ የበለጠ አመራር ያለው ብለው የገመቱት ስላ ድንጋይን ለማጥቃት ዓላማ ያለው 3ኛ የግራ በምስራብ መንዝ የሰፈረ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለአበበ አረጋይ ድጋፍ የሚሰጥ።

ጀኔራል ማለቲ በአበበ አረጋይ ብቻ ያነጣጠረ በ3 አቅጣጫ ጦር ለማሰማራት ወሰነ፤ የአበበ አረጋይ አደጋ ከሰወገደ በኋላ በሁለተኛ ዙር ወደ ዋቄ መንዲዳ ፊቱን ማዞር፤ የ3ኛ ቡድን ስለተባለው በመንዝ ስለሰፈረው ግን ወደ ጣሊያኖች ይዞታ በልቶ እንዳይመጣ ክትትል ማድረግ ብቻ የተወሰነ ዓላማ ነበረው። የጣሊያኖች ዓላማ በአሁኑ ወቅት አርበኞቹን ወዳሉበት ሄደው ለማጥቃትና ለመደምሰስ ሳይሆን በመከላከል አዘንብለው የደሴ አዲስ አበባ የመኪና መንገድ አርበኞች እንዳያቋርጡባቸው ዘብ መቆም ብቻ ነበረ። ትግሉ ለ5 ዓመት የቀጠለው በዚሁ መልክ ነበረ።

ጀኔራል ማለቲ በ3 አቅጣጫ በአበበ አረጋይ አዘመትኳቸው የሚላቸው የጦሩ ክፍሎች 1ኛ በቀኝ በኩል በኮሎኔል ጋይበ የሚመራ ቡድን ሌላ 2ኛ በግራ በጋሬሊ (Garelli) የሚመራ በመሐል በአንጀሊ (Angeli) የሚመራ አሰማራ። የማያ ንድፍ ተመልከት።

አፕሪል 3 እና 4 ደጋግመው ያጠቁ የነበሩ አርበኞች ነበሩ፤ በጫጫ እና በሬማ ወንዞች በኩል ወደ ወራና ዘልቀው ለመኪና መንገድ አደጋ እንዳያደርሱና ከበባ እንዳይፈጽሙባቸው ጣሊያኖች ስጋት ላይ ወድቀው ነበሩ። ጣሊያኖች አርበኞቹን ከመኪና ማራቅ ካልሆነ ለመደምሰስ ፍላጎትም ችሎታም

[1] Governo Generale A.O.I. ibd Testo P. 373 V II

ራስ አበበ አረጋይ



ታጋይ ይሞታል ትግሉ ግን አይሞትም የሚለው አባባል በኢትዮጵያ በተግባር ሲውል ታይቷል፡፡

ጣሊያኖች እነ ራስ ደስታን ደጃዝማች አበራ ካሣን ወዘተ በመግደል የኢትዮጵያውያንን የአርበኝነት ትግል የደመሰሱ መስሏቸው ነበር፣ ሆኖም ኢትዮጵያ በታሪኳ፣ ጀግኖች ሀገር ወዳዶች፣ የማይፈልቁባት አገር፣ የጀግኖች መሀን ተብላ ስለማትታወቅ በጣሊያኖች በግፍ የተገደሉትን የአርበኞች መሪዎች ፈለግ ተከትለው ሌሎች አርበኞች ታጋዮች እነ ራስ አበበ አረጋይ ትግሉን በመቀጠል በያለበት አፋፍመውት እንጂ ኢትዮጵያ ለጣሊያኖች ቅኝ ገዦች እጅዋን አልሰጠችም፡፡



አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ ከውጊያው በኋላ እንደአየፍላጎታቸው ወደ ነፃ መሬታቸው ወደ መርሐቤቱና መንዝ ለማፈግፈግ ይችሉ ነበር፡፡

ጣሊያኖች የሕልም ምኞት ፈውዳል የሚሏቸው እንደ ደጃዝማች አበራና አስፋወሰን ካሣ ካጠፉ በኋላ የአርበኞች የትጥቅ ትግል ያበቃል የሚል ስእምነታቸው ስህተት መሆኑን እምነው የተቀበሉ ይመስላል፣ እምነው ባይቀበሉም ጊዜው እየተደገፋቸው በመሄድ የ2ኛ የዓለም ጦርነት እየተቃረበ ይሄድ ነበረ፣ የቅኝ ግዛቶች ግብቲያም እየተቃረበ ይሄድ ነበረ፣የጣሊያኖች አስተሳሰብ ግን 100-200 ዓመት ወደ ኋላ የቀረ ነበረ፡፡

ማርች 28 ቀን ጀነራል ትራኪያ በላከው ቴሌግራም አንድ ግለሰብ ከአርበኞች ጋራ በምስጢር በግሲፋና የተደት ንግድ በማካሄዱ በፍቼ ተረሸነዋል ብሏል፡፡

አፕሪል 4 ጀነራል ግለቲ ስለተካሄዱ ጦርነቶች ባቀረበው ሪፖርት 2 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች ተገድለዋል 2 ቆስሏል፣ አስካሪና ባንዳዎች 11 ተገድለዋል 23 ቆስሏል፡፡ ከአርበኞች ወገን 360 በጦር ሜዳ የተገደሉ 62 ተማርከው የተረሸኑ፡፡ ከተገደሉ ውስጥ ብዙ ታዋቂነት የነበራቸው ነበሩ፣ እንደዚሁም 2 አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያን ነበሩ፡፡

በተደጋጋሚ የሚጠቅሷቸው ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ጣሊያኖች በአምሳላቸው የፈጠሩዋቸው ለጣሊያኖች ታማኝ ኤርትራውያን እንክርዳዶች እንዴት ሊገኙ ቻሉ በማለት በንዴትና በቅድሚያ ይገድሉዋቸው የነበረ በዚሁ የተነሳ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሚታየው ሁኔታ ስናስገናዝበው ጣሊያኖች ለኤርትራውያን 100 ዓመት ብቻ ጣሊያኖች ኤርትራ የሚል ስም ከሰጧቸው ጊዜ ጀምሮ ታሪክ እንዳላቸው እምነው እንዲቀበሉ የተሳካላቸው ይመስላል፡፡ Popoli Imbelli e guerrieri ጅሎችና ጦረኞች ለኢጣሊያ ቅኝ ገዦዮች አገልጋዮች ብቻ ለመሆን የተፈጠሩ፣በጣሊያኖች ትእዛዝ ኢትዮጵያን እንዲጠሉና እንዲወጉ የተፈጠሩ፣ ለጣሊያኖች ዘረኞች ቅኝ ገዦዮች፣ የዓለም ታሪክ ቀድሞ ሮም ባይቀድማቸው፣ ዓለማቸው ተሳክቶላቸው እንደነበረ እንረዳለን፡፡

አፕሪል 5 ጀነራል ግለቲ ባስተላለፈው ሪፖርት በጦርነቱ ስለተገደሉ ሰዎች በተጨማሪ ሲገልጽ ሌሎች 52 ተገድለዋል ካለ በኋላ ሕዝቡና 14 ቤተክርስቲያኖች ለጣሊያኖች ታማኝነታቸውን ገልጸዋል ብሏል፡፡ አበበ አረጋይ ወደ ምዕራብ መንዝ እንዳመራ ተረጋግጧል፣ ሆኖም ወደ አዳባይ እንደሚመለስ ይታመናል፡፡ በአዳባይ እንደ ሊቢያ ቺሬናይካ ብዙ ዋሻዎች ጉድጓዶች፣ ከቺሬናይካ በ1000 ጊዜ ተባዝተው የሚበልጡ ይገኛሉ ብሏል፡፡

አፕሪል 6 ጀነራል ግለቲ ባደረገው ሪፖርት ስለተደረጉ ጦርነቶች አስመልክቶ ሲጽፍ ባለፈው ያስተላለፈውን በማረም በጦር ሜዳ የተገደሉ አርበኞች 412 እንደነበሩ ተማርከው የተገደሉ 63 እንደነበሩ አብራርቷል፣ ብዙ የአርበኞች የእህል ጐተራም እንዲቃጠል ተደርገዋል ብሏል፡፡

አፕሪል 7 ጀነራል ግለቲ ባቀረበው ሪፖርት አበበ አረጋይ ቀድሞ በጣሊያኖች ላይ ጦርነት ከመክፈቱ በፊት ጣሊያኖች እንዲቀድሙት ወሉ ከሚገኘው የኢጣሊያ ጦር በመስማማት ጣሊያኖች ቀድመው ጥቃት እንዲፈጽሙ ለማድረግ እሞክራለሁ ብሏል፡፡

በድምሩ ግን በጣሊያኖች የተገደሉ አርበኞች 556 ነበሩ፡፡ ጣሊያኖች በመንዝ፣ በመራቤቴ፣ በሞረድ ብዛት ያላቸው አርበኞች የሰፈሩበት አርበኞችን ለመደምሰስ ዕቅድ ያወጣሉ፡፡ ይህ ከመደረጉ በፊት ግን በዋዩ ጅሩ፣ ወበራ በሰሎር የሚንቀሳቀሱ አርበኞችን ቅድሚያ በመስጠት ማጥፋት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ፡፡

# የእንሳሮ ውጊያ (ሳሀ ዳብር)

የእንሳሮ ሕዝብ የጦር መሣሪያ አላስረከብም ብሎ ነበረ፡፡ ጣሊያኖች አበበ አረጋይና ደጃዝማች አውራሪስ ወደ ሱዳን ወይንም ወደ ጅቡቲ ሀገር ለቀው ለመሄድ ሃሳብ እንዳላቸው መረጃ ስለደረሳቸው ከመርሐቤቴና ከእንሳሮ ወደ አባይ የሚወስድ መንገድ ሁሉ ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ የእንሳሮ ሕዝብን ትጥቅ ለማስፈታት ኮሎኔል ጆርዳኖ ስለተመደበ ኮሎኔሉ ስራውን ለማከናወን ወደ ለሚ መድኃኔ ዓለም የእንሳሮ ዋና ከተማ በማምራት ኤፕሪል 14 እቦታው ሲደርስ ኗሪ ሕዝብ ንብረቱን ይዞ ሀገሩን ለቆ ነበረ፡፡ ቦርሳና በተባለው ወንዝ አርበኞች መሰፈራቸውን ስላወቀ ኮሎኔል ጆርዳኖ አፕሪል 16 አሰሳ ለማድረግ ይሰማራል፣ ጃዲመለስ የተሰጠው ትእዛዝ ችላ በማድረግ ያለው ኃይል በቂ ነው ብሎ በማሰብ አሰሳ ሲጀምር፣ አንድ ክፍል ወታደሮቹ ኤፕሪል 17 ሳሀ ዳብር በተባለው ቦታ በአርበኞች ተከበበ፡፡ ከመንዲዳ እና ከፍቼ ረዳት ወታደሮች ስለተላኩለት ከእልቂት ሊድን ችሏል፡፡ ኤፕሪል 22 ከከበባው ካስለቀቁ በኋላ ከባድ አሰሳና ቅጣት በሕዝቡ ላይ አካሄዷል፡፡ በዚሁ ውጊያ በጣሊያን ወገን የደረሰ ጉዳት 3 የጦር መኰንኖች የቆሰሉ 41 ወታደሮች ሲሞቱ 50 ቆስሏል፡፡ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 432 ከአንድ ሺህ (1000) በላይ ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደርገዋል፡፡ ጣሊያኖች በ1 ዓመት ውስጥ ከአርበኞች ጋራ የተካሄደው ትግል ሲገመገሙ ጥሩ ውጤት እንዳልተገኘ አምኗል፡፡

ለዚሁም ብዙ ምክንያቶች ሰጥቷል፣ የመሬቱ ገደላ ገደል መሆኑ፣ የአርበኞቹ በፍጥነት እንደ እሞራ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሸዋ ሕዝብ ያለው የቆየ ስር የሰደደ በጣሊያኖች ላይ ጠላትነት፤ስለዚህ በሀገሩ ዘላቂ ሰላም ሊሰፍን የሚችለው በጊዜ ብዛት ነው በማለት አጠቃላይ ግምገማ ደርሰዋል፡፡

ኤፕሪል 17 ኮሎኔል ጋሬሊ ባስተላለፈው ሪፖርት ሻለቃ ጆርዳኖ ብዙ የአርበኞች ከብቶች እንደዘረፈ፣ በውጊያም 7 አርበኞችን እንደገደለ ገልጧል፡፡ ኤፕሪል 19 ጀነራል ግሰቲ ባስተላለፈው ሪፖርት ሻለቃ ጆርዳኖ በአርበኞች ተከቦ በአደገኛ ሁኔታ ይገኝ እንደነበረ ገልጸ ከአደጋ ሊያመልጥ የቻለው በ5ኛ ባታሊዮንና በኮሎኔል ጋረሊ ባደረጉለት እርዳታ መሆኑን አብራርቷል፡፡ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት የተገደሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት አንድ የመቶ አለቃ ያሉባቸው 17 ተገድለዋል 46 ቆስሏል፣ 22 የደረሱበት ያልታወቀ ከእነሱ መሐልም አንድ ኢጣሊያዊ መቶ አለቃ፤ በሚቀጠሉት ቀናት የምናደርስባቸው በጣም ከባድ እንደሚሆን ገልጧል፡፡

ኤፕሪል 21 ጀነራል ግሰቲ ባስተላለፈው ሪፖርት ኮሎኔል በላከለት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ለ10 ኪሎ ሜትር የበቀልና የመቀጫ እርምጃዎች ተወስዷል፣ በ18 እና 19 ውጊያ የተካሄዱባቸው ቦታዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቤቶች ተቃጥለዋል ወድመዋል፣ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ከአርበኞች ጋራ በመተባበራቸው ተይዘው ተረሸነዋል፡፡ በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የቆሰለ አንድ ብቻ ነው፣ የደረሱበት አልታወቀም ከተባሉ 2 አስካሪ ተገኝቷል ብሏል፡፡

ኤፕሪል 24 ጀነራል ግለቲ በላከው ሪፖርት የዓመቱ አንዳንድ ሹሞች እጃቸውን ለመስጠት ስለቀረቡ በዳውሊ መንደሮች ነጋድልስና ሁለት ሌሎች ባንዳዎች በመግደላቸው ሳደረገው ያሰብኩትን ቅጣት ቀንሻለሁ ብሏል፤ ሆኖም 680 ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል 206 ሰዎች ተይዘው ተረሸነዋል፣ የአሳገርቲ ሕዝብና ቤተክርስቲያኖች ቀርበው እጅ ነስተው ሰጦታ አቅርበዋል፣ በሕዝቡ ላይ የተፈጸመው ቅጣት ትክክልና ፍትሐዊ መሆኑን ሕዝቡ አምኖበታል ብሏል፡፡



በሌሎች ክፍለሀገሮችም የአርበኞች ትግል እንደቀጠለ ነበረ፡፡ ጀነራል ናዚ ፌብሩዋሪ 27 ባስተላለፈው ሪፖርት በተደረገው ክትትል ለአንድ ባራምባራስ ከፊታውራሪ በሐደ ጋራ ትብብር በማድረጉ ባሻ ካሊደ የጦር መሣሪያ ደብቆ በመገኘቱ ተረሸነዋል ብሏል፡፡

ማርች 10 ጀነራል ጀሉዞ በሰጠው ሪፖርት የዳረማ ባንዳ በዲላ አጠገብ ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ አርበኞች 850 ከብቶች ጥለው ሲሸሹ 30 ተገድሉባቸዋል፣ ከኢጣሊያ ባንዳ የሞቱ 18 የቆሰሉ 6 ነበሩ፡፡፡ የአዶላ ባንዳ አዛዥ ከቁኔ ተራራ አጠገብ 2 የቀድሞ የኢጣሊያ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያንን ማርኮ በጥይት ደብድቦ ገድሏቸዋል፣ እንደዚሁም የዳሎ ባንዳ 29 የኤርትራ የቀድሞ አስካሪ ከዳተኞችን ማርኮ ገድሏቸዋል፡፡

ማርች 16 ጀነራል ጀሉዞ ባደረገው ሪፖርት ከባንዳ ሮሌ (Rolle) አንድ ክፍል በሳንቶሮና በደ ሎረንዞ (Santoro e De Lorenzo) የሚመሩ 300 ከጊቤ እናሪያ በስተምዕራብ በብላታ ታከለ ወልደሐዋሪያት ከሚመሩ አርበኞች ውጊያ ተካሄዶ አርበኞች እንዲሸሹ አድርገዋቸዋል፡፡ ከጣሊያን ወገን የመቶ አለቃ ሳንቶሮ በጠና ቆስሏል፣ ከባድ 8 ሲቆሰሉ 8 ተገድለዋል፡፡ ከአርበኞች 50 በጦር ሜዳ ሲገደሉ 3 ተማርከው ተገድለዋል፡፡

ኤፕሪል 23 ጀነራል ጀሉዞ ባደረገው ሪፖርት 2 ባታሊዮኖችና ባንዳዎች ያቀፈ በኮሎኔል ማሮኔ (Marone) የሚመራ የኢጣሊያ ጦር 1500 ከሚገመቱ አርበኞች በኮንታ ውጊያ ተደርጎ ከጣሊያኖች ወገን አንድ ምክትል መቶ አለቃና 9 ባንዳዎች ሲሞቱ 16 ቆስሏል፣ ከአርበኞች 100 ተገድለዋል፡፡

ማርች 30 ኮሎኔል ሰራሊያ (Serraglia) በላከው ሪፖርት በቦካ ዋሊ አጠገብ ኮሎኔል ኮራዶ ባንዳ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን ብዙ ሞቷል፡፡ መንደሩ ሸፍታ በመሆኑ ወድመዋል፣ ከጣሊያን ወገን 3 ኢንዲጀኒ አስካሪ ተገድለዋል፡፡

ማርች 31 ኮሎኔል ሰራሊያ በላከው ሪፖርት የኮሎኔል ኮራዶ (Corrado) ባንዳ በባኮ 400 ከሚገመቱ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን 215 ተገድለዋል መንደሩ በሙሉ ሸፍታ በመሆኑ ተደምስሰዋል፡፡

ኤፕሪል 1 ቀን ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት የኮራዶ ባንዳ 300 ከሚገመቱ አርበኞች ውጊያ ገጥሞ ከጣሊያን ወገን 3 ሲሞቱ ከአርበኞች 32 ተገድለዋል፡፡ 13 አማራ ተማርከው ተገድለዋል፡፡

ኤፕሪል 13 ጀነራል ጀሉዞ በላከው ሪፖርት የኮሎኔል ማሮኔ ባንዳ ኤፕሪል 11 በወሶ ከአርበኞች ጋራ በገጠመው ውጊያ ከአርበኞች ወገን 10 ተገድለዋል፡፡ 4 አማራ ከነመሣሪያ የተገኙ ተይዘው ተገድለዋል፡፡

ኤፕሪል 20 ጀነራል ጀሉዞ በላከው ቴሌግራም በሰዶ አካባቢ ኤሶ የተባለው መንደር እንዲቃጠል ተደርገዋል፣ 21 አርበኞች ተይዘው ተገድለዋል፡፡ ዋካ በተባለው መንደር ደጃዝማች ድንቁና የሚከተሉት ሌሎች ተገድለዋል፡፡ 1. ፊታውራሪ ተሰማ ደመነ 2. ኃይሉ መኰንን 3. ሂርደ ታከለ 4. ታቸኒ 5. መሰፍን ብሩ 6. ወሰኔ 7. አሰፋው ፋሪስ 8. ተሰማ 9. 11ቀኛዝማች 10. 9 ግራዝማች

ኤፕሪል 23 ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት በቶሌ በሞሊነር የሚመሩ ባንዳዎች ከአርበኞች ጋራ ባደረጉት ውጊያ ከአርበኞች ወገን ብዙ መቶ ተገድለዋል፣ ቆስሏል፣ ብዙ ሹሞች ከሞቱና ከቆሰሉ ይገኙባቸዋል፡፡ በአርበኞች መሐል የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ተስተውለዋል፡፡ ከጣሊያን ወገን 13 ኤርትራውያን ተገድለዋል፡፡ የቆሰሉ አንድ ኢጣሊያዊ ሻምበል ሌላ ኢጣሊያዊ ዜጋ 34 ኤርትራውያን 3 ዓረብ ሶማል፡፡ የሞሊነር ባንዳ 27 አማራ ማርከው ገድለዋል፡፡ ጀነራል ፋሪነቲ (Farinetti) ጠባያቸው አጠራጣሪ ይመስል የነበረ 13 አማራዎች እንዲረሸኑ አድርገዋል፡፡ ከዚሁም

በላይ 32 አግራዎችና 100 ተከታዮቻቸው ተይዘው ታስረዋል። ጀነራል ደላ ቦና (ቢንቫንጉል) ሕዝቡ መግረፊያ እንዳያስረክብ ሲሰብክ ስለተገኙ ሁለት ሰዎች ተረሽነዋል።

ጅማ አጠገብ ተኛዝማች ሰገብ ፋንታ ተይዞ ተገድለዋል፤ እንደዚሁም ጀኮርሳ በተባለው መንደር 25 ኪሎ ሜትር ከጅማ ተኛዝማች በጋሰ ፋንታና 4 ተከታዮቹ ተይዘው ተገድለዋል።

አፕሪል 25 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት አንድ ተኛዝማች ያለባቸው አርበኞች በድንገት ተይዘው ተገድለዋል። የሞሊናር ባንዳ አንድ ተኛዝማችና 52 አግሬ አርበኞችን ማርኮ ገድለዋል። እንደዚሁም በቦንጌ አካባቢ በእሰላ የተያዙ 152 አግሬ ሽፍቶች (አርበኞች) ተገድለዋል። በሰቀምት ጀነራል ፋሬንቲ 32 የአርጆ አግሬ ሽፍቶች ረሽነዋል። ቢበቢ የተባለው ብቸኛ የቀድሞ ሹም በአርጆ አደገኛ ግለሰብ ተገድለዋል። ከመገደሉ በፊት ጥያቄ በሚደረግለት ጊዜ 6 ጥይቶች ካልታወቁ ሰዎች ስለተተኮሱ የአርጆ መንደር በሙሉ በእሳት እንዲቃጠል ተደርጓል፤ ስወደፊት ቁጥራቸው የሚገለጽ ብዙ ሰዎች ተገድለዋል።

አፕሪል 26 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው የማብራሪያ ሪፖርት በአርጆ የሕዝብ ጭፍጨፋ ስንት ሰው እንደተገደለ ገና አላውቅም ብሏል። በተቃጠሉ ቤቶች ብዙ የጦር መሣሪያዎች ተገኝቷል ወርቅ ግን አልተገኘም ብለዋል። የአርጆ ጉዳይ ለወደፊት ችግር እንደማይፈጥርብን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያከተመ ይመስላል።

የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ በኢትዮጵያ 1ኛ ዓመት ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ይመስላል። በቀሩት 4 ዓመታት የተፈጸሙት ወንጀሎች ከዚህ የባሱ እንጂ ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም። ጣሊያኖች በፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ በጦር ወንጀለኝነት ወይንም በር በማጥፋት ወንጀል

አልተጠየቁም። ብዙ ኢትዮጵያውያን ግን በነዛ ወንድሞቻቸው በፈጸሙት ወንጀል በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሷል። እንደ ደንቡ ከሆነ ኢትዮጵያውያን በነዛ ወንድሞቻቸው የፈጸሙት ወንጀል የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊባል አይገባም ምክንያቱም የፖለቲካ አክራሪነት ወንጀል ነው። በሌላ የዓለም ክፍሎችም የተከሰተ ነው። የዘር ማጥፋት የሚባለው ናዚስት ጀርመኖች በይሁዶች ላይ የፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ ነው። ጀርመኖች የመፍጀት ዓላማ የነበራቸው 6 ሚሊዮን ይሁዶች ብቻ አልነበረም፤ ዓላማቸው በዓለም ያሉትን ይሁዶች ሁሉ ለመፍጀት ነበር። ጣሊያኖችም ዘረኝነታቸው በጥቁሮች ላይ ስለነበረ እንደ ጀርመኖች ለማድረግ አይመስሉም ነበር። እጠቃላይ የጥቁር ሰው ፍጅት ያላደረጉበት ምክንያት በርሕሩሕነታቸው ሳይሆን ሁኔታዎች ስላልተመቻቹላቸው ብቻ ነው። ሌላ ምክንያትም ነበረ፤ ከፊል ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ፈጅተን ጨርሰን በመሬቱ ጣሊያኖች እናሰፍርበት የሚሉ ነበሩ፤ ሌሎች ጣሊያኖች ደግሞ ጥቁሮች ይጠቅሙናል አገልጋዮች እናደርጋቸዋለን መፍጀት የለብንም የሚሉ ነበሩ። በክርክር ላይ እንዳሉ ከሀገራችን ተዋርደው ወጥቷል። ጣሊያኖች ወራዳ መሆናቸው ስለማይሰማቸው አሁንም በነ አድራጊዎች ነን እያሉ እየለፈለፉ ይገኛሉ።



# ክፍል 2

## የኢጣሊያ ዘረኝነት
## ምዕራፍ አንድ ቅድመ ፋሺዝም ዘረኝነት

### 1. ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝና ዘረኝነት መሥራች 1891

ኢጣሊያ በዐድዋ ሽንፈት ከገጠማት በኋላ የኤርትራ ሀገረ ገዢ ብላ ሾማ ልኳ ለአሥር ዓመት ከ1897 ዓ.ም. ጀምሮ የነዛ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የተባለው ሰው የተሰካና ተወዳድ በኤርትራ ውስጥ እስከዛሬ ጨቋኝ የቅኝ ግዛት አስተዳደር በመመሥረቱ ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የኢጣሊያን ቅኝ ግዛቶች እንዲሰራበት ተደርጎ ኢጣሊያ ተወዳዳሪ የሌላት ጨቋኝ ቅኝ ገዥ እንድትሆን አድርጓታል። ይህ ሰው የኤርትራ ሀገረ ገዥ ተብሎ ከመሾሙ ከ6 ዓመት በፊት በ1891 ዓ.ም. በደረሰው መጽሐፍ የኢጣሊያ ዓላማ ዜጎቿን በኤርትራ ማስፈር ስለሆነ ለሀገሩ ተወላጆች የምታደርግላቸው እርዳታ ከምድረ ገጽ ቀሉ ብሰው እንዲጠፉ ማድረግ ብቻ ነው ብሎ ነበር። ከፋሺዝም በፊት ሆነ በኋላ መጽሐፉ ለአሥር ጊዜ ታትሞ የወጣ በመሆኑ በኢጣሊያን ሕዝብ ዘንድ መጽሐፉ ምን ያህል ተወዳጅነት እንደነበረው ያሳያል፤ የጣሊያኖች ገንነትም አጉልቶ የሚያሳይ ነው። 1/ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የእንግሊዝ ወይም ፈረንሳይ ዜጋ ቢሆን ኖሮ እንኳን ሹመት ሊሰጠው የሕዝብ ተቃውሞ ተነስቶበት በሕይወቱ ለመኖር በሚያሰጋው ደረጃ ይደርስበት ይችል ነበር። በኢጣሊያ ግን እጅግ ሰው የሚያሰኘው ነበር። በሕዝቡ ሊፓርላማ ለ45 ዓመታት ተመርጦ ሰርተዋል። ከኢጣሊያ ንጉሥ ልዩ አክብሮት አግኝቷል። በኢጣሊያ መንግሥታት ቅድመ ፋሺስትና በፋሽስት ዘመን ከፍተኛ ሥራና ሹመት ማዕረግ አግኝቷል።

Diario Eritreo የተባለው በሕይወት እንዳለ የደረሰው መጽሐፍ የታተመው ዘድሀረ ፋሺዝም በዲሞክራሲ የሚባለው የኢጣሊያ መንግሥት ጊዜ ነው። የእጅ ጽሑፍ ከልጁ የተረከበው መጽሐፍ በሚታተመበት ጊዜ ማርቲኒ ሞቶ ስለነበረ ልጁም ሞቶ ስለነበረ የእጅ ጽሑፉ ተረክበው እንዲታተም ያደረጉ ሰዎች መጽሐፉን ለማስታወቅ 60 ገጽ መቅድም በመጽሐፍ በአስተዳደር አዋቂነት በከፍተኛ ደረጃ አዋቂ በማድረግ እያወደሱ ጽፈውለታል። የኢጣሊያ መንግሥት እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ እንዳለው እያወቀ ሀገረ ገዥ ሹሞ መላኩ በዓላማው ተስማምቶበት ዓላማውን በሥራ እንዲያውለው ነው የላከው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በሥራ ላይ ለማዋል ያልሞከረበት ምክንያት ኢትዮጵያ፤ ሱዳን፤ ጅቡቲ፤ የኤርትራ ጎረቤቶች ስላሉ ሕዝቡ ወደእነዚህ ሀገሮች ለመሸሽ ስለሚችል ከንቱ ሙከራ ስለሆነበት ነው። አልሞከረም ለማለትም አይቻልም፤ በአነስተኛ ደረጃ ወደ አሰብ እና ወደ ደሴቶች ወደ ናቅፋ እየተላኩ የሚያጠፉቸው ሰዎች ነበሩ።

ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በመደነቅም ሆነ በመውቀስ ስለ ሻእቢያ ስለ ኢሕአዴግ እንደዚሁም ስለ እነገ መድህን ወዘተ... መከራከር ይወዳሉ፤ ስለ ጣሊያኖች ሲነሳ ግን ከታሪክ ምሁራን ሳይቀር እንዲነሳ አይፈልጉም፤ እነሱ ተኖቸው ያሉኝ ምሑራን እስታውሳለሁ። ትክክል አስተሳሰብ አይመስለኝም ዋና ጠላታችን ትተን እርስ በእርሳችን መነታረክ ውጤት ያለው አይመስለኝም።

በላይ 32 አግራዎችና 100 ተከታዮቻቸው ተይዘው ታስረዋል። ጀነራል ደላ ቦና (ቤንቫንቶል) ሕዝቡ መሣሪያ እንዳያስረክብ ሲሰብኩ ስለተገኙ ሁለት ሰዎች ተረሽነዋል።

ጅማ አጠገብ ተኛዝጎች ለገበ ፋንታ ተይዞ ተገድለዋል፤ እንደዚሁም ጀኮርሳ በተባለው መንደር 25 ኪሎ ሜትር ከጅማ ተኛዝጎች ቦጋለ ፋንታና 4 ተከታዮቹ ተይዘው ተገድለዋል።

አፕሪል 25 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት አንድ ተኛዝጎች ያለባቸው አርበኞች በድንገት ተይዘው ተገድለዋል። የሞሊናር ባንዳ አንድ ተኛዝጎችና 52 አግራ አርበኞችን ማርኮ ገድለዋል። እንደዚሁም በቦንጊ አካባቢ በአሰላ የተያዙ 152 አግራ ሽፍቶች (አርበኞች) ተገድለዋል። በሰተምት ጀነራል ፋሬኔቲ 32 የአርጆ አግራ ሽፍቶች ረሽነዋል። ቢበሺ የተባለው ብቸኛ የቀድሞ ሹም በአርጆ አደገኛ ግለሰብ ተገድለዋል። ከመገደሉ በፊት ተያቂ በሚደረግለት ጊዜ 6 ጥይቶች ካልታወቁ ሰዎች ስለተተኮሱ የአርጆ መንደር በሙሉ በእሳት እንዲቃጠል ተደርገዋል፤ ስወደፊት ቁጥራቸው የሚገለጽ ብዙ ሰዎች ተገድለዋል።

አፕሪል 26 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው የማብራሪያ ሪፖርት በአርጆ የሕዝብ ጭፍጨፋ ስንት ሰው እንደተገደለ ገና አላውቅም ብሏል። በተቃጠሉ ቤቶች ብዙ የጦር መሣሪያዎች ተገኝቷል ወርቅ ግን አልተገኘም ብለዋል። የአርጆ ጉዳይ ለወደፊት ችግር እንደማይፈጥርብን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያከተመ ይመስላል።

የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ በኢትዮጵያ 1ኛ ዓመት ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ይመስላል። በቀሩት 4 ዓመታት የተፈጸሙት ወንጀሎች ከዚህ የባሱ እንጂ ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም። ጣሊያኖች በፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ በጦር ወንጀለኝነት ወይንም ዘር በማጥፋት ወንጀል

አልተጠየቁም። ብዙ ኢትዮጵያውያን ግን በገዛ ወንድሞቻቸው በፈጸሙት ወንጀል በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሷል። እንደ ደንቡ ከሆነ ኢትዮጵያውያን በገዛ ወንድሞቻቸው የፈጸሙት ወንጀል የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊባል አይገባም ምክንያቱም የፖለቲካ አክራሪነት ወንጀል ነው። በሌላ የዓለም ክፍሎችም የተከሰተ ነው። የዘር ማጥፋት የሚባለው ናዚስት ጀርመኖች በይሁዶች ላይ የፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ ነው። ጀርመኖች የመፍጀት ዓላማ የነበራቸው 6 ሚሊዮን ይሁዶች ብቻ አልነበረም፤ ዓላማቸው በዓለም ያሉትን ይሁዶች ሁሉ ለመፍጀት ነበር። ጣሊያኖችም ዘረኝነታቸው በጥቁሮች ላይ ስለነበረ እንደ ጀርመኖች ለማድረግ አይመለሱም ነበር። አጠቃላይ የጥቁር ሰው ፍጅት ያላደረጉበት ምክንያት በርሕሩሕነታቸው ሳይሆን ሁኔታዎች ስላልተመቻቹላቸው ብቻ ነው። ሌላ ምክንያትም ነበረ፤ ከፊል ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ፈጅተን ጨርሰን በመሬቱ ጣሊያኖች እናስፍርበት የሚሉ ነበሩ፤ ሌሎች ጣሊያኖች ደግሞ ጥቁሮች ይጠቅሙናል አገልጋዮች እናደርጋቸዋለን መፍጀት የለብንም የሚሉ ነበሩ። በክርክር ላይ እንዳሉ ከሀገራችን ተዋርደው ወጥቷል። ጣሊያኖች ወራዳ መሆናቸው ስለማይሰማቸው አሁንም በነ አድራጊዮች ነን እያሉ እየለፈለፉ ይገኛሉ።



# ክፍል 2

## የኢጣሊያ ዘረኝነት
## ምዕራፍ አንድ ቅድመ ፋሺዝም ዘረኝነት

### 1. ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝና ዘረኝነት መሥራች 1891

ኢጣሊያ በዐድዋ ሽንፈት ከገጠማት በኋላ የኤርትራ ሀገረ ገዢ ብላ ሾማ ልካ ለአሥር ዓመት ከ1897 ዓ.ም. ጀምሮ የገዛ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የተባለው ሰው የተስካና ተወላጅ በኤርትራ ውስጥ እስከሬ ጨዳኝ የቅኝ ግዛት አስተዳደር በመመሥረቱ ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የኢጣሊያን ቅኝ ግዛቶች እንዲሰራበት ተደርጐ ኢጣሊያ ተወዳዳሪ የሌላት ጨዳኝ ቅኝ ገዥ እንድትሆን አድርጓታል። ይህ ሰው የኤርትራ ሀገረ ገዥ ተብሎ ከመሾሙ ከ6 ዓመት በፊት በ1891 ዓ.ም. በደረሰው መጽሐፍ የኢጣሊያ ዓላማ ዜጐቿን በኤርትራ ማስፈር ስለሆነ ለሀገሩ ተወላጆች የምታደርግላቸው እርዳታ ከምድረ ገጽ ቶሎ ብለው እንዲጠፉ ማድረግ ብቻ ነው ብሎ ነበር። ከፋሺዝም በፊት ሆነ በኋላ መጽሐፉ ለአሥር ጊዜ ታትሞ የወጣ በመሆኑ በኢጣሊያን ሕዝብ ዘንድ መጽሐፉ ምን ያህል ተወዳጅነት እንደነበረው ያሳያል፤ የጣሊያኖች ገንነትም አጉልቶ የሚያሳይ ነው። 1/ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የእንግሊዝ ወይም ፈረንሳይ ዜጋ ቢሆን ኖሮ እንኳን ሹመት ሊሰጠው የሕዝብ ተቃውሞ ተነስቶበት በሕይወቱ ለመኖር በሚያሰጋው ደረጃ ይደርስበት ይችል ነበር። በኢጣሊያ ግን አዋቂ ሰው የሚያሰኘው ነበር። በሕዝቡ ለፓርላማ ለ45 ዓመታት ተመርጦ ሰርተዋል። ከኢጣሊያ ንጉሥ ልዩ አክብሮት አግኝቷል። በኢጣሊያ መንግሥታት ቅድመ ፋሺስትና በፋሺስት ዘመን ከፍተኛ ሥራና ሹመት ማዕረግ አግኝቷል።

Diario Eritreo የተባለው በሕይወት እንዳለ የደረሰው መጽሐፍ የታተመው ዘድሀረ ፋሺዝም በዲሞክራሲ የሚባለው የኢጣሊያ መንግሥት ጊዜ ነው። የእጅ ጽሑፍ ከልጁ የተረከበው መጽሐፍ በሚታተመበት ጊዜ ማርቲኒ ሞቶ ስለነበረ ልጁም ሞቶ ስለነበረ የእጅ ጽሑፉ ተረክቦ እንዲታተም ያደረጉ ሰዎች መጽሐፉን ለማስታወቅ 60 ገጽ መቅድም በመጽሐፍ በአስተዳደር አዋቂነት በከፍተኛ ደረጃ አዋቂ በማድረግ እያወደሱ ጽፈውለታል። የኢጣሊያ መንግሥት እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ እንዳለው እያወቀ ሀገረ ገዥ ሹሞ መላኩ በዓላማው ተስማምቶበት ዓላማውን በሥራ እንዲያውለው ነው የላከው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በሥራ ላይ ለማዋል ያልሞከረበት ምክንያት ኢትዮጵያ፤ ሱዳን፤ ጅቡቲ፤ የኤርትራ ጎረቤቶች ስላሉ ሕዝቡ ወደእነዚህ ሀገሮች ለመሸሽ ስለሚችል ከንቱ መከራ ስለሆነበት ነው። አልሞከረም ለማለትም አይቻልም፤ በአነስተኛ ደረጃ ወደ አሰብ እና ወደ ደሴቶች ወደ ናቅፋ እየተላኩ የሚያጠፋቸው ሰዎች ነበሩ።

ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በመደነቅም ሆነ በመውቀስ ስለ ሻእቢያ ስለ ኢሕአዴግ እንደዚሁም ስለ እነግ መድህን ወዘተ... መከራከር ይወዳሉ፤ ስለ ጣሊያኖች ሲነሳ ግን ከታሪክ ምሁራን ሳይቀር እንዲነሳ አይፈልጉም፤ እነሱን ተኞቹው ያሉኝ ምሑራን አስታውሳለሁ። ትክክል አስተሳሰብ አይመስለኝም ዋና ጠላታችን ትተን እርስ በእርሳችን መነታረክ ውጤት ያለው አይመስለኝም።

ማርቲኒ ሌሎች ኢጣሊያኖችም በአየአጋጣሚ ነጭ ዘሮች ከውካዚያን አሪያን መሆናቸው መግለጽ ይወዳሉ፡፡ ነገር ግን ማርቲኒ የነጭ ዘር አልነበረም፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ጣሊያኖች የነጭ ዘር አሪያን አይደሉም፡፡ እኛ ስለራሳችን የጕሳዎች ክምችት ሙዘየም እያልን በመገናኛዎች እናስራጫለን፣ ነገር ግን ፈረንጆቹ ከእኛ የባሱ የጕሳዎች ክምችት ናቸው፡፡

ስለ ኢጣሊያ ጕሳዎች በየመጸሐፉ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ከዚህ በታች ያለው ግን የተወሰደው ከኢንሳይክሎፐዲያ ትሬካኒ 1938 ነው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| -1/ ላቲኒ Latini | 2/ሮማውያን Romani | 3/ፋሊሺ Falishi |
| 4/ ኢኩዊ Equi | 5/ ኤርኒቺ Emic | 6/ሳቢኒ Sabini |
| 7/ ኡምብሪ Umbri | 8/ ማርሲ Marsi | 9/ ፔሊኚ Peligni |
| 10/ ፒቼንቲ Picenti | 11/ ፓቱትሲ Patuzzi | 12/ቬስቲኒ Vestini |
| 13/ ማሩቺኒ Marrucini | 14/ካምፓኒ Campani | 15/ፍሬንታኒ Frentani |
| 16/ሉካኒ Lucani | 17/ብሩትሲ Bruzi | 18/ያፒቺ Yapici |
| 19/ቬልቪ Velvi | 20/ሳኒቲ Saniti | 21/ፔንቼዚ Pencezi |
| 22/ሜሳፒ Mesapi | 23/ሰለንቲኒ Selentini | 24/ ኤትሩስኪ Etruschi |
| 25/ግሬክ Greci | 26/ሊጉሪ Liguri | 27/ቬነቲ Veneti |
| 28/ጋሊ Galli | 29/ኢንሱብሪ Insubri | 30/ቼኖማኒ Cenomani |
| 31/ሊምፖኒ Limponi | 32/ሰኖኒ Senoni | 33/ሲኩሊ Siculi |
| 34/ሲካኒ Sicani | 35/ኤሊዮኒ Elioni | 36/ኮርሲ Corsi |
| 37/አንሲኒ Ansini | 38/ኤናትሪ Enatri | 39/ፖሌፊትኮሊ Polefittcoli |
| 40/ቪለዮቲያኒ Villeotiani | 41/ሳኒቲ Sanniti | 42/ካራቼኒ Caraceni |
| 43/ኢርፒኒ Irpini | 44/ላውዲኒ Laudini | 45/አፒጊ Apighi |
| 46/ሊንጐኒ Lingoni | 47/ቦይ Boi | 48/አውሶኒ Ausoni |

ወዘተ etc. ተራ ቁጥሩ እስከ መቶ ሊደርስ ይችላል፡፡

ኢንቺክሎፔዲያን ትሬካኒ የኢጣሊያ ጕሳዎች ዝርዝር ካቀረበ በኋላ በእርግጥ አሪያን ዘር ያልሆኑ ኤትሩስካውያን ናቸው ብሏል፣ አጠራጣሪ ሊጉሪ፣ ሳርዲ ኮርሲ ኢሊኒ ናቸው ብሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 1/ የኢጣሊያ ቋንቋ የፈጠሩ 2/ ኢጣሊያ በዓለም አቀፍ ስሟን የሚያስጠሯትና 90% በላይ የኪነ ጥበብና ጽሑፍ የፈጠሩ 3/ ለሮማውያን የሥልጣኔ መሠረት ያስተማሩ 4/ በዘርም ከሮማውያ ጋር የተዛመዱ 5/ በዛሬ ጊዜ ዋና ዘረኝነት የሚጸባረቅባቸው እና የዘረኝነት አራማጅ የሆኑ ኤትሩስካውያን ወይንም ቶስካና ናቸው፡፡ በኢንቻይክሎፐዲያ ትሬካኒ መሠረት በእርግጥ ነጭ ዘር እንዳልሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ ሌሎች እንደ ሊጉሪ ኢጣሊያ በመርከብ ጉዞ ስሟን ያስጠሩ በኢጣሊያ ምድር ቀደምት ነዎሪዎች ስለሆኑ አሪያን ነጭ ዘር እንዳልሆኑ ይታመናል፡፡ ቬኒሲያ በመካከለኛ ምስራቅ በንግድም በፖለቲካም ታዋቂነት የነበራቸው ከትሮያ ትንሿ እስያ የመጡ ናቸው በሚባሉ ምናልባት ነጭ ዘር አሪያን እንዳልሆኑ ይታመናል፡፡

በ2ኛው የዓለም ጦርነት ጀርመናዊ ሂትለር የኢጣሊያ የጦር ጓድ የነበረው አሸንፎ ቢሆን ኖሮ ንጹህ የነጭ ዘር ያልሆነ ሁሉ ለመፍጀት በነበረው ዓላማ መሠረት እነ ማርቲኒ እያበጠረ ስድስት (6) ሚሊዮን እስራኤላውያን የተፈጁበት እጣ ይደርስባቸው ነበር፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ የኢጣሊያ ጕሳዎች መካከል በእርግጥ አሪያን ዘር አይደሉም የተባሉ ኤትሩስካውያን የኢጣሊያ ታሪክ ሰረዶች መሆናቸው ኢጣሊያን ከ12ኛው መቶ



ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሬነሳንስ (Renaisance) በሁሉ መስክ ኢጣሊያን አንቱ ያሰኙዋት መሆናቸው በአሪያን ዘር የበላይነት የሚያምኑ ጣሊያኖች ትልቅ ውርደት ነው፡፡

ጣሊያኖች ትግራይን እርስ በእርስ እንዲጣላ ያደርጉ የነበረ ከአጼ ዮሐንስ ጊዜ ጀምረው ነው፡፡ በአጼ ዮሐንስና በራስ አሉላ መካከል ጣሊያኖች ለመጨረሻ ጊዜ መጠነኛ ቅራኔ ተፈጥሮ ነበረ ተብሎ የተወራው ወሬ የኢጣሊያ እጅ ስላለበት ነው ተብሎ ጥርጣሬ የነበረው ከእውነት የራቀ አልነበረም፡፡ እንደዚሁም በመተማ የደረሰ የአጼ ዮሐንስ የመጀመሪያ ሽንፈትና ሞት የኢጣሊያ እጅ እንዳለበት ይታመናል፡፡ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ለ10 ዓመት የኤርትራ ሀገረ ገዥ በነበረበት ጊዜ የትግራይ ሹማምንትን እርስ በእርሳቸው እንዲጣሉ ትግራይን ወደ ውድቀት ደረጃ እንድታመራ ያላደረገው ጥረት የለም፡፡ ደቡባዊ የኤርትራ አውራጃዎች በትግራይ የስለላ ድርጅት ማእከል የነው ያገለግሉ ነበር፡ እከሌ ተሾመ እከሌ ተሻረ እንክሊ ተጣሉ ታሰሩ ተፈቱ የሚሉ ጥቃቅን ዜናዎች እንደ ትልቅ ነገር ወደ ሀገሩ በማስተላለፍ የሀገሩ ጋዜጦች ሳይቀሩ የስለላ ድርጅት ነው ወይስ ሀገረ ገዥ ነው ብለው ሲተቹበትና ሲያፌዙበት ነበር፡፡

ፈርዲናንዶ ማርቲኒ በ1891 ዓ.ም. ወደ ኤርትራ የሔደው የኤርትራን ሁኔታ ለማጥናት የአንድ መንግሥታዊ ኮሚሽን አባልና ምክትል ሊቀመንበር በመሆን ነበር፡፡ ኮሚሽኑ በኤርትራ የቆየው ለሁለት ወር ነበር፡፡ በ1891 ዓ.ም. የአሁኗ ኤርትራ ከሞላ ጐደል በኢጣሊያን እጅ ገብታ ነበር፡፡ የኤርትራ ስም በአዋጅ የወጣው በ1890 ዓ.ም. ነበር፡፡ አጼ ዮሐንስ የሞተው በ1889 ዓ.ም. ነበር፡፡ በዚህ ዓ.ም. ጣሊያኖች አስመራን ያዙ፡፡ ኮሚሽኑ ስራውን አጠናቆ ወደ ምጽዋ ተመልሶ ወደ ጣሊያን ሀገር ከመመለሱ በፊት ከባላባቶችና ከታዋቂ ግለሰቦች በምጽዋ ስንብት በሚያደርግበት ጊዜ ማርቲኒ ከሁለት ግለሰቦች ያደረገው ውይይት በማተኮር ስለአፍሪካ የሰጡት አስተያየት ካዳመጠ በኋላ የራሱ ሃሣብም በማስፈር የጻፈው በሀገራችን ወሳኝ ስለሆነና የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ስለሆነ ዋና ዋና ውይይቶችና ማርቲኒ ከሰጠው አስተያየት ጋራ አቀርባለሁ፡፡ በመጀመሪያ ያነጋገረው ናሬቲ የተባለው ኢጣሊያዊ፣ ሙያው አናጺ ሆኖ ብዙ ዓመት ከአጼ ዮሐንስ ጋራ የኖረ ነበረ፡፡ ናሬቲ የቀድሞው ጌታው አጼ ዮሐንስ ትልቅነት፣ ደግነት፣ ማውራት ጀመረ፡፡ ናሬቲ በንግግሩ ስላልተስማማውና ደስ ስላላሰኘው ማርቲኒ እሱን አቋርጦ አፍሪካን የበለጠ የሚያውቅ እግረ መንገዱን በምጽዋ ይገኝ ከነበረው ከታዋቂው ጀርመናዊ ስቫይንፉርት ጨዋታ ጀመረ፡፡ [1] ስቫይንፉርት አፍሪካን ለብዙ ዓመታት ጐብኝቶ ለኤውሮጳ ያስታወቀ ሰው ነበረ፡፡ ማርቲኒ እና ስቫይንፉርት እንደ ሂትለርና ሙሶሊኒ በሃሣብ ተስማሙ፡፡ ስለአፍሪካ ሕዝብ ልዩ እውቀት ባለው መሠረት ስቫይንፉርት አስተያየቱን ስለ ኢትዮጵያውያን ሲሰጥ የሐበሻ ሕዝብ በድንቍርና ምክንያት ሁሉም ነገር ያወድማል፡፡ ሥራ በመጥላትም ማንኛውንም ነገር ሲበላሽና ሲገነጠል ዝም ብሎ ያያል፡፡ የሐማሴንና የትግራይ ሕዝብ እናንተ ምናልባት በድህነታቸው ርህራሔ ያድርባችሁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን እነርሱ በውዴታቸው ድህነት የሚፈጥሩ ናቸው፣ የተበላሹ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ለማንኛውም ነገር ችሎታ የሌላቸው ለማንኛውም ዓይነት ለማሻሻል ፍላጐት የሌላቸው ሕዝቦች ናቸው፡፡ ሱዳኖች የተሻሉ ናቸው የማእከላዊ አፍሪካ ጥቁሮችም የተሻሉ ናቸው፡፡ በነዚህ የሐበሻ ሕዝቦች መሐል ሥልጣኔ የማስፋፋት ምግሌ በመሆን ትምህርት ለመስጠት መሞከር ማለት የየዋሆች ሕልም ነው፡፡ የገርዖች

---

[1] F Martini ibd p 50-60

ፍላጐት ትልም አይደለም። አንድ የሰው ዘር አጥፍቶ በቦታው ሌላ የሰው ዘር ተክቶ ማስፈር ነው የሚያስፈልግ ከዚህ የተለየ ሃሣብ ያለው ሰው ፍሬ ቢስ ወሬ ያወራል፣ በሐንጉል የማያስብ ሰው ነው። ማርቲኒ ቫይንፋርት ስለ አፍሪካ ረጅም ጊዜ ልምድ እውቀት ካለው አስተያየት ከደመጠ በኋላ ሃሣቡን በማጠቃለል ከኢትዮጵያ ጋራ ያለው የንግድ እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጾ ለኢትዮጵያውያን ት/ቤት ስለመክፈት አስፈላጊ አለመሆኑም ብሎ ከአጥላላ በኋላ ስለዘረኝነት ያለው አስተያየቱ በመደምደም በሚከተለው ባይነት ያብራራዋል። (1) "አንዳንድ ሰዎች እኛ ወደ አፍሪካ የሔድን የአፍሪካ ሕዝብን ለማሰልጠን ነው የሚሉ አሉ። እኛ እንደዚህ ካለን ውሸታሞች ነን። ወደ ኢትዮጵያ ስልጣኔ እንዲስፋፋ ተስፋ እናደርጋለን ብንል ውሸታሞች ነን። ስለ አፍሪካ ጉዳይ ልክ እንደ ቫይንፋርት ለማወቅ አንድ ሰው ለብዙ ዓመታት በአፍሪካ መኖር አያስፈልገውም። በሚገባ ተጠቅሞ ለማጥናት ሁለት ወር ብቻ በአፍሪካ ማሳለፍ በቂ ነው። ኢትዮጵያውያን ኋላ ቀር ጉሥዎች የጣኦት እምነት ያላቸው አይደሉም። ከብዙ ምእተ ዓመታት ክርስቲያን ናቸው፣ የመንግሥታቸው መዋቅር የብዙ ምዕተ ዓመታት ታሪክ ያለው ነው። በዚህም ሀገር ወራሪዎችና ሀገር ጉብኚዎች ከብዙ ምእተ ዓመታት ጀምረው የኤውሮፓ ስልጣኔ ለማስገባት ሞክረው ነበር። ይህ ሕዝብ ግን አልፈለገም። ገዢዎቻቸው በብሉይ ኪዳን ጊዜ እንደነበሩ ናቸው። ባህሉቹ በሄሮዶትስ ጊዜ የነበሩ ናቸው። በሀገራቸው የቀረው አነስተኛ የሰው ሐንጉል ሥራ፣ ከማውደም ለማስቀረት ብለን እንጥር ይዞናል፣ የእርስ በእርስ ጦርነት እንዳይካሔዱ ለማድረግ እንጥር ይሆናል። ለዚህ ጉዳይ ብለን ዘየቀኑ ሐበሾች ሌሎች ሐበሾችን እንዲገድሉ እንቀጥራለን እንከፍላለን። እውነቱን ለመናገር እኛ በኤውሮጳ ቦታ ጠቦናል በኢትዮጵያም ሶስት አራት ሰዎች በአንድ ስኩየር ኪሎ ሜትር ይኖራሉ። ቅኝ ግዛቶች ለእኛ ሐጢያተኛ የሆኑ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ስልጣኔ ግን አትበሉት ኢትዮጵያ መሠልጠን አለባት የሚል ሰው ቢኖር በሃሰት ወይም በሞኝነት የተነሳ ነው። የዛሬ 30 ዓመት መንዚንገር እንደዚህ ብሉ ተናግር ነበር። ለእኛ ተግባር የሀገሩ ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ችግር ፈጣሪ ናቸው አስፈላጊያችን አይደሉም።

ስለሆነም እኛ ብንወድም ባንወድም እነሱ ዘሚጠሉት በዘመናዊ ሥልጣኔ መማሪያ ተጠቅመን አይሂችሁ ብለን እያበረታታን እንደቀይ ሕንዶች ከዚህ ዓለም እንዲጥፉ ማድረግ አለብን። ነገሩ አሳዛኝ ነው ነገር ግን ሃቁ ይኸው ነው፣ የዋህ ቅኝ ገዢዎች ይጽናኑ፣ እኛ የዛሬ ትውልድ ሰዎች ጀምረነዋል፣ የአፍሪካ የቀድሞ ነዋሪዎቹን ለማጥፋት፣ የሚቀጥሉ ትውልዶችም ይቀጥሉታል። የመጨረሻ አፍሪካዊ ሰው ግን አንገድለውም ጥቁሮችን በአፍሪካ ምድር አጥፍተን የባሪያ ንግድ በማስወገዳችን በሙዚዎ ሊያመሰግነን እንዲኖር ለሥልጠና በአንድ ኮሌጅ እናስገባዋለን። የዚሁ ጽሑፍ የመጨረሻ ገጽ የወጣ ፎቶ ኮፒ ተመልከት። ይህ ከላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ ለኢጣሊያ ዘረኝነት መሠረተ ድንጋይ የጣለ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ስለደቻዝጣች ባሀታ ሐጎስ(2) ሲጽፍ ወንድሙን በመግደሉ እንስቶ ማርቲኒ በዚህ አጋጣሚ ስለ ሐበሾች ጸባይ በአጠቃላይ ሲጽፍ ሐበሾች ለሃይማኖት አዲሶች አይደሉም። እንደጉም የሚጠፉ ሃይማኖት የላቸውም። ጥንታዊና የበሰሉ ሕዝብ ናቸው። በተግባር ሃይማኖትን አክባሪ ናቸው። አንዳንድ የሃይማኖት ሥነ ሥርዓት ወጐች ጥብቅ አክባሪ ናቸው።

---

(1) F : Martini ibd p 60-6
(2) F. M. ibd p 199



የውስጥ የሃይማኖት ፍቅር ግን የላቸውም፣ የሃይማኖት ወጐቻቸውን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ በሚፈልግ ሰው ሁሉ አምጸው ይነሳሉ። ከሃይማኖት ለኑሮዋቸው ትምህርት ለመቅሰም ችሎታም ፍላጐትም የላቸውም። የክርስቲያን እምነት አማኞች ሕዝቦች ናቸው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ትእዛዝን ከማክበር ግዴታ ነጻ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ ብሎ ጽፈዋል።

ማርቲኒ እንደሌሎች ጣሊያኖች በሙሉ ክርስቲያኖች ናቸው ከሁሉም በላይ እኛ ክርስቲያን ነን የሚሉ የካቶሊክ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ናቸው። ኤርትራውያን በጠቅላላ አፍሪካውያንን እንፈጃችኋለን እነሱን ፈጅተን ኤርትራ እንዲሁም መላው አፍሪካ ጣሊያኖችን እናስፍርበታለን ብለው በይፋ በመጻፍ አትመው ሲያወጡ የክርስቶስ ሃይማኖት ተከትለው ነውን? አብዛኛው ኢጣሊያኖች ማርቲኒም ጭምር የክርስቶስ ሃይማኖት አክባሪ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ አፍሪካን በሚመለከት ግን በሰው እኩልነት የሚደነግገው የክርስትና ሃይማኖት ጣሊያኖችን አይመለከታቸውም ማለት ነውን? ሊጥሱ እንደሚችሉ ከነፍስ አባታቸው አስፈቅደው ነውን? ከኢትዮጵያዊ መሐል ነፍስ ገዳዮች አሉ፣ በዘር ለይተው የጅምላ ነፍስ ገደዮች ግን በጣሊያኖችና በጀርመኖች ብቻ ነው የታየው። ስለዚህ ማርቲኒ ስለ ኢትዮጵያውያን የክርስትና እምነት መተቸትን ትቶ ለራሱ ጉድለት ማወቅ ይኖርበት ነበር። ማርቲኒ በራስ አሉላ ላይ ጠላቶቹን በቂም በቀል ያለማቋረጥ ያሳድዳል ብሎ ነበር። ይህ የቂም በቀል ግን በራሱ በማርቲኒ የሚታይ ጸባይ ነው። የማርቲኒ ቂም በቀል ደግሞ በጥቁር ሰው ዘርና በኢትዮጵያውያን ነው። ጣሊያኖች የፈጸሙብን ወንጀሎች ብዙ ናቸው ዋናው ግን ትምህርት መከልከላቸው ነው። ሌሎች ቅኝ ገዢዎች ቋንቋቸውና ባህላቸው ማስፋፋት ኩራት ሲሰማቸው ጣሊያኖች ግን ቋንቋቸውና ባህላቸው ምናልባት ቋንቋቸው እንዳይጠቁር በመፍራት እንደሆነ ቅኝ ተገዢዎቻቸው እንዲያውቁ እንዲማሩ አይፈልጉም ነበር። በዚህ መሠረት ፈረንሳይኛ እንግሊዝኛ፣ ፖርቱጋልኛ የአፍሪካውያን መንግሥታትና ሕዝብ ኦፊሳላዊ ቋንቋ የስነ ጽሑፋቸው ቋንቋ ለመሆን በቅቷል። የእስፔን ቋንቋ እንኳን በኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥታዊ ቋንቋ ሆኖአል። ኢጣሊያ ከቀድሞ የአፍሪካ ቅኝ ገዢዎች ብቸኛ ሀገር ቋንቋዋን ለማስፋፋት ያልቻለችና ያልፈለገች ሀገር ያደርጋታል። ይህ ሁኔታ ምን ያህል አስከፊ እንደነበረ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ያሳያል። የዚህም መሥራችና መሐንዲስ ማርቲኒ መሆኑን አያጠያይቅም። አስከፊ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው የቅኝ አገዛዝ ሥነ ሥርዓት የኢጣሊያ መንግሥትና ሕዝብ ድጋፍና አይዞህ ባይነት ባይኖረው በአንድ ግለሰብ ብቻ በማርቲኒ ሃሣብ ሊመሠረት አይችልም ነበር። በዓለም ብዙ ሰዎች፣ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ጭምር ቅኝ ገዢዎች ከነበሩ ሀገሮች ከሁሉ መጥፎዎች፣ ዘረኞች፣ እንግሊዞች መሆናቸውን ይገምታሉ። በሁለተኛ ደረጃ ፈረንሳዮች ወ.ዘ.ተ ይላሉ ስለ ኢጣሊያኖች ቅኝ አገዛዝ ሲጠየቁ ጣሊያኖች ደጐች ናቸው ሲሉ ይሰማሉ። ነገር ግን ጣሊያኖች ከሁሉ የባሱ ዘረኞች ብቻ ሳይሆኑ ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው። ዘረኛ የሚባል የደቡብ አፍሪካ መንግሥትም አይወዳደራቸውም። የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ወንጀለኛ ዘረኛ የሚያሰኘው በሁለት ነገሮች ብቻ ነው 1ኛ በአፓርታይድ 2ኛ የመንግሥት ሥልጣን ለብዙሃኑ ጥቁሮች አፍሪካውያን አለመስጠቱ ነው። በኢጣሊያ የጭቆና አገዛዝ ግን ከእነዚህ ሁለት ነገሮች አልፎ ማንኛውም ቅኝ ተገዢያቸው ወደ ሀገራቸው እንዳይሄድ በመከልከል ከ3ኛ ክፍል በላይ ትምህርት ቅኝ ተገዢዎቻቸው እንዳይማሩ ለማድረግ በመጨረሻም በጅምላ በሙሉ በተለይ በኤርትራውያንና በትግሬዎች በደረሰ ግፍ እልቂት ስለሚያስተውሉ እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ሁሉ ነበር። የኤርትራ ነጻነት መደገፍ ማለት የማርቲኒ ዓላማ ማራመድ ማለት ነው።

ኤርትራን ትግራይን! ኢትዮጵያን አፍሪካን! ማጣከምና ማዋረድ ነው እንጂ ማጠናከር አይደለም። ማርቲኒ በማያወላውል አነጋገር ገልጾታል። ጥቁር ሕዝቦችን ከአፍሪካ የማጥፋት ዘመቻ እኛ የዛሬ ትውልድ ጀምረነዋል፤ የሚቀጥሉት ትውልዶች ይቀጥሉታል ብሏል። ማርቲኒ የኤርትራ ሀገረ ገዥ እንደመሆኑ መጠን በነበረው ሥልጣን ተጠቅሞ ዓላማው በስውር ያካሄድ እንደነበረ አያጠራጥርም። ኤርትራውያን ማርቲኒ በሚያወጣላቸው ቅርጽ Fedelissimi eritrei በጣም ታማኝ ኤርትራውያን የተባሉ ኢትዮጵያ ሀገራቸው መሆንዋን ረስተው ከድተው ኤርትራ በኢጣሊያ የተፈጠረች ሀገር ብቻ ሀገራችን ናት እያሉ እንዲኖሩ ተደርገዋል። የሀገራችን ታሪክ ሰሪው እኛ ሳንሆን እነ ማርቲኒ ሆኑ። 30 ዓመት እርስ በእርስ የተደረገው ጦርነት እንደ ማርቲኒ በነደፉልን ታሪክ ተጠቅመን የእነሱ አስተሳሰብ ተገዢ ሆነን እንድንኖር የታቀደ ይመስላል እንጂ ለኤርትራ ነጻነት የተዋጋን ሊሆን አይችልም። ክብራችን ታሪካችን የብዙ ሺህ ዓመት ዕድሜ ያለው ነው። ከድሮ ቅኝ ገዢዎቻችን ኢጣሊያኖች የበለጠ ረጅም ታሪክ አለን። የዛሬ ምዕራባውያን ሥልጣኔ የተጀመረው ከግብጽ መሆኑን አይካድም። ጥንታዊያን ግብጾች ግን በዓረብ ዝርያ ያላቸው ሰዎች ተወረው ተውጠው ዛሬ ዘራቸው ጠፍተዋል። ንጹህ የጥንታውያን ግብጾች ዝርያ እኛ ኢትዮጵያውያን ስለሆንን የዱሮ ግብጻውያን ምን ይመስሉ እንደነበር ለማወቅ የሚፈልጉ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መረዳት ይችላሉ። ጥራዝ ነጠቅ ዝቅተኛ አስተሳሰብ ከድሮ ቅኝ ገዢዎቻችን ተምረን ታሪካችን የመቶ ዓመት ታሪክ ነው ማለት አንችልም። ማርቲኒ ሀገረ ገዢ ተብሎ ከመሾሙ በፊት ሀገረ ገዢዎች የነበሩ ጀነራሎችም በማርቲኒ መጽሐፍ በመመራት የማይፈልጉዋቸውን ኤርትራውያን ግዞት ብለው ወደ አሰብ ይወስዷቸው ነበር። ግዞቱን ጨርሶ የሚመለስ ሰው ግን አልነበረም። ሲወራ ግን የሚወስዷቸው ወደ ዐሰብ ሳይሆን ቀይ ባህር ውስጥ እየጨመሩ ይገድሏቸው እንደነበረ ነው። ጣሊያኖች ካደረሱብን የጅምላ ግዲያ genocide በማካሔድ ቅኝ ተገዢዎች እንዲጠፉ በማድረጋቸው ያጠቃልላል።

ማርቲኒ ስለ ሐበሻ ሴቶች[1] ሲጽፍ በአሥር ዓመታቸው ያገባሉ በአሥራ ሁለት ዓመታቸው ልጆች አይደሉም። በሃያ አምስት ዓመታቸው አርጅተዋል። በሰላሳ ዓመታቸው መጃጀት ይጀምራሉ እስከ ሃመሳ ዓመት ጃጅተው መኖር ይችላሉ ብሎ ነበር። የማርቲኒ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ1891 ዓ.ም. ነበር። ከዚህ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1895 ዓ.ም. ድረስ በአራት ዓመት ውስጥ በስድስት ጊዜ ታትሞ ወጥቷል። ይህ የሚያሳየው መጽሐፉ በኢጣሊያ ሕዝብ ብዙ ተወዳጅነት አትርፎ እንደነበረ ነው። የኢጣሊያ መንግሥት የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሰው መሆኑን እያወቀ ነው ሀገረ ገዢ ሹሞ የላከብን። ማርቲኒ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ መሥራች ነው። እሱ በኤርትራ የመሠረተው ቅኝ አገዛዝ አሰራር አርአያ በመሆን በሶማሊያም በሊቢያም በሥራ ላይ ውሏል። በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ስንማቅቅ የነበርን ሁሉ አንድ ግንባር ፈጥረን መተዛዘን ሲገባን ሶማሊያ የግዛት ይገባኛል ስታቀርብብን ሊቢያ ደግሞ እስላም እንድንሆንና ዐረብ እንድንሆን ትፈልጋለች። የኢጣሊያ ዓላማ ጣሊያኖችን ዜጎቻቸው በቅኝ ግዛታቸው ማስፈር ሲሆን ስፈራም በሰፊው የተካሔደባት ሊቢያ ናት። ለአንድ ኢጣሊያዊ ሰፋሪ አሥር ሊቢያውያን በቦታ መልቀቅ ስላለባቸው አሥር ሊቢያውያኖች መገደል እንደነበረባቸው የታወቀ ነው። በሶማሊያም ጣሊያኖች የሙዝ ተከላ ስለነበራቸው የሰፋሪዎች መበርከት ሰውን መግደል ምክንያት እንደሚፈጥር

[1] F Martini ibd p 171



አያጠራጥርም። ኢጣሊያ አነስተኛ አክብሮት የሊቢያውያን ትሰጥ የነበረችው ሊቢያ በምሥራቅ በኩል ከግብጽ ነጻ መንግሥት ስትዋሰን በምዕራብ በኩልም የፈረንሳይ ግዛት ሆነው በሙሉ የፈረንሳይ ዜግነት መብት ካላቸው ነጻ ሰዎች ስለምትዋሰን ነው።

ጣሊያኖች ንጹህ የአርያን ዘርም አይደሉም። ከአፍሪካውያን ዘርም የተቀላቀሉ ናቸው ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ዘርም ድብልቅ አላቸው። ብዙ ጊዜ ሀገራቸው ከአፍሪካ የመጡ ሕዝቦች ተወራለች ንጹህ ነጮች የሚመስሉ ጣሊያኖች ካሉ እነሱ ከምሥራቅ አውሮጳ ባሪያ በማድረግ ሮማውያን ያመጧቸው ሕዝቦች ናቸው። በአንድ ወቅት ከሮማ ከተማ ሕዝብ ሲሶ 1/3 ሮማውያን ከምሥራቅ አውሮጳ በባርነት ያመጧቸው ንጹሕ ነጭ ዘር ፀጉረ ቢጫዎች ስላቮች ሲሆኑ፤ የቀሩት ኢትሩስካውያን ከመካከለኛ ምሥራቅ ከትንሿ ኢስያ ትባል የነበረችው ከዛሬዋ ቱርክ የመጡ ነጭ ዘር ያልነበሩ ሕዝቦች ናቸው። እንደዚሁም ሮማውያን ራሳቸው ከኢትሩስካውያን የተዳቀሉ ነበሩ። ሌሎች ጎሣዎች እንደ ላቲኒ ወዘተ የሮማን ከተማ ነዋሪዎች ነበሩ። እስራኤላውያን ሳይቀሩ ከሮማ ሰፋሪዎች በቀደምትነት ከሌሎች ሕዝቦች እኩል ደረጃ እንዳላቸው የሚያምኑ አሉ። ጣሊያኖች ንጹህ ነጭ ዘር አለመሆናቸው ራሱ ማርቲኒ በደረሰው መጽሐፍ እንደገለጸው ለመረዳት እንችላለን። ማርቲኒ ስለአሽከሮች (ASCARI) /ባለቀለም የኢጣሊያ ወታደሮች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፤ በሐማሴን ወይም በትግራይ ተወላጅ ከሆኑ አሽከሮች ውስጥ አንድ ብቻ ሳይሆን አሥር ሃያ ሰላሳ፤ የሚሆኑ ልክ ኡጎ ፎስኮሎ Ugo Foscolo [1] የሚመስሉ አሉ፤ ኡጎ ፎስኮሎ በ1779 ዓ.ም. ተወልዶ በ1827 ዓ.ም. የሞተ የታወቀው ዝነኛ የኢጣሊያ ቋንቋ ስነጽሁፍ ሰው ነው። ጣሊያኖች ንጹህ ነጭ ዘር ለምሳሌ እንደ ስውዲን እንደ ኖርዌይ ቢሆኑ ኖሮ ማርቲኒ እንዳለው የሐማሴን እና የትግራይ አሽከሮች በምንም ተአምር ከኡጎ ፎስኮሎ ጋር በመልክ አይመሳሰሉም ነበር።

ጣሊያኖች ኤርትራውያንን Fedelissimi በጣም ታማኝ ብለው የሚጠሯቸው የፍቅር ምልክት አይባልም። የማዋረድና የስድብ አበራር ነው። ለጣሊያኖች ታማኝ የሚሆኑበት ምክንያት ምንድር ነው? እንዴት አንዱ ሕዝብ ለሌላ ሕዝብ ታማኝ ይሆናል? ጣሊያኖች ከሮማውያን እንወለዳለን ይላሉ ሮማውያን ራሱን የቻለ ሕዝብ አልነበረም። ጣሊያኖችም የሮማውያን ዝርያዎች አይደሉም። ሮማውያን የሚታወቁት ጥንታዊው ሥልጣኔ በማራመዳቸው ሳይሆን በአንዳንድ መጥፎ ተግባራቸውና የግሪኮችን ሥልጣኔ በማውደማቸው ነው። ጣሊያኖች የሮማውያን አንዳንድ መጥፎ ምግባር በመከተላቸው ሮማውያንን ይመስላሉ ልንል እንችላለን። ጣሊያኖች ኤርትራውያንን Fedelissimi በጣም ታማኝ ብለው የሚጠሯቸው እንደ ሮማውያን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ባሮቻቸው ለሮማውያን እስከ ሰሷ ሞታቸው ድረስ ታማኝ እንዲሆኑ ስልጠና ተሰጥቷቸው በኮሎሲዩም የሮማውያን መዝናኛ ቦታ በአንበሶች ከመበላታቸው በፊት SALVE ATQUE VALE, NOS MORITURI TE[2] SALUTAMUS. Hail and farewell, we who are about to die solute thee ትርጉሙም "ሰላም ለአንተ ይሁን ቄሳር ሆይ እኛ ለሞት የተዘጋጀን ሰዎች ሰላምታችንን እንሰጥሃለን" እያሉ በተመልካቾች ፊት ያልፉ እንደነበሩ ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ለኢጣሊያኖች በባርነት እንዲገዙ ሥልጠና ተሰጥቶአቸው

[1] F. Martini ibd p 110

[2] New Standared Encyclopedia v G p 147



ergente Dalmazio Birago, Medaglia d'Oro della «Disperata»

በፎቶ የሚታየው ኢትዮጵያዊ ይመስላል በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት አባል በመሆን በኢትዮጵያ የተገደለ የወርቅ ኒሻን ያገኘ ሰው ነው። ፎቶው ጣሊያኖች አሪያን ነጭ ዘር አለመሆናቸውን ያስረዳል።



ቅኝ ገዢዎቻቸው እንዲኖሩ ለማድረግ የኢጣሊያኖች ዓላማ ነበረ። ኮሉብዶም ማለት እንደ አንድ ስታዲየም አሰራር ያለው ነው። ባሪያዎች በሜዳው ገብተው ለቄሳር ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ከልብስ መቀየሪያዎች አንበሶች ወጥተው ባሪያዎችን ሲበሉዋቸው መመልከት ሮማውያን ደስታ ስለሚሰጣቸው ለሮማውያን የመዝናኛ ጊዜያቸው ማሣለፊያ አገልግሎት የሚሰጥ ነበር። ኤርትራውያንም እንዲሁም አፍሪካውያን በሙሉ በግርቲኒ ጥላን መሠረት ሲገደሉ አቅድ የወጣላቸው መሆኑን አውቀው እስከመጨረሻ ዕድሜያቸው ጣሊያኖችን እያመለኩ እንዲኖሩ ስልጠና ተሰጥቷቸው ይኖሩ ነበር ለማለት ይቻላል። ይህ ሕግ የሚመለከተው ለኤርትራውያን ብቻ አልነበረም ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ነው። በ1928 ዓ.ም. የተደረገው ጦርነት በኋላ ለሮማ ባሮች የተሰጣቸው ስልጠና ተመሳሳይ የሆነ በሸክላ የተቀረጸ ዘፈን በአማረኛ ይዘፍን እንደነበረ ይታወሳል። ዘፈኑም "አማኑኤል ቄሳር ንጉሠ ሰላም ይኑር ዘላለም" የሚል ነበር። ዛሬም ቅኝ አገዛዝ ቀርቶ ስውር የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሲራ እየተፈጸመብን ነው። ይህ በመሆኑ እርስ በእርሳችን እየተፋጀን እንገኛለን። እኛ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ከኢጣሊያኖች እናንስም ከሶማሊያ አንድ ግንባር ከፈጠርን ደግሞ በሕዝብ ብዛት ከጣሊያኖች ልንበልጥ እንችላለን። ሽማኀታችን እንደሆን ከአባቶቻችን በዶጋሊ እና በአድዋ አላይተናቸዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጣሊያኖች ቂም በቀላቸው ስለማይረሱ አሁንም እንደግርቲኒ ጊዜ "ሞት ለአፍሪካውያን" ብለው እንደሚያውጁብን ሁሉ ለእልቂት ስለሚመኙልን እኛም "ሞት ለኢጣሊያኖች" ብለን በመነሳት በተጠንቀቅ ጸረ ኢጣሊያ አቋም ይዘን መቆም ነበረብን። ነገር ግን እኛ የዋህ ሕዝብ ስለሆንን ጣሊያኖች የበደሉን በይቅር ረስተን እንኖራለን። የኤርትራ ነፃነትን የሚቀበልና የሚታገል ሁሉ ከላይ እንደገለጽኩት ጣሊያኖች በቀየሱት መሠረት የኢጣሊያ ባሪያ ለመሆን እንደተቀበለ ይቆጠራል፤ ጣሊያኖችን እያወደሰ ለመኖርና ለመሞትም እንደተዘጋጀ ይቆጠራል፤ ፈርዲናልዶ ግርቲኒ እንደገለጸውም የኤርትራ ቅኝ ገዢዎች መመሪያ ሆኖ የነበረ አፍሪካውያን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት እምነቱ የተቀበለ መሆኑን ይቆጠራል።

ይህ ሀቅነት እንደሌለው የሚጠራጠሩ ቢኖሩ ኤርትራውያን ግርቲኒን እንደሚወዱ አንድ ኢጣሊያ ደራሲ ስለ ግርቲኒ ሲነሳ ኤርትራውያን እንባቸውን ያፈሳሉ ብሎ እንደገለጸው መመልከት ይበቃል የኢጣሊያንኛ ፎቶ ኮፒውን(1) በቍጥር 1 በሚቀጥለው ገጽ ተመልከት

ከነፃነት በኋላ ጣሊያኖች በቀየሱላቸው አሜን ብለው ተቀብለው የነሱ ቅየሳ ተገዢዎች ሆነው ይገኛሉ። ቅኝ ገዢዎች ጣሊያኖች ከመምጣታቸው በፊት አንድ ትግራይ የነበረች ጣሊያኖች ትግራይና ኤርትራ እያሉ ተለያይተው እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል። ሁለት ክፍላተሀገር ተለያይተው በኢትዮጵያ ክፍላተሀገሮች ውስጥ ተገቢ ቦታ ሊይዙ አይችሉም። በ17ኛው ክፍለ ምእተ ዘመን ፖርቱጋሎች ከኢትዮጵያ ክፍላተሀገሮች ትልቋ ትግራይ-ናት ብለው ነበር። ይሄም ሁኔታ እስከ አጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ድረስ እንደዚሁ ሆኖ ቆይቷል። ይህም የምንልበት ምክንያት ትግራይ በስፋቷ ሳይሆን በቀይ ባሕር ጂኦግራፊ አቀማማጧ ጭምር ነው። በዛሬ ጊዜ ሁለት ክፍለሀገሮች ተነጣጥለው ለማንሰራራት በማይችሉበት ሁኔታ ጣሊያኖች እንደተመኙት ወድቀው ይገኛሉ። ኤርትራ ተገንጥላ ነፃ ሀገር ሆና ትልቅ ሀገር ልትሆን አትችልም። ትግራይ አሁን ባለችበት ለፋትና አቀማመጥ ከኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት በማንኛውም መለኪያ በመጨረሻ ደረጃ ቦታ ይዛ እንድትቀር አያጠራጥርም። ትግራይና ኤርትራን ወደ ውርደት የዳረጋቸው

(1) Orio Vergani: LA Via Nera: Viaggio In Etiopia Da Massaua a Mogadiscio p I4

Questa era Cheren culla degli ascari, valle di milizie africane, terra dei fedelissimi arcù, dove vivono in pensione gli sciumbasci con quarant'anni di servizio e la barbetta di lana grigia, quelli cui spuntano le lagrime quando parlano di Ferdinando Martini e han voluto partire ancora due anni fa quando la vecchia Cheren ha dato ai battaglioni settemila ascari di cui tanti non son più tornati dal Tembien e dal lago Ascianghi. Questa era Cheren meta delle nostalgie che assalgono ogni tanto anche il piccolo cuore bruno dell'ascari, e lo fa canticchiare lungo le piste lontane con una voce da orfano le sue nenie interminabili. Questa era Cheren nascosta dietro gli alberi del pepe, quarantanove anni di vita italiana, Cheren che sta all'Impero come certe piccole città del Piemonte stanno all'unità d'Italia.

A metà strada avevamo assaggiato il frutto del



እጼ ሚኒሊክና ጣሊያኖች በሆነም በተለይ ማርቲኒ በግላዊ አስተዳደሩ ምምር ቂም በቀልም ተዋጉባቸዋል። ዛሬ ኤርትራ ነጻ ሆነች የሚባለው ጊዜያዊ ድል ነው። በግንኙነውም ኢትዮጵያን ልትጠቀም አትችልም። ኤርትራ ተገንጥላም የትግራይ ድርሻ በኢትዮጵያ በጣም አነስተኛ ነው የሚሆነው።

የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝና የኢጣሊያ ዘረኝነት መሠረቶች

151. — VISITE E COLLOQUI

oramai le conquiste coloniali sono un'empia necessità, ma non parlate d'incivilimento. Chi dice che s'ha da incivilire l'Etiopia dice una bugia o una sciocchezza. Bisogna sostituire razza a razza: o questo, o niente: lo affermava il Munzinger trent'anni fa quando la schiettezza era lecita. All'opera nostra l'indigeno è un impiccio; ci toccherà dunque, volenti o nolenti, rincorrerlo, aiutarlo a sparire, come altrove le Pelli Rosse, con tutti i mezzi che la civiltà, odiata da lui per istinto, fornisce: il cannone intermittente e l'acquavite diuturna. È triste a dirsi ma pur troppo è così: i colonizzatori sentimentali si facciano coraggio: *fata trahunt*, noi abbiamo cominciato, le generazioni avvenire seguiteranno a spopolare l'Affrica de' suoi abitatori antichi, fino al penultimo. L'ultimo no: l'ultimo lo addestreranno in collegio a lodarci in musica, dell'avere, distruggendo i negri, trovato finalmente il modo di abolire la tratta!



FERDINANDO MARTINI

## 2. ሬናቶ ፓዎሊ ሌላ ኢጣሊያዊ ዘረኛ [1]

የማርቲኒ ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ደጋፊ የነበረው በሀገራቸው በፖለቲካ አስተሳሰብ የማርቲኒ ተቀናቃኝ ነበርኩ የሚለው ሬናቶፖዎሊ የተባለው ኢጣሊያዊ በ1908 ዓ.ም. ኤርትራን ጎብኝቶ በደረሰው መጽሐፍ "በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ዓይነት ነጮችና ጥቁሮች ተለያይተው ይኖራሉ። ጥቁሮች ግን መብታቸው የተከበረ ነው። የላቲኖች ቅኝ አገዛዝ ተብሎ የሚጠራው ጣሊያኖችን ግን የማያጠቃልል የእኩልነትና የመዋሃድ" መሆኑን ከገለጸ በኋላ በበኩሉ ሃሣብ ሲያቀርብ "የሚቻል ቢሆን እንደ ማርቲኒ ፖሊሲ በኤርትራ የሚገኙት ጥቁሮች በሙሉ አጥፍቶ ገድሎ በጣሊያኖች መተካት የተሻለ መፍትሔ ነበር። ነገር ግን ይህ በተግባር ሊውል የማቻል አይደለም"። ሌላ የራሱ አማራጭ መፍትሔ ብሎ ያቀረበው "ነጮችና ጥቁሮች በአፍሪካ አብረው እንዲኖሩ ነጮች በአፍሪካ አየር ንብረት ምክንያት የጉልበት ሥራ ለመስራት ስለማቸግራቸው በሌላ በኩል ደግሞ ጥቁሮች በልጅነታቸው የሰውነትና የአእምሮ ፈጣን እድገት ቢኖራቸውም በ30 ዓመት ዕድሜያቸው የሰውነታቸው የእርጅና ድክመት ብቃት ያጣሉ በአእምሮም ወደ ልጅነታቸው ይመለሳሉ። በዚህ ዓይነት ሁለቱ ዘሮች ተጋግዘው መኖር ይችላሉ" ብሎ ጽፍዋል።

በጣም ታዋቂ የነበረው ኢጣሊያዊ የስነ ጽሑፍ ሰው "ካርዱቺ" Carducci በማርቲኒ ጊዜ ይኖር የነበረ በ1839 ዓ.ም. ተወልዶ በ1907 የሞተ የማርቲኒን መጽሐፍ አንብቦ "ከብዙ ጊዜ ወዲህ እንደዚህ ያለ ግሩም መጽሐፍ አንብቤ አላውቅም" ብሏል። አስተያየቱ የፖወሊ መጽሐፍም ሊመለከት ይችላል። ይህ የሚያሳየው የማርቲኒ ኤርትራ አገዛዝ በእነ ፖወሊ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን መላው የኢጣሊያ ሕዝብ ድጋፍ እንደነበረው ነው።

## 3. ዘረኝነት በአፍሪካ ፀረ ዘረኝነት በኢጣሊያ

ጸረ ዘረኝነት ያለው አቋም ያለ አንድ ሰው መጽሐፍ የደረሰው ኢጣሊያዊ አላጋጠመኝም። እሱም ኤውካርዲዮ ሞሚሊያኖ ይባላል።[2] እሱ በ1946 ዓ.ም. የደረሰው አንድ መጽሐፍ ብቻ ጸረ ዘረኝነት አርእስት ነበረው። በሞሚሊያኖ አስተሳሰብ ዘረኝነት በኢጣሊያ ሀገር የተፈጸመው በፋሺዝም ጊዜ ብቻ መሆኑን ለማስረዳት የታቀደ ነበር። በ1946 ዓ.ም. ኢጣሊያ ከፋሺዝም አገዛዝ ኃላት ዲሞክራሲ ጉዳና መራመድ የጀመረችበት ወቅት ነበር። ያለፈውም የኢጣሊያኖች መጥፎ ጊዜ ዘረኝነት ታሪክ በሰፊው ለኢጣሊያ ሕዝብ ለማስረዳት ከደራሲው የሚጠበቅ ተግባር ነበር። ደራሲው ግን መጽሐፉን ሊጽፍ ያነሳሳው ምክንያት የመላው የኢጣሊያ ሕዝብ ስሜት በመከተልና በመወከል ጣሊያኖች ዘረኞች አይደሉም፣ ጥሩ ቅኝ ገዢዎች ናቸው። የጀርመኖች የጦር ጓዶች በመሆናቸው ግን በእስራኤላውያን ላይ አነስተኛ በደል ፈጽመዋል ብሎ ለማስረዳት ብቻ ነበር። ይሁዶች ዘረኞች የሚሏቸው እነሱን የሚጠሉ ብቻ ነው። በጥቁሮች ላይ የሚፈጸመው ዘረኝነት ግን እንደሚቀበሉት ያሳያል። ጀርመኖች ያለፈውን ጥፋታቸውን አምነው በየአጋጣሚው ሐዘናቸውን ለእስራኤላውያን እየገለጹ ናቸው። የኢጣሊያኖች ግን የሚያሳዝነው ከጀርመኖች በባሰ ሁኔታ በተለይ ፀረ ጥቁር ሕዝብ ዘረኝነት

(1) Renato Paoli : Nella Colonia Eritrea

(2) Eucardio Momigliano : Storia Tragica e grotteesca del razzismo fascista



የተከሰተባት ሀገር በመሆኗ ብቻ አይደለም፣ በይበልጥ የሚያሳዝነው እና የሚገርመው፣ በኢጣሊያ ሀገር ፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ አለመታየቱ ነው። እነ ማርቲኒ የአፍሪካ ጥቁር ሕዝቦች ከአፍሪካ መሬት እናጠፋቸዋለን በሚሉበት ጊዜ ጉዳት ማድረስ የሚችሉት ለእኛ ለቅኝ ተገዢዎቻቸው የነበርን ብቻ የተወሰነ ነበር። እውነት የአፍሪካ ሕዝብን መፍጀት ከተፈለገ አብዛኛውን አፍሪካ ይቆጣጠሩ የነበሩ ሁለቱ ሀገሮች ቅኝ ገዢዎች ማለት ከእንግሊዝና ፈረንሳይ መስማማት ነበረባቸው። መንግሥቶቻቸውም ፋሽስቶችና ዘረኞች መሆን ነበረባቸው፤ ይህ ግን ጨርሶ የማይታሰብ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሁለቱ ሀገሮች ከጥንት ጀምሮ በማይናጋ ዲሞክራሲ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ነው።

ስለዚህ ነው የኢጣሊያ ዘረኝነት እኛን ከመጉዳት በቀር ምንም ውጤት ሳያመጣ ከንቱ ድንፋታ ሆኖ የቀረው። ሞሚሊያኖ በኢጣሊያና በዓለም አቀፍ በጣም የታወቀ ሰው ነበረ። የደረሰው መጽሐፍ አፍሪካን በሚመለከት ግን የማርቲኒ ፖሊሲ የሚያጠነክር ሲሆን እስራኤላውያን በሚመለከት ብቻ ጣሊያኖች ከጀርመኖች ጎን በመሰለፋቸው ትንሽ ስህተት ሰርተዋል ለማለት የታቀደ ነበረ። ስለዚህ ሞሚሊያኖ በከፊል ዘረኝነቱ በከፊል ጸረ ዘረኝነት አስተሳሰብ ያለው ሰው ነው ለማለት ይቻላል። ሞሚሊያኖ ዜግነቱ ኢጣሊያዊ ቢሆንም ዘሩ ግን ይሁዳዊ ነው። ከቅድመ አያቶቹ ጀምሮ ለሁለት ሺህ ዓመት ኢጣሊያ ሀገር ነዋሪ ስለሆኑ ከአብዛኛዎቹ ጣሊያኖች በኢጣሊያንነቱ ቅድሚያ አለኝ የሚል ነው። የመጽሐፉ ፍሬ ነገሩም ጣሊያኖች ጥሩ ሕዝብ ናቸው ዘረኞች አይደሉም። ዘረኞች ጀርመኖች ብቻ ናቸው። ሙሶሊኒ ራሱ ፋሽዝም ቢሆን ዘረኛ አይደለም። ጣሊያኖች በጀርመኖች ተገደው ነው ዘረኞች የሆኑት ወዘተ። ደራሲው ዘረኝነት ብሎ የሚጠራው ጸረ እስራኤላውያን ዘረኝነት ብቻ ነው። ጸረ ሌሎች ዘሮች ግን ትክክለኛ ስለሆነ ዘረኝነት አይባልም ብሎ ያምናል። በአጭሩ ሞሚሊያኖ የኢጣሊያኖች እስራኤላውያን መብት ተከራካሪ ነው ለማለት ይቻላል። እኛ ኢጣሊያኖች የቅኝ ግዛታችንን ልናስፋፋ መብታችን ነው ይላል በኢትዮጵያ ያካሔድነው ጦርነት ተገቢና አስገራሚ ነው በማለት አድናቆቱን ይገልጻል። ቀጥሎም እኛ ኢጣሊያዊ ይሁዶች ለአብሲኒያና ለሶማሊያ ኔግሮች እንዲሁም ለሊቢያ ዐረቦች የተሰጠ መብት እንዴት እንከለከላለን፣ ዐረቦች በዩኒቨርሲቲ ገብተው ሲማሩ በሌላ ቦታም ሥራ ሲሰጣቸው እኛ ብቻ እንዴት እንከለከላለን ብለዋል። ሞሚሊያኖ ዐረቦች በኢጣሊያ ዩኒቨርስቲ ገብተው ሲማሩ አየቶ ይሆናል፣ ሊቢያውያን ግን አይደሉም። ጣሊያኖች ለሊቢያውያን ያደረጉላቸው ከእኛ ሻል ያለ አያያዝ ከግምት የሚገባ አይደለም። ትምህርት አልተከፈተላቸውም። ሌሎችም ለማኅበራዊ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አልተሰሩላቸውም። እንደደንቡ ከሆነ ኤርትራውያን Fedelissimi በጣም ታማኝ ይባሉ የነበሩ ኤርትራም Colonia Primogenita በኩር ቅኝ ግዛታችን ተብላ ትጠራ ነበረ። ነገር ግን እነ ማርቲኒ ካዘጋጁላቸው ከሞት መትረፍ የቻሉት ጉረቤታቸው ኢትዮጵያ ነጻ ሀገር ስለነበረች መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢትዮጵያ ጠንካራ ነጻ ሀገር ብትሆን ደግሞ የደረሰባቸው ጥቃት አይደርስባቸውም ነበር። በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ሥር ወድቀው ሲማቅቁ የነበሩ ሀገሮች በሙሉ የጋራ ዕድል ይጠብቃቸው ነበር፤ ይኸውም በማርቲኒ ፕላን መሠረት ሊገደሉ የተዘጋጁ ሕዝብ ነበሩ። ጣሊያኖች እርስ በእርሳቸው የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብ ይከተላሉ ስለሀገራችን ያላቸው አመለካከት ግን አንድ ነው። ፋሽዝም እኛን ነው የበደለው እናንተን አልበደለም ከኢጣሊያ ወስዶ ገንዘባችንን በከንቱ በእናንተ ሀገር ነው ያባከነው ለእናንተ ግን ጠቀማችሁ እንጂ አልጐዳችሁም፣ አሰለጠናችሁ፣ መንገድ ሰራላችሁ፣ ልብስ

መልበስ ተማራችሁ፣ በማንኪያ መብላት አስተማራችሁ፣ ትምህርት ቤት ከፍቶ አስለመናችሁ ወዘተ ይላሉ። የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ወተሳ የሚያስገ ኢጣሊያዊ የለም። ጣሊያኖች የሰሯቸው መንገዶችና ሕንጻዎች ለራሳቸው ጥቅም የተሰሩ ስለሆኑ አይመለከተንም። በትምህርት ስልጣኔ ግን የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ከሌሎች የሚለዩበትም ወለያ ምልክት ጠባብ እንደነበረ የሚያስረዳ ሐቅ ነው። በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ፍጻሜ በቅኝ ግዛቶቻቸው ሁለት ችግሮች ብቻ ብለው ተከትተው ነበር 1/ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር 2/ የቋንቋ ምርጫ ችግር። ለሊብያውያን የዳበረ የዐረብኛ ቋንቋ ስላላቸው ወደ ነፃነት ሲመጣጋገር ችግር አላጋጠማቸውም። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ በሰሜን አፍሪካ ማግሬብ ሀገሮች ከዐረብኛ ጎን በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሙበት የተደረገው ቅኝ ገዢው ቋንቋ የማይጠቀሙ ሊቢያውያን ብቸኛና ልዩ ያደርጋቸዋል። ሶማሊያውያንን ችግሩ የባሰ ነበረ በጣሊያንኛ ቋንቋ የአስተዳደር መዋቅር ስላልነበረ ትግርኛ የዳበረ ቋንቋ ስላልነበረ እንግሊዞች በቋንቋቸው ማስተዳደር ጀመሩ። ኢትዮጵያ አማርኛና እንግሊዝኛ ስለምትጠቀም ብዙ ችግር የተፈጠረ አልነበረም በሶማሊያም የባሰ ይሆናል እንጂ የተሻለ ሁኔታ አልነበረም። እዚህ በምሥራቅ አፍሪካ ብሊቢያ የተደረገው ቅኝ ገዢዎቻችን የጣሊያኖች ቋንቋ የማናውቅ የማንጠቀም እኛ ብቻ ነን። በተገኘ ጅቡቲ ሳይቀር ፈረንሳይኛ መንግሥታዊ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል። የኢጣሊያንኛ ቋንቋ በኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች እንዳይስፋፋ መሠረት ድንጋይ የጣለ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ነው። ዳንቴ አሊጊየሪ የተባለው ድርጅት የኢጣሊያንኛ ቋንቋን ለማስፋፋት የተቋቋመው በ1898 ቅርንጫፍ ለመክፈት ወደ ኤርትራ መጥቶ ነበር። ማርቲኒ ለነገሮች ትምህርት አያስፈልግም ብሎ ስላሳመናቸው በመጡበት እንዲመለሱ አደረጋቸው።

ጣሊያኖች የሚኩራሩባቸው ሮማውያን የሰሰት አረኞች የነበሩ ትልቅል ዘሮች ነበሩ። ተቲት ሰዎች ስለነበሩ በባሁሮችን ተውጠው ዘራቸው ጠፍቷል። ከበዙ ጥግዎች ሮማውያንን የወለዱት ዋነኛው ኢቱረስካውያን ነጭ ዘር አልነበሩም።

## 4. ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የመጨረሻ ወረራዋ ያደረገችው ዝግጅት ያዘጋጀና ያቀነባበረ

ሌላ የኤርትራ ሀገረ ገዢ እንደ ማርቲኒ ኢትዮጵያ ለመገንጠልና ለማውደም የሰለላ ድርጅት ሲያካሂድ የነበረው ኮራዶ ዞሊ ይባላል።[1] የኢሉ ተልእኮ ግን በግድየ ሽንፈት ለአዲሱ ጦርነት ቲም በቀል ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ሰለሆን ትግራይ ብቻ አይሸፍንም ነበር መላው የኢትዮጵያ የሚሸፍን ነበር። በ1928 ዓ.ም. ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ በከፈቱት ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ የመከላከያ አቋም ወድቆ ጣሊያኖች በድል አድራጊነት ሳይዋጉ እየዘፈኑ እንዲገቡ ነበር በጣሊያኖች የታቀደው። የኢጣሊያ ለጦርነት ዝግጅት የተካሄደው የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር እንደዳሬው በሁሉም አቅጣጫ ነበር። 1.በገንዘብ ጉቦ መኳንንት 2. በቆንስላዎች 3. በሕክምና ዕርዳታ ሽፋን 4. ለቤተ ክህነት የሐሰት ዕርዳታ በመስጠት ሽፋን 5. ከሀገረ ገዢዎች ጋር ግንኙነት በማድረግና በመደለል 6. በጣሊያኖች ሚሲዮናውያን አማካይነት ነበር። የቆንስላዎች በሚመለከት በጎንደር ብቻ ለ70 ቤተክርስቲያኖች የገንዘብ ዕርዳታ አድርገዋል። የሀገረ ገዢዎች የመሾምና የመሻር ጣሊያኖች ጣልቃ

[1] Corrado Zoli : Cronache Etiopiche



ለመግባት ይፈልጉ ነበር። የሕክምና እርዳታ የሚባለውን ለፖለቲካ ስብከት እንደሆነ ግልጽ ነው። ወይም ደግሞ በሰበቡ ሕዝቡን በመርዝ መፍጀት ካልሆነ በስተቀር አንድ የቅኝ ገዢ ዘረኛ ጠላት መንግሥት አንድ ሀገርን ለመውረር በቂም በቀል የሚዘጋጅበት ሰብአዊ ዕርዳታ ያደርጋል ለማለት የማያስችለው ነው። የትግራይ ሀገረ ገዢዎች በሙሉ ጣሊያኖች እርስ በእርሳቸው እያጣሉ በእጃቸው አስገብተዋቸው ነበር። ከመኳንንቶቹ ውስጥ 1/ ራስ ጉግሳ አርአያ 2/ ራስ ሰዩም መንገሻ 3/ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳ 4/ ደጃዝማች ከበደ አረጋዊ ነበሩ። ከነሱ ውስጥም የማይታመኑበት የነበሩ ራስ ሥዩም ብቻ ነበር ብሏል። ጣሊያኖች ያደረጉት ዝግጅት ብዙ ነበር። እንዳደረጉት ዝግጅት ግን ጥሩ ውጤት አላገኙም። በጦርነቱ ጊዜ የኢትዮጵያ ጦር በሚገባ ተቋቋመዋቸዋል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ በአምስቱ የአርበኝነት ዘመናት የደፈጣ ተዋጊዎች አርበኞች እርስ በእርሳቸው በመዋጋት ጣሊያኖች እንዳቀዱት አልተከሰተም። እርግጥ ማዕከላዊ አመራር ይጉድላቸው ነበር። ዓላማቸው ጣሊያኖችን በመውጋት የተመሰረተ አንድ ዓይነት ስለሆነ ውጤቱ እንዲሰምር እንቅፋት አልተፈጠረም። የደቡብ ክፍላተ ሀገር ሕዝቦችም በሰሜኖች ላይ ይነሳሉ የሚል የኢጣሊያኖች ምኞት አልተሳካላቸውም። በአንጻሩ አርበኞች የፈነደቁበት ለመሆን በቅቷል። ከብዙ ምእተ ዓመታት ለኢትዮጵያ የተደረገው አሁንም የሚደረገው እርስ በእርስ ጦርነት የክፍላተ ሀገራት ወይም የእምነት ልዩነት ወይንም የሥልጣን ሽኩቻ እንጂ የጎሳ ጦርነት ተካሂዶ እንደማያውቅ በፍጹምነቱ ለወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ጸንቶ ለመኖር ያለው ብሩህ ተስፋ የሚያመለክተን ነው።

## 5. ታላቋ ኤርትራና ሶማሊያ ግማሽ የኢትዮጵያ የመሬት ስፋት የሚያጠቃልል በኢጣሊያ መንግሥት ተቋቋመ

በመላው ኢትዮጵያ የኢጣሊያ አስተዳደር መዋቅር ተመስርቶ በነበረ ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከ1928 ዓ.ም. በኋላ በአምስት ዓመታት ኢትዮጵያን ለመገንጠልና የማውደም ሂደት በመቀጠል ትግራይ በኤርትራ ተውጣ በራሳቸው አምሳል ፈጠርናቸው ብለው የሚተማመኑባቸው በነበሩ በኤርትራውያን መሪነት የኤርትራ አንድ ክፍል ሳትሆን ለትግራይ ትልቁ ውርደት ሆነ። ኤርትራውያን በታማኝነታቸው ለቅኝ ገዢዎች መገሪያ በመሆናቸው ግፈር እንጂ መኩራት አይገባቸውም። ጣሊያኖች ኤርትራውያን በጣም ታማኝ Fedelissimi በመሆናቸው ትልቅ ውለታ እንድንከፍላችሁ እስቦን ትልቋ ኤርትራ ፈጠርንላችሁ ብለው አሰበው ይሆናል። ኤርትራውያንም የበለጠ ታማኝ በመሆን ሊያስመሰግኗቸው እንዲኖሩ ፈልገው ይሆናል። የኤርትራ ወሰን ከሰሜን ከከሰላና የግብጽ ወሰን ሊዘልቅ ይችል እንደነበረ ሁሉ በስተደቡብም ጣሊያኖች እስከፈለጉበት ሊስፋፋ ይችላል። ትግራይ ብቻ ሳይሆን በአዲሱ መዋቅር መሠረት አፋርን በሙሉ ከፊሉ ወሎም በጌን ሸዋ በኤርትራ ግዛት ውስጥ ተጠቃለው ነበር። የኤርትራ ብሔርተኞች ካሉ ይህን የመጨረሻ የኤርትራ ካርታ መቀበል ይኖርባቸዋል። በዚህ ዓይነት ግን የታሪካችን ባለቤት የሆኑ የሀገራቸው ታሪክ ሰሪዎች እነሱ አይደሉም ማለት ነው። ኤርትራ በምትባል ሀገር ተወላጆች ድምጽ ሳይኖራቸው በጣሊያኖች ተወስነው የሚሰጣቸው መሬቶች ብቻ ነበረ። ሀገራችን ብለው መቀበል ያለባቸው የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች የቀየሱት መንገድ ሕዝቡ ተከትሎ መሔድ የቅኝ ገዢዎች ዓላማ ነው የሕዝቡ ፍላጎት አይደለም።

## 6. በሥራ ላይ ያልዋለ የታላቅ ኤርትራና ታላቅ ሶማሊያ እቅድ [1]

1/ የመጨረሻ የኢጣሊያ ፕላን የቀረበ በስራ ላይ ያልዋለ በጀኔራል ጋባ የኢጣሊያ ጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም የነበረ የቀረበው ነው፡፡ እሱም የተነሳበት ዓላማ ባመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ አንድነት ማጥፋት መገንጣጠል ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በቀድሞዎቹ ታማኝ ቅኝ ግዛቶቻቸው ማለት ኤርትራና ሶማሊያ ሥር ጽኑ አንድነት መገንባት ነበር፡፡ ጣሊያኖች ሁለቱ ቅኝ ግዛቶቻቸው ኤርትራና ሶማሊያ መሬት ለመሬት እንዲገናኙ የብዙ ዓመታት ህልማቸው ነበር፡፡ አሁን በጀኔራል ጋባ ፕላን በተግባር እንዲውል ታስቦ ለጊዜው በተግባር ሳይውል ቀርቷል፡፡ በዚህ ፕላን መሠረት ትግራይ ወሎ ጐንደር፣ ከሰሜን ሸዋና ሰሜን ሐረርጌ ቆርሰው ከኤርትራ ጋራ ተጠቃለው ኤርትራ እንዲባሉ የዚሁ ፕላን ዓላማ ታማኝ የኤርትራ ቅኝ ግዛታቸው ከህነኛው ባሕር ጣና እወሳኝ ሆና አባይን መቈጣጠር መብት እንዲሰጣት ነበረ፡፡

2/ ሐረርጌን ኦጋዴን ባሌ ሲደሞ፣ ከሶማሊ ጋር ተቀላቅለው ሶማሊያ ተብለው እንዲጠሩ

3/ ምዕራባዊ ክፍላተ ሀገር ወለጋ ከፋ ኢሉባቦር ጋሞጐፋ በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ፕሮተክቶሬት

4/ ጎጃም በንጉሥ ተክለሃይማኖት ወራሾች መሪነት በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ፕሮተክቶሬት፡፡

5/ የሸዋ መንግሥት በአጼ ኃይለሥላሴ ዘሮች መሪነት በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ፕሮቴክቶሬት፡፡ በኤርትራና በሶማሊያ የተጠቃለሉ ክፍላተ ሀገሮች ማንነታቸውን ጠፍቶ እንደ ኤርትራና ሶማሊያ ለጣሊያኖች በጣም ታማኝ ሆነው እንዲታነጹ በእነሱ አምሳል Fedelissimi ሆነው እንዲወጡ መላዋን ምሥራቅ አፍሪካ ምግሊያቸው እንዲከተል የተደረገው ድልድል ነበረ፡፡ ምዕራባውያን ክፍላተ ሀገሮች (ኦሮሞ) በአማራ ላይ አመጽ ያካሄዱ ለኢጣሊያ መንግሥት ደጋፊ ይሆናሉ በሚል እምነት ነበር ለብቻቸው የደለደሏቸው ሆኖም ጣሊያኖች የተመኙት አልተከሰተም፡፡ ሸዋ አነስተኛ ክፍል አንድ ወይም ሁለት አውራጃዎች ለብቻው የተመደበው ኃይለሥላሴ እንደ አሻንጉሊት ሊጫወቱባት አስበው ነው፡፡ ጣሊያኖች ትግራይን እንዳጠፉ ሁሉ ሸዋም ዋና ተቀናቃኛቸው ለማጥቃትና ለማጥፋት የተደረገው አመዳደብ ነው፡፡ የጎጃም ለብቻው መመደብ ደግሞ ልዩ ታሪክ አለው፡፡ ሸዋ ጣቢያቸው አድርገው የነበሩ የኢጣሊያ የጂኦግራፊ ማኅበር አባላት ሁለቱ ቸኪና ኪያሬኒ የተሰጣቸው ተልእኮ ለመፈጸም ወደ ጅማ ሔደው ነበረ፡፡ ከዚያ ወደ ሕንድ ውቅያኖስ በማምራት ሀገሩን የኢኳቶሪያል ሐይቆች ለማጥናት ነበር ዓላማቸው፡፡ ጅማ አጠገብ ጌራ እንደደረሱ ግን ባልታወቀ ምክንያት በጌራ ንግሥት እጅ እስረኛ ሆኖ ይቆያሉ፡፡ ኪያሬኒ የተባለው ባልታወቀ ምክንያት ታሞ ይሞታል፡፡ ቸኪ ታስሮ ስለነበረ እንዲያስፈቱት ለንጉሥ ሚኒልክና ለአጼ ዮሐንስ አቤቱታ ያሰማል፡፡ አጼ ዮሐንስ የጎጃም ሀገረ ገዢ ለነበረው ለራስ አዳል መልእክተኛ ልከ ቼኪን እንዲፈታ ያደርጋል፣ ቼኪ ተፈቶ ወደ ጎጃም ሔዶ ምስጋና በሚያቀርብበት ጊዜ ራስ አዳል ከሚኒልክ በመወዳደር ወሊጋ ኢልባቦር ጅማ በቁጥጥሩ ለማድረግ ዓላማ ስለነበረው ቼኪ ደግሞ መሐንዲስ

[1] Lessona : Verso l' Impero



ነው ስለተባለ ከጎጃም ወደ ወለጋ የሚያሸጋግር በአባይ ወንዝ ድልድይ እንዲሰራለት ይጠይቃል፡፡ እሱም ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ከመንግሥቱ አስፈቅዶ እንዲሰራለት ቃል ይገባለታል፡፡ ብዙ ጣሊያኖች በድልድዩ ሰበብ ጎጃምን ጐብኝተው ይመለሳሉ፡፡ ድልድዩ ግን አልተሰራም፡፡ ጣሊያኖች የራስ አዳል ውለታ ምክንያት በማድረግ ለራሳቸው የፖሊቲካ መጠቀሚያ ሲያደርጉት ይታዩ ነበር፡፡ ወደ ኤርትራ ይሔዱ የነበሩ የጎጃም ተወላጆች ሰዎች ከወዳጅ ክፍለ ሀገር እንደመጡ አድርገው ይቀበሏቸው ነበር፡፡ አሽከርቹም ይመለምሏቸው ነበረ፡፡ ጣሊያኖች በጎጃም የሰለላ መረባቸውን ሲመዘርጋት ሰበብ ፈጥሮላቸው ነበር፡፡ አቅዳቸው ስህተት እንደሆነና እንደከሸፈባቸው የተረዱት በአምስቱ የኢጣሊያን ወረራ ዘመን ነበር፡፡ የጎጃም ሕዝብ በሙሉ ከጣሊያኖች ጐን ተሰልፎ የጣሊያኖች ግዛት ደጋፊ በመሆን ፋንታ በዐረበኝነት ተደራጅቶ ጣሊያኖችን በመዋጋቱ ነበረ የታወቀው፡፡ በሸዋ አንድ አሻንጉሊት መንግሥት የማቋቋም ሃሣብ የከሸፈው ንጉሡ በኢጣሊያ እጅ ባለመውደቁ ነው፡፡ የኢጣሊያ ዓላማ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር በሙሉ ማንነታቸው ጠፍቶ በአዲስ መዋቅር በኤርትራና በሶማሊያ ታማኝ የድሮ ቅኝ ግዛቶቻቸው ሥር በአዲስ መንፈስ እንደ እነሱ ለኢጣሊያን ታማኝ ሆነው እንዲዋሃዱ ነበር፡፡ ጣሊያኖች ከሀገራችን እንወጣለን ብለው ሃሣብ አልነበራቸውም ለዘላለም የራሳቸው የሆነች መስሏቸው ነበር፡፡ በተለይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመን ጋር ሆነው በአሸናፊነት ወጥተው ቢሆን ኖሮ ጀርመን ሱዳንንና ኬንያን ከእንግሊዝ አስለቅቃ በመውሰድ የራሷ ስታደርጋቸው ለኢጣሊያ ሕዝቡን ፈጅታ የራሷ ሕዝብ በሀገራችን ለማስፈር ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላት ነበር፡፡ ነገር ግን የሕዝቦችን ነጻነት ጠባቂ አሳፋሪ ዘበኛ ተብለው የሚጠሩ ሀገሮች በተለይ በግንባር ቀደም እንግሊዝ በናዚ ፋሽስቶች አልተበረከኩም በእነሱ ብርታት እኛ ነጻ ሕዝብ ሆነን በዚሁ ዓለም ለመኖር በቅተናል፡፡

## 7. ጣሊያኖች ብቸኛ ታሪካዊ ጠላቶቻችን

በወደቀው የደርግ መንግሥት በኤርትራ ስለነበረው ጦርነት ጉዳይ በሚነሳበት ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር የነበረ ዓረቦችን በማመልከት ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው የሚል ነበር፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ዐረቦች ታሪካዊ ጠላቶቻችን አይደሉም፡፡ የዐረብ ግዛት መስፋፋት እና ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረ ዘመን አቅጣጫቸው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሰሜን አፍሪካ ኤውሮጳ ነበር እንጂ ኢትዮጵያ በዐረብ በቀጥታ ተወራ አታውቅም፡፡ ባለፈው ክፍለ ዘመን ግብጽ ኢትዮጵያን ለመውረር ሙከራ ባደረገችበት ዘመን ራሷ ግብጽ ደካማ ሀገር በመሆንዋ ስፊ ወረራ ለማደረግ አቅም አልነበራትም፡፡ ሌሎች ከቀይ ባህር በስተምሥራቅ የሚገኙ ጐረቤቶቻችን የዐረብ ሀገሮች ግን ራሳቸው በእንግሊዝ ቅኝ ገዢነት ሲማቀቁ ስለነበሩ ሀገራችንን ለመውረር አቅም ስላልነበራቸው ጠላቶቻችን ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ዐረቦች ጣላቶቻችን ሊሆኑ የሚችሉ በሰላማዊ መንገድ የእስልምና ሃይማኖት በማስፋፋት ነው፡፡ ዐረቦች በሃይማኖት ብቻ አይወሰኑም የዓረብኛ ቋንቋ ያስፋፋሉ ከሀገሩ ሕዝብ በጋብቻ ይተሳሰራሉ፡፡ የሀገሩ ሕዝበ የራሉ ቋንቋ ረስቶ በዓረብኛ ቋንቋ እንዲጠቀም ያደርጉታል፡፡ በመጨረሻ ሕዝቡ ዘሩን ረስቶ ዓረብ ነኝ እንዲል ያደርጉታል፡፡ ባጭሩ ከፍተኛ የመሣብ ችሎታ አላቸው፡፡ ጐረቤታችን የሆኑ ሀገሮች እንደሱዳን ጅቡቲ ሶማሊያ፣ ዓረብ ሳይሆኑ ዓረብ ነን ሲሉ ይታያሉ፡፡ በሀገራችን ግን እንዲህ ያለ ሁኔታ እስካሁን አልተከሰተም፣ ስለዚህ ዓላማችንን ረስተን ዓረቦችን ታሪካዊ ጠላቶቻችን ማድረግ ተገቢ አይደለም፡፡ ዓረቦች ታሪካዊ ወዳጆቻችንና ጐረቤቶቻችን ብንላቸው ትክክለኛ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ

ለመሐመድ ተከታዮች እና ዘመዶች አስተናግዳለች። ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ የእስልምና እምነት እንድትከተል ለኢትዮጵያ ንጉሥ በጻፈው ደብዳቤ ንጉሡ የሰጠው መልስ አክብሮት የተመላበት ነበር። አንተ ስለ ክርስቶስ የነገርከኝ የእኛም እምነት ነው የሚል ነበረ። ቀጥሎም ስለእዳሉ የእስልምና ሃይማኖት መሐመድ ይሁዶችንና እምነት የሌላቸውን ይዋጋል። አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ያምናል ኢየሱስንና ማርያምን ያከብራል። ስለዚህ እንደ እኛ ኦርቶዶክስ ነው ብሏል። ሌሎች ሀገሮች ግን ለኢትዮጵያ ንጉሥ የተጻፈው ደብዳቤ ዓይነት ስለደረሳቸው እና ነብዩ መሐመድ ጥሪ ስለተቀበሉ ማንነታቸውን ጠፍቶ ዛሬ ዐረብ ተብለው ይጠራሉ። ለምሳሌ የግብጽ ጥንታዊ ታሪክ ሰሪዎች ምን ይመስሉ እንደነበረ እናውቅም። እንደዚሁም የካርታጅ ሰዎች ሀገራቸው በሮማውያን ተወር ተሸንፈው ከተማቸው ፈርሶ ከታረሰ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በዐረብ ወረራ ስለተዋጡና ስለጠፉ ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ ለማወቅ ያዳግታል። እኛ ኢትዮጵያውያን ግን በዐረብ ስላልተወረርን ዘራችንና ማንነታችን ጠብቀን እስካሁን እንኖራለን። የዐረብ ሀገሮች አንዳንዶቹ እንደ ሊቢያ ያሉት እንደ እኛ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ተሰቃይተዋል። ስለዚህ የጋራ ጠላታችን አንድ ብቻ ነው ይኸውም ኢጣሊያ ቅኝ ገዢ ናት። እኛ በኢትዮጵያ አማረኛ የመንግሥት ቋንቋ በመሆኑ የአማረኛ ተናጋሪ ሕዝብ ጠላት ነው ብለን ብንነሳ ለኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ እና ለኢጣሊያ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ተገዢነታችን እና በአስተሳሰባቸው መማረካችን ብቻ ነው የሚያስገነዝበን አማራ ማለት ኢትዮጵያዊ ማለት ነው እኛም አማራ ነን ሌላ ኢትዮጵያውያን የተለዩ ሕዝብ አይደለም። በኤርትራ የተቋቋመው መንግሥት በአገሩ እንዲቆም የዐረብ ቱጃሮች በገንዘብ ካልረዱት ራሱ ሊስተዳደር የሚችል አቅም የለውም። ዓረቦች መጠነኛ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ። ዋና አሸናፊ ግን የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ናቸው። ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጣሊያኖች እንጂ ዐረቦች አይደሉም።

## 8. ማርቲኒ የኢጣሊያን ዘረኝነትና ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር መሥራች 1898

ኢጣሊያኖች በአፍሪካ የነበሩዋቸው ቅኝ ግዛቶች ያስተዳድሩባቸው የነበረው በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው በዘረኝነት አገዛዝ ነበረ። በኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ዘረኝነትን የመሠረተው የኤርትራ ሀገረ ገዥ የነበረው ፈርዲናንዶ ማርቲኒ ነው። የኤርትራ ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሹሞ ምፅዋ በመርከብ ከገባበት ጃንዋሪ 14 ቀን 1898 ዓ.ም. በሁለት ሳምንቱ ጃንዋሪ 28 ምፅዋ የሚገኘው አንድ ትምህርት ቤት ለጉብኝት ሄደዋል። በዚሁ ጊዜ ጉብኝት ወደ[1] ትምህርት ቤቶች አይወሩም! እነዚህ የቅድስት ሐና መነኩሲዎች መሐይሞች ናቸው። ይህ የእነሱ ገዳም ሌላ አይደለም ሊሆንም አይችልም የአንድ አመቤቶች ክምችት ነው። ራሱ በትምህርት ቤት ውስጥ የነጮችና የጥቁሮች መቀላቀል በእኔ በኩል የማይሆን ነው። ጥቁሮች ከእኛ የበለጠ ከፍት ሊንገል ስላላቸው የማንኛውም የቅኝ ግዛት አስተዳደር መሠረት የሆነው የነጮች የበላይነት አልተከበረም። ከሁሉ በላይ ደግሞ የመጻሕፍቶች ጉዳይ ማሰብ ያስፈልጋል። የተለዩ መጻሕፍቶች ያስፈልጋሉ እሁንም በተቅም ላይ ያሉት እነዛ በ1891 ዓ.ም. Nell' Africa Italiana የሚለው መጽሐፍ የመሳሰሉት ናቸው።

(1) F Martini Diario Eritreo V I p 38



ልዩ መጽሐፍቶች ያስፈልጋሉ ስንል ነገር ግን ለማን ተብለው ይዘጋጃሉ? ብሎ ፅፏል። የማርቲኒ አባባል ግልፅ ነው በ1891 የደረሰው መጽሐፍ እኔም በዚህ ጽሑፍ ደጋግሜ ጠቅሼያለሁ በተለይ በኤርትራ ሕዝብ የነበረው አስተያየት ሕዝቡን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ነበር። እሁንም ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሹሞ ሲመጣ ከዚህ በፊት በደረሰው መጽሐፍ መሠረት ሃሳብ ለማስተዳደር እንደመጣ ሳያወላውል ገልጿል።

አፕሪል 18 ቀን 1898 ዓ.ም. ከሳንሚኒያተሊ[1] የተረበው ሪፖርት ይመረምራል ትምህርት ቤቶችን በሚመለከት ሳንሚኒያተሊ ለትምህርት ቤቶች የሚሆን ሕንፃ እንዲሰራ ጠይቋል ትምህርት ቤት ስፖርት እና የሙዚቃ ትምህርትም የሚያጠቃልል ነው። እንዲጂኒ ተማሪዎች በመንግሥት ኪሳራ ቤት! ልብሶችና ምግብ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ይህ ግሰብ የእውራኝ ሀገረ ገዥ ነበር። የእሱ ሐሰተኛ አስተሳሰቦች በአለቆች ድክመትና ቸልተኝነት በከረል ስራ ላይ ውለው ለመንግሥት በብዙ ሺህ ሊሬ የሚቆጠር ኪሳራ አስከትለዋል።[2] ሜይ 21 ቀን 1898 ዓ.ም. ለጉብኝት ከረን ነበረ። በቅድስት ሐና የሚጠሩ የሴት መነኩሲያን በ1895 ዓ.ም. ፀረ ኢጣሊያ ናቸው! ትምህርት ለኢንዲጂኖች ያስተምራሉ ተብለው ከኤርትራ የተባረሩት የፈረንሳይ ሴት መነኩሲያን ተከተው የሚሲዮን ስራቸውን ለማከናወን ወደ ኤርትራ የገቡ ናቸው። ማርቲኒ በምፅዋ ትምህርት ቤታቸው እንደነበረ ሁሉ በከረንም ለጉብኝት ይሄዳል። የቅድስት ሐና ትምህርት ቤቶች እንዝበኛለሁ ከምፅዋ የተሻሉ ናቸው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ለሐበሾች ፕሮፌሽን ማለት በቃል ፍርድ መስጠት ማለት ነው ጎደሉ ዐርፍተ ነገሮች /ሲላብ/ ነጠላና ተደራራቢ ሊሆኑ ይችላሉ። ከአንድ ፕሮፌሰር በር. ጎኛ የተባለው የተደረሰ መጽሐፍ ስለ ጠቃሚ ጥያዎች ተማሪዎች እንዲያነቡ ይደረጋል የጥኛች ሥራ ነው። ጠቃሚ ከሚባሉ ጥያዎች እንዱ የሜማ ሥራ ሙያ ነው። የተከበራችሁ እማሆይ እንዴት እድርጋችሁ ነው ለአበሾች የምታስረዱ ሜማ ማድረግ የማያውቁ? ከእነሱ አንዱ በጣም እዋቂና በትምህርትና የበሰለ እንደተናገረው "ሜማዎች እገሮቹን ያበላሻሉ" ብሏል።

ማርም እንዲጂና የኤርትራን መንግሥት ሳያስፈቅድ ወደ ኢጣሊያ መሄድ እንዳይችል የሚከለክል እዋጅ አለ። በቅድሞ ገኛው ካፈል በፍቃድ ወደ ሀገሩ በሚሔድበት ጊዜ የቤት ሰራተኛው እንዲጂና ይዞ እንዲሄድ ጠይቆኝ! ኢይቻልም ብዬ መለስኩለት! ምክንያቱም እንደኛው ሰራተኛው መጥፎ ሰው ነው! ሁለተኛም በብዙ ምክንያት እንዲጂኒ ወደ ኢጣሊያ እንድሄዱ ጥሩ አይደለም። የእኔ መልስ ለካፈል ደስ እላለውም ምንም መልስ ባይናገርም ሰራተኛውን ምፅዋን ትቶ ሄደ። እንዲሁም የመቶ አለቃ ማራዛኒ ምንም ሳይናገር ምንም እንኳን ከእለቃው ያስፈቀደ ቢሆንም አንድ አስካሪ ለፍቃድ ከእሱ ጋራ ይዞ ሄዶ ነበር። ከመቼ ጀምሮ ነው አስካሪ ለፍቃድ ወደ ኢጣሊያ የሚላኩ። ከመቼ ወዲህ ነው የጦር እዛዥ የሀገረ ገዥው ትዕዛዝ ማወቅ የማይፈልግ ወይንም የሚረሳው ወይም ማፍረስ የሚጠይቅ? በፖርት ሰይድ ላለው ቆንሲል አስካሪ እንዲመልሰው ስልክ አደረኩ። አሁን እንደሚገሩ ተሰፋ አለኝ በማለት ጽፈዋል።

ዛሬ እንኳን አንድ ግለሰብ ለፍቃድ በሺህ የሚቆጠሩ እንዲጂኖች ኢጣሊያ ይኖራሉ እንደ ማርቲኒ የመሰሉ ጣሊያኖች እንጀታቸው ይረር።

በጠበቃው ካኛሲ የሚመራው "የዳንቴ አሊጊሪ Dante Alighieri" ቅርንጫፍ ማኅበር ብዙ ነገሮች አስፈላጊ ያልሆኑ እደገኛ የሆኑ ነገሮች

(1) F Martini Diario Eritreo V I p 128
(2) F Marini Diario Eritreo V II p 164-165

ማድረግ ይፈልጋል፡፡ 1ኛ/ ነጥብ የነጮችና የጥቁሮች ድብልቅ ት/ቤቶች አይቻልም እንደገና አይቻልም፡፡ ኢንዲጂኖ ሕፃን ከነጩ የበለጠ ፍጥነትና ክፍት ሐንጎል አለው፡፡[1]

Un'altra de' militari. Han disfatto a Massaua baracche delle quali non avevano che l'uso e han trasferito il materiale ricavato dalla demolizione ad Asmara: auspice, s' intende il Genio, consenziente il colonnello che ha per il Genio una simpatia insofferibile. Resultato: il materiale è valutato 18.000 lire: la spesa del trasporto è ascesa a 25.600. A raccontarlo, mi direbbero che invento.

La « Dante Alighieri » che ha a capo l'avv. Cagnassi vuol fare una quantità di cose inutili e dannose. Vuole istituire scuole a Massaua ed ad Asmara. Punto primo: scuole miste di bianchi e di neri, no, no e poi no. L'indigeno, fanciullo, troppo più agile e pronta ha l' intelligenza del fanciullo bianco; evitare dunque raffronti. Scuole di bianchi? Ma deve pensarci il Governo e ci pensa. Scuole di neri? Giova lo istituirle? Noi non siamo nelle condizioni degli Inglesi a Cassala. Non possiamo servirci di indigeni alla Posta per esempio, o ai Telegrafo. E' sarà fausto giorno quello in cui potremo non valercene neanche come interpreti. E allora? A ciangottare un po' d' italiano impareranno da sè. Per ultimo la Dante Alighieri vuole avvisare ai mezzi di estendere l'italianità nell'Eritrea... e nelle regioni vicine. Ah! questo poi!...



IL COMMENDATORE FERDINANDO MARTINI.

[1] F Martini ibd V II p 472



ስለዚህ ግመናደር ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ለነጮች ትምህርት ቤቶች ከሆነ መንግሥት ያሳስበታል እያሰበም ነው፡፡ ለጥቁሮች ት/ቤት ግን፣ መክፈት ያስፈልጋል? እኛ በከሰላ እንግሊዞች እንደሚገኙበት ሁኔታ አይደለንም፡፡ ለምሳሌ በፖስታ ቤት በስልክ ቤት በኢንዲጂኖች መጠቀም አንችልም፡፡ እንደ አስተርጓሚዎች እንጠቀምባቸው የማንችልበት ጊዜ ከመጣም ደስ የሚያሰኝ ጊዜ ነው፡፡ ታዲያስ ተንተባትበው አንዳንድ የኢጣሊያን ቋንቋ ለመናገር ራሳቸው ይማራሉ በመጨረሻ ዳንተ አሊጊየሪ ማሕበር የኤርትራና የአካባቢ ሀገሮች ኢጣሊያንነት ለማድረግ ዓላማውን ማስፋፋት ይፈልጋል እስቲኝና አስፈገራሚ ነው፡፡

— Aptenchiel!
— Comandi.
— Fai le cassette.
— Partire?
— Partire.
— Io partire con te?
— No.
— Tu non volere.
— Non potere.
— Tu potere.
— Ho detto: non potere. Fai le cassette e basta.

Si piega su le cassette, vi mette le mani, ma lavora di malavoglia.

A un tratto:

— Chi comandare dove andare tu?
— Io comandare.

Rizzandosi in piedi di scatto:

— Allora tu comandare, tu potere. Io venire con te.
— Ho detto di no! Fingo un cipiglio fierissimo, ma la testardaggine di questo ragazzo mi piace.

Rimette le mani nelle cassette. Poi si riduce a brontolare:

— Io servire per te sempre. Io non sapere leggere, non scrivere. Tu avere promesso imparare per me.
— Ma io non potevo prevedere che me ne sarei andato così presto!
— Io non...
— Finiscila!
— Signorsì. (Pausa) Io sapere quattro per quattro, otto per otto, io sapere binoccolo; io sapere bussola; tu avere imparato per me.
— E può bastare.
— Tu stare buono con ascari: io vedere dentro tua testa.
— Basta: tu parlare troppo come donne.

Ma è vero; stamane siamo, un'altra e ultima volta, andati insieme, io avanti, lui dietro, in ricognizione nella zona. Strada facendo, avendo saputo che la sua scienza saliva fino alle quattro operazioni dell'aritmetica, ogni tanto a bruciapelo, lo assalivo.

— Aptenchiel.
— Comandi.
— Quattro per quattro.
— Aspettare: ora contare.
— Fai presto.
— Quattro per quattro... trentasei!
— Aighi (asino).
— Signorsì. Non fare trentasei?
— No. Sedici.
— Grazie. Fare ancora domanda.
— Quattro per quattro.
— Sedici.
— Bravo.

Altro po' di cammino: un altro assalto. Se non si sentiva di rispondere, si batteva le testa con le nocche delle dita e diceva:

— Mia testa stare... — Ma non sapeva dire come stava la sua testa.

Intervenivo io:

— Dura.
— Dura, signorsì.

[illegible] Ciangattare [illegible] to speak in a low indistinct tone; to utter inarticulate sounds a baby or idiot [illegible] 1ኛ [illegible][1]

Non lo dimenticherò più.

Alto e snello come una giraffa, nero come un [illegible], Ueldanchiel Tesfù [illegible]

[illegible]

*Ascari Ueldanchiel Tesfù, [illegible]*



Pensai alla mia dignità di caporale che non doveva essere menomata, ed anche alla suscettibilità del mio interlocutore che, infine, si esprimeva come meglio poteva e sapeva e, soprattutto, rispettosamente, e forzai i muscoli facciali ad una perfetta immobilità.

— Bene, *Ueldanchiel*, allora vieni domattina coi malati del tuo battaglione.

— Signorsì.

E, con un saluto perfetto, se ne andò.

Il giorno dopo, terminata la visita medica, facemmo amicizia, e da allora, malgrado i tiri birboni che io ed i miei compagni ogni tanto gli giocavamo, *Ueldanchiel* mi si dimostrò il più fedele, il più affezionato, il più servizievole degli amici.

Sono aneddoti brevi, di sapore tutto personale, quelli che mi accingo a raccontare, ma che daranno a chi legge un'idea esatta del valore morale di questi soldatini neri, figli anch'essi della grande Madre Imperiale, fedeli ad Essa quanto noi, di questi fratellini neri che combattono per il nostro stesso ideale di grandezza, mossi da affetti affini ai nostri, di questi fratellini neri cui, per essere felici e orgogliosi di un dovere magari aspro, compiuto attraverso difficoltà e pericoli, basta un *bravo*, o un *grazie*, o una stretta di mano.

Vi sono, nella vita militare come, del resto, in

(1) Vittorio Codovilla Verso l' Impero e oltre p 161-163



[illegible] ፎቶኮፒ አንድ ተመልከት።



quella civile, degli individui che sembrano venuti al mondo con la precisa missione di disturbare il prossimo ad ogni tratto e ad ogni occasione.

Uno di questi individui era, senza dubbio alcuno, il soldato D'Alberto il quale con giochi, con richieste ed obiezioni d'ogni genere, ed naturale risultato di rendersi inviso a tutti: superiori e camerati.

Da ultimo aveva preso di mira me; che, amante del vivere d'accordo con tutti, sopportavo con santa pazienza anche lui.

Diffida però della vendetta dei buoni.

Un giorno D'Alberto mi si presentò proprio all'ora della libera uscita, quando cioè, stanco per una giornata intera di lavoro, mi accingevo ad andarmi a godere qualche ora di fresco in santa pace.

— Vorrei misurare la temperatura.

— Va bene.

Il termometro segnò trentasei e sette.

— Stai benone.

— Però, vedi, di notte tossisco.

— Copriti bene, chè, qui, la notte è umida e bisogna essere prudenti.

— Non potresti darmi un po' di pasticche per la tosse?

— Ecco un tubetto di pasticche; ne prenderai una ogni due ore.

— Poi, senti, siccome ho la fauce secca, avrei bi-



sogno di un po' di clorato di potassio perchè ho la gola irritata.

— Ecco il clorato di potassio.

— Grazie.

— Prego. Andiamo?

— Sì. Ah, senti, ho comperato un portasigarette, guarda, ti piace?

E mi porse un astuccio di filigrana d'argento dorato, uno squisito lavoro d'oreficeria araba.

— Mi costa settanta lire, è caro?

In quel momento mi balenò l'idea feroce che doveva liberarmi per un pezzo dal fastidioso attaccabottoni.

Presi il portasigarette e lo esaminai con cura:

— Bello, veramente bello. Ueldanchiel.

— Comandi, *signor caporale*.

— Io debbo uscire un momento d'urgenza. Tu resti qui ad attendermi.

— Signorsì.

— La consegna è di non lasciar toccare a nessuno quello che c'è sul tavolo. Capito?

— Capito.

— Ciao.

E deposto sul tavolo, come sbadatamente il portasigarette del soldato D'Alberto, uscii in fretta.

Ritornai dopo due ore, e D'Alberto era ancora là, imbestialito, ad attendere il mio ritorno per ria-

1ኛ ፎቶኮፒ

2ኛ አንድ የአስኳሊሳ ኢጣሊያዊ ከጻፈው መጽሐፍ የተወሰደ ከአስካሪ ወልደኪኤል ተከሰ የተባለ ቃለ ምልልስ ነው። ኢጣሊያዊ አስር አለቃ የሐኪሙ ረዳት አስታማሚ ሲሆን ወልደኪኤል የተባለው ኤርትራዊ አስካሪ ሊቢያ የሰፈሩ ኤርትራውያን የታመሙ እና የቆሰሉ ወደ ሆስፒታል አመላላሽ ነው። አስር አለቃው ለኢትዮጵያኖች የተዘጋጀው ልዩ የኢጣሊያንኛ





dell'*ascari*, che, col suo sistema un po' esageratamente convincente, avrebbe potuto finire col procurar serie noie a sè stesso ed a me. Che non ne avevo colpa.

Devo dire che *Uoldanchiel*, come la maggior parte dei suoi connazionali, soffriva di una strana intolleranza per tutti i rumori che hanno affinità con lo scricchiolio, e, particolarmente per quelli che furono di gran moda fra gli oramai scomparsi scugnizzi napoletani i quali se ne servivano come efficace risposta a chi non dava il soldino ma una parola di rimprovero.

Vuoi giocare un tiro birbone ad un camerata? Fai, con la bocca, uno dei quei rumori mentre egli sta parlando con un ascari, ed il novanta per cento delle volte il camerata si buscherà un sonorissimo schiaffo.

Schiaffo dato non per vendicare l'offesa o lo scherno, dato per istinto, per scatto di nervi che agiscono all'infuori del controllo della volontà, così come agiscono i nostri costringendoci a dimenarci disordinatamente allorchè qualcuno ci fa il solletico.

*Uoldanchiel*, ho detto, era ipersensibile a questi suoni, e bastava uno scricchiolio, sia pure lieve, per fargli abbandonare tutto quello che aveva in cuore.

Quante volte, mentre il buon diavolo accostava verso il suo oggetto che l'ascari incorruttibile non gli aveva permesso a nessun costo di riprendere.

Un giorno mandai *Uoldanchiel* a comperarmi dei datteri, venti centesimi di datteri, chè là costano quasi niente, e dopo pochi minuti me lo vidi tornare dal mercato con un cartoccio iperbolico, pieno di frutti bellissimi, grossi come uova di piccione e perfettamente maturi.

Non ne avevo mai visti di così belli, nè assaggiati di così saporiti.

Ci presi gusto, e tutti i giorni, verso le quattro del pomeriggio, il buon ascari mi portava il cartoccio di datteri squisiti.

Un giorno seppi.

Il sistema usato da *Uoldanchiel* per convincere il mercante arabo a servirlo bene, era semplice quanto persuasivo. Gli teneva questo testuale discorsetto:

*Sagnor tanento ukim venda venti cientesimi datteri. Se tu dare datteri belli, bene; se tu dare datteri brutti, sagnor tenente fare chiudere tua baracca... motifo igienico... poi io rompere tua testa.*

Non so se fosse più la tema del provvedimento igienico, o quella del provvedimento personale che decideva il mercante a scegliere quanto di meglio teneva in serbo per i clienti di riguardo, il fatto sta che, da quando seppi il fatto, ritenni opportuno smettere di comperare datteri, almeno per mezzo



Ciangottare ቋንቋ 2ኛ ፎቶኮፒ ተመልከት ከአስካሪ ጋራ ሊነጋገር የነጭ ዘሬን ከብር ለመጠበቅ ኮስተር ብሎ እነጋገረው ነበር በግለት ጽፈዋል።

Ma il tiro più bello glielo giocai, credo, io.

Un giorno, l'afa meridiana era opprimente, tanto per rallegrare lo spirito, depresso, come il corpo, dal calore terribile che arroventava l'aria, volli tentare un esperimento: presi a parte l'ascari e gli chiesi:

— *Uoldanchiel, vuoi telefonare?*

— *Si, si, sagnor caporaro, ave barlare per me a telefono.*

Non aveva mai toccato un apparecchio telefonico, e fu con entusiasmo infantile che mi accompagnò in corpo di guardia ove se ne trovava uno.

Chiamai il telefonista del Comando Battaglione.

— Pronto? Calboli, ora parlerai con *Uoldanchiel*.

Una sonora risata dall'altra parte.

— Sì, fallo parlare, chè l'arrangio io.

Passai il ricevitore all'ascari.

— Parla col caporale Calboli.

— *Caporaro Calboli? Bene.*

Accostò più che potè la bocca al microfono.

— *Brondo? Brondo? Buongiorno sagnor caporaro. Barla ascari Uoldanchiel Taclè, quarto bottiglio-*

ጣሊያኖች የኢትዮጵያ የቀድሞ ሹማምንቶች እጃቸውን ከሰጡ በኋላ የኢጣሊያ ሰንደቅዓላማን እንዲስሙ ያደረጓቸው ነበር



(fot. « Illustrazione Italiana »

Un capo etiopico che bacia la bandiera italiana nell'atto di sottomissione

2ኛ ፎቶኮፒ

በዚሁም ቋንቋም ሊቢያዊ አስካሪም አስተናግዶ ሊሸኘው አስካሪ ሊቢያዊ Saida Sagnor Dottoro (Signor Dottore) እያለ እመሰግና ይሄዳል።





dine del giorno fra i bravi soldati neri, ma non sono questi soli che li caratterizzano.

L'ascari eritreo non è una caricatura di soldato, ma un soldato autentico, nel senso più serio della parola.

Resistente alle fatiche, ligio alla consegna sino alla morte, attivo, fedelissimo all'Italia, sinceramente affezionato ai suoi superiori, egli rende alla Patria, nelle sue colonie, servigi preziosi che noi, gente di altri climi, non potremmo mai renderle.

Quale bianco resisterebbe, per esempio, a tappe di cinquanta chilometri al giorno, percorsi a piedi sotto il sole sferzante d'Africa, in zona predesertica o desertica ove, ad ogni passo, la gamba affonda nella sabbia sin quasi al ginocchio?

Essi percorrono le loro tappe cantando, lieti del dovere che compiono, paghi ad usura se il loro ufficiale nelle soste si tratterrà in mezzo a loro a chiacchierare o ad ascoltare quelle loro nenie nostalgiche che portano nell'arido deserto un po' del profumo balsamico della foresta vergine.

Ed in combattimento, chi potrebbe resistere al loro impeto selvaggio?

Solo gli arditi, che in guerra hanno compiuto i prodigi che tutti sanno, possono essere paragonati ad essi.

Certo che bisogna imparare a conoscerli, ed educarli con sistemi speciali per ottenere tutto il rendimento che possono dare.

A volte, per correggere uno di questi magnifici bambini, vale più un rimprovero affettuoso che cento curbasciate, e per ottenere la pronta e buona esecuzione di un servizio vale più la parola paterna dell'ordine militaresco.

Allora si forma fra superiore e dipendente quell'atmosfera di affetto, quella comunità di ideali che culmina in episodi spesso sublimi di abnegazione e di sacrificio.

Non sono poche le medaglie al valore assegnate alla memoria di ascari morti facendo scudo del loro petto all'ufficiale in pericolo, come non sono rari gli esempi di ufficiali nostri che hanno saputo farsi largo fra i petti che li difendevano per trovarsi al primo posto in combattimento, al primo posto di fronte alla morte.

Basta, per accertarsene, sfogliare un qualsiasi libro di storia ove siano narrate le nostre guerre coloniali.

Ed ora, per chiudere bene il capitolo, ve ne racconto una carina, una marachella collettiva di cui si rese colpevole una intera compagnia di eritrei, marachella che fece sbottare dalle risa tutto il Presidio.

L'oasi di Misurata è molto vasta, e, per quelle

2ኛ ፎቶኮፒ




ለሶማሊያውያን ኢንጊሊዚኛ የተዘጋጀው ለፀ ኢጣሊያዊ Ciangottare ቋንቋ ተመሳሳይ ነው፣ ሆኖም በአማራ ሕዝብ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው የታለመ ነው። ዱባት (Dubat) ከተባለው መጽሐፍ የተወሰደው ሲሆን ደራሲው የዱባት (ሶማሊ ባንዳ) ኢጣሊያዊ መኮንን አዛዥ ነው።[1] 3ኛ ፎቶኮፒ ተመልከት።

L'impazienza è al colmo, i dubàt arrivano cantando [illegible], bandiera spiegata al vento ed al sole.

Le fanfare celebrano la vittoria: — [illegible] — L'[illegible] è sotto e sta nella trappola: A dir la verità il Re d'Italia ha avuto la luce. — [illegible] — L'[illegible], quel gran nome di potenza, con tutto l'opposto, con il negus si è nascosto. — [illegible] — Alzate le [illegible], fate bene fantasia; contentate il governo e [illegible] contenti. — [illegible] — Egli è il governo, ha gli aeroplani e noi lo festeggiamo.

Ancora una volta abbiamo salutato insieme la nostra [illegible]




3ኛ ፎቶ ኮፒ

[1] Giorgo De Vecchi di Val Cismon Dubat gli arditi neri p 235

ከዚህ በላይ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች ማርቲኒ ለኢጣሊያ ዘረኝነት መሠረት ድንጋይ የጣለ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ዘረኝነት በኢጣሊያ የተጀመረው በፋሽዝም ጊዜ አይደለም፡፡ ፋሽዝም የተነሳበት ዓላማ ብሔርተኝነት ነው እንጂ ዘረኝነት አለነበረም፡፡ ዘረኛ ያደረጉት በመጨረሻ በውስጡ ዘልቀው የገቡ አብዛኛው የተሰኘና ተወላጅ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው ጣሊያኖች እንደ ጀርመኖች ዐረ- አሰራኤላውያን አይደሉም፡፡ የኢጣሊያኖች ዘረኝነት በጥቁሮች ላይ ነው፡፡ በጥቁሮችም ሲሆን በእነሱ በሚገዙ ቀቁሮች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሌሎች ጥቁሮች ላይ የበለጠ አክብሮት አላቸው፡፡ ማርቲኒ በከሰላ ምሳሌ እንደ ገለፀው እንግሊዞች ጥቁሮችን በመደገፍ ከጥቁሮች ግን ተሰልፈዋል የጥቁሮች ወገን ሆነዋል ማለት ነው፡፡ የኢጣሊያ ዘረኝነት ብቸኛ የዘረኝነት ዓይነት የሚያደርገው ይኸው ነው፤ እንደ ማርቲኒ አቅድ የዘር ማጥፋት ዘረኝነት ነው፡፡ ጀርመናዊው ሰባይንፉርት በዓለም ካለው የሰው ዘር በሙሉ ከሁሉ የሚናቁ ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ የሰጠው ምክር በሙሉ ከሁሉ የሚናቁ ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ የሰጠው ምክር ለተከታታዩ ማርቲኒ የዘረኝነቱ መመሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል፤ ለተከታታዩ የኢጣሊያ ትውልድም አስተላልፈዋል፡፡ እነ ማርቲኒ ቅኝ በገዢ ገርዎች ሀተግባር ሲሰሩበት የነበረ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በያዙበት ጊዜ ሕግ ሆኖ በፋሽስት ስም በአዋጅ የዘረኝነት ሕግ ሊወጣ የቻለው ግለሰቦች በፋሺዝም ባሳደሩት ተፅእኖ ነው፡፡

# ምዕራፍ 2 የኢጣሊያ ዘረኝነት በፋሺዝም ዘመን

1. የዘረኝነት ሕጐች

ኢጣሊያ አፍሪካ ከገባችበት ጀምሮ 1869 ዓ.ም. ኢትዮጵያን እስከያዘችበት ጊዜ ድረስ 1928 (1935, 1936,) ዘሕግ ሳይወጣ ማርቲኒ በደገገው መሠረት በምሥራቅና ዘሰሜን አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿ ላይ በተግባር የዘረኝነት አስተዳደር መሥርታ ትገዛ ነበር፡፡ ዘ1937 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ከያዘች ዘኋላ ዘረኝነት ሕጐች ደነገገች የመጀመሪያ ስለዜግነት ጉዳይ ነው፡፡ 1ኛ ዜጋ በመባል መብት የነበራቸው ጣሊያኖች ብቻ ነበሩ፡፡ 2ኛ የሊቢያውያን ዲሴምበር 3 1934 ዓ.ም. ቁጥር 2012 በወጣ አዋጅ ሊቢያዊ ኢጣሊያዊ ዜጋ የሚል ዜግነት እንዲሰጣቸው ተደርጎ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደገና በ1939 ዓ.ም. ጀንዋሪ 9 በቁጥር 70 በወጣው አዋጅ ልዩ የሊቢያ ዜጋ የሚል ዜግነት ተሰጣቸው፡፡ 2ኛ ደረጃ ዜግነት ደረጃ በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙት የቅኝ ግዛቶቻቸው አንድ ዘር እንደ መሆናቸው መጠን ዜግነት የሚል መብት አይሰጣቸውም፤ ምክንያቱም የቅኝ ተገዢ ናቸው ተገዢነት መብት ነው ሊኖራቸው የሚችለው፡፡ ሰሁሉም አንድ ዓይነት የቅኝ ተገዢነት ደረጃ መብት ነው የነበራቸው፡፡ 3ኛ ኤርትራውያን እና ሶማሊያውያን በስማቸው ይጠራሉ

ኢንዲጂኒ ወይንም የቅኝ ተገዢ እንዳይባሉ በኢጣሊያ ጠቅላይ ሀገረ ገዢ የንጉሡ እንደራሴ ዲሴበር 29 ቀን 1937 ዓ.ም. በቁጥር 227.307 በወጣው አዋጅ ይደነግጋል፡፡ የሰው ልጅ እንደ እቃ እንደ እንስሳ በደረጃ መከፋፈል



እርግጥ ቀፋፊ ነው ለሕዝቡ ግን የሚጎዳ ወይም የሚጠቅም ነገር የለም፡፡[1]
3ኛ የዜግነት ደረጃ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኢንዲጂኒ ተብለው ይጠራሉ
4ኛ የዜግነት ደረጃ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን እንደያዙ አዲሱ ቅኝ ግዛታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ንግሥታት ብለው በመጥራት ለአምስት ክልል ነበረ የከፋፈሏቸው፡፡

ሀ/ የኤርትራ መንግሥት ትግራይና አፋር ቋንቋ ተናጋሪ የሚያጠቃልል
ለ/ የአማራ መንግሥት ዋና ከተማ ጎንደር
ሐ/ የሐረር መንግሥት ዋና ከተማ ሐረር ባሌና አርሲን የሚያጠቃልል
መ/ የጋላና ሲዳማ መንግሥት ዋና ከተማ ጅማ፡፡

ሸዋ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነበረ፡፡ የንጉሡ እንደራሴ መቀመጫ በመሆኑ እስከ አሁን የገዢ የነበረው ጎሳ መቀመጫ በመሆኑ የሥልጣን ተጠቃሚ ስለነበረ ሕዝቡ በኢጣሊያ መንግሥት ላይ ተቃዋሚ እንደሚሆን ስለሚገመት ሸዋ የነበረውን በመበታተን 1ኛ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት መንግሥት ተብሎ የሚጠራ የአዲስ አበባ አካባቢ 2ኛ የሰሜን ሸዋ ከአማራ መንግሥት 3ኛ የምሥራቅ ሸዋ ከሐረር መንግሥት 4ኛ የምዕራብና ደቡብ ሸዋ ከጋላና ሲዳማ መንግሥት እንዲጠቃለል ተደርጎ ነበር፡፡

ሰ/ የሶማሊያ መንግሥት ኤርትራውያንና ሶማሊዎ ከኢጣሊያኖች ጋራ በጦርነት በመሰለፍ በጀግንነት በመዋደቅ ኢትዮጵያን ለመያዝ አስተዋፅኦ በማድረጋቸው ውለታቸውን ለመክፈል ኤርትራ ትግራይና አፋር እንዳገኙት ሁሉ ሶማሊያም ሶማሊኛ ቋንቋ የሚናገሩ ኦጋዴን በሶማሊያ መንግሥት ክልል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ረ/ የሸዋ መንግሥት[2] በ1938 ዓ.ም. ብቻ ሸዋ እንደ አንድ መንግሥት በአዋጅ ተቋቁሞ 6ኛ መንግሥት ሆነች፡፡ ጣሊያኖች ኤርትራን እና ሶማሊያን የሚያጠቃልል ግዛታቸው የኢትዮጵያ ኢምፓየር የሚል ስም ለመስጠት አስበው ነበሩ ምክንያቱም ንጉሣቸው የኢጣሊያና የአለባኒያ ንጉሥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ይጠራ ስለነበረ ከሀገሩም አጠራር ይስማማል በሚል አስተሳሰብ ነበረ፡፡ ነገር ግን ሀ/ ጀግኖች ወታደሮች ኤርትራውያንና ሶማሊዎች ለገዢዋ ሀገር ያበረከቱት መሬታቸው አዲስ በተያዘ መሬት ስም ሊጠራ ፍታሐዊ አይደለም ለ/ ለኤርትራውያን አብዛኛዎቹ የጋራ የዘር ሐረግና የጋራ ሐይማኖት ስላላቸው ስሙን ለመስጠት የሚቻል ቢሆንም ለሶማሊዎች ግን የኢትዮጵያ አንድ አካል ሆኖ የምትታወቅ ሕዝቡም በዘርም በሃይማኖትም የተለየ ስለሆነ በኢትዮጵያ ስም መጥራት ዲሞግራፊ ታሪክና የዘር ሐረግ ማፍለስ ብቻ ሳይሆን ሁሉም በሶማሊዎች በኢጣሊያ ባንዲራ ስር ተሰባስበው ከኢትዮጵያ ነፃ ስማውጣት ፋሺዝም ያለው ዓላማ መርሳት ይሆናል፡፡

ሌላ ስም የታሰበው በምሥራቅ አፍሪካ የኢጣሊያ ኢምፓየር የሚል ነበር፡፡ በመጨረሻ 3ኛው ስም ኢጣሊያዊት ምሥራቅ አፍሪካ የሚል ስም ተመረጠ፡፡ ጣሊያኖች ዐረቦች ሊቢያውያንን ኢጣሊያዊ ዜጋ ባይሆኑም ሊቢያዊ ልዩ ዜጋ 2ኛ ደረጃ የዜግነት መብት ሲሰጣቸው የምሥራቅ አፍሪካ ጥቁር ሕዝቦች ግን ዜጋ በሚል ስያሜ ሊጠሩ አይገባቸውም በማለት የቅኝ ተገዢዎች ብለው ሰየሟቸው፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ የሚኖሩ ሕዝቦች በሙሉ በቀለምና በዘር ልዩነት ስለሌላቸው አንድ ዓይነት ደረጃ የቅኝ ተገዢዎች ብለው መድበዋቸዋል፡፡ ነገር ግን ስለ ኤርትራውያንና ሶማሊያውያን በሶስተኛ ደረጃ የሚያስቀምጣቸው ልዩ ዘዴ ፈጥረዋል፡፡

---

(1) Annali dell' Africa Italiana anno II N1 p 61
(2) Annali Africa Italiana anno II N 1 p 61

A titolo di particolare distinzione per i fedelissimi abitanti delle nostre vecchie colonie i quali tanto contributo di valore guerriero hanno dato alla conquista dell' Impero con disposoizione del Governatore Generale Vicere N 223307 del 29 Novembre 1937 - XVI é stato disposto che i nativi dell' Eritera e della Somalia siano designati anche negli atti ufficciali rispettivamente come eritrei e somali e non indigeni sudditi etc. Tale disposiziole ha solo un significato politico ed onorifico e non ha portata guridica.

ትርጉሙም በጣም ታማኝ ለሆኑ ለቀድሞው ቅኝ ግዛቶቻችን ነዋሪዎች ኢትዮጵያን ለመያዝ ከፍ ያለ አስተዋፆኦ ያበረከቱ ልዩ ክብርና ማዕረግ ለመስጠት በማሳብ ኖቬምበር 29 ቀን 1937 ዓ.ም. በቁጥር 227307 በወጣ ድንጋጌ የኤርትራና የሶማሌ ተወላጆች ይፋዊ በሆኑ ማስረጃዎች ጭምር ኤርትራውያንና ሶማሌውያን እንጂ እንዲጂኒ ቅኝ ተገዢዎች ወዘተ ተብለው እንዳይጠሩ ያዛል። ይህ ድንጋጌ የፖለቲካ እና የክብር ትርጉም ብቻ የሚሰጠው ሲሆን በሕግ ፊት ግን ዋጋ የለውም።

በ4ኛ ደረጃ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኢንዲጂኒ ተብለው ይጠሩ ነበር። ጣሊያኖች ሕዝቡን በዘር በመከፋፈል ጥላቻ እንዲፈጠር መሠረት ድንጋይ አኑረዋል። ይህ ሕግ መሠረት በማድረግ ይሆናል የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ትግሬ የሰለጠነ ነው ብሎ ሲናገር የሚለግና የኤርትራውያንንም እንደዚሁም ሶማሊያውያንንም አጉል የበላይነት መንፈስ የሚለግሳቸው። ከሌሎች ምዕራባውያን ሀገሮች ቅኝ ገዢዎች የዘረኝነት ሕግ የሌላቸው እንደ ፖርቱጋል ሆላንድ፣ ብሪታኒያ፣ ስፔን፣ ፈረንሳይ፣ በመተቀስ እና በማነፃፀር ጣሊያኖች የኢጣሊያ ሕግ የኢጣሊያኖችና የነጮች መብት የሚጠብቅ እንደዚሁም ጥቁሮች ላላቸው ተጨባጭ ፍላጐታቸው የሚጠብቅ ስለሆነ የተሻለ ሕግ ነው ብለውታል።

፭ ጣሊያኖች ሌሎች ዘረኛ ሕጎች በተከታታይ አውጥተዋል። ኤፕሪል 19 ቀን 1937 ዓ.ም. በቁጥር 880 አንድ ኢጣሊያዊ ከምሥራቅ አፍሪካዊ ሰው ጋብቻ ከፈፀመ እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ እስራት እንዲቀጣ የሚል ሕግ አውጥተዋል። በዚህ ሕግ መሠረት ልጁ ነው ብሎ ለማስተዋወቅ ወይንም በመንግሥት ሕጋዊ ልጅ እንዲሆንለት ማድረግ ወይንም ማሳደግ የተከለከለ ሆኖ ነበረ።

ጁላይ 1 ቀን 1937 ዓ.ም. በቁጥር 12723 በኤርትራ፣ በሶማሊያ ጁላይ 19 ቀን 1937 ዓ.ም. በቁጥር 14675 ከሀገሬ ገዢዎቻቸው የኢጣሊያ ዜጎች በሚመለከት ለኢንዲጂኒ የተወሰኑ ቦታዎች እንዳይሄዱ፣ በአንድ መጓጓዣ መኪና ከኢንዲጂኒ ጋራ እንዳይሄዱ፣ በኢጣሊያኖች የሚነዱ መኪናዎች ኢንዲጂኒ እንዳይሳፈሩ፣ ይሄን ሕግ ጥሰው የተገኙ እንዲቀጡ ድንጋጌዎች ወጥተዋል። የዚህ ዓይነት ሕጎች በሌሎች በኢጣሊያ የተያዙ ጠቅላይ ግዛቶች ወጥተዋል።

በከተሞች ለጣሊያኖችና ለኢንዲጂኒ የተለያዩ ሰፈሮች ተወስነው ጣሊያኖች ሕጎቹን እንዲያከብሩ ጥብቅ ተደርጓል። ሌላ ሕግ ከዓዕላይ የፋሽዝም ምክር ቤት የወጣ ጣሊያኖች ከሆምና ከሌም እንዲሁም ከግንኙነትም አሪያን (ነጭ) ያልሆነ የሰው ዘር ጋብቻ እንዳይፈፅሙ ይከለከላል። የኢጣሊያ ዘር ክብር (Prestigio di razza) የጣስ በኢጣሊያኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉ ናቸው።

ሀ/ ኢንዲጂና በማያውቀው ጉዳይ ተጠቅሞ አታሎ ጥቅም ማግኘት የፈለገ ሰው

ለ/ ጋብቻ የፈፀመ እንደተገለፀው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት እስራት ይቀጣል፡



ሐ/ ለኢንዲጂኒ የተወሰኑ ቦታዎች በማዘውተር እስከ ስድስት ወር የሚደርስ እስራት ወይንም በገንዘብ እስከ ሁለት ሺህ ሊሬ።

መ/ የጉልበት ሥራ ለኢንዲጂኒ ያበረከተ በገንዘብ እስከ አምስት ሺህ ሊሬ የሚደርስ ቅጣት ይጠብቀዋል። አንድ ሐኪም የሆነ ባለሞያ ግን አይመለከተውም፣ እንደዚሁም የቤት ባለቤት የሆነ ኢጣሊያዊ።

ሰ/ ሰካር ለኢንዲጂኒ የተወሰኑ ቦታዎች ያዘወተረ ኢጣሊያዊ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት እስራት ወይንም ከሁለት መቶ እስከ አምስት መቶ ሊሬ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይጠብቀዋል።

በቅኝ ተገዢዎች እንዲጂኒ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከላይ በተጠቀሱ ሕጎች ቅጣት ተወስኖ በአንድ ሦስተኛ ተጨማሪ ይቀጣል።

ክልሶች በሚመለከት እንደ ኢንዲጂኒ እንዲቆጠሩ ተወስኖአል።

የኢጣሊያ ዘረኝነት የሚንፀባረቀው በተለይ በትምህርት ቤት ነው። ኢጣሊያኖች ትምህርት ለኢንዲጂኒ በሕግ የተወሰነ የተፈቀደው ለአንደኛ ዝቅተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነው። ይኸውም ለአካባቢው የሚስማሙ በተግባር ለጉልበት ሙያ ጠቃሚነት ያላቸው ማተኮር አለበት ይላል።(1)

የተፈቀደው የትምህርት ዓይነትና ደረጃ ሦስት ናቸው (2)

ሀ/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በልምድ ያተኮረ በእርሻ ወይንም በእደ ጥበብ እንደ አካባቢው

ለ/ ሁለተኛ ደረጃ ባለ ልዩ ሙያዎች አስተርጓሚዎች፣ የሂሳብ ሠራተኞች፣ ፀሐፊዎች፣ ነበሬዎች፣ የእደ ጥበብ ወዘተ.. ከአንደኛ ደረጃ የጨረሱ የሚመለመሉ

ሐ/ ለባላባቶች ልጆች በልዩ ፕሮግራም በተወሰነ ቁጥር ብቻ ለኢንዲጂኒ አስተዳደር በቢተሰባቸው ታሪክ ባሕል ለጠታ ያላቸው የተመረጡ ለጊዜው ሥራ ማግኘት ችግር ስላለ ለግብርናና ለእደ ጥበብ ትምህርት ቤቶች አልተከፈቱም።

ጣሊያኖች ትምህርትቤትም ከፈትን ሊሉ አይችሉም። የዚህ ዓይነት ትምህርትቤት ሊያገለግል የሚችለው ሰው ልጅ ሳይሆን ከሰው እና ከእንስሳት መሐከል የሚገኙ ልዩ ፍጥረቶች አገልግሎት የሚውሉ መሆን አለባቸው።

ጣሊያኖችም የገመቱን እንደ እነሱ ሙሉ የሰው ፍጡር አልነበርንም። ጎዶሎ ፍጡሮች በመመደብ ነው ትምህርት የሚሰጠን፣ ጣሊያኖችን በጉልበት ሥራ እንድናገለግል፣ የነሱ ረዳት በመሆን አብዛኛው በእርሻ በከብት እርባታ፣ ችሎታ የማይጠይቅ የእደ ጥበብ ሙያ አሰልጥነን ተምረን እንደ እንስሳ ለመደፈት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወደ ሀገራችን የሚመጡ የኢጣሊያ ሠፋሪዎች አገልጋዮች ሆነን እንዲበዘብዙን ነው።

ትምህርት ቤት ከፈትን ብለው ደግሞ ያለ ምንም ሀፍረት ጣሊያኖች ከ1938-39 የትምህርት ዘመን በየአንዳንዱ ክፍሎች የነበሩ የተማሪዎች ቁጥር ዘርዝረው አውጥተዋል።

1/ በኤርትራ 4,000 ለኤርትራውያን ተማሪዎች በስማቸው እንዲጠሩ በሕግ እንደ ሹመት መብት የተሰጣቸው

2/ በሶማሊያ 896 ሶማሊያውያን ተማሪዎች ኢንዲጂኒ የማይባሉ መደበኛ ተማሪዎችና 50 የሚደርሱ ተማሪዎች የባላባቶች ልጆች ልዩ ስልጠና የተመደበላቸው

3/ በሸዋ 926 ለኢንዲጂኒ ተማሪዎች በስማቸው እንዳይጠሩ በሕግ የተከለከሉ

4/ በሐረርጌ 432 " " " " " "

5/ በአማራ 1034 " " " " " "

(1) Annali dell' Africa Italiana anno III N1 p 675

(2) Annali dell' Africa Italiana anno III p 694

6/ ጋላና ሲዳማ 700 ልጆች ለኢንዲጂኒ ተማሪዎች በስማቸው እንዳይጠሩ በሕግ የተከለከሉ

በአፍሪካ ለሚገኙ በቁጥር በጣም አነስተኛ የነበሩ የጣሊያኖች ቤተች ልጆች ግን እስከ ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ ትምህርትቤት ተከፍቶላቸው የተሟላ አገልግሎት የሚሰጡ ትምህርትቤቶች ተቋቁሞላቸው ነበር፡፡

በሕጎች ብቻ ሳይሆን በግንኙነትም ጋዜጦች መጽሔቶች መድረኮች ነበረ የኢጣሊያ ዘረኝነት ተግባራዊ ይሆን የነበረው፡፡

ሞሬኖ Moreno የተባለው በኢጣሊያ የአፍሪካ ሚኒስቴር የፖለቲካ ጉዳይ መምሪያ ዋና ዳይሬክተር በመሆን በፋሽዝም ዘመንም ከፋሽዝም ውድቀት በኋላም ዲሞክራሲ ተብሎ የተቋቋመው የኢጣሊያ መንግሥትት ውስጥም በታው ሳይለቅ ይሠራ የነበረ ነው፡፡ በ1941 ዓ.ም. ኢጣሊያ ከሀገራችን ተሸንፋ ወጥታ ነበር፡፡ በ1943 ከጀርመን የጦር ጓደኛዋ ተነጥላ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እጆዋን ለፀረ ፋሽዝም ጦር ጓዶች ሰጥታ ነበር፡፡ ሞሬኖ በ1942 ማርች ወር ስለ አፍሪካውያን በኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የነበሩ አንድ ጽሑፍ አውጥተዋል፡፡ ለአፍሪካውያን ትምህርት ቤት ስለመክፈት ጉዳይ በሚመለከት እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር "ለአፍሪካውያን መስጠት የሚገባውን የትምህርት ዓይነት የእርሻና የጉልበት ሥራ መሆን አለበት፡፡ ለእነሱ ትርፍ የሆኑ ማለት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርቶች መስጠት ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ በብዙ መቶ ዘመናት የተገኘው ሥልጣኔ ውጤት በአንድ ትምህርት ቤት ወንበር ለጥቂት ዓመታት ተቀምጦ ተምሮ ለማዋሀድ ይቻላል የሚል እስተሳሰብ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ የኤውሮጳ ዓይነት የተማረ ኢንዲጂና አፍሪካዊ ኤውሮጳዊ አይሆንም የኤውሮጳውያን ጆንጆሮ ነው የሚሆነው፡፡ በኤውሮጳውያን ዘንድም የተተፋ ነው የሚሆነው፡፡ በሀገሩ ሰዎች ዓይንም ጆንጆሮ እንደመሆኑ መጠን ጠቃሚነት የሌለው ትርፍ ነገር ስለሚሆ ቀጥሩት በድንጋይ ወርውረው ያባርሩታል"፡፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ ከተጠቀሱ የኢጣሊያ ዘረኝነት ሐሳቦች በባስ ሁኔታ የኢጣሊያ የቅኝ አገዛዝ ምን ያህል አስከፊ እንደነበረ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

"ዘረኛ ሕጎች በሚመለከት የነጭ የበላይነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቃውሞ አላገጠመውም፤ ነጮችና ጥቁሮች ጋብቻ የሚከለከሉ ሕጎች፣ እንዲሁም በመኖሪያ ቤትም በአገልግሎት ሰጪዎች ተቋሞች መቀላቀል የሚከለከሉ በኢንዲጂኖች ቅሬታ አልፈጠረም፤ አላስገረመም፤ እንዲያውም የዚህ ተቃራኒ ቢሆን ቅር ይላቸዋል፡፡ እነዚህ ሕጎች የቤተሰብ ጥበቃ የሚያደርጉ መሆናቸውን፤ ለኢንዲጂኒ ሴቶች ጥበቃ እንደሚሰጡም ይተርጉሙታል፤ እንዳእንድ ነጮችም በነጮች የበላይነት ሽፋን የፈለጉትን በደል ሁሉ ማድረግ እንደማይችሉ ገደብ የሚሰጥ በመሆኑ የሕጉ ጠቃሚነት ያምኑበታል" ብሏል፡፡

ደ ኒኮላ የተባለው ሌላው ኢጣሊያዊ ስለ ልዩ ልዩ የሲቢያ ዜግነት የፋሽዝም የላይኛው ምክር ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ በመጥቀስ የሲቢያ ዜግነት ለእስላሞች የተሰጠው ለኢጣሊያ የታማኝነት ምልክት በማሳየታቸው በተለይም ኢትዮጵያን ለመውረር በተደረገው ዘመቻ በውዲታቸው በመካፈላቸው ነው፡፡ ይሄም ቢሆን ሙሉ የኢጣሊያ ዜግነት የላቸውም፡፡ የሮማውያን Civitas Sine Suffragio ድምፅ መስጠት የሌለው ዜግነት የሚገነባር ነው፡፡ የሮማውያን ሆነ የሲቢያውያን ዜግነት የገዢዎችና የተገዢዎች መራራት የሚጠብቅ ነው ብሏል፡፡

ሞሬኖ በተጠቀሰው መጽሔት እንደ ወትሮ ልማዱ "ፖሊቲካ ኢንዲጂና" (Politica Indigena) በሚለው አርዕስት ሌላ ጽሑፍ አውጥተዋል፡፡ በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ ፋሽዝም መሪ ሙሶሊኒ ከሥልጣን ወርዶ ማርሻል ባዶሊዮ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ኢጣሊያ ከጦርነት ወጥታ



በቀጥታ በጦር ጓዶች ሀገሮች ወታደራዊ አገዛዝ ሥር ስትስተዳደር ነበረ፡፡ ኢጣሊያ በሽግግር ጊዜ ትገኝ ነበር፡፡ ሞሬኖ በ1942 ዓ.ም. ስለፖለቲካ ኢንዲጂና በመጽሔት ያወጣው ጽሑፍ ማስታወስ ከዚህ በፊት የገፋው በሰፊው ጽሑፉን ማንበብ በቂ ነበረ፤ አሁን እንደገና በጉዳዩ መመለስ አስፈላጊ አይሆንም ካለ በኋላ ነገር ግን ምንም እንኳን አሁንም አብዛኛው ከተነገሩ ጉዳዮች የምደግማቸው ቢሆንም ባለፈው ጊዜ ያልነበሩ ሁኔታዎች ስላሉ ጥናታችን ለመመርመር አስፈላጊ በመሆኑ እኔም የገፍኩትን ተመልጄ ላላነበውም ሌላ ሰውም እንዲያነበው አልጋብዝም በማለት ጽሑፉን ይቀጥላል፡፡

Nella politica religiosa è in parte assorbita, in Africa come in Oriente, la politica scolastica. L'istruzione degli indigeni deve, secondo il concetto italiano, mirare a due scopi:

1) incrementare la cultura tradizionale, conservando integro a coloro che accedono all'istruzione il loro patrimonio spirituale, affinché giovino al loro ambiente anziché estraniarsene;

2) migliorare la cultura tradizionale con quelle nozioni della cultura europea che realmente possono riuscire utili (come, ad esempio, l'insegnamento agricolo e manuale), escludendo il superfluo e respingendo l'idea che tutta una civiltà, frutto di secoli d'evoluzione, possa essere assimilata sedendo per pochi anni sui banchi di una scuola.

L'indigeno istruito completamente all'europea diventa non un europeo ma una scimmia degli europei, respinto da questi e inutile ai suoi conterranei che, da quella scimmia che è, lo prendono a sassate.

Le scuole religiose, integrate nelle materie di studio, dotate di buoni insegnanti e di adeguati sussidi didattici e largamente sovvenute, e le scuo-

ካለፈው ጊዜ አስተሳሰብም ምንም ለውጥ የለውም፤ ኢጣሊያ የሲቢያም ሆነ የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿ እንደሚመለሱላት እርግጠኛ ሆና ነው የሚያወራ፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ በ1936 ዓ.ም. እንደነበረች አናገኛትም፡፡ በ1941 ዓ.ም. እንደተውናት ሆና አናገኛትም፡፡ በሊቢያም ብዙ ለውጥ እናገኛለን ጽሑፉ አዲስ አስተሳሰብ አላቀረበም፡፡ የቀድሞ ዘረኝነቱን በማጠናከር ጥቁር ሰውና ነጭ ሰው በእኩልነት ሰም በመንገድ ተቀቅሎው ነፃነት እኩልነትን እና ወንድማማችነትን እየዘፈኑ ሽርሽር ቢሄዱ ከዚህ ሽርሽር መጨረሻ ነፈሱና ጥቁሩ የየራሳቸው ጥሩ ባሕላቸው ጠፍቶ እርስ በእርሳቸው መጥፎ ባሕል ስለሚለዋወጡ መጥፎ አፍሪካዊና መጥፎ ኤውሮጳዊ ይሆናል፡፡ ከፍተኛ ሥልጣኔ ከዝቅተኛ ሥልጣኔ ጋራ ሲገናኝ ሊያሻሽለው እንደሚችል የማይካድ ቢሆንም የሬዚዮሎጂ ሕግ ትክክል እስከሆነ ድረስ ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ከዝቅተኛ ሥልጣኔ አንጻር በኩል ተቀባይነት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የከፍተኛ ሥልጣኔን ጠባይ ማዋሀድ ሳይሆን ጭምጭሙን ያስከትላል ብለዋል፡፡ ሞሬኖ በጽሑፉ መጨረሻ ከኢትዮጵያ የተመለሱ ኢጣሊያኖች የሰጡት የምስክርነት ቃል በማለት ኢትዮጵያውያን የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ነዋሪዎች ከዚህ በፊት በጥቂቱ የጣሊያኖች ጥፋቶች ጣሊያኖችን ቢጠሉም ዛሬ ግን በፊት የነበሩ ገዥዎቻቸው ስለሚያውቁ አሁን የመጡትን ስላዩ በማነፃፀር ወደ ሕግ አልበኝነት፣ ጭቆና፣ ለድህነት ስለወደቁ ኢጣሊያ ተመልሳ እንድትገዛቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት እየጠየቁ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

## 3. የኢጣሊያ ዘረኝነት በይፋ ተመሠረተ

የኢጣሊያ ዘረኝነት በይፋ የተቋቋመው ጁላይ 26፡1938 ዓ.ም. ነው። በዚሁ ቀን የባሕል ሚኒስትር በተገኘበት በሚኒስትሩ የበላይ ጠባቂነት ታዋቂ ፕሮፌሰሮች እና ዶክተሮች ተሰብስበው ኢጣሊያ ልትከተለው የሚገባት የዘረኝነት ፖሊሲ በግርቀትና ዓላማውን በመደገፍ ባለ 10 ነጥብ መግለጫ አውጥቷል፤ በስብሰባው የተገኙት ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘረው ነው።

1/ ዶክተር ሊኖ ቡሲንኮ Lino Businco ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
2/ ፕሮፌሰር ዶክተር ሊዲዩ ቺፕሪያኒ Lido Cipriani ከፍሬንሴ ዩኒቨርስቲ
3/ ፕሮፌሰር ዶክተር አርቱሮ ዶናጂዮ Arturo Donaggio ከቦሎኛ ዩኒቨርሲቲ
4/ ዶ/ር ሊዮኑ ብራንዚ Leono Branzi ከሚላኖ ዩኒቨርሲቲ
5/ ፕሮፌሰር ዶ/ር ጉዊዶ ላንድራ Guido Landra ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
6/ ፕሮፌሰር ኒኮላ ፔንዴ Nicola Pende ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
7/ ዶ/ር ማርቼሎ ሪቺ Marcello Ricci ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
8/ ፕሮፌሰር ፍራንቼስኮ ሳቫርኛን Francesco Sovargnan ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
9/ ፕሮፌሰር ሳባቶ ቪስኮ Sabato Visco ከሮማ ዩኒቨርሲቲ
10/ ፕሮፌሰር ዶ/ር ኤዶዋርዶ ሳቮታሪ Edoardo Savottari ከሮማ ዩኒቨርሲቲ

ስለ ኢጣሊያ ዘረኝነት ፋሽዝም ያለው አቋም ብለው ያወጧቸው ባለ 10 ነጥብ መግለጫዎች የሚከተሉት ነበሩ።

1/ የሰው ልጅ በልዩ ልዩ ዘሮች የተከፋፈለ ነው
2/ ትልቅ ዘሮችና ትንሽ ዘሮች አሉ
3/ የሰው ዘር መሠረታዊ ልዩነት አስተሳሰብ የሚፈጠረው ዘባዩሎጂካዊ የምርምር ውጤት ብቻ ነው።
4/ የዛሬ የኢጣሊያ ሕዝብ ዘር መሠረቱ አሪያን ዘር ነው ሥልጣኔውንም አሪያን ነው
5/ ብዙት ያላቸው በታሪካዊ ወቅት አሪያን ያልሆኑ ሕዝቦች ከኢጣሊያን አሪያን ዘር የሆኑ ተቀላቅለዋል የሚለው አነጋገር ተረት ነው።
6/ የኢጣሊያዊ ንፁህ ዘር አለ።
7/ ጣሊያኖች በግልፅ ዘረኞች መሆናቸውን የሚገልፁበት ጊዜ አሁን ነው
8/ በምዕራብና ምሥራቅ ሜዲትራኒያን ሕዝቦችና የአፍሪካውያን ሜዲትራኒያን ሕዝቦች ያለው ከፍ ያለ ልዩነት እንዳለ ማወቅ ያስፈልጋል።
9/ እስራኤላውያን /ይሁዶች/ አሪያን ዘር አይደሉም
10/ አካላዊና መንፈሳዊ ንፁሕ ኤውሮጳዊ የሆኑ የኢጣሊያኖች የዘር መለኪያዎች በምንም ዓይነት መለወጥ የለባቸውም።

ከፋሽዝም ውድቀት በኋላ ጥቂት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በእስራኤላውያን ተማሪዎች አነሳሽነት በቀድሞ ፀረ- ጽዮናውያን ዘረኞች ፕሮፌሰሮች ተቃውሞ ሲያሰሙ በጥቁር ሕዝቦች ዘረኝነታቸውን ግን አንድም ወገን ተቃውሞ በአደባባይ የሚያሰማ እንዳልነበረ የዓይን ምስክሮች ሆነናል። ዲሞክራሲያዊ መንግሥትም ለፕሮፌሰሮች ፋሺስቶች ጥበቃ እያደርግላቸው ነበር። የዘርኝነት መግለጫ ከወጣ አንድ ሳምንት በኋላ የኢጣሊያ ዘረኝነትን የሚያሰራጭ በየሁለት ሳምንት ታትሞ የሚወጣ አንድ መጽሔት የዘር ጥበቃ Difesa della razza የተባለው መታተም ጀመረ። በዚሁ መጽሔት ሳይንስ በፕሮፌሰሮች መግለጫ መሠረት የዘረኝነት አቋም ወሰዶች ተብሉ ተወራለት።



የዘረኝነት አስፈላጊነቱ አስቸኳይና አንገብጋቢ የሆነው ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመያዝዋ ከጥቁር ሕዝብ ጋራ በሰፊው ግንኙነት አድርጋ በመገኘቷ ነው ተብለው በሰፊው ተልተጋብቷል። መጽሔቱ የፀረ-ፋሽዝም የጦር ጓዶች ኢጣሊያን እስከ ተቆጣጠሩበት 1943 ዓ.ም. ድረስ ለ 5 ዓመት ይወጣ ነበረ። ከኢጣሊያ ሕዝብም ፀረ- ጽዮናውያን የጥላቻ መንፈስ አልነበረም፤ ጀርመኖችን ለማስደሰት ግን ጣሊያኖች እስራኤሉችን ለማጥላላት በመጽሔቱ ላይ በሰፊው ተባብረዋል። በጥቁሮች ላይ ግን የኢጣሊያ ሕዝብ በሙሉ ጥላቻና ንቀት ጀርመኖች ከነበራቸው የባሰ ነበር፤ አሁንም በዲሞክራሲ ሥርዓት ዘረኝነታቸው የተቀነሰ ነገር የለም። ጥቁሮችን በሚመለከት በተለይ ኢትዮጵያውያን በ5 ዓመታት ዘረኞች ጣሊያኖች ምን ይጽፉብን እንደነበረ፤ የጀርመን ናዚዝቶች በጦርነቱ ቢያሸንፉ ኖሮ ለወደፊት በጥቁሮች ላይ ምን ያቅዱብንና ያልሙብን እንደነበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያቀው ያስፈልጋል።

የድሮ ጠላቶቻችንና ወዳጆቻችን ለይተን ማወቅ አስፈላጊቱ የማይታለፍ ነው፤ ምክንያቱም ዛሬ ለነፃነታችንና ለሥልጣኔያችን የምናደርገው ትግል ግን እንደሆነ ሀቀኛ የልብ ወዳጆችን በፖለቲክና በኢኮኖሚ በጎናችን መቆም የሚችለው በተቃራኒም ግን እንደሆነ ስውር ጂብ ሊፈጽምን የሚችለው ለመገመት ይስችለናል።

ከነሂዎች ውስጥ በደል የፈጸሙብን ጣሊያኖች ብቻ ናቸው፤ ሌሎች ፈረንጆች በወዳጅነት ከማስታወስ በስተቀር በጠላትነት እንደ ጣሊያኖች ልንመለከታቸው አንችልም። ጣሊያኖች የሚኮሩበት የነጭ ዘር ሌሎች ነጮች ወክለን እንግጥታለን የሚሉት ምን ያህል የነጭ ዘር አሪያን በደግቸው እንዳላቸው አጥንተን መርምረን ማወቅ ያስፈልጋል።

## 4. የኢጣሊያ ዘር

የኤውሮፓ ሕዝብ በዘር ለሦስት ዋና ዋና ክፍለች ይከፈላሉ፡-

1/ ሰሜንናውያን ንፁሕ ነጭ አሪያን ዘር የሚበዛበት ሰሜን ኤውሮጳ
2/ አልፒናውያን መሐል ኤውሮጳ የነጭ ዘር አሪያን ምልክቶች ቀንሰ የሚታይበት
3/ የሜዲትራኒያን የነጭ ዝር አሪያን ከሌላ ዘር ቅልቅል የበዛበት

በዚሁ የዘር አከፋፈል መሠረት ንፁሕ ነጭ አሪያን ዘር የሚገኙበት በስካንዲናቪያን ሰሜን ኤውሮጳ ራሺያ ወዘተ... ስለሆነ ለነጭ ዘር መቆርቆር የሚችሉ እነሱ ነበሩ። ጣሊያኖች በመጨረሻ ደረጃ የሚገኙ አይደሉም ለአሪያኖች ተቆርቋሪ የሚሆኑ። የዓለም ሥልጣኔ የዳበረበት ግን በሰሜን ኤውሮጳ ሳይሆን በሚዲትራኒያን ስለሆነ የሌላቸው ዘር ከመመኘት ጣሊያኖች ብእውነተኛ ዘራቸው መኩራት ነበረባቸው። ጣሊያኖች የሮማውያን ልጆች ነን ማለት ይወዳሉ። ለመሆኑ ሮማውያን ግን ነበሩ? የሮማውያን ቅድመ ታሪክ ተረት ነው። ጣሊያኖች ምሑራን ዘራቸው አሪያን ዘር መሆኑ ለማስረዳት ብዙ ይሞክራሉ። አፍሪካዊ ጥቁር ዘር እንዳይለጠፍባቸው ያላቸው ፍርሀት የሚያመለክት ነው። ጣሊያኖች የሮማውያን ዘር መሆናቸውን ለሚወዱ ስለ 10 ነጥብ የኢጣሊያ ዘረኝነት መግለጫ ያወጡት የኢጣሊያ ፕሮፌሰሮች በቁጥር 4-5-8 ጥርጣሬውን ለማስወገድ ሞክረዋል።

ከሮማውያን እንወለዳለን ስለሚሉት ነገር ብንመለከት ጣሊያኖች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ፈረንጆችም ሌላ የዓለም ሕዝብም ተገቢ ያልሆነ አድናቆት ለሮማውያን ስለሚሰጣቸው ጉዳይ የዘር ጥበቃ Difena della razza መጽሔት

አፕሪል 20/1940 ዓ.ም. 3ኛ ዓመት ቁጥር 12 ኤቮላ ያወጣው ጽሑፍ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይበቃል። መጀመሪያ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ስለ የሮማ ጥንታዊነት አንደነቅበትም። ሮማ የተመሰረተችበት ዘመን የሚባለው በታሪክ ሳይሆን በተረትና በአፈ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት 753 ሲሆን፣ ይህ ዘመን ለእኛ በአንፃራዊ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው። ተረት ሳይሆን ታሪካዊ የሆነ ሁኔታ ኢትዮጵያዊት ንግሥተ ሳባ የሰለሞንን እውቀት ለማድነቅ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ያደረገችበት ቀዳማዊ ሚኒሊክ የተወለደበት ዘመን 1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን በዚሁ ዘመን ግን ሮማውያን በታሪክም በአፈ ታሪክም ስማቸው ያልተጠራ መሆኑን እንገነዘባለን። ኤቮላ

1/ የሮማ አፈ ታሪክ የአሪያኖች ዘር ታሪክ የሚመሳሰል ነው በማለት ይጀምራል፣ ብዙ ምሳሌ በማቅረብ የሮማውያን አሪያንነት ለማስረዳት ይሞክራል

2/ ሮማውያን በተረትና በአፈ ታሪክ መሠረት ማርስ ከተባለው እግዚአብሔርና ሲልቫ ከተባለችው ሴት ንግሥት ጋብቻ ሁለት መንታ ወንድማሞች ሮሙሉስና ረሙስ ተወለዱ ነው የሚለው። ስለዚህ ሮማውያን ሁሉም ባይሆኑም የመጀመሪያ ንጉሣቸው ተራ ሰዎች ሳይሆኑ ከአምላክ የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆናቸውን ነው። ኤቮላ የተባለው ኢጣሊያዊ በአባት እግዚአብሔር በእናት የሰው ልጅ መወለድ በሮማውያን የተጀመረ አይደለም በጥንት ግሪኮች በሌሎችም አሪያን ሕዝቦች የተለመደ ነበር ካለ በኋላ በግብጻውያንም የተለመደ ነው ብሎ ጽፏል። የግብፃውያንም ቅድመ ታሪክ ከአሪያኖች የመጣ ነው ብሎ ይደመድመዋል። የጥንት ሥልጣኔ አባቶች ግብጻውያን ቆይተው ሥልጣኔ ካገኙ ከአሪያኖች ባሕል ወሰዱ ማለት ርካሽ የሆነ የታሪክ ማነባት ተግባር ነው።

3/ ሁለቱ መንታ ልጆች ሮሙሉስና ሬሙስ በአንድ ወንዝ ውሃ ተጥለው መገኘታቸው ብዙ ትርጉም ያለው ሲሆን፣ ይሄም ሁኔታ በሮማውያን የተጀመረ አይደለም፣ ኢቮላ በዘረኞች የተጠሉ የእስራኤላውያን ምሳሌ ይሰጣል። ሙሴ በውሀ ከመወሰድ ድኗል፣ ግብፃውያን አሪያን ናቸው እንዳላቸው፣ ሙሴ ግን አሪያን ዘር ነበረ አላለውም። ውሀ በአሪያኖች ባሕል ሚች፣ ተለዋዋጭ፣ መልአካዊ ያልሆነ፣ ሰሜታዊ የሆነ ነገር ሁሉ ምልክት ነበር። ደካማ ሰው በውሀ የማይወሰድ፣ የሚድን ግን ከሰው ፍጡር በላይ የሆነ ጀግናው ነቢይ ተአምራዊ መልአካዊ የሆነ ነው።

4/ ሁለቱ መንታ ልጆች በአንድ የበለስ የዛፍ ስር መጠለያ ይገኛሉ። የበለስ ፍሬ ከጥንት ጀምሮ በምግብነቱ የታወቀ ነበር። በአሪያኖች ባሕል ማንኛውም ዛፍ የሕይወት ምልክት ነው፣ በተለይም የበለስ ዛፍ፣ ስራም ወደ ሰማይ የሚዘረጋ ነው። በእስራኤላውያን ባሕል ከዛፍ የሚመገብ እንደ እግዚአብሔር የሚመሰል የእርግማን ምልክት ነው። በአሪያኖች ግን ተቃራኒ ነው ሮሙሉስና ረሙስ ከበለስ ዛፍ ፍሬ ሲመገቡ ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ምግብ እንደሚቆጠር ነው። በሮማውያን ተረት መሠረት የሴት ተኩላ ሮሙሉስንና ራሙስን በወንዝ ውሃ አግኝታ ጡቷን አጥብታ ያሳደገች ናት።

5/ ተኩላ በአሪያኖች ቋንቋ በግሪክና ላቲን ፀሐይ የሚል ትርጉም አለው። ስለዚህ ተኩላ በአሪያኖች ባሕል ሁለት ምልክት አለው ጨካኝ አውሬና የሚያንፀባርቅ ፀሐይ፣ ይኸውም በሚዲትራናውያን ግሪክና ላቲን ብቻ ሳይሆን በሰሜናውያን አሪያኖችም ሁለቱ የተኩላ ባሕሪያት ይታያሉ። ይህ ሁለት የተኩላ ባሕሪያት በሮሙሉስና ረሙስ ባሕሪያት ላይም ተከስቷል። ይኸውም የሁለት የወንድማማቾች ሁለት የሥልጣኔ ዓይነቶች የሁለት ሃይማኖቶች በግብፃውያን ወንድማማቾች ኦሲሪድና /Osiride/ ሴት / Set/



የተከሰተ ነው እንደ ፀሐይ ማንፀባረቅ ምልክት የሌለው የገሊነም ሥልጣኔቢስ ዐመፀኛ ምልክት በሮሙስና ረሙስ ከግብፃውያን ተመሳሳይ ባሕሪ አለው። ሮምሉስ ወሰኑን ምልክት በማድረግ ዘሰሙ የሮማ ከተማ የመሰረተ፣ ሕግ የሰጠ ሲሆን፣ ረሙስ ግን ቃሂንን ሕግ ያፈረሰ በዚሁ ምክንያት በወንድሙ እጅ የተገደለ ነው።

6/ በሌላ በኩልም የሮሙሉስና ረሙስ ቅራኔዎች በሁለት የሰው ዘሮች አሪያንና አሪያን ያልሆኑ ዘሮች ቅራኔዎች ምሳሌ ነው ብለው የተረጉሙትም አሉ።

7/ ሌላ የሮሙስና ረሙስ ምልክትም የሁለት የሮማ ፓላቲኖና አቨንቲኖ ኮረብታዎች ምሳሌ ነው፣ ፓላቲኑስ የሮሙሉስ ምልክት ሲሆን የአቨንቲኑስ የረሙስ ነው የቀድሞ አሪያን ሕዝቦች ፕላሰጂኮች የእግዚአብሔራቸው ልጅ ካሁን ከገደለ በኋላ በፓላቲኑስ ኤርኮለስ ኢቫንድሮ የተባለው ደጉ ንጉሥ ያገኛል በዚሁም ኮረብታ ለጀግንነት ንግሥት Regina Victoria ሐውልት ያሰራል ኤርኮለስ በግሪኮች እምነት መሠረት አቨንቲኖ ላይ አንድ የከሁ ዋሻ ለአሉምኒክ እግዚአብሔር እንደ ቤተመቅደስ ያሰራል የሁለት ዘሮች ትግል ተብሎ ተተርጉሞል የሮሙሉስ የአሪያን ዘር የሮማ መንግሥት መነሳት ተብሎ ተተርጉሟል።

አፈ ታሪክ እንደሚለው ሮማ ማለት የጎሳ ስም አይደለም የቦታ ስም ነው ትርጉሙም ከወንዙ አጠገብ ማለት ነው ሮማን አቋርጦ የሚያልፍ የቴቨሬ Tevere ወንዝ በዚሁ ወንዝ አካባቢ የሰፈሩ ሦስት ጎሳዎች ነበሩ። እነሱም 1/ ራሚ ወይንም ላቲናውያን 2/ ቲትሲ ወይንም ሳቢናውያን 3/ ሉሴሬ ወይም ኢትሩስኮውያን የተባሉ ናቸው። ሲጣሉ የነበሩ እነዚሁ ሶስት ጎሳዎች አንድ ላይ ተዋሕደው ከወንዙ አጠገብ የሚባለው የሮማ መንደር ቆረቆሩ። ሮማም የተዋሐዱ ሦስት ጎሳዎች የጎሳ መጠሪያ ሆኖ ቀረ። የተዋሐዱ ጎሳዎች ቋንቋቸው የላቲናውያን፣ ባሕላቸው በስልጣኔ የላቀ ደረጃ የነበራቸው የኢትሩስኮውያን ባሕል ወሰዱ። ኢትሩስካውያን ከትንሿ እስያ ፈልሰው የመጡ ስልጣኔም ይዘው የመጡ ናቸው። ኢትሩስካውያን ዋና ሰፈራቸው ዛሬ ቶስካና የምትባለው የኢጣሊያ ክፍል ሀገር ናት። ኢትሩስካውያን ወደ ደቡብ እስከ ናፖሊ ግዛታቸውን አስፋፍተዋል፣ ወደ ሰሜንም ማንቶቫ፣ ራቬና ቦሎኛ ወዘተ... የመሳሰሉት ከተሞች መሰርተዋል። ኢትሩስካውያን ሕክምና፣ ምሕንድስና ያወቁ ነበር፣ ማዕድናት ለምሳሌ በወርቅ ማዕድ ማውጣት ችሎታ ነበራቸው፣ የውሀ መሄጃ ቦይ ይሰሩ ነበሩ፣ ምርጥ ባሕርተኞች ነበሩ፣ በሸክላ ሥራም አዋቂዎች ነበሩ፣ መቃብሮቻቸው በተራራዎች ሥር በቁመት እየተቆፈሩ ይሰሩ ነበር፣ አርክ የፈለሰፉ እነሱ ናቸው ተብሎላቸዋል። ኢትሩስካውያን ሦስት ኮንፌዴሬሽን መንግሥታት መሥርተው ነበር 1/ የሰሜን ኢጣሊያ 2/ በካምፓኒያ ናፖሊ ዙሪያ 3/ በኢትሩሪያ። 1ኛ እና 2ኛ ኮንፌዴሬሽኖች ብዙ ሳይቆዩ ሲጠፉ ኢትሩሪያ ግን ለብዙ ጊዜ ኖራለች። ኢትሩስካውያን ሔሮዶትስ እንደተረከው ከትንሿ እስያ ፈልሰው ወደ አሁኗ ኢጣሊያ የሰፈሩ ናቸው። የሮማውያን የመጀመሪያዎቹ ማሐንዲሶች፣ የሐይማኖት መሥራቾች ናቸው። ሙሶሊኒ ይጠቀምበት የነበረ ፋሺዮ ሊቶሪዮ የኢትሩስካውያን ባሕል ነው። ቶጋ የተባለ የሮማውያን አለባበስ ከኢትሩስካውያን የተወሰደ ነው። በ1938 ዓ.ም. የታተመው የኢጣሊያ ኢንቺክሎፔዲያ ትሬካኒ እንዳስቀመጠው ኢትሩስካውያን አሪያን ነጭ ዘር አይደሉም። ጣሊያኖች አባቶቻቸውን ብለው የሚኮሩባቸው ሮማውያን በከፊል ከኢትሩስካውያን ስለሚወለዱ ሙሉ በሙሉ ነጭ ዘር አይደሉም፣ ሴማውያን ወይም ካማውያን ናቸው። አብዛኛው የኢጣሊያ ዘረኝነት አራማጆች እንደ

ማርቲኒና ሞፕሪያኒ የመሳሰሉት አሪያኖች አይደሉም፣ የቶስካና ተወላጆች እንደ መሆናቸው መጠን አሪያኖች አይደሉም። ኢትሩስካውያን የሮማውያን ዘር መሥራቾች ብቻ ሳይሆኑ ለኢጣሊያ ቋንቋ የሰጡ ናቸው። ኢጣሊያ በዓለም በእርኪቴክቸር፣ በስካልፕቸር፣ በፔንቲንግ ዝነኛ ያደረጓት ኢትሩስካውያን ናቸው። በትክክል ነጭ ዘር ጣሊያኖች ሎምባርዲያውያን በትኝ ግዛት ፍሩቲንትና በዘረኝነት የሚታወቁ አይደሉም። ዛሬ ኢጣሊያኖች ስለ ንፁህ ኢጣሊያዊ ዘር በያውሩ የሚቀበላቸው ሰው አያገኙም። ጣሊያኖች በጣሊያናዊ ቋንቋ የጋራ መጠሪያ ሊጠሩ ይችላሉ እንጂ የኢጣሊያዊ ዘር ግን የለም። የኢጣሊያ ዘር ጥሩ ይሁን መጥፎ ይሁን የራሳቸው ጉዳይ ነው መሬት ጠበበን እያሉ ከሚያለቅሱ ሰዎች ጋራ ጋብቻ መመሥረት የሚጓጓ ሕዝብ በዓለም ያለ አይመስለኝም። ዓለም አንድ መሆኑንን ተረድተው ሰፋፊ መሬት ካላቸው ሀገሮች እንደ አሜሪካ ብራዚል አውስትራሊያ ጋራ ተስማምተው በጋብቻም ሆነ በሌላም ለመስፈር መለመን ያለባቸው ጣሊያኖች ናቸው። ኢጣሊያ ሀገር ለመስፈር የኢጣሊያ ዜግነት የሚመኝ ሰው ከኢጣሊያኖች ጋራ በመጋባት የሚፈልግ ሰው በዓለም አይገኝም። የኢጣሊያ ዘር ከሌላ የሰው ዘር የሚበልጥ አይደለም።

## 5. የጣሊያኖች ዘር ጥላቻ በኢትዮጵያውያን ላይና በመላው ጥቁር ሕዝቦች

በአጠቃላይ እነጋገር ለመረዳት እንደሚቻለው ጣሊያኖች ዘረኞች መሆን የሚፈልጉት በሌሎች አውሮፓውያን ፊት በተለይም በእንግሊዛውያንና በፈረንሳዮች የበታችነት ስሜት ስለሚሰማቸው ነው Inferiority Complex። እነዚህ ሁለት ሀገሮች እንደኛ፣ የእኛን ፈለግ ተከትለው ለምን ዘረኞች አይሆኑም፣ አፍሪካውያንን ለምን ያስለጥናሉ፣ ጣሊያኖችና ጀርመኖች አፍሪካውያን እየፈጁና እያሰለቀቁ ለምን በአፍሪካ እንዲሰፍሩ አይፈቅዱም የሚል ቁጭት ነበራቸው። ጣሊያኖች ተጨባጭ ማስረጃ ሲያጡ የነጭ አሪያን የሰው ዘር ከጥቁር የሰው ዘር የሚበልጠው በባዮሎጂና በመንፈሳዊ ምልክቶች ነው በማለት በደፈናው ደምድመውታል። ጉዊዶ ላንድራ የተባለው ኢጣሊያዊ ፕሮፌሰር ከአስሩ የዘረኝነት መግለጫ ያወጡ ምሁራን አንዱ የኢጣሊያ ዘረኝነት መሠረተ ሀሳቦች በሚል አርእስት በዘረኛ መጽሔት ኦገስት 20, 1938 ዓ.ም. የታተመው የተለያዩ የጥንት ስእሎች በማቅረብ የሰው ዘር ልዩነቶች ይዘረዝራል። በጽሑፉ የተገለፀው የባዮሎጂ ማስረጃ ማቅረብ መሆኑ ቀርቶ የሰውን መልክ ይዘረዝራል። ካመጣቸው 9 ስእሎች የነጭና የሴም ዘር በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ የኢጣሊያ አውቶ ስእሊያን፣ ሁለት ምስል በቁጥር 1ኛ ቆንጆ ኢጣሊያዊ የተባሉ ሴቶች ስእል በማቅረብ የኢጣሊያ ሴቶች ቆንጆና ምሳሌ አቅርቧል። በቁጥር 2ኛ የታወቁ የጥንት ኢጣሊያኖች ወንዶች ሀ/ ሁሉ ገብ ምሁር ሊዮናርዶ ዳ ቬንቺ Leonardo Da Vinci ቶስካናዊ ለ/ ታዋቂው የስነ ጽሑፍ ሰው አልፌሪ Alfieri የተወለደው በፒላ የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር ያደገውና የኖረው በቶስካና ሐ/ ጋሪባልዲ Garibalgi የተወለደው በኒስ (Nice) ፈረንሳይ ለሕዝቦች ነፃነት በመታገል ከፍተኛ ዝና ያተረፈው መ/ በሊኒ Bellini በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢጣሊያዊ ሰእሊ የኢጣሊያ ዘር ወንዶች ምሳሌ ለመሆን አቅርቧል። ፕሮፌሰሩ የተነሳበት መሠረተ ዓላማ ሳይንሳዊ የሰው ዘር ዝቅና ከፍ የሚያደርገው ባዮሎጂና መንፈሳዊ መሆኑ ቀርቶ ወደ መልክ ውድድር መግባቱ ነው። 3ኛ ስእል ቁጥር የጥንት ግብጻውያን ስእል ነው። ከሴም ዘሮች ሁሉ የሰለጠኑ የጥንት ግብጻውያን በሜዲትራኒያን ከነጭ



ሰዎች ሜዲትራኒያን ሊወዳደሩ እና ሊተላተሉ እንደማይችሉ በስእሉ የሚታየው አፍንጫቸው፣ ከንፈር፣ ዓይን፣ በመመልከት ልዩነታቸው መገንዘብ ይቻላል በማለት አጥላልቶ ደምድሞታል። ሥዕል ቁጥር 4 የጥንታውያን አቢሲኒያውያን ከነጮች ከፍ ያለ ልዩነት ያሳያል ብሏል። ስዕል 5 የየመን እስራኤላዊ ሴት ሥዕል 6 የቱርኪስታን የእስራኤላዊ ወንድ ሥዕል፣ 7 እና 8 የሰሜናውያን አሪያን የነጭ ዘሮች የመልክ ምልክቶች ናቸው። ይኸውም የሴት የጥንት አማልክቶችና የወንድ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረ የስካልፕቸር አዋቂ ዶናቴሎ Donatello የተባለው ኢጣሊያናዊ በቶስካና የተሰራ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕል ነው። ሥዕል 9 የአንድ ይሁዳዊ ዘር ነው። የኢጣሊያ ዘር የሚወደበው የሰሜናዊ አሪያን ዘር ነው። የኢጣሊያ ዘር ጋብቻ የሚከለከለው ከ[illegible] ጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ሊግውያን ቅግውያን እንዲሁም እስራኤላውያን ጭምር ሲላም የሰው ዘር አሪያን ያልሆነ ሁሉ ነው ብሏል። ቀጥሎም ወደ ተነሳበት ዓላማ ወደ ባዮሎጂ በመመለስ በባዮሎጂ ሁለት የሰው ዘሮች ሲደባለቁ በአንድ ከፍተኛ ንፁህ ዘር ያለው የተስተካከለ ኑሮ ስለሚበታትነው የተራራቁ የሰው ዘሮች መዋሐድ እንደማይችሉ ያልተምራል ብለዋል። የሰው ዘር የችሎታ መጠን እየተራራቀ በመሄድ ላይ ነው የሚገኘው እየተቀራረበ አይደለም። ጥቂት ሀገሮች ናቸው እንደ ኢጣሊያ በዓለም ታሪክ ትላልቅ ሰዎች ያበረከቱ በማለት ጽሑፉን ደምድሟል።

ሊዲዮ ሞፕሪያኒ በዘረኛ መጽሔት በመጀመሪያ ዓመት ኦገስት 20 ቁጥር 1-2-3 እና 5 ጽሑፎች አቅርቧል። በኢጣሊያ ዘረኝነት ጥቁሮችን በሚመለከት ግንባር ቀደም አክስፐርት እራማጅና ቀስቃሽ ነው። ጣሊያኖች ዘረኝነታቸው በይፋ ሲመሰርቱ የዘረኝነት መግለጫ ካወጡ አስር ምሁራን በሁለተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰ ነው። በመጽሔቱ 2 ቁጥር የሰው ልጅ በሐቅምሉ ችሎታ ጭምር ደረጃ ብንለጠው የነጭ ዘር በአንደኛ ደረጃ ይገኛል የነጭ ዘር ከሌላ ዘር ጋራ ጋብቻ የሚፈቅዱ ሀገሮች ጥፋትነታቸው በጣም ከባድ ነው። የሰው ልጅ ነፍስ ሁሉ እኩል ነው ብለው የሚሰብኩ የማህበራዊ ኑሮ ሰዎች ናቸው። ከእነሱ የተማሩ አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎችም ስለ ሳይንስ በቂ ችሎታ ስለሌላቸው የሚፈጽሙት ወንጀል ከባድ ነው። ኋላ ቀር ያሉ ሕዝቦችና ነጭ ዘር ሲያገናኛቸው የማይችል የነጮች የመፍጠር ችሎታ ትምህርት እንዲቀስሙ የሚከለክሏቸው በመሐላቸው ትልቅ ጉድጓድ ተፈጥሯል። ስለዚህ እውነተኛ ሥልጣኔ ለማግኘት ምንም ተስፋ የላቸውም። በ3ኛ ቁጥር ሊፕቴምበር 5,38 ዓ.ም. ዘረኝነትና ቅኝ ግዛት በሚል አርእስት ባወጣው ጽሑፍ ነጮች ወደ አፍሪካ የመጡ አፍሪካውያንን ለማሰልጠን ነው የሚለው አባባል ከእውነት የራቀ ነው። ነጮች ወደ አፍሪካ የሄዱ የአፍሪካ ሀብት ለመበዝበዝ ነው። ነጮች ወደ አፍሪካ መፍለስ የማይቀር ነው። ዘረኞች በግልፅ ነው የሚናገሩት ነጮች መብትና ግዴታ ስላላቸው አፍሪካን እየገዙ ነው። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ነጮች ኑሮዋቸው በአፍሪካ ይመሰርታሉ። አንዳንድ የእንግሊዝና የፈረንሳይ የፓርላማ አባላት ግን ለወደፊት የአፍሪካ ዕድል ለአፍሪካውያን እንዲሆን ድምጻቸውን ሲያሰሙ ይታያሉ። ከኋላ ቀር ከሌላ ሕዝብ ተወዳድረው ወደ አፍሪካ የሚሄድ የሰው ኃይል ስለሚያንሳቸው ለጊዜያዊ መጽናናት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። አፍሪካውያን የዚህ ዓይነት መብት ማግኘት አይገባቸውም። ማንኛውም የአፍሪካ ክፍል ራሷ ችላ ለመተዳደር ችሎታ ያላት ሀገር የለም። አፍሪካ ለአፍሪካውያን ስለሚለው መፈክር ከዚህ በፊት የጻፍኩት ለመድገም አልፈልግም፣ ነገር ግን አፍሪካ ለአውሮፓውያን የሚለው መፈክር ቢቀየር የሰው ልጅ ሊጠቀምበት ይችላል ብሏል።

(1) በዘረኛው መጽሔት ቁጥር 5 ኢትዮጵያውያን በዘረኝነት አስተሳሰብ በሚል አርእስት ቺፕሪያኒ ሌላ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ የዘረኝነት ጽንሰ ሃሳብ በአንድ በኩል በአፍሪካ የሚገኙ ጉዳዮች ሲያስቀምጣቸው ለኢትዮጵያውያን ልዩ ስፍራ በመመደብ ለኢጣሊያ ጥቅም ሲባል ተገቢ ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በፊት ባለኝ ልምድ በስዚሁ ጉዳይ ወገናዊነት የሌለው አስተያየት ለመስጠት ችያለሁ፡፡ ያለኝ አዲስ ማጠቃለያ ሃሳብ ግን ኢትዮጵያን በሕክምና ለማዳን ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ወላድነቷ ማሰናከል እንደማይገባ ለማስገንዘብ ነው፡፡ በኢጣሊያ አገዛዝ የኢትዮጵያውያን የኑሮ ደረጃ እንደሚሻሻል ስለሚጠበቅ በሚቀጥሉት ጥቂት 10 ዓመታት የሕዝቧ ብዛት እጥፍ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ይህ ጉዳይ ማንሳቱ የተፈለገው በሌላ ወገን ሌሎች ሰዎች አደጋ ያመጣል ብሎ በመፍራት የዚሁ አስተሳሰብ ተቃራኒ ስለተገለጸ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ያለው የውስጥ ጉዳይ አደጋ ያመጣል ተብሎ የሚፈራ ከሆነ ይህ አደጋ የሚመጣው በዲቃሎች ክልሶች ቁጥር መበርከት ነው፡፡ ከኢንዲጂኖች ሕዝብ መበርከት አደጋ ሊመጣ አይችልም፡፡ ይኸንንም ለመረዳት የሕንጉላቸው አስተሳሰብ መመርመር ይበቃል፡፡ ምንም እንኳን ከሌላ ጥቁር አፍሪካውያን ሕንጉላቸው የበለጠ ከፍተ ቢሆንም ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ወደ ከፍተኛ ሕንጉል የሚጠይቅ ሥራ ከዚህ ቀደት አልደረሱም ለወደፊትም ሊደርሱ አይችሉም፡፡ እንደ በኢጣሊያ ሰልጣን እምነት ካደረባቸው በጥሩ ከተያዙ በኢጣሊያ ስር ከመሆን ሌላ ነገር አይመኙም፡፡ ለወደፊት ኢጣሊያ በአፍሪካ የምታደርጋቸው የማስፋፋት ጦርነቶች ከኢትዮጵያ ውጭ ከጥፏ እንደሚሰለፉ አያጠራጥርም፡፡ ይህን ለማድረግ የሚገፋፋቸው ለሚያከብሩት ሰው ያላቸው የተፈጥሮ ታማኝነትና በማንም አፍሪካዊ ተወዳዳሪ የሌለው ያላቸው የተፈጥሮ የጀግንነት መንፈስ ነው፡፡ በሌላ በኩልም ኢትዮጵያውያን በባህል ካልሆነ በቀር ከሌሎች አፍሪካውያን ዘዘር አይለዩም፡፡ ብዙ የሌም ዘር ደም የተቀላቀለባቸው ቢሆንም፣ ደምበኛ ጥቁሮች ባይሆኑም፣ በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው የሚገኘው አፍሪካዊ ዘር አንድ አካል ናቸው፡፡ ከሌላ ጥቁሮች የሚለዩበት አፍንጫቸው የተጨፈለቀና ወፍራም አይደለም፡፡ የአፍሪካ ግማሽ የሆኑ ባንቱም ከዚሁ ዓይነት አፍንጫ ያላቸው ናቸው፡፡

ቺፕሪያኒ ኢትዮጵ ያን ለኢጣሊያ ታማኝ ይሆናሉ ብሎ የተማመነበት በሺህ የሚቆጠሩ ኤርትራውያንና ሶማሊያውያን ከኢጣሊያ ጉን ተሰልፈው ተዋግተው መሞታቸውን በማየት እንዲሁም ጣሊያኖች ኢትዮጵያን እየተቆጣጠሩ በሔዱ ቁጥር ባንዳዎችን እየመሰመሉ ከጉናቸው እንዲዋጉ ያደርጓቸው እንደነበረ በማየት ይሆናል፡፡ የ1ኛ ዓመት በሚሰጡ ከምሥራቅ ኢጣሊያዊ አፍሪካ ማዕከላዊ መንግሥት የታተመ መጽሔት እንደሚገልጸው ከመጀመሪያ ዓመት ጀምሮ ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ኃይለኛ ተቃውሞ ሲያጋጥማቸው ግጭት በተደረገ ጊዜ በየቀኑ ብዙ ሰው ይገደል ነበረ፡፡ የሚማረክ ሰው አልነበረም፡፡ የተማረኩ ሁሉ ይገደሉ ነበር፣ መንደሮች ይቃጠሉ ነበር፣ ከሚገደሉት መካከል የኤርትራ ተወላጆች የጣሊያን ወታደር የነበሩ ከድተው ከአርበኞች ጋር የተቀላቀሉ ይገኙባቸው ነበረ፡፡

እንደሚታወቀው የአርበኝነት ውጊያ እየተፋፋመ ነው የሔደው እንጂ አልቀነሰም፡፡ ሰው መረሸንም እንደዚሁ ስለዚህ ቺፕሪያኒ ምን ያህል ፉት እንደነበረ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡ (2) ፒቺዮሊ Piccioli የተባለው ሌላ ኢጣሊያዊ በተጠቀሰው መጽሔት ቁጥር 5 በነጮች እና ጥቁሮች መካከል ጋብቻ መፍቀድ ሀገርን ማውደም ነው ካለ በኋላ ኢጣሊያ በሚሊዮን

(1) Lidio Cipriani : Ghi Etiopci secondo Il razzismo Difesa della razza Anno I N.5
(2) Nicloa Marchetto Difesa della razza Anno 2 No.5 gennaio 1939



የሚቆጠሩ ዜጎቿ ወደ ኢትዮጵያ ልካ ለማስፈር አቅድ አላት ብሏል፡፡ እ... ቢሆን በእንግሊዝ ሶማሊላንድ 12 ነጭ ሴቶች ሲኖሩ በአዲስ አበባ ብቻ 50... የኢጣሊያ ሴቶች ይኖራሉ ብሏል፡፡ በተጠቀሰው መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁጥር 5 ጀንዋሪ 5 ቀን 1939 ዓ.ም. ኒኮላ ማርኪቶ Nicola Marchitto የተባለው ሌላ ኢጣሊያዊ ስለ ጥቁሮችና ነጮች በአፍሪካ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ ጥቁ...ች ስራሳቸው ለመሰልጠን እንደማይችሉ የተረጋገጠ ስለሆነ ነጮች አፍሪ...ን ለማሰልጠን፣ መብትና ግዴታ አለባቸው፡፡ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች እ... አደረግንላችሁ እያሉ ጥቁሮችን እየዘበቢባቸው ይገኛሉ፡፡ ነጮች ከጥቁሮች ...ር በጋብቻ ማዋሀድ፣ ጋብቻ መፍቀድ ፈረንሳይ የምትከተለው ፖሊሲ እንግሊዝም በደቡብ አፍሪካ የምትከተለው ለነጮች ውድቀት የሚያስከትል ነው፡፡ ነጮች ብቻ ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች በእንግሊዞች ትልቅ ስህተት ምክንያት በደቡብ አፍሪካ ለጥቁሮች በመፍቀዳቸው የድሃ መደብ ሥራፊት ነጮች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ እውነተኛ የቅኝ አገዛዝ በአፍሪካ የኢጣሊያ የቅኝ አገዛዝ በንግድና በብዝበዛ የተመሰረተ የነጮች ክብር የማይጠብቅ ሳይሆን ከሌሎች ያረጀ በመውደቅ ላይ የሚገኙ የቅኝ ገዢ ሀገሮች ለየት ያለ ነው፡፡ ኢጣሊያ በጥቁሮች ላይ መላው ኤውሮጳ መፈጸም የሚገባት ተልዕኮ እንዳለ ትገልጻለች፣ ታስጠንቅቃለች፣ ትመክራለች፡፡ ከዚህ በፊት እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ቋሚ ሕዝብ በማስፈር ፋንታ ሀገሩን ብቻ በመበዝበዝ የተወሰነ የሚከተሉት የቅኝ አገዛዝ ስህተት ስለሆነ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ዜጎችዋን ማስፈር ትቀጥላለች፡፡ አዲስ አበባ ከተያዘች በሁለት ዓመት ውስጥ 28 ሺህ ጣሊያኖች በአዲስ አበባ ብቻ ይኖራሉ፡፡ 50 ዓመት ከእንግሊዝ አገዛዝ በኋላ በኬንያ የሚኖሩ ነጮች 17 ሺህ ብቻ ናቸው፡፡

(1) ማርቲኖ ማሪዮ ሞሬኖ በስኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ፖሊሲ በጥቁሮችና ነጮች የጋብቻ ሕግ መከልከል ሊጽፍ ሕጉ የተደነገገው በኢንዲጂኖች ላይ ንቀቱ ስላለ ሳይሆን ዘሩን (የኢንዲጂና ዘር) ለመጠበቅ ስለሆነ ተቃውሞ አላስከተለም፡፡ ሊያስከትልም የማይችለው እስላሞች ከሆኑ በሐይማኖታቸው ከክርስቲያኖች ጋር ጋብቻ አይፈቀድም፣ ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ነጮች ከኢትዮጵያ ሴቶች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈልጉት ጊዜያዊ ወዳጅነት እንጂ ቋሚ ጋብቻ ስላልሆነ ሕጉ የሚቃወሙት አይደለም፡፡ ከዚህ ሌላ ኢንዲጂኖች ሁሉ በኢጣሊያኖች የባሱ ዘረኞች ናቸው፡፡ አማራ ሆነ ሌላ በዘራቸው ይኩሩበታል የቺሬናይካ ዓረቦች እርስ በእርሳቸው ዘረኞች ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ሁሉም የኢጣሊያ ቅኝ ተገዢዎች በኢጣሊያ ዘረኛ ሕጎች ቅር አላላቸውም ብሏል፡፡ ሞሬኖ ከዚህ በላይ የጻፈው ሁሉ ትክክል ነው፡፡ ያኢትዮጵያ ሴቶች ጣሊያኖች በገንዘብ እያታለሏቸው ብዙ ክልሶች ተወልደዋል፡፡ አብዛኛው፣ በፍቅር የተገናኙ አይደሉም፡፡ ሁሉ ከሕጋዊ ጋብቻ ውጭ ነበሩ፡፡ ሴቶቹ ዘመዶቻቸው ከጣሊያኖች ሲወለዱ ደስ አይላቸውም ነበር፡፡ ሞሬኖ የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ጎሣዎች በነጭ ዘር የበላይነት ያምናሉ ብሎ የጻፈው ኢጣሊያኖች የተለመደ የሃሰት ወሬ ነው፡፡ ሞሬኖ አፍሪካውያን እንደ ኤውሮጳውያን መሆን የሚፈልጉ ወገኖች ያወግዛሉ ብሏል፡፡ የኢጣሊያኖች የትምህርት ዓይነት ለእስላሞች የዓረብኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ለክርስቲያኖች የግዕዝና የራሳቸው ቋንቋዎች እንዲሁም አንዳንድ የዕደ ጥበብ ሥራ የሚያስተምሯቸው ይወዳሉ ብሎ የጻፈውም ከእውነት የራቀ ነው፡፡

(1) Martino Mario Moreno Direttore generale deghi Affari Politici Del Ministero dell' Africa Italiana Politica coloniale dell' Italia Fascista Difesa della razza 2 Anoo N13

በመጽሔቱ በዚህ ዓ.ም. እና ቁጥር ሊኖ ቡሲንኮ Lino Businco[1] ያቀረና ተመሳሳይ ሃሣብ በማቅረብ የከፍተኛ ትምህርት አስፈላጊነት በማጥላላት በነጮችና በጥቁሮች መካከል የሚፈጸመው ጋብቻ በማውገዝ አንድ ረጅም ጽሑፍ አትርበዋል፡፡ ስለጋብቻ ጉዳይ ሁሉም ጣሊያኖች የሚጽፉት ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ከውጭ ዜጎች መጋባት በደስታ የሚቀበሉት አይደለም፡፡ ከልሶች የበዙባቸው ሀገሮች በሙሉ ጥፋት የተፈጸመው በነጮች ነው የሀገሩ ተወላጆች ዘራቸው እየጠፋ በመሄዱ ጉዳት እደረሰባቸው እንጂ አልተጠቀሙም፡፡ በዚሁ ምክንያት ሁሉም ወገን የሚስማማበት በመሆኑ ጋብቻ በጣሊያኖችና በአፍሪካውያን እንዳይፈጸም ከፈለጉ በወንጀለኛ መቅጫ እና በፍትሐብሔር ሕግ ማዕጅ አያስፈልጋቸውም ነበር፤ በቃል በትእዛዝ መሰጠት በቂ ነበር፡፡ አፍሪካውያን የኤሮጳውያን ትምህርት ይጠላሉ ማለት ግን በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች የተፈጠረ የሃሰት ወሬ ነው፡፡ በፈረንሳይና እንዲሁም በእንግሊዝ በአፍሪካ ቅኝ ግዛቶች የነበሩ አፍሪካውያን ያልገደብ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት ኤርትራን በ2ኛ የዓለም ጦርነት በተቆጣጠረ ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ ደምበኛ ትምህርት ቤቶች በመክፈቱ ከሕዝብ ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና አግኝቷል፡፡

[2] እንቶኒዮ ፐትሩችና ቲሲኖ Antonio Petrucci Trizzino የተባሉ ሌሎች ጣሊያኖችም በፋሌ የእንግሊዝና የፈረንሳይ የቅኝ ግዛቶች የአስተዳደር ከስረት ስለደረሰባቸው በሞት አፋፍ ይገኛሉ ብለው ጽፈዋል፡፡ ነጮች ወይም አሪያኖች የዓለም ስልጣኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማድረሳቸው በዘራቸው እርግጥ መኩራት ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን የስልጣኔ ጀማሪዎችና አባቶች አይደሉም፡፡ ብግብጽና በመካከለኛው ምሥራቅ የዓለም ስልጣኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረ ጊዜ ነጮች በስሜን እስያ ዘላኖች ነበሩ፡፡ ጣሊያኖችም ከአሪያኖች የ?ጨረሻ ደረጃ የያዙ ናቸው፡፡ ሮማ በአሁኑ ጊዜ የኢጣሊያ ዋና ከተማ ብትሆንም ጣሊያኖች የሮማውያን ልጆች ነን ሊሉ አይችሉም፡፡ ሮማ ዓለም አቀፋዊ ወሰን አልባ መንግሥት ነበር እንጂ የኢጣሊያ መንግሥት አልነበረም፡፡ ከሮማዊ ዘር ቢኖራቸውም ሮማውያን ላይ ዘራቸውን እንደዘረዘርኩት በከፊል ከኢትሩስካውያን ከትንሿ እስያ የመጡ አሪያን ያልሆኑ ዘር የተደባለቁ ስለሆኑ ንጹህ የአሪያን ዘር ነጭ ዘር አይደሉም፡፡ ጣሊያኖች የዘራቸው ክብር /Prestigio di razza/ መጠበቅ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ከጣሊያኖች የበለጠ አፍሪካውያንና ኢትዮጵያውያን የዘራቸው ክብር መጠበቅ ይችላሉ፡፡ አንድ ሕዝብ የራሱን ክብር መጠበቅ የማይችል ሌላ ሕዝብ የበታች ማድረግ አይችልም፡፡ የበላይነቱ ማሳየት አይችልም በመልክ ከሆነ እርግጥ ነጮች ከጥቁሮችም ከቢጫ ሕዝብም ሊበልጡ ይችላሉ፡፡ በስልጣኔ ግን በተለይ በአሁኑ ጊዜ የስልጣኔ መሪ ሆነው የሚገኘው የሰሜንና የምዕራብ ኤውሮጳ ሕዝቦች በዛሬ 2 ሺህ ዓመት አንዳንዶቹ ወደ ኤውሮጳ ገብተው አልሰፈሩም ነበር፡፡ ዛሬ ባርባሪያን ነበሩ የዓለም ስልጣኔ ግን የተጀመረ 5፣ 6 ሺህ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው፡፡ በዓለም ስልጣኔ አንጋፋው የግብጽ ስልጣኔ መሆኑን ፈረንጆች፤ ዘረኞች ጣሊያኖችም ጭምር የሚያውቁት ነገር ነው፡፡ የኢጣሊያ ዘረኝነት ርእስ ዘረኛ የሆነው ቺፕሪያኒ ለአፍሪካውያን የጻፈው ፀርካታ ጽሑፎች እንደመሰከረው ለግብጽ ስልጣኔ ቅድመ ሁኔታ የጣሉ አፍሪካውያን ናቸው ብሏል፡፡ ዙሉ ከሚባሉ ብደቡብ አፍሪካ ከሚገኙ ሕዝቦች ጀምሮ በመላው አፍሪካ የኢትዮጵያውያን የሚመስሉ አፍሪካውያን ይገኛሉ፡፡ ባንቱና በሩዋንዳና በሩንዲ፤ ባይላ

[1] Lino Businco : Difesa della razza Anno II N 13

[2] Antonio Petrucci ibd : Tramonto dell' Imperialismo Democratico Difea della razza Anno II N 13



በዛምቢያ፣ ባሉግ የተባሉ ከአጠገባቸው ከአሉ ባሕር ከተባሉ በመልክ በመለየታቸው ጆህሊንስን የተባለ እንግሊዛዊ ከግብጽ ሸሽተው የመጡ የግብጽ ወታደሮች ናቸው እስከማለት ደርሶ ነበር፡፡ ሰሉስና ዚንት የተባሉ እንግሊዛዊያን በ1891 ዓ.ም. በዚምባብዌ የጥንት ስልጣኔ ፍርስራሾች በሚያወጡበት ጊዜ ማካላንጋ የተባሉት ጎሳዎች በግብጽ ሐውልቶች የሚገኙ ሰዎች እንደሚመስሉ ገምቷል፡፡ በ1516 ዓ.ም. ዚምባቡዌን የጎበኙ ፖርቱጋሎች ተመሳሳይ አስተያየት ነበራቸው፡፡ ታዋቂ ዓረባዊ የታሪክ ምሁር ማሱዲ በ1000 ሺህ ዓ.ም. አካባቢ በደረሰው ታሪክ በደቡባዊ አፍሪካ የወርቅ ማዕድን የሚነግዱ ኢትዮጵያውያን የሚመስሉ ሰዎች እንደ ነበሩ ጽፏል፡፡ ሌላም ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ንጹህ ኢትዮጵያውያን ግን የሚገኙት በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ነው፡፡ ግብጻውያን ከነበራቸው ተመሳሳይ የቤት ቁሣቁስና መገልገያዎችም በመላው አፍሪካ ተገኝቷል፡፡ ይህ ሁሉ ከግብጻውያን ወደ መላው አፍሪካ የተስፋፋው የሰው ዘርና ባህል ሳይሆን ጥንታዊት የአፍሪካ ስልጣኔ ለራሱ ለግብጽ ስልጣኔ መሠረት እንደሆነው የሚያመለክት ነው፡፡ በመላው አፍሪካ ብዙ መንግሥታት ነበሩ፣ አንዳንዱ ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ ደርሰው ነበሩ፣ ሁሉም ከኢትዮጵያውያን የተዛመዱ ነበሩ፡፡ ስለዚህ የአፍሪካ ክፍለ አህጉር ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ዘረኞች ጣሊያኖች ቅኝ ገዢዎች እንደሚሉት ጥቁር ሕዝብ ለዓለም ስልጣኔ ምንም አስተዋጽኦ አላበረከተም ለማለት አይችሉም፡፡ ዘረኛ ቺፕሪያኒ ሳይቀር አስተዋጽኦ እንዳደረገ መስክሮልናል፡፡ ጥቁር ሕዝብ አስተዋጽኦ ከዚህ በፊት ባያበረክት እንኳን ዓለም ያሳለፈችው የስልጣኔ ዘመናት አጭር ስለሆነ ለወደፊት አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችል ይሆናል፡፡ ጣሊያኖች በመላው ነጭ ዘር አሪያኖች ስም መናገር አይችሉም፡፡ ከአሪያኖች መካከል የአውራ ዓይነት ጣሊያኖች የአንድ የሰው ዘር እየመረጡ ማጥፋት የሚፈልጉ ተፈጥረዋል፡፡ እንደዚሁም እንደ ኢጣሊያኖች ጥቁሮች በሙሉ የሰው ዘር አይደሉም የሚል ትምህርት ለማስተማር አይችሉም ሳይንሳዊ የባዮሎጂ አዕምሮዊ ሕግ ጥቁር ዘር ከነጭ ዘር እንዳይጋባ ይከለክላል እያሉ የሃሰት ሳይንስ እያቀረቡ በፍትሐብሔር ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በሚጥሱ ቅጣት የሚወስኑ ተፈጥረዋል፡፡ በተቃራኒ ደግሞ ሌሎች አሪያኖች ነጮች መንግሥታት የሰው ልጅ በመልክ በዘርና በቀለም ሳይለዩ የሚያከብሩ መንግሥታት መንግሥታቸው በማይናጋ ዲሞክራሲ የተገነባ በምዕራብ ኤውሮጳና በአሜሪካ ሰላሉ ጸረ ዲሞክራሲ አሪያኖች አሪያን ያልሆነ የሰው ዘር በማጥፋት የነበራቸው ዓላማ በ2ኛ ጦርነት ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡ ጣሊያኖች በእንግሊዞችና በፈረንሳዮች ከፍተኛ ቅናት ነበራቸው፡፡ በተለይ እነዚህ ሁለቱ ሀገሮች በአፍሪካ በነበራቸው ሰፋፊ የግዛቶች ይቀኑባቸው ነበር፡፡ በ2ኛ የዓለም ጦርነት ጣሊያኖች ከጀርመኖች ጉን የተሰለፉ ጦርነቱ በጀርመኖች አሸናፊነት እንዳበቃ አፍሪካ ለጀርመኖችና ለጣሊያኖች ለመከፋፈል ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራቸው ነው፡፡ ይህ ጉጉትና ምኞት የሚሆንላቸው መስሎዋቸው በእንግሊዞችና በፈረንሳዮች ያደረጉት የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍተኛ ነበር፡፡ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ያረጁ የበሰበሱ ሕዝቦች እንኳን ቅኝ ግዛት ሊይዙ ራሳቸውን ሀገራቸውም ማስተዳደር የማይችሉ አድርገው ነበር የሚገምቷቸው የነበረው፡፡ ፖርቱጋል በአፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿ የዘር ልዩነት እንደማታደርግ እየታወቀ ጣሊያኖች በፖርቱጋል ላይ የማጥላላት ዘመቻ ያላካሔዱበት ምክንያት ኃይለኞቹ ሁለቱ መንግሥታት እንግሊዝና ፈረንሳይ ካለወገዱ በኋላ ትንሿ ደካማዋ ፖርቱጋልን በቁጥጥራቸው ለማዋል የሚያስቸግራቸው ስለማይሆን ነው፡፡

[1] ቺፕሪያኒ በዘር ጥበቃ መጽሔት ቁጥር 6 ባወጣው ጽሑፍ የኢጣሊያ መንግሥት ፕሮግራም ሲያቀርብ እንደ አንድ ተራ ዜጋ መስሉ ሃሳቡን የሚያቀርብ አይመስልም። አቀራረቡ እንደ የኢጣሊያ መሪ ወይም እንደ አንድ ሚኒስትር ኃላፊነት እንደተሰጠው ነው። አፍሪካውያን ጥቁሮች የሰው ዘር ያላቸው ትክክለኛ ደረጃ የነሱ እንደሆኑ አገልጋይ ብቻ መሆናቸውን አውቀው እንዲቀመጡ ማድረግ ያስፈልጋል። አፍሪካውያን ሊሻሻሉ የማይችሉ ዝቅተኛ የሰው ዘር ናቸው። ነሱን ከአፍሪካውያን ጋር መዳቀል የኤውሮጳ ስልጣኔ የመግደል መሞከር ያህል የሚቆጠር ነው። መዳቀል ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካውያን ጋር መቀራረብም አያስፈልግም። ኤውሮጳውያን ያላቸውን ያህል ከፍተኛ ስልጣኔ ለጥቁሮች እናስተምራለን ብሎ መሞከር ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ የሞኝነት ነው። ኢትዮጵያውያን ራሳቸው ተጠቅመው ጣሊያኖችን እንዲጠቀሙ በተፈጥሮ ያላቸው አነስተኛ የማይሻሻል የማይለወጥ ችሎታቸው ተስማሚ የሚሆን ጤናቸውና የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል ያስፈልጋል። ቁጥራቸው ሲያድግ ለኢጣሊያ ስለማያሰጋት ቁጥራቸው እንዲያድግ ማበረታት ያስፈልጋል። በእነሱ ረዳትነት ኢጣሊያ መሬታቸውን ማልማት ትችላለች፣ እንደ እንግሊዞች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ መብት ሰጥተን ወደ ሀገራችን እንደማንመለስ የሚል ምኞት እንዳያድርባቸው ማድረግ ያስፈልጋል፣ ኢጣሊያ ምንጊዜም ነጻነት አትሰጣቸውም። ምክንያቱም የኤውሮጳ ስልጣኔ ሊቀበሉ የማይችሉ ዝቅተኛ ፍጡሮች ናቸው። ነሱችን እያገለገሉ ግን ሀገራቸው ሊለማ ይችላል። የፈረንሳዮች ዓይነት የእኩልነትና የመዳቀል ዘዴ ለኤውሮጳ ስልጣኔ ስድብ ነው። የኤውሮጳ ስልጣኔ ማለት ማንበብና መጻፍ ልዩ ልዩ እግዚአሐሮችን ማመስገን መቻል ብቻ አይደለም። የኤውሮጳ ስልጣኔ ማለት መርከቦችን፣ አውሮፕላኖችን፣ ሞተሮችን፣ መድፎችን፣ ፈንጂዎችን፣ ወዘተ ፈ መስራት መቻል ማለት ነው። የትኛው ቅኝ ገዢ ሀገር ናት እነዚህ ሁሉ ነገሮች ራሳቸው እንዲሰሩ የምታስተምራቸው? ይህ ካልሆነ ጉደሎ ስልጣኔ አስተምረው ራሳችሁ ትችላላችሁ ብሎ ነጻነት መስጠት ማታለል ነው። ጥቁሮች ዝቅተኛ ፍጡሮች መሆናቸውንና የኤውሮጳ ስልጣኔ ሊቀበሉ የማይችሉ ፍጡሮች መሆናቸውን ለማስረዳት ዘረኞች ጣሊያኖች ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።

ሀ/ እግዚአብሔርም እንደ ማስረጃ ቀርቧል፣

ለ/ ባዮሎጂ የሰው ዘሮች ዝቅተኛና ከፍተኛ መሆናቸውን ለመለየት የሚያስችል ብቸኛ የሳይንስ ክፍል ነው በማለት በማስረጃነት አቅርበዋል።

ሐ/ የፈረንሳይ አብዮት መፈክር እኩልነት የሚል ስለነበረ የኤውሮጳ ስልጣኔ ወደ ኋላ የቀለበሰ አብዮት ነው ብለውታል።

## ሀ/ የእግዚአብሔር ሕግ [2]

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ዕጽዋት፣ እንስሳት፣ ሰዎች፣ ያላቸው ጸባይ ሲፈጠሩ አስቀድመው በተወሰነ ሞዴል የተሰሩ ስለሆነ ድንገት አንዱ በልዩ ምክንያት ቢጠፋ በሞዴሉ መሠረት ሌላ ሊሰራ ይችላል። የሞዴሎቹ ዓይነት ብዙ ናቸው አዲሶቹም እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ፈጣሪው በመፍጠር ብቻ አልተወሰነም ፍጡሮች በሙከራ እንዲያልፉ አድርገዋል። ሙከራው አሸንፈው ያለፉ መኖር ይችላሉ ይኸውም ስጦታ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ በፈጣሪ የታሰበ እንደ ፍትሐዊ

(1) Lidio Cipriani : ibd Anno I N 6

(2) Difesa della razza Anno IV N 8 p 2



ነሻን ነው። ሰዎች በተፈጥሮ በሰውነታቸው ጥንካሬ ለውድድር አሸናፊ የሚሆኑ ከፍተኛ ዘሮች ናቸው። ፈጣሪ የሰው ዘር ከሌላ ፍጡር የተለዩ እንዳደረገ ሁሉ በሰው ዘር መሐልም ምርጥ የሆኑ ለይቶ ፈጥሯል። ልዩ ልዩ የሰው ዘሮች እርስ በእርሳቸው እንዳይቀላቀሉ በመፈለግ መራባታቸው እስ ችጋሪ በማድረግ መሰናክል ፈጥሯል። ፈጣሪ የሰው ዘሮች የራሳቸው ዘር በውስጣቸው ስሜት እንዲኖራቸው አድርገዋል። ይህ ስሜት በትምህርት የሚገኝ ሳይሆን በውርስ የሚመጣ ነው። ደረጃ የሚጠብቅ ሃይማኖታዊ ነው የተፈጥሮ ሕግ እንዳይቀለበስ የእስከፊነቱ ስሜት ነው፣ የሚያስከትለውም ጥፋት በተለይ ለቁጥፈዎች ለግለሰቦች ሳይሆን ለመጭው ዘራቸው የሚተላለፍ ስለሆነ በግለሰቦች ላይ የጭንቀት የሸብር፣ ስሜት ፈጥሯል። ጥፋቱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለመጭው ትውልድ መሆኑን ማንኛውም ሰው የዚህ አድራጎት የሚሰማው ስሜት አለ። እነዚህ ስሜቶች በአንድ ዘር የሚገኙ ሃይማኖታዊ ስሜቶች ናቸው። በመጀመሪያ በአንድ ግለሰብ ይመሠረታሉ። ከሱም ወደ ሕብረተሰብና ወደ መንግሥት ያልፋሉ። ሕብረተሰብና መንግሥት የግለሰቡ ስሜት የማይደግፉ ወደ ውድቀታቸው የሚያመሩ ናቸው። ይህ የዘር ስሜት ጉልታዊና ሃይማኖታዊ መሆኑ ከታወቀ ሳይገለጽም ደጋፊ ቢሆንም ከስሜቱ በ2ኛ ደረጃ የሚመጣ ነው። ይኸንን ሕግ የመጣስ ከፍተኛ ወንጀል ነው፣ ሰውን ከመግደል የባሰ ወንጀል ነው፣ ምክንያቱም አንድ ሰው መግደል ግለሰቡ ብቻ ነው የተጐዳው ተከታይ ዘሩ በሙሉ አይመረዝም አይወድምም። ልዩ ልዩ የሰው ዘሮች በጋብቻ እንዳይቀላቀሉ ሕጐች ወጥተዋል። ነገር ግን በቂ ቅስቀሳ አልተደረገም፣ ሕብረተሰቡና መንግሥት ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። ወንጀሉ በሰው ዘር በሙሉ የእግዚአብሔር በደረጃ በፈጠራቸው በሕይወታቸው መሠረታዊ ነገሮች የተሰነዘረ ወንጀል ነው። ሕዝቡ ስሜት እንዲኖረውና ደጋፊ እንዲሆን ቅስቀሳ ያስፈልጋል። በክልስንት በዲቃላነት ቸልተኝነት ግደየለሽነት ማሳየት የአንዳንድ ሕዝቦች የውድቀታቸው የመጀመሪያ የማያጠራጥር ምልክት ነው። አንድ በከፍተኛ ደረጃ ለሰለጠነ ሕዝብ ከፍተኛ ዘር ሳይጋፋና ሳይቃወም ከአንድ ዝቅተኛ የሰው ዘር በጋብቻ ሲቀላቀል ቅር ሳይለው ሲቀበለን በመስጠት ያለምንም ቅሬታም በሕዝብ አገልግሎት ሰጭ ቦታዎችም ሲደባለቅ ከማየት የሚያሳዝን ሌላ ነገር የለም። የሚያሳዝን ትርኢት በዛሬዋ ፈረንሳይ ምሳሌ የሚታየው ተመልካች መሆን ነው። ከግለሰብ ሥር ሰዶ የተመሰረተ ክልስነት የሚከለክል የዘርም ስሜትም ረቂቅ መንፈሳዊ መሠረት እንዳለው ያስገነዝባል። ስለሆነም የሰው ዘሮች መደባለቅ አንድ ተራ ወንጀል ብቻ ሳይሆን ከሁሉ የባሰ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው።

ለኢጣሊያ ዘረኞች ተቃውሞችን በአጠቃላይ ቢሆንም ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው ጽሑፍ በሚመለከት በሰው የማይደረግ ቢሆንም በእጽዋት ላይ ዘር ማዳቀል የተሻለ ዘር ለማግኘት ምርምር የተደረጉ ጥሩ ውጤት እያመጡ ናቸው ምሳሌ 1/ በኢክታር በቆሎ ፣ስንዴ፣ ወዘተ የሚመረተው ዱር ከሚመረተው የበለጠ ለማምረት። 2/ ድርቅ መቋቋም የሚችሉ እጽዋት 3/ የዕጽዋት በሽታ መቋቋም የሚችሉ ወዘተ በእንስሳትም ብዙ ወተት መስጠት የሚችሉ ላሞች ብዙ እንቁላል ለመፈልፈል የሚችሉ ዶሮዎች በማዳቀል የተገኘ ነው። ጣሊያኖች በእግዚአብሔር ስም ዘረኝነት መፈለጋቸው የዘረኝነታቸው ሌላ ማስረጃ ከማሳየቱም በቀር ማንም ሰው ሊያሳምኑ አይችሉም።

## ለ/ ባዮሎጂ ማስረጃ ለኢጣሊያ ዘረኝነት፣

በኢጣሊያ ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች የወጡ የዘረኝነት መግለጫ ከ10 ነጥቦች 3ኛው የዘረኝነት ጽንሰ ሃሳብ ባዮሎጂ ነው ብለው ደንግጓል፣ስለዚሁ

ጉዳይ የዘር ጥበቃ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 12 ሊዲዮ ቺፕሪያኒ[1] የጻፈውን እንመለከታለን፡፡ የሰው ልጆች በባዮሎጂ የተለያዩ ለሁለት ዘሮች ሊከፈሉ ይችላሉ፤ ከፍተኛ ዘሮች በተፈጥሮ የታደሉ ከፍተኛ የሐንጐል ችሎታ ያላቸው የዘራቸው ችሎታ እንዳይቀንስ ከዝቅተኛ የሰው ልጅ ዘሮች ሳይደባለቁ እንዲኖሩ የሚያስፈልግ፣ ዝቅተኛ ዘሮች እንዳይቀንስ ከዝቅተኛ የሰው ልጅ ዘሮች ሳይደባለቁ እንዲኖሩ የሚያስፈልግ፣ ዝቅተኛ ዘሮች ጥቁሮች ከሐንጐል የሚመነጩ ሥራዎችን ለማከናወን የማይችሉ ሊያሻሽሉት የማይችሉ ጉደሎ ፍጥረቶች ናቸው፡፡ ስለሐንጐል ችሎታ በምናወሳበት ጊዜ በተለያዩ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ማወዳደር ይቻላል፡፡ 1/ የአንድ ልጅ የከፍተኛ ዘር ሐንጐል እኖቂ ከሆነ ዝቅተኛ ዘር እኩል ከሆኑ የአዋቂው ሐንጐል ዝቅተኛ ነው ይባላል ምክንያቱም የልጁ ችሎታ ጊዜያዊ ነው የአዋቂው ግን ቋሚ ነው፡፡ 2/ የሴት ሐንጐል ከወንድ ሐንጐል ሊወዳደር እኩል ከሆኑ ወንዱ ዝቅተኛ ሐንጐል አለው ሊያሰኘው ይችላል፡፡ የሴት ሐንጐል ዝቅተኛነት የታወቀ ነው በተለይ ባልሰለጠኑ ሕዝቦች የሴቶች ሐንጐል ላይ ደምበኛ ጉድለት ይታያል፣ ለምሳሌ በአፍሪካ አንዳንድ የሴቶች ሐንጐል የሰው ልጅ መሆኑ ቀርቶ የእንስሳት ፀባይ አለው፡፡ 3/ የአንድ ጥቁር ሰው ሐንጐል በአንድ ነጭ ከሆነ ጎደሎ ዝቅተኛ ሰው አንጐል ሊወዳደሩ እኩል ከሆኑ ጥቁሩ ጎደሎ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የሰው ልጆች ችሎታ ሊመዘን የሚችለው በሐንጎል ሴሎች ብቻ ነበረ፣ ቺፕሪያኒ ግን ከዚህ በላይ በተጠቀሱ ልዩነቶች ሊያስረዱ የማይችሉ ምሳሌዎች አልፎታል፡፡

ቺፕሪያኒ ሰውና እንስሳት እንኳን የማይለያዩባቸው 1/ በደም ዝውውር 2/ በምግብ መዋሐድ 3/ በቆሻሻ ማስወገድ 4/ በመውለድ 5/ በሕመም ስሜት 6/ በላብ እጢዎች 7/በውስጣዊ ቆሻሻ አስወጋጅ እጢዎች 8/ በእድገት 9/ በጣፍያ 10/ በእንቅርት 11/በጉበት ክብደት 12/ በትርፍ አንጀት ማነስና መብዛት 13/ በቀጭን አንጀት ርዝመት 14/ በቆዳ ቀለም 15/ በፀጉር ዓይነት 16/ በጭንቅላት አሰራር 17/ በደም ውስጥ የሚገኙ ንጥረ ነገሮች 18/ ለበሽታ የመከላከል ችሎታ 19/ በካንሰር 20/ በውርዴ 21/ በስኳር በሽታ ማነስና መብዛት ጥቁሮችና ነጮች ይለያያሉ ብሏል፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ ማስረጃ የሚሆን ነጥብ የለም፣ተራ የኢጣሊያ ዘረኞች ፕሮፓጋንዳ ከመሆን አያልፉም፡፡

## ሐ/ የፈረንሳይ አብዮት፣

የሰው ልጅ እኩልነት አንግቦ የተነሳ የፈረንሳይ አብዮት ለኢጣሊያ ዘረኝነት ጠንቅ ስለሆነ ጣሊያኖች በይፋ ያጥላሉት ነበር፡፡ ፈረንሳዮች አብዮት ሲያካሒዱ እኩልነት ብለው የተነሳ በሀገራቸው ውስጥ ጉዳይ በክብርቴውና በተራው ሕዝብ የነበረው ልዩነት ለማስወገድ ነበረ፣ ከሌላ የሰው ዘር ለማወዳደር አልነበረም፤ አሁን ጣሊያኖች ከሚያራምዱት የዘረኝነት ዓላማ ጋራ አይገናኝም፡፡[2] የፈረንሳይ አብዮት የኤውሮጳ ስልጣኔ መቀልበስ የመጀመሪያ ምዕራፍ የሚል አርዕስት ረጅም ጽሑፍ ሲያቀርብ ሞንቴፍሬዲኒ Montefredini ዋቢ በማድረግ ነው ሞንተፍሬዲኒ Montefredini የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ በ1877 ዓ.ም ባወጣው ስለ ዲሳንቲስ Desantis መጽሐፍ ባቀረበው የማስታወቂያ መቅድም የፈረንሳይ አብዮት አንዳንድ የዋሆች ሰዎች እንደሚሉት የሕዝቦች ዳግም መወለድ የሚያበስር አይደለም፤ የኤውሮጳ ስልጣኔ የቀለበሰ የመጀመሪያ

---

[1] Lidio Cipriani : Il concetto di razza puramente biologico Anno V N 12

[2] L.d. La Rivoluzione Francese : Principio di regresso ibd Anno IV N12



ምዕራፍ ነው ብሎታል፣ የፈረንሳይ የመውደም ምልክት ነው፡፡ ፈረንሳይ ከእንግዲህ ለዘለዓለም ጥታለች ብሎ ጽፎ ነበረ፡፡ ግለሰቡ የፈረንሳይ አብዮት ተቃዋሚ ሲሆን ጀርመኖችን የሚወድ ደጋፊ ነበር፡፡ ሞንቴፍሬዲኒ Montefredini ስለ De Santis አድናቆቱም ሲጽፍ ጀርመን መሆን ይገባዋል፣በስህተት ነው በኢጣሊያ የተወለደው ብሎ መጻፉ የኢጣሊያ ዘረኞች ከጀርመኖች ዘረኞች ጋራ ወዳጅነታቸው አዲስ እንዳልሆነ ከድሮ ጀምሮ የነበረ መሆኑ ማስረጃ ሆኖላቸዋል፡፡ ከ12ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይኖሩ የነበሩ ጣሊያኖች ፀሐፊዎች እስከ ዘመናችን ፀረ - ፈረንሳይ ሕዝብና መንግሥት የሆኑት እየጠቀሰ አውጥቷል፡፡ በተለይ ዳንቴ Dante የኢጣሊያ ቋንቋ አባት ፈረንሳዮች ለራሳቸው ሀገር ለነገሥቶቻቸው የበላይነት ለማግኘት ብቻ የሚያስቡ ሮማ የሊቀ ጳጳሱ መቀመጫ መሆኑዋን ተቀብለው የማያከብሩ፣ ሮማ የንግሥተ ነገሥታት፣ ድሮ በሮማውያን ጊዜ በኋላም በጀርመኖች ጊዜ፣ ቅዱስ የሮማዊ ንጉሠ ነገሥት Holy Roman Empire መቀመጫ መሆኗን የማያከብሩ እያለ ወቀሳ በፈረንሳዮች ላይ ያሰማ ነበር፣ ምክንያቱም ፈረንሳዮች ጳጳሱን ወደ አቪኞን እንዲቀመጥ በማድረጋቸው ጳጳሱን ያዋርዱ ነበረ፣ ሮማን መቃወም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቃወም ማለት ነው ወዘተ የሚል አስተሳሰብ ነበረው፡፡ ፔትራርካም Petrarca ሮማ የከተሞች ንግሥት የንጉሠ ነገሥቱ መቀመጫ በማለቱ ተጠቅሷል፡፡

ማኪያቬሊ Macchiavelli አኒባል ካሮ Annibal Caro ጎንዛጋ Gonzaga አሪዮስቶ Ariosto ታሶ ታሶኒ Tasso Tassoni ቪኮ Vico ሌሎችም የፀረ ፈረንሳይ የሆኑት ጠቅሷል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢጣሊያ ከፈረንሳይ ጋራ የምትወዳደር ሀገር አልነበረችም፡፡ ዳንቴና የቀድሞ የኢጣሊያ ፀሐፊዎች ለኢጣሊያ መንግሥት ተሟጋቾች አልነበሩም፡፡ እነሱ እንደ ንጉሣቸው የሚያውቁት የጀርመኖች ቅዱስ ንጉሠ ነገሥት ነዘረ፡፡ የኢጣሊያ ፋሽስቶችም ወዳጅነታቸው ከጀርመኖች ጋራ ለማጥበቅ ወዳጅነታቸው ከጥንት ጀምሮ የኖረ ነው ለማለት እንደ ማስረጃ ተጠቅመውበታል፡፡ የፈረንሳይ አብዮት የእኩልነት መፈክር ለማጥላላት በሌላ ምክንያት ፈረንሳዮችን የተቃወሙ እነ ዳንቴ Dante በመጥቀስ የዘረኝነት ዓላማቸውን ለማራመድ በማስረጃ ተጠቅመውበታል፡፡

እንኳን ጣሊያኖች ጀርመኖችም ደንበኛ ብሔራዊ መንግሥት አልነበራቸውም፡፡ ጀርመኖች ደንበኛ መንግሥት ለማቋቋም የበቁት በቀዳማዊ ናፖሊዮን ጊዜ ነው፣ እንድነታቸው ከናፖሊዮን ባገኙት የአስተዳደር ለውጥ መሠረት በ1803 ዓ.ም. ናፖሊዮን ቀዳማዊ በ360 መንግሥታት ተከፋፍላ የነበረች ጀርመን በ82 እንድትከፋፈል አደረጋት፡፡ በ1806 ዓ.ም. ናፖሊዮን በደቡብ ምዕራብ ጀርመን የኮንፌዲሬሽን በመፍጠሩ ሌሎች የጀርመን መንግሥታት በመቀያየራቸው 1000 ዓመት ገደማ ጀርመን እንደ ዛሬ በአብሪት የተወጠረች ሀገር ሳትሆን ባርባሪያን እንደመሆኗ መጠን በራሷ ስም ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መቋቋም እንደማትችል ብላ በማመን ቅዱስ ሮማዊ ንጉሠ ነገሥት ተብላ ትጠራ የነበረች የጀርመን መንግሥት በናፖሊዮን ቀዳማዊ ንቃት በማግኘቷ የሮማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚል ስም ሕልውናዋ አብቅቶ በጀርመን መንግሥት ስም ብቻ ተተካ፡፡

የፈረንሳይ አብዮት ባስተጋባው አዲስ መንፈስና በናፖሊዮን ቀዳማዊ ብርታት አንድነቷን ያገኘችው ጀርመን በ1870 ዓ.ም. ፈረንሳይን ወራ ልታሸንፍ ችላለች፡፡ ጣሊያንም አንድነቷን ያገኘችው በ1859 በፈረንሳይ እርዳታ ነው፡፡ ናፖሊዮን 3ኛ ከሳርዲኒያ መንግሥት ጋራ ምስጢራዊ ስምምነት አድርጎ ሁለቱ መንግሥታት ሳርዲኒያና ፈረንሳይ በአውስትሪያ ጦርነት ከፍተው ባገኙት ድል የኢጣሊያ አንድነት ሊፈጠር ችሏል፡፡ አውስትሪያ 150,000 ወታደር አሰልፋ ነበር፣ሳርዲኒያ 85 ሺህ፣ በናፖሊዮን 3ኛ የሚመሩ የፈረንሳይ ወታደሮች ብዛት 140,000 ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የኢጣሊያ አንድነት

የአውሮፓ መንግሥታት የካቡር ቅዠት ነው ብሎ ያገሙቱት የነበረ በፈረንሳይ እርዳታ እውን ሊሆን ችሏል፡፡ ኢጣሊያና ጀርመን አንድነታቸውን ካገኙ 100 ዓመት ሳይሞላቸው ዓለምን በሙሉ ለመግዛት ሲመኙ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች መንግሥት ከቋቋሙ 1000 ዓመት የሆናቸው በእብሪት በሰው ዘር ጥላቻን እየፈጠሩ ዓለምን ለመግዛት አልተመኙም፡፡ ኢጣሊያኖችም ሆኑ ጀርመኖች አንድነታቸው የተገኘው ሳያስቡት በድንገት ነው፡፡ በሚጠሉት በፈረንሳይ አብዮት ብርታት ነው፡፡ ጀርመኖች ባርማውያን ያልተዘሁ ከሮማውያን ጋራ በዘርም በቋንቋም የማይገናኙ መንግሥታቸው ሮማዊ ብለው መጥራታቸው የሚያሳፍራቸው ነበር፤ ከዚህ የተላቀቁም በፈረንሳዮች አብዮት ስለሆነ ማመስገን ይገባቸው ነበረ፡፡ በፈረንሳይ አብዮት በአውሮፓ ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች ጣሊያኖችና ጀርመኖች ሲሆኑ በአሁኑ ዘመን ያገኙትን ጥቅም በመካድ የአብዮቱ ዋናዎች ተቃዋሚዎች ሆነዋል፡፡

በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ጣሊያኖችና ጀርመኖች ለሽንፈት በተቃረቡበት ወቅት በዘር ጥበቃ መጽሔት ጉዊዶ ላንድራ እንዳቀረበው ጽሑፍ ጣሊያኖች በዘረኝነታቸው ከጦርነቱ በኋላም እንደሚቀጥሉ በመጻፉ ቁጭት እንዳደረባቸው ያስገነዝባል፡፡ የኢጣሊያ ዘረኝነት ሊጠፋ የሚችለው ኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ጥያቄዋ ለሁል ጊዜ ሲታቆም ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ወቅት ግን ምንም ጊዜም ሊመጣ አይችልም፡ ስለ ይሁዶች ሲፅፍም በኢጣሊያ ሀገር እስራኤላውያን እስከሉ ድረስ፤ በዓለም ያሉት ይሁዶች በሙሉ ተሰብስበው ወደ አንድ የሚሰጣቸው ሀገር እስኪሔዱ ድረስ ፀረ ይሁዶች ትግል ይቀጥላል፡፡ የት ይሁን እዚሲ የእስራኤላውያን ሀገር ማዳጋስካር፤ አማዞንያ ሳይቤሪያ ወዘተ... ብውጥ የለውም፤ ኢትዮጵያም እንድትሰጣቸው ሃሳብ ቀርቦ ነበር፡፡ አሁን እስራኤል ሀገር የምትገኘው ከሜዲቴራኒያን አካባቢ ግን ሜዲቴራኒያን ባሕር የኢጣሊያ ባሕር እንደመሆኑ መጠን መሬት እንዳሰባቸው ብሎ ጽፏል፡፡

## 6 የጣሊያኖች ዘረኝነት በፈረንሣዮች ላይ

ጣሊያኖች በፈረንሳዮች ላይ የሕዝባቸው ብዛት እየቀነሰ በመሄድ ላይ ያለው፤ ራስ ወዳዶች፤ ልጅ መውለድ የማይወዱ፤ በመጥፋት ላይ ያሉ ዘር፤ የአውሮፓ ስልጣኔ ወደ ኋላ ያስቀሩ፤ በ1789 ዓ.ም. አብዮታቸው የእኩልነት መርሆዎች የሚመሩ በማለት ለማቸውን ያጠፏቸው ነበር፡፡ በአንድ ወቅት "ዱቼ" ሙሶሊኒ ፈረንሳዮችን በማስመልከት ያደረገው ንግግር እንዲህ ይላል "ጠንካራ ሕዝቦች ማለት ወላጅ ሕዝቦች ናቸው፤ በተቃራኒም መሐን ሕዝቦች ደካማ ሕዝቦች ናቸው፤ እነዚህ ደካማ ሕዝቦች የሽማግሌዎች ክምችት በሚሆንበት ጊዜ አንድ ወጣት ጌታ ሲመጣባቸው ምንም ሳይተነፍሱ ይወድማሉ" ፈረንሳዮች ጦርነት ሲነሳ በራሳቸው ዜጋ ሀገራቸውን ለመከላከል ስለማይችሉ የሚተማመኑ በሴኔጋላውያን ቅኝ ግዛታቸውና በእንግሊዞች ነው፡፡

(1) የኢጣሊያ ሕዝብ ብዛት እየጨመረ ስለሚሄድ በ1938 ዓ.ም. ከነበረው 43 ሚሊዮን 979,000 በሃምሳ ዓመት 72 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተተንብየዋል፡፡የፈረንሳይ ሕዝብ ብዛት ግን እየቀነሰ በመሄድ ላይ ስለሚገኝ በ1938 ዓ.ም. ከነበረው 41,450,000 በ50 ዓመት ወደ 28 ሚሊዮን ዝቅ እንደሚል ተተንብዮዋል፡፡ (2) በሩቅ ምሥራቅ የጦር ጓድ የነበረው ጃፓን በ1938 ዓ.ም. ከነበረው 73 ሚሊዮን ሕዝብ ብዛት በ1970 ዓ.ም. 100 ሚሊዮን

(1) Difesa della razza Anno II N 11 Anno II N 12 p 1
(2) Difesa della razza Anno II N 11 p 34



እንደሚደርስ ተተንብዮዋል፡፡ ከ50 ዓመት በኋላ የተገኘው ውጤት ግን ጣሊያኖች እንደተመኙት አልሆነም በ1986 ዓ.ም. የኢጣሊያ ሕዝብ ብዛት 57,221,000 ነበረ፤ የፈረንሳይ ሕዝብ ብዛትም 55,392,000 ስለነበረ እድገታቸው በእኩል ደረጃ እንደነበረ ያሳያል፡፡ የጦር ጓድ የነበረው የጃፓን ሕዝብ ብዛት ግን 121,492,000 ደርሶ ነበር፡፡ በትንቢያው መሠረት ትክክለኛ የመጣ የጃፓን ሕዝብ ብዛት ብቻ ነው፡፡ የ1789 የፈረንሳይ አብዮት በተለይ ለኢጣሊያ መጥፎ ዕድል ያመጣ ዓመት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ አብዮት የሁሉም ሀገር የቡርዥዋ ክፍሉ መደብ ለመሳብ በመቻልዋ በአውሮፓ የፈረንሳይ የበላይነት እንዲንፀባረቅ ረድቶዋል፡፡ በመላው ዓለም የፖለቲካ ወሰን የማይገድበው ለፈረንሳይ ድጋፉ አፍርቶዋል፡፡ በዚሁ የማይታይ የፈረንሳይ አስተሳሰብ ወሰን ክልል ውስጥም ኢጣሊያ ከ1876 እስከ 1914 ተጠቃልላ ነበር፡፡ እንደ ኢጣሊያ የስልጣኔ ምንጭ የሆነው ሀገር እንደገና ወደ ስልጣኔ ደረጃ ዝቅ አድርገዋታል፡፡ የፈረንሳይ አብዮት ፅንሰ ሐሳቦችና ቡርዥዋ የግልና የብሔራዊ ኢጣሊያዊ ስሜት በዜና ጥበብ፡ በባሕል፤ በሥነ ጽሑፍ፤ በግጥም፤ በኢኮኖሚ እንዲጠፋና እንዲታፈን አድርጓል፡፡ የ1798 ዓመት ኢጣሊያ ለፈረንሳይ ተገዥነት የሆነችበት ያበሰረ ዓመት ነው፡፡ ኢጣሊያ እንደ ሞተች ያደረጋት ዓመት ነው፡፡ በፈረንሳይ ብሔራዊ አስተሳሰብ እንድትመራ ያደረገ ዓመት ነው፡፡ ይህ የፈረንሳይ አብዮታዊ አስተሳሰብ በኢጣሊያ ስልጣኔ ጫንቃ ላይ ወጥቶ ለመመረዝ ችሏል፡፡ ዓለም አቀፋዊነት ያላቸው ይመስሉ የነበሩ የፈረንሳይ አብዮት ፅንሰ ሐሳቦች ከአስተሳሰብ አልፎ በተግባር እንዲውሉ አድርገዋል፡፡ ለኢጣሊያ አዲስ ዘመን መቁጠር የተጀመረው ከዳንተ መውለድ 1265 ዓ.ም. ጀምሮ ነው፤ ያለንበት ዘመንም መቁጠር የሚጀመረው ፋሽዝም ከተመሰረተበት መሆን አለበት፡፡ ከ1789 ዓ.ም. የፈረንሳይ አብዮት የአንድ ዘመን መቁጠር ከመጀመር ይልቅ በአሌሳንድሮ ቮልታ Alessandro Volta 1745-1827 የኤሌክትሪክ ባትሪ የፈለሰፈ የዘመን መቁጠሪያ መጠቀም በተገባ ነበር፡፡ ጣሊያኖች ከጀርመኖች በቀር ከሌላ ሕዝብ ጋራ ዝምድና እንዲኖራቸው አይወዱም ነበረ፡፡ ጉዊዶ ላንድራ (1) የጣሊያኖችና ፈረንሳዮች ሁለት ዘሮችና ሁለት ስልጣኔዎች በሚል አርእስት ፈረንሳዮችና ጣሊያኖች በመጥቀስ አንድ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ የፈረንሳዮች ዘር በይበልጥ በሜዲቴራኒያን በጀርመኖች በሰሜን በቸልቲኮች በሁሉም ቦታ የሚገኙ የተገነባ መሆኑን እና ከላቲን ዘር ግን ከቋንቋ በቀር ዘር እንደሌላቸው የሚል "ሆሞግማ" በፈረንሳዮች ፀሐፊዎች የቀረበ በዋቢነት አቅርቦ ጣሊያኖች በይበልጥ እንደሚቀበሉት ገልፀዋል፡፡ ፈረንሳዮች የተጠሉት አብዮታቸው እኩልነት የሚለው መፈክርና በቅኝ ግዛታቸው የዘር ልዩነት ስለማያደርጉ ነው፡፡ ጣሊያኖች ፈረንሳዮች ሁለት ዘሮች ሁለት ስልጣኔዎች ብሎ ላንድራ ያቀረበው ጽሑፍ ሐቀኝነቱ የሚያንፀባርቅ በአንቶኒዮ ፔትሩቺ Antonio Petrucci(2) ጥቁርና ነጭ በሚለው አርእስት አንድ ጽሑፍ ቀርቧል፡፡ ጽሑፉ ዌስተርማን Westerman የተባለው ፈረንሳዊ ስለ አፍሪካውያን የሰነዘረው አስተያየት መልስ ለመስጠት ነበር፡፡ ፈረንሳዊው አስተያየቱን ሲያጠቃልል ትምህርት ቤት መከፈትም ሆነ ሌሎች በጎ ተግባራት ከነጮች የሚሰጡ አፍሪካውያንን ለማሻሻል ወሳኝነት የላቸውም ራሱ አፍሪካዊ ዕድሉን በራሱ መወሰን አለበት፤ የወደፊት የአፍሪካ ዕድል በአፍሪካውያን እንጂ በነጮች ፍላጎት መወሰን የለበትም፡፡ ይህ በተግባር በሚውልበት ጊዜ ጥቅሙ ለነጮቹም ለጥቁሩም ይሆናል፡፡ ጣሊያኖች ዘረኞች እንደሚሉት ኤውሮጳውያን ነጮች በመሐላቸው እርስ በእርሳቸው በዘር በኩል የጎላ ልዩነት ያለ

(1) Guido Landra : Italiani e Francesi due razze : Due civilta' Difesa della razza Anno I N5
(2) Antonio Petrucci : Negri e Bianchi : Difesa della razza Anno I N 2

አይመስለኝም ሁሉም የአሪያን ዘሮች ናቸው፡፡ ሆኖም ኢጣሊያና ፈረንሳይ ሁለት ዘሮችና ሁለት ሥልጣኔዎች ሊባሉ የሚችሉ በባሕልና በስልጣኔ አስተሳሰብ ባላቸው ልዩነት ብቻ ነው፡፡

ኢጣሊያዊ ፔትሩቺ ለዚሁ ጽሑፍ መልስ ሲሰጥ የዌስተርማን ሐሳብ ከአንድ ታዋቂነት ያለው ሳይንቲስት የሚጠበቅ አስተሳሰብ አይደለም በማለት እናንቆታል፡፡ በደቡብ አፍሪካ በተሰበሰቡ ጥቁሮች አንድ አይሁኔቲስት ቄስ ሰባኪ በአንድ እሁድ ያደረገው ንግግር የሚመስል ነው ብሏል፡፡ ጥቁሮች ዝቅተኛ የሰው ፍጡር ለመሆናቸው ሐንጎላቸው ፔትሩቺ እንደ ሌሎች ጣሊያኖች ፀሐፊዎች የአንድ የነጭ የሕፃን ሐንጎል ነው ብሎ ሲያምን የፈረንሳዊው አስተያየት የተቃራኒ ነው፡፡ ስለ ትምህርት ጉዳይ ለአፍሪካውያን መስጠት ፈረንሳዊው ዌስተርማን Westerman ሲደግፈው ኢጣሊያው ፔትሩቺ ግን ነጮች በብዙ መቶ ዓመታት ያገኙት እውቀት ጥቁሮች ለጥቂት ዓመታት ተመርው ሊያዋህዱ አይችሉም የጥቁሮች ችሎታ ላይ ላዩን ብቻ ነው፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱት እውቀት ለማግኘት ሳይሆን ትንሽ ተምረው ሥራ ለማግኘት ነው፤ በቃላቸው ለመድገም ጥሩ ችሎታም ሲኖራቸው ይችላል የኤውሮጳ ትምህርት በጥልቀት ለመማር ግን አይችሉም ብሏል፡፡ ፈረንሳዊው በየመንደሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መከፈት አለባቸው በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያልተከፈቱ በጥቁሮች ሐንጎል ማነስ ሳይሆን ያስተማሪ ማነስ ጉዳይ ነው ብሏል፡፡ ነጮችና ጥቁሮች በኢኮኖሚ የሚጋጩበት ፔትሩቺ አፍሪካውያን ከውጭ የመጡ እስያውያንና ኤውሮጳውያን ካላስለጠኑዋቸው በስተቀር ራሳቸው የእርሻ ስራ እንኳን መሥራት አይችሉም፡፡ ልዩ ችሎታ የሚጠይቁ ስራዎች ጥቁሮች እንዲማሩ አያስፈልግም ምክንያቱም ነጮች ስራ ፈት ይሆናሉ እንደ ደቡብ አፍሪካ ደሐ ነጮች ሥራ ፈት ይበረክታሉ፡፡ ስለ ክልሶች ጉዳይ ፈረንሳዊው ሳይጠቅሰው አልፈዋል፡፡ ፈረንሳዮ በቀኝ ግዛቶች የኑሮ ደረጃ ስራዎች በነጮች ብቻ ማስራት የማይቻል ነው የአፍሪካውያን ካልተሻሻለ ነጮች ደረጃቸው ዝቅ እያለ መሔዱ አይቀርም ብሏል፡፡

ሌላ ኢጣሲያዊ በፈረንሳይ ቅኝ ግዛቷ አስተዳደር የሚወቅስ ቪንቸንሶ ቦናሲስ Vincenzo Bonassisi ነው፡፡ ዓለም ዓቀፋዊነትና ዘረኝነት በሚል አርእስት ባቀረበው ጽሑፍ በዘረኝነት ፈረንሳይ ያላት አቋም በመቃወም ነው፤ ፈረንሳይ የዘር አንድነት በሜዲቴራኒያን የለም ትላለች፡፡ ባንፃሩም ብዙ ዘሮች በሜዲቴራኒያን በታሪክ፣ በአቀማመጥ፣ በሥልጣኔ ማእከል የሆነው የአሪያን ዘር ሴማውያን ጋራ እንዲሁም የሰሜን አፍሪካ ዜጎች ጋራ የሚያጠቃልል አንድነት መፈጠር እንዳለበት ታምናለች፡፡ ቦናሲሲ ግን በአሪያኖች ከተገዙ ከሰሜን አፍሪካ ሕዝቦች አንድ ላይ አንድነት መፍጠር የማይሆን ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህ ዓለማቀፋዊነት አንድነት አደገኛ ነው፣ ራሱም የንፁህ ዘር ዘረኝነት ሳይሆን ዘር በማዳቀል የተመሰረተ ዘረኝነት ነው፡፡ እሱም ቢሆን በዓለም ታሪክ የበላይነት በመቀዳጀት ነው፣ ፀረ ፋሽስት ዩኒቨርስቲ ዓለም አቀፋዊነት ነው፡፡ ፈረንሳይ ማእከል ያደረገ በእኩልነት የተመሠረተ ወንጀለኛ አስተሳሰብ ነው፡፡ በሳይንስ መሠረታዊ አቋም የያዘውም የብዙ ዘሮች በጋብቻ መቀላቀል ጥንካሬ ይሰጣል እንጂ አደገኛ አይደለም የሚል ነው፡፡ ቦናሲሲ ግን ይህ የፈረንሳይ አስተሳሰብ ዘራቸው በመጥፎ ሁኔታ የሚገኘው እንደ ፈረንሳዮች ሲያዋጣቸው ይችላል እንደ ጣሊያኖች ዘራቸውን በከፍተኛ ሁኔታ የሚገኘው ግን ከደከመ፣ መሐን ከሆኑ ጋራ መቀላቀል ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ ከዚህም ሌላ ከፈረንሳይ ዘር ጋራ ጥቁር ዘር ተቀላቅለዋል፤ ይሁዶችም የፈረንሳይ ፖለቲካዊ እና ኤኮኖሚያዊ ኑሮ በቁጥጥራቸው በማግባታቸው በተለይ በሕዝባዊ ግንባር (Front Populaire) ጊዜ የፈረንሳይ ሕዝብ የዘር አንድነት ባይኖረውም የሀገር አንድነት ግን ያለው ሕዝብ ነው፡፡ የፈረንሳይ ሕዝብ ከኤውሮጳ ከሁሉም



እንጋፋና የደከመ ሕዝብ ነው፡፡ የፈረንሳይ ዲሞክራሲ የጀርመን ዓይነት ዘረኝነት የሚቃወም ነው፡፡ የፈረንሳይ አቋም ለዘረኝነት ግዴለሽነት የተነሳ አይደለም ውድቀቱ ያፋጠነው ፈረንሣይ ዕድሜዋን ለማራዘም ከሌሎች ዘሮች ጋራ በመዳቀል ነፍስ ለመዝራት የምታደርገው ሙከራ ነው፡፡ የፈረንሳይ መንግሥትም ሆነ ሌሎች ፓርቲዎች ከሁሉ በሜዲቴራኒያን የሚኖሩ ዘሮች ሁሉ የተውጣጣ የተቀላቀሉ የዘር አንድነት ለመፍጠር ይጥራሉ፡፡ ይህ ሥር የሰደደ በፀረ ጀርመን አቋም የተመሠረተ ራሱ ዘረኝነት የሆነ አንድነት ነው፡፡ ዓለም ዓቀፋዊ ዘረኝነት ነው፣ የዘረኝነት ተቃዋሚ ነው፣ በእኩልነት፣ ባዲሞክራሲያዊ ዓለም አቀፋዊነት የሚመራ ነው፡፡ ይህ አቋም ፋሽዝም እና ናዚዝም በቸልተኝነት አይመለከተውም፡፡ ከዚህ ቀደም ላቲን እህትማሞች እያሉ ይቀልዱብን ነበር፤ አይዛመዱንም፣ በመንፈስ እንመሳሰልም የባሰም አንድ ዘር ነን ማለት አይችሉም ምክንያቱም ዘር ቢኖርም በብዙ መቶ ዓመት ተበታትኖ ጠፍቷል፡፡

ሊኖ ቡሲንኮ ባወጣው ጽሑፍ በፈረንሳይ ሀገር የሚደረጉ አንዳንድ ፀረ ይሁዶች ቅስቀሳ በማስመልከት ሕዝባዊ ግንባር Front Populaire የተባለው የፈረንሳይ ፖለቲካ ፓርቲ ተግባሩን በማውገዝ ሴፕቴንበር 23 ቀን 1928 ዓ.ም. ከዚህ በታች የሚመለከተው መግለጫ እንዳወጣ ገልጿል "የፓሪስ ክልል ሕዝባዊ ግንባር የሚከተለውን መግለጫ በሙሉ ድምፅ አውጥቷል፡፡ የፓሪስ ክልል ሕዝባዊ ግንባር በአንዳንድ ክፍለተሀገሮች በተለይ በአልሳዚያና ሉሬን እንዲሁም በፓሪስ የፀረ እስራኤሎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ስላሳሰበው በፈረንሳይ ከሚገኙ የሂትለር የጠብ ተንኳሾችና ወኪሎች ሕዝቡ እንዲጠነቀቅ ያሳስባል፡፡ ባለስልጣኖች ለነፍስ ገዳይነት የሚገፉፉ ጋዜጦች እንዲከለከሉ ይጠይቃል፤ በዚሁ በምንገኝበት ወቅት የከባድ አደጋ ሁኔታ ጦርነትና ደህነትን የሚያመጣ የዓለም አቀፍ ፋሽዝም ተግባር ለማኮላሸት የዲሞክራሲ ኃይሎች አንድነት አስፈላጊ መሆንን ያስገነዝባል፡፡ ከ1789 ዓ.ም. ጀምሮ ፈረንሳይ በይሁዶችና በፈረንሳውያን መካከል ምንም ልዩነት እንደማይደረግ ያስታውሳል ቶታሊ ታሪስት የሚባሉ ሀገሮች ባሕል በሀገራችን ላይ እንዳይሰፍን ሀገራችንን የሚያዋርዱ ባሕሎች እንደማይፈቅድ ያስጠንቅቃል፡፡ ፈረንሳዮች በሥራ መስክ ከአይሁዶች ጋራ መወዳደር ካልቻሉ ቦታቸውን በመንግሥት አመራር በኢንዱስትሪ በይሁዶች ከተያዙ ይህ ይሁዶች የበለጠ ችሎታ አላቸው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፈረንሳውያን በሞያቸው ዝቅተኛ ከሆኑ የፈረንሳውያን የመምራት ኃላፊነት ይሁዶች ቢወስዱም ትክክል ነው ብለዋል፡፡

ጣሊያኖች የአሪያን ስልጣኔ የኤውሮጳ ስልጣኔ ብለው ማውራት ይወዳሉ፤ የዓለም የስልጣኔ ምንጭ ግን አሪያን ያልሆኑ የመካከለኛ ምሥራቅ ሕዝቦች ናቸው፣ ቀጥሎም አሪያኖች ግሪኮች ናቸው፡፡ ጣሊያኖችና ጀርመኖች ሌሎችም ኤውሮጳውያን ሁኔታ የአውሬ ጉልበት ጠባይ የነበራቸው ሮማውያንን ግድነት ግምስክ ይወዳሉ፡፡ የሮማ መንግሥት ወሰን የለሽ ሀገር አልባ ወታደራዊ መንግሥት ነበረ እንጂ በሥልጣኔ የተራቀቀ እንደ ግሪኮች ሶክራተስ፣ አሪስቶተሊስ፣ ፕላቶ ፍላስፎች፣ እንደ ዲሞስተነስ ተናጋሪዎች እንደ አሪኪሜደስ ፒታጎራ ወዘተ ሳይንቲስቶች እንደ ሆመር የስነ ግጥም ፀሐፊዎች እንደ ሄሮደትስ የታሪክ ፀሐፊዎች እንደ ታላቁ እስክንድር የሰው ዘር በሙሉ በእኩልነት የሚያስተዳድሩ ንጉሦች የመሳሰሉት በመፍጠር ታዋቂነት አላታረፉም፡፡ ፈረንሳይና እኛ በሚል አርእስት ጁሴፔ ግሪየኮ Giuseppe Grieco [1] የተባለው ፈረንሳይ በጀርመኖች ከደረሰባት ሽንፈት በኋላ ያወጣው ጽሑፍ የኢጣሊያ ምድር ጦር የባሕርና የአየር ኃይሎች በኤውሮጳና በመላው ዓለም

[1] Giuseppe Grieco : La Francia e Noi Difesa della Razza Anno IV N 3 Dicembre 5,1940

ለኢጣሊያ የማስፋፋት ዓላማ እስፈላጊ የሚሆናት በቂ ቦታ Spazio Vitale ለማስገኘት የሚያገኙበት ወቅት ነው ካለ በኋላ በዚሁ አዲስ ፖለቲካ ኃይል ሆና በተረፈች ኢጣሊያና እንደ ካርታጅ ትልቋ ነጋዴ መንግሥት እንግሊዝ መሐል የሚደረገው ወሳኝ እስከሬ ግፉና ጦርነት ፈረንሳይ ትልቅ ኃላፊነትና ብዙ የታወቁ ስህተቶች ተሸክማለች፡፡ ጥቂት ወንጀለኞችን ወደ ፍርድ በማቅረብ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተሸናፊዋ ፈረንሳይ ስሕተቶቿን ሁሉ አንድ በአንድ መክፈል አለባት፡፡ ከፈረንሳይ ጋራ የከፈትነው ብዙ ጊዜ የቆየ ሂሳብ በሙሉ መዘጋት ያለበት አለ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ነው ፈረንሳይ የፋሽስትና የናዚዝም አብዮቶች ለአውሮጳ በሚያወጡት ድልድል በሚፈቅድላት መሠረት ቦታዋን መያዝ የምትችለው፡፡ በተለይ ባለፈው 100 ዓመት ዘመን ፈረንሳይ ፀረ ሮማ አቋም እንደነበራት መርሳት የለብንም፡፡ የሮማ ስም እንዲደመሰስ ትጥራለች የኢጣሊያ የጥና ከተማዋ ሮማ ሆና ነፃ መንግሥት እንዳይመሠረት ትጥራለች፡፡ በሴዳን ተሸናፊው በሆነው ፈቃድ አይደለም የኢጣሊያ ነፃነትና አንድነት የተገኘው፡፡ ከእሱ ፈቃድ ውጭና በእሱ ተቃራኒና በፈረንሳይ ተቃራኒ በመቆም ነው የኢጣሊያ ነፃነት የተገኘው፡፡ ፈረንሳይ የነፃነት ሀገር ለተጨቆኑ ሕዝቦች በጦር ኃይሉቿ ነፃነትን የምትሰጥ ሀገር የሚለው ታሪክ ጊዜ ያለፈበት ተረት ሆኖ ቀርቷል፤ ማንም ሰው አያሳምንም፤ፈረንሳይ አለች እውነተኛዋ ፈረንሳይ ሮማዋ የነፃነት ሀገር ናት፣ ለራሷ ነፃነት፡፡ በሌላ ሀገር ግን የ Jamais የ /Passepots ፈረንሳይ ናት፡፡ በሮማ ትልቅ መንግሥት እንዳይመሰረት የምትጥር፣ በአንደኛ የዓለም ጦርነት ማብቂያ የጀርመን ቅኝ ግዛት የነበሩ ኢጣሊያ እንዳይደርሳት ተከለከለች፡፡የተገኘው ድልም የፈረንሳዮችና የእንግሊዞች ብቻ ሆኖ ተረ፡እህት ሳቲን ሀገር ትባላለች፡፡ ይህ እህትነት ግን ብዙ ሐዘንና ማታለል አድርሶብናል፡፡ ነፃነታቸው ከማግኘታቸው በፊት ጣሊያኖች ፈረንሳይን ያገዙ ነበር፡፡ ነፃነታቸውን ካገኙ በኋላ ግን የነፃነት ሀገር የተባለችው ፈረንሳይ ፀረ ሮማ ሆነች ሮማ እንደገና መነሳት የለባትም ብላ በመከራከር ብትቃወምም ፈረንሳይ ሳትወድ በግድ ሮማ እንደገና ተመሰረተች፡፡ በዚሁም ፈረንሳይ ምን ጊዜም ይቅርታ አታደርግልንም፡፡ ፈረንሳይ በዚሁ ብቻ ሳትወሰን እስከተሸነፈች ጊዜ ድረስ ያለማቋረጥ ፀረ ፋሽዝም አቋም ነበራት፡፡ የፈረንሳይ ፖለቲከኞች ዓላማ ፋሽዝም ለማውደም ነበር፡፡ ቢያሸንፉ ኖሮ እነሱ ከይሁዳዊ ብሉም Blum እስከ Reynaud ሬይና ድረስ ጀግኖች ይሆኑ ነበር፡፡ ፈረንሳይ ጥፋተኞችን ወደ ፍርድ ለማቅረብ ትችላለች፣ ችግሩዋ ነው፣ እኛን አይመለከትንም፣ ኃላፊዋ ፈረንሳይ ብቻ ናት ደላዲየ Daladier እና ጓዶቹ አይመለከቱንም፣ ተጠያቂዋና ከፋይ ፈረንሳይ ብቻ ናት፡፡ ለወደፊት ፈረንሳይ በአውሮጳ የሚኖራት ሚና እየቀነሰ በመሄድ ላይ ያለው የሕዝቧ ብዛት ታዋቂ ነው ተገቢ ቦታዋን ማግኘት ያምትችለው፡፡ ለመነሳት ከፈለገች ፈረንሳይ ስሕተቷን ከመክፈሏ ሌላ በአዲስ መንገድ መጀመር ይኖርባታል፡፡ ይህ ግን ከሮማዊ ቄሳር የተተለመላት የሮማ መንገድ ካስተከተለች ልታገኝም አትችልም፡፡

(1) የሊዮፓርዲ ሐሳቦች ተብለው በተከታታይ ከሚወጡ ጽሑፎች አንዱ ስለ ፈረንሳይ ዓየነ ሐፋርነት በዘረኛ መጽሔት እንደ ጽሑፍ ወጥቷል፣ ጣሊያኖች ፈረንሳዮችን ዓይነ ሐፋሮች ይሏቸዋል፡፡ እውነትም ቢሆን በበጉ ጉን አያዩትም፤ ድፍረት ማጣት ብለው ይተረጉሙታል፣ እንደ ሊሉች ሰዎች ሆኖ መኖር የሚል ፍልስፍና አላቸው ይሏቸዋል፡፡ እንግሊዞችም ዓይነ ሐፋሮች ይሏቸዋል፡፡ እንደ ጣሊያኖች ስድ አነጋገር ስለሌላቸው በሥነ ሥርዓት ስለሚናገሩ ይሆናል እንጂ በደፈናው እንግሊዞችና ፈረንሳዮችን ዓይነሐፋሮች ሊሏቸው አይችሉም፡፡

(1) Leopardo : Timidezza Francese : Difsa della Rozza Anno 3 N 15



ጀርመኖች ራሳቸው ዘረኝነትን የተማሩት ከሁለት ፈረንሳዮች ጎቢኖና (Gobineoud 1816 1882) ተወልዶ የሞተ እንዲሁም ደ ላፑጅ Vacher De Lapouge በ1854 ተወልዶ በ1936 የሞተ የተባሉ፡፡ እነዚህ ፈረንሳውያን በሀገራቸው ስለ ዘረኝነት ተሰሚነት ያላገኙ ነበረ፡፡ እነሱ ግን ከአሪያን ዘሮች ተቀባይነት በመጀመሪያ ደረጃ ያስቀመጧቸው እንግሊዞች ነበረ፡፡

ግሪኮች ቅድመ ክርስትና ዘመን አስደናቂ ስልጣኔ ለዓለም አበርክተዋል በክርስትና ዘመንም ለዓለም ስልጣኔ ጠቃሚ ሚና ይጫወቱ ይችሉ የነበረ በመስቀል ጦርነት ጊዜ እስላሞችን ለመዋጋት በዘመቱት የምዕራብ አውሮጳ ክርስቲያን ወዶ ዘማቾች ልክ እንደ እስላሞች ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በመሆናቸው ተጨፈጨፉ፡፡ በመጨረሻም በኦርቶማን ቱርኮች ለብዙ መቶ ዘመናት ለመገዛት ቢገደዱም ሃይማኖታቸውም ሳይቀይሩ ለሀገራቸው ነፃነት ትግል በማካሄድ የተቀጠቡበት ጊዜ አልነበሩም፡፡ የምዕራብ አውሮጳ ሕዝብ መንግሥታት እንዲሁም የሮማ ጳጳስ ንቃተ ሕሊና ምን ያህል ዝቅተኛ እንደነበረ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሕንጉላቸው ሊደነቁና ሊከሩ የሚገባቸው አሪያኖች ግሪኮች ናቸው እንጂ አብሪተኞች ጣሊያኖችና ጀርመኖች አይደሉም፡፡ ሌላ ጽሑፍ ከልበነትና ፈረንሳይ በሚል አርእስት የቀረበው በዝሎላ ማርኪቶ ነው፡፡[1] በነጭ ሰውና ጥቁር ሰው መሐል ያለው ልዩነት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ነጩ ወደ ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ ሲገኝ ጥቁሩ ግን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ከእንስሶች በጣም ቅርብ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከነዚህ ሁለቱ ዘሮች የተወለደ ፍጡር የአውሮጳ ስልጣኔ በዘር የሚወረሰው በሺህ ዓመታት የተገነባ ክልሱ ሊደርስበት አይችልም፡፡ 40 ሚሊዮን የሕዝብ ብዛት ያላት ፈረንሳይ ከቅኝ ግዛቶቿ ጋር ባለ100 ሚሊዮን ሕዝብ ብዛት መሆን ትፈልጋለች፡፡ በብሩክሴል Bruxelles የኮሎኒያል ኢንስቲቲውት በተደረገው ስብሰባ የፈረንሳይ መልእክተኛ ደ ፑቩርቪል De Pouvourvill የተባለው በ1924 ዓ.ም. ባደረገው ንግግር የፈረንሳይ ደም በትንሿ እንኳን በጥቁሩ ደም ከተገኘ ጥቁሩ ወደ ነጩ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል ብለዋል፡፡ በዘረኛነት የምንኩራበት አንድ ጠብታ እንኳን የፈረንሳይ ደም ጠፍቶ እንዳይቀር ያስገድደናል ብሏል፡፡ የዚሁ አስተሳሰብ ውጤቱ ጥቁር የጦር መኩንኖች ነጭ የፈረንሳይ ባታሊዮኖች እየመሩ በሰልፍ ሲያልፉ ይታያሉ፡፡ የፈረንሳይ የፓርላማ አባልና ምክትል ፕሬዚዳንት አንድ ጥቁር ነው፡፡ ፈረንሳዊት ሴት ከአንድ ወንድነቱ የደከመ ፈረንሳዊ ወንድ ከመገናኘት ይልቅ ሙሉ የወንድነት ፍቅር የሚሰጣት ጥቁር ሰው ትመርጣለች፡፡ በቅኝ የፈረንሳይ ግዛትም ፈረንሳዊ ወንድ ጥቁር ሴቶችን ፍቅር በማስያዝ ይኩራሉ፡፡ ኢስካል (Escale የተባለው ፊልም ከጥቁር ወንድ ጋራ ፍቅር የያዛት ሴት የሚያሳይ ፊልም በኢጣሊያ እንዳይታይ መታገዱ ትክክል ነው ብሎታል፡፡

ጣሊያኖች ከአሪያን ዘሮች ለመሆናቸው ለማስረዳት በዘረኛ መጽሔታቸው በ5 ዓመት ሕልውናዋ ብዙ ጽሑፎች ቀርበዋል፡፡ ጣሊያኖች ግን አሪያን ለመሆን የነበራቸው ጉጉት ንፁህ አሪያን አለመሆናቸው ስለሚያውቁ ነው፡፡ እንኳን ጣሊያኖች ጀርመኖችም ንፁህ ዘር አይደሉም፣ ቅልቅል አለባቸው፡፡ በጣሊያን ሀገር ንፁሕ የአሪያን ዘር ነን ሊሉ የሚችሉ በአንድ ቦታ ሰፍረው የተቀመጡ ሉንባርዲውያን ብቻ ናቸው፡፡ ሉንባርዲያውያን ወደ ኢጣሊያ የመጡ ከስካንዲናቪያ ነው፡፡ ወደ አውሮጳ ከመምጣታቸው በፊት የነበረ ታሪካቸው አይታወቅም፡፡ ወደ ጣሊያን ሀገር የመጡ በ1568 ዓ.ም. ዓስም ብዙ ሥልጣኔ አሳልፎ ወደ ጨለማ ዘመን ከገባ በኋላ ነው፡፡ አሪያኖች

(1) Nicola Marchitto ibd Anno 2 N.10

ከሌሎች የሰው ዘሮች የበለጠ ሐንጎል ያላቸው ከሆነ እንዴት የራሳቸው ስልጣኔ ሊፈጥሩ አልቻሉም?፡፡

በሰለጠነ ሀገር መጥተው ሰፍረው ነው ስልጣኔውን ሊያሻሽሉ የቻሉት፡፡ በዛሬ ጊዜ በኢጣሊያ የሎምባሪዲያ ክፍለ ሀገር የኢጣሊያ ኢኮኖሚውና ስልጣኔ የምታንቀሳቅስ ክፍለ ሀገር ናት፡፡ በ1985 በኢጣሊያ በኢንዱስትሪ ከሚሰሩ 6,715,000 ሰራተኞች ኢጣሊያ ካሏት 20 ክፍለሀገር ሀገሮች 1,625,000 ከሎምባሪዲያ ናቸው፡፡ በኢጣሊያ በመጨረሻ የሰፈሩ በስልጣኔ ግን በግንባር ቀደም ናቸው፡፡

ከሰው ዘር የበላይ ንፁሕ አሪያኖች ነን እያሉ የሚኩሩ ጀርመኖች ታቼተስ[1] የተባለ በ55 ዓ.ም. ተወልዶ በ120 ዓ.ም. የሞተ ሮማዊ ታሪክ ፀሐፊ ስለ ጀርመኖች ታሪክ የዘገበው እንዲህ ብሎ ጽፏል "ጀርመኖች ነጩዎዎቹ መርጠው ንጉሦች ያደርጋሉ፤ ከጀግኖች መርጠው የጦር መሪዎች ያደርጋሉ፡፡ ንጉሦች ፈላጭ ቆራጭ ስልጣን የላቸውም፤ ምሳሌ በመስጠት ነው የሚያስተዳድሩት፡፡ ቄሶች ካልሆኑ በቀር ማንም ሰው መቅጣት ማሰር አይፈቀድለትም፤ ቄሶችም በእግዚአብሔር ስለሚታዘዙ በተዋጊዎች መሐከል እግዚአብሔር ይገኛል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ወደ ጦርነት ሲሄዱ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸውን ይዘው ነው፡፡ ስለ ዋና ዋና ጉዳዮች አንድ ላይ ተሰብስበው ይወስናሉ፤ አብዛኛው ጊዜ የሚሰበሰቡ ሙሉ ጨረቃ ስትወጣ ነው፤ ስብሰባቸው ሁለት ሦስት ቀን ይቆያል፡፡ ሁሉም በስብሰባ ሲገኙ መሣሪያ ታጥቀው ነው የሚቀመጡ፡፡ ቄሶች በጥሞና ሕዝቡ እንዲያዳምጥ ያዛሉ፤ ንጉሡም ንግግር ያደርጋል፡፡ በስብሰባው ክስ ማቅረብ ይቻላል፤ ጥፋተኞችም በዛፎች ላይ ይሰቀላሉ፡፡ ወራዳ ስራ የፈጸሙ በደለሎች ይጣላሉ፡፡ በግልም ከብዙ ሰዎች ጋራ ቢሆንም ያለ መሣሪያ አይሄዱም፡፡ ከሕብረተሰቡ የተፈቀደለት መብት ያለው ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ማሣሪያ መያዝ አይችልም፡፡ በጦርነት አለቃ በጀግንነት ጭፍራው ሲበልጠው ነውር ነው፤ ጭፍሮቹም ካለቃው ለመወዳደር ይጥራሉ፡፡ እንደ ጭፍራ አለቃው በጦርነት ሞቶ ቤት ሊገባ ሕይወቱ ሙሉ እንደ ሐፍረት ነው፡፡ አንድ ከተማ ለብዙ ጊዜ በሰላም ሆና ከኖረች ወጣት ጦረኞች ጦርነት ወዳለበት መሄድ ይፈልጋሉ፡፡

ጀርመኖች በከተማ አይኖሩም፤ በአንድ ላይ በድንጋይ የተሰራ ቤት መኖር አይፈልጉም፤ አንድ ቤት በአንድ ምንጭ አጠገብ፤ ሌላ በእርሻ ሜዳ፤ ሌላ በዛፎች መሐል መኖር ይወዳሉ፡፡ መንደሮቻቸው እንደ እኛ የተያያዙ አይደሉም በመሐላቸው ምናልባት ቃጠሎ በመፍራት ባዶ ቦታ ይተዋሉ ወይንም በችሎታ ማነስ ሊሆን ይችላል፡፡ በሸክላ ቤት መሥራት ወይንም በእንጨት አያውቁም፡፡ ጥሎሽ ሚስት ለባሏ አትሰጥም ባል ነው ለእሷ የሚሰጥ እንደ ወላጆችዋ ፍላጎት፡፡ ጌጦች አይሰጡም፤ 2 በሬዎች አንድ ፈረስ ከነ ኮርቻው፤ ጋሻ፣ ጦር ይሰጣሉ፡፡ መንደሮቹ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን መሬት ይወስዳሉ መሬት በብዛት ስላለ በመከፋፈል ችግር አይፈጥርም፡፡ በየዓመቱ የተለያዩ መሬቶችን ያርሳሉ፡፡ አትክልት ጥራጥሬ አይዘሩም ስንዴ ብቻ ነው ማምረት የሚወድ፡፡ ሰው በሞተ ጊዜ ብዙ ሥነ ሥርዓት አያደርጉም፤ እንጨት ተሰብስቦ ክፍ ያለ ማዕረግ ያላቸው አስከሬናቸው ይቃጠላል፤ በእሳቱ ልብሶችም ሆነ ሽቶዎች አይጨምሩም፤ የሟቹ መሣሪያ ብቻ በእሳቱ ይጣላል፡፡ በአንዳንድ ጨዋ የሆኑ ሰዎች በእሳቱ ውስጥ ፈረስ ይጨመራል፡፡

ጀርመኖችም የዓለም ስልጣኔ ማወቅ የጀመሩት የሮማ መንግሥት ከወደቀ በኋላ በጭለማ ዘመን ነው፡፡ የሮማ መንግሥት አገል ያልነበሩና

[1] Augusto Lizier : Corso Di Storia Volume I p 56



የሚያውቁት መንግሥታቸው ለአንድ ሺህ ዓመት ሮማዊ ብለው መጥራታቸው አስደናቂ ነው፡፡

ትናንሽ የኢጣሊያ መንግሥታት ከፖርቱጋል ወይንም ከሆላንድ የማያንሱ የነበሩ ቅኝ ግዛት መፍጠር አልቻሉም፡፡ ጀርመኖችም አንድነታቸው ካገኙ በኋላ እንኳን በቢስማርክ ጊዜ ቅኝ ግዛት ለማግኘት ይቀናቸው ነበር፡፡ የቅኝ ግዛት ማብቂያ ጊዜ ስለማፈጣቸው ቅኝ ግዛት ለማግኘት ሽሚያ ገብተው በሚዘገንን ሁኔታ የሰው ልጆች እልቂትና ዘረኝነት ለመፈፀም ብቻ እውቅና ለማትረፍ በታሪክ አልፏል፡፡

የዛሬ ጀርመኖች የሕንድ ጥቁርነት እንዳይለጠፍባቸው ኢንዶ አሪያን Indo Arian Indo european ተብለው መጠራታቸው አይቀበሉም ይሆናል፤ በታቺቱስ ጊዜ ግን በብዙ ሺህ ዘመናት በዘላኝነት በሕንድና በእስያ በረሐዎች በሚኖሩበት ጊዜ እንደ ሕንዶች የሙታን አስከሬን በእሳት ማቃጠል የነበራቸው ባሕል ወደ ኤውሮጳ ከመጡ በኋላም ባሕላቸው እንደነበረ የታቺቱስ ታሪኮች ይመሰክራሉ፡፡

የዓለም ስልጣኔ የፈጠሩ አሪያኖች አይደሉም ጀርመኖችና ጣሊያኖች የሚኮሩበት የአሪያን ዘር ጭንቅላት ከሌላ የሰው ዘር የበላይ ቢሆን ኖሮ ለምን ከሌሎች የሰው ዘሮች አስቀድሞ ስልጣኔ አልፈጠሩም? አብዛኛው አሪያኖች የዓለም ስልጣኔ ከዳበረ በኋላ ናቸው፤ ከሰለጠነ ዓለም ጋራ ተደባልቀው ስልጣኔውን ለብዙ ዓመታት ወደ ኋላ ጎትተው ሚድል ኤጅ Middle Age የፈጠሩ፡፡ ስልጣኔ ወደ ተሻለ ደረጃ ከማድረስ በመጀሪያ መሠረተ ስልጣኔ መጣል ነው የሚከብደው፡፡ መሠረተ ስልጣኔ ከጣሉ ከመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች አሪያን ዘር የሆኑ ግሪኮችም ነበሩበት፡፡ እንደ ዛሬ የተገላቢጦች ሳይሆን ትልቁ የግሪክ ፈላስፋ አሪስቶተለስ[1] ስለ ሰሜናውያን አሪያኖች እንደነ ጀርመኖች የሐንጎል ችሎታ ሲጽፍ "የኤውሮጳ ሕዝቦች ብርዳማ ሀገሮች የሚኖሩት አብዛኛዎቹ ድፍረት አላቸው በእርግጥ ግን በአእምሮዋቸውና በእንቅስቃሴያቸው ዝቅተኛ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ነፃነታቸውን የያዙ ቢሆኑም በፖለቲካ ግን ሥርዓተ አልበኞነት ናቸው እና በሌላ ሕዝብ ላይ ገዝተው አያውቁም፡፡ በእንፃሩ የእስያ ሕዝቦች አእምሮአቸው ክፍት ነው ለኪነጥበብም ስጦታ አላቸው፡፡ ነገር ግን የወንድነት ጀግንነት መንፈስ ይጎድላቸዋል፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ የበታች ሆነው ይኖራሉ፡፡ በእነዚህ ሁለት ሕዝቦች መሐል የሚገኝ የግሪክ ሕዝብ ግን የሁለቱን ጥሩ ችሎታ ከፍተኛ አእምሮ ችሎታና ጀግንነት አጣምሮ ስላለው ነፃነቱን በመከላከል ለማቆየትና ጥሩ መንግሥትም ለመፍጠር ችሎታ አለው፡፡ አንድ መንግሥት ብቻ ቢመሠርት ዓለምን በሙሉ ይዞ መግዛት ይችል ነበር" ብሏል፡፡

## 7/ የኢጣሊያኖች ዘረኝነት በእንግሊዞችና በአሜሪካውያን ላይ

እንግሊዞችን በሚመለከት አርማንዶ[2] ቶስቲ ባወጣው ጽሑፍ ከድር ጀምሮ የብሪታኒያ ሠራተኛ ክፍል የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ከተረከ በኋላ የሕዝቡን ሞራል ብልሹነት ካወራ በኋላ ጃፓናውያን በእንግሊዝ ግዛቶች የሚፈጽሙት የውድድር ስራ ይጽፋል፡፡ የበሰበሰና ያረጀ የሰው ዘር ወጣት እንደ ጃፓናውያን ከሰው ዘር ጋራ ቢገናኝ በብሪቲሽ ኮሎምቢያ፣ በአውስትራሊያ፣ በኒውዝላንድ ቦታውን እያስረከበ ሲሄድ መታየቱ የሚያስገርም

[1] Armando Tosti : Difesa della Razza : Degenerazione della razza Anglo sassone Anno V I N 6
[2] Calogero Fazio : Corso Di Storia Volume I p 71

አይደለም፤ በፓሲፊክ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች በጃፓናውያን ሰፋሪዎች እየተወረሩ ናቸው፡፡ 40,000 ጃፓናውያን በካሊፎርኒያ ሰፍረዋል፤ በሐዋይ የጃፓናውያን ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ ጃፓኒያዊ ሰራተኛ በአንድ ቦታ ሲደርስ እንግሊዛዊ አባወራ ሰራተኛ ቦታውን ይለቃል ቢተሰቡም ብዙ ሳይቆዩ ይከተሉታል፡፡ በ1913 ዓ.ም. ቭሩማን Vrooman የተባለው በለንደን ኮሎንያል ኢንስቲትዩት "የብሪትሽ ኮሎምብያ ክፍል ሀገር ሁልጊዜ መሥራቃዊት እየሆነች እየመጣች ናት አሁን የእንግሊዝ ግዛት ትሁን ወይንስ ወደ ምሥራቃዊ ቅኝ ግዛት ተቀይራለች ብለን የምንጠይቅበት ጊዜ መጥቷል" ብለው ነበረ፡፡ በሌላ አነጋገር የእንግሎሳክሶን ዘር ጠንካራ ሕዝብ መሆኑን እያጣ ይገኛል፤ በአለፉ በመጨረሻ ዘመናትም የዘሩ ጥራት መቀነስ እየተጠናከረ መጥቷል ኃይሉም እስከ ውድመቱ መጨረሻ ትንፋሽ ስለደረሰ የአክሲሲ Axis የጦር ኃዶች በየቀኑ ዱላቸው እየሰነዘሩባቸው ይገኛሉ፡፡ የእንግሊዚ አካላዊ ውድቀት በሚል አርእስት በረኛው መጽሐት አራተኛ ዓመት ቁጥር 6 አርናልዶ ቶስቲ ባቀረበው ጽሑፍ ስለ እንጊሊዝ ጦር ሰራዊት ብቃት በማጥላላት ነው፡፡ የተመለመሉ አባላት ከድተው ይጠፋሉ ጦርነት ሲነሳ 60,000 ወታደሮች ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ በቅኝ ግዛቶች 12% ይከዳሉ ወይንም ይታሰራሉ፡፡ በፈረንሳይ፤ በጀርመን፤ በአሜሪካም ጭምር ብሔራዊ ውትድርና እንቢ ማለት የሚያሳፍር ሲሆን በእንግሊዝ ሀገር ግን የተለያዩ ምክንያቶች እያቀረቡ ከውትድርና ይሸሻሉ፡፡ ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዴታ ማድረግ የተሞከረው እንግሊዞች በጦር ሰራዊት ያላቸው ንቃት የተነሳ እንቅፋት ስለተፈጠረ ነው፡፡ በታሪካዊ ምክንያት ብቻ አይደለም በዘር የመጣ መሆኑን መገመት ያስፈልጋል መበዝበዝ የለመደ ካፒታሊዝም ጦርነት አይወድም፤ ከ1896 በፍቃደኝነት ለውትድርና ከቀረቡ 54,574 ሰዎች 23,000 ለውትድርና ብቁ ሳይሆኑ ቀሩ፡፡

በ1887 በፈቃደኝነት ለውትድርና ከቀረቡ 59,986 22813 ብቁ ሳይሆኑ ቀሩ

በ1898 በፈቃደኝነት ለውትድርና ከቀረቡ 63,501 23,287 ለውትድርና ብቁ አልነበሩም፡፡

በ1899 በፈቃደኝነት ለውትድርና ከቀረቡ 68,039 23,393 ለውትድርና ብቁ አልነበሩም፡፡

በ1900 በፈቃደኝነት ለውትድርና ከቀረቡ 88,402 23,105 ብቁ አልነበሩም፡፡

ወታደሮች የልምምድ ድካም አይወዱም፡፡ ቢሪታኒያ የቀድሞ ክብሩዋ አጥታ በአሜሪካኖች ቁጥጥር ስር ወድቃለች፤ መሳቂያ እያደረጋት ነው፡፡ ሰሰጃጆች ከአሜሪካ ጋራ እንድትቀላቀል እያሉ ከአንቶቿ እርዳታ ስትጠይቅ እየሳቁባት ይገኛሉ፡፡ በለንደን በአንድ ስብሰባ ሀገራችን ብሎ የተናገረ አንድ ሰው ከተሰበሰበው ሕዝብ በአንድ ድምፅ ሀገር የለንም የሚል ድምፅ ተቀበሉት፡፡ በ1910 ዓ.ም. ለፓርላማ በተደረገው ምርጫ አንዳንድ ተናጋሪዎች የጀርመን ወረራ አደጋ አለ ብሎ የተናገረ ከእንግሊዝ ሰራተኛ ወገን የተሰጠው መልስ በጀርመን መገዛት ምንም እንደማይጠሉ እንዲያውም በጀርመን መገዛት እንደሚመርጡ ገልጠዋል፡፡ እንደ ሰሜን ባይሆንም በደቡባዊ እንግሊዝም ስለ ሀገር ማሰብ ስሜት ጠፍቷል፡፡ በዚሁ ምክንያት እንግሊዝ ያረጀች የጃጀች ዘር ሆናለች፡፡ በሌላ ሀገር እርዳታ አነስተኛ ድል ብታገኝም በወጣት ሀገሮች የበላይነቷ ማግኘት አትችልም፡፡ ነገር ግን ከባሕር ማዶ ያሏት ነጋዴዎች እንዲያድኗት ተስፋ እያደረገች ነው፡፡

ኢጣሊያ በሁለተኛ ዓለም ጦርነት በ1940 ዓ.ም. ጦርነቱ ምን መልክ እንደነበረው ከማሳየት ጣሊያኖች ለጦርነት የሚፋለሙ እንግሊዞችና ጀርመኖች መሆናቸውን የሚያሳይ የጀርመንና የእንግሊዝ ጦር ሰራዊት የወታደር



ፎቶግራፎች ራሳቸው ጣሊያኖች በዘረኛ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 9 አውጥቷል፡፡ ጣሊያኖች ግን በጦርነቱ እንደሌለበት ከቁጥር እንደማይገቡ አምኗል ማለት ነው፡፡ ይኸውም ከእውነት የሚርቅ አይደለም ምክንያቱም ጣሊያኖች ትንሿ ግሪክ እንኳን ማሸነፍ አቅቷቸው በጀርመኖች እርዳታ ነበር ግሪክ የተሸነፈችው፡፡

የብሪታኒያ ዘረኝነት በሚል አርእስት ያቀረበው አንድ ፀሐፊ ጣሊያኖች ከፈረንሳዮች የባሰ እንግሊዞችን እንደሚጠሉ የሚያስመሰግብ ነው፡፡ ሌሎች ሀገሮች የሚፈጽሙት ኢሰብአዊ ተግባር ወቀሳ ማቅረብ የምትወድ ሀገር ብትኖር ብሪታኒያ ናት፡፡ ራሷ የምትፈጽመው ተግባር ሁሉ ትክክል ነው ትድሰት የለውም ብላ የምታምን ሀገር ብትኖር አሁንም ብሪታኒያ ናት፡፡ የእንግሊዝ ዘረኝነት በዚህ ዓለም ካሉት ሕዝቦች የጥቁርችም የነጮችም የእንግሊዛዊው ዘሩ የበላይ መሆኑን ያምናል፡፡ አንድ እንግሊዛዊ በአውሮፓውያን ላይ የበላይ መሆኑን ያምናል አንድ ኢጣሊያዊ ጀርመናዊ ወይንም ፈረንሳዊ እንደ እሱ እኩል መሆናቸውን አይቀበለውም፡፡ የዘረኝነት ምሳሌ የሆነች ሀገር አውስትራሊያ ናት ማንም ሰው ሀገራቸው ገብቶ እንዲሰራ አይፈልጉም፤ እንግሊዞችም ጭምር፡፡ በሕንድ መቀላቀልና መቀራረብ ያልተደረገው በእንግሊዞች የበላይነት ስሜትና በሕንዶች ከምዕራባውያን ጋራ በባሕላቸው ያለው የሚያራርቅ ጥላቻ ነው፡፡ በሕንድ ያሉት የእንግሊዝ አስተዳዳሪዎች ከማንሳቸው የተነሳ ተላላፊ ወፎች ናቸው ተብለውላቸዋል፡፡ እንግሊዞች በጥቁሮች ላይ ያላቸው ዘረኝነት በሚመለከት የባሪያ ንግድ በስፋት ያካሄዱ እነሱ ናቸው ካለ በኋላ በእንግሊዞች አስተዳደር ነጮችና ጥቁሮች አይደባለቁም፤ እንግሊዞች ጥቁሮችን የሚጠቀሙባቸው እንደ ሰራተኛ ለመበዝበዝ ብቻ ነው፡፡ ኑሮዋቸው ለማሻሻል ስለማይጨነቁ የሚሊዮናውያን ሚና በእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ እንግሊዞች ጥቁሮችን አፍነው አይዙም ባሕላቸው እንደ ልባቸው ማከናወን ይችላሉ፤ ነገር ግን ምንም ነገር አይሰጧቸውም፡፡ ወደ ስልጣኔ አይጠጉም የተባሉ በአውስትራሊያ፤ በካናዳና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የጥንት ተወላጆች ግን ተደምስሰዋል፡፡

እስራኤላውያን በሚመለከት ብሪታኒያ ዘረኛ አይደለችም ትባላለች፡፡ ነገር ግን በጥና ጥና ቁልፍ ቦታዎች የኃላፊነት ቦታ አይሰጧቸውም እንድ እንግሎሳክሶን እንድ እስራኤላዊ እንግሊዝ ነው ወይ ተብሎ ቢጠየቅ የሚሰጠው መልስ ረጋ ብሎ ኮስተር ብሎ እንግሊዛዊ አይደለም እስራኤላዊ ነው የሚል መልስ ነው፡፡ በዚሁ አኳኋን እንግሊዙ ፀረ ዘረኝነት መሆኑን ይናገራል፡፡

አሜሪካን በሚመለከት ማርች 30,1870 ዓ.ም. በወጣው ሕግ አንቀጽ 15 "የመመረጥ መብት በአሜሪካ በዘር በቆዳ ቀለም በቀድሞ ባርነት ምክንያት ማንም ሰው ሊከለከል አይችልም" ይላል፡፡[1]

አንቶኒዮ ፔትሩቺ በ2ኛ ዓመት ቁጥር 20 በአፍሪካ ደቡብና ምዕራብ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች የሥራ ግቆም አድማ ሰለ ተስፋፋ ይህ ክስተት የዲሞክራሲ ምልክት የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ጥንካሬ ተብሎ አልተገመተም በጣሊያኖች ተቃውሞ የማይፈቀድ ስለሆነ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የማከተም ምልክት ነው ተብሎ ተገምቷል፡፡ እንግሊዞች ቅኝ ግዛት ማስተዳደር አልቻሉም ለኢጣሊያኖችና ለጀርመኖች መልቀቅ አለባቸው ማለታቸው ነው፡፡

2ኛ የዓለም ጦርነት በኋላ ብሪታኒያ ስትሸነፍ ጣሊያኖችና ጀርመኖች እንደ ዛሬ ጊዜ አሜሪካንና ሩሲያ በአሪያን ዘር የተመሰረተ ኃያላንና ርዕሰ ኃያል መንግሥታት እስወገደውና ተተክተው ራሳቸው ልዕለ ኃያላን ለመሆን ሕልም ነበራቸው፡፡ /4ኛ ዓመት ቁጥር 18/ ጀርመኖች በምዕራብ አውሮጳ

(1) Prof. Guido A. Chiurco : La Sanità delle razze nell Impero Italiano p 1068

የሕዝብ ብዛት ያላቸው ናቸው። ሁሉም ባርባሪያን ኢውሮጳን ወረው የያዙ አጠቃላይ ስማቸው ጀርመን ነበር፣ ጀርመናውያን በቅድሚያ በኢውሮጳ ብቸኛ ኃያለኛ መንግሥት መመስረት የሚገባቸው ነበሩ። ነገር ግን ታሪክ የሰጣቸው ዕድል አልተጠቀሙበትም በመላው ዓለምም ግዛታቸውን ለማስፋፋት ብቸኛ ዕድል የነበራቸው ነበሩ። በእነሱ ስንፍና እንግሊዞች ተጠቅመውበታል። ፈረንሳዮች፣ ስፓኒሾች፣ ፖርቱጋሎችም ተጠቅመውበታል። የሮማ መንግሥት የአንድ ሀገር መንግሥት አልነበረም ዓለም አቀፋዊ መንግሥት ነበረ። ጣሊያኖች ሮማውያን አባቶቻችን ናቸው የሚሉ ከሆነ ከሮማ መንግሥት ውድቀት በኋላ ለመውረስ መጣር ነበረባቸው። ነገር ግን በወቅቱ ኢጣሊያን የሚባል ሀገር አልነበረም በክፍለ ሀገር ደረጃ በሮማ አካባቢ ወይንም በሌላ የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር አንድ መንግሥት ለማቋቋም ያደረጉት ጥረት የለም፤ ምክንያቱም በሮማ መንግሥት ተገዝተው የነበሩ የኢጣሊያ ጎሳዎች ተጨቁነው ኖራላቸው ወድቆ ስለነበረ እስከ 1860 ዓ.ም. ድረስ በባዕድ መንግሥታት ሲገዙ ነበር። አሁን ትልቅ ለመሆን ዕድል ካገኙ በኋላ በሰው ስራሽ በአሪያን ዘር ስም ልዕለ ኃያላን ለመሆን ቢፈልጉ ሊሳካላቸው አልቻለም።

በምንኖርበት ዓለም በዘራቸው መኩራትና መመካት የሚገባቸው ጣሊያኖችና ጀርመኖች አይደሉም። ከባልቲክ ባሕር እስከ ሰላማዊ ውቅያኖስ ግዛታቸውን ያስፋፉ በምሥራቅ ኢውሮጳ ሩሲያውያን መኩራት የሚገባቸው ሲሆኑ እንደዚሁም ብሪታኒያውያን በምዕራብ ኢውሮጳ ከመላው ዓለም ሰፊ ቅኝ ግዛት በመፍጠራቸው በኋላም ቅኝ ግዛቶቻቸው የነበሩ ለነፃነት አብቅተቸው 50 ነፃ መንግሥታት የጋራ ብልፅግና ሀገሮች በሚል ስያሜ አንድነት በመፍጠራቸው መኩራት ይገባቸዋል። በሁለት ግለሰቦች ሁለት ጎሳዎች ሁለት ሀገሮች መናናት ያለ ነው ወደፊትም ይኖራል። በሕግ ተደንግጎ የበላይና የበታች ዘር ተብሎ የዘር ማጥፋት ካልተፈጸመ በቀር ዘረኝነት ሊባል አይችልም። ጣሊያኖች በሁለቱ መንገዶች በግላቸው ዘረኝነት በመፈጸም ሰው በማዋረድ እንዲሁም የመንግሥታቸው ዘረኛ ሕግ በማክበር ዘረኞች ናቸው። በሁለተኛ የዓለም ጦርነት በሰው ልጅ በደል ያደረሱ ሀገሮች ጀርመኖች ለበደሏቸው ይሁዶች ይቅርታ በየጊዜው እየጠየቁ ይገኛሉ። ጃፓንያውያን በፈጸሙት መጥፎ ተግባር በየጊዜው ይቅርታ እየጠየቁ ናቸው፣ ጣሊያኖች ግን እንኳን ይቅርታ ሊጠይቁ ተመልሰው እንዲገዙን እንደሚፈልጉ ለማስረዳት ጥረዋል፣ አሁንም እየጣሩ ናቸው፣ አሁንም እርስ በእርሳችን የሚያጣሉን ጣሊያኖች ናቸው። በፈጸሙብን በደል ተጸጽተው ይቅርታ አስካልጠየቁ ድረስ ከእነሱ ጋራ ያለን በማንኛውም መስክ ግንኙነታችን በጥርጣሬ ዓይን ማየት ይኖርብናል። ጣሊያኖች በሰው ብዛት ኃያላን መንግሥታት ፈረንሳይ እና እንግሊዝ እኩል ናቸው በተግባር ግን የሁለተኛ ዓለም ጦርነት የጦር ጓዶቻቸው ለጀርመኖች ጉዳ ቸው እንጂ አልጠቀሟቸውም በኢውሮጳና በሰሜን አፍሪካ ዓለም ሙሉ ይዋጋው የነበረ ከጀርመኖች ጋር ነበረ ፣ ጣሊያኖች ከቁጥር አይገቡም ነበር። ድሮም ነፃነታቸውን ያገኙት በፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ ነበር። ብዙ ቅኝ ግዛቶችም ያገኙ በኤርትራውያን ተዋጊዎች ደም ነው። ጣሊያኖች ዘረኞች ነን ብሉ የሚለፈልፉ እውነት አምነውበት አይደሉም በአንዳንድ የኤውሮጳ ሀገሮች ፈረንሳይና እንጊሊዝ የበታችነት መንፈስ ስለሚሰማቸው ነው። አላይ እንደገለፅኩት ዛሬ የኢጣሊያ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነች የኢጣሊያ ክፍለ ሀገር ሎምባርዲያ 586 ነው ወደ ኢጣሊያ የተቀላቀለ። በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ በዓለም ከነበሩ ታላላቅ መንግሥታት አንዷ ነበረች። ጀርመኖችም በዚህ ወቅት የስልጣኔ ጮራ አላገኙም ነበር። በተደራጀ ስልጣኔ መሐል ገብተው ሲሰለጥኑ የሚያስደንቅ አይደለም። የአሪያን ምርጥ የበላይ ዘር ከሆኑ ዓለም ከተፈጠረ ጀምር እስከ ጨለማው ዘመን ሚድል እጅ



የት ነበሩ? ለዓለም ስልጣኔ ምን አስተዋጽኦ አደረጉ? ጣሊያኖች በአንድ ድምፅ ሆነው የሚያሰሙት ለእኛ በብዙ መቶ ዓመታት የአሪያን ዘሮች ያፈሩት ስልጣኔ ገብተን እንዳንሰለጥን እንፈቅድላቸውም ብለው ክለክሉን ለእነሱ ግን በብዙ ሺህ ዓመታት ከግብፃውያን 4500 ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ያፈራው ስልጣኔ ውስጥ ገብተው ነው ሊሰለጥኑ የቻሉት። ጣሊያኖች እኛ ጥቁሮች ትምህርት ቤት ገብተን መጠነኛ እውቀት ለማግኘት የማንችል መሆናችንን በሚል ሰበብ የምድር ጦር፣ በባሕር ኃይል፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ለማቋቋም መርከብ፣ አውሮፕላን፣ መኪና ለመስራት፣ እንዱስትሪ ለማቋቋም ስለማንችል ዝቅተኛ ዘሮች ናቸው ትምህርት ቤቶች ሊከፈትላቸው አይገባም ብለው ነበር እንዳንማር የከለከሉን። ጣሊያኖች በስልጣኔ የበለፀጉ አንጋፋ አሪያን ሕዝቦች እንግሎሳክሰኖች አሪያኖች ዘራቸው ዝቅተኛ ነው ብለው ለመናገር ደርሶ ነበር።

## የእንግሊዝ ዘር

አልዶሞኒካ[1] የተባለው በ1943 ዓ.ም. ባወጣቸው 5 ተከታታይ ረጅም ፅሁፎች (Articles) እንግሎሳክሰኖች የዘር ዝቅተኛነት ለማስረዳት ሞክረዋል። እንግሊዞች ማሕበራዊ ኑሮ አይወዱም በግላዊነት መኖር ይወዳሉ ይህውም የዝቅተኛ ዘር መሆናቸውን ምልክት ነው በማለት ይጀምራል። ምናልባት እንግሊዞች እንደ ኢጣሊያኖች ተሰብስበው እየጮሁ ስለማያወሩ ማለቱ ይሆናል ለእንግሊዞች በግላዊነት ጠባያቸው ሰው ሁሉ ከፍተኛ ዘር ናቸው ብሎ ይገምታቸዋል። ይህ ጠባያቸው ግን በሳይንሳዊ ምርምር ዝቅተኛነት የሚያሰጣቸው ነው ብሏል። ከእንስሳት ዘር ምርጥ ዘር ንብና ጉንዳን በማህበር የሚኖሩ ይጠቅሳል፤ ከሰው ዘር የሮማ መንግሥት ይጠቅሳል።

የስኮትላንድ፣ ጋለስና፣ አየርላንድ፣ ቢሪቶን በመሐበራዊ ኑሮቸው ከእንግሎች ይለያሉ። እስከ አሁን ዘመን የዘራቸው መጠሪያ በአንድ በታ ተወስኖ የመሠረቱ የግላዊ ፀረ ማኅበራዊ ኑሮአቸውን ያሳያል ብሏል። ምሳሌ ሳክሰኖች ለትናንሽ መንግሥታት ተከፋፍለው ሰሲክስ የደቡብ Sussex ወሰስ የምዕራብ Wessex ኤሴክስ Essex የምሥራቅ ሚድልአክስ Middlessex የመሐል ብሪታኒያ እስካሁን መጠራታቸው ነው። እንግሎም ምሥራቅ እንግሊየ East Anglia የሰሜን ሕዝብ Norfolk ደቡብ ሕዝብ Suffolk እየተባሉ ይጠራሉ። የእንግሊዞች የሁለቱ ፆታዎች ሲመረመር ልዩነት ይታያል ከሌሎች አሪያኖች የተለየ ያደርጋቸዋል።

1/ የእንግሊዞች ወንዶች የመተንፈስ አቅማቸው ከሴቶች ያነሰ መሆን ሲገባው ከሴቶች ይበልጣል ሴቶች በወር አበባቸው ምክንያት የመተንፈስ አቅማቸው መብለጥ ይገባዋል።
2/ የእንግሊዞች የደም ክብደት ዝቅተኛ ነው።
3/ የእንግሊዞች የሴት ዳሌ ከወንድ ዳሌ የተጠና የረዘመ ነው ይህውም የታይሮይድ እጢ ስራ መበርከት ነው የዝቅተኛ የሰው ዘሮች ምልክት ነው። በሜዲትራኒያን ዘር ሴቶች ከደረታቸው ቀጠን ያሉ ከዳሌያቸው ሰፋ ያሉ ናቸው።
4/ የእንግሊዞች ጭንቅላት የከፍተኛ የሰው ዘሮች ምልክት የሆነው ዶሊኮቼፋሊክ ከመሆን ፋንታ የልጆችና የዝቅተኛ የሰው ዘሮች ምልክት የሆነው ብራኪቼፋሊክ በአዋቂ እንግሊዞች ላይ ይታያል ይኸውም የእጢ እጢ ስራ

[1] Aldo Monica : Inferiorita' Razziale depli Anglo rassoni Difesa della Razza Anno VI N4-5-6-8-10

መበርከት ምልክት ነው፡፡ ይሄም ሁኔታ ከሴቶች ይልቅ በወንዶች የባዮሎጂ ዝቅተኛነት ዘር ያሳያል፡፡

5/ የእንግሊዞች ወንዶች ታችኛው የመንጋጋ አጥንት እንደ ሴቶች ዓይነት ነው የዳበረ አይደለም ጢም የማብቀል አቅሙም ያነሰ ነው በሜዲትራኒያን ግን የወንዶች የታችው መንጋጋ አጥንት የዳበረ ነው ብዙ ጠጉርም ያበቅላል፡፡ ብራኪቼፋሊክና ዶሊኮቼፋሊክ የጭንቅላት መለኪያ በጥቁሮች ዝቅተኛነት ለማስረዳት ተሞክሮ ውጤት አልሰጠም፡፡ አሁን በእንግሊዞች ላይ የሚጠቀሰው ጊዜ ያለፈበት በጥቁሮች ያልሰራ ነው፡፡

6/ የሴትና የወንድ ቁመት ልዩነት በእንግሊዞች ከሌሎች ሕዝቦች ይልቅ አነስተኛ ነው፣ ይኸውም 1.700 ለወንድ እንግሊዛዊ 1.600 ለሴት እንግሊዛዊት ሲሆን ለሜዲትራኒያን ሕዝቦች ግን 1.500 ለሴት 1.700 - 1.800 ለወንድ ነው፡፡

7/ የመወፈር ችሎታም በእንግሊዝ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ነው በሌላ ኤውሮጳ ዘሮች ግን ተቃራኒ ነው፡፡

8/ በ1215 የወጣው "ማኛ ካርታ" ለእንግሊዝ ሀገር እንደ ሕገ መንግሥት ሆኖ የሚያገለግል የቾልቲክ ማኅበራዊ ኑሮና የሳክሶኖች ግላዊ ኑሮ ግጭት ቅራኔ ሉጋም እንዲሆን የታለመ ነው፡፡ የንጉሡ ሥልጣን ለመቀነስ ለግላዊነት ዋስትና የታቀደ ነው፡፡ በሰሜን ዘሮች የፒቱዊታሪ፣ የእንቅርት፣ የታይሙስ እጢዎች ሥራ በሚያመነጩት ፈሳሽ ከሌላ ሕዝብ ሲነጣጠር በዝቶ ይታያል ይኸውም በጉ ተግባር ቢታይበትም በጣም ከበዛ ግን የግላዊና መጥፎ ስሜት አልባ ፀባይ ያመጣል Individualism ፡፡ በእንግሊዞች ወሲባዊ ስሜት አነስተኛ ይሆናል የራስ ወዳድነት ያበዛል፣ ይኸውም ጠባይ ከሴማዊ ሰብራዊ ጠባይ ይገጥማል፡፡ የታይሙስ እጢ የመብዛት አዝማሚያ ያላቸው ሰዎች ጉንፋን ያጠቃቸዋል እንደዚሁም ትርፍ አንጀት፣ ኮላይት፣ አዝማ፣ የሞራል ውድቀት፣ ከተቃራኒ ፆታ የመገናኘት ገና በልጅነት ዕድሜ ይቆማል፣ የሆሞሴክሱዋል ዝንባሌ ያመጣል፡፡ ይህ ሁሉ ፀባይ በአንግሎሳክሶኖች ይታያል፡፡ የወንድና የሴት ልዩነት አነስተኛ ነው፣ ሆኖም እንዳጋጣሚ እንደ ቸርችል የመሰለ የማስመሰል የወንድነት ይከሰታል፡፡ ጥፍሮችና ጥርሶች ደካሞች ናቸው፤ በዚህ ምክንያት የጥርስ በሽታ በአንግሎሳክሶኖች የበዛ ነው፡፡

9/ ከእንግሊዝ ጎሳዎች ቸልቲክ ወደ ማኅበራዊ ኑሮ ያዘነበለ ሲሆን የአንግሎችና የሳክሶኖች ግን ወደ ግላዊነት ያዘነበለ ነው፡፡ የአንዳንድ ሜዲትራኒያን ሕዝቦች ስሜት ሲያበዙ፤ እንግሊዞች ግን ስሜት አልባ ናቸው፡፡ የፒትዊታሪዝም ሲበዛ በሌሎች ሰሜን ሕዝቦች ታይሮይድ መብዛት ይቆጣጠራል፣ ሚዛናዊ ይሆናል፣ በእንግሊዞች ግን መቆጣጠር ባለመቻልዋ ስሜት አልባ ያደርገዋል፡፡

10/ በእንግሊዞች የፒትዊታሪዝም መብዛት የምግብ ፍላጎትና የመንቀሳቀስ ይበዛል፣ የወሲባዊ ስሜት ይቀንሳል፡፡

11/ በቃል የመያዝ ከፍተኛ ነው፣ በዚሁም ከይሁዶች ጋራ አንድ ዓይነት ያደርጋቸዋል፣ በቁጥአካላዊ ማተኮርም ያመጣል፡፡

12/ በሌላ በኩል እንግሊዞች ታይምስ እጢ በዝቶ ስለሚገኝ ረዘምና ቀጠን ያሉ ሰዎች በብዛት ይገኛሉ፤ ፀጉሮች ቀጭን ጥርሶችና ጥፍሮች ደካሞች ይሆናሉ፣ የደም ግፊት ያንሳል፣ የወሲብ ስሜት በልጅነት ዕድሜ ይቆማል፣ የልጅነት ዓይነት ዓይነ ሐፋርነት ይከሰታል፣ የወሲብ የመርጨት /ኮየውንዲ/ Coeundi ኃይል መቀነስ ይከሰታል፡፡

13/ ከሌሎች ሰሜን ዘሮች የሚለዩበት በነዚህ ሰሜን የኤውሮጳ ዘሮች ፒቱዉታሪ፣ ታይሮይድ፣ ታይሙስ፣ እጢዎች ተመጣጣኝ ሲሆኑ



# Catturato il capo termina la rivolta in Cirenaica

**Nominato nel 1930 vice governatore della Cirenaica, Graziani chiede pieni poteri per eliminare la guerriglia**

[illegible]



**Omar el Muchtàr**

*Il leggendario capo della rivolta in Cirenaica. Aveva 69 anni quando fu impiccato.*

ሲሬናይካ (ሊቢያ). ፀረ ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ታጋይ አርበኛ የማር ኢል ሙክታር

በእንግሊዞች ታይሮይድ ደከሞ ይታያል፡፡ በዚሁ ምክንያት ጨካኞች ቢሆኑም በማስመሰል ባሕሪያት ጠባያቸውን ይሸፍኑታል፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች አንግሎሳክሶኖች በባዮሎጂ ዝቅተኛ ዘር መሆናቸውን አልዶ ሞጊካ ማስረጃ ናቸው በማለት ደምድመዋል፡፡

# INFERIORITÀ RAZZIALE DEGLI ANGLOSASSONI

## V - I CARATTERI PSICHICI

ዘረኞች ጣሊያኖች የጥቁሮች ዝቅተኛነት ማስረጃ ሲያጡ የዝቅተኛ ፍጡር መሆናቸውን ማስረጃ ሆኖ የቀረበ የማይዳሰስ በደፈናው በባዮሎጂ ነው ብለው እንደደመደሙ ሁሉ፣ በእግሊዞችም የዚህ ዓይነት ተጠቅሟል፤ እንግሊዞች ግን ከእነሱ ከፍተኛ በመሆናቸው ነው ዘረኞችን ያበሳጫቸውና የቀኑባቸው፣ እንደዚሁም በእስራኤላውያን ላይ፡፡

## 8/ ዓለም በዘረኝነት አስተዳደር ስር ብትወድቅ

በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ዘረኞች ጣሊያኖችና ጀርመኖች ቢያሸንፉ ኖሮ ዓለም ምን ዓይነት አስተዳደር እንደሚኖራት ጣሊያኖች ቀዳማዊ እቅድ አውጥተው ነበረ፡፡ የቨርሳይ የሰላም ውል ምሳሌ በመውሰድ የምዕራብያውያን ሊበራል፡ ዲሞክራሲ ፅንስ ሐሳቦች ማስተወስ ያስፈልጋል፡፡[1]

1/ ተሸናፊ ሀገር የሚከፍለው የጦርነት ካሳ በወርቅ ወይንም በገንዘብ መሆን የለበትም፡፡
2/ ሀገሮች በሕጋዊ ብቻ የተቋቋመ መሆን የለባቸውም፡፡
3/ በሀገሮች መሐከል የሚኖረው ግንኙነት በሕጋዊ ብቻ የተመሰረተ፣ በእኩልነት፣ የማይቀየር፣ የማይዳሰስ መሆን የለበትም፡፡

እውነተኛ ሃብት ማለት ዞሮ ዞሮ መሬት ስለሆነ አሸናፊ ሀገር በማቱ የሚያጠቃልላቸው መሬቶች ከይሁዳዊ አስተሳሰብ የካሳ በወርቅ ከተሸናፊው ከመጠየቅ ይልቅ የነበረውን ሕዝብ አባሮ የራሱን ሕዝብ ማስፈር ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አሸናፊ ሀገር ከተሸናፊው የሚወስዳቸው ቅኝ ግዛቶች ማንኛውን የተሸናፊ ሀገር ዜጎች መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ አሰራር የዘረኝነት ኢኮኖሚ ነው፡፡ የካፒታሊዝም ማብቂያ በሥራ የተመሰረተ የአዲስ ወጣት ሀገሮች ዘመን መጀመሪያ ነው፡፡

ሀገር ማለት የ1789 አብዮት የፈጠረው ዓይነት ሀገር በእኩልነት ያተመሰረተ በዘረኝነት የተመሰረተው ሀገርና የሕዝብ ትርጉም የእኩልነት

[1] Emilio Canevari : La Politica della Razza e il nuovo ordine europeo Difesa della razza Anno N.9



Quale evoluzione
hanno avuto la Libia e la Somalia,
l'Etiopia e l'Eritrea?

# LE COLONIE DI IERI

Ecco un ritratto degli ex possedimenti e dei loro rapporti con l'Italia: collaborazione, stima, amicizia senza rancori.

*La banda militare della polizia in uniforme all'inglese durante una festa a Tripoli.*



የእንግሊዝ አፍሪካውያን ወታደሮች በሰልፍ

ሀገሮች አይቀበሉም ምክንያቱም ሁሉ ሰው በሕግ እኩል ስለሚያደርግ ነው። የአንድ ሀገር ዜግነት ለማግኘት ግንም ሰው ጠይቆ የሚያገኘው አይደለም። ዘረኞች የሀገርና የሕዝብ አስተሳሰብ በዘር፣ በሥጋ ዝምድና ያላቸው የሚገኝ ነው። እንደ ፈረንሳዮች በእዋጅ ዜግነት አይሰጥም፣ የተፈጥሮ ሕግ የሚቃወም ሰው ሰራሽ ነው። ስፌ ግዛት እምፓየር ለመፍጠር በስጋ ዝምድና የሚመሰረት መሆን አለበት። የስጋ ዝምድና የሌላቸው ሀገሮች በታሪክ እንደታየው ይወድቃሉ። የፈረንሳይ ሀገር ውድቀት ሌላ ሕዝብ ዝቅተኛ ዘሮች በማዋሐድ የተነሳ ነው። የ1789 የእኩልነት አብዮት የፈጠረው ሁኔታ ነው፣ ለእስራኤላውያን ማኅበራዊ ነው። በሀገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በሕግ የተመሠረተ እኩል ድምፅ ያላቸው በዲሞክራሲ ዓይነት ስለሚሆን ለምሳሌ ኢጣሊያ ከላይቤሪያ እኩል ትሆናለች። በዘረኝነት ግንኙነት ግን በኃይል ሚዛን የተመሠረተ ነው፣ ቋሚ ሳይሆን ተቀያያሪ ነው። በባለ እንዱስትሪዎች መሐከል ትልቅ ግጭት የተደረገው በ1ኛ ዓለም ጦርነት ነበር፣ በአንግሎሳክሰኖች የበላይነት ተደመደመ። በጀነቫ ችግሩን ለመፍታት ተሞክሯል፣ ይህ ሙከራ ከሽፏል። አሁን በኢጣሊያ በጀርመንና በጃፓን አዲስ ፕሮግራም ቀርቧል። በተወሰነ ክልል ለመኖር የሚበቃ Spazio vitale Autarchia ራስ ገዝ መፍጠር ነው። በነዚህ ወጣት መንግሥታት ውስጥ አንድ ትልቅ መንግሥት የከባድ ኢንዱስትሪ ባለቤት የሆነ፣ የዘረኝነት ፅንሰ ሐሳብ ያለው፣ በእሱ የሚመሩ ሌሎች አነስተኛ መንግሥታት የኢውሮጳውያን ከሌሎች ክፍለ ዓለማት የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተቀባይ የሚሆኑ ይኖራሉ። ይህ እቅድ በወቅቱ የተከሰተው በወታደራዊ ኃይል አስተማማኝ ኃይል የበላይነት ባለው የተመሰረተ ነው። የነገ ኢውሮጳና የነገ ዓለም ለተለያዩ ክልሎች Spazi vitali ይከፈላል። በክልሉ መሐል እንደ ፀሐይ ትልቅ አንፀባራቂ ኮከብ፣ በኢንዱስትሪ የበለፀገ ሀገር፣ ይኖራል፣ በዙሪያው ሌሎች ጭፍሮች ይኖሩታል። ብንፈልግም ባንፈልግም እነዚህ ትልቅ አንፀባራቂ ትልቅ ሀገሮች ዘረኞች ይሆናሉ። በአሪያን መንግሥታት የሚመሩ መሆን አለባቸው፣ ምክንያቱም ከባድ ኢንዱስትሪ ያላቸው አሪያን መንግሥታት ብቻ ናቸው። ጥሬ እቃ እንደ ከሰል፣ብረት ስላላቸው ሳይሆን በዘር ባላቸው ችሎታ ነው። ምክንያቱም የብረት ማዕድን ማለቂያ የሌለው የሚገኘው በቻይና ነው፣ ነገር ግን ማንም ከአሪያኖች በፊት አልተጠቀመበትም። የአሪያን ዘር ከፍተኛ በሀንጎል የመሥራት ችሎታ አለው፣ የመሪነት ችሎታ አለው፣ ደፋር ተዋጊ ነው። አንፀባራቂ ኮከብ የተባሉ ሀገሮች እነማን እንደሚሆኑ ግልፅ ነው። አሜሪካ ልትሆን አትችልም ምክንያቱም ኔግሮ Negro ሆናለች፣ ፈረንሳይ ልትሆን አትችልም ምክንያቱም ከጥቁሮች እየተጋባች ጠቁራለች፣ ብሪታኒያ ልትሆን አትችልም ይሁዳዊት ሆናለች፣ ሶቬት ሕብረት ልትሆን አትችልም በእግዚአብሔር የማታምን ናት፣ ዓለም አቀፋዊነት ዓላማ ያላት ናት፤ ይኸውም የእኩልነት የይሁዳውያን ፀባይ ነው። የነገው ዓለም በአሪያን ዘር የበላይነት ነው የሚገነባው፣ አንፀባራቂ ኮከቦች ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ጣሊያንና ጀርመን ናቸው፣ 3ኛዋ ጃፓን ናት። እያንዳንዳቸው ርዕሰ ኃያላን ዘረኞች መንግሥታት ብዙ ጭፍሮች መንግሥትና ሕዝቦች ይኖራቸዋል።

በሁለተኛ የዓለም ጦርነት የተደረገው ፍልሚያ በዲሞክራሲ ኃይሎች መደምደሙ ለሶስተኛ ዓለም ሕዝቦች በተለይ ለአፍሪካውያን ምን ያህል ወሳኝነትና ጠቃሚነት እንደነበረው ለመረዳት አያዳግትም። ዘረኞች መንግሥታት ርዕሰ ኃያላን እንግሊዞችን፣ የዓሳ አጥማጆች ደሴት እናደርጋቸዋለን የሚል ፉከራ እያሰሙ ነበረ፤ ፈረንሳይ ጣሊያኖችና ጀርመኖች ከተከፋፈሏት በኋላ በአንድ



በሊብያ (ሊቢያ) ዘራ ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ተቃዋሚ አርበኛ መሐመድ ማሕዲ አስ ሰኑሲ



Mohammed Mahdi es Sennusi, organizzatore della rivolta dei Senussi (novembre 1914)



ኤርትራውያን አስካሪ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች እንደ የሮማውያን ባሮች በኮሎሰዮ Colosseo ታማኝነታቸው በመሞህ ሲገልፁ

-ዘረኛ ርዕሰ ኃይል መንግሥት ትሆን ነበረ፣ አሜሪካውያን ነጮች[1] 25% የጀርመን ዝርያ 20% የእንግሊዝ ናቸው እየተባለ ሲነገር ነበረ፣ ስለዚህ በጀርመን የበላይነት አስተዳደር ትወድቅ ነበር፣ ከሁሉ በላይ አፍሪካውያን ዘራችን ይጠፋ ነበረ፣ በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን ዕድላችን ምን እንደሚሆን አትድ አውቀቶልን ነበረ፤እኛ Popoli Imbelli e guerrieri in Africa ተብለን ነበረ የምንታወቀው ትርጉሙም ጅሎችና ጀግና ጦረኞች ሕዝቦች በአፍሪካ ማለት ነው።



L. Cipriani,
ዘረኛው ቺፕሪያኒ

በሌላ አርዕስት አላይ እንደገለፅኩት ሊዲዮ ችፕሪያኒ ሰፊ ጽሑፍ ያቀረበበት ምክንያት እንደ ከብቶች በኢጣሊያኖች የቀኝ ግዛታቸው ማስፋፍያ ዓላማ መሣሪያ ለመሆን በየጊዜው በየቦታው በኢትዮጵያ በሊቢያ ስንዋጋላቸውና ስንሞትላቸዋ በማየቱ ነው።።ብዙ ኢጣሊያኖች በቅኝ ግዛታቸው በሰፊው የዜጎቻቸው ስፍረው የዜጎቻቸው ሰፈራ ለማካሄድ ይፈልጉ ስለነበረ በቅኝ ግዛት የያዝዋቸውን መሬቶች የሚኖረው ሕዝብ ለመፍጀት ዓላማ ነበራቸው። የሊጂዮ ቺፕሪያኑ አስተሳሰብ ግን የዚሁ ተቃራኒ ነው። ኢትዮጵያውያን እንደሌሉች ጥቁሮች ጎዶሎዎች ዝቅተኛ ፍጡሮች ጅሎች ናቸው። ነገር ግን ከሌሉች አፍሪካውያን ለየት የሚሉበት ጦረኞች በመሆናቸው ኢጣሊያ በሌላ ሀገር የተያዙ በአፍሪካ ቅኝ ግዛቶች ወደ ራሱዋ ለማጠቃለል ለወደፊት የምታደርጋቸው ጦርነቶች ጠቃሚ ናቸው የሚል እምነት ስለነበረው ነው።

በዚሁ መሠረት ቁጥራቸው በሚቀጥሉት ጥቂት 10 ዓመታት እጥፍ እንዲሆን በጠንነት እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል የሚል ሐሳብ ነበረው። የቀረቡ ሐሳቦች በሁለቱ መንገዶች ቢመጡብን እኛን ለማጥፋት እንጂ ጣሊያኖች ለእኛ በጎ ተግባር እንዳልመጡ ማወቅ ተስኖን ኖረናል፣ አሁንም እርስ በእርሳችን የምናደርገው መፋጀት የኢጣሊያን እጅ አለበት ብለን መገመት አልቻልንም። ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ጣሊያኖች ለሕልውናችን እየተፈታኑን ይገኛሉ። በተዋጋንላቸው በሞትንላቸው ቁጥር Popoli imbelli e guerrieri in Africa ጅሎች ጦረኞች ወይንም ሌላ ትብብር ባደረግንላቸው ቁጥር በእንግሊዝኛ imbeciles and warriors people in Africa ከብተኞችና ጅሎች ጦረኞች ሕዝቦች በአፍሪካ ከመባል አልፈን የምናገኘው ምስጋና የለም። ከምድረ ገጽ እንዳንጠፋ ያበቃን በሁለተኛ ዓለም ጦርነት የጦር ጓዶች የነበሩ እንግሊዛውያን፣ ፈረንሳውያን፣ ሩሲያውያን፣ አሜሪካውያንና ተባባሪዎቻቸው መሆናቸውን ምንጊዜም መዘንጋት የለብንም። በፀረ ፋሽዚም ናዚዝም የከፈሉት ክቡር መስዋእትነት ውጤት ነው።

በ2ኛ የዓለም ጦርነት ከተካሄዱ ወሳኝ ፈልሚያዎች የስታሊን ግራድ በሶቬት ሕብረት የኖርማንዲ በምዕራብያውያን የተደረጉ ጦርነቶች በጋል ስሜት ለዘለዓለም የምናስናተውሳቸው ናቸው።

---
[1] Difesa della Razza Anno IV N 12 p 30





ዱባት የሶማሌ ባንዳ



ኢትዮጵያውያን በኢጣሊያ ከመዛታቸው በፊት ከብቶችና ጅሎች ጦረኞች ሕዝቦች ነበሩ በእንግሊዝኛ imbeciles and warriors people in Africa በኢጣሊያ ከተገዙ በኋላ የተወለዱ ልጆቻቸው ደግሞ ሬታቸው የፋፋ Marmocchi ማርሞኪ ይመስላሉ በማለት ሌላ ቅጽል አውጥቶልናል። ማርሞኪ በአማርኛ ሲተረጎም ዝቅተኛ፣ ጅል፣ ሞኝ፣ ጎዶሎ እንደ ሕፃን የሚቆጠር ሰው ማለት ነው፤ ወይንም የአደን ውሻ የሚመስል ሰው ማለት ነው። በእንግሊዝኛ ብራት Brat child despised, hound ማለት ነው ይኸም ቅጽል የሰጠን አሁንም ሊዲዮ ችፕሪያኒ Lidio Cipriani [1] ባወጣው ጽሑፍ ነው። ቺፕሪያኒ ፀረ ጥቁር ሕዝቦች ብዙ መጽሐፍ በመድረሱ በኢጣሊያ መንግሥት እንደ ኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ከፈጠሩ አንጋፋ ጣሊያኖች አንዱ ለመሆን በቅቷል። ይህ ግለሰብ በግሉ አይደለም የሚጽፈው የኢጣሊያች ሁሉ ስሜት የሚያንፀባርቅ ነው። ጣሊያኖች የዘር ኩራት አላቸው ማለትም አይቻልም። ያልታረመ ንግግር፣ ስድብ በአንድ የውጭ ዜጋ፣ እንግዳ ሥነ ሥርዓት የጎደለው አነጋገር ማሳየት የዘር ኩራት አይደለም፣ የዝቅተኛነት መንፈስ ነው፤ ምክንያቱም ጥቁር ሰው ሲያዩ በንቀት በመጥፎ ዓይን ዓይተው አያልፉም፣ በመሐይምነት መንፈስ ይሸሹታል፣ በተለይ ልጆች ይደነግጣሉ። በዚሁ ረገድ ኢትዮጵያውያን የኢጣሊያኖች ተቃራኒ ናቸው፣ ማንም ነጭ ወይንም ቢጫ ሰው ሲያዩ ወይንም ከእነሱ ለየት ያለ ሌላ ጥቁር ሰው ሲያዩ ምንም ስሜት አይሰጣቸውም፣ መሳደብም ማድነቅም ጠባዩ አያሳዩም። ይህ ጠባያችን የምንኩራበት ነው። ከሁሉም የሰው ልጅ በእኩልነት መንፈስ ተደባልቀን መኖር ችሎታ እንዳለን የሚደነቅ ችሎታ ነው። አፋችንን ከፍተን ከዳር እስከ ዳር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንግዳ ተቀባይ ነው ለማለት እንችላለን።

ችፕሪያኒ በዚህ ጽሑፉ ኢጣሊያ እንደ ጥንታዊት ሮማ ሌላ ሀገር ስትያዝ ፊት ለፊት ወረራ በማድረግ ነው። እንደ ሌሎች ሀገሮች ሳትዋጋ፣ በዘዴ በጥበብ፣ በሐሰተኛ ማስመሰል በመመፃደቅ አይደለም። በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ፊት ለፊት ተዋግታ ነው የያዘቻት፤ ለወደፊትም ከባሕር ማዶ ማስፋፋቷ ትቀጥላለች። የኢጣሊያ አገዛዝ በተሸነፉ ሕዝቦች ላይ ሙሉ በሙሉ በሰበአዊነት የተሞላበት አያያዝ ነው ትክክለኛና ሚዛናዊ አያያዛችን ማስረጃዎች የሚሆኑ ከሕዝቡ ልባዊ ምስጋናን ከምናገኘው ሌላ አሁን በኢትዮጵያ በብዛት በመወለድ ላይ ያሉት የፋፉ፣ ጉንጫቸው ያበጠ፣ ማርሞኪ Marmocchi በኢትዮጵያና ለንጉሠ ነገሥታዊ ግዛታችን /ኢምፓየር/ ለወደፊት የብርሁ ተስፋ ምልክት ናቸው። ይኸም ሁኔታ በምሥራቃዊ ኢጣሊያዊት አፍሪካ የኑሮ መሻሻልና አስተማማኝ ፀጥታ እንደተፈጠረ ያሳያል። እንደዚሁም ለወደፊት ለኢጣሊያ ጠቃሚ ረዳቶች የሚሆኑ አዲስ ትውልድ እንደተፈጠሩ የሚያረጋግጥ ነው። ማርሞኪ Marmocchi በአማርኛ ዝቅተኛ፣ ጉደሉ፣ ሞኝ የሚቆጠር ጅል፣ እንደሕፃን፣ ወይም እንደ የአደን ውሻ የሚመስል ሰው ማለት ነው፤ በእንግሊዝኛ ብራት Brat Child despised hound ተብሎ ይተረጎማል። "ማንም ኢሮፓዊት ሀገር እንደዚ ያለ አያያዝ አላስመዘገበችም። በኤውሮፓውያን በተያዙ ቅኝ ግዛቶች ሁሉ ሀገሩ በነጮች በመያዙ የተነሳ የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የታየበት ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፣ አብዛኛው ግን ሕዝቡ ከምድረ ገጽ እየጠፋ ነው የሚታየው። በተጨማሪም ሕዝቡ ደስተኛ ሆኖ አይታይም፣ ለዚህም ምሳሌ ግብጽና ሕንድ መጥቀስ ይቻላል። በግብጽ ራስን የመግደል ተስፋፍቶ ይታያል፤ በሕንድም በሕዝቡ ላይ ድህነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመሔድ ላይ መሆኑን ይታያል። ጣሊያኖች በሚያስተዳድራቸው ሕዝቦች ግን መጥፎ

[1] Lidio Cipriani : Razza e metodi di conquista Difesa della Razza Anno III N3






Un battaglione eritreo in marcia in Cirenaica

አያያዝ አያከስትም፤ መከላከያ በሌላቸው ሕዝቦችም ጣሊያኖች ትዕቢት አያሳዩም" በማለት ጽሑፉን አጠቃሏል።

የኢጣሊያ ፕሮፓጋንዳ ከነ ፋርዲናንዶ ማርቲኒ ጀምሮ በሃሰትና ቅጥፈት የተመሠረተ ነው። የሕዝባቸው ስሜት ግን በሚስብና በሚያሳምን የተዘጋጀ ነበር። በፎቶግራፎች እንደሚታየው የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ወታደሮች ከኢጣሊያ ማርሞኪ Marmocchi ወታደሮች የበለጠ ወፍረውና የውትድርና ልብስ ለብሰው ሲታዩ፣ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ወታደሮች ግን የውትድርና ልብስ ያልለበሱ፣ ባዶ እግራቸውን ከሲታዎች ሆነው ይታያሉ።

በሌላ ጊዜ ቺፕሪያኒ ለሰው ዘር እኩልነት የሚሟገቱ የአንግሎሳክሶን ናቸው ብሎ ነበር[1] ዘረኞች የሚጠሉትን አንድ ሕዝብ ወይም ዘር ዕብራዊ መሆኑን ማስረዳት ከቻሉ የሕዝብ እንደ እስራኤሎች የሚጠሏቸው ከምድረ ገጽ የሚጠፋ ሕዝብ ነው። የዘረኛ መጽሔት[2] ለአምስት ዓመት ሥራ አስኪያጅ የነበረው ኢንተርላንዲ ሁለቱ ከእግዚአብሔር የተመረጡና የተባረኩ ሕዝቦች እንግሊዞችና እስራኤላውያን በሚል አርእስት ባወጣው ጽሑፍ እንግሊዞች እንደ ይሁዶች እንደሆኑ፣ ይሁዶች በለንደን ብቻ 100,000 /መቶ ሺህ/ እንደሚኖሩ፣ ይሁዶች እንዴት የእንግሊዝ ሀገርን እንደሚቆጣጠሩ ያስረዳል። የእንግሊዞች ከእስራኤላውያን መወለድ የሚያስረዳ የትውልድ ሐረግ ሰንጠረዥም አውጥቷል። በሰንጠረዡ መሠረት በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ብሪታኒያና ኮመንወልት Commonweath ሀገሮች ናቸው። ሆኖም አሜሪካም የአንግሎሳክሶን ስለሆነች በዚሁ ሰንጠረዥ ልትጠቃለል ትችላለች። በዚህም መሠረት ዓለምን የሚገዛ በነቢያት የተነገረ አሜሪካ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ብቸኛ ልዕለ ኃያላን ሀገር ስለሆነች በእግዚአብሔር የተባረከ ዓለምን የሚገዛ ሕዝብ መጥቷል ማለት ነው። የዚሁ አስተሳሰብ ደጋፊዎች ትንቢቱ ተፈጸመ ሊሉ ይችላሉ።

እናክ በዕብራይስጥ ውሃ የተኛበት መሬት ማለት ነው። በራት እናክ የተኛባቸው ደሴቶች ማለት ሲሆን ክባራት እናክ በግሪክኛ ወደ ብሪታኒክ ተቀየረ። በላቲንም ግሪክ ታሪክ ጸሐፊ ስትራቦ ብሪታኒክ የእንግሊዝ ደሴቶች መሆናቸውን መስክሮ ጽፏል። ስለዚህ እንግሊዞች የአብርሃምን፣ የእስራኤል ልጆች መሆናቸውን በሰንጠረዡ ተገልጿል። ነቢያት በተናገሩት መሠረት አማኒያን ያልሆኑ እየሩሳሌም ከገቡ ማንቦቿ ይፈርሳሉ ተብሎ የነበረው፣ ማንቦቿ የእንግሊዝ ወታደሮች በ1ኛ የዓለም ጦርነት እየሩሳሌምን ሲቆጣጠሩ ያልፈረሱ እንግሊዞች የይሁዶች ዘር ዓለምን በሙሉ እንዲገዙ በእግዚአብሔር የተመረጡ በመሆናቸው ነው።

እንግሊዞችና ይሁዶች አንድ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ዘረኞች የሁለቱ ሕዝቦች ሃይማኖቶች ተመሳሳይነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ብለው ያቀረበው ደሊሶላ (Dell' Isola) የተባለው ጸሐፊ[3] ያወጣው ጽሑፍ ነው። በዱሮ ጊዜ እንግሊዞች ካቶሊክ በነበሩ ጊዜ ይሁዶች በእንግሊዝ ሀገር አልነበሩም። ከ1665 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ክሮምወል Cromwell እንዲገቡ ፈቀደላቸው። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ የእንግሊዝ ሕዝብ ይሁዶች እንዲገቡ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ከተመረጠውና ከተባረከው የእስራኤል ሕዝብ እንደሚወለድ የሚል ታሪክ በመፍጠሩ፣ በኤውሮጳውያን ብቸኛ ሕዝብ ያደርገዋል። ይሁዶችም ያላቸው ገንዘብ በለንደን በማፍሰስ ወረታውን ከፍሏል። ወደዚሁ ለመድረስ ግን

---

(1) Lidio Cipriani : Considerazioni sopra il passato e l' avvenire delle popolazioni africane p 9
(2) Telesio Interlandi Due popoli "eletti" : Difesa della razza Anno 4 N. 7
(3) G.Dell' [illegible]la :Somiglianze tra il giudaismo e la religione degli inglesi :Difesa della razza Anno IVN2





I NOSTRI FEDELI ASCARI ERITREI. (Foto « Luce »).

## ጅሎችና ጀግኖች ጦረኞች ሕዝቦች በአፍሪካ



14. - Ascari Somali.

**(Popoli imbelli e guerrieri in Africa)**

ያመቻቸው የሁለቱ ሃይማኖቶቻቸው ተመሳሳይነት ነው። የእንግሊዞች ፕሪታን ካልቪኒስቱ ሃይማኖት ለእንግሊዞች የሚስማማ ሆኖ የተመሠረተው እንደ ይሁዳውያን ሃይማኖት የሆነው ሁለቱ በሁለት ነገሮች ይመሳሰላሉ። 1ኛ/ ሁለቱ ሃይማኖቶች በገንዘብ የሚያምኑ ናቸው፣ ሃብት ብቻ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ መሆኑን ብለው ያምናሉ። 2ኛ/ ሁለቱ ሃይማኖቶች ዋሁዶችና እንግሊዞች ከእግዚአብሔር የተመረጡ[1] የተባረኩ ሕዝቦች መሆናቸውን ያምናሉ። በእንግሊዛውያንም ሆነ በይሁዶች ዘንድ ሰው ቅዱስ የሚሆነው ገንዘብ ማከማቸት ሲችል ነው። በዚህ የተነሳ እንግሊዞች ድሆችን አይወዱም። ሃይማኖታቸው ሃብታም መንግስተ ሰማይ ያገኛል ድሀ ይኰነናል የሚል ነው። ጣሊያኖች በይሁዶች ላይ ጥላቻ የላቸውም፣ ይሁዶችም በኢጣሊያ ጥቂት ናቸው። ጣሊያኖች በአሜሪካና በሶቬት ሕብረት ቅራኔ የላቸውም፣ ስለዚህ ልዩ ጥላቻም የላቸውም። የጣሊያኖች ምኞት ወደ አፍሪካ ይተኮረ ስለነበረ ቅራኔና ጥላቻ የነበራት አብዛኛው አፍሪካን ያስተዳድሩ በነበሩ በፈረንሳይና በብሪታኒያ ላይ ነበር። ቺፕሪያኒ የወደፊት የአፍሪካ ዕድል ለአፍሪካውያን ነው የሚለው አስተሳሰብ አይቀበለውም። የእንግሊዝ ፓርላማ እንደዚሁም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሚኒስቴር አመሪ Mr Amery(1)። በተለይ ምሥራቅ አፍሪካን በሚመለከት የወደፊት ዕድገቱ ሥልጣኔው ለአፍሪካውያን ይሆናል ብለው የሰነዘሩት አስተያየቶች መሠረት የሌለው ነው ብሎታል። አፍሪካውያንን እኛ ስለጥናለን ብሎ ማሰብ ከንቱ ድካም ነው(2)። አፍሪካ ለአፍሪካውያን የሚለው እንቅስቃሴም አይሰራም(3) ። የእንግሊዝ መንግሥት ለአፍሪካውያን በተለይ በደቡብ አፍሪካ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች በግደየለሽነት ወይም በመደገፍ የሚያሳየው አቋም አግባብ አይደለም(4) ። አፍሪካ ምንጊዜም ለአፍሪካውያን አትሆንም። አፍሪካ ለኢጣሊያ ሕዝብ መሆንዋ የማይቀር ነው ወ.ዘ.ተ. ብሏል(5) ።

ጁሴፔ ግሪየኮ Giuseppe Grieco የፈረንሳይ ከጦርነቱ በኋላ የወደፊት ዕድሏ በሚመለከት የሰጠው አስተያየት ከዚህ በላይ ገልጬዋለሁ። ስለብሪታኒያ የወደፊት ዕድሏ ባወጣው ጽሑፍ ጥንታዊት ሮማና ካርታጅ በፑኒክ ጦርነቶች ጊዜ በማነጻጸር ነው። ካርታጅ በኢኮኖሚና በሃብት ብልጽግና የምትጓብር ሀገር ተብላ ትገመት ነበር። ሮማ ግን በውትድርና ብቻ የዳበረች ነበረች። ካቶ Cato የተባለው የሮማ ባለስልጣን ከ2ኛው የፑኒክ ጦርነት በኋላ በካርታጅና በኑሚዲያ Numidia የዛሬ ምዕራባዊ ማግሬብ ሀገር መሐከል የነበረው ጠብ ለማስታረቅ ወደ አፍሪካ በሔደበት ጊዜ የካርታጅ እንደገና መነሳትና በኢኮኖሚ መበልጸግ ተመልክቶ ለሮማ አስጊ መሆኑን ስለገመተው ወደ ሀገሩ ሲመለስ በሮማ ሰነይት Senate የሚያደርጋቸው ንግግሮች Cartago dolenda est cartage must be destroyed በታሪክ ዝነኛ የሆነው የተናት መፈክሮች ንግግሩን ያበቃ ነበር። ግሪየኮ ብሪታኒያና ኢጣሊያ በ2ኛ የዓለም ጦርነት እንደ ካርታጅና እንደሮማ በማነጻጸር ነው ጽሑፉን ያቀረበው። ዛሬ ኢጣሊያና ብሪታኒያ የሚያደርጉት ትግል ለወደፊት ዕድላቸው፣ ሕልውናቸው ወሳኝነት ያለው ነው። የኢጣሊያ ባለጋራ በቀላሉ የምትገመት አይደለችም፣ ኃይለኛ መንግሥት ናት፣ ተስፋ በመቁረጥ የመጨረሻ ዕድሏ ትሞክራለች። እንደ ፑኒክ ጦርነቶች ጊዜ ዛሬ የሚጋፈጠን ጠላት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ሃብታም ነጋዴ መንግሥት ነው። ትግሉ ከባድና ወሳኝ ነው፣ በሁለቱ ሀገሮች ያለው

(1) Lido Cipriani ibd p 157
(2) Lido Cipriani ibd p 153
(3) Lido Cipriani ibd p 144
(4) Lido Cipriani ibd p 143
(5) Lido Cipriani ibd p 162



(Popoli imbelli e guerrieri in Africa)

ሕንዳዊ የእንግሊዝ ወታደርና የኢርትራውያን የኢጣሊያ ቅኝ ገዥ ወታደሮች

[illegible]



ጅሎችና ጀግኖች ጦረኞች ሕዝቦች በአፍሪካ

Il ten. Partini caduto a Cassala

(fot. Varonini .

Il comandante del distaccamento indiano di servizio alla Legazione britannica di Addis Abeba



a Mogadiscio nel 1907: in alto, la compagnia di sbarco della R. N. *Marco Polo*; in basso, il battaglione ascari eritrei.

ጠብ ለድርድር የሚቀርብ ወይም በድርድር የሚፈታ አይደለም፡፡ ጦርነቱ የሚካሔደው ሮማ ወይም ለንደን የሚል መፈክር አንግበን ብቻ ነው፡፡ ከሁለቱ ተፋላሚዎች አንዱ መጥፋት ያለበት ትግል ነው፡፡ ብሪታኒያ አሸንፋለሁ ብላ ትሞኝ ይሆናል፤ ኢጣሊያ ግን በማያጠራጥር ሁኔታ ለማሸነፍ ርግጠኛ ናት፡፡ ኢጣሊያ የተነሳችበት ቅዱስ ዓላማ አላት፤ በማደግ ላይ ላለው የሕዝቧ ቁጥር በቂ መሬት ለማግኘት ስለሆነ፤ እንደዚሁም በሞራል የበላይነት ለላላት ድልን ለመቀዳጀት ብቁ ያደርጋታል፡፡ ብሪታኒያ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እጅዋን እስካልሰጠች ድረስ ጦርነቱ ይቀጥላል፤ የሞትና የሽረት ጦርነት፤ ያሸናፊና የተሸናፊ የሚለይበት ጦርነት ነው ወ.ዘ.ተ በማለት ጽሑፉን ደምድሟል፡፡

ጦርነቱ በብሪታኒያና በጦር ጓዶቿ አሸናፊነት ተፈጸመ፡፡ ከብሪታኒያ ጋር የተፋለመች ሀገር ግን በኢውሮጳም በሰሜን አፍሪካም ጀርመን እንጂ ኢጣሊያ አልነበረችም፡፡ ኢጣሊያ የጀርመን አነስተኛ ጭፍራ ከመሆን አልፋ ብቻዋ በጦርነት ከብሪታኒያ ጋር ለመወዳደር ደረጃ ደርሳ አታውቅም፡፡



ኢርትራውያን በጉንደር የኢጣሊያ ቁንስላ
poli imbelli e guerrieri

ጅሎችና ጀግኖች ጦረኞች ሕዝቦች በአፍሪካ





የፈረንሳይ አፍሪካውያን ወታደሮች
የፈረንሳይ ዜግነትና መብት ያላቸው

Un soldato della "grande Francia"

<u>ዋቢ መጻሕፍቶች</u>


1. ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ አክሱም ዛጔ
2. ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለሥላሴ
3. " " " " አፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት
4. " " " " አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት
5. C. Conti-Rossini Storia d' Ethiopia
6. C. Conti-Rossini Etiopia e genti d' Etiopia
7. Ferdinando Martini Nell' Africa Italiana
8. Ferdinando Martini Diarco Eritreo
9. Ministero dell' Africa Italiana Gli Annali dell Africa Italiona
10. La Formazione dell' Impero Coloniale Italiana (FICI)
11. La Guerra Italo - Abisaina 1895-1896
12. Raimondo Franchetti : Nella Dancalia Etiopica
13. Antonio Cecchi Da Zeila alle frontiere di Caffa
14. Gustavo Bianchi : Nella Terra dei Galla
15. Difesa Della Razza
16. Carlo Boidi Legionari Universitarisul fronte Somalo
17. Sandro Sandri : Sei mesi di guerra sul fronte somalo
18. Rodoffo Graziani : Rronte Sud
19. Ettore Cozzani : Vita di Guglielmo Massaya
20. Pietro Badoglio : La Guerra d' Etiopia
21. Luca Dei Sabelli : La storia di Abissinia
22. Arata Salvatore : Vita del Beato Giustino De Jacbis
23. A. Gaibi : Manuale di Storia politico militare della colonie Italiane
24. A. Pollera : Le Popolazioni Indigene dell' Eritrea
25. Vico Mantegazza : Da Massaua a Saati
26. Vico Mantegazza : La Guerra in Africa
27. Jean Doresse : Histoire Sommaire dela corme Orientale d' Afrique
28. G. Sapeto : Etiopia
29. Emilio Bellavita Adua
30. G.B. Licata Assab e Danachili
31. Alessandro Lesson : Verso L' Impero
32. Camillo Beccari : IL Tigre
33. Alberto Pollera : Storia leggende e favole nel paese dei Negus
34. Alberto Pollera : Lo Stato Etioico e la sua Chiesa
35. Alberto Pollera : Lo Battaglia di Aduo
36. Magg. Ruffillo Perini : Diqua dal Mareb; Mereb- Melasc
37. Corrado Zoli : Cronache Etiopiche
38. Corrado Zoli : Etiopia d' Oggi
39. Corrado Zoli: La Conquista dell' Impero
40. Giuseppe Piccinini : La Guerra d' Africa Campagna 1888
41. Carlo Rossetti : Storia Diplomatica duranteil Regno di Menelik
42. G. Sapeto : Assab : e i suoi critici
43. Verner Munzinger : Studi Sull' Africa Orientale
44. Carlo Zaghi: Le origini della Colonia Eritrea
45. Leopoldo Traversi: Let Marefia





46. Vico Mantegazza . L'assedio di Macalle
47. Lidio Cipriani : Un Assurdo Etnico l' Impero Itiopico
48. Edoardo Scarfoglio : Abissinia 1888-1896
49. G. Giacchero e Bisogni La Vita di Giuseppe Sapeto
50. Eucardio Momigliano : Storia Tragica e grottesca del Razzismo Fascista
51. Ugo Caimpenta L' Italia in Africa
52. Enrico Cerulli: Etiopia Occidentale
53. Governo Generale A.O I Stato Magiore: I Anno dell' Impero
54. Edouardo Ximenes: Sul campo di Adua mazzo giugno 1896
55. Coulbeaux : Histoire Politique et religieuse d' Abyssinie
56. Enciclopedia Treccani
57. New Standard Encylopedia
58. Renato Paoli Nella Colonia Eritrea
59. Carlo Annaratone : In Abissinia
60. Agenore Frangipani : Equivoco Abissino
61. Raffacle di Lauro : Tre anni a Gondar
62. Gen. L. Frusci : In Somalia sul fronte Meridionale
63. Vittorio Bottego : Il Giuba Esplorato
64. Arnaldo.Ciplla : Abissinia in Armi